ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
6me ANNÉE № 1

ሐሙስ ታኅሣሥ ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ፡ም።
JEUDI 2 JANVIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Dirèction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደ/ክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መላዘት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በሲዳሞ የተማሪ ቤት በተከፈተ ጊዜ የተደረገ ንግግር።

ክቡር ሆይ።

ከ፶፪ ቍጥር የቀረ ።

በታላቅ ለምለሚ በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ማድቤት አድርገው ከሚገዙት ሲሦአቸው በተቀር ጥንት ዳግማዊ ምኒልክ በሕይወታቸው ሳሉ ግዛት ከሰጥዋቸው መኳንንቶች ጋር እንደዚሁ አሁንም የተሰጣቸው መኳንንቶች አገረ ገዦዎች። አሉ ነገር ግን እነዚሁ አገረ ገዦዎች ሁሉ ከጥቂቶቹ ሌላ ያን በግዛታቸው ውሥጥ ከሚገኘው ጥቅምና ግብር (ማለት ገንዘብ መሰብሰብ) በተቀር አንድም በየአገሩ የተሰራጩ የፈረንሳዊና የእንግሊዞች ሚሲዮን እንደዚሁም የውጭ አገር ሰዎች የሥልጣኔ ጐዳናን ሚስፋት ስለወደዱ ካቆሙት ተማሪ ቤቶች በተቀር አንድ መኳንንት እንኳን በግዛቱ ውሥጥ አንድ የተማሪ ቤት አቁሜ የሀገሬን ሕዝብ አሠለጥናለሁ ነጻነትንም እንዲያገኙ አድርጋለሁ ብሎ ያደረገና የተመኘ ወይም ለሕዝቡ ያሰበ የለም ነበር። አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ብሩ ከጥንት ጀምሮ የደጉን ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክን አሳብ ስላወቁና በልባቸውም ውስጥ አድሮ ሌት ተቀን ሲያሳስባቸው የነበረውን የልባቸውን አሳብ ለመግለጽ ቈርጥ አድርገው መጀመሪያ አስተማሪዎችና ሐኪም ዕውቀት ከሕይወት ጋር እንዲሆን ፈቅደው ለማስመጣት በቁ ።

ነገር ግን ምንም እንኳን ከስመጡን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ታላቁ አሳባቸው የሚገለጽበት ቀን መጨረሻ አልደረሰም ነበርና ዛሬ በታላላቅ መኳንንትና ሠራዊት ደግሞም ጥበብንና ትምህርትን እንዲሰጧቸው የፈቀዷቸው ልጆች በተሰበሰቡበት ጉባኤ መሐከል ሊገልጹ ስለተነሡ ከዚህ ቀጥዬ የጻፍኋትን ቲንሽ ቃል ፤ ለክቡራን ሁሉ ልነግራችሁ እፈቅዳለሁ ክቡራን መኳንንቶች ሆይ፤

ሰው ሁሉ ምንም በዓለም ላይ ሲኖር ጉልበታም፥ ባለገንዘብ፥ ሀብታምም ቢሆን እንኳን በጥቂቱ የገንዘቡን ልክ ለማወቂያ ወይም ለጉልበቱ የሚሆን እውቀት ቢኖረው በሞትኩ ጊዜ ለልጆቼ ወይም ለዘመዶቼ ይሆናቸዋል ብሎ ገንዘብ በማከማቸት አይኖርም ነበር ማለት ቢያስቀምጥላቸውም ያ ገንዘብ ለልጆቹ በሆነ ጊዜ በከንቱ ጠፊ ነው ይህ መሆኑ ልጆቹም ትምህርትና አእምሮ ስላጡ ነው ከዚሁም በኋላ ያልታደሉት ልጆች ከባታቸው የወረሱትን ገንዘብ ጨርሰው አጕል ከውስልትና ስፍራ ይደርሳሉ ይልቁንም በብዙ ገንዘብ ይኖሩ የነበሩትን ትዳር ሲያጡ የሰው ገንዘብ ለመቀማትና ለመስረቅ ነፍስም ለመግደል ይደርሳሉ በዚያን ጊዜ የእገሌ ልጆች እንደዚህ ሆኑ እየተባሉ ያባታቸውን የሞተውን ስም እነሱም እራሳቸው ሳይቀሩ ይወቅሳሉ ።

ክቡራን ሆይ ።

ከዚህ ሁሉ የምታድን መጀመሪያ የተማሪ ቤት ናት ይህችንም የተማሪ ቤት ክቡር ደጃዝማች ብሩ አስበው በራሳቸው ገንዘብ አቆሙላችሁ እንግዲህስ ጠንክራችሁ ልጆቻችሁን አስተምሩ ልጆቻችሁም ለማወቅና አባቶቻችን ባላቸው እውቀት ያቈዩትን አገራችንን ኢትዮጵያን ለመጠበቅ እንዲበቁ እናንተም ይህን የመሰለ ያደረጋችሁላቸው እንደሆነ ብዙ ገንዘብ ያለውቀት ከምትሰጧቸው ጥቂት እውቀት እንዲያገኙ ብትጣጣሩላቸው በኋላ በልጆቻችሁ በኩል የተመሰገናችሁ ትሆናላችሁና አሁንም ክቡር ደጃዝማች ብሩ በእጃቸውና በገንዘባቸው የተማሪ ቤት የከፈቱበትን ቀን አትርሱት እሱም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ የሥልጣኔ ጐዳና የተጀመረበት ቀን ነውና አሁንም የሥልጣኔ ጐዳና መሪያችንን የዳግማዊ ምኒልክን ነፍስ ይማርልን። እንደዚሁ ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ ዕረጅም እድሜ ይስጥ-

ልን ደግሞ በጨለማው ውስጥ የውቀት ብርሃንን አብርቶ ለሕዝቡ ሁሉ ለገለጸው ለክቡር ደጃዝማች ብሩ ከዕድሜና ጤና ጋር አረጅም ዘመን ይስጥልን። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ምሥራቅ ተፈሪ ።

አንትሙኒ ድልዋኒክሙ ንበሩ ። እስመ በጊዜ ኢተሐዘብክሙ ይመጽእ ወልደ እጓለ እመሕያው መኑ እንጋ ውእቱ ገብር ምእመን ጠቢብ ዘይሠይሞ እግዚኡ ውስተ ቤቱ ከመ የሀበሙ ሲሳዮሙ በጊዜሁ፥ ብፁዕ ውእቱ ገብር ዘመጺኦ ይረክቦ እንዘ ዘንተ ይገብር አማን እብለክሙ ከመ ዲበ ኵሉ ጥሪቱ ይሠይሞ እንደተባለው ሁሉ ።

ግርማዊ ንጉሥን የመሰለ ብርሃንና የነፃነት አባት የሀገር አውራ አገራችን ስለ አፈራችልን ደግሞ በእሳቸው መሪነትና በእግዚአብሔር ቸርነት ከጨለማ ወደብርሃን ከሐሰት ወደ ጽድቅ መንገድ የምንሸጋገርበት ክቡር ደጃዝማች ብሩን ስጥቶ ከዚህ ሰዓት ስላደረሰን ክብርና ምስጋና ላምላካችን ለእግዚአብሔር ይሁን ለወደፊቱም በግርማዊ ንጉሥ መሪነትና በተከታዮቻቸው በክቡር ደጃዝማች ብሩ አረዳትነት ሕፃናቶቻችን ከሁን ይልቅ ለሚመጣው ዘመን በትምህርትና በሥልጣኔ ከፍ ከፍ ብለው እንዲሄዱና ወደፊታቸው እንዲገፉ ጥርጥር በሌለው በሙሉ ሐሳባችን እየተመኘን ሳናቋርፅ በብዙ ተስፋ እንጠባበቃቸዋለን–መኳንንቶቻችንም የጌታችንን በረከት ተካፋዮች ሁናችሁ ስላዲሱ ትምህርት ቤት መከፈት በዓሉን ለማክበር ስለተሰበሰባችሁ። ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ እነዚህም ለትምህርት የሚጣጣሩ ወጣቶችን እግዚአብሔር ረድቷቸው ከፍ ታለው–ደረጃ እንዲደርሱና የሀገራቸውን ክብሩንና አረድኤቱን ለመውረስ ያብቃቸው ስል በፍጹም ልቤ እመኛለሁ ነገር ግን በዚህ በሀገራችን እንደዚህያለ ከከብ የሆነ ተማሪቤት ሲበቅልልንና የማናውቀውንና ያላየነውን የሚያሳይ ትምህርት የሚባል ከከብ ብርሃኑን አብርቶ እውቀት የሚባለውን ምንጭ አዘጋጅቶ እኛን ሕዝቦቹን ለመመገብ የሚአፋጠን ስናገኝ ፈጣሪችንን እያመሰገን በተቻለን ሁሉ እንድንረዳዳና ይኸንም ጣፋጭ ምግብ ለዘለዓለሙ የማይቈረጽ ልናደርጋ በሙሉ ልቤ አተጋጋችኋለሁ።

ወአንተሰ ብእሴ እግዚአብሔር ወልደ ዮሐንስ ሤመከ ታእምር ወትገብር ፈቀደ ኃይለ ሥላሴ ይመልዕ ለዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ እም ከርሠ እሙ ዘአቡሁ ምኒልክ ወእሙ አስካለ ማርያም ቡሩክኑ አንትሙ ደቂቀ ኢትዮጵያ ።

አሁንም ለግ ፡ማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዕድሜና ጤና ለክቡር ደጃዝማች ብሩና ለመኳንንቶቻችን ብርታትና ኃይል ይሁንልን በማለት ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ለተማሪ ቤቱ እርዳታ ፫፻ ብር ሰጥቻለሁ ።

ይቤ አለቃ ኃይለ ሥላሴ።

ምክረ ቃል ለሕፃናት ዘክቡር ደጃዝማች ብሩ።

ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ። ከሁሉ በፊት ፈጣሪያችሁን እግዚአብሔርን አመስግኑት ። በንጹሕ ልቦናችሁ ትእዛዙን ፈጽሙ ። ያባታችሁን ስም ዘወትር አክብሩ ። አገራችሁን ውደዷት ጠብቋት ። በኢዮቤልዩ ፲ሳችሁ እንድትመሰገኑና እንድትወደዱ ተግታችሁ ሥሩ ። ከዚህ ዓለም በሞትም በተለያችሁ ጊዜ ጽድቅ እንድታገኙና በሕይወት እንድትኖሩ በጥበብ ጀምራችሁ በእርምሞ ፈጽሙ ። በመጽሐፍ የተባለውን አስተውሉ ። ኑ ልጆቼ ስሙኝ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ ። ሕይወትን የሚሻ ሰው ማነው በጎ ዘመንን ያይ ዘንድ የሚወድ ማነው። ይኸንን ግን የወደድህ ሰው ልሳንህን ከክፉ ጠብቅ ከክፉ ነገር ራቅ ። በጎን ነገር አድርግ። ፍቅርን ሆነ ብለህ ሻት ። ብታገኛትም ተከተላት የእግዚአብሔር ዓይኖቹ ወዳጆቹን ይመለከታልና ። (መዝ ዳዊት ፴፫ ቁ ፲፩ ፲፭።

አሁንም ክፉ ነገር ከመናገር ዝምታ ይሻላል ። ከክፉ ጋራ ባልንጀርነት ከመግጠም ብቻ መኖር ይሻላል ። ከምታውቁት በጥቂቱ ተናገሩ ። ሥራችሁም ሁሉ በግልጽ ይሁን ። ምንም በስውር ብትሠሩት ሳይገለጥ አይቀርምና በወንጌል እንደተባለ ማንም መብራት አብርቶ በእቃ የሚከድን የለም ወይም ከልጋ በታች የሚያኖር፤ ነገር ግን በመቅረዝ ያስቀምጠዋል እንጂ የሚመላለሱ ሁሉ ብርሃን ያዩ ዘንድ የተሸሸገ የለምና የተገለጠ የማይሆን የተሰወረም ሳይታወቅ ወደ ብርሃንም ሳይደርስ የሚቀር የለምና።እንዲሁም ልጆቼ ሆይ ይህ ያሁኑ የሕፃንነታችሁ ወራት ሳያልፍ ለመልካም ትምህርትና ለበጎ ነገር ተፋጠኑ። ከሁሉ ዕውቀት ትበልጣላችና የውቀትምንጭ አታምልጣችሁ ።

በቀና ሐሣብ መያዝ እርስ በራሳችሁ መፋቀር ደግ ሥራ መሥራት ዘወትር ከክፋት መራቅ ። የሚመጣውን አዲስ ጥበብ እንደሚያስፈልግ መማርና ማወቅ ሰው አለማማት በማናቸውም ክፉ ነገር አለማሰብ በማናቸውም ነገር ሁሉ እራስን ከፍ አድርጎ አብልጦ አለመናገር መከባበር ይገባችኋል ። ነገሮቻችሁም ሁሉ ለጓደኞቻችሁ የተስማሙና አንድ ዓይነት የሆኑ ይሁኑ። አትጣሉ ፥ አትፎከከሩ ፤ አትኰሩ ፥ በሥራችሁ ፥ በንግግራችሁ በሀሳባችሁ፥በምታደርጉት ነገር ሁሉ ትክክል እውነተኛ ሥራን ወዳድ ሁኑ ። እኔም አባታችሁ እንደዚህ ሁናችሁ በትምህርታችሁ ላይ ጠንክራችሁ ለሀገራችሁ ጥቅም ስትፋጠኑ ያየኋችሁ እንደሆነ ደስ እያለኝ እንደሚገባችሁ ሽልማታችሁን አላጎድልባችሁም ። ቸርነቱ የማያልቅ የአገራችሁ የኢትዮጵያ አምላክ የጀመራችሁትን ትምህርት ያስፈጽማችሁ ። መዝሙሮችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ሕያው ትሁን።

ተማሪዎቹም አባታችን ጌታችን ወዳጃችን ለዘለዓለም ይኑሩልን። ሐሳብዎን ያስፈጽምልን።ብለው ባማረ ቃል እየመላለሱ በተናገሩ ጊዜ ከዚያ የተሰበሰበ መኳንንቱና ፈረንጁ ሳይማሩ እንዲህ ያለ ቃል የሰጡ ፩ ዓመት በተማሩ ጊዜ በጣሙ ልብ የሚነካ እንደበት ያዘጋጃሉ እያሉ በጣም አመሰገንዋቸው።

እንዲሁም የተማሪ ቤቱን ሥርዓት ከፈጸሙ በኋላ መልካም ግብዣ ተጋበዙና መኳንንቱም ይኸን ያስጀመርከን አምላክ ፈጽሞ በዚህ አገር የሚደረገውን ታሪክ ሳታሳየን ዕድሜ አችንን በከንቱ አታሳልፍብን ብለው ወደ ቤታቸው ገቡ ።

ለማይቀር ሞት አመጣጡ ሲያምር ሞት አይደለም። ስም ሕይወት እየጨመረች ትሔዳለች።

ባለፈው ጋዜጣችን የክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ዕረፍት ከአይሮፕላን አደጋ ያገኛቸውን ስላስታወቀን እንዲ

BRITISH MUSEUM 24 JUL 36

ሁም ብልሁ ነጋድራስ አፈወርቅ እንደጻፉት ለመንግሥቱና ለሀገሩ እንደዚህ በፍቃድ ፈጻሚነቱ የሞተ አሟሟቱ ታላቅ ማዕርግና ስም ነው።ይልቁንም ሰው ምንም መንግሥቱንና አገሩን ቢወድ ለማይቀረው ሞት እንደዚህ ዕድለኛ ሰው ሲሆን ለት ስሙ ከሕዝብም፡ ከታሪክም እንደትክል ሐውልት ለዘለዓለም ስሙ ሕይወት እየጨመረችና እየተዋበች፡ እየተመሰገነች ትኖራለች።እንድ አንድ ሰዎች ከኤውሮፓ ታሪክ ውሥጥ እንደ ምንመለከተው ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ብዙ ልዩ ልዩ መከራ ያገኙና ከማያውቁት በረሀ በውኃ ጥም እየተቃጠሉና ድካምን እንደሚያገኙትና ሀገራቸውን ለብዙ ጥቅም ያደርሱና ከብዙም ነገር ያዳኑ ስማቸውና ማዕርጋቸው ከሕይወታቸው በኋላ እስከሁን የምንሰማው ስማቸው እየገነነ ሒዷዋል ። በኛ አገር እንኳ ብዙዎች ልክና ስፍር የሌላቸው እንደዚሁ ለሀገራቸው እየታገሉና እያሰፉ ታላቅ ስም እንደተከሉ እስከሁን እንደሚነገርላቸው ማንም ሰው አይስተውም ።

ስንኳን መሰፍንትና መንግሥትም ቢሆን ለሀገሩ ማስቃወሻ ካላደረገ የስም መታሰቢያ አያገኝም ። ገንዘብ ቢበዛ ከሕይወት በኋላ ምንድነው ? ለመንግሥቱና ለሀገሩ የሚደክም ግን ከዕረፍቱ በኋላ ታላቅ ማዕርጉ ነው።ለዚሁም ሰሎምን በምሳሌው ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ትበልጣለች ብሎ ያስጠነቀቀናል። ስንኳን በጥቅምና በቋም ነገር ሳይሆን አሁን በቅርቡ ከኤውሮፓ ውሥጥ አንድ ሰው ሚስት አጭቶ የሰርጉ ጊዜ ሲደርስ ሰርጌን ከመሬት ላይ አላደርግም ብሎ በአይሮኦፕላን ከአየር ላይ ቄሱንና ወዳጆቹን ይዞ ወጥቶ ቃል ኪዳን አድርጎ ፈንጠዝያ ተደርጎ ሻንፓኝ ተጠጥቶ በኪሎሜትሩ ልክ (ፓሹራት)እንደ አንድ (ጃንጥላ የሚመስል) ማውረጃ አይሮኦፕላኑ ከአየር ላይ እንዳለ እነሱ ወረዱ ብሎ አውርቷል ይህም እንደ ስም ነው ። እንዲሁም እጅግ ለወሬው የሚያስደንቅና የሚያስገርም ብዙ ነገር ይሠራበታል።ለወደፊቱም እንደዚሁ አዲስ አዲስ የሆነ ነገር ለመሥራት ይደከሙበታል፤በአይሮኦፕላን በየጊዜው የሚያደርጉትን ለመጻፍ ይቅርና ለማንበብ ያሰለቻል ይህ ሁሉ ለስም መሆኑን መመልከት ያስፈልጋል። ይቅርና ለሞት ከሆነ ከመሬት ላይ መልከም ሁኖ መንገድ የተደለደለለት አቶሞቢል ሲሮጥ ከመንገድ ተስፈንጥሮ ወጥቶ ከገደል ወይም ከጕድባ ገብቶ፤ እንዲሁም ከመልካሙ መንገድ ተገልብጦ ሰዎችና መኪናውስ ይንኰተኰት የለምን?አንድ ሰው መንገድ ሲሔድ እግሩ ከጕድጓድ ወይም በዕንቅፋት ምክንያት ይወድቅና ይሞት የለምን? ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ነው፤ አይሮኦፕላን ወይም አቶሞቢል ነጂ ከራሱ ባልባሰበት ነበር።የሆነ ሁኖ አቶሞቢሎች በሀገራችን እንደበዙ እንዲሁም ዐቀበት ቍልቍለት ደልድሉልኝ፥ አስተካክሉልኝ የማይል ታላቁ የሥልጣኔ ሥራ ከእልፍ አእላፋት የበዙ ንግድንና ጥቅምን የራቀውንም መንገድ ከመ ቅጽበተ ዓይን የሚያቋርጡት አይሮኦፕላኖች በአየራችን የሚራወጡ ያብዛልን እያልኩ ለኢትዮጵያ አምላክ ምኞቴን በየጊዜው ማመልከቴን አላቋርጥም ።

ጥሩነህ ከ ።

ለስ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ሞት ።

እንደ ሞት እርግጥ የለም ፤ እንደ ሞት ቀንም ያልተገለጠ የለም ። ስለዚህ ሰው ሁሉ በ፩፩ ዘመዱና ወዳጁ ሞት በደረሰበት ቍጥር እንደ አዲስ ሁኖበት እጅግ ይደነግጣል።አጥብቆም ይጨነቃል ፤ ይህ ሳይቀር ተስፋ ቈርጦ በማዘኑ ሃይማኖቱን እስኪያስነቅፍ ድረስ ከመጠን ያለፈ ኀዘን ያዝናል ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴም ሞት ስንኳን እኛ ሁላችን እሳቸው እራሳቸው ቅሉ መዋቲነታቸውን ያውቁት ነበር ። ነገር ግን በላይ እንደ ተናገርን ቀኑና ሰዓቱ ስላልታወቀልን በድንገት ሞት ሞቱ እንላለን ። እውነት ነው ፤ ግና ሁላችንም በያንዱ አንዳችን የምንሞተው ሞት ድንገት ነው። (ማለት) ታመን እንኳ ቢሆን ሰዓቱንና ልኩን ስላላወቅነው እንድናለን በማለት ተስፋ ሳለን ነውና የሰው ሁሉ ሞት ድንገት መሆኑ እርግጥ ነው ። ይልቁንም ጀግኖች ወታደሮች ዘወትር እንደዚሁ ናቸው ። ሊሆኑም ይገባቸዋል ። የጀግኖች ሐሳብ ለንጉሣቸው ታዝዘው አገራቸውን መጠበቃቸውን፤ ጠላት ማጥፋታቸውን ያስባሉ እንጂ ድንገት እንሞት ይሆን ብለው አያስቡም ። ካሰቡም ስንኳን ጀግኖች ወንዶች ሊባሉ አይገባቸውም ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴም ለንጉሥ መታዘዛቸውን፤ ለሀገራቸው ሰላም ማድረጋቸውን አሰቡ እንጂ እንደ ሌሎቹ የድንገት ሞታቸውን አላሰቡምና ጀግና ሁነው በጀግንነት አሟሟት ስለ ሞቱ እያመሰገንን እናዝንላቸዋለን።

በዚህ ሰሙን በያደባባዩና በየቤቱ ለደጃዝማች ወልደ ሥላሴ የማያዝን ሰው አልነበረምና ነገር አንሥተን ስንጫወት አቶ የተሻ ወርቅ የሚከተለውን የልቅሶ ግጥም በርሳስ ጻፍ ጻፍ አደረጉና ወረቀቱን ወደ ኪሳቸው ሲያገቡት አይቼ የዚሁ ነገር ሳይሆን አይቀርም ብዬ ተጻፈርሁና ላየው ፈቃድ ጠየቅኋቸው። እሳቸውም በፍጥነት ተኪሳቸው አውጥተው ሰጡኝና አየሁት። እንዲህ የሚል ነው።

ለግርማዊ ንጉሥ ወንድማቸው ማነው፤ ወልደ ሥላሴማ ተቋጥሮ ዘመድ ነው።

እንደዚህ ያለ ሰው ዝምድና የሚወድ። ደግሞ በአውሮፕላን ተቋጥሮ ሊዘመድ

ከዚህ በኋላ እኔንም ያቶ የተሻወርቅ ሐሳብ አነሳሳኝና የሚከተሉትን ሁለት ያህሉ መስመሮች እንደ ዓቅሜ አወናከርሁ

የንጉሥ መልክተኞች ታዘው ተነሥተው። ሊቀሩ ፈለጉ መንገዱን ፈርተው።

ወልደ ሥላሴ ነው የታመነ አሽከር። ከታዘዘ ወዲያ ቢሞትም አይቀር

የጌታውን ምሥጢር ለሰው ሳያወጣ። ተፈጸመ ኵሉ ብሎ መልስ አመጣ።

ዓለማዊ ሲመስል ብፁዕ ኖሯል ለካ ። ነፍሱ ባየር ወጣች ምድር ሳትነካ ።

እቱም ወንድሞቼም ሚስቱም አሽከሮቹም አታልቅሱ ናችሁ ። ሙቶ አለመቅረቱን አስቡ እባካችሁ ።

አለቅስለታለሁ መጥቼ ላርባው ። ከሞተ ዝምዶ ገና ሐያው ነው ።

ወልደ ጻድቅ ጋሼ።

ለደጃዝማች ወልደ ሥላሴ መታሰቢያ

መውወስ ።

ደመወ ዓይን ወርኅ ቀትረ ዓርብ ፣
ወፍጡነ ጸልመ ፡ ገጸ ቀፈረ ፀሐየ ላዕሉ ።
ወልደ ሥላሴ እግዚእ ፡ ቤዘ ፍጥረተ ሰብእ ኵሉ ።
ነፋሳተ ዓውሎ ሐራ ሰማይ ፡
ማእከለ ክልኤቱ አክኑ ሰቀሉ ።
ወእኅዙ ይትከፈሉ ።
ኃይለ ውርዘዊሁ ክዳነ እንበለ ይእኅሙ ወይፍትሉ ።
ይትአመርሂ ወልደ ሥላሴ በፍሬ ሕይወት እክሉ ።
ወበደቂቀ ኃይል አዕፁቂሁ በኃይለ ሥላሴ ዘአሕመልመሉ።
ሰሎሞን ጥቀ ፡ በዘመነ ክብሩ ወብዕሉ ፣
አምጣነ ኢለብሰ አልባሰ ጽድቅ ከመ አሐዱ እምኔ እሉ ።

አለቃ ዳንኤል እ ደስታ ።

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

፩ኛ በታኅሣሥ ፱ቀን መክብብ የሚባል ሌባ ሲሳይ የሚ-ባለውን ሰው ልብስ ሰርቆ በድንገት ስለተያዘ ሌብነቱን አስተ ማምኖ ልብሱን ለመውሰድ ሲል በመጀመሪያ የዘበኛ መጠበ-በቂያ ክፍል ላለው ዳኛ አቀረበውና የዚህን ነገር ብቻ ሲመረ ምረው ሳለ ጥልቅ በሆነው አመራመሩ ይልቁንም ያልታሰበ-ውን ነገር ከአዲስ አበባ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ውሥጥ ባለፈው ዘመን በመጋቢት ወር ፲፱፻፳፪ ዓም ስጋጃና መጋረጃ ሁ ለተኛም በሐምሌ ወር በመቅደሱ በር ያለውን ደማስ ዓይነት መ ጋረጃና ዳባም ካገር ቤት በየሰው ቤት በየቀኑ እየሰረቀ የሸጠውን እቃ ሁሉ እየዘረዘረ ተናገረና ወዲያው መጋረጃውን ከሁለት ክፍ ፎ ተፈሪና ወልደየስ ለሚባሉ መኪና ሰፊዎች ሸጬዋለሁ አለ።

ከዚህ በኋላ እነዚሁኑ መኪና ሰፊዎች ዘበኞች ሲፈላልጉ-ለጊዜው ተፈሪ የሚባለውን አገኙትና ቢጠየቅ መጋረጃውን መግዛቴ እርግጥ ነው ። የገዛሁትም ለት መጋረጃውን የዕጣን-መዓዛ አለቀቀውም ነበረና ጠርጥሬ ሰርቀሽዋል ወይ ብዬ ብጠይቀው ከመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን መስረቁን ነግ-ሮኛል ። መጋረጃውንም አሥራ አምስት እጀጠባብ ሰፍቼ ሸጬዋለሁ ብሎ የመክብብንና የራሱንም ጥፋት አስተባብሮ ስለመሰከረ በታኅሣሥ ፲፫ ቀን በግራዝማች አማረ በኩል ወደ ግርማዊ ንጉሥ ችሎት ሁለቱም ጥፋተኞች ቀርበው አርባ ፵ ጅራፍ ከተገረፉ በኋላ መክብብ የሚባለው ዋናው ሌባ እስከ ዕድሜ ልኩ እንደታሠር፣ ተፈሪ የሚባለው ግን እስከ ፫ወር ድረስ ታሥሮ እንዲቄይ ፍርድ ተቀበሉ ።

፪ኛ) በየነና ኪረታ የሚባሉ ሰዎች በገበያ ውሥጥ እየ-ተሯሯጡ ሲሔዱ በመጀመሪያው የዘበኛ መጠባበቂያ ክፍል ያሉ ዘበኞች የአካሔዳቸውን ልዩነት አይተው ተከታትለው ይዘው ወደ አለቃቸው ዘንድ አቀረቧቸው ።

ይኸውም የዘበኛ ዳኛ በየነንና ኪረታን በምን ምክን-ያት ነው ከሕዝብ የተለየ አካሔድ የምትሔዱት ቀብድላችሁ ነውን ወይስ በድላችሁ ነው አሽከርነታችሁስ የማን ነው ብሎ ቢጠይቃቸው ። አሽከርነታችን የደጃዝማች ዋቄ ነበርን ። ነገር ግን የአካሔዳችን ነገር ከሕዝብ የተለየ ሁኖ ከማስያዝ ያደረሰን ሐረር የጌታችንን የደጃዝማች ዋቄን ግምጃቤት ሰብረን አራት መቶ ዘጠና ብር ስለሰረቅን ወደ አዲስአበባ መጥተን መማ ፘናየጌጥ እቃ ገዝተን ነበረና ምናልባት የሚያውቀን ሰውአግኝቶ ያስይዘናል በማለት ወደ ሰፈራችን ስንሸሽ ዘበኞች ጠርጥረው ያዙን ሰፈራችንም ያልነው ቀኛዝማችፊኖ የሚባል የገሞ አገር ሰው አቃቂ ላይ አለ ለሱ አንድሙክትና አንድ ምንጣፍ ሦስት ጠርሙስ አረቂ ስለሰጠነው ከቤቱ አሰንብቶናል ብለው ተናገሩ ።

ቀኛዝማች ፊኖም ካለበት ሥፍራ ተፈልጎ በዘበኞች እጅ ተይዞ መጥቶ ቢጠየቅ ይህነኑ ሌቦች የተናገሩትን (እጅ መንሻ) ዋጋ ተቀብሎ ከቤቱ እንዲሰነብቱ ማድረጉን ባላመነ ሦስቱም አንድነት የሚገባቸውን ቅጣት እስቲያገኙ ድረስ ታሥረው እን-ዲቄዩ በዘበኞች እጅ ወደ ዘብጥያ አልፈዋል ።

ደጃዝማች ዋቄም የተሰረቀውን ገንዘቤን አገኛለሁ ብለው ሳያስቡት ይህነኑ በላኩበቸው ጊዜ ሐረር ላይ ያለውን ገንዘቤን የአዲስ አበባ ከተማ ዘበኞች መጠበቃቸው ነውና በዚህ አያያዛ-ቸው በጣም ላመሰግናቸው ይገባኛል ብለው ተናገሩና ከሌቦቹ እጅ የተገኘውን እቅና መሣሪያ ገንዘቡን ተረከበዋል ።

፫ኛ በታኅሣሥ ፲፬ቀን አቶ አብዲ የሚባል የሀያ አምስት አለቃ በመጀመሪያ መጠባበቂያ የዘበኛ ክፍል በኩል ከምሽቱ በአራት ሰዓት እየዞረ እንደተሰጠው የሥራ ሕግ ሲመረምር ሳለ የእንግሊዝ ዜጋ የሆነ ሐጂ ሰዲቅ የሚባል አረብ ከተ-ከራየው ሱቅ ሲደርስ መብራት ሲበራ አይቶ ከዚህ ሱቅ አለ-ወትሮው መብራት የሚበራበትን ምክንያት ለመረዳት የሚገባኝ ነው ብሎ ወደ ሱቁ ቀርቦ ሁኔታውን ሲመለከት ከሱቁ ውስጥ ሙላቱ የሚባል ሰው ብቅ አለና እኔ በሐጂ ሰዲቅ በኩል ሱቁን እንድጠብቅ የተቀጠርሁ አሽከሩ ነኝ አንተም መብራት ሲበራ አይተህ መምጣትህ ሌባ ቢሆን ልትይዝ ነበረና ነገ ለጌታዬ እስትነግርልህ ድረስ ላሁኑ ይህንን ሰሀን እንድትቀበለኝ ፈቃ-ድህ ይሁን ብሎ አቀረበለት። አቶ አብዲ ግን እውነተኛው ወታደር ነውና የዚህን ሰውዬ አነጋገርና አደነጋገጥ ብቻ ደመ-ለከት ነበረና ሊሰርቅ ማሰቡን ስለተረዳው ለእኔ መንግሥት የሚሰጠኝ የወር ደመወዝ የሚበቃኝ ነውና የሰውን ገንዘብ በከንቱ ለመቀበል አያስስበኝም ይህኑም የጠየቅሁህ በታዘ-ዝሁት በውነተኛው ሥራዬ ነው እንጂ ይህነን ለመቀበል ሐሳብ ኑሮኝ እንዳይመስልህ ። አሁንም ቢሆን አንተ የዓረብ አሽከር መሆንህን አውቃለሁና ጠንክረህ መጠበቅ ነው ብሎ እንዳይ ገነግን አፅናንቶ የመሔድ ምልክቱን አሳይቶ በስተሱቁ ኋላ ተሰውሮ ሙላቱ የሚባለው የሚያደራጀውን የስርቆት መን-ገድ ይመለከከተው ጀመረ ።

ከዚህ በኋላ ሙላቱ ከውጭ ሌባ ጋራ ተነጋግሮ ኑሮ ያ የተነጋገረው ሌባ በመጣለት ጊዜ መስኮቱን ከፍቼ የምሰጥህን ዕቃ ሁሉ ተቀበለኝ እያለ ሲናገር አቶ አብዲ ስለሰማው በበሩ በኩል ወዲያው በፍጥነት ዞሮ ሙላቱን ያዘውና የሙላቱን ምኝታ ቢገልበኘው አንድ መትረየስ ሽጕጥና የአቡጀዲ ጣቃ ሌላም ዕቃ በየዓይነቱ ምንጣፉን አልብሶ ስላገኘ ሱቁን ሲጠ-ብቅ አድሮ በጧዋት ለሐጂ ሰዲቅ አስረክበ ከሙላቱ ላይ የያ-ዘውን የተሰረቀውን ዕቃ ሁሉ አንድነት ከሌባው ጋራ ይዞ

ወደዘበኛ አለቃው ወደግራዝማች አማረ ዘንድ አቀረበውና እንደምን አድርገህ ነው የሰረቅኸው ብለው ቢመረምሩት ሥራዬ እርግጥ ሱቅ መጠበቅ ብቻ ነው ። ነገር ግን ሐጂ ሰዲቅ የሚባለው ጌታዬ ሱቁን ዘግቶ አስረክቦኝ ሲሔድ እንደመሸንት ብዬ የበሩን ቍልፍ ተከፍቶ ውሥጥ ሰርቄ እጅ አድርጌ ቈይቼ ነበረና አራት ሰዓት ሲሆን የሚመለከተኝ ሰው አይገኝም መስሎኝ ሽኰጡንና ጣቃውን አውጥቼ፤ደግሞ ሌላም ዕቃ ላወጣ በሰናዳ አቶ ዓብዲ ይዘኛል ። መጀመሪያም መጥቶ መብራቱን እንዳበራሁ መጠየቁ እርግጥ ነው ብሎ ለላመኑ ሐጂ ሰዲቅን አስጠርተው የተሰረቀ ዕቃውን አስረከቡት ።

ሐጂ ሰዲቅም ከዚህ በላይ እንደተነገረው የስርቆቱንና የሌባውንም አያያዝ ካስረዱት በኋላ እኔ ከሌብ ያድንልኛል መስሎኝ እምነቱን በሱ ላይ አድርጌ ደመወዝ እየሰጠሁ የቀጠርሁት ጠባቂዬ እራሱ ሌባ ሁኖ ሊያጠፋኝ ሲል የመንግሥት ዘበኛ በጥርጣሬ ነቅቶ ከብዙ ከማራና ከብዙ ጕዳት ተከላክሎ ስላዳነኝ መቸውንም ቢሆን የከተማ ዘበኞችን የትጋትና የውቀት ሥራ ሳላቋርጥ በየጊዜው እንዳመሰግን የሚገባኝ ነው ብሎ ደስታውን እያወራ ወደንግዱ ተመለሰ።

እነዚህ የከተማ ዘበኞች የሚይዙትና በምርመራም የሚያገኙት ጥፋት እንደምንሰማው በኤውሮጳ አገር ያሉ ዘበኞች የሚሠሩትን የዘበኝነት ሥራ እየመሰለ የዘበኝነቱ የጥበቃ ሥራ እየተሻሻለና እየተከናወነ መሔዱን ከዚህ ቀደም የተነገረላቸው ደስ የሚያሰኝ የዘበኞች ሥራ ሳያስረዳ አልቀረም። ወደፊትም ዳግም ልዩ ልዩ የሚያስመሰግን ሥራ ለመሥራት እንደሚያስቡ ከዚህ በላይ የተጻፈው ቃል የበቃ ምስክራቸው ነው ብሎ ለመናገር ይችላል። ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ፣ ደጉ ይመር።

ይድረስ ከቶ ተመልከች ።

ባታኅሣሥ ፩ቀን ስለጕዳይህ ወደ ገበያ ወጥተህ በጣም ያልተረጋገጠ የሚያሳዝን የወሬ መርዶ ድንገት አግኝቶህ ስላዘንክበት ነገር የልማዱን ያህል እግዝአብሔር ያጥናህ ። ርኅራኄ ካልተደረገለት በቀር በዚህ ዓለም ውሥጥ መቼም ቢሆን ከሰው ዘንድ ስሕተትና ጥፋት አይታጣም ። ከዚህም የበለጠ ጥፋት እየተገኘባቸው ዘብጥያ የታሠሩትን ሰዎች አንተም ሳታውቃቸው አትቀር ። ምንም ጥፋታቸው ቢበረታ ምግብና ልብስ አልተከለከሉም።ልብስ መግፈፍ የዳኛ ሥራ አይደለም ። የሕዝብ ሥራ ለሚሠሩ መንግሥት ለማያውቁ ወምበዴዎች ነው። ምን ጊዜም ሐሜት ከዳኛ ላይ ርቆ እንዳያውቅ ይህ ደምሴ ታሥሮ ውሎ አድሮ አማላጅ ልኮ ቢሆን ያሳግ ነበር።ሌባም ቢሆን ሁለት፤ሦስት ጊዜ ካልሆነው በመጀመሪያው ጥፋት አይገረፍም የዚህ የፍርዱን ሥራ አኳኋንና ደምቡን የማያውቅ ሰው ግን አስቀድሞ መረዳትና ማወቅ ይሻለዋል ፤ ዳኛ ማለት የእግዚአብሔር ሹም ማለት ነው ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አንድም ሰው ሊሾም አይሆንም ፤ ይህ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሾመ ሰው በዚያው በተሰጠው አእምሮ እንደ ተገለጸለት በሚገባው ሕግ ርኅራኄ የእግዚአብሔር ልማዱ ስለሆነ። በፍጡር ላይ ፍጡር መጨከን የተገባ አይደለምና ፤ የአቶምቢል ደምብ መጠባበቂያ ጽሕፈት ቤት ሹም በሱ በኩል ያሉትን አሥረኞች ደምሴ እንዲያቀርብ ሹሞት ስለነበረ ከዚህ ከአቅራቢነቱ ተከልክሎ እንደዘበኛው ሕግ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ጥፋት መቀጫ ይከፍላል። በሦስተኛው ጥፋት ከሥራው ይወጣል ተብሎ የተጻፈውን ደምብ በመከተል ያንድ ጊዜ ጥፋተኛ በመሆኑ አምሳ ብር መቀጮ ጥሎ በሁለት ዋስ መፍታት የተደላደለና የተገባ ፍርድ ነው። ነገር ግን ፩ምስክሮች መስክረውበት ገዳዩ ተረታ ሳልከው ነገር ፪ምስክሮች ተቈጥረው ሦስት ምስክሮች መስክረው ተሸምተው በዕድል ቈይቷል እንጂ ተመልከቼ ገዳዩ ተረታ ያልከው ጆሮህ አደላድሎ አልሰማልህም ። ሰሚው ።

ስለ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ አመጣጥ ።

ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ዮሐንስ ገና ፓትሪያርክ ሁነው ሳይሾሙ ፤ ኢትዮጵያን ለማየት ብዙ ምኞት ነበራቸው ። ፓትሪያርክ ሁነው ከተሾሙ ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ ሔጄ የሃይማኖት ልጆቼን አይቼ እመለሳለሁ እያሉ ሲያስቡ ነበርና ፤ ባለፈው ዓመት የኢትዮጵያ መንግሥት አለጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ዘውድ ጭነው መንግሣቸውን ቢሰሙ ወደ ኢትዮጵያ ሔጄ እንኳን ደስ አለዎ ብዬ ለመመለስ ዋና ምክንያት አገኘሁ ብለው ለመነሣት ቍርጥ አሳብ ካደረጉ በኋላ በመካከሉ ከኢትዮጵያ መምህራን ውሥጥ ተመርጠው ጳጳሳት እንዲሾሙ የታሰበው አሳብ በርሳቸው ደግነት ፤ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ትጋት፤ ለጳጳስነት የተመረጡት መምህራን ወደ ምድረ ግብፅ ወርደው ነበርና በዚህ ምክንያት ባለፈው ዓመት ሳይመጡ ቈይተው ነበር ። አሁን ግን ኢትዮጵያንና የሃይማኖት ልጆቻቸውን ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱናንና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን፤ ሕዝቡንም ሁሉ ለመጐብኘትና ለመባረክ እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን ጊዜ ስላደረሱ በታኅሣሥ ፲፩ ቀን ከምድረ ግብፅ ተነሥተው በታኅሣሥ ፳፱ ቀን ጥዋት ጂቡቲ ደረሱ ።

እስከ ጂቡቲም ሊቀበልዋቸው የወረዱት ብፁዓን ጳጳሳት፤ አቡነ አብርሃም፣ አቡነ ጴጥሮስ፣ አቡነ ሚካኤል ፣ አቡነ ይስሐቅ፣ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ፣ ደጃዝማች ገድሌ ፣ ደጃዝማች መስፍን ። ከአድባራቱ አለቆችም የሔዱ ነበሩና በደስታና በክብር ተቀብልዋቸው ።

ወዲያውም የምስር ቆንሲል ሙሴ ሚካኤል ፓትሪያርኩን ለመቀበል ወርደው ነበርና በደኅና ጂቡቲ መድረሳቸውንና ማታውኑ ወደ ዲሬድዋ መሳፈራቸውን ፤ ከፓትሪያርኩም ጋራ የመጡትን ሰዎች ቍጥራቸውን ጨምረው ለውጭ ጕዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ለክቡር ብላቴንጌታ ኅሩይ በቴሌግራም አስታወቁ ። በታኅሣሥ ፳፫ ቀን ከጥዋቱ በ፪ ሰዓት ድሬዳዋ በገቡ ጊዜ ካህናቱም መኳንንቱም ብፁዕና ቅዱስ አቡነ ዮሐንስን አክብሮ ባማረ አቀባበል ተቀበላቸው ።

ከባቡሩም ሲወርዱ የሚቀመጥዋቸው አቶሞቢሎች ቀርበው ነበር ። እርስዋው ግን ለማየት እንዲመቸኝ ብለው፤በቀኝና በግራ ተሰልፎ የቆመውን ሰው እየባረኩ እስከ ቤተ መንግ-

ሥቱ በአግራቸው እየሔዱ ደረሱና ለግርማዊ ንጉሥ ተሠርቶ የነበረው አዳራሽ ታድሶ እንደሚአስፈልግ ሁኖ አጊጦ ነበረና በዚያ ዓርፈው የከህናቱን ወረብ ሲያዩ ቈይተው ሦስት ሰዓት ሲሆን ተነሥተው ወደ ቤተመንግሥቱ እንደ ገቡ በቴሌግራም ሸማን ።

ወረቡም ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው መጀመሪ« አበ ኵልን አበ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት አስተጋብአነ ለስብሐተ እግዚአብ ሔር«ሁለተኛም«ፈኑ ብርሃነከ ዮሐንስሃ ሊቀጳጳሳት ወጽድቀከ ኃይለ ሥላሴ ውስተ ኢትዮጵያ ቅድስት ሀገረ አስከለ ማርያም ብለው ወረቡ ።

በአዲስ አበባም ብፁዕ ቅዱስ ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስን ለመቀበል በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ መሰናዳት ተይ-ዟል ።

ብርሃንና ሰላም ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ዮሐንስን በደኅና ያገባዎ እያለ መልክም ምኞቱን ያቀርብላቸዋል ።

ቁጥኝን እንዴት አድርጎ ስለ ማከም ።

የኤውሮጳ ልዩ ልዩ መንግሥታት ቂጥኝና ጨብጥ ይል-ቁንም ቂጥኝ በሕዝብ ውሥጥ በለሚያደርገው አደጋ በውነት ደንግጠአል ።

በዓለም ውሥጥ ሞትን አጣድፈው የሚያመጡ በሽቶች ቱቤርክሎስ ፡ ካንስር ፡ ቂጥኝ ናቸው ። በመቶ ከሚሞቱት ሰዎች ከመቶው ሰባ አምስቱ በነዚህ በሦስቱ በሽቶች ነው የሚያልቁት ። ከዚሁም ሠላሳ አምስቱ በቂጥኝ ጠንቅ ነው የሚሞቱት ። ከሚወለዱት ሕፃናት ከመቶው ሠላሳው ቂጥኝን እንደወረሱ ይወለዳሉ ።

የዚህም ሁኔታ በአፍሪክ የባሰ ነው ። ምክንያቱም ብዙ ነው ። መጀመሪያ በአየሩ ፡ ሁለተኛ ጤናን የመጠብቅ ሥራ ስላልተዘጋጀ ፡ ሦስተኛ በሽተኞች ራሳቸውን ለማሳከም ስላል ጣሩ ነው ። ስለዚህ የመካከል አፍሪክ ሕዝብ ቢቈጠር በመላው-ቂጥኝም ሁኖ ተገኘ ። ወደ ሆስፒታል ከሚገቡት በሽተኞች ከመቶው ስድሳ ስድስቱ ቂጥኛሞች ሁነው ተገኙ ። እንዲህም ሁኖ ከታየ በኋላ ማስደንገጡ የታወቀ ነው ።

ነገር ግን የዛሬው ዘመን እውቀት ይህን ያህል ሠራዊት የሚፈጀውን የቂጥኝን በሽታ ፈጽሞ ለማከም መድኃኒት ስላ-ገኘ ደስ ይለናል ። ይህ ሁሉ ሲሆን ተካንስርና ተቱባርክሎስ ፈጽሞ የሚያድን መድኃኒት እስከዛሬ ባለመገኘቱ ብጣም ያሳዝናል ። ተቂጥኝ ለመዳን የሚፈልግ ሰው ሐሳቡን ቀኑርጥ አድርጎ የሚገባውን መድኃኒት መፈለግ አለበት ። ከጥንት የታወቀው መድኃኒት በዜቃ ነበር ። ከዚያ ወዲህ በርሱ ፈንታ የተተከው አርሴና ቤንዞል ይባላል ። ነገር ግን ከስምንት ዓመት ወዲህ ሐኪሞች አንድ አዲስ መድኃኒት ማፍቀር ጀምረዋል። ይህም ከተገኘ ወዲህ በብዙ ተፈትኖአል ። በሽተኛውንም ሳይጐዳ በሥራው ብርቱ እንደሆነ ተገኝቷል ።

ይኸውም መድኃኒት ኪንቢ ይባላል ። በፈረንሳይ አገር ተሠርቶ መላው ዓለም ይታከምበታል ። የፓሪስ ከተማ ሆስ-ፒታሎች የፈረንሳይ መንግሥት የጤና ሚኒስተር፡ የጦር ሚኒስተር፡ የቅኝ አገር ሚኒስተር፡ የቂጥኝ ማከሚያ ቤታቸው በደንብ ተቀብለውታል ።

ለሚመጣው ጋዜጣ አንዳንድ የሆነውን ምሳሌ እያሳየን እንዴት እንደሚሠራና እኛም ቂጥኝን ያድናል ብለን እንዴት ተስፋ ማድግረጋችንን እንገልጣለን። ዶክቶር አምባር።

ስለ ኢትዮጵያ ሰብል ።

ወሬ ስንሰማ ዘንድሮ በኢትዮጵያ ሰብል በኢያገሩ ሁሉ ብዙ መልክም ሁነዋል ማለትን ሰምተን ነበር።አሁን ግን ከወ-ረይሉ ጀምሮ እስከ ትግሬ ዝናም እንደከረምት ይዘንግል አሉ፡ ይልቁንም በምዕራብ በኵል ከጉደር እንሥቶ እስከ ወለጋ ድረስ ክፉኛ ይዘንማል እህሉም አልታጨደም አሉ እጅግ የሚያሳዝን ነገር ሆነ።አሁን ዝናቡ ያልነካው ይኸን መሐል ሸዋ ከአዋሽ በላይ ያለውን አገር ነውና ይኸነኑ የዝናቡ አደጋ ሳያገኘው የእርሻ ምኒስቴሩም ሕዝቡ ቶሎ እህሉን እንዲወቃው በአዋጅ ቢያስገድደው በለርስቶቹም ገበሬያቸውን ኢያስቸኰሉ ቶሎ ቶሎ ቢያስወቁት እህሉ ይተርፋል። በቸልታ ቢቈይ ግን የታች አምናው እረሐብ ደግሞ እንዳይመጣ ያስፈራል። ይኸን ምክር መጻፍ የሚገባ ለሕዝቡ ለገበሬው ነበር።ግን ጆርናሉን የሚያነቡት ከ፪፻ ሽህ ሰዎች የማይበልጡ ስለሆነ የማይጠቅም ነው እነዚሁም ፪፻ ሺህ ያልናቸው በየከተማው የሚኖሩ ናቸውና ስለዚህ የእርሻ ምኒስቴሩ የሚያስፈልገውን በፍጥነት እንዲያ-ደርጉልን በማክበር እንለምናለን ። ፊ ዴፊሳ ።

የከተማ ወሬ ።

ታኅሣሥ ፰ ቀን በ፲ ሰዓት የአይሮፕላን ነጅዎችን ማስተማር የሚሆን ከኢጣልያ አገር የመጣ ትንሽ አይሮፕላን ወደ አዲስ አበባ ገባ። ከዚያ በኋላም ትንሽ ቈይቶ ንሥረ ተፈሪ ጳስጣ ይዞ ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ ።

የአይሮፕላን መብረር ።

ባለፈው ሰሞን ደሴ ላይ በሆነው በአይሮፕላን አደጋ ምክንያት ጥቂት ቈስሎና ሰውነቱም ተናውጦ በደሴ ሆስፒታል ተኝቶ የነበረውን ሚካኤልያን ለማምጣት አይሮፕላን በታኅሣሥ ፳፫ ቀን ከጧቱ በ፩ ሰዓት ተኩል ከአዲስ አበባ ተነሥቶ ልክ በሦስት ሰዓት ደሴ ደረሰ ።

ይኸውም አይሮፕላን ወደ ደሴ ሲሔድ አንድ ሰው ከወሎ ግዛት ውሥጥ የሆነ የፈታውራሪ አርቢሴ የባላባቱ የወንድም ልጅ ወደ ግርማዊ ንጉሥ ችግሩን ለማመልከት መጥቶ ነበርና ግርማዊም እንደሚያስፈልግ ጕዳዩን ጨርሰው ደስ ካሰኙት በኋላ የመንገድ ድካም እንዳይጐዳው በአይሮፕላን እንዲሔድ ፈቃዱ መሆኑን ቢያስታውቁ ግርማዊ ንጉሥ ፈቀዱለትና የሚያስፈልገውን የብርድ ልብስ ሁሉ አዘውለት የሚገባውን ጥንቃቄ ተደርጎለት በዚህ አይሮፕላን ተሳፍሮ ሔደና በደኅና ደሴ ደረሰ።አይሮፕላኑም በአምስት ሰዓት ተሦስት ሩብ አዲስ አበባ ተመልሶ ገባ ።

የመንገድ ጥቅም ።

ወደ ጅሩ የሚወስደው የካሚዮን መንገድ አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንገዱ ተደልድሎ ካሚዮን የሚመላለስበት ስለሆነ ሕዝቡ ሁሉ በደስታ ተመልቷል። ክራይ እየከፈለ ለመሒድ ብዙ ሰው በየመንገዱ እየጠበቀ በፍራ እየጠበበው በከንቱ ደክሞ ይመለሳል ።

አውቶሞቢል የሔደበት በፍራ ለእህል አይበጅም የሚሉ የከፉ ሰዎች መላ ተሰምቶ ስለነበረ በመጀመሪያው ጊዜ እምብዛም አልተናፈቀም ነበር ። አሁን ግን ጥቅሙን ስለተረዱት እኔ ልሳፈር እያሉ በመሽቀዳደም በካሚዮኑ ላይ ትንቅንቅ ብቻ ሁኖአል ። ነገር ግን የመሳፈሪያው ስፍራና ጊዜ በሥርዓት ስላልተወሰነ ፡ የክራዩንም ዋጋ ነጂው እንደፈቃዱ በግምት የሚጥለው ስለሆነ ከሠራተኞቹ የዚህ ድንጋጌ ጕድሎአል ብዬ ላመልከት የሚገባኝ ነው ። ከሳምንት ሁለት ጊዜ እንኳ ደንበኛ ካሚዮን ለመንገደኛና ለዕቃ ቢደነገግ ጥቅሙ ክልክ ያለፈ ይሆን ነበር። እነሆ ከጅሩ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት አንዱን ሰው ከ፪ እስከ ፫ብር ቢያስከፍሉት በደስታ ይኳዛል። እንዲሁም ደግሞ በደነበና በየሌላውም ስፍራ እንደማቢያ መሳይ አድርጎ ቀጠሮ ቢሰጡት መንገደኛው በዝቶ ቢተርፍ እንጂ ካሚዮን ባዶውን ይሄዳል ማለት ብርቱ ሐሰት ነው ። ዳሩ ግን አንድ ነገር አለ ። ጥቅምን ከብዛት መፈለግ ይሻላል እንጂ በመጀመሪያ ዋጋ አብዝቶ ማስታወቅ መንገደኛውን የሚያሳንስ ይመስለኛል ፤ ማለት ከጅሩ እስከ አዲስ አበባ በላይኛው ግምት ቢሆን ከዚያም ወዲህ ባሉት አገሮች እንደ መጠኑ ቢወሰን በደስታ ይፈጸማል።ደግሞ የካሚዮኑ ጕዞ ዛሬ በ፪ ቀን ነውና ወደፊት በ፩ ቀን እንዲገባ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም የሚበጀው አሮጌውን ካሚዮን ትቶ አዲሱን ያልፈጨውን መተካት ነው ።

እኔ ከአገሬውና ከመንገደኞቹ የሰማሁትን ለመግለጽ ብዬ ነው እንጂ የሥራው አላፊዎች ብልሆች ሰዎች እንዳሉበት አውቃለሁና እነሱ እንዲተጉበት እያስታወስሁ ነገሬን እጨርሳለሁ።

መንገደኛው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S. E. A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንዖር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኩላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊ.ን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።

የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፪
6me ANNÉE № 2

ሐሙስ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 9 JANVIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣሁት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ለሀገር ፍቅር ብሎ ለሚሞት ሰው መታሰቢያ

ታላቁ ናፓሊዎን የመላ ኤውሮፓ ንጉሠ ነገሥት ኤውሮፓን እንደ ገል ቀጥቅጦ፥ እንደ ሰም አቅልጦ የገዛው ኃያሉ ንጉሥ ከመስኮብ አገር ሕዝቦች ጋራ ጦርነት አድርጎ ሲዋጋ ሳለ ጦርነቱም ኃያል ነበርና በጦርነቱ መሃከል የናፓሊዎንን አንዱን የጦር አበጋዙን የመስኮብ ጦር ከንጉሡ ለይቶ ለብቻው ከነአርበኞቹ ነጥለው ስላስቀሩት ። ናፓሊዎንም ሠራዊቱንና አርበኞቹን በመነጽር ሲመለከት ሳለ የጦር አበጋዙ በአንድ በኩል ከወታደሮቹ ጋር ከወገኑና ከደጀኑ ተቈርጦ ለብቻው መለየቱንና መቅረቱን ናፓሊዎን አይቶ ከተረዳ በኋላ ያንን ተቈርጦ የቀረውን የጦር አበጋዙን ለማፅናናት ሲል ወረቀት ጻፈለትና የጻፈውንም ወረቀት በእጁ ይዞ ከአሽከሮቹ ውሥጥ አንደኛውን ታማኝ አሽከሩን ጠራና ይኸነን ወረቀት ለጦር አበጋዙ ስጥ ብሎ አዘዘው።ያም ታማኝ ወታደር ደስ እያለው እሞታለሁን ሳያስብ በጠላቶቹ ጦር መሃከል መላክቱን ይዞ ሲሔድ ለጊዜው ይዋጉ ነበርና ያ የናፓሊዎን መላክተኛ በድንገተኛ ዓረር እግሩን ስለተመታ እተላከበት ቦታ መልክቱን ለማድረስ ስላልተቻለው የጌታውን መልክት ለማስቀረት የማይቻለው ስለሆነም የተመታውን እግሩን እየጐተተ ወደመጣበት ቦታ ተመልሶ ሔደና ለናፓሊዎን እተላኩበት ቦታ ሳልደርስ እግሬን በዓረር ተመታሁ ስለተመታሁም መልክትህን ሳላደርስ በዓረር ተመትቼ በመቅረቴ በጣም እዝናለሁ ብሎ የሰጠውን ወረቀት በጁ መለሰለት ።

ናፖሊዎንም ዳግም ሁለተኛውን ታማኝ አሽከሩን ጠራና ይኸነን ወረቀት ይዘህ ሒድና ተቈርጦ ለቀረው የጦር አበጋዜ ስጠው ብሎ አዘዘው። ይኸውም ታማኝ የናፖሊዎን ወታደር ትእዛዙን በደስታ ተቀብሎ ሲሔድ ተነግና እሱም ይህ መላክተኛ ብልህና ሥልጡን ነበርና የጌታዬን መልክት ያለመሰናክል ለማድረስ ምን ምክንያት ይሻለኛል ብሎ አሰበ አስቦም አልቀረ።እንደ ሴት ልብሱን ለውጦ ለብሶ ወረቀቱን ይዞ እታዘዘበት ቦታ ደርሶ ወረቀቱን ሰጠና ናፖሊዎን ወዳለበት ተመልሶ ሲመጣ መልክቱን ለማድረስ ወደዚህ ስመጣ እንደሴት የለበስኩበት ምክንያቱ የጌታዬን መልክት ሳላደርስ በመሃከሉ መሰናክል እንዳያገኘኝ ብዬ ነበር ። አሁንስ የጌታዬን መልክት በቀጥታ አድርሼ ከፈጸምኩ ወንድ ልጅ ነኝና ጥንቱንም ሰው ሲፈጠር ለሞት ነው እኔ ሐሳቤና ችግሬ የጌታዬን መልክት እስከደርስ ድረስ ነበር። ለመንግሥቱና ለሀገሩም ያላገለገለና ሕይወቱን ያላሳለፈ ምንም የሀገር ፍቅር አለበት ተብሎ አይታሰብምና ከእንግዲህ ወዲህ መከራም ቢያገኘኝ ደስታ እንደወንድ ለብቼ ልሒድ ብሎ በጦሩ ውሥጥ አቋርጦ ወደጌታው ዘንድ በደኅናው ደረሰና ወረቀቱንም እንደተላከው ማድርሱን ለናፖሊዎን አስታወቀው።ናፖሊዎንም መልክቱን ስላደረሰለትና በድፍረት ትእዛዙን ስለፈጸመለት ለሀገሩና ለመንግሥቱ ማሰቡን አጠገቡ ላሉት ሰዎች አስረድቶ እንደ ጀንበር የሚያበራ ሊሻን በደረቱ ላይ አደረገለት ይባላል ።

እንደዚሁም ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ለሞታቸው ሳይፈሩ በማያውቁት አውሮፕላን ወጥተው ለመንግሥታቸው እረዳለሁ ብለው የሞት አደጋ በመቀበላቸው እንደ ሐውልት የተመሠረተውን ስም ስለተቀበሉ የሀገር ፍቅር በልባቸው ያሳደሩ ሰዎች ሁሉ ሳያስቧቸው አይቀሩም ። ዳሩ ግን ሐዋርያቶች እንኳን ለጌታቸው ሲሉ በዮዳይነቱ በታላቅ ፈተና እየሞቱ ሰማዕትነትን ተቀበሉ ።

ከመልካም ሽቶ መልካም ስም ይሻላል ከብዙኅ ባለጠግነት ክብርና ሕይወት ይበልጣል ።

ነገር ግን ከሀገሩና ከመንግሥቱ፡ከጌታው አብልጦ የራሱን ጥቅምና ነፍሱን የሚወድ ሁሉ ሐሳበ ጐዶሎ መሆኑ ነውና መቼውን ለሰው ልጅ የማይቀረውን ሞት ከማማረጥ እንደ ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ መሞት የተመሰገነ መሆኑን ለብርሃን ተመልካቾች አሳስባለሁ።

አክባሪ ወንድማችሁ በቀለ ዘለቀ ።

ዘመን ያነሣውን ጊዜ የወለደውን ተንኰል ስለማወቅ ።

ከዕለታት ባንድ ቀን የልብ ወንድሜ የሚሆን ሊጠይቀኝ ከቤቴ መጥቶ ሳለ ። ምንጊዜም ቢሆን ተማማኝ ባልንጀራ ሲገናኝ ። የሚያስፈልገውን ነገር መጫወቱ አይቀርምና ለጊዜው ትዝ ያለኝን ነገር ልጠይቀው ወደድሁ ። ጥያቄውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ዘመን የወደደው ጊዜ የወለደው ምን ይመስልሀል ብለው። ታማኝ ወንድሜ ሆይ ፣ ይህን ሳታውቅ ትኖራለህን ደህንማ ካላወቅህ ምን አለሁ ትላለህ አለኝ ። ነገሩን ባልረዳው ነው እንጂ ካወቅሁትማ ወንድሜን በጥያቄ አላደክምህም ነበር አልሁት ። ካልተረዳኸውስ ስም ለበስ የሚሉት ቅኔ ነው ። በዛሬው አማርኛም ረቂቅ ፖለቲክ ይባላል ። ለሰሚው የሚጠቅመው አስመስሎ ተናግሮ ሰውየውን የሚያታልል ነው አለኝ ። በቀድሞ ዘመን እንደ መስክረኛ ፀሐይ ደስ የሚያሰኝ የተቀባ ንጉሥ በምግባርና በሃይማኖት፣ በኃይልና በዕውቀት፣ በፍርድና በለጋስነት ፡ በፍቅርና በጌትነት ፡ ከዚህ ይቀረዋል የማይባል የተዋበ ንጉሥ ነግሦ ነበር ይባላል ። ሠራዊቱም እንደ አንበሳ የሚገረሙ እንደ ተኵላ የሚፋጠኑ ኃያላን ነበሩ ። ግን ከነድማሳ ሥንዴ ውሥጥ ብዙ ክርዳድ እንዳይጠፋ በውሥጣቸው አንዳንድ ቀበሮዎች ነበሩ ይባላል ። ቀበሮ ሳይሞት የሞተ መስሎ ተኝቶ ። ከሆዱ ክፉ ሽታ እያወጣ ። ቃናናሽ ፍጥረቶች ምግባቸውን ለመፈለግ ከጠገቡ ሲቀርቡ አዘንግቶ ይዞ ያጠፋቸዋል ።

የዚህን ቀበሮ አመል የያዘ ሰው ማናቸውንም ፍጥረት ለጊዜው ሊያታልልና ሊያጠፋ ይችላል ።

የራሱን ጥቅም ረቆ ጠልቆ ሲፈልግ የብዙ ሰው ጥፋት አያሳዝነውም። ኃጥኡን ጻድቅ፣ ጻድቁን ኃጥእ አስመስሎ ሲናገር ይከናወንለታል፡ ለብርሃናዊው ንጉሥ እግዚአብሔር በሰጣቸው ሥልጣን እያደር ይህ ተንኰል ተገልጾ የማታ ማታ ሐሰት ድል ሳይሆን ይቀራል ብዬ አልጠረጥርም።ወንድሜ ሆይ የኢትዮጵያ ልጅ እግዚአብሔር ቀብቶ ላነገሠው ንጉሥ በፍጹም ልብ መገዛት የሚገባ ነው ። ሮሜ፣ ም ፲፫ ቍ፪ ወዘሰ አበየ ተኰንኖ ለመኰንን ትእዛዘ እግዚአብሔር አበየ ብሏል ። የበላኀር እናት አባት አሮጌ በሬ አርደው ልጃቸውን የዳሩ እንደሆነ የርሻ በሬያችንን አርደን ድረንህ እያሉ ሲወቅሱት ይኖራሉ ። እግዚአብሔር የቀባው ንጉሥ ሰፊ ሀገር፥ ብዙ መንደር ፡ ፈረስ በቅሎውን፣ ጫሜና ሙጣውን ለሚወደው ሲሰጥ በዚህ ጊዜ ይህን አርጌልህ አይልም ። ይልቁንም በየጊዜው የሚሠሩት የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ቸርነት በየክፍሉ በይጻፍ አንድ ሰው ጽፎ ሊፈጽመው አይችልም ነበር ። ለተናጋሪው ከማያስመሰግን ፡ ለሰሚው ደስ ከማያሰኝ ከሐሰት ወሬና ከምቀኝነት ተጠብቀን ። ለሰላማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዕድሜ እየለመን በያለንበት በቀና ልብ ብናገለግል ለኛም ፈጣሪያችን እንዲለመነን የታወቀ መሆኑን ማንም አይስተውም ።

ጸጋ ሥላሴ ጌታሁን ።

መልስ

አንድ ፭ሰዎች በከተማ ውሥጥ በአኤሮፕላን ተልከው የሔዱትን መላክተኞች ደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ድንገተኛ አደጋ አግኝቷቸው ቢሞቱ ፈርተው ቀሩ እያሉ የመንግሥቱን ታማኞች በሐሰት ስማቸውን እያረከሱ ያወራሉ ። ከነዚሁም አንዱ ወልደ ጻድቅ ጋሼ የሚባለው ታኅሣሥ ፲፩ቀን በወጣው ብርሃንና ሰላም በመጀመሬው ርቀቱ ሰው ሁሉ በ፭፩ ዘመዱና ወዳጁ ሞት በደረሰበት ቍጥር ተስፋ ቈርጦ በማዘኑ ሃይማኖቱን እስኪያስነቅፍ ከመጠን ያለፈ ኀዘን ያዝናል ይላል ።

እውነት አንድ ፭ ሰዎች በጣም የሚወዱት አቅራቢያቸው ሰው ሲሞትባቸው እጅግ ያዝናሉ እንጂ በ፩፩ ዘመዱና ወዳጁ ሞት በደረሰበት ቍጥር ሃይማኖቱን እስኪያስነቅፍ ከመጠን ያለፈ ኀዘን ያዝናል ያለው ፈጽሞ ውሸት ነው።ይልቁንም አሙሮ ፓውያን ኀዘናቸው የቀለለ መሆኑን ያለ እሱ የማያውቅ የለም።

፪ኛ፣ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ለንጉሥ መታዘዛቸውን፡ለሀገራቸው ሰላም ማድረጋቸውን አስቡ እንጂ እንደ ሌሎቹ የድንገት ሞታቸውን አላሰቡም ይላል ።

ስመ ጥሩውን ክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ለማመስገንና የሌላውን ሰው ክብር ማሳነስ አያስፈልግም ነበር ። ሌሎች የምትላቸው የኢትዮጵያ ጀግኖች ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ እንደጻፉት ለሀገራቸው ሰላም ለሚሆን ነገር ስንኳን ንጉሥ አገዘዋቸው በፈቃዳቸውም ቢሆን ደማቸውን ለማፍሰስ ሕይወታቸውን ለማሳለፍ የተዘጋጁ መሆናቸውን የቀድሞ ሥራቸው ይመሰክራል ። ከቶ ምን ጊዜ ይሆን የድንገት ሞታቸውን አስበው ለንጉሣቸው እንታዘዝም ያሉት ? ። እንዲያው በማይገባህ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጀግኖች ያዋረድህ መስሎህ ነው እንጂ የክቡር ደጃዝማች ወልደ ሥላሴን ጀግንነትና ሞታቸውም ታላቅ ጉዳት መሆኑን ስንኳንስ ብዙውን ሚያቸውን የሚያውቁት ወንድሞቻቸውና አንተም አውቃለሁ ትላለህ ።

፫ኛ፣ አቶ ወልደ ጻድቅ ያቶ የተሸወርቅ ሐሳብ አነሳሣኝና ሁለት ያህሉ መስመሮች አወናክራለሁ ብሎ የንጉሥ መላእክተኞች መንገዱን ፈርተው ሊቀሩ ፈለጉ ይላል ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ወልደ ጻድቅ ጋሼ የሚባል ሰው ምንም ለንግግሩ የድፍረት ነጻነትን ቢሰጠው የታዘዙትን በመፈጸማቸው በሱ አፍ ሊዘልፋቸው ማሰቡ የማይገባውን ምሥጢር ተካፋይ ለመሆን ይሆን ? ወይንስ መሳሪያዬ ናት ብሎ በያዛት ሐሰቱ ሊገሥፃቸው ሥልጣን ተሰጥቶታልን ። ከቶ ይህ ለሰሚው ግራ ነው ። ወልደ ጻድቅ ጋሼ ከመናገር በፊት አስብ የሚለውን ተመልክቶ በሆነ መንግሥታችን ረዳቱ በሞቱበት ምክንያት መጐዳቱ አንሰት ከተረፉት ታዛገሮቹና አሳቢዎቹ ላይ ያበሳጨ መስሎት የሰው ሐሳብ አነሣሥቶት የሐሰት

ቃል ባልጸፈባቸውም ነበር ። የሆነም ቢሆን ስንኳን የመንግሥት መላክተኛና የሌላም ሰው ቢሆን የተላከው ሰው ትእዛዙን መፈጸም አለመፈጸሙን ያው የላከው ሰው ጠይቆት መልሱን ይነግረዋል እንጂ ማንም ሰው ያለ ሥራው እንደምን ሊሰድበው ይችል ነበር። አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ ምንም ደፍሮ በሐሰት ቢጽፉባቸው ጓደኞቹ አይደሉምና የቀድሞ ሥራቸውን ከብዙም በጥቂቱ ልጽፍለት አያስፈልግም ። ደግሞ አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ አኤሮፕላን ላይ መውጣትን እንደ ታላቅ ጀግንነት አስመስሎ መሳልሶ ይጽፋል።

መጀመሪያ የሚመሰገን የአኤሮፕላኑ ጥቅም ነው ።ስንኳን ኢትዮጵያ በሚአስፈልግበት በታ ሁሉ የሚበቃ የምድር ባቡርና የካሚዎን መንገድ የሌለበት ይቅርና በአውሮፓም ብዙ ልዩ ልዩ መገናኛዎች በአሉበትም አገር ቢሆን ለተላላቅ ጥቅም እንደ ተሠሩት መሣሪዎች እኩል እንዲአገለግል እርግጥ ነው ።እን-ደዚሁም በሀገራችን እንደ ተጀመረው በግርማዊ ንጉሥ ብር-ታትና ቸርነት የአኤሮፕላን ግልጋሎት ቢለመድ መጠን የሌለው ጥቅም እንዲሰጠን የታወቀ ነው። በዚሁም ነገር መንግሥታችን በርትቶ እንዲአስብበት ብልሕ ክቡር ነጋድረስ አፈወርቅ ጥቅሙ-ን አጋንነው ጽፈውታል። ፪ኛም የአኤሮፕላን ነጂዎችን አቀለጣ-ጠፍና ብርታታቸውን በብዙ ልናመሰግን ይገባናል እንጂ የሀ-ገራቸውን ነጻነት ጠብቀውና አሳፍረው የሚኖሩ የኢትዮጵያ ጀግኖች ሙያ ምን ያህል እንደሆነ የሚአውቅ ሰው አኤሮፕላን ላይ መውጣትን ጀግንነት ነው ብሎ እንዳያስብ የታወቀ ነው። እንግዲህ አደጋ የማይደርስበት የለምና በባቡር፣ መርከብ፣ በአ-ቶሞቢል ላይ የወጣ ሁሉ ጀግና ሊባል ይሆን። ነገር ግን እንደ ታዘዘ መትረየስ ተኩሶ በምብ ጥሎ ጠላት ቢአጠፋ ምሽግ ቢአፈርስ ይህነን የመሰለ ሙያ ሠርቶ ደስ ካሰኘ ታላቅ ምስ-ጋናና ዋጋም ሊያገኝ ይገባዋል ። ከቶ አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ በሰው ሐሳብ ተመርቶ አወናክራለሁ ቢል የሱ ሐሜት እንዳይ-ጎዳ ምስጋናውም እንዳይጠቅም የታወቀ ስለሆነ የሱን ሐሳብ መከታተል ምኞቱን ማስፈጸም ይሆናልና እንዲያው መተው ይሻላል ። ው ወ ማ ።

የአየር ባቡር።

በታላቁ በአውሮፓ ጦርነት ጊዜ በመሬትም ውጊያ እንደ ነበረ እንደዚሁም በአየር ላይ ውጊያ ነበርና የአየር ባቡሮች እየወጡ ሲዋጉ ብዙም ይድናል ብዙም ይወድቃል ። በመሬት ዘመቻ እንኳን ብዙ ሰው እየሞተም እየዳነም እየገደለም እንደሚመጣ ሁሉ በአየር ላይ እንደዚሁ እየተዋጉ ሳይወድቁና ሣደጋ ሳያገኛቸው ይልቁንም ዠብዱ ሥራ ይሠራሉ ። ከብዙ-ዎቹ አንዱ ካፒቴን ጊኔሜር የሚባል የፈረንሳዊ አቢያተር በታላቁ ጦርነት ውሥጥ በሺ፱፻፲፬ ዓ ም በፈቃዱ ለሀገሬ እረዳለሁ እሞታለሁ ሲል የመንግሥት እዝ ሳያስገድደው ፈቃደኛ አቢያተር ሆነ ። በዚያን ጊዜም የ፳፩ ዓመት ልጅ ይሆናል ። ይኸውም የአየር ጦረኛ ልጅ በጦርነቱ ውሥጥ አንድ እውከትና አደጋ ሳያገኘው በአየር ላይ እየተዋጋ (፶፱) አምሳ አራት አይሮፕላን አወረደ ። ፳፭ ጊዜ ዠብዱ ሥራውን አስቈጠረ ። እንደዚሁ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው ሲሉ ሞታቸውን እያወቁት እየወጡ እየተዋጉ አንድ አደጋ ሳያገ-ኛቸው የዳኑ በስንት ሺ ቍጥር ናቸው። ያውም በአራት ዓመት ጦርነት ውሥጥ ሁኖ ነው ። ይኸውም ልጅ በሕፃንነት ወራት ላገሩ ሲል ይኸን ሁሉ ሥራ ሲሠራ ምንም አደጋ አላገኘውም ነበር ። በኋላ ግን ራሱ ቢሞትም እንኳን ስሙ በመንግሥቱና በሀገሩ ለዘለዓለም መታሰቢያ ተጽፎለት ቀረ ። እሱም በፓሪስ በሺ፰፻፺፬ ዓመት ተወለደ በሺ፱፻፲፬ አመት በጦርነቱ ውሥጥ ገባ ። ከሦስት ዓመት ውጊያ በኋላ በሺ፱፻፲፯ ዓመተ ምሕረት በጦርነቱ ውሥጥ ሞተ ። ለሀገሩ ይኸን ሥራ ሠርቶ ስለሞተ ስለሀገሩና ስለመንግሥቱ ውለታ ዘለዓለም ስሙ በታሪክ ሲጠራለት ይኖራል ። እንደዚሁ ላገራቸውና ለመንግሥታቸው ሲሉ የሞቱ ሞልተዋል ። ነገር ግን ያልተለመደና ያልታወቀ ነገር በዓለሙ ሁሉ በመጀመሪያ አዲስ ነገር ሁል ጊዜ ማስ-ፈራቱና ማስቸገሩ አይቀርም ።

እንደዚሁ ያልታወቀ ነገር በድንገትና በመጀመሪያ ሲሆን ማስፈራቱና ማስቸገሩ እውነት መሆኑ አይቀርም። ጥቅሙ-ሲታወቅ ግን ከመቈርቈርና ከማዘን በተቀር በታሪክ ከመጻፍ በተቀር ሌላ ምንም የሚሆነው ነገር የለም። በኛም አገር በን-ጉሡ በግሀለ ሥላሴ ጊዜ አንድ ሰው በገደለ እስከ ፯፣ ሰባት ትውልድ ድረስ ይወረስ እየተባለ ያልገደለው ሁሉ ዘር በሆነ እየተወረሰ ያባቱን ርስት ሳያውቅ የቀረው ሞልቷል።ዛሬ ግን ሕጉና ደንቡ እየተሻሻለና አሮጌው ባህል እየተለወጠ ሥርዓቱ እየነጠረ ስለሔደ ይኸው ነገር ተረት ሁኖ ቀርቷል ። በመጀመሪያም ጊዜ የምድር ባቡር በተዘረጋበት ሰዓት በባቡር እንወጣም ድልድዩ ቢነክት ባቡሩ ቢወድቅ እያለ ብዙ ሰው እየ ፈራ አይወጣም ነበር ፤ ነገር ግን ዛሬ ሥፍራ እየተጣበበ ጓዙን እያጨቀ አንዱ በአንዱ ላይ እየተደራረበ ይሔዳል ። እንዲያውም የሰው ብዛት የበሩ መግቢያና መውጫ እየተጨ-ናነቀና እየጠበበ አንድ አንድ ጊዜ በመስኮቱ እየተንጠላጠለ ሲወጣና ለስፍራው ሺሚያ ሲጯጯህ ለዘረፋ የተሠማራ ወታደር መስሎ ይታያል። በአንድ አንድ አደጋ እንኳን ባቡ-ሩም ቢሰበር ድልድዩም ቢበላሽ በድንገት አደጋ ሰውም ቢሞት ሕዝቡ ግን ጥቅሙን በዓይኑ ስለተረዳውና መርምሮ ስላወቀው መሳፈሩን አልተወም።እንደዚሁ አቶሞቢል በገባ ጊዜ ብዙ ሰዎች እንደ መጥፎ ነገር ይመለከቱት ነበር። ክብት በማ-ስደንበሩና አንድ አንድ ነጂዎች በድንገት አደጋ ሰው ስለጻ-ጨቡባቸውና ስለሞተባቸው ነው፤ ነገር ግን ዛሬ ከብቱም ጥቂት በጥቂት እያለ ስለለመደ ለሰውም መቀመጫውና ፍጥነቱ የሚ-መች በመሆኑ በአንድ አንድ አቶሞቢል ላይ ከልክ እያለፈ ብዙ ሰው እየተቀመጠ እየተንጠላጠለበት ይታያል የአቶሞ-ቢል የጥንቃቄ ዘበኞች በየጊዜው ሲተናነቁና ከደንቡና ከልክ ያተረፈውን ለመቀጫ ሲይዙ እናያቸዋለን። ስለሕዝቡ ፍቅርና መውደድ የተነሣ አቶምቢል በጥቂት ዓመት በከታማው ሞላ። አቶሞቢሉም በድንገትም ምክንያትና በነጂውም ጥፋት ሆነ በተዳጨውም ሰው ጥፋት አንድ አንድ የሞት አደጋ ቢደርስ-በት ሕዝቡ ግን በአቶሞቢል መሔዱን አልተወም።

በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ለሞት የታዘዘ አደጋ በበሽታም ቢሆን በሌላም ዓይነት ቢሆን የሞት ልዩነት የለውም ። ይልቅ

ለሀገሩ ሲል የሞተ ሰው የተለየ ክብር አለው ። የአይሮፕላን መንገድ እንደማያጠራጥር የሚያስረዳን ይኸው በቅርቡ ከጥቂት ወራቶች በፊት በዚሁ ዓመት የጀርመን ባንዜፔሊን ዓለምን ሁሉ ዞሮ ሲገባ በቤርሊን ከተማ ከ፹ሺ ሰው ይበልጥ ተቀበለው ። የአንድ ሰዓት መንገድ ሳይሆን ዓለሙን ሁሉ ሲዞር ያለአንድ ሁከት የዓለምን አየር ዞሮ ሲገባ አቤትም ተቀምጦ ቢሆን ከሚደርስ ከድንገተኛ አደጋ በተቀር የአኤሮፕላን መንገድ በአየር ላይ ምንም እንደማያስፈራ ይኸው ዓለምን ሁሉ ዞሮ በደኅና የገባው ዜፔሊን ያስረዳናል። ዜፔሊን የተባለ የአየር መኪና ባቡር ከ፰ሺ ሜትር ኩብ የሚበልጥ ብሎም (volume) አለው ። ቁመቱ ከ፪፻ እስከ ፫፻ ሜትር ድረስ ይሆናል ። በሦስት ወይም በአራት መኪና (ሞተር) ይሔዳል። አንዱ መኪና (ሞተር) የ፬፻፶ ፈረስ ኃይል አለው። አራት መኪና (ሞተር) የሺ ፈረስ ኃይል አለው ። አንድ ቤት አንድ ላይ ተያይዞ ከላይ አንድ ጥቅል ሁኖ ተሠርቷል ። በውስጡ ብዙ ትንንሽ ክፍል መኝታና መቀመጫ አለበት ። እያንዳንዱ ክፍል መኝታ አንድ አንድ ባለጋዝ ባሎን አለው ። ለመኪናው ማስኬድ እስከ ፴ ሠራተኞች ይይዛል።

በትልቁ ጦርነት ጊዜ እንስራና ጋን የሚያህል በንባውን እየተጫነ ከተማ ለማጥፋት በምብ ለመጣል ይጓዝነበር። በታላቁ ጦርነት ውስጥ እንደዚሁ ያለው ኃይል የአየር መኪና መውጣቱን ብሰማ እኔም በሀገሬ እንዲሠራ እመኝ ነበር። ይልቁንም ለኛ ለኢትዮጵያ በየአውራጃው የምድር ባቡር ባልተዘረጋበትና የፍጥነት መገናኛ መንገድ በሌለበት አገር በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የአየር መንገድ የግድ የሚያስፈልገን ነው። ይልቁንም እንደዜፔሊን ያለ የአየር ባቡርና ሌላም በየዓይነቱ እየተጨመረ እየበረከተ እንዲሔድ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በትልቁ መሪያችን በግርማዊ ንጉሥ ሙሉ ተስፋ እናደርጋለን ታኅሣሥ ፳፱ ፡ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት።

ኪዳኔ ማ ተ ።

የጨረታ ወረቀት ።

የግቢ ሚኒስቴር ።

አንድ የጽሕፈት ቤት ለማሠራት አስቧልና ይኸነን ሥራ የምትፈልጉ ሰዎች ከግቢ ሚኒስቴር መጻፊያ ቤት ድረስ ጥር ፫ቀን ቅዳሜ ከጧቱ በ፫ሰዓት መጥታችሁ የቤቱን ሥዕልና የሥራውን ዝርዝር አይታችሁ በቊርጥየምትሠሩበትን ዋጋ ልክና ለዚሁ ለሥራ የሚዋሳችሁን ዋስ አገሬ ነው ብላችሁ ወረቀቱን በአንቦለብ ዘግታችሁ በጥር ፲፫ቀን ማክሰኞ ከጧቱ በ፬ሰዓት ከግቢ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ሰጥታችሁ በዚሁ ቀን የጨረታው ወረቀት ሁሉ ታይቶ ደኅና ዋስ ላለውና ዋጋውን ላሳነሰ ሰው እንሰጣለን ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ካዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ቀን ፲፱፻፳፩ ዓ ም ተነሥተን አጅቡቲ በ፳፫ ቀን ገባን።አጅቡቲም ስድስት ቀን ተቀምጠን በ፯ተኛው ከጅቡቲ በመርከብ ተሳፈርን ሐምሌ ፴ ቀን ስፕሪክስ ኤም ኤምክ በሚባለው መርከብ በሕንድያን ባሕር ስንጓዝ ሳለን ከ፫ ሁንጋሪያን ስነጋገር ሳለሁ ፥ ስለ ኢትዮጵያ ሲያደንቁ ነበሩ ። ከነሱም አንዱ ዓለምን ሁሉ ዞርኩ ግን ኢትዮጵያን የመሰለ አገር ከቶ አላየሁም አለ።ደግሞ አንዱ ፡ እግዜር የወደደው የዚችን አገር ሀብት ይበላል ያገኛል አለ ። ፫ተኛ፥ ደግሞ እኔ ምንም ቢሆን መቃብሬ በኢትዮጵያ ነው አለ።የነኚህም ሁንጋሪዎች ስም ይህ ነው። ቢልያም፡አልማሺ፡ ቢል፥ ሐልን፡በርሺ፥ስሚዩል፥ሥራቸው ሚካኒስ ነን ይላሉ ። ከፖርት ሰይድ ተነሥተው እስከ ጅቡቲ ሲደርሱ ። የመርከቡ ከቢቴን ይዞ መረመራቸውና ፥ እነሱም ወደሐበሻ ሔደን ሥራ እንሠራለን አሉት።እንዲሁም በመርከብ ውስጥ ያለፓስ ፖርት ስለተገኙ ወደኮሎምቦ ያጉዛቸው ኅበረ እግዘት ለማግባት ። እንዲሁም ባገራችን የሚረቡ፥ የማይረቡ፥ እንደነዚህ ያሉ የውጭ አገር ሰዎች አገራችንን የሚያበላሹ ፥ ወንድሞቻችንን የሚያዋርዱ ከዚህ ቀደም ብዙ ገብተዋል ። ከቶውንም ሐበሻ የጊሪክ ውሻ የሚሉ፥የገቡትንም መመርመር ለወደፊቱም፥ ሥርዓቱን ማጥበቅ የሚከፈልም ማድረግ በተለየ በጣም የሚያስፈልግ ነው ።

ነሐሴ ፳ቀን ኮሎምቦ ከሚባል ከተማ ስንደርስ ፥ ከተማውን ለማየት በጀልባ ወርደን ከመርከብ ከተማውን ስናይ ወደሱቅ ኀራ ብለን ብዙ ዓይነት ቀርጾና ለወይዛዝርት የሚሆንጌጥ የገበታም ልብስ ድንቅ ሁኖ እንደመረብ የተሠራ ብዙ ዓይነት እቃና ደግሞ ማየቱ ደስ የሚያሰኝ ነገር አየን፥ ይኸም ሁሉ ዓይነት እቃ የሚበዛው በባላገሮቹ ነው የተሠራው። የመንገዱ ጽዳት ፥ ያውቶሞቢሉ ብዛት ፥ ደግሞ በኤሌትሪክ የሚሔድ ትራምና ቤሳ አውቶሞቢል ብዙ ብዙ ሰው የሚያመላልስ በጥቂት በጥቂት ዋጋ ስፍር ቍጥር የለውም ። ባዲስ አበባ ፬ት ፭ት ቤሳ ያገኘ ሰው በየለቱ ብዙ ገንዘብ ሊያገባ ይችላል ። መንገዱ መልካም ቢሆን ።

ደግሞ የሂንድን ሰዎች የመሰለ በጠጉር አምልኮ የተያዘ የለም በወንዶቹና በሴቶቹ ልዩነት አላየሁምና ።

ስለ ልብሳቸውም በጣም ተደነቅሁ ፥ ከወገባቸው በላይ ቲንሽ ወንደቤ አጥልቀው ከወገባቸው በታች የሚሆነው ረጅም ግልድም ነው ሲራመዱ እያሰናከላቸው፥መቀነቷን እንደፈታች ሴት ፲፫ ጊዜ ከፍ እያደረጉ መያዝ አለባቸው። ይህነንም ባየሁ ጊዜ ያገራችን ሱሪ አስተማጠቅ መልካም እንደሆነ አሳሰበኝ። ደግሞ በመርከብ ስንጓዝ የፈረንሳዊ ሴቶች ከቋንጃቸው በላይ መልበሳቸውን ሳያስቡት በመርከብ በረንዳ ቁመው ሳሉ፥ ወደባሕሩ አንዳች ለማየት ጎምበስ ሲሉ ለሚያያቸው ሰው ያገራችን ሴቶች በቀሚስ አለባበሳቸው ላይ ዘመን አመጣሺ ሱሪ መታጠቃቸው በጣም አኰራኝ።ደግሞም እንደዚያ ያለ መልካም ሱሪ ታጥቆ ቀሚስን ቢያሳጥሩ ምንም የሚያስከፋ አይመስለኝም።

ደግሞ ስለጃፖን ወጣቶች ጥቂት ልጽፍ ወደድሁ ። ከጅቡቲ ተነሥተን ከማርሴይ በመጣው መርከብ ስንገባ፥ብዙ የጃፖን ወጣቶች አገኘን ። እንዲሁም አብረን ስንጓዝ ሳለን ከመዋል ማደር ተላመድናቸውና ፥ የት እንደ ነበሩ ለምንስ ከገራቸው እንደወጡ ጠየቅኋቸው ። እነሴቶቹ መንግሥታችን ለት

ምሁርት ልኮን ነበረ ትምርታችንን ጨርሰን መመለሳችን ነው አሉኝ ። ደግሞ እኩሌቶች ፤ በዘመድ የመርከብ ሥራ እየሠሩ እፈለጉበት ደርሰው ፤ እኩል ቀን እየሰሩ እኩል ቀን እየተማሩ የሚበቃቸውን ያህል አውቀው መመለሳቸው ነው ። ጃፖኖች እውጭ አገር እየሰደዱ የሚያስተምሩ ወንዶችን ብቻ አይደለም ። ሴቶችንም ደግሞ እየላኩ ያስተምራሉ ። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ጃፖኖችን የረዳቸው፡ መጀመሪ አንድነታቸው፤ ፪ተኛም ሀገራቸውን መውደዳቸው ፤ ፫ኛም፤ ለሑንግሥታቸው፤ የታመኑ መሆናቸው ነው።፬ኛም፤በገራችው ዙሪ ኃርበር ማኅኘታቸው፡ ፭ኛ በተገናኙበት ሁሉ መደጋገፋቸው፡ ፮ኛተጣጥረው ብዙ መርከብ መሥራታቸው ፯ተኛም ቄራጥ መሆናቸው ፤ ፰ተኛም ሌትና ቀን አፈር እስቲመስሉ መሥራታቸው ነው እስከዚህ ያደረሳቸው ። እንዲሁም ለምለምዋን ሀገራችንን በውነት የሚወድ ሁሉ ፈጽሞ ጃፖኖችን ይምሰል እንጂ ጃፖኖችን ለኢትዮጵያ ምሳሌ እያደረጉ መጻፍ ብቻ የሚበቃ አይመስለኝም። ሥራቸውንና ሐሳባቸውን መከተል በጣም የሚያስፈልግ ነው ። ከጃፓን በያመቱ በሺ የሚቈጠሩ እውቀት ለመማር ከመንግሥት በሚላኩም በዘመድ እየሔዱ በሚማሩም አል ደነቅም ። የኛም ሀገር እናታችን ርኅሩኂቱ ንግሥተ ነገሥታችን ርኅሩሁና ቸሩ ግርማዊ ንጉሣችን ስለዚህ ነገር ሌትና ቀን እንዲደክሙበት አያጠራጥርም ። ነገር ግን ባድግዳና ጣራ የሚከተለውንም ሁሉ ያስፈልገዋል ለጽኑ ምሰሶ ቤትን ለመሥራት ከተሠራ በኋላ ብዙ ዓይነት መሳሪና ዕቃ እንዲሁም ለቤት ብዙ ነገር እንደሚያስፈልግ ፤ ላገርና ለመንግሥትም እንዲሁ ነው።መንግሥት ያውቃል ብሎ ዝም ከማለት ብያሉበት ሁኖም በጅ ከመሆጠት የታመኑ ሁኖ እንደጥቂት ሰዎች አገልግሎቱን ማሳየት ለሀገር አንድ ትልቅ እርዳታ ነው ። በነገር ተያይዘው እርሻቸውን እየተዉ የሚመጡት በቅንነት ነገራቸውን ጨርሶ ፤ እንዳያገረሽ እንደሚቻል መጠን ብልዙን አውጥቶ መስደድ ፩እርዳታ ፤ አራዳ ሽቅጠውና ቤሳ ቀለሀ አትርፈው የሚገቡን ሳያጻፉና ሳያንገላቱ እንደደምቡ መቀበል ፪እርዳታ ። በሥራት፡በመሬት ግብር፤ በዳኝነት ፤ በመቀጮ ፤በቀረጥ ፤ በጠምቆሎ ፤ በሹራ ፤ እንዲሁም እንደሚከተለው ሁሉ፤ የተገኘውን ገቢ የታመኑ ሁኖ ማግበት ፫እርዳታ ለመንግሥት ምን አድርገን እንርዳ የሚሉ ቢገኙ እንደዚህ የመሰለ እርዳታ ሊረዱ ይችላሉ ። ይመስለኛል በሌላም በብዙ ነገር ለመርዳት ይቻላል ።

መንገድ ለመሥራት እንዴት እንርዳ።

መንገድ መሥራትና ኅዲድ መዘርጋት፡ሆስፒታል ማቆም፤ የጅ ጥበብ መማሪ ቤት ማቆም።

ለሀገርና ለሕዝብ ልማት ከሺ ዓመት በላይ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ የሀገር ፍቅር የሚባል የተለየ ስጦታ ባመት ፫ብር ቢገባ ከያንዳንዳችን ከመላው ኢትዮጵያ ካንድ ወገን የዘመመውን ሊያቀና ይችላል። ምናልባት አባቶችና ጌቶች ወንድሞችም እኩሌቶች ከሄት አምጥተን እንከፍላለን ይሉ ይሆናል እኩሌቶችም ይህ አዲስ ቅጥል ግብር ምንድነው ብለው ይቈጡ ይሆናል ባጭሩ ሰው ስለሀገሩ እንኳን ይህን ቲንሽ ያገር ፍቅር ስጦታ ሕይወቱንእንኳ ማሳለፍ አለበት የሚያስፈልግ ሲሆን።ደግሞም በጅ የያዙት ዕንቍ ብረት ይመስላል እንደሚሉት ሁኖ ነው እንጂ ሀገራችን የወርቅና የፍሬ መሠረት ናት እንደምታውቁት ይህም ስለማሳጠር ነው ። ደግሞ አንድ ነገር በጣም ሲያስተክዘኝ ይኖራል።የመንደር ቱኪና አልፈው አልፈው የሚገኙ ፍርድ ገምድሎች እነ እንብላው እነምንም አያደርጉን በኢትዮጵያ ሆድ እንደኮሶ ተፀንሰው ያገር ቍርጠት ሁነው ድሆችን እንዳንፈራገጡና እንዳንፈራፈሩ ይኖራሉ ምንም መድኀኒት አልተገኘላቸው እስከዛሬ ይህንንም የጻፍኩት አዲስ አበባ ስላየሁት ብቻ አይደለም በኢትዮጵያ የሚበዛውን አገር ስለዞርኩ አይቼና ሰምቼ ስለተረዳሁት ነው እንጂ ። እዲሁም ከንደዚህ ያሉ የዘላለም ደዌ ነጻነት ለማግኘት የተፈተነ አብነት ያስፈልጋል ።

ንጉሥ ንጉሥ ይላል ሕዝብ ንጉሥ የሚበላውና የሚጠጣው ያንድ ሰው ያህል ነው። ግን ለሕዝቡ ማገልገልና ባምስቱ ዓለም ክፍል ሐሳቡ እየተዘራ መዋተት ነው ትርፉ አስቡና መርምሩ ይህ ሐሰት ወይም ወዳሴ ከንቱ እንደሆነ ወይም ከውሥጠ ሕሊና እንዲሁም አዛገሮችና ታዛገሮች እንደ ጥቂቶቹ ታማኞች ከሥጋቸው ሳይከፍሉ ወገን ብለው ሳይለዩ በቅንነት ለመንግሥታችን ቢአገለግሉ በውነት የጃፖን ሥልጣኔ ይገኛል ። ትንቢትም ይፈጸማል ያገራችንም በረከት በልጆቿ ላይ ያርጋል ።

ሲንጋፖር ስንደርስ፤ መርከብ ስለቆመ ከተማውን ለማየት ከመርከብ ወርደን ሳለን አንድ ሰው መጣና ባማርኛ አነጋገረን እኛም ስለርሱ ተደንቀን ብዙ ጠየቅነው ። ይህም ሰው በውነት ካገራችን የወጣ ሰው ነበረ ። ከኢትዮጵያም ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው እኛንም ስላገኘ በጣም ደስ አለውና ፤ ግዱንም ብሎ ቡና ጋበዘን ከተጋበዝንም በኋላ አብሮን የማይዘልቅ ስለሆነና ከርቡጋራ ለመቈየት ስላልቻልን መርከብ የሚያመልጠን ስለሆነ በጣም አዝነ ተሰናበተን። የዚህም ሰው ስም ዮሴፍ ይባላል ይህም ሰው ላገራችን በመቈርቈሩ ባለበት ሁኖ በጣም ደስ አለኝ ይኸ ሰው ወደውጭ አገር እንደመውጣቱ ፤ ደግሞ ተመልሶ አገሩን አለመርዳቱ በጣም ያሳዝናል ።

ካፕቴ ማሪ ፕራ ኑራ ።

ካፕቶ ማሪ ፕራ ኑራ የሚባል የሲያም አገር ልጅ በቺና ውስጥ ከጅቡቲ ተነሥተን እስከ ሴጎን እስክንደርስ ድረስ ባንድ ክፍል ነበርንና ስንነጋገር ሳለንምን እንዲሠራ ከወዴት እንደመጣ ወዴት እንደነበረ ጠየቅሁት ።እርሱ አፈረንሳይ አገር ለትምህርት ሔዶ፤የፈር ባይ የቋንቋ ዩኒበርሲቲ ጨርሶ ወደአገሩ መመለሱ ነበረ ። የትምርቱንም ዘመን ብጠይቀው ፲፩ ዓመት ይሆነኛል አለ። የተማረውም ፈረንሳዊ ጣሊያን እንግሊዝ ሽሚትዝናችና ደግሞ ጥቂት ጥቂት የሚያስቸውላቸው ፫ ቋንቋች ነው ። ይህንንም ከነገረኝ በኋላ አገርህ ስትድርስ ምን ማድረግ ታስባለህ አልኩት እርሱም መልሶ ምን አደርግ ይመስልሀል ብሎ ጠየቀኝ እኔ ይህን ያህል ብማር አገሬን ልረዳ በቻልኩ ነበር በመቅኔ አልኩት ይህንን ስላልኩት አዝኖ አለ ፤ አባቴ ፳፭ ዓመት ተምሮ በትልቅ ማዕርግ ጊዜውን አሳለፈ ወንድሜም እንደ አባቴ ተምሮያባቱን ሹመት ይዟል እኔ ግን እንዳንድ ጸሐፊ ሁኜ ብኖር አባቱን የሚያውቁ ሰዎች ምን ይሉ ይመስልሃል አለኝ

ይህ ወጣት ልጅ የኤሮፕላን ሥራ ለመማር ተስፋ አለው ። ይኸነን ሁሉ ሲግር ሳለ አትማሪ ቤት ስለኖረበት ያገሩ መንግሥት የስድስት ዓመቱን ክሳሩ ቻለልኝ አለ የቀረውን ግን እየሠራ ነው ።

ነሐሴ ፲፪ ቀን ሲንን ደረስን ።

ከዚያም አርፈን ሳለን ብዙ ነገር አየሁ ። በለገሮቹ አፍንጫ ደፍጣጦች ወይም አፍንጫ ሰፊዎች ፡ ፊተ ሰፊዎች ፡ ዓይነ ልሞች ፡ ጭንቅላታሞች ፡ ደረታሞች ናቸው ። ያይናቸውም ቅድ ቷንሽ ልዩነት አለው ። ሲረመዱ ሞያሌ እንዳዬሰለው ሽን ከፍ ሽንከፍ ይላሉ ። አግራቸው ጠፍጣፋ ነው ። በሥራ የማይደክሙና ፈጣኖች ናቸው ። በሚሠራው ሥራ ሁሉ ከራሳቸው በቀር እንግዳ አይገባበቸውም ። በሚችሉት ሥራ ሁሉ እርፊታቸው ምን ሰዓት እንደሆነ አይታወቅም ሌትም ሆነ ቀን። የብርታታቸው ብዛት በምን እንደሆነ አይታወቅም።ይህም ሳይቀር ሁል ጊዜ በደስታ ፊታቸው በርቶ ሲሠሩ ይታያሉ ። ሀገራቸው በጣም ፍሬያም ነው ። ሩዝና ፡ ፍሬ ፡ አማና ፡ በያይነቱ የውሀ ትል ፡ እባብና ፡ ዘንዶ ፡ ኤሊና ፡ አርጃኖ ፡ በያይነቱ ሌላም ብዙ ይበላሉ ። ይህንንም ሁሉ በየሁ ጊዜ ሥጋ ሁኖ የተገኘ ነገር አይተው እንዳይምሩ ተሰማኝ ። አንድ እንኳ ሰነፍና አም በጓሮኛ ሰከራም አላየሁባቸውም ።

ሆንግ ኮንግ የሚባል እንግሊዝ ኃርበር በደረስን ጊዜ ካሚሪካ የሚመጣ ቴሌግራም ለመጠበቅ ብለን ተቀምጠን ሳለን ፡ በከተማ ውሥጥ ብዙ የሚያስገርም አየሁ በሆንግ ኮንግ የሚኖሩ ያገር ልጆች ቀለማቸው ብጫ ነው ። ደግሞ ያይንና ያፍንጫ ነገር ከላይ እንደተጻፈው ነው ከከልሶች በቀር የሚበዙት ጤናሞችና ብርቱ ሠራተኞች ናቸው። ሥራቸውም ሌትና ቀን ነው ። አንድ ጥምልምልያለው ከወገቡ በታች የሞተ ሽባ በግር መሔድ ስለቀረበትና መንፉዋቀቅ ደግሞ ስለጠላ ፡ ርዝመታቸው ፩፩ ክንድ በሚሆን በ፪ባርጩሞች ክንዱ ወዳንዱ እየተቀባበለ በርጩሞችንም ፩ን ባንድ እጁ ሀተኛውንም እንዲሁ እያራመደ ፈጠን ብሎ በጣሩ እንደሚሔድ ሰው፡ ምድር ሳይነካው፡ አውቶሞቢል አቋርጦ ሲሔድ ያየሁት ሳየው ሰው በጣም ያስደንቃል ። ይህ ሰው እንዲህ ማድረጉ ከሰው በታች መሆኑን አጥብቆ መጥላቱን ያስረዳል ። ስለመብላቸው በተቻለኝ መጠን አጥብቄ መረመርኩ ግን ከሲንን ሰዎች መብል ምንም ልዩነት የለውም ።

በሆንግ ኮንግ የሚኖሩ የተለዩ ሥራቸው ፩ኛው ስጋጃ በያይነቱ ። ፪ኛው ከተለማጭ እንጨት የሚሠራ ፡ ገበታና ወንበር አልጋና ማጥን ሌላም ብዙ የፈንጠዝያ እቃ ማየቱ ብዙ ደስ የሚያሰኝ ። ፫ኛ በያይነቱ ቅርጽ በሰውና በብዙ ልዩ ልዩ እንስሳና ተንቀሳቃሽ ምሳሌ፡ከዝሆን ጥርስና ከዕብነ በረድ ከመስተዋት ከድንጋይ ከእንጨት ከናስና ከመዳብ የተሠራ የሸክላ ፍንጃልና በብዙ ዓይነት ጌጥ የተሠራ የመዳብና የናስ ድስትም በያይነቱ በጨርቅ ረገድም ብዙ ሐርን የሚመስሉ ይገኛሉ ። በቀረውም ሥልጣኔያቸው በጣም ከፍ ያለ ነው ። ደግሞ የሚያከብሩትንና የሚያርፉበትን ቀን ምንም አላየሁም ሌትና ቀን ከመሥራታቸው በቀር ቅዳሜ እሑድንም አያውቁም ክጥቂቶች በቀር የነሱም ቢሆን እነሱ አይሥሩ እንጂ ሠራተኞቻቸው ምንም አያቋርጡም ። ደግሞ የቀሩት እንደምትሰሙት ሃይማኖታቸው ብዙ ነው ።

ስለቺና ሴቶች ጠጕርና እግር በጣም ተደነቅሁ። ያገራችን ፊረሶች ጭራ እንኳ ተርፎ በጣም መሬት አይነካም ከጥቂቶች በቀር የቺና ሴቶች ከፍ ባለ ወንበር ተቀምጠው የተጐነጐነው ጠጕራቸው አመሬት ያርፋል ካልሰበሰቡትና ካልተጠነቀቁለት ዳግም ሴቶች ልጆች ሲወለዱ ጫማቸው እየተኮረተመ እየተሰበረ ያድጋሉና ጎጆ ማቆሚያቸው ሲደርስ ለባል ይሰጣሉ ። እንዲሁም እግራቸው እንደሌሎች መሆኑ ቀርቷልና የቤት ጠባቂ ሁነው ይኖራሉ የሠለጠኑት ግን ከዚህ አደጋ ተርፈዋል። እንዲህም ጫማ ቸው ታጥፎና ተከርትሞ ማደጋቸው ፩ኛው ምክንያት ባል እንዳያገቡ ነው፤ሁለተኛውም እንደሀሳባቸው እንዳይሔዱ ነው እንዲህ ያለውን እግር ብዙ አየሁ ለመራመድ በሉ ጊዜ ብዙ ሲጨነቁ ። ኃይለ ጊዮርጊስ ሀብተ ማርያም።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጆዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ነህ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋሰው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ

የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል ፯ መሐ
የማርኛ ምሳሌ ፯ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንደር) ፯ መሐ
አሳብና ምኞት ፰ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት ፰ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም ፱ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ ፱ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ ፱ መሐ
የበገና ግጥም ፱ መሐ

የርሻና የንግድ ማስፈፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቤታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፱ ብር ተ፫ሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፬ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፬ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር ተኩል
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፩ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፩ ብር
ባለ ድመ ።		፻፹
ባለአህያ ።		፻፶፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፷፩
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳
“ “ ጃፖን		፻፸፫ብር
ሱካር	ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር ፬ ፍራንክ ከ፶ሳቲንም
በአንድ ብር ፯ ሊሬ ከ፩ሳንቲም
አንድ ጊኒ ፲፱ ብር ፳፭ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ ፴፱

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄበኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገናል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።



በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ፀ ፊ. ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኲላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ በለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፭
6me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 16 JANVIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዘት ለፈስገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የእስክንድርያና የኢትዮጵያ የኖብያም ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ ወደ አዲስ አበባ የመጡበትን ምክንያት ከዚህ ቀድሞ በኅሣሥ ፳፬ ቀን በወጣው ጋዜጣችን አስታውቀናል ።

በታኅሣሥ ፳፬ ቀን ከድሬደዋ ተነሥተው በ፳፰ አዲስ አበባ ገቡ ። በባቡር መቋሚያና በከተማው ውሥጥ ያሉት ትልልቆቹ መንገዶችና የመንግሥት ሥራ ቤቶች ሁሉ በኢትዮጵያ ባንዴራ አጊጠው ነበር ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም መኳንንቱን ሁሉ አስከትለው በባቡር መቋሚያ ይጠብቁ ነበርና ሊቀ ጳጳሳቱ በደረሱ ጊዜ በክብር ተቀብለው በዚያው በባቡሩ መቋሚያ ፴ ደቂቃ ያህል ቈይተው ነበርና ሊቀ ጳጳሳቱ ኢትዮጵያ በመምጣታቸውና የሃይማኖት ልጆቻቸውን በማየታቸው እጅግ ደስ ስላላቸው ለእግዚአብሔር የምስጋና ቃል ተናግረው ለሕዝቡ ሁሉ ጸሎትና ቡራኬ አደረጉ ።

ለማረፊያም የተዘጋጀላቸው ስፍራ በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ቤት ግቢ ነበርና ግርማዊ ንጉሥ ሊቀ ጳጳሳቱን አቡነ ዮሐንስንና የኢትዮጵያን ጳጳስ አቡነ ቄርሎስን በራሳቸው አውቶሞቢል አስቀምጠው ለማረፊያ ወደተዘጋጀላቸው ቤት ወሰዱዋቸው ።

በማግሥቱ በታኅሣሥ ፳፮ ቀን ቀዳሚት በቤተ መንሥት ትልቅ የክብር አቀባበል ሊደረግላቸው ታስቦ ሳለ ስለ ሽምግልናቸውና ስለ መንገድ ርቀት ሰውነታቸው ደክሞ ነበርና በዚያ ቀን ለመውጣት የማይቻላቸው መሆኑን ሐኪሙ አስታወቀ። ስለዚህም ሶስት ቀን ያህል ዕረፍት እንዲያደርጉ ነገሩ የተቈረጠ ሆነ ።

በታኅሣሥ ፳፱ ቀን የልደት በዓል ነበረና በዚሁ ቀን በቤተ መንግሥት ትልቅ የክብር አቀባበል እንዲደረግላቸው ስለ ታሰበ መኳንንቱና ወታደሩ ከጧቱ በ፫ ሰዓት ከግርማዊ ንጉሥ ግቢ ጀምሮ እስከ ቤተ መንግሥት ድረስ መሰለፍ ጀመሩ ። ሊቃውንቱና ካህናቱም አጊጠውና ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በቤተ መንግሥቱ ይጠብቁ ነበር ።

የውጭ አገርም የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ ለዚሁ በዓል ተጠርተው መጥተው ነበር ። አራት ሰዓት በሆነ ጊዜ ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ዮሐንስ ከጳጳሳትና ከመኳንንት ፤ ከሊቃውንትና ከቀሳውስት ጋራ በክብርና በደስታ እንደ ማዕርጋቸው በልዩ ልዩ አውቶሞቢል ተቀምጠው ወደ ቤተ መንግሥት ደረሱ ።

ይህም የሊቀ ጳጳሳቱም ወደ ኢትዮጵያ አመጣጥ አዲስ ነገርና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ክብር የሚሰጣት ስለ ሆነ ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ዘውዳቸውን ጭነው በዙፋን ተቀምጠው ይጠብቁ ነበረና ሊቀ ጳጳሳቱ ከአውቶሞቢል ወርደው ወደ ዙፋኑ ሲቀርቡ እየተነሡ ቆመው ቡራኬ ተቀበሉ ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ድካም ስለ ተሰማቸው ቆመው ለማንበብ የማይችሉ ቢሆኑ ከምድረ ግብፅ ተከትለዋቸው የመጡት የኪና ጳጳስ አቡነ ሉቃስ ስለ ሊቀ ጳጳሳቱ ሁነው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ግርማዊት ንግሥት ሆይ
ግርማዊ ንጉሥ ሆይ
የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ

እኔ ሊቀ ጳጳሳት አባ ዮሐንስ ዓሥራ ዘጠኝኛ የቅዱስ ማርቆስ ተከታይ ፤ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ። ለልዕልት መነንና ለክቡራን ቤተ ሰዎቻቸው ለክቡራን ካህናትና ለክቡራን መኳንንቶች ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዋርያውን በረከት ይስጣችሁ እያሉ በዚህ

ጊዜ በኢትዮጵያ ውሥጥ በታመኑ ልጆቿ መከከል ሁኖ ጥልቅ የሆነ ፍቅራቸውና ደስታቸውን አገልጻለሁ ።

ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ፡ ክቡራን የኢትዮጵያ ሕዝብም የተቀበላችሁኝ አቀባበል በልቤ ለዘለዓለም የማይረሳ ነውና ለቤተ መንግሥቱና ለተወደዱ ሕዝብ ሁሉ ስሙ ይባረክና ኢየሱስ ክርስቶስን በጸሎቴ እለምንላችኋለሁ ።

በምስር አገር ከሕዝባችሁ ጋራ በወንድምነት ራሱን የሚቈጥር ሕዝብ እርግጥ መኖሩን አገልጥላችኋለሁ።እሱም በደስታ በሞላ ልቡ ከፍ ፡ ከፍ እንድትሉ ይወድላችኋል። ልዕልት መነን አስቀድመው ምስር አገር መጥተው በመካከላችን ሁነው ክብሬታ እንደሰጡን እንደዚሁም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን መጥተው ጥልቅ ክብሬታ ሰጥተውናል ።

እሳቸውም የሕዝባችን መውደድና ደስታ በሆነ አቀባበል የፍቅሩን ብዛት እንደብርሃን ሁኖ በይናቸው አይተውታል ኢትዮጵያን በጣም እንድንወዳትና በፍቅርዋ ማሠሪ አጥብቀን እንድንታሠር ከብዙ ዘመንና ዘመናት ከክርስቲያንነት ኀጋት ጀምሮ አንድነት በሃይማኖት ለሁላችን ቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ አንድ አስተማሪ ሁኖ ሰበከልን።በዚች ቀጥታ በሆነችው በንዲት ሃይማኖታችን ቅዱሳኖቻችንና ቅዱሳኖቻችሁ ባንድ የጋራ ነገርና በንድ ከፍ ያለ ምሳሌ በንዲትም ትምህርት ደማቸውን አፈሰሱ። ይኸንን መሥራቱ ፍቅርና ሰላም የሆነ ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሮን ለኛ ብሎ ከመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ አዳነን ።

ክርስቲያን ከሆነ ጀምሮ በቅዱስ ማርቆስ ወንበር የተቀመጡ የግብፅ ኦርቶዶክሳዊያን ሊቃነ ጳጳሳት ለኢትዮጵያ ሊቀነ ጳጳሳትና የሃይማኖት መምህራኖቹን እስከሁን ድረስ ፲፻፮ ዓመት ምንም ሳይለያዩ ይልኩላት ነበር ።

ግብፅና ኢትዮጵያም ምንም ልዩነት የላቸውም ። ሁለቱንም ኢየሱስ ክርስቶስ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን የሚሰበስባቸውና ባንድ መቅደስ የሚቈርቡ ናቸው ። እነሱም በልባቸው በፍቅራቸውም በጸሎታቸውም ሳይለያዩ ይኖራሉ።

እስካሁንም ከግብፅ የተሾሙት ሊቃነ ጳጳሳት ፻፲፫ ሆኑ። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁኖ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ከተቀመጥሁ ገና ፩ዓመት ሊሞላኝ በእርጅናዬ ላይ ምንም የመንገድ ድካም ሳይከለክለኝ ልጠይቃችሁና ልባርካችሁ የፍቅር ጥበብና ሰላምታ ልሰጣችሁ መጣሁ ።

አሁንም በመካከላችሁ ሁኜ ጥልቅ የሆነ የልጅነት ፍቅራችሁንና በናንተ ተከበው የደስታችሁን ብዛት ባይ ድካሜን ረሳሁ ። ይህችን ደስታ የሞላባትን ሰዓት እግዚአብሔር ስላሳየኝ ይትባረክ ስመ እግዚአብሔር ብዬ ክብርና ምስጋና ለእግዚአብሔር አቀርባለሁ ።

አዲስ የተሾሙላችሁን ሊቀ ጳጳሳት በደስታ ስለከበባችሁና ስለተቀበላችሁ እጅግ ደስ ብሎኛል ።

እሊህንም የከበሩ ጠባቂ በርምጃቸው ሁሉ እንዲመራቸውና ጤናና ሰላም ለማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ አቅንቶ እንዲፈጽምላቸው አምላክን እለምናለሁ ።

የቤተ ክርስቲያናችን አምላክ ይህችን ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታችንንና ልማዳችንን ባለፈው ያገናኘችን አሁንም የተገናኘንበት ፡ ለወደፊቱም የምታገናኘን ፡ የተቀደሰች መሣሪያችንን እንዲጠብቅልንና ፈቃዱ ሁኖ ጸሎታችንን ፡ ልመናችንንም እንዲቀበልልን ተስፋ እናደርጋለን ።

እኛም በወገናችን ይህችን የፍቅር መሣሪ በፍጹም ጸሎታችን እንድትበረታ የማይረጋችኋን እርግጥነቷን ታውቃላችሁ። ስለዚህ ምክንያት ያማርኛን ቋንቋ በመንፈሳዊ ተማሪ ቤታችን አጣብቀን የሚያስተምሩንን መምህራን ከኢትዮጵያ አምጥተናል ።

ከዚህ አስቀድሞ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በኢትዮጵያ ልጆቻችሁን የሚያስተምሩ ግብፃውያን አሉና ፤ አሁንም አገራችሁ ከፍ ከፍ እያለና እየተሻሻለ እንዲሔድ ሌሎችም ቢያስፈልጓችሁ የግብፅ ወንድሞቻችሁ እንዲረዱዋችሁና የፈለጋችሁትን ሁሉ ደስታን በተመላ ልባቸው እንዲፈጽሙላችሁ የተሰናዱ ናቸው ።

ዋና ለማስታወቅ የምንፈልገው ጎረቤት የሆነ ሕዝብ በወንድምነቱና ጥልቅ በሆነ ፍቅሩ ሀብትና በረከት ይመኝላችኋልና ከዚህ ሕዝብ የምትፈልጉትን ወንድም ከወንድሙ ለመጠየቅ እንደሚገባው እንድትጠያየቁ ይገባችኋል ።

ዕድሜ ለግርዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር፥ ብለን ለሕዝቡ ሁሉ ጤናና ሀብት እንዲሰጥና ከዚህም ያባትነት መንበኝት የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ክብረት እየተሻሻለ እንዲሔድና የሁለቱም ሕዝብ የፍቅር ማሠሪያቸው እንዲበረታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንለምናለን አሜን ።

ከዚህም በኋላ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ አቡነ ዮሐንስ ወደ ኢትዮጵያ ስለ መምጣታቸው ደስታቸውን ለመግለጽ ሲሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ብፁዕ አባታችን የእስክድርያ የኖባ ያምስቱ አህጉርና የኢትዮጵያ መንግሥት በትረያርክ ዘነበረ በመንበረ ማርቆስ ወንጌላዊ ብፁዕ እምብፁዓን አባታችን አቡነ ዮሐንስ ሆይ ።

ልቤን ያለመጠን ደስታ የሞላው፥ አካሌንም ሁሉ ይባቤ ያከበበው ሁኜ በሐዋርያ ጌትነትዎ ፊት ቆሜ በተለየ ሰውነቴ ሳባትነትዎ እንዳድ ልጅ ሁኜ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ብፁዕነትዎን ለማመስገን ለኢትዮጵያ እልቅናዋ የኔ ስለሆነ ምትክ ሁኜ ለብፁዕነትዎ በጣሙን ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ይህችንም ሥልጣን በመጀመሪያ ያገኘኋት ከቤተ ክርስቲያን ጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃድ ሁኖ ነው ።

ሁለተኛም የተቀደሰውን እጅዎን በኔ ላይ አድርገው እኔን ለዚህ ሥልጣን አብቅተው ቀድሰው ስለ ባረኩኝ ለብፁዕነትዎና በተዋሕዶ ለተለዩ ልጆችዎ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ኤጲስ ቆጶሳት ከላይ እንደተነገረው ሁሉ ይህችን መልካም ጊዜ ያማረች የተተካከለች በተዋሕዶ ሃይማኖት ክብሩ የፀናች በብፁዕናዎ መምጣት ምክንያት በከበረችው ቀን ለዋሐርያ ጌትነትዎ ደስታዬንና ምስጋናዬን በግልጽ አቀርባለሁ ።

ደግሞም ይህንኑ ለጌትነትዎ ምስጋና ማቅረቤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሙላ ደስታዋ በፍጹም ስለ ሆነ በታላቅ ሐሳብና በፍቅር በይበልጥ የሃማኖቷን ጌታ ዋና ጠባቂዋን የጳጳሷን ሊቀ ጳጳስ ንጹሐ ንጹሓኑን በምስርና በሱዳን በምስቱ አህጉር ምዕራብና በኢትዮጵያ በቅዱስ ማርቆስ መንበርና በፓትረያርክ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ነዎት ስል ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሁሉ በሙላ ወደተባረከው የኢትዮጵያ መንግሥት መምጣትዎ ያለመጠን ደስ አላቸው።ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ወደኢትዮጵያ በመምጣትዎ በጣሙን የበዛ ደስታ ደስ ይበላት ።

ይህም መምጣትዎ ሃይማኖትን የሚያፀና ያበትነት ትምህርትና ማቅናት ዋና ታላቅ ምክር ይገኝበታልና ።

ይህንም ማዕርግ ሊቀ ጳጳሱ ዋናው በትረያርክ ወደ ሀገሯ መምጣቱን ኢትዮጵያ ተከልክላ ብዙኅ ትውልድና ዘመን ይህንን ተስፋ ሳታገኝ ትኖር ነበር ።

አሁን ግን የኢትዮጵያ መንግሥት በተለየ ደስታ ደስ ይበላት ንጹሕ በሆነ በሐዋርያነትዎ መንፈስ ቅዱስ የተጠመቀች ትሁን የኢትዮጵያ መንግሥት በተለየ ቤተ ክርስቲያንዋም በሙላ የሰላም አስተማሪዋ በተዋሕዶ ያከበራት የሃይማኖት አባቷ መጥቶላት እንደምን ደስ አይላት ።

አሁንም ብፁዕ አባታችን ሆይ መንግሥቱንና ቤተ ክርስቲያኑን ባንድነት ባዲስ ሰላምና ባዲስ ኪዳን አስማምተው የሚያስተምሩ ነዎ ። የተባረኩት የተቀደሱት የሰላም እግሮችዎ እዚህ ከረገጡ በኋላ በርእሰ ሰላም በታላቁ በጠባቂዎች ጠባቂ በጌታችን ባንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል የሁለቱን የመንግሥቱንና የክህናቱን ሰላምነት የሚያፀይ ይሁን ።

የኢትዮጵያ አገር ሁሉ ዛሬ ትዘምራለች የደስታ ቅኔዋንም ትመራለች ከዳዊት መዘምር ጋር እንዲህ ስትል በኢትዮጵያ አገር ላይ ያለ ሰውም እንስሳውም ቡቃያውም አትክልቱም በውኆችም ውሥጥ ያለ ተንቀሳቃሽ ሁሉ በያይነቱ ምስጋና ያቀርባሉ ።

የዖፍም ዓይነቶች በየዛፉና በየተራራው ላይ ሁነው ስለ ደስታው የምስጋና ቃል ይሰጣሉ ወደፊት ለሚመጣው ደስታ ቅኔ ምክንያት ስለዚህም ከሰው ልጅ ደስታን ይከፈላሉና ።

ደግሞም ስለመድኃኒታችን አለቃ ምትክ ሁነው ሕዝባቸውን ሊያስታውሱ የሃይማኖትን ዓምድ ሊያፀኑ አስበው ስለመጡ ይላልና እሱም እውነተኛው ጠባቂ ነው በበር የሚገባ መንጎቹም ቃሉን ያውቁታልና፥ ይከተሉትማል በጎቹ ናቸውና፥ ይህም ከሆነ አሁን እኔን ይገባኛል ፍጡራንን ሁሉ ባንድነት ለመጥራት ሰውንም እንስሳውንም ተራራውንም በዚህ በተናገርሁት ሁሉ የቅዱስ እግዚአብሔርን ስም እንዲያመሰግን ይህንም ፍጡር ሁሉ በቃል ባይናገር ምሳሌው ለሐዋርያው ጌትነትዎ እንኳን ደኅና ገቡ እያለ ምስጋና ያቀርባል ።

ደግሞ አሁን እኔ ለራሴ ለቅዱስነትዎ እስከዚህ ድረስ እንኳን ደኅና ገቡ ማለቴን በታላቅ ደስታ ክብርና ምስጋና አቀርባለሁ ። ደግሞም እንደዚሁ ሁሉ ምስጋናዬን ለሁለቱ ክቡራን ከብፁዕነትዎ ጋራ ለመጡ በቤተክርስቲያን ሥራ ሁሉ ለሚረድዎ ለአቡነ ሉቃስና ለአቡነ ዮሳብ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

— እነሱም በዚህች በተባረከችው ጕዞዎ ከቅዱስነትዎ ጋራ ስለመጡ ክብር ደገባቸዋል የመንፈስ ቅዱስ ርኅራኄ በነብፁዕነት አድሯልና ። ደግሞም እንደዚሁ ሁሉ ከፓትረያርክነትዎ ጋር ለመጡት ለተባረኩት ልጆችዎ ሁሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ።

ደግሞ በመንገድና በውኃ ላይ ደክመው ከእስክንድርያ ከሐዋርያው መንበር ከማዕርግ ሹመትዎ ላይ ተነሥተው ወደዚህች ሩቅ ወደ ሆነች አገር መምጣትዎ እጅግ አድርጎ ደስ ያሰኛል ።

እንዲያውም ይህ ነገር የተባረከውን የኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ በሙላ ከልብ ማፍቀርዎን በውነት ያመለክታል ።

በውነት ነው በኢትዮጵያ ሕዝብ መከከል በሀገሯ ውሥጥ መገኘትዎ በረከትን ሃይማኖትን ትሩፋትን ሁሉ ፍጹም እምነትንም እንድታገኝ የታወቀ ነው ። ይህ ሩቅ ነገር አይደለም የተከበረው ሰውነትዎ ለትሩፋት ሁሉ መሠረትና ለፈሪሃ እግዚአብሔር አድራሻ ነዎትና ።

ለምሉእነትና ለቅዱስነት ብርሃን ነዎ ። በረከትም የሚገኘው ከእናንት ነው በናንተም ሃይማኖት ትፀናለች። እናንተም የሐዋርያ ጌትነታችሁም ለዘለዓለም የሚቈይ ይሁን።ለሕዝብዎም ማሰብዎ፥ለቅዱስ ማርቆስ ወንበርሕዝብ በሙላ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ዋና ሐሳብዎ ለዘለዓለም ይሁን።

እኔም ደካማው ለዚች ለትንሽ ቃል ፍጻሜ ወደቤተ ክርስቲያን አምላክ እማልዳለሁ ። ይህችን መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን ማየትዎ አዲስ መጀመሪያ በጎ ነገር እንዲያደርገው በበረከትና በምሉእ ሰምሁና በደስታ ሁሉ የታሠረች እንድትሆን

በኢትዮጵያ ዙፋን ላይ በተቀመጡት በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጥላ ውሥጥ ትሁን። የሁለቱንም ግርማዊነት ከላይ በቸርነቱ ጠብቆ በበጎ ሕይወት የተያዘች ከኃዘን የተለየች ምሉእ የሆነች ሰላምና ረጅሙን ዕድሜ ይስጣችው። ዙፋናቸውንም በየጊዜውና በየዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔር ይጠብቅላቸው በረከትና ሰላም ለዘለዓለሙ ይሁን አሜን ።

በመጨረሻውም አቡነ ዮሐንስ ተነሥተው አጭር ቃል ተናግረው ግርማዊት ንግሥትንና ግርማዊ ንጉሥን መኳንንቱንና ሕዝቡንም ሊቃውንቱንና ካህናቱንም የውጭ አገር የዲፕሎማቲክን ሰዎች ሁሉ ባርከው አቡነ ዘበሰማያት አሳርገው ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ሊቃውንቱና ካህናቱ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ቀርበው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ወረብ ወረቡ።ቄርሎስኒ ይቤ ነዋ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት አሐዱ እምቅዱሳን ቀደምት መጽአ ይርድአኒ። አፅንዓኒ ወይቤለኒ ብእሴ እግዚአብሔር ቄርሎስ ኢትፍራህ ዕናዕ ወተዓገሥ ።

ወእንዘ ይትናገረኒ ፀናዕኩ በኢትዮጵያ ሀገረ ንግሥት እስከለ ማርያም። ወእቤሎ ንግረኒ እስመ አፅናዕከኒ ወይቤለኒ ሰብ ተአምር ዳዕሙ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥክሙ ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ እንደ ገና ሕዝቡን ሁሉ ባርከው በእጀብና በክብር እንደመጡ በእጀብና በክብር ወደ ማረፊያቸው ስፍራ ተመለሱ ።

ብታኅሣሥ ፴ቀን የዳግማዊ ምኒልክን መታሰቢያ ቤት ጎበኙ።

ከዚህ በላይ እንዳስታወቅን አቡነ ዮሐንስ ስለ ሽምግልናታቸውና ስለ መንገዱ ርቀት ደክመው ነበርና ብዙ ቀን በአ ዲስ አበባ ለመቈየት የማይቻላቸው መሆኑን ሐኪሙ ስለ አስ ታ ወቀ በጥር ፬ቀን ዓርብ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የሚያ ስፈልጋቸው መሆኑን ቍርጥ አድርገው ተናገሩ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪም ሊቀ ጳጳሳቱ በቶሎ ወደ ሀገራ ቸው ለመመለስ ቍርጥ አሳብ ማድረጋቸውን በሰሙ ጊዜ ባለፈው ዓመት የሀገሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከመምህራንዋ መካከል ጳጳሳት ስለ ተሾሙላት ትልቅ ክብር አግኝታ ሳለች አሁን ደግሞ ራሳቸው ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ዮሐንስ ሊጎበኟዋት በመምጣታቸው ትልቅ ክብር ተደርጎላታልና ደግሞ የበለጠ ክብር እንዲሆንላት የደብረ ሊባኖስን እጨጌና ደግሞ ሌላ አንድ መምህር ጳጳሳት አድርገው ይሹሙልን ብለው በፍቅርና በወዳጅነት ለመኗቸው ።

ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ዮሐንስም የጀመሩትን መንፈሳዊ የሆነ የደግነት ሥራ ለመፈጸም ሲሉ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን አሳ ብና ልመና ተቀብለው በጥር ፩ቀን በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ቅዳሴ ቀድሰው የደብረ ሊባኖስን እጨጌ ገብረ መን ፈስ ቅዱስን የጳጳስነት ቅባት ቀብተው ስማቸውን ሳዊሮስ ብለው ጳጳስነት ሾሟቸው ። ሁለተኛውን መምሕር መርጣችሁ ወደ ምድረ ግብፅ በሰደዳችሁልኝ ጊዜ በዚያው እሾመዋለሁ ብለው የታመነ ቃላቸውን ለግርማዊ ንጉሥ ሰጥተዋል ።

ከዚም በኋላ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ስለ መውደዳቸው መታሰቢያ የሚሆንነገርለመስጠት ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ አሰበው ፈቃዳቸውን ቢጠይቋቸው የኢትዮጵያና የግብፅ ልጆች የጥበብና የዕውቀት የመንፈሳዊ መጽሐፍና የሃይማኖት ትምህርት ቤት አቁመው ለማስተማር ፈቃዳቸው መሆኑን ገለጹላቸው ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥም ይህ አሳብ ለኢትዮጵያ ልጆችና ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ጥቅም የሚያመጣ መሆኑን ስለ ተረዱት ሁለቱም ፈቅደው ዋጋው እስከ ፸ሺ የሚሆን ቦታና ቤት ገዝተው ርስትነቱን ለኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት መጀመሪያ አባት ለቅዱስ ማርቆስ ሰጥተናል። ስሙ ግን እርስዎ ኢትዮጵያን ለመውደድዎ መታሰቢያ እንዲሆን የአቡነ ዮሐንስ ትምህርት ቤት ተብሎ በስምዎ ይጠራልዎ ብለው ግርማዊ ንጉሥ ከሊቀ ጳጳሳቱ ጋራ ከዚያው ከቦታው ድረስ ሔደው አስረከቡዋቸው።

በጥር ፪ ቀን የሊቀ ጳጳሳቱ ወደ ሀገራቸው መመለስ የተቈረጠ ነገር ስለሆነ ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ፡ ልዕልት መነንና ሌሎችም ወይዘዝሮች ሊቀ ጳጳሳቱ ን ለመሸኘትና ቡራኬ ለመቀበል ወደ ባቡር መቆሚያ ወርደው ይጠብቁ ነበርና በሁለት ሰዓት ተኩል ሊቀ ጳጳሳቱ ደረሱ ።

ጎሥር ደቂቃ ያህል እንደ ዓረፉ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ሊቀ ጳጳሳቱንና መኳንንቱንም ሕዝቡንም ሁሉ ደስ ለማሰኘት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ብፁዕ ወቅዱስ ፓትረያርክ ሆይ ።

በዘመንዎ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተደረገላትን ክብር በቃላችን ተናግረን አንጨርሰውም ።

የግብፅና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንድነት ከተጀመረ ምንም ዘመኑ ብዙ ቢሆን ያንድነታቸውና የፍቅራቸው ማሠርያ እየጠበቀና እየሰፋ የሔደው በቅዱስነትዎ ዘመን መሆኑን የማያውቅ ሰው አይገኝም ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ ።

እግዚአብሔር ነፍሳቸውን ይማርና ፓትረያርኩ አቡነ ቄርሎስ ገና በሕይወቱ ሣሉ በ፲፱፻፲፰ ዓመት ወይዘሮ መነን ደግሞ በ፲፱፻፲፯ ዓመት እኛ ራሳችን ምድረ ግብፅን በጐበኘን ጊዜ ቅዱስነትዎ በእስክንድርያ በመንበረ ማርቆስ የሃይማኖት ወንድሞቻችንን ሁሉ ሰብስበው ያደረጉልንን የክብር አቀባበል ለዘለዓለም በልባችን እንደ ሥዕል ተሥሎ ይኖራል ። በዚያም ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ለማየት እየተመኙ የነገሩንን መንፈሳዊ አሳብዎን ሳንዘነጋው እንኖር ነበርና ፤ አሁን በእግዚአብሔር ፈቃድ አሳብዎ ስለተፈጸመ በመምጣትዎ ደስታችን ታላቅ ሆነ ።

ደግሞ አሁን ባለፈው ዓመት ብፁዕነትዎ የክርስቶስና የሐዋርያው የቅዱስ ማርቆስ ተከታይ መሆንዎን በዓለም ሁሉ ለመግለጽ ሲሉ በኢትዮጵያ የሚኖሩ የሃይማኖት ልጆችዎ አርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸውን መውደዳቸውና በርስዋም መፅናታቸውን ተመልክተው በግብፃውያንና በኢትዮጵያውያን ልጆችዎ መካከል ምንም ልዩነትና አድልዎ ሳያደርጉ አስተካክለው ይህን እጅግ የከበረና ትልቅ የሆነ የጳጳስነት ማዕርግ በመስጠትዎ እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሌሎችም አገሮች ሕዝብ አመስግኖዎታል ።

ከሁሉም ይልቅ ልባችንን በደስታ የመላውና በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ለዘላለም ሲነገር የሚኖረው፤ የመንገድ ርኅቀት፤ የሽምግልና ሰውነት ሳይከለክለዎ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና እኛን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ልጆችዎን ለማየት መምጣትዎ ከመጡም በኋላ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መን በር ላይ ቅዳሴ ቀድሰው ላብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የጳጳስነት ማዕርግ መስጠትዎ ነው ።

ብፁዕ አባታችን ሆይ

ወደ ፊት የሚነሡትን የግብፅንና የኢትዮጵያን ልጆች አንድነታቸውን እያፀናን ለመሔድ መፍቀዳችንን ለመግለጽ ትናት ና ማታ በአጭሩ እንዳስታወቅነዎ ባዲስ አበባ ከተማችን መካከል የኢትዮጵያና የግብፅ ልጆች የሚማሩበት ቦታና ቤቶች ለመስጠት ማሰባችን ምንም ርስትነቱን ለቅዱስ ማርቆስ ብናደርግ ቅዱስነትዎ ኢትዮጵያን ለመጐብኘዎት የስምዎ መታሰቢያ እንዲሆን ብለን በሰጠነዎ ቦታ ላይ የትምህርት ቤት ለማቆም ማሰብዎን ስለ ገለጹልን፤ እስክንድርያ በመጣንበት ጊዜ በቅዱስ

ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በትጋትዎ ያቆሙትን የትምህርት ቤትና የሚማሩትን ልጆች አይተን ነበርና ይህንም የትምህርት ቤት እንደዚያው በአስክንድርያ እንዳቆሙት የትምህርት ቤት አድርገው ያስፋፉታል ያለሙታል ብለን በፍጹም ልባችን ደስ አለን ።

ደግሞ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚራሩ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አቡነ ቄርሎስን መርጠውና ሊቀ ጳጳሳት አድርገው ስለ ሰደዱልን እናመሰግንዎታለን ። እሳቸውም ገና ከመምጣታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየሰፋችና በኦርቶዶክስ ሃይማኖቷ እየፀናች የምትሔድበትን አሳብ በማሰባቸው አይግ ደስ ብሎናል ደኅንም መልክም አሳባቸውን እንዲፈጽሙ በሚቻለንና በሚገባን ነገር ሁሉ እርዳታችንን እናጉድልባቸውም ።

ደግሞ ቅዱስነትዎን ተከትለው መጥተው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የጎበኙትንና በመንፈሳዊ ሥራ የረዱዎትን ብፁዓን አባ ሉቃስንና አባ ዮሳብን እናመሰግናቸዋለን። ደግሞ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ላቆሙትና እኛም ላቆምነው ትምህርት ቤቶች ስለ ረዱት እርዳታ እናመሰግናለን። ብፁዕ አባት ሆይ እግዚአብሔር ኃይልና ፅናት ሰጥቶ በመምጣትዎ እንደ ጠበቀዎ እንደዚሁ በመመለስዎም ኃይልና ፅናት ሰጥቶ እንዲጠብቅዎ። ወደፊትም ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ እንዲሰጥዎ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በእኛም በራሳችን ስም በሙሉ ኢትዮጵያም ሕዝብ ክርስቲያን ስም ሁሉን እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

Très Saint Patriarche,

Il Nous serait impossible d'énumérer de vive voix toutes les marques d'honneur qui, de votre temps, ont été prodiguées à l'église Ethiopienne.

Bien que l'union des Eglises Copte et Ethiopienne remonte à une époque très reculée, nul ne peut ignorer leur unité ainsi que les liens d'affection qui les unissent et qui ont été rendus plus étroits dans le temps de votre Saint Patriarcat.

Très Saint Père,

A l'époque où le Patriarche Abouna Kerlos don l'âme repose en Dieu, était encore en vie à l'occasion de Notre visite en Egypte, celle de Woisero Manen en 1915 et la Notre en 1916, Votre Sainteté réunit à Alexandrie, siége Apostolique de Saint Marc, tous les Frères de Notre Foi et la reception que vous nous avez réservée est restée gravée dans notre cœur.

Nous nous souvenons toujours des pensées inspirées de l'Esprit Saint que vous nous avez exprimées en ce temps én nous faisant part de votre désir de visiter l'Ethiopie et notre joie est maintenant très vive d'avoir vu ce projet se réaliser avec la grâce de Dieu.

L'année dernière, en outre, Votre Sainteté désireuse de manifester devant le monde entier qu'elle est le digne Vicaire de Jesus-Christ et de Saint Marc, en considérant que Vos enfants spirituels Ethiopiens persistent dans leur Foi et restent attachés à la religion orthodoxe leur fit l'honneur le plus grand en leur conférant la dignité épiscopale afin qu'il n'existe aucune distinction entre les fidèles Coptes et Ethiopiens, marquant ainsi la volonté de les rendre égaux. Non seulement, la reconnaissance du Peuple Ethiopien vous a été acquise, mais aussi les autres peuples vous en ont rendu grâce.

Et par-dessus tout, le fait d'avoir entrepris ce voyage sans vous laisser impressionner par des considérations de distance ou d'âge, le fait que vous êtes venu visiter l'Eglise Ethiopienne, vos enfants Orthodoxes et nous-même, et qu'après votre arrivée vous avez consacré l'Abouna Sawiros en célébrant vous même le Saint Office dans notre Eglise Ethiopienne, ont rempli d'allégresse notre cœur et ces événements resteront éternellement enregistrés dans l'hitoire de notre Eglise

Très Saint père,

Désireux de resserrer à l'avenir les liens entre a jeunesse Ethiopienne et Copte, nous avons formé le projet, ainsi que nous vous l'avons brièvement exprimé hier soir, d'affecter dans notre Capitale un terrain et bâtiment dans lesquels la jeunesse Ethiopienne et Copte pourra s'instruire Nous avons été très touché du désir que vous avez bien voulu nous exprimer d'édifier en école sur ce terrain que nous avons offert en souvenir de la visite que votre Sainteté a rendue à l Ethiopie, bien que la propriété de ce terrain doive rester au siège de saint Marc

En nous rappelant la visite que nous avons faite à Alexandrie, lors de note passage, aux élèves du collège édfié à côté de l'Elise saint Marc par votre sollicitude, nous ressentons une vive joie à la pensée que vous ferez cette école fructueuse et prospère à l'égale de celle d'Alexandrie.

Nous tenons, en outre, à vous remercier d'avoir choisi la personne d'Abouna Kerelos qui est animé de la plus grande mansuétude envers le peuple Ethiopien soumis à la volonté du Très-Haut. Nous avons la satisfaction de constater que, dès l'époque de son arrivée il a eu le désir de faire tout ce qui

était en son pouvoir pour fortifier et répandre la Foi orthodoxe au sein de l'Eglise Ethiopienne. Nous ne manquerons pas de lui accordrer Notre concours dans tout ce qui sera possible et utile à la réalisation de ses excellents desseins

Et Nous remercions également Leurs Béatitudes Aba Loukas et Aba Yosab, collaborateurs spirituels de votre Sainteté qui, ont visité l'Eglise Ethiopienne.

Nous vous remercions des dons que vous avez bien voulu faire au Lycée créé par Sa Majesté l'Empereur Menélick II et à celui que Nous avons fondé.

Très Saint père,

Au Nom de Sa Majesté l'Impératrice Zaouditou, en Notre Nom personnel, et au Nom du peuple chrétien d'Ethiopie tout entier, Nous prions le Très-Haut de vous donner pour le voyage de retour la même force qu' il vous a donnée pour venir de vous accorder longue vie et de vous conserver en bonne santé.

Vive l'Ethiopie.

ሊቀ ጳጳሳቱም ለግርማዊት ንግሥትና ለግርማዊ ንጉሥ ለመኳንንቱና ለሊቃውንቱ ጸሎትና ቡራኬ ከዳረጉ በኋላ ከግርማዊት ንግሥትና ከግርማዊ ንጉሥ ጋራ ፎቶግራፍ ተነሥተው ወደ በቡር ገቡ ።

ግርማዊ ንጉሥ ግን ሊቀጳጳሳቱን እስከ አዋሽ ድረስ ለመሸኘት ቍርጥ አሳብ አድርገው ነበርና አቡነ ቄርሎስን፥አቡነ ሳዊሮስን፥አቡነ ጴጥሮስን፥ ልዑል ራስ ካሣን፥ክቡር ራስ ከበደን ፥ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴን፥አስከትለው እስከ አዋሽ ሸኝተው ተመለሱ።

ሊቀጳጳሳቱንም እስከ ጅቡቲ ለመሸኘት ያገር ግዛት ሚኒስቴር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅና የገንዘብ ሚኒስቴር በጅሮንድ ዘለቀ እየታዘዙ ወረዱ ። የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያ ሆይ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን የረዱዋትን እርዳታና የሰጡዋትን ክብር እያሰብህ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ታሪክ በምትጽፍበትና በምታነብበት ጊዜ ሁሉ የአቡነ ዮሐንስን ስም ለመርሳት የማይገባህ መሆኑን እንድታሰብ ብርሃንና ሰላም ይለምንሃል ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ስለ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ጵጵስና የተደረገ የደስታ በዓል ።

ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመት በታላቁ በአፄ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ብፁዕ ወቅዱስ በትረ ያርክ አቡነ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ከተከተሏቸው ከግብፃውያን ቀሳውስትና ዲያቆናት ጋራ ቀድሰው ብፁዕ እጨጌ ገብረ መንፈስ ቅዱስን በቀድሞ መዓርጋቸው ላይ ስማቸውን ሳዊሮስ ብለው ከፍ ያለ የጵጵስና መዓርግ ሾሟቸው ። ይኸውም የተደረገ አቡነ ዮሐንስ ወደሀገራቸው ለመሔድ ስለ ተፋጠኑ በድንገት ነበርና ጥር ፴ ቀን እንደገና የጵጵስናውን በዓል ለማክበር በረድኤታቸው የተሰበሰቡ መዘምራን ሌሊት ማኅሌት ቁመው አድረው ቅዳሴ ውጭ ሲሆን ልኡካኑም አክሊል ደፍተው ልብሰ ተክህኖ እንደ ለበሱ ወጥተው በደረጃው ላይ በአቡነ ሳዊሮስና በአቡነ አብርሃም ዙሪያ ተደርድረው ቁሙ መዘምራኑም አበ ኵልነ አበ ሳዊሮስ አስተጋብእነ ለስብሐተ እግዚአብሔር እያሉ በሽብሸባ ፫ጊዜ ዑደት ተደርጎ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ቆሙና ምክር እዝናት ጀመሩ ቃሉም እንደሚከተለው ነው ።

ወንድሞቼ ልጆቼ ሆይ እኒህ በእርግና የደከሙ ሽማግሌ ለኢትዮጵያ ፍቅር ብለው የመንገዱን መከራ ታግሠው እስከዚሁ መጥተው ይኸ ለኔ ያደረጉት ሥራ አሁን ለናንተ ቀላል ቢመስላችሁ ለኋላ ትውልድ የማይረሳና የማይናወፅ መሠረት ነውና ይኸን ላደረገል አምላክ ምስጋናችነን ሁል ጊዜ እናቅርብለት ። ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም በኢትዮጵያ ላሉ ልጆቼ ሁሉ በጸሎታቸው እንዳይረሱኝ ንገርልኝ ስላሉኝ አስታውቃችኋለሁ ። እኔም እስከ ዛሬ ድረስ በራሴ ፈቃድ ነበር ያለሁት ። አሁን ግን በዚህ በከባድ ቀንበር ስለገባሁና በሕዝብ ደም አላፊ ስለሆንሁ በጸሎታችሁ እንዳትረሱኝ አጥብቄ እለምናችኋለሁ።

እናንተም ልጆቼ በፍቅር ተጸምዳችሁ ቀናውን መንገድ ያዙ ብለው ዕንባ ጭምር የሚያሳዝን ምክር መክረው ከጨረሱ በኋላ፤ አቡነ አብርሃም መዝሙር ፺ዘየኀድር በረድኤተ ልዑልን እስከመጨረሻው ተርጕመው ልብ የሚነካ ምርቃት መርቀው አሳረጉና በብዙ አጀብ ወደ ቤታቸው ሔዱ ። በቤታቸውም ሁለቱን ጳጳሳት በቀኝ ፪ን ጳጳሳት በግራ ቀጥለው ሊቃውንቱን አስቀምጠው ሙሉ ግብር አድርገው ቅኔው እንደ ውሃ ሙላት ሲፈስ ዋለ።የግብሩን አኳኋን ዘዕፁብ ለነጊር ይለዋል ። ከዚህ ቀደም በሀገራችን ተደርጎ የማያውቅ ይኸ ትልቅ ክብር ዛሬ ለዕድላሙ ለአቡነ ሳዊሮስ ስለተደረገ ለኢትዮጵያ የክብሯ ተቀዳሚ መሆኑ አይጠረጠርም ። (ወይ መታደል) ከሀገራቸው ሳይወጡ ከቤታቸው ሳይናወጡ፤ባቀኑት መቅደስ ውሥጥ በሊቀ ጳጳሳቱ እጅ ጵጵስና መቀበላቸው የክብራቸውን ገናንነት ያስረዳል ። ብፁዕ ወቅዱስ ውእቱ ዘረከበ ክፍለ በትንሣኤ(ጵጵስና) እንተ ትቀድም መጺአ፣ ራእይ፤ም ፳ ቁ ፮ ።

እኔም እዚያው ሁኜ ስላየሁ በቦታ ርኅቀት ላላዩና ላልሰሙ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ከሙሉ በክፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ጽፌ አበረክታለሁ ።

ተክለ ጊዮርጊስ ዘደብረ መንክራት ።

ስለ ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዘማኔል ።
ወደ አዲስ አበባ መግባት ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ስለ ጤናቸው አየር ለመለወጥ ከክብርት ባለቤታቸው ከወይዘሮ ዓፀደ ጋራ ወደ አውሮጳ ሒደው ነበርና አሁን ከሕመማቸው ድነው በጥር ፪ቀን ማታ ወደ አዲስ አበባ ገቡ ።

ክቡር ከንቲባ ነሲቡንና ባለቤታቸውን ለመቀበል ብዙ መኳንንትና የከተማ ዘበኛ የከተማ ነጋዴዎችም ወደ ባቡር ማረፊያ ወርደው ነበር። ክቡር ከንቲባ ነሲቡ በገቡ ጊዜ መኳንንቱና ነጋዴው የከተማ ዘበኛም አክብሮ በትልቅ ደስታ ተቀበላቸው። ክቡር ከንቲባ ነሲቡ በአቶሞቢል ወደ ቤታቸው ለመሔድ በተነሡ ጊዜም መንገዱ ከባቡር ማረፊያ ጀምሮ እስከ ከተማው ውስጥ ድረስ ከአቶሞቢል ብርሃን የተነሣ ፀሐይ የበራበት መስሎ ይታይ ነበር ።

ብርሃንና ሰላም ክቡር ከንቲባ ነሲቡ ጤና አግኝተው ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ በደኅና ስለገቡ ደስታውን እየገለጸ እንኳን ደኅና ገቡ ይላል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቈሚል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶትሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ-

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን- ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES&SONS,

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናን ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

በዳሮማዊ ንጉሥ ቀ.ኃ.ሥ. መኩንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፬
6me ANNÉE № 4

ሐሙስ ጥር ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 23 JANVIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጻዘት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የብፁዕ አባ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ወኖብያ ወኢትዮጵያ ከምስር ወደ ኢትዮጵያ መንገዝ ።

ብፁዕ አባታችን አባ ዮሐንስ በእግዚአብሔር ፈቃድ በጣብፅ ሕዝብ ፍቅር አምና በ፲፱፻፳፩ ዓ ም በ፯ ታኅሣሥ እሑድ ቀን በካይሮ ከተማ ሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ ወኖብያ ወኢትዮጵያ ተብለው የአቡነ ቄርሎስ ፻ ተኛ ተከታይ ሁነው በቅዱስ ማርቆስ መንበር ተቀመጡ ። ከዚያ ቀን ጀምሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍቅር በጣም አድሮባቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ደስ ለማሰኘት የፍቅር አባትነታቸውን ለመግለጽ ቢወዱ በደብዳቤም ሆነ በቴሌግራም ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ከግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ጋራ ሁለ ጊዜ ተግተው ይላላኩ ጀመር። የእውነተኛ ፍቅራቸውን መግለጽ የሚያስረዳ ከዚህ ቀደም ተደርጎ የማይታወቀው የኢትዮጵያን መምህራን በ፳፬ ሰኔ ፲፱፻፳፩ ዓ ም አብርሃም ? ይስሐቅ ? ሚካኤል ? ጴጥሮስ ብለው ሰይመው ፬ጳጳሳት ፭ኛ ሊቀ ጳጳሳት ቄርሎስ ብለው ሰይመው ሹመው ለልጆቹ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሑሩ ወመሀሩ ብለው ልከዋል ።

ደግሞ የሞቀ ፍቅራቸው በዚሁ ብቻ አልተወሰነም ፤ በወሬ ከመስማት ሁዶ ማየት ይበልጣል ብለው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ንጉሦችዋንና ሕዝብዋን ለማየት ለመባረክ በጣም ናፈቃቸው ። በ፳ታኅሣሥ ንጉሥ ፉአድን የምስርን ንጉሥ የኢትዮጵያን ንጉሦችና ሕዝብዋን ሒጄ ለማየት ይፍቀዱልኝ ብለው ጠየቁ ። ንጉሥ ፉአድም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ የፍቅር ወዳጅነት ለማፅናት በጣም ፈቃዳቸው ነውና ይህነን የብፁዕ አባታችነን ምኞት እንደሰሙ ደስ ብልዋቸው ከዚያ ሒደው የሁለቱን መንግሥት አገር ሕዝብ የፍቅር ወዳጅነት አጥንተው እንዲመጡ ተስፋ አለኝና በጣሙን ደስ ይለ-ኛል በደኅና አድርሶ በደኅና ይመልስዎ ብለው ፈቀዱላቸው ። ከዚያ በኋላ ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መጥቼ ለያችሁ አስቤ አለሁና እናንተስ ውዳችሁ ነውን ሲሉ በቴሌግራም ጠየቁ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥም ብፁዕ አባታችን ፈቃድዎ ሁኖ መጥተው ሲባርኩን በጣሙ ደስ ይለናል ደስታችነንም በቴለግራም ለመግለጽ አንችልም ብለው መለሱ ።

ከዚህ በኋላ ብፁዕ አባታችን ዮሐንስ የፍቅር ምላሽ ከልጆቻቸው እንደሰሙ የፍቅር ናፍቆታቸው በቶሎ ለመንሣትና የጌታችነን የብርሃነ ልደቱን በዓል ከልጆቻቸው ጋራ ለመዋል አስቸኰላቸው ። በ፲፬ ታኅሣሥ ከጥዋቱ በ፫ ሰዓት በባቡር ወደ ፖርትሰዒድ ተጓዙ። በ፱ሰዓት ገቡ፤ በፖርተሰዒድ ያለው ሕዝባቸው ከባቡር መቋምያ መጥቶ ተቀብሎ ወደ ተሰናዳላቸው ማረፊያ ድረስ ሸኛቸው። በ፲፭ታኅሣሥ ከሌሊቱ በ፱ሰዓት መርከቡ ይገባል እንደገባም ወዲያው ይነሣል ተብሎ ነበርና ሕዝቡ ሁሉ አባታችን ከመርከብ እስኪገቡ እንሸኛለን ብሎ ሲጠባበቅ አመሸ፤ መርከቡ ይገባል ከተባለበት ሰዓት አሳልፎ ከሌሊቱ በ፯ሰዓት ገባ ። መቼ ይነሣል ተብሎ ቢጠየቅ ነገ በ፱ሰዓት ከጥዋቱ ተባለ ሕዝቡ ይህነን ሰምቶ በየቤቱ ተመልሶ አደረ ። በ፲፮ ታኅሣሥ ከጥዋቱ በ፭ሰዓት ብፁዕ አባታችን ዮሐንስ በካህናትና በሕዝብ ታጅበው ከመርከብ ገቡ ። ከመርከቡ አዳራሽ ገብተው ቊጭ እንዳሉ ቀኝና ግራቸው ካህናቱና ሕዝቡ በወንበር ተቀመጠ ወምበር ያልደረሰውም እንደቆመ ፲ደቂቃ ያህል ጸጥ አለ ። ከዚህ በኋላ ከሕዝቡ ጉባኤ አንዱ የስንብቻ ቃል ሊናገር ተነሥቶ ከመሃከል ቆመ ። የተናገረው ጉባኤም የሚከተለው ነው።

ብፁዕ አባታችን ዮሐንስ ፤ ወደ ኢትዮጵያ አገር ሊሔዱ መነሣትዎን ሰምተናል ከመርከቡ እስቲገቡ ድረስ ቊርጥ መነሣትዎን አልተረዳነውም ነበር። አሁን ግን ከመርከብ መግባትዎን

አይተን በቀኑርጥ መነሣትዎን ከኛ መለየትዎን ተረዳነው። ከብዙ ዘመናት ጀምሬ እታችሁ ልጆችሁ ነኝ ከማርቆስ ልጅነት ክክርስቶስፍቅር የሚለየኝ የለም ፍቅራችሁን የሚያስረሳኝ የለም የምትለን የእታችን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ሕዝበ ክርስቲያን ለመጠየቅ በቀኑርጥ መንዝዎን ተረድተናል ። እኛ ልጆችዎ ግብፃውያን ለጊዜው ከኛ መለየትዎን አይተን ተደናግጠናል ፤ ምነው ያለርስዎ ጠባቂ ጠያቂ የለንምና ከሰው መርጦ በጎቼን መንጎቼን ጠብቅ ብሎ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ያስቀመጠዎ አምላክ በጸሎትዎ ጊዜ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ የዮሴፍ አምላክ መንጋህን ጠብቅ ርስትህን ጠይቅ እያሉ ይዘክሩን ። አለርስዎ አሳቢ የለንምና ፤ ልጆችዎን አይርሱን የተባረከችውን አገር የኢትዮጵያን መንግሥት ያሉ ሕዝብዋን ያብዛ፡የዓባይን ምንጭ እያጎረፈች የምትልክልንን በረከትዋን እያየን እንደምናስባት ያስታውሱልን ።

እርስዎም የአባትነትዎን ፍቅር አሳስበዋት፡ አበረድተዋት፡ ባርከዋት፡በደኅና ተመልሰው እንዲመጡልን በተስፋ በናፍቆት እንጠብቀዎታለን። ዛሬ እያለቀስን እያዘን እየተከዝን እንደሸኘ ነዎት በደኅና ተመልሰው መጥተው በደስታ እንድንቀበልዎት ልዑል እግዚአብሔር በፊት በኋላ ከበ በክንፉ እንደጋርደው ከድካም ከጕዳት ጠብቆ ካሰቡት አድርሶ በደኅና ይመልስዎ አሉና ፫ጊዜ የአባታችንን የአባ ዮሐንስን ዕድሜያቸውን እግዚአብሔር ያርዝመው እንበል አሉ ። ሕዝቡ ሁሉ ተነሥቶ እንደዚሁ ቃል ተናገረ። ቀጥሎም የንጉሥ ፋሩድንና የአልጋ ወራሻቸውን ዕድሜ ያርዝመው አሉ ። ቀጥሎም የኅርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱንና የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪን ዕድሜ ያርዝመው ብሎ ሕዝቡ በጭብጨባ ጨረሰ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ብፁዕ አባ ዮሐንስ እንባታቸውን ደፍተው እንባቸው አልቃገድ ብሎ እየተንቈረቈረ በመሀረም ሲጠርጉ ነበር ። በዚሁ ምክንያት ለሕዝቡ የስንብት ቃል ለመመለስ አልተቻላቸውምና በቀኛቸው ተቀምጠው ለነበሩት አባ ጴጥሮስ ለተባሉት ጳጳስ ኋላም አብረዋቸው የሚጓዙ የሕዝቡን ልብ የሚያረጋጋና የሚያፅናና ቃል ባጭሩ ተናግረው አባታቸውን ከልብ በመሸኘታቸው አመስግነው ሕዝቡን እንዲያሰናብቱት ነገርዋቸው ። አባ ጴጥሮስም ባጭር ቃል አባታችንን በክብር ተቀብለው በክብር በመሸኘታቸው አመስግነው አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው ሕዝቡን አሰናበቱት ። ሕዝቡም አሜን አባታችንን በደኅና ይመልስልን እያለ እጃቸውን እየሳመ ተሰናበተ ። መርከቡም ይነሣል የተባለበትን ሰዓት አሳልፎ ከማታው በ፲፪ ሰዓት ተነሣ ። ብፁዕ አባታችንና አብረዋቸው ያሉት ሁሉ ካሰቡት በደኅና ገብተው የኢትዮጵያ ሕዝብም ሲገቡ በቀባበሉ በማስተናገዱ በደስታ ብእልልታ በእምቢልታ ተቀብሎ ሲመለሱም በደኅና በመልካም መሸኘቱ ደስ እንደሚያሰኛቸው ተስፋ አለን ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ሊቀ ጳጳሳት መጥተውለት እንዲያው እንግዳን ማክበር ፤ መቀበል ፤ ይወዳልና በእግን ወልደ አብርሃም ያሰኘዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ቀደም ያልሆነው ያልተሰማው አገሩ ኢትዮጵያ በሊቀ ጳጳሳት ዘእስክንድርያ እግር መረገጥዋን መባረክዋን አያየ ከዚህ ቀደም የነበሩት ትውልድ ያላዩትን በማየቱ ፈጣሪውን እንዲያመሰግን ለንግሥታችን ዘውዲቱና ለንጉሣችን ተፈሪ ዕድሜያቸውን ያርዝምልን እያለ ለመለመንና ለማመስገን ልቡና ይስጠው ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ወደ አዲስ አበባ በመጡ ጊዜ በአዲስ አበባ የተደረገ የክብር አቀባበል ።

የእስክንድርያና የኢትዮጵያ ፤ የኖብያም በትረ ያርክ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ለማየት ነገሥታትዋንና ጳጳሳትዋን ካህናትዋንና ሕዝብዋንም ለመባረክ ከእስክንድርያ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣታቸው የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ከልጅ እስከ ሽማግሌ ፤ ከጌታ እስከ ሎሌ የሁሉም ደስታ ከልክ ያለፈ ሆነ ። ይልቁንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዱሮ የበለጠች ሁና እየሰፋች እንድትሔድ ከመምህራኖችዋ ጳጳሳትን ስለ ሾሙላትና መጥተውም ስለ ጐበኙዋት የሆነላት ደስታ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሆሣዕና ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ በገባ ጊዜ ለተደረገው ደስታ ምሳሌ የሚሆን ነው ።

ከደስታቸውም ብዛት የተነሣ በአዲስ አበባና በውራጃዋ ያሉት አድባራት ሊቃውንትና ካህናት በየክፍላቸው የገሠሡትን ግሥና የተቀኙትን ቅኔ ከዚህ ቀጥለን በየተራው እንጽፋለን።

ግሥ ዘራጉኤል ደብረ ኃይል ።

ተጋቢአሙ በደመና ሰማይ ኵሎሙ ሐዋርያቲሁ ተበሀሉ በበይናቲሆሙ ምንትኑመ እስተጋብአነ ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ውስተ ዛቲ ኢትዮጵያ ሀገረ ምኒልክ ወይቤሎ ዮሐንስ ለቄርሎስ ጻሊኬ እኁየ ቄርሎስ በእንተ አስካለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ወይቤሎ ቄርሎስ ለዮሐንስ እሮ እነ እጼሊ ዘእምቅድሜክሙ እስመ ሐዲስ ተክል እነ ወተፈሥሑ ኵሎሙ ሐዋርያት በእንተ ዘይቤሎሙ ቄርሎስ አብእዋ ቤታ ለአስካለ ማርያም ።

ግሥ ዘዑራኤል ደብረ ጽጌ ።

ብፁዕ አንተ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘሀለወከ ታእምር መንግሥተ ምኔልክ ንጉሠ ነገሥት ወተሐውር ቅድመ ንግሥትነ አስካለ ማርያም ወንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ጻሊ በእንቲአነ ውስተ ርእሰ አውደ ሃይማኖት ኢትዮጵያ ተጽሕፈ ስምከ ባርከነ ንጉሣእ በረከትከ ።

ግሥ ዘመካነ ሥላሴ ።

እምላከ አበዊነ ኄመከ ታእምር ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ። ትግበር ፈቃዶ ለኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ዓለም ። ወትሰብክ ቃላቲሃ ለአስካለ ማርያም። በስብከተ ወንጌል ወበዕሩይ ሃይማኖት ዘሎቱ ተጸዋዕከ ወሰላም ለምጽአትከ ።

ግሥ ዘጊዮርጊስ ገነተ ጽጌ።

መጽአ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ወሠረፀ ጽድቅ በመንግሥተ አስካለ ማርያም ወበእንተዝ ይረድአ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥነ ወራሴ መንግሥት ያደ እድያመ ኢትዮጵያ እንዘ ይሜህር ቃላተ ወንጌል።

ግሥ ዘሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ደብረ መንክራት ።

በዕሃሌታ ፡ ብፁዕ አንተ ዮሐንስ ዘሀለወከ ታእምር እስከለ ማርያም ወተሐውር ቅድመ ኃይለ ሥላሴ ጻሊ በእንተ ምኒልክ ውስተ ርእሰ ዓውደ ጳጳሳት ተጽሕፈ ተዝከርከ ብርከ ለኢትዮጵያ ትንሣእ በረከተከ ።

ናስተበፅዕ ትሕትናከ ሊቀ ጳጳሳት ዮሐንስ ሰማዒ ከዊና ቃለ አብ አትሒቶ ርእሰ ሰገደ በብረኪሁ ኀበ ፈጣሪሁ ዮሐንስ ሊቅ ሊቀ ጳጳሳት ሰአል ወጻሊ በእንቲአነ ።

ግሥ ዘገብርኤል መንበረ መንግሥት ።

ብፁዕ አንተ ዮሐንስ ዘኀረየከ ኃይለ ሥላሴ ትዌድሰከ ኢትዮጵያ ወትብለከ እስከለ ማርያም ንሣረነ አንተ እለሄሙከ ሊቀ ጳጳሳት ወይቤላ ዮሐንስ እንሰ አዕበይኩ ክህነተ ወተሠየምኩ ሊቀ ጳጳሳት ንባብኪ እዳም ለኪ ካህናት የዓርጉ ስብሐተ ።

አንተሰ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኮንከ ብርሃነ ለኃይለ ሥላሴ እስመ ተሰምዐ ዜናከ ውስተ ኵሉ ምድረ ኢትዮጵያ ቃለራትዕ ሃይማኖተ ወትሢም ክህናተ ቀዋሚሃ ለእስከለ ማርያም ኪያከ ኀረየ እግዚአብሔር ።

ግሥ ዘደብረ ሰላም መድኃኔ አለም ።

አንተ ውእቱ ዮሐንስ ዘኅቡእ እምኅቡአን አስተርአይከ ለነ ወኀደርከ ምስሌነ ብርሃንከ ምስለ ከዋክብት እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ። ወትሕትናከ ምስለ ጳጳሳት ገሃደ አስተርአይከ ለነ በኢትዮጵያ እንዘ ትብል ዝንቱ ውእቱ ቄርሎስ ወልድየ ዘሠምረት ነፍስየ ወሎቱ ስምዕዎ ።

ግሥ ዘገብረ መንፈስ ቅዱስ መከነ ሕይወት።

እክሊሎሙ አንተ ለጳጳሳት ወያሚሆሙ ለክህናት መድኃኒቶሙ ለነገሥት እስከለ ማርያም ወኃይለ ሥላሴ ዜናዊ ሀማየ ሕይወት ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ሰበኩ ለነ ምጽአተ ዚአከ አበዊነ ጳጳሳት ከመ ንንግር ኵሎ ስብሐቲከ በአናቅጺሃ ለኢትዮጵያ።

ግሥ ዘላእከ ብርሃን መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ሙሴ ክህነተ ወዮሐንስ ጥምቀተ ኀቢሮሙ ፈጺሙ ሥርዓተ እለ ኀብሩ ወአርትዑ ሃይማኖተ ለክህናት ነገሩ ሥርዓተ ከመ ያዕርጉ መሥዋዕተ ወጸሎተ ርትዕተ ሃይማኖተ ኀቢሮሙ ለእግዚአብሔር ያዓርጉ ።

ግሥ፥ ቄርሎስ ክህነተ ወዮሐንስ ጥምቀተ ኀቢሮሙ ፈጸሙ ሥርዓተ እለ ኀብሩ ወአርትዑ ሃይማኖተ ለክህናት ነገሩ ሥርዓተ ከመ ያዕርጉ መሥዋዕተ ወጸሎተ ርትዕተ ሃይማኖተ ኀቢሮሙ ለእግዚአብሔር የዓርጉ ጳጳሳት ደቂቀ ኢትዮጵያ ።

ዓዲ ይቤልዎ ሕዝብ ለአበ አበይዶ ነዓ ፃእ እምብሔረ ግብፅ ከመ ትንበር ኢየሩሳሌም ነዓ ንሑር በሀየ ንትራከብ ኵልነ ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ።

ግሥ፥ይቤልዎ ለዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ንጉሠ ኃይለ ሥላሴ ወንግሥት እስከለ ማርያም ነዓ ፃእ እምብሔረ ግብፅ ከመ ትንበር ኢትዮጵያ አዳዚት በሀየ ንትራከብ ኵልነ ምስለ ቄርሎስ ወልድከ ወምስለ ኵሎሙ ጳጳሳት ደቂቀ ኢትዮጵያ ሥልሰ በ፪ ለእለ ኀረዮሙ ወጸውዖሙ ምሥጢረ ኀቡእ ከሠተ ሎሙ ወተከየደ ምስሌሆሙ ለያዕቆብ ወለዮሐንስ ደቂቀ ዘብዴዎስ ክቡራን ዓዕማደ ቤተ ክርስቲያን ወይቤሎሙ ኀረይኩክሙ ትከውኑኒ አርድእትየ መዋርስትየ ዘኪያክሙ ሰምዐ ኪያየ ሰምዐ ዘኪያክሙ አምነ ኪያየ አምነ አምኖ ለዘፈነወኒ።

ግሥ ይቤ ዮሐንስ ሊቀ ጳጳሳት ለእለ ኀ ወጸ ም ሳ ከሡሎ ወተ ም ለአብርሃም ወለይስሐቅ ለጴጥሮስ ወለሚካኤል ደቂቀ ኢትዮጵያ ክቡራን ቤተ ክ ወይ ትከ አሀድ መዋ ዘኪ ስ ኪ ሰ ዘኪ ኣ ኪ አ አምነ ለዘፈነወኒ ማርቆስ ወንጌላዊ ሊቀ ጳጳሳት ።

ኢትዮጵያ የልዕልና አበባ እያበበችና የክብር ፍሬ እያፈራች ስለሔደች የተጻፈ ግጥምና ቅኔ ።

መጽሐፍ ተዘርግቶ፥ተርጓሚ ተደራጅቶ፥ አንባቢው ተሰ-ልፎ ስብከቱን የሚሰሙ ምእመናን ዙሪያውን ተሰብስበው የመምህራን ስብከት እንደ ምርት ሲመርት የስብከቱን ምርት ማፈስ ቀርቶ አንድ ሰነፍ ወይም ዝንጉዕ የሆነ ሰው ከዚያ መካከል እንቅልፍ ወዶ ቢያንቀላፋ ወይም ሌላ ነገር ቢያስብ። ይህ ሰነፍ አእምሮው እራሱን የሚያጠፋና የእግዚአብሔር ጠላት መሆኑን ስለተረዳሁት እስከሁን ድረስ በብርሃንና ሰላም አውድማነት ከሚመርተው ከሥልጣኔ አነጋገር ማንቀላፋቴንና መስነፌን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ ተስፋ አድርጌ በጠጠር የተመሠረተ አንደኛ የዕውቀቴን ደረጃ ከዚህ በታች በሚከተለው ግጥምና ቅኔ እገልጻለሁ ።

ዮሐንስን ስሙት አድምጡት በጣም ።
ለኢትዮጵያ ሲያቀርብ ግጥም ።
ከቅዱስ ዮሐንስ ከክብረ ባላችን ።
ደኅና ያድረሰን ይክበር አምላካችን ።
ብርሃኑን ያዘጋጅ ሁሉ በየቤቱ ።
ቅዱስ ዮሐንስ ነው መጭው ዓውዳመቱ ።
ያገራችን ዕድል እጅግ ዕፁብ ድንቅ ።
ዮሐንስ መጽአ ወሠረፀ ጽድቅ ።
ያበሻን አውራጃ ቢዛወር በእግሩ ።
ልጅነት አገኘን ተጠምቀን በፍቅሩ ።
ለቅኔው ዋዜማ ጥቂት ልዘምር ።
ንግሥት ዘውዲቱ ዘላለም ትኑር ።
ከመልካሙ ንጉሥ ከተፈሪ ጋር ።

መወድስ ።

ኢትዮጵያ ትመስል ሕጠተ ሰናፔ
እምከመ ዓበየ ኮነት በኪደተ እግሩ ለዮሐስ ።
እስከ ታሕቴሃ አጽለሉ ጠበብተ ምድረ ዕርዕ ወፋርስ።
እስመ ለዮሐስ ቡራኬሁ ወክፍል ሎቱ ለቄርሎስ ርእስ።
ወተናግዶቱ ለአብርሃም
እንዘ መዓዛሁ ለይስሐቅ ወሰዋስዊሁ ለጴጥሮስ።

ሚካኤልሂ ይኬልላ በክንፈ ጸሎቱ ሐዲስ ፡፡
ወመንበረ ማርቆስ ዘአብርሀ ሰበኬ ወንጌል ሳዊሮስ ፡፡
እስካለ ማርያም ምክሕነ ወኃይለ ሥላሴ ንጉሥ።
እስመ ተዚያነውዳዓናሃ ለኢትዮጵያ ቤተ መቅደስ ።
ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ዘሥዕል ቤተ ማርቆስ ።

ጉባኤ ቃና ።

ፍሩሀከ ንበር አውልዐ ገጻም ምድራዊ ።
እስመ በደመና ተአቀኈረ በረደ እሳት ሳዕላዊ ።

መወድስ።

እምሥራቀ ፀሐይ ብሩህ እስከነ ዓረብ ።
በአፈ መላእክት ወሰብእ ትትአኰት ኃይለ ሥላሴ።
እስመ ኢተዘከርከ ምንተ እንበለ ርኅሩኄ ድምሳሴ ።
ወትከይድ ግርማዌ እንበሳ ወከይሴ ።
ወከመ ኢትትዓደዉ እምወሰና ።
ገሥጽካ ላባሕር በበትረ ኢየሱስ ሙሴ።
ያዕቆብኒ አመ ገብረ ባርኮ ብዙኀ ውዳሴ ።
እእዳዊሁ አስተኃለፈ ለባርኮ ኤፍሬም ወምናሴ።
አንተሰ በጽድቅ ከመ ትሴሲ ብእሴ ።
ኢፈለጥከ ጊዜ ውሂብ ነግደ ወፈላሴ ።

ሁለተኛ መወድስ ፡፡

ለኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ዘግርማ መንግሥት ።
ድኅሬሁ መብረቅ ወነደ እሳት ቅድመ ገጹ ።
መትረየስ ወመድፍ እበመ ይረውፁ ።
በአፍራስ እሳት ወሰረገላ ።
ወስብሐቲሆሙ ዘመፍርህ ድምፁ።
ወእንዘ ፀሀሙ ይረውፁ ።
በዶሮ ለመድፍ መትረ ኢየሱስ ቢጹ ።
አግብአሂ ኃይለ ሥላሴ ሰይፈ መቅረፁ ።
እምጣነ ይሰይም ውስተ ደመና ቀስተ ደመና ወቀበተ ሐፁ።
ወአንበርተ ሐዲስ ፍጥረት አመ በሰማይ ሐወጹ ።
በአግረ ምሳሌ ዘብልጣሰር መትከፈ ደመናት ይረግጹ ።
አለቃ ማዘንጊያ ዘግላውዴዎስ ።

ጥዜማ ፡፡

ዘርአ ወዝናመ ኢኀሠሠት ምንተ ገራኅተ ዡሉ ዓለም ፡፡
እስመ ዘርዕ ወልዳ ወወልዳ ዝናም ።
ወአመ አብሰራ ገብርኤል በዘኢይትሔሰው ሕልም ።
ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ።
እስመ ቃሉ እምዡሉ ጥዑም ።

ክብር ይእቲ ።

መፍትው ንሴሰይ ሥጋ አግዓዚ ጠበብተ አፍአ ወውሥጥ።
አኮኑ ይትረከብ ዘእንበለ ንዑስ ሤጥ ።
ሥጋ አግዓዚሰ ይትርፍ ደቂቀ አዳም ወሎጥ ።
አጥረዩ ርግበ በበዕልፍ ሀየንተ ረኃበ ሥሉጥ ።

ዕጣነ ሞገር ።

በዘመነ ልደት ዓቢይ ከዊኖተ እግዚአ ለመደ ።
ደቂቀ አዳም ቅድመ ዘተዋረደ ።
ማይ ወመዓር አምጣነ ኮነ አሐደ ።
ወይሴሰይ ዘፈቀደ ።
ወእምነ ፃማ አዕረፈ እግዓዚ ለእመ ፈነወ እደ ።
አድባራት አኮኑ ኮንዋ አዝማደ ።
ኢትዮጵያ ትትፌሣሕ ወትትኃሠይ በኃይለ ሥላሴ ገሀደ።
ለአምጽኦ ዮሐንስ አብ ፈረሱ እስመ አድማሰ ፆደ ።
ወአመ ጸጸሳተ አፈድፈደ ።
በኢትዮጵያ ዓቀመ ዘዓሚን ዓምደ ።
ወንግሥት ረሰየቶ ወልደ ።
ደብተራ ወልደ ኪዳን ዘሐረር መድኃኔ ዓለም ።

ስለ በትረ ያርክ ዮሐንስ መታሰብያ

መወድስ

ዕበነ ኑፋቄ ጽኑዐ አዕቃጼ ሰኰና ፤ ኃይለ ሥላሴ አዕተተ
ኢይትዓቀፉ አዕጋሪሁ ።
በፍኖተ ሰላም ብርሃን፤ እስመ ያንሰሱ ለሊሁ ።
ወሰማዕተ ብርሃን ዮሐንስ፤ዘዓዲመ ቅናት ቀነተ ሐቌሁ።
ከመ ያስተራትዕ ፍናዊሁ ።
እንዘ ይሰብክ ጥምቀተ፤ ተፈነወ በቅድሜሁ ።
ኢንኀዝንሂ ለእመ ረስዓ ወለእመ በልየ ናሁ ።
ለዮሐንስ አንተ ንበር ሃማኖተ ቄርሎስ ሰብእናሁ።
በኃይለ ሥላሴ እሳት፤ እንተ ይነድድ ቅድሜሁ ።
እምጣነ ይትሔደስ ከመ ቀዲሙ ሃማኖተ ቄርሎስውርዛዌሁ

ዳግመኛ መወድስ ።

ባሕረ ሃይማኖት ኢይትርፍ እምከመ ተከፍለ ፤ በበትረ
ያርክ ነቢይ ክብረ በተዋህዶ ።
እምከመ ይሠጠም ፈርዖን፤ ግብረ ተካህዶ ።
ኃይለ ሥላሴ እስመ ጸውዐ
እምግብዕ ሃይማኖተ አበው ዘያፈቅር ወልዶ ።
ወእምጽአ ተከይዶ ።
ዓፅመ አቡሁ አሚነ፤ እምሀገረ ግብፅ ምድረ ተሰዶ ።
ተጠምቀሂ በዮሐንስ፤ ውስተ ባሕረ ጥበብ ወሪዶ ።
እመንፈስ ቅዱስ እአምሮ ዳግመ ለተወልዶ ።
ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ አንተ ገዳመ ጾም ወሰዶ።
ክንፈ ኤሮፕላን መንፈስ ቅዱስ ዘበ እምሳለ ርግብ የዓው
አለቃ ዳንኤል እንግዳ ደስታ።

ስለ ጥምቀት በዓል አከባበር ።

ጥር ፲ ቀን በአዲስ አበባ ውሥጥና በአዲስ አበባ ዙሯያ ያሉ አድባራት እንደልማዱ በየአውራጃቸው ወደላው ወንዝ ወርደው አደሩ ።

በዚሁ ቀን በ፲ ሰዓት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ወደ ጥምቀተ ባሕር የሚወርዱ ታቦታትን ለመሸኘት ከቤተ መንግሥቱ በማረ ዓጀብ ወጡና ሠራዊቱ ሁሉ በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሠልፎ በፊት በፊት ሰይፍ ጃግሬዎች ቀጥሎም ቀሳውስትና ዲያ–

ቆናት ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው ታቦታት ይዘውን በመካከል፥ ቀጥሎም አቡኖቹ ያማረ ያማረ በቅሎ ተቀምጠው ይሔዱ ነበር።ከዚህ ቀጥሎ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባማረች በቅሎ ተቀምጠው ከፍ ብለው ይታዩ ነበር ። ቀጥሎም ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንቶች ካባ ካባቸውን ለብሰው በየመዓርጋቸው ሰልፋቸውን እያሳመሩ ይከተሉ ነበር ። ዓጀቡ እንዳማረ እጃን ሜዳ መከከል ደረሰና በጃንሜዳ ተሰልፎ የቈየው ሠራዊት የተገባ ሰላምታውን ሰጠ ። ታቦታቱ በጃንሜዳ ዓረፉና የየአድባራቱ ካህናት ወረብ ወርበው ያስረግጡ ጀመር ወረቡም ከተጨረሰ በኋላ አሳረጉ ። በዚያን ጊዜ ወታደሩ በየረድፉ ተሰልፎ ከብ ዙሪያ አድርጎ ቀጥ ብሎ ቈሞ ነበርና እየቈዩ ሙዚቀኞች ወታደሮች ደስ ደስ የሚያሰኝ ዜማ ያዜሙ ነበር። ከዚህ በኋላ ታቦታቱ ወደ ወንዙ ለመውረድ ተንዙና ግርማዊ ንጉሥ ሸኝተው ተመለሱ።ብዙ መኳንንቶችም ታቦታቱን ዓጅበው እስከወንዙ ወረዱ ።

ጥር ፲፩ ቀን ጥዋት ግርማዊ ንጉሥ ባማረ ዓጀብ ሁነው ወደ ጥምቀተ ባሕር ወረዱ ። በዚያን ጊዜ በወንዙና ከወንዙ ግራና ቀኝ ያለው ቦታ ሁሉ ከሰው ብዛት የተነሣ ተጨናንቆ ነበር ።

የጥምቀቱን ሥርዓት ከደረሱ በኋላ ግርማዊ ንጉሥ ወደ ሜዳው ወጥተው ተቀመጡ ጳጳሳቱና መኳንንቱም እንደማዕርጋቸው በግራና በቀኝ ሁነው ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ ታቦታቱ ከድንኳን ወጥተው በተራ ቆሙ ፡ ካህናቱና ሊቃውንቱም የማዓርግ ልብሳቸውን እየለበሱ በሥርዓት ቆሙና ሃሌ ሃሌ ሃሌሉያ ተጠምቀ ሰማያዊ በእደመሬታዊ እያሉ ሲወርቡ አምረው ታዩ።

ከዚህ በኋላ ነጋሪት እየተጐሸመ መለከትና እምቢልታ ጡሩምባም እያቀራራ ወደ ጃን ሜዳ ጕዞ ተጀመረ። በፊትና በኋላ በቀኝና በግራ የተሰለፈው ሠራዊት የሰልፉ ማማር ልዩ ሁኖ ይታይ ነበር ። በያለበት እንደ ውሀ ሙላት ይጐርፍ የነበረው ሕዝብም የብዛቱ ነገር ያስደንቃል ። ሰልፉ እንደ አማረ ጃንሜዳ በደረሰ ጊዜም ሰልፈኛ ወታደር በግራና በቀኝ እንዳጥር ሁኖ ተሰልፎ በፊት ታቦታቱና ካህናቱ ሊቃውንቱም ቀጥሎ አቡኖቹ ፡ ከነሱ በኋላም ግርማዊ ንጉሥ ከክቡራን መኳንንት ጋራ በመከከል ሁነው ሲሔዱ ማየቱ የሚያስጐመጅ ነበር ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በሜዳው መከከል አምሮ በተሰናዳላቸው ዙፋን ላይ በተቀመጡ ጊዜ በግራና በቀኝ ጳጳሳቱና መኳንቶቹ ። ተቀመጡ ። በዚያን ጊዜ ካህናቱና ሊቃውንቱ «ወወፂአ እማይ ፡ ተርኅወ ሰማይ ፡ መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ፤ ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር እያሉ ወረቡን ከሰመሩ በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ስለ ሥርዓተ ጥምቀት ተርከው ጥቅሙን አስረድተው ባርከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት። ከዚህ በኋላ ሰልፉ እንዳማረ ታቦታቱን ዓጀበ ይጓዝ ጀመረ ፡ ታቦታቱ እየተለዩ ወደየስፍራቸው ሲሔዱም የየአጥቢያው መኳንንትና ሠራዊት እያጀበ ወደየቤተ ክርስቲያናቸው ገቡ ። ታቦታቱ ወደየቤተ ክርስቲያኑ ከደረሱ በኋላም ግርማዊ ንጉሥ ባማረ ዓጀብ ወደቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ስለ ቃና ዘገሊላ በዓል አከባበር

ጥር፲፪፡ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከናቱ ከመቤታችንና ከደቀመዛሙርቱ ከአባቶቻችን ጋራ ወደ ሠርግ ቤት ተጠርቶ በሔደ ጊዜ የሚጠጣው ወይን ቢያልቅባቸው ውሀውን መልክም የወይን ጠጅ ስላደረገላቸው ሐዋርያው ይህን ተአምራት የጌታችን የተአምራቱ መጀመሪያ ብሎታል ዮሐ ምዕ፪፡ቍ፲፩። ይህም ቀን ስለጌታችን ከሚከበሩት በዓላት አንዱ ስለ ሆነ ክርስቲያን ሁሉ ያከብረዋል ። ይልቁንም በኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን ብርሃን የተባለው ቅዱስ ያሬድ በዚሁ በዓል የሚነገር ብዙ የምስጋና ቃል በየዓይነቱ ስለተናገረ የኢትዮጵያ ጳጳሳትና ነገሥታት ሊቃውንትና ካህናት ሕዝብና መኳንንት ሁሉ በመልካከም ልዩ ልዩ ዓይነት መሣርያና አልባሳት አጊጠውና ልዩ ልዩ ምስጋናቸውን አከናውነው በፍጹም ደስታ የሚያከብሩት ስለ ሆነ የየካ ሚካኤል ታቦት በውራጃው በኵል ወዳለው የቀበና ወንዝ ለጥምቀት እንደ ወረደ ደግሞ ከዚያው ያድራልና በዚሁ ቀን ግለዳ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በማለፊያ ሰጋር በቅሎ ተቀምጠው ታቦቱ ወዳለበት ስፍራ በተጓዙ ጊዜ ከሚከተሉዋቸው መሳፍንትና መኳንንት ሕዝብና ሠራዊት ብዛት የተነሣ ምንገዱ ለመተላለፍ እጅግ ጭንቅ ነበር። ደግሞም የኢትዮጵያ ጳጳሳትና በአዲስ አበባና በአውራጃዋ ያሉት ሊቃውንትና ካህናት ሁሉ ተሰብስበው ነበረና ታቦቱን አጅበው ጕዞ ተጀመረ ። ከቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ ሲደርሱ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አምሮ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተቀመጡ። ጳጳሳቱም በታቦቱ አጓያ በወምበር በወምበር ተቀምጠው ነበር።መሳፍንቱና ታላላቁ መኳንንቶችም ብዙም የውጭ አገር ሰዎች ዙርያውን ከበው ተቀምጠው ነበር። በዚያን ጊዜም ካህናቱ እየወረቡ ሲያስረግጡ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ፡ ሽብሸባውም ካለቀ በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ዮሐ ፪ ስለ ቃና ዘገሊላ የሚነገረውን ቃል አከናውነው ተርጉመው ለሕዝቡ አስረዱ። ይልቁንም ወዝንቱ ቀዳሚ ተአምር ዘገብረ እግዚእነ ያለውን ከጊዜው ጋራ እያስማሙ አሁን በኢትዮጵያ ጳጳሳት ስለ መሾም ደስ እንደሚያሰኝ አድርገው በሦስት በአራት አወራረድ እየተረጐሙ ደግሞም ቅዱስ ዳዊት ወበሀየ አበቍል ቀርነ ለዳዊት ወአለብሰሙ ኀፍረተ ለጸላእቱ ወበቱ ይፈሪ ቅድሳትየ ያለው ስለ ዘሩባቤልና ከእርሱም ቀጥሎ ለተነሡ ስለ ንጉሥ ተፈሪም እንደ ተነገረ ሲያገናዝቡት የቃላቸው ልዝብነትና የአንደበታቸው መርታት አጥንት የሚያለመልም ይመስል ነበር ። ሁለተኛም ኰንን በጽድቅ ነዳያነ ሕዝበከ ወአድኅኖሙ ለደቂቀ ምስኪናኒከ ያለውን ተርጉመው የሰሎሞንን ጥበብ ከስረዱ በኋላ በሰሎሞን ዘመንከ ላይ እግዚአብሔርን ከታች ንጉሥ ፈርተው መኳንንቱ የሐሰት ፍርድ አይፈርዱም ነበር፥ አሁንም ዛሬ የኢትዮጵያ መናብርትና መኳንንት ከላይ እግዚአብሔርን ከታች ንጉሥን ፈርተው ፍርድ ጐደለ ድኻ ተበደለ የሚሉ ያድርግልን ብለው ከብዙ ምረቃት ጋራ አሳረጉና ባርከው ሕዝቡን አሰናበቱ ። ከዚህ በኋላ ታቦቱ ገባና ሁሉም ወደ ቤቱ ተመለሰ ።

የመናናቅ ፍሬ ።

መናናቅ የሚመነጭበት ከድንቍርና፡አእምሮ ከመጥበብ ፥ አስፍቶ ካለመመልከት ፡ እንዲሁም ከመሰለም ከጨለማ ወንዝ ነው ።

ነገር ግን ሰው በግልብጥ ሲመለከተው ይኖራል። የሚንቅ ራሱና ሲንቅ የሚያዩውት ሰዎችም ከንቀፊና ከናቀ የሚበልጥና የተሻለ ቢሆን ነው በሚል አሳብ ይታሠራሉ።ስለዚህም ሰው ሁሉ ከክፉ ባሕሪውና ከድንቍርናው እያፈለቀ ያ በዚያ ተቀምጦ ይህን ሲነቅፍ ይህም በዚህ ተቀምጦ ያን ሲነቅፍ ይኖራሉ ። ሰው ሁሉም በዚህ ነገር እርስ በራሱ ሲባላ ፡ ሲንቃቀፍ ፤ ሲናናቅ ጊዜውን ያሳልፋል ። ምክንያቱን ግን እንደግመዋለን ። የጨለማ ኃይል፤ የአእምሮ መጥበብ ፡ አስፍቶ ያለማየት ነው ። ከዚህ ነገር የተነሣ ከሌላ ይልቅ በገራችን ውሥጥ እጅግ አድርጎ ሊጎዳ የሚችል መናናቅና መነቃቀፍ በጣም ተነሥተዋል ።

አሁን ለጊዜው ዋና ጕዳት ሁነው ያሉ፤ለወደፊቱም ሰው በእውነተኛ መረዳት እስኪረዳቸው ድረስ የሚያስፈሩ ነገራት ግን ሁለት ናቸው ።

እነዚህ ሁለቱም ማስተዋልና ቮጣንነት ናቸው ። አነቃቀፋቸውና አናናቃቸው ግን እንደምን መሆኑ ከእየአንዳንዱ የኢትዮጵያ ልጅ የተሠወረ ነገር አይደለም። የእግዚአብሔርን ፍጥረት ከራሳችን ጀምረን እስከ መሬት ድረስ ብንመለከት ሊቈጠር የማይቻል በየይነቱ የሆነ ተፈጥሮ ሁኖ እናገኘዋለን። ነገር ግን ተፈጥሮ ለየብቻው ይሁን እንጂ ወይ ለመርዳት ወይ ለቀጣት የማይሆን እንደ ስጦታውም ሥራውን የማይፈጽም ፍጡር የለም ።

ጀግኖች በአእምሮዋቸውና በዕውቀታቸው የሚታመኑትንና የሚያገለግሉትን ሰዎች ሲንቁዋቸውና ሲያቃልሏቸው ሳሉ ጭራሽ ለከንቱ እንደ ተፈጠሩ እነሱ ባንዲት ደቂቃ የሚሠሩዋትን ሞያ በምሉ ዕድሜያቸው ሊያደርጉዋት እንደማይችሉ አድርገው ይገምቱዋቸዋል።ባሳባቸውና በቃላቸውም ይህን ይወስናሉ ብልሆች አዋቂዎች ሰዎችም በጅግንነታቸው የሚታመኑትንና የሚያገለግሉትን ሰዎች ሲንቁዋቸውና ሲያቃልሉዋቸው ሳሉ ፍጽም ለከንቱ እንደ ተፈጠሩ እነሱ ባንዲት ደቂቃ የሚሠሩዋትም እነዚያም በምሉ ዕድሜያቸው ሊያደርጉዋት እንደማይችሉ አድርገው ይገምቱዋቸዋል።ባሳባቸውና በቃላቸው ይህን ይወስናሉ። በዚህ ምክንያትም ሰው ሁሉ ከነገዘ አከላቱ ጋራ ሲዋጋ ይኖራል ። ነገር ግን እነዚህን ሁለት ለየብቻው የሆነ ስጦታ ያላቸው ሰዎች በፍቅርና በመከባበር በመመሰጋገንም ሊኖሩ ለዚያ የሚያስፈልግ ነገር ሲመጣ ያለዚህ ለዚህም የሚያስፈልግ ነገር ሲመጣ ይህ ለዚያ ሁነው በየስፍራቸው እየተገኙ ለሕዝባቸው ደኅንነት ላገራቸው ልማት የሚሆንን ሥራ ሊፈጽሙ እንጂ ሊናናቁ አይገባቸውም ነበር።

ሰው ሰውን መናቁ የሌላውንም ስጦታ ማቃለሉ ምክንያቱ ፊት እንዳልነው ለጥፋት ራሱን የቻለ ጨለማና ድንቍርና ነው ። ደግሞ ባንድ መንገድ ብናይ ሰው እየርያው ባጠገቡ ያለውን ነገር እንጂ ከርሱ ራቅ ያለውን ነገር ለይቶ ለማየት እንደማይቻል እንደዚሁም ቢያይ እንኳ ያችን ከሰውነቱ ያለችውን ስጦታ እንጂ በሌላ ያለውንስ ለማየት በጣም ችግር ነው ። ቢያይም ሰው ራሱን ከጣዖት አብልጦ ስለሚያመልክት የሌሎችን ጕድለትንና የራሱን ሙላት ብቻ ነው የሚያይ። ነገር ግን ከመናናቅ እንድንድን በገዛ ሰውነታችን ያለውን አካላት እንመልከት በዚያም ሥራቸውን ማንም ሊመረምረው የማይችል ጕልሆችና የማይመረመሩ ደቂቃን አካላት ከሕያው አምላክ የተሰጣቸውን ሥራ ሳይነቃቀፉ ሲፈጽሙ እናገኛቸዋለን። ከነሱ አንድ ቢጐድልም ለሁሉ ወይ ለሞት ወይ ለጕዳት ይሆናል ። ዓይን ሥራው ትልቅ ነው ። ነገር ግን የሚመጣበትን አይቶ ለሌሎች ባለ ሥራዎች ያመለክታል እንጂ የማትታየውን ትቢያን እንኳ ሊያግድ አይችልም ። ጆሮ የሚሆነውን ይሰማል ። ነገር ግን አእምሮ ነገሩን ያስረክባል እንጂ እርሱ ራሱ ከዚያ አልፎ አንዳች ነገር አይሠራም። አእምሮም ኃይል ቢያስፈልግ ለኃያላን፥ ጽፈት ቢያስፈልግ ለጸሐፊዎች እየሥራው ይከፍለዋል እንጂ ከማሰብ አልፎ አንዳች ነገር አይሠራም ። እነዚህ ልንቈጥራቸው የማንችላቸው ሰውነታችን ግን እንድነታቸው የፀና እያንዳንደ ሥራውን ሊፈጽም ከልሆነም አንዱ አንዱን ሊነቅፍ የማይገኙ ስለሆኑ ሥራቸው እየብቻው ሁኖ ባንድ ደቂቃ ጕዳያቸውን ሊፈጽሙ ይችላሉ ። ነገር ግን እግር አይንን ሚዳውንና ዳገቱን አይተሽ እንደምን ዝም ትያለሽ እንቺ ካልተራመድሽ እኔ መሔዴን አልቃጣውም ቢል፤ እጅም እንደዚሁ አሳብን አንተ ይህ ነገር ሊሆን ከወሰንህ እንግዲያስ ባለቤትህ ሥራ ቢል፤ ጆሮና ዓይንም አለኛ ሩቅ የሚመለከትና ከሩቅ ድምፅ የሚያመጣ ማነው ብለው ኵርተው ሥራቸውን እስከ መፍታት ቢንቀባረሩ።አእምሮም ጭራሽ እኔ በማስተዳደሬ ሆድን አዝዤ ካልመገብኋችሁ ምን ኃይል አላችሁ ቢል ። ይህንና እንደዚህ የመሰሉትን ልንቈጥራቸው የማንችል ነገራት አሉ ። ግን አንዱ አንዱን አይናቀውም ሁሉ ይራራሉ ይከባበራሉ።ይጠባበቃሉ ሥራውን የሚፈታም የለም። እንደዚህስ ባይሆኑ ሲፈካከሩ በበረኻ በመሸባቸውና ለአውሬ መጫወቻ ይሆኑ ነበር ። መሬት እንኳ አንድ ስትሆን እንደ ተፈጥሮ ስጦታዋ ሊቈጠር የማይቻል በየይነቱ የሆነ ፍሬያትና ሌላም በረከት ትሰጣለች እንጂ በአንድ ፍሬ ብቻ ሥራዋን አትፈጽምም ።

እንግዲያስ በሕሪው እንደኔ በሕርይ ስጦታው እንደ ስጦታ ካልሆነ አይረባም ማለት ድንቍርና ነው ። የተለያየ ባሕርይ ባይኖር የተለያየውን ነገራት ለመሥራት በየይነቱ ከሆን ከጠላት ጋራም ለመቃወም አይቻልም ነበር ። በተሰጠው ስጦታ እንደ ባሕሪው ለመልከምነገር የሚተጋና የሚጣጣር ከሆነ በማንም ይጐድላል ሊባል አይቻልም።ለማናቸው ሰዓት ለማናቸው ሥራ የማይሆኑ ሳይሠለጥኑ የሠለጠኑ አንዳች ሳይኖራቸው ባለአእምሮ ለቁም ነገር ሊሆኑ የሚችሉ የሚመስላቸው፤ነገር ግን ከጀግኖች ስፍራ የተወሰኑ ከአእምሮና ከማስተዋል ጫፍ በጣም የራቁ ፍሬያቸው የበነነ ገለባ የሆኑ ሰው ሁሉ ሊንቃቸውና ሊጸየፉቸው ልጆ እግሮች መንገዳቸውን እንዳይከተሉ መከልከል የሚገባ አሉ ።እነሱ ሥልጣኔያቸው የሽቱና የመጠጥ ስም ማወቅና ባረቄና በክፉ መጠጥ የሰውን በረከት ሊመጡ

ለመጡት ሰዎች ምርኩዝ ናቸው ። ደማቸውንና ግርማቸውን በብራቸው በተገዛ በመጠጥ ዋገምት ለመምጠጥ በየመጠጥ ቤት ጠረጴዛ ሲታገሙ የሚውሉ ሕሊናቸው ሳይነካ ነገሩንም ሳይነኩት እግዚአብሔርን መክድና ሰውን ማምረር ሥልጣኔ መስሎዋቸው የሚለቀቁ ለከንቱ ንግግር የሚጎናፉሉ መጨረሻው ሥልጣኔ ዘፈንና በያይነቱ የሆነ ቅሌት መስሎ የሚሰማቸው ለራሳቸው ለቤታቸው ለሕዝባቸውና ለመንግሥታቸው ለውርደትና ለጎዘን እንጂ ለማንም የማይረቡ ናቸው ።የቀረው ሁሉ ግን ሊከበበር ሊመሰጋገን ሊረዳዳ እርስ በራሱ ሰላምንና አንድነትን ሊመሠርት ከኔ ጎለ ሰጦታኮ በእገሌ ያለ ሰጦታ ይበልጣል ቢል እንጂ የራሱን ሞያ ብቻ እንዳይመለከት ያስፈልጋል ፤ ስጦታ ልዩ ነው ። መንፈስ ግን አንድ ነው ። ተወ መድኅን ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት መከፈት።

በልደትና በጥምቀት በዓላት ምክንያት ትምህርት ቤቱ ተዘግቶ ነበርና አሁን ጥር ፲፱ ቀን በ፪ሰዓት መከፈቱን እናስታውቃለን ።

ወደ ትምህርት ቤቱ ሊገቡ የሚፈልጉ አዲስ ልጆች እትምህርት ቤት መጻፊያ ቤት እየመጡ የመከፈቱ ጊዜ ሳይደርስ አስቀድመው ሊያስታውቁ ይችላሉ ።

በኢትዮጵያ አገር ዕውቀትና ትምህርት እንዲሰፋና እንዲሠለጥን ፈቃዳቸው የሆነ ደጋግ ሰዎች ለድኆች ተማሪዎች የሚሆን እርዳታ ገንዘብ ሰብስበዋልና ፤ የትምህርት ፍናቶት ያላቸው ድኆች ልጆችም ቢሆን መጥተው መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን ከዚህ በላይ ያልናቸው ድኆች ልጆች የዕውቀታቸውና የስጦታቸው ልክ እንዲታወቅ ፈተና ይደረግላቸዋል።

Lycée Tafari Makonnen.

Les cours du 2e trimestre commenceront lundi 27 courant à 8 heures.

Les enfants et les jeunes gens désireux d'entrer au Lycée devront se présenter à la Direction le plus tôt possible. D'autre part des bourses fondées par des personnes généreuses s'interessant à l'avenir intellectuel de l'Ethiopie sont à la disposition des candidats qui subiront, pour leur obtention, un examen de classement.

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጪ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመቃ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፭
6me ANNÉE № 5

ሐሙስ ጥር ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 30 JANVIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ይጻፉ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፭ኛ ዓመት የ፩፻፲፰ ገጽ ተከታይ።

የኢኮኖሚያ ፖለቲክ።

፭ኛ ፤ የሚያንሱና የሚያድጉ ወረታዎች በሁለት ፋቶሪ ሥራና ካፒታል ከመረመርነው ወደ ሦስተኛይቱ ፋቶሪ (ነገር) መሬት እናልፋለን ። መሬት ከሌሎች ቤጼ (ጥሪት) ልዩ ዓይነት እንደሆነች ታሳያለች ። እስዋ ለሰው የፍለጋው ዋና መሠረትና ለዘለዓለም ነዋሪ ነች ። እንደ ሸንሲያቲ (አዋቂዎች) እና ባለ ሃይማኖቶች ባህል ዘለዓለማዊት ሁና ባትኖርም እስዋ እስካለች ድረስ የሰው ዘር ይቈያል እንደማለት ነው ። ስፋትዋና ብዛትዋ የተወሰነች ነች ። ይህነን ጠባይዋ ብዙ የሚረባ ጥቅም አለው። ይልቅም ለባለመሬቶች የምትሰጠው ፕሮፊቶ የሚባል ልዩ ጥቅም ብቻ አይዶለም ፥ ለሕዝብ ሁሉ በምትሰጠው ምግብና ማተሪዬ ፕሪሚ (የፍጥረት ካብት) ለኢንዱስትሪ በምትሰጠው ነው እንጂ ። ሥልጣኔ ሲሰፋ መሬት በብዙ ችሎትና መከናወን እየለማች እንደምትሔድ ጥርጥር የለበትም ። ማለት ፍግ በመነስነስ የሚሸራርፉትን የወሀ ጐርፍ በማገድ መስኖን በማግባት እርጥብ መሬትን በመኪና እየመጠጡ በማድረቅ ፥ የምታርስ የምታጭድ የምትወቃ መኪና በማበጀት እየለዋወጡ በመዝራትና በማሰረፍ እርሱን በመሰለ ሁሉ መሬት ለልማትዋ ልትሻሻል ትችላለች ። በዚሁ አካሔድ ሥራና ካፒታል ይገዝዋታል ። ግን በፊት እንዳመለከትነው የእርሻን ወረታ ፍሬውን እያነሰ የሚሔድ የሚባል ሕግ ባሕሉን እንዳቆመ በአንድ መሬት (ቀላድ) ሥራና ካፒታል ከልኩ አሳልፈህ ብታሳድግ ፍሬውን ፕሮፖርሲዮን ልክ ሁኖ አያድግም ። ፍሬ የሰወስቱን ፋቶሪ (ነገሮች) መሬት ሥራ ካፒታል ነውና የሚገዛ ፤ እስከሚችል ድረስ የበለጠ ፍሬ ለማግኘት ሦስቱን ፋቶሪ ፕሮፓርሲዮን (ልክ) ሁነው በስምም ሊቆሙ ያስፈልጋል ። ብዙ ሥራና ብዙ ካፒታል ብቻ አይበቃም ፥ ብዙ ሰፊ መሬትም ያስፈልጋል እንጂ ። ይህ ሕግ ባይኖር አንድ ቀላድ ላንድ አገር በበቃ ነበር ፥ ግን ምንም ቢያደርግ አይሆንም።

፮ኛ፤ የመሬትን ዋነኛ ሰው ትርፍና ገቢ እንደኛይቱ የፍሬ ክፍል እንደ አገር ልምድና ወግ ፥ ለባለ መሬት ትሰጣለች ማለት ባለ ቀላድ (ርስት) ባለ ሚኔራል (መአድን ባለ ወንዝ ጐድጓዳ ቦታ የተሠራ ቤት ዋና በመሆኑ ብቻ ፥ ተፈራውን ፍሬ ሳይሠራ ቊጭ ብሎ ቢሆንም የሚያገኘውን ገቢ ሬንዲታ ይባላል። ስለ ሆነ ግን ዋነኛ ሬንዲታው ለቤትና ፋብሪካ ማሠሪያ ለሚኔራል ማውጫ ለመሬት ማልሚያ በሆነ ካፒታል ወለድ ቁመዋል ። ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል አሠሪ ሰው በክራይ ስም ወይም የእርሻ ፍሬ ዋጋ ለባለ መሬቱ ሬንዲታ ይሰጠዋል ።

፯ኛ፤ ሬንዲታ እንደምን እንደምትበቅል ምክንያቱ ማወቅ በጣም የሚያስፈልግ ነው ። አለዚያ የመሬትን ዋነኛ ከተፈራ አንድ ክፍል ሳይሠራ ማግኘቱ ስለምን እንደሆነ ለማወቅ አንደርስም ። አንድ ዓይነት ለሆኑ የእርሻ ፍሬ የመስማማታቸው ዋጋ አንድ ነው ። የመሬቱ ዋነኛ ሰው ለማፍራት ካዋለው የካፒታሉ ወለድ በላይ ከሬንዲታ የተባለ ገቢ ሬንዲታ የተባለ ትርፍ ፍሬ ያገኛል ። ግን መሬቶቹ (ቀላዶቹ) ሁሉ ፍርያምነታቸው አንድ አይደለምና ፥ የሚጨርሱትን ካፒታልና ሥራ ልክ ቢሆንም የሚሰጡትም የፍርያቸው ብዛት ልክ አይደለም። በፊት እንዳመለከትነው ምክንያቱ መሬቱ ወፍራም በመሆኑ ፥ በፍርያምነቱ መስኖ በማበጀቱ የሚበቃ ፀሐይና ዝናም በማግኘቱ፥ በገባያ ቅርብ በመሆኑ ሕዝቡ ከመገዛቱ የተነሳ መሬቱ ብዙ ልዩ ልዩ ሊሆን ይችላል ብለናል ። አለዚያ መሬቱ በሞላች ሥራና ካፒታል (ገንዘብ) ልክ አጥፍቶ የምትሰጠው ፍሬ ብዛቱ ልክ በሆነ ሬንዲታ የሚባል ትርፍ ልይነት ባል-

ኖረውም ። ግን አይደለም። በአንድ አንድ ስፍራ መሬቲቱ ሜዳዋን ከረፍታዋ ለምለም ፍርያም ትሆናለች ፤ በአንድ አንድ ስፍራዋ ደግሞ ሜዳዋ በአሸዋ የተሸፈነ ፤ ወይም ጭንጫ የመላበት የረቀቀች ደረቅ መሰይ፥ወይም የሚበቃ ፀሐይና ዝናም የሌለበት፥ ወይም አምቦችዋ በበረዶ የተሸፈኑ ይሆናልና ፥ የምትሰጠው ፍሬ እጅግ ያነሰ ይሆናል ። ማክሉክህ የሚባል ሰው እንዲህ ሲል በአራት ክፍል ይወስነዋል ።

ሀ) የአንድ መሬት ፍሬ ለማፍራቱ የጠፋ ገንዘብናሥራ ልክ ፕሮፓርሲዮን ቢሆን ሬንዲታ ባልነበረም።

ለ) የአንድ መሬት ፍሬ ለወጭው ገንዘብ ልክ ፕሮፓርሲዮን ሁኖ ሊያድግ አይችልም ግን ግልብጥ ነገር ፕሮፓርሲዮኑን መጨረሻ እስከሌለው በማነሱ ፋንታ እያደገ ይሔዳል።

መ) ወጭ ገንዘብ በትንሽ የምታፈራ መጨረሻይቱ ክፍል፥ የካፒታልን ኢንተሬሲ የምትሰጥ ነች።

ሠ) ሌሎቹ የበለጠ የሚያፈሩ ክፍሎች ወለዳቸው ከልክ አልፎ ሬንዲታ የተባለችን ትርፍ ያቆማሉ ። ዲያክ ግራማው ቀጥሎ እንዳለ ፫ኛ ሥዕል ተሰጥቶ ይቆማል ።

የሀብት ዕውቀት።



፫ኛ ስእል።

የመስመሪቱ (ቀ) (ዘ) የመሬቲቱ ርዝመትና ለማፍራት የዋሉ የሚያድጉ ካፒታልና ሥራ እናስበዋለን ። የትርፍን እየጐደለ መሔድ በ(ሀ)በ (መ)የተያዘች ጐባጣ መስመር እናመለከታለን ፥ ማለት የጐባጣይቱን ስፋት የፍሬን ልክነት ታሳያለች ። ስፔዜን (በ (ቀ) ሰ)ሲደርስ የተፈራው ፍሬ በ ቀ ሀ በ ሠ የተያዘ ስፋት ይሆናል ።ስለዚህ አፍሪ ገበሬ የተገባ የሚበቃ ውለታውን አንዱ ክፍል በ (በ)መ)የተያዘ መስመር ፍሬ ካገኘ ፤ ከፊተኞቹ ክፍሎች የበለጠ መጨመር ሊፈልግ አይገባውም ። አንዲት ቀጥ ያለች መስመርም በ ነ (በ)ተ) የተያዘች እንጨምራለን ። ለስፔዛ የዋሉትን ሁሉ ውለታቸው በ (ቀ ነ በ ሠ የተያች ፍሬ ይሆናል ። በ ነ ሀ በ የተያዘች ስፋት ደግሞ የማፍራትን ትርፍ ያመለክታልና ሬንዳታን የተባለ ትርፍ ይሠራል ። ይህንን ምሳሌ ያቀረብነው ስእል በሁለተኛ መሬት ርስት) ወይም ቀላድ)ብንደግመው በ) ቀ) ለ) (ረ) የተያዘ ፍሬ እናገኛለን ። ከዚሁ በ (ነ) (ለ) የተያዘች ክፍል ሬንዲታን የምትባል ትርፍ ታመለክታለች ። ስለዚህ ሬንዲታን ከመሬት ዋነኛ እንዳልሆነች የምትገዛ ለማወቁ የቀለለ ይሆናል ። እስዋ ለሕዝብ ሁሉ ደግ ትሠራለች የሕዝብን እየበዛ መሄድ ፥ የመሬቱን ማልማት የእርሻን መሠልጠን ማለት ፍሬውን ማደግ ሬንዲታን በጣም ያሳድጋታል። የእርሻን መሠልጠን የወረታውን ውለታ እያነሰ መሔድ ሕግ ነፃ አውጥተው ዜሮ እስካትደርስ ድርስ ያሳሳታል ። ስለዚህ እርሻን በጣም ከሠለጠነች ወዲህ ሬንዲታን በማደግ ፈንታ እያነሰች ፣ ሄዳለች ምክንያቱ ሌላ አይደለም የእርሻን ማፍራት እያደገ በመሄድ ነው እንጂ። መሬትን ለማፍራት የአሠራርዋ አይነቶች አከፋፈል ደግሞ ቀጥለው ያሉ አራት ኋለኞች የተወሰኑ አሳቦች ናቸው።

፬ኛ) በባርነት ጊዜ አኳኋን ይልቁንም በደቡብ በአማሪካ ሀብታም ባለመሬት ባለ ሥራ ነበር ። ጌታው ባርያውም እንደበሬና እንደ አህያ እንደካፒታል ይቈጥረዋልና ፥ ባርያው እውነተኛውን ዋጋ ሊያገኝ ስለማይችል የሚሠራ በብዙ ልግም ነውና ለኤኮኖሚያ ብዙ ጉዳት ይሆነዋል ። ማለት ደጋግመን በፊት እንዳመለከትነው ፥ መሬት ፥ ካፒታል ሥራ ፕሮፓርሲዮን ልክ ካልሆኑ ማፍራትን አትሠለጥንም ። የሆነ ሁኖ በኤኮኖሚያ ባርነት ጥቅም ወይም ጉዳት እንደሆነ ለመናገሩም አያስፈልግም።በሞራሊቲ ትልቅ ጸያፍ እንደሆነ ጭራሹን ተፈርድዋልና ። በባርነት ጊዜ የማፍራትን ፋቶሪ የሚባሉ ነገሮች እንደሚከተለው ዲያግራማ ተሰጥተው ነበር ።

የባርያ ጌታ ።

መሬት ካፒታል ሥራ ።

ከባረነት በኋላ ርዮት የሚባል አይነት ፥ በህንድ በግብጽ በትርክ በፔርስያ አገሮች የሚገኝ ከሁሉ የባሰ ሥራት ነው ። በዚሁ አገሮች ከመሬቱ የሚበልጥ እጅ በመንግሥት እጅ ነውና ሬንዲታና ግብር ሊሰጡት ለገበሬዎች ያከራያቸዋል ።ይልቁንም የእርሻ ፍሬ ያነሰ ሲሆን ጊዜ ገበሬዎቹ የሚከፍሉትን ከማጣት የተነሣ ባለዕዳዎች ይሆናሉና በሚያስደነግጥ ችግር ለመውደቅ ይደርሳሉ ። ስለዚህ የመስከቦች እንኳ ባለ መሬቶችን እየወረሱ (እየነቀሉ) መውሰድ ቀርተዋል ። የሆነ ሁኖ መሬትን የመንግሥት ሲሆን ዲያግራማው እንደዚህ ይቀርባል ።

መንግሥት ።	ገበሬ።
መሬት ።	ካፒታል ሥራ ።

፭ኛ፥ የእኩል እርሻ የሚባል ዓይነት እስከዛሬ ድረስ በጣም የተለመደና የሰፋ ነው።ዋነኛው ሰው መሬትና አንድ ክፍል ካፒታል ገበሬና አንድ ክፍል ሥራ አገጣጥመው እንደ ማኅበርነት ያህልይቆማሉ።ዲያግራማው ቀጥሎ እንዳለው ይሰጣል።

ዋነኛ።	ገበሬ ።
ሜሬት ካፒታል ።	ካፒታል ሥራ ።

ከጌታውና ከገበሬው የፍሬውን ክፍፍል ውል ። ሁሉ ጊዜ እንደስሙ እኩል በእኩል ብቻ አይደለም የሚከፋፈሉት ግን እንደጊዜው ወይም ከአገርና አገር እንደልምዱና ወጉ

የተለያየ ነው እንጂ ። ሁለተኛ ዓይነት ክራይ ደግሞ ፤ ይልቁንም ለም ባልሆነ መሬት ፕሬንዲቶሬ የሚባል አሥራ ፤ እንደሙሉ በዓመት የተወሰነ ገንዘብ እየከፈለ ለረጋርም ጊዜ ወይም ጭርሱን ለሁሉ ጊዜ ይከራያል ።

፯ኛ፣) ከሁሉ የተሻለ የእርሻ ዓይነት ገበሬው የመሬት ሡነኛ ሲሆን ነው ። ስለምን በእጁና በካፒታሉ ስለሆነ የሚሠራው ፤ በብዙ ትጋትና መከናወን መሬቱን እየተከባከበ በብዙው ያፈራል። በዚህ ዓይነት ሦስቱ የማፍራት ነገሮች መሬት፣ ካፒታል፡ሥራ በእጁ ናቸው።ስለዚህ ዲያግራማው እንደዚህ ይሰጣል።

ሚካኤል ተሰማ። በሚመጣው ቍጥር ይቀጥላል ።

ባገራችን ያለ ዋና ጕዳት ።

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ሥር ይዞ የተቀመጠ ክፉ ልምድ አለ ። ይኸውም በጣም የሚጐዳና የተጠላ ሥራ መፍታት የሚባለው ነው ። በዚያ የተነሣ አገራችን ስለ ሥራ ፈትነት እየደኸዩች ትሔዳለች ። እንግዲህ ሥራ ፈቶ ጊዜ በማሳለፍ ምን ጥቅም ይገኝበታል ።

ግን ሥራ በለመሥራት ሁለት ጕዳት አለ ። አንደኛው ዋና ጕዳት ያ ቀን ሥራ ፈቶ የሚውል ሰው በከንቱ ሥራውን ፈትቶ የሚያርስ ሰው እርሻውን ሌላም ሥራ ያለው ያነኑ ሥራውን እንደመፈጸም በዙረትና በቧልት ያላንድ ጥቅም ተቀምጦ ጌዜውን በቀልድና በፌዝ ያጠፋል ። አንዳንድ ከዚያ ሲመለስ ኑሮው ይቸግረውና ማታ ሲርበው የሚበላው በጣ ጊዜ ታገር ለመሰደድና መጥፎ ነገር ለመሥራት ያስባል አገራችን ኢትዮጵያ እንኳን ልጅዋ ተመርሮ መጥፎ ነገር ሊያስብና ሊርበው የማይረበውን ልምድ ሁሉ ከሥሩ እየነቀሉ ዘወትር የሚሻለውን እየያዙ ቢሠሩ ለራስ ተርፎ መልቶ ያለ ጥርጥር ለሌላም አሳልፎ ለሕዝብ የሚቸግረውንና ላገር የሚሆነውን ዕቃና መሳሪ ሊያስመጡበት በተቻለ ነበር።ጌታ ለአዳም ሠርተህ ብላ ብሎ በማይሻር ቃሉ እንዳዘዘው ሰዎቹ ሁሉ እየሠሩ ሌሎችንም ቢያሠሩ አገራችን ያላንዳች ነገር እየተሻሻለች ሕዝብም እየበለጠገ ወደ ፊት ይሄዱ ነበር ግን ራስም ሳይሠሩ ሰውም ሳያሠሩ በከንቱ ቢቀመጡ ወምበዴ እየበዛና አገሩዋም ትደኸያለች እንጂ አትበለጥግም ። ሁለተኛው ሥራ የፈታ ሰው በሥራ ፈንታ ልዩ ልዩ ጭቅጭቅ በማብዛቱ ሹማምንቱን ያስቸግራል። በሌሎች አገር ማናቸውም ሰው ሁሉ ሰውን ሥራ ማስፈታት ያገርን ጥቅም መንሣት መሆኑን ተረድቶት ወደ የሥራውም ሆነ ወይንም መንግሥት በላከው አገር ሔዶ የታዘዘውን ጕዳይ ይፈጽማል ።

ደግሞ በነዚህ አገር ያለውን መጽሐፍና ጋዜጣ ስናነብ እንኳን እንደዚህ ያለ መጥፎ ልምድ መሠረት ይዞ ሊጎድድና በፊት ይሻላል ተብሎ የተያዘው በያመታቱ ይታደሳል ደግሞ ይህን የመሰለ ነገር ሁሉ በፈቃዳቸው ለመተው የሚችሉትን ይቅርና ላገራቸውና ስማቸውን ለማስጠራት ሲሉ ተነፍስ ላይና ከመሬት ወድቀው የሚቀሩት ቍጥራቸው የበዛ ነው ።

እኔም አሁን ሥራ ፈትነት ላገራችን ጥቅም(እረብ)የሌለው ለሕዝብም የሚጐዳና ከበሬታ የሚነሣ ስለሆነ ነው እንጂ መጻፌ ምቀኝነት አድሮብኝ አይደለም ነገር ግን ላገር ሲሉ የሚበጅውንና የሚከፋውን በጋዜጣ ጽፎ ማስታወቅ ይገባል ስለ ማለት ነው።

አበበ በላቸው ።

ሕይወትን ስለመጠበቅ

ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም የሚያሰክር መጠጥ የሰውን ሕይወት የሚያበላሽ ስለሆነ ሰው ሁሉ ከሚያሰክር መጠጥ እንዲጠበቅ ተጽፎ ነበር ። በ፲፱፻፲፯፣ ዓ ምሕረትም አረቂን መጠጣት ሰው ሊጠየፈው ጀመረና በያሌ ድግስ አረቂን ማጠጣት እንደተወ ተጽፎ ነበር ። ግን አሁን አረቂ እየጠጡ የሚሰክሩ ሰዎች በጣም ብዙ ናቸው ። ያላወቀ ሰው ድንገት ጠጥቶ ቢሰክር እጅግ አያስደንቅም ። ግን የሚያሰክር መጠጥ ጠጥቶ አእምሮውን አጥቶ ከእንስሳ ብሶ ተዋርዶ የታየው ሰው ተመልሶ ወደ ጕዳትና ውርደት ያደረሰውን መጠጥ ሲጠጣውና ሲያስጠጣ መገኘቱ እጅግ ይገርማል ።

በዚህ ሰሞን አንድ ሰውዬ ከሥራው ውሎ ማታ ወደ ቤቱ ሲመለስ አያሌ የሰከሩ ሰዎች ገጠሙትና አንዳንዱ ነፋስ እንደነካው መቃ አንድ ጊዜ ወደግራ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ እየተወዛወዙ ሲሔዱ አገኘ። ይልቁንም አንዱ የሚመጣው ከአራዳ ወገን ነበረና መንገዱን ወደ ቀኝ ትቶ ድጥ ወደ አለበት ገደል መሳይ እወጣለሁ ሲል ወድቆ እየተንከባለለ ወደ ቍልቍል ወረደ።አብረውት የነበሩ ሁለት ሰዎችም ከተኛበት ጭቃ አስነሥተው ወደ መንገዱ አገቡትና እየጐተቱ እንሒድ ቢሉት መንገዱን ትቶ በገደሉ ታልሄድሁ በማለቱ በጣም አስጨነቃቸው።ግን አንዱ ባልንጀራው ሁለቱን ትቶዋቸው ከመንገዱ ወደ ቆኝ ባለው ገደል ወረደ። እርሱም ከዚያ አይሻልም ነበረና ነው መሰለኝ። አንዱ ሰውዬ ግን ያነን እጭቃው ላይ ሲንከባለል የነረበውን ሰውዬ በገደሉ ታልሔድኩ ብሎ ስላስቸገረው አለቅም በማለት እንደተናነቁ ትቻቸው አለፍኩ ግን ዘበኛ በሚቆምበት ስፍራ አጠገብ ነበሩና ጕዳት ቢመጣ ዘበኛው ሳይረዳቸው አይቀርም ይመስለኛል ብሎ ተናገረ ።

በስካር ምክንያት የሚጐዳና ጤንነቱን የሚያጣ ሰው እጅግ ብዙ እንደሆነ ማንም አይስተውም።ከስካር በኋላ ሊቈጠር የማይቻል ብዙ ክፉ ነገር ይከተላል ። በስካር ነገር ሰውነት ይጐዳል ደም ይበላሻል ደሙ የተበላሸ ሰው መላ አካላቱ ተበላሸ ማለት ነው ። ድንገት ትንሽ ቍስል በአካሉ ላይ ቢወጣ ሥጋ የሚሆን የሚያቀብለው የደሙ መንገድ ይዞት የሚመጣ የተበላሸ ደም ስለሆነ ትንሹ ቍስል በመሻር ፈንታ እየሰፋ ይሔዳል። ብዙ ሰዎችም በዚህ ምክንያት ቍስሉ መላ ሰውነታቸውን የሚያበላሽ ስለሆነ እጃቸውን ወይም እግራቸውን ወደ መቈረጥ ይደርሳሉ ።

የመጠጥ ጕዳት ገንዘብን ማክሰር ብቻ አይደለም ሰውነትንም ደግሞ አበላሽቶ ክፉ አገዳደል የሚገድል መርዝ ነውና ከሚያሰክር መጠጥ በመራቃችን ሕይወታችንን እንጠብቅ።

ኪ. ባ።

ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት ።

ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ላገራቸው ልጆች እርዳታ እንዲሆን ብለው አንድ መልክም መጽሐፍ ጽፈው ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት ብለው ሰይመው በዳርማዊ ንጉሥ ማተሚያ ቤት እንዲታተምላቸው ገንዘባቸውን ከፍለው እንዲታተም አድርገዋል፤ይህ ላገራቸው ልጆች ጥቅም እንዲሆን የሚያስተምሩት መጽሐፍ እስከ ሁለት ወርድረስ እንዲፈጸም ተስፋ እናደርጋለን።

ከዚህ ቀደም ሥጋዊ ዕውቀትና ትምህርት የሚሰጡ መጻሕፍት በማርኛ እምብዛ የለንም ። ግን መንፈሳውያን መጻሕፍት ለነፍስ ጥቅም የሚሆን ምክር አዝናት እንደሚሰጡ ሁሉ የዓለም ወይም የሥነ ፍጥረት መጻሕፍትም በኑሮዋችን ጥቅም የሆን ከመንፈሳዊ ትምህርት ጋራ የሚስማማ ዕውቀት በመስጠታቸው አእምሮዋችንን የሚያጎለምሱ እውነተኞች ሰዎች ወደ መሆን የሚያደርሱን ናቸውና በጣም ልንወዳቸው ይገባናል ።

አገራችን ኢትዮጵያ ያዩዋት ሰዎች ሁሉ ስለ ለምለምነትዋና የተፈጥሮ ሀብታምነትዋ መስክረውላታል እያደነቁም ጽፈውላታል ። ግን እኛ ሕዝብዋ እንደሚገባ እየሠራን ለራሳችን ከድኅነት ወጥተን ብልጽግናዋ ትርፍ ተገኝቶበት ስምዋን ክፍ ሳናደርግ በመቅረታችን አላመሰገኑንም ። የሚያሰገፈገም ክልዩ ልዩ ምክንያት ጋራ እንደሚገባ ባለመሥራታችንና ጥቂት ጥቂት የእርሻ ትምህርት ባለማግኘታችን ነው ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ቀደም ዋና ማስተዳደሪያው እርሻና ከብት ማርባት ነው ። ይህ ኑሮ የሚያስፈልገው ትምህርትና ዕውቀት ከተገኘበት የበለጠ የተድላ ኑሮ እንደሚሆን ጥርጥር የለበትም ። ከተማሩና ዕውቀት ከገኙ በኋላ የሚሠራ ሥራ ሁሉ የተከናወነና ደስ የሚያሰኝ በመሆኑ ድካሙም ስለ ዕረፍት ይቈጠራል ።

ስለዚህ የአገራችን ሕዝብ እንደዚህ አሁን የሚታተመውን መጽሐፍ የመሳሰሉ መጻሕፍት ሲታተሙለት በቶሎ እየገዛ ማንበብ ያስፈልገዋል ። ዕውቀትን ያህል ገንዘብ ገዝቶ ማግኘት መታደል ነው ።

ልዩ ልዩ ዓይነት ዕውቀት ተምረው የመጡ ያገራችን ልጆችም እንደዚህ የመሳሰሉ የዕውቀትን መጻሕፍት ላገራቸው ልጆች እየጻፉ እንዲያበረክቱ በተስፋ እንጠብቃለን ።

ይህ ስለ እርሻ ትምርት የተጻፈ መጽሐፍ በፍጥነት ሳይፈጸም ማስታወቃችንም በሩቅ ያሉ ወንድሞቻችን አውቀው አስበውት እንዲቈዩ ማለት ነው እንጂ ፤ በከተማ ያሉስ ባለቀ ጊዜ ዕለቱን ያገኙታል ።

የግብፅና የኢትዮጵያ የኖባም ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ። የሃይማኖት ልጆቻቸውን ስለ መጐብኘታቸውና ስለ መባረካቸው መታሰቢያ ።

መጀመሪያ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሥልጣን የቀድሞውን የጭንቅ አገዛዝና ግብር አጥፍተው አገራቸውን ከሽፍታና ከወምበዴ ጠብቀው በኃይላቸውና በዕውቀታቸው ያገኙትን ገንዘብ እያበሉ እያጠጡ እያለበሱ ከጐንደሬና ከትግሬ ከጐጃምና ከሌላውም ሀገር ለመጣው ሠራዊታቸው ላም ላለ ላም ፤ በሬ ላለ በሬ ፤ ብር ላለ ብር ፤ ከዚህ ሌላ የሚያስፈልገውን ሁሉ እየሰጡ ሲገዙ ይገዙ እንደሚባል ሕዝባቸውን ደስ አሰኝተው ስለገዙት ከሥልጣናቸው በታች ያለው ሠራዊት ሁሉ ከዕድሜያችን አንድአንዱን ዓመት ላፄ ምኒልክ በሰጠልን እያለ ይመኙ ነበር ። ይኸም ዳኘ ነው ። ከዚህም ሌላ ገናናው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ያስቀሩትን የጭንቅ አገዛዝ ሁሉ በዝርዝር ለመጻፍ የሚበቃ ወረቀት አናገኝም። ከምሉው በከፍሉ ከብዙው በጥቂቱ ለሰሚ እናመለክታለን። ካራኝ የሚባል አረመኔ ያጠፋውንና ያፈረሰውን ሀገር አደሱ አብያተ ክርስቲያናትን አሠሩ ። ለሠራዊታቸውም የሚያስፈልገውን ሁሉ አጠገቡት ። የክርስቲያንም ምግባርና ሃይማኖት በመላ ኢትዮጵያ ሰፋ ገነነ ። የዳግማዊ ምኒልክ ዘመን በሙሉ ተድላ እንደተፈጸመ ያልተረዳ ይገኝ አይመስለኝም ። መዝሙር ፹፰ ቍ ፫ ፬ ከመረጥሁት ከወዳጄ ጋራ ቃል ኪዳን አደረግሁ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ ። ዘርህን ለዘለዓለም ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እንድተክልልህ ያለው የእግዚአብሔር ቃል ለዳግማዊ ምኒልክ ስለ ተፈጸመ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሕዝባቸውን በዕውቀትና በቅንነት ጠብቀው ። እናት ለልጅዋ እንደምትራራ ለሠራዊታቸው ተጨንቀው ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ስለደከሙላትና አምላክ ፳ ኤልም የሰላም ዘመን ስለሰጣቸው ሠራዊታቸው ሁሉ ሐር አዘውትሮ ለበሰ ። ከተማቸውም እንደ አውሮፓውያን ሥርዓት በጥቂት ዘመን በሚያስፈልገው መማሪያና ቤት ከነጓዙ በመንገድ መኪናም ይህን በመሰለ ነገር ሁሉ አጊጦ ያሰቡት ነገር ሁሉ በጥቂት ወራት የሚከናወንላቸው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በመከተላቸው መሆኑን ማንም አይስተውም።

ይልቁንም ሩቅ ባለው በኢትዮጵያ ቈላና ደጋ የባቡርና የአቶሞቢል መንገድ እስቲሰናዳ ብዙ ዘመን የሚያስፈልግ ስለሆነ ዱሩን ጥረጉልኝ መንገዱን አሠልጥኑልኝ የማይል ያየር ባቡር በዘመናቸው መምጣቱ ለዘለዓለም በሰው ልብ እንደ ሐውልት ተቀርጾ የሚኖር ነው ። ሁለተኛም የግብፅና የኢትዮጵያ የኖባ ሊቀ ጳጳሳት ብፁዕ ቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በሰላማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በዳርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዘመን ኢትዮጵያን ራሳቸው መጥተው መባረካቸው እጅግ መታደል ነው ። ከዚህ በፊት ባፄ እንድርያስ ዘመን ዘስመ መንግሥቱ ሕዝብናይ የግብፅና የኖባ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ስማቸውም እንደዚሁ አቡነ ዮሐንስ የሚባሉ ላቡነ ዜና ማርቆስ ዕረፍት መጥተው በደብረ ብስራት በነ በነ ተአምራት ስለተደረገላቸው በኢትዮጵያ አንድ ዓመት ተቀምጠዋል ይኸውም በገድለ ዜና ማርቆስ ይገኛል ። ይህም ከተደረገ ፮፻ ዓመት ይሆናል ።

ደገኛው አባታችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ዮሐንስ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ ስማቸው ለዘለዓለም ሲታሰብ እንዲኖር የሚገባቸው ነው ። የሰላማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ

ስለ እመቤታችን የዕረፍት በዓል አከባበር ።

ጥር ፳፩ ቀን የእመቤታችን የዕረፍትዋ በዓል ስለሆነ በየሀገሩ ያለው ክርስቲያን ሁሉ በልዩ ልዩ ዓይነት አከባበር ያከብረዋል በዓሉም አስተርእዮ ማርያም ይባላል አስተርእዮ፡ የተባለበትን ምክንያት በዚሁ ጋዜጣ ፩ኛ ዓመት ቍጥር ፭ ገጽ ፴፮ እስታ ። ቀናል ። በአዲስ አበባና በአውራጃዋም ካሉት አብያተ ክርስቲያናት በእመቤታችን ስም የታነፁት አድግብዙዎች ስለሆኑ በዚሁ ቀን ግርማዊት ንግሥተነገሥታት ዘውዲቱ በብዙ መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ወደ እንጦጦ ማርያም ፡ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንም በብዙ መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ወደ አዲስ ዓለም ማርያም ሒደው ነበር ።

ሲሔዱና ሲመለሱም ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ ሰፊው መንገድ ጠባብ መስሎ ይታይ ነበር፡ከፊትና ከኋላም የፈረሱ አገዳ የአውቶሞቢሉ ነጕዳ ዓይን የሚያጥበረብር ጆሮ የሚያደነቍር ነበር፡ጳጳሳቱም እንደዚሁ በየኪያቸው ካሉት የእመቤታችንን አድባራት አክብረው ዋሉ ።

በወጪጫ ማርያም የተነገረ የአስተርእዮ ቅኔ ።

ክብር ይእቲ

እመ ይሁዳ ሰፈረ ክርዳደ ቃሉ፡ በዘሰፈረ ኄሮድስ።
ምልእተ ንባቡ ኢኅፀ እመስፈርተ ጽድቅ ክርስቶስ ።
ሐመልማለ ፍዳ ጌጋየ ከመ ያሕመልምል በለስ ።
በአእዳዊሃ ለሔዋን እስመ ተእንመ ስሕተተ አዳም ልብስ።

ዕጣን ሞገር

ዘርአ መሐላ ዘወድቀ በገራህተ ዮሴፍ ልብ ።
እምእደ ዘይዘርእ ሕግ ፡ ያዕቆብ ።
ኢክህለ ተሠውሮ እምአዕይንቲሃ ለርግብ ።
ወግርማ ርእየቱ ለኤልያብ ።
እምኀበ ድንግል ይትፈኖ ኀበ ዘይትኤዘዞ ሕዝብ ።
ተኀትመ በማሕተመ ኣብሩ እፈ ሞት ንበብ ።

እሠረ ንጉሥ

እምዐዕቀ ምኒልክ ቀሰመት ጾጌ መንግሥት እስክለ ማርያም ንህብ ።

እስመ ላዕሌሃ ሠረቀ ብዕለ ጸጋሁ ለአብ ።
ወጠለ ኄሩቱ ዘያጸኣብ ።
ኃይለ ሥላሴ ላዕሌነ ከመ ያንጠብጥብ ።
ሐፀነቶ በጥበ ጥበብ

ወ ጊ ወ ዮ ።

የበጋ ዝናብ ።

በየባላገሩ ያለ እህል የቈላ የቈላው ከገባ በኋላ የደጋና የወይናደጋ ታጭዶ ከተከመረ በኋላ ተወቅቶ እንዳይገባ ዝናብ አስቸግሮታል ። በዚህ ሰሞንም በአዲስ አበባ ዝናም እየዘነበ ደመናው ተጫጭኖ ክረምት መስሏል ። ይልቁንም ጥር ፲፱ ቀን ብርቱ ዝናብ ጥሏል ። ያሁኑ ዝናብ ለሚወቃው እህል በጣም ያበላሸዋል፥ ግን ለበልግ በጣም ማለፊያ ነውና የበጋ እህል ይከተላል ።

የውጭ አገር ወሬ ።

ጥር ፳ ቀን በተጻፈ በኢጣልያን ሌጋሲዮን ራድዮ ከህንድ አገር የሚመጣ ወሬ ትላንት በህንድ አገር በካልኩታና በሌሎች ከተሞች ህንዳውያን የነጻነታቸውን በዓል እንዳከበሩ ይወራል ይላል ። የኮሚኒስቲ ወገን የህንድ የጥንት ሰንደቅ ዓላማ ቀርቶ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ይሁን በማለት ሁከት ለማድረግ ሞክረው ነበር ።

የእህል ገበያ

	ብር	መሐ
ጤፍ አንድ ዳውላ	፱	
ሥንዴ	፰	
ገብስ	፭	
ዘንጋዳ	፯	
ዓተር	፰	
ባቄላ	፯	
ሽንብራ	፰	
በቆሎ	፯	
ተልባ	፰	
ኑግ	፯	፰
ሰሊጥ	፲፪	

የከብት ገበያ

በሬ አንድ ሰንጋ	፴፫
ላም መሲና	፲፫
በግ	፲፪
ፍየል ሙክት	፱
በቅሎ	፻፳
ፈረስ የኰርቻ	፺፫
ጥሩ አህያ	፳፫
መናኛ አህያ	፲፫

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፩ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፫ ብር
ነህ ጽባሕ	፫ ብር

ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳	መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፬	ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ወዳጅ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የቁጥር ትምህርት	፩	ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር
የብድር ደንብ	፩	ብር
የነፃነት ደንብ	፩	ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩	ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩	ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳	መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፲	መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳	መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፲	መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳	መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፲	መሐ
አሳብና ምኞት	፭	መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፭	መሐ
የልብ አሳብ ማጥም	፪	መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ
የበገና ማጥም	፪	መሐ

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት



ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኳላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረን ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ—

QUALITÁ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዳሮማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
6me ANNÉE № 6

ሐሙስ ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 6 FEVRIER 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIÈRE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፴፫ ገጽ ተከታይ ።

የኢኮኖምያ ፖለቲክ ።

ገበሬ

መሬት ካፒታል ሥራ

የመሬቱ (ቀላዱ)ዋነኛ እሱ ራሱ ገበሬው ሲሆን እንደ-ፈቃዱ ለማድረግ ነፃ መሆኑን ይሰመዋልና ጥቅሙን ለማሳደግ በብዙ ጥንካሬ ስለሚሠራ ጥቅሞቹ ብዙ ይሆናሉ ። ማለት በየ-ጊዜው መሬቱን ስለሚያሻሽለው ሀብቱ እያደገ ይሔዳል። ስለ ዚህ የትንንሽ መሬቶች ዋነኞች ርስታቸውን በጣም ያፈቅራሉና የሥራና የመሻሻል ሥርዓት ናቸው ። ከትልቁ ጦርነት በፊት በጀርመን ሰፋፊ የነበረ የመንግሥት መሬት እየቈራረጠች ለታ-ናናሾቹ ዋኖች ትሰጣቸው ነበረች ። ግን ቢሆንም በዚሁም ጉዳት አይታጣበትም ፤ ስለምን ትንሽ ዋነኛ በገዛ ራሱ የሚያ-ርስና የሚቈፍር ድሐና ደንቆሮ ሰው ነው ፤ ስለምን ሀብታም ቢሆን ሌሎችን ማሠራት በፈለገ ፤ አዋቂ ፤ ብልህና ቻይ ቢሆን በትንሺቱ መሬት እየተታገለ እውቀቱን እንደሚገባው ሳያፈ-ራበት ማባከን (ማለት ብዙ ሰፊና ትልቅ ሥራ ለመሥራት ይቻ-ለው የነበረ) ብዙ ጉዳት በሆነ ። በዚሁ ላይ ደግሞ የካፒታልን ጒድለት መሬቱን ለማልማት የማይቻል በሆነ ማለት መልካ-ሞች መሣርያዎችና ቻዮች ማኪኖች ለመግዛት ባልተቻለውም። አዲስ (ድንግል) ፍርያም መሬት ካልደረሰውም ለሥራ ውለታውም ባልበቃውምና ፤ በችግርም በደረሰ እውነት ነው ፤ በርስቱ ፍቅር ተይዞና ተገፍቶ በብዙ ጥንካሬና ትጋት በሥራ ግን በኤኮኖሚያ መንገድ ስላይደለ እንደዚሁ ብዙ መሥዋእት እያገኘ በድህነት እንደተያዘ ይቀራል ። ለዚሁ ተአምራት በግ-ልጥ የሚያስረዳ መሬታቸው ብዙ ፍርያም ያልሆነ አገሮች ሰዎች ቀንና ሌሊት በብዙ ትጋትና ድካም ይሠራሉ ። ግን ሳት ብሎ ካልሆነ ምንም ቢሆን ሀብታሞች ሊሆኑ አይችሉም በች-ጋር ይኖራሉ እንጂ በዚሁና አንድ አንድ ጊዜም በልዩ ልዩ ምክንያት እርሻው ሲጐዳ ፍሬው አንሶ ራብ ሲበዛ ምስኪኑ ገበሬ እንደዋስነት መሬቱን አስይዞ ዕዳ (ብድር) ለመጻበ ይገደዳል ስለዚህ አንድ ሀብታም አበዳሪ ዋነኛ ይሆናልና ፤ የብዙዎቹ መሬት ተጠቅልሎ በእጁ ይገባልና የመሬትና የካ-ፒታል ዋነኛ ለመሆን መጀመርን ይይዛል ዲያግራማው እንደ ዚህ ይቆማል ።

አበዳሪ	ገበሬ ።
መሬት ካፒታል	ካፒታል ሥራ።

የመሬትን ዋነኛ ከመሬት ስፋት የተነሣ ከቤተ ሰብ ጋራ ሁሉ መሬቱን ሁሉ ለመሥራት ከልቻለ ሌላ አጋዥ ሠራተኛ ለመቅጠር ይገደዳል። ዲያግራማው ቀጥሎ እንዳለነው ።

ዋነኛ	ሠራተኛ
መሬት ካፒታል ሥራ	ደመወዝ

ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል እንደበላ ኢንዱስትሪዎች አሠሪ እንዲሁ የመሬቱ ዋነኛም መምራትና ማሠራት መጠባበቅ ብቻ ቢሆን ሥራው ደግሞ ዲያግራማው እንዲህ ይቀርባል ።

ዋነኛ	ሠራተኛ
መሬት ካፒታል	ሥራ

ይህነን ዓይነት የመሬት ዋነኛውን በቦታው(በገጠር) የሚ-ቀመጥ ቢሆን መሬቱና ሥራውን ይጠባበቀዋልና ማልካም ትርፍ ይሰጣል ። የመሬቱ ዋነኛ በከተማ የሚቀመጥ ቢሆን ግን ገበ-ሬዎቹ ስለማይመለከታቸውና የማያበረታቸው ለሥራው የሚ-ያስፈልግ የሆነ ሁሉም በጊዜው ስለማይፈጽመው ብዙ ጉዳት ይሆናል ።

፫ኛ አይነት ደግሞ የክራዩ አኳኋን ነው ። ማለት እርሻን እየለማችና እየሰፋች ስትሔድ ሁሉ ጊዜ የበለጠ እውቀትን ትፈልጋለችና ብዙ የሥራን ክፍፍል ይገጥማታል። ልዩ ልዩ የሆኑ ክፍሎችዋ ቀጥሎ እንዳለ ዲያግራም ናቸው ።

ዋነኛ	ባለክራይ	ሠራተኛ
መሬት ክፒታል	ክፒታል ሥራ	ሥራ

ብዙ ጊዜ መሬት የሀብታም ሰው ነውና በኤኮኖሚያ ለማፍራት የማያውቅ ወይም የማይችል ወይም የማይፈልግ ይሆናል። እሱ (ሀብታሙ) የመሬት ዋነኛ ስለ ሆነ ሬንዲታ የሚባል ገቢና ለመሬት ማልምያ ያዋለው ክፒታል ወለድ ያገኛል ። ባለ ክራይ ደግሞ ኢምፕሬንዲቶሬ የሚባል መሬት ክፒታል ሥራ አጋጥሞ የሚያቆም አዋቂና ቻይ ሰው ነው ። ማለት መሬት ይከራያል መሥርያዎች (ከብቶችና መኪናዎች የእጅ ሠራተኞች) ያቆማል እሱ ራሱም መሪና አሠሪ ሠራተኛም ይሆናል ። ከእርሳቸው ዓስበ ፃማው ባገኘው ፍሬው ለመሬት ዋነኛ ክራይ ለእጅ ሠራተኖች ደመወዝ ሰጥቶ ፤ ትርፉን ለራሱ ይወስዳል ። የባለ ክራይ እርሻ አኳኋን የተማረ አዋቂና ባለ ብዙ ክፒታል ነውና የሚሆነው የአሁኑ የሥልጣኔ ጊዜ መማርያ ገዝቶ መሬቱን በጣም ለማፍራት ቀላዩቹን በአንድ ቦታ ተገጣጥመው ብዙ ሊሆኑ እጅግ ደግ ነው። ለምን ትልልቆች መኪናዎች ይገዛል። ሥራዎችም የተከፋፈሉ ይሆናሉ ።

ግን ይህም ጉድለት አይታጣበትም ።

ሀ) የእርሻ ሠራተኞች ከኢንዱስትሪ ሠራተኞች ያነሱ ናቸውና ደመወዛቸውን፥ እየተውት ወደ ከተማ ስለሚሰበሰቡት የእጅ ሠራተኞች ያንሳሉ ። የቀሩትም ሀብታሞች ለመሆን አለመቻላቸው ተስፋ ያቈርጣሉና ሥራቸው የልማም ስለ ሆነ ፤ ብለ ብዙ ጉድለት ይሆናሉ ።

ለ) ባለ ክራዮች መሬቱን በጣም ያለሙት እንደሆነ የውላቸው ቀን ሲደርስ የመሬቱ ዋኖች እንደሚያስለቅቁዋቸው ወይም ክራዩን እንደሚያበዙባቸው ያውቃሉና ፤ መሬቱን እስተሚቻላቸው ድረስ ያስፋፋታል እንጂ ፤ አይከባከቡትም ። ስለዚህ መንግሥት አገሩን ለማልማት ቢፈልግ ለተከራዮቹ ጥግ ሁኖ መሬትን በማልማት ለበለጡ ሰዎች ከባለ መሬቶች የዓስበ ፃማ ዋጋቸው ፤ ክራሱም ጉርሻ ገንዘብና እንደነ ልሻን የመሰለ የማዕርግ ሽልማት እንደሚያገኙ የተደላደለ ሕግ ሊያቆም ይገበዋል ።

አሁን የእርሻን ማፍራት ልዩ ልዩ የሆኑ ዓይነቶች እየመረመርን ከተመለከትን ዘንድ በጥንት ከሁሉ ይልቅ በባሮች እጅ እየተሠራች እንደምትፈራ እንደነበረች ፤ ኋላ ቈይታ ደግሞ በአሽከሮች (በአለ ዓስቦች) ዋጋቸውን ትንሽ መሬት እየተሰጡ ትሠራ እንደነበረች ፤ ትልልቅ አዲስ ዓለሞች እንደ አሜሪካ የመሰሉ ከተገለጡ ወዲህም ደህናን የአረማውያን ሥራ የእጅ ሠራተኞች በማነስ ያህል በምስኪኖቹ ደግሞ ግፉ እንደተደገመ አግኝተነው ተረዳን ።

በሚመጣው ሳምንት ይቀጥላል ። ሚካኤል ተሰማ ።

በሚገባው ሁሉ ፀንቶ በመንፈሳዊ አንጻር ሥጋዊውን አርበኝነት መሥራት እንዲገባ ።

ሥጋዊ ርስትና መንፈሳዊ ርስት የሚወረስበት የሥራው ምክንያት ትክክል ነው ። ሥጋዊው ልበ ሙሉነት ያስፈልገዋል። መንፈሳዊውም ጥብእተ ልብ ያሻዋል ። ከሁለቱም መካከል ልሙት ወይም ድል ላድርግ የማለት ሐሳብ እንጂ እሞታለሁና ልቅር ፤ እያዛለሁና ልሽሽ ፤ የማለት ሐሳብ የራቀ ነው ። መንፈሳውያን አርበኞች ስለሀገራቸው ስለ መንግሥተ ሰማያት ፍቅርና ፤ ንጉሣቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ዘኢያረ መስቀለ ሞትየ ኢይክል ይጸመደኒ ያለውን ትእዛዝ ለመፈጸም ሲሉ ብዙ ብዙ መከራ ታግሠው ይቀበላሉ ። ሥጋዊ አርበኛም ነጋሪቱ ውጋ ውጋ ፤ በለው በለው ፤ ገብር ገብር ፤ እያለ ሲጐሰም፥ ጀግናው ሲያጕረመርም ፤ ሰይፉ ሲያብለጨልጭ ፤ ስለቱ ሲያፏጭ ። መድፉ ሲያገሳ ፤ አቧራው ሲነሣ፥መትረየሱ ሲንጣጣ፥ የጀግናው ሬሳ እንደ ቃጠበ ልብስ ሲሰጣ ። የዚያን ጊዜ ደፋሩ ጀግና ልበ ሙሉ ቈራጥ የዓመፀኛውን አንገት ሲቈራርጥ ። ገድሎ ሲፎክር አንዱን ገድሎ ወዳንዱ ሲንደረደር ። የቀረበውን በሰይፉ ሲያቀማጥል፥ የራቀውን በዲሞትፈሩ ሲጥል አይቶ ከፊቱ የሚቆምእንዴት ያለ ጠላት ይሆን?።ደግሞ ከፊቱ ያለውን በእግሩ ሩጦ የሸሸውን በፈረሱ ጋልቦ አስድጦ ፤ የጠላቱን ወንድነት ወደሴትነት ለውጦ ሀገሩን አሳፍሮ ፤ ጠላቱን አባርሮ ። መንግሥቱን አስከብሮ ፤ ያገሩን ዙርያ በመፈራት አጥር አጥሮ። የሀገር ጋሻ ፤ የንጉሥ ትከሻ ሁኖ ሕይወቱን ሞት ፤ ሞቱን ሕይወት ያደርጋል ። ዳግመኛም የአረሩን መራወጥ ፤ የመትረየሱን ማስደንገጥ ፤ ጕዳይ ሳይል የመድፉን ወላፈን እንደ ልብስ ለብሶ ሀገሩ በጠላት እግር እንዳትረገጥ ሽፍታውን አማናዊ፥ዓመፀኛውን ሰላማዊ ያደርጋል ። ይልቁንም ዓመፀኛው ልገብር፥ ልቀቅል ፤ በወንድ ልጅ እምላክ አታጥፉኝ እያለ በግምባሩ ተደፍቶ እሳኪለምነው ድረስ የአንበሳ ግርማ ተጐናጽፎ እያራደ እያንቀጠቀጠ ያስጨንቀዋል ። ነገር ግን ጕብዝና ያለውሰው ምሕረት አያጣምና እንዲህስ ካልሀ ምሬሃለሁ ይለዋል። ሥርዋፅ፥ ይህን ሁሉ የጀግንነት ሥራ ለመሥራት ከፍሬ ነገሩ የሚያደርስ የንጉሥ ፈጻሚ ፈቃድ መሆንና ሀገርን መውደድ ነው። ከላይኛው ነገራችን እንመልስ። ዳግመኛም እኛም ወንድ፥ እናንተም ወንድ፥ ወንድ ለወንድ ይዋጣልን የሚል የጠላቶቹን ሐሳብ በጀግንነቱ እንደ ሰም አቅልጦ ፤ እንደ ገል ቀጥቅጦ፥ አጥፍቶ ሀገሩን አንበሳ እንደሞላበት ዱር አስፈርቶ ንጉሡን ተከትሎ የንጉሡን ፈቃድ ፈጽሞ በሀገሩ አውራጃ የመጣውን ፈያት፥ የቀንማውን ጠላት ለማጥፋት በታዘዘ ጊዜ ትእዛዙን በደስታ ተቀብሎ ይህን የተቈጠረውን ሁሉ የጀግንነት ሥራ። በፍጥነት ለመፈጸም የተዘጋጀ ጀግና በዚህም ዓለም የምድራዊ ንጉሥ ተካፋዩ በወዲያኛውም ዓለም የጻድቃን የሰማዕታት ተክ ቃይ እንደሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክሩለታል ።

የታሪክ መጻሕፍትም ስሙ ዘለዓለም ከትውልድ እስከ ትውልድ፥ከነገድ እስከ ነገድ፥ ሲነገርና ሲደነቅ እንዲኖር የመታሰቢያ ሐውልት ያቆሙለታል ። በገበሬም ይመሰላል ፤ ገበሬ

ከእርሻው መከከል ገብቶ ከአዝመራው የሸተ የሸተውን ሳይፈር ሳያፍር እየቈረጠ እንዲመገብ፡ሥጋዊ አርበኛም ከጠሩ መከከል ገብቶ የዓመፀኛውን አንገት በሰይፍ እየዘለሰ ሲጥል ፍርሃት የሚሉ አያውቀውም።(ጢሞ ክል ፪ ፲፫።)

የጦርነት ሰልፍ ወዳለበት ስፍራ ጀግኖች እንዲቀዳደሙና እንዲሮጡ አታውቁምን ። የሚዋጋ ሁሉ እሳቱን ስለቱን ታግሥ ይቀበላል ። የምስጋናውንም ዋጋ ይቀበል ዘንድ ፀንቶ ይዋጋል።(ቆሮ ቀዳ ፱ ፳፬) ።

ከጦርነት መከከል ገብቶ የሸመውን ንጉሡን ደስ ያሰኝ ዘንድ ሲዋጋ የዚህን ዓለም ንብረት የሚያስብ የለም ።

ማለት፡ሳም አረዱ ጠጅ አውርዱ የሚል የለም። አርበኛ ሰልፈኛ የሆነ ሰውም በሚገባው ፀንቶ ካልተዋጋ አይመሰገንም ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ሥጋውያን አርበኞችን ለመንፈሳውያን አርበኞች ምሳሌ አድርጎ ተናግሮዋል። ይህንም የሚያስረዳ ነገር የነጌዴዎንን፥ የነሰምሶንን ፥ የነባርቅን ፥ የነዮፍታሔን፡የነዳዊትን፥ የነሳሙኤልን፡የሌሎችንም ነቢያት የጀግንነታቸውን ታሪክ ተርኬ እነግር ዘንድ አእምሮ ያንሰኛልና ምን እላለሁ።(ዕብ ፲፩ ፴፪፡)

ምንም ቢያንሰኝ ትንሽ ታሪክ ለማስረጃ ያህል ከዚህበታች እስከትላለሁ።የዳዊት የጭፍራው አበጋዞች አዲኖን ኢያቡስቴ፥ ኤልያና የንጉሣቸው የዳዊትን ፈቃድ ለመፈጸም ሲሉ የጠላቶቻቸውን የኢሎፍላውያንን ሰልፍ በታትነው የወንድ በር ከፍተው እነዚህስ ሳያላውጡ አይለወጡም ተብለው ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው ለመስጠት እንደጨከኑ የዚህን ታሪክ ማንም አይስተውም።ቢስተውም(፪ሳሙ ም ፳፫ ፲፮ ።) ይመልከት ።

ይሁን እንጂ ይህነን ሁሉ የጀግንነት ሥራ ተርከን መናገራችን ላሁን ጊዜያችን ብለን አይደለም ። ያሁንስ ጊዜያችን ዘመኑ ሰላም ነውና ይህ ሁሉ ጣጣ የለብንም ። ነገር ግን ገበሬ ዛሬ በዓል ነውና ሥራ የለብኝም ብሎ ቡሬውን አውልቆ ዝልጕን እንዳይውል እንዲሁም ጀግና የሆነ ሰው ልብሱ ጀግንነት ነውና ከልብሱ ተራቍቶ መቀመጥ አይገባም ብለን ነው እንጂ ። ይልቁንም የኢትዮጵያ አርበኞች አንበሳ የላምን ፍለጋ ተከትሎ ሒዶ በቅጽበት ሰበብሮ እንዲጥለው እነሱም የጠላታቸውን ፍለጋ ተከትለው ከገባበት ገብተው በወንድነታቸው ግርማ ግርምመው በረዶ እንደወረደበት ቅጠል አድርገው ድራሹን እንዲያጠፉት ከዚህም ቀድሞ ተመስክሮላቸዋል።እንግዲህም ወዲህ ይህነኑ ለማድረግ የታመኑ ናቸው ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

የጀግኖች መታሰቢያ ።

ጌታና አሽከር በፍቅርና በእምነት ከኖሩ ኃይልንና ክብረትን ከጉብዝናና ከድፍረት ጋር ያሰፋፉሉ ። ታላቁ ናፖሊዎን የድፍን ኤውሮፓ ንጉሠ ነገሥት በጊዜውና በመንግሥቱ እስካለ ድረስ የፈረንሳይን አገር አስከብሮና አሳፍሮ ይኖር ነበር ይባላል። ምንም ድፍን ኤውሮፓ ለፈረንሳዊ መንግሥት ተገዢ ሁነው ቢታዘዙና ቢዳኙ ፩ አንድ ጊዜ ፩እንዶቹ ወገኖች እንደ ሽፍታና እንደ ወንበዴ እየሆኑ እያደሙ ናፖሊዎንን ይወጉት ነበር ይባላል ።

ናፓሊዎንም በእግዚአብሔር ፈቃድ የነገሠና ግርማ ያለው ንጉሥ ስለሆነ ምንም ቢያድሙበትና ቢመክሩበት እስከ ጊዜው ምንም ሊጐዱትና ሊያጠቁት አልቻሉም ድመት ያየች አይጥ ዞላ ወደ ጕሬዋ እንደምትደበቅ ሁሉ ፥ በናፖሊዎን ላይ የሚያድሙና መጥፎ ሐሳብ የሚያስቡ ናፖሊዎንን ባዩት ጊዜ የመከሩት ምክራቸው እየጠፋ ከመገዛትና የናፓሊዎንን ትእዛዝ ከመፈጸም በተቀር ምንም ሊያደርጉት አልቻሉም ነበር ።

በናፖሊዎን ጊዜ መሳፍንቱና መኳንንቱ ናፖሊዎንን ለማጥፋት እያሰቡ እየደፈሙና መጥፎ ሐሳብ እያሰናዱ ሲዘጋጁ ናፖሊዎንም እየሰማ እየያዘ ወደ ቅጣትና ወደ ሞት እንደፈረደባቸው ይኖር ነበር ።

በናፖሊዎን ጊዜ ድኃና ባላገር ወታደር ናፖሊዎንን በመውደድና በማፍቀር እሱኑ መስለው ሲገዙለትና ትእዛዙን ሲፈጽሙለት ይኖሩ ነበር።ነገር ግን ናፖሊዎን በጊዜው ከድካምና ከጦርነት በተቀር ምንም እረፍት አድርጎ እንደ ዓለም ነገሥታት ዐርፎ ተቀምጦ ገዝ የሚበልበት ጊዜና ዓመታት ቍጥር ምንም ያህል አይበዛ' ።

ታላቁ ናፖሊዎን የድፍን ኤወሮፓ አንበሳና ንጉሥ የሌሎቹም አገር እጮኛ ፩ጊዜ የአንድ ክፍል ሕዝቦች በሱ አንገዛም ብለው አደሙና ሊወጉት ተሰናዱ ። ናፖሊዎንም ይህነን በሰማ ጊዜ ፩መጥፎ በር ነበረችና ሂደህ ያችን በር ጠላቶቻችን ሳይዟት አስቀድመህ ይዘህ ቈየኝ አለና የጦር ሚኒስቲሩን አዘዘው ምኒስትሩም በድንገት ተነሥቶ ያንን የተያዘበትን በር ለመጠበቅ ፳፻ የሚያህሉ ወታደሮች ይዞ ቢደርስ ጠላቶች አስቀድመው ያችን በር እልፍ መስፈርት የሌለው ሁነው ይዘዋት አገኘ ።

ያም የጦር አበጋዝ ሒዶ እንዳይወጋቸውም ለጦርነት የበቃ ጦርም አልነበርና ለጌታዬ ላስታውቅና ጦር ጨምረው ልኝ ልዋጋ ወይንስ እነኝሁኑ ያሉኝን ይዤ ልዋጋ ብሎ ሐሳቡቹን ሲያወጣና ሲያወርድ ሳለ ኃያሉ ናፖሊዎን ፻፪ እንጋቾች ይዞ ከመ ቅጽበት እጦር አበጋዙ ዘንድ ደረሰና ምነው እዚህ ዓርፈሃል? ብሎ የጦር አለቃውን ጠየቀው ።

የጦር አለቃውም ልጠብቀው ያዘዙኝን በታ ጠላቶቻችን ቀድመውኝ ስለ ያዙት ተቸግሬ ለመዋጋትም ጦሬ ጥቂት ስለ ሆነና በከንቱ ሕዝባችንን ማስጨረስ መስሎ ስለ ታየኝ ይኸንኑ የተላከበትን ነገር ሳወጣ ሳወርድ እርስዎ ደረሱልኝ ብሎ መለሰለት ።

ናፖሊዎንም ለጦሩ እለቃ እንዲህ ብሎ መለሰለት አንዳንድ ጊዜ ድፍረትና ብርታት ነው እንጂ ድል የሚያደርገው የሰው ብዛት አይደለም ብሎ መለሰለት ወደዚያው ከወንዶች በላይ ወንድ የሆነው ናፖሊዎን ወደ ጠላቶቹ ዘንድ ድፍረቱንና ብርታቱን አሰፋፍቶ ተጓዘ ከጠላቶቹ ጋራ ውጊያውን ጀመረ ውጊያውንም ከመጀመሩ ናፖሊዋን ከጠላቶቹ ወገን ያለውን መድፈኛ በጠመንጃ ገደለው ያኔውኑ ናፖሊዎን መድፈኛውን በጠመንጃ ከመምታቱ የጦር አለቃው ከናፖሊዎን አልፎ መትረየስ ተኳሹን በሾተል አንገቱን ቀማውና ጠላቶቹም ድል ሆኑ ናፖሊዎንም የጦር አለቃውን ሥራ ድፍረቱንና ጉብዝናውን ስለተረዳው ለጦር አለቃው የፈረስ ስም ሲያወጣለት

Brave des braves) የጐበዞች ጐበዝ ብሎ ጠራው ይባላል። ይህ የናፖሊዎን ታሪክ እስከ ዛሬ ድረስ ለአርበኞችና ሀገራቸውን ለሚያፈቅሩ ሁሉ ትልቅ መሠረተኛ ነገር ሁኖ በታሪክ ሲነገርላቸው እንደምንሰማው ጊዜ የሚያመጣው አይታወቅምና የሀገሬም የጦር አርበኞች ከናፖሊዎን ወታደሮች የበለጠ ምስጋና እናገኛለን በማለት እያሰቡ ተሰናድተው እንዲኖሩ ሙሉ ተስፋና ምኞት አደርጋለሁ ማለቴን ላባቶቼና ለታላላቆቼ ሐሳቤን አቀርባለሁ ። በቀለ ዘለቀ።

ፍቅርና አንድነት እንዲጠቀም፡ጠብና መለያየት
እንዲጐዳ የሥልጣኔ ፍፍቶች እነጋገር ።

በሀገራችን ሥልጣኔ እንዲገባ ሕዝብና መንግሥት ተስማምተው በንድ ልብ ሁነው አሁን የተንቀሳቀሱበት ጊዜ ነው። የኢትዮጵያ ልጆች በመሐሏም በዳርዳሯም ያለን ሁላችን ሆይ ባንድነት ነቅተን ለሥራና ለትምህርት ተነሳሥተናል እያልን እርስ በርሳችን በመመሰጋገን ፍቅርን ስንዘራ ከርመናል ። የሥራንና የትምህርትን ፍሬ ጥቅም አዝመራውን ጠንክረን እንጠብቅ ። የፍሬውን ምርት እስትናገኝ የትምህርትንና የሥራን ፍሬ ጥቅሙን የሚሰጠን አንድነትና ፍቅር ነው ። ጠብና መለያየት የሚያመጣውን ጉዳት ከታሪክ የተመለከትኩትን ጥቂት ላስረዳችሁ ።

በጠብና በመለያየት ብዙ ታላላቆችና ኃይለኞች መንግሥታት ከኃይላቸው እየወደቁ የጠላት መዘባበቻ መጫወቻ ሁነው እንደጭቃ ተረግጠው፡ እንደ ጉደፍ ተጥለው ከጠላት እጅ ወድቀው በብርቱ ቀምበር ተጨንቀው እንደ ተገዙ በብዙ ታሪክ ይገኛል ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ አንድነትንና ፍቅርን ይዛ በነበረች ጊዜ በቀድሞ ዘመን ኃይልና ብርታቷ የግዛቷንም መስፋት በብዙ ታሪክ ተረድተነዋል ። ኋላ ግን ፍቅር በማጣት መከፋፈልና መለያየት ሁናባት ከኃይሏ መድከም በግራኝ ጊዜ ተጀመረባት። ይህም የሆነ በንጉሡ ትዕቢት በመኳንንቱ መለያየት በሕዝቡ እርስ በርሱ መጣላት ነው። ግራኝ የኢትዮጵያን አገርና መንግሥት አጥፍቶ ንጉሡን አፄ ልብነ ድንግልን አጥቅቶ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥሎ መጻሕፍትን ቄነጻጽሎ ንዋዬ ቅድሳትን አርክሶ ብዙ ደምን አፍሶ ፲፫ ዓመት ሙሉ አጠፋ።

ከዚህ በኋላ ብድር አይቀርምና ባፄ ገላውዴዎስ እጅ ሞተ። ከ፲፱ ዓመተ በኋላ አፄ ገላውዴዎስን ደግሞ የግራኝ የኅቱ ልጅ ኑመር የተባለ ገደላቸውና ወደ ከተማው ወደሐረርጌ ሔደ ። ይኸውም አገር በዚያም ጊዜ የኢትዮጵያ ግዛት ነበር ። ግራኝም ከነወገኖቹ የኢትዮጵያ ንጉሥ ገባሮች ነበሩ። ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ዙሪ ያለ አረመኔ ሁሉ ሠለጠነ ። እንኳንስ ሌላ ክርስቲያን የተባለውም ተከፋፍሎ በየራሱ ሆነ።በጐንደር ነገሥታት ዘመን ክርስቲያኑ ተጠቅሎ ለጊዜው አንድ ቢሆንም በዙሯዋ ያለ አረሚና እስላም ግን አንድ ጊዜ ሲገብር አንድ ጊዜ እምቢ ሲል ሁል ጊዜ ሲያስቸግር ይኖር ነበር ። አደጋ እየጣለ ክርስቲያኑን ሲገድልና ሲዘርፍ ነገሥታቱም ሁል ጊዜ እየዘመቱ ሲፈጁት ሲዘርፉት ይኖሩ ነበር።ነገር ግን በዘረፋና ሁል ጊዜ በመረሳ መምታት ቀጥ ብሎ ምንም አልተገዛምና አልገበረም ። በጐንደር መንግሥት ፍጻሜ ካፄ ተክለ ጊዮርጊስ መንግሥት በኋላ ። እንኳን ዳርዳሩን ያለው አረሚና እስላም ሊገዛ ። እንዲያም ፸ ዓመት መንግሥትና አንድ ጠቅላይ ንጉሥ ጠፍቶ ክርስቲያኑም በየራሱ በየመሳፍንቱ በየወገኑ ተከፋፈለና ተለያየ ።

ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ኃይል ኢትዮጵያ እንደጥንቱ አንድ መንግሥት ሆነ ። ነገር ግን በያገሩ ሽፍታ እየወጣ በቸው ሕዝቡ እየተናወጠባቸው አንድ ጊዜ ሳያርፉ ሽፍታ አለበት በተባለው አገር ሲገስግሱ ይኖሩ ነበር ። መኳንንቱና ሠራዊቱ ሕዝቡም ቢከዳቸው ። ኢትዮጵያን አገራችን ለባዕድ አሳልፈን አንሰጣትም ሲሉ ተዋግተው ደማቸውን አፍስሰው ሕይወታቸን ለኢትዮጵያ አሳለፉላት ። ለሀገር ፍቅር ማለት እንዲህ ነው ። የዛሬ ልጆች ያፄ ቴዎድሮስን ውለታ በልባችን እየመዘንላቸው ሐውልት እንዲሠራላቸው የማይመኝ የለም። እግዚኣብሔር ኢትዮጵያን እንደጠበቃትና የሚያስብላት ንጉሥ እንደሰጣት ይኖራል ክብሩ ይስፋ ። ባንድነትና በፍቅር ከለምለሙዋ ሀገራችን ላሙን ፥ በሬውን ፥ እያረባን ። ከለሰለሰው ማሳ ጨብን ጥቀኑን በያይነቱ እህሉን እያመረትን የሚጠብቀንን መንግሥትን እየመረቅን ፈጣሪያችንን እግዚአብሔርን እያመሰገንን እየወለድን አሳድገን ልጆቻችንን አየዳርን የልጅ ልጆቻችንን እያየን ደስ እያለን መቀመጣችን ባንድነትና በፍቅር ነው ።

ሰሚ ጆሮ ያለው ብልህ ኢትዮጵያዊ ፍቅርንና ጥቅምን የሀገርን ልማት ፈላጊ ይስማ።በጠብና በመለያየት ወልዶ ማሳደግ፡አስድጎ መዳር፥የልጅ ልጅ ማየት አይገኝም። ላሙን በሬውን ማርባት እያሰቡ ማርድ አይገኝም ። በጠብና በመለያየት ማረስ እህሉን በያይነቱ ማምረት፥ በጐተራ መክተት አይገኝም ።

በጠብና በመለያየት ሀገር ይራባል፥ ገበያ ይፈታል፥ የሚተላለፍ ነጋዴ ይቆማል፥ ውርደትና ጕስቍልና ያመጣል።

በጠብና በመለያየት ከሥልጣኔ መንገድ ወደኋላ መቅረት ደናቍርት ተብሎ መሰደብን ያመጣል ።

ጠብና መለያየት ካገር ሽማግሌን ከመንደር ሕፃናትን ያሳጣል፥ ጠብና መለያየት ዘመድን ከዘመዱ፥ ወዳጅን ከወዳጁ፥ አባትንና ልጅን መለያየት ያመጣል ።

ጠብና መለያየት ስደትና መከራን ሞትና አገር ባዶ መሆንን ያመጣል ። ከዚህም የሚብሰውን ሁሉ ጉዳትን ያመጣልና ይህ ሁሉ እንዳይ ደርስብን መሐሪ እግዚአብሔር አንድነታችንንና ፍቅራችንን ጠብቆ አገራችን ኢትዮጵያ ለምለሚ ወደሥልጣኔው ደረጃ እንድትቀዳደም ያድርግልን ስል በፊት ጀምሬ የምመኘውን አሁንም እስታውሳለሁ ። መኩብብ ደስታ

ፈኑ ኅብስተከ ውስተ ገጸ ማይ ።

እንጀራህን በውኃ ውሥጥ ስደድ ፤ ከብዙ ቀን በኋላ ታገኘዋለህ ቢል ምሥጢሩ አያጠግብም። እንጀራህን በከርሠ ርኁባን፥ መጠጥህን በጕርዔ ጽሙኣን፥ ልብስህን በዘባነ ዕሩቃን አድርግ ከውኃ ዳር የዘራ እንዳያጣ ከእግዚአብሔር ዘንድ

ቆበነ ሥራ ዋጋህን አታጣም ሲል ነው ። ሰሎሞን የተናገረው መክብብ ፲፩ ፩) ቸር ሰው የሚራራ ነው ። የሚያበድርም ነው ። በተነ ፤ ለችጋረኞችም ሰጠ ጽድቁ ለዘለዓለም ይኖራል በክብርም ከፍ ከፍ ይላል ። መዝ ፻፲፪ ፭ ፱) ምስጋና ይገባዋል ለሚሰጥ ከሚወስድ ይልቅ ። ግብረ ሐዋ ፳ ፴፭ እንደ ዚሁ ሁሉ የክቡር ደጃዝማች ብሩን የትሩፋት ጅምራቸውን እጽፍ ዘንድ እወዳለሁ ።

ከሁለት ዓመት በፊት በወለጋና በአቢጋር ግዛታቸው ሳሉ የርኅራኄ በጎ ሥራቸውን የሚያስረዳ በአእምሮና በብርሃንና ሰላም አንብበናል ። በየጊዜውም ዓይን ከማየት ገሮ ከመስማት የማይጠግብ ነውና እነሆ አሁን የሲዳሞና ያውራጃዋ ሁሉ ገዥ ሁነው ከወረዱ በሕዝቡ ላይ የነበረውን ከበድ ከበድ ሸክም ብጣም አሻሽለው አስወግደውለታል ይህንንም በየክፍሉ መረዳት የሚፈልግ አእምሮንና ብርሃንና ሰላምን ይመልከት ።

ባለፈው ኅዳር ፳፪ ቀን የትምህርት ቤት ሲያቆሙ ወግፍዕም ለውእቱ ቤት ወኢወድቀ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ ያለውን ቃል አስበው ምንም አሁን በተሰጣቸው ሥልጣን እስከሉበት ዘመን ለመምህራኑና ለሆስፒታሉ ለትምህርት ቤቱ በሚያስፈልገው ሁሉ ገንዘብ ቢሰጡና እርዳታቸውን በያጐሉ መሠረት ያለው ለኋላ የሚሆን የተቈረጠ ገንዘብ መስጠት ያስፈልጋል ብለው ፲ሺ ብር ሰጡ። ባለቤታቸው ክብርት ወይዘሮ አማከለች ፫ሺ ብር፥ እናታቸው እማሆይ አዲሴ ፫፻ ብር ሰጡ በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡት መኳንንትና ሕዝብ ሁሉ የውጪ አገር ሰዎች ሳይቀሩ እንደመጠን እንደመጠኑ ከመቶ አምሳ እስከ ዓሥር ብር ድረስ ሰጡ ። ያሰጣጡም ሁኔታ በ፪ ክፍል ጸሐፊዎች ተቀምጠው እኔ ልስጥ እኔ ልስጥ በማለት ሲቀዳደሙ ላየ ሰው እጅግ ያስደንቅ ነበር ። ገንዘቡም ምን አልባት ባልሳሳት በግምት ፪ሺ፭፻ ብር ይሆን ይመስላል ፤ ከዚሁም ውሥጥ በመት በመት እንሰጣለን ያሉም አሉ ፤ መቸውንም የኢትዮጵያ ሕዝብ በፍቅር ከመሰሉት በጎ ነገር ለመሥራትና ያለውን ለመስጠት እጁን የዘረጋ ነው ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የተባለው ቃል በስመ ኅዳሬ ደጸዋዕ ማኅደር ሁኖ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝጵብ ለስጦታ እጁን የዘረጋ ነው ብንል አያሳፍረንም ወደታዘዘበትም ለመሔድ የተጋ የነቃ ነው ።

ክቡር ደጃዝማች ብሩ ይህን በጎ ሥራ ማሰባቸው ከቀሩት አገረ ገዥዎች ይልቅ ገንዘብ አግኝተው አይደለም ። የቀድሞ አበቶቻችን የኢትዮጵያ አርበኞች ጠላት በማጥፋት አገር በማቅናት ከጦርነት ስላላረፉ ለጊዜው የሚበቃትንና የሚያስፈልጋትን ሳያጐሉ አስፍተው አቅንተው ከጠላት ጠብቀው በመልካም አቈዩን እኛ ደግሞ ልጆቻቸው አሁን አገራችንን በሚያስፈልጋት አዲስ ነገር ከገንዘብ ይልቅ ሕይወታችንን እስከማሳለፍ ወደኋላ የማንልበት ናትና ከዚው በገኘነው ወገኖቻችን በጥበብና በእውቀት እንዲጐለምሱ እንረዳ።የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ፍለጋ አጥብቀን እንከተል በማለት ነው እንጂ ብዙ ሳለው የማይሰጥ አለ፥ ሳይኖረው ተበድሮ የሚሰጥ አለ ችሮታ የርኅራኄ በሕርይ ላለው ሰው ብቻ መሆኑን አናስተውል ብለው እነሆ ቀድሞ ፥ የነበሩ አገረ ገዥዎች ገንዘብ መጥቀሙን ሲያውቁ በማኖር ብቻ ደስ አይበለን ለወገኖችን በመስጠት፥ በማብላት፥ በማጠጣት፥ በመሸለም፥ይሁን ብለው ተበድረው እስተመስጠት የደረሱ ብዙ ናቸው ፤ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸውም ጊዜ ለሕዝብ በማብላት፥ በማጠጣት፥ በመሸለም፥ ዕዳ ቢገኝባቸውም ላርበኞቹ መንግሥት ዕዳ ከመክፈል ወደኋላ አይልም የቀረው መኳንንት በማጥን ከቶታል በምሰማር መቶታል ። አባ ሻውል ደምስ ለጉበዝ ናኝቶታል ይባል ነበር ።

ውንጌል ተምሯልወይ ያባተ ፈረስ ይትረፍ ለነገ አይልም ምንም ቢደገስ ። ይህም ችሮታቸው በጊዜው ትምህርት ቤት እንደማቆም ሁሉ ሁኖ ሊቈጠርላቸው የሚገባ ነው ።እኛም ወታደሮቹ ልብችን የሚነካ የሽን በመሰለ ነገር ነው። ወደቀደመው እንመለስ ለትምህርት ለተሰበሰቡት ሕፃናትም በ፮ ሰዓት ምግባቸውና መጠጣቸው ተሰናድቶ ከትምህርት ቤት ድረስ እንዲመጣላቸው ክቡር ደጃዝማች ብሩ ከቤታቸው ስለፈቀዱ ሕዝቡ እጅግ ደስ ብሎታል።የሕፃናቱን ቍጥር ለመናገር እየዕለቱ ይበረክታሉና አሁን እንታገሣለን።በየዕለቱም እየሔዱ የትምህርት ቤቱን ይጐበኙታል። ሕፃናቱንም ደስ በሚያሰኝ ቃል ጥበብ ትኄይስ እምኵሉን መዛግብት ያለውን አስቡትጉ አሁን እላንት ሕፃናት ለኔ እንደ ሐዲስ ተክል ሁናችሁ ትታዩኛላችሁ በየጊዜው ማደጋችሁን እንደምመኝ እላንተም ላገራችሁ ፍሬ እንድታስገኙ አስገነዝባችኋለሁ ማለታቸውን የሰሙ ጐበዛዝት ወየው ልጅነት የምትገኝ በሆነ የነዚህ ሕፃናት በረከት በደረሰን፥ ከክቡር ደጃዝማች ብሩ ረድኤት በተከፈለን ያሉ ብዙዎች ናቸው ።በሆስፒታሉም ያሉትን ሕመምተኞች እየሔዱ ይጐበኟቸዋል በይተዋሮች የሆኑትንም ሕመምተኞች በምግብና በልብስ እየረዱ በነጻ ያስታምሙዋቸዋል።ይልቁንም በሆስፒታሉ ሥራ የሲዳሞና ያውራጃዋ መኳንንትና ሠራዊት ገባርና ባላባት ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ብዙ ዘመናት ዕድሜ ይስጥልን፥ ክቡር ደጃዝማች ብሩን የመሰላ መልካም ገዥ የሰጡን እያለ ምስጋናው የዘወትር ነው። ይህም ትልቅ ዕድል ነው። አሁን ደግሞ አዲስ አበባ ለመምጣት ስለ ተነሡ ለወታደሮች በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ያለመጠን ደስአሰኝተዋቸዋል ልብ ከተመኘው አፍ ከተናገረው አንድም አላጐደሉባቸውም። ክቡር ደጃዝማች ብሩ መልካም ገዥ ላገሩና ለሕዝቡ ዋስና ጠበቃ ነው የተባለውን ፈጽመዋልና እንደቀድሞም ልምዳችንን ባለመዘንጋትም የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን ፍለጋ በመከተልም የኢትዮጵያ ልጆች የሆንን ሁሉ የዚያችን ዕለት ደስታ ተካፋዮች መሆናችንን ጌታችን ይወቁት በማለት እነሆ ገልጸናል ። ሮሜ ፲፩ ፤ ፲፱፳ ፤ አወድማለሁ ለመልካም ነገር ጠቢባን ትሆኑ ዘንድ የዋሃንም ለክፉ ነገር ሁሉ ። እግዚአብሔርም የሰላም አምላክ ሰይጣንን የኢትዮጵያን ጠላት ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጥቅጠው።የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከላንት ጋራ ይሁን አሜን። ኢትዮጵያ ከገዦዎቿና ከርበኞቿ ጋራ ዘለዓለም ትኑር ኢትዮጵያ እንድትከብሬ ፈጽመሽም እንድትኰሬ ሺ ዓመት ያንገሥ

ተፈሪ ዘርአየ በዓይኑ ወዘሳማዐ በእዝኑ ነበበኒ ከመ እክሥት ለዥሉሙ ውሉደ ኢትዮጵያ ። አ ወ ደ ።

ስለ አገር አስተዳደር ።

ጃንሆይ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ለሀገራቸው ሕዝብ በጣሙ ርኅሩኅና አዛኝ ቸር ናቸው ፡ ሰዱ የገበውን በየጊዜው ይምራሉ የማይማረውን ያክፈሉልኝ ቢል ያከፍሉታል ። ይልቁንም በጣሙ ቀረ የበዛበት ወለጋና ጐድሩ አውራጃ ነበር። የቀረም ልክ በ፲፱፻፲፩ ጀምሮ እስከ ፲፱፻፳፩ ድረስ ፶፫ሺ ፫፻፳፯ጉንዶ ፲ዋንጫ ቀረ ተገኘ፣ ይኸነን ማሩት፡ ሥሪም በሙት ፯ሺ ነበር፡ ፪ሺ ያግባ ብለው ወሰኑለት።ይኸነን ሁሉ ማድረጋቸው ድሀው እንዳይበደል በዚህ ምክንያት የሚአርስበትን በሬ እየሸጠ ለሰዳ እየከፈለ ደሀው እንዳይራብ ነው ። ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንቶች በየውራጃው የምትገዙ እንደዚሁ ለሕዝቡ አስተዳደር ብታደርጉለት ሰዳም የገባ እንዳለ ብትምሩት አገሩም ይጠግባል ድኃውም በቀጥታ ያርሳል ያረሰውንም እህል በጥንቃቄ ጠብቆ ያገባል ፡ ለድሀ አስተዳደር ተሰጡ አገር እንዲጠግብ የታወቀ ነው ። ይኸውም ክቡር ደጃዝማች ደስታ የሚገዙት አገር ምስክር ሁኖ ይናገራል ተዚህ ቀደም ጉማ የቡና አገር ነው እህል አይደፍርም እየተባለ በየጐረቤቱ እየሸመተ ሲበላ ይኖር ነበር ። አሁን ደሀው አስተዳደር ቢአገኝ ተዋናው ግብር ሌላ በሰበብ መቃሥር ቢቀርለት የራሱን አገር አጥግቦ ሊሙ ጅማ በያቅራቢያው ያለ ሁሉ ተጉማ እየሸመተ ይበላል ። በማንም ጊዜ ተጉማ እህል ተሸምቶ ተብሎ አያውቅም ። መሻሻሚ ነው እንጂ ።

ክቡር ደጃዝማች ደስታም ያቆሙት ሕግ ያዘዙት ትእዛዝ ይጸናላቸዋል።ሥራቸውም ሁሉ ደግነት ነው።ንጉሥ ወልደጊዮርጊስ የሠሯቸው ጥሩ ጥሩ አብያተ ክርስቲያናቶች ከፋ ነበሩ በመት ባመቱ ሳር እየተከደኑ ፍሳሹ አላቆም እያለ በስእሉ ላይ ሁሉ ያፈስበት ነበር።አሁን ግን ክቡር ደጃዝማች ደስታ ፩ ቆርቆሮ በ፫ ብር እስተኪራዩ ፰ ብር እየገዙ እንዳራቻ መድኃኔ ዓለምን በቃ ሥላሴን ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የሰሩአቸው ኪዳነ ምሕረትን፡ሚካኤልን ራሳቸው ሰርተው ቆርቆሮ ከደኑ፡ጉማ ሚካኤልን ገንቢውን ከዲስ አበባ አውርደው አሠርተው ቆርቆሮ ከደኑ፣አገሮ ማርያምን ተመሐዲሱ ተቋርጠው ሥራተጀምሯል አገሮ ሲአልቅ በልፎ ጊዮርጊስን ይሰራሉ ይባላል። ከፋም ላይ የተማሪቤት አቁመው የከፋው ልጅ ሁሉ ተመልምሎ ምግባቸውንና ልብሳቸውን ችለው ብዙ ሕፃናት ይማራሉ። ለታመመም ሰውመታከሚያ ሆፒታል ተሰርቷል የሚታከምም ሰው ዋጋ አይከፍልም።በሳቸው ገንዘብነው የሚታከም፣ተሀገሩ ላይ የሚወጣው ገንዘብ ለሚሰጡት ስጦታና ለሚሠሩት ሥራ አልበቃቸው ብሎ ተዚህ ወደታች እየወሰዱ ነው ሥራ የሚሠሩት። ይልቁንም ከዚህ ላይ የተጻፉት አብያተ ክርስቲያናቶች ይከደኑ በተባሉ ጊዜ ደሀው የሚጐላላው ባዳፋኝ የሚወጣው ገንዘብ ልክ የለውም ነበር ደሀውንም ብዙ ዘመን ተችግር ማቆየታቸው ለዕድሜ ማስረዘሚያ ለነፍስ መታደጊያ እንዲሆናቸው የታወቀ ነው ።

መሐሪ ረታ

የዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፯ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፭ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፱ ብር ተኩል
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፩ ብር
ባለ ድመ ።		፻፵፰
ባለአህያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፳፭
ባለ አንበሳ አሚሪከ		፻፳፬
“ “ ጃፖን		፻፸፲ብር
ሱክር	ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፱ ፍራንክ ከ፳፫ሳቲንም
ባአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፭ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፱ ብር ፲፬ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ ፵፰	

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና በለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ነሀ ጽባሕ	፭ ብር

ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፱ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የንቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንድር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፲ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፲ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፮ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፮ 〃 ሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፮ መሐ
የአንቀጣጣሽ ግጥም	፮ መሐ

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

አስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኰኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እኼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፯
6me ANNÉE № 7

ሐሙስ የካቲት ፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 13 FEVRIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በግዛታቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፵፪ ገጽ ተከታይ ።

የኢኮኖምያ ፖለቲክ።

በፊት ደጋግመን እንዳመለከትነው የአሁኑ በሠለጠኑ አገሮች የተለመዱ ዓይነቶች አኳኋን ግን መጀመሪያ የኤኮኖሚያ አቈነጣጠብ የመሬቱ ዋነኛ እርሻውን በገዛ እጁ ሲሠራ ይህ የተሻለ ዓይነት ይባላል።ግን ይህነንም ጒድለት አለው ብለናል፥ ማለት የትንሽ መሬት ዋነኛ የተከናወኑ የእርሻ መሳርያዎች ሊገዛ ከባለ ካፒታሎቹ እምነት አግኝቶ (ታምኖ) ብድር ሊያገኝ አይችልምና።

ሁለተኛ ፤ የእኵል እርሻ አኳኋን የምትባል ደግሞ በዋነኛውና በገበሬው መኻከል እንደማኅበር ዓይነት ነች ማለት ዋነኛው መሬትና ካፒታል (እንደ ቤትና መሳርያ መቈፈርያ የመሰሉ ሁሉ) ገበሬው የካፒታል አንድ ክፍልና ሥራው ሁነው ይገጣጠማሉ ። ፍሬው እንደስምምነታቸው ወይም እንደ አገሩ ወግና ደንብ በሁለቱ ይከፋፈላሉ ።

ሦስተኛ ፤ የክራይ አኳኋን የሚባል የመሬቱ ዋነኛ በገዛ እጁ በመሥራት ፈንታ ለኢምፕሬንዳቶሬ የሚባል አሠሪ ሲያከራየው ነው።የተኛው ኢምፕኙሬዳቶሬ የእጅ ሠራተኛና ካፒታል አገጣጥሞ ሥራውን ያቆማል።ይህነን ዓይነት በአንድ ወገን ብዙ ጥቅም አለበት፤ስለምን ብዙ ካፒታል በሥራ ሊውል ይፈቅዳልና፤በአንድ ወገኑ ደግሞ ብዙ የመሬት ጕዳት አለው፥ ስለምን የመሬቱ ዋነኛ መሬቱን አይከባከበውምና።ተከራዩ ደግሞ መሬቲቱን እስከሚቻላት ድረስ ማፍራትዋ ብቻ ይገደዳል። ስለዚህ የፍጥረት ሁሉ እናት የሆነች መሬቲቱ በጣም ትጐዳለች ።

፴፱) የሠራተኛ ውለታ ወይም ደመወዝ ።

በድፍን ደመወዝ የሚባል የእንጒል ይሁን የእጅ ሠራተኛ ውለታ ነች ። ግን ለያይተን በረቂቁ ብንመለከተው ይልቁንም የእንጒል ሠራተኞች ደምወዝ እውነተኛ ስሙ ተለያይቶ እናገኘዋለን ። ማለት ፕሮፌሲዮረስቲ የሚባሉ እንደ ሐኪም፥መሐንዲስ፥ ሕግ አዋቂ የመሰሉ ከሰው በታች ሳይሆኑ በገዛ ራሳቸው ሠራተኞች ደመወዝ ኦኖራርዮ ይባላል።ኢምፒፓቲ እንደነ የፍርድ ቤት ወታደር፥የጒምሩክ፥ስልከኛ፥ ፖስታ የመሰሉ ሹማምንቶችና ሠራተኞች ደመወዝ ስትፔንዲዮ ይባላል ። የባለ ባንኮችና ኢንተርሜዳያሪ የሚባሉ አስማሚዎች (ደላሎች) ኮሚሲዮናሪ የሚባሉ ተላላኪዎች ትርፍ (ደመወዝ አጅዮ እና ፕሮቢጂዮኔ ይባላል ። ስለዚህ ደመወዝን (ሳላርዮ) ስንል የሰፋውን ልዩ ልዩ አሳብ በጠባቡ እንጠቀልለዋለን ። እንደገና በሬያሌ የሚባል እውነት የሆነ ደመወዝና በኖሚናሌ የሚባል የጥሬ ስም ደመወዝ ሁኖ ይለያል ። ሬያሌ የማፍራቱን ብዛትና ሠራተኛው ሊሰጠው በሚችል ሥራ ብዛት ተሰጥተዋል።ናሚናሊ ሠራተኛው በብር የሚያገኘውን ብዛት ተሰተዋል (አስረጅ) ሬያሌ ማለት በፊት ዘመን አንድ ሠራተኛ ዓሥር ብር ቢያገኝ ብዙ ነገር ሊገዛ ይችል ነበር። ናሚናሌ ማለት ደግሞ በዛሬ ዘመን ሠራተኛው ሐያ ብር ቢወስድም እንደ ድሮ በዓሥር ብር ያገኘው የነበረ ጥቅም እንኳ ሊገዛ አይችልም እንደ ማለት ነው ። በእውነተኛው ሬያሌ የሚባል ደመወዝና ናሚናሌ የሚባል የጥሬ ደመወዝን አዘራዘር ለመመልከት ብንመለስ የሠራተኞችን ክፍል ሁሉ በሬያሉ የሚባል ደመወዝ እንደተጠመደ እናያለን፥ማፍራት ስታድግና ስትሻሻል የኖሚናሊ ደመወዝ ሳያድጉ የሬያሌ ደመወዝ ያድጋሉ ። ስለዚህ መጀመሪያ ባለ ዕድል የእጅ ሠራተኛ ይሆናል ።

ደመወዝ ሠራተኞች ሥራ ስለ ሠሩ የሚያገኙት ውለታ ነው እንጂ ሌላ አይደለም ብለናል ። የሚከፈሉት ጊዜም ዋኖችና ሠራተኞች ተዋውለው እንደተስማሙት በቀን ወይም በስምንት፥ወይም በወር፥ ወይም በመንፈቅ፥ወይም በዓመት፥እየ-

ሆን ነው።ደመወዝ ከተፈራው አንድ ክፍል ማለት ከመሬት ከፒታል ሥራ እንደሆን የታወቀ ነው። ግን ለሠራተኞቹ የሚሰጥ ደመወዝ ተሠርቶ ከተፈራው ዓይነት ክፍል ማለት ፡ ልብስ ፣ ወይ ጫማ፡ወይ ስሐን ፥ ወይ ጠረጴዛ ፤ወይ አውቶሞቢል የመሰለ ሁሉ ከእቃው አንድ ክፍል የሚሰጥ ቢሆን ለሕይወቱ መያዣ ለምግብ ልብስ ስፍራው ቤት የመሰለ ለፍለጋው መጀመርያ ሁሉ በቶሎ ለማግኘት የግድ ይሆንዋልና ከዋጋው ጉድሎ ዝቅ አድርጎ በርካሽ ለመሸጥ በተገደደና በተጐዳ ነበር ። አንድ አንዱም ጭርሱን ገዢ ባያገኝ በችግር ወድቆ በቀረ ነበር።ግን ደመወዙ በብር (ምኔታ) ስለ ሆነለት ለሕይወቱ የሚያስፈልገውን የሆነ ነገር ሁሉ በፍጥነት ስለሚያገኝ በደኅና አኑዋዋር እየኖረ ሥራውን በወደጌት ይገፋል። ብር መወደዱ ሊበላ ፡ ወይም ሊጠጣ ፡ ወይም ሊለበስ የሚቻል ሁኖ አይደለም። በፊት እንዳመለከትነው የሰው ፍለጋ ብዙ ነውና የሥራውን ልውጫ በብር ምግብ፡መጠጥ፡ ልብስ፡ ስፍራ፡ቤት፡ እቃ፡ የሥልጣኔ ትምህርት፥ ጨዋታ፡የመሰለ ሁሉ ሊያገኝ የሚችል ስለ ሆነ ነው እንጂ ።

ግን ከሠራተኞቹ በብዛት ቊጥራቸው የሚበልጥ በአንጐል እውቀታቸው የሚያንስ የሆኑ ሁሉ ደመወዛቸው ቢበዛላቸው ሀብታሞች ለመሆን እንደሚችሉ ያምናሉ።ግን ይህ ባህል ሁሉ እውነት አይሆንም አስረጅ) ከትልቁ ጦርነት በፊት ጥቂት ደመወዝ የወሰዱ የነበሩና አሁን ብዙ ደመወዝ የሚወስዱ ሀብታቸው (ኑሮዋቸው) አንድ ትክክል ነው ። ስለምን ከጦርነት በፊት ለፍለጋቸው የሚሆን ሁሉ ርካሽ ስለ ነበረ ፡ ዛሬ ግን ሁሉ ውድ ስለ ሆን ነው ። ምሳሌ) በፊት ዘመን በከተማችን አዲስ አበባ አንድ ሠራተኛ ሰው ፲፫ ብር የወር ደመወዝ ቢያገኝ ፡ አንድ ኩንታል እህል በሁለት ብር፡ አንድ ጫማ በግ በሁለት ብር፡ ክራይ ቤት አምስት ብር፡ ልብስ አምስት ብር፥ ገረድ አንድ ብር ለመግዛት ይችል ነበር ። ዛሬ ደግሞ ደመወዙ ዕጥፍ፡ ሁኖ ፴ ብር በወር ቢያገኝ ፡ ግን አንድ ኩንታል እህል አራት ብር፡ አንድ ጫማ በግ አራት፡ ብር ክራይ ቤት ዓሥር ብር ፤ ልብስ ዓሥር፡ ብር ፡ ገረድ ሁለት ብር በፈጀበት (ለስሙ ነው እንጂ) ያው ነው ፡ ከፊተኛው ሀብቱ (ጥቅሙ) አልጨመረ ወይም አልጐደለም እንደ ማለት ነው ። ስለዚህ ሀብትን የሚያሳድጋት ሥራን ማሠልጠንና ማስፋት ነው እንጂ ደመወዝ ማብዛት እንዳልሆነ አለጥርጥር ሕሊናችን ተረድቶት ልናምን ይገባናል። ማለት ሸቀጥን ሁሉ በትንሽና ቀላል ሥራ በብዙ የተፈሩ እንደሆኑ በዝቅተኛ ርካሽ ዋጋ ይሸጣሉ ። እንድ አንድ የዋህ ቂል ቢጤ መሳይ ሰው አንድ አንድ ጊዜ ነጋዴ ሸቀጡን ዋጋው ከፍ አድርጎ ይሸጣልና ብዙ የሚከስብ ይመስለዋል እንጂ ፥ ጨራሾቹን (ገዢዎችን) እቃው ሲወደድ አይቶው መግዛታቸውን ወዲያው እንደሚወስኑ እና ነጋዴውን ዕቃው ስለ አስወደደው የሚገዛለት አጥቶ በጭንቅ በአንገቱ እንደ ሚያዝ በሁለተኛው ዓይኑን አይመለከትም።ግን ሸቀጥን ዋጋቸው ርካሽ ሲሆን ጨራሾች በብዙ ርካሽ ዋጋ ስለገዙ ነጋዴዎች በብዙ ስለሸጡ ፥ ጥቅሙን ለሁሉ ለገዢዎች ይሁን ሻጮቹ ጥሮፖርጺዮን ሁኖ ይከፋፈላል ።

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ይከተላል። ሚካኤል ተሰማ።

አንድነት ኃይል ይሰጣል ።

ሰው ብቻውን ከመጀመሯ በውቀቱ ችግርን (ኑሮውን) ሁሉ አላሸነፈም እርስ በርሱ እየተጋገዘ ነው እንጂ ።

ከብዙ ዘመን በፊት አንድ ታላቅ ናዳ አንድ ሰውዬ የሚኖርበትን ከብርድና ከዝናም የሚድንበትን ዋሻ በራፉን ዘግቶበት ነበር እየተባለ ይተረካል። ሰውዬውም ከዋለበት ተመልሶ ለመግባት ቢሞክር ታላቁን ድንጋይ ለማንሣት አቃተው። ደግሞም እንደዚሁ ሌላ አንድ ሰው በዚያ በኩል ሲያልፍ ለማንሣት ቢቃጣ የማይችለው ሆነ። ከዚያ በኋላ ተጠረቃቀመው በዙና አንድ ሽሕ ሆኑ። በዚያን ጊዜ አንዱ ከመሐከላቸው በራሱ አንድ ሐሳብ ብልጭ አለበትና ተነሡ እንድ ጋር እንሰብሰብ ያለንንም ኃይል በድንጋው ላይ እንጣል አለ።የቀሩትም የሱን ሐሳብ ተከትለው ድንጋውን ባላቸው ዓቅም ያዙና አንሥተው ጣሉት መግቢያው ነጻ ሆነ።አሁንም ይህ ተረት ይመስላል እንጂ አንድነት በመሆን ብዙ መከራና ጭንቅ ችግርና ጠላት ይሸናፋል ስለዚህ ሰው ሁሉ በመተጋገዙ አያሌ የሚያስደንቅ ሥራ ሠራ ።

መሸሸል

ሰው እንደተወለደ ድንግል የነበረችው መሬት ካሁኑ ዓይነቷ በጣም አትማሰልም ነበር ። ፍሬያሟ ምድር ዛሬ እህል የምታበቅለው በታላቅ ደን የፀሐይ ጨረር ለማግባት በሚከለክል ተሸፍና ነበር ። ከየዛፉም ተቀጥላ ሁሉ መጀመሯ ምግብ የነበሩት ፍሬዎች ተንገርግገውባት ነበር ። በነዚህም ዛፎች ጥላ ውሥጥ በያይነቱ እባቦች ተደብቀውበት ነበር ፍሬውንም ለመልቀም አደጋ ይገኛል በማለት በጣም ችግር ነበር ። ብዙ አውሬዎችም መንጋ እየሆኑ በደኑ ይሰመሩ ነበር። እልፍ እልፍ ሲሉ በየበታው በሽታ ያለባቸው ዡሬዎች ይገኙ ነበር ።በየስፍራውም ሁሉ ሊሔዱባቸው የማይቻል ብዙ ተራራዎች የወኃ ፏፏቴዎችና ገደሎች ነበሩ ። በዚያን ጊዜ ዕራቊታሙና ደካማው ሰው ያለ እጆቹ ሌላ መሣርያ የሚድንበት የሌለው እነዚህን የሚያስፈሩ አደጋና ጭንቅ ለማምለጥ እንደ አዕዋፎች ለመብረሯ ክንፎች እንዳንበሳ ጥርስና ጥፍር እንደዝሆንም ኮምቢ የለው ነበር። ይሁን እንጂ በዝባታ የጊዜውንመ ጨከን የሚያስቸግረውን መሬት አውሬዎችንም አሸነፈ ። የመጀሯ መኖሪያውም ዋሾች ነበሩ ። መሣሯዎቹም ድንጋዮች ። በነዚህም ጦሮች ቀስቶች ቢላዎች መጥረቢዎች ሠራ። መጀመሯ የሚለብሰው ልብሱ የገደላቸውን የአውሬቆዳ ነበር ። አንድ ቀን ሁለት ድንጋዮች አማቃና እሳትን አወጣ ይኸውም ለመሞቂያው ፥ ፋሾቹን ለማብራት ፥ የሚበላውን ሥጋ መቀቀያ ከመቀመጫው አውሬዎችን ማባረሯ ሆነለት።ዳግም የዛፍግንድ እየቈረጠ ፈልፍሎ እንደ ጀልባ ዓይነት እየሠራ ወኃን ለመሻገር ቻለ። የመጀመሯ ጐጆዎቹንም ከጠላቶቹ ከአውሬዎች ለመጠበቅ ሲል በየወንዙ ዳር ዳር ሠራ ። እንደዚሁም አጠንክሮ መሬት ሲቈፍር ብረትን አገኘ እንደምን ዓይነትም እንደሚሠራው ተመልክቶ የመጀመሯ የሚጠቀሙትን መሣሯዎች አበጀ። ሰው አዳኝ፡እሣ ወጋሪ ከሆነ በኋላ ገበሬ ሆነ ። በርሻውም አጠገብ ለራሱና ለልጆቹ ጐጆች ሠራ ። ጐጆቹ በዝተው መንደር

ሆኑ መንደሮቹም ሰፈር፥ሰፈሮቹም፥ከተማ አውራዎቹም ለመዱ ። ፈረሶች፥በቅሎች፥ ግመሎች፥ከንዱ ስፍራ ወደ አንዱ ስፍራ ለሰው መመላለሻው ሆኑ ። ደግሞም በሬ ላም ጊደር በግ ፍየል አረብ ሴቶቹ መፍተል ተማሩ በንደዚህ ያለ ጠጕርና ቆዳ ለልብስ ተገኘ ሥጋና ወተትም ለምግብ ። እንደዚሁም እያደር ለሰው ጐጆ አልበቃ ቢለው ቤትና አዳራሽ ሠራ።የእንስሳ ቆዳ ለልብስ ባይመቸው የሚሞቅና የሚለሰልስ ልብስ ሠራ ። ፈላሽ ውኃ-ዎችን አገዶ ምንጮችን ወደ መኖሪው አቀረበ።ወንዞችን መስኖ አገባ፥ ብዙ ቍጥር የሌለው ፍሬ ዘርቶ አበቀለ፥ከየተራራውም ላይ ታላላቅ ዛፍ እየቈረጠ መርከብ ሠርቶ ባሕሮችን ተሻገረ፥ ከንዱ አገር ወደ አንዱ አገር ያለ ድካም እንዲያመላልሰው የመሬት ባቡርን ሠራ። ሐሳቡን በየገሩ በፍጥነት እንዲያደርስለት ፈልጎ ኤሌትሪክን ሠራ ። ይህንኑም ደግሞ በሌሊት እንደ ቀን እንዲያበራና ማናቸውንም መኪና እንዲያስነሣ አደረገው ። እንደ ወፎች ለመብረር ቢያምረው የአየር ባቡርን ሠርቶ በሰማይ ያንዣብብ ጀመር ። ስለዚህ ወንድሞቻ ሆይ ሁላችንም እላይ የተባለውን ነገር ከልባችን እያስታወስን እርስ በርሳችን ብንፋቀር ያለማቋረጥ እየተሻሻልን እንሔዳለን።ጠላቶቻችንንም እናስፈራለን ያለበለዚያ ሁሉም ከንቱ ነው ። ሰላምን ዘወትር መለያየት ለጠላት ተስፋና ጥቅም ነው ። አበበ በላቸው ።

እግዚአብሔር በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ያስተዳድርን ሥራትና የአምላክነቱን ነገር ለመረዳት ስነ ፍጥረቱን የዕውቀት መሪ ፥ የሥርዓት አስተማሪ አድርጎ እንደ ሰጠን ።

እግዚአብሔር በያይነቱ በየወገኑ አድርጎ ፍጥረቱን ሁሉ ሲፈጥር አንዱን ፍጥረቱን ላንደኛው ፍጥረቱ ማስረጃና ምሳሌ እያደረገ ፈጠረ ።

መጀመሪያ ራሳችን ለራሳችን ሕግ ሁኖ የዚህን ዓለም አስ ተዳደርና እግዚአብሔርን የምናምንበትን መንገድ ይመራናል። ቁመተ አካላታችን እንደ ሙቀጫ ተድበልብሎ ፥ እንደ ሸንበቆ መለል ብሎ፥ዕዝል ቅጽል እንደሌላት እንደ ዓሣርቱ ሁኖ እን ዳይቀር አእጹቅ በቅጠላቸውና በጽጌያቸው ማማር ደስ እንዲ- ያሰኙ እኛንም እንደ ሸንበቆ መለል ብሎ በወጣው አካላችን ላይ የፈጠረው አንደኛው ሕዋስ ዓይን ይባላል ።

ከርሱም የምናገኘው ጥቅም ብዙ ነው ። ከብዙውም ሁለ ቱን ያህል በሚከተለው መስመር እንጽፋለን ። ገደል ወድቀን፥ ባሕር ጠልቀን እንዳንሞት ። እሾህ እንዳይወጋን እንቅፋት እን ይመታን፥ ሥራችንም ሁሉ የተከናወነና ብርሃን እንዲሆን፥ ሁለ ተኛምው ጥቅም ፤ አገሌ ዓይናማ ነው ተብሎ የመወደድ ጌጽ እንዲያገኝበት በልሙጽ ግምባር ላይ ዓይንን ፈጠረ ። ይህም ይህን ያህል ጥቅም የምናገኝበት ዓይን አምላክነትህን መርምሮ ለመረዳ ሕግ ሁኖልናልና የዘላለም አምላክ ለምትሆን ላንተ ብቻ ምስጋና ይገባል እያልን ሀሳባችን በፍቅሩ የተወሰነ ይሆ- ናል ። የዓይናችንም ሕግነት የምድራዊ ንጉሥን ሥራት ይሰ- ብክልናል ። ዓይን ማንኛውም የደዌ ዓይነት መጋራጃ ሁኖ ቢሸ ፍነው በሰውዮው ከፊቱ ላይ የነበረው ብርሃን የጨለማ ምርት ይሆንበታል ። ሜዳው ገደል ፥ ገደሉ ሜዳ ፥ እህሉ አፈር ፥ ብሩ ጠጠር ፥ እንጀራው ቅጠል ፥ ይመስለዋል ። ነገር ግን የደዌው መጋረጃ የተገለጸ እንደሆነ ጭለማ ይርቅለታል ። እንዲሁም ንጉሥ የሀገር ብርሃን፥ የሕዝብ ፀሐይ ነው ።ከዚህ መካከል እ- ንድ-ዘንፉቅ ልቡ ከደዌ የባሰ ምቀኝነት ወይም ሀገር ዕረፍት የምታገኝበትን ሐሳብ የዓመፅ ሣጥን ከሚሆን ከልቡናው ቢያ ፈልቅ ፥ አምላክ ለአምላክነቱ ፥ ንጉሥ ለመንግሥቱ ቀናኢ ነውና ፥ በዚህ ምክንያት የታመኑ አሽከሮቹን ሒዱችሁ አገሌን እጁን ይዛችሁ አምጡልኝ ብሎ ያዘዘውን ትእዛዝ በደስታ መቀበል የሀገር ብርሃን ፥ አለመቀበል የሀገር ጨለማ እንደሆነ የዚህ መምራችንና ሕጋችን ዓይን ነው ። ሁለተኛም ጥቅም በመሆን ዓይን የአካል ጌጽ እንደሆነ ንጉሥም የሀገር ጌጽ ነውና ። ፪ኛ ፤ በአፍንጫችን በጎ በጎውን መዓዛ ከክፉው ለይ- ተን ስለማወቃችን ፥ ደግሞም የፊታችን አማራረዱ በአፍ- ንጫ ምክንያት የመወደድ ቅርጽ ስለማግኘቱ የእግዚአብሔር ያምላክነቱን ዕፁብ ድንቅነት መርምሮ ለመረዳ አፍንጫ መም ህርና ሕግ ሁኖ ሃይማኖትን ይሰብክልናል ።

ይልቁንም ክፉ መዓዛ ወደውስጣችን ገብቶ ሰውነታችንን እንዳያናውጽ እስትንፋስ ክፉ ክፉውን መዓዛ ወደውጭ እያ- ስወጣ በጎ በጎውን መዓዛ ወደውስጥ እያስገባ ላፍንጫ ማገ- ልገል ግዴታ እንዳለበት ፥ ንጉሡም ያዘዘውን ሁሉ ትእዛዝ መፈጸም ለሕዝቡ ሁሉ እንዲገባ አፍንጫ እንደ ንጉሥ እስ- ትንፋስ እንደ ሕዝብ መሆኑን ስነ ፍጥረታችን ይሰብክልናል። ፫ኛ፤ በአፋችን የጣፈጡትን የምግብ ዓይነቶች ሁሉ ስለመመ- ገባችን ፥ ደግሞም የፊታችን ቅርጹ እንደ ዕንቍላል ድፍን ሁኖ ጕልቻ መስሎ እንዳይቀር ጌጽ የሚሆነው መስኮት ያለው ሕ- ዋስ ስለማግኘታችን የእግዚአብሔርን ጌትነት ማድነቅ አፍ አስተማሪነትን ገንዘብ አድርጓል ። እንዲሁም የጣፈጠ የጣፈ- ጠው ምግብ እያቀረበ ጣዕም የሌለውን እያንጓለለ የሚያስቀር ታዛዥ የሚሆን መላስ በመናቸውም በምግብ ሥራ ሁሉ ፈቃ- ዱን እንዲፈጽምለት፥ ለንጉሥም ደስ የሚያሰኘውን ሥራ ሁሉ እየሠሩ መኖር እንዲገባ አፍ እንደ ንጉሥ መላስ እንደ ሕዝብ መሆኑን ከአካላችን መምህርነት ስብከትን እንሰማለን። ፬ኛ በጆሮ- ችን ከዕሩቅ የተወረወረውን ከቅርብ በለኆሳስ ከተነገረውን ቋንቋ ሁሉ ስለመስማታችን፥ደግሞ ምንም ጆሮ ቀርፈፍ ያለ ስነ ፍጥረት ቢሆን እንደመጠኑ የአካል ጌጽ መሆን አይቀርበትምና ለአካላችን ጌጽ ስለመሆኑ የእግዚአብሔርን ቸርነት ዕፁብ ድንቅ ብሎ ማድነቅ እንዲገባ ጆሮ ሕግ ሁኖ ያስረዳናል ። እንደዚሁም ጆሮ የሰማውን ነገር ሁሉ ለመርማሪ ልቡና እያቀበለ እንዲያ- ገለግል ለንጉሥም በማናቸውም ነገር ማገልገል እንዲገባ ጆሮ ሕጓን ይወስንልናል ።

፭ኛ፥ በእግራችን ሒደን በእጃችን ጨብጠን ማናቸውንም ጕዳይ ስለማድረጋችን ። ደግሞም የአካላችን አቋቋም ጕንድሽ ሁኖ ወዲያ ወዲህ መላወስ እንዳይቸግረን እንደመኪና የሚላ- ወሱ እግሮችና ሥራ የሚሠሩ እጆች በለሰጠን የእግእብሔር የጥበቡ ምላት ስፋት ምን ይረቅ ምን ይጠልቅ እያሉ ማድነቅ እንዲገባ እጅና እግር ሊያስረዱን ይችላሉ። እግር እየሔደ እጅ እየሠራ ለሕይወታችን ታዛዦች እንደሆኑ እንዲሁም ሕይወት

እንደ ንጉሥ ሕጅና እግር እንደ ሕዝብ መሆናቸውን የአካላታ-ቸን ቅርጽ በሥራው መምህር ሁኖ ይሰብክልናል። የሽ ፍልጥ ማማሪያው አንድ ልጥ እንዲሉ ፤ የነዚህ ሁሉ ንጉሣቸው ልብ ነው ። ልብ አስተዋይና ልዩ ልዩ ዕውቀትን መርማሪ ነው ። በልቦችን ማናችውንም የዕውቀት ረገድ መርምረን የምንረዳ ስለሆነ እንዲህ ያለ አስተዋይ አካል የፈጠረ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደ ገባ እሱው ራሱ ልቡና ሕግና መምህር ነው። ልብ ማናቸውንም ነገር አስቦ እግርን ወዲያ ሒድ ወዲህም ቀመ ለስ እጅንም ይህን አንሣ ይህንም ጣል።ዓይንንም ይህን እይ፤ ያንንም አትይ ። አፍንም ይህን ብላ ይህንንም አትብላ። አፍ-ንጫንም ይህን አታሽት ያንንም አታሽት።ጆሮንም ይህን ስማ ያንንም ለትስማ ብሎ ጽኑ ሥራቱን በወሰነባቸው ጊዜ በነዚህ ሁሉ ትእዛዙን ለመፈጸም ግዴታ ይሆንባቸዋል ። እንዲሁም ከሥልጣኑ በቃች ያሉት ሠራዊት ሁሉ የንጉሥን ትእዛዝ በፍ-ጥነት መቀበል እንዲገባቸው ልብ ተርጓሚ የቀሩት ሕዋሳት እንባብያን ሁነው ሥርዓተ መንግሥትንና የአምላክነቱን ቸርነት ይሰብኩልናል ። እነዚህ ሁሉ የተቈጠሩ በአካላችን ያሉ የሰነፍ ጥረት መምሮች በየሥራቸው ጸንተው ለልብ ታዛ-ዦች ሁነው ይኖራሉ እንጂ ፤ ዓይን አላይም ጆሮ አልሰማም አፍ አላላምጥም ፤ አፍንጫ አላሸትም እግር አልሔድም እጅ አልጨብጥም የማለት ሩክክር የለባቸውም ። ደግሞም ዓይን እኔ እንደመስታወት እያብለጨለጭሁ እንዳጥቢያ ኮከብ እያቍ-ለጨለጭሁ ስለምን ነው ጆሮ አለመሆኔ አትልም።ጆሮም እኔ እንደ ጋሻ ቀርፋፋ ሁኜ ነፋስ ሲቀፈቅፈኝ ስለምን ነው ዓይን አለመሆኔ አትልም ። አፍም እኔ ክፍት ሁኜ ክፍታፍ እየተ-ባልሁ ስሰደብ መኖሬ ስለ ምን ነው ብላ ከሌሎቹ ሕዋሳት እንዳንዱ ልሁን አትልም።እጅም እኔ እንጀራ ቈራሽ ወጥ ጠቃሽ መሆኔ ስለምን ነው ብላ ከሌሎቹ ሕዋሳት እንዳንዱ ልሁን አትልም።እግርም እኔ እንቅፋት ሲመታኝ እሾህ ሲወጋኝ ውርጭ ሲያንቃቃኝ ዘወትር መከረኛ መሆኔ ስለምን ነው ብላ ከሌሎቹ ሕዋሳት እንዳንዱ ልሁን አትልም ።

እያዚሁም ሁሉ እነዚህን ስነ ፍጥረቶች መምሮች አድርጎ ሕዝቡም እንደሕብነቱ አራሹም እንደ አራሽነቱ ሻለቃውም እንደ ሻለቃነቱ ካህኑም እንደካህንነቱ ከዚህም ሌላ ማንም ሥራ ያለው ሁሉ እንደሠራተኛነቱ በየሥራው ጸንቶ ለንጉሥ ታዛገር ሁኖ መኖር እንዲገባ የሚያስተምሩን መምሮቻችን ከእ-ግር ጥፍራችን እስከራስ ጠጕራችን ያሉ ሕዋሳታችን መሆናቸ-ውን በዚህ እንረዳው ።

ኛ፤ ከተፈጥሮአችን ልዩ የሚሆኑ ተንቀሳቃሾችም ለእኛ ምሳሌዎች ሊሆኑ ይቻላቸዋል ። ምሳሌነታቸውንም ባንደኛው ተንቀሳቃሽ እናስረዳለን።ንብ አውራውን አክባሪ ነው።ከሰፈረበት ክበ ይሰፍራል ። ከዘመተበትም ይዘምታል አውራውን አክብሮ ይኖራል ። ይህ ተንቀሳቃሽ በኢነባቢ ተፍጥሮው ይህን ያህል የተገባ ሥራት ሲሠራና ሕግ ሲያቆም በማናቸውም ሁሉ ከርሱ የምንበልጥ እኛማ የርሱን ያህል ሥራት ማስተካ-ከልና ሕግ ማጽናት እንዴት ይጐድልብን ? ደግሞም ይህችው ታሪከኛ ተንቀሳቃሽ ያለዕረፍት ከየትም እየዞረች ከእየዛፉና ከየታክልቱ አበባ እየቀሰመች እያመጣች እየሠራች የደከመችበ-ትን ከእርሱ በላይ ሌላ ጣዕም የሌለ መዓር የሚባል ገንዘቧን ለመ ውሰድ ማንም ሆነ ከቀፎዋ አጠገብ ጠጋ ያለእንደሆነ በተፍጥሮ በገኘችው ከአካሏ ላይ ባለው በጦር መሣሪዋ እያባረረች ትነ-ድፈዋለች። ይህንም ማድረጓ ገንዘቧን ለመጠበቅና ቦታዋን ለማ-ፈር፤አውራዋንም ለማስከበር ስትል ነው። ይልቁንም የሚያስ-ደንቀው ነገር ምክር ሳይመክሩ ዱለት ሳይዶልቱ አንድነታቸውን አፅንተው፤አጀባቸውን አሳምረው ላውራቸው ቃል ታዝዘው መኖራቸው በነዚህ ምክንያት እግዚአብሔርን ማመስገን እን-ደ ገባና እነሱን አይቶ ተመልክቶ የንጉሥን ትእዛዝ መፈጸምና ለንጉሥ ሥልጣን መገዛት እንዲገባ ከነሱ ጉባኤ የሚጠቅመውን የሕዝብና የንጉሥን አስተዳደር መማር አእምሮ ላለው ሰው የሚያስፈልግ ይመስላል ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

ስለ አስተማህሪነት ሥራ

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ። ቀድሞ የኢትዮጵያ ተማሪ እየቀፈፈ ጥሬ በልቶ ደበሎ ለብሶ በችግር መከራውን ታግሦ የጠነከረ ሰው ብቻ ይማር ነበር እንጂ ለተማሪና ላስ-ተማሪ የሚያስብላቸው አልነበረም።በዚህም ምክንያት የተማረው ሰው በልክ ስለ ሆነ በሀገራቸው እውቀት እንዲሰፋ ሕዝባቸውም ሁሉ በትምህርት እንዲሠለጥን ሕፃናቱም ከባት ከናታቸው ቤት ሳወይጡ ያለችግር እንዲማሩ ብለው በገዛ ርኅራኄያቸው አስበው በጨርጨር አውራጃ በየመቅደሱ ላአስተማሪ የብር ቀለብ ስላቆሙልን የነባብ ፥ የዜማ ፥ የቅኔ ፥ አስተማሪ የሆነሰው ሐረር በጨርጨር ክፍል የደብረ ወገግ መምህር ገብረ አብን ጠይቆ ባስተማሪነት ደንብ ለመግባት ይችላል ። መምህር ገብረ አብ።

ስለ ሀገር ፍቅር ስለ መሣሪያና ስለ ጀግኖች ጥንቃቄ ማሳሰቢያ ።

የውጭ አገር ሰዎች በሀገራቸው ስለ ወታደር ጥንቃቄ ብዙ የሥልጣኔ ትምህርት እንደሚአደርጉለት ለመጻፍ እን-ሞክራለን።አስቀድሞ የወታደርን ደንብና ማስጠንቀቅ የወታደሩ ሹም መሳሪያቸውን በየጊዜው እያስወለወላቸው ሊአስጠነቅቃ-ቸውም የጥይታቸውንም አኳኋን ማለፊያና መጥፎ ማለት (ክልስ) ከዝናራቸው እንዳይገኝ በጣም ሊአስገድዳቸው ይገ-ባዋል ። እንዲሁም ከአንድ ወር ወይንም ከሁለት ወር በኋላ የጥይት ችግር ቢሆንበት ስንኳን ከሁለት እስከ አምስት የሚሆን ጥይት ለአንድ ወታደር ፍቃድ እያደረገ ይላማ ተኵስ መፈተንና መሞከር ማስተማር በሰላም ጊዜም ቢሆን ተሰናድቶ እንዲቀመጥ የሚአሳስብ ነው።ይህም እንደሚአስፈልግ በአው-ሮፓ የሚገኙ ወታደሮች በየጊዜው የይላማ ትምህርት ይደ-ረግላቸዋል። ቈይተውም በኋላ የተኵስ (ኤግዘመን) ፈተና ይደረጋል። ከዚሁም በፈተና ብዙ ጊዜ እየደጋገመ ተሞክሮ ተኵሱ የበለጠ ወታደር መጀመሪያና ተከታይ እየተደረገ ከወርቅ እስከ ብር እንደ ኒሻን ዓይነት ምልክት ከቆቡ ላይ ተደርጎለት ገንዘብም ጭምር ሌላም በያይነቱ ስለተኵሱ ማዕርግ ይሰጣል ።

ይህች ክቶቡ ላይ የምትደረግ ሽልማቱ ግን ምንም ቢሆን ክቶቡ ላይ አትለይምና ወንበዴ አውሬ ወይንም የድንገተኛ ነገር በሩቅ የታየ እንደሆን ከዚህ ከማዕረገኛ ወታደር ብስተቀር ማንም ሊተኵስ አይችልም።ያው ማዕረገኛው ወታደር እገሌ ናተብሎ ፍቃድ ይሰጠውና ተኵሶ ይጥላል ይህም መደረጉ ያ የድንገተኛ ነገር ማንም ተኵሶ የማያውቅ ተኵሶ እንዳይስት መሆኑን መመልከት ያስፈልጋል።እንደዚሁ ሁሉ ማድረግ የተገባ ነው። ስለጥይትና ስለመሳሪያ ዳግመኛ መጠንቀቅ ከሁሉ ይልቅ ይበልጥ የሚአሳስብ ነው።አንድ የድንገት ወይንም የጦር ነገር የተገኘ እንደሆነ ጠመንጃው በመልከም ሳይወለወል ከጠላቶቹ ጋር ሲገጥም ከአንድ ሁለት ሲተኵስ ከለመጠረጉ ምክንያት ለመከፈትና ለመዝጋት ብዙ ችግር እየሆነበት ያስቸግረዋልና እንዲሁ ከመልካሙ ጠመንጃ ያልሆነ ጥይት ቢአገቡበት አይተኰስም ቢተኰስም ሊገዳ አይችልም ። መልካሙ ጀግና በንደዚህ ያለ ሥራ ሐሳቡ አይከናወንለትም ለደዚህ ያለ ሁሉ ማሰብና መሳሪያን መወልወል፡ጥይትን መምረጥ መጠንቀቅ የሚያስፈልግ ነው ።

ስለ ሀገር ፍቅር ።

የሀገር ፍቅር በአፍ ብቻ አይበቃም ከልብ ጭምር ነው ሀገራቸውን የሚወዱ ያለፉትን አርበኞች ያገኙትን ገናና ስም ከሕይወታቸው በኋላ መመልከትና ማሰብ ነው ።

የሀገር ፍቅር በሰውነታቸው የተገዛ የገናናው የአፄ ቴዎድሮስን ውለታ በልባችን እየመዘንላቸው ሐውልት እንዲሠራላቸው የማይመኝ የለም ብሎ አቶ መክብብ ደስታ ባለፈው ሳምንት ያስታወቀን እውነትም ብልህ አስታዋሽ የሆነ ኢትዮጵያዊ የሳቸው ስም ሕይወት ከሕይወት ሚሊዮን ጊዜ የበለጠ ስማቸው ሕይወት እየጨመረች እንደምትሔድ ጥርጥር የለውም።

አፄ ቴዎድሮስ እንዳንድ (ዲፕሎማቲክ) ሰው ነበሩ አሳባቸው ሁሉ የታላቁ ሥልጣኔ መንገድ ነበርና ሕዝቡንና የሀገሩን አስተዳደር በሥልጣኔ መንገድ ልምራህ ቢሉት መቸም ያልሠለጠነ ሕዝብ ጥቅሙን የማያውቅ የመንፈቅ ሕፃን ልጅ ይመስላልና ሐሳባቸውን አልተቀበላቸውም ነበር፡እንዲሁም የሚገዙት አገር በየወረዳው እየሸፈተ ያውከቸው ነበርና ቢያቀትትም እንደገና እየሸፈተ ስላስቸገራቸው በብስጭት ብዙ ልዩ ልዩ ቅጣት ስላደረጉ ብዙ የተለየ ስም ሰጧቸው።መቸም ምንም ሥልጣኔ ቢኖራቸው ከላይ እንደጻፍነው እረዳት ደጋፊ ተከታይ አላገኙም። የሚያደርጉትና የሚያስቡት ሁሉ በአብደት ተቈጠረባቸው።መቸም በዚህ ዓለም ከመቶ ሽፍታ ሙሥጥ አንድ ይቅርና ዓሥሩ በነሱ ውሥጥ ተደባልቀው መልካም ነገር ቢያሰቡ እነዚህ ሰዎች ሽፍቶች ናቸው ይባላል።እንዲሁም በሥራ ላይ ወይንም ባንድ ነገር ላይ የበዙት ሌቦች ሁነው ጥቂቶች ደኅኖች ቢሆኑ እነዚያ ሌቦቹ ደኅኖቹን ሌቦች ብለው ይሰድቧቸዋል ። እንዲሁም ሥልጣኔ የማይወዱ ሰዎች ያነን የሥልጣኔ መንገድ ሊአሰፉ የተነሣውን ሰው አገራችንን ሊአጠፉ ያልሆነ ነገር ሊተክልብን ብለው ያልሆነ ስም ይሰጡታል። እነሱ የሀገር ጠላት ሆነው ያ የሀገርን ጥቅምና መንገድ ሊአሰፋ የተነሣ ሀገሩን ወዳጅ የሀገር ጠላት ነው ብለው ይስድቡታል።በኋላ ግን እንዳሁኑ የሥልጣኔ ጮራ ብርሃኑን ሲሰድ እንደገናናው አፄ ቴዎድሮስ ስም ይተከላል ።

— ምንግዜም እንኳን ባልሠለጠነ ሕዝብ ይቅርና በሠለጠነ ሕዝብም ቢሆን ደንብና የበለጠውን የሥልጣኔ ነገር እተክላለሁ ሲል ብዙ መከራና ስቃይ መቀበሉ የታወቀ ነው። ያሰበውንም ባይፈጽመው ከመቶው አምስቱ ሳይሆንለት አይቀርም እንዲሁ ለስሙ መጠሪ ለሀገሩ ማክበሪ ለማዕረጉ ማኵሪ ይሆንለታል። የሀገርን ፍቅር ሲፈልጉ ሀሜትን ይሉኝልን አስወግዶ በሐሳቡ መግፋት ነው። ዳግመኛም የኢትዮጵያ ጀግኖች ወንዱም ሴቱም ልጁም ምንም ለሥልጣኔ ባይቸኵል በሀገር ፍቅር እንደሚቃጠል ከታሪክም እደተመለከትነው የኢትዮጵያ ጀግና የጦር ጊዜ እንኳን ባይሆን በሰልፍ ቀን ከጌታው ፊት የማዕረግ ልብሱን ይለብስና ከደነደነ ፈረሱ ይቀመጥና ጥንድ ጦሩን ይይዝና ጋሻውን ያነግብና ጠመንጃውን ከትከሻው ያነግትና ጐራዴውን ይመዝና (ዘራፍ ዘራፍ) እኔ አሽከርህ ከፊትህ ነው የምሞት እያለ ፉከራውን ሲደቀድቅ ለጌታው የሚያኰራ ለተመለከተው ልብ የሚመስጥ ነው ።

እንደሮከረውም ከጦርነቱ ውስጥ የመንግሥት ባሯያ እውነተኛ ሀገሩን ወዳጅ እያለ ከጠላቱ ደርሶ በጠመንጃ መቶ አንገቱን በጐራዴ ነጥቶ እየተገማለለ ተመልሶ ለጌታው ስለሀገሬ ሕይወቴን የምሰጥላት እኔ አሽከርህ እያለ ፉከራውን ሲደቀድቅ ከደስታው የተነሳ ሰውነቱ ይሰወራል (እውነቱ ነው)ይበል ይሮከር ይኵራ ከሁሉ የበለጠች ሀገርን መውደድና ማሳፈር እኔ ሳለሁ ምን ልትሆን ማለት ነው ሴቷም እንደዚሁ አርበኛ ባሏ ወንድሟ ዘመዷ ቢሆን ወደዘመቻ ሒዶ የኔ ባል ይገላል ይማርካል ደስ ብሎት ደስ ይለኛል ከመንግሥቱ ማዕርግና ሽልማት ያገኛል እያለች በመጓጓት ተስፋዋን ትንተራሳለች እንደ ይሞታል ይቈስላል ብላ ልታስብና ልትሰጋ ይቅርና ጥርጣሬ ስንኳን አታደርግም (ትበል ደስይበላት) የጅግና ሚስ፣ አብልጣ ልትኰራ ይገባታል እንደ ምን ባሏ ለሀገሩ አሳፋሪ ነው ስለዚህ ደስታ ሊወርሳት ይገባታል ። ልጁም ቢሆን ከልጅነቱ ጀምሮ መጋለብ መመከት፡መታገል ፡ መሮጥ ፡ የጕብዝና መንገድ ሲመለከት ቈይቶ አባቱ ወደ ዘመቻ ሲሔድ እያገለገለና (በሽለላ በድፍረት) ወደ ጦርነት በድፍረት ሒዶ እየተጋደለ እየማረከ ከባቱ ከወዳጆቹ ጋር በደስታ ይመለሳል።እውነተኛ የሀገር ፍቅር ከጀግናው ሴቱ እስከ ልጁ ድረስ አገርን መውደድ ለሀገር መሞት እንደዚህ ነው።

የሀገር ፍቅር የግድ በጦርነት ብቻ አይወሰንም ከላይ እንደጻፍነው አገርን ማሠልጠን ትክክል መፍረድ መልካም ምክር በጽሕፈት ለሀገሩ ሕዝብ መግለጽ የራስን ጥቅም አለመመልከት እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ነገሮች ሁሉ ማድረግ ነው ምንም ቢለያዩ እንኳን ዙረው ማሰሪአቸው የሀገር ፍቅር ጥቅም ማጽኒያ ማጠበሪ ናቸው። መሮከከር ምን አግኝቼ ለማን ብዬ ይደክመኛል ያመኛል አልሠራም አልሠራም ብሎ ትእዛዝን አለመቀበል አለመስጠትም የሚያደርጉ ማለፊያ አናጢ በሠራው ወንበሮ ተቀምጠው ጠረጴዛ ተመርኵዘው ለነሱ መንገዳቸውና አሳባቸው እንደጠረጴዛው የተስተካከለ እየመሰላቸው ያልሠሙትን ያላዩትን መጥፎ ወሬ እየፈተፈቱ የሀገራቸውን ጕዳት

የማይመለከቱ ያለፈውን የማያስታውሱ የሀገር ፍቅር በፍ ብቻ የበለጠ በጕልሁ (ትሬትር)ሀገራቸውን የማወይዱ ክሐዲዎች ይባላሉ ። ስለሆነ ቢአስቡም ሊገዱም የማይችሉ አመለኞች ይባላሉ። እውነተኛ የሀገር ፍቅር ያለው ከነዚህ አላይ ከተነገሩት ቃሎችአጥብቆ ሊሸሽ ይገባዋል፡ስለሀገር ፍቅር ከብዙውብረጋር የሚነገረው ይህ ይበቃናልና ወደሥራችን ተመልሰን ገበሬም እርሻውን፡ነጋዴም ንግዱን፡ ሠራተኛም ሥራውን እያከናወነ አ-ርበኛም ያለፉትን የአባቶቹን ጀግንነት እንዲሁም ተመልክቶ ትጋትና ብርታቱን ይስጠው በማለትና እንዲሁ በተሰጣቸው ሥራ ሁሉ እነኚህን የመሰሉ ነገሮች እንዲበረቱ ወደ ታላቁ ደረጃ እንዲደርሱ መትጋት ያስፈልጋቸዋል ጀግና ከሆኑ ልጆ-ችሽ ጋር በነጻነትሽና በሐብትሽ፡ በውበትሽ እንደኰራሽ ወደ-ታላቁ ሥልጣኔ ደረጃ ያድርስሽ እያልኩ ነገሬን አሳጥራለሁ ።

ጥሩነህ ከ ።

ስለ ሹመት

የካቲት ፪ ቀን ክቡር ራስ ከበደ የተገባ የማዕርግ ልብስ ለብሰው ደሉባበርን ተሾሙ ።

ክቡርደጃዝማች አስፋው ደምሰው ወለጋ ውስጥ ጕድሩን ተሾሙ።

ክቡር ነጋድራስ ጠና ጋሻው ወሀኒ አዛጋር ተብለው አን-ኮበርን ተሾሙ ።

ክቡር ፊታውራሪ ጐበና ደጃዝማች ተብለው ጋራሙለታን ተሾሙ ።

ክቡር ፊታውራሪ መንገሻ ይልማ ደጃዝማች ተብለው ጊሪና ጕርሱምን ተሾሙ ።

ክቡር ልጅ ይልማ የደጃዝማች ሥዩም ልጅ ፊታውራሪ ተብለው ሸዋ ጊሚራን ተሾሙ ።

ክቡር አቶ ተፈራ ንጉሤ ወለጋ የነጋድራስ ጠና ጋሻው የነበረውን ነጋድራስነት ተሾሙ።

ክቡር ፊታውራሪ ግፋወሰን የይፋትን ምስለኔነት ተሾሙ።

ልጅ ተድላ የደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ልጅ ያባቱን ሰዎች እንደያዘ ቀኛዝማች ተብሎ አንያን ግዛት ተሾመ ።

ልጅ ብርሃነ መስቀል የደጃዝማች ወልደ ሥላሴ ልጅ ባላምባራስ ተብሎ አንያ ውስጥ ግዛት ተሾመ ።

ክቡር በጅሮንድ ተሰማ ባንቲ በግርማዊ ንጉሥ ግምጃ ቤትነትን ተሾሙ ።

ግራዝማች ኃይሌ ብሩ እቃቤትነትን ተሾሙ ።

ግራዝማች ይፍሩ ቀኛዝማች ተብለው የግራዝማች ሥዩም የነበረውን ሻበልነት ተሾሙ ።

ብርሃንና ሰላም አዲስ ሹመት ለተቀበሉ ክቡራን መኳንንት እንኳን ደስ ያላችሁ እያለ ሹመታቸውን እግዚአብሔር እንዲያጸብርላቸው ይመኝላቸዋል።

ያገር ውስጥ ወሬ ።

ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ክቡር ደጃዝማች እምሩ ወደ ተቀ-በሉት ግዛታቸው ወደ ወሎ ደርሰው ደሴ ከተማ ገቡ ።

የወሎ አገር ሰው የክቡር ደጃዝማች እምሩን መምጣት በሰማ ጊዜ በየመንገዱ እየተሰበሰበ ይቀበላቸው ጀመር። ይል-ቁንም ወደ ከተማ ሲቀርቡ መኳንንቱና ሰራዊቱ ሊቃውንቱና ካህናቱ ሴቱና ወንዱ የደሴ ከተማ ሰው ሁሉ በትልቅ ሰልፍና ዓጀብ በእልልታም ተቀበላቸው ። የወሎ ሰው ሁሉ ክቡር ደጃዝማች እምሩ ትክክለኛ ዳኛ የመሆናቸውን ዝና ሰምቶ ነበርና ክቡር ደጃዝማች እምሩ የወሎ ገዢ ስለ ሆኑለት እን-ደትልቅ መታደል ቆጥሮታል የሚል ወሬ ስለሰማን እጅግ ደስ ብሎናል።ክቡር ደጃዝማች እምሩ በሐረር ግዛታቸው አስተዳዳሪነትና ዳኝነት እንደተመሰገኑ በወሎ አገርም የበለጠ እንዲቀናቸውና እንዲመሰገኑ እንመኝላቸዋለን ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚሁ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ጎሀ ጽባሕ	፬ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኀቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር

ቋብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
ቋጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
ቋኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፲ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፲ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ክጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንድር)	፲ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ማጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የእንቀጣጣሽ ማጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩	፲ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፯ ብር ተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፫ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፭ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር ተኩል
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፯ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፪ ብር ተኩል
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይ- ነት የተሰማ እሺ፡ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሰምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጒርጒ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው





አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረን- ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።
ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።
የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።
የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፰
6me ANNÉE №. 8

ሐሙስ የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 20 FEVRIER 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ደረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የ፶ ገጽ ተከታይ ።
የኢኰኖምያ ፖለቲክ ።

የደመወዝ ልዩነት ማደግ ተእምራት ።

ሳላርዮ ሬያሌ የሚባል እውነት የሆነ ደመወዝ ከምን እንዲያዝ ትርጓሜውን ለማወቅ ብንፈልግ፤ እንዲህ ስንል ባሁሉን እናቆማለን ። እሱም ከእርነት ጋራ ጥያቄና የማቅረብ ሕግ ቁመዋል ። በብዙ ልዩ ልዩ ዓይነቶች ሠራቶኞች ብዙ የተለያዩ ደመወዞች አሉ ። እነሱ ሠራተኞቹ ልዩ ልዩ ዓይነት ፍሬ ከሚያፈሩት ይገዛል ። አንድ ሥራ አንድ የብልህ ጥበበኛ እጅ ብትፈልግ የአርነት ባለጋሮችዋ ጥቂቶች ይሆናሉና ፤ የበለጠ ደመወዝ ታገኛለች ። ስለዚህ ልዩ ልዩ በሆነ ሥራ የደመወዝን ትርፍ ማደግና ማነስ ምክንያት ለይቶ ማወቅ ፥ የግድ ያስፈልጋል ። በሠራተኞቹ መኻከል አንድ ወገን የሚበልጥ ደመወዝ፥ አንድ ወገን የሚያንስ ደመወዝ ሲያገኙ ሲታዩቸው ፥ አንደኞቹ በልጠ ያገኙትም የማይገባ ሥራት ይመስላል ። ግን እስዋ (ብልጫ) ከሠራተኞቹ ችሎትና ብልህነት ማለት በአእምሮ ይሁን ፥ በኃይል ፤ በሥልጣኔ ትምርት ይሁን ፤ በሥራ መልመድ ፤ በጕልበት ይሁን ፥ ትእዛዝና ሥራት በማጥናት ፤ በጥንቃቄ ይሁን ፥ በመታመን ፥ ምክትል መጥታ ነውና የተያዘች ፥ የደመወዝን ልዩነት የግድ የምታስፈልግ ሥራት ነች ። እንደ ወንጌልና ሶቻሊስቲ የሚባሉ የአንድነት ማኅበር ወገን ባህል ግን ፤ ሰዎች ሁሉ ትክክል ናቸውና ተፈጥረው የተወለዱ፥ ፍጥረት የምትሰጠውን ጥቅም ሁሉ በትክክል ሊከፋፈሉት አርነታቸውና ሥልጣናቸውም ልክ ሊሆን ይገባል ይባላል። በቴዎርያ የሚወጣበት አልነበረም ፥ ግን በፕራቲክ እስከ ዛሬ ዘመናችን ድረስ ምንም የማይቻል ሁነዋል ። ለሚመጣም የሚደርስ አይመስልም ። ስለምን በዓለም ካሉ ሁሉ ቀጠል እንኳ ፥ ሁለቱ ቅጠል ብቻ ልክ የሆኑ አይገኙም ይባላል።እንዲሁም ወደ ሁለት ሚሊያርድ የተቃረበ ፥ ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ፥ሁለት ሰዎች እንኳ ፥ አእምሮዋቸው፥ ብልህነታቸው፥ ችሎታቸው ፥ ትዕግሥታቸው ፥ ጠባያቸው ፥ ፍለጋቸው ፥ ኃይላቸው ፥ ጕልበታቸው፥ መልካቸው ፥ ድምፃቸው ፥ ልክ የሆኑ አይገኙም ይባላል ። እንዲያውም በድፍኑ አንድ ሰው ከኻያ ዓመት የሚበልጥ የጤና አእምሮውና ገንዘቡን እየጨረሰ ተምሮ ደክቶር (አዋቂ) የሆነና ፤ አንድ ሥራ ፈት በዘንተኛ ፥ ምናምንቴ ሁኖ ያደገ ቂል ሰው ፥ ወይም፥ በተፈጥሮው አንድ ጥንቁቅና ቈጣቢ የሆነ ሰውና፤አንድ ሰካራም ገንዘብ አባካኝና ንዝህላል የሆነ ሰው አንድነት ይሁኑ ማለት ደንቆሮ ሥራት ነው።

ስለዚህ ሳላርዮ የሚባል ደመወዝ ሳፎዮ የሚባል ትርፉን ከማቅረብና መስጠት የተገዛ ነው ። ሸቀጥን በገባያ ብዛታቸውን ያነሰና በጣም የተፈለጉ እንደሆኑ የልውጥ ዋጋቸውን ውድ እንደሚሆን ፥ እንዲሁ ሠራተኞቹም ብዛታቸው ያነሰና ሥራቸውም በጣም የተፈለገ እንደሆነ ፥ ደመወዛቸው ያድጋል ። እንደነ ጎልያድ የመሳሰሉ ታላላቆች ሰዎች በዓለም ካሉ መጠነኞች ሰዎች ይልቅ ፥ ብዛታቸው በጣም ያነሰ ነውና ፥ እነሱ ብቻ የሚፈጽሙት ዋና ሥራ ቢኖር ፥ የሥራ ዋጋቸው በጣም ከፍ ያለ ይሆን ነበር ይባላል ። ግን የሚያደክሙና ጠንካሮች ሥራዎች ሁሉ በመኪና ነውና የሚሠሩ ፥ ታላላቆች ጕልበተኞች ሰዎች ምንም አይፈለጉም ። ለዚሁ (መኪናዎች)የሚፈጥሩና የሚያስኬዱም ብልሆች አእምሮኞች ጥበበኞች ፥ አዋቂዎች ፥ ትዕግሥተኞች፥ ቻዮች ፥ ፈላጊዎች ፥ ትጎች ፥ ናቸው የሚፈለጉ። ስለምን በሥልጣኔ ትምህርት መካከል ካደጉ ብዙዎች ሰዎችም የሥራ ዋጋቸውን ልውጫ ከፍ ያለ ብዙ ደመወዝ የሚያገኙ የጠለቀና የረቀቀ አሳብ በተከናወነ ንግግር ጸፊዎች ፤ ትልልቅ ሐኪሞች ፥ እሳቶች የሆኑ ሕግ አዋቂዎች (አቦካቲ) መልካሞች

መሐንዲሶች ፡ ድምፃቸው ደስ የሚያሰኝ ዘማሪዎች ፡ ትጎችና የታመኑ ቻዮዎች ኢምፕሬንዲቶሮችና ነጋዴዎች ፡ የመሰሉ ሁሉ ናቸው ። ስለምን ደመወዝ የሚያድግ የሥራውን ፍሬ እንደመፈለጉና የሥራውን ጥቅም እንደ መስጠቱ ነውና ። ግን በዚህ ዓለም ምሉ ነገር አይገኝምና ፡ ይኸውም ጉድለት አይታጣበትም ። እንባቢ ስለምን ቢል ፡ ምስኪኖቹ የሃይማኖት የፊሎስፍያ (የዕውቀት ወዳጅ) የከዋክብት ፡ የሸንጸ (ዕውቀት ሁሉ ዕድሚያቸውን ሁሉ ባምርመራ የሚያሳልፉ ሰዎችም ትልልቆች ነበሩ ፡ ግን ምንይደረግ የሚያሳዝኑ ዕድሚያቸውን ምሉ አራቍታቸውን የቀሩ ደሆች ናቸው ።

መከተቻው እንደ አዳም ዝሚትህ ባህል ደ፯ም ፡ የደመወዝ ማደግ ቀጥለው ባሉ አምስት ነገሮች እንደተገዛ ይቆማል ። ፩ኛ) ሥራው ተወዳጅ በመሆን ፡ ምሳሌ)ኡፊቻሊ የሚባሉ የወታደሮች መኳንንቶች እንደሚገባቸው ልክ ትንሽ ደመወዝ ነው የሚወስዱ ፡ ስለምን በሰላም ጊዜ ሥራቸው ትንሽ ቀላልና ተወዳጅ ነው ። ፪ኛ) የኤኮኖሚያ ማርቀቅ ስለምን ሕዝቢቱ ድሀ ስትሆን ለልጆችዋ ትልቅ የሥልጣኔ ትምርት ማስተማር አይቻላትምና፤ ስለዚህ ልጆችዋን የሚበቃ ጥበብ ስለሌላቸው ሸካራና ቀላል ሥራ ስለሚይዙ ፡ ውለታቸው (ደመወዛቸው) ትንሽ ይሆናል ። ፫ኛ አንድ ሰው ሥራ ሲይዝ ዓመቱ በሞላ የተወሰነ ደመወዝ እንደሚያገኝ ከስረገጠ ፡ ትንሽ ቢሆንም ደመወዙ ደስ ያሰኘዋል ። እንዲሁ ለምሳሌ የመንግሥት ሠራተኛ ፡ የሥራውን ዋጋ የተቈረጠለትን ደመወዝ ሁለ ጊዜ እንደሚወስድ (እንደሚያገኝ) ፡ ቢታመም ወይም ቢያረጅ ደግሞ ፡ በፊት ከሚወስደው የነበረ ሲሶው የሚሆን አነስ የሚል ለኑሮው የሚበቃ ማለት ለሕይወቱ መያዢያ ተገምቶ እንደሚወስደው ፤ ለሥራ ያልደረሱ ልጆች ትቶ ቢሞትም መንግሥት እንደሚያሳድጋቸው ሕግ እንዳለ በርግጥ ያውቃልና ፤ ከፕሪባቶ የሚባሉ ዋኖች በታች ሁኖ ተቈጥሮ ለጊዜው ብዙ ደመወዝ ከሚያገኙ ሠራተኞች ይልቅ ደስ ይለዋል ። ፬ኛ) የሥራ ቤት ጥንቃቄና ፡ የሥራ ጥያቄ ፡ ለተሰጣቸው ሰዎች ደመወዛቸውን ያሳንስባቸዋል ። ማለት ያልታመኑና ጠባያቸው ደግ ያልሆኑ ሰዎች ትልቅ የቁምነገር ሥራ ሊያገኙ አይችሉምና ። ፭ኛ) ከሥራ መውጣት ጥርጣሬ፡ማለት አንድ ሥራ ለመያዝ ለማግኘት ቀላል ሲሆን ሁሉ ይፈልጉታልና፡ ደመወዝ ዝቅ ያለ ይሆናል።

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ይከተላል ። ሚከኤል ተሰማ ።

የአየር ባቡር ።

በነዚህ ባለፉት ወራት የልዩ ልዩ መንግሥቶች ዋና ዋና ሚኒስትሮች ከንግዲህ ወዲህ ጦርነት እንዳይነሣ የሚበጀውን ብልሃት ለማግኘት ብዙ ደጥራሉ ። እንደዚህ ያለ ስምምነትም የተደረገ እንደሆነ ጦርነት ከማንሣት ለመጠንቀቅ ይቻላል ብለው ተስፋ በማድረግ አሜሪካን ፡ እንግሊዝ ፡ ፈረንሳዊና ሌሎችም መንግሥታት የጦር መርከቦቻቸውንና የወታደሮቻቸውን ልክ ለመወሰን ልዩ ልዩ ጉባዔን ያደርጋሉ ። ጦርነትን ለማስቀረት ቢደረስና ፤ በልዩ ልዩ መንግሥታት መካከል የሚነሣውን ነገር ለመጨረስ የሚያስፈልገው ሥልጣን ለሕዝብ ማኅበር ቢሰጥ ሰው ሁሉ እጅግ ደስ እንዲለው እርግጥ ነው ። ደግሞ ለወታደር መሣሪያ የሚበልጠው ወገን የግብር ገንዘብ ከሚወጣ የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻል ቢወጣ ይልቅ ሰውን ሁሉ ደስ ባለው ነበር ፤ ስለሆነ ግን የመንግሥቶችን አለቆች ሁሉ ቶሎ ባንድ ጊዜ ገራሞች ሁኑ ለማለት አይቻልም። ይልቁንም ወደዚህ ወደ ደግ አሳብ የሚገፋፉቸው ግዴታ መሆኑን እናምናለን ፤ በውነት ፖሊቲክና መልካም አሳብ ሊሰማሙ አይችሉም ፤ የልዩ ልዩም መንግሥቶች ፖሊቲከኞች አለቆች ጦርነትን የሚያስቀር ስምምነትን ሊፈርሙ መፈለጋቸው ለወደፊት አንድ አዲስ ጦርነት ቢደረግ የዓለም ጥፋት መሆኑን በመልካም አድርገው በመረዳታቸው ብቻ ነው ።

(የሲያንስ) የዕውቀት ሥልጣኔ እጅግ እየሰፋ ሔዷልና ለወደፊት አንድም አዲስ ጦርነት ለማድረግ የማይቻል ነው። ልዩ ልዩ መንግሥቶች የሚሠሩት (ሱማሬን) የሚባሉ አዲስ የወጡ የባሕር ውሥጥ መርከቦች በጣም አድርገው የሠለጠኑና ታላላቅ አደጋ የሚጥሉ አንድም ሌላ መሣሪያ ሊያጓዳቸው የማይችል ናቸው ።

በሌላም በኩል (ሺሚ) የሚባለው የዕውቀት ሥራ አዳዲስ ነገር አውጥቷልና አዲስ የወጣው (ጋስ አስሬክሲአንት የሚባል የመርዝ ነፋስ ባንድ አፍታ ብዙ ሺ ሰዎች ለመፍጀት ይችላል ።

የአየር ባቡሮች ግን በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ማስተዋል መንግሥታችን እነዚህን መሣሪያዎች ማደራጀት ጀምሯል እነዚህም መሣሪያዎች እጅግ የሠለጠኑ ምንም የማይጎድላቸው ሁኖዋል ።

እነሆ ለፍጥረት ሁሉ መልካም ሥራ የሚሠሩ (ሱማሬን) የሚባሉ ባሕር ውሥጥ የሚሔዱ የጦር መርከቦች (ጋዝ አስሬክሲአንት) የሚባሉ መርዝ ያለበት ነፋስ " ያየር ባቡር (ዜፕሌን) መሣሪያዎች ናቸው እንደ የጊዜው ፖለቲከኞች ሰዎች አይደሉም ። ከንዳንድ ወራቶች በፊት አንድ ዜፕኑኤን ከጀርመን አገር ተሥቶ ወደ መስኮብ አገር ወደ ምሥራቅ ጫፍና ወደ አሜሪካን አገር ሔዶ ከዚያም ወደ ጀርመኑ አገር ተመለሰ ። ከጥቂት ቀን በፊት አንድ አዲስ የአየር ባቡር ቤንዚን ለመሙላት እመሬት ሳያርፍ ሺህ ኪሎሜትር ለመሔድ መቻሉ ተፈትኖ ተከናወነ ፤ ይኸውም መቶ ስልሣ መንገደኞችና ከአሥር ቶን የሚበልጥ ዕቃ የሚይዝ ነው ።

እንግዴህ እጅግ የራቀውንም መንገድ ለመዝለቅ የሚችሉና በመንገደኞችና በዕቃም ፈንታ ቦምብ አሲይዘው ቢሰዱዋቸው ከዓለም ላይ እጅግ ታላቅ የሆነውን ባንድ ሌሊት ለማጥፋት የሚችሉ አኤሮፕላኖች አሉ ።

ከለፈውም ዘመቻ ወዲህ በምብና የቦምብ መወርወሪ መሣሪያዎች በጣም ሙሉ የሆኑ መሣሪያዎች መሆናቸውን አለመዘንጋት ነው ዛሬ አንድ የጦር አኤሮፕላን እስከ ሦስት ሽህ ሜትር የሚሆን ርቀት ወደ አየር ወጥቶ በምብን ለመጣል ያሰበውን ለማድረግ አሳምሮ ይችላል ። እንደዚህ ከሆነ አንድ ሐያ የሚሆን አኤሮፕላን ይዞ ባንድ ሌሊት ባንድ ዋና ከተማ ላይ ቢጥል የሚያመጣውን አደጋ አስቲ አስቡት ።

እሩብን ለመጠበቅ የሚያስፈልገው ብልሃት በከተማ ላይ እንዳይደርሱ የጠላትን አኤሮፕላን የሚከለክሉ ሌሎች አኤሮፕላኖች ማግኘት ብቻ ነው ። እንዲህ ጦርነት በምድር ላይ በመደረግ ፈንታ በአየር ላይ ይደረጋል። የሚያሸንፈውም እጅግ የበለጡና ከሁሉም የሚሻሉ አኤሮፕላኖች ያለው መንግሥት ነው፡፡ነገር ግን አኤሮፕላኖቹ በድንገት በታላላቅ ከተሞች ላይ ሳይታዩ ለመድረስ የሚችሉ የሆኑ እንደሆን የአየርን ድንገተኛ አደጋ ዘወትር ለመከልከል ይቻላልን? እንደዚህ ያሉትም ከተሞች ካንድ የሰዓት እሩብ በኋላ በመላ በፍጹም ይጠፋሉ ። ደግሞም አቢዮን መምጣቱ በድምጹ እንዳይታወቅ የዛሬ ጊዜ መኪናው ድምፁ የማይሰማ መሆኑን መመልከት ነው ።

እንዲህ ታላላቅ ከተሞች ባንድ አደጋ በሚጥል ድንገተኛ ነገር የሚጠፉ ከሆነ ምንስ እድል ቢገኝ ጦርነትን መቀስቀስ ለምን ይበጃል ።

ይህንንም ማለት አንዱን መንግሥት ከንዱ መንግሥት ጋራ ጦርነት እንሥቶ በዚሁ ምክንያት ትልልቆች ከተሞች የጠፉ እንደሆን ጥቅሙ ምንድነው ።

ስለዚህ ይህንን ጦርነትን የማስቀረት አሳብ የሚነግሩቸው ካዴታና የጥበብ መሻልል ነው እንጂ የታላላቆች የፖሌቲክ ሰዎች አሳብ ብቻ አይደለም ።

በፍቅርና በአንድነት ስለ አሚገኘው ጥቅም፡፡ ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እንዲሉ ።

፩ ልጅ በ፲ዓመቱ ጥበብ መንፈስዊና ጥበብ ሥጋዊ እነሳሳውና አባቱን ከተማሪ ቤት እንድገባ ፈቃድህ ይሁንልኝ ብሎ ለመነው። አባቱም ሲሆን እኔ አስቤ እንድትማር አድርግ ነበር ። ያለዚያ ግን አንተን እግዚአብሔር በጎ ነገር አስመልክቶ የኔንም ስም በበጎ አጠራር የሚያስጠራና አንተንም ከዕውቀት ወደ ዕውቀት፡ ከመሻል ወደ መሻሻል በሚመራ መንገድ ልሔድ ብትል ፈቃድ እከለክልሀለሁን እኔስ ፈቃዴ ነው ፡ የእግዚአብሔርም ፈቃዱ ይሁንልህ ብሎ ለተማሪ ቤቱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሰጥቶ ሰደደው ይባላል ። ያም ልጅ በድኅንፃ መንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ነውና ከተማሪ ቤት ገብቶ እንደ ተማሪ ቤቱ ደንብ ከሚጀመርበት ትምርት ጀምሮ በየክፍል በየክፍሉ ጥበብ መንፈሳዊንና ጥበብ ሥጋዊን ፍጽምጽም አድርጎ ሊቅነቱ ከሁሉ የበለጠ ሆነ። ከዚህ በኋላ ብዙ ቢማሩ በንደኛው ሥራ ይኖሩ ነውና ፡ ከወቃቸው ዕውቀቶቹ ሁሉ ለሕይወቱ መኖሪያ የሚሆነው ማናቸው እንደሆነ ያወጣ ያወርድ ጀመር። አውጥቶ አውርዶም የቀሩት ትርፍ ሙያ ይሆኑኛል፡ለሕይወቴ መኖሪያ ግን ይህ ይበቃኛል ብሎ አንደኛውን መረጠ ። የመረጠውም የሥራው አይነት ይህ ነው ። የዘመዶቹ ቦታ ከተማ ስለሆነ ጠበብ ያለው ነበርና ወደ ውጭ ወጥቼ ጠፍ ሀገር አቅንቼ ፡ ዱሩን መንጥሬ ፡ አውሬውን አብርሬ ፡ ሚካውን አልምቼ ፡ እርሻ አርሼ ዘር ዘርቼ፡ ምርት አምርቼ እኖራለሁ ብሎ የፈለገውን ወደሚያገኝበት ቦታ ጉዞ ጀመረ ። ከመሔዱም አስቀድሞ አባቱን ሲሰናበት እንዲህ አለው ። በከንፈሩ ከሚወሳልት ሰው ተጠንቀቅ ። ምንም እፉን በመሐላ ውሀ ቢጉመጠመጥ ልቡናው አይነጻምና ። ከዚህም ሌላ ለናቱም፡ለባቱም፡ ለዘመዶቹም ሁሉ በውነት እሳንችኋለሁ ። እባግዕ ወዳሉበት ቦታ በበር ያልገባ፡ አጥር ጥሶ ቅጥር አፍርሶ የገባ ሌባ ወንበዴ ነው።በዋናው በር የገባ ግን እውነተኛ የበጎች ጠባቂ ነው። ለርሱስ በረኛው ይከፍትለታል። በጎቹም ቃሉን ይሰሙታል። እሱም በጎቹን በየስማቸው ይጠራቸዋል ። ከለምለም ቦታ ከሰፊ ሜዳ ያሰማራቸዋል ። ካሰማራቸውም በኋላ በፊት በፊታቸው ይሔድላቸዋል ። በጎቹም ይከተሉታል ። ቃሉን ያውቁታልና ብሎ ይህን ትምርት መሰናበቻ አድርጎ አስተምሩዋቸው ወዲያው በዚህ ዓለም የምኖራት ሕይወትህ ብዙ ትሁን፡ እኔን ልጅህን እንድማር አድርገሀልና ብሎ ምርቃት አዛውሮ አባቱን ይመርቀዋል ።

አሁንም ከተማርኋቸው ትምርቶቼ ሁሉ የእርሻ ሥራ የሚጠቅመኝ ሁኖ አግኝቼዋለሁና ሰፊ መሬት ካለበት ሒጄ አገር እንዳቀና ፈቃድህ ይሁንልኝ አለው ። አባቱም የልጁ ሐሳብ ጥቅም ለሚገኝበት ነገር እንደሆነ ስለተረዳ፡ ልጄ ሆይ ምን ጊዜም ያንተ ሐሳብ ወደ በጎ ነገር እንደሆነ አውቃለሁና ሒድ እግዚአብሔር መንገድህን ያቅናልህ አለው ። ለአዳም የምትረዳው ሴት እንፍጠርለት ተብሎ በጌታ ቃል የተነገረውን ያውቃልና አንዲት መልከ መልከም ሴት ልጅ ከናትከባቷ አስፈቅዶ፡ሁለት ንበዛዝት አስከትሎ፡ በሁለት አጋሰስ ለርሻ መሰሪያ የሚሆኑ ዕቃዎች አስጭኖ፡ሁለት ጥንድ በሬ፡አንድ ኩርማ አንዲት ላም፡ ከሌሎችም እንስሶች ለዘር እንዲሆኑ ተባትና ወንድ እያደረገ ይዞ ሔደ ። እግዚአብሔር ያሰቡትን ነገር መፈጸም ልማዱ ነውና ከፈለገው ቦታ አደረሰው ይባላል ። ወዲያው ዕለቱን ሳይውል ሳያድር ጫካውን እየመነጠረ ማረስ ጀምሮ እስከ ሰባት ዓመት ድረስ ያችን አገር አቅንቶ የዘሩባትን የምታበቅል የተከሉባትን የምታጸድቅ አድርጎ፡እንተ ታውሕዝ ሀሊብ ወመዓረ ከተባለችው ሀገር እኩል አስተካከላት ። እነዚያም ይዟቸው የሔደው የእንስሳ አይነቶች እንደ ሰማይ ከከብ እንደ ባሕር አሸዋ በዙ ፡ ከሴትዮዋም ብዙ ልጆች ወለደ ። በዚያም ወራት ሕዝቡ ያለመጠን በዙ፡ ቤተ ሰብ ከበዛ ዘንድ መፎከከርና መተያየት አይቀርምና እርስ በርሳቸው እየተያዩና እየተፎከከሩ አባታቸው ሲደክም አገልግሎታቸውን ብቸልታ ለማድረግ ሐሳብ ይነሣባቸው ጀመር ። እርሱም ይህን አይቶ እየጉድ ልጅ ደረሰ፡ ቤት ፈረሰ ማለት ይህ ነውን እያለ ያዝን ጀመር ። አንድ ቀንም ሁሉንም ሰበሰበና ምክሬን ስሙኝ፡ እኔ በብዙ ድካም ጫካ ውጧት የነበረችውን ይችን አገር አቅንቼ የወይኑ ዘለላ ጋን የሚሞላ፡ የስንዴው ዛላ እፍኝ የሚሞላ አድርጌ እንደዚህ ያለች ገነት የሆነች ሀገር አቄየኋችሁ እናንተም በፍቅር አንድ ሁናችሁ ተዛዝናችሁ ተከባብራችሁ እንዳንድ ልብ መክሬ፡ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁናችሁ የበዙር ወንድማችሁን አለቃ አድርጋችሁ እኔ አባታችሁ በመዓልትና በሌሊት ድምፀ አራዊቱን፡ግርማ ሌሊቱን ታግሼ ወዚ ጠብ ጠብ እስቲል ድረስ እየደከምሁ ያቀናኋትን ሀገር መውረስ አይሻላችሁምን፡ አንድነት ካልኖራችሁና ካልተፋቀራችሁ ግን ሀገሪቱም ሀገር አትሆንም።እናንተም ኃይል አታገኙም ብሎ የማቴዎስ ወንጌልን ፲፱ ከ፳፩ እንሥቶ እስከ ፳፯ ድረስ አንብቦ ተፈጸሞ

አስረድቶ ይህን ምክሬን ብትቀበሉኝ ሀገራችሁን ትወርሳላችሁ፤ ባትቀበሉኝ ግን እናንተም የጠላት ተገዢዎች ትሆናላችሁ። ይህችንም መልካሚቱን ሀገራችሁን በጠላት እጅ ሁና ታይዋታላችሁ ሰማችሁኝ ልጆቼ ሆይ ፤ ይህችን በታችነን ፍየል እንዳየ ነብርና ቀጠል እንዳየ ፍየል የጠላት ዓይን ትኵር ብሎ ሲመለከታት ለማስተዋል የተዘጋጀ ዓይን ልቡና የላችሁምን። አሁንም በአንድነት ገመድ ተሣሥራችሁ በፍቅር ሰንሰለት ተቈራኝታችሁ ባለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል የተባለውን ተመልክታችሁ የኖራችሁ እንደሆን የሀገራችሁ ተወራራሾች ትሆናላችሁ ። ከዚህም እያይዞ የቅዱስ ጳውሎስን ምክር ያስረዳቸዋል። ፍቅራችሁ በግብዝነት አትሁን፡ ክፉውን ትቃችሁ መልካሙን ያዙ ። በሥራም አትስነፉ። እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ ። ከዚህም ሌላ ጳውሎስ አበውን ለውሉድ ምርሴ አድርጎ እንዳስተማረ እርሱም ይህን የሚከተለውን ቃል ያስተምራቸዋል ። እግዚአብሔርን አትፈታተኑ ፤ የተፈታተኑ ጠፍተዋልና ። አታንጐርጕሩ። ያንጐራጐሩትን ቸነፈር ፈጅቷቸዋልና ። እነዚያንም ያገኛቸው ይህ ሁሉ መከራ በኋላ ዘመን ለምን ነግ ለእኛ ምክር እዝናት ሊሆን ተጽፎልናል እያለ የትምርቱ ማሳረጊያ የሰማችሁትን በልቡናችሁ ያሳድርብችሁ ብሎ በዚህ ምክሩን ጨረሰ ። የዘሩብትን የሚያበቅል መሬትና የመከሩትን የሚሰማ ሰው እጅግ የታደለ ነውና። እነሱም ኢሳይያስ ማየት ታያላችሁ አትመለከቱም እንጂ ፤ መስማት ትሰማላችሁ አታስተውሉም እንጂ ማወቅ ታውቃላችሁ ልብ አታደርጉም እንጂ ፤ ያለው እንዳይደርስባቸው ምክሩን በፍጥነት ተቀብለው። በትምህርትና በሥራ ባንድነት ጽሙአን ሁነው፤ በጸሎትም ባንድነት ማእዱን እየባረኩ ኖሩ ። ያንድነታቸውንም ጽናት በየ ጊዜ ሥጋዊ ደማዊ ጠላት ይፈራቸው ጀመር ። በሀገራቸውም ድንቅ ድንቅ የሆነ የፍቅር ሥራ ይሠራ ጀመር ። ሌሎችም ሰዎች ሁሉ በነሱ ፍቅር እየተሳቡ ገንዘባቸውን እየያዙ እየመጡ ከነሱ ማኅበር ይገቡ ጀመር ። ሁል ጊዜም እንዳንድ ልብ መክሬ ፤ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ይኖሩ ጀመር ። ምግባቸውንም ይህ የኔ ነው ፤ ምነው የኔ ነው እንጂ ሳይባባሉ ደስ እያላቸው በቅን ልቡና ሁነው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይመገቡ ጀመር።በሁሉም ዘንድ መወደድና ባለሟልነት ነበራቸው።እግዚአብሔርም በፍቅር አንድ ቢሆኑለት ይወዳልና በነጋ ጊዜ እየለት እየለቱ ማኅበራቸውን እያሰፋላቸው ያብልህ አዋቂ አባታቸው በመከራቸው ምክር አንድነታቸውን አጽንተው ኖሩ ይባላል። እነሱ ያባታቸውን ምክር ሰምተው ባንድነትናበፍቅር ስለጸኑ ከሀገራቸው ዳር ቻ ማንም ጠላት ድርሽ ሳይል እንደኖሩ፤እኛም ያንድነታችንን መሠረት በፍቅር ላይ መሥርተን ከስምምነት ደረጃ ላይ ቁመን አይዞህ አይዞህ ተባብለን የኖርን እንደሆን ድመት ከምትጮህበት ስፍራ ያይጥ ድምፅ ድምጥማጡ እንዲጠፋ ምናልባት በሀገራችን ክፉ የሚያስብ ማንም ቢኖር የሚሮጥበት ሜዳ፤ የሚገባበት ቀዳዳ፤ የሚመከተው ጋሻ፤ የሚሸሽግበት ዋሻ፤ የሚጠጋበት ቀጠል፤ የሚንጠለጠልበት ገደል የሚያገኝ አይመስለኝም።ይህንም የምታነቡ ጌቶቼ ሁሉ ባልተደላደለ ዕውቀቴ ይህን ስለ ተናገርሁ ይቅርታ እንድታደርጉልኝ እለምናለሁ ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

ትንሽ በረከት

ኢትዮጵያ ኑሪ ክብርሽ ነው ተፈሪ

በድንቍርናዋ ታጥራ የነበረች ።
በምቀኛ ወሬ ታጥራ የነበረች ።
በፖሊቲክ አጥር ታጥራ የነበረች ።
ዛሬ በተፈሪ ዤኔብ (Genève) ላይ ቍጭ አለች ።
ከዓለም ጉባኤ ተካፋይ ሁናለች ።
ከዓለም መንግሥታት ማኅበር ገብታለች ።
ከመንግሥታት ጋራ ፍቅሯን አስፍታለች ።
መንበረ መንግሥቷን አስከብራዋለች ።

የሥልጣኔ በሩን መንገዱን ገልጠህ ።
የምቀኛን አጥር ነቃቅለህ ጥለህ ።
ለሚመጣው ትውልድ ምሪቱን ሰጥተህ ።
ለመንግሥትህ ክብር ዓርማው ለናትህ ።
በታሪክ ደጳፉል ይኸ ውለታህ ።

በዝና በታሪክ ትኖር የነበረች ።
የፍቅሯን አታክልት በሮፓ ተከለች ።

ፍቅሯንም ለመዝራት ከልቧ በሙሉ ።
ሚኒስቴሯን ላከች በየስፍራው ሁሉ ።

መንግሥታቱ ሁሉ እጅግ ያደንቃል ።
ማኅሌትህ ዘልቆ ከባሕር ደምቋል ።

ከባሕር መልሰ እግዜር ያቈየልን ።
እኛን ለማዳን ነው የተፈጠረልን ።
ጨለማውን አንሺው ብርሃኑን ስጪቸው ።
ለኋላ ሰቀቀን እንዳይሆንባቸው ።
ጨለማ የወደደ ብርሃን አይታየው ።
እነሱም አያውቁት ጸጸቱ ያንቺ ነው ።

ብርሃን የሌለው ሰው በምን ይታየዋል ።
በጨለማ ሲሔድ ያደናቅፈዋል ።
ለምን በኛ ብቻ ይመከኝብናል ።
ብርሃን የሚጠላ ከወዴት ይገኛል ።
የሮፓ መኳንንት በጣም ይገረማል ።
የተፈሪ እውቀትህ ከባሕር ዘልቋል ።

በዚሁ ዘበን ያልወጣ ብርሃን ።
ዛሬ ባንተ ጊዜ ተገለጸልን ።
ሲደፈን ሲከፈት ያልተቃናውን ።
ይኸው በጥቂት ጊዜ ብርሃን አሳየን ።

ለምን በዚህ ብቻ ሰው ይገረማል ።
የተፈሪ ዘውዱ ከሮፓ ያበራል ።
ብርሃን የሌለው ሰው በምን ይታየዋል ።
በጨለማ ሲሆን ያንፀባርቀዋል ።

ጕርብጥብጡን አቅናው መንገዱን ምራው ፡፡
በጨለማ አይታይ ብርሃን ካልሆነው ፡፡
ግራና ቀኝ ቃኘው ጐዳናው ይከፈት ፡፡
አርበኞችህ ሁሉ እንዲናፈሱበት ፡፡
የኢትዮጵያ አርበኛ የኢትዮጵያ ጀግና ፡፡
ወታደርነቱን አስመስክሯልና ።
እግዜር በሰጠው ኃይል አገር ሁሉ ቀና ፡፡
የኢትዮጵያ ጀግና ያጊጥ ያምርበታል ፡፡
ተንቀሳቃሽ ሕመም ማከም ያውቅበታል ፡፡
ለተንቀሳቃሹም ሥራው ምንሆነና ፡፡
ለእንዲህ ያል በሺታ አርሚቱ ነውና ፡፡
የኢትዮጵያ አርበኛ በጣም ያኰራታል ፡፡
ብንዲራዋን ይዞ በደሙ አንጸታታል ፡፡
በመድፉ ጕድብ ባጠሩ አቂሚታል ፡፡
ምቀኛዋ ሁሉ ይዘታል እፍረት ፡፡
በምን ይጣላታል መንገድ ከሲያዙት ፡፡
ተኝተው ተቀምጠው ቢያልሙም ቢያልሙም ፡፡
እጃቸውን ማግቢያ ቀዳዳ አላገኙም ፡፡
ለጭውውቱማ ኢትዮጵያም ያውቃል ።
ሡከሩና ማሩ ከቆላይ ይፈልቃል።
ኢትዮጵያ እደጊ ኢትዮጵያ ኑሪ ።
ኩብርሽን አንድ ጊዜ አርጎታል ተፈሪ ።

ኪዳኔ ማ ተ ፡፡

ስለ ፍቅር መተባበር መታሰቢያ

ታላቁ ቴዎድሮዎስ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የአፍሪክ አጮኛ ንጉሡ ቴዎድሮስ በጊዜው እስካለና እስከገዛበት ጊዜ ድረስ ስሙንና አርበኞቹን በገናና ወታደርነት እንዳስጠራና ሀገሩንም እንዳስከበረ ጕረቤቶቹንም በግርማውና በአርበኝነቱ እንዳንቀጠቀጠና እንዳሸበረ ይኖር ነበር እየተባለ ሲወራና ሲነገር ከጥንታውያን ሽማግሌዎቻችን ቃል እንሰማለን።

ይሁን እንጂ ታላቁ ቴዎድሮስ ግርማውና ኃይሉም የገነነ ሁኖ የሚነገረው ባርበኝነቱና በድፍረቱ ሀገሩን በማፍቀሩና ጠላቶቹን በየጊዜው ድል እየዳረገ በመግዛቱ ነበር እንጂ ፍጡርነቱና ሰውነቱ ከፍጡር የተለየ አኳኋን ኖሮት አይደለም ።

ኃያሉ የመላ ኤውሮፓ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዎን በንስፖርት እንደተባለው ሁሉ ። ኃያሉ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስም ኢትዮጵያ ሀገሩን ባርበኝነቱና በደፋርነቱ እስከ ጊዜውና ሕይወቱ እስከለረች ድረስ ስሙንና የሀገሩንም ጀግኖች ስም አዳስጠራቸውና እንዳስከበራቸው ይኖርነበር።

ምንም ቴዎድሮስ ሀገሩን ለማስፋፋትና ለማቅናት ጠላቶቹንም ድል እያደረገ ድንበሩን ለማሰናዳት ቢያስብ ለጊዜው ሕዝቡ በኃይለኝነቱና በድፍረቱ ስላልወደዱት አንድ አካል አንድ አምሳል ሁነው ሐሳቡን ተቀብለው ሊፈጽሙለት ስላልወደዱ ከባዕድ ጋራ መከረው ጦር አስነሡበትና ሕይወቱን በገዛ ራሱ እስኪገለው አደረሱት ይባላል።ይኸውም የምቀኝነት ሐሳብ ሳይሆን አይቀርም የፈረንሳይ ሕዝቦች ስመጥሩውንና የመልክም መሬ ንጉሣቸውን ሐሳብና ትእዛዝ ስላልፈጸሙ ንጉሣቸውን ናፖሊዎን ቦን ስፓርትን የጕዱ መስሏቸው ከመንግሥቱ እንዲወጣ አድርገው በጠላት እጅ ለመታሠር ስላደረሱት ናፖሊዎንን ምንም የጐዳው ነገር የለም ግን እራሱ የፈረንሳይ ሕዝብና አርበኛ ተጐዳ እንጂ፡የተጐዳበትም የፈረንሳይ ሕዝብ ፩ኛው በናፖሊዎን ጊዜ የፈረንሳይ ንጉሥ ኤሮፓን ይገዛ የነበረው ከናፖሊዎን በኋላ ሁሉም በክፍል በክፍሉ ንጉሥ እየወጣ በፈረንሳይ መንግሥት ባለመገዛቱ፤፪ተኛም የፈረንሳይ መንግሥት የአውሮፓ ንጉሠ ነገሥት መባሉ ቀርቶ በሀገሩ መታገዱና ጥንት የገዛውን ሁሉ መልቀቁ ባለመስማማትና የንጉሣቸውን ሐሳብ ባለመቀበላቸው መሆኑ አይጠረጠርም ይኸው የናፖሊዎንን ታሪክ ለሚመለከቱ ፈረንሳዮች ሁሉ ግዛታቸውን ለቀው በራሳቸው ርስት ብቻ ስለተቀመጡ ናፖሊዎንን ሳያስቡት አይቀርም በማለት ሽማግሊዎች ይተርኩልናል፡፡ሰው ግን ወይም ካልሔደ ወይም ካልሞተ መጥቀሙና ማጕደሉ አይታወቅም እንዳሚባለው ሁሉ ናፖሊዎን በቁሙ የፈረንሳይን መንግሥት የጠቀመውን ሕዝቡን ባያውቁለት አሁን ከሞተ በኋላ ሁሉም እንዳጐደላቸው አውቀው ይጸጸታሉ ይባላል ።

ነገር ግን ኃያሉን ናፖሊዎንን የፈረንሳይ አርበኞችና ጀግኖች በመጀመሪው ጊዜ በፍቅርና በስምምነት ትእዛዙንና ሐሳቡን እንደሚፈጽሙለት ሁሉ ለኢትዮጵያው ንጉሥ ለኃያሉ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ አርበኞች ሐሳብንና ትእዛዙን እሱ እንደሚላቸውና እንደሚአዛቸው ቢከተሉና ቢፈጽሙ ለትኑሮ ናፖሊዎን የኤውሮፓ ንጉሠ ነገሥት እንደተባለው ሁሉ ቴዎድሮስም የአፍሪክ ንጉሠ ነገሥት እንዲባል ጥርጥር የለበትም ነበር ።

ያለመስማማትና ያለመፋቀር ኃይልን ያሳንሳል። ጠብም ያዋርዳል አንድነትም ያስከብራል እያሉ ሽማግሌዎች እንደሚተርኩት ሁሉ ሕዝቡ ቴዎድሮስን ባለማፍቀራቸውና ባለመከተላቸው ለሞት አበቁት መባሉን እንሰማለን።ነገር ግን ቴዎድሮስ ለሀገሩ ሲያስብና ሲጥር ለሞት ቢያደርሱት የሞተው ቴዎድሮስ ስሙን በጀግንነት እንዳስጠራውና እንዳስከበረው ይኖራል እንጂ ምንም የጐዳው ነገር የለም ። ስለ ሆነ የቴዎድሮስና የሕዝቡ አለ መስማማትና አለማፍቀር ኢትዮጵያን ጐዳት እንጂ ባዕድን የጐዳው ነገር የለም።

እንዳዲህ የደከሙበትን ጕዳታችንን የሐሳባችንን መሰናከል እያሰብንና እየተመለከትን የውዲን ሀገራችንንና የመንግሥታችንን ትእዛዝ እየፈጸምን መቃመጥና የገዢዎቻችንን ትእዛዝ ማከናወን ይገባናል እንጂ ባልሆነ ነገር ኢትዮጵያ እናታችንን ተወዳጅና ርኅራኄ ለሕዝቡ የሚያደርገውን መንግሥታችንን በሆነ ባልሆነው ነገር ብናስቀይመውና ብንጐዳው እንደልባችን ተናግረን እንደፈቀድን ሁነን መኖርን እንኳንስ በውናችን በሀልማችን እንኳን ልናገኘው አንችልም ስል አእምሮ ላላቸውና ማስተዋልን ለሚያፈቅሩ ለሀገሬ ጀግኖችና አርበኖች የልጅነት ምክሬን በተቻለኝ መጠን አቀርባለሁ ።

በቀለ ዘለቀ፡፡

የማዕድን መፈለጊያና የማውጫን ፈቃድ ለሌላ ሰው አሳልፎ ስለመልቀቅ ወይም ስለመሸጥ የወጣ ።

አዋጅ ።

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ትእዛዝ የማዕድን ሥራ ቤት በመንግሥቱ ስም ሁኖ ይህን አዋጅ አውጇዋል ።

፩ኛ የማዕድን መፈለጊያና የማውጫ ፈቃድ ከመንግሥት የተቀበለ ማናቸውም ባለውል የሆነ ሰው ወይም ማኅበር የተቀበለውን ፈቃድ ለሌላ ለመልቀቅ ወይም ለመሸጥ ቢፈልግ አስቀድሞ ለመንግሥት ሳያስታውቅና ሳያስፈቅድ አሳልፎ ለመልቀቅ አይቻለውም ።

፪ኛ ያለመንግሥት ፈቃድ ውሉን ወይም ፈቃዱን አሳልፎ ለሌላ የሚለቅ ሰው ሁሉ መሸጡ ወይም መልቀቁ አይረጋለትም የኮንሴሲዮኑም ውል ይፈርስበታል ።

፫ኛ መንግሥትም ከፈቀደ በኋላ ለሌላ ለሚለቀቅ ፈቃድ በፈቃዱ ውስጥ ተወስኖ በተመለከተው መሬት ባንዳንዱ ሔክታር አንዳንድ ብር ወይም ባንዳንድ ጋሻ መሬት ፵ ፵ ብር ቀረጥ ለመንግሥት ይከፈላል ። የካቲት ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።

A O U A D J E

Concernant

La Cession des Permis de Recherches et d'exploitations Minières

Par ordre de S M le Negus Teferi Héritier du Trône et Régent Plénipotentiaire de l'Empire d'Ethiopie, Le Département des Mines,

Au nom du Gouvernement Impérial

Decrète:

1°, Aucun permis de recherche ou d'exploitation Minière ne peut être cédé à l'insu et sans l'assentiment préalable du Gonvernement Impérial

2° Toute cession faite sans l'accord du Gouvernement sera considérée comme nulle

Elle entrainera la déchéance de la concession,

3° La cession autorisée par le Gouvernement est soumise au paiement d'un droit de I thaler par hectare de terrain compris dans le périmètre du permis Addis-Abeba, le 18 février 1930

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

— ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚሁ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሀ ጸባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጀ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የንግድ ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ግመልከቻ	፪ መሐ
የእንቀጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩	፲፪ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፯ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፮ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፬ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸፭ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፬ ብር
ባለ ድመ ።		፻፸፰
ባለእሆያ ።		፻፵፫
ባለሳቢ ግመል ።		፻፷፰
ባለ አንበሳ አሜሪክ		፻፷፭
" " ጃፖን		፻፲ ብር
ሱካር	ጁኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብርተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲ ፍራንክ ከ፷፭ ሳቲንም
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ፸ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፫ ብር
አንድ ወቄት ወርቅ	፵፱

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቈሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የድማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኒይ።
አ ቡ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፱
6ᵐᵉ ANNÉE № 9

ሐሙስ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 27 FEVRIER 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በክፉ ልማድ አገር ስለ መጐዳት።

ልማድን ለመተው እንደምን ዓይነት አድርጎ ይቻል ይሆን? ጫት የሚባል ቅጠል ብዙ ሰዎች ፥ በልማድ እየበሉ ያመልኩበታል ። ይልቁንም ይህ ጫት በሐረር አውራጃ ብዙ ሕዝብ ጐድቶ ይኖራል ፥ እንግዲህ የዚህን የጫትን ታሪክ ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ ፥ ጫት ቃሚ የሆነ ሰው ጫቱን ለቅሞ ወይም ገዝቶ በሽማሙ ሙሉ ይዞ ሁለት ሰስት ጊዜ ባፉ እየሞላ በልቶ እንደ ልማዱ ወሀ ተጐንጭቶበት በዋጠው ጊዜ ሐሰበ ሰውነቱ ሁሉ ደለወጥና የሆነያልሆነውን ይቀበጥራል። ከዚህም የተነሣ ክሞት ደደርሳል ፥ ይኸንንም ለመጻፍ ያነሣ-ሣኝ ፥ ሐረርጌ አንድ ጫት ቃሚ የሆነ ሰው ከዕለታት አንድ ቀን ጧት ለሥራ ከቤቱ ተሠምርቶ እርሻው ውሥጥ ሔዶ ዘወ-ትር ጫት ከሚቅምበት ከርሻው ማህል ባለ ዛፍ ስር ሔዶ ቁጭ ብሎ ከብዙ ሰዎች ጋራ ጫቱን ለቅሞ ሲቅም ውሎ ይኸውም ሰው ካለልክ አብዝቶ ቅሞ በሰከ ረ ጊዜ የሰውነቱ ሐሳብ ሁሉ ተለዋውጦ አብረውት የሚቅሙትን ሰዎች እናንት ሰዎች አሁን ይህ ጫት ያወራኝን ነገር ሰማችሁ አላቸው።ምን አወራህ ቢሉት በናንተም ሆድ ውሥጥ ያለውን ሐሳብ ሁሉ ገልጾ ነገረኝ።እኔም ክንፍ አውጥቼ እበራለሁ አላቸውና ተነሣና በዚያ በትልቅ ሰን-ጤት ላይ ወጣና እጫፉ ሲደርስ ክንፍ ያወጣ መስሎት እጁን ዘረጋና ለመብረር ከንጩቱ ጫፍ ከተቀመጠበት ላይ ብድግ ብሎ ዘሎ እበራለሁ ሲል ወድቆ ሞተ እያሉ ሲያወሩ እሰማ ነበር ።

ይልቁንም በዚህ በጫት መብላት ምክንያት ሃይማኖቱን ትቶ የሰለመ ክርስቲያን አይቻለሁ። እንደዚህም እስላምም ሆነ አማራ ጫት ቃሚ ቃልቻ የሆነ ሰው ሁሉ ጨርቁን ያጠቀ፡ርና የራሱን ጠጕር ያሳድግና በፊቱ እስቲንቄረቄር ድረስ ቅቤ ይቀባና በራሱ ላይ የጠቄረ ጨርቅ ይጠመጥምና ፲ና ፬መንታ ያላቸው ሁለት ዘንግ ይይዝና የጫት መያዣውን ስልቻ ያንጠለጥልና በአገር ቤት ውሥጥ እየሔደ ዛር አረጋግጣለሁ የታመመ አድ-ናለሁ ፈልፈላ አወጣለሁ እያለ ባንድ መንደር ይሔድና ካንድ ሰው ቤት ይገባል። በዚያም በገባበት ቤት የመንደሩ ሰው ሁሉ እንደዚህ ያሉ አዋቂ የሆኑ ቃልቻ ከገሌ ቤት መጥተዋል እያሉ ያንን ልማደኛ ጫት እየገዙ ቡናውን ዕጣኑን ቆሎውን በያይነቱ ወተቱን ዳቦውን ቂጣውን ቅቤውን እየያዙ ሴቱም ወንዱም ይሰበሰባል።አራትና አምስት ቀን ለሊትና ቀኑን እዚያው ተሰብ-ስበው የዛር ዘፈን ይዘፍናሉ ቃልቻውም የተሰበሰቡትን ሰዎች የዛር ዘፈን እያዘፈነ የአምልኮ ምርቃቱን በመረቀ ጊዜ የተሰበ-ሰቡት ሰዎች ሁሉ በተራ እየተነሡ እጁንና እግሩን እያገላበጡ ይሰሙታል።እንደዚህ እየሆኑ አራትና አምስት ቀን ካደሩ በኋላ ቃልቻው ደግሞ ወደአንድ አገር እንደዚሁ ለማታለል ይሔዳል እነዚያም አብረው ሲያጨበጭቡ ከሰነበቱት ሰዎች ሴቶቹ በግማሾቹ ሁለትና ሰስት፡በግማሾቹም አራትና አምስት፥ዓይነት ዛር ይፈልቅባቸውና የዘላለም ደዊአቸውን ተሸክመው በየ ጊዜው ሲያጕሩ ይኖራሉ። የነዚህም ሴቶች ባሎቻቸው በዚሁ ምክንያት የተነሣ ጫት ቃሚ ይሆኑና ለሚስቶቻቸው ዛር ጭዳ እየተባለ በመት በመቱ ላንዱ ዛርም ሴት ሐያና ሰላሣ በያይነቱ ዶሮ፤ አምስትና ስድስት በያይነቱ በግና ፍየል እየገዙ ለሚስ-ቶቻቸው ዛርዘላለሙን ሲገብሩ ይኖራሉ። እንደዚህም የሆኑት ሕዝቦች ሁሉ ቃልቻና ዛራም እየሆኑ በየአገር ቤት ውሥጥ እየተልከሰከሱ ይቀራሉ እንጂ ለመንግሥታቸው አይረዱም። ከነዚሁም ውሥጥ አንዴ የትዳሩን ሥራ ይተውና ጫት ቃሚ ይሆንና ከመቄየት ዘንድ ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃልቻ ዓይነት ሁኖ አገር ላገር እየሔደ ሲያታልል ይኖራል ።

የቃልቻው ማታለልና የሕዝቡ መታለል ብዛት ።

ይህ ጫት ቃሚ ቃልቻ ለሊት በጨለማ እየሔደ ተደብቆ እሰው ቤት ደጃፍ መሬት ይምስና በስላምና የተጻፈ ወረቀት ጠቅልሎ ይቀብርና ሰው ሳያየው ተመልሶ ይሔዳል ፲ና ፲፭ ቀን ያህል ይቈይና ከዚያ በኋላ መቸም ያንን ወረቀት መቅበሩን ያውቃልና እዚያ እቀበረበት ቤት ሔዶ እንግዳ መስሎ የቃልቻ ምልክቱን አድርጎ እንዴት ዋላችሁ ብሎ ከዚያ ቤት ይገባል ። እነዚያም ባለቤቶች ቃልቻ መሆኑን በወቁ ጊዜ ብጣም ደንግጠው አክብረው ይቀበሉታል ። ከዚያ በኋላ መቸም ለዚያ ለቃልቻ ዋና ምግቡ ያው ልማደኛ ጫት መሆኑን ሕዝቡ ሁሉ እንደአዋጅ ያውቀዋልና ጫት ባለበት ስፍራ ብግር በፈረስ ተልኮ ይገዛላታል ፡ ጫት ለመግዛትም የተላኩት መልክተኞች ጫቱን ገዝተው ተሸክመው ሲመጡ ይኸን ጫት ይዘን ክፉ ነገር የተነጋገርን እንደሆነ ይህ የተሸከምነው ጫት ለኒያ ለቃልቻ ሔዶ ይነግራቸዋልና ክፉ ነገር በሆዳችሁም እትያዙ እየተባባሉ እየፈሩ እየተንቀጠቀጡ ያን ጫት ይወስዳሉ ። ጫቱን ወስደው ለቃልቻው በሰጡት ጊዜ ያ ቃልቻ እነዚያን ጫት ገዝተው ያመጡለትን ሰዎች ይመርቅና ምራቁን ይተፋባቸዋል ፡ እነሱም ምርቃታቸውን ተቀብለው እንደተለመደው እግርና እጁን አገላብጠው ስመው ይቀመጣሉ። ከዚያ በኋላ ያ ቃልቻ የጫት መቃሚያውን የግምጃ መሐረብ ይዘረጋና ጫቱን በዚያ ላይ አድርጎ እንደእንስሳ በፉ ሙሉ ጕስጕሶ እያመነገኸ እየዘየረ የጥንቶቹን ቃልቾች ስም በዝየራ እያንሣሣ ይቅማል። ጫቱን ቅሞ ቅሞ በሰከረ ጊዜ ለቀሶ ይዠምራል።ማልቀስ ግን ጫቱ እስክሮት ነው ፡ እነዚያ የተሰባሰቡት የቃልቻው ማኅበርተኞች ግን ቃልቻው ጫት አስክሮት ለቅሶ ብጀመረ ጊዜ ምን ታይቷቸው ይሆን ምን መዓት ይመጣብን ይሆን እያሉ ይጨነቃሉ። ያም ቃልቻ ምንም ቢሰክር ልቡን ትንሽ ትንሽ አያጣምና እያለቀሰ እቤት እቤት እቤት እቤት እናንተ ሰዎች ብዙ መዓት መጥቶብናል ከዚህ ከመጣው መዓት አላህ ይሠውራችሁ አላህ ይጠብቃችሁ እያለ ይመርቃል። እነዚያም ሰዎች እንደልማዳቸው ምርቃቱን ተቀብለው ከፊተኛው ጭንቀታቸው ይታገሣሉ።ማለት ቃልቻው ተመረቁን ማነኛውም ነገር አይነካንም በሱ ምርቃት የሚመጣብንን መዓት ሊያሳልፍልን ይችላል እያሉ በሆዳቸው ያስባሉ። ከዚህ በኋላ ቃልቻው ያች የቀበራት ወረቀት አለችና እናንተ ሰዎች በዚህ በቤታችሁ ፈልፈላ ተቀብሮባችኋል ይኸንን ፈልፈላ ያወጣሁላችሁ እንደሆነ ምን ትሰጡኛላችሁ ይላቸዋል። ይኸንን ባላቸው ጊዜ እየተሸቈጠቈጡ ውነት ሳይሆን አይቀርም በዚህ ጊዜ ከብቶቻችን አለቁብን በዚህ ጊዜ እንደዚህ ታመምን ክብትም አልረባላችሁ አለን ገንዘብም አልበረከትላችሁ አለን ለካ ፈልፈላ ቢቀበርብን ነው እያሉ እየተገረሙ ጌታዬ በርስዎ መጀን ይሁንና ፈልፈላውን ካወጡልን እርስዎ ያሉትን ያህል ገንዘብ እንሰጣለን እያሉ ይኸንኑ ሲያደንቁ ከቃልቻው ጋራ ጫት እየቃሙ ሲያጨበጭቡ ያድራሉ፡ሲነጋ ጧት ያ ቃልቻ ተሰብሰቡ ፈልፈላውን ላውጣላችሁ ይልና ሰዎቹ ሲሰበሰቡ ያንን የቀበረውን ወረቀት ይቈፍርና ያወጣላቸዋል። ያንን ባዩ ጊዜ እየተገረሙ የመንደሩ ሰው ሁሉ ዛሬ በገሌ ቤት የመጡት ቃልቻ በነገሌ ፈልፈላ ተቀብሮባቸው ኖሮ አወጡላቸው እያለ ሕስላም እማሬው ሁሉ እየተደነቀ ያወራል ። ያም ቃልቻ እንደዚህ ያታልልና ብዙ ገንዘብ ይሰጡትና ይሔዳል ይኸው ማታለሉ ለዘላለም መታሰቢያ ሁኖት በዚያ አገር ተመልሶ በመጣ ቍጥር ሕዝቡ ሁሉ እንደታቦት አክብረው ይቀበሉታል። ወንድሞቼ ሆይ ፤ በጣም የሚገርመው ግን ከቃልቻው ማታለል የብዙው ሰው መታለል ነው ። ይልቁንም ደግሞ የሚገርመው እነዚህ የቃልቻው ማኅበረተኞች በየቤታቸው ባሉ ጊዜ ቃልቻው በሌለበት ቦታ የቃልቻውን ስም ለማንሣት ይፈራሉ። ድንገት አንድ እንግዳ ሰው እንኳን እቤታቸው መጥቶ በጨዋታ የተነሣ የዚያን የቃልቻ ስም ያነሣ እንደሆነ የቤቱ ሰው ሁሉ ተው ተው የሳቸውን ስም አታንሣ በሳቸው መጀን ደሉና ዕጣን ያጨሳሉ። እደዚህም የሚሉበት ምክንያት የቃልቻ ስም ቃልቻው በሌለበት በክፉ የተነሣ እደሆነ ባለበት ቦታ ለማወቅ ይችላልና አድ ጊዜ ሊፈጀን ይችላል እያሉ ነው በሆዳቸው የሚያስቡት ።

ይኸም ሁሉ ነገር መንሥኤው ጫት ነው ይኸም ሕዝብን ሲያታልል የሚኖር ቃልቻ መዮመኘ ጫት መቃም ባይለምድ ቃልቻ አይሆንም ነበር ።

ይህ ጫት በሐረር አውራጃ አራሽ ገበሬን ባለምድርን ጕድቶ ይኖራል ፤ እንግዴህ ገበሬ ባለመሬት የሆነ ሰው ሁሉ በማንኛውም ጊዜ ዘር ለመዝራት የዘራውን ለማረም፡ለማጨድ፡ለመውቃት፡ለመሰብሰብ ይኸንን ለመሰለ ሥራ ሁሉ በየጊዜው እንደመጣ አምሳ ወይም መቶ ፤ ሁለት መቶ ሰው እርሻውን እንዲሠራለት ጉዛ ይለምንና በቤቱ ሙሉ እንደተቻለው ጠላውን ጠጁን ምግቡን የርድ ሠንጋውን ይኸንንም የመሰለ ሁሉ በያይነቱ ሲደግስ ይከርምና የሥራ ቀጠሮው ቀን ሲደርስ ያንን ልማደኛ ጫት ለማስገዛት ፪ና ፫ ሰው ይልካል።ይኸውም ጫት የሚባለው ቅጠል ዕለቱን የተቈረጠ ቀን ካልሆነ በተቀር ተቈርጦ ውሎ አድሮ ከጠወለገ በኋላ አይበላምና እነዚያም ጫት ለመግዛት የሔዱ ሰዎች በ፫ና በ፬ ሰዓት ጫቱን ገዝተው ይመጣሉ። ያም ለጉዛ ተለምኖ ለሥራ የተሰበሰበ ሰው ሁሉ ጫቱ እሲቲመጣ ድረስ በየዕንጨቱ ጥላ ሥር ይተኛል እንጂ ጫቱ መጥቶ ካልቃመ አይነሣም ያም ጫት ከመጣ በኋላ ጫቱን ይከፋፈልና እየቃመ እንደእንስሳ ሲያመነዥህ ሁለትና ሶስት ሰዓት ይቀመጣል። ከዚያም በኋላ ፯ና ስምንት ሰዓት ሲሆነው ለሥራ ይነሣል። ጊዜውም የዝናብ ወቅት የሆነ እንደሆነ የገበሬው እርሻ ሳይሠራለት ይዘንብና ድካሙ ሁሉ በከንቱ ይቀራል ። እንግዴህ ያ ገበሬ በቤቱ የደገሰው መጠጥና ምግብ ለሰውነት የሚስማማ ጥንካሬ የሚሰጥ ከቤቱ እያለ ጫት የሚባል ቅጠል ሥራውን ሁሉ ማስታጐሉ በጣም አይገርምም? ያም ገበሬ ዘወትርም በየጊዜው እንደዚሁ ጉዛ ለምኖ ከቤቱ ደግሶ ለማሠራት እያሰበ ይህ ጫት ሥራውን ያስታጕልበታል። ለጉዛ የተለመነውም ሰው ጫቱን ቅሞ ለመሥራት በተነሣ ጊዜ ያ የቃመው ጫት እንደስካርና እንደዕብድ እያደረገው የገበሬውን እርሻ ያበላሽበታል እንጂ ደኅና አድርጎ አይሠራለትም። በከ-

ንቱ ሥራው ባክናበት ይቀራል ባላገርም የጫትን መበልጠዋ እያየ እህል ማረሱን እየተወ እርሻውን ጫት ብቻ እየተከለ ብዙው መሬት ጫት እየተተከለ ጠፍ ሁኖአል የእህል ገበሬ ከስንት አንድም አይገኝ ።

ይልቁንም የመንግሥት ግብርና የበለ ርስት ጢሰኛ የሆነ አራሽ ገበሬ፣ያረሰውን እህል በሁለትና በሦሬት ቀና አንዳንድ ጭብጥ ጫት ዘወትር እየገዛ ዓመት ሙሉ ለፍቶ በጕድጓድና በጕተራ የከተተውን እህል ይጨርስና እንደገና ከነቤተሰቡ ችግር ይገባና የዘራው እህል እስቲደርስለት ድረስ በችጋር እየተቈላ ይኖር ነበር።(ይህ ጫት ብዙ ታሪክ አለው ዘወትር ጫት የሚቅም ሰው መኻን ይሆናል ልጅ አይወልድም፣ ማለት ጫቱ ያመክነዋል) አሁን ግን የጨርጨር አውራጃ አበጋዝ ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት የራሳቸውን ጥቅም ሳይፈልጉ ድካማቸውን ሳይመለከቱ በተሰጣቸው እውቀትና ጕልበት ለጌታቸው በውነት በትክክል የሚያገለግሉ ትጉህ መሆናቸውን ማንም ሕዝቡ እንዲመሰክርላቸው ያለጥርጥር እምናለሁ፣(ግን አንዳንድ ሰነፎች እውቀት የሌላቸው የሰውን ገንዘብ ለመንጠቅ የሚያስቡ በገንዘብ የሚታለሉ ሰዎች ሳይጠሏቸው አይቀሩም ይመስለኛል) እንግዲህ ክቡር ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት እሳቸው በጨርጨር ሳይሾሙ አስቀድሞ በፊት የጨርጨር አስተዳደር በጣም የሚያሳዝን ነበር። ደካማ ለፍቶ ያገኘው ገንዘቡን ሳይበላ ሹሙና ጕልበተኛ ወስላታ እየነጠቀ ይበላበት ነበር።በዚያ ጊዜ ጨርጨር በጨለማ ተሸፍና ታውካ መኖሯን ማንም ሰው አይስተው በማለት ዘርዝሬ አልጻፍኩትም ።

እንግዲህ ወደልማደኛው ጫት እንመለስ ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ይህ ጫት የሚባለው ቅጠል ሀገር የሚያጠፋ መሆኑን ተረድተው ይኸንን ጫት ተሀገር ተነቅሎ እንዲጠፋ ለማድረግ አሰቡ ። ይኸንኑ አሳባቸውንም ለግርማዊ ንጉሥ አመልክተው ግርማዊ ንጉሥም መልካም አሳባቸውን ተረድተው ፈቀዱላቸው ።

ከዚህ በኋላ ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት በጨርጨር አውራጃ ውሥጥ ያለ ጫት ሁሉ የጫቱ እግር በወረዳ ምስለኔና በቡርቃ ሹም እየተቈጠረ ባንድ እግር ጫት ፩፪ መሐለቅ ግብር ባመት ይከፈል ። ይኸውም ግብር ባመት ባመቱ በንዳንዱ እግር ጫት ፩፪ መሐለቅ እየቀጠለ ይሔዳል። ለመገበር አልችልም የሚል ግን ይንቀል ብለው ለሕዝቡ በዋጅ አስታወቁት።(መቸም ይኸንን ጫት አንድ አነስተኛ ደኻ ፫ና፬ሺህ እግር ጫት አያጣምና) ስለዚህ ግብር ለመክፈል የማይችል መሆኑን እየተረዳው አሁን በጨርጨር አውራጃ ውሥጥ ሁለት እጅ የሚሆን ጫት ተነቅሎ አንድ እጅ የሚሆን ቀርቷል ። ይኸውም የጫት ግብር ባመት ሁለት መሐለቅ በመቀጠሉ ዛሬ ባመቱ አካሔድ ያንዱ እግር ጫት ፯ስድስት መሐለቅ ሁኖአል። እስከ አንድ ዓመት ግን በጨርጨር አንድ የጫት እግር ይገኝ አይመስለኝም ።

አራሽ ገበሬና ባለምድርም ለግብርናው አውኮት የሚኖረው ጫት ተሀገር ተነቅሎ በመጥፋቱ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሣችን እያለ ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትን እያመሰገነ ብዙ ተስፋና ደስታ አድርጓል ። የግብርናውም ሥራ ጫት በመጥፋቱ ተከናውኖለታል ። ይልቁንም ደኻ ገበሬ (ገባርና ጢሰኛ) ዓመት ሙሉ ለፍቶ ያመረተውን እህል ጫት እየገዛበት እህሉን እየጨረሰ እችግር ይገባ የነበረው አሁን ጫት በመጥፋቱ ደኻ ገበሬም የእህል ቀርስ እያገኘ በደኅና ይኖራል። አንዳንድ እውቀት የሌላቸው ሀብታሞች በጫት ሽያጭ ብልጥግና ያገኙ የነበሩትና ጫት ቃሚ ቃልቻዎች ግን ጫት ተነቅሎ በመጥፋቱ በጣም ቅር ሳይላቸው አይቀሩም ይመስለኛል። ወደፊት ግን ከ፫ዓመት በኋላ ድንገት እውቀት አግኝተው ጫት የነቀሉለትን መሬት ቡና ሌላም አታክልት ተክለው የበለጠ ጥቅም ባገኙ ጊዜ፣ቃልቻዎችም ጫት መቃም ረስተው ለሰውነት ጤና የሚሆነውን እህል እየበሉ የሰውነታቸውን በጎ መሆን በተረዱት ጊዜ ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሣችን እያሉ ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያትን ማመስገናቸው አይቀርም ።

ይኸንንም ማለቴ ጥንት ጨርጨር በመላው የእህል ዓሥራት በውድማ እየተሰፈረ ዘካው ለመንግሥት እጕድጓድ ይገባ ነበር ። በዚየም ጊዜ ለዚሁ ሥራ ታዘው የሚወጡት ሠራተኞች ከባለእህሉ ጋራ በገንዘብ ውሥጥ ለውሥጥ እየተስማሙ ሁለቱን እጅ ዘካ በውድማ ሽምተው እያስቀሩ አንድ እጅ የሚሆን ነበር ለመንግሥት የሚባለው። ከዚህም በተቀር የዚህ የዘካ ሥራ ብዙ ጕዳት በውሥጡ አለ (ማለት መንግሥትንና ሕዝብን ጕድቶ ይኖራል ። አይስማሙም ነበር ፥) በጕድጓድም የገባው እህል ከመቈየት ዘንዳ ሁለቱ እጅ እየበሰበሰ እየፈሰሰ አንድ እጅ የሚሆን ብቻ ነበር ለመንግሥት ጕዳይ የሚሆነው ። በኋላ ግን ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ይኸንን ሁሉ ተረድተውት ዘካ እንዲቀርና ሀገር በቊርጥ ግብር እንዲያድር ከግርማዊ ንጉሥ አስፈቅደው የጨርጨር አውራጃ በመላው የእህል ዓሥራት ቀርቶ በቊርጥ ግብር አደረ በዚያም ጊዜ ብዙ ሕዝብ ቅር ብሎት ቊርጥ ግብርን አልወደደም ነበር ። በኋላ ግን እያደር ጥቅሙን ተረዳውና ቊርጥ ግብርን ወደደ። ይልቁንም ዛሬ ማንኛውም አራሽ ገበሬና ባለምድር የሆነ ሁሉ ጥቅሙን በጣም ተረዳውና በጣም ደስ አለው ። አንዳንድ ሥራ የማይወዱ ሰነፎች ሰዎች ግን ዛሬውኑም ቅር ብሏቸው ቊርጥ ግብርን አልወደዱም። እነሱም ወደፊት እያደር ከቀን ብዛት የሥራን ጣዕም ተረድተው ስንፍናቸውን አስወግደው በተሰጠ ጕልበታቸው ለጥቅማቸው ሠርተው ጥቅም ባገኙ ጊዜ ቊርጥ ግብርን መውደዳቸው አይቀርም ብዬ ነገሬን ጨረስሁ ።

የዓሰበ ተፈሪ ቢሮ ሳንትራል ጸሐፊ ሺፈራው ወልደየስ ።

መመካት እንዳይገባ ።

ሁላችን የሰውን ሥራ እየነቀፍን እኔ ብሆን እንዲህ ባደረግሁ እንጂ እገሌ እንዳደረገው ባላደረግሁም ነበር እያልን መመካት ልማዳችን ነው ።

እንደዚህ ሁሉ አንድ ቀን አንድ ንጉሥ አደን ፍለጋ ወደ ውጭ ወጣና አንድ ጫካ አጠገብ ደረሰ ። በዚያ ሲያልፍ ድምፅ ሰማና ለማዳመፅ ቢቀርብ አንድ ሰው ከሚስቱ ጋራ

ሁኖ አየ ባልዋ ስንጨት ሲቈርጥ ሳለ ሚስቱ እግዚአብሔር ከቶውንና በጎውን ከምታስታውቅ ዛፍ ፍሬ አትብለ ብዒቸው ሲያበቃ ሔዋን ከፍሬዋ በመብላትዋ ብዙ አጥፍታለች ። እርስዋ ያምላክን ቃል ጠብቃ ብትሆን ሁሉ ቀን እንዲህ ባለ ብርቱ ድካም ባለበት ሥራ መከራችንን አናይም ነበር አለች ። ባልዋም ሔዋን አትብሉ ካለችው ፍሬ በመብላትዋ እውነት አጥፍታለች ። ግን አዳም ያለችውን ሰምቶ አስተውሎ አይሆንም ማለት ይገበው ነበር ። እኔ አዳም ብሆን አንችም ሔዋን ብትሆኝና ከተከለከለው ፍሬ ብላ ብትይኝ እንቢ ባልኩ ነበር እያለ ሲመከ ንጉሥ ይኸንን በሰማ ጊዜ ወደነሱ ቀረበና እንዴት ባለ ብርቱ ሥራ ትጨነቃላችሁ አላቸው ።ነዎን ጌታችን ቦጧት እስከ ማታ ብርቱ ሥራ እየሠራን የሚበቃ የዕለት ምግብም አናገኝም አሉት ። ንጉሡም እንዳች ሥራ ሳትሠሩ እኔ እመግባችኋለሁና ከእኔ ጋራ ኑ ብሎ ይዟቸው ወደ ቤቱ ሔደና ያማረ ስፍራ በየዓይነቱም የሚያስፈልጋቸውን ምላብ ልብስ የተሰናዱ አሽከሮችም ሰጥቶ አስቀመጣቸው።ምግባቸው ም በገበታው ላይ ልዩ ልዩ ዓይነት ሁኖ ይቀርብላቸው ነበር ። ግን ከልዩ ልዩ ዓይነት የመብል ፊቀው ጋራ አንድ የተዘጋ ረዘም ያለ ሣጥን አይለይም ነበር።

ሚስቲቱም በሣጥኑ ውሥጥ ያለውን ነገር ማየት ፈለገች ግን በዚያ የነበሩ መኳንንት ማንም ሰው እንዳይነካው ክልክል መሆኑና በዚያ ውሥጥ ያለውን ነገር ማንም ሊያየው ንጉሡ አለመፍቀዱን ነገሩት አንድ ቀንም ባልዋ ቢመለከት ሚስቱ መብል አልበላም ብላ አዝና ተክዛ አየት የዚያን ጊዜ ምን ሁነሻል ብሎ ቢጠይቃት በሣጥኑ ውሥጥ ምን ነገር እንዳለ ታላየሁ ዕረፍት አላገኝም አለችው ።እርሱም እንዴት ያለሽ ሞኝ ነሽ ፤ እንዳንነካው መከልከላችንን ታውቂ የለምን ብሎ ተቈጣት ። በዚያን ጊዜ ሚስቱ እያለቀሰች እንባዋን እያፈሰሰች ሣጥኑ ካልተከፈተ ራሴን መግደሌ ነው ስትለው ጊዜ ባልዋ ወዲያው ሐሳቡን ለውጦ ሣጥኑን ከፈት ቢያደርግ ከሣጥኑ ውሥጥ አይጥ ወጥታ በረረች ። በዚያን ጊዜ አይጥዋን እየተከታተሉ ቢሮጡ ከንድ ቀዳዳ ውሥጥ ተሸጕጠችና ሊያገኙዋት አልቻሉም ። ንጉሡም መጥቶ አይጢ ወዴት ገባች ብሎ ቢጠይቅ ሰውዬው ጌታዬ ባለቤቱ በሣጥኑ ውሥጥ ያለውን ነገር ታላየሁ ብላ ብታስቸግረኝ ሣጥኑን ከፈት ባደርገው አይጢ በርራ ሔደች ብሎ መለሰ ። ንጉሡም እዬ ፤ እዬ ፤ አሁን አንተ አዳም ሁኜ ብሆን የሔዋንን ምክር በጅ ባላ፡ኩም ነበር ስትል አልነበረም ። ተስፋ የሰጠኸውን ቃል መጠበቅ ይገባህ ነበር ብሎ ወደሴትዬዋ መለስ አለና አንች ሰነፍ ሴት የሚያስፈልግሽ ምግብ እንደፈለግሽ አግኝተሽ ነበር ። ግን እርሱ አልበቃብሎሽ እኔ እንዳትነኩትና እንዳይከፈት ከዘገኩት ሣጥን ልትበዪ ፈለግሽ ። አሁንም ወደ ድኻ ተመልሳችሁ ሥራችሁን ሥሩ እንደገናም አዳምንና ሔዋንን አትሙ እናንተ ከነሱ የምትብሱ ሰዎች በነሱ መመካት አይገባችሁም አላቸው።

የእግዚአብሔርንና የንጉሥን ትእዛዝ አክባሪዎችና ጠባቂዎች እንሁን። ወደፈተና እንዳንገባም ከትምክሕት እንራቅ ።

ዶክቶር ባዚል ማሮኮስ የጥንት የግርማዊ ንጉሥ ሠራተኛ የርሻ መሐንድስና የከብት ሐኪም፤የንብ ማር ባች ሥራ አዋቂ ዋና የሰብልን ጠላት አንበጣን ለማጥፋት ቀጥሎ ያለውን ይመክራሉ ።

አ ን በ ጣ ።

በዚህ ዓመት በኛ አገር ውሥጥ ላለው እጅግ ከዚህ ከሚያስፈራ እንስሳ ለመዳን ከመጀመሪያው ጀምሮ የሚያስፈልገውን ካላደረጉ በፍጹም የርሻን ሥራ እንዲያጠፋ የታወቀ ነው ።

ትንሽና ትልቅ የግብርናን ሥራ የሚሠሩ ሰዎችና በገሩ ውሥጥ እርሻን ለማከናወን የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ይህነን እንስሳ እንደተቻለ ያህል ለማጥፋት የሚገባቸው ነው ።

እንዲያውቁትም ቀጥሎ ያሉትን ማስረጃዎች እንሰጣለን። አንበጣ የሚጠፋበት አደጋ አኳኋኑ እንዲህ ነው ። የዚህ የንስሳ መምጣት ትልቅ አደጋ ማምጣት የሚችል ነው ። ደግሞም ለርሻ በጣም ጥፋት ነው ። ላትክልትም ፤ ለደንም ፤ ለጫካም በሙላው ለቅጠላ ቅጠል ሁሉ ማለት በሰብል ወራት ይህ እንስሳ በመጣ ጊዜ በጣም ጠንቅ ነው ።

ለዚሁም ምሳሌ ባውሮፓ ባንዳገር ያለ የሌላቸውን አንበጣ በልቶባቸው አያሌ ሰዎች የነበሩበትን በታ ትተው በዚህ ባደጋ ምክንያት ከሌላ በታ ተዛውረው የጥንት በታቸውን ለመልቀቅ ማዴታ የሆነባቸው ሰዎች አይተናል ።

በጭሩ አንበጣ ትንሽ ወይም በጣም -ኢሚዲቴ) ቀዝቃዛ የሆነ በታ ይወዳልና ይልቁንም ዘለቄለም የሚቀዘቅዝ አገር ይወዳል ።

ከመሬት ወይም ብዙ ሣር ካለበት ላይ አያርፍም ያልፈዋል ፤ በዶ የሆነና ካልታረሰ ሥፍራ ላይ ማረፍ ይወዳል ፤ አንበጣ ተልቅና ትንሽ ዓይነት ነው ትንንሾቹ ክንፍ ያነሳቸው እየዘለሉ ነው የሚሔዱ ፤ ትልልቆቹ ክንፍ ያላቸው ግን ከንድ አገር ወዳንድ አገር ርቀው ይዘዋወራሉ ።

በሚሔዱበትም ጊዚያት በነፋሱ አመራርና አኪያሔድ ነው የሚጓዙ ጠላታቸው አንበጣንና እንቍላላቸውን የሚበሉ ተቃዋሚዎቻቸው አዕዋፍ በራሪዎች ናቸው። አንበጣው በሚያርፍበት ስፍራ ደረቅ ሣር ሰብስቦ በዙሪያው አድርጎ እሳት ለኩሶ አንበጣውን ወደ እሳቱ እንዲቀርብ እያደረጉ መምታት ነው ።

ደግሞ ቀጥሎ ባለውም አኳኋን ለማድረግ ይቻላል ።

ወይንም ካደረበት ስፍራ ማልዶ አንድላይ እንደሰፈረ በበትር መፍጀት ነው ። ደግሞ እላይ እንደተባለው በደረቅ ሣር ማቃጠልና መፍጀት ነው ። ማለት የተሰበሰበው አንበጣ ሁሉ ጢስ ባየ ጊዜ እየተነሣ ወደሌላ ቀጥታ ይሔዳል። ደግሞ ብዙ ነጭ ጨርቅ ዘርግቶ ካንድ በኩል ወደተዘረጋበት ጨርቅ እንደሚሔድ እያደረጉ ነድቶ እጨርቁ ላይ ሲያርፍ እየጠቀለሉ በከረጢት ውሥጥ እያገቡ ያለችግር መፍጀት ይቻላል ።

ወይም ካደረበት ስፍራ አንድ ላይ እንደተሰበሰበ በጧት ወይንም ማታ ሲሰፍር ጋዝ የረጩበት እንደሆነ ጋዙ ሲነካው ሁሉም በጭራሽ ይሞታል። በብዙ ያስፈልጋል እንጂ በአሲድ ፌኒክም ረጭቶ ማጥፋት ይቻላል። ይህ ክፉ እንስሳ በሚመጣበት

ብፍራ ያገሩ ሹም ባላገሮቹን አዘ አሰብስቦ ከዚህ በላይ እንደተባለው አንበጣው እንዲጠፋ ማድረግ ነው ። በውሮፓ ይህን ክፉ እንስሳ ለማጥፋት በአየር ላይ እንደደመና ጠቍሮ ሲሔድ ባውሮፕላን ወጥተው (በኤር ኦ ሰፊክሲዎን) በሚባል የጢስ መርዝ ያጠፉታል ።

እኔም ካንድ አገር አንበጣ ቢመጣባቸው ጠመንጃቸውን እየያዙ እየወጡ ይህን ክፉ እንስሳ ለመቃወም ብዙ ሰዎች ተሰብስበው ሲቃወሙ አይቻለሁ ለዚሁም ያይን ምስክር ነኝ።

ስለ ቅበላና ስለ ጾም

ቅበላ ማለት፥ ንጉሥ ወደ ውጭ ሀገር ወጥቶ በተመለሰ ጊዜ፥ መኳንንቱና ሠራዊቱ፥ ጳጳሳቱና ካህናቱ የማዕርግ ልብስ ለብሰው፥ በወርቅ መጣሪያ አጊጠው ከተማይቱም እንደ መስ- ከረምና እንደ ጥቅምት በስነ ጽጌያት ተሸልማ፥ባንዲራው በየ- ደጃፉና በየቤቱ ላይ ቢል ቢል እያለ ሰልፉ ግሩና ተኝ ተሰልፎ በልልታ በእቢልታ እንኳ ደኅና ገቡ እያለ ንጉሡን መቀበል እንዲገባ።ሙሽራም ሚስቱን ይዞ በተመለሰ ጊዜ በመንደሩ ያለ ወንዱ ሴቱ፥ልጁ አዋቂው በዘፈን በጨዋታ፥ በከበከብ በደስታ እንዲቀበሉት፥ እዲሁም በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን እኛም በፍቅር ጌጽ አጊጸን። የፍቅር ባንዴራ ከልቦናችን ላይ ሰቅለን አፋችንን ክፉ ነገር ከመናገር፥ዓይናችንንም ክፉ ነገር ከማየት፥ ጆሯአችንንም ክፉ ነገር ከመስማት ከልክለን የልቡናችንንም ከተማነት በጽጌ ፍቅር አስጊጠን ከኃጢአት ሁሉ ርቀን ከእግዚ- አብሔር ዘንድ የነፍሳችንን መድኃኒት የምናገኝበት ጾም ገባልን እያልን ጾምን መቀበል እንዲገባ የቅበላን ትርጓሜ በንጉሥና በሙሽራ እናስታውቃለን ። ጾምም ማለት የነፍስን ቍርል የምትፈውስና የሥጋን ፈቃድ ሁሉ የምታደክም ማለት ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምን ዕፀ በለስን በመብላት ምክንያት ዲያብሎስ ድል እንደነሣው በባሕርይ ዕውቀቱ ስላወቀ እርሱም ገዳም ገብቶ መጾም በጀመረ ጊዜ ሰይጣን እንደለመደ ተልባ መስሎሽ፥ ሰናፍጭ ትቀምሽ እንዲሉ እንደ አዳም በመብል ምክንያት ድል የምነሣው መስሎት በቀዳዳ ሽልቻ ዳቦ የያዘ መስሎ ሁለት ደንጊያ በጁ ይዞ እሊህን ደንጊያዎች ኅብስት ይሁኑ ብለህ እዘዝና አንተም እኔም እንመገብ ብሎ ቢፈታተነው ሰው የሚድን በእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ በኅብስት እንዳይደለ ተጽፎብሀልና ፈጣሪህ እግዚአብሔርን በመብል ምክንያት ልትፈታተን አትችልም ብሎ ሰይጣን ከኋላዬ ወግድ ባለው ጊዜ እንደጢስ ተኖ እንደትብያ በኖ ጠፍቷል ።

እኛም በእግዚአብሔር ቸርነት ነው እንጂ ምንም በሥ- ራችን ዋጋ ማግኘት ባንችል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ የሠራውን ሥራ ሁሉ በርሱ ፈጻሚነት እርሱን አብነት አድርገን እየሠራን አፋችንን በጸሎትና በአርምሞ ልጓም ጕትተን ልቡናችንን በፍቅረ ቢጽ ወስነን ፥ ዓይናችንን በአንቃዕድዎ ፥ እጃችንን በሰፊሕ ፥ እግራችንን በቀዊም ወስነን ፥ ሥራችን በግብዝነት ሳይሆን ውሥጡና አፍአው እንደታጠበ ሳህን ላያችንንና ውሥጣችንን ንጹሕ አድርገን ፥ ጾማችንን ሰው ይይልን ብለን ለሰው ይምሰል ሳናደርግ ፥ ሐሜትን ፥ ቅንአትን፥ ምቀኝነትን ፥ ቍንኩልን ፥ ፀብን ፥ ክርክርን ፥ መለያየትን ፥ ቂምን ፥ በቀልን ፥ መናናቅን ከእኛ አርቀን ለሥጋዊ መብል ሳንሳሳ ለነዳያን እንደችሎታችን ከገንዘባችን ምጽዋት እየሰጠን እገሌ ኃጥእ ፥ እገሌ ጻድቅ ፥ እገሌ አማኒ እገሌ መናፍቅ ሳንበባል ይህን ጾም በስምምነት የጾምን እንደሆነ አገራችን ከክፉ ነገር ትጠበቃለች።እኛም ከሰይጣንና ከጠላት ፈተና እን- ድናለን፡ከታዘዘ መቅሠፍት እናመልጣለን፡ከብርሃነ ትንሣኤው ም በደኅና እንደርሳለን ።

መወድስ ።

መቃብረ አበው ኀዘን በእንተ ሲሳዩ ።
እስመ ከረሠ አብ ስምዖን ህየንተ መቃብር ተፈጥረ ።
ባሕቱ ይትፌሣሕ መቃብረ አበው ድኅረ ።
እስመ ስምዖን ዘምስለ ደቂቁ ውስቴቱ ኀደረ ።
እንዘ ኢያተርፍ ሕፃናተ።
ሊቀምርፋቃት ሞተ ጥኢሞ እስከ አንከረ ።
ስሞዖንሂ መፍቀሬ ሰብእ እንተ ኢይጸግብ ወትረ ።
ኢያትረፈ ለዘመዱ ዘርአ ወማዕረረ።
እስመ ኢፈለጠ ስሞዖን ድኅረ ምስለ ሰብእ ኅብረ ።
ብእሲቶ ወብእሲ ዘእግዚአብሔር አስተጻመረ ።

እጭር ዋዜማ ።

ለስምዖን ጽድቀ አንቲእሁ በዓለም ተዐውቀ ።
እስመ ተሴሰየ ስምዖን ፍሬ ጻማሁ ደቂቀ ።
ደብተራ ወልደ ኪዳን ዘሐረር መድኃኔ ዓለም።

ስለኦቶሞቢል ዘበኞች ትጋት ።

የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ሐሙስ ለጕዳዬ በ፰ሰዓት ወደገበያ ሄጀ ነበርና ጕዳዬን አከናውኜ በ፱ሰዓት ወደቤቴ ስመለስ አንድ የግሪክ አገር ሰው እሙሴ ግሊዝ ሆቴል አቅ- ራቢያ በኦቶቢስኪሊት ተቀምጦ ሲሄድ አንዱን መንገደኛ እግ- ሩን አስዳጠና ጣለው። ይኸውም የተዳጠው ሰው መውደቁን ዘበኞች አይተው በፍጥነት መጥተው ያስዳጠውን ሰው ከነኦቶ ቢስኪሊቱ ያዙትና ናና ወደቢሮ እንሂድ ይኸንን ያስዳጥከውንም በሽተኛ ይዘን ብለው ቢሉት በሽተኛውን እናንተ ወደሐኪም ቤት ይዛችሁ ሂዱ እኔ ወደሥራዬ እሄዳለሁ ብሎ ወደቢሮ ለመሄድ እንቢ ብሎ እሩብ ሰዓት የሚሆል ከዘበኞቹ ጋራ ሲጨቃጨቅ ቈይቶ ነበረና በኋላ ግን ሕግንና ደንብን መመልከ- ትና መሥራት የዘባቸው ሁኖ የከተማውን ጥበቃ ሥልጣን የተሰጣቸው ታማኝ ዘበኞች እስካሁን ድረስ ሰው አስድጠህ ወደቢሮ በሽተኛውን ጭምር ይዘን እንሂድ ብለንብንልህ እንቢ በማለት እስካሁን አውክህ አቈየኸን። አሁን ግን በማክበር ለምንንህ እንቢ ካልክና ማዕረግ ከጠላህ ሰው አስድጠህ እንዲሁ ያስዳጥከበትን እኳኋኑንና ሥራቱን እቢሮ ሄደህ አለቆቻችን ሳይመረምሩህ እንቢ ብለህ ለመሄድ አንተ እንኳን ብታስብ እኛ ታማኞች ዘበኞች ሰው አስድጠህ በናይህ አንተን ለመልቀቅ የተሰጠን ደንብ የለምና በክበሬታና በማዕረግ መሄድ ከጠላህ

ብግድ እንፁስድሃለን ብለው ኃይላቸውንና ጉልበታቸውን መን-ግሥታቸውን አድርገው ይኸንኑ ያስዳጠውን ሰውዬ ወደ ጽዳት ቢሮ ዳኝነት ቤት ለመሔድ ፈቃደ ሁኖ እሺ ስላላለ ቀኝ እጁን ይዘው ከመቅጽበት እያዳፉ ተለምኖ እንቢ ያለውን በመንገድ እየገፉ ይዘውት ሲኼዙ የአቶሞቢል ዘበኞችን ላያቸው በትጋታ-ቸው አኳኋን በጣም ደስ ያሰኙ ነበርና ይኸንን ብትጋት ሀብ-ታምና ደኻ ሳይመርጡ በታዘዙበት ሥራ ላይ በትጋት በርትተው በመሥራታቸው ለተመልካቾችና ሕግና ደንብን ለሚከተሉ ሁሉ ደስ የሚያሰኙ ስለመሰሉኝ ይህችን ያየኋትን እውነተኛ ነገር ገልጩ ጻፍኩ ። የጥፋት ሥራ የሠራ ሰው የመንግሥት ዘበኞች ሥርዓታቸውን ለመፈጸም ሲፈልጉት ትልቅም ቢሆን ትንሽ መታዘዝ ይገባዋል እንጂ እምቢ ማለት የማይገባ ነው። እምቢ የሚል ቢገኝም እንደዚሁ ውርደት ያገኛል እንጂ ጥቅም አያገኝም ። በለዚህ ለመንግሥት ዘበኞች መታዘዝ እንዲገባ ላንባቢዎች እናመለክታለን ። በቀለ ዘለቀ ።

ስለ ሁለት አታላዮች ።

አንደኛው አታላይ ለዚያ አብሮት ላለ ኋደኛው ዛሬ ጥቅማችን ቀርቶ ሳንጠጣና ሳንሰክር እጅግም ደስ ብሎን እንዳንውል ቀኑ የተረገመ ቀን ሆነብን እስኪ ምን እንዲሻለን አስብ አለና ብሶቱን ነገረው ።

ሁለተኛውም አታላይ አለው፤ አሁን እንኳንስ ለኛ ይቅርና ለብዙ ሰው አጥጋበን እንውልም ይመስለኛልን ፡ የዚህስ ነገር ሐሳቡ ቅርብ ነውና በል እንካ ይዘህ ሒደህ ሙሉ ልብሴን በሐ-ራጅ ስፍራ እንዳወጣ ሽጠው አለና ሰጠው።ይህም የኋደኛውን ምክር ሰማና ታዛዡ አታላዩም ኋደኛው እንዳለው ልብሱን ወስዶ እንዳያወጣ ሸጠው። ነገር ግን ባለ ልብሱ በጕን ሁኖ ገዢና ሻጩ ሲሰማሙና ገንዘብም ሲቀባበሉ ያስተውል ነበርና ኋደኛው ገንዘቡን ከጁ እንዳገበ በወቀ ጊዜ ገንዘቡን ይዞ ዘወር እንዲል ባይኑ ጠቀሰውና በሩጫ ሔደ ። ያንን ገንዘቡን አፍሶ የገዛውን አትራፊ ሰውዬ አንተ ሸማዬን ማን ሰጠህ ብሎ በዳኛ ከሶ ሸማው-የሱ መሆኑን አስመስክሮ ተቀበለው በዚህ ነገር ግን የ፫ቱም ደስታቸው እኩል ሆነ፤ ያም በገንዘቡ ገዝቶ ልብሱንም መልሶ በመሔዱ ሳይቈጭ እጅና ፈንጅ ሁኖ ተይዞ ባጭር በመገላገሉ፥ እነሱም በጥቅማቸው በጣም ደስ እያላቸው ለመለያየት በቁ። እኔ ግን ያ ለመንግሥት አሹራ የሚከፍል ደላላ በመክሰሩ አዝኜ ይህን አሰብሁ ስለዚህ ነገር ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አሮጌ ዕቃ የሚሸጥ ለገዢ ሲወስድ ገጋሮው እመዘጋጃ ቤት ድረስ ይዞት መጥቶ ተመርምሮለት በነፃ ሊገዛና እንዲያተርፈው መርማሪ ሊአደርጉለት ይቻላቸዋል ። ወዳጄነህ ገብረ ኢየሱስ ።

የከተማ ወሬ ።

የቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል ዋና ሐኪም ክቡር ዶክቶር ሐነር ለዕረፍት ወደ ሐገራቸው ሔደው ነበርና የካቲት ፳ ቀን ከክብርት ባለቤታቸውና ከረዳቶቻቸው ጋራ ወደ አዲስ አበባ ገቡ ።

ብርሃንና ሰላም እንኳን ደህና ገቡ እያለ ደስታውን ይገልጻል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት-አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ነሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክብር ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፹ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፹ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፸ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፸ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፸ መሐ
አሳብና ምኞት	፴ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፴ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የእንቆቅልሽ ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፮ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፬ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኮረጃ	፻፸፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፩ ብር
ባለ ድመት		፻፵፰ ብር
ባለ አህያ		፻፵፫ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፺፫ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪክ		፻፳፭ ብር
ጃፖን		፻፲ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፵፩ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ ከ፸፭ሳንቲም
ባንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፳ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፫ ብር
አንድ ወቄት ወርቅ ፵፱	

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።
የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።



Borsalino



አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረን- ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርና ዲስና ልጆቹ ። የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE

BORSALINO

ALESSANDRIA (ITALIA)

MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

በዓርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲
6me ANNÉE № 10

ሐሙስ የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 6 MARS 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መሻገት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ጊዜን ስለማክበር ።

ብዙ ሰዎች የወርቅና የብር ሰዓት በኪሳቸው እየያዙ ያጌጠ ሰንሰለትም አድርገውበት በዚያ እየጐተቱ አውጥተው ብቅ እያደረጉ በማየታቸው ደስ ይላቸዋል ። እርሱ ሳታቋርጥ የምታመለክተው ዋና ነገር ግን ክቡር ጊዜ ሳያቋርጥ መሔዱን ነው ። ብዙ ሰዎች ግን ሰዓቲን ተሸክመው እርሷ የምታመለክተውን ጊዜ በከንቱ ያሳልፉታል። ጊዜውም ክቡር መሆኑን አያስቡትም።በከንቱ በመጥፋቱ ቅር አይላቸውም ። እንስሶችን ተመልከት ። ሁሉም የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሸተው ዘወትር ይሠራሉ ። ወፍ በብዙ ፃዕርና ትጋት ሣሩንና ቅጠሉን በተሰጣት ኃይል እየተሸከመች እያመጣች ቤትዋን ትሠራለች ሸረሪት ለድርዋና ለምግብዋ የሚሆኑ እንዳች ትናንሽ እንስሶች ለማጽመድ እስከተቻላት ድረስ በትጋትና ባለማረፍ ሥራዋን ትሠራለች ። ንህብም ለማር የሚሆን ጣፋጭ ጣፋጩን አበባ ከእየዛፉና ከእየሐረጉ ለመቅሰም ከቀፎው እየተንፎለፎለ በያኳያው እየተሰመረ ይውላል ። ጕንዳንም ምግቡን እየሰበሰበ በጕድጓድ ለመከተት ይጣጣራል ። የጊዜን መክበር ያስተዋሉ ሰዎችም ስንፍናን እርቀው ባጭር ታጥቀው ጥቅም ለሚገኝበት ሥራ ሲጥሩ ይኖራሉ። ከእኛም በውጭ ያለውን ዓለም እንመልከት።ዕውቀትን እየመረመሩ ሥራ እየሠሩ በጥበብ የሠሯቸው መርከቦች የንግድ ዕቃና መንገደኛውን ሁሉ እየተሸከሙ በባሕርና በውቅያኖስ ላይ ይሽቀዳደማሉ ። በከተሞችም ነጋዴዎች ከብትን ለማድለብና ለማትረፍ ሲገዙና ሲሸጡ ሲኰናተሩና ሲጃመሉ እናያለን ። ሹማምትም ቢሆኑ በጕዳይ ለመጡ ሰዎች ሳያስጠብቁ ሲያሰናብቱና በሚሠሩበት የሚገኝ የመንግሥት ጕዳይም በፍጥነት ሲያቀኑ ሁሉንም በሥርዓት እንዲሆን ሲደክሙ እናያለን ። ማናቸውም በከተማ የቆመ ሠራተኛ ልቡን ከሥራው ላይ ጥሎ ሲጥር እናያለን ። ለሕዝብ ዋና በረከት የሚያመጣ ሥራ መሥራትና ከጊዜ ጋራ መሽቀዳደም ነው እንጂ ሥራን ጠልቶ መስክ እያሹ በመዋል ፥ መንደር ለመንደር በመዞር፥እጅን ሸጕጦ በማስቀመጥ፥በዐዘንና በስንፍና አይደለም። ከዓለምም ጠቢባን የሆኑ ፥ ከድኽነት ወደሀብታምነትና ወደ ስመጥሩነት የደረሱ ብዙዎች ናቸው ። እንግዲያስ ዓለም እንዲህ አድርጋ በዕውቀትና በሥራ እየከበረች የምትሔድ ከሆነ እጆችህን አስተላልፈህና አስተቃቅፈህ ዝም ብለህ ሥራ ፈት ሁነህ የከበረ ጊዜህን አታሳልፍ ። ሥራ ፈት ሁነህ ውለህ ማታ ከማን ሰደቃ እጅህን ታጥበህ ትቀርብ ይሆን?።

ጊዜያችን አጭርና ክቡር ነው ። በፍጥነትም ያልፋል ከለፈብንም በኋላ እንዳንጸጸት ከጊዜ ጋራ እየተሽቀዳደምን ለራሳችን ለሀገራችን ለመንግሥታችን ጥቅም የሚሆን ሥራ እንሥራበት። በኪሳችን የምንይዘውና በቤታችን የምንሰቅለው ሰዓትም ጥቅምነቱ ጊዜያችን በከንቱ እንዳያልፍ እንዲያስታውሰን ነው። ስለዚህ የከበረ ጊዜያችን በከንቱ እንዳያልፍብን ተጠንቅቀን እንጠብቀው።

ስለሦስቱ አርእስተ ኃጣውእ ።

ሰውን ከክብር ወደ ኃሣር፥ከሕይወት ወደ ሞት፥ከነፃነት ወደ ባርነት የሚወስዱ በሰው ልብ ላይ ሰይጣን የደለደላቸው ሦስት የኃጢአት ጕዳናዎች አሉ ።

፩ኛው ፥ ሰው የያዘውን ማዕርግ ወደታች አድርጎ እየተመለከተ ሽቅብ ፥ ሽቅብ አንጋጦ እያየ ከበላዩ ያለውን የወንድሙን ሀብት ለመንጠቅና ለመውሰድ ሲል ከክፉ አሳቡና ምኞቱ ትዕቢቱን ያፈልቃል ። ምንም ላርሱ የማይገባው ቢሆን ይገባኛል ይላል እንጂ አይገባኝምና እንዳቅሜ ልደር ሳይል፥ዓቅሙን እያውቅ የሚባለውን የተረት ቃል ሳይመለከት

እግዚአብሔር ያልሰጠውንና ያላዘዘለትን ከርሱ በላይ ያለውን የወንድሙን ሀብት አገኛለሁ እያለ በትዕቢት ወናፍ ተነፍቶ፡ በምኞት ገመድ ተጐትቶ የሰይጣንን ምክር ሰምቶ ገበሬ ብንጉሥ ፡ መበለት በቄስ እንዲሉ ፡ በወንድሙ ሀብት ቀንቶ፡ የራሱን ማዕርግ ንቆ አጥቅቶ ያሰበውን ለማድረግ ሲል ከምኞት ባሕር ገብቶ ብቅ ጥልቅ እያለ መዋኘት ይጀምራል ። ይህንም የሚያስረዳ ነገር እግዚአብሔር አዳምን አሳምሮ ራሱን አስመስሎ ፈጥሮ አክብሮ ከርሱ በታች የምድር ንጉሥ አድርጎ በሁሉ ላይ አሠልጥኖ ፃዕር ፡ ጋር ፡ ሕማም ፡ ድካም የሌለበት አድርጎ ግዛ ንዳ ብሎ በገነት አኖረው። ነገር ግን የገገርና የተገዛ ምልክት እንዲሆን ብሎ ጌታ አዳምን በገነት ካሉት ከሦስቱ ዕፀዋት አንዱን የበላችሁ እንደሆን የሞት ሞት ትሞታላችሁ ብሎ ትእዛዝ ወሰነበት ። ከዚህ በኋላ አዳም ለጊዜው ጥቂት ዘመናት የጌታን ቃል ጠብቆ ኖረ ። ኋላ ግን ሰይጣን ሒዶ ዕፀ በለስን እትብሉ ያላችሁ እንጂ አምላክ ሁናችሁ የርሱን መንግሥት እንዳትቀሙት ነው ብሎ ተንኰሉን በጕልት ነገር ሠውሮ ውሸቱን በለቀቀው ጊዜ ሔዋን በፍጥነት ይህን ምክሩን ተቀብላ ሒዳ አዳምን፡ አዳም ሆይ ሞኝ ነህን ስንኳን የፈጣሪነት መንግሥትና የፍጡርነት መንግሥትም በዋዛ አይገኝም ። ደግሞም መንግሥት የሚገኘው ተርበ ተጠምቶ ዘምቶ ተዋግቶ ነበር ። እኛ ግን ሳይርበን በልተን ሆዳችነን ሞልተን መንግሥት በመብል ሲገኝ በቸልታ ይቀርብናልን ? ። አሁንም ሳትዋጋ ንጉሥ ቢሉት ካድ ተዋግቼ የተባለው ተረት እንዳይደርስብን ብላ የሰይጣንን ምክር እውነት አስመስላ ይችን ቅጠል እንብላና የፈጣሪን መንግሥት ቀምተን የሰማይና የምድር ነገሥታት እንበል በላቸው ጊዜ አዳምም ለካን እንዲህ ያለውን መንግሥት እንዳናገኝ ብሎ ነው አትብሉ ያለን ብሎ አሁንም በዚህ ምክንያት የባሕርይ አምላክነትን የምናገኝ ከሆነ ምን ከፋኝ ብሎ በዬ አሁንም በፍጥነት እምጭልኝ አለና እርሱም እርሷም በልተው ንግድስ የቀረለቀለት በአራት ገዝቶ ለሁለት እንዲሉ የማይገባቸውን ሀብት እናገኛለን ሲሉ ከነያዙትም አጡት ። የቄጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች እንዲሉ የጌታን መንግሥት እንቀማለን ሲሉ የራሳቸውን ተቀሙ ። እንገዛለን ሲሉ የሰይጣን ተግዢዎች ሆኑ።

አሁንም የአዳም ልጅ ለሚሆን ሁሉ ይህ ያልሰጡትን መሻትና የማይገባውን መመኘት እንዳይገባ በዚህ መመከር ማዴት ይሆነበታል ። እስኪ አንድ ነገር አሁን ወሀ በክረምት ጊዜ እጅግ ብርታትና ኃይል ያገኛል ፡ ነገር ግን ኃይል አግኝቻለሁና ብሎ ቍልቍል ከመፍሰስና ከመውረድ በቀር አንድ ቀን ስንኳ ሽቅብ ልፍሰስ ብሎ ተመኝቶ አያውቅም ።

፪ኛውም ፡ የጸገበች ነፍስ የማር ወለላ ትረገጣለችና ፡ ጫማውን ቈረጠ ፡ ቅቅሉን ውጦ ፡ ጠጁን ጨልጦ ጥጋብ በተሰማው ጊዜ እንደኔ ያለ ጌታ ያስታጥቃል እንጂ ይታጠቃልን ብሎ ውካታ ድንፋታ አድርጎ እምቢ አለ በለው እያለ እንደበቱን አጥፎ ዘርግቶ እግዚአብሔር መርጦ ቀብቶ ባነገሠው ንጉሥ ላይ የማይገባ ቃል ይናገርና ወዲያው የሰውደም በከንቱ እንዲፈስ ለማድረግ ክልቡ ርኅራኄን ያርቃል ።

ይህም እርሱ ወዶ አይደለም ፡ ከራሱ ላይ ሰይጣን የድንቍርና ኩርቻውን ጭኖ በዚያ ላይ ተቀምጦ እየኰረኰረ አላሳርፍ ስላለው ነው እንጂ ። እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት እርሱ ራሱ እንደፈጠረ በወቀ እንዲሞት ያድርጓ እንጂ በኔ ምክንያት ስለምን የሰው ደም በከንቱ ይፈሳል ሳይል ቍርጥ አሳብ ያደርጋል ። ምንም አሳቡ ባይፈጸምለት ለጊዜው ውኒጥ ውኒጥ ማለቱ አልቀረምና ይህ ኃጢአት እጅግ ከኃጢአት የበለጠ ሳይሆን አይቀርም ። ስለምን ማለት ፡ እግዚአብሔር ራሱን አስመስሎ ስለፈጠረው ስለሰው ፍቅር ሲል ልዑል ባሕርዩን ዝቅ አድርጎ አዝኖ ራርቶ ፍጥረቱ በገሀነም ተኰራምቶ እንዳይኖር በአይሁድ እጅ መከራ ተቀብሎ ተሰቅሎ ሙቶ በወርቀ ደሙ የዋጀውን ፍጥረት እርስ በርሱ ደሙን እንዲፋሰስ አድርጓልና ።

፫ኛውም ፡ በልቶ ጠጥቶ ተገኝቶ ተነሥቶ በሰገነቱ ሲመላለስ ከበታቹ ያሉ ሠራዊት ሲቆሙ ሲቀመጡ፡ሲፈቱ ሲታጠቁ አዩቶ በዚህ ምክንያት ፈቲው ደቈራኘውና በልቡ ክፍ ካለ ማዕርግ ለመድረስ ማሰብ ይጀምራል ። ወዲያው ያዛቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም እንዲሉ ፡ ይህን ሲያወጣ ሲያወርድ አንድ መጻእያትንና ኃላፍያትን አውቃለሁ ባይ ይመጣና ለጌታዬ ንገሩልኝ በቈይታ የሚነገር ረቂቅ ምሥጢር ይዣለሁና ብሎ ላሽከሮች ባስታወቀ ጊዜ አሽከሮቹ ፈጥነው ገብተው ነግረውለት ግባ በሉት ይላቸውና ገብቶ ከፊቱ በቆመ ጊዜ እስኪ ይንገሩኝ አባቴ ይለዋል ። ያም ለሰይጣን ነገረ ፈጅ ሁኖ የመጣ ዋሾ ጠንቋይ የሐሰት ወሬውን ሊነፋለት ይጀምራል። ከዕለታቱ ባንድ ዕለት ስለርስዎ አዝኜ ተከዤ አቍጣሮዬን አድርሼ በመከነ ጸሎቴ ዓረፍ ብዬ ሳለ እንቅልፍ ተደሞ መጣብኝና ግሩም የሆነ ራእይ አያለሁ ።

አንድ መልአክ ከእግዚክብሔር ዘንድ ተልኮ መጥቶ እገሌን በዚህ ወራት ፡ በዚህ ዓመት ፡ በዚህ ዕለት ፡ በዚህ ሰዓት የበለጠ ማዕርግ ታገኛለህና ተዘጋጅተህ ተቀመጥ በለው ብሎኛል ያለዋል ። ከዚህ በኋላ የትዕቢት ዕንስ በሆዱ ይፀንስና እኔም እክ ተራ አለኝ እያለ ለምሥጢር ተከፋዮች ያወራል ።

ያልሆነ ደቀመዝሙር ከመምሩ ጋር ሳለ ክሕደቱን እንዳይገልጽ ከመምሩ ተለይቶ ጉባዔ ሠርቶ ማስተማር በጀመረ ጊዜ ክሕደቱን እንዲገልጽ እርሱም አገር ተሹሞ በወጣ ጊዜ ዓመፃ ወዕአት እመዛግብቲሃ እንዲል ከዚያ በኋላ ንግሬ ደረሰ እያለ ያሐሳዊ ነቢይ የነገረውን ለመፈጸም ሐሳቡን በከንቱ ያበክናል።ነገር ግን ያሰበውንም ሳያገኝ ይቀርና ያ የተነሣሣበት መንፈሰ ሐሰት ከተተከል ግንድ ከተታታ፡ ገመድ ያደርሰውና ሌላውን ደኅዋ ለማሳት ዘወር ይላል ።

አሁንም ይህን እደዚህ ያለውን ሐሰተኛ ነገር መከተል ፅኑ ኃጢአት ነውና በዚህ ወጥመድ ማንም ሰው እንዳይያዝ ጥንቃቄ ያስፈልግዋል ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ቀርቶ በሐሰተኛ መንፈስ ትከሻ ተመርቶ መሔድ መሪውም ተመሪውም በጥፋት ጕድጓድ ወድቆ ለመቅረት እንደሆነ ምናልባት ጥቂት ምክር ቢቀበል ስለዕውራን የተጻፈውን ቃል አንበ ምሥ–

ጢሩን ቢረዳው ያ ተስፋ የሚያደርገው በውሸት ቀለም የተጻፈ ትንቢት ሳይርቅለት አይቀርም ነበር ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

ስለ ደም መዛወር ።

ለደም መዛወር ዋና መሣርያ የሚሆን ልብ ነው ። እርሱም በደረት ውሥጥ ያለ ውሥጠ ክፍት ሥጋ ነው ። ልብ በሁለቱ ሳምባ መካከል ጫፉን ወደ ግራ አዙሮ ይገኛል ። ልብ ውሥጡ ባንድ በሥጋ መክፈያ ከሁለት የተከፈለ ነው ። እርሱም የቀኝና የግራ ክፍል ይባላል ። ከዚህ ክፍልም እያንዳንዱ ባንድነት ያለ ነገር ከሁለት ተከፍሏል ። እርሱም ላይኛውና ታችኛው ክፍል ይባላል ።

ልብ የሚንቀሳቀስ ስለሆነ ደም ከልብ ተነሥቶ በሥሮች ሊመላለስ ይችላል ። ሥሮች ሁለት ወገን የሚሆኑ ቀጫጭን ቦይ ናቸው ። እነርሱም በሰውነት ሁሉ ተዘርግተዋል አንዱ ወገን ሥር ወሳጅ ነው። አንዱ ወገን ሥር ደግሞ ደምን ወደ ልብ የሚመልስ መላሽ ነው ። ወሳጁ ከልብ ጋራ በስተ ግራ በኩል ባለው ክፍል ይገኛል።መላሹ ደግሞ በስተቀኝ በኩል ባለው ከልብ ክፍል ይገኛል ። ደም የሚንቀሳቀስበት ምክንያት ሁለት ወገን ነው ። ትልቅና ትንሽም ይባላል ። በትልቁ መንገድ ሲሄድ ደሙ ቀይ ሁኖ በስተ ግራ በኩል ካለው ከልብ ክፍል ተገፍቶ ወደ ወፍራሙ ሥር ይገባል። ከዚሁም ወደ ሰውነት ሥር ሁሉ ተነቀጫጭኑ ሥር ሳይቀር ይሔዳል። ይህ ትልቅ መንገዱ በተደረገ ጊዜ ደም ለሰውነት ጥቅም የሚሆነውን ነገር ሁሉ በያይነቱ ይዞ ይሔዳል ። ቀይ ከሚሆን ከጥሩ መልኩም ወደጨለማነት ይመለሳል ለመጥቆርም ይቀርባል ። እንዲህም የሚሆንበት ምክንያት ጥሩ ጥሩው አልቆ አተላው ስለቀረ ነው ። ወሳጅ የተባለው ቀጭኑ የደም ሥር መላሽ ከተባለው ከቀጭኑ ስር ጋራ ይጋጠማል።ያም መላሽ የተባለው ቀጭኑ ሥር ደሙን ተቀብሎ ወፍራም ወደሆነው ወደ መላሹ ሥር አድርሶ በስተቀኝ በኩል ወዳለው ወደልብ ክፍል ያገባዋል ። በሁለተኛው መንገዱ ያ ጠቁሮ ተመልሶ በስተቀኝ በኩል ወዳለው ወደልብ ክፍል የገባ ደም በሌላ ትንንሽ ቦይ ወደ ሳምባዎች ሔዶ ኃይል ይቀበላል ። ወደዚያው ወደሳምባ ከገባ በኋላ አዲስ ጥሩ አየር በማግኘቱ ይጠራል ፥ ይቀላል ።ከዚያ በኋላ በሌላ የደም መንገድ በልብ በስተ ግራ ወዳለው ክፍል ይገባል ።ከዚሁም ከሞት በቀር በምንም የማይቈረጥ መዞሩን እንደገና ይጀምራል ።

የልብ መንቀሳቀስ ።

በደረታችን በስተ ግራ እጃችንና ጆሮ ግንዳችን ፥ እንዲሁ በመሰለ ሥራም ብንጭን በመታቱ ይገለጽልናል። በየእንዳንድ ደቂቃ የልብ አመታት ከሰባ እስከ ሰማንያ ያህላል። የሰውነታችን ሙቀት በጨነበት ጊዜ እስከ ሦስት መቶ ሰማንያ አምስት ሳንቲ ግራድ ያህላል።እንዲህም መሆኑ ከደም አካሔድ እንደሆነ እርግጥ ነው ።

የደም ዓይነትና ብዛት በትንፋሽ ከሚገባው አየርና ምግብ ነው ። በጥሩ በውጭ ቦታ ሽርሽር ማለት ፥ ጤናማ ምግብ፥ ማጡብና ፥ መታጠብ ፥ ከሥራ በኋላ የተገባ ዕረፍት ፥ በልክ መጫወት እነዚህ ለደም ብርታትና ኃይል ይሰጣሉ ።ጥሩ ደም ያለው የሆነ በሽታ አይነካውም ። እንደዚህም ሁሉ ደም በአሥራው እየተዛወሩና እየተሯሯጡ ለሰውነት ጤንነትንና ልምልሜን እንደሚሰጡ እንዲሁም ንጉሥ እንደልብ ነውና በንጉሥ ፈቃድ እየተዛወሩና እየተላላኩ ሀገር የሚያሰፉና የሚያስተዳድሩ አገረገዢዎች እንደጤነኛና ጥሩ ደም ሁነው ለሚገዙት አገር ልምላሜና ሕይወት ሊሆኑ ይገባቸዋል ። ደመደጎና የሆነ ሰው ሰውነቱ ጤነኛ እንዲሆን ደጎና የሆኑ አገረገዢዎችም ላገራቸው ሕይወት ናቸው ።

ስለ ሀገር ፍቅር

ጥቁር ነኝ ጥቁር ነኝ እጅግ ጥቁር ነኝ።ትኩር ብሎ ላየኝ በጣሙ ውብነኝ ።

ለተወለድኩብሽ ኢትዮጵያ አገሬ ። አልተው ካለኝ ፍቅርሽ ልናገር ደፍሬ ። ምንም ቢሸግረኝ ጠሚንኳን ባድር ። መርዳቴን አልተውም ስለሀገሬ ፍቅር ። እስክገባድረስ እስክሆን አፈር።እስኪ ላነሣሣት ኢትጵያን። አክብሩ የምትመግብ ወዳጅ ልጆችዋን። እክብረን ብኒዛት እናታችነን።ምቀኝነት ጠፍቶ አንድነት ብንሆን ። ወርቅ አልማዙ የኛ ሚኒሮ የሚሉን ። አሰማምተህ መግዛት ነው ጠቅል መኰንን ። ወዳጅ ጠላት ሳትለይ አንድ ልብ አርገን ። ይኸም ምኞታችን ባፍ ብቻ እንዳይሆን ። ገልጸን ማሳየት ነው በየሥራችን ። አይሰሙሽም እንጂ የሚሰሙሽ ቢሆን ፍቅር በሰጡሽ።የምትመግቢያቸው ሲሳይ መች አጣሺ። ምን ጊዜም ለምለም ነሽ ምን ጊዜም ወርቅነሽ። ካዓለማቱ ሁሉ አንች ትበልጫለሺ ። ክረምትና በጋ ልይ የለብሺ ። ዧዙሮ ያየሺ ሰው መቸም አይጠግብሺ ። ሌት ቀን የሚደክም አንጋፋ ልጅሺ። ለትንሽ ትልቁ ብርሃን ሆነልሺ ። ወንድማማች ሁኖ መኖር ባንድነት።እንደምን ደስ ይላል ለወላጅ እናት።ጠብን የሚነዛ በዚህ ባንች ቤት።ላሁኑም ለኋላም በጣም ወዮለት ። በብሉይ በሐዲስ የተጻፈልሺ።ዓለማት በሙሉ ያመሰገኑሺ።አንችን ለሚወዱ ደስ ታሰኛለሺ ። ጠላቶችሽ ሁሉ ምንም ቢመኙሺ ። ሃይማትሽ ዕሑዕ ቃል ኪዳን አለሺ ። ግንባርሺ ተፈሪ ጠቅል አለልሺ። አንችን አላገኙም ምንም ቢመኙሺ።ኢትዮጵያ አገራችን ምንጣፏ ለምለም።በውን አትጠገብ እንኳንስ በሕልም። ብርሃንና ሰላም አርጎ ቢሰብክልን። ማነው ይቅር የሚል ሐዋርያችነን። ዧዙሮ ቢሰብከን እውቀት ቢሰጠን ። ጎበ ጥንተ ነገር ንግበእኬ ሊሉን። ይጠቃቅሳሉ ዙሯ ገባውን። ኢትዮጵያ አገሬ እኔ ልንገርሺ። አንችን የሚረዳ ዘመድ አይነስሺ። አንድነት ከልሆኑ መቼም አይረቡሺ። ደንብና ሕግ ሰጥተው ደስ እንዲያሰኙሺ። አንቺም ምን ቸገረሽ ተፈሪ እያለሺ።በውጭም በግቢም ብርቱ ነው ጋሻሺ። እስከመቸም ድረስ ኀዘን የለብሺ።ወልደሽ ያሳደግሽው ሚዛን ነው ልጅሺ ። አወይ ያለመማር ያለመመልከት።ባንበሳ እጅ አድርጎ ሥልጣን ቢሰጣት።ምቀኞች ተነሥተው ከዚፍ ሊያገቧት ። ከንቱ ይደክማሉ አንዱን ሳያውቁት ። የማይሞት አለሙይ ለወላጅ እናት ። ይኸን ሁሉ ትተህ ፈጽም አሳብከን። አይሰማም ደንቆሮ የብልህ ነገሩን ።

ዚዙረህ ካየኸው የሮፓን አገር ። ሥልጣን እንዲሰጠን አንተም እንድትከብር ። ሕዝብም ደስ ይበለው ተኝቶ ይደር ። ነገሩን የሚገልጽ አንድ ሕግ ስጠን ። እንዲያው በውጋ ውጋ እንኖራለን ። የሚያገኘው ጥቂት ብዙው ጠም አዳሪ ። በንጹሕ አድርጎ እያጣ መርማሪ ። ዘየገሩ ፈታሽ ብታደርግ ምነው ። በዝርዝር ይገኛል የተጐዳ ሰው ። በዝርዝር አልሚም አጥፊም ሰው ። ሁሉን የምታውቅ ዝም አትበል ብርሃኑ ። ለተበዳለ ሰው መንግሥት ነው ዓይኑ። ሁሉም ይጠብቃል ሕግ እንድት- ሰጠው። ነገሩ ገብቶታል የኢትዮጵየ ሰው ። እኛ የምንኖረው አንተን ታምነን ። በሐሳብ ሰልችተን እንዳንበተን ፤ ከሎሬህ እስነክን ሳያልቅ ዕድሜያችን ። አምላክ ይጠብቅህ ዕድሜ ይስጥልን ። ሁላችን ባንድነት እንበል አሜን ።

ፊ. ፊንታ ወልደ ገብርኤል።

ደግ አሳብ ስለማሰብ ።

የዚህ ዓለም ሰዎች የአንድ አምላክ ፍጥረቶችና የአንድ አባትና ያንዲት እናት ልጆች ወንድማማች መሆናቸውን በመዘንጋታቸው አጅግ ያስገርማሉ።ስለ ምንቢሉ ሰው በሰው ላይ ግፍ ሲሠራና ሲያምጽ እንመለከታለን ። በዚህ ፈንታ ሰው ሊያደርገው ይገባ የነበረውን ግን፣ እርሱ በርሱ ሊረዳዳ፣ ማለት በሥራ ሊተጋገዝ ነው።ይህ መተጋገዝ ያልነውም ደግሞ ያወ- ቀው ላላወቀው ያለችውን ዕውቀት ሊያካፍለው በትምህርትም፣ በሥራም፣በማናቸውም ጥቅም ሁሉ እንደተቻለው መጠን ከደረጃ ወደደረጃ ሊያራምደው ነበር።ቁመትና ዕውቀት አስተዳደጋቸው እንዴት እንደሆነ በኑሮዋችን ሁሉ እንረዳዋለን። ቁመት ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተገኘ ስጦታና ከወላጅ ባሕርይ የተገኘ ርጎራጌና ምግብ ነው ። ይህ ሁኔታ ግን ከሰዎች ብቻ ያይደለ በእንስሶች ዘንድም እናየዋለን። እንዲህ ያለ አድራጎት በኛ ግን ወዲያው እንደተወለድን እናልቅ ነበር እንጂ ቁመታችን እስከ ማደግና ሰውነታችንን በገዛ ራሳችን አሰበንና ሠርተን እስከ- መርዳት አንደርስም ነበር።ዕውቀት ወይም ደግሞ ጥበብ እንዲሁ- ናት ፤ አንዱ ያወቃትን ለሁለተኛው ሲያካፍለውና ሲገልጽለት ብቀን ብዛትና ምክርን በመደጋገም ያንዱ አእምሮ ከንዱ ጋ፦ ሲዋሐድና ሲያድርበት ፤ እግዚአብሔር ባደለው ማስተዋል የጐደለበትን ለመምላትና የጠመመበትን ለማቅናት፣የተሠወረ ብትን ለመግለጽ ፤ የጠፋበትን ለማግኘት ይጣጣራል ። ወዲ- ያውም በተገለጸለት ብርሃን አእምሮው በሕሊናው ርቀትና በሥራው ትጋት ከፍ ካለ ደረጃና ማዕረግ ይደርሳል ። በዚያው ብደረሰበት ማዕረግ ደግሞ ደስ እያለው የሕይወቱ ልምላሜ ይታደሳል ።

አሁን ግን በተሰጠን አእምሮ ብንመለከት ወይም ብናስተ- ውል አንዱ የሌላውን ከመፈለግ በተቀር በምን ነገር ይጣላል። ይህ ሥራ ደግሞ ክፉ ምኞት የተባለው በገነት ወላጆቻችንን እንዳታለላቸው እናውቃለን።እስቲ እንመርምር።አሁን በአዲስ ምክር ተወስኖ ሰው ሁሉ ያችን የተወለደባትን አገር ብቻ ርስት አድርጎ ፤ አገር የተባለች ሁሏም ለየአገርዋ ልጅ ንጋ እየተገዛችና እየገበረች በነፃነት ብትኖር ምንኛ መልካም ነው ። ከዚህም አስከትላ ፍቅርንና ስምምነትን እያደረገች የሚያስተምር በማስተማሩ ፣ የሚሠራ በሥራው ፣ የሚነግድ በንግዱ ፣ እየሆነ አንዱ ባንዱ ሳይመቀኛኝ አንዱ ያንዱን በረከት ለመቀማት ሳይመኝ በመተማመንና በወንድምነት ፍቅር ወንቶ ቢኖር ሕያዋን ፍጥረቶችን የሚፈጅ መሣሪያ በያይነቱ ባልተሠራም ነበር። ሁሉም በፍቅር አዳሪና ለንጉሥ ቃል ታዛዥ ሁኖ በስመምነት ከኖረ የወታደርም ብዛት ባላስፈለገም ነበር። ስላምን ብንል የወታደር ብዛት የሚፈለገው ሕዝቡ በፍቅር ተለያይቶ ጠብ አንሥቶ በተለያየ ጊዜ ዓመፃኛውን ለመቅጣት ነውና ።

መንግሥቶችም ለጦር መሣርያና ለወታደር ምግብ ሲሉ ገንዘባቸውን ማውጣታቸው ዓመፀኛው በዝቶ ፍቅር ጠፍቶ አገር ለመጠበቅ ግድ የሚያስፈልግ በለሆነባቸው ነው ። ሰላ- ምና ፍቅር በዓለም ቢፀና ግን የዓለም ሥልጣኔ ከሁኑ ይልቅ የበለጠ ሁኖ እየተሻሻለ እንዲሔድ እርግጥ ነገር ነው።ሕዝብም እ፡በዛና አገር እየለማ ይሔዳል ምናልባት እንዲህ ቢሆንማ መሬት ይጠብ የለምን? የሚል ቢገኝ መሬትንስ ከበላይዋ ለሚኖሩ ፍጥረቶች ሁሉ በቂ እድትሆን አድርጎ እንደፈጠረ-ት የተወሰነ ነገር ነው! ስምምነት ከሌለ ግን የተሠራው ቁም ነገር ሁሉ ከንቱ ሁኖ ይቀራል ስፈውም ይጠባል።

ለአሁኑ ጊዜ ትውልድ ግን ሕያዋን ፍጥረቶችን የሚያሳልቅ መሣሪያና ሰውም እርስ በርሱ መጋደል ካልቀረለት ያው እንደ ዱሮው እንደነበረው ነው እንጂ ምን አዲስ ሥልጣኔ አገኘ ወይም ተማረ ያሰኛል። ከዚህ ወዲያማ ያልሠለጠኑቱ የበረሃ አውሬዎችስ ቢሆኑ ከርሻቸው ያነሰውንና የደከመውን ፍጥረት ሁሉ እየገደሉ ከመብላት በተቀር ሌላ ምን ጥፋት አለባቸው ? ። ለሰዎች ተምረዋል ሠልጥነዋል የሚያሰኛቸው ግን ፤ የሌላውን ገንዘብ ሳይፈልጉ የሰው ደም እንዳይፈስ የሚጠነቀቁ በዕው- ቀትና በሥራም አገር የሚያሻሽሉ በማስተማርም የሚደክሙ- ናቸው ። ብፁዓንም ይባላሉ ። ይህ ሥራም በጣም የሚያስገ- ድደው ደግሞ አብልጦ ለክርስቲያኖች ነው ። ክርስቲያኖች የሆን ሁላችን የአንድ ክርስቶስ አካል እንደሆን እናውቃለን እናምናለንም ። ምልክታችን ደግሞ ፍቅርና ስምምነት ነው ። እንዲህ ያለ የደግነት ሥራ ባይገኝብን ግን በጣም ራሳችንን እንጐዳለን፣ ጥቅምም የለንም ። እጅግ ያሳዝናል ከዚህ ሁሉ የሰው ዕውቀትና እእምሮ የሰላምና የስምምነት ምክር ሳያቆም መኖሩ በያይነቱና በየመንገዱ ብዙ ልዩ ልዩ ብልኃትና ጥበብ በዓለም ላይ ሲገለጽ ስምምነት ብቻ ከሰው ዘንድ እንደተሠ- ወረች ትኖራለች ።

ገዛኸኝ አፍለኝ ።

ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖች መታሰቢያ በዓል ።

የካቲት ፳፫ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ የወር በዓል ነው የዓድዋ ጦርነትና ስላገራቸው የሞቱ ጀግኖች መታሰቢያ በዓል ስለ ሆነ ይህ በዓል በኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘንድ በየ ዓመቱ ይከበራል ። ይልቁንም ከአዲስ አበባ ውሥጥ አራዳ ላይ በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም በታነፀው ታላቅ ቤተ ክር-

ስቲያን ሊቃውንቱና ካህናቱ በሀርና በወርቅ በተሠራው ልዩ ልዩ ዓይነት ሸልማት እያጌጹ እጅግ የተወደደና ደስ የሚያሰኝ ማኅሌታቸውን ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ።ነገሥታትና መሳፍንቱ መኳንንትና ሠራዊቱም እንደየማዕረጋቸው በልዩ ልዩ ዓይነት መሣርያ አጊጸው ሰልፍ በማድረግ ይህን በዓል ያከብራሉ ። ዘንድሮም ቀኑ እሑድ ስለ ሆነ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ከጠዋቱ ቀደም ብለው ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሔደው ነበር። ማኅሌቱና ቅዳሴውም ከተፈጸመ በኋላ ዑደት ተደረገና ግርማዊ ንጉሥ በማረ ዙፋን ላይ ሲቀመጡ ከዙፋኑ ዙሪያ ጳጳሳቱ በክህናት በኩል፥ መሳፍንቱም በመኳንንት በኩል እንደ የማዕረጋቸው ተቀመጡና ዘበኛውም በተራ ተሰልፎ መዘምራኑ በልዩ ልዩ አልባሳትና መሣሪያ አጊጸው ሲያስረግጡ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ከዚህም በኋላ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ቅዱስ ጊዮርጊስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለ ሃይማኖቱ በመሞት ዋጋውን እንዳገኘ የኢትዮጵያ ጀግኖችም በንጉሣቸው ስም ስለ ሀገራቸው ደማቸውን በማፍሰሳቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋቸውን በሀገራቸውና በሕዝባቸው ዘንድ መታሰቢያቸውን እንዲያገኙ አረጋግጠው ተናገሩና ከዚህም ሌላ ሕዝቡን መክረውና ባርከው አሰናበቱ። ወዲያውም ጽዕጊዜ መድፍ ተተኰሰና በኋላ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ግርማዊ ንጉሥ በማረ ዓጅብ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሱ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ገድሌ ዕረፍት ።

ክቡር ደጃዝማች ገድሌ ታመው ለጠበል በጥር ወር ወደ ደብረ ሊባኖስ ወርደው ሰንብተው ነበ ና በዚያ ሕመማቸው ፀንቶባቸው በየካቲት ፲፱ ቀን ዓርፈው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ልዑል ራስ ካሣ ከክቡራን መኳንንትና ሠራዊት ጋራ መጥተው በትልቅ ክብር ተቀበሩ ። በአዲስ አበባም የካቲት ፳፬ ቀን ውሎ ተደርጎ ተለቀሰላቸው ። ሲሞቱም ዕድሜያቸው በድሳ አራት ዓመት ሁኖ ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች ገድሌ ከአፄ ምኒልክ ጀምረው እስከ ዛሬ ድረስ ለመንግሥታቸው የታመኑ አገልጋይና ጀግና ነበሩ ።

ብርሃንና ሰላም ለልጃቸው ለክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድና ለወንድሞቻቸው፥ ለቤተ ሰባቸው እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

የማይገባ ወሬ ለመስማት ስላለመቻኰል ።

አንድ አንድ ሰዎች ሥራቸውን ይተዉና በየመንገዱ እንደበር ዕንጨት ይገተሩና አላፊ አግዳሚውን ወጭ ወራጁን እስቲቼይ ወንድሜ ይሉና ቁሞ በቈያቸው ጊዜ እንዴት ውሎ- ሀል ከወዴት መጥተሀል ብለውት ከየትም እንደመጣ ወዴትም እንዲሔድ ከነገሩቸው በኋላ ምን ወሬ ይዘሀል እስኪነገረን ይሉታል እርሱም ዝም ብሎ መንገዱን መሔዱን ይተውና የሆነ ያልሆነውን ይቀባጥርላቸው ይሆናል ። ሌላስ ወሬ የሰማኸው የለምን ብለው አስጨንቀው ይይዙታል። ደግሞ እንዲህ ያለ ፡፡ሬ ሰምቻለሁ እያለ የሀገር ጥፋት የሕዝብ ጒዳት የሚሆነውን ነገር ይነግራቸውና ወዲያው እገሌ ነገረን ብላችሁ ለማንም አትነገሩ ይላቸው ይሆናል።አትንገር ያሉት ሰው መንገር ልማዱ ነውና እነዚያም ሰዎች ከመሸታ ቤት ይገቡና የሰውን ስም ሲያከፉ፥አንዱን ሲያነሡ አንዱን ሲጥሉ፥ከዚያ ሰውዬ የሰሙትን ወሬ እያወሩ ሌላም ከራሳቸው አንቅተው ያልሆነ ወሬ እየጨማመሩ የሐሜት ማዕድ ከፊታቸው ሠርተው የተሰበሰበውን ሁሉ ሲመግቡት ይውሉ ይሆናል። ነገር ግን ክርስቲያን ለሆነ ሰው እንዲህ ያለውን የወሬ ፈቃድ ከልቡና አርቆ በሥራ ላይ ተወስኖ ለወሬ የለው ፍሬ ነውና ለወሬ ሳይቸኩሉ የሰሙትንም ነገር ለማንም ሳያከፍሉ ፥ ትልቁንም ትንሹንም በቤት ውስጥ ሁኖ በሐሜት ሳያነሡ፥በለጸጋን በቤትህ ውሥጥ አትማ የሰማይ ዖፍ ነገርህን ያወጣብሀልና ያለውን ቃል እያሰቡ እንደበትን ጠብቆ ከነገር ርቆ በጸሎትና በትዕ- ግሥት ላገሩና ለመንግሥቱ መልካም ነገር በማሰብ ተወስኖ መኖር እጅግ መልካም ነው ።

ስለትምህርት ማስፋት ።

ከዚህ ቀደም ለሀገራችን ያሰቡና የተቈረቈሩ ብዙ ሰዎች ስለ ሥጋዊና ስለመንፈሳዊ ትምህርት ድንቁርና እንዲጠፋ፥ ዕውቀትና ሥልጣኔ እንዲስፋ፥ልብ እንዲታደስ፥ አእምሮ እን- ዲጐለምስ፥ ሲሉ ብዙ ጊዜ በብርሃንና ሰላም ማንም ሰው ሆነ ትምህርትን እንዲሻትና እንዲከተላት አስታውቀው ነበር ። መዠመሪያ ነገር እግዚአብሔርን ፈርቶ እየኖረ ጥበብን እየመ- ረመረ የተገለጸለትን ዕውቀት ለሌላው እያስተማረ ያልተገለጸትን እየተማረ፥የእጅ ሥራ እያዘወተረ መኖር እንዲባ ያገራችን ሕዝብ ጥቅምነቱን ተረድቶት ልጁን ሁሉ ወደተማሪ ቤት ማግባት ጀምሩዋል ።

ስለዚህም አሁን ሕፃናቱ ሁሉ በብዙ ቋንቋ መነጋገርና መጫወት ጀምረዋል።እንዲህም መሆኑ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ብርታትና ቸር- ነት በከተማው ውሥጥና በሌላውም ሀገር የትምህርት ቤት እንዲከፈት ስለፈቀዱና ስላሰቡ ነው ።

ግርማዊት ንግሥትንና ግርማዊ ንጉሥን ተከትለው ብዙ አገረ ገዦዎችም በየግዛታቸው ውሥጥ የትምርት ቤት የከ- ፈቱ ለመክፈትም ያሰቡ አሉ ። እንዲሁም ከጥንት ከባቶቻችን ጀምሮ ሲነገርና ሲያያዝ የመጣው የቤተ ክርስቲያናችን ትም-

ርትና ሥርዓት እያነሰና እየተቀነሰ እንዳይሔድ እግዚአብሔር በቸርነቱ ብዛት በጸሎታቸው እንድንጠበቅ በትሩፋታቸው እንድንጸድቅ በዕውቀታቸው እንድንራቀቅ በቡራኬያቸው እንደንመረቅ ሲል መፈሳውያን የሚሆኑ አባቶቻችን ከሀገራችን ጳጳሳት አድርጎ ስላስነሣልን በየድባራቱ ያሉ ሕፃናት ሁሉ በመንፈሳዊና በሥጋዊ ትምርት እንዲሠለጥኑ እንደሚያስፈልግ በየይነቱ መምህራን እንዲሰናዱና እንዲዘጋጁ የአባቶቻችንን ትጋት ተስፋ እናደርጋለን ይህንም ማለታችን እነሱ ከእኛ የበለጠ ሳያስቡበት ይቀራሉ ብለን አይደለም እኛም በተቻለን ማስታወስ ይገባናል ብለን ነው እንጂ ።

ልጅን ስለ መውለድ ።

የካቲት ፳፫ ቀን ማዳምዋዜል ማሪ ጆርጦን የክቡር ሙሴ አቤርሰን በልዩ የቆመ ፍርድ ቤት አማከሪ ልጅ ስለተወለደች በደስታ እናስታውቃለን ።

ብርሃንና ሰላም ለሙሴ አቤርሰንና ለማዳም አቤርሰን እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል ።

የከተማ ወሬ ።

ስለ እስላሞች ዓረፋ ።

የካቲት ፳፪ ቀን የእስላሞች ዓረፋ ስለሆነ እስላሞች ሁሉ ተሰብስበው መድፍ እየተተኰሰ የበዓላቸውን ደስታ ገለጹ ። በከተማው ያለ እስላም ሁሉ አዲስ አዲስ ልብስና ጌጥ እየለበሰ ሴትም ወንድም በአቶመቢል ፤ በፈረስ ፤ በበቅሎ ፤ በእግር ሽርሽር ሲልና የደስታ ጨወታውን ሲጫወት ሰነበተ ።

ማስታወቂያ ።

ቤተ ሳይዳ ዘተፈሪ መኰንን ሆስፒታል መጋቢት ፩ ቀን ይከፈታልና ክቡር ዶክቶር ሐነር የሕክምና ሥራቸውን እንደሚጀምሩ እናስታውቃለን ።

ከእሑድ በተቀር በሳምንቱ ሁሉ ከጥዋቱ ፫ ሰዓት አንስቶ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ በሽተኛውን እየተቀበሉ ያክማሉ።

የውጭ አገር ወሬ ።

በኢጣልያን ሌጋሲዮን የመጣ ራድዮ ።

ሎንድራ ፤ አንድ የእንግሊዝ ሠራዊት ኮሎኔል የአውስትሪያ አርቺዱኪሳ ማሪያ ቴሬዛ በምንት ሚሊዮን የሚያወጣ እደራ የተቀበለውን የአልማዝ ዕንቊ ለመሸጥ ወደ ኒዮ ዮርክ ስለደረሰ የእንግሊዝና የአመሪካ ፖሊስ የገባበትን ይፈልጋሉ። ግን ገና ምልክትም አላገኙም።

ካይሮ ፤ የአሜሪካ አርኬዎሎጂኮች የጥንት ነገር ከመሬት እየቈፈሩ የሚያወጡ ከአላና ሮው የሔዱ በማይዲም አቅራቢያ በፈረዖኖች ጊዜ የተሠራ መቃብር ቤት ውሥጥ ሰላሳ መቃብርና ዋጋው ከፍ ያለ ብዙ ዕቃ አገኝተዋል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጆኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ድጓሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሁ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፶ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፶ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፶ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፶ መሐ
የሣልና የንቀርሳ የምክር ቃል	፶ መሐ
የግርኛ ምሳሌ	፶ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፶ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንድር)	፶ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደል ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የእንቍጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፱ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፭ ብር ተኩል
ዝባድ	፩ ወቄት	፫ ብር
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፶፮ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፬ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፫ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፫ ብር
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፬ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፹፩ ብር
ባለ ድመት		፻፶፫ ብር
ባለ አህያ		፻፸ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፳፫ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፵፫ ብር
ጃፖን		፻፹ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፮ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር ተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፫ ፍራንክ
ባንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፳ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፯ ከ፶ ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ ፵	

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶጕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳዊ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅላ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮፓ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺ፡ መዚቃ ሸክላ ይገኛል። መዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX,) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኚካላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥሩ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
6me ANNÉE № 11

ሐሙስ መጋቢት ፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 13 MARS 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በስምምነት ሁኖ ስለ መበርታት ።

ምን ጊዜም አንዱ የመከረውን አንዱ ሲለውጥ፥ አንዱ ያነፀውን አንዱ ሲያፈርስ መኖር ለሰው ልማዱ ነው። ነገር ግን ይህን ድል የሚነሣ ስምምነት ነው ። አሁን የሚሚገት ሰው ጠበቃውን ገዝቶ በቤቱ ሳለ ጠበቃውና እርሱ ራሱ የሥራቱን መንገድ ይህ ያወጣናል፥ይህ ግን አያወጣንም እያሉ አውጥተው አውርደው በሚያወጣቸው የሥራት መንገድ ስምምነትን ከደረጉ በኋላ ጠበቅዬው ዋነኛውን እንግዲህ የነገሩን አድራሻና አኳኋን ስላስረዳኸኝ እኔ የጐደለውን ሞልቼ፥ የጠመመውን አቅንቼ፥ነገሩን አቀላጥፌ ሥራቱን አቀናዋለሁና አንተ በጐድኔ ቁመህ አይዞህ እያልህ ከኔ ሳት ያለውን ነገር አሳስበኝ እንጂ አጕል ነገር እያመጣህ እንቅፋት እንዳትሆንብኝ አጕል ነገር ተናግረህ ስምምነታችንን ብታፈርስ ግን ሥራታችን በጳውሎስ በጠላትነት እንደተነሡበት ሰዎች ሥራት ይሆንብናል ብሎ ያስጠነቅቀዋል ። ለአንባቢ መጽሐፍ ቅዱስ ዘርግቶ ምዕራፉንና ቁጥሩን አውጥቶ እስኪመለከት ድረስ የሥራው ጊዜያት እንዳያልፍበት የጳውሎስንና የጠላቶቹን አኳኋን እነዚህ ቀጥለን በግልጽ እናስረዳለን። ሰዱቃውያንና ፈሪሳውያን ጳውሎስን በጠላትነት እየከሰሱና እየተጣሉ ባስቸገሩት ጊዜ ጠላትን ባፈር በቅጠል ብሎ ድል መንሣት እንዲገባ እርሱም ዕውቀትና ትምህርት ማገዙ አይቀርምና እነዚህ ሁለት ዓይነት ወገኖች የሚለያዩበትን ምክንያት በምንም እንደሆነ መረመረ ። መርምሮም ሰዱቃውያን ከፈሪሳውያን፥ፈሪሳውያን ከሰዱቃውያን ስምምነት እንደሌላቸው ባውቀ ጊዜ ባደባባይ መካከል ቁሞ እኔ ትንሣኤ ሙታን አለ እያልሁ የትንሣኤ ሙታንን ነገር ስላስተማርሁ መከራ የምቀበል ፈሪሳዊ የምሆን የፈሪሳዊ ልጅ ነኝ ብሎ አሰምቶ በጮኸ ጊዜ በዚህ ምክንያት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን እርስ በርሳቸው ተለያዩ ። ስለምን ማለት፥ ሰዱቃውያን ሙታን ከሞቱ በኋላ ፈርሰው በስብሰው ይቀራሉ እንጂ አይነሡም ። መልአክም መንፈስቅዱስም የለም ባዮች ናቸውና ። ፈሪሳውያን ግን መልአክም ፤ መንፈስ ቅዱስም አለ። ሙታን ተነሥተንም እንደገና ቤት ሠርተን ሚስት አግብተን ሕፃናት ወልደን እንኖራለን ባዮች ናቸውና በዚህ መለያየታቸው ጽኑፍጅት ሆነ። እርስ በርሳቸውም ይከራከሩና ይጣሉ ጀመር ከጳውሎስም ጋራ የተቋቋሙበት ሥራት ከንቱ ሁኖ ቀረ ።

አሁንም ምሳሌ መስለን፥ትርጓሜ ተርጕመን፥ የተናገርንበት ምክንያት አንድ አንድ ሰዎች ኢትዮጵያ ስምምነት እንደ ሌላት አድርገው በስሕተት ደረጃ ላይ ቁመው የማይገባ ፖለቲክ ሳይነዙ አይቀሩምና ስለዚህ የአገራችን ስምምነቷ የማይፈርስ አንድነቷ የማይበጠስ መሆኑን ብርሃንና ሰላም አስረድቶ ከስሕተታቸው እንዲመልሳቸው ብለን ነው ። ይልቁንም በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ የጥበብ ዕንስ በኢትዮጵያ ልጆች ሆድ ተፀንሶ ዛሬ በግርማዊት ንግሥትና በግርማዊ ንጉሥ ዘመን የሚወለድበት ወራት ስለገባ የኢትዮጵያ ልጆች የጥበብን አበባ እየቀሰሙ የዕውቀት ነዶን እየተሸከሙ፥ መጥተው ኢትዮጵያ በጥበብ ጌጽ እንድትሸቀረቀር፥ በዕውቀት ሽልማት እንድትሸኰነተር ሲሉ ለትምርት የተዘጋጁ ሕፃናትን ከያውራጃው በየመንግሥታቶቹ አህጉር እንዲማሩ በማድረጋቸው ስምምነት እየፀና፥አድነት እየበረታ፥ፍቅር እየሰፋ፥ሰላም እየፋፋ፥ ይሔዳል እንጂ ፀብ ክርክር መለያየት የሚሉት አይታሰብም ። ከንደዚህ ያለው መለያየት ለመራቅና ለማምለጥ ሲሉ በዕውቀትና በትጋት ስለፀኑ የኢትዮጵያ ልጆች ምሥጢር ከልቡናቸው፥ነገር ከንደበታቸው፥ ብዕር ከእጃቸው የተዘጋጀላቸው ናቸውና በልቡናቸው መርምረው ባንደበታቸው ተናግረው በእጃቸው ጽፈው የስምምነታቸውን

ደብዳቤ የፍቅር መመላሽ በሚሆን በኢትዮጵያ በር ላይ ለጥፈው በሰላምና በአንድነት አጣብቀው ስላኖሩት ማንም ሆነ ያንን እያነበበ አንድነቷን አመስግኖ ይሔዳል እንጂ ኢትዮጵያን በትዕቢት እግር ሊረግጣት የሚችል የለም ።

ስለርኅራኄና ስለቸርነት ።

በርኅራኄና በቸርነት መካከል ያለውን ምሳሌ ብንመረምር ወላጅ እናትና ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በርኅራኄ ሚዛን ትክክል ናቸው ። ወላጅ እናት የናቱን ማኅፀን የሚከፍት ወንድ ልጅ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ይባላል ተብሎ በተነገረው ቃል መጀመሪያ የወለደችውን የበኵር ልጇዋን አጥብታ ባሳደገችበት በጡቷ ከርሱ በኋላ የሚወለዱትን ልጆቿን ሁሉ እኔ የምወደው፤ የእናንተም አለቃችሁ የሚሆን የበኵር ልጄን እያጠባሁ በሳደግሁበት ፀጡቴ እናንተን አጥቢቼ አላሳድግም ሳትል ጡቷን ለሁሉም እያጠባች እንድታሳድግ እንዲሁም ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ እንጌ የቤት አሽከር ነውና ለእርሱ ብቻ ቸርነቴ ይብዛለት። እገሌ ግን የውጭ አሽከር ነውና ቸርነቴ ይከፈልበት ሳይሉ ዘረወ ወወሀበ ለነዳይ ያለውን የዳዊትን ቃል እየተከተሉ እራበኝ ጠማኝ ፥ አጣሁ ነጣሁ ፤ደኸየሁ ተቸገርሁ ፤ ታረዝሁ ተራቄትሁ ላለው ሁሉ እንደሐሳቡና እንደምኞቱ ያደርጉለታልና በእናት ሊመሰሉ አገባብ ነው። ማንም የኢትዮጵያ ተወላጅ የተፈሪን በረከት ያልተሳተፈ አይገኝም ። ለንደዚህ ያለው ለንጉሥ አባት ጠንክሮ እንቅልፍ ሳያበዙ ዕድሜያቸውን ያርዝም ፥ ጠላታቸውን ያድክም እያሉ ወደ እግዚአብሔር ማመልከት ያለሐሰት በውነት ይገባል ።

መዝሙር ሐዋዝ ።

ደጋጉን አስማምተህ ፡ ደግነው ተፈሪ ።
ጥጡን ዳምጠህ ነድፈህ ፥ እንድትሠራው ሱሪ ።
እጀ ሥራ አግብተህ ፥ ልብሱን ከሠራኸው ።
መልከም ልብስ ይሆናል ፥ ባይበዛ ማጣፈያው ።
ልብሳችን ተቀዶ ፡ እንዳናጣ ሱሪ ።
መጥቀም ልማድህ ነው ፥ መርፌያችን ተፈሪ ።
ቤትህ የደመቀው ፥ ያማረው ሰልፍህ ።
ብትመታለት ነው ፡ ጥሩንባ አብዝተህ ።
ዋዚህ የጥሩንባህ ፤ የዜማ እንጕርጕሮ ።
ሳይደርስ የማይቀር ነው ፥ ከፈጣሪ ጆሮ ።
ሆዱን ታጥ እንዳይቀር ፥ የወዳያው ሕዝብህ ።
ጣጣቱ ተከሰው እራሱን ይዞህ ።
እየሰጠሀቸው ፥ እንተ ማር ማሩን ።
እነሱ የሚሹ ፥ ከዳ ከዳውን።
ብቻ ተከተተ ፥ ካንተ ወዲያ ዳኛ ።
ተፈሪ መኰንን የሕይወት መገኛ ።

ስለ መምሬ ማመጫ ።

ሰላም ብሎ አዚሞ ፥ መቍረብ ካቃታቸው ።
መምሬ ማመጫ ፥ ይቅር ሥልጣናቸው ።
መምሬ ማመጫ ፥ ያልተማሩ ቄስ ።
በእንተ ሰላሙን ፡ ጥለውት መሰስ ።
መምሬ ማመጫ ፡ መምሬ እንጕሉ ።
ቢታሠሩስ አሁን ፥ እግዚር ይፍታ ሲሉ ።
ለቤተ ክርስቲያናቸው ፥ ደጅ ሰላም የለው ።
ይህ የጕበኞቻት ፥ ወደት ላይ ሊያርፍ ነው ።
ማን ሊሰማቸው ነው ፤ ብሎ ቁም ነገር ።
ኪዳን የሚያደርሱ ፤ መንደር ለመንደር ።
ምን ቸግሩዋቸው ነው ፡ ትምህርቱን ቢወዱ ።
መማሩን ጠልተውት ፥ ከመንገዳገዱ ።
የነፍስ ልጅዎን ፥ መምሬ ይምከሩ ።
ሕብሮ ከመዋረድ ፥ ሳይባደረደሩ ።
ራስን አዋርዶ ፤ ይሻላል መኖሩ ።
ምን ያሉ ቄስ ናቸው ፤ የሚወዱ አባዜ ።
የሚነቀፍ ነዎይ ፤ እንዲህ ያለው ጊዜ ።
ምንም የላቸውም ፤ ሃይማኖት ምግባር ።
ደም አፍስሱ ካሉ ፤ እንደ ባለ ዛር ።
መምሬ ማመጫ ፤ ቅኔ ፈልገው ።
ይዝረፉልኝ አሉ ፤ ከቤቴ መጥተው ።
ዘረፉውስ ይሁን ፤ ይዝረፉላቸው ።
ከዘረፋው ኋላ ፤ ማን ሊያስፈታቸው ።
መምሬ ማመጫ ፤ ቅዳሴሁ ይቅር ።
ሰላም ካላወቁ ፤ በምን ይጀመር ።
የኛማ ቅዳሴ ፤ ተቀደሰ ደኅና ።
ግባሬ ሠናዩ ፤ ተፈሪ ነውና ።
ተፈሪ መኰንን ፤ የማይጠፋ ፋና ።
ጨለማን አርቆ ፤ ይመራል ጐዳና ።
የሚሔድ ሰው ሁሉ ፤ በርሱ ብርሃንነት ።
ለእግሩ መሰናከል ፤ የለበት እንቅፋት ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ስለ ሀገር ጥበቃ።

ሀገር በኀያላኖቿ በሕይወት ትኖራለች። በሰነፍ ወታደሮቿ ተዋርዳ ትሞታለች። ምሳሌ ባቢሎንና ጢሮስ ሙተዋል እንላለን ጋራዎቻቸውና ወንዞቻቸው ግን አሉ። የጥንት ኀያላኖቻቸው ዘራቸው ጠፍቷልና ። አሁንም ሀገራችን ኢትዮጵያን ከጥንት ጀምረው እስከ ዘመናችን ድረስ ኀያላኖቿ በየጊዜያቸው እንደ ዘመኑ ሲጠብቋት ኑረዋል። እነዚያም ኀያላን አባቶቻችን ስማቸው ከሀገራቸው ጋር በሕይወት እንድትኖር ደማቸውን አፍሰውላታል እንደ ዘመኑ ማለት በፊትም በቀስት ፥ በጦር በጠመንጃ ጠበቋት፤ በሚመጣው ዘመን ግን የነገር (የፖለቲክ) ጦርነት ሳይበረታ አይቀርምና የሀገራችን ሰው ስላልለመደው መጠንቀቅ ያስፈልገናል። እነዚያ ከጥንት እስከሁን ኢትዮጵያን የጠበቁ ኀያላኖች ሃይማኖታቸው (እምነታቸው) አንድ አልነበረም። ከጥንትም በጣዖት በኋላም በኦሪት በወንጌል ያመኑ ነበሩ። በዚሁም ያላመኑ አሉ፤ በመንፈሳዊ መንግሥት ይለያዩ እንጂ በሀገር ክብር አይለዩም። ሰው አርበኛ ተብሎ ለመጠራት

የመፈተኛ ጊዜ ያስፈልገዋል።ጌዴዎን ሰላሣ ሺህ ሰው ለጦርነት አዘጋጀ።የተመረጡና የተፈተኑ ሦስት መቶ ሰዎች ተገኙተዋል ሰነፎችና ፈሪዎች ወደ ድንኳናቸው ተመልሰዋል።ስንፍና በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው ። ሰነፍ ከሩ ስንፍና ያፈልቃል የሚጮህ አንበሳ በመንገድ አለ እያለ ምክንያት እያበዛ የሰነፉን የባልንጀራውን ልብ ያቀልጣል ኃያላኖችሽ እንኳን አንበሳ አለ ብለዋቸው ሊያድኑ ይሄዳሉ ለሰልፍም የተዘጋጁ ናቸው። ከሕዓ ለወጡ ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር ። ኢሳይ ያስ ምዕራፍ ፵፰ ቍጥር ፳፪ ።

ክብርት ኢትዮጵያ ክፍንት ጀምረሽ ። ሰይፍ ንጉሥሽን ጨብጠሽ ቁመሽ ።

መኳንንት ጉፈርሽን ደረብ አድርገሽ ። ኃያላን ጋሻሽን መከት አድርገሽ ። ወታደር ልብስሽን ለብሰሽ አጊጠሽ ። አላለቀም እንጂ ካለቀ ልብስሽ ። በዩ ማሬው ያውልሽ ። እንደ ያምርብሽ ።

ንጉሥ ሰው አዘዋል ደላማ በተኵስ ። ደፈተናል አሉ ይኸ ሁሉ ነፍስ ። ይኸንን ፈተና ፀምን ጠላሁት ። የሳተ ሰው ያፍራል በንጉሡ ፊት ። ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

መወድስ ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ ።

እመ ሙስናሃ ለሳሌም እምገራህተ ሙሴ ።
እመ ፍሬ ትንቢት ተቀስመ ትእምርተ አቤሜሌክ ከንቱ።
በምንት እምከነ ኢንበልሂ ትእምርቱ ።
ወርኃ ዘርአ ወወርኃ ጽጌ ፤ ለወሊድ መዋዕለ ጽጌሃ
ወርኃ ዘርአ አልቦቱ ።
ወኀጠተ ልማደ ዘርአ ብእሲ ፤ ምንትኒ ኢወድቀ ላዕለ
ማርያም ገራህቱ ።
ሰዓትሂ እመ ተኃጥአ ወእመ ኢሀሉ ሰዓቱ ።
ማዕከለ ብሂል ተዋሐደ ወብሂለ ተቀብዓ በትስብእቱ።
ኦሃይማኖት ርትዕት በዘከመዝ ልደቱ ።
እለ ለኪ ይትቀነዩ ምዕመናን ኢይመውቱ ።

ቅልዕ መወድስ ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የሃይማኖት ጽርየት ።

እምኃይለ ሥላሴ ይትመሀር፤ጽንዓ ተዋህዶ ዘኢተወልደ
እሙን ከመ ልደተ ዕንቍ ጽሩይ ።
ኢይወርስ ምንተ መንግሥተ ሰማይ ።
ጽንዓ ሃይማኖቱ ያጠይቀነ፤ ረቂቅ መንፈሰ ጥበቡ ቃለ
ንስር ኀሩይ ።
እስመ ኀበ ፈቀደ ይነፍሕ ወቃሎ ትሰምዕ ማዕከለ ጠፈር
ላዕላይ ።
ዳግመሂ ወለደነ እመንፈስ ቅዱስ ወማይ ።
ውስተ ክርሠ ጎንደር ዘየኀቱ ኃይለ ሥላሴ ዕንቈ ባሕርይ።
አመኒ ሥልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ዓቢይ ።
መንግሥቱ ዘለዓለም ለኃይለ ሥላሴ ወልደ ዕሜይ ።

ሣልስ መወድስ ስለ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ገናንነት ።

ቦ እምሕዝብ እለ ይቤሉከ፤ ኃይለ ሥላሴ ብርሃን ከመ
ነቢየ ጽድቅ ኤርምያስ ።
ወመንፈቆሙ ይቤሉ ከመ ኤልያስ ።
ላዕለ ደብረ ታቦር እስከ ርእዩ ። ዘየዓቢ ግርማ መንግሥትከ በሥጋ ወነፍስ ።
እስመ ኀበ ሀሎ ብዝኃ ኃሢሥ ።
ፍኖተ ዓለም ካልዕ ወፍኖተ ክርስቶስ ንጉሥ ።
አንተኑ ዘትመጽእ ውስተ ቤተ መንግሥት መቅደስ ።
ወካልዕ ዘንሴፎ ኃይለ ሥላሴ ቴዎድሮስ ።
ወአቀመ ለከ ስምዓ ፤ አርአያ ስምዓ ጽድቅ ክርስቶስ ።
ወንጌለ መንፃትከ ተዋሕዶ ዘሰበከ ዮሐንስ ።

መተርጕመ ሐዲሳት አለቃ ኃይሉ።

ስለ ሐረር የትምህርት ቤት መቆምና መታደስ ።

ከብዙ ጊዜ በፊት በሐረር በዋና ከተማዋ ውሥጥ ሁለት የትምርት ቤቶች ተከናውነው ቁመው ሥራቸውን በትክክል ሲያስኬዱና ሁቃዮቻቸውንም በጥበብ አከባክበው ሲያሳድጉ ለሚያፈቅራቸውና ለሚከተላቸው ሁሉ ደምቀው ሲታዩ ይኖሩ ነበር ።

እነዚሁም የትምህርት ቤቶች ፩ኛው የኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት ቤት፥ ፪ኛውም የሚሲዮኖች ነበሩ ።

በነዚሁም የትምህርት ቤቶች ትምህርታቸውን የተማሩና ሐሳባቸውንም ለውቀት ያደረጉ የኢትዮጵያ ሕፃናቶች በውኃ ዳር የተተከለች መልካም አትክልት ልምላሜና አበባ ሁልጊዜ ሳይለያት ፍሬዋንም ለባለቤቷ እንደምትሰጥና ደስ እንደምታሰኝ ሁሉ ያንጊዜ በወቅቱ ተማሪ ቤቶቹ በተጀመሩበት ጊዜ በትጋት የተማሩት ሕፃናቶች ሁሉ ይኸውና አሁን ለለምላሟ እናታቸውና ለገናናው መንግሥታቸው በተሰጣቸው እውቀታቸው እየሠሩና መንግሥታቸውንም በሥራቸው ደስ እያሰኙ ሲሠሩና ሲያገለግሉ ይኖራሉ ።

እነዚሁም ሁለት የትምህርት ቤቶች ብዙ ሕፃናቶች ባመት ባመቱ ለሥራ ያህል የሚበቃ ትምህርት እያስተማሩና እያፈሩ ይኖሩ የነበሩት የትምህርት ቤቶች ከትንሽ ጊዜ በኋላ የመጀመሪያ ትጋታቸውንና ማስተማራቸውን ትተውታል እያሉ እዚያ ሲማሩ የነበሩ ተማሪዎች አጫወቱኝ። እነዚሁም ተማሪዎች ሐረር የሚበቃ ትምህርት አላገኘንም እያሉ ድሬ ዳዋ ለትምህርት ብለው መጥተው ነበር።ያጫወቱኝ እኔም የነዚህን ተማሪዎች ነገር ሰምቼ መጀመሪያ በትጋትና በመልካም ትምህርት ቤት ስመጥሩ የነበሩት ትምህርት ቤቶች በኋላ የመሰነፋቸውን ዝና ሰምቼ ለተማሪዎቼና ለሕፃናቶቼ የበቃ ትምህርት በማጣታቸው እያዘንኩ ስገረም እኖር ነበር ።

ግርማዊው የኢትዮጵያ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ሀገራቸውን በሥራና በትምርት ደረጃ እንደጕረቤቷ ለማድረግ የሚጥሩት ንጉሣችን ለሐረር ከተማ የትምህርት ቤት በትጋትና በጥንቃቄ የሚያስተምሩ መምህሮች አሁን በቅርብ ጊዜ እንዳጣች ስለተረዱና በነገሩም ስላሰቡበት የአዲስ አበባ የአሊያንስ ፍራንሴ ዋና ዲሬክተር የነበሩትን ሙሴ ሞሬል የሚባሉትን ፕሮፌሰር አሐረር ኢትዮጵያ መንግሥት የትምህርት

ቤት አስተማሪ ሁነውና ለተማሪ ቤቱም ዋና ሁነው እንዲሠሩ ላኳቸው ። እኝህም ሙሴ ሞሬል ብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ ሀገራችን ሲያስተምሩና ተማሮቻቸውን ወደ ትክክለኛው ዕውቀት እያበረቱና እየመሩ እየጠበቁ ትምህርቶች ሲያስተምሩ በመኖራቸው በሳቸው ክፍል ገብተው የተማሩና የጐበኙ ሁሉ ሳይረዱት አይቀርም ። አሁን ግን ግርማዊ ንጉሥ የሐረር ከተማ ባስተማሪ እጦት መቸገሯን አይተው እንደዚህ ያለውን መልካም ሐሳብ አስበው የትምህርት ቤቱን ስላደሱት ዳግም ትጋታቸው የታወቁትን መምህሮች በመላካቸው በሐረር አውራጃ ላሉት ወጣቶችና ብላቴናዎች ሁሉ ትልቅ ደስታና መልካም መታሰቢያ ሁኑዋል ።

እንደዚሁም አሁን የጥንቱን የኢትዮጵያ መንግሥት በሐረር ያቆሙትን ትምህርት ቤት ለማደስና ለማከናወን አስበው ሐሳባቸውንም ፈጽመው ያደረጉትን ንጉሣችን እንደዚሁም በያውራጃዋ ከተማዎች ሁሉ የትምህርት ቤት ያቆሙልናል ሲሉ ሕዝቱ በደስታ ይጠባበቃል ። ግርማዊም የሕዝቡን ሐሳብ እንዲሞሉለትና የትምህርት ቤቶች በየአውራጃዋ እንዲያቆሙለት መላው በተስፋና በምኞት ተቀምጧል ።

ውዶችና ተወዳጆች የሐረር አውራጃ ተማሪዎች ሆይ እንደዚህ አስበው መልካም የትምህርት ቤት ላቆሙላችሁ ጌታችሁ በትጋትና በድፍረት ስንፍናንና ፍርሃትን አስወግዳችሁ ተምራችሁ በተቻላችሁ ትምህርታችሁም እንድታገለግሉና ሐሳቢያችሁንም ደስ እንድታሰኙ ስል አሳስባችኋለሁ ።

አስታዋሽ በማጣት ተዝንግቶ ሲኖር ።
ታደሰ ጥበብሽ ደመቅሽልን ሐረር ።
ጥንትም መጀመሪያ ነሽና የውቀት በር ።
ጥቂት ተጉሳቍለሽ ስትታዩ ነበር ።
አስታዋሽ ጌታሽ ደኸው አረገሽ ክብር ።
ልጆችሽን አትጊ እንዲሆኑ መምር ።
ለዳር ድንበሮችሽ እንዲሆኑሽ አጥር ።
አገልጋይ ተብለው ለመንግሥት ለሀገር ።
እንድትከበሪ ትምርትን በማፍቀር ።
ልጆችሽ ቢሰንፉ ምቻቸው በገር ፍቅር ።
ውሥጡን ከሶ አድርገሽ ላዩን በማሳመር ።
ልጆችን ምከሪ ሐረር መልካሟ ዘር ።
ይኸ ያልኩሽ ነገር አያረሽ እንዳይቀር ።
አሳስብሽአለሁ ቢስማማሽ ያለም ክፍል ።

በቀለ ዘለቀ ።

ስለሀገር ፍቅር መልስ ።

፮ተኛ ዓመት ባሥረኛው ቍጥር በ፸፰ ገጽ ብርሃንና ሰላም ፊታውራሪ ፈንታ ወልደ ገብርኤል ጽፈውት እንዳነበብነው ። ለሚያፈቅሯት ልጆችዋ ኢትዮጵያ ደግማ እንዲህ ትላለች ። እኔን አትዩ እኔ ጥቍር ስለሆንሁ ። ነገር ግን ልጆቼ ሁሉም ሰይፍ የያዙ ሰልፍ አዋቆች ኃያላን ናቸው ። ከርሳቸው ሰው ሁሉ ሰይፉ በወገቡ ነው ። መቸውንም ከሚነሣው ጠላት የተ-ነሣ ። እናንተ ነፍሴ የሚወዳችሁ ልጆቼ ሆይ እንዴት ትጠብቁ-ኛላችሁ ።

ወልጄ አሳድጌ ድሬአለሁ ከጥንት
ማንም አይደርስብኝ እሱን ካልከድኩት ።
ደጋውን ወዳችሁ አትፍሩ በረሐ ።
እኔ ስቀናንስ እንዳትሆኑ ድኻ ።
እኔን አስባችሁ ፍቅራችሁ ከበዛ ።
እጠቅማችኋለሁ አታድርጉት ዋዛ ።
ተወ. ፍቅር ይብዛ ምክሬን አትናቁ ።
የናታችሁን ወል ባንድነት ጠብቁ ።
እኔ ሲሳይ ሰሆን የጠባችሁ ነገር ።
ሆዴን ይበላዋል እፌ ባይናገር ።
እዘኑ ልጆቼ በፍጹም ልቡና ።
እንደመለያየት ክፉ የለምና ።
ድንቍርና አሚሉት ያክፉ ጠላት ።
መምጫው አይታወቅ አደጋው ድንገት ።
ፍቅር እያዘነ ሲሔድ አየሁት ።
እናንተ ልጆቼ ካልተፋቀራችሁ
እዩው እናታችን ለምን ትላላችሁ ፣
ከንቱ አለቀስኩ እንጂ የለም የሰማኝ ።
ድንቍርና ማርኮ ሲያስብ ሲገድለኝ ።
የሰው ጕድ በራሴ ሲወራ እሰማለሁ ።
የልቅሶዬ ዘመን ሳያልፍ አበቃለሁ ።

ትላለች ኢትዮጵያ ። እኔ ተኝቻለሁ ልቤ ግን ነቅቷል ። ራሴ ምዝምዝ ወርቅ ነው ። ሲሳዩ እጅግ ጣፋጭ ነው ። ሁለንተናዬ የከበረ ነው ። የከበረ ነው፤ የከበረ ነው። የተወደዳች እናታችን ኢትዮጵያ እንዲህ አድርጋ ስትመክረንና ስትወደን ፍቅርን እንዴት አድርገን ብንፈልጋት ትገኝልን ይሆን ። ወይ ድካም ብንጽፈውና ብናነበው ምን ይሆናል ። ሥራውን ካልሠራነው የከንቱ ከንቱ እንደሆነ አስቀድሜ እኔው በራሴ አፈርዳለሁ ። እምላክ በምሕረቱ ፍቅርን ያውርድልን ስል ጥልቅ ምኞቴን ለክቡራን ወንድሞቼ አቀርባለሁ ። መኩብብ ደስታ ።

ስለ ኢንፉሉዌንስ

ስለ ኢንፉሉዌንስ ወይም ስለ የማትታይ ኃይል በለሚና በተ-ወደደችው ኢትዮጵያ አገራችን ውሥጥ ኢንፉሉዌንስ የምትባል ኃይል ከረጋሮው በጭሩ፡ከብዙው በጥቂቱ፡ ከዚህ በታች እንደ ጻፍነው ነው ። ለኢትዮጵያ አገራችን ልጆች አሳስባቸዋለሁ፤ይህን የኢንፉሉዌንስ ኃይል እኔ በልቤ ተረድቼ ሕሊናዬም ወቅሶኝ ለሀገሬም ልጆች ደግሞ እንዲሁ እኔ እንደተረዳሁት እንዲረዱ-ብዬ ይህን ጻፍሁ ። ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅ-ማል ። መጀመርያ የድንቍርና ዕውርነት ዓይን ይከፈታል ። ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት የፍጥረቱንም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ስፋት ያይ-በታል ። ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቈረቈረ እስከዚህ ዘመን የሆነውን ሁሉ ነገር ስማር ጥንት እንደተፈጠሩ እስከ ቀድሞ እንደነበሩ ሁኖ ያውቃል ። በዓለም ያሉን ልዩ ልዩን ሕዝብ

አገራቸውንና ጠባያቸውን የአምልኮታቸውን የመንግሥታቸውን ሥርዓትና አኗኗራቸውን በታሪክ ሲመለከት ሲመረምር ሲኖ ተውልም በቤቱም ተቀምጦ ዓለምን ሁሉ ዞሮ መርምሮ እንዳየ ሰው ይሆናል ።

የሰውንም ደካማነትንና ብርቱነትን ክፋትንና ስንፍናን ብልሀትን ሐሰትንና እውነትን ቁም ነገርንና ተረትን ተንኰልንና ቅንነትንም ያለበትን ነገር ሁሉ አይቶ ያውቃል። ለሀገሩና ለመንግሥቱም የሚጠቅመውን ለማድረግ ይተጋል። በዓለም የሚደረገውን ክንቱነት ሁሉ ይንቃል። ለበጎ ነገርም ይተጋል። የሰውም ጠባይ ደካማነትንም አውቆ ልቡን በማስፋት ይታገሣል ክፉ ነገርንም እየተወ ለበጎ ነገርም ይነሣሣል። በዕለቱም ወደፊት በዕውቀትና በብልሃት በበጎነትም ልብ ይታገሣል ሰነፎችንም በምክሩና በትምህርቱ ከድንቁርና ወደ ጥበብ ይመልሳል። እንዲሁም አገሩንና መንግሥቱን ያደረጅና ያሰፋል ። አሁንም እኛ በኢትዮጵያ አገራችን ያለአገራቸው ከውጭ አገር የመጡ ሰዎችን ብዙ ጊዜ ባይናችን አይተን በልባችንም ተረድተናል ማለት እነዚህ የውጭ አገር ሰዎች በሕዝባችን ላይ ኢንፌሉዌንስ ኃይል ያደርጋሉ። እንዲሁም የኢንፌሉዌንስ ኃይል በከተማው ሰውና በባላገሩ ላይ እያደረጉ ያ ኢንፌሉዌንስ ይቀጣውና ይገሥፀዋል ግዛት ሳይኖራቸው ኃይልም ሳያገኙ ሳይኖራቸው ። በንደዚህም ያለ መንገድ በግ ጠባቂዋ እንደ ሚመልሳት እንዲሁም የሕዝቡን ልብ ይመልሳሉ። አሁንም በአያሌ መንግሥታት ብናይና ልብ ብናደርግ ብዙ ኰሎኒዎች እንዴት ኰሎኒ እንደሆኑ ብንመለከት በፊት በኢንፌሉዌንስ ኃይል ይመክሩታል ግን በኢንፌሉዌንስ ልቡ የማይመታ እንደሆነ ይተዉታል። እንደምን ብንል እንኳን በጠርነት ብናሸንፋቸው በኢንፌሉዌንስ ልቡ አልተማታም ብለው። የሆነ ሁኖ ሕዝብ በኢን ሉዌንስ ቢመታ ጥቂት በጥቂት አገሩን ይይዛሉ ቶሎ ሳይያዝ እንፌሉዌሱን መበታተን ነው እንጂ በፊት እግር ሲያዝ ቀጥሎም ክፍ ሲል ቀጥሎም ወገቡን ቀጥሎም እጅ ሲቀር ምንቀረ ኃይሉም ሁሉ ተይዞ ምንም አይቀረውም ሳይያዝ መታገል ያስፈልጋል እንጂ እንኳን ሌላው ቀርቶ የአገራችን ጕበዛዝት ከውጭዎች ጋራ ሲገናኙ አርግጥ ጕበዛዝትን ኢንፌሉዌንስ ሲመቷቸው እናያለን። ለሕዝባችንስ አንተ ምንድርነህ ልክ እንደ እኔ ነህ በጠባይም በአኳኋንም በሐሳብም ብቻ የሚገባህን ክብረት አሰጥሀለሁ ማለት ይገባዋል ኢንፌሉዌንሱንም በንደዚህ ያለመንገድ ይበታትንበት ነበር። እንፌሉዌንስን እናጥፋ በሕወታችንም በሞታችንም በኢትዮጵያ ዘወትር መኖር ደስ ያሰኘናል በሌላ አገር ያለ ጌጡ ቢበልጥ እንኳን ለኛ ግን አገራችን ይበልጥብናል የወላጃችን ፍቅር በዚህ አሳደገን የተፈሪ የውሀት በውእቀት ደገፌን ።

በትምክህታችንም ደስ አለን አምላክ የሰጠን። አገር ከሁሉ ደልቅ ተፈሪ ክብራችን ሁኖ ታየን። አባቶቻችን ስለእኛ የለፉት ለአርነት አሁን። ተፈሪ ስላለ ርኅሩኅ ቸር አባት። እኛም በዚህ ልንቀመጥ በክብረት ከውርደት። ይህ ጊዜያችን ያለኢንፌሉዌንስ ሲጨርስ ከአባቶቻችን መሬት። ከዘመዶቻችን ጋር ልናርፍ በአንድነት። ደስ የሚለውን ፈቃድ ለአገር እናቅርብ በተፈሪ ደስታ በትህትና በጭንቅም በየውሀትም እውነት። ፍቅር ለአባቶች መሬት የቀና መታዘዝ ለመንግሥት። የኢትዮጵያ ገጋሮዎችን አምላክ ይባርክ ይምራ ምክራቸውን ዘወትር ከስሕተትም። እንደ አባት ሕዝብን ያያሉ በየውሀት ። ከውጭ አገር ሰዎች ኢንፌሉዌንስ ለመፍታት በብልሀት። እንታገል ለሀገር እናሳይ ለሕዝብ ድፍረት። በሥራችን ተግተን ለሕዝብ ሁሉ በኆነት። ሁልቀን ታጥቀን እንጠብቅ ሕዝባችንን አገር በኛ ሊለማ እናድርግለት ውለታ ፩ለዚህም በሕይወት። ወይም በሞት። ጊዜ አለን ተበሩ እርሱ ይረዳናል በጭንቃችን አሁን ደስ ይለዋል ልባችን ስለዚህ እርሱን እና መስግን ለማገልገሉም እንፍጠን ተፈሪ ሁን ኃይላችን ሕዝብህን ከሞት አድን። ከስሕተትም መልስ ማህበርህንም በዓለም አግንን። ጠብቅ ግዛ ርስትህን አደራጅ ሰኛ ብሥድር። ክፍ ክፍ አድርገን በክብር ።

አባይፉ ብርቄ ።



በለክብርት ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ ዕረፍት

ክብርት ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን አክስት ታመው ሰንብተው በ፸፰ ዘመናቸው የካቲት ፳፰ ቀን ዓርፈው ትልቅ ልቅሶ ሁኖ ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ጳጳሳቱም መኳንንቱና ሠራዊቱ ሁሉ እሥላሴ ቢተ ክርስቲያን ድረስ መጥተው ነጋሪቱ በኀዘን አመታት እየተመታ ብርቱ ልቅሶ ተደርጎ በትልቅ ክብር ተቀበሩ ። ቀብሩም ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ኀዘንተኞችን የሚያፅናና ለክርስቲያንም ተስፋ የሚሆን ከእግዚአብሔር ቃል እየጠቀሱ ተናግረው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱት ።

ብርሃንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና ለግርማዊ ንጉሥ ለልዕልት መኳንን ለዘመዶቻቸውም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

የኀዘን ማስታገሻ ።

ግርማዊ ንጉሥ ስለ ክብርት ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ ሞት በሰስተኛው ቀን ለኀዘንተኞቹ ያስነበቡት ቃል ።

የከበደውን የውነተኛ ጕዳቴንና ኀዘኔን ለመተው ግድ የሆነብኝ ይህ ጊዜ መኳንንቱና ሠራዊቱ ወደጦር የወጡበት ጊዜ ነውና ለነሱ ማሰብና መጨነቅ የሚገባ ስለሆነ ነው ወደማንቀርበት ዓለም ለሔዱት ማዘኑን ታግሣችሁ ከእንግዲህ ወዲህ እሳቸውን በማጣት የተጐዳሁት እኔ ነኝ እንጂ ለናንተ እኔ በሚቻለኝ አለሁና ስለ መንግሥቱም ስለ እኔም እዘኑልኝ ይኸነን ያሰኘኝ ያለፈው ኀዘን ሳይርቅ ይኸነን የተካ ፈጣሪያችን ወደ ብስጭት ቈጥሮ እንዳይቀየመን በመፍራት ነው ።

ስለክብርት ወይዘሮ ክብረተ ወርቅ ዕረፍት ።

ክብርት ወይዘሮ ክብረተ ወርቅ የፊታውራሪ ጣሰው ባለቤት ብዙ ቀን ታመው ሰንብተው ነበርና የካቲት ፳፰ ቀን ዓርፈው ትልቅ ልቅሶ ሁኖ በዚሁም ቀን ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ክብርት ወይዘሮ ወለተ ዮሐንስ ዓርፈው ነበርና ስለሁለቱም ዕረፍት ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ፣ ጳጳሳቱና መኳንንቱ፣ ሠራዊቱም ሁሉ ከሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ድረስ መጥተው ብርቱ ልቅሶ ተደርጎ በትልቅ ክብር ተቀበሩ ። ሲያርፉም የዕድሜያቸው ልክ ሀያ አንድ ዓመት ከሰስት ወር ሁኖ ነበር ።

ብርንና ሰላም ለግርማዊት ንግሥትና ለባለቤታቸው ለክቡር ፊታውራሪ ጣሰው ለዘመዶቻቸውም ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

ለደጉ አሳባችን እንቃዛገ ።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ።

በአዲስ አበባ ሰውና እንሰሳ የብሔርዛፍም ስለበዛ ቤቶችና መንገዶች የተሠሩበት ቦታ ከዝናብ ስለተክለከለ ።

ምንጮችም ደረቁ ። በየወንዙ ያለውም ወሀ ለመውረድ ዓቅም አጣ። ለአዲስ አበባ ስለ ወኀው ሥራ አስቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል አዲስ አበባ ያለሱ ደኅና መኖርያ አትሆንም ።

ስለመንገድ ።

ከአዲስ አበባ ወደ ምዕራብ ፪፻ኪሎ ሜትር የሚሆን የብረት መንገድ ቢሠራ የከተማው ችግር ቀላል ይሆናል።ስለ ሥራውም እርዳታ ተሸካሚው የንጨት ማዕዘን አግዳሚው ብረት ይሆናል

ስለሽክም።

ማዕዘንና ሳንቃ የሚጫንባቸው የጋማ ከብቶች ብዙ ቀን ሳያገለግሉ በጭንቅ ይሞታሉ ለነዚህ ለማይናገሩ እንስሳዎች ጪንቀታቸውን ተመልክተን እንዝንላችው ሳንቃውና ማዕዘኑ በመኪና እንዲጫን እንስሶቹም የሚገባቸውን እዲሸከሙ

ስለ ሥራ ።

ለካህናቶች ቤተ ክርስቲያ ለሕፃናቱም የተማሪቤት ለወታደሮችም አዳራሽ ተሠርቷል።የኢትዮጵያ ልጆች ሥራ የሚሠሩበት በአዲስ አበባ ከተማ ፩ ትልቅ የስራ ቤት (ሆርሻ)ያስፈልጋል ።

ዓለሙ አብተ ሚከኤል ።

አቶሞቢል በአዲስ አበባ ።

በከተማችን በአዲስ አበባ ውሥጥ አቶሞቢሎች እየበዙ እንደሔዱ አይተናል ። አቶሞቢሎች የሚጠቅሙ ብርቱ ጉዳይ ላለው ሰው በፍጥነት አድርሰው ጉዳዩን ጊዜ ሳያልፍበት ሊፈጽም በመቻሉ ነው።እንዲያው ካንድ ቦታ ወዳንድ ቦታ በእግር ወዩም በከብት እዳይሔዱ ለጉልበታቸው ሳስተው ለመንሸራሸር ብቻ ለሚቀመጡት ግን ድኆች ቢሆኑ ያከስራቸዋል፣ ለሀብታሞችም ገንዘባቸውን ያጉድልባቸዋል ሰውነታቸውን ያሰንፍባቸዋል የአቶሞቢል ኪራይ ያልተወሰነ በመሆኑ ፤ቶሞበ ል የተቀመጠ እንግዳ እንደ ባለአቶሞቢሉ ቸርነት መጠን በመክፈሉም ይጎዳልና የአቶሞቢል ኪራይ በመንገድ ርዝመት እየተለከ ቢወሰን መልከም ነው።

የውጭ አገር ወሬ ።

በኢጣልያን ሌጋስዮን የመጣ ራድዮ ።

ፓሪጂ ፤ የሬፑብሊኩ ፕሬሲዳን ደሚርግ ካማከሬ ቤት ፕሬሲዳን ታርድዮና ሚኒስቴር ማራውድ ጋራ በጎርፍ አደጋ የጠፋውን ቦታ ለመርዳት የሚሠራውን ሥራ ለማየት የጎርፍ አደጋ በወረደበት ቦታ ሔደው አዩ ሥራውም በጣም ጭንቅ ነበረ ። እስካሁን ድረስ የጠፉ ሰዎች ከአምስት መቶ በላይ ሁነዋል ። የከብት መንጋዎችም ብዙ ሺ ናቸው ። የውጭ አገር መንግሥታት ለፈረንሳዊ መንግሥት የኃዘናቸውን ተካፋይነት እየገለጹ ብዙ ገንዘብ እርዳታ ይልካሉ ። በነዚሁ መካከልም ሙሶሊ አደጋ ላገኛቸው የኢጣሊያን ቤተሰቦች ሀያ አምስትሺ ሊረ መጀመሪያ እርዳታ ልከዋል ።

የባቲካን ከተማ ፤ ጳጳስ በጎርፍ አደጋ ስለጠፉ ጥልቅ ኃዘናቸውን እንዲገልጽላቸው ፥ ደግሞ እርዳታ የሚሆን መቶ ሺ ሊሬ ጨምረው አንሲዮን ወደ ፓሪስ ልከዋል ።

ፓሪስ ፤ በብርቱ ጐርፍ አደጋ የተደመሰሱትን የደቡብ አውራጃ የፈረንሳዊ አገሮች ከሬሳውና ከበሰበሰ ነገርና ከጭቃ ብዛት የተነሣ ክፉ ቸነፈር ተነሥቶ እንዳይፈጃቸው ለባላገሮች የባሰ ፍርሃት ሁኑዋል ። የጤነነት ሚኒስትር የበሽታ ትሎች የሚፈጅ ነገርና (ዲሲንፌክታንት) ብዙ መድኃኒት የተጫኑ ባቡሮች ከብዙ ሐኪሞች ጋራ ወደተጐዱት አውራጃ ልኳል ።

እለክድርያ ፤ ምስር የቤልጂግ ንጉሥና ንግሥት ወደ መርከብ ማረፊያ ደርሰው ፕሬንስ ቱሳን በምስር ንጉሥ ስም ተቀበሏቸው ። የፋሺስት ወኪሎችና የኢጣልያ ጠረኞችም ለንግሥቲቱ የሚያምር የተጐነጐነ አበባ ሰጡ ።

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
ዝባድ	፩ ወቄት	፳ ብርተኩል
ሰም	፩ ፈረሲላ	፴፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፪ ብርተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፴፯ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፭ ብር
ባለሰይጣን		፻፹ ብር
ባለ ድመት		፻፶፭ ብር
ባለ አሀያ		፻፵፫ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፳፰ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፭ ብር
ጃፖን		፻፹ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፵፪ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፬ ብር ተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፳ ፍራንክ
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፳ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፯ ከ፶ ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ	፶፫

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግር ማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።



Borsalino



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። ሀጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አከሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዳርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
6me ANNÉE № 12

ሐሙስ መጋቢት ፲፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 20 MARS 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ናፍቆትና ስለ መተዛዘን ።

እናት ልጅዋ ወደ ውጭ የወጣበት እንደሆነ ልጄን ለምለም ሣር አያንቅፍብኝ፡እሾህ አይውጋብኝ፥ እያለች እያለቀሰች ዕንባዋን በደረቷ ላይ እያፈሰሰች ልጇ ከሔደበት አገር ደኅና ተመልሶልኝዓይኑን አይቼው፡ጕንጫጕንጩን አገላብጬ ስሜው፡ ፍቅሩን ጠግቤው ብላ እየተመኘች ከልጋ ወርዳ፡ከመሬት ተኝታ ማቅ ለብሳ፡አመድ በሰውነቷ ላይ ነስንሳ፥ ጥሬ በልታ እፍኝ ውኃ ተጐንጭታ ልቧን በናፍቆቱና በፍቅሩ ላይ ሰቅላ ልጅዋ ከሔደበት አገር ደኅና እስኪመለስላት ድረስ በእንደዚህ ያለ ጭንቀትና ኀዘን ተጨንቃ ተጠባ እንድትጠባበቀው ።

እንደዚህም ሁሉ ወደ ዘመቻ ከሔዱት ከጌቶቻችንና ከወንድሞቻችን ተለይተን በከተማ የቀረን እኛም ስለዘመቱት ጌቶቻችንና ወንድሞቻችን ቀኝ መንገድ ምራቸው በሕይወት በጤና ወደቤታቸው መልሳቸው አንድ ሰው ስንኳ ከቍጥር አታጕድልባቸው ። ከነከብታቸው ከነጓዛቸው አቅፍ ድግፍ አድርገህ፡ጠላታቸውን በእግራቸው እርግጥ በእጃቸው ጭብጥ አድርገህ፡በየሰፈሩበትና በያደሩበት ስፍራ ሁሉ ረድኤትህንና በረከትህን ሰጥተህ ደስታቸውን አብዝተህ፥ኀዘናቸውን አርቀህ፥ በሰላም ተመልሰው ከቤታቸው ለመግባት አብቃቸው እያልን ሳቃችንን ወደለቅሶ ፥ ደስታችነን ወደኀዘን መልሰን በትካዜ ሁነን የፍቅር ያንድነት ፥ የሰላም የምሕረት ባለቤት የሚሆን እግዚአብሔርን እንለምነው ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ፥ ይህን መጻፌ ቃል አሳማሪ ምሥጢር መርማሪ ነኝ ብዬ አይደለም ። ምንም ይህ እንደዚህ ያለው የመተሳሰብና የመተዛዘን ሐሳብ በየሁሉ ልቡና የታሰበ ቢሆን በሐሳብ ብቻ እንዳይቀር በገቢር እንዲፈጸም ሊማሳሰብ ትንሽ ትልቅ አያሰኝምና የመንገደኞቹ ናፍቆትና ፍቅር እያነማማ አላስችል ስላለኝ ነው።

ወንድም የወንድሙን ደም እንዳያፈስ ስለሚደረግ ምክር

ብዙ ጊዜ በታሪክ እንደምናነበውና ከሽማግሌዎች እንደምንሰማው አገር የሚጠፋው መንግሥት የሚፈርሰው ፍቅር ጠፍቶ መለያየት በዝቶ በዚህ ምክንያት ሕዝቡ መንግሥቱን፥መንግሥቱ ሕዝቡን ባለመከተልና ባለማፋቀር ነው ። ያገሩ መኳንንትም በመስማማትና በመፋቀር ፋንታ ሲመቀኛኙና ሲለያዩ በመኖራቸው አገራቸውን ያስጠቃሉ። መንግሥታቸውን ያፈርሳሉ ። ኃይላቸውንም ያስንሣሉ ። ሁከት ይሰዳል በረከት እንዲሉ በበረከት ፋንታ ጥፋት፥ በልማት ፋንታ ጕዳት ያገኛሉ ።

አገራችን ኢትዮጵያ በበረከታምነቷ የተመሰገነች ባንድነቷ የፀናች በኃይሏ የተፈራች ናት ። እኛም ልጆቿ ትንሹም ትልቁም ሀብታሙም ድኃውም እንደመጠናችን የበረከቷ ተካፋዮች፥የአንድነቷ ተከታዮች የፍቅሩዋ አገልጋዮች ነን ። በእግዚአብሔር ቸርነት ከርስዋ የምናገኘውን በረከት ፍቅርን፥ አንድነትን፥ስምምነትን፥ በጎ ነገርን የማይወድ ሰይጣን ከእጃችን አውጥቶ እንዳያጠፋብን ስምምነትን ጋሻ ጦር አድርገን ሰይጣንን ድል ነሥተን መንግሥታችን እንዲከበር አገራችን እንዲታፈር ሲል ብርሃንና ሰላም ምክር የሚያውቁ፥ ነገር የሚጠነቅቁ፥ በምክራቸው ደም የሚያደርቁ ሊቃውንቱና መኳንንቱ ሽማግሌዎቹ ለትምርቱ እንዲተጉበት ለምክሩ እንዲያስቡበት የሚያነቃቃ ቃል ከዚህ በታች ያስታውቃል።

ሊቃውንትና መኳንንት ሽማግሌዎችም፥ የሚሰማን የለም ማን ሊሰማን ብላችሁ ዕውቀታችሁን፥ምክራችሁን ሰውራችሁ ሕዝቡ ትምርት ባለመማሩ ምክር ባለመስማቱ ጕዳት እንደያገኘው ። የተወረወረው ጦር እንዲመለስ፥ የተመዘዘው ሰይፍ እንዲከተት፥የተለጐመውም ጠመንጃ እንዳይተኰስ ፥ የመላው ደም እንዳይፈስ፥ የሰው አንገት እንደይበጠስ፥ የጋለው ጠብ

እንዲበርድ ስምምነት ከፍቅር ጋራ እንዲዋሐድ ምቀኝነት ንእ-ዲጠፋ ፍቅር እንዲሰፋ፡ ንባር ወኢታርምም ያለውን ተመል-ክታችሁ ከመጽሐፍ ጠቅሳችሁ ከልቡናችሁም አንቅታችሁ በየወረቀቱ በየጋዜጣው ጽፋችሁ በገራችን ውሥጥ በከተማው ብውራጃው በደብሩ በገጠሩ ዝናም ምክራችሁን ብታዘንሙበት በቀትር ጊዜ እንደሚፋጅ ዋዕየ ፀሐይ ሁና የጋለው ጠብ ሳይቀዘቅዝ አይቀርም ።

ደግሞም ቃልን ብቻ በወረቀት ጽፎ ልክ መቅረት አይዶለም የመስማት ድርስ ንገሩ የሚረዳው ሲማየት ነውና በእግራችሁም ሒዳችሁ ሰው እውነት መንሰቅ የያዘውን ሐሰት በምክራችሁ አርቃችሁ በሐሰት መንገድ የሚሔደውን በውነተኛው መን-ገድ አስኪዳችሁ ፍቅርንና ስምምነትን ዘርታችሁ ብትመለሱ ክሰማይ ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዘሮ አስተምሮ ከእ-ግዚአብሔር ጋራ ተጣልቶ የነበረ ሰውን በመስቀል ያስታረቀ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትመስሉላችሁ ። ሰላምን የሚያደ-ርጉ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ክተባሉትም ትቈጠራላችሁ።

እንደዚህ ግን ካልሆነ ሕዝቡ ምክር አንሰቶ ትምርት ጐድሎበት አንድ ሐሰተኛ መምር የመጣውን የሐሰት ትምርት ተከትሎ ሩቅ ያለውን ወንድሙን በቅርብ ካለው ወንድሙ ጋራ ሁኖ እየነቀፈ ስምምነትን አጥፍቶ እርስ በርሱ ቢፋጅና ቢጣላ ግን መንግሥት ይጐዳል፡ አገር ይጠፋል ፡ ሕዝብ ያን-ነል፡ በረከት ይቀንሳል ፡ ወልዶ መሳም፡ዘርቶ መቃም፡ ነግዶ ማትረፍ፡አርሶ ማምረት፡ አርሮ መተኛት፡ውሎ መግባት፡ እን-ደልብ ወዲያና ወዲህ ማለት አይገኝም ።

ግን እንደዚህ ያለው ሐሳብ በልቡናችሁ ሳይታሰብና በቃላችሁ ሳይነገር ቀርቶ አይደለም ። ነገር ግን ክንግ ክሠለስት እናደርገዋለን በማለት ቀኑ ደረዝምና ወንድምና ወንድም የሚጣላበት ጊዜ ይደርስና ያገሩ ጥፋት የሕዝቡ ጕዳት እን-ዳይፋጠን የናንተ ምክርና ትግሣጽ እንዲቀድም ብርሃንና ሰላም በለሀገሩ ፍቅር እያዘነ እየተቈረቈረ ይህን ያሳስባችኋል ።

የእግዚአብሔርን ስጦታ አክብሮ መያዝ እንዲገባ።

ይድረስ ክክቡር ወዳጄ ከመምህር ብርሃንና ሰላም እግዚ-አብሔር በረድኤት አይለየዎ ብዬ የጸሎት ሰላምታዬን በማክበር አቀርባለሁ ። ሥራ በዝቶብኝ ሳንገናኝ ሰነበትን ። ነገር ግን እንደ የሚገርም ነገር አይቼ ሳላስታውቀዎ እንዳልቀር ብዬ ብዚያች ድውይ በምጠይቀበት።ሙት በምቀብርበት ።ቤት ክርስ-ቲያን እጅ በምነሳበት የዕረፍት ቀኔ ደህችን ቃሪክ ጻፍሁልዎ።

የገነትን እግርነት ዙሬ ከጠገብኋት በኋላ የሳሙኤል ዘወገግ ገዳምን መቅናቴ ብሰማ ለማየት ስሔድ ከበረሀው መካከል አንድ ትልቅ ተራራ ደንጊያው ፍጹም ወርቅ ። አፈሩ ብር ። ዛፉ ጕናጕና ቅጠሉ ከወርቅና ከሐር የተሠራ ግምጃና ብረ ዘቦ ይመስላል ። አንዳንድ ትልልቅ ቋጥኝ በዙርያው አለ ሲፈነ-ቅሉት ትኰስ ዳብ ይሆናል ። ፪ የወተትና የወይን ፈሳሾች ይንሻሻሉ እንዲት መልከማ ርግብ። ክንፎቿ በብር ። ጕድንና ጕድንዋ በወርቅ ያጌጠ ከጕናጕናው ወይም ከከበ ተቀምጣ ያስ-ተያየቷ ነገሯ ያስደንቃል። እኔም ይህ ነገር ምትሐት ይሆናል ወደ ጻድቁ ገዳም መሔድ ስላሰበሁ ጌታዬን ኢየሱስ ክርስቶስን የተፈታተነ ሰይጣን ሊፈታተነኝ ይሆናል እንጂ ይህን ያህል ክብር እሚዳ ላይ ላልበቃ ሰው አይገለጥም ብዬ ቀረብ ብዬ ዳብ የሚመስለውን ደንጊያ ብፈነቅለው። የሚገመስ፡የሚዳስስ የሚቈረስ፡የሚጕረስ ሆነ ። ክፈሳሾች ብሔድ የሚጠጡ፡ የሚ-ጣፍጡ ። ቅጠሉን ከጕናጕናው ብዘነጥፈው ያማስ የሚለበስ የሚያምግስ በሆኑልኝ ጊዜ ፈጣሪዬን አመስግኜ ይህን ትቶ የተ ይኬዳል ብዬ አንድ ባዶ ቤት አግኝቼ እዚያ ገብቼ ያነን እየተመግበሁ ሁለት ዓመት ያህል ከተቀመጥሁ በኋላ ከበታቹ ያለውን ነገር ለማየት ስሔድ አገዛ አገዛ የለበሱ ፫ ባላገሮች አንድ ጃኖ ለባሽ ጭቃ ሹም መሳይ ጋሊት የዐ በጁ ይዞ ይቀበ-ጥራሉ ። ቀረብ ብዬ ብሰማቸው እንዲህ ያለ መከራ። የሰው አገር ሁሉ ጋራ፡አጣጥ አጋም፡ ግራር፡ቀጋ፡ ያበቀላል የኛ ብቻ ወርቅ። ወርቅ አጥር አይሆን ማገዶ አይሆን እያሉ ያጕረጕራሉ እኔም ይህን በሰማሁ ጊዜ ጆሮየን ይዤ ጮሁ ። እንዲህም አልኋቸው ። እናንተ ሰዎች መዓት ሳታመጡ አትቀሩም ። ወርቁ ግብዝነት የሌለው ጥሩ ። ዘአልቦ ቀምያን እንደል ። መፍጼ ለዳ የሚያልፍ ። ልብሱ ብሩህ ዋካ ልብ የሚያስመክ ዳበው የሚያጠግብ ። የሚያነደረብብ። ከዚህ ያማረ ኑሮ ምን ፈልጋችሁ ነው ። የኔን አገር ተራራ በነግራችሁ እንዴት በገረ-ማችሁ ብላችሁ ግንበራቸውን ቋጥረው በልስቲ ንገረን ባሉኝ ጊዜ እሸህ ቢሆን መልቶበታል ነገር ግን መሐንዲሶች ወርቅ እናገኝበታለን ብለው ከሸሁ እየተናነቁ ቢቈፍሩት እንድም ቅንጣት ለምልክት አጡበት። ከጥቂት ዘመን በኋላ የብር አፈር ምልክት አግኝተው መቶ ዳውላ አፈር ነፍተው አንጓለው ባመት ሰስት ብር ካወጡ በኋላ አርማፍ አርገው ተውት ብላቸው። ይሁና ለበረት አጥር የሚሆን እሸህ አግኝተን ሁሉም ይቅር ይጠንጠን ባሉ ጊዜ እግዚአብሔር ይፈርድብኝኋል። ጡር ይደ-ርስበችኋል ብዬ ስነግራቸው የቃሌን ሳልጨርስ። ክንፍ ያለው የሚመስል ነገር እንዳን ቋጥኝ ቢነካው የሰው እጅ ሳይነካው ተፈንቅሎ ወርዶ እኒያን ሰዎች ቀጥቅጦ አመድ ትብያ አድር-ጓቸው ቀመልሶ ተራራ ሆነ።እኔም ያለ ርኅራኄ ይበላችሁ። ለካ በጅ የያዙት ወርቅ ክብረት አንድ ነው የተባለው ይህ ነው ብዬ መንገዴን ሔድሁ ። አሊቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን።

ስለሕዝብ ምክር።

ሕዝብና መንግሥት ጆሮና ልብ ናቸው ወይም ዓይንና ልብ ናቸው ዓይን ያለልብ፡ጆሮ ያለልብ፡ልብ ያላይንና ያለጆሮ፡ ማየ-ትና መስማትና የሌለ መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ስለዚሁ ነገር የሚገባው እንዳይን እንደጆሮእንደልብ ተስማምቶ መኖር የተ-ገባ ነው።ምሳሌ ልብ መ፡ዓይን ሕ፡መጀመሪያ ዓይን ልብ፡አክ-ብሮ እሱ ያሰበውን ልዩ ልዩ ነገር ሁሉ እየተከተለ መሔድ ያስፈልግዋል ነገር ግን ልብ እንዳሰበ በስሕተት የሚሔድበት ጐዳና ገደል ወይም ጕድጓድ የሚሆን የሆነ እንደሆነ ይህ ጕድ-ጓድ ነው ይህ ገደል ነው ይህንን ጐዳና ትተን የተሻለ ጐዳና ይዘን እንሒድ ብሎ ማመልከት የተገባው ነው።ደኸውም ሲሆን ልብ ያሰበውን ጐዳና ሳይለቀ አበጣ ጐበጣውን ትቶ ቀና ቀናውን መሔድ የሚያስፈልግ ነው።ነገር ግን ልብ አንድ ማሰብ አለበት

አንድ አንድ ዓይን ዘወርዋራ ሸውራራ የሚባል ዓይን አለ አንዱን ያየ መስሎ አንዱን የሚያይ አሱን መከተልና የሱንም ሐሳብ ከመፈጸም በጣሙ መጠንቀቅ የሚያስፈልገው ነው ዘወርዋራ ሸውራራ ስለሆነ ሜዳ ያየ መስሎ ገደል እንዳያገባ ።

ሁለተኛ

መንግሥት እንደአጥር እንደመዝጊያ እንድም እንደግድግዳ እንደጣራ ይመሰላል አጥርና መዝጊያ ወንበዴ ጊዜ ያለጊዜ የሰው ገንዘብ ከሚፈልጓ ሌባና አውሬ እንዳያድን መንግሥቱም ሕዝቡን እንደዚሁ ያድናል ይጠብቃል ደግሞ ጣራና ግድግዳ ከዝናብ ከብርድ ከሌላ ከልዩ ልዩ ነገር ሁሉ እንዲያድን መንግሥትም ልብስ ለሌለው ልብስ ጉርስ ለሌለው ጉርስ ሰጥቶ ከረኀብ ከብርድ ከዝናብ ያድናል እንዲህ ከመሰለው አደጋና ጭንቅ ላዳነን መንግሥት ዋጋውን ዕድሜ እንዲሰጥልን የእስራኤል አምላክን በየጊዜው ሳናቋርጥ ለመለመን የተገባን ነው።ሰስተኛ መንግሥት የሚመገበው ከንድ ሰው አይበልጥም የሚመግበው ግን ስሙ ተጠርቶ ቀኅጥሩ ተቈጥሮ የማይዘለቅ ነው አንድ ፩ ሰው በቤቱ ፻ና፲፭ ፳ና፳፭ ተቀሳቢ ቤተ ሰብ ያለ በት እንደሆነስንቱ ፣ ቀልቤ የምዘልቅ ነኝ ብሎ ምነው ዘንድሮ ሞቴን ባቀረበው ብሎ በለቤቱ የሚፈርደውን የሞት ፍርድ በቤቱ ቀኅጭ ብሎ ይፈርዳል እግዚአብሔርንም ያስቀይማል ለዚች ለቲንሽዋ ቍጥር ሰው፤ መንግሥት ግን ቍጥሩ ተቈጥሮ የማይዘለቀውን ስሙ ተጠርቶ የማይደረሰውን አስቦና አሳድሮ ልሁል እግዚአብሔርንም ያለማማረር አመስግኖ ይኖራል እኔ ይህ ደሃ ፳ና ፳፭ ቤተ ሰብ ሲቀልብ የሞት ፍርድ የፈረደ እንደመንግሥት ቍጥሩ የማታይወቅና ስሙ ተጠርቶ የማይዘለቀውን ሕዝብ አሳድር ቢሉት ስንት ጊዜ ሊሞት ነው እዬ ጉድ እዬ አለመታደል ይህንን ልብ ይዞ የሰው ማሰብ ይህ ድሃ የሕዝብ ግጋር ቢያደርጉት ባንድ ሰዓት አገርሆን እልም አድርጎ ያጠፋት ነበር።ይህ ሁሉ መሆኑ እግዚአብሔር ባልሰጠው ስጦታ የሰው በማሰብ ነውና።መንግሥት ግን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው አለመመረርና ያለመሰልቸት እምላኩን አመስግኖ ባለቤቱ በቃ እስኪል ይኖራል ።

አራተኛ ምሳሌ ባጭርና በረጅም ።

አንድ አጭር ሰው በከተማ ላይ ሲኖር ብዙ ረጃጅም ሰዎች እያየ ይቀና ነበር ። እንደነሱ እኩል ለመሆንም ያስብ ነበር ይህንኑ ሐሳቡንና ምኞቱን ለሰው ያከፍል ነበር።ከዕለታት አንድ ቀን ፩ አናጢ አንት አጭር ሰው ሁልጊዜ በረጃጅሞች ሰዎች ስትቀናና እንደነሱም እኩል ለመሆን ስታስብ እሰማለሁ ነገርግን ጥያቄ አላደረግኩም ነበር አለው ይህንኑም ሐሳብህን ልፈጽምልህ እችላለሁ አለው በደስታም ተቀበለው ያንጊዜውኑ ከነኛ ከረጃጅሞች ሰዎች እኩል የሆነ መሰለው እንጂ ምንም አጭር የሆነ አልመሰለውም ነበር ምን ማድረግ ነው የሚሻለው ብሎም ጠየቀው። አናጢም መለሰ።መጀመሪያ አንድ ረጅም ጥራ አለው። ሁለተኛም የሚባልጥህን ያህል ለክተህ ስንት ሳንቲ እንደሆነ አስታውቀኝ አለ።ያም አጭር ያዘዘውን ሁሉንም አደረገ ስንት ሳንቲ እንደሚበልጠውም ለክቶ ሰጠው። ያም አናጢ የእንጨት ጫማ ሠራለትና ከጨረሰለት በኋላም አደረገው። ለጊዜው አጭር ሆይ ሒደና ከዚያ ከረጅሙ እኩል የሆነ መሰለው እንጂ ምንም ሒዶ ከጭሩ እኩል ሆነ ለመባል አልተቻለም ። ትንሽ እንደተወላከፈ ከንድ ትንሽ ጉድጓድ ገብቶ ተሰበረ ዳሩ ግን እግዚአብሔር መሐሪ ጌታ ነውና ምሕረት ልማዱ ስለሆነ ከሞት ዳነ። እግሩ ተሰባብሮ ይንፏቀቅ ጀመረ. አረ እግዚአብሔር በሥራው ላይ ሰው ለመቀጠል ማሰብ እንዴት ያለ ተራራ ነው እንዴትም ያለ የራቀ ነው አያችሁ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠውን ስጦታ በራሱ ስጦታ አገኛለሁ ማለት ለዚህ ያደርሳል ። እግዚአብሔር የሰጠውን ቁመት ከሱ እኩል እሆናለሁ ብሎ ቁሞ የሚያየውን ረጅም ተቀምጦ አየው እግዚአብሔር ያልሰጠንን ስጦታ ከማሰብ ይሠውረን ፤ ልባችንንም ከዚህ ያርቀው ስል ልመናዬን ለእግዚአብሔር አቀርባለሁ ።

ግ ጥ ም ።

እግዜር ያልሰጠውን ምኞት መሔኘት ።
ቁሞ የሚያዩትን ተቀምጦ ማየት ።
ወድቆ ተሰባብሮ ራስን ማጥፋት ።
ራስ አለኝ ይላል እንደ ባለ አእምሮ ።
ረጅሞችን ሲያይ ልቡ ተሠውሮ።
ይኸው ቀረላችሁ ወድቆ ተሰባብሮ ።

፭ት ምሳሌ በእባብ ።

አረ አያዘልቅም አጭር ከረጃጅም ቁመትን ቀላውጦ ።
እንደእባብ መጣል ነው እራሱን ቀጥቅጦ ።
ቀጥቅጦ ከልጣሉት ራስ እራሱን ።
እባብ ክፉ አውሬ ነው ያስታል ሁሉን ።
ሌላ እንኳን አልቀረው አዳም ሔዋንን ።
ክፉ አውሬ ነውና መርዙን ሳያበክን ።
ጉድን ጉድኑን ማለት ነው በመውዜር በለባን ።
እጉድጉ ላይ በለው ለደሙ አላፊ ነኝ ።
የሱን ቁመት ትቶ የሌላውን ሲመኝ ።
ለባብ አትሳሳ በመጽሐፍ ተጽፏል ።
ተጉድጉ ተውና እራሱን ብለህ ጣል ።

፮ት ምሳሌ በውኃ ።

ይኸ ሰፊ ጅረት እንደጉድጉ ስፋት እንደምናየው ።
የሚወስድ ይመስላል ሰው የማይቀረው ።
ለጊዜው ነው እንጂ ከፍ ብለው ሲያዩት መነሻም የለው ።
እንደደጀን ብዛት እንደ ፌታውራሪ ።
ይመስለው ይሆናል ሁላችንም ቀሪ ።
ጉድንን ተመልክቶ ሰውን ሊወስድ መጣር ።
ጉምን በበለሴ ጨብጦ መቋጠር ።
ለዚህ ለጉድናችን የብዛቱን ነገር እንደምናየው።
ከፍ ብለው ሲያዩት እራስም የለው ።
ጠን ጠን በለው አይዘህ አትፍራው ።

፯ተኛ ምሳሌ በዛፍ ።

የዚህ የዛፍ ጌታ እራሱ መጥፎ ነው ።
ያን ዙሉ ቅርንጫፍ ሊያስመለምለው ነው ።

እንደኔ እንደኔ እንደኔማ ሐሳብ።
ራሱን ጣልና ቅርንጫፉን ሰብስብ ።
ግንዱ አንድ ራሱን ቢወድቅም አይጐዳ ።
ወይ ለገዳም አይሆን ወይም ለከተማ ።
ለሞፈር እንኳ አይሆን እራሱ ጠማማ ።
ቀድሞም አስቀማጩ ያንን ጠማማ ዛፍ ማስቀመጡ እንዲያው ነው
እራሱን በገመድ ተብትቦ መጣል ነው ።
ይህነን ቅርንጫፍ ጭሰማውን ተወው ።
አድጎ ከወፈረ የሚረዳ እሱ ነው ።
ይኸ ጠማማ ግንድ በቅርንጫፍ ተዛት እንደዚያ ሲጠር ።
ቈራርጠው ቢጥሉት ብቻውን ሲቀር ።
ይኸ ጠማማ ግንድ እንዳመሉ ክፋት እንደምናየው ።
ገላልጠማ ቢያዩት ረብም የለው ።
ዞሮ ተጠምጥሞ ራሱን ያጥፋው ።
እንዳይንና እንደልብ እንደጆሮ ሁነን ።
በሦስቱ ምሳሌ ፍቅርን አብዝተን።
ለገጋሮው ተገጋር ሁነን ተከባብረን ።
ብንኖር መልካም ነው በዚችማ ዘመን ።
የዘውዲቱንና የተፈሪን ዕድሜ ያርዝመው አያልን ።
ያምላክን ምሕረና እያቀራረብን ።
ብንኖር መልካም ነው በዚች በገራችን ።
አሁንም መልካም ነው አሜን አሜን እያልን ።
ኅብረ ድንግል ድበቡ ፡

የምቀኝነት ፈንጠዝያና ከወሰን መተላለፍ ።

ምቀኝነት በዓለም ሁሉ አለ በባላንጣነትና በመወዳደር ምክ ንያት ይዱ በአገዱ ይመቀኛል።ዛሬ በአገራችን ግን ከወሰን አልፎ ፈንጥዚል እንኳን ለሰውና ለአገራቸውም ሳይቀር ምቀኛ መሆን የጀመሩ ሰዎች ይኖራሉ ብለን እንጠረጥራለን ። ሰው አላወቀብኝም አላየኝም ብሎ ክፉ ነገር መሥራት ስሕተት ነው ምንም ቢሆን ነጌታ ወቅ አይቀርምና ወደ ፊት ለሚገፋ ለመልካም ሥራ ሁሉ ዕንቅፋት ለሚሆኑ ሰዎች ወዮላቸው ወየው በስማቸው ብዙ የኢትዮጵያ ሕፃናት ታሪኽ ለመጻፍ ተነሥተዋልና እንደዚህ ቀደሙ በግልጽ ወይም በሥውር ክፋትን ሠርቶ ማምለጥ አይገኝም።ታሪክ ጸሐፎች የተሠራውን ሥራ ወደፊት በግልጽ ወደ ብርሃን ያወጡታልና መጠንቀቅ ያስፈልገናል።ክፋት ሸሽገን ሠር ተን በአፋችን መልካም ተናግረን ደግ እንምሰል በማለት የምና መልጥ አይመስለኝምና በታሪክ ላይ ክፉ ስም ተጽፎብን ለልጆ ቻችንና ለልጅ ልጆቻችን ኀዘንና ንዴት እንዳንሆናቸው ይሁን። መልካም ሥራንና ብርሃን ምንም ቢሆን ተቃውሞ ማስቀረት አይቻልም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የክርስቲያንነትን ትምህርት ለማስቀረት ስንት ሰዎች ደከሙ ግን ብርሃንን ለመ ከልከል፥ የማይቻል ነውና አልቻሉም።በኤውሮፓስ ስንት ብዙ መልካም ሥራና ዕውቀት እንዳይሰፋ የተጋደሉ ሰዎች ነበሩ።ግን የነሱ ስም በታሪክ ተበላሸ እንጂ መከልከሉን አልቻሉም።አሁ ንም መንግሥትም ቢሆን ሕዝቡም ቢሆን ለአገር ጥቅም አቁ መው የሚሠሩትን መልካም ሥራ እርዳታ አስመስለው በተን ኰል የሚቃወሙና ለራሳቸው ጥቅም ፍላጐት መልከሙን ሥራ የሚጐዱ ወየው ለስማቸው ።
ይፍሩ ታሪክ ።

ዕውር ከገደል አፋፍ ላይ ቁሞ ከመሪው ጋራ ሲጣላ ስለተገኘ ።

መሔድ ፡ ያስያል ጕድ ፡ መዘር ያሰያል ግሩም ነገር ፤ ከሰለታቱ ባንድ ሰለት ወደ ውጭ አገር ወጥቼ ቀልቀሉቱን ወርጄ ዳገቱን ወጥቼ ከፋፉ ላይ ስደርስ ዙሪያው ገደል የሆነ ለማረፊያ ያህል የሚሆን ጥቂት ሜዳ አይቼ ዓርፋለሁ ፡ ብዬ ብሔድ አንድ ዓይነ ሥውር ከገደል አፋፍ ላይ ቁሞ ጠብ እን ሥቶ ከመሪው ጋራ ተጣልቶ መሪውን ይዞ ለመደብደብ እየ ፈለገ ደንበር ገጥር ሲል መሪውም እረተው ወንድሜ ምን አልሁ ቀልቀሉቱን አዝላሚ ዳገቱን አስታምሚ አሾህ እን ዳይወጋህ ዕንቅፋት እንዳይመታህ ተጠንቅቄ እየመራሁ ከዚች ከጥቂት ሜዳ ያደረስሁህን እኔን ብርሃንህን ጠልተህ በምን ነገር ትጣላኛለህ ። መጣላቱንስ ይሁን ተጣላኝ ከሰው ሳላደር ስህ ከቤት ሳላገባህ ከዚህ ከገደል አፋፍ ላይ ቁመህ ሳለህ እኔ ትቼህ ብሔድ አንተ ከዚህ ገደል ወድቀህ ተንኳቶተህ መቅ ረትህ አይደለንም ይልዋል ። ያም ዕውር በትመራኝ ተወው ምስጋን ድንግህ አንተ የሔድህ እንደሆን እኔ አቶ ደንበሴ እጉዳ ይሆናል ብሎ ፡ ባፍስ በባሕር ይሞላ ዓሣውን ዓሣ ይበላ እን ዲሉ ከቶውንም መሪውን እመታለሁ አለና የያዘውን ምርኩዝ ቢወረውረው ገደል ተሽቀንጥሮ ገባ። መሪውም ከዚህ ከገደል አ ፋፍ አውጥቼ ከደልዳላ ቦታ አደርስሀለሁ ብዬ ነበር አንተ ልብህ እንዳይገነህ ጠፍቶ አይሆንም ከልህ ምን አደርጋለሁ ብሎ በጎ አጋርዋን ጠላት ማለት ይህ ነውን እያለ ጥሎት ሲሔድ አይቼ እኔም እስቲ እሺ ቢል ልምከረው ብዬ ጠጋ አልሁና ወንድሜ እንዴት ዋልህ አደርህ ብለው ደግሞ ይህ ተየት የመጣ ነው ደኅና ባልውልና ባላድር ምን ቸግሮህል ብሎ እኔን ለመም ታት የጭፍኑን ደንጊያ አፈልጋለሁ ሲል በዚያ በገደል ተን ከባሎ ከመከከል ሲደርስ ቀጫጭን ሐረጎች ጠልፈው ይዘውት ከነሱ ላይ ተንጠልጥሎ ሳለ እኔም እንደዚያ ~~ሰውዬ ልሔድ~~ እንጂ ምን አደርጋለሁ ብዬ ወደ አሰብሁት ጕዳይ አልፌ ሔድሁ። እኔ ከሔድሁ በኋላ ያ መሪው ከቤቱ ደርሰ ጎርፎ ሳለ ነገሩ ግርም አለውና ለዘመድ ለባዕድ መፈረሪያ እንዳይሆን ሲል አንድ ሰው ጨምሮ ለሁለት እንደምንም ብለን እናመጣዋለን ብሎ ቢሔድ በገድሉ ተንከባሎ ከመከከል በሐረግ ተንጠልጥሎ አገኘው።ደንግጦ አዝኖ በርኅራኄ ቃል ተጣርቶ ወንድሜ ሆይ የኔን የወንድምህን ምክር ሰምተህ ቢሆን ይህ ሁሉ መከራ ባል ደረሰብህም ነበር አሁንም ገመድ እንስደድልህ ገመዱን ጨብ ጠህ በዚያ ተንጠላጥለህ እኛ እየጐተትን እናውጣህ ቢለው ዓይንህን ያውጣውና እኔው እራሴ እወጣለሁ እንጂ አንተ ታወ ጣኛለህን እያለ ደበሳጭ ጀመር ጨለማ ገልማጭ እንዲሉ ብስጩ ለልማዱ ባልሆነው ነገር ሁሉ ይበሳጫልና ።

መሪውም አሁንም አትተወውምን ጠጣ ተይዞ ትዘፍን እንዲሉ ጨለማ ውጦህ ከገደል ላይ ተንጠልጥለህ እነዚህን ሐረጎች ምናምን ቢበጥሳቸው ማረፊያህ ወዴት ይመ

ሽልሀል አለና ያደኑስ መታወር ይሁን ልቡ ደግሞ ዕውር መሆኑ በራሱ ኃጢአት ይሆንን ¿ ወይስ በዘመዶቹ ኃጢአት ይሆን እያለ የኀዘን እንጒርጒሮ እያንጐራጐረ ወደቤቱ ተመለሰ ። ያም ዓይነ ስውር ከዚያው ከገደሉ መካከል እንደተንጠለጠለ ቀረ ።

ነገር ግን ምክር ሰምቶ ልብ ገዝቶ ቢቆይ አጸድቅ ያለ መንገደኛ ጕትቶ ሳያወጣው አይቀርም ።

እንተ ወንድማችን ፡ አትጥላ መሪን ።
ተመልክቶ ቃኝቶ ፡ ቢመራ አቡኑን ።
ደልቅስ ልንገርህ ፡ የሚገባውን ።
እንተም ደግሞ እንዳርሱ ፡ ምራ ሰላሙን ።
ወሚጥ መዓትክ ፡ ብለህ ዜማውን ።
አልሰማህ ይሆን ወይ ፡ ቀለ ወንጌልን ።
ሲሰብክ ሲያስተምር ፡ እንዲህ ሲል ሕዝቡን ።
ሥራው የከፋ ሰው ፡ ይጣላል ብርሃን ።
እንዳይገልጥብኝ ሲል ፡ ክፉ ምግባሩን ።
ከመሬ ተጣልቶ ፡ ከመዓበት ገደል።
ይሻል ይመስለኛል ፡ መሪን መከተል ።
እንዴት ያለ አራሽ ነው ፡ የሆነ እንኰል ።
የሚዘራ እንክርዳድ፡ከሥንዴው ማሀል ።
እኛ ምን ቸገረን ፡ ቢዘራ እንክርዳድ ።
የገዛ ራሱ ነው ፡ የሚንገዳገድ ።
አሁን ማንን ጐዳህ፡አንተ ዓይነ ስውር ።
ከገደል መካከል ፡ ተጨንቀህ ብትቀር ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

ለኢትዮጵያውያን ወይዛዝር ማስታወሻ ።

ከሁን ቀደም የእናንተና የኀፃኖቻችሁን ሐሳብ ሁሉ በጥብብ አጐልምሳ በመልክሙ የሥልጣኔን ጐዳና ወደምታስተምር የትምህርት ቤት እየሔዳችሁ እንድትማሩና መሃይምን ናቸው ከመበል ስማችሁ በጥቂትን እንዲጠራ በማለት ብዙዎቹ ተቈርቋሪዎቻችሁ በየጊዜው እየጻፉ አሳስበዋችሁ ነበር እነሱም መጀመሪ እንዲህ ሕመምተኛሰውነታችሁን በሻሽ ሸፋፍናችሁ ስለምትጓዙት። ፪ኛም ቀሚሳችሁን በጭር እንደመታጠቅና እንደመቀልጠፍ ሁሉ ከቁመታችሁ አስተርፋችሁ ፳፫ ሳንቲም ያህል እያንዘረፈፋችሁ በግራችሁ ስትጓዙ የበቡሩን መንገድ አቧራ ትርፉ ልብስ ስለሚጠርገው ሶስተኛም አቤታችሁ ተቀምጣችሁ ሥራ በመሥራትና ጐጆአችሁን በማሰናዳት ፈንታ ደጅ ጥናት ሕለብን እያላችሁ ከአንዱ ዘንድ ወዳንዱ ዘንድ በመመላለሳችሁ ባለመማር ነውና እስኪፈጠን ብላችሁ በጭሩ ተጣጥቃችሁ ክንንበችሁንም አስወግዳችሁ ደጅ ጥናት የሚበለውን ርስት ንቃችሁ ወደተማሪ ቤት ቢሆን ሐሳባችሁና ሥራችሁ እንዴት ያለውን ክብር ባገኛችሁት ነበር ።

በሶርያና በፓላስቲን ያሉትን ክርስቲያኖች በመማርና በማወቅ ክንብንብን ንቀው በግልጽ ሁነው ቀሚሳቸውን በጭር ታጥቀው ትምህርትን አፍቅረው ለጐጆዋቸው ጥረው ይኖራሉ።

ምነው አይከናነቡም ብለን ከዚያ አገር የመጡትን ሰዎች ብንጠይቃቸው ክርስቲያን መሆናችንና ክርስቲያኖች መባላችን ያለኃፍረት በድፍረት ከስንፍና ወደ መሥራት ከድንቍርና ወደ ትምርት እያሰብን ልንሠራና ልንፈጽም ነው እንጂ የሚገባን ፩ኛ እንደቍስል ለመሸፋፈን ፪ተኛም እንደሴብ ወይም እንደጕደኛ አታላይ ተሸፋፍነን አሸንጕሊት መስለን መሔድ አይገባንም እያሉ ነው አሉ በግልጽ የሚሄዱት ።

እንደዚሁ ኃፍረትን አርቃችሁ ብርታትና ትጋትን አሰፋፍታችሁ እንድትኖሩና እንድትመሰገኑ ደጅ ጥናት በማፍቀር ፈንታ ትምህርትን ወዳችሁ ተምራችሁ አዋቂዎች ተብላችሁ እንድትኖሩ የሥልጣኔና የትምህርት ደጅ ጥናት ይደርባችሁ ስል ብዕሬን አግዳለሁ ግና ቢሆን እያደርኩ አርእስተ ነገሩን እጽፍላችኋለሁኝ ።

ዓለምን ሲያሳሳ ውቡ ፀዳላችሁ
ሁልጊዜ ሲያስፈራ የጥበብ ሥራችሁ
እንዴት ትታሙብን ባለመማራችሁ
እረጅሙን ቀሚስ ባጭሩ ታጥቃችሁ
በወቅቱ ተማሩ አሁን በጊዜያችሁ
ሻሽ የሚባለውን ክንብንብ ንቃችሁ
የትምርትን ማሾ ብርሃኑን ይዛችሁ
በርቱና ተማሩ እንደተቻላችሁ
ሥልጣኔን በድፍረት ገንዘብ አድርጋችሁ
ኃፍረትም እንዲርቅ ትጋትን ለብሳችሁ
አሁን ነው ወይዛዝር የሥራ መሥሻችሁ
ይኸን የኔን ሐሳብ እዩት መርምራችሁ
ቢከፋም ቢለማም ይቅርታ አድርጋችሁ

በቀለ ዘለቀ

የልጅ ወቀሳ ።

ቤትሽ ለማማሩ ሰው ሲቀናብሽ
መልስ ለማፍረስ ምነው መጣርሽ
መስትዋቱን ከፍተሽ ብርሃን ሲታይሽ
እንዲጨልም ነው ወይ በቀን መዝጋትሽ
ቀኑ እንኳን አለመሽ ገና ብርሃን ነው
በሩ መንገርበሱ በቀኑ ምነው
ለስምሽ ማስጠሪያ ጥቂት ይበቃሻል
ይኸ የቁም ተስካር ቢቀር ይሻልሻል
አርጅና በዝቶበት ደከመኝ እያለ
ጐረቤቶችሽም ያስተዛዝናሉ
ለተስካሩ እርዳታ በጣም ይጥራሉ
የቁም ተስካርማ ካወጣሽላቸው
ለማኙ ብዙ ነው በመካከላቸው
የናታችን ፍቅር ሰቀቀን ይዞን
ላሳዳጊ ሞግዚት እንዳትጥይን
ልጆቿን ማሳደግ አታውቅም እያሉ
እናታችን ሳለሽ ሞግዚት ይመኛሉ
እኛን ለማሳደግ ሲጣጣር ልጅሽ

ምነው በዘኵልሽ አለመርዳትሽ
ለእንግዳ በሆነ ይኸ ድግስሽ
ለገዛ አሽከሮችሽ ምነው ማረግሽ
ምግቡን አሳመርሺው ደኅና ተሰናዳ
የሚገባው ግብር በሆነ ለንግዳ
እንግዳ ሲመጣ መብቱንግዶ አለብሽ
አያሳፍርም ወይ አሽከር ማስጨረስሽ
ላሽከር ብታደርጊው ምን ያደርግልሻል
ለንግዳ ይቀመጥ ባልቴት ያሰኝሻል
የቀረበው ምግብ ብዙ ነው ዓይነቱ
እንጀራ ለመብላት የተሰለፉቱ
ራብ እንኳን አዶል ጥጋብ ነው ግዚያቱ
መድፍ ሲተኰስ ነው ግብሩ የሚገባው
የተሰናዳውን ጕራሹ ብዙ ነው
የቀስከሩ ምግብ ወጡ እየጣፈጠ
ትንሹም ትልቁም ሁሉን እቈመጠ
የዛሬውስ ምግብ እንደሳት ያፋጃል
ወጡ አይቀመስ ብዙ ሰው ይፈጃል
ምን ዓይነት ምግብ ነው እንዲህ የሚፋጅ
ከላይ ደኅና ወርዶ እታች የሚፈጅ
እንደዚህ ያለ ምግብ የተደረጀው
ባለመሠልጠኝ ነው ሰው የሚፈጀው
ግብሩ ተሰናድቶ ሲገባ ሲያውት
ለስምሽ ማስጠሪያ እንዳያደርጉት
ሥልጣኔ እንቢ ብለው ማግጠው የሚኖሩ
በግድ ተይዘው ከመተሳሠሩ
ይሻላቸው ነበር በደኅና ቢማሩ
ንብረትና ጕዡ ሳኒዝ ልጆችሽ
እኛን ለማሠልጠን ምነው አቃተሽ
ሥልጣኔ ብንማር ጕገር ያወጣናል
ሥልጣኔ ከሌለን ምን ንብረት ይሆናል
በናታችን ጊዜ ሳንሠለጥን
ለእንጀራ እናታችን መሳቂያ እንዳንሆን
ሱዳን በጥጥ ዝሪት ሲወዳደርሽ
ሺራፊ አገሮችሽ ሲፎካከሩሽ
ምነው በላያቸው አለመሆንሽ
ሥልጣኔ ገሥመረች እያሉ ሲሉሽ
ለትዳር መሆኑ እየታወቀሽ
ለካብትሽ መሆኑ እየታወቀሽ
ለራስሽ መሆኑ እየታወቀሽ
ምነው ለንብረትሽ አለማሰብሽ
ምቀኞችሽ ሁሉ ሲዘባበቱብሽ
እነሱም ሲስቁ አንቺም ትስቂያለሽ
እረ በስንት በሖል ቃስወቅሽናለሽ
በዓለም ሁሉ በጣም እንድትከበሪ
ጨለማ አስለቅቆ ያኑርሽ ተፈሪ

ኪዳኔ ማ ተ ።

ስለ ቦምብ ፈተና በአይሮፕላን ።

በመጋቢት ፰ ቀን ከዲስ ዓለም ወደ አዲስ አበባ ስመጣ በ፲ሰዓት ገፈርሳ ላይ ስደርስ እንዳጋጣሚ አይሮፕላን በሰማይ ላይ ሲበር አይቼ የሚያርፍበትን ቦታ ለመመልከት ቆሜ ሳለ ፡ ሚዳውን አንድ ጊዜ ከዞረ በኋላ በዚያው በየረ ላይ እንደሆነ ቦምባውን ጣለው ፤ የቦምባው ም አወራረድ ከአይሮፕላኑ ሲወጣ ወፍ መስሎ ይታይ ነበር ፤ ዝቅ ሲል ግን እስኪያርፍ ድረስ ድምጡም አይሰማ በይንም ለማየት አይቻልም ። ባረፈም ጊዜ ድምጡ ከመድፍ ኃይል ይበልጥ ጮኾ ተሰማ የወደቀበትንም መሬት ጓናየው በበሬ የታረሰ ቅብቅብ መሰለ ። በምበውንም ለመጣል አይሮፕላኑ ወደ አየር የወጣበት እርቀት እስከ ፻፶ ሜትር ድረስ ነው አሉ ። የዚሁንም በምብ የሚያደርገውን ጉዳትና ጥቅም ብጠይቅ ለጦርነት ሥራ ይልቁንም ለተከበበና አምባ ውሥጥ ዘግቶ አልወጣም ላለ ዓመፀኛ መቅጫ ነው አሉኝ ። የኃይሉም ብዛት እመሬት ካረፈ በኋላ እርቀት ጣራና ቀኝ ሲበትን እስከ ፻፶ና ፪፻ሜትር ድረስ እየራቀ ይገድላል ያቆስላል አሉ ። በአይሮፕላኑ አኳኋን ስንደነቅ ላገር መጠበቂያና ለክፉ አድራጊ መቅጫ እንደዚህ ያለ ባለግርማ መሣሪያ መጥቶ በዘመኔ ዘማየቴ እጅግ ደስ ብሎኝ ፤ ይህንን ለማሳየት በዕድሜ ያቆየኝን ፈጣሪዬን አመስግኜ ወደ ሰፈሬ ገባሁ ። ደብተራ ክንፌ ።

ስለ አቶ ጕሣ ኪሮስ ዕረፍት ።

አቶ ጕሣ ኪሮስ ብዙ ቀን ታሞ ሰንብቶ መጋቢት ፭ ቀን ዓርብ በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ባለው መቃብር ተቀበረ ። በልጅነቱ በሰሞተም ለዘሞዶቹ ሁሉ ትልቅ ጕዳትና ሐዘን ሆነባቸው ።

ብርሃንና ሰላም ላጕቱ ለብላቴን ጌታ ወልደ ማርያም ፤ ለወንድሙ ለአቶ በቀለ ኪሮስ ፤ ለእህቶቹና ለቤተ ዘመዶቹ ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል ።

በባቡር መሳፈር ።

ክቡር አቶ ወዳጆ በአስመራ የኢትዮጵያ ቆንስል እንዲሆኑ ተሾመው ፤ ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ መጋቢት ፲ ቀን በባቡር ተሳፍረው ወደ አስመራ ሔዱ ።

በዚሁ ቀንም የክቡር ራስ ሥዩም ወኪል ክቡር ፊታውራሪ መስፍን ወደ አገራቸው ወደ ዓድዋ እንዲሔዱ በባቡር ተሳፈሩ።

ክቡር ሚስተር ቤዋን የመጽሐፍ ቅዱስ ማሕበር ወኪልም ከክብርት ባለቤታቸው ጋራ ወደአገራቸው ወደ እንግሊዝ አገር እንዲሔዱ በባቡር ተሳፈሩ ።

ብርሃንና ሰላም እግዚአብሔር ወዳሰቡት ቦታ በደህና እንዲያደርሳቸው ይመኝላቸዋል ።

የዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተኩል
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር ተሩብ
ገብስ	፩ ወቄት	፰ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮሪጃ	፲፬ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮሪጃ	፳፮ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮሪጃ	፻፹ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፰ ብር
ባለ ድምፅ		፻፺ ብር
ባለ አህያ		፻፶፫ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፳፰ ብር
ቤሎ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፫ ብር
ጃፖን		፻፹፯ ብር
ሱካር	፩ ጁኒያ	፴፱ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፬ ብር ተኩል

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፳ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፭ ከ፶ ሳንቲም
አንድ ወቄት ወርቅ	፶፫

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄክኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፮ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጆማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርናንዲ ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ክነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

በማርማዊ ንጉሥ ቀፊፊ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
6<u>me</u> ANNÉE № 15

ሐሙስ መጋቢት ፲፰ቀን ፲፱፻፳፪ዓ ም ።
JEUDI 27 MARS 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ
ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays
la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumiére et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ጸሐፊው ይበታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ላአገራቸው ሲሉ ያደረጉትን መልካም ሥራ ማስረጃ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የልዑል መኰንን የታዘነላቸውና የታወቁት ልጅ በሐምሌ ፲፰፻፹፩፡ ዓ ምሕረት ተወለዱ ። በልጅነታቸው ከአፄ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ገቡ ። አደጉ ። ታላቁም ንጉሥ በተለይ የፍቅር ጥበቃ እያደረጉላቸው በርሳቸው ላይ ሐሳባቸውን መጣል አልተውም ነበር። ብልሁ ዓይናቸውም እኒህ ወጣት ልጅ የበጎ ሥራና የቀና ሐሳብ ሶጦታ እንዳላቸው ለመግለጽ አልዘገዩም። በዚያን ጊዜ አልፍኝ አደግ ነበሩና ታላቁ ንጉሥ እኒህ ልጅ ብዙኅ ተስፋና አያሌ የሚያስደንቅ ነገር እንዳላቸው ተነበዩ። እነሆ ዛሬ ትንቢታቸው የውነት ሁኖ በመድረሱ ለብዙ ጊዜ ይከበራል ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ባ፲፯ ዓመታቸው ደጃዝማች ተብለው የሀብታሙዋ የሲዳሞ ወረዳ ገዥ ነበሩ ከጥቂት ዓመት በኋላ በሰፊው በሐረር አገር እንደዚሁ ደጃዝማች ተብለው ተሾሙ ። አገሩም ልዩ ዘር ያላቸው ሰዎችና የሚኖሩበትና የሚበልጡት እስላሞች ነበሩ።ስፍራውም ለማጥመጃና አደጋ ለመጣያ የተመቸ ነበር። ግን ግርማዊ ንጉሥ የፖሊቲካና የሥራ እውቀታቸውን ለማስታወቅ አልዘገዩም።ባገዛዛቸውም ብርታት ያማረ ጠባይ ጨመሩበት ይኸውም በቶሎ ከተገዦዎቻቸው አፋቀራቸው የደግነትና የበጎ ብርሃን ከበባቸው ይኸውም እየሰፋ በኋላ ሔደ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በመጀመሪ ቀኖቻቸው እልጋ ወራሽ እንደተባሉ የሠሩዋቸው ሥራዎች ተጽፈውም አያልቁ።የመንግሥቱን ልጓም ከጨበጡ በኋላ እንደ ገና በተነሡት ሰዎች መሐል ድንብ ለመሥራትና ጸጥ ለማድረግ ጠረኛውን ለማርጋትና ለማሠልጠን በቈስቋሾቹ በመጠንቀቅና ዘወትር አድማ የሚያደርጉትን በማጥፋት እንደዚህ ያለውን ብዙኅ ዓይነት የሚያስቸግረውን ሁሉ ለማሸነፍና አገሩን ለማዘጋጀት እንዴት ያለ ኃይል እንደምን ያለ ዕውቀት እንዴት ያለ ብልሃት አስፈለጋቸው። ይሁን እንጂ ግርማዊ ንጉሥ ይኸን ሁሉ ባሚአስደንቅ (በሚያስገርም) ፈጸሙት እምቢ ባዩን ጉልበተኛ አሸንፈው ቀምበር አሸከሙት።ሥልጣናቸውን ይዘው መቀመጫቸውን አጠነከሩ። ለሹማምንቶች ሁሉ የኢትዮጵያን የተገባትን ነፃነት አስረገጡ። ሕዝቡም ምግባሩን አስታውሶ እንዲሠራ (እንዲፈጽም)እውቀትን ባገሩ ውሥጥ ሰጡ ይህን ሁሉ አስበውና ሠርተው ለማግኘት ጀመሩ ያነሱት አጋዛዋቸው የበዙት አሰናከለዋቸው ።

በጣም በውነት የሚያስደንቅ ነው እንደዚህ ያሉ አልጋ ወራሽ ሰውነታቸው ረቂቅና ለስላሳ ብዙኅ ኃይል ማግኘታቸው በመንግሥቱ ከነገሡ ጀምሮ የያዙትን ከባድ ሸክም ችሎውት እስከ ዛሬ ከሰውነታቸው አልወረደም ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ባውሮፖ ጉዟቸው ምክንያት ስማቸውን በብዙህ አስጠሩ።የነገሥታት ጋዜጦች ሁሉ የደግ ሥራቸውንና የተመረጠ ሰውነታቸውን እንደ አንድ ዋና የመንግሥት ሥራ አዋቂና ዲፕሎማቲክ መሆናቸውን አደነቁ።ሕዝቡንም ወደ ታላቅ ዕድሉ እንዲያደርሱት ከመለከት የተመረጡ ሰው ናቸው ብሎ ለማስረገጥ ይቻላል ። በሚያስገርምም ብርታት ሕዝቡን በደኅና ልምድና በሥራ አፋፍተው ከዚህ እትልቁ ደረጃ አደረሱት ይኸውም በኢትዮጵያ በሽሕ ዓመታት ታሪኳ ውሥጥ ወደ አዲሱ መጀመሪ ሥልጣኔ ደረጃ መውጣቷ ይጻፋል ።

የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ድካም (ሥራ)

የመንግሥት ሠራተኞች በራሳቸው አዳሪ ገዥና ተገዦዎች ጌቶችና ገበሬዎች የግቢና የውጭ ፖሊቲክ ሁሉም ወደርሳቸው ይመጣሉ ብዙኅ ሰዎችም ያቤቱታቸውን ደብዳቤ ያቀርቡላቸ-

ዋል ጭራሹን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ የሕዝቡን ጕዳይ ወይንም የራሱ ጕዳይ የሚያስታውቃቸው አይጠፋም። እቤተ መንግሥትም ባቢ ሁነው አውሮፓ ከተሞች ካሉት ወኪሎችና ምኒስትሮች እንደዚሁም በፓሊቲክ መልክት ከተላኩትም ሰዎች የሚቀበሉትን ደብዳቤዎች ይሠራሉ ። ከዚህ ሌላም ከዲስ አበባ ያሉትን የውጭ አገር ሌጋሲዮኖች ጕዳይ ይቀበላሉ። የመኳንንቱንም ጕዳይ ይፈጽማሉ።በሳምንት ሁለት ጊዜ ታላቅ ችሎት ያደርጋሉ እንደዚሁም ልዩ ልዩውን ነገር በመጅሊስ ያያሉ ይኸውም ከማለዳ አንሥቶ እስከ ተሲያት የቈያል።የመንግሥቱንም ሥራ ሁሉ በሥልጣን ደንብና ሥሬት በዲሱ ዓይነት ያዘጋጁታል ። ለሕዝቡም ካደረጉዋቸው ሥራዎች ውሥጥ በጣም የሚጠቅሙና የሚታወቁ ሆስቢታልና የተማሪ ቤቶች ናቸው ፡ ደግሞ የርሳቸው ሥራ በንግድና በርሻ፡ በፖስታና በቴሌግራም ቤቶች፡ በልዩ የቆመ ፍርድ ቤት፡በጕምሩክና በዩስፍ ወረቀቶች በማዘጋጃ ቤትና በዘበኞች በሌላም በብዙ ነገር ሰፍቷል ።

ደግሞ ከዚህ በላይ በብዙን ትጉኀታቸው የተከናወኑ የሚከተሉት ሥራዎች አሏቸው። የኢትዮጵያ ነገሥታት ማኅበር መግባት የነፃ ባሪ ደንብ ማቆም የኢየሩሳሌምን ግርቱውን ነገር መገላገል የብርሃንና ሰላም ጋዜጣ መታተም (ይኸውም የኢትዮጵያ ልጆች ማደጊያ ነው ለማለት ይቻላል)ከኢትዮጵያ ሰዎች አቡኖች ማሾም፡የፈረንጆች መጻሕፍት መተርጎም፡የጤንነት ደንብና የተማሪ ቤት መጻሕፍቶች መታተም ባገራችን መጀመሪ አኤሮፕላን ማግባትቀ ደግሞ ሌላም ።

ይህን ሁሉ የሚያስቡበትና የሚሠሩበት የግርማዊ ንጉሥ የሥራ ጊዜያቸው በማለዳ ጀምሮ እስከ ውድቅት ነው አንዳድ ጊዜ እስከ እኩለ ሌሊት ይቈያሉ በዚህም ሰዓት ውሥጥ ግርማዊ ንጉሥ መንቃታቸው ብቻ አይደለም ከመንግሥቱ ታላላቅ ሰዎች ጋር ይነጋገራሉ ለመንግሥት ሠራተኞችምክር ይሰጣሉ ወይንም ለጸሐፊዎች ትእዛዝ ያከፍላሉ ።

በክብረ በዓል ቀንም በግርማዊ ንጉሥ አዳራሽ የደስታ ግብር ምሳና ራት በመልክዥ ተዘጋጅተውና ተሰናድተው ይደረጋሉ በንደዚህ ያለ ምክንያት ሁሉም የሚደረገው በሥልጣን ደንብና ሕግጋት ነው።ዘወትር በዳራሽቻቸው የሚጋበዙት መኳንንቱና ሕዝቡ ደግሞ የዲፕሎማቲክ ሰዎች ናቸው የተጋበዙትም የሚመጡት የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ነው። ከሚሠሩበትና ሰው ከሚቀበሉበት በቀር ግርማዊ ንጉሥ ጥቂት ፋነስ ጊዜ ሲያገኙ ለያንዳንዱ ሰው መልካም የችሮታ ሥራ ሲሠሩበትና የታመመውን ከሆስፒታል በመጠየቅ ሌላም በመጐብኘት ይውሉበታል ። ዘወትር አብልጠው በልባቸው የሚወዱቸው ሦስት ነገሮች ናቸው ማለት የተማሪ ቤቶች፡ሆስፒታልና ማተሚያ ቤት እነዚህም ሥራዎች ስማቸውን የሚጠሩና በውነትም የርሳቸው ድካም ናቸው ።

በበዓል ቀንና በክብር ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዳሉ። እንደ እውነተኛ ቅዱስ አማኝ ናቸው ደግሞ ዘወትር ጾምና ጸሎት አጠንክረው ያደርጋሉ ቀኑንም የሚጀምሩት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ ነው።

ከቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ።

እንዲህ ያሉ ንጉሥ ቀን ከሌሊት እያሰቡና እየሠሩ ላገራቸውና ለሕዝቡ የሚደክሙ የኢትዮጵያ አምላክ ሲሰጠን ጊዜ ዘወትር የሳቸውን ሐሳብና እርምጃ እየተከተልን በተቻለንም ዕውቀት በታዘዝንበት ስፍራ እየረዳን ኢትዮጵያ አገራችንን ማጠንከርና ማልማት ይመስል እንደ ት ያንድ እናት ልጆች ሁነን እርስ በርሳችን እንግጣ። ከዚህ ቀደም ባለፈው ጋዜጣዬ መለያየት ለውጭ ሰው ደስታና ጥቅም ነው ብዬ አስታውቄ ነበር እስቲ ነገሩን ተመልከቱት በልባችሁ አስታውሱት ቸልታና ጥል ከሰው በታች አድርጎ ያዋርዳል ግን ፍቅርና መተባበር ኃያል ሰጥቶ አገርን ያስከብራል። አበበ በላቸው

በእንተ እኀለ ጸራዊ ።

እኀለ ጸራዊ ማለት ሥልጣኔ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ወሀ ፈሳሽ መስሎት ኢትዮጵያ በሠለጠነችበት ወራት የሥልጣኔዋን ዕድሜ ለማሳጠር የሚጣጣር ፥ ከልቡናው ምድጃነት እሳት ምቀኝነትን የሚጭር ፥ ሕገ እግዚአብሔር ፍቅርን አፍርሶ ፥ ሕገ አጋንንት ቅናትን አንግሦ ፥ የቀደመ ክብሩን፥ የኋላ ኃሣሩን ሳይመለከት የምቀኛ ሰው ባሕርይ ተረማማጅ ነውና ፥ በጳጳስ ወንበር ቄስ በንጉሥ ዙፋን ራስ ሊቀመጥበት እንዴት ይገባል ! ሳይል ማዕርጌ ምጡቅ ፥ ጥበቤ ረቂቅ ወደ ማለት እጓጊ ሐሳቡን ያቀዳድማል ። አንቺ በእንደዚህ ያለ ሰው ልብ ያለሽ ሐሳብ ተዩ እባክሽ ተመከሪ ፥ ቀፈቶ ልብሽን አስገጋር ለተፈሪ ፥ ይቅር እንዲልሽ ፈጣሪ ። ምቀኝነት ጥርሱን ነቅሎ ያሳደገውን ልጅሽን ሕገ ሰላሥን አስተምሪ ። ነገር ግን ድመት መንኵሳ ፥ አመሏን አትረሳ እንዲሉ ፥ አይ እኔ ለምኔ ብዬ ክፉቱ ተሰማምቶኛል ምቀኝነቱ ጥሞኛል ብትዩ ግን እንዳማረሽ ፥ እንደሸተተሽ ፥ አትቀሪም እኀትሽ ወይዘሮ ስም አይጠሩ የቀመሰችውን ትቀምሻለሽ ፥ የጠጣችውን ትጠጪለሽ። የቀለብሽን የኃሣሩን ላዳንና መስፈሪያ በእጆችሽ ትሰፈሪያለሽ። የሚሰማ ይስማ ፥ የማይሰማ ይቀወው ለራሱ ደበሰው ። ይህነን ነቢይ የማትሰማ ጆሮ ትውደቅ ተመታትራ ፥ ኑራስ ምን ልትሠራ ።

እንቺ ሥልጣኔ የዕውቀታችን አበዛ ።
በምን ምቀኛሽ እንዲህ በዛ ።

ሥልጣኔ ማለት ምን ማለት ይሆን ? ። እስኪ ከባሕረ ሐሳብ ውኃ በኵስኵስት ቀድተን በምርመራ ጥምቀት አጥምቀን የተቀበረ ስም እናውጣላት ። ሥልጣኔ ማለት ፥ መጀመሪያ ነገር እግዚአብሔር እንዳለ አውቆ ተረድቶ ፥ ፈታሒነቱን ፈርቶ ፥ የኃጢአትንና የድንቍርናን ልማድ ትቶ ፥ ሀገሩ የምትከብርበትንና ነፃ የምትሆንበትን ሥራ ሠርቶ ፥ የፊቱንና የኋላውን ኑሮውን አነጻጽሮ ተመልክቶ በፊተኛው ኑሮው ኀፀዕ ቢገኝበት ኀፀዑን መልቶ፥ የራሱንም ባሕርይ መርምሮ፥ሰካር እንደሆነ ስካሩን ትቶ፥ሌሰኛ እንደሆነ ንጽሕናን ሽቶ፥ ሰነፍ እንደሆነ ስንፍናን ጠልቶ፥ ፀበኛ እንደሆነ ፀብን አርቆ፥ ትዕቢተኛ እንደሆነ ትሕትናን ለብሶ፥ ምቀኛ እንደሆነ ምቀኝነትን አስወግዶ ፥ ፎካሪ ተከራካሪ እንደሆነ እፊ ገራም

እጀ ሰላም መንግሥት አክባሪ አገር አፍቃሪ ሁኖ ለንጉሥ አልገዛም ያለ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያፈረሰ ነው ያለውን ጽሑፍ ተከትሎ ንጉሡ ሲጠራው አቤት ሲልከው ወዴት እያለ ትእዛዝ ፈጻሚ አገር ጠቃሚ ሁኖ መኖር አልነበረምን አልነበረምይ? ።

ኢትዮጵያ እናታችን ፤ የራብ መድኀኒት ።
ልጆችሽ ተርበው ፤ እንዳይሆን ጉዳት ።
የጋገርሽልንን ፤ የፍቅር ኅብስት ።
እንዳይቈረረስ ፤ ይብሉት በንድነት ።
መጠጥ መጠጥ ብለው ፤ እንዳይጠምቁ ጠላ ።
መተኰሱ ይቅር ፤ የሠራሽው ሽክላ ።
ሠርተሽው ከቀረ ሳይተኰስ ጋኑ ።
ይቀራል ጠመቃው ፤ የድግስሽ ወይኑ ።
የበቅሎሽ ልጓሙ ፤ አይውለቅ ይሁን ።
ተለጕሞ እንዲውል ፤ ሳይበላ ሣሩን ።
ሰው ሁሉ ሊያርፍበት ፤ ለሠራሽው ቤት ።
ወጨፎ እንዳይገባው ፤ ስብሳብ ይብዛለት ።
ተፈሪ መኰንን ግርማዊት ንጉሥት ።
ሁለቱ እንጂ ናቸው ፤ ያንቺ ብርሃናት ።
ቤትሽ እንዲፀና፤እንዲሆን ገነት ።
ለማገር ፍለጋ፡ ነው የሚደክሙት ።
ቍርጥማት እንዳይሆን፡ ይህ የራስ ምታት ።
እርሱ ራሱ ይምጣ፡ ከሐኪሙ ቤት ።
ቅቅሉ ጕርንቶ፡ ከተሠራ በጉ ።
ግሣቱ ይከፋል፡ አይስማማም ሕጉ ።
ይኸ ወፍራም ምጣድ፡ ባይጣድ ይቅር።
አልሰማም ብሎ ነው የሚያንኰራኵር።
ይኸንን ሰላምታ፡ ይኸንንም መዝሙር ።
እግዜር ደቀበለው፡ ያሳርገው ከምድር ።
ፀብ ክርክር ቀርቶ፡ እንዲፀናልን ፍቅር ።
አሜን ወአሜን፡ ለይኩን ለይኩን ።
ጨለማ ያርቃል፡ የተፈሪ ብርሃን ።

ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ።

ለልጅ ወቀሳ የናት መልስ ።

ቤቴ በማማሩ ሰው ቢቀናብኝ
ቢጐብጥ ቢቀና፡ ምንም አይጐዳኝ
ዘውዲቱ ተፈሪ ልጆች ሳሉልኝ
ሁለቱ ልጆቼ ምሰሶ ሁነዋት
እስከመቸም አትፈርስ የቤቴ መሠረት
መስተዋት ዘርዓቼ ብመለከት ፊቴን
ግርማዊት ዘውዲቱ ሳይኔ ሆነች ብርሃን
ተፈሪ መኰንን ያበሸ ፀሐይ
ጠላትህ እንደሰም፡ ይቀልጥ የለም ወይ
ተፈሪ መኰንን፡ ዘውዲቱ ብርሃን
እስከመቼም አይመሽ ይህ የናንት ቀን
ከቆመው ሰው ሁሉ በበኩ ዙሪያው
ገርባባም የለበት ሁሉ ሥልጡንነው
ለስሚ ማስጠሪያ ምን ጥቂት ይበቃል
የልጆቼ ዝና ካለም ሁሉ ደርሷል።
ለማውጣት የሚደክም የቁም ተዝካሩን ።
ልጅ የሌለው ሰው ነው የሚያስብ ስሙን።
እንደኔማ እንደኔ ማነው የታደለ።
የልጆቼ መንግሥት ፀሐይ የመሰለ።
ድካም የለብኝም እርጅናም አልፈራ።
ታድሼ እኖራለሁ እንደኄኖክ ዕዝራ።
አድገዋል ልጆቼ፡ ምንም ሞግዚት አያሻቸው።
ስምምነትን ነው እነሱ ሐሳባቸው።
ግርማዊት ዘውዲቱ የዘውድሽን ፀዳል ።
አይከለክለውም ደፊር ጠፊር ገደል።
እኔ እናታችሁ ታደልሁ ምንኛ።
የፍቅራችሁ ዕናት ሁኖ እንደዘበኛ።
አልፆም ድርግም አለ ማንም ዓመፀኛ
ለንብረት ማኀደር ማሰቤ ምነው።
የሁሉ ማኅደር ልጆቼ ናቸው ።
አልተጐዳብኝም አንድ ሰው በቍጥር።
ጥፋት ከፈለገው ካንድ ሰው በቀር።
ፍቅሬን በልጆቼ አሳድራለሁ ።
እንዲፋቀሩልኝ እነሱም እንዲሁ።
ይህበ አንዱ ልጄ አሁን ምን ቸገረው።
ከማኅበር ወጥቶ በይለይ ከሰው።
ለተለዩት ሁሉ ምን ጠቀማቸው።
ተለይተው ሲቀሩ በግዝት ታሥረው።
የስሜ ንበቡ ወይንም ትርጓሜው።
ለዚህ ለሰውዬ አሁን ምን መሰለው።
እግዓዚት መባሌን ምሥጢሩን ሳያውቀው።
ልናገረው እስቲ መርምሮ ቢረዳው።
እመቤት ማለት ነው ያላት ነፃነት።
ከልጆችዋ በቀር ማንም አይገዛት ።
ብርሃንና ሰላም የተማረ መምህር።
እናትና ልጁን አዋቅሶ እሚያፋቅር።

ወይዘሮ እግዓዚት።

ትንሽ ሐሳብ ።

ትምህርት ዕውቀትን፡ ዕውቀት የጥበብንና የመንፈሳዊን ምክር ለመስሚ መሪ ነውና፡ መጋቢት ፲፩ ቀን በቍጥር ፲፪ ብርሃንና ሰላም የተጻፈ ቃል አይቼ፡ ምንም ያልተማርኩ ዕውቀት የሚጎድለኝ ብሆን የሀገር ፍቅር እንደ ብልሆቼ ትክክል ይሰማኛልና ይህን ለመጻፍ ተዳፈርኩ። ሀገራችን ከጠላት ተጠብቃ እንደምትኖር፤ኢትዮጵያ እጆዋን ወደእግዚአብሔር ዘርግታለች ሲል ልበ አምላክ ዳዊት ተንብቶታልና የተማሩ በጸሎት፤ ያልተማርንም በምህላ፡ ጸሎት ማድረግ ግዴታ አለብን። እነሆ የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔር መዓት እንደመጣ ባዩ ጊዜ እንስሳ ሣር እንዳይበላ ፤ ሕፃናት ጡት እንዳይጠቡ፡ አድርገው ጾም

ጸሎት ቢያደርጉ ሊወርድባቸው የነበረው መዓት እንዲሰቀቅላቸው ከኔ ይልቅ ክቡራን እንባቢዎች የምታውቁት ነው ። በብርሃንና ሰላም እንደተጻፈው ቃል፡ ጾም ጸሎት ያሁኑን ክበድ ሐሳባችንን እንዲያቀልልን የታወቀ ነው። ክበድ ማለትም ነገሩ ክብዶ እጥፉት ያደርሰናል ብዬ አይደለም። ነገር ግን አንድነትና መተባበር በሚሆናበት ወቅት የሚያጕድሉንን ልዩ ልዩ ሥራዎች ለሀገራችን ጥቅም ለመሥራት በምንጣደፍበት ሰዓት ብዙ ሠራዊት ሰዓቱን በከንቱ ማስተላለፉ ሰውና ከብት እንበለ ጥቅም መኰላላቱ፡ በጣም የሚያሳዝን ነውና ማዘን የሚገባን ነው ። ይልቁንም ኢትዮጵያ በሥልጣኔ እርምጃ መራመድ ጀምራለች እየተባለች ምስጋናዋ ሲጀመርላት ይህን የመሰለ ለበዕድ ሰው መዘባበቻ ያደረገንን ጠላታችንን በዚህች ዓለም ውርደትን ሳያገኝ አይቀርም ፡ እኛም አገራችንን ከክፉ ሥውርልን እያልን ምሕላ ማድረግ ቁስ መነኩሴ ዲያቆናት ጸሎት ማድረግ የተገባ ነው እበው ከሀናት ቀሳውስት መነኮሳት ሆይ እውነት እናንተ በጸሎት በርትታችሁ ቢሆን ይህ ነገር በልዩ ረሰም ነበር ። አሁንም ከዘረታችሁ ይህም ቀርቶ ሁለተኛ በኢትዮጵያ ይህን የመሰለ ነገር እንዳይደርስብን ወደ ፈጣሪያችን ብትጸልዩ የታወቀ መሆኑን በጥልቅ እክብሮ አስታውሳችኋለሁ።

ማህሉ ጽጌ ።

የሰጡትን ትቶ ያልሰጡትን ስለሚፈልግ

መጀመሪያ

ቅዱስ ላሊበላ አባ ዮሴፍ በሚባለው ወረዳ ዝንጀሮ የተሰጣውን ሥንዴ የተዘራውን ገብስ ባየ ጊዜ ከመኖሪያው ውሥጥ ወጥቶ የሚገባውን ለመመገብ ጕዞ ይጀምራል።ከደረሰም በኋላ የሚገባውን እንክርዳዱን፡አረማሞውን ሲናሩን በልቶ የማይገባውን ስንዴውን፡ገብሱን፡ ትቶ ይሔዳል ይላሉ ባለቤቱ እንኳን የሚገባውን እንክርዳዱን፡አረማሞውን፡ሲናሩን፡ቢከለክለው ቀለ የሚገባኝ ነውና ልትከለክለኝ አትችልም ብሎ ፀብ ክርክር ሊያነሣም አይችል እንኳንስ የማይገባውን ሊፈልግ አረ አእምሮው ያልተደላደለ የማይናገር የዱር አውሬ የሚገባውንና የማይገባውን አውቆ ሲሠራ አእምሮው የተደላደለ የሚናገር የሚያውቅ ሰው የማይገባው መሆኑን ከተረዳው በኋላ የሚገባኝ ነው ብሎ ላንዱ የሚገባውን ማሰብ ከየት የመጣ ሕግ ነው ደግሞ እንደዚህ ያለው ሕግ ቢፈርስ የማይጐዳ ነው ።

ሁለተኛ

አንድ ሰው ፫ ክፍል ቤት ሠራ በኋላ ከባቱ ጋራ የቈዬ አንድ ሰው ነበረና ፩ደኛውን ፤ አነስተኛውን ክፍል ቤት እንዲቀመጥበት ፈቀደለት ሲፈቅድለትም እሱ የሚያዘውን ሁሉ ሊቀበልና ሊታዘዝ ነው ። ከቲንሽ ዘመን በኋላ ላንተም የምታዘዝ አይደለሁም አንተም ያለህበትን ፪ ክፍል ቤት ለኔ የምትለቅ መሆንህን ተረዳው ብሎ ባባቱ ቤት እጅ ይዞ ያስገቡት እጅ ይዞ ያስወጣ እንዲሉ ይህነን ተናገረው ዳሩ ግን ትልቅ ሰውና ሰጭ የሆነ የሚችል ስለሆነ ትዕግሥት አደረገ ለዚህ ፩ ምሳሌ አለሁ አንድ ሰው በመንገድ ላይ ደክሞት ርቦትም ቀኑም ዓርብ ነበረና ጭብጦውን ሲጕራርስ ፩ የከተማ ሰው ደረሰ ምነው ወንድሜ የመብሊያ ጊዜ ሳይደርስ ባርብ ምድር ትበላለህ ብሎ ቢጠይቀው ከወንዝ ወዲህ ማዶ ነበረና ያለው ምንም መልስ ሳይሰጠው ተነሥቶ ወንዙን ተሻግሮ እማዶው ሲደርስ ወንድሜ እዚህ አሙስ ምድር ሁኜ እበላለሁ ብሎ መለሰለት መቸውንም ያ ሰው በንድ አገር ውሥጥ ዓርብ ግማሹ አሙስ ግማሹ ይሆናል ብሎ አይደለም ለጊዜው መስሎት ነው እንዲ ይህም በንድ መሠረት ውሥጥ እንደ የኔ ነው ፥ ብሎ ማሰብ እንዲህ ያለ ነው ያባቱ መሬት እንኳ ቢሆን ቅሉ ሊከራከር ይችል ነበር ይህ ግን ድፍረት ነው ሲያውቁ በድፍረት ሳያውቁ በስሕተት እንዲሉ ።

ግብረ ድንግል ድባቤ ።

ስለንሥረ ተፈሪ ቅኔ ።

መወድስ ።

እምላክ ወሰብእ ንሥረ ተዋሕዶ።
እስመ በኵለሄ ምሉእ ከመ ያስተፃምር ኵሎ ።
ሕሊና ቅሩብ ሳሌም ወሕሊና ርኁቅ አዘሎ።
ወእግዚአብሔር ንሥረ ተፈሪ ።
በበነግህ ለኢትዮጵያ ይሬእዩ ማህሎ።
ንሕነሰ በተሐብሎ ።
ኑፋቄ ኢንግበር እስመ የዓቅበነ እምተኀጕሎ ።
እመ ያደሂ ንሥረ ተፈሪ ደመና ነፋስ ወዓውሎ ።
እንጠብጠበ ዝናማተ መልእክታተ ፍቅር ለዘተሰእሎ።
ወላዲትነሰ ሐረር ለእመ ትሰምዕ ቃሎ ።
ምጽአቶ ከመ ትንግር ነገደት ምድረ ወሎ ።

ዓሩይ ወልደ አማኑኤል ዘሐረር መድኃኒ ዓለም ።

ስለ ኢትዮጵያ የግጥም ምስጋና ።

ብርሃንና ሰላም ኢትዮጵያ አገሩን በገናውን እየደረደረ፥ መዝሙሩን እያንጎራጎረ ያመሰግናል ።

እንቺ ኢትዮጵያ የውበት ሰፈር ።
ላመስግንሽ እኔ በጥዑም መዝሙር ።
ይፈትላሉ እጆችሽ ስምምነት ሐር ።
ሁነሽ ተቀምጠሽ በፍቅር ወንበር ።
ይህም ብቻ አይደለ የእጅሽ ጥበብ ።
ደግሞም ትሰፊያለሽ የፍቅር መሰብ ።
እንዲመገቡበት ያንቺ ቤተ ሰብ ።
ግርማሽ ዘውዲቱ ናት ሞገስሽ ተፈሪ ።
እሊህን ሁለቱን ይጠብቅ ፈጣሪ ።
እስኪ ላመስግንሽ እኔ አንደኛው ልጅሽ ።
ምን በኔ ብቻ ቃል ትመሰገኛለሽ ።
ዳር እስከ ዳር ያለው ሁሉም ያመሰግንሽ ።
ተፈሪ መኰንን ከሆነ ብርሃንሽ ።
በብርሃን ተከበሽ ጨለማም አይነካሽ ።
ግርማዊት ዘውዲቱ የነገሥታት ንግሥት ።
ጨለማ እንዳይነካሽ ሆነችሽ ማኅቶት ።

እኛ ለነርሳቸው ዕድሜ እንለምን ።
እነርሳቸው ለእኛ ከሆኑ ብርሃን ።
አንቺ ኢትዮጵያ አንቺ እናታችን ።
ሁለቱ ጡቶችሽ የሚያምሩ ለዓይን ።
ያንጠበጥባሉ ፡ ፍቅር ወተትን ።
ማን ያህልሻል ብዬ ላውጣልሽ ስምሽን ።
የፍቅር ባለቤት አምላክ ይመስገን ።
አብልጦ ከሁሉ ካላቀሽ አንቺን ።
እነዚህ ልጆችሽ በቀሉውን ይውደዱ ።
ፈረስ ፈረስ ብለው ፈጥነው እንዳይሔዱ ።
ባንድነት ተወልደው ባንድነት ይደጉ ።
ሥራቱ እንዲፀና ያንድነትሽ ሕጉ ።
የፍቅርሽ መሠረት ይበል ፀና ፀና ።
ነፋስ እንዳይጥለው እዲኖር በደኅና።
ብርሃንና ሰላም እኔ ያንቺ ልጅ።
እንዲህ ያል ምስጋና ደረሰሁልሽ እንጅ፡
የምስጋናሽም ቃል በዚህ ይፈጸም።
ያኑርልኝ አንቺን እስከዘላለም።

ተንኰልን በተንኰል ስለማሸነፍ ።

አባቶቻችን ጨዋታ ለመጫወት በፈለጉ ጊዜ ተረት እየተረቱ ምሳሌ እየመሰሉ የሚያስደንቅ ነገር ሲጨዋወቱ እኛም ልጆቻቸው በባጠገባቸው ሁነን እንሰማ ነበር። ምሳሌና ተረት ብብዙ አራዊትና በልዩ ልዩ ፍጥረት ሊነገር ይቻላል ። ይልቁንም በቀበሮ የሚነገር ብዙ ተረትና ምሳሌ አለ ። ከብዙ አንዱ ከዚህ ቀጥሎ የሚጻፈው ቃል ነው ።

የቀበሮ ባሕታዊ ባቷን ላቷን ለማየት ከበግ መካከል ይጸልያል እንደሚባለው ተረት።

አንድ ቀን አንዲት ቀበሮ እርቦዋት ምግብ ፍለጋ ስታንኰተኵት ከመንደር ጠገብ በደረሰች ጊዜ አንድ ዶሮ ከዛፍ ተሰቅሎ አየችና አንተ ዶሮ እንዴት ዋልህ አለችው እርሱም እግዚአብሔር ይመስገን ብሎ ሰላምታ ከመለሰላት በኋላ ምነው ወንድሜ ተለይተህ አንተ ብቻ መቅረትህ አለችው ። እርሱም ደንግጦ ተለይቼ የቀረሁት ከምን ነው በዬ አላት ። እርሷም ያልሰማው መጣ አዬ ጉድ ብላ የሚታለልልኝ መስሏት የተንኰል ፖለቲካዋን እያስመሰለች ትለቀው ጀመር ። ዛሬ እኮ እንስሳት የዱር አራዊት የሰማይ አዕዋፍ ተሐዋስያን የተባሉ ሁሉ አንድ ሳይቀሩ ከሰፊ ሜዳ ተሰብስበው የሰላምና የፍቅር የስምምነት ጉባኤ ተደርጎ ጉልበታሙ ደካማውን እንዳያጠቃው ሁሉም ተከባብሮ እንዲኖር ሥራ ተሠርቶ ተደንግጎ ተወስኖ አንደኛው ማህበረተኛ እኔ ነበርሁና ከዚያ ውዬ ይኸውና አሁን መምጣቴ ነው አለችው ።

ያም ዶሮ ተንኰሏን ስላወቀባት ፡ ለካ ከዚህ ከኛ በላይ ካለው ስፍራ ወደኛ እየሮጡ ሲመጡ የማያቸው ውሾች እንዳንች መልካም የምሥራች ሊነግሩኝ ነውን ብሎ እንቴ ሆይ አሁንም ቈይ ይህን እንደዚህ ያለውን ደስ የሚያሰኝ ነገር እነርሱም ይምጡና እኔም ልውረድና ሁላችንም ፈንጠዝያ አድርገን በዓሉን አክብረን እንዋል ብሎ የውሾቹን መምጣት በወረላት ጊዜ ። እባብ ለእባብ፤ ይተያያሉ በካብ እንዲሉ በተንኰሉ ተንኰሏን ድል በነሣው ጊዜ ተወው ተወው ረስቼው ዛሬስ የሚያስቸኵል ጉዳይ አለብኝና በሌላ ቀን ይሁንልን ፥ ብላ እየሮጠች እግሬ አውጭኝ እያለች ወደ ስፍራዋ ሔደች።

የዚች ቀበሮ ያወራችለት የዕርቅ ወሬ እውነት እንዳልነበረ ዶሮውም ያወራላት የውሾቹ መምጣት ወሬ እውነት አልነበረምና ያ ዶሮ እየሳቀ እየተንከተከተ ከዛፉ ላይ ወርዶ በደኅና ወደ ቤቱ ገባ እያሉ ሲጨዋወቱ እንሰማ ነበር ።

አሁንም ይህ ዶሮና ይች ቀበሮ የሠሩት የተንኰል ሥራ የሚያስፈልጋቸው ነበር፤ስላምን ብሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር ያች ቀበሮ አዳርዋ እየአደነች፤ዮፍ እየአነቀች በጣም፤እየነጠቀች ነውና ስለምግቧ ያችን ዶሮ አታላ የምትይዝበት ምክንያት መፈለግ ስለትዳሯ ነውና የሚስፈልጋት ነገር ነበር። እውነት ነገር ነው። ያም ዶሮ ከጠላቱ የሚአመልጥበትን ነገር መርምሮ እንደዚህ ያለ ምክንያት ማድረጉ ሕይወቱን ስለመጠበቅ ነውና የሚያስፈልገው ነበር።

ስለ ወይዘሮ አከሉ ዕረፍት።

ወይዘሮ አከሌ የአቶ ንዋይ ባለቤት ብዙ ወራት ታመው ነበርና መጋቢት ፲፪ ቀን ዓርፈው ወደ ዝቋላ አቦ ወስደው ቀበርዋቸው።

ብርሃንና ሰላም ለባላቸው ለአቶ ንዋይና ለዘመዶቻቸው ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል።

ስለ በቀለ ማሙዬ ዕረፍት።

ወለጋ ከደጃዝማች ሀብተማርያም ወደ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ሊማሩ ከመጡት ልጆች በቀለ ማሙዬ የሚባል የግራዝማች ማሙዬ ልጅ እጅግ የተዋበ ብልህና ቅን እጅግ ጠባየ መልካም ትሑት በሰው ሁሉ ዘንድ የተወደደ ነበር ወደ ትምህርት ቤታችን ተገባ አምስተኛ ዓመቱ ከባልንጀሮቹ እንኳን ፩ቀን ተጣልቶ አያውቅም ነበር በትምህርቱም ደስ አሰኝቶ ብዙ ጊዜ በትምህርት ለበለጡ ተማሪዎች የሚገባውን ሽልማትና ኒሻን ተሸልሞ ነበር ዳግም በፋትበል በግር እሚመታ ኳስ መጀመሪ ሁኖ ሽልማት ተሸልሞ ነበር። እኛም በየነው ጊዜ ሁሉ ለቁም ነገር በደረሰ ጊዜ ለሀገራችን ማዕርግና ግርማ ይሆናል እያልን ስናስብ መቸም ይህ ዓለም የደኅች ዓለም አይደለምና በትንሽ በሽታ ታሞ ባሥር ቀን በተፈሪ መኰንን ሆፒታል ጉለሌ በመጋቢት ፲፫ቀን ሞተና በብዙ ፍታትና ክብር በመድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ከሮፓ የመጡት መምህራንና የኢትዮጵያ መምህራን የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ሙሴ ጋሪ ኰይክስ ወንድሞቹ ተማሪዎችና

ሠራተኞች እጅግ አለቀሱለት። ብርሃንና ሰላም አባቱንና እናቱን፣ የሚያውቁትንና የሚወዱትን ሁሉ እግዚአብሔር ያጽናችሁ ይላል።

ማኅተመ ወርቅ እሸቴ።

ስለ ሸመታ መሸልና ስለገበያ መጥገብ።

በዚህ ባለፈው ወራት ዝናሙ እየዘነመ ስለአስቸገረና ደመናው ግጥም አድርጎ ስለያዘው አዝመራውን ለመሰብሰብ ስላስቸገረው ሰዉ ተደናግጦ ነበር ። አሁን ግን ዝናሙ ለቀቅ አርጎ አዝመራው ታጭዶና ተወቅቶ ተሰብስቦ ከቤት ስለገባ ሰው ሁሉ ደስ ብሎታል ገበያው ጠግቧል። ሸመታውም ተሸሎታል። የበልጉም አገር ሁሉ የበልግ ቡቃያ ማብቀል ጀምሯዋል ይህ የመከሩ አዝመራ ተሰብስቦ ስለገባ ገበያው እንደጠገበ ደግሞ ይህ የበልጉ አዝመራ ከፍሬ ደርሶ ታጭዶ ለመመረትና ለመሰብሰብ ያብቃው ሲል ብርሃንና ሰላም ምኞቱን ያቀርባል።

ስለ አርመኖች ትምህርት ቤት የተደረገ የሙዚቃ ጨዋታ።

መጋቢት ፲፫ ቀን ሐይጋንፖርታራን ስለተባለ የአርመኖች ትምህርት ቤት በሙሴ ግሴዝ ሆቴል የሙዚቃ ጨዋታ ተደርጎ በዚህ ጨዋታም የፈረንሳዊ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ሙሴ ደረፌይ ነበሩ ብዙ አርመኖች ተሰብስበው ጨዋታው ደምቆላቸው አመሹ።

ስለ ግሪካውያን በዓል ።

መጋቢት ፲፯ ቀን ግሪካውያን የነፃነታቸው በዓል ስለሆነ በቤተ ክርስቲያናቸውና በትልልቁ ቤታቸው ሁሉ የግሪክና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎ ባንዲራው እየተውለበለበ በየቤቱም ልዩ ልዩ ዓይነት ጌጥ ተደርጎ በዓላቸውን በትልቅ ደስታ አከበሩ ።

ብርሃንና ሰላም ለወዳጆቹ ግሪኮች ሁሉ እንኳን የደስታ በዓል አደረገላችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ያቀርባል ።

የአሜሪካን ሚሲዎን የሴቶች ተማሪ ቤት ።

ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም የትምህርት ቤት ለሴቶች ልጆች እንከፍታለንና ልጆቻችሁን ትምህርት ቤት ለማግባት ፈቃዳችሁ የሆነ ሰዎች አንድ ሳምንት አስቀድማችሁ አሜሪካን ሚሲዮን እሴቶች ትምህርት ቤት ድረስ መጥታችሁ ልትነጋገሩ ትችላላችሁ ።

የተማሪ ቤቱ ዋና ሹም ።

ወይዘሮ ኬሚል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኅሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፶ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፸፭ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸፭ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፸፭ መሐ
የሟልና የንቀርሳ የምክር ቃል	፸፭ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸፭ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፸፭ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፸፭ መሐ
አሳብና ምኞት	፶ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፶ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፳፭ መሐ
ፈደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳፭ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳፭ መሐ
የእንቅጣጣሽ ግጥም	፳፭ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፱ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፰ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኩረጃ	፲፱ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኩረጃ	፳፮ ብር
አቡጀዲ መነጸር	፩ ኩረጃ	፻፸፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፱ ብር
ባለ ድመት		፻፶ ብር
ባለ አህያ		፻፶ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፶፫ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፱ ብር
ጃፖን		፻፹፯ ብር
ሱካር	፩ ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፬ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር ፳ ፍራንክ
በአንድ ብር ፯ ሊሬ ከ፭ ሳንቲም
አንድ ጊኒ ፲፫ ከ፫ ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ ፶

የርሻና የንግድ ማስፌያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲ኒ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒክላ።





አዲስ ዓይነት በርሳሊን ብርኔጣ መጥቶትችሁ አዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣምውድ አይደለም ። በተለየ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምበር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ሼር ዳኔይ።
አ ቡ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጼሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ፀሐፊ መኰንን ተፈሪ መኩንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
6me ANNÉE № 14

ሐሙስ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ.ም።
JEUDI 5 AVRIL 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣሁት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ነፃነት ።

ነፃነት ምን እንደሆነና ምን እንደተባለ ከመጻሕፍት ጠቅሰን ከታሪክ ተመልክተን ለማስረዳ ያህል ከዚህ በታች እንጽፋለን። ነፃነት መጀመሪያ አንድነትን ከስምምነትና ከፍቅር ጋራ አስተካክሎ ይዞ የጠላት ቀንበር እዳይነካ ለማምለጥ በስምምነትና ባንድነት በተማሠረ ኃይል የጠላትን ቀንበር ሰብሮ ለመጣል ብዙ ትጋትና ብዙ ፍቅር ያስፈልጋል ።

የነፃነት ደመኛው መለያየትና መናናቅ ነው። መለያየትና መናናቅም ከሆነ ዘንድ ስምምነት ይጠፋል ኃይል ይደክማል በዚህም ምክንያት የጠላት ቀንበር ተሸካሚ መሆን ይመጣል። የጠላትም ቀንበር ከትከሻ ላይ ከዐጣ በኋላ ያቀንበር እስኪወርድ ድረስ ብዙ ያዳግታል ። ለዚህም ትንሽ ምሳሌ መስለን እናስረዳለን አሁን ትንሽ የወርክ ቡቃያ ዕለቱን አንድ ብላቴና ነቅሎ ሊጥላት ይችላል ። ከዋለች ከደረች በኋላ ግን ብዙ ሰው ብዙ መጥረቢያ ብዙ መጋዝ ብዙ መጫኛ እንድታስፈልግ እንዲሁም ቀንበርን ከትከሻ ላይ እንዳትወጣ አስቀድሞ በስምምነትና ባንድነት ካልከለከሏት እጅግ ከባዳና የማትቀል ሸክም መሆንዋን ማንም ሰው አይስተውም ።

ኀዘንን ያልመቀሰ ኀዘንን አያውቅምና የቀንበርም ከባድነት ከጠላት ቀንበር በታች ያሉ ሰዎች ሲጨዋወቱ ብዙ ጊዜ እንሰማለን። እነሱም ከቀንበር ለመለቀቅ ነፃነትን ለማግኘት ብዙ ጥረት ይጥራሉ ብዙ ሐሳብ ያስባሉ ። ነገር ግን ወይ ጣጣ በዚህም አያስወጣ እንደሚባለው ተረት መውጫ ቀዳዳ ጠፍቶባቸው በተገዢነት ይኖራሉ ።

እኛም ይህ ያለንበቱ ዘመን የነፃነት ጊዜው የትምህርት፥ ሰዓቱ የዕውቀት ነውና በዕውቀታችን መርምረን በትምርታችን ተመልክተን ነፃነት ከሀገራችን ወጥታ እንዳትሔድብን ስምምነትንና አንድነትን ብንይዝ እነሱ አጥር ሁነው ይከለክሏታል።

የውጭ አገር ታሪክ ስናነብና ስንመለከት የብዙ አገር ሰዎች ስምምነትን ባለመያዝና፥ አንድነትን ባለማፅናት ስለኖሩ በዚህ ምክንያት ለጠላቶቻቸው በር ሰጥተዋቸው ነፃነታቸው ወደባርነት ተመልሶ ተገዥች ሁነው ሲኖሩ እናያለን ። ነገር ግን አሁን ስምምነትን አጥፍተን አንድነትን አፍርሰን ብንኖር እንጂ ነው እንዲህ የጠላት መፈንጫ መሆናችን ብለው ነፃነታቸውን ለማስመለስ ሲሉ ስምምነትን አንድነትን ይዘው ብዙ ልዩ ልዩ ፍልስፍና ይፈለስፋሉ ብዙ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይጣጣራሉ በጕልበታውም ስለሀገራቸው ብዙ ድካም ይደክማሉ ሕይወታቸውንም መሥዋዕት አድርገው ያቀርባሉ ። እኛም ደግሞ ለባሪያ ነፃነትን በሰጠንበት ወራት ለሰው ተገዥ እንዳንሆን በሀገራችን ፍቅርን ዘርተን ስምምነትንና አንድነትን አብቅለን የነፃነትን ፍሬ ብንሰበስብ ያገራችን ብዕሏ እየበዛ ኀይሏ እየበረታ ይሔዳል። እስኪ አሁን በልባችን ብንመረምረው የሥራ ፋብሪክ ባለመብዛቱ ብዕሏ በመሬት ተቀብሮ በልዩ ልዩ የውቀት ሥራ ከመሬት ወጥቶ ባለመገኘቱ ልጆቿ በድኽነት ሳሉ በዚህ ላይ ፍቅርና ስምምነት ጠፍቶ አርስ በርሳቸው ጠብ እያነሡ ያንዱን ሕይወት አንዱ እንዴት ያሳልፋት ።

ይህስ እንደዚህ ያለው ኃፍረት ሊናገሩት ያሰቅቃል ። «ነገር ግን የነፃነትን ክብረቷንና የክብደቷን ሚዛን» ከባርነት ቀንበር በታች ካለ ሰው በቀር ሌላ ማንም ሊያውቀው አይችልምና ነው እንጂ ቢያውቀውስ ስምምነትንና አንድነትን ለመተው ባላሰበም ነበር ። ሁለት በሮች ቀንበር ተሸክመው ተጠምደው በጅራፍ እየተገረፉ ከትልሙ እየተዳፉ በብዙ መከራ ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ ሲያርሱ አንደኛው ያልተጠመደ በሬ ከላሞች መከከል በዳር ሁኖ እየተንጐማለለ እንደነዚያ ቀንበር የማይነካው መስሎት እያገሳ ሣሩን እየነጫጨ

ሻጠገቡ ካሉትም ጋራ አልስማማ ብሎ በቀንዱ እየተጋጨ ባስቸገረ ጊዜ ባለቤቱ ይሔድና ና እስቲ አላርፍ ታልክ ምን ይደረግ ይልና ያንን ይነክው ያልመሰለውን ቀንበር ያሸክምና ልቡ ጥፍት እስቲል ድረስ በሾራፍ እየነጨ ሲያኳትነው ይውላል ።

አሁንም ለእኛ የሚያስፈልገን በማናቸውም አገር ሆነ ከጠላት ቀንበር በታች ያሉትን ሕዝቦች በመከራና ፃዕት አገዛዝ መኖራቸውን ጠይቀን ተረድተን አይተን ተመልክተን እግዚአብሔር ለጠላት አሳልፎ እንዳይሰጠንና ነፃነታችንን እንዳናጣ ሁላችንም በያንዳንዳችን ስምምነትን ለማስናት ፍቅርን ለማልማት አንድነትን ለማስፋት ብንጣጣር እጅግ መልካም ነገርና የሀገር ጥቅም ሳይሆን አይቀርም።

መጽሐፍ ቅዱስ ተመልካች ለሆነ ሰው እስራኤል መከራ የመጣባቸውንና በሰው አገር ሕዝብ እጅ ለመጥፋት የደረሱት በምን ምክንያት ይመስለው ይሆን? ። ከስራኤል አዙሲቶቿ በሹመት ምክንያት ፍቅር አጉድለው ስምምነትን አፍርሰው ከአንጥያኮስ ዘንድ ሔደው በሀገራቸው የተንኰል ምክር መክረው አንጥያኮስን ስበው አምጥተው የሀገራቸውን ክብር አዋርደው ነፃነቷን ለባርነት ለውጠው ሕዝቧን ግማሹን ለስለት፡ ግማሹን ለስደት፡ ግማሹን ለእሥራት ያደረሱ ስምምነትን በማፍረሳቸው አይደለምን?።አሁንም የኢትዮጵያ ተወላጆች የምንሆን ሁላችንም አሮንና ሖር በሙሴ ግራና ቀኝ ቁመው ሙሴ ሁለቱን እጆቹን ዘርግቶ እጆቹ እንዳይታጠፉ ሁለቱም ተሸክመው ቁመው በዋሉ ጊዜ ለእስራኤል ኃይል ይሰጣቸው ጠላት ይርቅላቸው እደነበረ«ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር እንዲል» እናታችን ኢትዮጵያ ስለኛ ስለልጆቿ ወደ እግዚአብሔር እጆቿን ዘርግታ ትለምናለችና እኛም ስለእርሷ ኢታር እየን ሙስናሃ ለኢትዮጵያ እያልን ወደ እግዚአብሔር ለሰብ ችንን መልሰን ስምምነትና አንድነትን አጽንተን መለያየትንና መጣላትን አርቀን ፍቅርን እንደ ልብስ ለብሰን የኖርን እደሆነ መንግሥታችን ተከብሮ አገራችን ተፈሪ ስማችን ገናና ኃይላችን ፅኑ ሳይሆን አይቀርምና ክፉ ክፉውን ሐሳብ ትተን በጎውን ለመሥራትና ነፃነታችንን ለማጠንከር እንትጋበት ስንል ጥልቅ የሆነ የሀገራችንን ፍቅር በግልጽ እናስረዳለን ።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ከኛም በፊት የነበሩትንና ዛሬም በእኛ ጊዜ ያሉትን የኃይላቸውንና የጉብዝናቸውን ታሪክ ለመጻፍ ብዙ ወረቀትና ብዙ ጊዜ ያፈጃል።ነገር ግን ከብዙ ጥቂቱ ከምሉ በክፍሉ ከዚህ በታች ጥቂት እንጽፋለን ።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ።

አንድነታቸውን አጥባቂ፡ ጠላታቸውን አጥቂ፡ ወገባቸውን በኃይል ዝናር ታጣቂ፡ እንደ አንበሳ ደቦል ፍርሃት ከልቡናቸው የራቀ፡ ስማቸው የታወቀ፡ ስለሆነ የኢትዮጵያ የነፃነቷ ዱብዳቤ በወርቅ ቀለም ተጽፎ ከጥንት ጀምሮ በዓለም ሁሉ ነገሥታት ሲነበብና ሲነገር ይኖራል ። አንበሳ ባገሣ ጊዜ የፀነሰች ላም ከድንጋጤ የተነሣ እንድትጨነግፍ የኢትዮጵያም ጀግኖች በሆ-ግራቸው በዙሪያዋና በአውራጃዋ ጠላት ተነሥቷል ሽፍታ ተቀስቅሷል ባሏቸው ጊዜ ንጉሣቸውን አንተ ከልጋህ አትውረድ ከከተማህ አትውጣ ከሰው መርጦ ቀብቶ ያነገሠህ እምላክ ኃይሉን ይስጠን ግምባርህ አይታጠፍብን ብለው ንጉሣቸውን አክብረው ተሰናብተው ከዚያ የሽፍታ ወሬ ከተነሣበት ሀገር ከዳሩ ደርሰው ቃላቸውን ባሰሙ ጊዜ የዚያ የጠላት ሐሞቱ ይፈሳል ኃይሉም ፀሐይ እንደነካው ቅቤ ይቀልጣል። እነሱም በዙሪያውና ባውራጃው ተዛውረው ዓመፀኛውን አሳምነው ከአመነውም ለመንግሥት የሚገባ ግብር ተቀብለው ለንጉሣቸው ያስገባሉ ። ይልቁንም የሚያስደንቀው ነገር የተተኰሰውን ዓረር የጠጠር ያህል ፡ የተወረወረውን ጦር ያርጩሜ ያህል የተመዘዘውን ጐራዴ የላንቄ ያህል ሳይቈጥሩት አቋርጠው ከሰልፉ መካከል ገብተው ጠላታቸውን ማርከውና ገድለው ፉከራቸውን ሲያንደቀድቁ ጐራዴያቸውን ሲነቀንቁ አንጀቱ ላያቸው ሰው ደስ ሲያሰኙ። እዩ የኢትዮጵያ የናታችን ማኅፀን እንዴት የተባረከ ነው። እንደነዚህ ያሉ ኃያላን ፀንሶ የሚወልድ « ብፅዕት ከርሥ ኢትዮጵያ እንተ ያረቶሙ ለእሉ ወብፁዓት አጥባቲሃ እለ ኀፀናሆሙ » በፍቅር ጡቷ በስምምነት ወተቷ እነዚህን አጥብታ ያሳደገች ኢትዮጵያ ንእድ ክብርት ናት። የዳዊት ግርማና ኃይል በጀግኖቿ አድሮባቸው ይኖራል የዳዊት ግርማና ኃይል እንደምን ነው ለሚል ሰው ናባል በዳዊት ላይ ያልሆነ ነገር ተናግሮ በዚህ ምክንያት ዳዊት ናባልን ሊጣላው ሔዶ ሳለ ፥ ለናባል ዳዊት እንኳ ሊጣላህ መጣ ባሉት ጊዜ ከተቀመጠበት ደንጊያ ሁኖ ቀርቷል ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ጀግኖች መጡ በተባለ ጊዜ የጠላት ጕልበት ይንቀጠቀጣል። ዓመፀኛውም ሁሉ ቅጡ ይጠፋዋል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ነፃነቷ ለዘለዓለም የሚኖር፡ ሥልጣኑዋ የማይሻር ፥ አምባዋ የማይሰበር ፥ አንድነቷ የማይፈርስ፥ ስምምነቷ የማይደመሰስ፡ፍቅሯ የማይለወጥ፡ ኃይሏ የማይደክም ሁኖ ከልጅ ልጆቿ እንድትኖር ጀግኖችዋ በሥራቸው ይመሰክሩላታል ።

የኢትዮጵያ ፥ ነፃነቷ እንዳይጐድል ።
ልጆቿ አደጉ ጐለመሱ በኃይል ።
አንቺ ኢትዮጵያ ፥ ልብሽ አይደንግጥ ።
ኃይልሽ ተፈሪ ነው፥ የሚያንቀጠቅጥ ።
ምነው ድምጡ ጠፋ ያወንድማችን።
ራሱን ተመቶ ቃሞ ይሆንን ።
እቀማለሁ ብሎ የሌላውን ወርቅ።
የጁን ጥሎ ሔደ ፥ ያኖኛ ጻድቅ ።
የሚበላው ምግቡ፥ የሚፋጅ ነበረ ።
የሚያበርደው አጥቶ፥ አለወሀ ቀረ ።
ደጃች ሙሉ ጌታ፥ ፈጻሚ ትእዛዝ ።
ተብለው ይጠሩ ራስ ፥ ሙሉ ጉበዝ ።

መወድስ ።

ኃይለ ሥላሴ ቄርሎስ ዓምደ ሃይማኖት
በመዝራዕተ ዓቢይ ኃይልከ መትከፈ ዕልዋን ዘትሰብር፤
ለቤተ ይሁዳ ወኤፍሬም ከመ አንበሳ ወነምር።

እስመ ከመ መብረቅ ዘይወፅእ ።
ዘእሙር በብርሃነ ዓይኑ መንግሥትከ ንሥር።
በአየረ ጎንደር ዘይሠርር።
ዓለመ ጎንደር ይሬኢ ወከርሠ ቀላያት ይኄጽር ።
ትልበስኒ ኃይለ ሥላሴ ዓለመ በክፉ ጎንደር ።
ኃይለ ሥላሴ ዕንቈ ባሕርይ እስመ ለዕሩቃን ልብሰ ክብር።
ወልቡናየ ተመስጠ በመዓዛ ልብስከ ፍቅር ።
ሥላሴ ዘአነምዎ በመንበረ ብርሃንደብረ ታቦር።

መተርጕመ ሐዲሳት አለቃ ኃይሉ።

የዘመቻ ወሬ ።

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ከራስ ጉግሳ ወሌ ጋራ ተዋግተው ድል ስላደረጉ ።

የቤጌምድር ገዥ ራስ ጉግሣ ወሌ የታዘዙትን የመንግ ሥት ትእዛዝ ስላልፈጸሙ ፥ የጦር ሚኒስቴሩ ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ነገሩን ሁሉ ለመመርመር ታዘው ሒደው ነበርና ራስ ጉግሣ ወሌ ከደብረ ታቦር ገሥግሠው ከደጃዝማች ሙሉ ጌታ ላይ አደጋ ለመጣል ያሰቡት አሳባቸው ተሰምቶ ደጃዝ- ማች ሙሉ ጌታ በፍጥነት አሰልፈው መጥተው መጋቢት ፳፪ ቀን በቋና አውራጃ አንችም በሚባል ስፍራ ተዋግተው ድል አደረግዋቸው ።

ነገሩ እስከ ጦርነት የደረሰበትንና የጦርነቱንም አኳኋን በሚከተለው ቍጥር በዝርዝር እናስታውቃለን ።

የሰውን ወሮታ ስለሚያቀሉ ሰዎች ።

አንዳንድ ሰዎች የማያልፈውን ወሮታ የሠሩላቸው እንደ ሆነ በሚያልፈው ረብ ነገር ይለውጡታል ። እንግዲህ ያ ልቡ የቀና ደግ አድራጊ እንደነሱ ተከትሎ ክፉን ይሥራ ወይስ በን አዩ ጉድ ። በጣም የሚያስቸግር ነገር ነው ጉዳናቸውን ተከትሉ ክፉ እንዳይሠራ በእግዚአብሔር በቃል የተጠላ ነው። ደጉን እንዳይሠራ ሰተት አድርጎ የደለደለውን መንገድ አጠ- መመት ። ይህን የጠመመ መንገድ ለማለፍ እንደምን ይጨንቃል ። ዕውቀት አለኝ ይላሉ ጋራ የሚያህል ድንቍርና ተሸክሞዋል ። በልቡ አያልፍብኝም የማለት አሳብ ያለበት ይመስላል ። ዋ ከመቅጽበት እንዲጠፉ አያውቅም ። እንዲሁ ለራሳቸው ረብ እየፈለጉ እውነተኛውን ነገር ለማጣመም የሚፈልጉ ሁሉ እንዲህ ባንድ ሚስኪን ድኃ ልብ ቀለው የታዩ ከልዑል እግዚአብሔር ፊትስ እንዴት ይቀሉ ይሆን ። ዋ ሰው- ሆይ ።

ከደግ መወለድ መልካም ምግባር እንደሚሰጥ ።

፮ተኛ ዓመት በሥራ አንደኛው ቍጥር ፳፪ ገጽ ብርሃንና ሰላም አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ ጽፎ እንዳነበብነው እውነት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በዘመናችን የወጡልን ብርሃን ደጉ ሥራቸው ሁሉ ስንቱ ተነግሮ ይወሰናል ሁሉንም አሰማምቶ የሰጣቸው ፥ ሕግ አጥባቂ ፥ ንጹሕ ፥ ትዕግሥተኛ፥ ቶሎ የማይቈጡ ልበ ሰፊ ፥ ቸር ናቸው ። ትውልዳቸውና ምግባራቸው ከደጎች ወገን የሆነው ብልህነትን ፥ እውነተኝነ- ትን ፥ አለመዘንጋትን ፥ ለንጉሥ የሚገባውን ጠባይ ሁሉ እግዚአብሔር አስተካክሎ ሰጣቸው ። ይህነኑ ደግ ጠባይ ሰው ሁሉ እንዴት እያመሰገነ ለድሚያቸው ይሳሳላቸዋል ። ዕውቀት፥ ቅንነት ፥ አለመዘንጋት ፥ ፍርድን ሚዛን ማድረግ ፥ መቻል፥ ጥፋተኛውን መማር ፥ ልብን ማስፋት ፥ እንቅልፍ ሳይወስድ ለሕዝብና ለመንግሥቱ ጥቅም የሚሆን ደንብ ማሻሻል ፥ ቤተ እግዚአብሔርንና ቃለ መጻሕፍትን ፥ መምህራንን፥ ማፍቀር፥ እነዚህ ዘጠኙ አንድነት ሁነው ለንጉሥ የተገቡ ጠባዮች ናቸው ። በነዚህ መሰላሎች ላይ ሁኖ ንጉሥ የመንግሥቱን ኃይል የሕዝቡን ደኅንነት አጥንቶ ይሠራበታል ። ይህን ሁሉ ምግባር ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አስቀድሞ ታድለዋል ። እግዚ- አብሔር ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ዕድሜ ሰጥቶ አብሮ ለሚቈይ ሰው በሚመጣው ዘመን ለሕዝባቸው ደኅንነትና የኢትዮጵያን ከፍተኝነት የሚሠሩትን ለሚያይ ዓይን ምስጋና ይገባዋል ፥

አሁን የውቀት ማድ በኢትዮጵያ ተዘርግቶ ሁሉም እጁን ቃጥቦ አንዳንዱም እየቈረሰ ጕርሶ ያላመጠውን ሳይውጠው ፥ አንዳንዱም ለመቍረስ እጁን እንደዘረጋ ፥ በትቢትና በተንኰል ተነሥቼ ይህን የውቀት ማድ ባስተጓጕል ፥ጠላትነቴ ለኢትዮጵያ ብቻ አይደለም ። ኢትዮጵያ ዓይንዋን ከፈተች ወደውቀት ደረጃ ልትረመመድ ነው እያሉ በፍቅር ለሚጓጉላት ወዳጆቿ ሁሉ ነው ። አሁንም ሁሉን ቻይ የሆነ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ፥ የነገሥታት ንጉሥ ፥ የገዦዎች ገዥ ፥ መሐሪው አምላክ የማይሰለች እግዚአብሔር ፍቅርንና ሰላምን በምሕረቱ ያውርድልን ብለን እንለምነው ።

መክብብ ደስታ ።

አገራችንን እያየን እናስብላት አስበንም በማገልገል እናሳምራት

የርሻ ምኒስቴርና የሥራ ምኒስቴር ሥራቸው ከምድር ጋራ ነው ።

ምድር ካላፈራች መንገድ ካልተሠራ ለንግድ ምኒስቴር አይ- መቸውም። የሮቱ ምኒስቴሮች ሥራ ከበረታ ካገር ውሥጥ ብዙ ጥቅም ይገኛል ።

ባገራችን በየቈላው የዝናብ ወኃ እየተከተረ ኵሬ መሆኑ የጥንት ብልሐት ካባቶች የተገኘ ነው። ነገር ግን የኵሬው ወኃ ድፍርስ ሁኖ ሳይጣራ ይጠጡታል። ይኸውም ባላገሮች በብዙ የሚጠጡት ጠላ ነውና በመሀምጠጥ እየፈላ ለጊዜው ሚክ- ሮቡን ያደክመዋል ። ምንም ቢሆን ወኃ መጠጣት አይቀርምና ያነኑ ድፍርስ ወኃ በጠጡ ጊዜ ለበሽታ ሰበብ ይሆናል። ስለዚህ ከላይ የተከተረውን ድፍርሱን የተላውን ወኃ ከመጠጣት ዝቅ ብለው እኵሬው ሥር ጕድጓድ ቢምሱ ድፍርሱ ወኃ እየ- ተጣራ ምንጭ ይሆናል ።

አታክልት በሚሆንበት አገር

አገረ ገዢዎች የዝናቡን ወኃ እያስከተሩ ትልልቅ ኵሬ ቢያስደርጉ ። ኵሬ ለማድረግ እንኳ ባይመች ያታክልቱ ቦታ በያመቱ የሚዘንበውን የዝናብ ወኃ በጣም እንዲጠጣ ቢያደ-

ርት ብዙ ሲሳይ ይገኛል፡ በፀሐይ የበሰለውን የመሬቱን ጉድፍ የዝናብ ወሀ ላይ ላዩን እያጠበው ቢጐርፍ ትልቅ ጥፋት ነው·

ባ፲፱፻፲፰ ባ፲፱፻፳፩፡ ዓመት ባዲስ አበባ ዲንችና ሽንኩርት ሌላውም አይነት አታክልት ችግር ነበር። ከገር ውሥጥ የተገኘው አልበታ ብሎ ከበሕር ማዶ እየመጣ በውድ ተሸጠ ። ያውም ብርቅ ሁኖ ነበር ። ውድ የሆነበትን ምክንያት ሰነፉ ልባችን ያውቀዋል ። ዘንድሮ በየደጃችን ሽንኩርቱን ዲንቹውን ተማ- ትሙን ጐመኑን ብንተክል ለየቤታችን ሲሳይ ይበቃናል ።

የኢትዮጵያ ሰዎች ምግባችን እህል ብቻ ስለሆነ አታክልት ምግብ አይመስለንም ። በፈረንጅ አገር ከእህል ይልቅ ምግ- ብቸው አታክልት ነው ።

የዲንች ምግብና ጥቅም ከበቄላና ከተር አያንስም ።

አታክልት ሳይታይ እንደ ሚያድግ። ጥበብም ቀስ እያለች ብዙ ሥራ ትሠራለች ። ዓለሙ አብተ ሚካኤል።

ስለ ወይዘሮ አግዓዚት መልስ ።
የልጅ ወቀሳ ።

የክብርሽን ጥራት አሁን ምን ያስወራል
የስፍ ሽ ታሪኩ በዓለም ላይ ያበራል
ሐሳብ ባሳስብሽ የባላንጣችንን
ምነው መሰልሽብን የእንጀራናታችን
በሜን ላሳውቀው ለልጅሽ እያልሽ
እየተወለድሁሽ በንጻው ደምሽ
እናቴ መሆንሽን ተጠራጠርኩሽ
ወይዘሮ አጣዓዚት አስመሰሉብሽ
ኢትዮጵያ እናቴ በጣም ትኰራለች
ባለ ግርማ አንበሶች አሏት ወታደሮች
ከርበኞቿ ጋራ ማንይወዳደራል
አንዱ ወታደሯ ከ፲ ይቈጠራል
ብዙ ሚሊዮኖች አርበኞች አሏት
ማንም ማን ቢሆን አይማከታት
መከታው እንዳይቀር ደስ ማሰኘቱ
ጋሻው የሷ ሆነ የግርማ መንግሥቱ
በግርማቸውና በንበስነታቸው
ከመገምረው ነው በለም ላይ ቍጥራቸው
ያንድ ልጅ ወቀሳ እንዴት ግረመሽ
እንሠልጥን ባልኩሽ ምን አጠፋሁሽ
ለመጸደቂያሽ ብለን ማኅበር ገብተን
ጠበል በራሳችን አፈሰስሽብን
የክርስቲያን ሥራት እንዴት ያለው ወጣ
ጣትን እያሲያዙ ክዳትን አመጣ
ምን አይነት ክዳት ነው እንዲህ ያለ ጣጣ
ወዴት ይኬድ ይሆን ከሰማዩ ቍጣ
ምክሩማ ዝክሩማ እንዲህ ቢሰማሽ
ከወቀሳው ሁሉ መች ትደርሽለሽ
እንዲያው ለይስሙላው ብናወራልሽ
ለወሬው ባላንጣ አፍራሽ አለብሽ
ዩሸ ዘበን እግዚአብሔር ሰቶሽ
በመንፈሳዊነት ጽድቀት አግኝተሽ
ልጆች ለማስተማር እንዴት አቃተሽ
የልጆችሽ ትዳር እየተጋነነ
ስም እያስነሳም ወይ ባላንጣ ለሆነ
የሾህ አጥር ነበር የታጠረብሽ
ነቃቅሎ ነቃቅሎ ልጂሽ ጣለልሽ
የቃል ሥልጣኔአችሁ እያሉ ሲሉን
የወቀሳው ብዛት መድረሻ አሳጣን
ኢትዮጵያ እናቴ እንዴት ልውቀስሽ
በሕፃንነቴ አልደፍር እያልኩሽ
ላስታውስሽ ብዬ ነው ለተጻፈብሽ
በሩቅ ያለው አጥር እንደዚያ ሲያምር
ጭላንጭ እያሳይ የቤትሽ አጥር
የዙሪያው አጥርሽ እንዳይሰሳብሽ
አጥብቀሽ አጠረው አንቺ በግርማሽ
መንፈሳዊነትሽ እየተሰማን
እረድኤትሽን እንጠብቃለን
ለሕፃናቶቿሽ እንዲወርድልን
ንብረት እንድንወጣ ባንቺ ሠልጥነን
ክብርሽ እንዲጨመር በዓለሙ ሁሉ
በጣም እንዲጋነን ለመንግሥቱ ሁሉ
እንድትታፈሪ በባላንጣሽ ሁሉ
የውቀትሽ ገበታ ይዘርጋ በሙሉ
በብርሃን በሰላም ሁል ጊዜ እንድትኖሪ
ጨለማው እንዲለቅ አንድ ጊዜ ተፈሪ
የውቀትህ ጉዳና ተዘርግቷልና
እየታየው ይሒድ የብርሃንህ ፋና
አንድ ጊዜ ተፈሪ ተብለሀልና
ዘውዲቱ ምኒልክ የነገሥታት ንግሥት
የፀናው መንግሥትሽ እንደ ንጉሥ ዳዊት
በዳዊትሽና በጸሎትሽ ብዛት
ተደነቀ በጣም የመንግሥትሽ ግዛት
ሲደምቅ እየታየ የልጅሽ ጉዳና
ዘለቀ ከባሕር የመንግሥትሽ ዝና

ኪዳኔ ማ ተ ።

በቃለ ማሙዬ መልክሙ ወጣት ወንድማቸው ስለሞ- ቀባቸው ወንድሞቹ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ያለቀሱት የልቅሶ ዜማ ግጥም ባለፈው ጋዜጣ ስፍራ ጠበን አቈይተነው ነበር ።

፩ መልክሙ ቡቃያ የልባችን ተስፋ።
በቀለ ስንለው ምነው ቶሎ ጠፋ።
፪ የወንድም ቤት ሲፈርስ ምነው ዝምታችን።
ብዙ ማዘን መልቶ ዘንድሮ አገራችን።
፫ኛ የሕማምና ሞት እዴት ቢሰፋ ነው አዳራሻቸው።
ቶሎ ቶሎ ጠሩ ብዙ ደግሰው።

፭ኛ ወሬም ብንሰማ ቀርበንም ብናየው።
አዳራሹ ሕማም አሳላፊው ሞት ነው።
፮ኛ አልበላሁም ብሎ ለምን ሰውን አማ።
መቃብር እንጂ ነው የሥጋ ቤቱማ።

የክፉና የደግ ሰው መለያቸው በሞታቸው ቀን ነው።ክፉ የሆነ እንደሆነ እንኳን ሞተ አገር ሀረፈ ይባላል። ደግ የሞተ እደሆነ ግን ያልተወለደ ያልተዘመደው ሁሉ ያዝንለታል ለዚህም ደግ ልጅ ይህች ጽሕፈት መታሰቢያው ሁና እንድትኖር አሰብንለት።

ስለ ክቡር አቶ ጣሰው ገብሬዬ ዕረፍት።

አቶ ጣሰው ገብሬይ መንግሥታቸውን አክባሪ ለሀገራቸው ተቈርቋሪ ወገናቸውን አስከባሪ ነበሩ። ለመንግሥታቸው የወታደር አለቃ ሁነው በጅጅጋና በድሬደዋ ሲያገለግሉ ብዙ ጊዜ ኑረዋል።በታዘዙት ሥራ ሁሉ የታመኑና ጠንካራ ነበሩ። ከዚህ በኋላም ወደ አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ተዛውረው ይሠሩ ነበር። ነገር ግን ውሎ አድሮ ምንም ቢያገለግሉና ባያገለግሉ ሞት አይቀርምና ታመው መጋቢት ፲፱ቀን ዓርፈው በቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ክቡር ከንቲባ ነሲቡ የማዘጋጃ ቤት ሹማምትንና ዘበኞችን አስከትለው ሒደው በክብር ቀብረዋቸው።

ብርሃንና ሰላም ለክብርት ባለቤታችው ለወይዘሮ አየለችና ለዘመዶቻቸው እግዚአብሔር ያጥናችሁ ይላል።

ስለ ክቡር አባ ኪዳነ ማርያም ዕረፍት ።

ክቡር አባ ኪዳነ ማርያም ንጹሕ ድንግል መነኵሴ ሃይማኖተ ፅኑ፥ ምግባረ ቅኑ፥ ስመ ጥሩ፥ ግብረ መልካም፥ቅን ሰው ነበሩ ። ሀገራቸው ሐማሴን ወረዳ በኢጣልያ ግዛት ውሥጥ ነው ። በልጅነታቸው በደብረ ቢዘን ገዳም መንኵሰው ሲኖሩ ልዑል ራስ መኰንን ከትግሬ ወደ ሸዋ ሲመለሱ ልዑል ራስ መኰንን ተከትለው መጥተው አብረው ወደ ሐረር ወርደው ከልዑል ራስ መኰንን አስፈቅደው በጅቡቲ በኩል በመርከብ ተሳፍረው ወደ ተቀደሰችው ምድር ወደ ኢየሩሳሌም ወርደው ጌታችን በሕይወተ ሥጋ የኖረበቸውንና ልዩ ልዩ ተአምራት የሠራባቸውን ቅዱሳት አድባራትና ገዳማትን ስመው ከዚያም ወደ ሮማ አልፈው የቅዱስ ጴጥሮስን ቤተ ክርስቲያንና የሮማን ከተማ ውበትና መልካምነት አይተው ተመልሰው ወደ ምስር ወረዱ። ከዚያም የቅዱስ ማርቆስን ቤተ ክርስቲያን ስመው ከብፁዕ ፓትርያርክ ከአቡነ ቄርሎስ ቡራኬ ተቀብለው ወደ ገዳማቸው ወደ ቢዘን ተመልሰው ሲኖሩ ከጥቂት ቀን በኋላ የኢትዮጵያን መንግሥትና ሕዝብ ስለ ወደዱ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በጕለሌ ሩፋኤል አጥቢያ ሲኖሩ ዓሥራ ስምንት ዓመት ያህል እንደ ተቀመጡ በስድሳ ዘመናቸው በድንገት ታመው በሰባተኛው ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም መጋቢት ፲፯ ቀን ከሌሊቱ በ፯ ሰዓት ዐርፈው ታላቅ ልቅሶ የጕዞ ፍትሐትና ጸሎት ተደርጎላቸው በጕለሌ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ከቤተ ልሔም አጠገብ ባለው በታ በመልካም ማዕርግና ክብር ተቀበሩ። ይልቁንም ስለ መልካም ሰውነታቸው የሚመሰክር ሥራ በዓቢይ ጾም ማንም ሰው ቢሞት በከበሮና በጸናጽል ፍትሐትና ጸሎት አይደረግለትም ነበር ስለ አባ ኪዳነ ማርያም ግን ሊቃውንቱና ካህናቱ አንድነት መክረው ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር የተባለው ክብር ይገባቸዋል ብለው ያረፉበት በታ ከክቡር አለቃ ሠርፀ ቤት ነበርና ዕረፍታቸው እንደ ተሰማ ወዲያው ካህናቱና ሊቃውንቱ ሁሉ በደወል ተሰብስበው ከዚያው አስከሬናቸው ካለበት ቤት ሌሊቱን ሁሉ ማኅሌት ቆመው ሲፈቱ አድረው ቀኑንም የጕዞ ፍትሐት ሲፈቱ ውለው በታላቅ ልቅሶና ኀዘን በመልካም ማዕርግና ክብር ቀበሯቸው። ደግሞም ለካህናት እንደ ሚገባ ክብር በአስከሬኑ አጐበሩ ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ ሁነው እንተ ኪዳነ ማርያም ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼድቅ እያሉ በኀዘን ዜማ እየወረቡ ሲጓዙ ልብን ያሳዝኑ ነበሩ ። የከተማውም ሕዝብ ባልተወለዱበትና እምሳ ስድሳ ዘመን ባልተቀመጡበት አገር ስለ ሃይማኖታቸውና ስለ መልካም ሰውነታቸው መኳንንቱ፥ ወይዛዝሩ፥ መነኰሳቱ፥ ካህናቱ፥እሰሩግ ሕፃናቱ ሁሉ ተሰብስበው ታላቅ የልቅሶ ዋይታ አድርገው ልብ የሚነካ ፅኑ ኀዘን አዝነውላቸው ዋሉ ። ይልቁንም በማልስታቸው ማለዳ ስፍር ቍጥር የሌለው ሕዝብ ተሰብስቦ ከቀብሯቸው ላይ ትንሽ ትልቁ ልጅ አዋቂው ሲፋጅና ሲላቀስ ላየ ሰው ያገሩ ተወላጅ ያገሩ ገጋርና ባላባት ይመስሉ ነበር እንጂ የሰው አገር ሰው ባይተዋር እንግዳ አይመስሉም ነበር።ይህ ሁሉ የመልካም ሰውነታቸው ፍሬ ምስክር መሆኑን ያስረዳል ። ለዘመዶቻቸው ለወዳጆቻቸውና ለባልንጀሮቻቸው እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

ዮሐንስ ማርቆስ ።

ማስታወቂያ።

ከማዝያ ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ጀምሮ በ፲፩ ጥቅምት ፳፩ አክቶ-ብር ፲፱፻፳፫ዓ ም የወጣው ታሪፍ ተለውጦ ከሚያዝያ ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ጀምሮ ለገቢና ለወጭም ዕቃ አዲስ ታሪፍ መቆሙን ለነጋዴዎችና ለሌሎች ሰዎች ሁሉ እናስታውቃለን። ታሪፉንም ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች ሁሉ ከአረዳ ወይም ከለጋር ጕምሩክ በጠየቁ ጊዜ ከሚያዝያ ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ጀምሮ ይሰጣቸዋል ።

ከ፲፱፻፳፪ ዓመት ሚያዝያ፩ቀን ጀምሮ ስለጉምሩክ አቀራረጥ የእንግሊዝ ወርቅ ሽረኑ በ፲፮ብር ነው የሚታሰበው ማሪያ-ቴሬዛ ዮኑም እንደቀድሞው ከሮፓ ከእስያ ከምስር ላይ ለሆነው ፋክቱር

ሁሉ ከመቶ አምሳ ከአደን ላይ ለሆነው ፋክቱር ከመቶ ሠላሳ ከጅቡቲ ላይ ከመቶ ሀያ አምስት።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ።

ማስታወቂያ ።

ከአዲስ አበባ እስከ ጅሁር አፋፍ ድረስ የአቶሞቢልና የካሚዮን መሔጃ መንገድ በተሠራው አሁን ለጊዜው ሰውም ዕቃም እንዲሔድበት ካሚዮን አቶሞቢል ስለተሰናዳ ቀጥሎ የተጻፈውን እናስታውቃለን ።

መጀመሪ ።

ካሚዮን በየሳምንቱ ሰኞና ሐሙስ ከአዲስ አበባ ወደ ጅሁር ይሔዳል።ከጅሁርም በየሳምንቱ ሰኞና ሐሙስ ወደ አዲስ አበባ ይመለሳል ።

ሁለተኛ ።

ከአዲስ አበባም ወደ ጅሁር፡ከጅሁርም ወደ አዲስ አበባ የሚሔድ ሰው ላንድ ጊዜ ሦስት ብር ዕቃም ለጫኚ በመቶ ኪሎ ሒሳብ አራት ብር ይከፍላል ።

ሦስተኛ ።

ከአዲስ አበባ እስከ ጅሁር በተሠራው መንገድ ላይ በማናቸውም በታ ለመሔድና ለመመለስ ዕቃም ለመጫን የፈለገ ሰው የበታው መራቅና መቅረብ በኪሎሜትሩ ታስቦ ዋጋውን ከፍሎ ለመሔድ ይችላል ።

አራተኛ ።

በማናቸውም ቀን ለመሔድና ዕቃም ለመጫን የፈለገ ሰው አስቀድሞ ወደ ካሚዮንና አቶሞቢል ጽሕፈት ቤት መጥቶ ተነጋግሮ ለመሔድ ይችላል ። የጽሕፈት ቤቱም በቤተ ሳይዳ ሆስፒታል አጠገብ ነው።በዚሁም በተሠራው መንገድ ላይ ከመንግሥት ካሚዮንና አቶሞቢል በቀር በራሱ ካሚዮንና አቶሞቢል የሚሔድ ሰው ላንድ ጊዜ እግር ለካሚዮን ሐያ ብር አቶሞቢል ዓሥር ብር ታክስ ከፍሎ ለመሔድ ይችላል ። ለዚሁም ሥራ ዴሬክተሩ ልጅ ግርማ ያየህ ይራድ ነው ።

ማስታወቂያ።

ሙሴ በጎስ ኤቢያን ማለፊያ የሆነ የነቀምት ቅቤ አንዱ ቆርቆሮ በሀያሁለት ብር ይሸጣል።ቤታቸውም በጉለሌ መንገድ በሰባራ ባቡር አጠገብ ነው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚሁ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጆኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ጎሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፶ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፸፭ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸፭ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፸፭ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፸፭ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸፭ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፸፭ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፷ መሐ
አሳብና ምኞት	፴ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፴ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፳ መሐ
ፈደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳ መሐ
የእንቀጣጣሽ ግጥም	፳ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኩረጃ	፲፪ ብርተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኩረጃ	፳፺ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኩረጃ	፻፸፫ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፱ ብር
ባለ ድመት		፻፶ ብር
ባለ አህያ		፻፵ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፵፰ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፪ ብር
ጃፖን		፻፹፯ ብር
ሱካር	፩ ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ፭ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፭ ከ፸ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ	፶

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሚል።የማኅበሩ ዋና ቤታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሹቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኳ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዷሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው



አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ· ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዳግማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
6me ANNÉE №. 15

ሐሙስ ሚያዝያ ፪ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም.
JEUDI 10 AVRIL 1950

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Sa Majeste le Roi Teferi Makonnen, profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉት ወደ ዲሬክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ዕረፍት ።

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በ፲፰፻፷፰ ዓመተ ምሕረት በሚያዝያ ፳፩ ቀን ተወለዱ ። በ፲፱፻፱ ዓመተ ምሕረት በየካቲት ፬ ቀን በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተውና ዘውድ ጭነው ንግሠው ንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ተባሉ ።

ከነገሡም ካንድ ዓመት በኋላ ላባታቸው ለዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ሕንፃው እጅግ ያማረና የተዋበ ቤት ሥራ ጀምረው በሰባተኛው ዓመት ተጨረሰ። እስከ ዓሥራሁለት ዓመት ድረስ ከሰው ሁሉ በሚበልጥ ተዝካር በያመቱ በዘመናቸው አውጥተው ቀጥሎም የእቴጌ ጣይቱና የሊቀ ጳጳሱ ያቡነ ማቴዎስ አፅም በዚያው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ እንዲገባ አድርገው አሠሩ ።

ደግሞ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እጅግ የታደሉ መሆናቸውን የሚያስረዳ ነገር በዘመናቸው ከኢትዮጵያ መምህራን መካከል ፭ መምህራን ተመርጠው ከሊቀ ጳጳሱ ከአቡነ ቄርሎስ ጋራ ጳጳስነት ተሾሙ። ከዚህም ቀጥሎ ቀድሞ በኢትዮጵያ ተደርጎ የማያውቅ የእስክንድርያው ፓትረያርክ አቡነ ዮሐንስ ወደ አዲስ አበባ መጥተው መንግሥቱንም ሕዝቡንም ባርከው ወዲያውም በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ቅዳሴ ቀድሰው ሥጋ ወደሙ አቀበሏቸው ።

ለእጨጌውም እዚሁ ጵጵስና ሰጥተው ሔዱ ። ለፈጣሪያቸውም ሰውነታቸውን መሥዋዕት አድርገው የነገሡብትንም ዘመን ሁሉ በጾም በጸሎት በንጽሕና ጨርሰው

ለቍጥርም እጅግ የበዙ አብያተ ክርስቲያናት አሠርተው ንዋየ ቅድሳቱንም ለሁሉ በመስጠት አድርሰው ለምግባርና ለትሩፋት አብነት ሁነው፤መንፈሳዊት ሥራቸውን ሁሉ ከጨረሱ በኋላ ከመጋቢት ፳ ቀን ጀምሮ ጥቂት ጥቂት ሲያማቸው ሰንብቶ ነበርና ከመጋቢት ፳፩ ቀን በኋላ ሕመማቸው እየጠናባቸው ስለሔደ በተወለዱ በ፶፫ ኛው ዓመት፣ በነግሡ በ፲፬ኛው ዓመት በ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት መጋቢት ፳፬ ቀን ከቀኑ በ፰ ሰዓት ዓርፈው በአባታቸው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤት ተቀበሩ።

በኢትዮጵያ ልማድ ነገሥታት ሲሞቱ አልጋ ወራሹ በዙፋኑ ከተቀመጡ በኋላ በሌላ ጊዜ ይለቀስ ነበር እንጂ ዕለቱን አይለቀስም ነበር። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባረፉበት ቀን ግን ስለደግነታቸው ብዛት ግርማዊ ንጉሥም መኳንንቱና ወይዛዝሩም ኀዘናቸውን ለመታገሥ የማይቻላቸው ስለሆነ ካረፉበት ከ፰ ሰዓት ጀምሮ እስኪቀበሩ ድረስ፤ከተቀበሩም በኋላ ሌሊቱን ሁሉ በግልጽ ሲለቀስ አድሮ በማግሥቱም እንደተለቀሰ ዋለ ።

በማልስቱም እንደገና ግርማዊ ንጉሥ መኳንንቱንም ወይዛዝሩንም ሕዝቡንም ሰብስበው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ በወለሉ ላይ ዙፋን ተዘርግቶ ፎቶግራፋቸው ተደርጎ መኳንንቱና ሠራዊቱ ልዩ ልዩ የሆነ ፎቶግራፋቸውን ይዘው በመታሰቢያ ቤቱ ዙሪያ እየዞሩ በታላቅ ኀዘን ተለቀሰላቸው ። ጳጳሳቱም ከካህናቱ ጋራ ፍትቱን ሲፈቱና ሲያስለቅሱ ዋሉ ።

የጦር ሚኒስቴሩ ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋር ስለ መዋጋታቸውና ድል ስለማድረጋቸው ።

በ፲፱፻፳፩ ዓመተ ምሕረት ራስ ጉግሣ ወሌ የቤገምድር ግዛት ይቅርብኝና ያባቴን አገር የጁን ስጡኝ ብለው ደብዳቤ ጽፈው ቢለምኑ ።

ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ የለመኑትን ለመስጠት ቍርጥ አሳብ አደረጉ ። ነገር ግን በዚያ ወራት ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ በኢትዮጵያ ስሜን ያለውን አገር ለማየትና በፍርድም በስጦታም ሕዝቡን ደስ ለማሰኘት ወደወረኢሉና ወደደሴ ብቅ ለማለት አስበው ነበርና ወዲያው ራስ ጉግሣ ወሌ የለመኑትን የጁን ለመስጠት ፈቃድ አድርገው ወረኢሉ ድረስ እንዲመጡ ብለው ቢልኩባቸው እሺ እመጣለሁ ካሉ በኋላ እንዲመጡ በታዘዙበት ቀን ሳይነሡ ቀሩ ።

ከዚህ በኋላ ነገ ሠልስት ሲሉ ክረምቱ እንዳይገባ ተብሎ ቶሎ እንዲመጡ እንደገና ቢላኩባቸው ንጉሥን ወረኢሉ ድረስ ምን የሚያስመጣ ነገር አለ ። ደግሞም ወረኢሉ ድረስ እንድትመጣ ከተባልኩ ይኸው ልነሣ ነው ብለው ከስታወቁ በኋላ ሳይነሡ ቀሩ ። ለመገናኘቱ ምክንያት እያበዙ ከስቸገሩ ብይሆን ወደ አቅርቢያቸው ይታዘዙና የልግማቸው ቍርጥ ይታወቅ ተብሎ በዚያው ዓመት የራያና ያዘቦ ጋላ እርስ በርሱ እየተዋጋ ይጋደላል ከብትም ይዘረፋል የሚባል ወሬ ተሰምቶ ነበርና የዘር ወራት ስለሆነ ባላገሩ እንዳይቸገር ፥ ከርብ ወዲህ ያለውን ባለማደሬውን ሰው ብቻ ይዘው ወደየጁ ብቅ ብለው የተዘረፈውን ከብት እንዲያመላልሱ ለሞተውም እንዳገሩ ደሞቡ የነፍስ ዋጋ እያቀባበሉ እንዲያስታርቁ፤እንቢ ቢልም እንዲወጉት ተብለው ቢታዘዙ ያልተፈቀደላቸውን ከርብ ወዲያም ከርብ ወዲህም ያለውን ባለመደሬውን ባላገሩንም በሙሉ አዘው ባልታዘዙበት አገር ከሰኔ ጀምረው ዋድላ ሰፍረው ክርመው በሽታው በሚጸናበት በጥቅምት ወር ቆላ ወርደው አንድም ሥራ ሳይሠራ ሠራዊቱን በበሽታ አስፈጅተው ወደ የጁ ተመለሱ ፥ በበሽታና በዘመቻ ለተጐዳውም ሠራዊት ብር ከደሴ እንዲያስወስዱ ካንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ ቢላክባቸው ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ ለሕዝባቸው የማያዝኑ ለማስመሰል ብሩንም ሳይቀበሉና ሳይወስዱ ቀሩ ።

ደግሞ የሚዋጉ መስለው መንግሥቱን አታልለው ጋላውን የምወጋበት ጥይት የለኝም ብለው ለምነው ከወርኢሉም ካዲስ አበባም በግስጋሴ ቢላክላቸው ምንም ሥራ ሳይሠሩበት ለኋላ አሳባቸው እንዲመቻቸው ከሳቸው ጋራ ለመከረ ላመፀኛው ባላገር አከፍለው ያኑ ዓመፀኛውን ሸልመው ተመለሱ።ከዚህ በኋላ ምንም ሳይሠሩ የሠሩ ለመምሰል እርስ በርሱ የሚዋጋው ጋላ በእርቅ ገብቶልኛል ብለው ቢልኩ እኔ ወደደሴ መምጣቴ ነውና በዕርቅ የገባውን የጋላውን ባላባት ይዘው ደሴ ድረስ እንዲመጡ ብለው ግርማዊ ንጉሥ ቢልኩባቸው እሞኛል ብለው አመከኙ። እርስዎ ከታመሙ በዕርቅ ገብቶልኛል ያሉት የጋላውን ባላባት ሹማቸውን ጨምረው ሳይልኩ ፩ ምንም አጥፊ ሳያስሩም ሳያስታርቁም ከዚህ በኋላ ከጨጨሆ ላይ ከሚመስላቸው ጋራ ሴራ አድርገው የተከተላቸውንም ቤገምድር በገዘንብ በሐሰት ወሬ አባብለው አታልለው ከየጁ ከድተው እሞኛል ብለው የነበረውን ሐሰት መሆኑን ለብርቱ ግስጋሴአቸው እያሳዩ ቀድሞ ሲዘምቱ በብዙ ቀን የተጓዙትን መንገድ በግስጋሴ በጥቂት ቀን ቈርጠው ደብረ ታቦር ገቡ።

ከገቡ በኋላ የሳቸውን ሴራ ወደ ቤገምድሬው በሐሰት አዙረው አመከኝተው የቤገምድር ሰው ለዘመቻ ከወጣ ቀኑ ስለ በዛበት ባንድ ቃል ሁኖ ወዳገራችን ይመልሱን ቢለኝ ጠይቄ ምላሽ ልስጣችሁ ብላቸው ለመጠየቂያ ጊዜ አንሰጥም ብለው ቢያስቸግሩኝ በዘመቻ የደከመውን ሰሙ አሳርፌ ያልዘመተውን ሰው አስከትዬ ንጉሥ ወረይሉ ሲመጡ እመጣለሁ ብዬ ሔድሁ ብለው የስልክ ቃል ቢያሳልፉ ግርማዊት ንግሥት፤የንጉሥም ጓዝ ተነሥቷል፤እሱም እኩሌታውን መንገድ የሚሔደው በአቶመቢል ስለሆነ በቅርብ ቀን ወረኢሉ ይደርሳልና አንተም ገስግሰህ ለየካቲት ኪዳነ ምሕረት ወረኢሉ እንድትገባ ይሁን ብለው በጥር ፳፰ ቀን ቢያሳልፉላቸው ።

ራስ ጉግሣ ወሌም ወረኢሉ ለመምጣት ፈቃዳቸው አለመሆኑን የሚአስረግጥ እመጣለሁ ብለው የነበረውንም ቃላቸውን ትተውት በኰርቻ በዘር ነው የከረምኩት ምነው አያዝኑልኝም ወይ ብለው ወቀሰው ንጉሥ ወረኢሉ ካልመጡ አልመጣም ማለታቸውን የሚያስረዳ የካቲት ፩ ቀን ላኩ ።

ከዚህ በኋላ ወታደር እየሰበሰቡ ማማላቸው ፡ በግርማዊ ንጉሥም ላይ የሐሰት ወሬ በማስወራታቸውና የመክዳታቸውን ነገር ስለተገለጠ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ የቤገምድር አገር እንዳይጠፋ ፡ ራስ ጉግሣ ወሌና ሠራዊቱም እንዳይጐዳ ሰላሰቡ ነገሩን በጭሩ ለማስተረት ሲሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ወደ ራስ ጉግሣ ወሌ መላክ ጀመሩ ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ ።

ባንተ ላይ የምንሰማው ነገር ሁሉ ቢያስቸግረኝ እንፊታውራሪ ወደ ሚካኤል በቶሎ ይምጡ ብዬ ከዚህ ቀደም በስልክ ልኬብሀለሁ ። እኔ ግን የምሰማውን ነገር ሁሉ ታደርገዋለህ ብዬ አልጠረጥርም ። ሰው እያገነነ ሲያወራው ጊዜ ቢቸግረኝ ነው ።

የእቴዬ ጣይቱ ልጅ ሁነህ የወሌ ልጅ ሁነህ ፡ ከኔ ጋራ ብዙ ዘመን አብረን ኑረን ። በደግህበት መንግሥት ክፉ ነገር ታስባለህ አይመስለኝም ።

የተከፋህበትስ ነገር ቢኖር በእንደዚህ ያለ ተቀይሚአለሁ ይህንአድርጉልኝ ብለህ ሳትልክብኝ ሌላ አሳብ ታስባለህ አልልም

አሁን እኔ ይኸን ሁሉ ነገር መጻፌ የሚከፋብሀን ነገር የሚነግሩህ እናትህ እቴዬ ጣይቱ አባትህ ራስ ወሌ የሉምና እንደእናትም እንደ አባትም እንደወዳጅም እንደዘመድም ሁኘ በመንግሥቱ ስም ሳይሆን በተለየ ዝምድናዬ ነው ።

አሁንም ንጉሥ ተፈሪ ወደደሴ ሊነሣ ነውና ያልዘመተውን ሰው ይዤ ንጉሥ ተፈሪ በመጡ ጊዜ እመጣለሁ ብለህ አንተው እንደላከው ቃል በዚህ ቀን እንገናኝ ብሎ በላከብህ ጊዜ አንተም በዚያው ቀን ተነሥተህ እንድትመጣ ይሁን

ሰው የከዳትን ነገር አውርቶብኛል ብለህ ልብህ እንዳይሰጋ እምነቱን በኔ ላይ ጥለህ እንድትመጣ ይሁን ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ከዚህም በላይ ለተላከባቸው ቃል ምላሽ ሳይሰጡ ስለቀሩ ምላሽ በመንግሣታቸው ለጥፋት መቍረጣቸውን አውቀው ግርማዊት ንግሥት እንደገና ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ላኩባቸው

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ ።

ከዚህ ቀደም ይህን ያልሆን ወሬ እንደሰማሁ ጥር ፳፱ ቀን በስልክ ልኬብህ ነበር አልደረሰልህምን ። አሁንም ያንኑ የላክሁብህን ቃል በውል ተመልክተህ ይኸንን ያልሆነ ክፉ አሳብ ከልቡናህ አጥፍተህ አንተም ባልሆነ ነገር እንዳትጠፋ እኔም ባላሰብኩት ባልተነጋገርነው ነገር ንግሥት ልከውብት ነው ይህ ሁሉ ነገር የተነሣው እየተባለ ሰው ሁሉ ያወራብኛል አንተስ በዚህ የተነሣ ከሞት ስፍራ ብትደርስና ተዋርደህ ብትወድቅ ምድነው ጥቅምህ ።

አሁንም ባባትህ በወዳጅህ ባዬ ምኒልክና በናትህ በእቴጌ ጣይቱ ባባትህም በወሌ አፅም ብለህ እንደዚሁ እንደላኩብህ ቃል ወረይሉ ድረስ ቀደም ብለህ ገስግሠህ እንድትመጣ ይሁን።

ነገር ግን ለእጄ አፈራለሁ እቃሠራለሁ እንዳትል ከዚህ ቀደም እንደላኩብህ እምነትህን በኔ ላይ አድርገህ ዋስህም ጠበቃህም እኔው ነኝና በመድኃኔ ዓለም በወዳጅህ በተሰቀለው ጌታ ብለህ እንድትመጣ ይሁን የካቲት ፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ከዚህ በላይ የተጻፈው የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት የስልክ ቃል ከሔደላቸው በኋላ ራስ ጉግሣ ወሌ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል መለሱ ።

ይድረስ ከግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ።

የፊታውራሪ ወልዴ ሚካኤልን መድረስና ደግሞ በፊታውራሪ ኪዳኔ ቍጥር የላኩልኝ የስልክ ቃል ደረሰልኝ በየሁትም ጊዜ እጅግ አዘንኩ ።

አሁንም ቢሆን ከመገዛቴ በቀር የጃንሆይን አልጋ ንግሥትን የጠላሁበት ነገር የለኝም። ነገር ግን ንጉሥ ተፈሪን ስለፈራሁ እሥራት መሮኛልና ከንጉሥ ጋራ የሚያስታርቀኝ ሽማግሌ አላገኘም ብዬ ነው ።

አሁንም በስልክ ነገር አይቈረጥምና በደብዳቤ ልኬአለሁ ፊታውራሪ ወልዴ የጻፍንስ መጣስ መጥ ይገባል ። ነገር ግን እንደዚህ እንደላኩብዎ ነገሩ የሚሆን አይመስለኝም ብለው አጭር የትዕቢት ቃል ላከው ልታረቅም አልታረቅም ሳይሉ ቀሩ ። የካቲት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ም ።

እሱን ልብ ቢነሣው እኛ ልናስጨርሰው ይገባናልና የኛን ቃል ከጠላው እስኪ እናንተ ደግሞ ላኩበት ተብለው የራስ ጉግሣ ወሌ መልክተኛ ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል አዲስ አበባ ደርሶ የራስ ጉግሣን ደብዳቤ ከሰረከበ በኋላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል በስልክ አሳለፈ ።

ይድረስ ከጌታዬ ከራስ ጉግሣ ወሌ ።

ግርማዊት ንግሥት ፊትም እኔ ሳልደርስ ፤ እኔም ከደረስሁ በኋላ ወደርስዎ የጻፉትን የስልክ ቃል አሳዩኝ በየሁትም ጊዜ እጅግ አዘንኩ ።

ለኔ እንዲህ ያሳዘነኝ ለእርስዎማ እንደምን ያሳዝንዎ ይሆን ብዬ አሰብሁ ።

መልሱ ግን ቈይቶ በየካቲት ፲፫ ቀን የላኩትን የስልክ ቃል አሳዩኝ እንደ ህ ተጨንቀው ሲልኩብዎ ጊዜ ያልተገለጸ መልስ እንደምን ይጻፋል።የዕርቁን መንገድ አንድም አይናገር። አሁንም በቶሎ ገልጸው ይላኩባቸውና ቢታሰብበት ይሻላል ።

በዚህ ነገር እንኳን ንግሥት ጳጳሳቱም ሚኒስትሮቹም ለጅዎ የሚታመኑ ናቸው ። የዚህ መልስ ነገሩ እንዲበርድ በቶሎ ይምጣልን ስል ለጌታዬ አመለክታለሁ።የካቲት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

እሽከራቸው ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤልም የዕርቁን ነገር ገልጠው ያስታውቁ ብሎ ከላከባቸው በኋላ አሁን ቢያዝኩት በበጌምድር ግዛት ላይ አሁን የዘመትኩበትንና የደከምኩበትን ያባቴን አገር የጃን ንግሥትም ንጉሥም ፈቅደው ከሰጡኝና ንጉሥም ከማሩኝ ፤ ንግሥትም የሚያስምሩኝ ከሆነ እሽ እታረቃለሁ ብለው የካቲት ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፪ዓመተ ምሕረት ወደግርማዊት ንግሥት አሳለፉ ።

ራስ ጉግሣ ወሌም በበጌምድር ላይ የጁን ደጨምሩልኝና እታረቃለሁ ብለው ከመለሱ በኋላ ግርማዊት ንግሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል አሳለፉላቸው ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ

ሊቃውንቶች መጽሐፍ ሲነግሩን አንተ ሰው ከሚመጣብህ ነገር ሁሉ ተጠበቅ ታገሥ እያሉ ይነግሩናል። አንተም ታውቀዋለህ ።

ደግሞ እኔ ልንገርህ፡አንተስ ከአባትህ ትበልጣለህ፡አባትህስ ካንተ ያንሣሉ ፤ ጃንሆይ ታመው እነራስ ተሰማ ይምጡ ብለው ቢልኩባቸው ያገራቸው ሰዎች ግን ቢጠሯዎ ይሄዳሉ ኋደኛዎ ራስ ተሰማ እኮ ነው የነገሡው ያም ልጅ ገና ሕፃን ነው ጌታምዎ ታመዋል ፤ አገራችን ላይ እንምታለን እንጂ ከእንግዲህ ወዲያ ወደሸዋ ሄደን አንዋረድም ቢሏቸው ፡ የምኒልክን መንግሥት እኔ መጀመሬ አልከዳም ብለው መጥተው ጥቂት ቀን እንኳ ቢጕላሉ የሃይማኖታቸው ብርታት የጌታዬን መንግሥት መጀመሯ አልከዳም ብለው በመምጣታቸው እንደገና ተሾመው አገራቸው ገብተው በሠሩት መቃብር ቤት በማዕርግ አልተቀበሩምን ። አሁንስ አንተ እንደዚሁ እንዳባትህ መንግሥት አልከዳም ብለህ ብትመጣ ምን የሚጐዳህ ነገር አለ ።

ደግሞስ እነፊታውራሪ ወልደ ሚክኤል ከመጡ ወዲህ ለነገርኋቸውና ለላኩብህ የመለስከው ቃል የሚገባ መልስ መሆኑ ነው። ምነው ነገሩስ እንዲህ ጠፋህ ። ምክርስ ለምን አልሰማ አልክ ። ነገር ግን ብዙ ዓይነት ምክርና ብዙ ተግሣፅ ብልክብህ ለሚጠፋ ሰው መድኃኒት የለውምና አልገባ አለህ ከእንግዲህ ወዲያ ግን ሁለተኛም መላክ የለብኝም ። ብትሞትም አንድ ነገርም ብትሆን ኀዘንና ጸጸት የለብኝም እወቀው። ከኔ በኩል ቆረጥሁ ። ያጠፋና የተጣላስ ሰው የጥየቃ ቃል ሲመጣበት ጊዜ እጄ እንዳይያዝ አስታርቁኝ ይላል እንጂ በቀድሞ አገሬ ላይ አገር ጨምራችሁልኝ ልታረቅ ብሎ መላክ የሚገባና የሚያወጣ መስሎ ታየህን እኔማ እዲያው ለነገሩ የኋላውን ኀዘን እዳያስቀርልኝ ከሆዴ ያለውን አሁን ልወጣው ብዬ ነው እንጂ በምኒልክ አፅም በናትህ ብጣይቱ እጽም ብዬ ብልክብህ የማይረባ ቃል ከመለስህ ወዲያ እንዲያው ልቤ አልችል ብሎ እናገራለሁ እንጂ ነገሩ በቅቶኛል።ከእንግዲህ ወዲያ ግን እወቀው የኔም የመጨረሻ ቃሌ ነው አሁንም ለእጅህ የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ከንጉሥ ጋር ቈርጠን ተነጋግረናልና ብትመጣ ነው መልካሙ የካቲት ፳ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ከዚህ በኋላ ራስ ጉግሣ ወሌ ንግሥትንም አልከዳሁም የሚል የማታለል ቃል እየመላለሱ ስለላኩ ግርማዊት ንግሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለሱ ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ ።

በ፳፫ የካቲት የላክህብኝ የስልክ ቃል ደረሰልኝ ለምልክብህ ነገር ሁሉ ከፈቃድዎ አልወጣሁም አሁንም አልወጣ እያልክ ትልክብኛለህ፡ከፈቃድ መውጣት ማለት ሲጠሩት አለመምጣት አይደለምን ። እንኳን ትእዛዜ ልመናዬስ ሁሉ መቸ ቀረ በቀድም እንደላኩብህ ቍርጥ ቃሌን ሰጥቼ ነበር።አሁንም ምክሬን የምትሰማኝ ከሆነ ቈረጥኩ ብዬ ጥፋ አልልህምና ለምትሰጋውለእጅህ ነገር ቀድሞም አልታሰበብህ ወደፊትም አይደረግብህምና ለዚህ እምነት ትፈልግ እንደሆነ እኔም ንጉሥም እንድንታመንልህ እዚህ ላሉት አሽከሮችህ ላክባቸውና በነሱ ፊት እንታመንልሃለን ከዚህ በቀር ግን የመንግሥቱን አገር ከውስታ አግብተህ መጻፍህ የሚገባ አለመሆኑን አንተም ማወቅህ ደግ ነው ።

ለላኩብዎ ወቀሳ ምላሹን ሳይልኩብኝ ቀረ ላልከው ግን ለወቀስከው ነገር ሁሉ ለመንግሥቱ ሥራ ሲባል ነው እንጂ አንተ እንድትበደል ተብሎ የተሠራ ነገር አይደለም። የታዘዘ ሰውስ ለምን እንደዚህ አዘዛችሁኝ ብሎ ይጠቅሳልን ስለሰውም ጕዳት እያዘንን ሁለት ጊዜ ብንልክብህ አንተ አይሆንም ማለትህን ልብህ ያውቀው የለምን ።

ሌላ ሌላውም ነገር ሬት የላክኸውን ቃል ሁሉ የስልኩን ረቂቅ አትመለከተውምን ። ወቀሳውንም እንኳን ሌላ ሰው ያየው እኔም ከውሥጡ ያገኘሁለት ነገር የለም ። ይህ ሁሉ የሚረባ ነገር አይደለምና ላንተም የሚሻልህ ለእጅህ እምለህ በቃልህ መዋቀስ ነው ። እንግዲህ መጨረሻ ቃሌ ነውና ምላሹ ለነገ ይምጣልኝ ። ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ ም ።

ራስ ጉግሣ ወሌም የግርማዊት ንግሥት የስልክ ቃል ብዙ ጊዜ ከተላከባቸው በኋላ ዕርቁን እሽ እታረቃለሁ ፤ ነገር ግን የዕርቅ ነገር በሽማግሌ ነው እንጂ በስልክ አያልቅምና ሰው ሰድጄ በመሀላ ነገሩ ቢጨረስ መልካም ነው።ንጉሥ ግን የዕርቁ ነገር ሳይጨረስ ጦር እያዘዙ ይሰዳሉ ብለው በየካቲት ፳፪ ቀን በስልክ ቢያሳልፉ ግርማዊት ንግሥት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን መለሱ ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ ።

በየካቲት በ፳፪ ቀን የላክኸው የስልክ ቃል ደረሰልኝ ። የተቈረጠ ቃል ስልክብህ አንተ ያልተቈረጠ ምላሽ እየላክህ ምነው እኔንስ ታስቸግረኛለህ ። ጦሩንስ እኔ ሳልሰማው ንጉሥ ብቻ የሰደደው ይመስልሃልን እኔንስ ለምን ከሱ አሳብ የተለሁ ታስመስለኛለህ ። ጦሩንም የላክነው ለራያ ጋላ ነበረ ፤ ነገር ግን በንዛ እጅህ ወዳንተው ልታደርገው ነው።አሁንም የዕርቁ ነገር እስቲቈረጥ ይኸው ጦሩን ደላንታ ላይ ስፈር ነውና ያልነው እንዳይጋጭብህ ሰውህ ካገርህ ድምበር እንዳያልፍ አድርግ ። ደግሞ የርቅ ነገር በስልክ አያልቅም ላልከው ይህን ያህል ለዕርቅ የሚያስቸግር ምን ያህል የጠነከረ ጠብ ኑሮህ ነው ። ለመሀላውስ እንኳን የምታምነው ሽማግሌ አሽከርህ ፊታውራሪ ወልደ ሚክኤል እዚህ እያለ የኔውስ ቃል ብቻ ይበቃህ አልነበረምን ። አሁንም እንግዲህ ወዲህ ገና ከዚህ ሰውልከን ከዚያ ተመልሶ መጥቶ እንደዚህ እስቲመላለስ ድረስ የዘመተውስ ሰው አገሩስ ይጐዳ የለምን ።

አሁንም ከፈቃድ አልወጣም ዕርቁንም አልጠላም የምትለው እውነትህ እንደሆነ ላንተ የሚሻልህ ለእጅቱ

ሕምለህ በቃልህ መዋቀስ ነው ። ለን ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤልም እስከ መጋቢት ፪ ቀን ድረስ ምላሹን ላከባቸውና መታመናችንን አይተውልህ ሲመጡ እኛም ከነሱ ጋራ ዋና ሰው ሰደንልህ ገሥላሥህ መጥተህ ብትስማማ ነው የሚሻለው ብተረፈ ግን እንደዚህ እየተጨነቅሁ በየጊዜው ስልክብህ እንግዴህ እንደዚህ እንዳለፈው ያለ ያልተቈረጠ ነገር አትላክብኝ ፤ እኔም ከባቴ አልጋ ያንተ ነገር አይብስብኝም ። የካቲት ፴ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ግርማዊት ንግሥትም ብዙ የምክርና የተግሣፅ ቃል ወደ ራስ ጉግሣ ወሌ እየላኩ፤ራስ ጉግሣ ወሌ አኅባቸውን የማይለውጡና ቍርጥ የሆነ ምላሽ የማይሰጡ ስለሆነ ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ፤ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ላኩባቸው ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ

ደኅው በግርማዊት ንግሥት በኩል ፱ጊዜም ለኔ የመጣውን የወቀሳ ወረቀት እየሁት ምላሹንም ከንግሥት ጋራ ተማክረን መልሸልዎ ነበር ። ከወደርስዎ የሚመጣው ምላሽ ግን የልብ ያልሆነ ቍርጥ የማያስታውቅ ቃል ሆነ መወቃቀስስ ቢሆን ምን የሚያስተፋፍር ትልቅ ጠብ ኑሮን ነው ለእጅዎ እስከመስጋት ያደረስዎ። አባቶቻችንስ ያቈዩን ፍቅር ነው እንጂ ምን ጠብ አለን። አሁንም ከዚህ ቀደም ያለውን ጠብ እርስዎ ከበረዱት ለእጅዎ ክፉ አሳብ የለኝምና ይመኑኝ። ወደ የጁስ ወጥተው ያገኝዎን ችግር ሁሉ ከዚህ ወቀሳ ያገቡት የጁን መፈለግዎን እኛ ሳናስበው እስዎ አስበው ይለውጡልኝ ብለው እንደላኩብኝ ልብዎ ያውቀዋል።

ዘመቻውስ ቢሆን ለመንግሥቱ ሲባል የተደከመውን ድካም ባይሆን ሠረታዬን ቍጠሩልኝ ይባል ነበር እንጂ እንዴት ድካምዎን ለኔ መውቀሻ ያደርጉታል ፤ አሁንም የተናገሩት ቃል ኃፍረት መስሎዎ እርስዎም እየገፉበት ጠሩም እየገፋትጋጩና ደም የፈሰሰ አደሆነ ከዚህ ቀደም ቀላል የሆነው ጠብ እጅግ ትልቅ ሁኖ ከባትዎ ጀምሮ እስከስዎ ድረስ ከመንግሥታችን ጋራ ጠብ ያልነበሩትን ዛሬ በጠብ እንዳንራራቅ የክርስቲያን ደም በከንቱ እዳይፈስ ስለ ክርስቲያን አምላክ፤ ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ብለው ይምጡና እንገላለጠው።ይህንኑም ቃል በየካቲት፴ቀን ላለፈልዎ ቃልና ለዚህም አሁን ለላኩብዎ ቍርጥ ምላሽ ሲልኩብን ይህኑ ቃል በማኅተምም ቢሆን እልክብዎታለሁ። የካቲት ፴ቀን፲፱፻፳፪ ዓ ም።)

ለዚህም ምላሽ ንጉሥ የላኩብኝንም የቍጥር ቃል አየሁት ። እሺ ዕርቁን ዕታረቃለሁ ብለው ነገሩ ቈይቶ ጠሩ የሚጐዳበትን ቢልኩና ጠሩም ግዛታቸው ወዳልሆነው አይለፍብኝ ስላሉ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ቃል አለፈላቸው ።

ንጉሥ ተፈሪ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ።

ይድረስ ከራስ ጉግሣ ወሌ።

የላኩትም የስልክ ቃል ደረሰልኝ ለዕርቁም ነገር ላሳለፉት ሕኛ ባጭሩ እንዲያልቅ ስንል ሠራዊት ዘምቶ ነገሩ እየተጓተተ እንዳይቈይ እውነቱን እንዲያውቁት አሽከሮችዎ አሳምነውልዎ እንዲመጡ እንልክብዋለን እስዎ ግን ለዚህ ምላሽ ሳይመልሱልን ሌላ_የማቈያ ቃል ብቻ ይልኩብናል እንዲህማ እየሆነ ሰዎችን ከተጉላላብን እንደጦርነት ያለ ጉዳት ሊያገኘው አይደለምን ።

አሁንም እነፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል አሳምነውልኝ ይምጡ ፥ ወይም የነሱን ማሰመን አልፈልግም ማለት የዚህን ቍርጥ ብቻ ይላኩብን ።

ስለ ጠሩም ወደ ደላንታ አይምጣብን ላሉት ድንገተኛው አሳብዎ ጠሩን ከዚያ ላይ እንዲቈይ አደረገው እንጂ ይህ ጦር የታዘዘበትን ቀድሞውን ለርስዎ የተነሣ አለመሆኑን ከዚህም ቀድሞ አስታውቀንዎ ነበር። ለደላንታውም ሰፈርና አገርዎ አልገባ ምን የሚያገናኛችሁ ሁኖ ላኩት። መጋቢት ፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ።

ከዚህ በላይም የተጻፈው የግርማዊ ንጉሥ የስልክ ቃል ከደረሰላቸው በኋላ ። ራስ ጉግሣ ወሌም ቂም ላይዙብኝ ። እንዳሁን ቀድሞ ሳድር በዚህ ነገር ከኔ ጋራ የተነሣውን ሰውና አገሩንም ሊምሩልኝ ንግሥትም ንጉሥም ይማሉልኝና ዕታረቃለሁ የሚል ቃል አሳለፉ ።

ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥም ያገር ሹም ሽር ነገር ከመሀላው ውስጥ አይገባም እንጂ እጅህን ሳንይዝ በምትገዛው አገርና በምታዘው ሰው ላይ በዚህ ነገር ቂም ላንይዝ እንምላለን ። ነገር ግን እዚህ እኛ ሳንተ አምነህ በላከሃቸው አሽከሮች ፊት ስንምል ከኛምወገን አንተ ስትምል የሚሰሙ እፈ ንጉሥ አረጋይን ባላባራስ ተክለ ማርቆስን የኔን ጸሐፌ ገብረ ማርያምን በአውሮፕላን ልንሰዳቸው ነውና ለአውሮፕላኑ ማረፊያ ደብረ ታቦር ጃን ሜዳ የሚባለውን ሥፍራ አስደልድለህ እንድትቈይ ይሁን ።

የምትምልበትም ቃል ከዚህ ቀጥሎ እንዳለው ነው ።

፩ኛ፤ከእንግዲህ ወዲህ ደም የሚያፋስስና መንግሥት የሚበድል የጥፋት ሥራ ላትሠራ ።

፪ተኛ፤ በኔም በንጉሡም በቂም የተንኰልና የልግም ሥራ ላትሠራ ።

፫ተኛ፤አዲስ አበባ ለመምጣት ተነሣ ባልንህም ቀን ተነሥተህ ልትመጣ ።

በዚህም በሶስቱ ነገር ከማልክ በኋላ ለኛም እዚህም ላሉት አሽከሮችህ በስልክ እንድታስታውቀን ። መጋቢት ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ከዚህ በኋላ ራስ ጉግሣ ወሌ ለተጻፈላቸው የዕርቅ ቃል ምላሽ ደብረታቦር ላይ ያለው ጃንሜዳ የሚባለው ሥፍራ እጅግ ተበላሽቷልና ሥራው ባንድ ወርም አያልቅም ስለዚህ እነ እፈንጉሥ አረጋይ ባግሥጋሴ ቢመጡ ይሻላል ። ለነሱም እንዲቀርባቸው ወደ ጋይንት ሆኜ እጠብቃቸዋለሁ የሚል ቃል በመጋቢት ፲፪ ቀን አሳለፉ ።

ግርማዊት ንግሥትም እነ እፈንጉሥ አረጋይን በአውሮፕላን እንልካለን ማለታችን የርቁ ነገር በቶሎ እንዲጨረስ ብለን ነበር እንጂ ለሌላ አልነበረም ።

ነገር ግን አንተ ወደ ጋይንት ስትመጣ እዚያ ያለው ዘማቹ ሌላ ነገር እንዳይመስለውና እንዳይጋጭ አንተ እዚያው ደብረ

ታቦር ቈይተህ አይሮፕላኑ መጥቶ ሳያርፍ የዕርቁን ቃል ወረቀት ጥሎልህ ይመለሳል ።

አንተን የሚያስምሉ ሰዎች ግን ከዚያው ደጃዝማች ሙሉጌታ ዘንድ ካሉት መኳንንቶች እናዛለን የሚል ቃል መጋቢት ፲፫ ቀን አለፈላቸው ።

ከዚህ በኋላ ለዚህ ምንም ምላሽ ሳይሰጡ ፡ አዋጅ አስነግረው ከደብረ ታቦር ተነሥተው ደጃዝማች ሙሉጌታ ወደሰፈሩበት በግሥጋሴ ለመሄድ መነሣታቸውን ደጃዝማች ሙሉጌታ ቢሰሙ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ላኩባቸው።

ይድረስ ከክቡር ራስ ጉግሣ ወሌ ።

መጋቢት ፲፫ ቀን ራስ ጉግሣ ታመኑልኝና ልግባ ብሎ የርቅ ቃል ልኮብናልና ፡ እናንተም ወደቤገምድር እንዳትወርዱ ራስ ጉግሣም ከደብረ ታቦር እንዳይወጣ ልከንበታል የሚል የግርማዊት ንግሥትና የግርማዊ ንጉሥ የስልክ ቃል መጥቶልን ነበር።አሁን ግን እኛ በታዘዝነው ቃል ቁመን ወደርስዎ አገር ሳንገባ እርስዎ ወደኛ የጓዙ ማለትን ሰማን ። ዕርቁን አልተውት እንደሆን አሁን ካሉበት አገር ሳይጓዙ የርቅዎን ንግግር ይጨርሱ።ከዚያ አልፈው ወደዚህ የተጓዙ እንደሆነ ግን እነዚህ የታዘዙት አይሮፕላኖች የሰፈሩን መቃረብ አይተው ጠብ መደረጉ ነው ብለው በምባውን መጣላቸው አይቀርምና በነዚህ በወደቁት በምበዎች ክርስቲያኖች ወንድሞቻችን ያለቁ እንደሆነ ደሙ በርስዎ እንዳይሆን ዛሬ ከሰፈሩበት በታ እንዳያልፉ በኔም በመንግሥቱም ስም ሁኜ በማክበር አስታውቅዎታለሁ ።

ደኸንንም ወረቀት ያያችሁት መኳንንቶች ሁሉ ምስክሬ ናችሁ መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ተጻፈ ።

ከራስ ጉግሣ ወሌም የጦር ፊታውራሪዎች ሁነው የሄዱ ደጃች ነጋሽ ፡ ደጃች ገብሬ፡ ደጃች ኃይሉ ፡ ፊታውራሪ አደሉ ነበሩና ። ራስ ጉግሣ በስተ ኋላ ሁነው የምንዋጋው ጨጨሆ ላይ ነውና ጨጨሆን እንዳታልፉ ፡ በቀኝም በግራም በስተኋላም ያሉትን ። ዘመዶቻችንና ወዳጆቻችንን ሁሉ እነቃቁ አበረታቱ እያሉ እየተላላኩ ደረሱላቸው ። በመጋቢት ፳ ቀን ከደጃዝማች ሙሉ ጌታ ሰፈር የሁለት ሰዓት መንገድ ያህል ቀርበው ሰፍረው ነበር ።

ደጃዝማች ሙሉ ጌታም የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ብለው ለጦርነቱ ሳይቸኩሉ ታግሠው የዕርቅ ቃል ቢልኩባቸው እምቢ ብለው እንደገና በመጋቢት ፳፪ ቀን በማለዳ ተሰልፈው ተነሥተው ጉዞ ሲጀምሩ ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ለመሰለል የላኩት አውሮፕላን ተሰልፈው መምጣታቸውን አይቶ ከነገራቸው በኋላ በነጋሪትና በመለከት አሰልፈው መከት ሁነው ተጋጥመው ፩ ሰዓት ያህል እንደተዋጉ ራስ ጉግሣ ወሌ ድል ሁነው በጦርነቱ ውሥጥ ሞተው ተገኙ ።

ግርማዊት ንግሥትና ግርማዊ ንጉሥ በራስ ጉግሣ ወሌ ምክንያት የክርስቲያን ደም እንዳይፈስ ነገሩ ሁሉ በዕርቅ እንዲጨረስ በብዙ ደክመውበት ነበረ ። ራስ ጉግሣ ግን የዕርቁን ነገር እምቢ ብለው የክርስቲያንን ደም በከንቱ ስላፈሰሱ ፍዳቸው በራሳቸው ላይ ሆነ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፭ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ነህ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፸ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፸ መሐ
የማልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፸ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፷ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፷ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የእንቆቅልሽ ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፱ ብርተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፮ ብር
አቡጀዲ መንጸር	፩ ኮረጃ	፻፸ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፱ ብር
ባለ ድመት		፻፶ ብር
ባለ አህያ		፻፶ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፶፫ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪክ		፻፳፪ ብር
ጃፓን		፻፹፯ ብር
ሱካር	፩ ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ
ባአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፫ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፭ ከ፫ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ	፶

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂሳኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዳቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፌኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊኖ ባርኔጣ መጥቶታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በዋጋውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።
ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።
የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በያይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።
የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባሉ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጅዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በዳግማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
6me ANNÉE № 16

ሐሙስ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ ም።
JEUDI 17 AVRIL 1950

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
I Hayle Sellassé Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጠውንም የሚፈልጉት ወደ ጸረክተሩ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዘት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት መከፈት በጅጅጋ ከተማ ።

መጋቢት ፲፫ ቀን የልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት በጅጅጋ ከተማ የሚከፈት ስለሆነ በዓሉን ለማክበር በከተማው ነዋሪ የሆኑ ብዙ የውጪ አገር ሰዎችና ያገራችን መኳንንት ወደ ትምህርት ቤቱ ተጠርተው ነበር ። ልዑል ራስ መኰንን ያረፉት የዛሬ ፵፬ ዓመት በ፲፰፻፺፰ ዓ ም መጋቢት ፲፫ ቀን ነበርና ለመታሰቢያቸው የተሰራው ትምህርት ቤት በዚያው ቀን የሚመረቅ ስለሆነ በቀኑ መታበበር ሰው ሁሉ እያደነቀ መታሰቢያቸውን ያጋንን ነበር ። የትምህርት ቤቱም በኢት-ዮጵያ ባንዴራ አጊጦ አምሮ ይታይ ነበር ። በ፱ ሰዓት ተኩል በሰልፍ ትምህርት የሠለጠኑት ወታያሮች መጥተው ግራና ቀኝ ተሰልፈው ይጠባበቁ ጀመር ። ልክ ፲ ሰዓት ሲሆን ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚከኤል የተጠሩትን መኳንንቶች አስከትለው በደረሱ ጊዜ የሠለጠኑት ወታደሮች በሥርዓት ቆመው የተለየ ሰላምታቸቸውን ሰጥተው ተቀበሉ ቀጥሎም በጅጅጋ ከተማ የተቀመጡት የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ካፒቴን ኤች ኤ ሎንግና ሌሎቹም የተጠሩት እንግዶች ሲገቡ እንዲሁ ሰላምታ ሰጥተው አሳለፉዋቸው ። ከዚህም በኋላ ክቡር ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተሚከኤል የተጠሩትም እንግዶች ተማሪዎቹን በየክፍላቸው እየዞሩ ያዩ ጀመር ። ለእንግዳ መቀ-በያ ወደ ተሰናዳውም ቤት ገብተው በተቀመጡ ጊዜ ክቡር ፊተውራሪ ታፈሰ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡራን ሆይ ።

በልዑል ራስ መኰንን ስም ተሰይሞ በጅጅጋ ከተማ ላይ ለሚቆመው ትምህርት ቤት የደስታችን ተካፋይ በመሆን የተከ-ፈተበትን ቀን በዓል ለማክበር ጥሪአችንን ተቀብላችሁ ስለመጣ-ችሁልን አመሠግናችኋለሁ ።

ጌታችን ልዑል ራስ መኰንን እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ዘመን ድረስ በእውነተኛ ታማኝነት መንግሥታቸውን ደስ ለማሰኘትና የሀገራቸውን ነፃነት ለማስከበር ሰውነታቸውን ለ-መሥዋዕትነት አዘጋጅተውት እንደነበሩ ብዙዎቹ የማይረሱት ሥራዎቻቸው ይመሰክራሉ ።

ይህ አሁን ያለንበት አገርና አውራጃው ሁሉ ፫፻፲፱ ዓመት ያህል የክርስቲያን ዘር የተመተረበት የአረመኔነት ሥራ የሠለ-ጠነበትን ስፍራ ሆኖ ይኖር ነበር። ይኸውም ኢትዮጵያ በእስላም ሃይማኖት ምክንያት የተጐዳችበት ዘመን ተብሎ በታሪክ የሚነገረው ነው ። ኋላ ግን ኢትዮጵያ ወደ ጥንታዊ አንድነትዋ እንድተመለስ የእግዚአብሔር ፈቃዱ በሆነ ጊዜ ፲፰፻፸፱ ዓ ም ስማቸው የማይረሳው ታላቁ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ከአረመኔ እየተዋጉ የምስራቅ ኢትዮጵያን አስለቅቀው ለታመኑት ወን-ድማቸው ለልዑል ራስ መኰንን አደራ ከሰጧቸው በኋላ በትጋታ ቸውና በጀግንነታቸው የምስራቅ ኢትዮጵያን እንደዚህ እንደ-ምናየት አድርገው አድሰው የሕዝቡን ክብርትና ያገራቸውን ወሰን እያሰፉ አቆዩ። የሁከትና የፍርሃት መፍለቂያ በነበረውም ስፍራ እነሆ ዛሬ ሰላምና ጸጥታ ሠልጥኖባታል ። ተማሪ ቤትም ቆሞበት ያገሩ ልጆች ትምህርትን በናፍቆት ሲፈልጉ ይታያሉ።

ልዑል ራስ መኰንን ስለ ሀገራቸው ነፃነት በሐረርና በአድዋ በዓረብ አገር ያደረጉትን ውለታ ሁሉ ባሁኑ ጊዜያችን ተናግረን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ አይቻልምና እንዲሁ ጀምረን መተዋችን ነው ።

ይህም ሳይቀር እግዚአብሔር በረቂቅ ጥበቡ በወሰነው በፍጥረታዊ ሕግ የብርሃናችን የግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ አባት መገኛ ስለሆኑልን ስማቸውን እየመላለስን እናመሰግነዋለን ።

የአገልግሎት ዘመናቸውና የደግነት ዕድሚያቸውም በተፈጸመ ጊዜ በ፲፰፻፺፫ ዓ ም ከሚያስቡላት አገራቸው ተለያይተው ወደማይቀረው ርስታቸው ሄዱ ። ይህም ከሆነ ዛሬ ፴፱ኛው ዓመት ተፈጽሞ ፵፫ኛው መጀመሩ ነው ። በ፳፫ኛው ዘመን ደጉ ንጉሣችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ለመልከሙ አባታቸው መታሰቢያ አድርገው ይህን ተማሪ ቤት በማቆማቸው የጀግናውን የልዑል ራስ መኰንን ስም ዘወትር የምናስብበት ምክንያት ሰጡን ይህም ዕለት ጊዜ አጋጥሞት ልዑል ራስ መኰንን ያረፉበት ቀን ስለሆነ መታሰቢያነቱ ከፍ እንዳለ ይኖራል።

ይህንንም የሥልጣኔ ትምህርት ቤት በድሬዳዋ ከተማ ላይ ለመሥራት ከግርማዊ ንጉሥ ዘንድ የመታዘዝን ክብር ስላገኘሁ ለደስታዬ ወሰን የለውም ። ሥራውም በ፲፰ ቀን ውሥጥ ተዘጋጅቶ አሁን ለትምህርት ፵፯ ሕጻናት ተቀብለናል ።

የዚህን ትምህርት ቤት ሥራ ለማስኬድ የታዘዘው ሹም አቶ መርስዔ ኀዘን በትጋቱና በሥራው ደስ ስላሰኘኝ አመሠግነዋለሁ ። የነዚህም ሕጻናት አባቶች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤቱ በትጋት በመላካቸው እውቀት ወዳጆች ሆነው መልካም አርአያቸውን አሳይተዋልና ምሥጋና ይገባቸዋል ።

አሁንም እውቀትን ፍለጋ ለተሰበሰባችሁት ልጆች የምነግራችሁ ትምህርትን መፈጸሙ እንጂ መጀመሩ ብቻ አይጠቅምምና ትምህርት የመረረችውን ያህል ትጣፍጣለች የተባለውን እያሰባችሁ እስከ መጨረሻው በርትታችሁ እንድትማሩ ፡ ለትምህርት ቤቱ ሹምና ለመምህሮቻችሁም የተወደዳችሁ ታዛገሮች እንድትሆኑ እለምናችኋለሁ ።

ክቡራን ሆይ ። በየቦታው የትምህርት ቤት ማቆምና የሕዝብ ጤና መጠበቂያ ሆፒታል መክፈት ለግርማዊነታቸው እንግዳ ነገር አይደለም ። አሁንም በዚሁ በድሬዳዋ የሕዝቡ ጤና እንዲጠበቅ ሆፒታል ሊከፈት እንደ ተዘጋጀ ታዩታላችሁ። ሥራውም እስከ ስምንት ቀን ድረስ ይጀምራል ።

ክቡር የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ሆይ ። ዛሬ የዚህ ደስታችን ተካፋይ በመሆንዎ በግርማዊነታቸውና በራሴ ስም ሆኜ የማቀርብልዎትን የተለየ ምሥጋናዩን እንዲቀበሉኝ እለምንዎታለሁ ።

ወሰን የሌለው አምላክ ለግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ረጅም ዕድሜ ከሰላም ጋራ ሰጥቶአን በጎ ሐሳባቸውን ያስፈጽማቸው ዘንድ እለምናለሁ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ። ብለው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ እያስተጋባ ተጨበጨበ

ቀጥሎም የትምህርት ቤቱ ሹም አቶ መርስዔ ኀዘን የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ።

ክቡር ሆይ ።

ክቡራን ሆይ ።

አዲሱ የትምህርት ቤት በልዑል ራስ መኰንን ስም ተሰይሞ በሚመሠረትበት መታሰቢያው በማይረሳ በዛሬ ቀን ከመካከላችሁ ቆሜ ይህችን ቃል እናገር ዘንድ ክብር በማግኘቴ ለደስታዬ ወሰን የለውም ።

ትምሕርት በአእምሮ ጠባይ ውስጥ ተሠውራ ያለችውን የእውቀት ብርሃን የምትገልጽበት የአእምሮ መክፈቻ ስለሆነች የሀገርን ጥቅም ለማስፋት የሕዝቡን አንድነት ለማጽናት በመጀመሪያ የሚያስፈልገው ዋና መሣሪያ ትምህርት እንደሆነ እያደር ተገልጿዋል ።

ይህንንም ሁሉ መርምረው የተረዱት ብልሁ ጌታችን ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ሕዝባቸውን በሥልጣኔ ለማደስ የሁልጊዜ አሳባቸው ስለሆነ በዚህም ከተማ ይህን የሥልጣኔ ትምህርት ቤት በመልካሙ አባታቸው በልዑል ራስ መኰንን ስም ሰይመው አቆሙት ። ለዚሁም ሥራ ግርማዊነትዎ በታማኝነት ስለላኩኝ ለደስታዬ ወሰን የለውም ።

ክቡር ሆይ ። ትምህርት የሚፈልጉ ፵፯ ሕጻናት ተሰብስበውልን ሥራውን ጀምረናል ። አሁን በመጀመሪያው ጊዜ የተማሪዎቹ ቍጥር ይህን ያህል ከሆነ ወደፊት ሥራችን እየሰፋ እንዲሄድ የተረገጠ ተስፋ ለማኖር እንችላለን ።

እናንተም በዚህ የቆማችሁት የልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ። ክቡር ፊተውራሪ ታፈሰ የሰጡችሁን ምክርና ምሳሌ እያሰባችሁ በትምህርታችሁ ትጉሆች በሥራችሁ ንቁዎች እንድትሆኑ እለምናችኋለሁ ።

ክቡር ሆይ ድካማችንን ወደ ፍሬ ለማድረስ የክቡርነትዎን እርዳታ ዋና ደጋፊዬ መሆኑን እተማመናለሁ እግዚአብሔር ለደጉ አሳቢያችን ለግርማዊ ንጉሥ ረጅም የጤና ዕድሜ ይስጥልን ኢትዮጵያ በነፃነትዋ እንደከበረች ትኑር ። ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ።

ቀጥሎም አቶ ብሩ ሀብተ ዮሐንስ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ።

ጌታ ሐዋርያትን በማቴዎስ ወንጌል በ፲ ምዕራፍ ከ፭ እስከ ፰ ቁጥር የአሕዛብን መንገድ አትሂዱ ከዚያ የሚበልጥ ወደ ጠፉ በጎች ወደ እስራኤል ቤት ሂዱ እንጂ በሄዳችሁም ጊዜ አስተምሩ እያላችሁ መንግሥተ ሰማያት ቀረበች ብሎ እንዳዘዛቸው ሁሉ እናንተንም ግርማዊ ንጉሥ ጌታችን በድሬዳዋ አውራጃ ከሁን ቀደም የትምሕርት ቤት አለመቆሙን አውቀው በባታቸው በልዑል ራስ መኰንን ስም እናንተን እንደ ሐዋርያት ሂዳችሁ የትምሕርት ቤት ከፍታችሁ አስተምሩ ብለው ስላዘዟችሁ ለብርሃን መሪ ለሆኑ ጌታችን እድሜ ይስጥልን።እናንተንም ይህን የጀመራችሁትን ዘርዕ መጀመሪያ ቡቃያውን ሁለተኛ አበባውን ሶስተኛ ፍሬውን አይታችሁ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል በ፲፮ ምዕራፍ ከ፲፰ እስከ፳ቁጥር ቅዱስ ጴጥሮስን የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጣለሁ ብሎ ሥልጣነ ክህነትን እንደሰጠው ለናንተም የድካማችሁን ዋጋ ከጌታችን እንድታገኙ ያድርጋችሁ እያልን እንመኛለን ።

ክቡር ጌታችንን ፊታውራሪ ታፈሰን ለዚህ ሁሉ ሃሳብ መሪ ስለሆኑ ይህን ጥልቅ የሆነ ሐሳባቸውን በደስታ ያስፈጽምልን እያልን እንመኛለን።ቅዱስ ጳውሎስ ወፈጽፋደስ አጽሕቅ ለብሔረ ሮሜ እንዳለ እኛም ለዚች ላለንበት ሀገር ማስብ ግዲታችን ነውና ባንድነት ሆነን በትሕትና እየተረዳዳን ይህን በውስጧ የሚዘራውን ዘር አፍርቶ ፍሬዋን ለማየት እንዲያበቃን ስል እለምናለሁ ይህንም ከጠባብ እውቀቴ ያገኘሁትን ምስጋና ደፍሬ በናንተ ፊት ስለተናገርኩ ይቅርታ እለምናለሁ። ብለው ሲጨርሱ ተጨበጨበ ።

ከዚህ በኋላ የሻይ ግብዣ ሆነና በሻምፓኝ ጊዜ የእንግሊዝ መንግሥት ቆንስል ክፒቴንኤች ኢ ሉንግ ደስ የሚያሰኝ ንግግር ተናግረው መረቁ ።

ከዚህ በኋላ ሰው ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነሣ የልበ ሙሉውን ጀግና የልዑል ራስ መኰንንን ስም እያነሣ ሲመርቅና መታሰቢያቸውን ሲያከብር ነበር ። የትምህርት ቤቱ በዓል በእንደዚህ ያለ አኳኋን ተፈጸመ። የብርሃንና ሰላም ተላላኪ ።

ስለ ቃዲነት ።

ቃዲ ማለት ዳኛ ወይም ፈራጅ ማለት ነው ፈቂህ ቢል በእስላም ሃይማኖት የተጻፈውን ሕግ ይዞ በመንፈሳዊ ነገር እንደ ተጻፈው የሚፈርድ ነው ። ቃዲ ግን ማንኛውም ዳኛ ቃዲ ይባላል ። ለዚህም ለቃዲነት ወይም ለፈቂህነት የሚሾመው ሹም የተማረና ግብረ ገብ መሆኑን አይቶ ሕዝብ ይመርጠዋል ። በዚህም በመንፈሳዊ ሹመት የሚሾም ሰው ሁሉ በአክሒዳና በኑሮው መጽሐፍ እንደዘዘው ሊኖር ይገባዋል ። ስለምን መዝመዝ የመንፈሳዊ ዳኛ ነውና ለሕዝቡ ሕብነት ሁኖ ለማስተማር ያለ ነውር ሊኖር ይገባዋል ። ፪ኛም በሕዝብ ላይ ፈራጅ ነውና እሱ በሚሠራው ኃጢአት በሰው ላይ ሊፈርድ የማይገባው ስለሆነ ነው ።

በዳኝነት ረገድ ፪ሰዎች አይለዩትም እነዚህም ሰዎች የተማሩ ግብረ ገቦች የሆኑ የመጻሕፍትን ምሥጢር በአረቢ ቋንቋ የመረመሩ ናቸው ። ጸሐፊዎችም እንደዚሁ ያሉ ሊሆኑ ያስፈልጋል።ዋናው ሹም ፈቂው በማንኛውም ነገር ነውር የሌለበት ሊሆን ይገባዋል። ብለናልና ይልቁንም በኃጢአት መከሰስ ያልበዛበት ቢከሰስም ያልተረታ ፤ ስካር የሌለበት ፤ አታላይ ያልሆነ ፤ በሰበብ ባስባብ እያለ የሰውን ገንዘብ በከንቱ የማይወስድ ፤ የማያጻላ ራትዕ የሆነ ሊሾም ይገባል ። አባት እናት የሌላቸው ልጆች አካለመጠን እስኪያደርሱ ድረስ ገንዘባቸውን የሚጠብቅላቸው እሱ ነውና ይልቁንም በገንዘብ ነገር የታመነ ሊሆን ይገባዋል ።

ደግሞ በሃይማኖት ነገር ሰው ሁሉ ፍጹም ነጻነት ኋለው። የጋብቻ ሥርዓት ኒካ ይባላል ። ይህም ኒካ የሃይማኖት ሥርዓት ነውና ሰው ሁሉ በኒካ ነገር ነጻ ነው። ማለት ሁለቱ የሚጋቡት ባልና ሚስቱ ዘመዶቻቸው ከተስማሙና ጋብቻ የሚከለክል ነገር በመሐከላቸው ከሌለበት አወደዱት ዘንድ ሂደው ኒካ ማድረግ ይችላሉ ።

ነገር ግን ከዚህ በላይ እንደተጻፈው በመጽሐፍ ሕግ ያልጸና ፤ የተማረና ግብረ ገብ ያልሆነ አንድ አንድ ቃዲ ወይም ፈቂህ ነኝ እያለ እግዚአብሔርን ከለመፍራቱና ራሱን ብቻ ከመውደዱ የተነሳ ከለኔ በቀር እሌላ ዘንድ ለምን ኒካ አደረጋችሁ እያለ ሰዎችን በገንዘብ ይቀጣል ። መንግሥት እንኳ ደምብ ቢያወጣ በመላ መንግሥቱና ሕዝቡ ላይ ያወጣል። እንጂ እንደዚህ ለይቶ በ፩ወገን በእስላሞች ብቻ የተለየ ደምብ አያወጣም። ስለዚህ መንግሥት ያልፈቀደለትን ፤ በመጽሐፋችንም የሌለውን የኒካ ሞኖፖል እኔው ብቻ ልያዘው ብሎ ሕዝብን ማስጨነቁ ሰላማዊ የነበረውን የእስላምነትን ሕግ ሽሮ ለራሱ ብቻ ከረጢት መስፋቱን በፍጹም ያስረዳል ።

ሲሆን በመጽሐፋችን የታዘዘውን ሕግ ሁሉ አክብሮ ሊጠብቅ ፤ ታጋሽ ፤ ቸር ፤ ርህሩህ ሊሆን ይገባው ነበር ። በዚህም ሁሉ ፍጹም ለመሆን ባይችል ከምሉ በከፍሉ ከብዙ በጥቂቱ በዚህ ዡርናል ጠቅሼን የጻፍናቸውን እንኳ ዘወር ብሎ የማያይ በመሆኑ እጅግ ያሳዝናል ።

ሕጉንም ካላከበረና ካልጠበቀ እንደዚህም ያለ የተከለከለ ነገር ከሠራ ምንም እንኳ ለጊዜው ሕዝብ ቢመርጠው ሕጉ ይሽረዋል ። ስንኳንስ ሹም ሁኖ በሕዝብ ላይ ሊፈርድ እንደ ሕጋችን የሆነ እንደሆነ ሌላ ሹም እንኳ ሲመረጥ እሱ ድምጥ ሊሰጥ አይችልም ይላል ።

ይኸንንም ልጽፍ ያሳሰበኝ ኤሹራ የሚባል ጋዜጣ ስመለከት ያገኘሁት ቃል አነሣስቶኝ ነው ። ይኸውም ጋዜጣ በምሥራቅ አገር ሁሉ የበደልንና የጥቃትን ነገር የሚመረምር ነው ። በሺ፱፻፵ ዓ በ፲፱ ማርስ በ፪፻፳፯ ኑሚሮ እንዲህ ይላል ። የየመን ንጉሥ የግርማዊ ኢማሞ ያህያ ልጅ አሚር አህመድ ሰይፉል እስላም የሚባል ዘራኒቅ የሚባሉትን ሽፍቶች ወግቶ ድል ነሥቶ ሲመለስ ሁዲይዳ በምትባል ከተማ ገብቶ ለሕዝቡ እንዲህ የሚል ድስኩር ተናገረ (ይኸች አገር አገራችሁ አገራችን ናት የሚያስፈልጋትን ግዳጅ ሁሉ ልንፈጽምለት ይገባታል ። እናንተም የሚጉድላትን ነገር ልታስታውቁን ግድ አለባችሁ ። ማንኛውም ሰው በሀገር ውሥጥ ፩ጉድለት ነገር አይቶ ባያስታውቀን አገሩን በደለ ራሱንም ። ስለዚህ ኃጢአቱ በራሱ ላይ ነው - እኛም በሀገር ውሥጥ ሕዝብ የሚበደልበትን ነገር ካላመለከታችሁን ልናውቀው አንችልምና ሁላችሁም በየአንድ አንዳችሁ ያያችሁትን ልታስታውቁን ይገባችኋል ።) ብሎ ተናገረ ይላል ። ስለዚህ እኛም የኢትዮጵያ ልጆች እስከሁን ድረስ ያየነውን የሰማነውን የምገልጽበት ቦታ አጥተን እርስ በርሳችን ስንናድድና ስንተማማ እንኖር ነበር ። አሁን ግን የምንገላለጽበት ብርሃንና ሰላም ሳወጡልን እድሜ ለግርማዊ ንጉሣችን እያልን የምንኖርበት ጊዜ ስለሆነ። እኔም በሀገር ውሥጥ ያየሁትን በደል በብርሃንና ሰላም ልገልጸው ግድ ሆነብኝ ።

ሐ ዓ አ ሸሪፍ አፈንዲ

ቤገምድር ቤተ ልሔም የምትባል አገር ስለ ኖረች ይህን ቅኔ አሰብሁ

መ ወ ድ ስ ።

ኃይለ ሥላሴ ዳዊት በጊዜ ፈቀድከ ።
ማየ ጸብዕ ትስተይ ለቤተ ልሔም እምዓዘቅታ ።
መላሕቅተ ሐራከ ወጽኡ እንዘ በፀጋሞሙ ወልታ ።
ወበየማኖሙ ኲያንው መንታ ።
ከመ ይትቃተሉ በውስቴታ ።
ወይመጥው ነፍሶሙ ቤዛ ንጉሦሙ በኤፍራታ ።
ኅዳጥሂ እንዘ የዓክል ልበ ዓማጽያን ማርታ ።
ለምንት እንበለ ዓቅም ትሰርሕ ለባሕቲታ ።
ማርያምሰ ልብከ ዘመንግሥተ ምኒልክ መክፈልታ ።
ዘኢህይድዋ ከልዓን ኀርየተ በትእግሥታ ።

ሥላሴ

ኃያላን እርዳኢሁ ።
ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ።
እመ በትእዛዙ ፈነወ ኃሣሢሆ ሀገረ ምኩናን ሲሳየ።
ሳምራዊት ንግሥተ ነገሥት ተረክበት በሀየ ።
እምዓዘቅተ ዓይን ትቀዳሀ ለእሉ ማየ እንብዓ ገጽ ጽሩየ።
ንጉሠ ነገሥት እስከ ጸለየ ።
እንዘ ይብል ሀብኒ እሰተይ እንብዓኪ ማየ ።
ወጸውዒ ምተኪ ኀቤየ ።

እለቃ ዳንኤል እ ደስታ ።

ሠናይ መዝሙር ፡ ወጥዑም ነገር ።

ጨዋታን በምሥጢር ከላፈቀቁት፡ ነገርን በእንደበት ቅላለበቀሉት ደስ እየሰኘምና ምሥጢር ከንበብ እያሰማማሁ ስለሀገሬ ጀግኖች ከዚህ በታች ጥቂት ግጥም እጽፋለሁ ።

እንቺም ተይ ይቅርብሽ ዋሾ አድረገሽ ።
ብጠየቁሽ ቁጥር ማዬ ማዬ እያልሽ ።
ሁለት ጀግኖች ታግለው አንድ ወደቀ አላችሁ ።
ጠያቂ ሲመጣ ማዬ ትላላችሁ ።
የራሱን ጥፋት ነው ሁሉም የሚያወራ ።
እለ እግዚአብሔር ፈቃድ በንቺም አልተሠራ ።
ምን ምስክር ያሻል ዓይን እያየው ።
ተላይ ያለ እንደጥል የታወቀ ነው ።
እንቺም ይህን ነገር ዳግመኛ አልሰማብሽ ።
ቀጭ እንደሌለው ሰው ተፈሪ እያለብሽ ።
እንደት የሚያርስ ሰው በተላከበት ።
ሙሉ ጌታ እንዲህ ነው የማይጉድልበት ።
ተከፋይ በዛበት ደኸ ሥራችን ።
እንዴት ሙሉ ጌታ መግጠም ያውቃልን ።
አታዳንቁጥይ ይኸንን ነገር ።
አባቱ በጠጣው ልጁ ቢሰክር ።
በራሴ አሳብ አለ እንድትመከር ።
ተማች ነው ከሉት ይፈራል አሽከር ።
መንገድ ሲጠፋ ነው ግጥም የሚያሳንስ ።
እንደርስበት ነበር በግር በፈረስ ።
የበሰለ ነገር ምን አስፈለጋችሁ ።
ሲስንቅማ ብሩ እያለ በጃችሁ ።
መሸሻ ያላቸው ሲሰለፉ አይታችሁ ።
በከንቱ አጉል በታ ወድቃችሁ ቀራችሁ ።
ይፈተናል መስሎን ሳይበዛ በጥቂት ።
በሙሉ ኑሯል ወይ ያሁን ጠርነት ።
ምክር የሚቀበል ራስ ባይኖራችሁ ።
ምር አረጋችሁት በጉግሥ እንስታችሁ ።
እንቺም ላገርሽ ሰው ምንም አልፈባሽው ።
በዚህ በትንሽ ቀን ሁሉን ገድ አስባስሽው ።
ተማሪስ ገባበት ባሁኑ ምክር ።
ይህን አይሠራውም ብቻ ወቃደር ።

ደመወዛቸውን ሲለኩ ሲያበጁ ።
እንዴት ተቋረጡ እንዴት ተፈጃጁ ።
የንጉሥን ትእዛዝ የሚፈጽም ሰው ።
ራሱንም ቢጥል ሙሉ ጌታ ነው ።
እንዳልሰለጠነ እኔም አላጣሁት ።
ባላገር ሁኜ ነው እንዳንዱን የጻፍሁት ።

እለቃ በዛብህ ።

በንጉሠ ነገሥት ተፈሪ የምሥራች ስለ መጣላቸው በደሴ ከተማ መምሕር ገብረ አምላክ ያሰበኩት ምስባክ ።

እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ ።
ወብዙኀ ይትሐሠይ በአድኅኖትከ ።
ፍትወተ ነፍሱ ወሀብኮ ።

የሉቃስ ወንጌል ። ፳፱ ክፍል ፲፩ ቁጥር እንዘ ይሰምዑ ዘንተ መሰለ ሎሙ (እስከ ሀበ ይብል)ወባሕቱ ለእልክቱሰ ጸላእትዩ እለ ኢይፈቅዱኒ ያንግሡኒ አምጽእዎሙ ዝየ ወርግዝዎሙ በቅድሜየ ። የሚለውን ካስነበቡ በኋላ እንገርጋሪ ርእዩ ዘገብረ እግዚአብሔር ለእለ ያፈቅርዎ ነግሡ በጽድቅ ወልብሱ ድርዓ ጽድቅ ወተአጽፉ ብርሃነ ጽድቅ ወተቀጸሉ ጌራ መድኃኒት በትፍሕት ። ከዚህ ቀጥሎ እስመ ለዓለም ብከ ንወግዖሙ ለኵሎሙ ፀርነ ይቤ ዳዊት በመንፈሰ ትንቢት በእንተ ዝንቱ ዕጸ መስቀል ዘተሰቅለ ዲቤሁ ቃለ አብ ወበስምከ ነኀሥሮሙ ለእለ ቆሙ ላዕሌነ ወከዕበ ይቤ ወወሀብኮሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምሥጡ እምገጸ ቅስት ወይድኃኑ ፍቁራኒከ ወንሕነኒ ንትፌሣሕ ዮም ወንግበር በዓለ በዛቲ ዕለት በእለ እግዚእነ ።

የደሴ መድኃኔ ዓለም አለቃ መምሕር ገብረ አምላክ ።

አ ዋ ጅ ።

ን ጉ ሥ ተ ፈ ሪ መ ኰ ን ን ።

ሳናስበው ፈጣሪችን በሕዝቡ አድሮ መርጦን እንዳናገረው አዋጅ የናትና የልጅ ቃል ኪዳናችን ሳይፈርስ በሱ ሕግና ትእዛዝ ሰው ሆኖ ከመሬት የሚቀር የለምና በጥቂት ቀን ሕመም ስለአረፉና ስለተቀዳደምን ምንም የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ማለፍ ለኔም ለመላ ኢትዮጵያ ኃዘናችን ቢሆን የሕዝቡ እረኛ ንጉሥ ሲሞት ንጉሥ መተካቱ የቆየ ልማድ ስለሆነ እኔም በታጩሁበት መንበረ ዳዊት ሆኜ በእግዚአብሔር ቸርነት እጠብቅሃለሁና ነጋዴም ነግድ ገበሬም እረስ ከአባቶቼ ሲያያዝ በመጣው ሕግና ደምብ አሳድርሃለሁ መጋቢት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

የግዕዝ ግጥም

ስብሐተ ንሥረ ተፈሪ ።

ንሥረ ተፈሪ መፍርሕ እመ የዓርግ ሰማየ ለለጽብሑ ።
እድለቅለቀት ምድር ወሕዝበ ኢትዮጵያ ተፈስሑ ።
ኃይለ መንግሥቱ ዘክሕዱ እንበለ መጠን ፈርሑ ።
ልቡና ተፈሪ ዘበኃይለ ኤልያስ የሐውር በጥበቢሁ ።
ይእዜኒ ፃአ ትርዓያ አዋልደ ኢትዮጵያ ለንሥረ ተፈሪ ክነፈሁ።
እንዘ ይሬስዮሙ ኃይለ ሥላሴ መንፈሰ ለመላእክቲሁ ።
ግፋአሂ ወገፋኢ እንዘ ይትባደሩ በጽሁ ።
ውስተ ደብረ ጽዮን አዲስ አበበ እንዘ የሐሥሡ ሰላመ እምኔሁ።
ይእዜኒ ፃዓ ትርዓያ አዋልደ ኢትዮጵያ ለንሥረ ተፈረ ክነፈሁ።
ለተፈሪ ሰሎሞን ፍትሕ ዘሀሎ ኀቤሁ ።
እስመ ከመ ምኒልክ ቀዳማዊ ወከመ ዳንኤል በጺጋሁ ።
ወከመ ዕፀ ገነት ዘይሁብ ፍሬሁ በበጊዜሁ ።
ይእዜኒ ፃዓ ትርአያ አዋልደ ኢትዮጵያ ለንሥረ ተፈሪ ክነፈሁ።
እስመ ድምፀ ነጐድጓድ ስብሐቲሁ ።
ስብሐት ለኪ ኢትዮጵያ ለምኒልክ መርዓቱ ።
ስብሐት ለኪ ኢትዮጵያ ለኃይለ ሥላሴ ወላዲቱ ።
ስብሐት ለኪ ኢትዮጵያ ለልብሰ መንግሥት ታቦቱ ።
እምኵሎንኬ ኢትዮጵያ ኪያኪ እፈቱ ።

አባ ተሰፋ ሚካኤል ከ ሥ ።

ይድረስ ።

ለክቡራን ወንድሞቼ የብርሃንና ሰላም ወገኖች

ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

ባለፈው ወር ከጥር ፲፱ ቀን ጀምሬ ታምሜ ነበር ። በዚህም በ፪ወር የሆነውን ኀዘንና ደስታ ሁሉ ከህማሜ ጋራ ነው የተካፈልሁት፡ በዚህ ሳምንት ግን ተሽሎኝ ወደ ደጅና ወደ ቤት ስል ቆይቼ አልጋዬ ላይ ተኝቼ ሳለሁ የትምህርት ቤቱ ስልከኛ መጥቶ ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ ወደ ግቢ ይጠሩሃል አለኝ ። ያን ጊዜ ድህነቴን እጅግ እጅግ አመሠገንሁ ሹም ሁኜ ቢሆን ወደ ግቢ ተጠርተሃል ሲሉኝ ምን አጥፍቻ ይሆን ብዬ እደነግጥ ነበር ። ካን በላይ እንደ ጻፍሁት እኔ ነኝና ደስ እያለኝ ሂድሁ ወዲያው ባላባምራስ ተክለ ማርቆስን አገኘሁና የብርሃንና ሰላም ድሬክተር ሁነህ እንድትሠራ ታዝሃል አሉኝ እኔም እጅ ነስቼ እግዚአብሔር ፍጥረቱን ንጉሥ ሠራዊቱን ባለመርሳቱ እየተደነቅሁ ጃንሆይን እያመሠገንሁ ወደቤቴ ተመለስሁ።ስሜን በየሳምንቱ እምትናፍቁ ወዳጆቼ ሁሉ በየሳምንቱ ስሜን ተጽፎ በማግኘታችሁ ደስ ይበላችሁ ።

የምስራች ።

እምትጽፉልኝንም ሁሉ እየመረመርሁ አሳትምላችኋለሁና ለሀገራችንና ለመንግሥታችን የሚጠቅም ነገር ሁሉ እየጻፋችሁ እንድትልኩልኝ አሳስባችኋለሁ ።

የብርሃንና ሰላም ዲሬክቴር ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

የልቅሶ ግጥም ።

፩ደኛ ፡ ዘመኑ ማርቆስ ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ።
ወራቱ መጋቢት ቀኑም ሮብ ለት ።
ወዲያው በዓላቱ ተክለ ሃይማኖት ።
ግርማዊት አረፉ በስምንት ሰዓት ።
ሰውም አለቀሰ መታሰቢያ ቤት
፪ተኛ ፡ እንደምን አድርጌ እንደምን ልርሳት ።
መኳንንቱን ሁሉ ስታሸሞነሙነው በወርቅ ቀሚሰና በወርቅ መረሻት ።
ሴት ወይዘሮዋንም ስታሸሞነሙናት በወርቅ መረሻት ።
ሰው በሞት ጊዜ ስታለቅስለት ።
እንጀቴ አለቀሰ ግርማዊት ንግሥት ።
፫ተኛ እደረጃ ቆሜ ብመለከታት ።
አልፍኝም ገብቼ ብመለከታት ።
ዘውዲቱ ምኒልክ መታሰቢያ ናት ።
፬ተኛ በሕይወቷ ሳለች የሠራችው ቤት ።
መንግሥተ ሰማያት የምትገባበት ።
መታሰቢያ ሆነች ግርማዊት ንግሥት ።
፭ተኛ ማን ይቃከላታል በጾም በጸሎት ።
ደግሞም በደግነት በርህሩህነት ።
ኢትዮጵያ ሆና ኢየሩሳሌም ላይ በሰራችው ቤት።
አላፊው አግዳሚው ሲአመሰግናት
እገነት ያግባልን ዘውዲቱን ንግሥት
የክርታ በታዋ መንግሥተ ሰማያት
፮ተኛ በጸሎት በምጽዋት ደግሞም በስግደት
ዘውዲቱ ምኒልክ የሰራችው ቤት
አትከለከልም መንግሥተ ሰማያት
ይኸን አውቀውታል ሊቀ ጳጳሳት
፯ተኛ ቤተ ክርስቲያን ወዳጅ እንደ ማር ወተት
ቆማ ስታስቀድስ አማይስለታት ።
ለዲኃ እምትራራ አምታዝንለት ።
ያጼ ምኒልክ ልጅ ግርማዊት ንግሥት ።
አረገፈችብን አወይ ሰውነት ።
፰ተኛ ፡ እኛ ብናለቅስ ምን ሊአደርግላት ።
ከሉንም ብንለብሰው ምን ሊአደርግላት ።
በቁሚ ሰርታለች የሰማዩን ቤት ።
እግዚአብሔር ያውርሳት መንግሥተ ሰማያት
፱ኛኛ ፡ ከደረጃ አልፍኝ ስንቀባረር ።
ስንወጣ ስንገባ እንደ ልባችን ።
እመጋረጃ ውሥጥ ስንሸሞነሞን ።
በባሕሪአችንም ችለው ሲአኖሩን ።
የኢትዮጵያ ንግሥት እውቀቷ ብርሃን ።
አፈር ሆነችብን እመቤታችን ።
፲ኛ ፡ የልፍኝ አሽከር ሁሉ ስሙት ይህን ቃል ።
ሃሰቴም እንደሆን ማንም ይመስክር ።
አንድ ቀን ሳይቆጡን ሆድ ሰያስቡሱን ።

የትም ከርመን መጥተን ሳንገባ እልፍኛን ።
እንደ አጣፋን ሲአውቁ ምሕረት ሲሰጡን ።
እንደ አባት እንደ እናት እመቤታችን
ከመ ቅጽበት ሄደች የዓለም ብርሃን ።

፲፩ ፤ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ሲናገር ።
ተዘከርኩ በሌሊት ስመከ እግዚኦ ወአቀብኩ ሕገከ
ወይእቲ ኮነተኒ ብሎ ያለውን ።
የኢትዮጵያ ንግሥት ይኸን ሰርቃ ሄደች አለጥርጥር ።
ሃሰቴም እንደሆን ሊቀ ጳጳሳቱ ሕዝቡ ይመስከር ።

፲፪ኛ፤ ስለ ኃይማኖቷ ትንሽ ልናገር ።
መጽሐፍ ትወዳለች ንባብ ትርጉሙን ።
የሚያስተረጉሙት የለት የለቱን ።
ቃሉን ትወዳለች ቅዱስ ወንጌሉን ።
ተቀበለዋለች ሥጋና ደሙን ።
ምንም ቢሆን አይቀር ሰው አፈር መሆን ።

፲፫ኛ ለዝክረ ስምኪ ብዬ ልጀምር ።
የሞት ተስካር አውጭ የአለም ብርሃን ።
የታመምን እንደሆን እምትጠይቀን ።
ባስፈለገን ሁሉ መታመማችንን እምትሰጠን ።
አዩዩ አዩዩ አወይ ሰው መሆን ።
አፈር ሆነችብን እመቤታችን ።
ሳይሰጣት አቀርም የሰማይ ጽድቁን ።

፲፬ተኛ ፤ በዓለም ላይ ሆና ዓለም እምትንቅ ።
ወርቀ ዘቦ ግምጃ ደግሞ ሙከሽ ጨርቅ ።
በሃይማኖቷ ጸንታ እጅግ ስትደነቅ።
አለምን ንቃለች ዘውዲቱ ጻድቅ።

፲፭ተኛ፤ሁላችሁም ስሙ አድምጡ በውነት።
ዳዊቷን ስትደግም ለሊት በመብራት።
ወንጌሏን ስትደግም ለሊት በመብራት።
ማልዳ ስትነሳ የማይሸለቻት።
ዘለአለም ጸሎት ነው ዘለአለም ስግደት።
እባክህ አምላኬ በአመ ይመጽ ጊዜ አቃሳፍራት።
አርስቷን አርግልን መንግሥተሰማያት።

፲፮ ፤ ሮብ ወደማታ እቃ ጠፍቶብን።
ስንፈልግ ስንፈልግ ቀኑ መሽቶብን።
በአዋጅ በነጋሪት ንቁም በበህላዌኑ ብሎ ሲነግረን።
ተፈሪ ብርሃን እውቀት መጣልን።
ለንጉሠ ነገሥት አደረገልን።
እኛም አለመጥን እጅግ ደስ አለን።
ይኸን ላደረገ ምስጋና እናቅርብ ወደ አምላካችን።
ለትውደ ትውልድ አምላክ ያብቃልን።
አሚን ወአሚን ለይኩን ለይኩን።
ልጅ ዘለቀ ወልደ ገብርኤል የልፍኝ አሽከር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገ ራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የዳግማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጂዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሁ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፶ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፷፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፷ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፷ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፷ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፷ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፷ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፶ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፶ መሐ
አሳብና ምኞት	፴ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፴ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፳ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፳ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፳ መሐ
የእንቆቅልሽ ግጥም	፲ መሐ

ያዲስ አበባ ገበያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፳ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፪ ብር ተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፯ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፸፭ ብር
ባለሰይጣን		፻፸፱ ብር
ባለ ድመት		፻፶ ብር
ባለ አህያ		፻፵ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፶፰ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪካ		፻፳፬ ብር
ጃፓን		፻፹፯ ብር
ሱካር	፩ ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፰ ፍራንክ
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፭ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፭ ከ፸ ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ ፯	

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝ ኒ ት የ እ ጅ ሰ ዓ ት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ
ሸከላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፈኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጪ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ጫማ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንከራ ባለጌጥ የኦቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የኦቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጉርጉርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ፔር ዳኒይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
6me ANNÉE № 17

ሐሙስ ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 24 AVRIL 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
I Hayle Sellassé Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumiére et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወቅር እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ለስ ጌታችን ስቅለትና ስለ ትንሣኤው።

በሚያዝያ ፲ ቀን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስቅለት መታሰቢያ ነበርና ሕዝቡ ተሰብስቦ በየቤተ ክርስቲያኑ ሲሰግድ ዋለ ። ይህም በተያዘበት ሌሊት ላብ እስቲወጣው ሰገደ ጸለየ ይላልና ወንጌል።ስለዚህ በየዓመቱ ለመታሰቢያ እን- ዲሆን ሊቃውንት ሕግ ስላደረጉት እስከ ዛሬ ይኖራል።በነጋውም ቀዳሜ ሥዑር ሆነ። ማለትም የሰይጣን ሥልጣን የተሻረበት ቀን ማለት ይመስለኛ ል።በዚሁም ቀን ካህናቱ ቄጠማ ይዘው የምስራች ይላሉ ። ይልቁንም ወደ ንጉሡ አደባባይ ሄደው በክብሮ ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ እያሉ በንጉሡ ፊት ይዘምራሉ።በማርኛ በመስቀሉ ዕርቅ አደረገ፡መነ- ሣቱንም ገለጸ ማለት ነው በዚሁም ቀን እንደ ልማዳቸው ካህናቱ ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ትንሣኤሁ አግሀደ እያሉ በዙፋኑ ፊት ለፊት ቁመው ይዘምሩ ነበር። ጃንሆይም በዙፋንም ላይ ተቀምጠው ይመለከቱ ነበር። ሊቀ ጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስና የኢትዮጵያ ጳጳሳት የውጪ አገር መልዕክተኞችም በግራና በቀኝ፥ የሀገራችን መኳንንትም በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ። ገብረ ሰላመ በመስቀሉ ብለው ከጨረሱ በኋላ የንጠጠ ማርያም ካህናት ታቦር ወአርሞንዔም በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ወይሴብሑ ለስምከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ባሉ። ጊዜ ኃይለ ሥላሴ ወራሴ መንግሥት ይባል የነበረው ተስፋ በመ- ፈጸሙ ምቀኝነት የሌለበት ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አለው ከዚህ በኋላ በኖኅ ርግብ ምሳሌ የተደረገውን ቅርጥብ ቄጠማ ይዘው ወደ ሊቀ ጳጳሳቱ ቀረቡና ሊቀ ጳጳሳቱ ለጃንሆይ ሰጡ። ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ አሳርገው ስለ ክርስቶስ መስቀልና ትንሣኤ መልካም ስብከት ሰበኩና አሳረጉ ።

~~በሚያዝያ ፲፪ ቀን የትንሣኤ በዓል ሆነ።ሌሊት በ፯ሰዓት~~ ቱኩል በጾም መግደፊያ ጊዜ መድፎች ተተኰሱ።እንኳን ለብርሃን ትንሣኤው አደረሳችሁ ይባባል ነበር።መቸም የደስታ ቀን ነውና በዚያው ቀን ወይዘሮ ተናኘወርቅ የደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ባለቤት የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ በደኅና ተገላገሉ የሚ የደስታ የምስራች መጣና ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አለው እንኳን በደ- ኅና ለመገላገል አበቃዎ ።

ለብርሃንና ሰላም አዲስ ዲሬክተር
ለክቡር አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።

የብርሃንና ሰላም ዲሬክተርነት የመሾምዎን የምሥራች የምትገልጽ ቃል ባነበብሁ ጊዜ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ሆነ ። የደስታዬም ብዛት እሁለት ተከፍሎ ነው ። መጀመሪያው ስለ ርስዎ መሾም ። ሁለተኛም ታላቁ ደስታዬ የተማሩ ምሁራንና ብልሆች ሰዎች የተማሩ በትምህርታቸው ያልተማሩም በልማድ እውቀታቸው ለመንግሥት ለማገልገል የሚችሉ ሥራ ያልያዙ ሥራም የያዙ በከፍተኛ የሥራ ሹመት ለመሾም የሚገባቸው ብዙዎች አሉና ያለ አጋር ያለ አስታዋሽ እንዳሁኑ እንደእር- ስዎ በጃንሆይ መራጭነት <u>ብቻ ከሉበት ሥፍራ እየተጠሩ ሥራ</u> መያዝና የሥራ ሹመት እንደሚያገኙ የታመነ ሙሉ ተስፋ በማግኘታቸው ነው ። ምንም እርስዎ የተማሩ ቢሆኑ ያለ ደጅ ጥናት ከቤትዎ ተጠርተው በሚገባዎ የሥራ ማዕርግ ስለቀመጡ- ዎት ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እረጅም ዕድሜ አምላካችን እንዲሰጣቸው በብዙ እየተመኘሁ ዕውነ- ተኛውን ሥራቸውን ከልቤ የሚፈልቀውን ምስጋናቸውን አን ደበቴ ለመናገር አያቋርጥም። ለሥራ ሹመት መመረጥዎ ከማ ዕርግ ሹመት ከፍ ያለ ነውና እንኳን ደስ ያለዎ ሹመት ያዳብር ።

~~ብርሃንና ሰላም መልኩን አሳመረ ።~~
በወርቅ ማኅተም መታተም ጀመረ ።

እንግዲህ እንጸና ስንፈት ሳይገባን ።
በወርቅ ማኅተም ከታተመልን ።

ማህሉ ጽጌ ።

የእሳት አደጋ በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ።

ሚያዝያ ፲፪ ቀን ከጧቱ በ፪ ሰዓት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የእሳት አደጋ ተሥነቶ መንበሩ ከጫፍ ከጫፉ እስኪከስል ድረስ ተቃጠለ ። የተቃጠለበትም ምክንያት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙቶ ፤ የተነሣበት በዓል መታሰቢያ ስለሆነ በቅድስተ ቅዱሳን ፬ መብራት በምሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ በ፬ቱ ማዕዘን ከመንበሩ ላይ ተበርተው አድረው ነበር ። ካህናቶቹም ግብራቸውን ሲአደርሱ በከበሮና በጸናጽል ብጭብጨባ ሲዘምሩ አድረው ከሌሊቱ በ፲ሰዓት ቅዳሴ ገብተው በስምንት ሰዓት ከቅዳሴ ወጡ ። ስለትንሣኤ የምስራች ፯ ጊዜ መድፍ ተተኵሶ ወዲያውም ሕዝቡ ሁሉ ወደቤቱ እየሔደ ደስታውን ይከፈል ነበረ።ቄሶችም ቤተክርስቲያኑን ዘግተው እሳ- ቱን ሳያጠፉ ትተውት ሒደው ኖረው እሳቶቹ በንጨት መቅረዝ ነበሩና ሻማው ሲያልቅ ተያይዞ መንበሩ እስኪነጋ ድረስ ተቃጥሎ ከጧቱ በ፪ ሰዓት ጢስ ሲጤስ ሰወች አይተው በቶሎ በሩን ከፍተው ቢገቡ ይህ የእሳት አደጋ መሆኑን አይተው ሰዎችና ደወል ተጨጩጩሁ። ወዲያውም የከተማው ሰው በፍጥነት እየሮጠ ወኃ አፍሰው እቃውን አውጥተው ምንም ከመንበሩ በቀር ሳይቃጠል እሳቱን አጥፍተው አዳኑት ቤተክርስቲያኑ ጣራው እሩቅ ስለሆነ እሳቱ በጣራው ላይ ሳይወጣ ቀረ ። ጩኸት በሰሙ ጊዜ የመጡ መኳንንት እሊህ ናቸው ።

መጀመሪያ የሥላሴ ቤተክርስቲያን ሹም ሊቀ ጠበብት ጽጌ ።

፪ተኛ ክቡር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል ከነጭፍራቸው ሙኃና የዛፍ ቅጠል አሲዘው በክብት ጋልበው ደረሱ።

፫ትኛ ክቡር ሊጋባ ወዳጆ በግራቸው ሲሮጡ መዛቸው ብፊታቸው ይንጠባጠብ ነበር።

፬ተኛ ክቡርፌታውራሪ ደቻሳ ተቃጠለ ብለው ደንግጠው ዋይ ዋይ እያሉ ይሮጡ ነበር። ባይናቸው እንባቸው እየፈሰሰ።

፭ተኛ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የአገር ግዛት ምንስቴር ተጨንቀው ያዝኑና ይገረሙ ነበር።ከዚያ ወዲያ መኳን ንቱና ሕዝቡ ተሰብስበ ሳይቃጠል በመቅረቱ ደስ ይለው ነበር። ወዲያውም ስለቤተ ክርስቲያኑ መዳን ክቡር ሊጋባ ወዳጆ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፍጥነት ሒደው አስታወቁ አፄ ኃይለ ሥላሴም ሳይቃጠል መዳኑን በሰሙ ጌዜ ደስ ብሏቸው የአኳኋኑን ነገር ለመመርመር በኦ- ቶሞቤል ሒደው አይተው ስለእሳቱ መጥፋት እግዚአብሔርን አመስግነው ወደቤተ መንግሥት በሕዝባቸው ታጅበው ተመ- ለሱ።ከዚያ በኋላ ብፁዕ አቡን ቄርሎስ መጥተው ቤተክርስቲያኑ ን ባርከው ወደ ቤታቸው ሔዱ። ይህ ሁሉ ሽብርና ድንጋጤ የመጣ ዲያቆኖች ሳይጠነቀቁ ስለቀሩ ነው። የሥላሴም ቤተ ክርስቲያን በመንግሥታችን ውቃቢ በእግዚአብሔር ቸርነት ታቦቱና ቤተ ክርስትያኑ ሳይቃጠል ቀረ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አሳባቸው ቤተ ክርስቲያን ለማሠራት ስለሆነ በራሳቸው ከነወታደራቸው ደንጊያ ተሸክመው አሻዋ አዛዘው ታላቅ ቤተክርስቲያን ጀምረዋል ። ይኸውም ቤተክስቲያን አጀማመሩ በኢትዮጵያ ታይቶ አያውቅም ። ሕዝቡም ሁሉ ዕድሜ ሰጥቶልን ጅምራቸውን ለማስፈጸም ያብቃልን እንላለን ።

ትስፋ ገብረ ሥላሴ ቡልጋ አዲስ አበባ

(ምሳሌ)ከቤት ከናቴ ተለይቼ በተማሪ ቤት ኑሬ ስመለስ ከሁሉ ከፍ ያለ አደልዳላ በታ ላይ የበቀለች ከዓለም ዳርቻ ሁና የምትታይ ፍሬዋም ለዘለዓለም የማያቋርጥ አንዲት ዛፍ አገኘሁ። የሥሩዋም ዳርቻ ከዚህ ነው ብሎ ለመወሰን አይቻልም በጥላዋም ውሥጥ ያለው አትክልት የሚያፈራው ፍሬ በዚህ ጊዜ ተበልቶ ያልቃል አይባልም።ገበሬዎቹም ዶማቸውን ይዘው በየጊዜው አትክልታቸውን ሲኰተኵቱና ፍሬዋንም አትክልት የሚያጠፉ የዱር አውሬ መጥቶ እንዳያጠፋባቸው ሲጠብቁ ለተመልካቻቸው ያስፈራሉ።ለጌታቸውም ደስ ያሰኛሉ።በዚህች- ውም ዛፍ ከፍ ብሎ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚ- አብሔር የሚል ጽሕፈት ተጽፎ ዙሪያውን በሰስት ቀለም በንዲራ ተጌጦ ይታያል ፤ ከዛፏም ሥር የሰላምና የጥበብ መምህር የ- ሚል ጽሕፈት የተጻፈበት ዘውድ የጫነ አንበሳ ሃይማኖትና ምግባር የሚባለውን ጋሻና ጦር ይዞ ቸርነት የሚባለውን ሰይፍ መዞ ያትክልቱን ሠራተኞች እያተጋ ጊዜ አሰጊዜ የዱር አውሬ መጥቶ አትክልቱን እንዳያጠፋበት ተግቶ ይጠብቃል ። ይህቺ ኑም ዛፍ ፍሬዋን ለማጥፋት የዱር አውሬዎች ይመጡና ያንን ጠባቂዋን አንበሳ ሲያጉረመርም በሰሙ ጊዜ ለተመለከታቸው ሰው እንኳንስ ፍሬዋን ለመብላትና ከገበሬዎቹም ሰፈር ሳይደር- ሱ ተመልሰው ውርደት ከሚባለው አገራቸው ገቡ። ሁለተኛም እንዚያ የዱር አውሬዎች ከሀገራቸው ተመልሰው መጥተው ለማዳ ሁነው ካትክልቱ ፍሬ ተፈቅዶላቸው ሲበሉ አየኋቸው እኔም ደነቀኝና አውሬዎቹ ለማዳ የሆኑበትን ብጠይቃቸው የዚህቺ ዛፍ ጠባቂ አንበሳ የዱር አውሬ ሁሉ ገጋር መሆኑን ስለተረዳነውና የኛም ጓደኞች ሳያውቁ ውርደት የሚባለውን አገራችንን ሲያቀኑ ወህኒ የሚባለው ሽፍታ ስለገዳላቸው እኛም እንደነሱ ሽፍታ እንዲያጠፋን ይኸው ገገርችን አንበሳ ምሕረት የሚባል አብሮ አደግ አሽከር ነበረውና እሱ ይዞ አመጣን አሁንም እምነት የሚባለውን የገበሬዎች ሹም ባልደረባ ተቀብ- ለን ትእዛዝና አገልግሎት የሚባሉትን የርሻ በሮች እየጠበቅን እንኖራለን አሉኝ። እኔም ይኸንን ሁሉ ቁሜ ስመለከትና ስነ- ጋገር ለመንገዴ የያዝኩት ስንቅ ጥቂት ስለሆነ አልቆብኝ ነበርና ለነኛ ላገልጋይ ገበሬዎች ሥራችሁም ወደፊት እየሰፋ አትክልታችሁም እየለማ እንዲሄድ የሚጠብቃችሁን አንበሳ ያቈይልን ብዬ ከዚያ ካትክልት ፍሬ ለስንቄ የሚሆን ሰጥተውኝ በተቻለኝ አቅሜ በዚያው ባትክልቱ ውሥጥ ጥቂት ጥቂት ሥሬ እመለከታለሁ ።

ስለመንግሥት ጉዳትና ስለሠራተኛ አገልግሎት ።

በኢትዮጵያ ውሥጥ ያሉ የመንግሥት ሠራተኞች ሁሉ መጀመሯ ለመንግሥታችን አገልጋይነት ያድሩና በሥራቸውም ከሠለጠኑ በኋላ በንግድ ሥራ ለመጡ ለውጭ ሀገር ነጋዴዎች ሎሌነት ተቀጥረው ለቤተ ሰዎቻቸውና ለትዳራቸው የሚበቃ ደሞዝ እየተቀበሉ በስደት ያገለግላሉ ። (ማመልከቻ)

ከዕለታት ፩ቀን አንድ ሠራተኛ የዕለት ረኃቡንና የቤተ ሰዎቹን ንዝናዜ ይልቁንም ያየሥራ አለቃው በየጊዜው የሚሰጠውን ተስፋ ያስታውስና የተጠቀምሁ መስሎት በዚያ በውጭ ሀገር ነጋዴ ቤት ይሄድና ዕቃ ገዢ መስሎ የሚሠራውን ዕቃ ዓይነት ይህ ዕቃ ዋጋው ምንያህል ነው ብሎ ይጠይቅና የዚህን ሥራ ዓይነት ለመሥራት እችላለሁ ብሎ ያመለክታል። የዚያን ጊዜ ነጋዴውም ሠራተኛውን እኔ በከፍተኛ ደሞዝ አሳድርሃለሁ አንተም የመሰሉትን የሠለጠኑ ከያይነቱ ሠራተኞች በገኝ እቀጥራለሁ ብሎ ይመልስለታል ያም ሠራተኛ ነጋዴውን አባክዎ ጌታዬ ከሉስ ይስሙኝ ጉዳቴን ልንገርዎ ብሎ ከንጹሕ ልቡ ያስቀመጠውን የድኅነት ሐሳቡንና ምኞቱን ሊዘከዝክለት ጀመረ። አቶ በውነቱ የሚበሉጡ ጓደኛችን ስለሞተ የሱን ቀለብ የሥራ አለቃዬ በሽ ተስፋ እሰጥሃለሁ ብለውኝ ዓሥር ብር በወለድ ተበድሬ ጉቦ ሰጥቼ ነበር ያንንም ቀለብ ሳላገኘው አቶ ፈቃደ እግዚአብሔር የሚባሉ የሟቹ ያቶ በውነቱ የጡት አባቱ ነበሩና በሳቸው አማላጅነት ለልጆቹ ማሳደጊያ ይሁን ተብሎ ተፈቀደላቸው። እኔም በሽ ተስፋን ደጅ ስጠና እገኛለሁ በማለት ተገዳሁ አሁን ግን ዕዳዬም ወለዱ ከዋናው ሊበልጥብኝ ነው ገና ሙቼ ተዝካር ይወጣልኛል ልጆቼም የመንግሥት ቤት ነውና ያድጉልኛል ብዬ የመንግሥቴ ፍቅር ይዞኝ እስከ ዕለተ ሞቴ ድረስ በዕዳ ተጨንቄ ብሞትም ዕዳ የሚባለውን ርስት ለልጆቼ አውርሻቸው ልሄድ ነውን አሁንም ጌታዬ እዚሁ እርስዎ ቤት ተቀጥሬ እየሠራሁ ዕዳዬን ልክፈል ይኸንንም ስላሰቡልኝ እግዚአብሔር ያስብልዎ የርስዎንም የመሥሯ ቤት ያመለከተኝ ዘመዴን የመሰለ ሁሉ በያለበት ይኑርልኝና ለዚያ ለነጋዴ ሄዶ ሎሌነት ያድርና ሠራተኞችም እየሰበሰበ ያመጣለታል። ነጋዴውም በደስታ ይቀበለውና በከፍተኛ ደሞዝ ቀጥሮ ያሠራዋል እነዚህም በያይነቱ ሥራ ሠልጥነው ወደነጋዴ ቤት የሄዱ ሠራተኞች ቍጥራቸው ከ፳፱ አያንስም። የሥራቸውም ሥልጣኔ ስምና ዓይነት ከ፩ እስከ ፲፫ ቍጥር ይደርሳሉ እነዚህም ሠራተኞች የዕለት ረኃባቸውን መታገሥንና የደሞዛቸውን ብዛት ተመልክተው ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው ጉዳት መሆኑን አልተረዱትም ይመስለኛል ።

የሥራ ማስታወሻ ።

መንግሥት አክብሮ ያስቀመጣቸው ክቡራን ባለሥልጣን ሚኒስቴሮችና ሹማምንቶች ለንግድ አቅራቢያ በሚሆን ቦታ ላይ በየአውራጃው ባንድ ክፍል የሥራ ቤት ባንድ ክፍል የንግድ ቤት በመንግሥት ስም አቁመው ከንግዱም የተገኘውን ትርፍ ለሠራተኞቻቸው ደሞዝ እየሰጡ መንግሥትም ያሰበውን ዕቃ ያለችግር በቶሎ እንዲያገኝ ቢያስቡለት ለተራቡም የመንግሥት ሠራተኞች ለኑሯቸው መግፊያ የሚበቃ ደሞዝ ሰጥተው ቢያሠሯቸው በሥራቸው ሁሉ እርዳታ በታሰበላቸው ነበር። ሠራተኛም ረኃቡና ችግሩ ሲወሰንለት ዕውቀቱ እየሰፋ በልቡ መልቶ ሊሠራ ይችላል። ይኸውም ቤት በየአውራጃው የኢትዮጵያ መንግሥት የንግድ ማስፊያና የዕቃ ማሰናጃ ቤት ተብሎ ባለሥልጣን ሚኒስተሮች እንደ ሥራቸው አገባብ ቢሠሩ የሠራተኞቻቸውን ደሞዝ ችለው ትርፍ ገንዘብ ለመንግሥት ሊያገቡ ይችላሉ። አገሪ ገዥ መንግሥት ያከበራቸው ሻለቆችና መኳንንቶች በየአውራጃቸው በማናቸውም ዓይነት በኢትዮጵያ ውሥጥ የሚሠራውን ዕቃ በፈለጉ ጊዜ ከዚሁ ከቆመው ቤት መንግሥት በቈረጠላቸው ዋጋ እየገዙ ለሀገራቸው ጥቅም ቢሠሩበትና ገቢያቸው ለመንግሥታቸው ቢሆን ጥቅሙ ለራሳቸው በሆነ ነበር ። ማለት ወጭው ለራሳቸው ነውና መንግሥታችንንም ያለገቢ ወጭ በየጊዜው ብናበዛበት ጉዳቱ ለራሳችን መሆኑን ማንም አይስተውም ። ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ይህችን ትንሽ ሐሳቤን ማሰቤ መንግሥትን ነጋዴ ለማድረግና የውጭ ሀገር ነጋዴዎች ሥራቸውን እንዲፈቱ ንግዳቸው እንዲቆም አላሰብሁም። ነገር ግን የእጅ ሥራ ተከናውኖ በኢትዮጵያ በመላው እንደ አውሮፓ ፋብሪክ እስኪቆም ድረስ ከአውሮፓ ተሰናድቶ የሚመጣውን ዕቃ እንድንገዛቸውና ለነሱም የሀገራችንን ሥራ እንደናሳያቸው የሰማምነት ሥራ እንድንሠራ ነው ። ክቡራን ሆይ ፤ ከዚህ በላይ ፤ የተጻፈውን ያጠፋሁትን አርማችሁ በጋዜጣ መልታችሁ እንድታስቡበት አስታውሳችኋለሁ ።

ደምሴ ወልደ ሐዋርያት ።

ራስ ኃይሉ ።

የጐጃምና የዳሞት ያገውና የሜጫ ገዥ በሚያዝያ ፲፬ ቀን ወደ ግቢ ገብተው ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሞት እጅግ ተለቀሱ። ለወሬ የለው ፍሬ የተባለው ተረት አንዳንድ ጊዜ መልክም ነው በዘንድሮ ጉርፍ ዓባይ እጅግ ሞልቷልና አይመጡም እየተባለ ሲወራ ማዕበሉንም ጉርፉንም አልፈው በደኅና ስለ ገቡ እጅግ ደስ ብሎናል ።

ያልታሰበ ወሬ ባከተማችን የሚአወራውንም መንግሥት እያሰለለ እንዲአፋው ተስፋ እናደርጋለን ።

ማስታወቂያ።

በ፯ኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ፲፯ኛ ቍጥር ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፱፻፳፱ዓ ም በ፲፱፻፳፱ገጽ በወጣው ብርሃንና ሰላም በስሙ ሞክሼ አለቃ በዛብህ ስለ ሀገር ጥቅም ያወጡት ጋዜጣ የኔ አለመሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አመለክታለሁ።

አለቃ በዛብህ ዘደብረታቦር።

ራስ ጉግሣ ወሌ ድልሆነው የምሥራቹ የመጣለት በጃንሆይ ቃል ለመኳንንቱ የተነበበ ።

ፈጣሪያችን ኢትዮጵያን ዘወትር እንደጠበቃት ነው አሁንም እንኳን በዚህ ባሁኑ ጠብ የክርስቲያን ደም እንዳይፈስብኝ እንደተቻለኝ ጥሬ ነበር ። ምንም ኃይሉን ለፈጣሪዬ ብርያው ለመባል ለማልበቃው የቸርነቱን ቢሠራ ከዚያም ወገን ከኛም ወገን የሞቱት ወንድሞቻችን ናቸውና ለፈጣሪያችን ምስጋናና ደስታችንን ለመግለጫ ደኸው ከነግሀ እስካሁን በደስታ ዋልን ። የንግደሁን ደስታ ለውጠን ፈጣሪያችንን ለማሰብ አንድርገው ፤ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይጠብቃት። መጋቢት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፱

ስለ ቤጌምድር ሹም ሽር ።

ራስ ጉግሣ ወሌ በተንኰል መንገድ ተነሥተው ለሕዝብም ላገርም የመጥፊያ ምክንያት መሆናቸውንና እርሳቸውም መጥፋታቸውን ባለፈው ሳምንት በ፲፩ ቍጥር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ላይ አይታችሁታል ።

ነገር ግን ምንም ያገር ውሥጥ ጉዳትና ጥቅም ቢሆን በኢትዮጵያና በንጉሥ ነገሥቷ በሕዝቡዋም ላይ የተነሣው ክፉ አድራጎት በእግዚአብሔር ኃይልና ቸርነት ስለ ተረጸመ እጅግ ደስ ያሰኛል ። ስለሆነም በጌምድርን ያህል ታላቅ አገር ባልሆነ ወሬ አገሩም ሰውም በመጐዳቱ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አስበውና አዝነው ችግሩን የሚያመለክትለት በደኅንነትም የሚጐበኝውና የሚጠብቀው ልዑል ራስ ካሣን አገረ ገዥና ዳኝነት ጠባቂ አድርገው ሾሙለት ። ይኸውም አገር ለልዑል ራስ ካሣ ሲሰጥ የተነገረው አዋጅ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ሞ ዓ አ ን በ ሳ ።

ደድረስ ከደጃዝማች ብሩ (ደብረ ታቦር) ።

ሚያዝያ ፫ ቀን የላክኸውን የስልክ ቃል አየሁት ።

ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋር ዘምቶ ሄዶ የተመለሰው በያገር ቤቱ ተሰራጭቶ እርስ በርሱ ይቃማል ያልከውን ይኸውና ያዋጅ ቃል ልኬልሃለሁና እዚያው እናንተ ዘንድ ደብረ ታቦር ላይ በሌላ በሌላውም ከተማ ሁሉ በየስፍራው ልከህ አዋጁን እንድታስነግር ይሁን ።

አ ዋ ጅ ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ለራስ ካሣ ከርብ በላይ በጌምድርን ሳይንትን (በእራት ክርብ በታች በቆራጭነት ስጥቻለሁና የበጌምድር ሰው ራስ ጉግሣ ወሌ ቀድሞ ወደየጁ ያዘውሩኝ ብለው ቢለምኑ የአዝመራ ጊዜ ነውና የበጌምድርን ዘማች ሳያስነሡ ከርብ በላይ ያለውን ባለትዳርና አሽከሮችዎን ይዘው መጥተው በፊት የከዳውን ጋላ ይውጉ ብለን ለይተን ብናዛቸው እናንተንም አለፈቃዳችን አስነሥተው በክረምት አጕላልተው ።

በመጨረሻውም ያልተሠራ ውሸት ነገር አስወርተው ከዚህ ሁሉ ጥፋት የደረስከው በናንተ አለማወቅና በራስ ጉግሣ ተንኰል መሆኑን መርምሬ አውነቱን ስላገኘሁት ደም መፍሰሱ አልቀረምና የሚቀጣውን ገላህን ምሬሃለሁና ።

መንግሥት የወጋህ ጥፋተኛውም ያልወጋኸም ፈቃደኛ ከሰጠሁህ ደኛ ድረስ ደብረ ታቦር ገብተህ ላግኝህ ።

እስከ ዳግም ትንሣኤ ገብተህ ፈቃደኛነትህን ያላስታወቅህ ግን ከአዋፊ ትቈጠራለህ ። ሚያዝያ ፬ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ ።

ልዑል ራስ ካሣም እንኳን እንደዚህ ላለው ሳያስበውና ሳያውቅ የድንገት አደጋ ለወደቀበት አገርና ሕዝብ ይቅርና የዳኝነታቸው ትክክልነት የታወቀ ስለሆነ ይህ ጠፋ የተባለው አገር ባንድ ዓመት ውሥጥ እንደ ለማ ተስፋ አለን ።

ለተስፋችንም ኃይል የሚሰጠው እስከ ዛሬ ያልነበረውን በጐንደር ከተማ የመንግሥት ከንቲባ ብላታ ተስፋዬ በመሾማቸው የመንግሥት ነጋድራስ በመደረጉ በየጠረፉም ባለደመወዝ ዘበኛ በመቆሙ ነው ። የሆነ ሆኖ ምንም የቤጌምድር ጥፋት ቢሰማን የዚያው አገር ባላባቶችና መኳንንቶች ሊቃውንቶችም ብዙ ባለተስፋዎች በቀለብና በደሞዝ ደጅ የጠኑ ባደባባይ የሚጕላሉ ሰዎች ነበሩና ላባታቸው አገር በቁ። እነዚሁም ከርብ በታች ባላው አገር የተተከሉ እነደጃች ተስፋ እነደጃች መልኬ እነፊታውራሪ ካሣ መሻሻ እነደጃች ኃይሉ ንጉሤ ናቸው። ደግሞ ራስ ጉግሣ ወሌ የነቀሏቸው ዛሬ በያገራቸው የገቡ ፊታውራሪ ይመር ጕሹ ፤ እነ ፊታውራሪ ኃይሉ ወንዴ እነቀኛዝማች ተሰማ ወንዴ ፤ እነ ፊታውራሪ አስፋው የስማደው ግራዝማች ብጡል የተሰማ ውቤ ልጅ ሌሎችም ሁሉ እሉ እነዚሁም በየተወለዱበት አገር ትዳርና ሹመት በማግኘት ወደ አገራቸው እንዲገቡ ከልዑል ራስ ካሣ ጋራ እየተጋጠሙ በመሔዳቸው እንኳንስ ለተደረገላቸው ይቅርና ላየና ለሰማው ሁሉ ደስ የሚያሰኝ ሆን ።

ለነዚሁም መኳንቶች ለእጃቸው መዛሪያና በቅሎ ስንቅ ለካህናቱም የገንዘብ ዳረጎት እንደየማዕረጋቸው እየሰጡ ሰደዷቸው ይኸውም ደስታ አገር ላገኙት ብቻ ሳይሆን የጌቶቻችንን ፍጻሜ እናያለን ብለው አብረው ለሚጕላሉ አሽከሮችና ጓዞች ባገር ቤትም ላሉ ባለተስፋ ዘመዶች መሆኑን ማንም አይሰተውምና ይኸንን ላደረጉ ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጥልን እንመኛለን ።

መ ወ ድ ስ ።

ይትፌሥሐ ዮም በስመ ዚአከ ።
መከነ መንግሥትከ ታቦር ፤ ወአርሞንኤም ጐንደር ።
ኃይለ ሥላሴ ሰሎሞን ልዑለ መንበር ።

አምጣነ መዘራሰትከ ምስለ ኃይል፡ ወትወጽአ እምአጽቀ
ዕሜይ መንግሥትከ በትር ።
መርዔተ አባግዕ በዘትርዒ፡ ወትኬንን ከዕበ እምባሕር
እስከ ባሕር ።
ኃይልከኒ ተሰብሐ፡ በደብረ ታቦር ።
ምሥጢረ መንግሥትከበላዕሌሁ፡ንሩቀ ልቡናከመ ያእምር።
ከመ ምድረ ጐንደር፡ ትትረመም ወትትነከር ።
እምጣነ ከሠትከ መንክራተ፡ውስተ ዓድያሚሃ ለቤጌምድር።
ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

እሚሉን የሚቻለኝ ሁኖ ቢሆን በሙሉ ዓለም እንድትሞገሱ ያሁን ስንፋናችሁንና ልምዳችሁን ግብዝናችሁን ወደዚያ አባርሬ የሚገባችሁን ሥልጣኔ ለማስያዝ እስገድጄ ባደረስኳችሁ ደስ ባለኝ ነበር። አሁንም ኢትዮጵያንና የብርሃንና ሰላምን ወታደር እረዳት ክስነሣሁ ተመርቃችሁ ከብርሃን እንድትደርሱ ተስፋ አለኝ ።

በቀለ ዘለቀ።

የኢትዮጵያ ቆነጃጅት እነሆላችሁ የምክር በረከት

ባለፉት ወራቶችና ከዚያም በፊት የንቍጣጣሽን በረከት (ምክር)በብርሃንና ሰላም ጉባዔ ያቀረብንላችሁ ጥቂቶቹ ወይዘሮች ይሉኝታን ለመናቅ ክፉውን ልማዳችሁንም ከናንተ ወደዚያ ለማስወገድ እጀማመራችሁ መልካም ይመስላል።ምንም ምክርን በቶሎ ለመፈጸም ይህ አዲሱ ሥልጣኔ እንግዳ ነገር ቢመስላችሁ የሀገሬ ወይዘዝር መላው አፋራሞች ናችሁና ትዘገያላችሁ ስለሆነም ባውሥጡ ዘይት የመላ የጅ ፋኖስ ይዛችኋልና ወደሥልጣኔ ስትገሰግሱ እረማመዳችሁ ምንም ጥቂት ጥቂት ቢሆን ደስ ይላል ። ግብዝ ሰው ከሃይማኖቱ ይልቅ ልማዱን ያጠብቃል እንደሚሉ እንዲሁም ብዙዎቹ ቆነጃጅትና ወይዛዝርም ሁሉ ይህ የሥልጣኔ እረማመድ ትምህርትና ሥራ ጥቅም ያለው ፍሬ እንዲሰጥ አያምኑም ይመስላል ። አሁን ግን ብናስብ መልካም ጌጥ ለመሸለምና ለማማር ለመቀልጠፍና ለመታመን ሴላውንም እንደዚህ የመሰለውን የሰውን ክብር መግለጽ ሁሉ ከመከከላችሁ ምነው እኔ ባገኘሁና ደስ ብሎኝ በኖርኩ ብሎ የማይመኝና የማይፈልግ በልቡም ሁልጊዜ የማያስብ ከቶ የለም ። እንግዲህ ይህቺ በልባችሁ ያለችምኞት ሁሉ የምትገኝ በትምህርትና በሥልጣኔ ነው እንጂ ተሸፋፍናችሁ በመጓደድ ተደግፉችሁ በመሄድ አይደለም ። ደግሞ በዚቹ መስመር ሳይበለችቱ ንግግር ቆነጃጅቶች ቅር ይላቸውና ምነው የጸረፉ ቃል ተናገረን ይሉኝ ይሆን? ። ይህስ የከንቱ ማጕረምረም ይሆናል በራሳቸው ያለውን ጕድለት በምክር ለመግለጽ የሚከፉ እንዳይደለ እራሳቸው ይገንዘቡት ይልቁንም ያገሬ ተወዳጆች ውብ የሆኑ እመቤቶች ወደሥልጣኔ ለመራመድ ወይም ትምህርትን አተኵረው ለማየት የሚንቀሳቀሱበት ልማዳቸውንም የሚተውበት የከበረው ዘመን መልካሙ ቀን መቼ ተፋጥኖ ይደርስ ይሆን? እያልኩ እናፍቃለሁ ። እነሆ የልብ ወዳጅ ምኞት ባንድ ትልቅ ጉባዔ ብተደረገበት ቦታ በጦርነት ላይ የቈሰለ መልካም ጐበዝ ተቀምጦ ሳለ ስለአካሉ ጕድለት ያዝኑ የነበሩ ወገኖቹ እንዲህ ብለው ፈረዱ (ተመኙለት) ይባላል። እንዲህ ለመሰለው ጀግና የሰነፉን አካል ለውጦ መስጠት በተገባ ነበር ። እንዲሁም በውበት የተከናወናችሁ በደም ግባት የተመላችሁ የኢትዮጵያ ቆንጆዎች እንደ ዓረብ አገር ሴት የሚያስመስል ክፉ ልምዳችሁን ሽፍንፍናችሁን ለማስተው ሁለተኛ እኛም እንደምናየው ጕረቤቶቻችን እንደሚናገሩት የኢትዮጵያ ሴቶች ያንድ ግዜ ልብስ ላንድ ሴት ያንድ ጣቃ (ኑስ)ወይም አይተርፍም ስለ

ስለ ወንጌል ቃል መፈጸም ።

የወንጌልን ቃል ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጣሙ ፈጽመዋል ይህንኑ የወንጌልን ቃል አፈጻጸማቸውን ከሙሉ በክፍሉ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች እጽፋለሁ ። መጀመሪያ ጌታ በወንጌል ሲሳየን ዘለስ ዕለትነ ብሎ የተናገረውንና ያስተማረውን አይተው ተመልክተው አንብበው ተርጕመው በየዕለቱ በግርቆስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የተለየ ቤት አሠርተው ቀኍጥራቸው በየዕለቱ የበዙትን ነዳያን ይመግባሉ ። ይህም ሲሆን እዚያው ከቤተ መንግሥታቸው የሆነ እንደሆነ ወጥ ቤቷ በወጥቤትነቷ እንጀራ ቤቷ በንጀራ ቤትነቷ ጠላ ቤቷ በጠላ ቤትነቷ በሥራ ምክንያት በሥራ ብዛት የተነሣ ጌዜው ተላልፎ እነዚያ የለመዱት ነዳያን በጊዜው መተላለፍ የተነሣ እንዳይሰቀቁና እንዳይራቡ ፩ የተለየ ሰው አውጭ ቀጥረው ያም ሰው አስበ በዚያው በምሳ ጊዜ የሚገባውን ሁሉ ይመግባቸውል ። የእንጀራውም አወፋፈር በጣም የሚያስጐመጅ ነው ። እንጀራ ወጣ በኢትዮጵያ ወጣ ወጣ ወጣ ይህ ነው እንጀራ ማለት ሲሳየን ዘለለ ዕለትነ ብለው ሲመግቧችሁ ኅበነ ዮም ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ወኢታብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም ብላችሁ መቀበል ይገባችኋል ።

ሁለተኛ በየጥፋታቸው ወህኒ ለታሠሩት ሌቦችና ሌላም ልዩ ልዩ ኃጢአት ለሠሩት ሕዝቦች ሥጋ እንዳያምራቸው ብዙ ብዙ ሠንጋ እያስጣሉ ይመግቧቸዋል። ይህንን ማድረጋቸው መንግሥት የሕዝብ ጠባቂ (እረኛ) ስለሆነ ነው ሽማግሎች ልጆቻቸው እንማር ብለው ባወኩ ጊዜና የውስልትና ጕዳና በጀመሩ ጊዜ በግርብረት (በግረ ሙቅ) እያሠሩ እንዳያምራቸው ሥጋ፥ እንዳይርባቸው እንጀራ፥ እንዳይጠማቸው ጠላ እንዳይበርዳቸው ልብስ፥ እያለበሱና እየመገቡ ያቈዩዋቸዋል ማሠራቸው እግራቸው ሲያዝ ወደውስልትና ጕዳና አይቀዳደሙም ትምህርታቸውን ብቻ እየተመለከቱ ጥቂትም በቈዩ ጊዜ የትምህርት ጣሚን ሲቀምሱ በትጋት ተምረው ለመንግሥታቸው አገልጋይ ይሆናሉ። የሃገራቸውንም ከፍታ ፈላጊዎች ይሆናሉ በማለት ነው። ይኸውም እየተፈጸመ እየነው።

እንዲሁ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እነዚህን በወህኒ ያሉ ጥፋተኞች እግራቸው ሲያዝና በዚያም ቦታ መከራ ሲቀበሉ የጥፋትን ጕዳና ትተው ለመንግሥታቸው አገልጋይ ሁነው ለሃገራቸው ከፍታን ፈላጊ እንዲሆኑ እንደአባት እንደእናት እንዳ ይራቡ ሥጋና እንጀራ አብልተው እንዳይጠሙ ጠላና ጠጅ

እንዳይታረዙ በላይ በታች አልብሰው ሕዝባቸውን ይጠብቃሉ ከእግዚአብሔር የታዘዙ ቸርጠባቂ ማለት እሳቸው ናቸው ።

ስስተኛ፥ጌታ ቀድሞ በአሪት እግዚአብሔር ለአብርሃም ሰዶምንአጠፋለሁ ብሎ ቢነግረው፥ጌታ ሆይ ጻድቁንና ኃጥኡን አብረህ ታጠፋለህን በሃገሪቱ ውሥጥ ፶ጻድቅ ቢኖር ሁሉን ታጠፋለህ ቢለው ጌታ ስለ፶ው አገሪቷን እምር ነበር ከ፶ው ፭ ቢጐድል ወይም ፴ ወይም ፳ ወይም ፲ ቢገኙ አትምርም ቢለው ስለ፲ሩ ሃገሪቱን እምራለሁ አለው፤በአንድ ሃገር ውሥጥ ሁሉ ጥፋተኞች ሁነው ፲ሰው ቢገኝ ስለነዚያ እምራለሁ ብሎ ቃል ኪዳኑን ለአብርሃም የነገረ አምላክ እኛም ብዙች በሃገራችን ውሥጥ ሁላችን ጥፋተኞች ሁነን ብንገኝ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደግነት ሃገራችን ጥፋት አያገኛትም በማለት ያለመጠራጠር ሙሉ ተስፋ አለኝ። ነገር ግን ይህንንም ስላልኩ እኛ እናጥፋና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደግነት እንድናለን ማለቴ አይምሰላችሁ።ይህንም የጻፍሁት እሳቸው ያሳተሙልንን ወንጌልና መጽሐፍ ቅዱስ በመመልከት ነው እንጂ የተማርኩ ሁኜ አይደለምና ጥፋት ብታገኙብኝ እንዳታሬዙብኝ አጥብቄ እለምናለሁ ።

ግብረ ድንግል ድባቤ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ብር እጅግ አድርጎ ስለረከሰ በተራ ወረቀት ላይና በሪኮማንዴም ላይ በሚለጠፈው አሁን ለጊዜው ከሚያዝያ ፳፫ቀን ፲፱፻፵፪ ዓመት አንሥቶ በመቶው ፶ መጨመሩን የኢ-ትዮጵያ ፓስታና ቴሌግራፍ መሥሪ ቤት ለሕዝብ ያስታውቃል ሚያዝያ ፳ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓመት አዲስ አበባ ።

የኢትዮጵያ መንግሥት ፓስታና ቴሌግራፍ ዋና ዲሬክተር

AVIS au PUBLIC

L'Administration des postes et Télégraphes a l'honneur de porter à la connaissance du publique par suite de la baisse excessive de la monnaie thaller M. T. tous les affranchissements des correspondances ordinaires tant que récommadés seront provisoirement majorés de 50 o/o à partir du Ier Mai 1950.

Le DIRECTEUR GENERAL des POSTES et TELEGRAHPE.

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የዳግማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጆኦግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሁ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፲ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፲ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የእንቁጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ

ያዲስ አበባ ገባያ አኳኋን

የጅማ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
የሲዳሞ ቡና	፩ ፈረሲላ	፲፩ ብር ተሩብ
ዝባድ	፩ ወቄት	፱ ብር ተሩብ
ሰም	፩ ፈረሲላ	፳፬ ብር
የዝሆን ጥርስ	፩ ፈረሲላ	፻፺፫ ብር
የበሬ ቆዳ የጅማ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የወላሞ	፩ ፈረሲላ	፲፪ ብር
የበግ ቆዳ	፩ ኮረጃ	፲፪ ብርተኩል
የፍየል ሌጦ	፩ ኮረጃ	፳፮ ብር
አቡጀዲ መነጽር	፩ ኮረጃ	፻፴፮ ብር
ባለሰይጣን		፻፳፱ ብር
ባለ ድመት		፻፶ ብር
ባለ አህያ		፻፵ ብር
ባለ ሳቢ ግመል		፻፶፫ ብር
ባለ አንበሳ አሜሪከ		፻፸፪ ብር
ጃፖን		፻፹፯ ብር
ሱኳር	፩ ጆኒያ	፴ ብር
ቻይ	፩ ነጥር	፩ ብር

ስለ ምንዛሬ

አንድ ብር	፲፰ ፍራንክ
በአንድ ብር	፯ ሊሬ ከ ፹ ሳንቲም
አንድ ጊኒ	፲፰ ከ፹ ሳንቲ
አንድ ወቄት ወርቅ ፱	

የርሻና የንግድ ማስፌያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር።

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግር ማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል።የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥የደን፥ የማዕድን ሥራ፥ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።



ዝ ኒ ት የ እ ጅ ሰ ዓ ት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት







አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣምውድ አይደለም ። ከተለየ አስመጭ በኢትዮጵያና በፈረን–ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ ። የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ–ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX,) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኑኑላ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ጥሩ ሩጫ ለሴትም ለወንድም የሚሆን ጠንካራ ባለጌጥ የአቶሞቢል እቃ በየይነቱ የሚፈልግ ከሙሴ ሚሼል ቤት በርካሽ ይገኛል ።

የአቶመቢል ጥሩና ርካሽ ዓይነት ዘይት የጅ ፋኑስ ባለ ኤሌትሪክ ዋና ዓይነት ከነመድኃኒቱ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በየይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባ ሳል ። የልብ ።የደረት ። የጉበት ። የኩላሊት ። የጅማት የጨብጥ የቂጥኝና የቋቁቻ። የሚያዋልድ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከበምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፰
6me ANNÉE №. 18

ሐሙስ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም።
JEUDI 1 MAI 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
I Hayle Sellassé Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ሕዝብ ጕዳት ማሰብ እንዲገባ ።

በዳር አገር ውሥጥ በከምባታ ክፍል በሥራ ምክንያት ተቀምጬ ባይኔ ያዩሁትን የሕዝብ መከራና ጭንቀት ሳይበዛ በጥቂቱ ሳይረዝም በጭሩ የኀዘኔ ተካፋዮች እንዲሆኑ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሐሳቤን አገልጽላቸው ዘንድ ወደድሁ።

አውጫጭኝ ወይም አፈርሳታ ።

በዚሁ አገር ባንድ ዓመት ውሥጥ በያንዳንዱ ሰንጋ ቆሮ ክፍል ሶስት አራት ጊዜ ሌባና ቀማኛ ፈንጋይ ቤት አቃጣይ እንዲወጣ ተብሎ አፈርሳታ ይቀመጣል ፡ ይህንንም አፈርሳታ ይቀመጥልኝ ብሎ የሚለምን ሰው ቤት የተቃጠለበትና ከብት የጠፋበት ብቻ አይደለም ። ሆነ ብሎ መተያያ ይዞ አጥቂ አገረ ገገርውን ጥዋት ማታ የሚነዘንዝ ያገር ባላባት ነው ፥ ይህ ባላባት ያልነው ከላይኛው መስመር በመለክትነው ደጅ ጥናት (ማለት መተያያ ብዛት) ነገሩ ይከናወንለትና እሱም ራሱ የመረጠውን ዳኛና ጸሐፊ ይዞ ይሔዳል። ከሔደማ በኋላ ምኑ ይጠየቃል ዳኛውና ጸሐፊው ከደጓና ቤት ይመራና ለእግራችሁ ሁሉ ድጋፍ፥ ለራሳችሁ ትራስ፥ ለሆዳችሁ የምትጐርሱት፥ ለገላችሁ የምትለብሱት ከምኑ ጐደላችሁ እያለ ያላረባውን የሰባው ሙክት እንደወገን ሲነዳላቸው ደክሞ ያልሰበሰውን የደሃ ብር እንደበረዶ ሲያዘንምላቸው ፥ እነሱም በንዳፍታ ይለወጡና ለሕዝብ ለደሐ ላገር ለመንግሥት ማሰባቸውን ትተው ከሌባው ጐሬ ከባላባቱ ጋር አንድ አካል እንድ አምሳል ይሆናሉ፥ እሱም ባሕርያቸውን ወደሱ እንደተለወጠ ካየ በኋላ አጥር አልታጠረም፥ ሕዝብ ጨርሶ አልከተተም እያለ እያመሀኘ ሌባ ቀማኛውን ፈንጋይ ቤት አቃጣዩን እየጠቃቀሰ ከሞት ከቅጣት ከሥራት ከግርፋት እያዳናችኋለሁ እያለ የብር ምርቱን ይሰበስባል ፤ የልቡም ከደረሰለት በኋላ ወጉና ሕጉ አይቀርም። የሱን መንገድ የማይቃወሙትን አይቶ ነቃሽ አነገሌን ሙርጠናል ብሎ ያስታውቃል። ነገሩም በእሽታ ያልቃል ። ቀድሞውም አፈርሳታ ይቀመጥልኝ ያለበት ምክንያት ለገንዘብ መሰብሰብያ ያህል ነውና ባገሩ ውሥጥ ያለ ሌባና ቀማኛ እንዳይወጣበት እየሸፋፈነ ወፍ ሁነው የሚያወጡትንም እያስፈራራ ያዳፋኝ ያጥር ሰባሪ እያለ መሬት ቈፍሮ ከሚያድረው እውነተኛ ገባር ብሩን ይዘርፋል ።

እውነተኛውም ገባር የደረሰውን በሚያጭድበት ያልደረሰውንም በሚኰተኵትበት ወራት ሌባና ቀማኛ ካገር ላያጠፉለት ቀኑልቀኑለት ወርዶ ዳገት ወጥቶ ቀን በፀሐይ ሌት በውርጭ ደክሞ ለፍቶ ያጠራቀመውን ገንዘብ ለመዝረፍ ባላባትና ያፈርሳታ ዳኛ እንደእንስሳ ባጥር ውሥጥ አጕረው ይጫወቱበታል ። ደሀውም (ባጥር) በበረት ውሥጥ ሁኖ እንደላም እምቧ እያለ ለልጆቹ ምግብ ለመልከኛው ግብር የሚያፈራበት ክረምት ጊዜውን በከንቱ ያባክናል ። መጨረሻውም የሚያርስበት ጊዜ ከማጣት የተነሣ አውጫጭኝ በተቀመጠ ሰዓት ለባላባትና ላፈርሳታ ዳኛ የሚሆን ገንዘብ አላገኝም ሲል ተወልዶ ከደገባት ለምለም መሬቱ አለውድ በግድ ሲያዝን ሲተክዝ ይለያል። ማለት ስደት ይሔዳል።በዚህ ምክንያት በዳር አገር ያለ የግምት መሬት ለም ሁኖ ገባር ከያዘው ይልቅ ጠፍ ሁኖ መልከኛ የያዘው ይበዛል ። ባይበዛ ሳያጋምሰው አይቀርም ለማለት እንችላለን ። ይህንንም የደሀ ኃዘን (ልቅሶ) ወደመንግሥት ጆሮ ባይደርስ ወደ አምላክ ጆሮ ሳይደርስ የሚቀር አይመስለኝም ስል እንደኔ ለምትቈረቈሩ አሳስባችኋለሁ ።

ካሁንቀደም መንግሥታችን የሕዝቡን ቀምበር ለማቅለል ሲል ብዙ ሰፊ ዘመናት ደሀ ሲያበርር አገር ሲያመዘብር የኖረውን ሌባሻይ አጠፋልን። የኢትዮጵያ ሕዝብም ከሊቅ እስከደ-

ቂቅ ሌባሻይ ስለቀረለት ባንድ ልብ ሁና መንግሥቱን እመሰገነ።አሁን ግን ያፈርሳታ ሥራ ከሌባሻይ ጥፋት ይልቅ ዓሥር እጅ የሚከፋ ሆኖ ስለተገኘ ደሀው በጣም አዘነ ማለት በሌባሻይ ጊዜ አንድ በሬ የጠፋ እንደሆን ወይም አንድ ቤት የተቃጠለ እንደሆነ የሰረቀ ወይም ያቃጠለ ደኅና ተኝቶ ሳለ ሌባሻይ ባንድ ደኅና ሰው ላይ ይወድቃል። አንድ ቤት ተዘጋ (ጠፋ) ማለት ነው ። ዛሬ ባንድ በሬ ጥፋት ወይም ባንድ ቤት ቃጠሎ አውጫጭኝ እንዲያወጣ ከ፫፻ በላይ የሚሆን ሕዝብ ይሰበሰባል ። ስለዚህ በላይኛው መስመር እንዳመለከትነው ሁሉ ሶስት መቶ ቤት ተዘጋ ለማለት እንችላለን ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ እንዲህ ብዬ መጻፌ ሕዝባችን ወገናችን በፈርሳታ ምክንያት የሚያገኘውን ጉዳት እንድትረዱት ብዬ ነውእንጂ ሌባሻይ ይሻላል እንደጥንቱ ይሁን ለማለት አይደለም ።

አሁንም በመጋቢት ወር ፲፱፻፳፱ ዓ ም ውስጥ የወላሞ አውራጃ ሥራ ኃላፊነቱ በኔ ስለሆነ ከከምባታ ወደወላሞ ስሔድ አንጋጫ በሚባል ከተማ አራት ትልልቅ አጥር ቆጥሮ ቀኛዝማች ወልደ ማርያም የሚባሉ የሻምበል ዳኛ ሁነው ግማሹ ገበር ተራዳ ተሸብሞ በዘመተበት ግማሹ የመልከኛውን ቤት ዘብ በሚጠብቅበት ግማሹም በልግ በሚዘራበት ወራት አንድ ብረት ተቀማሁ በሚል ሰው ምክንያት ስድስት ሰዓት በሚያስኬድ ጉዳና የተለያየ የሰባት ሰንጋ ቆሮ አገር አስጨንቀው መውጫ መግቢያ ቀዳዳ አሳጥተው ይዘውት አየሁ፤ እኔም በዚያ ሳልፍ አንዱን ጋላ ጠቀስሁና ባጥር ውሥጥ ከገባችሁ ስንት ቀን ሆናችሁ እስከመቼስ ትለቀቃላችሁ ብዬ «ብጠይቀው ከገባን ወር ታሥር ቀን ሁኖናል፣ የምንወጣበትን ቀን ግን እኛ ምን እናውቃለን ባመት ይሁን በለት ዳኞቹ እንዳሰናበቱን ነው ። አሁን ግና እኛ ራሳችን አውቀን ለዳኛና ለባላባት ለጸሐፊ ከሰጠነው መታያያ በቀር ሰባት ሺ ብር ጥሎሽ ጥለውብናል።ይህነን ብር ለማውጣት ትንትን ይዘናል።ጥንቱንም የደሃ ብር ለመዝረፍ ነው እንጂ ሌባ ለመያዝ አልመጡም» አለኝ እኔም ከሱ ጋር ስነጋገር አንድ የታሠረ ሰው አየሁና ይህ የታሠረ ሰውስ ምን የሠራ ነው ብዬ ብጠይቀው «የንድ ወረዳ አገር ሰንጋ ቆሮ ስሙም ባላምባራስ ቃሬብ ይባላል ዋታሠረበት ምክንያት ግን እንዴት በዚህ ሰዓት ግማሹ ገበር ተራዳ ተሸክሞ በዘመተበት ግማሹም የመልከኛውን ቤት ዘብ በሚጠብቅበት፥ በልግ በሚዘራበት አሁን አፈርሳታ ይቀመጣል እዚህ ተቀምጠ የመልከኛው ቤት የተሰረቀ እንደሆን ከፋዩ እሱ አይደለም ወይ ባገር ባግራችን ሌባና ቀማኛ ያለብን ከባላባት ጋር ሁነን አውጥተን እንስጥ ባላባትና ቆሮ ያላወቀው ሌባ የለ ደሃው ዘማች እስኪመለስ ድረስ ዘብ የሚጠብቅ የሚያርስ እርሻውን ይረስ ለምን ይጉላላል ብሎ በስልክ ወደመንግሥት ቢጮህ ባላባትና ያፈርሳታ ዳኛ አሠሩት እንጂ ሌላ ጥፋት የለበትም» ብሎ ነገረኝ።እኔም በነገሩ ሁሉ ሳዝን ስተክዝ መንገዴን ሔድሁ ።

ወላሞ ደርሼ ስመለስም ባላባቱና ዳኛው ባላምባራስ ቃሬብ ለጮኸበት ነገር መልስ መጥቶባቸዋል መሰለኝ ቆሮውንና ጭቃ ሹሙ ያገር ሽማግሌ እየመረጡ አይነግ አፈርሳታ ያውጣልን እያልህ ፈርም ብለው ያጣድፉት ነበር።እንዲህ ማድረጋቸው ግን የራሳቸው ጥቅም እንዳይጉድልባቸው ነው እንጂ ለደሃ አዘኔታ አልመሰለኝም።

አሁንም ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ መንግሥታችን የሕዝቡን ቀምበር ለማቅለል ሲል በዳር አገር ውሥጥ ለሚሠራው ያፈርሳታ ሥራ ሌላ የተሻለ ደንብ ቢያወጣለት አገሩ ለምለም የጠዳ ሕዝቡ ሀብታም ባለጸጋ በሆነለት ነበር ስል የሰናፍጭ ቅንጣት በምታህል ዕውቀቴ እስቤ የጻፍኳትን ቃል አቀርብላችሁ ዘንድ ደፈርሁ።ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም።

ስለ ተስፋ ።

ተስፋ ሆይ በከንቱ ቤት እየገባህ የሰውን ሐሳብ ታጥናናለህ በሁሉም ቤት እኔ አለሁ እያልህ የሰውን ሐሳብ እያበረታህ ግማሹን ደስ ታሰኛለህ ግማሹን በፍጻሜ ታሳዝናለህ። ሰው በተርፋ የማይደርስበትንና የማይገባውን የማይችለውን ሲያስብ ምኞቱ ወደ ሰማይ ይደርሳል።የሰው ሐሳብና የውሻ ጅራት ሁል ጊዜ ወደላይ ነው።ስለዚህ ሰው በተስፋ ጠላቱን አጥፍቶ ምኞቱን ለመፈጸም ፈቃዱ ስለ ሆነ በሰውላይ ሕግ ተሠርቷል ከሕግም ያለፈ በሕግ ሲቀጣ ለሁሉም ቀር አይል ። ግን በዚህ ባሁኑ ብርሃን መሪና ደጋፊ እያለን በያለበት መደናቀፍ ያሰድበናል የሥራ መሠረት አንድነትና መስማማት መታዛዝና እሺ ማለት ነበር ጃንሆይ ንጉሥ ሕዝቡን አንድነት ሰብስበው በፍቅር ለማስማማት ፲፫ ዓመት የሰው ደም እንዳይፈስና ሀገራቸው እንዲጠበቅ የሰውን ጠባይና አመል በትዕግሥት ስለ ተሸከሙ ብዙህ ልዩ ልዩ የሆነ ፈተና ቢደርስባቸው አልተበሳጩም።ይኸንንም ያለፈ ዘመን ጊዜ በማሳለፍ አንቀጡ ጠርው የሥራ መሠረት እንበለው ።

እዚህ ሥራ ይዘን በዚያ ዓመት ባል ኑሮ ።
በነፍስ ጨዋታ ታዘዘ ዘንድሮ ።
ግማሹ በፈረስ ግማሹም በተኩስ ።
ግማሽ በሽቅድድም ግማሹ በጉግሥ ።
በሞት ተወራርዶ ሌት ሲገሰግሥ ።
የውጭውም ሲስቅ የጓቢው ሲያለቅስ ።
ባየር ላይ ቢቀድም የጠቅል ፈረስ ።
ጭብጨባው ተሰማ እስከዚህ ድረስ ።
በሽቅድድም መስሎት ጉግሣያውቅ ኑሮ ።
ከፈረሰላይ ወድቆ ቀረ ተሰባብሮ ።
ተወራርዶ ነበረ ተረታ በሞት ።
ጓዙን ጠቀለለ ተውት አታንሡት ።
ያበረደው መስሎት ያሳቡን ጥማት ።
የጠማው ልጅ ጠጣው ይኸንን እሳት ።
ተጽፎ የለም ወይ በቀድሞ ዘመን ።
ካራ እፎቱን ሲቆርጥ ደበም እራሱን ።
እኛ እሚያሳዝነን የሚጸጽተን ።
የስንቱን ቤት ዘግቶ ያ ስለቅስ ይሆን ።

ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ ሰማዕት ።

እውነተኛ የምስጋና ቃል ።

ክቡራን ጌቶቼና ወንድሞቼ ሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ባለፈው ሰፊ ዘመናት ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ተብለው ይህችን ለምለም አገራችንን ከብዙ ነገሥታት ጋር አስተዋውቀው ሕዝቧንም ከድንቁርና ወደውቀት፤ ከጥፋት ወደሕይወት፤ከጨለማ ወደብርሃን መርተው አስከብረው አሳፍረው አቂየዋት። አሁንም ንጉሠ ነገሥት ከተባሉልን ከዚሁ የበለጠ ሥራ እንዲሠሩላት ብዙ ተስፋ አለንና ለዚሁ ደግ ሥራቸው ተቃዋሚ አሰናካይ የሚሆን ሁሉ እንዲጠፋ ከሀናት በጸሎት፤ ምንስቴር በምክር፤ ወታደር በጕልበት እንዲረድዋቸው ርኅሩኅ አምላክን እንለምናለን ፤ ንጉሣችን ሺህ ዓመት ይግዛ መንግሥቱ ለልጅ ልጅ ይሁን፤ የኢትዮጵያ አድነት ለዘላዓለም ይኑር ብዬ ምኞቴን እያቀረብሁ ከዚሀ በታች ትንሽ ግጥም አጽፋለሁ ።

«አዋጅ ስማ ስማ ያገሬ ሰው ሁሉ ።
ዳኛችን ተፈሪ አምላክ ነው ይላሉ ።
ሙታን የሚያነሣ ፈጽሞ በቃሉ ።
ሾላችን አፍርቷል ዛሬ በጥቅሉ ።
እስራኤል (የኢትዮጵያን) ወፈፉ ያንን እየበሉ ።
ከነዚያም መሃከል አሉ ያልታደሉ ።
ፍሬውን በያመቱ እንዳይካፈሉ።
ምነው በየዛፉ ባይንጠላጠሉ።
በየዛፉ ሁሉ የተንጠላጠሉ ።
እነማን አፈሩ እነማን በቀሉ ።
አረው ረግፈው ቀሩ በዚያው እንደዋሉ ።
  እኔ ላባ ጠቅል ጽፌ ተአምር ።
መንግሥቱ ሰመያት እንዳገኝ ሀገር ።
ለሰሚዕ ደስ ይላል የሚያምር ነገር ።
ለቅድስት ሀገሩ ሲረዳ በምር ።
እውነቱን ገልጦ ነው ሳይጠራጠር ።
ጥዑመ ሃይማኖት ያረመኔ ክር ።
  መልክም ሸማ ፈትሎ ሸዋ በየቤቱ ።
ሁሉም ባደበባይ ለብሷል እንዳአበቱ ።
ጥበብ ላባ ጠቅል ብትሰጠው ዘውዲቱ ።
ለምንት እንገለጉ አሕዛብ በከንቱ»

ስላንድነት ።

የኢትዮጵያ ጀግና በሄድህበት በታ።
ያገርህ አንድነት እንዳይላላ ታታ ።
እንኳንስ ሊፈታ መላላት አያምረው ።
በደኅና ጊዜ ነው የተጠቀለለው።
ገመዱን ለመፍታት የምትሞክር ዘመድ።
የኢትዮጵያ ጀግና ያደርግሃል አመድ ።
ተፈሪ አባ ጠቅል ያከረረው ክር።
ያገሩን አንድነት አስሮ በፍቅር ።
ያስተካከል ጀመር ዳርና ደንበር።
«የቶጵያ አንድነት ብረት ነው ጠንካራ ።
የእግዚአብሔር ሕንፃ ነው መሠረቱ ኖራ ።
እንኳን መፍረስና መዝባት አያስፈራ ።»
ብሎ ጽፎ ነበር ነጋድራሳችን።
ዛሬም ደጋገምነው ቢጥመን ቃሉን ።

ስለምንኩስና ።

ምንያለው ጭንቅላት እንዴት ያለ ራስ ነው ።
አንዱንም ሳይማር መጠምጠም ያማረው ።
ያገራችን ራሶች ቆብ መጫን ፈለጉ።
የምንኩስናው ደንብ ሳይማሩ ወጉ ።

ያገሬ ሊቃውንት በጣም ተምረዋል ።
ለማይገባው ሰው ሥልጣን ከልክለዋል ።
የቆብ ስፍ የሚያውቁ አባ ዳንው ናቸው።
ለሁለቱ ብቻ ሰፍተው ተዉላቸው ።

አሁንም አንድ ሰው ቆብ መስፋት ተምሯል ።
ቶሎ አደራጅቶ በራሱ ደፍቶታል ።
አባ ብቻ እንዳይሆን እንዲባል ቀደስ ።
በዙርያው ከበውት ስድስት ጳጳስ ።
እንዲህ ያለ ዕድል እንዲህ ያለ ንግሥ ።
አምስተኛ ሁኖ ገብቶ በመቅደስ ።
በገዛ ሥልጣኑ ሆነ መነኩስ ።

እንዲያው አለመማር እንዳይሆን ሥልጣን።
አሁንም የኛ ራስ አወቀው ቍርጡን ።
ይሻልህ የነበር ከጥምጥምህ መኖር።
ለማይገኘው ቆብ አጕል ከመጣጣር ።
«ሺበም የበከረ ልጅ ቆብ የሚያገኝ መስሎት ።
ወርዶ ሕጥቶ ቀረ ዳገት ከቍልቍለት ።
አንዲቱ ሴት ተገኘች የምታውቅ ቆብ መስፋት ።
ሹልክ ብላ ገባች ራሱን ለመለከት ።

ወዲያው በቀስታ ምሥጢር አካፍላ።
ቶሎ ተመለሰች ራሱን አንጠልጣላ ።
ሊታረድ የነበር ብዙ በግ ለድግስ ።
ጠሙን ተመለሰ ዲያቆን ከቆመስ ።
የኢዮአብ ጭፍራ በጣም ደስ ብሎታል ።
ስለጥቃቅን በግ ሙክት ታርዶለታል»

(፪ሳሙኤ ፳ም ፩ ፳፪)

ዛሬም ያገሬ ሰው ይህን ምክር ሰምተህ።
ሙክቱን ማረድ ነው ጥ፡ቅኑን ትተህ ።

እኒሀ ጥቃቅኖች ብዙ ነው ጥቅማቸው ።
አልበ መጠጣት ነው ወተት ወተታቸው ።

ያነበብነው ሁሉ እንዲሆን ይሁን ።
ወይበል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን ።
ብሎ ይፈጽማል አጭር አሳቡን ።

ከምባታ (ሆሣይና ከተማ) ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘተሐረ አክሱም ።

ክቡር አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ።
የብርሃንና ሰላም ዲሬክተርነት በመሾምዎ ወዳጆችዎ
ሁሉብጣም ደስ ብሎናል ፡እንኳን ደስ ያለዎ ።

ክቡር የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ከዚህ ቀጥሎ የጻፍሁ- ትን ቃል እንዲያሳትሙልኝ በማክበር እለምንዎታለሁ ።

የተላከ ከናታችሁ ከምትወዳችሁ ከምታከብራችሁ ከኢ- ትዮጵያ ይድረስ በየሀገሩ ወደምትኖሩ ልጆቼ እጅግን እንደት ናችሁ እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደኅና ነኝ። ከዚህ ቀደም ታላቅ ወንድማችሁን ነፍሰ ጡር ሁኜ ጤና እጦቼ እኖር ነበር- ሁኝ።አሁን ግን በእግዚአብሔር ቸርነት በናንተ ጸሎት የውበት መጨረሻ የሆነውን ልጄን ቀዳማዊ (፩ኛ) ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያን ወለድሁ ። ደስ እንዳለኝ ደስ ይበላችሁ የንብረቴንም ልኩን አወቃሁት፡ መልኬም እየደረ እያማረ እየ ተዋበ ሄደ፡ እኔንም ለማግባት ያልተመኘ አልነበረም እግዚአ- ብሔር ይመስገን ሀኃይለ ሥላሴ ታጭቼለሁ፡ ጠላቶቼም አፍረው እንደቀሩ እናንተም ሳታውቁት አልቀራችሁ፡ይህም የበሀር ልጄ እናንተንና ድምበሬንም ጠብቆ የሚኖረው እውነተኛ የዘላለም ምርቃቴን የሰጠሁት ነውና እናንተም ደግሞ ከክፉት ርቃችሁ ለዕድሚው እየሳሳችሁ እንድትረዱት አጥብቄ እለምናችኋለሁ ክቡሩን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ከዚህም ቀጥሎ ጥቂት ቃሎች እጽፋለሁ ፡ ከነውረኛ ልጅ አስተዋይ ባሪ ይሻላል ያለውን ሰሎሞን በሰበው መጀመሪ ያገለግል እንዲያርፍ ይገ- ብዋል ማለት ስለመሰለኝ በሀገራችን ባዬ ዮሐንስ ጀምረው ያገለገሉ ብዙ ሽማግሌዎች አሉ፡ ልጆቻቸውንም ለሥራ ያደረሱ ብዙ ይገኛሉ።እነዚህ ሲያገለግሉ የኖሩ ሽማግሌች ግን እተሰ- ጣቸው ጎዞትና ርስት እየሔደ ዕድሜ (ሳ፩ኛ) ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያሉ ቢጦሩ ደስ ያላቸው ይመስለኛል። አባቶቻቸው እንዳገለገሉ ደግሞ ልጆቻቸውና የገራችን ወጣቶች ተስማምተን ወገን ሳንለይ በሰላም ስሀገራችንና ለመንግሥታችን ልናገለ- ግል ጊዜያችን ነው። እህል ተዘርቶ ካልታረመ ፍሬ አይሰጥም ሽማግሌም ልጁን ተክቶ ካላረፈ ደስ አይለውም።ይኽንንም ቃል እንድጽፍ ያነሣሣ አንድ ቀን በመ ንገድ ስሔድ ፫ሽማግሌች እፊት እፊቴ ሲሔዱ እኔም በቤቴ አኳኋንና በችግሬ እየተከ- ከዝሁ በኋላቸው ስሔድ እርስ በርሳቸው እንዲህ እያሉ ሲጫወቱ ሰማሁ፤፫ ንጉሥ አግልግለን አሳለፍን፤አሁን ደግሞ ብወር ተራና በማናውቀው ሥራ ኑ ሥሩ እያሉ ያለፉናል ምነው ከማደጎችን ግማሽ ባማሹን መንግሥት እየወሰደ ይህን በከ- ተማ ውሥጥ ሥራ የፈታ ወጣት ሁሉ በየሥራው ባገቡልን ደግ ነበር እያሉ ሲወያዩ ስለ ሰማሁ ነው እንጂ እኔ ዕውቀት አለኝ ብዬ አይደለም።ላሁኑ የታየኝን በማኅተም እንዲታተምልኝ ብዬ ጽፌያለሁ በገደፍሁም ማኅተሙ ያርመው ።

ከጨለማ ብርሃን ይሻል እንደሆን ።
ያገሬ ወጣቶች አብረን እንሁን ።
አንተ ካሣ ገብሬ ምነው ፍራትህ ።
በኃይሌ አደለሞይ እኔ እምጠጋህ ።

መፍቀሬ ብሄሩ ባሕሩ ኒከላ ።

ሕልም አይታመንም ።

ሕልም ታዳነው የገደለው ይበልጣል።ያዳነውም በያዕቆብ በነዮሴፍ ጊዜ ነው እንጂ ። በሀገራችን ሕልም ተመግዶል በቀር ያዳነው የለም ። መጀመሪ አፄ ዮሐንስን የመሰለ አገሩን ወዳጅ ንጉሥ ገደለብን።አገዳደሉም እንዲህ ነው፤ሰኃጢ ወርዶ ው ከውጪ የመጣ ጠላታቸውን ለመውጋት እምሺግ ውሥጥ ገብቶ በዚያ በረሃ ሰፍረው ተቀምጠው ሲጠባበቁ ንጉሥ ምኒልክን በሸዋ፡ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በጐጃም እንዲሠው ነበርና ሁለት ንጉሦች እንዴት ላንድ ንጉሥ እንገዛለን ኢትዮጵያን ለሁለት አድርገን ተክፍለን እንግዛት ብለው ቢከድዋቸው ከቤቱ ያለውን ጠላት ትቼ ከውጪ ጠላት ምን አጣለኝ ብለው በክረምት ገሥ- ግሠው ወደ ጎጃም ተሻገሩ። ንጉሥ ተክለሃይማኖትም ወደ አምባ ገቡ ። አገሩም እጅግ ተዘረፈ ይባላል። በኋላ ተንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታርቀው ወደ ሸዋ ለመምጣት ተነሡ፤ በዚያን ጊዜ ሕልም አላሚዎች ቀርበው ጃንሆይ ወደ ሸዋ የሄዱ እንደሆን መንግሥትዎ ይቄያል፤ ወደ መተማ የወረዱ እንደሆን በሰማዕ- ትነት ይሞታሉ አልዋቸው ። እንዲህም ማለታቸው አፄ ዮሐንስ መንፈሳዊ ናቸውና ይህን ቃል ሰምተው እምቢ አይ- ሉንም ብለው ነው።እነሱም ይህን ምክር የተቀበሉት ከጠላቶ- ቻቸው ነው ይባላል ።

ይህንም ነገር አፄ ዮሐንስ በሰሙ ጊዜ ከምድራዊስ መንግሥት የሰማያዊ መንግሥት ይሻለኛል ብለው ወደ መተማ ወርደው ከድርቡሽ ጋር ሲዋጉ ለጊዜው ድሉ ለሳቸው ሊሆን ነበር።በኋላ ቢአስቡ ሕልም አላሚው የመንግሥተ ሰማይን ተስፋ ነግሯቸው ሞትን አስመርጧቸው ነበርና መንግሥተ ሰማያት እንዳትቀርባቸው ሞታቸውን ወደዱ። ከዚህ በኋላ ከወዳጃቸው ከእጬጌ ቴዎፍሎስ ጋራ ተመካክረው በሩቅ እንዲያሰያቸው በወርቅ መጣምር በተጫነ ፈረስ ተቀምጠው፤ግምጃ ጥላቸውን አሲዘው፤ ጳጳሱም እጨጌውም ግምጃ ግምጃ ጥላቸውን አሲዘው ወደ ምሽጉ ሲቀርቡ ንጉሡ በፊት ነበሩና ፈረሳቸው በፊት ቈሰለ። ከዚህ በኋላ ደግሞ ሌላ ሌላ ፈረስ አቅርቡልን ብለው አዘዙ፤ እጨጌም ቢገላግሉ ያችን የመንግሥተ ሰማይን ተስፋ ከአላሚው የሰሙትን አረሱምና እምቢ ብለው ሁለተኛ በሌላ ፈረስ ተቀምጠው ወደ ምሽጉ ቀርበው ጭንዎን ቈሰሉና ወደቁ የሚፈልጉትን ከተቀበሉ በኋላ የቀድሞ ሰው እንደ ዛሬ ሰው ችሎል አልነበረምና ንጉሡን ወደ ድንኳን አግብተው ልጅ አግርን ሰው ሁሉ ከልፍኝ ከልክለው ሽማግሎች በጃንሆይ ቃል አዋጅ አስነግረው ሕዝቡን ሰብስበው ይዝዋቸው ተመለ- ሱ፤መቀሰላቸውን ጠርጥሮ በነገው ደርቡሽ ተከተላቸው፤በዚያን ጊዜ ብዙ ሕዝብ አለቀ።ጃንሆይም እዚያው ቀሩ እሚበልጠ- ውም ሠራዊት ጥሉአቸው ሸሸ ፤ የታመኑ አሽከሮቻቸውም ሣጥናቸውን ተደግፈው ተታኩሰው እዚያው ቀሩ፤እርስ በርሱ የተፋጀውማ ሕዝብ ልክ የለውም።እንደኛ ሀሳብ ግን ያን ጊዜ ድል አድርገው ቢሆን ኢትዮጵያ ትሰፋ እንደነበረች ጥርጥር የለውም ።

ይልቁንም ሰማዕትነት አገኛለሁ ብለው ባይሞቱ ብዙ ሕዝብ አያልቅም ነበር ። ምን ይሆናል ያለፈ ነገር አይመለ-

ብም እንጂ ጽድቅስ ሰውን በማዳን ነበር ። በመጨረሻ ተጠልፎ እማይወድቀው አንበሳ በትንሽ ክር ተጠልፎ ወደቀ ። ፪ኛ፡ራስ ዘውዴ የጃንሆይ ያጼ ምኒልክ አሽከር የታመኑ ጀግና ሌባና ወምበዴ እማይወዱ መልክም ዳኛ ነበሩ።ራስ ወልደ ሥላሴንና ልጃቸውን ደጅ፡ዝማች ነጋሽን ወግተው ስሜንን በጌምድርን እየገዙ ለጌታቸው ታማኝ ሁነው ሲኖሩ፡ ባለ ሕልም መጥቶ ይነግሣሉ አላቸው እሳቸውም እውነት መስሎአቸው በዚያን ጊዜ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ወደ ከፋ ዘምተው በለቤታቸው ወይዘሮ ላቀች ከጥቂት ሠራዊት ጋር ቀርተው ነበርና ጐጃምን ለመያዝ ሲአስቡ ሰምቶ አዝማሪው ንጉሥ ወደ ከፋ ታደረጉ ጉዞ፡ዘውዴን ዘውድ አማረው ራስ ወርቁን ይዞ፡ ብሎ ገጠመ ከዚህ በኋላ ማፋከር ሆነ ። ጃንሆይም ቢጠሩአቸው እምቢ አሉ ። ከዚህ በኋላ ራስ ወሌን ከየጁ አዝዘው በበጌምድር መኳንንት ሁሉ ወረቀት ላኩባቸው መኳንንቱም ራስ ዘውዴን ምንም ብንወዳቸው በመንግሥታችንና ባገራችን አንለውጣቸውም ብለው ራስ ዘውዴን ከዷቸውና ወደ ራስ ወሌ ገቡ። ራስ ዘውዴም ሸሽተው ማር እምባ ገቡ ።

ከዚህ በኋላ እጃቸውን ሳይነኩ ወደ ጃንሆይ ሊወስዷቸው ታረቁና እጃቸውን ሰጡ ። ራስ ወሌም ራስ ዘውዴን በቀምበር አነዷቸው ። ምነው እጄን ሳትነከኝ ምለህ አልነበርህምን ቢሏቸው አሁንም እኔ መሀላዬን አላፈረስሁም እንገትህን ነው እንጂ እጅህን አልነካሁም አሏቸው።በቀምበር እየጐተቱ አዲስ አበባ ድረስ ሳኳቸው። ጃንሆይም ቀምበሩን አውልቁለት ብለው ምን ሆንህና ከዳኸኝ ብለው ቢጠይቋቸው ጃንሆይ ሕልም አለሚነዋ እንዲህ ያደረገኝ አሏቸው። ጃንሆይም ወይ የመንግሥትን መከራ አለማወቅ አሳብህን በሰው ላይ ጥለህ መኖርህን ትተህ ብለው ወደ እሥራት ሰደዷቸው ። ዘውድ የተባለውም እሥራትና ውርደት ሆኖ ቀረ ።

፫ተኛም፡በራስ ጉግሣ ወሌ ይህን ሁሉ መከራ ያመጣባቸው ሕልም ሳይሆን አይቀርም።መጀመሪ መኳንንቱን ሰብስበው ከዚህ ቀድሞ ወደ ራያ ታዝዘን ይህን ያህል ጊዜ ቈየን።አሁን ደግሞ ሠራዊትህን ሰብስብና ወደ አዲስ አበባ ና ብለውኛልና እንዴት እናድርግ አገራችን ላይ እንሙትን ወይስ እንሒድ እስቲ ምከሩ ቢሉ፡አዛዥ ቃምራት የሚባሉ ታላቅ ሽማግሌ ተነሥተው ለሰው የተገዛ ሰው ማታቢልኩት ማታ ጧት ቢልኩት ጧት ይሄዳል እንጂ ይህ ምን ያማክራል ቢሏቸው አስወጣ ብለው አስገፍተው አወጧቸው ። ከዚህ በኋላ አሳባቸውን አወቀና ሕዝቡም እዚሁ እንሞታለን እያለ ይፎክር ጀመር።ግን ይህ ስሕተት የተጀመረው ከምሥጢረኛቸው ከአለቃ መኰንን ተክሌ ሳይሆን አይቀርም።እንዲህም ማለታችን እሱ የተማረሰው ነበርና አገራችንን ሕዝባችንን አጥፍተን የሐሰት ምስክሮች ሁነን ብንሞት ምን ጥቅም አለን ብሎ መምከር ይገባው ነበር ብለን ነው ። ደጃዝማች ነጋሽ የሚባሉ የራስ ጉግሣ ወሌ የሀገር እንደራሴ በጦርነቱ ውሥጥ በመድፍ እግራቸው ተሰብሮ ተገኙና ሐኪሙ ቃልተቈረጠ አይድኑም ቢላቸው ለኔስ ሞት ነውና የሚገባኝ እባካችሁ ጨርሱኝ ብለው ለመኑ፡ ይህም እንዳልሆነላቸው ባዩ ጊዜ ኑዛዜአቸውን ጀመሩ ።

በራስ ጉግሣ አትፍረዱ፡አጥፊዎች እኛነንና ጨፌሆ ስንደርስ ተወ ለማንጠቀምበት ነገር ይመስለኛልና እጄን ልስጥ ቢሉ ደብረታቦር ሁነው የተናገሩትን ቃል ረሱት ወይፈ አይሆንም ሞት ይሻለናል አላቸው አለቃ መኰንን አሉ ይባላል። ይህንም ማለቱ የዚያ ሕልም መላከተኛ እሱ ይሆናልና ነገሩ እንዳይታጠፍበት ይሆናል እንጂ ራስ ጉግሣ ወሌ ቢሆን ምሕረት ባይሆንም ታሥረው ከጠጅ ከክብረት ይለያሉ ብሎ አዝኖላቸው አልነበረም ። እሱም ጮሌ ነውና እዚያው አብሮ ሞተ። ሕልም የበደለውን ምንም በጋዜጣ ጽፈን ባንጨርሰው በቅርብ ጊዜ የሆነውን ጽፈናል።መቸም እግዚአብሔር በቸርነቱ በሕልምም ሆነ በራእይ ጥቂት ጥቂት ምሥጢር ይገልጽ ይሆናል ነገር ግን ሲሆን ማወቅ ነው እንጂ ሳይሆን ማመን አይገባም።

በክፋትና በተንኰል ስለተደረገ ነገር መጻጸት ይገባል ደላል።

ነገሩ የሚያስፈልግ ነው

በኛ ጊዜ ብርሃንና ሰላም ንስሐ ግቡ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለሥላሴን መንገድ አብጁ፡ ጐዳናውንም አቅኑ እያለ በኢትዮጵያ የሚጮህ ያዋጅ ነጋሪ ድምፅ እርሱ ነው ነቢዩ የጻፈለት ። እነሆ ፀሐይ ሊወጣ አቅራቢያ በሰማይ ጥግ ሳይታይ ምሥራቅን የሚያነጣ ጮራውን ይሰዳል።ይኸውም የቀን መልከተኛ ስለሆነ ነግህን ያመለክታል። እንዳዚሁ ሁሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለዚህ መንበረ ዳዊት በታጩ ጊዜ በግርማቸው ብርሃን ሳይታዩ አስቀድመው ብርሃንና ሰላምን በፊታቸው እንዲሔድ በቅርቡ መንግሣቸውን የምሥራች እዲል በጮራቸውና በጥበባቸው ጌጥ አበሩት።

ነገር ግን ይህ ሁሉ ሲሆን ሥራዎቻቸው የሚበቃ ምስክር ከሚሆኑዋቸው ከንጉሠነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በፊት ብርሃንና ሰላም እንዲቀድም ስለምን አስፈለገ ? ቢሉ መጀመሪያ አበቱ እእምሮ አንተ ሕፃን የልዑል ነቢይ ትሆናለህ ብሎት ነበርና የርሳቸውን ታላቅነት ለኛ ሊያስተምረን ነው። ሁለተኛም የመጀመሪያዎቹ ምስክሮች በራሳቸው ሳይሆኑ ከሌሎች ይመጡ ዘንድ ስለተገባ ነው። እንበለዚያ እርስዎ ለራስዎ ይመሰክራሉ።ምስክርነትዎ ምንም አይደል ብለው ይከራከሩዋቸው ነበር።የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንገድ የሚያዘጋጀው በዚህ የሥልጣኔ ምክር ነው በዚህ በሥልጣኔ ምክር ሳናሰናዳ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥትን የውቀት ጥምቀት ለመቀበል አንችልምና ነው ። በዚህም የሥልጠኔ ምክር ቃል የብርሃንና ሰላም ቅናት ይታያልና እንደርሱም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መስበክና ማስተማር ይገባቸው ነበርና ጊዜው መድረሱን አይቶ ብርሃንና ሰላም ዕድሜው ፯ዓመት ያህል ሲሆን የ ግ ን ነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንገድ ለማዘጋጀት ስብከትን ጀመረ። ጸሐፊው ብርሃንና ሰላም ይኖርበት የነበረውን ኢትዮጵያ ሲል በማስከተሉ አዲስ አበባ መሆኑን ያመለክታል። በአዲስ አበባ ውሥጥ ስብከቱ ለተሳዳቢ ሕዝብ ማጕረምረሚያና መሰለቂያ ሳይሆን በእውነተኛ መንፈስ ቃሉን ከሚቀበሉና ከሚሰሙ ሰዎች በተቀር ሌሎች አልተገኙም ።

ንስሐ ግቡ ፤ ባደረጋችሁት ነገር ተጸጸቱ ብሎ መንግሥተ ሰማያት ከሰማያት የተሰጣችሁ መንግሥት በቀረበ ጊዜ ንስሓን የሚሰብከው ስለዚህ ነው ። የተነቀለን ስርጥ የሚደለድልልን ከክህደት ገደል እንዳንወድቅ የሚመልሰን እምቢተኝነትን ከውርደት ጋራ በማሳሰብ ፤ ሁለተኛ ተመልሰን እንዳናደርገው ቍርጥ ሐሳብ (ፈቃድ) የሚያስደርገን ንስሓ ግቡ ማለት ትርጓሜው ባደረጋችሁት ተጸጸቱ ማለት ነው ። እነሆ ብርሃንና ሰላም በመቅደሙ ብቻ ቸርነትና ምሕረት የመላው የንጉሠ ነገሥት መላክተኛ መሆኑ ያስረዳናል ። እንደምን ቢል የክፋትንና የበደልን መርሰት ተስፋ ያስደርጋል እንጂ ኃፋዎችን አያስፈራራም ነገር ግን ብርሃንና ሰላም ምን ያስገድደናል ቢሉ ንስሓ ግቡ ባደረጋችሁት ተጸጸቱ ይለናል እንዴት ያለ ታላቅ ደስታ ነው ተጸጽተን ክፉ ሥራችንን በተውን ጊዜ ከድኅነት በራቀ ሀብት ያበለጽገናል ። ፍጻሜው ከሰማያት ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተሰጣቸው ፍርድ ትክክልነት ዕዳችንን በጸጸት በከፈልን ጊዜ በኢትዮጵያ ሀብት አሳባችንን እናገኛለን እንጂ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የምንሰጠው ነገር የለም።ንስሓም (ጸጸት) ልባችንን ያነጻል፡ አእምሮዋችንን ያበራል። ዕውቀትን ለመቀበል ሰውነታችንን ያዘጋጃል ፡ መንግሥተ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀርቧል ሲል የሚያስከትለው ከጠገቧዮችም ከናዝሬውያናችም (ናዝራዊ) ከታላቆችም አፍ ያልተነገረው በዚህ በሚሰብከው ነገር አዲስነት ምኞታችንን ቀስቅሶ እንማሥቶ ለዚህ መንበረ ዳዊት የተገቡ መሆናቸውን ካስረዳን በኋላ በእውነት እንድንወዳቸውና በፍጹም እንድንከተላቸው ይገልጽልናል። መንግሥተ ሰማያት ፪ት ልዩ ነገር ትሆናለች፡መጀመሪያ የእግዚአብሔር መንግሥት በውሥጣችሁ ነው ሲል ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ይሆናል።ሁለተኛ የእግዚአብሔር መንግሥት ከላንት ትወሰዳላች ፍሬዋንም ለሚያደርጉ ትሰጣለች ሲል ስለ ሹመት ይሆናል። ሌሎቹ ሁለቱ ስለቅድስት ቤተክርስቲያንና ስለ ዘለዓለም ሕይወት ይሆናሉ።እንደዚሁም በምድር ስንኖር በቅድስት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ስንፈጽም ለእንደራሴዎቹ ለነፍስና ለሥጋ ግንባሮቻችን ብንታዘዝ የዘለዓለም ሕይወትን እንወርሳለን መንግሥተ ሰማያትን እንከፈላለን ።

ደግሞ ባነጋገራችን ዓይነት ድምፅ ሲጮህ እንሰማለን ብርሃንና ሰላምም የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃ ውራሪ ድምፅ መባሉ ለሰው ሁሉ የልዑል ራስ ሥኮንንና የዳግማዊ ምኒልክ ልጅ ቃል የሚያሰማ ምሥጢራዊ ድምፅ ስለሆነ ነው፤ ድምፅ በራስ ድብልቅልቅ ያለ ያልተፈጸመ ምንም የልብን ምሥጢር የማይገልጥ ነው፤ብቻ ድምፁን ከፍ የሚያደርግ አንድ ሐሳብ ሊያስታውቅ እንደሆነ ያመለክታል ።

እንደዚሁ ብርሃንና ሰላም ድምፅ የተባለ ስለምን ? ቢሉ ኢትዮጵያ ብርሃንና ሰላም የምኞቷን ድልብ(መዝገብ)እንዲያስታውቅ አልመረጣቸውም ያሰናዳቸውን አንድ ታላቅ ሐሳብ የምሥራች እንዲል ነው እንጂ የናትነት ፈቃዷን ምሥጢራውያን ሐሳቦች የሆኑ እንደሆነ በብሩህነታቸው አከታተል በልጇ በቃልዋ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንድትገልጽላቸው ተስፋ እናደርጋለን ለዘለዓለም ይኑሩ። አስፋውአንዳርጌ ድሬ ዳዋ ።

የስቅለትና የትንሣኤ በዓል በግሪክ ቤተ ክርስቲያን።

የአኩስም ጳጳስ ፓትሪያርክ ኒኮላ ቀድሞ እዚሁ የነበሩት አሁን ደግሞ እንደገና ወደ አዲስ አበባ መጥተው ዓርብ በ፫ ሰዓት በዓለ ስቅለትን ለማክበር ግሪካውያን ም ሁሉ በቤተ ክርስቲያናቸው ተሰብስበው መብራት አብርተው ውዳሴ አደረጉ ። ፓትርያርክ ኒኮላም ስለ ኢትዮጵያና ስለ ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ስለ ልዕልት ወይዘሮ መነንና ስለመኳንንቱ ስለ ሕዝቡ ሁሉ ጸሎት አደረጉ።

በበዓለ ትንሣኤም እንደዚሁ በከተማ ያሉ ግሪካውያን ሁሉ ተሰብስበው ፓትሪያርክ ኒኮላ ቀድሰው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ተናገሩና ሕዝቡን ደስ አሰኝተው አሰናበቱት።

የሳት አደጋ በአዲስ አበባ ።

በሚያዝያ ፳ ቀን ሰኞ ከሌሊቱ በ፫ ሰዓት ሱቁን ዘግተው ሠራተኞች ከወጡ በኋላ ሙሴ ክርስቶና ሙሴ ጆርጂ ካሉ ጆርጥሎስ ወንድማማቾቹ የሚነግዱበት የወይዘሮ በለጥሻቸውና የደጃዝማች መሸሻ ወርቄ ሱቅ ተቃጠለ ፤ የተቃጠለውም ዕቃ ሒሳብ እስከ ፪፻፳ሺ ይሆናል ። ትጉሁ ከንቲባ ነሲቡ ዘበኞውን ዘጥሩንባ አሰብስበው ከእሳት ያዳኑት ዕቃ እስከ ፳ሺ ብር ይገመታል ። ሲቢርቶ የነበረበት ጓዳ እንዳይቃጠል በጐረቤት የነበሩ ባንያኖችና ዘበኞች ውሀ እየቀዱ በብርታት ባያጠፉት በተራው ያለ ሱቅ ሁሉ አይተርፍም ነበር ።

ሙሴ ጆርጂ ከንቲባ ነሲቡና የረዷቸውን ሰዎች ሁሉ እጅግ ያመሰግናሉ፡ ሙሴ ክርስቶና ሙሴ ጆርጂ በአዲስ አበባ ንግድ ከጀመሩ ፳ ዓመት ይሆናል ። በትንሽ ጀምረው ብዙ ዓይነት ዕቃ ከነሱ ቤት ነበር እሚገኘው፤ ለመንግሥትም ብዙ ይጠቅማሉ ከወጪና ከገቢ ዕቃቸው ለጉምሩክ የሚከፍሉት ቀረጥ ባመት እስከ ፻፶ሺ ብር ይሆን ነበር። በጅማና በሲዳሞ ሱቅ ከፍተዋል ። ደግሞ በወሎ ሱቅ ሊከፍቱ ነበር ።

መንግሥቱና ሕዝቡ እጅግ አዝኖላቸዋል፡ቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴም እጅግ አዝነውላቸው የተቃጠለውን ሱቅ ዓይተው አይዟችሁ ብለው ተስፋ ሰጥተዋቸዋል ። እሳቱ የተነሣበትን ምክንያት ሙሴ ጆርጂን ብጠይቃቸው የተነሳበትን ምክንያት አላወቅሁም የተነሣው ከውሥጥ ነው። የስጋራ ትርኳሻም እንደሆነ የከብሪትም ትርኳሽ እንደሆነ እርግጡን አላወቅሁም አሉ፡ ምንም ጉዳቱ ለሁላችን ቢሆን እግዚአብሔር ይርጠባችሁ ። ይላል ብርሃንና ሰላም ።

ማስታወቂያ

ከግንቦት ፩ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ጀምሮ ስለ ግምሩክ ቀረጥ አከፋፈል ፻፳፫ አንድ መቶ ሐያ አምስት ፍራንክ ሽረፋው በአንድ ሊብር ስቴሌንግ ሒሣብ ታስቦ ደግሞ አንድ ሊብር ስቴሌንግ በ፲፮ አስራ ስድስት ብር ሒሣብ ሽረፋ ሁኖ እንዱ ደንቡ ቀረጡን ይከፍላል የጉምሩክ ዋናዲሬክተር ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፱ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፩ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፮ ብር
ዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፮ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ጎሀ ጽባሕ	፬ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፹ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፸ መሐ
የሚልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፸ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፸ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፸ መሐ
አሳብና ምኞት	፶ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፶ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፴ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፴ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፴ መሐ
የእንቀጣጣሽ ግጥም	፴ መሐ

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ። ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምበር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጉርጎርዮን ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሩው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



ዝ ኒ ት የ እ ጅ ሰ ዓ ት ።

በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም ዘየዓይነቱ እንደ ሲንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኰኛክ በፈረንሳይ አገር ኰኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናዲ-ሰናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
6me ANNÉE № 19

ሐሙስ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 8 MAI 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ቤተ ክርስቲያን ።

በሚያዝያ ፳፫ ቀን የጊዮርጊስ በዓል ነበርና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከመኳንንቱ ጋራ ወደ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ነበር ።

ካህናቱ ከቅዳሴ ከወጡ በኋላ ታቦቱ ወጣና ውደት ተጀመረ፥ ካህናቱም ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሞት አዝነው ነበርና ማኅሌቱን እንደ ቀድሞው አላደመቁትም፡ቀለም ሲናገሩም እንባ እንባ ይላቸው ነበር፥ የለበሱትም ማቅ ነበር። እውነታቸው ነው፥ እንኳን በቅርቡ ጊዜና ለመቸውም ቢሆን በነገሡ ጊዜ የነበረው ደስታ ከነገሡበት ስፍራ ሲጠፋ ውለታ ላለው ሁሉ እጅግ ሲአሳዝን መኖሩ አይጠረጠርም ።

የከተማ ወሬ ።

የትግሬ ገዦዎች ።

ራስ ጉግሣ አርአያና ባለቤታቸው ወይዘሮ የሸሸወርቅ ይልማ ራስ ሥዩም መንገሻና ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው። ወደትግሬ ተልከው ሂደው የነበሩት ቀኛዝማች ታደሰ ገነሜ፥ ደግሞ ወደ ምስር ተልከው ሂደው የነበሩት የገንዘብ ዲረክቴር አቶመኰንን ሀብተወልድ የማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር አቶ አየለ ገብሬ ። ጂቡቲ ተገናኝተው በሚያዝያ ፳፬ ቀን በ፲፩ ሰዓት በምድር ባቡር አዲስ አበባ በደኅና ገቡ ።

የተቀበሏቸው መኳንንት ።
የወላሞ ገዢ ደጃዝማች ይገዙ ።
የዱረኒ ገጀ ፊታውራሪ ዓምዴ ።
የውጭ ጉዳይ ዋና ዲሬክተር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ።
የአዲስ አበባ ከንቲባ ነሲቡ ።
ሊቀ መኳስ አምባቸው ገሠሠ።

የምድር ባቡር ሹም ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ ።
ግራዝማች ሣህሌ የመድፈኞች አለቃ ።

ግራዝማች አማረ የከተማ ዘበኞች አለቃ፥ብዙ ዘበኞች ጨምረው ከላይኛው ግቢም ሥራት ያወቁ ዘበኞች ብዙ ሁነው መጥተው ነበርና ሁሉም ባንድነት በሥራት ተሰልፈው የሚገባ ሰላምታ ሰጧቸው፥የሰዉ ብዛት እንደ ውሀ ሙላት ይጋፋ ነበር ። ሌሎችም ብዙ መኳንንት ነበሩ ። ከሰዉ ብዛት የተነሣ በየስሙ መጻፍ አልሆነልኝምና ስማችን አልተጻፈ ብላችሁ እንዳትቀየሙብኝ እለምናችኋለሁ።እኔህም ጌቶች በነሱ ምክንያት ብዙ ሰው እንዳይጉላላ ብለው በስመረ በምጥዋ በባሕር ባቡር ገብተው በጅቡቲ በምድር ባቡር ገብተው ወደ አዲስ አበባ ስለመጡ ሕዝቡንም ከብዙ መከራ ስላዳኑት እጅግ እናመሰግናቸዋለን ። ደኅና መከር ያለበት ቤት አለጊዜው አይፈርስም ሁለቱም ባንድነት ሲጫዋወቱ ባየኋቸው ጊዜ እጅግ ደስ አለኝ ። ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ «(የወንድማማቾች ባንድነት መቀመጥ ምንኛ መልካም ነው) ያለውን የዳዊትን ቃል አሰብሁ ። ያንድነታቸውንና የፍቅራቸውን ነገር ሰምቼ አላውቅም ነበርና እጅግ ተደነቅሁ። እንኳን ዝምድና ያለው ሰውና ባዕድም ቢሆን ጉረቤት የሆነ ያገር ገጀ መስማማትና መፋቀር መመካከር ይገበዋል። ሁለቱ ጉረቤቶች ካልተስማሙ ግን የባላገሩ ጉዳት ይበዛል ከአንዱ አገር ሰው ገሎ በጨኸት አገር ተሰብስቦ ሲከተለው ያንዱን አገር አልፎ ወደ አንዱ አገር ግዛት የገባ እንደሆነ ወደ ሰው አገር መግባቱን ፈርተው ይመለሳሉ።ጅብ በማያውቁት አገር ሂዶ ቀርበት አንጥፎልኝ ይላል እንደ ሚባለው ተረት እሱም ጨዋ መስሎ በማያውቁት አገር ይኖራል፥ የተስማሙ እንደሆነ ግን ተአገረ ገጀው ወረቀት ይዘው ይሄዱና እገባበት ተከትለው ይይዙታል ። በሁለቱ አገረ ገጆዎች መሀከል ሌባና

ወምበዴ ይጠፋል ። ነጋዴ እንደልቡ ይነግዳል፤ ገበሬ እንደ ልቡ ያርሳል ። ሽማግሌ እንደ ልቡ ይጦራል ። ሕፃንም ተመችቶት ያድጋል ። ደግሞ ሁለቱ ተስማምተው ቢገዙ አገሌ ክፉ ገጋር ነው ። አገሌ መልካም ገጋር ነው ከመባል ያድናል ። ለዚህ ሁሉ መሣሪው ፍቅር ነው ። ለኢትዮጵያ ገጋሮችና ኃያላኖች ፍቅርን እንመኝላቸዋለን ። መንገደኞችንም እንኳን ደኅና ገባችሁ እንላለን ።

ሠርግ

በሚያዝያ ፳፮ቀን አቶዮሐንስ ሣልደ ማርያም ልጇን ጽጌ ዮሐንስን ሲድር ተጠርተን የተሰበሰብነው ሰዎች ብዙ ነበርን ። ከሮፓውያንም ጥቂት ሰዎች ነበሩ።እኔ እማውቃቸውም የአሜሪካን ዩናይትድ እስቴትስ መንግሥትዋይስ ኮንስልና ጕዳይ ፈጻሚ ሚስተር ሎዳርፓርክ፤የስዊድን ሚስዮን ተማሪ ቤት አለቃ ሙሴ ሻርኒ ከባለቤታቸውና ከልጆቻቸው ጋራ ሌሎችም ሴቶች አስተማሪዎች፤ሌሎችም ስማቸውን ያልጻፍኋቸው የሮፓ ሰዎች ነበሩ።

እንጀራውና ወጡ አልጫው በያይነቱ ቀርቦ ከተበላ በኋላ እንደ አገራችን ልማድ ብርንዶ ሥጋ ለሚፈልጉ ሰዎች ቀረበላቸው። ከዚህ በኋላ የአሜሪካን ዩናይትድ እስቴትስ መንግሥት ዋይስ ኮንስልና ጕዳይ ፈጻሚ ሚስተር ሎዳርፓርክመቸም ብልህ ናቸውና እኛን ደስ ለማሰኘት ብርንዶ ሥጋ ቈረጡና በድቅስ አድርገው ይበሉ ጀመር ። አብረዋቸውም ያሉት እሳቸውን ደስ ለማሰኘት ይበሉ ጀመር።አዋቂን የመሰለ አሁን ምን መልካም አለ።ባገራቸው ብርንዶ ሥጋ እንዳገራችን ያሳማ ሥጋ ሲጠላ እኛን ደስ ለማሰኘት ስለቀመሱልን እጅግ ደስ አለን ትልቅ የዲፕሎማቲክ ሰው መሆናቸውንም በውነት አወቅን ።

ክፉውን ሐሳብ ሳይከተል ለመንግሥቱና ለሀገሩ የሚስማማውን መልካም ሥራ የሠራ ሰው ዋጋውን አያጣም።

ከራስ ጉግሣ ወሌ ዘንድ ደንቢያንና ሰቀልትን ጣቁሳንም ክርብ ወደያ ያለውን አገር ወምበርነት ተሾመው የነበሩት ቀኛዝማች መኰንን የሚባሉ ሰው ስለ ሀገራቸውና ስለመንግሥታቸው ስለወገኖቻቸውም ፍቅር ሲሉ ዘንድሮ የሠሩትን ጥቅምና እርዳታ እውነተኛ መልክተኞች ከሆኑት ሰዎች ዘንድ እንደሰማሁ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለማሰማት ስል እነሆ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት መስመሮች ላይ ጽፌ አበረክታለሁ ።

በ፲፱፻፲፮ ዓ ም ራስ ጉግሣ ወሌ ወደጥድላ ዘልቀው የታዘዙትን የመንግሥት ትእዛዝ ሳይፈጽሙ ስለተመለሱ ቀኛዝማች መኰንን አብረው ዘምተው ነበረና ራስ ጉግሣ ከመንግሥት መክዳታቸውን ስለተጠራጠሩ ራስ ጉግሣን እንዲህ አሏቸው። ጌታዬ ሆይ የታዘዝንበትን የመንግሥት ጕዳይ ሳንፈጽም ሰዎችን በመንገድና በበሽታ ተጕላልቶ አንድ ሥራ ሳንሠራ በምን ምክንያት እንመለሳለን ብለው ይህነን የነገር መጀመሪያ አድርገው እውነተኛ ምክራቸውን አቀረቡላቸው።ራስ ጉግሣ ግን ክፉ ሐሳብ ስላደረባቸው እውነተኛውን የቀኛዝማች መኰንን ምክር ባልሆነ በሐሰት ወሬ አሰናክለው ሳይቀበሏቸው ስለቀሩ ከመንግሥት መክዳታቸውን አስረግጠው ተረዱትና ከዚያ ወዲያ ቀኛዝማች መኰንን ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው የሚስማማውን እውነተኛውን ነገር ለማድረግ ቍርጥ አድርገው በሐሳብ እያወጡ እያወረዱ ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ አብረው ደብረ ታቦር ገቡ ። ከዚህ በኋላ ራስ ጉግሣ ወሌ ያንኑ ያሰቡትን ክፉ ሐሳብ ለመፈጸም መዘጋጀታቸውን፤መኳንንቶቻቸውን ሰብስበው ምክሩን በከፈቷቸው ጊዜ ቀኛዝማች መኰንን እንደዚህ ብለው ተናገሩ። (ጌታዬ ሆይ) እኔን ድኃዎን አክብረው ሾመው ሸልመው ክርብ ወዲያ ባለው አገር ላይ የወንበርነት ሥልጣን ሰጥተው ብዙ ዘመን ስላስገዙኝ ባዘዙኝ ሥፍራ እስከተቻለኝ ድረስ ለመድከምና ደሜን አፍስሼ ወረታዎን ለመመለስ መቸውንም ቢሆን እንዳልመለስ ያለጥርጥር ያውቁታል ። እንደዚሁም ሁሉ እርስዎንም ጌታዬን ታላቁ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሙሉ ቤጌምድር ኃላፊ አድርጎ እምነቱንም ባርስዎ ላይ ጥሎ በእንደዚህ ያለ ከፍተኛው ማዕርግ ላይ ሥልጣን መስጠቱ ሀገሩንና ድኃውን እንዲጠብቁለት ዓመፀኛውን እንዲቀጡለት ነው እንጂ መንግሥትን የሚበድል ክፉ ሥራ እንዲሠሩ አይደለምና ስለዚህ ለመንግሥትዎ የሚገባውን ወረታ በመክፈል ፈንታ መንግሥትዎን የሚበድል ክፉ ሥራ ለመሥራት ማሰበዎ የሚገባ አይደለም። መንግሥትስ ከዚህ ወዲያ ምን ሊያደርግልዎ ነው። ደግሞስ ምን ያስከፋዎ ነገር አለ። እኔ ቢሆን በመንግሥታችንና በሀገራችን ላይ ጠላት ሲመጣብን አንድነታችንን አፅንተን ደማችንን እናፈሳለን እንጂ መንግሥትንና ሀገራችንን የሚበድል ክፉ ሥራ እንሥራ ለማለት አልደፍርም። አሁንም ሲሆን ይህነን ሐሳብዎን ፈጽመው ከልብዎ እንዲያርቁት አጥብቄ እለምንዎታለሁ እያሉ ከጫማቸው ላይ ወድቀው ይለምኑአቸው ጀመር ።

ነገር ግን ራስ ጉግሣ ወሌ ክፉ ሐሳባቸውን የማይለውጡ ስለሆነ አንተ የምትከዳኝ እንደሆን ነው እንጂ በመኳንንቶቼ መካከል ይህንን ቃል አትመክረኝም ነበረ ። ይልቁንስ በደምቢያና በሰቀልት በጣቁሳ አውራጃ ክርብ ወዲያ በግዛትህ ውሥጥ ያሉትንአሽከሮቼንና የሀገሩንም ዘማቾች ሁሉ አስከትተህ እንድትመጣና ሰው እንዲቈጠር ይሁን ብለው መጨከናቸውንም ገልጠው በቍጣ ቃል ተናገሯቸው። ቀኛዝማች መኰንንም ራስ ጉግሣ ወሌ ከክፉ ሐሳባቸው እንዳልተመለሱ ከተረዱ በኋላ እኔስ ከልቤ ያለውን ሐሳብ ለጌታዬ አከፍዬ ነገሩ እንዲበርድ ይሆናል መስሎኝ ነበረ እንጂ ይህን መናገሬ እንግዲያውማ በዚህ ነገር ጌታዬ ጨክነው ጠርነቱ የማይቀር ከሆነ ሞትዎ ሞቴ፤ ሕይወትዎ ሕይወቴ አይደለምን ፤ እሺ ትእዛዝዎን እፈጽማለሁ ብለው ወደ ደምቢያ ወረዱና እንደ ትእዛዛቸው ቃል በደምቢያና በሰቀልት በጣቁሳ አውራጃ ክርብ ወዲያ ያለውን ባላባትና ፈረሰኛ ደምበኛውንም ሁሉ ባዋጅ አስከትተው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምክር ቃል አቀረቡላቸው ።

ክቡራን አባቶቼ ወንድሞቼ ሆይ፤ እኔ አሁን የመጣሁት እናንተን ሰብሳቤ ወደደብረ ታቦር ወስጄ እንዳስቈጥርና ለጦርነቱም ተዘጋጅታችሁ እንድትነሡ ለማድረግ ከጌታዬ ዘንድ ተልኬ ነው ። ነገር ግን አሁን የምላችሁ ካባቶቻችን ጀምሮ

ሲወርድ ሲዋረድ እኛ ለመንግሥት ታዛዦችና መንግሥት በዘዘን ሥፍራ እየሔድን ከረመኔ ጋራ እየተዋጋን ደማችንን እያፈሰስን የሀገራችንን ወሰን መጠበቅ ፤ ሁለተኛም መንግሥት የሰጠንን ገጋር አክብረን ተቀብለን ትእዛዙን እየፈጸምን የሚገባውን የደንቡን ግብር መስጠት ነው እንጂ መንግሥትን የሚበድል ክፉ ሥራ እስከዛሬ ድረስ በሀገራችን ተሠርቶ አያውቅም ። አሁን ግን የኔ ጌታ ያሰቡት መንግሥት የሚያዝንበትን ሀገሩና ሕዝቡ የሚበድልበትን ክፉ ሥራ ሠርተውራሳቸውም ሰውም ጨምረው ለማጥፋት ነው ። እኔም በየጊዜው እስከተቻለኝ ድረስ ምክሬን በቀርብ አልተቀበሉኝምና አሁንም ወደ ጦርነቱ ለመሔድ ልባችሁ እንዳያስብ የሚያስወሩትም ከንቱ ወሬ ሰው እንዲተበበርላቸውና ከጦርነቱ እንዳይቀርባቸው ብለው ነው እንጂ ወሬያቸው እውነተኛ እንዳይመስላችሁ ። ምክሬንም የተቀበላችሁኝ እንደሆነ እኔ እንደ ሚመስለኝ ሀገራችንና እኛም ከጥፋት ለመዳን የሚያስፈልገው ነገር እንደዚህ ነው፤አስቀድመን መከዳታችን የተገለጠ እንደሆነ እኛኑ ተመልሰው እንዳያጠፉን አሁኑ እንደተሰበሰብን ለጦርነቱ የተዘጋጀን መስለን ሂደን ጠሩን እናስቈጥርና የጦርነቱን ነገር ቍርጥ አድርገው ከደብረ ታቦር ወጥተው ወደዚያው በተቃረቡ ጊዜ እኛ እንደዚሁ እንዳማርን ሳንለያይ ተመልሰን ሀገራችንን መጠበቅ ነው ።

ደግሞ ምናልባት ከጦርነቱ ድል የሆንኩ እንደሆነ አርባ ምንብ ከሚባለው ኰረፍታ ተዋሻው ውስጥ ነውና የምገባው ዋሻው ተጠርጎ ይቈየኝ ብለው ዪኸው አስጠርገውታልና ወደ አምባው የሚሔዱ ከሆነ በኛ ላይ መምጣታቸው አይቀርምና ያን ጊዜ ራስ ጉግሣን ይዘን ለመንግሥታችን ለመስጠት ይቻለናል ብለው በተናገሩ ጊዜ የሀገሩ ሰው ቀኛዝማች መኰንንን እጅግ አድርጎ ያምናቸዋልና ከልጅ እስከአዋቂ ድረስ በንግ[illegible] ልቡ ተመልቶ የርስዎ ሐሳብ ሐሳባችን ነው ። ይህንንም ወሬ ከሰማን ጀምሮ እስካሁንም ድረስ ዋና ሰብሳቢ ሰው አጥተን ነው እንጂ እውነት መንግሥታችንን ከድተው ከመጡት ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ ሆነን እንዋጋለን ብለን እንዲያውም አናስበም እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ከጥንት ጀምሮ እስከሁን ድረስ ስለሀገራችን ስለመንግሥታችን ስለሃይማኖታችንም እያልን ደማችንን እናፈሳለን እንጂ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሳይናወጽ የኖረውን ታላቁን ጥንታዊ የሆነውን መንግሥታችንን ከድተን ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ ዓመፀኛ እንሆናለን ለማለት እንኳን እኛ አእምሮ ያለን ሸማግሎችና አእምሮ የሌላቸው ሕፃናትም ቢሆኑ ደህን አያስቡትም። አሁንም የኢትዮጵያና የተፈሪ አምላክ ምክራችንን አፅንቶ እንዳንለያይ ያድርገን ብሎ በመጋቢት ፲ቀን ጉራምባ ሚካኤል በሚባለው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተማምሎ ወደደብረታቦር ተጓዘ።ራስ ጉግሣ ወሌንም ቀኛዝማች መኰንን ጥንቱንም ቢሆን ጦርነቱ እንዲደረግ አልወደደምና ይከዳዎታል ለምን ላኩት እያሉ ባለሟሎች እየነገሯቸው ተጠራጥረው ሳለ በመካከሉ ቀኛዝማች መኰንን ጦሩን አሰብስበው በመጡ ጊዜ ይኸውላችኋ እኔማ አሽከሬን መቸ እጠረጥረው ነበረ እናንተ ይከዳል እያላችሁ ነው እንጂ ያጠራጠራችሁኝ

አሁንም ቀኛዝማች መኰንን ላመጣው ጦር በተለይ ግብር ይደረግለት ብለው ከዚህ በፊት ፲፩ዓመት ሲኖሩ ለሥራ እንጂ ለመብል ፩ምቀን ፈቅደውት የማያውቁትን ሕዝብ እጅግ ያማረ ግብር ስላደረጉለት ሕዝቡ ለሞት ጊዜ ግፈር በመብላቱ እየተደነቀ ተጋብዞ ወጣ ። ከዚህ በኋላ ራስ ጉግሣ ወሌ የጦርነቱን ነገር ቍርጥ አድረገው ጉዞ በጀመሩ ጊዜ ቀኛዝማች መኰንን ምክራቸውን አፅንተው የሰበሰቡትን የሀገር ዘማችና ፈረሰኛውን ደምበኛውንም ይዘው ወደሀገራቸው ፊታቸውን መልሰው ማታ ተነሥተው የ፫ቱን ቀን መንገድ ባንድ ሌሊትና ባ፩መዓልት ቈርጠው በግሥጋሴ ወደደምቢያ ገቡ።ወዲያውም እንደገቡ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አዋጅ አደረጉ። እንግዴህ መንግሥታችን የሚልክልን ጠባቂያችን እስቲመጣልን ድረስ ገበሬም እረስ ነጋዴም ነግድ ደምበኛና ፈረሰኛም የሆንክ ከዚህ ቀደም በያዝከው አገር ፀንተህ እንድትቈይ ይሁን፤ይኸውም የግርማዊ ንጉሥ ቃል ነው ብለው በየገበያው ላይ አዋጃቸውን ባደረጉ ጊዜ ሕዝቡ በፀጥታ ሁኖ እንዳዋጁ ቃል በየሥራው ተሠመረ። ከቀኛዝማች መኰንን ጋራ ያለው ጦር ባርባምበ መንገድ ላይ ተሰልፎ የራስ ጉግሣ ወሌን ፍጻሜና አኳኋናቸውን ይጠባበቅ ነበረ ። እንግዲህ ከዚህ በላይ እንደተነገረው ቀኛዝማች መኰንን ለሀገራቸውና ለድሀው ቤዛ ሁነው የመንግሥታቸውንም ክብር አጻነው ይህነን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ስለሠሩ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብራቸውን፤የመንግሥት ዘንድ ታማኝነታቸውን ያጣሉ ለማለት አያስጠረጥርም። የዚያ አገር ሕዝብ ከዚህ ቀደም በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ራስ ዘውዴ መንግሥቱን ቢከዱ ተገጋር የነበረው ድጎ መንግሥትን በርግጥ ተከዱ ከመንግሥታችንና ከሀገራችን የሚበልጥብን የለምና ብሎ አንድነት በስምምነት ተባብሮ ራስ ዘውዴን ይዞ አምጥቶ ለዳግማዊ ምኒልክ አስረክቦ ነበረና ሥልጥንናውና የመንግሥት ታማኝ መሆኑ ያንጊዜ እርግጠኛ ሁኖ ሲነገር ቈይቷል።አሁንም የሠራው የሥልጣኔና የታማኝነት ሥራ ለሚመጣው ትውልድ መሠረት ሁኖ በታሪክ መጽሐፍ ላይ ተጽፎ ሲነበብ ሊኖር የተገባ መሆኑን ማንም አይስተውም።ለዚህ ለሠለጠነውም ሕዝብ አፄ ፋሲል በቈረቈሩት ከተማ በጎንደር ላይ መንግሥት በቸርነቱ ተማሪ ቤት ቢከፍትለት እንዴት አድርጎ በተማረና ከሥልጣኔው ላይ ሥልጣኔ በጨመረ ነበረ ።

ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ ።

ኃይለ ሥላሴ እግዚእ ከበቴ አበሳ፡ ብፁዓንሰ ይብሉ መ እንዘ ኢይሬእዩ አለ አምኑ ።

ለጠበብተ ጕንደር አኃው ድልዋነ ስብሐት ላዕከኑ ።

አኮኑ ረከቡ ዘለዓለም ሕይወተ በስመ ዚአሁ ወእሞት ድኅኑ ።

ወአስተዳለዎሙ ይትኰነኑ።

በሥልጣን ልዑል ዮሐንስ ዘረፈቀ ውስተ ሕፅኑ ።

(ለጕንደርሂ)ሀገረ ንግሥ መቅደሰ አሮን ክህኑ።

ዳታን ወአቤሮን ኢይበውዕዋ ድኅረ ሰእኑ ።

እንዘ በውስቴታ ያርኢ፩ብዝኃ ብርሃኑ ።

ቀሲሰ አእምሮ ኃይለ ሥላሴ ወንጉሠ ነገሥት ዘበሥልጣኑ።

እስመ አውረዶሙ ቅድመ መንጸፈ ደይኑ ።
ቀሲሰ አእምሮ ኃይለ ሥላሴ ወንጉሠ ነገሥት ዘበሥልጣኑ ።
ወየብቡ ለኃይለ ሥላሴ በቃለ ትፍሥሕት ።

ደጉ ይመር ።

ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖች መታሰቢያ ።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ሕዝብን በመጠበቅ ፡ ዓመፀኛን በማራቅ፥ ለተራብ በማብር ፡ ላተበደለ በነገር ፡ በመገኘት ፡ ለንጉሥ ታዛዥ ፡ ለግዚአብሔር ተገዥ በመሆን የተዘጋጁ መሆናቸው ጽንፍ፥ እስከ ጽንፍ ደርሶ በዓለም ሁሉ ላይ ይነገርላቸዋል ። ደግሞም ያንደኑታቸው ጠፈር በፍቅር ሐር የተቈነጠጠ ፡ በስምምነት ግምጃ የተለበጠ እንደሆነ በየጊዜው የሚሠሩት ሥራ በግልጽ ያስረዳል ።

እጃቸው ከመወርወር ፡ ቃላቸው በጎ ምክር ከመምከር አይሰንፍም ። ከዚህም የተነሣ የጠላታቸው አገር በሰይፍ ታጭዶ በምርኮ ይቃረማል ። እኛንም ጥሶ ሀገራችንን ወርሶ ለመኖር ያሰበ የጠላት ልቡም ጉልበቱ፥ ውሀ ሐሳቡ ምትሐት ይሆናል ። ደብ ራሱን ስለት ድጉሱን እንዲሉ ። የሠራው ትንኰል ተመልሶ ራሱን አጥፊ ይሆናል ። ባወጡት ዳኛ ቢረቱ በቈረጡት በትር ቢመቱ የእግዚአብሔር ግቡ ከብቱ እንዲሉ ። በሚረው ክብሪት ተቃጥሎ በቈፈረው ጉድጓድ ወድቆ ተሰባብሮ ይቀራል ። የኢትዮጵያ ጀግኖች የሀገራቸው ምድሩ እንዳይፋለስ ፡ ደንበሩ እንዳይፈርስ ፡ ጠላት እንዳይቀሰቀስ ሲሉ ወሰን አላፊውን ፡ ድንበር ገፊውን ለማስገወድ ፡ ዓመፀኛውን ለማሳመን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሳይቀር በረሀ ጥሰው ዳዋ ለብሰው ፡ ደንጊያ ተንተርሰው እንደ ባሕታዊ ቅጠል ጎርሰው ፡ጤዛ ልሰው፥ በየመንገዱ ያለውን መከራ ታግሠው ግስግሰው ሒደው ጠላታቸውን ሳያጠፉ ይቀራሉ ማለት ውሸት ነው ።

ይልቁንም ምንም መዋዕለ ውርዙቱ ያለፈ ፡ ዕድሜው ክቊጥር የተረፈ ሽማግሌም ቢሆን ተነሥቼ ሒጄ ከጠላቴ ጋራ ተዋግቼ ከሀገሬ ደንበር ልሙት ይላል እንጂ ፡ እኔ ሰውነቴ የደነዘዘ ፡ ዓይኔ የፈዘዘ ፡ ጉልበቴ የደከመ መቃብሬ የተማሰ፥ ልጤ የተራሰ ፡ ሽማግሌ ነኝ ከዚሁ ልሙት እንጂ ሒጄ ምን አደርጋለሁ አይልም ። ፀሐይ ከመመላለስ ፡ ነፋስ ከመንፈስ፥ ዓባይ ከመፍሰስ እንዳያቋርጥ የኢትዮጵያም የጀግኖቿ ሥራ ሳያቋርጥ ይኖራል ።

አንቺ ኢትዮጵያ ፡ የልጆችሽ ዝና
ታወቀ ባለም ላይ ፡ አገኘ ልዕልና
የስምሽ ታሪኩ፥ባለም ላይ ሊነገር
ልጆችሽ ታጠቁ ፡ የጉብዝና ዝናር
ስድ ሁኖ እንዳይቀር፥ይህ የሠራሽው ቤት
አፄ ኃይለ ሥላሴ፥መከታ ሆነለት
እጅግ ያስፈራሉ ፡ እኒህ ያንች ሕዝብ
እየተናደፉ ፡ እንደቀትር ንሀብ
ተፈሪ አደረጉት ፡ አውራቸውንም
ጉዣቸው ደመቀ ፡ አማረ በጣም
ሥልጣን ተቀብለሽ፥ ከትምርት አቡን።
ቀድሽው ያውልሽ፥ መላ ሐበሻን ።
በዚህ በሥልጣንሽ፥ ጠንክር ጠንክር በዩ።
ደግሞም ሌላ ማዕርግ፥ እንድትቀበዩ።
ልጆችሽ ያውቃሉ፥ የዜማውን ትምርት።
የዚያን የሰማዕት መልክ፥አመርባደው ጻፉት።
የውቀትሽ እንጀራ ቢያምራቸው ልስልሱ።
ከመጻፍ ቅዱስ ወጥ፥ በሉ እየጠቀሱ።
ንጉሥ ነገሥቱን፥ ያንግሠው ሽህ ዓመት።
እንደነዳዊትም፥ መንግሥቱ ትጽናለት።
ለምለሚ አገራችን፥ እንድታገኝ ዕረፍት።
አምላክ ፈጣሪያችን፥ ይክበር ይመስገን።
በኢትዮጵያ፥ ለይኩን ብርሃን።
ብሎ የፈጠረ፥ ኃይለ ሥላሴን
ከምሥራቅ የወጣው ተፈሪ ፀሐይ።
ጮራውን ነዛበት ባለም ሁሉ ላይ።

ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ።

የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ታላቅ ቁም ነገር አስበው በአዲስ አበባ ቤተ መቅደስ ስለ መሠረቱ የሚከተለውን ለመጻፍ አሳሰበኝ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታላቅ ዕድሜና ጤንነት ሰጥቶልን የኋላ ክብርዎን ለማየት አብቅቶ በዚች ቤተ ክርስቲያን ሁላችን በአንድነት ተባብረን እግዚአብሔርን ለማመስገን ያብቃን ።

መጀመሪያ አዲስ አበባ ላይ ጸሎት ቤት ተሠራ።
በኃይለ ሥላሴ ያማረ ጠንክራ ።
የረቀቀ ንጉሥ ለድሐ የሚራራ ።
ለትልቅ ትኒሹ አንድ ቀን አይኰራ ።
አዲስ አበባ ላይ ቤተ መቅደስ ሠራ ።
የተመሰገነ ባያለበት ስፍራ ።
በሐረር አውራጃ የፈጸመው ሥራ ።
ቢጻፍም አያልቅም ቢወራ ቢወራ
ድንጋይ ተሸክሞ ከአሽከሮቹ ጭፍራ።
ተፈሪ መኰንን ቤተ መቅደስ ሠራ ።
፪ተኛ በጣም ያስገርማል የውርዱ መሠረት ።
ኃይለ ሥላሴ ያመጣው ብልሐት ።
፫ተኛ የስፋቱ ነገር የአጀማመሩ ።
የኃይለ ሥላሴ ጥልቅ ነው ነገሩ ።
፬ተኛ ጭራሹን ያሳየን ይፈጽምለት ።
አዲስ አበባ ላይ የሠራውን ቤት ።
ዕድሜ ይስጠንና ክብርዋን እንያት ።
በኢትዮጵያ አይገኝም እንደዚህ ውበት ።
፭ተኛ ሥራውን እያያችሁ በጣም ልብአድርጉት ።
ደንብና ትእዛዙ የለበት ስሕተት ።
ኃይለ ሥላሴ ረቂቅ ፍጥረት ።
፮ተኛ ለሕዝብ ላገሩ የለበት ሐኬት ።

ገና ዛሬ ሆነ ሰላምና ዕረፍት ።
፯ተኛ፡ወንበዴ ቢነግሥ አገር ለማጥፋት
ይመረምረዋል የሁሉን ክፉት ።
ይመክረናል ደግሞ እንዳባት እንደናት ።
፰ተኛ፡ በሕይወት ያኑረው ኃይለ ሥላሴን።
እንደአባትና እናት ለሚአስብልን ።
፱ኛ፡ዘሩ፡ይባረክና መንግሥቱ ይስፋለት ።
የኢትዮጵያ መንግሥት ምን ስሕተት አለበት ።
፲ኛ፡ለሚአደርገው ሁሉ አሳቡን ያቅናለት ።
ለኢትዮጵያ ልጆች የሚመራ በውቀት ።
ሽማግሌ ሕፃናት ደንቡን ፈጽሙለት ።
፲፩ኛ፡ትእዛዝ የማይጠብቅ የማይሰማ አዋጅ ።
ውሸት የለመደ ሁልጊዜ ቀላጅ ።
ጎበዝ ሰው እርሱ ነው በከንቱ እሚያረጅ ።
፲፪ተኛ፡ መንግሥትን የሚንቅ ወትሮ የሚሸፍት ።
ንጉሥ ይቀጣዋል ያገኘዋል ሞት ።
፲፫ተኛ፡ቤቱን የሚሠራ በግፍ መሠረት ።
ቶሎ ፈርሶ ያርፋል ኋላም ወዮለት ።
፲፬ተኛ፡ የንጉሥ አዋጅ ሲነገር ብሰሙት
ደንቡን አታፍርሱ ትእዛዙን ፈጽሙ ።
ቀኝ ግራ አትበሉ በሥዓርት ቁሙ፡
ቀብቶ ያነገሠው እግዚአብሔር በዓለሙ
ቀጣሙ ያቃጥላል ቶሎ አይበርድም ቁሙ
፲፭ተኛ፡ ለከበረ ስሙ ድኃን አትቀሙ
በነፍስም በሥጋ እንድትጠቀሙ
፲፮ተኛ፡ መንግሥትን ታዘዙ ሳትነጣጠሉ
በኃጢአተኛ ምክር እንዳትቃለሉ
ሰይጣን ያታልላል ውሸት ቢከሉ
ደግደጉን ነገር ሁላችሁ አስተውሉ
፲፯ተኛ፡ከግብዞች ጋራ እንዳትንገላቱ
ደግ ደጉን ነገር አሁን ተመልከቱ
፲፰፡አሁን ከዚህ ክፍል እንደምትሰሙት
እንደተናገሩ ቀድሞ መጽሐፍት
ሰሎሞን እንዳለ ስለዚህ በውነት
ዙፋኑ እንዲጠና እንዲቆም መንግሥት
ዓመፀኛን ማራቅ ከዙፋኑ ፊት
፲፱ኛ፡ የተናቀን ነገር አትተውሉ መጥላት
መልካም መልካም ነገር በየቀን መሥራት
በኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
የሚአዘውን ሁሉ በቶሎ መስማት
፳ኛ፡ለድኃና ምስኪን ገንዘብ መመጽወት
እገበታ አቅርቦ እንጀራ ማብላት
በመልካም ብርሌ ጠጅ መጠጣት
፳፩ኛ፡ ኃይለ ሥላሴ ጽድቅ ነው በውነት
ተሰማይ እንጀራ ሲሳይ ይምጣለት
፳፪ተኛ፡ገበሬም እረሱ ሲሳይ መጣላችሁ
ነጋዴም ነግዱ ብዙ ትርፍ አላችሁ
ሰነፎችም ሥሩ በጣም ጠንክራችሁ
ስደተኛም ሁሉ ግቡ በገራችሁ
ስንፍናን ወዳችሁ መንከራተታችሁ
የረሳችሁ አሳብ ተፈጸመላችሁ
ተቀድሞ ባርነት ነጻነት ወጣችሁ
ግብር በዝቶባችሁ ተርስት የወጣችሁ
፳፫ኛ፡ተማሪ ተማሩ በቤት ውሥጥ ሁናችሁ
ያ የዱሮ መዘር ዛሬ ቀረላችሁ
ጥበብ ያስተምራል ታላቁ ጌታችሁ
ክብሯን ታላያችሁ ትንሽ ቄይታችሁ
ኢየሱስ ክርስቶስ ጤንነት ይስጣችሁ
፳፬ኛ፡አንባቢና ሰሚ ይህን አስተውል
ነገሩን አስበው ሳታወላውል
ተስፋ ገብረ ሥላሴ ዘብሔረ ቡልጋ ።

በትንሹ ዕፁ ቀቴ ምስጋና ማቅረቢያ ።

በዚህ በመላዋ ኢትዮጵያ ሕዝብ የተሰማውን ምሥራች በሃሳብ ለመግለጽ የማይቻለውን የተባረከውንና የከበረውን የታላቁን ድል ደስታ ይሉኝታ የሌለውን ጠላትዎ በእግዚአብሔር የተወደዱትንና ጀግናውን ንጉሣችንን ለማወክ የተነሣውን ክፉ አሳቡን ለቈረጠበት ለእስራኤል አምላክ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።ይቺን ቀዳማዊት ኢትዮጵያን በማናቸውም ሥልጣኔ ረገድ ብትጋትና በድካም ሠርተው እዚህ ደረጃ ድረስ እንዳደረሷት ማናቸውም አገሩን ወዳጅ ኢትዮጵያዊ ። ሊረሳው አይችልም ። ከአሥራ አራት ዓመት ጀምሮ በወራሴ መንግሥትነትዎ እዙፋንዎ እስከ መቀመጥ ለሥልጣኔ የተጠማቺዋንና በስንት ጕዳት ላይ የነበረቺዋን ኢትዮጵያን በአሥራ አራት ዓመት ውሥጥ በታላቅ እርምጃ በፍጹም መሠረቷን አድሰው የተዋበች ሙሽራ እንዳደረጓት ማናም አገሩን ወዳጅ ኢትዮጵያዊ ሊረሳው አይችልም ። ደገኛው አንበሳ ጕልበቱ ተሰምቶት ዛሬ በሚአስፈልገው እርምጃ ላይ በታላቅ ግርማ ይራመዳል በተገበው ኃይል ለተባረከቺው ለቅድስቷ ኢትዮጵያ ለወራሴነት የበቁ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አሁንም የእምለው ያ፲፱፻፱ ዓ ም ኢትዮጵያ እንዴት እንደነበረችና በ፲፱፻፳፱ ዓ ም ምንኛ ከሥልጣኔ ተራራ ላይ እንደወጣች ማንም አገሩን ወዳጅ ኢትዮጵያዊ ሊረሳው አይችልም ። ይቺውም በዕውቀትና በሥልጣኔ በበልሃት ያበራቺው ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር መንፈስና አዋቂነት የተሸለሙት የጀግናው ንጉሣችን ልፋትና ትጋት መሆኑን ። እንኳን የመላ የኢትዮጵያው ሕዝብ አሰት በሌለበት አሳቡና የውጭ አገር ሰዎችም በጣም ተረድተውታል ። አሁንም በታላቁ በእስራኤል ንጉሥ ፊት ተንበርክከን ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ መሠረት አዳሽ ለሆኑ ንጉሠ ነገሥታችን ረጅም ዕድሜ ብዙ ጤንነት እንዲሰጣቸው ውጥን ሥራቸውንና ሰፊ አሳባቸውን እንዲፈጽምላቸው ስንል መጸለይ ይገባናል ዕድሜ ለንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ለኢትዮጵያ አርበኞች ። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ስል ቀጥዬ ይቺን ጣጥም ጽፌአለሁ ።

ደስ ይበለዎ ንጉሥ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ ደስታ ነውና።
ኢትዮጵያን በውቀት ያረጓት ገናና ።
እኛም ልጆችዎ እናቀርብ ምስጋና
ለሥልጣኔአችንም በርቶልናል ፋና
ሥራዎም መስከረል ለዚህ ለምስጋና
ትምህርት ቤት መሥራት ሆፒታል መክፈት
መንገድን ማሳመር በአገር ሥራት
አድባራት ኤሌክትሪክ ይኸንን መሥራት
ዕቃችንም መጣ በባቡር ፍጥነት
የውጭአገር ወሬም በስልክ ለመስማት
አየሮፕላን መጣ ለአገር ልማት
ፓስታና ራዲኦ ለሕዝቡ መልክት
ታንክም ጠባቂነት ለመጣ ጠላት
የንግድ ማኅበር ለሕዝቡ ረዳት
በራሳቸው ገንዘብ ለኛ የቆሙት
መንገድም ተሠርቷል ጅማ ለመግባት
አጉሩን ለሚወድ ሹመትም መስጠት
ይቺን መልካም ወይን ዋሎ አስከበረት
አሳባቸውም ነው ከፍ ላለ ክብረት
ይኸው ምሳሌ ነው ለንጉሡ ሰወቀች
ከዚህ የበለጠ ምንድነው ልፋት
ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጸጋ ሲሰጡት
ይህ ሁሉ ሠራዊት ሲኖር በእምነት
ራስ ጉግሣ ብቻ እምነትን ከዷት
ምነው በጐንደር ላይ የኛን ፊለንት
ተሰማምቶ ነውንጂ አገርን ማስፋት
ወዳጅን ማሳዘን ጠላትን ደስ ማሰኘት
እንዲህ ከሆነማ መች ይገኛል ክብረት
ሁላችን ባንድ ልብ በእምነት መሥራት
የሥልጣኔን መንገድ ደረጃ መውጣት
እንደዚህ ሁኖ ነው መንግሥትን መርዳት
እንድንመስገን በውጭ ነገሥታት
ደገኛው አንበሳ ተነቃልን በውነት
ይቺን መልካሟን ወይኑ ሌላ እንዳይቀጥፋት
ትምርትን ሥልጣኔን ሲሰጠን ብልኀት
የባንዲራውም መልክ የውቀት መሠረት
መገዛት ነውእንጂ በምንት በደስታ
በቶሎ እንድንደርስ ወደ ክበሬታ ሚካኤል ስ ማክራስ።

የህንድ ጉዣራቲ ማኅበር አዲስ አበባ ላይ ።
ለሕንዳውያን ሕፃናት ተማሪ ቤት ማቆም ።

የህንድ ጉዣራቲ ማኅበር ተማሪ ቤቱን ለማቆም በጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ሐሳቡን ለመቍረጥ ጉባኤ አድርጎ ነበርና በዚሁ ቀን ነገሩ እፍጻሜ ደረሰ ።

ለዚሁ ተማሪ ቤት የሚሆን ወደ ባቡር ማረፊያ ከሚያ-ወርደው መንገድ ዳር ያለውን ያቶ ኪዳኔን ቤት ማኅበሩ ተከራይቶ ነበርና በስምንት ሰዓት ተኩል ተሰብስቦ በብር ቍልፍ ተቈልፎ የነበረውን በር አብዱላ ባይ ኬራ ከፈቱት ።

ከዚህ ቀደም ተማሪ ቤቱ ሳይከፈት ለትምህርት ቤቱ መቋቋሚያ ስምንት መቶ ብር ያህል ተጠራቅሞ ነበር። የተከ-ፈተ ዕለት ግን አብዱላ ባይ ኬራ ፪፻፶ ብር ዋንማሊ ቢርጂ አንድ ሺሕ አንድ ብር የባንያንወጣት ልጆች ሦስት መቶ አንድ ብር ለምርቃው የነበሩ ልዩ ልዩ ሰዎች አምስት መቶ ያህል ብር ሰጡ ። ከነዚሁ መካከል አቶ አራዶም የሚባሉ ኢትዮጵያዊ በድንገት መጥተው ነበርና በታላቅ ችሮታቸው ሐያ አምስት ብር እርዳታ ሰጡ። ይኸው ስጦታቸው ምንም ለተማሪ ቤት እርዳታ ቢሆን ይልቁንም ሐሳባቸው በህንዳውያን ሕፃናት ትምህርት ቤት መቋቋም ስለሆነ ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ቤት ማኅበር ወዳጅና ረዳት መሆናቸውን ይገልጻል ።

በምርቃው ቀን ለትምህርት ቤት የተዘጋጁ ሠላሳ ልጆች ተሰብስበው ነበርና አያሌ ሰዎች ለትምህርት የሚያስፈልገውን ደብተር፣እርሳስ፣ ቀለም፣ መሐረም፣ይህነንም የመሳሰለ ነገር እር-ዳታ ሰጡ። ማኅበሩም ለተማሪ ቤቱ ወደፊት ከውጪ አገር ከሚያስመጣው የንግድ ዕቃ ስለ ደንባው ታክስ ከመቶ አርባ አምስቱን በገንዘብ ሊሰጥ ቍርጥ ሐሳብ አደረገ ።

ከዚህ በኋላ የተማሪ ቤቱ ሴክሬቴር ተነሥቶ በተማሪዎች ስም ሁኖ ለትምህርት ቤቱ እርዳታ አስበው ለሰጡ ሁሉ ጥልቅ የሆነ ምስጋና በመልካም ንግግር አቅርቦ ተጨበጨበለት ።

ሴክሬቴሩ የምስጋናውን ቃል ተናግሮ ከጨረሰ በኋላ ለምረቃው የነበሩት ሁሉ ቁመው ይህ የበጎ ሥራ መልካሙ-ሐሳባችን ለመከናወንና እፍጻሜ ለመድረስ የቻለው በጃንሆይ-ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በልዕልት መነን ጊዜያት ስለሆነ ሕያው-እግዚአብሔር ከንጉሣዊ ቤተ ዘመዶቻቸው ጋራ ረዥም ዕድሜ ይስጥልን፤ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ሕዝቧም ይጠብቅልን ብለው መረቁ ። ሚያዚያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

የተማሪ ቤቱ ሴክሬቴር ቺመንላል ኬ ሻህ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውን ማናቸውንም ዓይነት ጨው ሁሉ በፍራንኮ ኢትዮጵያ ማኅበር እጅ ብቻ እየገባ እንዲሸጥ ለዚህ ማኅበር በተለየ ፈቃድ ስለተሰጠ ከዚ-ህ ማኅበር በቀር ሌላ ሰው ወይም ሌላ ማኅበር ወደ ኢትዮጵያ ማናቸውንም ዓይነት ጨው እንዳያገባ አጥብቆ ክልክል ነው-ወደ ኢትዮጵያ ግዛት በድብቅ ጨው አግብቶ የተገኘ ማናቸ-ውም ሰውና ማኅበር ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ በተከ-ለከለ በንግድ ዕቃ መቀጫ ደንብ በ፲፰ኛው ክፍልና ስለመቀጫው ገንዘብ በ፲፯ ኛው ክፍል በጉምሩክ ደንብ ይቀጣል ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገ- ራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና የውርጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ድጓዋ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፫ ብር
ኀሀ ጽባሕ	፫ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መማሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክሬት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፲ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፲ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፬ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፬ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፬ መሐ
የእንቍጣጣሽ ግጥም	፬ መሐ

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ። ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የሆሳሲት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጊርጊ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የዱን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
6me ANNÉE № 20

ሐሙስ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 15 MAI 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ደረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ተዝካር።

በግንቦት ፫ ቀን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ተዝካር (መታሰቢያ) ነበር ። በአዲስ አበባና በቅርብ ያሉ አድባራት ክህናት ተጠርተው የመጡት ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ።

በአዲስ አበባ ያሉት አድባራት ክህናት።

የእንጦጦ ማርያም ክህናት
የራጉኤል ክህናት
የዑራኤል ክህናት
የሥላሴ ክህናት
የጊዮርጊስ ክህናት
የአቃቂ መድኃኔ ዓለም ክህናት
የሩፋኤል ክህናት
የሥዕል ቤት ኪዳነ ምሕረት ክህናት
የየካ ሚካኤል ክህናት
የአዲስ አበባ መድኃኔ ለዓም ክህናት
የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ክህናት
የጴጥሮስ ጳውሎስ ። ክህናት
የቂርቆስ ክህናት
የእንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ክህናት
የእስጢፋኖስ ክህናት
የአቦ ክህናት
የዮሐንስ ክህናት
የእልፍኝ ማርቆስ ክህናት
የበእታ ክህናት
የልደታ ክህናት
የአማኑኤል ክህናት
የዮሴፍ ክህናት
የቍስቋም ክህናት
የኢየሱስ ክህናት

ያልተቈጠሩም የበዙ አድባራት ክህናት ነበሩ ይልቁንም ተያገሩ በልዩ ልዩ ምክንያት ወደከተማ የመጡ ክህናት እጅግ ብዙዎች ነበሩ ።

ተከተማ ውጪ የመጡ ክህናት

የደብረ ሊባኖስ ክህናት
የዜና ማርቆስ ክህናት
የጀር ክህናት
የዝቋላ ክህናት
የእቲሳ ክህናት
የደብረ ብርሃን ክህናት
የሳማ ሰንበት ክህናት
የእንጐለላ ክህናት
የድምባሮ ክህናት
የገሬባ ጊዮርጊስ ክህናት
የአዲስ ዓለም ክህናት
የገነተ ማርያም ክህናት
የገነተ ሚካኤል ክህናት
የሙናገሻ መድኃኔዓለም ክህናት
የመናገሻ ማርቆስ ክህናት
የዋጅቱ መድኃኔዓለም ክህናት
የኤጀርሳ ለፎ ጊዮርጊስ ክህናት
የኤጀርሳ ለፎ ገብርኤል ክህናት ናቸው

ሌሎችም ያልጻፍናቸው ብዙ አድባራት ነበሩ ። ደግሞ በጥንት ከተማ እንኮበር ተደግሶ ብዙ አድባራት ተጠር-

ቀው በዚሁ ቀን ተጋብዘዋል ። ዐርላ ድንጋይ በደብረ በግዕም እንዲሁ ተደጓስ ብዙ ካህናት ተጠርተው ተጋብዘዋል

ደግሞ ተከተማ ውጪ ያሉ አገረገዦዎች ሁሉ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ፍቅር ለገንዘባቸው ሳያዝኑ በየከተማቸው ብዙ ገንዘብ አዋፍተው ብዙ ብዙ ካህናት ጋብዘዋል።ሰዓተ ሌሊቱንም ደኅና አድርገው አስፈትተዋል። በሐረርጌ በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አጻራሽ አጠገብ ትልቅ ዳስ ተሠርቶ የብዙ አድባራት ካህናት ተጠርተው በትልቅ ድግስ ተጋብዘዋል ይባላል ። እንግዲህ ወደ መጀመሪው ነገር እንመለስ፤በግንቦት ፪ቀን ወደ ማታ ዋዜማ ተቁሞ አመሸ በየአድባራቱ ወዲያውም ከሌሊቱ ፬ና ፭ሰዓት ሲሆን ማኅሌት ተቁሞ በየቤተ ክርሲቲያኑ ሲዘመር አደረ። ፍታቱና ቅዳሴውም ከአለቀ በኋላ ካህናቱ በሊቀ ካህናቱ በመልአከ ገነት ወልደሐና ማኅተም ተጠርተው ነበሩና በአንድነት ተሰብስበው ወደ ጃንሆይ ግቢ መጡ።፭ሰዓት ተኩል ሲሆን ጃንሆይ ከልፍኝ አጻራሽ ተንሥተው ወደ ዳሱ ገቡ።ዳሱም እጅግ ሰፊ ነበር፤እንደ አጻራሽ ብቆርቆሮ ተከድኖ ያማረ የሚኖር ቤት ይመስል ነበር እንጂ ዳስ አይመስልም ነበር።መጋረጃውና ምንጣፉም እጅግ ያማረ ነበር። የዳሱም ስፋት እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

ያቀማመጥ ተራ ።

ጃንሆይ ለማየት በሚመች ስፍራ በወምበር ተቀምጠው ነበር።

ከጃንሆይ በኋላ ልዑል አስፋ ወሰን በወምበር ተቀምጠው ነበር ።

ከጃንሆይ ቀኝ ብፁዓን የኢትዮጵያ ጳጳሳት በወምበር ብወምበር ተቀምጠው ነበር ።

፩ኛ አቡነ ሳዊሮስ
፪ኛ አቡነ አብርሃም
፫ኛ አቡነ ሚካኤል
፬ኛ አቡነ ጴጥሮስ
፭ኛ አቡነ ይስሐቅ ነበሩ

በጃንሆይ ግራ በወምበር በወምበር ተቀምጠው
የነበሩ ታላላቆች መኳንንት ።

፩ኛ ራስ ኃይሉ
፪ኛ ራስ ሥዩም
፫ኛ ራስ ጉግሣ አርአያ
፬ኛ ራስ ከበደ መንገሻ
፭ኛ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ነበሩ ።

ቆቀሩት በየስፍራው በወምበር እየተቀመጡ
ያስተናብሩ የነበሩ መኳንንት ።

ቢት ወደድ ወልደ ገብርኤል
ደጃዝማች ይገዙ
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ
ደጃዝማች ወንዲራድ (ወንድ ይራድ) ነበሩ ።

ቁመው ወዲያ ወዲህ እየዞሩ ያስተናብሩ የነበሩ መኳንንት

ሊጋባ ወዳጆ
መልአከ ገነት ወልደሐና
ፊታውራሪ ዓምዴ
ፊታውራሪ ወልደ ማርያም
ፊታውራሪ ዓሥራት ወልደ ገብርኤል

ቀኛዝማች ከልክሌ የቀሩትም አጋፋሪዎችና ብዙ መኳንንትና የሠራተኞች ሹማምት ነበሩ ። የግብገሩና የዐጡ የማር ጠጁና የወይን ጠጁ ብዛት ልክ አልነበረውም ። እንኳንስ እኛ ከኛ በፊትም የነበሩ ሽማግሎች እንዲህ ያለ ምግብና መጠጥ ዓይተንም አናውቅ አሉ ። የወጡና የጠጁ ዓይነት ብዛት እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

በመጠጥም ብዛት ራሱ የተጐዳ ሰው እንዳይንገላታ ዘበኞች ተውጪና ተባቢ እንዲጠብቁ ከንቲባ ነሲቡ ታዝዘው ነበርና ራሳቸው ከንቲባ ነሲቡ ወዲህና ወዲያ እያሉ ዘበኞችን ሲአተጉ ዋሉ ። አቶ መቢልም እንዳይሔድ ተከልክሎ ዋለ ። እንዲህም መደረጉ በመጠጥ የተጐዳውን ሰው አቶ መቢል እንዳይገፋው ነው ። በከንቲባና በዘበኞች ብርታት ሰው ሳይጐዳ በመቅረቱ እጅግ ደስ አለን ።

በነጋውም በግንቦት ፬ ቀን ማለዳ ያርባ ልቅሶ ተለቀሰና ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን ለድሆች መጋበዣ ብዙ ድንኳን ተቀጣጥሎ በጉተራው አጠገብ ባለው ሰፊ ሜዳ ተተክሎ ነበርና ጃንሆይ ወደዚያው ድንኳን ገቡ።የአቈልቋዩ ገበታ አረዛዘም እጅግ ያስደንቅ ነበር ። ለድሆች የተጣለው እንጀራና ወጥ ለመኳንንት የተሰናዳ ይመስል ነበር ። ወዲያውም በዚያ ሰፊ ድንኳን መበለቶች በመጀመሪ፤ቀጥለው ወንዶች ገቡና ተቀምጠው ነበር ። ቅቅልና ብርንዶ ሥጋ ብዙ ብዙ እየቈረጡ ይሰጧቸው ነበር ። ጠላና ጠጁንም ጠጥተው የተረፋቸውን በቅላቸው ገለበጡ፤ የተረፋቸውንም እንጀራና ሥጋ በከረጢታቸው ከሞሉ በኋላ ብዙ ብርና ብዙጣቃ አቡጀዲድ መጣና በጃንሆይ ፊት ተከመረ።ከዚህ በኋላ ፲፭ ፲፭ ክንድ አቡጀዲድና ፭ ፩ ብር በተራ ያድሉት ጀመር። ደግሞ ብዙ ፈረስና በቅሎ የተጫነና ያልተጫነም በጃንሆይ ፊት ቀረበና እጅ እግር ለሌላቸው ድኆች በሽታቸው ለበረታባቸ ተሰጠ ። ከዚህ በኋላ ልብስም ብዙ ብርም ለበሽተኞች ድኆች ሲታደል ዋለና በስምንት ሰዓት ጃንሆይ ከድንኳኑ ተነሥተው ወደ ግቢ ገቡ። ድኆችም የደጊቱን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክን ነፍስ ይማር የጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንም ዕድሜ ያድንዝም እስከ ልጅ ልጅ ያንግሥልን እያሉ በየቦታቸው ሔዱ ። በዚህ ተስካር የጠፋው ገንዘብ እጅግ ብዙ ነው ቢገመትም ከመቶ ሺ ብር ይበልጣል ። የእግዚአብሔር ስጦታ ልዩ ልዩ ነው ። አንዳንድ ልጅ ያባቱን ርስት ይሽጣል አንዳንዱ ልጅ የዘመዱን የወዳጁን ስም ያስጠራል።

ለጥቅማችን አዋጅ ማክበር እንዲገባ

እኛም ፥ እንደሰማነው አባቶቻችንም እንደነገሩን ፥ ደግ ንጉሥ ለሕዝቡ አዝኖ በሰንተል ነጋሪት፥ በቈልማማ ዕንጨት አዋጅ ሲነግር ሕዝቡ ደስ ይለውና ዳር እስከ ዳር ይብጅ ያድርግ ይላል ። ነቢዩ እንዳለ እነሆ ክረምት አለፈ፥ ዝናም አለፈ ወደኋላውም ተመለሰ።አበባ በምድር ተገለጠ፥ የዝማሬም ጊዜ ደረሰ የዋላም ቃል በምድራችን ተሰማ ። በለስ ጨበጨበ

ወይኖችም አበበ ጊዜ የሽቶቻቸውን መዓዛ ሰጡ ። ተነሽ አንች ወዳጄ አንችም ውብ ነይ ። ያለውን አሁንም የተወደድሽ ኢትዮጵያ ሆይ ይህን ደስ የሚያሰኝ ያዋጅ ቃል ስሚ፤የክብርሽ ጊዜ መጣልሽ ግርማዊ ንጉሠ አልጋ ወራሽ ሁነው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚጠቀምበት ነገር ሁሉ ሲመሩት ሲያወጡትና ሲያገቡት ሳለ ጠማማ ልብ ካላቸው ክፉ ሰዎች በተቀር ንጉሠ ነገሥትነታቸውን ያልተመኘና ያልናፈቀ የለም እሰይ ጃንሆይ አዋጅዎን ይብጅ ያድርግልን።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ኢትዮጵያን የጥቂት ዓመቶች ሁከቷን ሊታረቃት ሲል እነሆ አንድ ጠቅላይ ንጉሠ ሰጣት። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ንጉሠ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ካረፉ እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ትዳሯ እንዳልተመቻቸ ልሒድ ልኑር ስትል ልቧ እየዋለለ የቤቷን ሥራ አከናውና ለመሥራት ያቃታትን ቆንጆ ትመስል ነበረች ። ሕዝቡም ተጨንቆ አውታሩ እንደተነቀለበት ድንኳን ወዲያና ወዲህ ሲዋልል ነበር።ስለሆነ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከመጠበቅ ቸል አላላትምና ልበ ሰፊ አልጋ ወራሽ ስላደረገላት በብልኅታቸውና በትዕግሥታቸው ሕዝቡ እንዳይፈጃጅ አድርገው ዘመኑን ሁሉ ጠንክረው ጠበቁት። እንዲህ ነው የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን የሚያስረዳ የናትና የልጅ የፍቅራቸው መሠረት ሳይናቃነቅ በማይቀረው ጽዋ ቢለያዩ ኃዘኑም ቢነካቸው ሕዝቡን ለመጠበቅ ሲል በጥበቡ መንበረ ዳዊቱን ሰጣቸው። እንግዲህ የሥልጣኔን ጉዳና ስንናፍቅ የነበርን ሁላችን እርስ በርሳችን በፍቅር ስንገናኝ ሰላምታችን የጃንሆይን ዕድሜ መለመንና የተመኘነው የሥልጣኔ መንገድ ሊገለጥልን ነው የምሥራች ይሁን ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወርቅ በሆነ ትንፋሻቸው ከባቶቼ ሲያያዝ በመጣው ደምብ አሳድርሃለሁና አይዞህ ስላሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከዳር ያለው ልቡ በደስታ ተነክቶ ቀምበሩ የከበደበት ሁሉ የተሻሻለውን ደምብ የሚሰጡትን የጃንሆይን ትንፋሽ ተስፋ አድርጎ ይጠባበቃልና እንዲፈጽሙለት ክንፉን ዘርግቶ መልአኩ ይጠብቅልን፤ የንጉሥ ፊት ሲበራ ሕይወት ነው፤አሽታውም እንደጥብሐት ዝናብ ነው ያለውን አስታውሳለሁ

የመንግሥትን ፈቃድ በመፈጸም ክብርና ሞገስ እንደሚሰጥ

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ገና በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ አፄ ምኒልክ የውቀታቸውንና የሥልጣኔያቸውን ነገር ተምልክተው ማዕረጋቸውንም ከፍ አድርገው እንደወለዱት ልጅ አድርገው ይወዷቸው ነበር ። አሁንም በኛ ዘመን ካሁኑ ጊዜ ሥልጣኔ ጋራ የተስማሙ ዕውቀት ያደረባቸው ብልህ። ከቤተ መንግሥትም የቃመኑ በታዘዙበትም ሁሉ ስንፍ እማይገባቸው እውነት ልበ ሙሉ በመሆናቸው መኳንንቱና ሠራዊቱ ክብራቸውንም ከፍ አድርጎ በፍቅር ይወዳቸዋል ። ስለምን ማለት ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ከሁሉ የበለጠ ከፍ ያለ ማዕረግ ሳላቸው የተማሩናቸውና ትቢትን እንደጉድፍ ጣል አድርገዋት ትንሽ ትልቁን እንደባልጀራ እያነጋገሩ ሰው ያቀርባሉ ። ለሰውም ሰላምታ ሲሰጡ እጅ ሲነሷቸው እንዴት ዋልክ አገሌ እንዴት ሰነበትክ አገሌ ብለው በስም በስሙ ክብር እየሰጡ ደስ ያሰኙታል እንጂ የሚያውቁትን እንደማያውቁት እጅ ሲነሷቸው በይናቸው አይተው ዝም እንደሚሉት አይደሉም ። አምና ከቤታቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አባ ጠቅል ከመንበረ ዳዊታቸው ላይ ተቀምጠው ሠራዊቱን ሁሉ ያስደነቀውን ግብራቸውን ያበሉላቸው ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ራሳቸው እየዞሩ ሕዝቡን ሲያስተናብሩና ሲአስቀምጡት ያለመዘንጋታቸውንና ሕግጋቱንም እንደምን እንደሠሩት ነገር እጅግ አድርጎ ያስደንቅ ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ በውቀታቸው ሁል ጊዜ የሚሠሩት የቤተ መንግሥት ጉዳይ ሁሉ እንዲተከናወላቸው ነውና ከፍ ያለ ምስጋና የሚገባቸው ናቸው።ደግሞ ዛሬ የኢትዮጵያ ልጆች በእግዚአብሔር ኃይል በንጉሣችን መሪነት ወደሥልጣኔው መንገድ ተቀዳድመን ዕውቀት ደረጃ ላይ እንድንቀመጥና አገራችንን እናስከብራታለን ብለን ያንድነትንና የፍቅርን መሣሪያ ለማቆም በምንጣጣርበት ጊዜ እንደገና ወደ ጨለማ ገፍትሮ ለመጣል ክፉ ሐሳብ ያደረበትን እናቲቱንና ልጅቱን ባንድ ውጪ ድብልቅልቅ አ ድርገዋለሁ ብሎ የተነሣውን ዘንዶ እንኳን የጣለና ። አንድ ሰው ከቤቱ በማለዳ ወጥቶ ወደዱር ገብቶ ጨፈቃ ሲቈርጥ ውሎ አሥሮ ተሸክሞ ከቤቱ በራፍ ሲደርስ ከትከሻው ላይ አውርዶ እረብ ሲያደርገው ከቤት የዋለው ሰው ሁሉ ወጥቶ እንኳን ደኅና ገባህ ተበረክ፤ጉሽ ጣል፤ ዝሆን ጣል ፤ ወንድሜ እንዲህ ያውደቅ ይሉታል ። እሱም ያነን ልፋቱን ሁሉ አይቈጥረውም። በዚሁም ምስጋና ደስ ብሎት ከቤቱ ገብቶ ይቀመጣል ። ዝም ያሉት እንደሆነ ግን ከቀኑ የባሰ ድካም ፀልቅ ይሰማውና ልቡን ከፍቶት በውጭ እንደቈመ ይቀራል። ስለዚህ ኃያላኑ ጀግኖች ታዘው ወደዘመቻ ሲሔዱ ያገሩን ጉዳት ከማያውቅ ከደነዝ በተቀር ሐሳብና ኃዘን ያልያዘው ሰው የለም ነበር እግዚአብሔር በቸርነቱ ኃይሉን አሳድሮባቸው የመንግሥታችንን ፈቃድ ፈጽመው ዓመፀኛውን ቀጥተው እምቢተኛውን አሳምነው በደኅና ስለተመለሱ ለጦር ምንስቴሩ ለክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታና ለክቡራን መኳንንቶች ላርበኞች ወታደሮቹም እንኳን ደኅና ገባችሁ ስል ከልብ የሆነ ምስጋናዬንና በዚሁ ሥራ ታዘው ሔደው ያረፉትንም ጀግኖች ልዑል እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት በመጽሐፈ ሕይወቱ መንግሥትም በታሪክ ነገሥቱ ስማቸውን ይጻፍላቸው እያልኩ በትሕትና የከበረ የምርቃን ሰላምታቸውን በማክበር አመለክታለሁ ።

የጀግኖች መቀበያ የክብር ሰላምታ ጥልቅ አማርኛ ግጥም።

አጋፋሪ ሁነው እኒህ ደጃች ሙሉ
በፍጥነት ገስግሠው ከበር ይቆማሉ
እንደልጅ ሆኑ ወይ ትልቁ ሰውዬ
ሉሬዎን ከፍ አርገው ጉልበትዎ ታዬ
ከልክዩ ዝም አትበል በሩን ና ክፈተው
ክብር ያገኛልና ለመንግሥት የሞተው

ቶው በዚሁ ቀን ተጋብዘዋል ። ቦርላ ድንጋይ በደብረ በግዕም እንዲሁ ተደግሶ ብዙ ካህናት ተጠርተው ተጋብዘዋል

ደግሞ ተከተማ ውጪ ያሉ አገረገዦዎች ሁሉ ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ፍቅር ለገንዘባቸው ሳያዝኑ በየከተማቸው ብዙ ገንዘብ አጥፍተው ብዙ ብዙ ካህናት ጋብዘዋል።ሰዓተ ሌሊቱንም ደኅና አድርገው አስፈትተዋል። በሐረርጌ በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አዳራሽ አጠገብ ትልቅ ዳስ ተሠርቶ የብዙ አድባራት ካህናት ተጠርተው በትልቅ ድግስ ተጋብዘዋል ይባላል ። እንግዲህ ወደ መጀመሪያው ነገር እንመለስ፤በግንቦት ፪ቀን ወደ ማታ ዋዜማ ተቁሞ አመሽ በየአድባራቱ ወዲያውም ከሌሊቱ ፱ና ፲ሰዓት ሲሆን ማኅሌት ተቁሞ በየቤተ ክርስቲያኑ ሲዘመር አደረ። ፍታቱና ቅዳሴውም ከአለቀ በኋላ ካህናቱ በሊቀ ካህናቱ በመልአከ ገነት ወልደሐና ማኅተም ተጠርተው ነበሩና ባንድነት ተሰብስበው ወደ ጃንሆይ ጣቢ መጡ።፲ሰዓት ተኩል ሲሆን ጃንሆይ ከልፍኝ አዳራሽ ተንሥተው ወደ ዳሱ ገቡ።ዳሱም እጅግ ሰፊ ነበር፤እንደ አዳራሽ በቆርቆሮ ተከድኖ ያማረ የሚኖር ቤት ይመስል ነበር እንጂ ዳስ አይመስልም ነበር።መጋረጃውና ምንጣፉም እጅግ ያማረ ነበር። የዳሱም ስፋት እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

ያቀማመጥ ተራ ።

ጃንሆይ ለማየት በሚመች ስፍራ በወምበር ተቀምጠው ነበር።

ከጃንሆይ በኋላ ልዑል አስፋ ወሰን በወምበር ተቀምጠው ነበር ።

ከጃንሆይ ቀኝ ብፁዓን የኢትዮጵያ ጳጳሳት በወምበር በወምበር ተቀምጠው ነበር ።

፩ኛ አቡነ ሳዊሮስ
፪ኛ አቡነ አብርሃም
፫ኛ አቡነ ሚካኤል
፬ኛ አቡነ ጴጥሮስ
፭ኛ አቡነ ይስሐቅ ነበሩ

በጃንሆይ ግራ በወምበር በወምበር ተቀምጠው
የነበሩ ታላላቆች መኳንንት ።

፩ኛ ራስ ኃይሉ
፪ኛ ራስ ሥዩም
፫ኛ ራስ ጉግሣ አርአያ
፬ኛ ራስ ከበደ መንገሻ
፭ኛ ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ነበሩ ።

ቆቀሩት በየስፍራው በወምበር እየተቀመጡ
ያስተናብሩ የነበሩ መኳንንት ።

ቢት ወደድ ወልደ ገብርኤል
ደጃዝማች ይገዙ
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ
ደጃዝማች ወንዲራድ (ወንድ ይራድ) ነበሩ ።

ቁመው ወዲያ ወዲህ እየዞሩ ያስተናብሩ የነበሩ መኳንንት

ሊጋባ ወዳጆ
መልአከ ገነት ወልደሐና
ፊታውራሪ ዓምዴ
ፊታውራሪ ወልደ ማርያም
ፊታውራሪ ዓሥራት ወልደ ገብርኤል

ቀኛዝማች ከልክሌ የቀሩትም አጋፋሪዎችና ብዙ መኳንንትና የሠራተኞች ሹማምት ነበሩ ። የግብዣውና የሀጡ የማር ጠጁና የወይን ጠጁ ብዛት ልክ አልነበረውም ። እንኳንስ እኛ ከኛ በፊትም የነበሩ ሽማግሎች እንዲህ ያለ ምግብና መጠጥ ዓይተንም አናውቅ አሉ ። የወጡና የጠጁ ዓይነት ብዛት እጅግ ያስደንቅ ነበር ።

በመጠጥም ብዛት ራሱ የተጐዳ ሰው እንዳይንገላታ ዘበኞች ተውጪና ተጣቢ እንዲጠብቁ ከንቲባ ነሲቡ ታዝዘው ነበርና ራሳቸው ከንቲባ ነሲቡ ወዲህና ወዲያ እያሉ ዘበኞችን ሲአተጉ ዋሉ ። አቶ መቢልም እንዳይሔድ ተከልክሉ ዋለ ። እንዲህም መደረጉ በመጠጥ የተጐዳውን ሰው አቶ መቢል እንዳይገፋው ነው ። በከንቲባና በዘበኞች ብርታት ሰው ሳይጐዳ በመቅረቱ እጅግ ደስ አለን ።

በነጋውም በግንቦት ፬ ቀን ማለዳ ያርባ ልቅሶ ተለቀሰና ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን ለድሆች መጋበዣ ብዙ ድንኳን ተቀጣጥሎ በጉተራው አጠገብ ባለው ሰፊ ሜዳ ተተክሎ ነበርና ጃንሆይ ወደዚያው ድንኳን ገቡ።የአቄልቋዩ ገበታ አረዛዘም እጅግ ያስደንቅ ነበር ። ለድሆች የተጣለው እንጀራና ወጥ ለመኳንንት የተሰናዳ ይመስል ነበር ። ወዲያውም በዚያ ሰፊ ድንኳን መበለቶች በመጀመሪ፤ ቀጥለው ወንዶች ገቡና ተቀምጠው ነበር ። ቅቅልና ብርንዶ ሥጋ ብዙ ብዙ እየቈረጡ ይሰጧቸው ነበር ። ጠላና ጠጁንም ጠጥተው የተረፋቸውን በቅላቸው ገለበጡ፤ የተረፋቸውንም እንጀራና ሥጋ በከረጢታቸው ከሞሉ በኋላ ብዙ ብርና ብዙጣቃ አቡጀዲድ መጣና በጃንሆይ ፊት ተከመረ።ከዚህ በኋላ ፲፭ ፲፭ ክንድ አቡጀዲድና ፩ ፩ ብር በተራ ያድሉት ጀመር። ደግሞ ብዙ ፈረስና በቅሎ የተጫኑና ያልተጫኑም በጃንሆይ ፊት ቀረበና እጅ እግር ለሌላቸው ድኆች በሽታቸው ለበረታባቸ ተሰጠ ። ከዚህ በኋላ ልብስም ብዙ ብርም ለበሽተኞች ድኆች ሲታደል ዋለና በስምንት ሰዓት ጃንሆይ ከድንኳኑ ተነሥተው ወደ ግቢ ገቡ። ድኆችም የደጊቱን የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክን ነፍስ ይማር የጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንም ዕድሜ ያርዝም እስከ ልጅ ልጅ ያንግሥልን እያሉ በየቦታቸው ሔዱ ። በዚህ ተስካር የጠፋው ገንዘብ እጅግ ብዙ ነው ቢገመትም ከመቶ ሺ ብር ይበልጣል ። የእግዚአብሔር ስጦታ ልዩ ልዩ ነው ። አንዳንድ ልጅ ያባቱን ርስት ይሸጣል አንዳንዱ ልጅ የዘመዱን የወዳጁን ስም ያስጠራል።

ለጥቅማችን አዋጅ ማክበር እንዲገባ

እኛም ፥ እንደሰማነው አባቶቻችንም እንደነገሩን ፥ ደግ ንጉሥ ለሕዝቡ አዝኖ በሰንተል ነጋሪት፥ በቈልማማ ዕንጨት አዋጅ ሲነግር ሕዝቡ ደስ ይለውና ዳር እስከ ዳር ይብጅ ያድርጓ ይላል ። ነቢዩ እንዳለ እነሆ ክረምት አለፈ፥ ዝናም አለፈ ወደኋላውም ተመለሰ።አበባ በምድር ተገለጠ፥ የዝማሬም ጊዜ ደረሰ የዋላም ቃል በምድራችን ተሰማ ። በለስ ጨበጨቡ

ወይኖችም አበቡ ጊዜ የሽቶቻቸውን መዓዛ ሰጡ ። ተነሽ አንች ወዳጄ አንችም ውብቴ ነይ ። ያለውን አሁንም የተወደድሽ ኢትዮጵያ ሆይ ይህን ደስ የሚያሰኝ ያዋጅ ቃል ስሚ፤የክብርሽ ጊዜ መጣልሽ ግርማዊ ንጉሥ አልጋ ወራሽ ሁነው የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደሚጠቀምበት ነገር ሁሉ ሲመሩት ሲያወጡትና ሲያገቡት ሳለ ጠማማ ልብ ካላቸው ከክፉ ሰዎች በተቀር ንጉሠ ነገሥትነታቸውን ያልተመኘና ያልናፈቀ የለም እሰይ ጃንሆይ አዋጅዎን ይብጅ ያድርግልን።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ኢትዮጵያን የጥቂት ዓመቶች ሁከቷን ሊታረቃት ሲል እነሆ አንድ ጠቅላይ ንጉሥ ሰጣት። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ንጉሥ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ካረፉ እስከ ዛሬ ድረስ ኢትዮጵያ ትዳሯ እንዳልተመቻች ልሒድ ልኑር ስትል ልቧ እየዋለለ የቤቷን ሥራ አከናውኖ ለመሥራት ያቃታትን ቆንጆ ትመስል ነበረች ። ሕዝቡም ተጨንቆ አውታሩ እንደተነቀለበት ድንኳን ወዲያና ወዲህ ሲዋልል ነበር።ስለሆነ እግዚአብሔር በቸርነቱ ከመጠበቅ ቸል አላላትምና ልበ ሰፊ አልጋ ወራሽ ስላደረገላት በብልኃታቸውና በትዕግሥታቸው ሕዝቡ እንዳይፈጀጅ አድርገው ዘመኑን ሁሉ ጠንክረው ጠበቁት። እንዲህ ነው የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን የሚያስረዳ የናትና የልጅ የፍቅራቸው መሠረት ሳይነቃነቅ በማይቀረው ጽዋ ቢለያዩ ኃዘኑም ቢነካቸው ሕዝቡን ለመጠበቅ ሲል በጥበቡ መንበረ ዳዊቱን ሰጣቸው። እንግዲህ የሥልጣኔን ጉዳና ስንናፍቅ የነበርን ሁላችን እርስ በርሳችን በፍቅር ስንገናኝ ሰላምታችን የጃንሆይን ዕድሜ መለመንና የተመኘነው የሥልጣኔ መንገድ ሊገለጥልን ነው የምሥራች ይሁን ።

ንጉሠ ነገሥቱ ወርቅ በሆነ ትንፋሻቸው ከብቶቼ ሲያገዝ በመጣው ደምብ አሳድርሃለሁና አይዞህ ስላሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ዳር እስከዳር ያለው ልቡ በደስታ ቀንክቶ ቀምበሩ የከበደበት ሁሉ የተሻሻለውን ደምብ የሚሰጡትን የጃንሆይን ትንፋሽ ተስፋ አድርጎ ይጠባበቃልና እንዲፈጽሙለት ክንፉን ዘርግቶ መልአኩ ይጠብቅልን፤ የንጉሥ ፊት ሲበራ ሕይወት ነው፡እሽታውም እንደጥብሐት ዝናብ ነው ያለውን አስታውሳለሁ

የመንግሥትን ፈቃድ በመፈጸም ክብርና ሞገስ እንደሚሰጥ

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ገና በልጅነታቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ አፄ ምኒልክ የውቀታቸውንና የሥልጣኔያቸውን ነገር ተምልክተው ማዕረጋቸውንም ከፍ አድርገው እንደወለዱት ልጅ አድርገው ይወዷቸው ነበር ። አሁንም በኛ ዘመን ካሁኑ ጊዜ ሥልጣኔ ጋራ የተስማሙ ዕውቀት ያደረባቸው ብልህ። ከቤተ መንግሥትም የታመኑ በታዘዙበትም ሁሉ ስንፍ እማይገባቸው እውነት ልበ ሙሉ በመሆናቸው መኳንንቱና ሠራዊቱ ክብራቸውንም ከፍ አድርጎ በፍቅር ይወዳቸዋል ። ስለምን ማለት ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ከሁሉ የበለጠ ከፍ ያለ ማዕረግ ሳላቸው የተማሩናቸውና ትቢትን እንደጉድፍ ጣል አድርገዋት ትንሽ ትልቁን እንደባልጀራ እያነጋገሩ ሰው ያቀርባሉ ። ለሰውም ሰላምታ ሲሰጡ እጅ ሲነሷቸው እንዴት ዋልክ አገሌ እንዴት ሰነበትክ አገሉ ብለው በስም በስሙ ክብር እየሰጡ ደስ ያሰኙታል እንጂ የሚያውቁትን እንደማያውቁት እጅ ሲነሷቸው ባይናቸው አይተው ዝም እንደሚሉት አይደሉም ። እምና ከቤታቸው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ አባ ጠቅል ከመንበረ ዳዊታቸው ላይ ተቀምጠው ሠራዊቱን ሁሉ ያስደነቀውን ግብራቸውን ያበሉላቸው ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ራሳቸው እየዞሩ ሕዝቡን ሲያስተናብሩና ሲአሰቀምጡት ያለመዘንጋታቸውንና ሕግጋቱንም እንደምን እንደሠሩት ነገር እጅግ አድርጎ ያስደንቅ ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታ በውቀታቸው ሁል ጊዜ የሚሠሩት የቤተ መንግሥት ጉዳይ ሁሉ እንደተከናወላቸው ነውና ከፍ ያለ ምስጋና የሚገባቸው ናቸው።ደግሞ ዛሬ የኢትዮጵያ ልጆች በእግዚአብሔር ኃይል በንጉሣችን መሪነት ወደሥልጣኔው መንገድ ተቀዳድመን ዕውቀት ደረጃ ላይ እንድንቀመጥና አገራችንን እናስከብራታለን ብለን ያንድነትንና የፍቅርን መሣሪ ለማቆም በምንጣጣርበት ጊዜ እንደገና ወደ ጨለማ ገፍትሮ ለመጣል ክፉ ሐሳብ ያደረበትን እናቲቱንና ልጅቱን ባንድ ውጪ ድብልቅልቅ ኣ ድርገዋለሁ ብሎ የተነሣውን ዘንዶ እንኳን የጣለና ። አንድ ሰው ከቤቱ በማለዳ ወጥቶ ወደዱር ገብቶ ጨፈቃ ሲቈርጥ ውሎ አሥሮ ተሸክሞ ከቤቱ በራፍ ሲደርስ ከትከሻው ላይ አውርዶ እረብ ሲያደርገው ከቤት የዋለው ሰው ሁሉ ወጥቶ እንኳን ደኅና ገባህ ተበረክ፤ጕሽ ጣል፤ ዝሆን ጣል ፤ ጠላትህ እንዲህ ይውደቅ ይሉታል ። እሱም ያነን ልፋቱን ሁሉ አይቈጥረውም። በዚሁም ምስጋና ደስ ብሎት ከቤቱ ገብቶ ይቀመጣል ። ዝም ያሉት እንደሆነ ግን ከቀኑ የባሰ ድካም ይልቅ ይሰማውና ልቡን ከፍቶት በውጭ እንደቈመ ይቀራል። ስለዚህ ኃያላኑ ጀግኖች ታዘው ወደዘመቻ ሲሔዱ ያገርን ጉዳት ከማያውቅ ከደነገዘ በተቀር ሐሳብና ኃዘን ያልያዘው ሰው የለም ነበር እግዚአብሔር በቸርነቱ ኃይሉን አሳድሮባቸው የመንግሥታችንን ፈቃድ ፈጽመው ዓመፀኛውን ቀጥተው እምቢተኛውን አሳምነው በደኅና ስለተመለሱ ለጦር ምንስቴሩ ለክቡር ደጃዝማች ሙሉ ጌታና ለክቡራን መኳንንቶች ላርበኞች ወታደሮቹም እንኳን ደኅና ገባችሁ ስል ከልብ የሆነ ምስጋናዬንና በዚሁ ሥራ ታዘው ሔደው ያረፉትንም ጀግኖች ልዑል እግዚአብሔር በመንግሥተ ሰማያት በመጽሐፈ ሕይወቱ መንግሥትም በታሪክ ነገሥቱ ስማቸውን ይጻፍላቸው እያልኩ በትሕትና የከበረ የምርቃን ሰላምታቸውን በማክበር አመለክታለሁ ።

የጀግኖች መቀበያ የክብር ሰላምታ ጥልቅ አማርኛ ግጥም።

አጋፋሪ ሁነው እኒህ ደጃች ሙሉ
በፍጥነት ገስግሠው ከበር ይቆማሉ
እንደልጅ ሆኑ ወይ ትልቁ ሰውዬ
ሱሪዎን ከፍ አርገው ጕልበትዎ ታዬ
ከልክዩ ዝም አትበል በሩን ና ክፈተው
ክብር ያገኛልና ለመንግሥት የሞተው

ክልክዩ ሲጋፋ ጣብሩ ሲጋነን
በፊት ዘለቀው ወንዱ በወሰን
ምነው ሕዝቡ ሳሳ ይኸ ስንቅ የሌለው
በጣምበር ገሥግሦ የገባው እያሌው
ጣጥሶ ሊገባ ሕዝቡ መብል ሲሻ
ጨፍጭሮ መለሰው አሳጣው መሸሻ
ማሠሯ የሚይዝ የላቸውም ዘመድ ።
በቶሎ ተፈታ የቋጠሩት ገመድ ።
አልበቃው አለና የተሠራው ዳስ።
ከሜዳ ላይ ጣሉት ያን ሁሉ ድንኳስ ።
ኣዝር ያማራቸው ቢገቡ እየሳሱ ።
ሳይሞላ አንድ ሰዓት አለቀ ድግሱ ።
ዝናቡን አስበው ከደጅ ያለውን ።
አሁን ግባ ባሉት ያንን መኰንን ።
ማሩን ከገዙበት ተረፈና ብሩ
ይሻማ ጀመረ አልፎ ወታደሩ
እንዲህ ያል ወታደር የመሰለ አሞራ
ጥርግርግ አረገው ያንን ሁሉ እንጀራ
ሊጋበው ነበረ ንጉሡን አክባሪ
የጦር ምንስቴሩ ሁነዋል አጋፋሪ
አጋፋሪ ሁነው ሕዝቡ ተንገላታ
ራስ ይመታሉ ደጃች ሙሉጌታ
ወደላይ ከፍ ብለው ቢቆሙ ይሻላል
ንጉሥ ደቄጡና ራስኩን ይሉኻል
እሱ ሙሉ ጌታ ሚስቱ በለጥሻቸው
ራስ እየመታ ይጥላል ጠጃው
በግራና በቀኝ ዝናም ተሰማ
እንግዲህ ማን ቀሞ ከርስዎ ፊትማ
መችም ልማዱ ነው የርስዎን ድግስ
ጠጣው ጠጣው ሲሉ ያስመታሉ ራስ
እራስ እየመቱ ሕዝቡ እንዳይከፋ
እንዳምናው ይጋብዙት ጕበዝ እንዲፋፋ
አምና የተበላው መቸ መና ቀረ
ቆንቋና አልተባሉም ሕዝቡ መሰከረ
ያስበጠበጥሽው ጠጅ አንችም በለጥሻቸው
የጠጣው ሰው ሁሉ ተመታ ራሳቸው
ታይቶም አይታወቅ እንደዚህ ያል ድግስ
ስም እንዲህ ሲወጣ ከሰማይ ሲደርስ
ጠጁ አለቀ አለችው ልቡን ልትሰልለው
እንቺም ማዬ ብሎ ሒዶ አዘነበለው
መቸር የለመደ ይሰጣል ለሁሉ
ጠጁም አላለቀ ተገኘ በሙሉ
ቅዳው አስተካክለህ ስጥ አንተ አሳላፊ
ገና ያበላሉ አዳራሹ ሰፊ
ለካ ክልካይ ኖሯል ያግራዝማች ኀይሌ
አጣድሮ መለሰው የጓጓውን ሎሌ
ሙያ ሲቋጠሩ ጀግኖቹ ሲገቡ
የጠቅል እንጂ ነው መቸውም ነሲቡ
በተስኪያን ካመሒድ ከመስማት ቅዳሴ
አልፍኝዎ ሞልቷል በፍቅረ ሥላሴ
ሕዝብዎን ደስ አለው ያዋጅዎ ቃሉ
ባንድነት ተስማምተው ሁሉም ለጥ ይበሉ
ሕዝቡም ይውጣ ደጓባ ጃንሆይ ይዘዙ
ሽማግሎች ሁሉ ምክርዎን ይገዙ
ሥራ መች ይቀናል ፀሐይም በንደራሴ
ሁሉም ተፈጸመ በግብረ ሥላሴ
ሥራ እንኳ ባይዙ አይርብ አይጠማ
ሲሳይ አይደለም ወይ የንጉሡ ከተማ
ግብርዎ ሰፊ ነው ሁል ጊዜ ደግሰው ።
በማዕረግ ከፍ ብሎ ይበላል ያጣ ሰው ።
ይስጡት ለጸሐፊው እንዲያነብልዎ
ብርሃንንና ሰላም ቀርቧል ከፊትዎ
ማነው ያነበበው ያን ሁሉ ዝርናል
በጣም ተመስጣኖ ይባላል ኃያል
ለሕዝቡ ሲያስቡ ሁል ጊዜ ንጉሥ
ሃይማኖት አፀኑ ተክለው ማርቆስ
እንዲህ ያለ ዘመን መችም አላገኘሁ
በጣሙ ደስ አለኝ እሰይ ዓለም አየሁ
እንዴት አማረበት ይኸ ማኅተም
ባንድነት ተጽፎ የጀግኖቹ ስም
ነጋዴ እንዲነግድ እንዲያርስ ገበሬ
ደስ የሚያሰኝ አዋጅ ተነገረ ዛሬ
ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቅርብ ዝማሬ

መክብብ ደስታ

የድሬዳዋ አውራጃ ወሬ ።

ባለፈው ሰሞን በሚያዚያ ፳፱ ቀን ሙሴ ዶሬክፌ የሚባሉ የሚክ ሥራ ውል የተዋዋሉና ዶዣሞ ሙሴ ካሚ የሚባሉ ሁነው ፫ፈረሶቻቸውን በካሚዎክ ካዲጋላ ጣቢያ ወደጅጅጋ ሲሔዱ ካሚዎኑ አመንገድ ተሰናክሎባቸው ኖሮ ፮ቀን ሙሉ ባዲጋላም በጅጅጋም በኩል ቢጠየቅ የደረሱበት ወሬአቸው ስለጠፋ የነዚሁ ቤተ ሰዎች ከድሬዳዋ ወዳዲስ አበበ ቴሌግራም አሳልፈው ነበርና ይኸንኑ ጃንሆይ ሰምተው በያውራጃው ቴሌግራም እንዲያልፍና ፈረሰኛም እየተከታተለ በየቦታው እንዲጠይቅ ብርቱ ትእዛዝ ሰጡ ። ከዚህም በቀር አገሩ በረኻ ስለሆነ የደረሱበትን ለማወቅና ያገኛቸውም አደጋ እንዳለ ለመመርመር በግንቦት ፩ቀን ወደድሬዳዋና ወደ ኢሳ በረኻ አይሮፕላኑ ተላከ ። ነገር ግን ባለካሚዎኖቹን የመንገዱ አለመ-ቃናት አስግሮአቸው ነው እንጂ ደኅና ናቸው የሚል ቴሌግራም ከሐረርም ከጅጅጋ መጣ አይሮፕላኑም ጅጅጋ ደርሶ እዚያው አድሮ የደኅንነታቸውን አኳኋን ሁሉ አስረግጦ ወዲያው ከጅ-ጅጋ ከተማ የጃንሆይን ፪ለማዳ ግልገል አንበሶች ከነ ከርዲያቸው

ይዞ ከጅጅጋ በ፩ ሰዓት ተንሥቶ በ፫ሰዓት ተኩል አዲስ አበባ ገባ ። ስልክ በሌለበትና ለድንገት ትእዛዝ ለሚሆን ጉዳይ ችግር ሁሉ የዩሮፕላን መላክተኛ መጥቀሙን ያስረዳል ።

የከተማ ወሬ ።

ክደጃች ሙሉ ጌታ ጋራ ዘምተው በጦርነት ለቈሰሉ ሰዎች መታመሚያ ለምግብም ሆነ ለልብስም ለሚያስፈልጋቸው እንዲያደርጉት ፲ሺህ ብር ከደሴ ግምጃቤት በአይሮፕላን ተጭኖ እተዋጉበት አገር ድረስ ሒደላቸው ማለትን ሰምተን ነበርና ገና ወደከተማ ሳይገቡ መንግሥታችን እጅግ ደስ የሚያሰኝና የበዛ ርኅራኄ በማድረጉ የማይረሳ ቸርነት ነው ።

ደግሞ አሁን ፲፰ የሚሆኑ ቍስለኞች በካሚዎን ቀድመው መጥተው ነበረና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል እንዲገቡ አዘዙ። በ፪ተኛውም ቀን ጃንሆይ ራሳቸው እሆፒታል ድረስ ሒደው ጠየቋቸው ቍስለኞቹም እዚያው እንደተኙ የለመኑትን የመሬትና የገንዘብ ልመና በደስታ አደረጉላቸው ።

እንደዚህ የሚያስብ እርኅራኄ ያለውን መንግሥታችንና አገራችንን፣ የኢትዮጵያንም ጀግኖች እግዚአብሔር ይጠብቅልን ስንል እንጸልያለን ።

አቶ በቀለ ዘለቀ ለኢትዮጵያውያን ወይዛዝር ማስታወሻ ስለጻፉት መልስ ።

መጋቢት ፲፯ ፲፱፻፳፪ ዓ ም በ፯ኛው ዓመት በ፲፪ኛው ቍጥር በወጣው ብርሃንና ሰላም ።

አቶ በቀለ ዘለቀ የኢትዮጵያ ወይዛዝርት የሥልጣኔን መንገድ እንዲከተሉ እያሉ አዘውትረው የምክርና የወቀሳ ቃል ይጽፋሉ እኔም ዘወትር ለሚጽፉት ሁሉ መልሱን ለመጻፍ እያሰብኩ ያለሁበት አገር ስለራቀ እየተላለፈብኝ ቈየብኝ አሁን ግን አቶ በቀለ ዘለቀ እየመላለሱ ምክራቸውንና ወቀሳቸውን ስለጻፉ ምንም ያለሁበት አገር ቢርቅ የግድ መልሱን መጻፍ የሚያሳስበኝ ስለሆነ ይህን ለመጻፍ አሰብኩ። መቼም ሰው አንድ ነገር ሲያስብ የሚከተለው ያንኑ ሐሳቡን ነው እንጂ ሌላውን ሐሳብ አያስተውልም ። እንዲሁም አቶ በቀለ ዘለቀ ለኢትዮጵያ ወይዛዝር መልካም መልካሙን ምክር ሁሉ ሲጽፉ አንድ ነገር ሳያስታውሱ ቀርተዋል ። ይኸንኑም አቶ በቀለ ዘዘቀ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የጻፉትን የምክር ቃል ሳልነቅፍ የቀረውን ሐሳብ ከዚህ ቀጥዬ ባልታረመችና ባልተቃናች በሒዋን አእምሮዬ አስታውሳለሁና ስሕተትም ቢገኝበት ይቅረታ ጭምር እንዲነበብልኝ ለአንባቢዎች ልመናዬን ከቀረብኩ በኋላ ሐሳቤን እቀጥላለሁ። አቶ በቀለ ዘለቀ የሚመክሩን ፩ኛ ሴቶች ልጆቻችን ተማሪ ቤት እንድንሰድ።፪ኛ መሸፋፈንን እንድንተው ። ፫ተኛ ቀሚሳችንን እንድናሳጥር ። ፬ተኛ ደጅ ጥናትን ትተን ለጕዳዮቻችን በርትተን እንድንሠራ ነው።ይኸንኑም እሳቸው ልብ አድርገው ባያስተውሉት ነው እንጂ።ቅዱስ ጴጥሮስ በ፩ኛ መልእክቱ በምዕራፍ ፫ በቍጥር ፩ እንደሚያዘው ለኛ ገጋር ዎቻችን ባሎቻችን ስለሆኑ ባሎቻችን ሥልጣኔን ካገኙ ይህ ሁሉ እሳቸው ያሰቡት ነገር በባሎቻችን በኩል እንዲፈጸም የማይጠረጠር ነውና መጀመሪያ ወንዶች በፍጹም የሥልጣኔን መንገድ እንዲከተሉ ምክራቸውን ማበርታት ይገባቸዋል ። ይኸንኑም በቅዱስ መጽሐፍ የተጻፈውን ብንመለከት በጣሙን እንረዳለን ማለት ። ሮሜ ም ፲፩ ቍ ፲፮ እርሾው የተቀደሰ ከሆነ ቡሆውም የተቀደሰ ነው፤ ሥሩም ንጹሕ ከሆነ ጫፎችም እንደዚሁ ናቸው ይላል። ደግሞ ፩ኛ ቆሮንቶስ ም ፯ ቍ ፲፬ና ፲፯ ብንመለከት እንደዚሁ ያስረዳናል ። ደግሞም አቶ በቀለ ዘለቀ የአውሮፓ ወይዛዝርት እንደምን አድርገው ወደ ሥልጣኔ እንደ ደረሱ ገልጸው አልጻፉልንም ግን እኛ የውጭ አገር ታሪክ ከአነበቡ ሰዎች እንደሰማነው የአውሮፓ ወይዛዝርት ሁሉ እስከዚህ ሥልጣኔ የደረሱት በባሎቻቸው መሪነት እንጂ እነሱ በገዛ እጃቸው እስከዚህ ሥልጣኔ እንዳልደረሱ ተረድተናል። ስለዚህ ወንዶች ሁሉ በውነት የሥልጣኔን መንገድ ከተከተሉ የኛ ሥልጣኔ ቅጽበተ ዓይን እንደማይቆይ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ያስረዳል ።

መጀመሪያ ስለሴት ልጆቻችን እኛ መቸም ወንድ ወይም ሴት ልጅ ቢሆን ያላንድ አባት ለመወለድ አይቻለንምና ስለዚህ ወላጅ አባት የሆነ ሁሉ ሴት ልጅን ማሳደግ ዓይነ አፋር እንድትሆን እጓዳ ደብቆ ነው እንጂ ደጅ ለደጅ ያሳደጓት እንደሆነ ጋንጢጥ ወይም ባለጌ ትሆናለች እያሉ እንጓዳ በመደበቅ ፋንታ ሴቶች ልጆቻቸውን በሕጻንነታቸው ወላጅ አባቶቻቸው ወደ ተማሪ ቤት እንዲሒዱ ቢያዙ እኛ ከልክለን ባላሳጣንም ነበር ። አሁንም ቢሆን ሴቶች ልጆቻችን ትምሕርት ለመማር የሚችሉት ባባቶቻቸው ፈቃድ ነው እንጂ የኛ ፈቃድ ከልክሎ እንዳያስቀራቸው የታወቀ ነው ።

ሁለተኛ ስለመሸፋፈናችን አሁን ሽፍንፍናችንን ትተን ተገልጠን እንሂድ ብንል ባሎቻችን ጕረምሳ ለማየትና ፊታቸውን ለማሳየት ነው እያሉ ይቆጡብናል ይኸንን በማለት ፋንታ ወደ መንገድ በሄድን ጊዜ እኛ እንኳን እንደልማዱ ለመሸፋፈን ብናስብ ገገርዎችን የሆኑ ባሎቻችን መሸፋፈን ነውር ሁኖዋልና ሳትሸፋፈኑ በግልጽ ሒዱ ብለው ቢገሥፁን ጥንት የተለመደ ሁኖ ምንም ሐፍረት ሐፍረት ቢለን በግድ የባሎቻችንን ፈቃድ ለመፈጸም ሽፍንፍናችንን ትተን በግልጽ በሔድን ነበር ።

ሶስተኛ ስለቀሚሳችንም መርዘም እንደዚህ ቀሚስ አጠር አድርገን በለበስ ጊዜ አሁን ባትና ተረከዛቸውን ለማሳየት ብለው ነው እያሉ በማጕረምረም ፋንታ። የቀሚሳችን መርዘም የሚያስከፋ ሁኖ ሲታዩ ባሎቻችን እንደሚያምርና ለሰውነት እንደሚመጥን አድርገው ቀሚሱን አስፍተው ይኸን ልበሱ ረጅም ቀሚስ መልበስ ነውር ሆኑአል ብለው ቢያዝዙን በግድ ፈቃዳቸውን ሳንፈጽም ባልቀረን ነበር ። ደግሞ ስለመሸፋፈኛና ቀሚስ ስለማሳጠር ነገር ካሁን ቀድሞ ክብርት ወይዘሮ ሉል አደይ ዛማኔል እንደጻፉት ከላይ ቢጀመርልን እኛም ዕለቱን እንደምንከተል ጥርጥር የለበትም ፤ በዚህ ማኸል አንድ የሚገርመኝን ነገር እጽፋለሁ።አቶ በለቀ ዘለቀ እንደጻፉትና እኛም እንደምንያቸው የአውሮፓ ወይዛዝር ወደ ሽርሽር በሔዱ ጊዜ ደረታቸውን በግልጽ ጥለው የቀረውን ጌጣቸውን አጊ–

ጠው ከባሎቻቸው ሳይሆን እነሱ የሚያውቁት ሰው ከሆን ከማንም ጋራ ቢሆን እጅ ለጅ ተያይዘው የደስታ ጨዋታ እየተጫዋወቱ ይንሸራሸራሉ ባሎቻቸውም እምነትን ሰጥተዋ-ቸዋልና ደስ ይላቸዋል እንጂ ምንም አይከፉቸውም።እንግዲህ የሀገራችን ወንዶች የሥልጣኔን መንገድ የተከተሉ ከሆኑ እንደዚህ ያለውን እምነት ለኛ ለሴቶች አለመስጠታቸው ምን ይሆን ። እንዲያውም ከሚስቶቻቸው ጋራ አብረው እጅ ለጅ ተያይዘው ለመሔድ በጣም ሐፍረት ይመስላቸዋል ። በተረፈ እኛ እንኳን ከሌላ ሰው ጋር እጅ ለጅ ተያይዘን መሔድ ይቅርና እገሌ ትክ ብሎ አየሽ እገሌን ትክ ብለሽ አየሽው ተብለን የሚመጣብን ቊጣ እጅግ ብዙ ነው ። እንግዲህ እኛ ይኸን ፈርተን ሰው እንዳያየን ቀሚሳችንን ብናስረዝምና ብንከናነብ እንደምን በነውር ሊቈጠርብን ይቻላል ።

አራተኛ ስለደጅ ጥናታችን ። ይኸንኑ የሚያገዙን ባሎ-ቻችን ናቸው እንጂ እኛ በመጀመሪ እንዲሁ እንጀምረውም ማለት ባሎቻችን ችግር በገኛቸው ጊዜ እኛ ብቻችንን ስን-ደክም እናንተ ለምን አትረዱንም አሁንም በዚህ ነገር ተቸ-ግረናልና በበኩላችሁ በዚህ እንኳን ብትረዱን እስቲ ወደ-መቤቴ ሒዱና ለዚህ ለተቸገርነበት ነገር እመቤቴ እንዲረዱን ለምኑልን ባሉን ጊዜ እኛም የባሎቻችንን ትእዛዝ ለመፈጸም ባሎቻችን የተቸገሩበት ነገር እስኪፈጸም ድረስ ደጅ ጥናት ስንሔድ መቸም የጕጅ ነገር አይሞላምና አንዱ ደጅ ጥናት ሲያልቅ አንዱ ሲተካ በዚሁ በደጅ ጥናት እንደከማለን እንጂ እኛ እንኳን ታላቅ ሴት ወይዘሮነታችንን ሰው እንዲያውቅልን ለደጅ ጥናት ለመሔድ ብናስብ ባሎቻችን አትሒዱም ብለው ፈቃድ ቢከለክሉን ደጅ ጥናትን ትተን ዝም ብለን የጕጅዋችንን ሥራ በሠራን ነበር። እንግዴህ እኛ ባማናቸውም ነገር ቢሆን በባሎቻችን ትእዛዝ አዳሪ መሆናችንን ከስረዳሁ በኋላ ። አን-ድና ሁለት ብቻ ሳይሆኑ ወንዶች ሁሉ በመላው የሥልጣኔን መንገድ ከተከተሉ የኛ ሥልጣኔ ቅጽበተ ዓይን እንደማይቈይ በዚህ ለመረዳት ይቻላል አሁን የኢትዮጵያ ወይዛዝር ሁላ-ችንም የሥልጣኔን መንገድ ለመከተል ፈቃዳችን ነው ። ማለት ፤ኔ እራሴ በልጅነቴ ምንም ትምህርት አልተማርኩም ነበር። ግን ለዓቅመ ሔዋን ደርሼ ጕጅ ከያዝኩ በኋላ የሥልጣኔን መንገድ በየጋዜጣው ሲነበብ ስለሰማሁ ባለመማሬ በጣም ተጸጽቼ እቤቴ አስተማሪ ተቀጥረውልኝ ስለተማርኩ ይኸው የተጻፈውን አይቼ ለማንበብ በልቤ ያሰብኩትን በጄ ለመጻፍ ቻልኩ ። ለዓቅመ ሔዋን ደርሼ ጕጅ የያዝኩበት ዘመን ፲፬ ሲሆን የተማርኩበት ዘመን ፮ ነው እንደዚሁም ብዙ የኢት-ዮጵያ ወይዛዝር ሁሉ የሥልጣኔን መንገድ ለመከተል ፈቃዳ-ቸው መሆኑ እርግጥ ነውና ። ደግሞ የኢትዮጵያ ወንዶች ሁሉ በሙሉ በጣሙን የሥልጣኔን መንገድ ወደውና ተከትለው እኛን ተገዦዎች የሆንን ሚስቶቻቸውን ወደ ሥልጣኔ መንገድ ለመምራት ያብቃቸው እያልን እንመኛለን።ይኸንኑም የጻፍኩት እኛን ሴቶችን የሥልጣኔን መንገድ ተከተሉ ከማለት በፊት ወንዶች አብልጠው የሥልጣኔን መንገድ እንዲይዙ አጥብቆ መምከር ይገባል በማለት ነው እንጂ እቶ በቀለ ዘለቀ የጻፉ-ትን ቃል ለመንቀፍ አይደለምና ቃሉን አመዛዝናችሁ ከይቅ-ርታችሁ ጋር እንድታነቡልኝ እለምናለሁ ። ምዕራብ ወለጋ

— — ወ አምሳለ ጥበብ ወልደ አብ

ስለ ዘበኞች ትጋት

በዓለም ሁሉ አንዳንድ ጥፋተኛ እንደማይታጣ እርግጠኛ ነገር ነው። ሙሴ ግሮቴርያን የሚባሉ የጀርመን መንግሥት ጥገኛ የሆኑ የንግድ ሥራ ለመሥራት የንግዳቸውን ዕቃ ጭነው በመጋቢት ፲፪ ቀን ወደ አሩሲ ለመሔድ ካዲስ አበባ ተነሥተው ማታውኑ በሴ ላይ ሰፈር አደርገው አድረው ሳሉ ፈይሳ የሚ-ባል ብዙ ዘመን ያገለገለ አሽከራቸው አብሯቸው ሊሔድ ተነሥቶ ነበረና ከመንገዱ ሳይነሡ አስቀድሞ ከሌቦች ጋራ ክፉ-ምክር መክሮ ኑሮ በዚያው በሰፈሩበት ስፍራ ላይ ሌቦች ደርሰው ሳያስቡት በድንገት አደጋ ጥለው ሙሴ ግሮቴርያንን በጠበንጃ አቍስለው የንግድ ዕቃቸውን ሁሉ ዘርፈው ስለው ሰዱባቸው የሙሴ ግሮቴርያንን መቍሰልና መዘረፍ በምሥጢር ሰላዮች በኩል ወደ ከተማ ዘበኛ አለቃ ዘንድ ወዲያው በፍ-ጥነት ተሰምቶ የዘበኛው አለቃ ግራዝማች አማረ በማስጋሌ ዘበኞቻቸውን አስከታትለው ከቈሰሉበት ሰዓት ምንም ያህል ሳይቈዩ ደረሱና ሙሴ ግሮቴርያንን ከቈሰሉበት ስፍራ አንሥተው በአቶሞቢል ወደ አዲስ አበባ አምጥተው ወደ መንግሥት ሆስፒታል ባሳረፏቸው ጊዜ የሙሴ ግሮቴርያን ቤተ ዘመዶች የሆኑት ሰዎች ጕዳታቸውን ሰምተው ወደዚያው ለመሔድ ሲደራጁ ሳለ ሙሴ ግሮቴርያንን ግራዝማች አማረ በአቶሞቢል ይዘው ሲመጡ ባዩ ጊዜ ጭንቅ ከሆነ ሐሳባቸው ታግሠው ይልቁ-ንም የዘበኞችን ፍጥነትና የትጋት ሥራ በማድነቅ የወንድማቸ-ውን ጕዳት እጅግም ያህል አላሰቡትም ነበረ ።

ሙሴ ግሮቴርያን ግን በሆስፒታል ፫ቀን እንደታከሙ-ሞቱ።ግራዝማች አማረም ያንጊዜውኑ ቍስለኛውን ከሆስፒታሉ ከስተኙበኋላ ፈይሳ የሚባለው የሙሴ ግሮቴርያን አሽከር በያለበት እንዲፈልግ የበረታ ትእዛዛቸውን ለዘበኞቻቸው አሳል-ፈው በትጋት ሲፈላለጉ ይኸው ፈይሳ የሚባለው የሙሴግሮ-ቴርያን አሽከር መስቃ ከሚባል ከጕራጌዎች አገር መኖሩን ጥልቅ በሆነ አመራመራቸው ከተረዱ ወዲያ የአገረ ገዢ ሹም ለዘበኞች እርዳታ እንዲያደርግላቸው የበረታ ቃል አሳልፈው የመቶ አለቃውን ባሻ ኤፍሬምን ዋና ኃላፊ አድርገው የከተማ ዘበኞቹን ወደ መስቃ ላኳቸው ያገረ ገዢውም ሹም ቃሉ በደረሰው ጊዜ በዚህ ነገር በጣም አስበ የተፈለገውን ፈይሳንና ይልቁንም ሌሎቹንም በሙሴ ግሮቴርያን ላይ አብረው ጥፋት ያደረጉትን ሁለት ሰዎች ጭምር ሰላገኘ አብሮ ይዞ ለዘበኞች አሳልፎ ሰጣቸው።ከዚያም በኋላ እነዚህ የተያዙት ሌቦች ለያን-ዳንዳቸው ቢመረመሩ አንድነት ተባብረው በሙሴ ግሮቴርያን ላይ ጥፋት ማድረጋቸውንና የተከፋፈሉ መርጋ የሚባል የወለኔ አገር ሰው መሆኑን አስረድተው ስለተናገሩ የከተማ ዘበኞች የመርጋን ፍለጋ በትጋት ሲከታተሉ እስን ፉሪስ የሚ-ባለውን የመርጋን በልንጀራ ተጠያይቀው በድንገት አገቡያ ላይ ያዙት።ይህም እስን ፉሪስ ጓደኛው መርጋ ያለበትን መርቶ

ለዘበኞች አሲይዞ አንድነት ቢጠየቁ ሁለቱም በርግጠኛ ጥፋ-ተኞች መሆናቸውን ስላመኑ ሙሴ ግሮቴርያን በነዚህ ሌቦች እጅ ብቻ መጐዳታቸውን መርምረው የዘበኛው አለቃ ከተረዱ ብኋላ እንደሚያስፈልግ የምርምሩን ቃልና የጥፋታቸውን አኳኋን ጽፈው እንደ ደንቡ ፍርዳቸውን ጥፋተኞቹ እንዲቀበሉ ለማ-ድረግ አዘጋጅተዋል ።

የከተማ ዘበኞች ትጋትና የውቀት ሥራቸውማ የከተማውን ሕዝብ ደስ ከማሰኘት ምን ጊዜም አያቋርጥም ይልቁን የሚ-ያስደንቀው በመስቃ አገር ያለው ያገረ ገዢው ሹም ለሀገሩና ለመንግሥቱ አሳቢ ሁኖ በነዚህ ሌቦች አያያዝ ነገር እርዳታውን እንዳደረገና ከዘበኞቹም ጋራ አብሮ ድካምን እንደተቀበለ መልክተኛ የሆኑት ዘበኞች የገነነ ምሥጋና አቅርበው መስ-ክረውለታል ።

ስለዚህ የዚህን ያገረ ገዥ ሹም እርዳታ ያስተዋሉ (አን-ባቢዎች) ሌሎች አገረ ገዥ የሆኑት ሁሉ ይህን በመሰለ ብማንኛውም በሚያስቸግል ነገር የመንግሥትና የሕዝብ ጉዳት መሆኑን እያሰቡ እርዳታቸውን ለማድረግ ወደፊት በተስፋ ሳ-ይዘጋጁ ይቀሩ አይመስለኝም ። ደጉ ይመር

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ክጐሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሣባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበ-ላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ፤

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኰላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጐርጎርዮን ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይ- ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX,) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል።

ፔር ዳኒይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርናዲ-ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
6ᵐᵉ ANNÉE № 21

ሐሙስ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 22 MAI 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lùmière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ደረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፱ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የዘማቾች በደኅና አዲስ አበባ መግባት ።

በግንቦት ፲፪ ቀን በትልቁ ግቢ እሰገነቱ ሥር ሁለት ድንኳን ተተክሎ ነበርና

ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የጦር ምንስቴሩ
ደጃዝማች ብሩ የሲዳሞ ገዥ
ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ የከምባታ ገዥ
ደጃዝማች መኰንን ገርማሜ የጎሞ ክፍል ገዥ
ደጃዝማች ደበበ የጎሞ ክፍል ገዥ
አዛዥ በየነ ዋናው አዛዥ
ከንቲባ ማተቤ
አዛዥ ወሰኔ

ግራዝማች ኃይሌ እንደብልሀቱ አጋፋሪው ። የቀሩትም ብዙ መኳንንት በማለዳ ገብተው ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እጅግ አለቀሱ ። ጃንሆይም በክብር ተቀብለው ወደልፍኝ ይዘዋቸው ገቡ ። ሰው ሁሉ በብርቱ ናፍቆት ተገናኛቸው ።

በግንቦት ፲፫ ቀንም ሰው ሁሉ ወደ ጃንሜዳ ይጓዝ ነበር። ፫ ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ በዙፋንዎ ላይ ተቀመጡ። መኳንንቱና የውጭ አገር ሰዎችም በየማዕረጋቸው ተቀመጡ። ወዲያው ደጃዝማች በየነ በፊታውራሪ መልሴ እጅ ተግዘው ከነበሩበት ተምረው መጡ ። ደንጊያ ተሸክመው ። በቆሙም ጊዜ መሓሪው ጌታቸው ጃንሆይ ማሯቸውና እጅ ነሥተው ተቀመጡ ። ፬ሰዓት ተኩልም ሲሆን ዘማቾች ተሰልፈው ቀረቡ ። በፊት ልጅ በቀለ ወርዶፉን በፈረስ፥ቀጥለው አጋፋሪ መሸሻን በበቅሎ ላኳቸውና መጀመሪ የጎሞ ገዥ የደጃዝማች መኰንን ሠራዊት አምሮ ተሰልፎ መድፍና መትረየሱን እመሀል አድርገው የቤት አሽከሮች በኋላ ተሰልፈው እየፎከሩ እጅ ነሥተው አለፉ ። ደግሞ የደጃዝማች መኰንን ጭፍሮች ፊታውራሪ ተሰማ ጋረደው ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል ዶሪ፥ የቀሩትም የሻለቆችና ጀግኖች ወታደሮች አስደንቀው ፎከሩ። ይልቁንም ከፎከራ በኋላ ፊታውራሪ ወልደሚካኤል አካላቴ ብቻ አይደለም ወፍራም ልቤም ወፍራም ነውና ዳግመኛም ጠላት ቢነሣብዎ ይላኩኝ ባሉ ጊዜ ሰው ሁሉ እጅግ ደስ ብሎት ሳቀ ። እሳቸውም እጃቸውን ባረር ተመትተው ቈስለዋል ። ከዚህ በኋላ ሙሴ ማዬ በአይሮፕላን ሁነው በአየር ላይ የአይሮፕላኑ ድምጥ ሲአጕረመርም የሚፎክር መስሎ ይሰማ ነበር ።

የጎሞ የጦር አለቆች ፊታውራሪዎችና የቀሩት ጀግኖች ሁሉ ወደ ዙፋኑ ቀርበው ሲፎክሩ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር።

ቀጥለው አዛዥ ወሰኔ የወለኔን ጦር አስከትተው ተሰልፈው እየፎከሩ ገቡ። ከፍከራቸውም በኋላ ደግሞ ጠላት ቢነሣብዎ ይላኩኝ ለኔ ግን ብድር መመለስ አለብዎ ባሉ ጊዜ አዛዥ ወሰኔ ሁሉን አስደንቀው እጅ ነሥተው አለፉ ።ቀጥለው በደጃዝማች ሙሉጌታ ውሥጥ ጉመር ያለው ጦር በቀኛዝማች መንገሻ አየለ እግር ተሰልፎ በሚአስደንቅ ፍከራ እጅ ነሥቶ አለፈ።ፊታውራሪ ተፈረደኝ የሚባሉ ሽማግሌ ፊት በፈረስ ኋላ በእግራቸው ሲፎክሩ እጅጓ ያስደንቁ ነበር ። የማረኳቸውን ፲ ጠበንጃና ፪ ጐራዴዎች በጃቸው ይዘው ነበር እሚፎክሩም ላያቸው ። ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ ።

አርበኞች ሲፎክሩ እግረ ቀጭን እንደ ሰሳ ልበ ደፋር እንደ ኣንበሳ ይሉ ነበር እውነት ነው አቀበት ቍልቍለት ሲወጣና ሲወርድ እማይደክመው ለሞቱ እማይፈራ እንደ ኢትዮጵያ ያለ አርበኛ የት ይገኛል?።

ሶዶ በደጃዝማች ሙሉ ጌታ ውሥጥ በሻህ ታምሬ ፥ ደስታ ወልደኪሮስ የሚባሉ ጀግኖች ሲፎክሩ እጅግ ደስ አሰኝተው እጅ ነስተው አለፉ።ቀጥሎ ከምባታ የደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ጦር

እምሮ ተሰልፎ መጣ።በመጀመሪያ ሁለት ወንድማማቾች የፊታውራሪ ቢሻው ልጆች ገና ወጣቶች ነበሩና የአንበሳ ለምዳቸውን ለብሰው ሲፈክሩ እጅግ ያስደንቁ ነበር።ቀጥሎ ነጋሪቱ ገብር ገብር እያለ መድፍና መትረየሱ ተጭኖ መለከቱ እምቢልታው ጥሩምባው እየተነፋ ካለፈ በኋላ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ በበቅሎ ተቀምጠው ነጭ ጥላቸውን አስይዘው እየፈከሩ ወደ ዙፋኑ ቀረቡና ተበቅሎ ወርደው አሁንም አለሁ ብለው እጅ ነስተው አለፉ። ቀጥለው በውስጣቸው ያሉት መኳንንት የሰልፍ አለብበሳቸውን አሳምረው ሲፋከሩ እጅግ ደስ አሰኙ ። ከኒህም አንዱ ፊታውራሪ ወልደ ጻድቅ የሚባሉ ሽማግሌ የምርኮ መሣሪያቸውን ይዘው ሲፈክሩ እጅግ ያስደንቁ ነበር ። ከዚህ በኋላ ደጃዝማች ብሩ የሲዳሞን ጦር በሥራት አሰልፈው ከፍ ብለ በቅሎ ተቀምጠው መጡ። በፊታቸው ደስ የሚአሰኝ ጥሩምባ እየተነፋ መድፍና መትረየሱ ተጭኖ ነጋሪቱ ገብር ገብር እያለ ደስ አሰኝተው አለፉ ። ቀጥሎ የፈረስ ዘበኞች ተአለቃቸው ተቀኛዝማች ንዋይ ጋራ ተሰልፈው እየፈከሩ ደስ አሰኝተው አለፉ ። ቀጥሎ የቤት ወደድ ጌታቸው አባተ ሰዎች አምረው ተሰልፈው እየፈከሩ ደስ አሰኝተው አለፉ። ቀጥለው የጦር ሚኒስቴሩ ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የተማረኩትን መኳንንት ደጃዝማች አስፋው ወሴን፣ ደጃዝማች ኃይሉ ማርያም ወሴን፣ ፊታውራሪ ሽምዬ ጃሎን ሌሎችንም መኳንንት በሰንሰለት እጅ እጃቸውን አቄራኝተው በፊታቸው አድርገው ከራስ ጉግሣ ወሌ የተማረከውን ራስ ወርቅና መሰሿ ነጋሪቱን ጨምረው ከላይኛው ግቢ በዘመቱት በሰልፍ አዋቂዎች ዘበኞች ታጅበው ባለፉ ጊዜ ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ።

ቀጥለው ግራዝማች ያረጋል የጃንሆይ አጋፋሪ በጦሩ ጊዜ ተልከው በአይሮፕላን ሒደው ለጦር ተሰላልፈው ሲሄዱ ጊዜ እዚሁ እሞታለሁ እንጂ ወደከተማ አልመለስም ብነው በጦርነቱ ውስጥ በጀግንነት ውለው ነበርና የማረኩትን ፲፩ ጠመንጃ በአጋሠሥ ጭነው ሲፎክሩ፡ መቅደላ ገዳይ ከዳገቱ ፤ በጌምድር ገዳይ ከወንድሞቹ ፤ ባሉ ጊዜ ሰው ሁሉ ተደነቀ። ቀጥለውም ባራዝማች ኃይሌ አደብልሀቱ የደጅ አጋፋሪው ከነጭፍራቸው አምረው ተሰልፈው እየፈከሩ አለፉ። እሳቸውም የሚያስደንቅ ንግግር ተናግረው እጅ ነስተው አለፉ። ቀጥለው የመድፈኞች አለቃ ግራዝማች ማህሌ እጅግ የጅግንነት ሥራ ሠርተው ነበረና ከነሠራዊታቸው ተሰልፈው እየፈከሩ አለፉ። እሳቸውም ወደ ዙፋኑ ቀርበው ፈክሩ የሚያስደንቅ ንግግርም ተናግረው እጅ ነስተው አለፉ ።

ቀጥለው ባለሚሎኙ የሚባሉት የቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ ጭፍሮች ተሰልፈው ፈክረው እጅ ነስተው አለፉ ። ቀጥለው ብልደራሶች የቀዝማች ገብሬ ጊዮርጊስ ጭፍሮች ተሰልፈው ፈክረው እጅ ነስተው አለፉ ።

ቀጥለው የአዛጋር በየን ሠራዊቱ ጭፍሮችና አሽከሮች ባማረ ሰልፍ ፈክረው አለፉ።አዛጋርም በበቅሎ ሁነው ፈክረው ደስ አሰኝተው አለፉ።ቀጥለው ጓዶችና ዕቃቤቶች ተሰልፈው ፈክረው አለፉ። ቀጥለው የጸሐፊዎች አለቃ ግራዝማች ተክሌ ከነጭፍሮቻቸው ባማረ ሰልፍ ተሰልፈው ፈክረው አለፉ።ጅግናው ሁሉ ተምበርክ ሲፈክር እንደ አንበሳ ያስፈራ ነበር ። ደልቁንም እጅግ የሸመገሉት ከ፹ዓመት በላይ እሚመሉትና የ፲፪ና የ፲፭ዓመት ልጆች የሚመስሉት የማረኩትን መሠሪ ይዘው ሲፈክሩ ላያቸው እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። ሽላይም እንዲህ አለ፣ መድፉን መትረየሱን ምነው መሚናቸን ። ሴላ ሰው አልመጣ በገዛ አሽከራችን ። ደሳሞ ጃሎ መገን አለና ፤ እንኳን ሳይበደል ምንስ ሆድ ቢብሰው ። ወንድማማች ሁኖ እንዴት ይከዳል ሰው ። አለና ሰውን ሁሉ አስደነቀው ።

ፉከራ ማለት በግዕዝ ቋንቋ ተረጉመ ማለት ነው።አርበኛም ያገዳደሉንና የሙያውን ነገር ተርጉሞ አስታጠቀ ማለት ነው።

ከዚህ በኋላ የሰልፉና የፉከራው ነገር አለቀና ደጃዝማች ሙሉ ጌታ የጦር ምንስቴሩ ፩ኛ ልሻንና የወርቅ ሰገባና የወርቅ ውላጋ ባለፈርጥ ሰይፍ ከጃንሆይ ተሸለሙና ፫ ጊዜ ተጨበጨበ። ቀጥለው ደጃዝማች ብሩ የሲዳሞ ገዥ የሚነገት ፪ኛ ልሻን ተሸለሙና ተጨበጨበ።ቀጥለው ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ፫ኛ ያንገት ልሻን ተሸለሙና ተጨበጨበ ። ደጃዝማች መኰንን ገርማሜ ታመው በቤተ ሣይዳ ሆፒታል ተኝተው ወደ ሰልፍ ስላልመጡ ደስ እሚአሰኝ ልሻን ሆስፒታል ድረስ ላኩላቸውና ጃንሆይም ወደ ሆስፒታሉ ሒደው ጠየቋቸው ። በጦርነቱ መሀል ደጃዝማች መኰንን ገርማሜ የተደነቀ ሥራ ሠርተዋል።

ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ምንስቴር የጦር ምንስቴሩ ዳጃዝማች ሙሉጌታ ያቀረቡትን ዲስኩር አነበቡ፣ ቃሉም ቀጥሎ የሚመጣው ነው ።

ጃንሆይ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ደገኛይቱ እናትዎ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ከዚህ ዓለም በሞት ማለፋቸው ምንም ኀዘኑ የመላችን ቢሆን በተለየ ለጃንሆይ መሪር ኀዘን ነውና በራሴና ከእኔ ጋራ ባሉት መኳንንቶች በሠራዊቱም ስም ሆኜ እግዚአብሔር ያጥናዎ እያልሁ የኀዘንዎ ተካፋዮች መሆናችንን ከገለጽሁ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ቃል ለመናገር የግርማዊነትዎን ፈቃድ እለምናለሁ ።

ጃንሆይ ።

ከጥቂት ወራት አስቀድሞ ራስ ጉግሣ ወሌ ከፈቃድዎ መውጣታቸው ምንም እንኳ ጥቂት ጥቂት ቢወራ ግርማዊነትዎ እርግጥ ነው ብለው ለጊዜው አልተቀበሉትም ነበርና ከአዲስ አበባ ስነሣ የታዘዝሁት እርስ በርሱ የሚዋጋውን የራያንና የአዘቦን ጋላ ለመቅጣት ነበር ። ጅሩን ካለፍሁ በኋላ ግን ራስ ጉግሣ ወሌ ከፈቃድ መውጣታቸውንና ሹፈታቸው ወሬው እየሰፋ ስለሔደ ግርማዊነትዎ ሠራዊቱን እያስከታተለ ይልክልልኝ ጀመር ።

ቢሆንም እኔ እንደተረዳሁት ጃንሆይ አሳብዎና ጭንቀትዎ ክርስቲያን የሆነ የወንድማማች ደም በከንቱ እንዳይፈስ ነበርና የበጌምድርን ድንበር እንዳላልፍ ትእዛዝዎ ስለመጣልኝ በዳሩ ሰፍሬ ተቀመጥሁ ።

ራስ ጉግሣ ወሌ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም አጥፍተው የማይገባቸውን ክብር ለራሳቸው ለማግኘት የሐሰት ወሬ እያስወሩ የዋሁንና ደጉን ሕዝብ ማታለላቸውን ሰምቼ ለጃንሆይ በመለክት ደግነትዎ የበዛ ነውና እርሳቸው መጥተው ይውጓችሁ እንጂ እናንተ የበጌምድርን ድንበር አትለፉ የሚል ትእዛዝዎ ቢመጣብኝ በታዘዝሁበት ፀንቼ ተቀመጥሁ ።

ራስ ጉግሣ ወሌ ግን በኢትዮጵያና በግርማዊነትዎ ላይ ያሰቡት ክፉ አሳብ የሚፈጸምላቸው ስለ መሰላቸው ከደብረ ታቦር ገስግሰው ወደ እኛ ቢመጡ ጃንሆይ የዕርቅ ነገር ጀምረናል ብለው ልከውብኛልና የዚህ ነገር ሳይጨረስ ወደኛ አይምጡ ።

በዚያውም ላይ እናትዎ እቴጌ ጣይቱ ፡ አባትዎ ራስ ወሌ የደከሙበትንና የሞቱበትን አልጋ ለማፍረስ ቢነሡና የወንድማማች ደም ቢፋሰስ ለስምዎ ጉዳት ለርስዎም ጥፋት ነውና ስለ ሕያው እግዚአብሔር ብለው ይመለሱ ። ወይም ባሉበት ሰፍረው ይቆዩ ብዬ የትሕትና ቃል ብልክባቸው እምቢ ብለው ወደ ሰፈራችን መጡ ።

ከዚህም በኋላ እኛ የታመንን ባሮችዎ በቋና አውራጃ አንችም በሚባል በጠራ ሜዳ ላይ ጦርነት ተጋጥመን በእግዚአብሔር ኃይል ፡ በግርማዊ ንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግንባር ለሞታቸው በማይፈሩ አርበኞችዎ ብርታት ድል አደረግናቸው ።

ወደያውም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሁኖ ግርማዊነትዎ ክፍ ባለው በንጉሠ ነገሥት ዙፋን መቀመጥዎንና ኃይልና ጸጋ መልበስዎን ስለ ሰማን ደስታችን ከልክ ያለፈ ሆነልን ።

አሁንም በግርማዊነትዎ ትእዛዝና ፈቃድ ከተለቀቁት ምርኮኞችና ላገር መጠበቂያ ወደ በጌምድር ከተመለሱት መድፎችና መትረየሶች በቀር ያመጣናቸውን ምርኮኞችና የጦር መሣሪያዎች በግርማዊነትዎ ፊት ያቀረብንበት የዛሬው ቀን የዘላለም መታሰቢያ ሁኖልን እንዲኖር አንጠራጠርም ።

ከአዲስ አበባም ከተነሣንበት ቀን ጀምሮ ተመልሰን እስከ መጣንበት ቀን ድረስ ችግራችንን ለማቅለል ባስልክም በደብዳቤም የግርማዊነትዎን ትእዛዝ ዘወትር ማግኘታችን ለሠራዊትዎ ከልብ ማሰብዎን ያስረዳናልና ለደስታችንና ለምስጋናችን ወሰን የለውም ።

ደግሞ በአንድ ወር የሔድነውን መንገድ በሦስት በሦስት ሰዓት በአይሮፕላን እየተመላለሱ ትእዛዝዎን ያስታወቁንን ። በጦርነቱም ከኛ ሳይለዩ ሲረዱን የዋሉትን ሙሴ ማዬንና ሙሴ ክርዝርን ለነሱም መሪ የሆነውን አገልጋይ አሸከርዎን ግራዝማች ያረጋልን በግርማዊነትዎ ፊት ልናመሰግናቸው ይገባናል።

ደግሞ የፈረንሣዊ መንግሥት ከቀድሞ ጀምሮ ምንም የኢትዮጵያ መንግሥት ወዳጅ ቢሆን ዛሬ ደግሞ በተለየ ከሀገሩ የመጡ አይሮፕላኖች ባደረጉልን ትልቅ እርዳታ ምስጋና የሚገባው መሆኑን ለግርማዊነትዎ ለማሳሰብ ብናገር ድፍረት አይሆንብኝም

ጃንሆይ ።

በታላቅ እምነት የጦር ሚኒስቴር አድርገው ከሾሙኝ በኋላ በግርማዊነትዎና በመንግሥትዎ ላይ የተነሣውን ዓመፀኛ ለመቅጣት ከታመኑት መኳንንቶችዎና አርበኞችዎ ጋራ ሒጄ ድል ማድረጋችንን የምስራች በደብዳቤ እንዳስታታወቅሁዎ አሁን ደግሞ በግርማዊነትዎ ፊት ቁመን በቃላችን ለመናገር በመቻላችን ለደስታችን መጠን የለውም ።

ለመቸውም ቢሆን በግርማዊነትዎና በመንግሥትዎ ላይ የሚነሣውን ዓመፀኛ ሞታችንን ሳንፈራ ለመቅጣትና ትእዛዝዎን ለመፈጸም ቃል ኪዳን መግባታችንን እንገልጽልዎታለን። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ዕድሜ ለአርበኞችዎና ለሕዝብዎም ሰላምና ዕረፍት እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን እንለምናለን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።

ቀጥለውም የጃንሆይን ዲስኩር አነበቡና ፫ ጊዜ ተጨበጨበ

ባንድ በራስ ጉግሣ ወሌ ምክንያት የወንድማማች ደም መፍሰሱ ምንም እንኳ ጉዳቱ የራሳችን ቢሆን፥ የኛን የዘውድ ክብር ለመጠበቅና የኢትዮጵያን መንግሥት ለማፅናት ባንድ ልብ፥ ባንድ ኃይል ሁናችሁ በመዋጋታችሁና ትእዛዛችንን በጥንቃቄ በመፈጸማችሁ ደስታችን ትልቅ መሆኑን እንገልጽላችኋለን።

ደግሞ የራስ ጉግሣ ተከታዮች ደማቸውን በከንቱ እስኪማሰስ የደረሱበት ዕውቀት ስላሌላቸው ጉዳቱ የመላው የኢትጵያ ሕዝብ መሆኑን ባያውቁት እንደሆን አይጠረጠርም ። እናንተ ግን ጉዳት መሆኑን ስለተረዳችሁት በችሎላ የክርስቲያንና የወድማማችን ደም ለማፍሰስ ሳትቸኰሉ ኃይል ሳላችሁ እንደሌላችሁ ሁናችሁ ትእዛዛችንን በመፈጸም ወደ ሰፈራችሁ እስኪመጡ ታግሣችሁ በመቆየታችሁና ከመጡባችሁም በኋላ በርትታችሁ በመዋጋታችሁ ድል በማድረጋችሁም ትልቅ ምስጋና ይገባችኋል ።

አንተም ደጃዝማች ሙሉ ጌታ ከቀደሞ ጀምሮ በልዩ ልዩ የመንግሥት ሥራ ላይ ምንም ታምነህ የቈየህ ብትሆን አሁን የጦር ሚኒስቲር አድርገን ከሾምንህ ወዲህ በመጀመሪያ መታዘዝህ እግዚአብሔር ይህን ድል ስለሰጠህ ዕድለኛነትህን ይገልጽልናል ።

አሁንም ከራስ ጉግሣ ወሌ ጋራ በተደረገው ጦርነት ውሥጥ ከነተ ጋራ ታዘው ከዘመቱት ሰዎች መካከል ለሞቱት ለልጆቻቸው ማሳደጌያ ። ለቈሰሉትም መታመታሚያና መጧሪያ እንሰጣቸዋለንና፥ በየስማቸውና በየባልደረባቸው ጽፈህ እንድታቀርብ ይሁን ።

ለንጉሡና ለመንግሥቱ ፀእምነትና በቅንነት የሚያገለግል ሰው ዋጋውን የማያጣ መሆኑን እያወቃችሁ በሥራችሁ ሁሉ እንድትበረቱ ይሁን ። ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ቀጥለውም ደጃዝማች ሙሉ ጌታ አበረኞችን አቅርበው በየስማቸው አስታውቀው ስለ ዘማቾች ደስታ ፲ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ስምን መላክ ያወጣዋል የሚባል ተረት እውነት ነው በውነት ሙሉጌታ ሆኑ በዘመናችን እንዲህ ያለ ዕድል ያገኘ የለም ።

ስለ አፈርሳታ መልስ ።

በ፲፫ ቁጥር ብርሃንና ሰላም በሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት አቶ ፍስሓ ወልደ ሚካኤል ስለጻፉት ስለአፈርሳታ ነገር።

በዚሁ ጋዜጣ ውሥጥ የአፈርሳታ ሥራ ከሌባሻይ ጥፋት ይልቅ ዓሥር እጅ የሚከፋ ሁኖ ስለተገኘ የተባለውና ሌባሻይ የሚያጠፋው ፩ ሰው ብቻ ነው የተባለው ስሕተት ይመስለኛል።

ሌባሻይ የሚጐዳው ብዙ ሰው ነው ። መጨረሻውም ፍሬ የሌለው ነገር ነበር ። መንግሥትም ይህንኑ አውቆ ሌባሻይን አስቀርቶልናልና የሌባሻይን ነገር ዝርዝሩን መጻፍ አንባቢ- ዎችን ማሰልቸት ይሆናል ።

የአፈርሳታ ጉዳቱ በጣም ትንሽ ነው: ጥቅሙ ግን ብዙ ነው ። እስከሁንም እንደታየው አገር የሚያውክ ወንጀለኛ ሁሉ ብአፈርሳታ ይገለጣል:የአገርም ዋና ጥቅሙ አገር የሚያውከው ወንጀለኛ ተይዞ መቀጣቱ ነው ።

እንደሮፓ አገር ወንጀለኞችን የሚፈልጉና የሚመረምሩ ዘበኞችና ሹማምቶች ለማድረግ በልዩ ልዩ ምክንያት አሁን ለጊዜው የማይቻል ይመስለኛልና አፈርሳታ የማይቀር ደንብ ው ።

በአፈርሳታ ምክንያት ሕዝቡ የሚጐዳበት ፫ ነገር ነው ።

፩፡ አፈርሳታ የሚቀመጥበትን ቀን መወሰን ያስፈልጋል።

፪፡ ሕዝቡ ለአፈርሳታ እንዲሰበሰብ የሚታዘዝበት ጊዜ ብዙ ሥራ የማይሠራበት ወራት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

፫፡ ስለአፈርሳታ ነገር ለመቀጫና ለእሥራት የተወሰነ ነገር ማድረግ ያስፈልጋል ።

ይህንኑም ቀጥሎ እንደተጻፈው አድርጎ ማሻሻል መልካም ይመስለኛል ።

ማመልከቻ ።

በአፈርሳታ ስለመሰብሰቢያ ጊዜ ።

፬፣ ለአፈርሳታ መሰብሰብ የሚያስፈልግ በሆነ ጊዜ አፈር- ሳታ ይውጣ ብሎ የሚያዝ አገረ ገዢው እንዲሆን።

፭፣ የሕዝቡ መሰብሰብና የምርምሩ ነገር ከ፫ ቀን እንዳያልፍ።

፮፡ በእንደዚህ ያለ ስፍራ አፈርሳታ ተሰብስቡ ተብሎ እንደ ሚገባ ከተለፈፈ በኋላ በሕመም ምክንያት ካልሆነ በቀር ወደአፈርሳታው ያልወጣውን ሰው በግድ አምጥቶ ከአ ፈርሳታው እንዲገኝ ማድረጓና ከአፈርሳታው በኋላ፫ ቀን ብቻ ስለቅጣቱ እንዲታሠር ።

፯ ፤ ለትንንሽ ለስርቆት ነገር ፯ ከልሞላ በቀር አፈርሳታ እንዳይደረግ።

፰ ፤ ትንንሽ የማያስቸኩል ነገር የሆነ እንደሆነ አፈርሳታ የሚወጣበት ጊዜ የሥራ ወራት እንዳይሆን ።

፱፤ የነፍስ ግዳይ የቀማኛ ነገር የሆነ እንደሆነ ግን በሥራ ወራትም ቢሆን አፈርሳታ እንዲወጣ ማድረግ።

በአፈርሳታ የተሰበሰበው ሕዝብ ወንጀለኛውን አለሐሳብ አለፍርሀት በቶሎ እንዲያወጣ

፲፡ በአፈርሳታ የወጣው ወንጀለኛ ነገሩ ተመርምሮ ካገር የመ ሰደድ ፍርድ እንደፈረድበት ያስፈልጋል።ይህ ካልሆነ ግን በአፈርሳታ የወጣው ወንጀለኛ የተፈረደበትን ቅጣት ከፈጸመ በኋላ ተለቆ ወደ አገሩ በገባ ጊዜ በመሰከረበት ሰው ላይ ቂሙን ይወጣል። ሕዝቡም አፈርሳታ ብናወጣ ወንጀለኛውን ዳኞች መልሰው እየለቀቁት ወፍ ሁኖ በወጣውሰው ላይ ብዙ ችግር ያመጣበታል ። ስለዚህ ወንጀለኛውን ከማውጣት መቀጮ መክፈል ይሻለናል እያሉ ሲመረሩ ብዙ ጊዜ እንሰማለን ።

ጥንት በመስከብ አገር እንደሮፓ ቍጥር እስከ ሺ ፲፱፻፲፯ ዓመት ድረስ ፩ ሰው አገር ያስቸገረ እንደሆነ ያገሩ ሰዎች የሚበልጡት ካገራችን ይውጣልን ብለው ፈርመው ለሹሞች ያመለክታሉ ። ሹሞቹም ነገሩን መር- ምረው ካገር ያስወጡታል ።

፲፩ ፡ በገራችንም ፩ ሰው ብርቱ የወንጀል ሥራ ሠርቶ በአፈ- ርሳታ በወጣ ጊዜ የአፈርሳታው ዳኛ ከገራቸው እንዲ- ወጣላቸው ይወደ እንደሆነ ያገሩን ሽማግሎች ጠይቆ እነሱም ወፍ ሁነው ያወጡትንም አገርም ያውከልና ካገር ይውጣልን ያሉ እንደሆነ ካገር ወጥቶ ላገር ግዛት ሚኒስቴር ተሰጥቶ እሱ ባዘዘለት በሌላ በሩቅ አገር እንዲኖር ማድረግ ።

፲፪ ፡ ወንጀለኛው በስደት ከሚኖርበት አገር ባገር ግዛት ሚኒ- ስቴር ትእዛዝ ላገረ ገዢው ተሰጥቶ አገረ ገዢው ቦታ ወስኖለት ከአንዱ አገር ወዳንዱ አገር መሔድ የማያ ስፈልግ ሥራ እየሠራ እንዲኖር ማድረግ ።

፲፫ ፡ ወንጀለኛው በስደት ከሚኖርበት አገር የጠፋ እንደሆነ አገረ ገዢው ላገር ግዛት ሚኒስቴር አስታውቆ ባገር ግዛት ሚኒስቴር ትእዛዝ ተፈልጎ በተያዘ ጊዜ እንደገና ስደቱን ቅጣቱን ማበርታት ።

፲፬ ፡ ወንጀለኛው በስደት ከሚኖርበት አገር ፫ ዓመት አመ- ሉን አሳምሮ በሥራው ተጓቶ ከተቀመጠ በኋላ ከገሬ ልመለስ ብሎ የለመነ እንደሆነ የሚገባ ጥያቄ መሆኑ ተመርምሮ የተፈቀደለት እንደሆነ መጀመሪያ ከነበረበት አገር እንዲገባ ማድረግ ።

፲፭ ፡ በስደት የሚኖረው ወንጀለኛ ወደአገሩ እንዲመለስ የጠ- የቀው ጥያቄ የማይፈቀድለት የሆነ እንደሆነ አሁን በሚ- ኖርበት ግዛት ውሥጥ እንደወደደ እንዲኖር መፍቀድ ።

ስለአፈርሳታ መቀጫ ።

፲፮ ፡ በአፈርሳታ የተሰበሰበው ሕዝብ ወንጀለኛው እንዳይወጣ የሸሸገ እንደሆነ መቀጫ ሊጣልበት ይቻላል ።

፲፯ ፡ በሕዝቡ ላይ የሚጣለውን መቀጫ ነገር አገረ ገዢው ሐሳቡን ጽፎ ማመልከቻውን ለመንግሥት ይስጥና የሚ- ያስቀጣና የማያስቀጣ መሆኑን የመቀጫውንም ልክ የሚቈርጥ መንግሥት እንዲሆን ።

፲፰ ፡ የአፈርሳታ አስወጭ ሠራተኞች ራት እየተባለ በሌላም በአፈርሳታ ምክንያት ከሕዝብ ላይ ገንዘብ እንዳይቀበሉ ትእዛዝ ማድረግ ።

እንደዚህ የተደረገ እንደሆነ የአፈርሳታ ጉዳቱ ቀርቶ ጥቅሙ ብቻ ይቀር ይመስለኛል ።

የመንግሥት መሠረት ዳኝነት ነው ። የንጋዴም የገበሬም፥ የትልቅም፥ የትንሽም ጠባቂውና ቤት ንብረቱ ንጉሥና ዳኝነት ነው ። ዳኝነትም የሚተከከለው የተጻፈ ደምብ ሲኖር ነው ።

ደምብ ሁሉ በ፭ ክፍል ይከፈላል ። ፩ደኛ፥ስለርስትና ስለገንዘብ ነገር ደምብ፥ እሱም በፈረንሣዊ ክድ ሲቢል ይባላል፡፪ተኛ፥ስለርስትና ስለገንዘብ ነገር የዳኞች አሠራር ደምብ (ሥርዓት) ። በፈረንሣዊ ክድ ደፕሮሴዱር ሲቢል ይባላል። ፫ተኛ፥ ስለንግድ ነገር ደምብ ። በፈረንሣዊ ክድ ደኰሜርስ ይባላል። ፬ተኛ፥ ስለወንጀል ነገር ደምብ በፈረንሣዊ ክድ ፔናል ይባላል ። ፭ተኛ፥ ስለወንጀል ነገር የዳኞች አሠራር ደምብ በፈረንሣዊ ክድ ደአንስትሩክሲዮን ክሪሚኔል ይባላል ። የአፈርሳታም ነገር በዚህ በ፭ተኛው ክፍል ደምብ ውሥጥ የሚገባ ነው ።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዘመን ይህ ፭ቱ ክፍል ደምብ ወጥቶ ዳኝነት እንዲተከክል ተስፋ አለን ። ቅጣው ይታጠቁ ።

የመንቀሳቀስ መጀመሪያ።

ሰው ከትቢያ ተፈጥሮ በረቂቅ ባሕርዩ በኩል በዘመን ብዛት አስሔደን እያሰመረ የአእምሮውን ሀሰል እየወለወለ የምድር ጌታዋ ለመሆን ደረሰ። በአዳኋንና አንቀጹም ከአራዊትና ከእንስሶች የተለየ ባህል አመረጠ በዓለም ላይ እንደ ፀሐይ ለዛ ያለው ብርሃን አበራ። ከአዳም ተወልደናል ብለው የሚያምኑ ሕዝብ ብልጫቸው ጥቂት በጥቂት በትጋትና በመሥራት ከወንድሞቻቸው እየላቀ የማዕረግ መብራቱን ታደለ። ማናቸውም ነገድ ሥጋዊ መንገዱን በንድ ጊዜ ፍጹም ጕዳና አላሲያዘትም። ተስፋ ሳይቈርጥ ምቀኝነትና፥ ተንኰልን ትዕቢትን ሽሮ በመተባበር ከ፱ ስዩ ትኍሳትና ከመከራ አሳት ጋራ በመታገሉ የኑሮውን የመሻት አገባብ መደንገግ ጀመረ። ወዲያውም በንድ አንድ የዓለም ክፍል ማኅበር ሁና ነዋሪ ሕዝብ የሀገሩን ክብር የራሱ መሆኑን እየተረዳ በልዩ ልዩ ስልት አከባከባት። ደምብና ልማዱንም ጊዜ ስለሚለዋውጥበት በየብልልቶቻቸው ያቆማቸውን የተሳሰሩ ጥቅሞች እያሻሻለ ወደ ኋላው ሳይመለስ ወደፊቱ ገፋ። ጥንከሬም መልካሟ ረድኤት በሕይወት ታሥራ ትኖራለችና ለተከተላት ሕዝብ ኃይሏን እንደመጠኑ አልነሳችውም። ስለዚህ ሰው ለሆነ ሁሉ ያረጀውን ወግ የድንቍርና ጠባይ እንደተጻየፈ አስተውሎ ለሥቃይና ለዘን ባርያ እንዳይሆን ከሰውነቱ ከንቱ ሥራን ያስወጣና የልቡን ደንዳንነት፥ ያንገቱን ጠማምነት አቅንቶ የስንፍናን ሥር ነቅሎ የወረወራት ወገንም በማይመረመር የታላቅ ሥራ ተአምራት እስከ ፍጻሜው የማለዳ ኮከብ መስሎ ይታያል።ልቡ ጠቢብ የሆነ ሕዝብ ኃይልና ግርማው ታላላቆች ተራሮች ናቸው ። የትኛውም ጥቅም ከመሬት ማኅፀን ከሰው ዘር እንሥቶ መገናኙ ተረገጠ። ምድርም በጀርባዋ ቢንሳፈፉባት የሆዱዋን ውሥጥ አታሳይም።ለዚህ የደበቀችውን ለመመልከት አለአንድ ዘዴ አይሳካምና ብልሆቹ የአዳም ልጆች በማረሻ ምድርን ይሰቀስቃሉ። ፍሬዋንም በግድ እየነጠቁ ይመገባሉ ። ከመካከላቸው በነገሥታት ሁሉ የአገር መክበሪአወች እንደ ጨረቃና ከከብ ማዕረግ የተለያዩ ይገኛሉ። እነሱም ገበሬና ነጋዴ ከነዚያውም ዋናው የመንግሥት ጕልበት ገበሬ ነውና የገበሬ መከራው ሲከማችበት ለሀገሩ ውርደትና ድኅነት ነው። አሁን የሰሌት ሥራ ያለበት ሰው ሲያስብ ሕዝቡ ዙሪያውን ከበውት ሲንጫጩበት የሥራውን ሒሳብ ፭ና፭ን ለማጋጠም ይቸግረዋል ጊዜው በመበሳጨት ያልፍበታልና ጕዳቱ ለባለሒሳቡ ነው እንጂ ሰወችስ የየራሳቸውን ሐሳብ እንደየፈቃዳቸው ይፈጽማሉ። የገበሬም በያለበት መባከን ለመንግሥቱና ለሀገሩ ነው ጕዳቱ። እሱስ የመረረች ዘመኑ ስንዝሩዋ እንደ ፃሺ ሜትር ሁናበት ስታልፍ ለተከታዩ ዕድለቢስ አውርሶት ይሄዳል ። እንዳባቱ የግምበሩን ወዝ ይጨርስ ዘንድ። የገበሬን ኑሮ ነገር ከሁሉ አስቀድሞ ማደላደል የተገባ ሥራ ነበር። ታላላቆቻችን በቍርጥ ግብር ወሰነው የርሻ ሥራውን በነጻነት እንዲያከናውን ቢፈቅዱልን ለትጉሁ የኢትዮጵያዊ ገበሬ ችግር ሲቀልለት የሙታን ትንሣኤ ያህል ይሆንለታል።ይኸውም ታላቅ የሥልጣኔን ደጅ መክፈት ይባላል። ድንቍርናም ወደ ወደደችበት ተሸኝታ ታድራለች። ላ፩ ሰው ጥቅም የሆነ ነገር ለ፪ኛው ጕዳቱ ነው። አዳም በሚስቱ፥ ሚስቱ በባቢቱ ተንኰል ከገነት ርስታቸው ተነቀሉ ብሎ መጽሐፍ እንደሚነግረን መንግሥትም የገበሬ ነጻነት ሲቀርበት ይጐዳል።ይህነንም የምናውቅ እንሁን።ነገር ግን ደስ ማሰኘት የቀኖች ነገሥታት ሁሉ ልማድ ስለሆነ። የሀገር ደምበር ወታደር፥የሥራ አዋቂ እንገርኒዬር፥የሕግአውጪ መምህር፥ ለመንግሥት ነፍስ ገንዘብ የተፈለገ እንደሆነ ። ገበሬ በየበታውና በሥራው ሁሉ ለማገልገል የተሰናዳ ነው። ይህም ላስተዋይ ሕሊና፥ለንቁ ልብና፥ አይሰወርበትም ። ምንና ምን ቢባል ዘርና ነበር። የገበሬ ቍርጥማት። ዱግ፤ ጭቃ ሹም ። ወረዳ፤ አውራጃ ሠራተኛ ሆይ። ገበሬ ወደወይኑ ባለቤት ወኪል ነቢዩ ንጉሠ ነገሥታችን ተስፋውን አዘንብሏል ይመስለናልና በውነተኛው ብርሃንየምታምን የደነዘ ልብህን የተውለበለበች ተንኰልህን በሀገር ፍቅር ብንለውጥ ለሰውነትህ ፈውስ ነበር። የኢትዮጵያ ባላገር ከዶስታ የተነሣ ፀዳሉ በወደረኞቹ ፊት መብረቂያው ደረሰ። እንግዲህ ቀማኞች ይደነግጣሉ፥ከመሠረት የጭካኔ ደዌያቸውም ለመፈወስ ተናወጹ። የታላቁ ባለግርማ ንጉሣችን ፈቃድ ትእዛዙን በሰሙት ላይ ከመልካም መንፈስ ይወርዳል። ልቡ የማይገዛር ጃውሳ ግን ሥራው ይመሰክርልበታል። ለምስኪኑ ገበሬም የምሥራች ይነግርለታል። ማንም የነጻነትና የጥበብን ምንጭ ሊከለክለው አይችልም። በትምህርት የመጠመቂያው ጊዜ ደረሰ።ምስክሮቼም እውነትና ቅንነት ናቸው።ለክፉ አድራጊ የሚሔዱበትን መንገድ የሚወድቅበትን አዘቅት እነሱ ይነግሩታል። የተንኰል አባት ሆይ የጥበብ ልጆች በነበልባል ሰይፍ ሐኬትህን ሊቃወሙህ ከተነሡ ፲፬ ዓመት ሆናቸው።እንግዴህ ግን የእሳት ፍሕም ወዳለበት ሥፍራ ሳይጥሉህ አይቀሩም ።

እየለ ገዳ ዘብሔረ ወግዳ።

የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ተዝካር እሑድ ሁኖ ፍትቱና የመወድሱ አደራረስ ስለ ገጠመ ፍትቱ ተፈጽሞ መዝሙሩ ከተባለ በኋላ ስለግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ መታሰቢያ በራጉኤል የተደረሰው ቅኔ ከዚህ በታች እንደተጻፈው ነው ።

መወድስ ።

አስከለ ማርያም ዘቆመ ዲበ መንበርኪ ።
ለእመ እኮ ዘመልአ ኃይለ ሥላሴ ባሕረ ኂሩት ።
እፎ እምሐልቀ፡ ክህናትኪ ዓማት ።
ወእምየብሱ እፎ፡ ሕዝብኪ እትክልት ።
እምጣነ ሀሐይ ኂሩትኪ፡ይሠርቅ ሎሙ ለለዓመታት ወዕለታት
እም፡ኃየሉ ሂ ከመ ይግበሩ በእንቲአኪ ለሞት ።
መዋዕተ ርእስ ዘተወዋነ በሙሴ ወበዳዊት ።
ባሕቱ ይብለነ፡ ለሀገረ ዙፋ ንግሥት ።
እነ እረድእ ወእሣሃላ ከመ ትክት ።

ሊቀ ጠበብት ድንቄ ዘራጉኤል

ሥላሴ

ዳዊት ንጉሡ ጽድቅ፡ ከመ ነገረነ በመዝሙር
እንተ በጉሕሉት መሐለ ለቢጹ፡ ዓለመ ሥጋ ኃሣሥ ።
እስመ ኢይበውእ ለአምላክ መቅደሶ ።
ለእንተ በጕሕሉት መሐለ ዓማጺ፡ በሊዐ መሐላ እምሐሰ
ቅድመ ገጸ ሰብእ ለተወድሶ ።
ለዓርከ መራዊ ንጉሥ እምይት በአሰ ።
ወእምያምትር ከጣይ ወርሰ ።

መወድስ

ሠለስተ አብያጸ መሰፍንት ምድር፡ ኃይለ ሥላሴ ጸውዐ በስምዐ ሰማዕታት ሠለስቱ ።
እከኑ ይቀውም፡ ነገረ መንግሥቱ ።
ወበወንጌላዊ ኃይለ ሥላሴ፡ ዘተጽሕፈ ቃለተ ወንጌል ሲጻሳት ስድስቱ ።
በአምጣነ ርትዕት ሃይማኖቱ ።
ይሚህሩን ምግባረ ወተፋቅሮ በበዕለቱ ።
ዓርገሂ ሰናክሬም ርእሰ ዓመፃ ለሞቱ ።
መንግሥተ ሕዝቅያስ ኃይለ ሥላሴ እንዘ ዓሠርቱ ወአርባዕቱ (ቀዳማዊ ነገሥት ፲፰ ቁ ፲፫)
በሰይፈ ሚካኤል መነነ ወሰይፈ ሥላሴ ጸሎቱ ።
ለሕዝቅያስ ኃይለ ሥላሴ አምጣነ ተመትሩ ጸላእቱ ።
(ቀዳማዊ ነገሥት፡ ም ፲፱ ቁ ፴፭ ፴፮)አለቃ ዳንኤል እ ደስታ።

ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች ላገር ደም ማፍሰስ

ለስማቸው መነሻ።ለክብራቸው ማስታወሻ ባማርኛ የቅኔ አነጋገር ስለ መዋያቸው ። ማደርያቸው መዋያ ማለት ሥራ ማደሪያ ማለት ኑሮ እገሌ መዋያው ማደሪያው አይታወቅም ማለት ሥራ የሌለው ኑሮ የለውም ማለት ይመስላል።

ግዕዝ ቅኔ

ጸውዖሙ ኃይለ ሥላሴ። ወበጥበብከ እንቅሖሙ ።
ከመ ኢይኑሙ ምዕረ እለ ለከርሙ አርዌ ።
ጠበብት እስመ ይጼውዑ ስመ ሰብእ ደማዌ ።
ኢይኅጣእ ሰብእ ደማዊ ጥንተ ሕይወቱ ነፍሳዌ ።
ዓዲ ተበቀል እለ ነነዌ ።
ኢይግሥሡ ነደ ገሞራዌ ።
ዘከልአሙ ዘዮናስ ምንታዌ ።

መጣቶች ከቡራን ማእምራን የብርሃን ወዳጆች የሰላም ልጆች ያገራችን የንግግር መንገድ መሪ ግዕዝ መሆኑንና የማርኛ መንገድንት ብዙ መንታ መሆኑን ያለ መሪ ቢሔዱ ካላሰቡበት እጕል ስፍራ መጣሉን አትስቱትምና ለንባብ መስሚያ ያህል ዘይቤ ማወቅን ትሻላችሁ ብዬ ፍጹም ተስፋ አለኝ አለቃ መርሻ።

የሚያሳዝን ሞት ።

ወይዘሮ ጥበበ ሥላሴ መስፍን ያዒ ዮሐንስ የእንታቸው የልጅ ልጅ በናታቸውም የወይዘሮ በለጤ አየለ ወርቅ ልጅ የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ማህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የጃንሆይ ያክስት ልጅ፡ ልጅ ኤፍሬም ዘውዴን የራስ ዘውዴን ልጅ አግብተው ሲኖሩ ። በሳል ሕመም ታመው ተባላቸው ተለይተው ቀርተው ወንድሞቻቸው ልጅ ግዛው ባንተይዋሉና ልጅ ፊለቀ ባንተ ይዋሉ መንፈቅ ሙሉ በየሐኪሙ እያዞሩ ቢአስታምሙ ምንም ዘመድ ቢደክም ተጕዳት እንጂ ከሞት አያድንምና እወንድማቸው እልጅ ግዛው ባንተ ይዋሉ ቤት ባግንቦት ፱ ቀን ዓረፉና አዲስ አበበ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በብዙ ክብርና ፍታት ተቀበሩ።ዕድሜአቸውም ፳፪ ዓመት ነበር ደግሞ የሰስት ዓመት ልጅ አለቻቸው ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ከብዙ ሕዝብ ጋር ተሰብስቦ እጅግ አዘኑላቸው ።

ማስታወቂያ የሚሸጥ አዲስ
ጥሩ ባለፎቅ ቤት ።

ከዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በታች ያለው ከትልቁ መንገድ ፊት ለፊት የሚገኘው የሙሴ ባስልዮስ ፊሊስ ቤት ይሸጣል። ቤቱም ባለ ፎቅ ሁኖ በፎቁ ከሰገራውና ከውጥቤቱ በቀር ስድስት ክፍል ያማሩ ቤቶች አሉት ። እታች አንድ ትልቅ ሱቅ ሳንቃ የተነጠፈ ፡ ደግሞ አንድ ክፍል የጽሕፈት ቤት የሚሆን አለው ።

የቦታውም ስፋት ከቤቱ ጋራ ፩፻፶ ሜትርካሬ ነው ጥሩ የውሀ ጕድጓድም አለበት ። ይህን ቤት መግዛት የሚፈልጉ የቤቱን ዋና ሙሴ ባስልዮስ ፊሊስን ይጠይቁ ።

ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

ለክቡር ብርሃንና ሰላም

ሚያዝያ ፳፭ ለ፳፮ አጥቢያ ፲፱፻፳፪ ዓ ም አዲስ አበባ ላይ ዝማኅተም የፊታውራሪ ከሳ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኝ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ከሌባ እጅ ተገኝቶ ይኸው ማኅተም በእማኞች ፊት መሞረዱን በማክበር አስታውቃለሁ ።

ፊታውራሪ ከሳ መሸሻ ።

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ መ ን ግ ሥ ት

በልዩ የቆመ የፍርድ ቤት ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ሙሴ ሀራድ ዛማኒያን ስለ ፊታውራሪ ወንድም አገኘሁ ወኪሉ አቶ ደሳለኝ አምበርብር ነው ብለው ከሰው በሰኔ ፫ ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በልዩ በቆመው የፍርድ ቤት የፈረደውን ፍርድ ለማስፈጸም ተከሳሾቹ የሔዱበትን አገር ስላላወቀው ስለዚሁ ነገር ተከሳሾቹ ወይም ስለተከሳሾቹ ኃላፊ የሚሆን ሰው እስከ ሰኔ ፤ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ድረስ ወደ ልዩ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ እናስታውቃለን ።

እስከ ሰኔ ፤ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ድረስ የሚቀርብ ሰው የታጣ እንደሆነ እስከተቈረጠው ቀን ድረስ ጠብቆ የተከሳሾቹ የተያዘውን ካሚኦንና ገንዘብም ፈልጎ በልዩ በቆመው የፍ ርድ ቤት በሰኔ አሥርቀን በሐራጅ እንዲሸጥ ቈርጠናል

ግንቦት ፤ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከገዐዝ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሣባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ፤

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጕበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቍቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጐርጐርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር
የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፤ የርሻ፤ የፋብሪክ፤ የደን፤ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የ ወ ር ቅ ሰ ዓ ት

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅቅ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX,) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገናል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኳላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣምውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
6me ANNÉE № 22

ሐሙስ ግንቦት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።
JEUDI 29 MAI 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማተሚያ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የፈረሶች መቀዳደም

በግንቦት ፲፰ ቀን በጃንሜዳ ፈረሶች የሚቀዳደሙበት ቀን ነበር።፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን ጃንሆይ በአቶሞቢል ሁነው ከመኳንንቱ ጋራ ወደ ጃንሜዳ መጡና በተዘጋጀው ዙፋን ተቀመጡ። የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ አገር ሰዎችም በየመዓርጋቸው ተቀመጡ።ሩብ ሰዓት ቈይቶ የፈረሶች መቀዳደም ተጀመረ ።

የመጀመሪያው መቀዳደም የሚዳውርቀት ፰፻ ሜትር ነው

፩ኛ፥ ጉራ የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫና ፵ ብር ተሸለመ ።

፪ኛ፥ ደርቢ የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፴ብር ተሸለመ ።

፫ኛ፥የልዑል አስፋው ወሰን ፈረስ ሆነና ፲ ብር ተሸለመ።

የሁለተኛው መቀዳደም የሚዳው ርቀት ፩ሺ፭፻ሜትር ነው።

፩ኛ፥ ሱዳን የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፩የወርቅ ዋንጫና፶ ብር ተሸለመ ።

፪ኛ፥ ዳዊት የስር ሲድኒ ባርተን ፈረስ ሆነና ፴ብር ተሸለመ።

፫ኛ፥ ሽሬፍ የሙሴ ባሮን መዚ ፋልኮኒ ፈረስ ሆነና ፳ብር ተሸለመ ።

የሦስተኛው መቀዳደም የሚዳው ርቀት ሺ ፰፻ሜትር ነው።

፩ኛ ፥ ሳሂብ የሙሴ ኮራ ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫና ፶ ብር ተሸለመ ።

፪ኛ፥ ሐሊል የሙሴ ባሮን መዚ ፋልኮኒ ፈረስ ሆነና ፴ብር ተሸለመ ።

፫ኛ፥ ግሬደው የሙሴ ትሩት ቤክ ፈረስ ሆነና ፲ ብር ተሸለመ።

የአራተኛው መቀዳደም የሚዳው ርቀት ፩ሺ፪፻ ሜትር ነው ።

፩ኛ፥ ሐረር የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫና ፶ ብር ተሸለመ

፪ኛ፥ቲሮን የመዳም ሽምባር ፈረስ ሆነና ፳፭ ብር ተሸለመ።

፫ኛ፥ወዳጆ የልዑል አስፋው ወሰን ፈረስ ሆነና ፲፭ ብር ተሸለመ ።

የአምስተኛው መቀዳደም የሚዳው ርቀት ፪ሺ ሜትር ነው።

፩ኛ፥ ሩብር የመዳም ሽምባር ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫና ፶ ብር ተሸለመ

፪ኛ፥ ሲሞስ የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፴ ብር ተሸለመ ።

፫ኛ፥ጉራ የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፳ ብር ተሸለመ ።

የስድስተኛው መቀዳደም የሚዳው ርቀት ፫ሺ ፪፻ ሜትር ነው።

፩ኛ፥ በለው የልዑል መኰንን ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫና ፶ብር ተሸለመ ።

፪ኛ፥ክናዳ የስር ሲድኒ ባርተን ፈረስ ሆነና ፵ብር ተሸለመ።

፫ኛ፥ፍቼ የግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ፈረስ ሆነና ፳፭ ብር ተሸለመ ።

የሰባተኛው

እጅግ ከፍ ብሎ ስምንት ስፍራ ላይ ሁለት ሁለት አግዳሚ ዕንጨት ተደርጎ ነበር።ይህንኑ በተራ አንድ አንዱን ፈረስ ሲአዘልሉ

፩ኛ፥ ራስ የሙሴ ኮራ ፈረስ ሆነና ፩ የወርቅ ዋንጫ ተሸለመ ።

፪ኛ፥ በላይ የጃንሆይ ፈረስ ሆነና ፶ብር ተሸለመ ።

ደግሞ ሁለት ሁለቱን ፈረሶች አንድ ጊዜ ሲአዘልሉ
ሙዲ ገማ የሚባሉ የሚሲቴር ኮሎኔል ሳንድሮርድና የሙሴ አድሪ ፈረሶች ፩ኛ ሆኑና ተጨበጨበላቸው ።

ደግሞ የኢትዮጵያ መላክተኛ ጋዜጣ ዲሬክተር የሙሴ ዶሮቢ ያር ገና ያልተዳረች ልጃቸው አብራ ከወንዶች ጋራ በዚሁ በሚአስፈሩ ዝላይ ስታዘልል ፈረሱ ፈርቶ ዋቂት ዘወር ባይልባት ዕድሉ ለርስዋ ሳይሆን አይቀርም ነበር ። ምንም በፈረሱ መሸሽ ምክንያት ቢቀርባት የንቃትዋና የድፍረቷ ነገር ደስ ስላሰኝ ጃንሆይ የወርቅ ልሻን ሸለምዋት ። በዚህ ጊዜ ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ ወልደ አብ የጻፉት ቃል ትዝ አለን ። ይህ ሁሉ የሚደረገው በንስተዳጅኣ ልምድ ነው ። በዚሁ ቀን ዕድል (ሎ ፡ ሪ) ያገኙ ሙሴ ብሪአ ፩ሺ ብር ።

ሙሴ ኮሌር ፭፻ ብር ፡ ሙሴ ጃንቦ ፪፻፶ ብር ፡ ከንት ዞር የኢጣልያ መንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ፪፻፶ ብር ። አንድ የሙሐመድ አሊ ሰው ፪፻፶ ብር ፡ እኚህ ናቸው ።

ስለማይገባ እሚሚት

አሁን ባለፈው ሰሞን የሆነ ፕሮፌሶር ፒዛኒ የሚባል የኢጣሊያን ዜጋ በገዛ እጁ ያሚሚቱ ነገር እጅግ ይገርማል። ይኸ ፕሮፌሶር ፒዛኒ የሚባለ የኢጣልያን ዜጋ በገዛ እጁ ያሚሚቱ ነገር እጅግ ይገርማል ይኸ ፕሮፌሶር ፒዛኒ ከኢረትሪአ ኣገት ከስመራ መጥቶ አክብት ክትባትማኅበር ቤት ይሠራ ነበር ። ዘንድሮ ከፋሲካው በዓል በፊት በገዛ ራሱ ላይ ሽጉጥ ተኩሶ ክፉኛ ቈስሎ በእግዚአብሔር ቸርነት ሐኪሞች አክመውት ከዳነ በኋላ በዝምድና አስጠግተውት በኒኃድሪስ አፈወርቅ ቤት ተቀምጦ ነበር ፡ ያልታደለው ፕሮፌሶር ፒዛኒ እንኳን ለራሱ ለሰውም መምከር ይችል የነበረ የቀድሞውን የጎደለ ሐሳቡን አድሶ እንደ ገና ሽጉጥ ፈልጎ ጉለሌ ሳይ በሚአወጣው መንገድ ዳር ወደዘፍ ውሥጥ ተጠግቶ ዛሮ ግንዱን በሽጉጥ አፍርሶት ሙቶ ተገኘ ። በገዛ እጁ ወዲያው እንደተኰሰም ዘበኞች ደርሰው ሬሳውን አስኪአነሡት ድረስ በሰሙንቱ ውሥጥ ነፍሱ አልቈየችም። በገዛ እጁ አንድ ጊዜ ተመትቶ ከዳነ በኋላ ቁስጭቱ ከልቡ ውሥጥ ሳይጠፋ ቈይቶ ሁለተኛም በገዛእጁ ራሱን የሚገድል ሰው በዚህ አገር ገና ዛሬ ማየታችን ነው ምንም የሞቱ ብትን ምክንያቱን ሥሩን መርምረን ባናውቀው በገዛ እጁ ተጣጥሮ ራሱን ለማጥፋት በመድረሱ ከትልቅ ስሕተት እንቈጥርበታለን ፈጣሪያችን ምንም ብንበድል የምንታገሥበት አእምሮ ሰጥቶን ሳለ ሰውነታችንን አበሳጭተን በእንደዚህ ያለ እሚሚት ብንሞት ከታላቅ ድንቍርና የሚቈጠርብን ስለሆነ ሌሎች ሰዎች ይኸን ዓይነት የጭከና መንገድ እንዳይከተሉ ተስፋ እናደርጋለን ።

ሁለተኛ፡ክፉንና ደግን እውቃለሁ እያለ የማይመስል ከንቱ ወሬ እያወራ አንዳንዶችን (ኅብዞች) በድብቅ ሲያታልል የነበረ ጐሸ ጐዳ የሚባል ጠንቋይ አገሩ ወላሞ ሕመምተኛ የሆነ ውሻ ንክሶት ኑሮ በተነከሰ በ፰ ቀኑ አእምሮ ተነስቶት እራሱን በፈቃዱ ለማጥፋት አስቦ ከንገቱ ላይ ገመድ ሲጠመጥም አይተው ጐረቤቶቹ ለዘበኞች ስላስታወቁ ዘበኞች ይዘው ለጊዜው ከጥፋት አድነውት የውሻ ሕመም መድኃኒት አለና ወስዳችሁ አሳክሙት ብለው ወዲያውም እንዲጠብቁት ለወገኖቹ አስረክበው ነበር።ነገር ግን ይህ ያልታደለ ሰው እንደገና ከጠባቂዎቹ ላይ ጠፍቶ ሒዶ ኑሮ በቢላዋ አንገቱን ቈርጦ ወዲያና ወዲህ እያለ ሲወራጭ ቢላዋውን እንደ ያዘ ቈይቶ ስለሞተ በገዛ እጁ ታርዶ መሞቱን ዘበኞች መርምረው ለሐኪም አሳይተው አስቀብረውታል ። ጐሽ ጐዳ በገዛ እጁ የአሚሚቱ ነገር ባበደ ውሻ ምክንያት መሆኑ ምንም ቢያሳዝነን እንደሱ ያሉት አታላዮች ለሰው እናውቃለን ሲሉ በራሳቸው ላይ የሚመጣባቸውን ፍርድ ሳያውቁ በድንገት የሚጠፉበት ቀን የሚደርስበት ስለሆነ የተጠላውን የጥንቈላ ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች ይህ ምሳሌ ሁኑአቸው እንዲመክሩበትና በውሻ የሚነከሱም ሰዎች በቶሎ ወደ ሐኪም መሔድ እንዲያስፈልጋቸው በምክር ለማስጠንቀቅ ብለን ጻፍነው

ደጉ ይመር

የኢትዮጵያ መንግሥት ደግነትና የዋህነት

የኢትዮጵያ መንግሥት ደግነትና የዋህነት ከልክ ያለፈ ርኅሩኅና ቸር መሆኑን የሚአስረዳ ምንድርነው ብትለኝ ፩ መልስ ለሕዝቡ (ታሳ ቢመስትረ) የሚባል በማናቸውም ንግድ ለሚነግድ ነጋዴ የሚከፍለው የሁለት ወር ግብርና ከመንግሥት ሠራተኞች በመላቸው ከ፳፭ ብር በላይ ደመወዝ ለሚቀበሉ ከ፲ ብር አንድ አላድ አበል (ርተኑተ) ማስከፈሉ ከገር ገጋሮችም ሁሉ የተገባና የተተከከለ ያመት ግብር መቀበሉ ይቀርና ባገሩ ውሥጥ አላንድ ልዩነት የፈቀዳቸውን ንግድ በያይነቱ ለሚነግዱ ነጋዴዎችና ባለጠጎች ማኅበረተኞችና ቱጃሮች ባለባንክዎችም ሁሉ ያመት ግብር እነደሀብታምነቱ ሒሳብ ገንዘብ መክፈል የሚገባቸውን አላንድ ለመንግሥት ግብር ሳይከፍሉ በብዙ ነጻነትና ከበሬታ ይኖራል ።

፪ኛ ደጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ከዚህ ቀድሞ ባገሩ ውሥጥ ለሚኖሩ ነጋዴዎች ሁሉ ከነሱ የሚገባውን ግብር ማስከፈሉን ትቶ ምንም ምሕረት ቢያደርግላቸው ለወደፊቱ ላገሩ ጥቅም ለመንግሥቱ ብርታት የሚሰጠው ብልጥግና ማሰብና ለማኅበረተኞችና ቱጃሮች ኩባንዮችና ለባለሆቴሎችና ተያትሮኖች አናጢዎችና ገንቢዎች ወርቅና ብር ፒላቲን ብረት ሠራተኞች የማናቸውን ፋብሪካ ሰሪዎች ወደ ኢትዮጵያ ለጥቅም ንግዳቸው ለሚገቡና ለሚወጡ ሰዎች ነዋሪዎችም ሁሉ ሆኑ። ተደምብ በፍጥነት የሚያቆሙ ሊቃውንቱን አስጠርቶ ባቆመው ደምብ ልክ በያይነቱ ግብር ቢቀበላቸው ለመንግሥታችን እጅግ አድርጎ የሚያስመሰግነው ሥራ ሁኖ ታይቶኛልና ከኔ የቀረውን ሞልታችሁ የተሳሳተውን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንዲያስተካክሉት እለምናለሁ ።

፫ኛ ከዚሁም ውሥጥ ራሱ በፈቃዱ በወታደር ደምብ ገብቼ አድራለሁ ለመንግሥት ባገለግል እጠቀምበታለሁ ብሎ ያልፈቀደ ሰው ካልሆነ በተቀር (አብልንቶርዮ) ነህ ተብሎ በግድ ወታደር ሁን እለደመወዝ ሁለት ዓመት ያህል ለመንግሥት አገልግል ብሎ ሰውን አለማስገደዱና ማስጨነቁ ስለ ወታደርነት ፈንታ ለመዳን የሚከፈለውን ገንዘብ ደሐውን አለማስከፈሉ የነጻነት መንግሥት ተብሎ ተጠርቷል፡ይጠሩልም።

ይሁን እንጂ ሕዝብ ከመንግሥት ባገኘው ብዙ ደግነት መንግሥትን እንደሚገባ አድርጎ በትክክልነትና ሐቀኝነት ባያገለግል በገሩና በርስቱ ከልቅናና ከልተቈረቈረ ለወደፊቱ ብዙ ጉዳትና ጥቃት እንዳይመጣበት ያስፈራል። በ፳፫ ም ወንጌሉ የተናገረው ቃል በኛ በኢትዮጵያ እንዳይደርስብን አስቀድመን የመንግሥታችንን ጥቅምና ብርታት የሕዝባችንን ብልጥግና የመስማማት አንድነት ማሰብ እንደሚገባን ለኢትዮጵያ ወጣቶች አሳስባለሁ ። ተስፋ ሚካኤል ትጉእ

ምሳሌ ።

አንድ ቀን በእስያ አገር አዳኞች ሊያድኑ ወደ በረሃ ሔዱ። በዚያ ። በበረሃ ሲያድኑ አንድ ቀን ሌሊት ተኝተው ሳሉ በበረሃው ዙርያ የሚኖሩ ሕዝብ አዩታጡምና ከነርሱ የተቃጠለ እሳት አዳኞች እስከነበሩበት ድረስ መጣ ። ከተኙበት በፍራ ጥዋት ቢነሡ በዙሪያቸው ሁሉ በእሳት ቃጠሎ እንደተከበቡ አዩ ። ቀኝ ቢሉ ግራ የነበሩበት በረሃ ሰፊ ሜዳ ነበርና ከጥፋታቸውና ከሞታቸው በቀር ሌላ አልታያቸውም። ተስፋ ቈርጠው ከዚች ዓለም የሚሰናበቱበት ቀን እንደ ደረሰባቸው እንጂ የሚድኑበት ብልሀት ለጊዜው አልተገኘላቸውም ነበር ። ነገር ግን አንዱ ከነርሱ ብልሀ ሰው ኑሮ በነበሩበት በፍራ ቀኅጭ ብሎ ጓደኞቹን እኔን ምሰሉ እያለ ሣሩን በእጁ ይነቅል ጀመር። ከጓደኞቹ አንዱ ከዋጣን ምን ክፉን እንነቀል እያሉ እንደርሱ ሣሩን ይነቅሉ ጀመር ። የቀሩት ግን በእጃችን ስንቱን ያህል ሜዳ ነቅለን እሳቱን እንዳያደርስብን ልናመልጠው ነውን ። ሞት ሳይቀርልን እስከዚያው ድረስ ምን ያደክመናል ሲሉ የተስፋ መቍረጥ ቃል ተናገሩ ። ብልሁ ሰውዬ እንዲህ ሲል መለሰላቸው ። ወታደር በሰልፍ ጊዜ ምን ማድረግ እንዲገባው አበቶቻችሁን ወይቃችሁ በነበረ ወታደር በሰልፍ ጊዜ አለቃው ያዘዘውን ቃል ከመቃዘዝ በቀር የሚያደርገው ነገር የለውም ሲሉ ይመልሱላችሁ ነበር ። አሁንም እናንተ እኔ የምንግራችሁን ነገር በሰማችሁና እንደኛ ሣሩን ብትነቅሉ ይሻል ነበር።ከዚያ በኋላ የሚያድናችሁን መንገድ ታያላችሁ ። ከዚያ ወድያ የሚበጅ ያድርገው እያሉ ሁሉም ሣሩን ይነቅሉ ጀመር። ከዚያ በኋላ ሣሩን ነቅለው ያጠሩት ምድር ስፋቱ አራት አውድማ ያህል ነበር።የተነቀለውን ሣር እያነሡ ዙርያውን እንዲጥሉት አዘዛቸው። እነርሱም እንደዚሁ ካደረጉ በኋላ ብልሀተኛው ሰውዬ የጠበንጃውን ባሩድ ተኩሶ ሣሩን ዙሪያውን ሁሉ አቃጠለው።። ጓደኞቹ ግን የእሳቱን መቃጠል ባዩ ጊዜ እንዲህ አሉት፤ወዳጄ ምነው ጠላትን ወዲያ በማራቅ ፈንታ በቶሎ ወደኛ እንዲደርስብን ቃደረግዋለህን፤እርሱም እንዲህ አለ።ወንድሞቼ ጥቂት ቈዩ አትቸኩሉ፤እሳትና እሳት ሲጣላ ታያላችሁ፤ እሳት እሳትን ይቃወመዋል።እሳቱም ሣሩን እያቃጠለ ከነርሱ እየራቀ ሔደ። እነርሱንም እንኳን መቃጠል የእሳት ወላፈን ሳያገኛቸው ቀረ በእንደዚህ ያለ ብልሀት ከሞት ከጥፋት ዳኑ ። እንግዴህ ከዚህ ምሳሌ ምን መያዝ ይገባናል ብንል መጀመርያ በማናቸውም ነገር ተስፋ አለመቍረጥ ነው ። የሚያስቸግር ነገር ቢመጣ መውጫ ማምለጫ ይገኝበታል፤ እሳት እሳትን እንዲመልስ ዕውቀት ዕውቀትን ይመልሰዋል አሕመድ ፈሪድ ።

ክፉ ልማድ ።

ክፉ ልማድን ለመተው እንዴት አድርጎ ይጨንቃል ።? ክፉ ልማድ በሀገራችን በየአንድ አንድ ምክንያት እየሆነ በሰው ላይ ሠልጥኖ ይኖራል።፩ኛ፤በዳር አገር ያልተማሩ የጋሎች ሚስቶች በየጊዜው ጨሌ ወይም ዶቃ በንገታቸው ላይ እንደ እምበሳ ጥጃ እንዘርፍፈው ደረታቸውን ግምባራቸውን ጥሬ ቅቤ እየለቀለቁ ከሰናዱት ምግብ ከያይነቱ አክላታቸውን እያስነኩ እልል እልል ሲሉ ያመሻሉ። ይህም ሲሆን እነዚያ ያልተማሩ ሰዎች ሲሆን አብረው ሳይሆንም በልጋቸው ላይ ተኝተው ይመለከቷቸዋል እንጂ ይህን ክፉ ልማድ ተዉ ብለው ሚስቶቻቸውን አይገሥፁዋቸውም። ስለዚህ መጽሐፍ እንዲህ ይለናል፤ እጅህም እግርህም ብታስትህ ክንተ ቍርጠህ ጣላት ይሻልሀልና ወደ ሕይወት ብትገባ አንካሳ ወይም ጕንድሽ ሁነህ ። ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኑሮህ ወደዘላለም እሳት ከምትቃጠል። ማቴ ፲፰ ፰። ፪ተኛ፤ በየቤቷ ቡና የምታፈላ ሴት ሁሉ ቡናው ከማጀት ወጥቶ ሊጠጣ በቀረበ ጊዜ በደጅአፏ ላይ ዕጣን ወይም ከርቤ እያጨሰች አንተ የጀበና አምላክ በደኅና አውለህ በደኅና አሳድረኝ እያለች ልመናዋን ታቀርባለች ። ወይጕድ አለማወቅ ምንኛ ክፉ ነው ። ጀበናውን ከፈጠረ አምላክ ይልቅ እስዋን ራስዋን የፈጠ አምላክ አይበልጥምን፤ በደኅና አውሎ በደኅና የሚያሳድራትስ የፈጠራት አምላክ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ እንዲህ ይለናል።እኔንም አምላካቸውን ተውኝ፤ ለእጃቸውም ሥራ አመለኩ።ዘፀአት ፴፪ ፩። ፫ተኛ፤ በጣም የሚገርመው ነገር በየዓመቱ የግንቦት ልደታ በዓል የታላቂ ንጉሥ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት እመቤታችን የተወለደችበት ቀን ስለሆነ መታሰቢያ በዓል ይመስለኛል ። ነገር ግን በዚሁ ቀን በጋሎች ደጅ የሚሠራው ክፉ ልማድ በጣም ያስደንቃል። ሰው ሁሉ በየሀገሩ በየደጁ የተቻለው ሰንጋውን አርዶ ያልተቻለው ሙክቱን አርዶ ደግሞ በጣም ድኻነት የተጫናቸው ሰዎች ቡናውን በጀበና ጥሬውን ከየዓይነቱ በቀና ዳቂቱን በገበቴ ይዘው ዘመድ ጐረቤቱን ጠርተው ጥንት አመድ ሲያፈሱበት በነበረው ቀያቸው ተሰብስበው ይታፈጉና ያንን የመዋጮ እህል አብስለው ሲጨርሱ ከሁሉም ዓይነት ሰው ሳይቀምሰው ያንን እንደዚያ የሚጣፍጠውን እህል እንደአፈር ባመዱ ላይ ግራና ቀኝ እየበተኑ አንቺ የቀያችን አድባር ልጆቻችንንም ከብቶቻችንንም በደኅና ለላመት ያደረስሽልን እንደሆነ ከዚህ የበለጠ ክብር እናደርግልሻለን ብለው ይሳሉና መብል መጠጥ ይጀምራሉ ። በልተው ጠጥተውም ሲበቃቸው ያንን የተረፈውን ለቃቅመው ይዘው የ፫ደቂቃ ያህል መንገድ ይሔዱና ያንን በትነው ጥለው ሲመለሱ ያን ጊዜ ሴቱም ወንዱም እየተዥጎረጎረ አንዱ ባንዱ ላይ ሲወድቅ ሲነሣ ላያቸው ሰው እንዴት አድርጎ ያስቃል ። ይኸውም የሚዥጎረጎሩበት ምክንያት ከነዚሁ አንዱ ምናልባት ወደኋላ የቀረ እንደሆነ አድባሯ ትቈጣና በሽታ ወይም ጕንፋን ይይዘዋል በማለት ነው ይባላል ። ስለዚህ ክፉ ልማድን ስለማይተዉ ሰዎች እግዚአብሔር እንዲህ ይለናል ። ሌሎችን አማልክት አትፍሩ አትስገዱላቸውም ። አታምልኳቸውም።አትሠዉላቸውም። ነገር ግን

እግዚአብሔር አምላካችሁን ከምስር ምድር ያወጣችሁን እርሱን ፍሩ፥ለርሱም ስገዱ፥ ለርሱም ሠዉ። ነገሥት ፲፯ ፴፭።

ከሁሉን እንባቢዎች ሆይ ፤ ይህንንም ደፍሬ መጻፌ ለነዚሁ ይህንን ክፉ ልማድን አጥብቀው ለሚወዱ አምላካቸውን ለማይፈሩ ሰዎች ነው እንጂ ከኃሎች ብዙ ብልሆች የተማሩ ሴት ከእንቅልፍ ቀን ከሰንፍና ታግሠው ፍቅርን እንደ ሸማ ለብሰው ትዕቢትንና ምቀኝነትን ከልቡናቸው አርቀው፥አንድነትን ጠብቀው ከሀገራችን ክፉ ልማድ እንዲርቅ ዕውቀት እንዲሰፋ ጥበብ እንዲፋፋ ፀብ ክርክር እንዲጠፋ ሌት ከቀን አስበው የሚጥሩ ብዙ ናቸው ። ነገር ግን እነዚህን ብልሆች የተማሩ አባቶቻችንን ሐሳብ ሳይከተሉ ምክራቸውን ሳይቀበሉ ሰምተው እንዳልሰሙ ሁነው ክፉ ልማድን በላያቸው ላይ አሠልጥነው ለሚኖሩ ሰዎች ይህን ከዚህ በላይ የተነገረውን ቃል ለመጻፍ ግድ ሆነብኝ ።

ሥላሴ

ዓግአዚት ኢትዮጵያ ተፈሥሒ ዮም ትፍሥሕተ ልብ፥
ኃይለ ሥላሴ ወልድኪ እንተ ቀዳማ ለበኵር ።
በሰማይ እስመ ሰብሕዎ አዕዋፍ ወንሥር
ወኃይለ ሥላሴ ይሰመይ መስተገብሬሃ ለምድር።
በብዝኀ ጥበብ ወበክብር።
እበመ አስተደለወ ለነ ማዕረረ ፍቅር ።
ያድኅነነ እምእኩይ ግብር ። ኀሩይ በንጻው።

መንገድን በማሠራት ስለሚገኝ ጥቅም

መንገድን መሥራት መንግሥትን ስለሚያበለጽግ፥ሕዝብንና ከተማን ስለሚያለማ ተረድተውት ትጉሁና ዐውቀተኛው ክቡር ፊታውራሪ ተክለሐዋርያት የዶክሙብት፥ከተማችን ለምቶ ጥቅሙን በንግድ እንድናገኝ ስዚህበታች እንደማስታወሻ አድርጌ ጽፌአለሁ፥ከዓስበተፈሪ ሚኤስጣበ የሚያገናኘውን መንገድ ለአቶሞቢል እስደልድለው ስላሰጨረሱት ብዙን የውጭ ታጁሮችና የከተማውና ጣቢያው አቅራቢያ በመሆኑ ለንግድ የሚመች በመሆኑ መንገዱ በተሰናዳ ሰዓት በዓስበተፈሪ ከተማ ንግድ እናቆማለን እያሉ ሲመኙ ነበር።ነገርግን የእግዚአብሔር ሐሳብና የሰው ሐሳብ የተራራቀ ስለሆነ ከ ፊ ተ ሐ የድልድሉን ሥራ አስጨርሰው የድልድዩን ከገንቢዎች ከተቋረጡ በኋላ ሥራው ስለቆመ የታጁሮቹም ሐሳብ አብሮ ስለቆመ በጣም የከተማው ሰው ሁሉ አዘነ ። በውነትም ማዘን ይገባዋል (በለምንቢሉ) እንደኛም አዘኑ ከተማ ያለ ቱጃር ባለመልማቱ ፱ኛም ኃዘኑ የተጀመረው ሥራ በለመፈጸሙ ይመስለኛል ለዚሁ ም የሚያስረዳ ነገር ያንጊዜ መንገዱ ሲሠራ የከተማው ሰው ከተማው እንደሚለማ ስለ ተረዳው ፩የከተማ ቤታ እስከ፺፲ብር መገዛዛት ተጀምሮ ነበር ዛሬ ግን የመንገዱ ሥራ ስለ ቆመ መቶም ብር አያወጣም ነገር ግን አሁን ክቡር ፊታውራሪ መዝለቂያ ኅጨርጨር አውራጃ ስተሾሙልኝ ከዓስበተፈሪ ሚኤስ የተሠራውንና ከዓስበ ወደጌርና የተጀመረውን ደኅዋ ወደበደሳ በሚያስኬድ በሚመቸው መንገድ እንዲሠራልንና ንግድ እንዲሰፋልን እንመኛለን ሥራው ተከናውኖልን ከተማው ለምቶልን እኛም የኢትዮጵያ ልጆች በንግድ አግኝተን መንግሥታችንን እንድንረዳ እንመኛለን፥ ለማስታወስ ያኘሣሣኝ መንገድ ከልተከፈተ ሥልጣ-

ኔና ማግኘት በቶሎ እንዳይገኝ ስለተረዳሁት ነው ስለዚሁም መንገድ ማሠሪ በክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት አዘጋጅነት (በጃንሆይ)ቸርነት ለትዳሬ የሚበቃ ከሰጡኝ ካገኘሁት ደሞዜ ላይ ፤መንገዱ ሥራ በተጀመረ ጊዜ ፭ ብር እርዳታዬን ዓስበ ተፈሪ ግምጃ ቤት እሰጣለሁ እንደዚሁ ሌላም ሰው የሚረዳ ቢገኝ ሥራው በቶሎ እንዲፈጸም ማንም አይስተውም ።

ቲንሹ ልጃችሁ ወዲሁም መላክተኛችሁ የዓስበ ተፈሪ ቢሮ ሰንትራል ሥልከኛ ማናለ ይግላጡ ።

ግልግል ።

ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ ወልደ እብ በግንቦት ፯ቀን በቍጥር ፰ብርሃንና ሰላም አቶ በቀለ ዘለቀ ያገራችን ወይዛዝ-ሮች የሥልጣኔን መንገድ እንዲከተሉ ብሎ ስለጻፈው የምክር ቃል መልስ የጻፉትን ከሥር እስከ ጫፍ ብመለከተው ሴቶች የሥልጣኔን መንገድ አልጠላንም ። ነገር ግን መሪዎቻችንና ጋሻጃግሮቻችን ወንዶች ናቸውና አስቀድመው እነሱ ሥልጣኔን ከገኙ እኛም በፍጥነት እነሠለጥናለን ሲሉ ነው ።

እውነት ነው ለሴቶች ገጋሮቻቸው በሎቻቸው መሆናቸው አይጠረጠርም።ነገር ግን ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ ከጻፉት ክብ-ሁው ነገር እንደኛው ያስደንቀኛል ። ያውሮፓ ወይዛዝር ከባ-ሎቻቸው ሳይሆን እነሱ የሚያውቁት ሰው ከሆነ ከማንም ጋራ ቢሆን እጅ ለጅ ተያይዘው የደስታ ጨዋታ እየተጫወቱ ይንሸረሸራሉ ። ባሎቻቸውም እምነትን ሰጥተዋቸዋልና ደስ ይላቸዋል እንጂ ምንም አይከፋቸውም ። የሀገራችንም ወንዶች የሥልጣኔን መንገድ የተከተሉ ከሆኑ እንደዚህ ያለውን እምነት ለኛ ለሴቶች ሰጥተው ከማንም ጋራ እንዋል ሲሉ ወንዶችንመውቀሳቸው ነው ።

ነገርግን አቶ በቀለ ዘለቀ የጻፈው የምክር ቃል የሀገራችን ወይዛዝሮች ለቅልጥፍና የሚያስቸግረውን አሮጌውን ልማድ ትታችሁ በቅልጥፍና የሚሠራውን ሥልጣኔ እንድትይዙ ነበር እንጂ ከማንም ጋር መዋል ሥልጣኔ ነው ሲል አልጻፈላችሁም ነበር።

እንግዲህ ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ አስቀድሞ ሐሳባቸውን ሲጽፉ ሔዋንን እንሥተዋልና በሔዋን አስመስዬ ብጽፍላቸው ይከፋቸው አይመስለኝም ።

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በገነት ባስቀመ-ጣቸው ጊዜ አዳምን ከሔዋን ፈቀድ አትውጣ ብሎት ነበር ይባላል። ስለ ዚህ መቼም ቢሆን ሴት ስሑት ናትና ሔዋን የማይገባትን ክብር ተመኝታ፥ አዳምን ከቀደመ ክብሩ አዋርዳ ወደ መከራ እንዳደረሰችው የተረገጠ ነገር ነው ።

ስለዚህ እኛ ለሴቶች ፍጹም እምነት መስጠት እንደ ቀድ-ሞው ጥፋት እንዳይመጣብን ያጠራጥረናልና መጠንቀቅ ግድ ይሆንብናል ።

ይሁንና መቼም የተጠየቀ ሰው ሐሳቡና መልሱ እንዲከና ወንለት ይጥራል እንጂ የሚጎድልበትን አያስተውልምና ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ መከናነቡንና ቀሚስ አለማሳጠርን ሴቶች ልጆ-ችንም ወደ ተማሪቤት አለመስደድን ያጅ ጥናት አለመተውንም ምክንያቱን በወንዶች ላይ ጣል አድርገውታል ።

እሺ ይሁን ይኸ ይቈይና። እረ ከቶ የኛ አገር ወይዛዝሮች ብቅሎ ተጭኖ በቀረበላቸው ጊዜ ሰው ሳይሸከማቸው እንደአውሮፓ ወይዛዝሮች ዛብ ጨብጠው እርካብ ረግጠው አለመውጣታቸው ምክንያቱ ምን ይሆን ። ሴቶች እኩብት ላይ በግዛእጃቸው ለመውጣት ቢያስቡ፥ወንዶች እኛ ሳንሸከማችሁ አትውጡ ብለው የከለከሏቸው አይመስለኝም። ይሁን እሺ ተሸከመንም እናውጣቸው። ከወጣናቸው በኋላ ዛብ ጨብጦ በቅሎይቱን የሚመራ ሌላ ሰው ይፈልጋሉ። እንግዲህ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ይኸንንም ወንዶች ከለከሉን ሊሉን ይሆንን? ያውሮፓን ወይዛዝር ከማንም ጋር መዋላቸውን ብቻ ሥልጣኔ መስሏቸው ምሳሌ አድርገው ሲጽፉ፣ ሌላውን የቅልጥፍና ሥራቸውን ሁሉ ወዴት ዘንግተውት ይሆን ።

አሁንም እኔ ሐሳቤ አቶ ፀቀለ ዘለቀ የጻፈውን ቃል ሁሉ ዛሬ በፍጹም መቀበል ይገባችኋል ማለቴ አይደለም ። ልብስን ማሳጠርና ገላን ሁሉ ሥጣል በዛሬው ጊዜያችን እብድ ያሰኛል ደግሞ እጅ እግር እያለ በተሸካሚ መውጣት መውረድ ይልቁንም ከበቅሎ ላይ ተቀምጦ ዛብ ሌላ ሰው አሲዞ መሔድ ሽባ ያስመስላል ።

እንግዲህ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ የሚሉት ከማንም ጋራ መዋል ቢቀር ቢጠቅም እንጂ አያጐዳም። አቶ በቀለ ዘለቀም የሚለው ልብስን አሳጥሮ ገላን ሁሉ እንዲያው መጣል ቢቀር ይጠቅማል እንጂ አይጐዳም።ለዚህም አንድ ምሳሌ ባመጣ አይከፋም።እኛ ወንዶቹ ከፊታችንና ከእጃችን በቀር የቀረውን ገላችንን አልጣልንም። ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ እንደሚሉት ሁሉ ለሴቶች መሪዎቻቸው እኛ ስንሆን እኛ ያላደረግነውን አድርጉ ማለት አይገባንም ።

ያውሮፓም ወይዛዝሮች ሴቶቹ ሁለመናውቸን ይጥሉ እንጂ ወንዶቹ እንዳቸውም ገላቸውን አልጣሉም። ይህም ያውሮፖን ወንዶች ሴቶች ስሕቶች ናቸውና ወንዶቹ ገላቸውን ሳይጥሉ ሴቶቹ ገላቸውን በመጣላቸው ሳይገሥፁ መቅረታቸው የዋሆች ያሰኛቸዋል እንጂ ከሥልጣኔ አይቈጠርላቸውም ።

የሆነ ሁኖ እኔ የመሰለኝን ጽፌያለሁና ስሕተት ቢገኝበት ይቅርታ አድርገው እንዲያነቡልኝ አንባቢዎችን እለምናለሁ ።

ተሰፋዬ ካሣ

የማይረሳ አብነት።

ልዑል ራስ መኰንን ከሐረርጌ ታዘው ትግሬን ሁለት ዓመት ገዝተው ወደሸዋ ሲመለሱ አገሩ ለሪ ወሎ ብጡል ስለተሰጠ እሳቸው መቀሌ የገቡ ቀን ልዑል ራስ መኰንን ሠራዊታቸውን በትልቅ መዓርግ አሰልፈው ከተቀበሏቸው በኋላ ጠጅቤታቸውንና ጠላቤታቸውን ፍሪዳውንና ማሩን የሀል ጉተራቸውንና ግምጃቤታቸውን ፭ሺህ ጥሬ ብር ጭምር አድርገው አስረከቧቸው ይባላል።

ጠያቂ በማን ትእዛዝ? ያለአገር ፍቅርና የዋህነት በተቀር አንድም ያዘዛቸውና የለመናቸው ሰው የለም ነበር።

እንደ ልዑል ራስ መኰንን አብነት አድርገው የኢትዮጵያ መኳንንቶች ሲሻሩ ለተሾመው ሻለቃ ሁሉንም ቢያስረክቡና አስረካቢውም መኳንንት ከተሾመበት አገር ሲደርስ በመዝገቡልክ ቢረከበው ለሁሉ ብዙ የጋራ ጥቅም ነበረባቸው። ሻለቆች ግን እንኳንስ እንደዚህ ያለ የማይረሳ የዋህነትና አብነት ለለምለሚቱ ኢትዮጵያ ያገራቸው ጥቅም ሊያስቡና ሊሠሩ ይገባቸዋል። ያገሩ ከዳተኛ ሰው ትርፉ ምንድርነው? የመንግሥቱ ጕዳት የራሱ ጥቃትና ክፉ መጥፎ ስም ለዘላለም ኵነኔ የጠላቶቹ ደስታና ረዳት መሆኑ ባይታየው ይሆናል እንጂ አእምሮ ያለው ሰው አገሩን አሳልፎ አላንድ ጠርነት ለጠላቶቹ አስረክቦ እንደ ለማኝ ምስኪን መከረኛ ሁኖ መቅረቱንና መንከራተቱን አይመኝም ነበር።

የከዳ ሰው ምን ይገባዋል ምንስ ይደረጋል ።

ፈቱን ዙሮ በጀርባው ጥዪት ይተኰስበታል ። ቢማርም ወህኒቤት ገብቶ ይበሰብሳል የናቱና የልጆችዋ እልፍ አእላፋት ነፍስ ገዳይ ክፉ ጨካኝ ደንቈሮ እብድ ተብሎም ይጠራል። አእምሮ ያለው ታማኝ የሻለቃ ግን እንኳንስ የመንግሥት ትእዛዝ መተላለፉና መክዳቱ ይቅርና ከደሐና በውስጡ ካሉት መኳንንት በሞላቸው ተስማምቶ ጠብቆ ችግረኛውንና ራብተኛውን ሰው ሁሉ ረድቶ ለመንግሥት በብዙ መንቀጥቀጥ ፈርቶና ታዞ ካላደረ እንኳንስ እሱ ራሱ ልጆቹም ለሹመት አይገቡም ተብለው ይከለከላሉ እምነት አጥተው ተረስተውም ይቀራሉ። ለዚሁም በአህመድ ግራኝ የተለመደውን ክፉ የከዳት ልማድ በቶሎ የሚያጠፋ ደንብ በፍጥነት ማቆም ያስፈልጋል።

ተመልሰን ወደፊተኛው ነገራችን እንግባ። ልዑል ራስ መኰንን የጀመሩትን እውነተኛ አገልግሎትና ጥልቅ የሆነ ያገር ፍቅር የዋህነትና መስማማትን የኢትዮጵያ መኳንንትና የሻለቆች በቶሎ የልዑል ራስ መኰንንን አብነት እንዲከተሉና ፃማቸውን ከመንግሥታቸው የመሳፍንትነት ማዓርግ እደሚቀበሉ አይጠረጠርም። ስመ ጥሩ ናፖሊዎን ዘወትር ኤውሮጳ በሞላው እንደሚያመሰግነው አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ ለአገራቸው ፍቅር ሕይወታቸውን አሳልፈው ብጦርነት ውሥጥ በማይረሳ በሰማዕትነት መሞታቸው። ልዑል ራስ መኰንንና ክቡር ራስ አሉላ ላገራቸው ብዙ ጥቅም በመሥራታቸው ለዘለዓለም የሚሆን ምስጋናና መታሰብያ የሚገባቸው መሆናቸውን ለኢትዮጵያ ወጣቶች አሳስባለሁ።

ተስፋ ሚካኤል ትኩእ።

ስለቃደኒት መልስ ።

በብርሃንና ሰላም በ፯ኛው ዓመት በ፲፯ኛው ቍጥር በወጣው ጋዜጣ ሐጅ አሸሬፍ አፈንዲ ስለቃዲኒት ሲጽፍ እንዲህ ይላል። ለቃዲኒት ወይም ለፈቂህነት የሚገባውን ሰው ሕዝብ ይመርጠዋል አለ ። እውነት ነው የተማረና ግብረ ገብ ከሆነ እሱ እንዳሰው ሁሉ በክሔዱና በጠባዩ የተመሰገነ ከሆነ ሊሾም ይገባዋል ። ይኸም ሕግ በእስላሞች ብቻ አይደለም ፤ በክርስቲያኖችም ፤ በሌላም ልዩ ልዩ ወገን ሁሉ ለሹመት የሚሆን

ሰው ምንም እንኳ ቢማርና ሊቅ ቢሆን ፤ ሸፋጭ ተንኰለኛ ራሱን ወዳጅ ሰካር ሴሰኛ ከሆነ ስንኳን ሊሾሙት ይቅርና ሲቀጡትና ካገር ሲያሰጡት ነው የምናይ ።

ይኸ ግን ሸሪፍ አፈንዲ የጻፈለቱ ቃዲ ዓባይ ገነን ፥ባለ ወገን ይሆናል እንጂ ፡ ሕዝብ የመረጠው ቃዲ ይኸን ሥራ ይሠራዋል ብዬ አልጠረጥርም ። ለጊዜው እንኳ ቢሾም እንደዚህ ያለ ሃይማኖት የሚያስነቅፍ ሥራ ከሠራ ሕዝቡ እንዳይታገሡት ያለ ጥርጥር አምናለሁ።

ከዚህ ቀደም እንኳ በሐረርጌ ቃዲው ዓረቱ በመጠጣቱና በስካሩ ተመስክሮበት ተቀጥቶ ነበር ። ፪ተኛም አባት እናት የሌላቸውን ሕፃናት ገንዘባቸውን በልቶ በዚሁ ተቀጥቶ ቃዲው እስከ መታሠር መድረሱን ሰው ሁሉ ያውቃል ። ነገር ግን እነዚያ ቃዲ የዘመተባቸው ሕፃናት ገንዘባቸውን ተዘርፈው በመቅረታቸው እስከ ዛሬ ወደአምላካቸው ሲያለቅሱ መኖራቸውን ሸሪፍ አፈንዲ ቢያውቅ ኑሮ ጋዜጣ መጻፉን ? ቶ ምርኩ ለማስመለስ በተጋደለ ነበር ።

ሸሪፍ አፈንዲ ሆይ በቃዲ ላይ ጋዜጣ እንደ መጻፍህ ለእስላም ሃይማኖት የቀናህ ለድሆች የተቈረቈርህ ትመስላለህ። ነገር ግን ፩ ነገር ቀር አስኘተኸናል ። እንደት ስትዮ ሐዲ ለቃዲ ላይ ባኳን ከሰስክ ። ቃዲም ና ብሎ ጠራው ። ሰውዬው ግን ብዶ እጁን ወደ ቃዲ ለመሔድ ስለ ፈራ ቢዘገይ፡ተፈትተሽልና ሐጂ እንዶልብሽ ሁኚ ብሎ ቃዲ ለሰትዮይቱ ወረቀት ሰጣት ። ኋላ ባልዮው በተራው ሐዶ ቢጠይቀው አልተፈታችምና ሚስትህን ውሰድ ብሎ ለሱም ወረቀት ሰጠው።እንደዚህ እያደረገ በሕዝብ ቲአትሮ የሚጫወተውን ሸፍነህ በመተውህ የቃዲው ወዳጅነትህን ይገልጥብሃል ።

፫ኛ መጠጥ የሚጠጣ ሰክሮም ቃዲነት አይሾምም ትላለህ፡ እነሆ ጋዜጣ የጻፍህለት ወዳጅህ፡ እንዳይርቀው እመሸታ ኀጮቹ መሀከል ቤቱን ተከራይትዋል ።

፬ኛ ሁለቱ የሚጋቡት ባልና ሚስቱ ከተስማሙ እወደዱበት ኒካ ማድረግ ይችላሉ ስትል ወዳጅህ እንዳይነክብህ ቃዲው ገንዘብ ፈላጊ መሆኑ ከታወቀ በዘመድ ዳኛ መጋባት ይችላሉ የሚለውን በመተውህ አዝነናል ። ሁሉንም እንተው እንዳልኸው ሁሉ ጊዜያችን የብርሃንና የሰላም የመገላለጫ እንጂ የመተማሚያ የመሻፋፈጫ አይደለምና ይልቁንስ ሕዝቡ እንዳይነሡበትና ከፊተኛው የተባሰ እንዳያገኘው ወዳጅህን በሥውርም በግልጽም ምከረው ።

እኛም የኢትዮጵያ ልጆች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥታችን በሥራቸው ሁሉና በገዛዛቸው የተተከከሉ እስላምና አማራ የማያነገዋልሉ መሆናቸውን ይልቁንም እኛ የሐረር ልጆች ቀደም ብለን ተረድተነዋልና ታሪካችን የሚያድፍበትን ሃይማኖታችን የሚነቀፍበትን ነገር አይተንና ሰምተን ዝም ብንል ጕዳታችን በስንፍናችን ይሆናል እንጂ በመንግሥታችን ሐሚትና ነቀፌታ የለበትም ።

አቡበክሪ አዱስ ሐረር ።

ሹም ሽር

ደጃዝማች ሙሉጌታ የጦር ምንስቴርነታቸውን እንደያዙ የተጨመረላቸው ማዕርግ ቀጥሎ የሚመጣው ነው ። አረንጓዴ ሱሪ ባለወርቅ ከረፍ ታጥቀው ባለ ወርቅ ሙካሽ ቀሚስ ለብሰው ። የሐር ድሪ ታጥቀው ጥሩ ድርብና ጥሩ የወርቅ ላንቃ ለብሰው ። ራስ ወርቅ አሥረው አረንጓዴ ጥላ አስይዘው ፊታውራሪ ተብለው ቀጥሎ የተጻፈውን አገር ተሾሙ ። እስከ አሁን ይዘይውት በነበረው በሰዮ ወረዳ ላይ

ጨቦን

አመያን

ውሊሶን

የገምንና

የጋርዱላን

የኮምሶን

የዘይሴን ቈረጭነት ። ስለተሾሙ ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አለው።የእግዚአብሔር መዓቱም ምሕረቱም ሊመጣ ተቀጣጥሎ ነው።ስለዚህም ከጦር በደኅና መምጣት ዋና ደስታ ነው። ደግሞ የገቡለት ልሽንና ባለ ፈርጥ በለወርቅ ሰገባ ሰይፍና ልሽን በንጉሠ ነገሥት እጅ መሸለም ዋና ደስታ ደግሞ በደባባይ በነጋሪት እንዲህ ያለ ማዕርግ ያለው ሹመት መሾም ዋና ደስታ ነው ።

መግለጫ ።

አማርኛ ተግዕዝ የወጣ ነው ሲሉ አዋቂዎችን ሰምተን ግሥ የሌለውን መግለጫ ጽፈናል።ባለፈው ሳምንት በብርሃንና ሰላም የሰልፉን ነገር ስንጽፍ በልማድ ፎከረው እሚባለውን ፈከረው አለፉ እያልን ጽፈን ማስረጃውን ፈከረ ማለት በግዕዝ ቋንቋ ተረገመ ማለት ነው ። አርበኛም የሙያውንና ያገዳደሉን ነገር ተርኮም የሚያስታውቅ ስለሆነ ፈከረ ይባላል ያልነው ፉከራ ተብሎ ታትሟልና ፍክራ መሆኑን ለአንባቢዎች እናመለክታለን ።

ደጋም በልማድ የፈረስ እሽቅድምድም የሚባለውን ። ቀደመ ጓሥ ብለን እን፡ ሺን ባዕድ አናገባም ብለን እንደ ግሡ የፈረሶች መቀዳደም ብለነዋልና ስሕተት የመሰላችሁ ሰዎች እንድታስታውቁን እናመለክታለን ።

ማስታወቂያ ።

ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርት ያሳተሙት ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት የተባለ ብዙ ዕውቀት የሚሰጥ መጽሐፍ ዋጋው ሁለት ብር ተአላድ ነው ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታገኙታላችሁ ።

ማስታወቂያ የሚሸጥ አዲስ ጥሩ ባለሮቅ ቤት ።

ከዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት በታች ያለው፡ከት-ልቁ መንገድ ፊት ለፊት የሚገኘው የሙሴ ባስልዮስ ፊሊስ ቤት ይሸጣል። ቤቱም ባለ ሮቅ ሁኖ በሮቁ ከሰገራውና ከወ-ጥቤቱ በቀር ስድስት ክፍል ያማሩ ቤቶች አሉት ። አታች አንድ ትልቅ ሱቅ ሳንቃ የተነጠፈ ፤ ደግሞ አንድ ክፍል የጽሕፈት ቤት የሚሆን አለው ።

የቦታውም ስፋት ከቤቱ ጋራ ሺ፻ ሜትርከሬ ነው ጥሩ የውሀ ጉድጓድም አለበት ። ይህን ቤት መግዛት የሚፈልጉ የቤቱን ዋና ሙሴ ባስልዮስ ፊሊስን ይጠይቁ ።

ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

ለክቡር ብርሃንና ሰላም

ሚያዝያ ፳፫ ለ፳፬ አጥቢያ ፲፱፻፳፪ ዓ ም አዲስ አበ ላይ ዝማንትም የፊታውራሪ ክሳ የሚል ማኅተሜ ጠፍቶብኝ ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ከሌባ እጅ ተገኝቶ ይኸው ማኅተም በአማኞች ፊት መጥረዱን በማክበር አስታውቃለሁ ።

ፊታውራሪ ክሳ መሸሻ ።

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ዮኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት [illegible]ንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕመምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን ባታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሣባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ባላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በቃመሙ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላይ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበ-ላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ፤

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም እምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ብዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፣ የልብ፤ የደረት፥ የጉበት፤ የኵላሊት ፣ የጕማት፥ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፤ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጐርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፤ የርሻ፤ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፮ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ. ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ፡ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርናዲ-ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

COGNAC SA E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማተክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
6me ANNÉE № 23

ሐሙስ ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 5 JIUN 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ደረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዡት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የድልድይ ምረቃ ።

የጃንሆይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽ እንደራሴ ከተባሉ ጀምረው አሳባቸው የኢትዮጵያን መንገድ ለማስተካከል ነበርና ከዚህም በንዱ ክፍል በጅማ መንገድ የታመኑ አገልጋያቸው አዛጋ ወርቅነህን ሹመዋቹዋልና ብዙ ጊዜ የደከሙበትን ምንገድ ይልቁንም የሚያስደንቀውን የአቃቂን ድልድይ ለማስመረቅ ጃንሆይን ከመኳንንቱ ጋራ ጠርተው ነበር። ጃንሆይም በተቀጠረው ሰዓት መጥተው ነበር፤አዛጋ ወርቅነህም ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ጋራ ያማረ ድንኳን አስተክለው ያማረ ያማረ ስጋጃ አስነጥፈው ጥሩ ጥሩ ወምበር ደርድረው በበጎች አምሳል የተሠራውን ብስኩትና ሽምፓኝ ደርድረው ለዓይን እጅግ አምሮ ይታይ ነበር ።

ከዚህ በኋላ አዛጋ ወርቅነህ ያቀረቡትን ዲስኩር ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ አነበቡ ። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በገንዘብና በሌላም ልዩ ልዩ ሀብት ከሌሎች አገሮች ብትበልጥ እንጂ አታንስም ። እስካሁንም ድረስ በርትተው ለሠሩና ለተሾሙት ሁሉ ሀብቷን ከመስጠት አላቋረጠችም ።

ነገር ግን ሀብት ማለት ሕዝቡ ተባብረው ሥራ ሠርተው (ማለት) አርሰው ነግደው ልዩ ልዩ የሆነ የጅ ሥራ ሠርተው የሚገኘው ገንዘብ ነው እንጂ ተሹሞ በግብር ምክንያት ብቻ የሚገኘው ገንዘብ ሀብት አይባልም ። ይኸውም እንኳን ቢገኝ ተሹመው ለሚገዙ ለጥቂቶች ጌቶች ብቻ ነው እንጂ፤ ለብዙዎች ለሀገራችን ሕዝብ ሁሉ አይሆንም ።

ደግሞ ያገር ሕዝብ እሸሉ እያረሰ እሸሉ እየነገደ እሸሉም ልዩ ልዩ የሆነ የጅ ሥራ በያይነቱ እየሠራ ለመንግሥትም የሚገባውን እየሰጠ የሀገሩን ሀብት ካላገኘና ካልበለጠገ መንግሥት በነዚህ በጥቂቶች ሹሞች ሀብት ብቻ ልትጠነክርና ልትኖር አትችልም ።

የአውሮፓ መንግሥትም እንደሰማነውና ባይናችንም እንዳየነው ፥ ላገራቸው የተደላደለ ደንብ አውጥተው ሕዝባቸውን አሳምረው ከስተዳደሩ በኋላ አልፈው ተርፈው አሜሪካንን ያህል ለብቻው የተለየ ፩ ዓለም አቅንተው ፤ ደግሞ ሌላውንም በአፍሪካና በእስያ ክፍሎች ያለውን ሕዝብ ለማሠልጠንና ለማሰልጠኛ የደረሱት ፤ ሀብታሙና ድኃው ተባብረው ከመንግሥታት ጋራ ተማምነውና ተዋውለው ገንዘባቸውን አዋጥተው ትልልቅ ሥራ እርሻ ንግድ የጅ ሥራ ይኸንንም የመሰለ ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው የሚጠቅም እያሰፉ ከመተባበራቸውና ከመተማመናቸው የተነሣ መንግሥታቸውን አፅንተው ሕዝባቸውን አበርክተው ለሌላውም መግንሥትና ሕዝብ የሚጠቅሙ ሆኑ ።

ክቡራን የኢትዮጵያ መኳንንቶች ፤

እኛም በተሰጠን ዕውቀት ከዚህ በላይ እንደተጻፈው እርስ በርሳችን ብንተባበርና ከመንግሥታችንም ጋራ ብንተማመንና ገንዘባችንን እያዋጣን ከመንግሥታት ጋራ እየተዋዋልን ዋና ዋና ሥራ አቁመን ብንሠራ ጥቅሙ መዠመሪያ ለራሳችንና ለልጆቻችን ነው ፪ኛ ለመግሥታችን ነው ። ፫ኛ በሥራው ውሥጥ ለሚያገለግሉ ላገራችን ድኆች ነው ። እንዲያውም ከሁሉ የሚበልጠው እስከ ልጅ ልጅ ስማችን በቁም ነገር መጠራቱ ነው ። አሁን እኛ ግፋ ቢል ፲ ፥ ፲፭ ፥ ፳ ፥ ፴ ዘመን ብንጨምር ነው ። ሥራችንና ስማችን ግን ከመንግሥታችንና ከሕዝባችን ጋራ እስከ ዓለም ፍጻሜ ፀንቶ የሚኖር ነውና፤ ከሁሉ የሚበልጥ ልጆቻችን ማስተማር የተገባ ነገር ነው ።

እንሆ ዛሬ ያለፈው አልፎ ዘመናችንና ጊዜያችን ደግ የሆነ የተሻሻለ ይመስለኛል (ማለት)ንጉሣችን በዕውቀት የተ- ተከከሉ፥በአእምሮ የተደላደሉ፥ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ከፍታ የሚጥሩ ቸር ታጋሽ ናቸው።መኳንንቱም ንጉሣቸውን አክባሪዎች ለመንግሥታቸው ታዛገሮች ናቸው፥ ሕዝቡም እግዚአብሔርን ፈርተው በሃይማኖታቸው ፀንተው በጽኑ ሠርተው ለመን- ግሥታቸው ተገዝተው ኑዋሪዎች ናቸው ።

እንደዚህ ከሆነ አገረ ገዥዎች መኳንንቶችና መንግሥት ባንድነት መክሮ በርሻና በንግድ በማንኛውም የጅ ሥራ ሁሉ ሕዝብ የሚከስርበትን ትቶ ሕዝብና መንግሥት በአንት የሚ- ከብርበትን ደንብ አውጥቶ በአዋጅ አሰንቶ ለማስተዳደርና አገርን ለማስከበር የሚያስቸግር ጊዜ አይመስለኝም ።

ይኸ ከዚህ በላይ የጻፍሁት ቃል የየሁላችሁ ሐሳብና ምኞት እንደሆነ አውቃለሁ ። ነገር ግን ይኸነን የተጀመረ ሥራ ልታዩት ከፈቀዳችሁ ዘንድ ተፋጥኖ ያልተሠራበት ምክንያት ከገንዘብ ማነስ የተነሣ መሆኑን ብትረዱት በጥቂት ቀን ለማፋጠንና ለመሥራት እንድትተጉበት ስለ አመንሁ ነው።

ይኸም መንገድ ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ተሠርቶ ቢያልቅ ለሀገራችን የሚበቃ ሁኖ አይደለም ነገር ግን ይኸ የተጀመረው ከለቀ ሌላውን ለመጀመር የማይቻል ስለሆነ ነው ።

ሥራውም በ፲፱፻፳፩ ም በመጋቢት ወር ተጀመረ። ከከ- ተማው እስከ ትልቁ አቃቂ ደንጊያ እየተነጠፈ የተሠራው መንገድ አምስት ኪሎ ሜትር ነው። ቁመቱ ፭ሺ ሜትር ሲሆን ስፋቱ ደንጊያ የተነጠፈበት ፯ሜትር ነው ። ግራና ቀኝ በአፈር እስከተደለደለው ፰ሜትር ይሆናል ። ይኸውም አንድ ላይ ከከተማው እስከ ትልቁ አቃቂ አቅራቢያ ድረስ አርባ ሺ ሜትር ካሬ ነው።ደግሞ ከትልቁ አቃቂ እስከ ወጨጫ ማርያም በፈር ድልድል ተሠርቷል ።

ድልድዮችም አራት ትልልቅ ድልድዮች በጥርብ ደንጊያ እየሆኑ በቅስት ተሠርተዋል ፤ የቀረው ትንንሽ ወንዝ በዕንጨት ተ ሠርቷል ።

ለዚሁ ሥራ መጀመሪያ ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ሕዝ ቡን ለገዛ ጥቅሙ ለማደፋፈርና በጎ አርአያ ለማሳየት ሲሉ ገንዘባቸውን አውጥተው ተጀመረ ። ይኸም ውለታቸውና በጎ አድራጎታቸው እስከ ልጅ ልጅ ሐውልት ሁኖ ሲመሰገን እንዲኖር ጥርጥር የለውም ። ፪ኛ ለዚሁ ሥራ እርዳታ ገንዘ- ባቸውን የሰጡ ክቡር ራስ ከበደንና ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴን፥ ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴንና ክቡር ቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴን እናመሰግናቸዋለን ። በተለየ በብዙ ድካምና መታመን የመንገዱን ሥራ ከትንሹ አቃቂ እስከ ወጨጫ ያሠራልኝ አቶ መንገሻ ከፈላን አመሰግነዋለሁ ። አሁንም ለወደፊቱ ገንዘብ እየተጨመረና ማኅበርነቱን የሚፈቅዱ መኳንንቶችና ሀብታሞች ከልተጉበት ድካማችን ተበላ አጥቶ እንዳይቀር ለክቡርነታችሁ አሳስባለሁ።

ከ፲፱፻፳፩ ከመጋቢት ወር ዠምሮ ለጅማ መንገድ ሥራ የተቀበልነው ገንዘብ ገቢና ወጪው ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ነው ።

ከጃንሆይ ግምጃቤት	፺፰ሺ. ብር
ከማዘጋጃ ቤት	፳፭ሺ. ብር
ከቤተ መንግሥት ጓዳ	፲ሺ. ብር
ከራስ ከበደ	፭ሺ. ብር
ከደጃዝማች ገብረ ሥላሴ	፫ሺ. ብር
ከፊታውራሪ ዓምዴ	፪ሺ. ብር
ከቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ	፩ሺ. ብር
የጅማ መንገድ ገቢ	፯፻፶፬ ብር

የገቢ ድምር ፩፻፵፬ሺ.፯፻፶፬

ከዚሁ ለመንገዱ ሥራ በየክፍሉ የወጣ

የከሚዎን ማቆሚያ ቦታ የተገዛበት ።	፳፭ሺ.፯፻፲፬ ብር
በዚህ ቦታ ላይ ለቤትና ላጥር ሥራ	፱ሺ.፫፻፹፯ ብር
ለድልድዮች	፵፩ሺ.፩፻፴፰ ብር
ለመንገዱ ሥራ ለደንጊያና ለሙያተኛ	፵፭ሺ.፯፻፺፭ ብር
እቃና መሣሪያ የተገዛበት	፯ሺ.፫፻፵፱ ብር
የሠራተኞችቀለብ	፲፩ሺ.፯፻፳፪ ብር
ለልዩ ልዩ ጉዳይ ለመንገዱ ሥራ	፩ሺ.፪፻፳፩ ብር

የወጭ ድምር ፩፻፵፪ሺ.፪፻፺፭

ከወጪው የተረፈ ተላላፊ ገንዘብ ፪ሺ.፫፻፶፱ብር ነው ።

ይኸነንም የተጀመረ ሥራ ለማየት ግርማዊነትዎ ፈቅዶ ስለ መጡልን በራሴም በሠራተኞቹም ስም ሁኝ የማቀርበው ምስጋናዬ ጥልቅ ነው

ክቡራን መኳንንቶችም የሥራውን መጀመር ሰምተው፥ ዶስ ብሏቸውና ግርማዊነትዎን አክብረው ስለ መጡልን የተ- ለየ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር

ተነቦም ሲጨረስ ሦስት ጊዜ ተጨበጨበ ። ከዚህም በኋላ የነበሩት መኳንንት ለመንገዱ እርዳታ የሚሆን ገንዘብ ሰጡ ። የመኳንንቱም ስምና እርዳታቸው ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው።

ራስ ኃይሉ	፳ሺ. ብር
ደጃዝማች ብሩ	፲ሺ. ብር
ልዑል አስፋ ወሰን	፲ሺ. ብር
እራ ንጉሥ አረጋይ	፫ሺ. ብር
ደጃዝማች አበራ ተድላ	፭ሺ. ብር
ሊጋባ ወዳጆ	፪ሺ. ብር
ፊታውራሪ ታፈሰ	፩ሺ. ብር
ፊታውራሪ ዓሥራት	፩ሺ. ብር
ፊታውራሪ ጣሰው	፩ሺ. ብር
ቀኛዝማች ቅፍረ ሥላሴ	፪ሺ. ብር
ባላምባራስ ቸርነት	፻ ብር
ልጅ በልሁ	፻ ብር

አቶ ተሰማ እሸቴ ፲፭ሺ.ዙርያ ሜትር የሚ- ሆን ጅማ የከተማ ቦታቸውን ለከሚዎን መቋሚያ ሰጡና ጃንሆይም ችግራቸውን ስላወቁ ይገመት አሉ።ከዚህ በኋላ በሸምጋች ተመረቀና ጃንሆይ ተነሡ መንገዱም እድግ መልክም

ነው። ይልቁንም የተራራው አከፋፈል በጅቡቲ ከአየናቸው ተራሮች ክፍል አንደኛውን ክፍል ይመስላል።ይኸም መንገድ ደኅና ቢፈጸም ለብዙ ሰው ታላቅ ደስታ ነውና የተጀመረውን በደኅና ለመጨረስ እንዲያበቃልን ለንጉሣችን ዕድሜ መለመን ይገባናል ። ለአዛጋር ወርቅነህም ኀይልና ብርታት ከጤና ጋራ ይስጥልን አሜን ።

ጊዜው ስለ መሸ ያልተነበበ የሠራተኞች ዲስኩር

መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እውነተኛ መንገድ እኔ ነኝ ። በኔ መንገድነት ካልሔዳችሁ ወደ አብ አትደርሱም ። መንግሥቱ ለማየት አትገቡም ይላል ።

ያለ መንገድ ከሰቡበት ለመድረስና አንዳች ሥራ ለመሥራት እንዳይቻል ሲያጠይቅ፤ባለቤቱ ራሱን በመንገድ መስሎ ተናገረ።

እውነት ነው ስንኳን ኢትዮጵያን የሚያህል መንግሥት ሥራና፤ ያንድ ገበር መሬት እንኳ ቢሆን፤ ያለመንገድ አንዳች ለማድረግ እንዳይቻል፤ በሰው ሁሉ ልቡና የተረዳ ነገር ነው። ያለም ነገሥታትም ሀገራቸውን ያሰፉ ፤ ጠላታቸውን ያሸነፉ ። ሀብታቸው ያደገ፤ ሕዝባቸው የበለጠገ፥ ሥራቸው የተፋጠነ፤ መንግሥታቸው የገነነ ። የሠረገላና የምድር ባቡር መንገድ አብዝተው ከሠሩ ወዲህ መሆኑን ፤ ታሪካቸው ይነግራል፤ ሥራቸውም ይመሰክራል ።

በሀገራችንም በኢትዮጵያ፤ ከጅቡቲ እስከ አዲስ አበባ ፤ የምድር ባቡር መንገድ ከተሠራ ወዲህ፤ብዙ ሥራዎች እየተፋጠኑና እየተከናወኑ ሔደዋል ። በአዲስ አበባ ከተማም የዛሬ ፲ዓመትና ፳ዓመት፤ በየመንገዱ የነበረው ጭቃ ሕዝቡን ከመንገዱ እያስታጎለ ያለፈቃዱ ቴአትሮ ሲያጫውተው ይውል ነበር። አሁን ዛሬ እንደምናየው፤ ስንኳን በአቶሞቢል፤ በከብት የሚሔደው ይቀርና፤ እግረኛው እንኳ፤እሰበበት ደርሶ፤ በፍጥነት ተመላልሶ፤ ጉዳዩን ጨርሶ፤ መዋሉ፤ መንገዶች ደኅና ሁነው ከተሠሩ ወዲህ ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም፤ የተወደደች ሀገረዎ፤ ልማቷና ስፋቷ በትምህርት ቤቶችና፤ በመንገዶች መሠራት እንደሆነ ስለ ተረዱት፤የሚበልጠው ድካምዎ ወደነሱ እንዲያደላ እናውቃለን

ለሀገርዎና ለሕዝብዎም ጥልቅ የሆነ የተለየ ፍቅረዎን የገለጡባቸው ሥራዎች ብዙ ናቸው ። ነገር ግን፤ አሁን በየክፍላቸው ዘርዝረን ለመናገር ጊዜ የለንምና ይዘነው ወደአለ ወደ መንገዱ ሥራ እንመለሳለን ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ፥ እስከ ጐሬና እስከ ጋምቤላ ድረስ፥ አሁን በመዠመሪያ ፥ የካሚዎን መንገድ እንዲሠራ ። ኋላም ለምድር ባቡር ሐዲድ እንዲነጠፍበት ብለው ፥ ጥልቅ በሆነ ሐሳባቸው መርምረው ፥ በራሳቸው ስም አድርገው ውሉን ጨርሰው ከተዋዋሉ በኋላ። ንጉሣችን የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የማይፈልጉ ስለሆነ፥ የኢትዮጵያ መኳንንትና ሀብታሞች ፥ ሕዝቡም ሳይቀሩ ፥ በማኅበሩ ገብተው እንዲሠሩና ፥ ጥቅሙንም እንዲካፈሉ ሲሉ፤ ያደረጉልን ውለታ ፥ ከራሳቸው አብልጠው ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን እንዲወዱ፥ ያለጥርጥር ያስረዳናል ።

ሁለተኛም ያገራችን ሕዝብ ድፍረቱ ለጦርነትና ተላልፎ ለመሞት ነው እንጂ ፥ እንደዚህ ያለ መሠረትነት ያለው ፥ ለዘለዓለም የሚኖር ጥቅሙ እስከ ልጅ ልጅ የማያቋርጥ ሥራ ለመሥራት ፥ ከዚህ በፊት በሀገራችን አልተለመደም ነበርና ለገዛ ጥቅሙ ሕዝቡን ለማደፋፈር ሲሉ ፥ ከገንዘባቸው ዘጠና ስድስት ሺሕ ብር አውጥተው ሥራውን ማስዠመራቸው ብቻ የኑሮአችንን ክፍታ በጥቂት ቀን ለማሰደግ ፥ ቤዛዊ የሆነ መረነታቸው እንደተቻኰለ ይታያል ።

ሥራውም በክቡር አዛጋር ወርቅነህ ታማኝነት በ፲፱፻፳ ዓመተ ምሕረት ። በመጋቢት ወር ተገመረ ። መንገዱም ከከተማው አንሥቶ ፥ ይኸው ዓይናችን እንደሚያየው፥ እየተደለደለ፥ ዕጥፍ ድርብ እየሆነ ደንጊያ ተነጥፎበት ግራ ቀኙ የውኃው መንገድ ተጠርጎለት ፥ እስከ አቃቂ ማዶ ደርሷል ደንጊያም ያልተነጠፈበት በፊር የተደለደለው፥ ከአቃቂ ወዲያ ከአምስት ኪሎ ሜትር የሚበልጥ መንገድ ተሠርቷል ። ካሚዎንና ኦቶሞቢልም፥ እስከ አዋሽ እየሔዱ ፥ ለመንገዱ ሥራ የሚሆነውን ግዳጅ ይፈጽማል ።

ድልድዮችም ከከተማው እስከ ትልቁ አቃቂ ፥ ቀስተ ደመና እየመሰሉ፥ መሠረታቸውን እያጠነከሩ፥ ተሠርተዋል ። ይልቁንም ፥ በትልቁ አቃቂ ሙሴ ኪርያኮስ ፥ ከመሠረቱ ዓለት ጋራ ሥረጠጥ ሕንፃ አስመስለው የሠሩት ድልድይ አዋሽና ግቤን አጭቶ ሊያገባ ይደገማል ።

ሥራውም እስካሁን ዝግ ያለበት ምክንያት ፥ ጃንሆይ፥ የመንገዱን ሥራ ማኅበርነት ፥ ለሕዝብዎ ከፈቀዱ ወዲህ ፥ የምንቀበለው ገንዘብ ስላነሰብን ነው ። አሁን እንኳ ከቅርብ ቀን ወዲህ፥ ድልድዩንና የመንገዱን ሥራ ፥ ግርማዊነትዎ ሊጐበኙው ከፈቀዱ ዘንድ ፥ አብረው የመጡ መኳንንቶች፥ ክቡር ራስ ከበደና ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ።ክቡር ፊታውራሪ ዓምዴና ክቡር ቀኛዝማች ኀይለ ሥላሴ ገንዘብ ማውጣት እንጀመሩ፤ የቀሩትም መኳንንቶችና ሀብታሞች ከመስጠት ቸል ባይሉ፥ እስከ አሁን መንገዱ በደንጊያ እየተነጠፈ አዋሽ እንዲደርስና ድልድዩም እንዲዠመር፥ ጥርጥር የለውም ነበር ።

ነገር ግን ክቡር አዛጋር ወርቅነህ ፥ የዕርፌት ጊዜያቸውን ለድካም የለወጡላት ሀገራቸውን ለመርዳት ምንም ቢጣጣሩ፥ በቃሉ የሚሠራ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ፥ ያለገንዘብ ለመሥራት ባለመቻላቸው ፥ እጅግ እናዝናለን ።

ከ፲፱፻፳ ዓ ከመጋቢት ወር ዠምሮ።ለጅማ መንገድ ሥራ የተቀበልነው ገንዘብ፥ገቢና ወጪው፥ ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው ነው።

ከጃንሆይ ግምጃ ቤት	፺፮ ሺ
ከማዘጋጃ ቤት	፳፫ ሺ
ከቤተ መንግሥት ጓዳ	፲ ሺ
ከራስ ከበደ መንገሻ	፫ ሺ
ከደጃዝማች ገብረ ሥላሴ	፩ ሺ
ከፊታውራሪ ዓምዴ	፪ ሺ
ከቀኛዝማች ኀይለ ሥላሴ	፩ ሺ
ከጅማ መንገድ ገቢ ።	፮፻፳፬

የገቢ ድምር ። ፻፴፩ ሺ ፮፻፶፬

ከዚሁ ለመንገዱ ሥራ በየክፍሉ የወጣ ።

የካሚዎን ማቆሚያ ቦታ የተገዛበት	፳፭ሺ፯፻፲፬
በዚሁ ቦታ ላይ ለቤትና ላጥር ሥራ	፱ሺ፫፻፹፮
ለአምስቱ ድልድዮች ሥራ	፵፩ሺ፻፴፫
ለመንገዱ ሥራ ለደንጊያና ለሙያተኛ	፵፰ሺ፯፻፶፰
ዕቃና መሣሪያ ፡ ካሚዎኖችም ፡ የመሐንድሶችም መኪና የተገዛበት	፯ሺ፫፻፵፱
የሠራተኞች ቀለብ በየወሩ የሚሰጥ	፲፩ሺ፯፻፳፱
ለልዩ ልዩ ጉዳይ ፡ ለመንገዱ ሥራ	፩ሺ፱፻፳፩
የወጪ ድምር	፻፵፱ሺ፱፻፶፰

ከወጪ የተረፈው ተላላፊ ገንዘብ ፪ሺ፫፻፶፱ ብር ነው።

ይኸ ከዚህ በላይ በቍጥር ያመለከትነው ገንዘብ ሁሉ የጅማ መንገድ በቅርብ ቀን የሚከፍለው ዕዳው ነው፡ ማለት ከዚህ ቀደም በ፪ ዓመት ውሥጥ ለተሠራው ይኸን ገንዘብ ስለተበደረ ወደፊትም አብዝቶ ቢበደርና ሥራውን አፋጥኖ ቢጨርስ ላበደሩት ማኅበረተኞቹ በ፪በ፪ ዓመት እንዲከፍላቸው ቢታሰብ ተበድሮ ሥራውን ከሠራበት ቀን ልክ ሳይደርስ ዓሥር ዕጥፍ እያደረገ እንዲከፍላቸው አይጠረጠርም ። ይኸም ጥልቅ በሆነ በግርማዊነትዎ ሐሳብ ተመርምሮ የተመሠረተ ነገር ነው ።

አሁንም ክቡር አዛጋር ወርቅነህ በግርማዊነትዎ ትእዛዝ ከውጪ አገር ያመጧቸው መሐንድሶች ለሥራው ተዘጋጅተው ይጠብቃሉና ፡ ቤዛዊ የሆነ መሪነትዎን የሚከተሉ የኢትዮጵያ ክቡራን መኳንንቶችና ሀብታሞች ከግርማዊነትዎ ጋራ በትጋት እንዲፈጽሙት የታመኑ ናቸው ስንል ሙሉ ተስፋችንን እንገልጻለን ።

እኛም የግርማዊነትዎ ታዛገሮች የሆን ባሮችዎ ፤ በክቡር አዛገር ወርቅነህ ቃል » ጸሐፊ ፍኖቶ ለልዑል ፤ ወዓርዩ መጽያሕቶ ፡ መርቱዐ ኅበሩ » ተብለን ስንታዘዝ የሚሰማን ደስታ » ኢያስተርአየ ኅሡሬ ዘከመዝ (ንጉሥ) በውስተ ኵሉ እስራኤል ከሚለው ያደርሰናል ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ፡ ንጉሡ ሕያው ይሁን

ወልደ ጻድቅ ጋሺ ።

፬ተኛ ያቃቂ ድልድይ ምረቃ ።

በግንቦት ፳ ቀን ልዕልት ወይዘሮ መነን በዓለ ማርያምን ለማክበር ወደ አዲስ ዓለም ሔደው ነበር በ፳፩ኛው ቀን በዓሉን አክብረው ለካህናቱና ለተከተላቸው ሰው ግብር አድርገው ውለው አዛጋር ወርቅነህ ያሠሩትን ያቃቂን ድልድይ ለማስመረቅ አዛጋር ወርቅነህ ስለጠርዋቸው እመጣለሁ ብለው ተስፋ ሰጥተዋቸው ነበር ። የተቀጠረውም ቀን በግንቦት ፳፪ ነበርና ምንም ጭቃና ዝናም ቢሆን ተቀጠሮዬ አልቀርም ብለው ከአዲስ ዓለም መጥተው በዚያው በኩል ወደ አቃቂ ሔደው ነበር። ግን ልዕልት አይመጡም ብሎ ያልታመነ ሰው ለአዛጋር ወርቅነህ ስለ ነገራቸው አልነበሩምና የልዕልትን ወደአቃቂ መሔድ ሰምተው አዛጋር ወርቅነህ ወደአቃቂ ሲሔዱ ልዕልትም አቃቂ ደርሰው ሲመለሱ በመንገድ አገኟቸው ። የልዕልት ደግነትዎና ትሕትናዎ እጅግ ይበዛልና የአዛጋር ወርቅነህን ኀዘን አይተው በነጋው ደግሞ እንዲመጡላቸው ተስፋ ሰጥተዋቸው ነበርና የራስ ጉግሣን ባለቤት ወይዘሮ የሸሽ ወርቅን፡የደጃዝማች አምኑን ባለቤት ወይዘሮ ጽጌ ማርያምን፡ ሌሎችንም ወይዛዝር አስከትለው በግንቦት ፳፫ ቀን በ፲ሰዓት ወደ አቃቂ ሔደው አምሮ በተዘጋጀ ድንኳን ተቀመጡ። አዛጋር ወርቅነህም የሚከተለውን ዲስኩር አቅርበው ተነበበና ፫ጊዜ ተጨበጨበ። ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ግርማዊት እመቤታችን።

ይኸንን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሐሳቡና ትእዛዝ የተጀመረ ሥራ ለመጐብኘት ፈቃድዎ ሁኖ ተክቡራት ወይዛዝሮችዎ ጋር ስለመጡልን የማቀርበው ምስጋናዬ በፍጹም ደስታ ነው።

ክቡራት ወይዛዝሮችም የሥራውን አጀማመር በማየታቸው ፍጻሜውን እንዲመኙ እምናለሁና በግርማዊትነትዎ ፊት ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ።

በሀገራችን ልማድ እስካሁን ድረስ ሴት ወይዛዝሮች በንደዚህ ያለ በዋና በዋና ሥራ አይገቡም ነበር። ዛሬ ግን በግርማዊ ንጉሣችንና በግርማዊት እመቤታችን መሪነት፣ የሀገራችን ወይዛዝሮች ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ እንዲሠራልን ተስፋችን ፍጹም ነው።

ወንዶችና ሴቶች በማንኛውም ሥራ ሊመካከሩና ሊረዳዱ ይገባል ስለምን በወንዶች የሚገኘው ደስታ ለሴቶቹም እንዲደርሳቸው፣ መከራም ችግርም ቢሆን እደዚሁ ነውና በሥራ ሁሉ ሊመካከሩና ሊረዳዱ የተገባ ነገር ነው።

እግዚአብሔር እንደ ወንዶች የጕልበት ኃይል ባይሰጣቸው ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ረቂቅ መስማትና ትጉህ አእምሮ አላቸው። ለወንዶች ያልተገለጸ ምሥጢር በቶሎ ይገለጽላቸዋል፤ ይኸንንም በክርስቶስ ትንሣኤ እንረዳዋለን ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠንን መካሮችና ረዳቶች አማክረን ተረዳድተን ብንሠራ ብዙ እርዳታና ጥቅም እናገኛለን ። ነገር ግን ሴቶቻችንን ንቀንና አጥቅተን እኛ እናውቃለን በኃይላችን እንገዛለን ብለን የእኩልነት ነፃቸውን ብንነሣቸው ፤ ውርደቱና ጥቃቱ ለሀገራችንና ለልጆቻችን መሆኑ እርግጥ ሊሆን ነው። ይኸም በግርማዊ ንጉሣችንና በግርማዊት እመቤታችን ሐሳብ የታወቀ መሆኑ አይጠረጠርምና በቅርብ ቀን ሴቶቻችን የእኩልነት ነፃቸውን አግኝተው ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሚረዱ እንዲሆኑ ሙሉ ተስፋ አለን።

ትላንትና ግርማዊት ቀጠሮዎንአክብረው ሲመጡ በመላክተኛ መሳሳት እኛ ከዚህ ባለመገኘታችን በጣም ተጸጽቼ ፍጹም ይቅርታዎን እለምናለሁ።

ይኸ ሥራ ለጊዜው ጃንሆይ ከዘጠና ሺሕ የሚበልጥ ገንዘብ ሰጥተውኝ ተጀመረ ኋላም እንደ ሐሳቤ መቻኮልና እንደ ድካሜ ብዛት ሳይፋጠንልኝ የቀረ በገንዘብ ማነስ መሆኑን ስለተረዱት ከጃንሆይ ጋራ ግርማዊነታቸውን ተከትለው የመጡ መኳንንቶች በብዙ ገንዘብ ተስፋ አስደርገውኛ ል።

በሀገራችን ብዙ የትምህርት ቤት ካልቆመ ፥ በያውራጃው መንገዱ ካልተሠራ የሀገሪቱን ልማትና ሥልጣኔ ለማግኘት ሽቶ የማይቻል ነገር ነው።እንደዛሬው አኳኋን የገንዘባችን መ-ፎከስ የወጪው የንግድ ገንዘባችን (ዕቃችን) ማነስ የሚያስፈራ ነገር መሆኑን ማሰብ ይገባናል ።

አገራችን ብዙ ሀብታምና ለምለም ሁና ሳለች ከራሷ የተረፋትን ወደ ውጪ አገር በመሸጥ ፋንታ ከውጪ አገር እህል መሸመቷ በገር ውሥጥ የሥረገላ፤ የባቡር መንገድ በማጣቷ መሆኑን ያልተረዳው የለም ።

በየዳርአገራችን እህሉ ከሰው ተርፎ ለነቀዝ ሲፈስ፥ ማቃረቢያ መንገድ ከማጣታችን የተነሣ ሕዝባችን ሲቸገርብን ጊዜ መንገድ ከወደተሠራበት ከወደውጪ አገር ልንሸምት ግድ ይሆንብናል።

ይኸንም በግርማዊትነትዎ ፊት መናገሬ ፤ ለሀገርዎና ለሕዝብዎ ጥቅም ሲሉ በገንዘብዎ የትምርት ቤት እንዲቆሙ ስለአወቅሁ ተከታዩ የመንገድ ሥራ መሆኑን ምንም ግርማዊትነትዎ቉ ቢረዳው እኔም እንዳመለክት ግድ ስለሆነብኝ ነው።

ነገር ግን ይኸ ሁሉ ሥራ መታሰቡና መጀመሩ በግርማዊ ንጉሣችንና በግርማዊት እመቤታችን መሪነት ስለሆነ ይኸ የምንመኘው ነገር ሁሉ በቅርብ ቀን እንዲፈጸምና ደስታችንን እንድናይ ። ፀተኛም ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ለግርማዊት እመቤታችን ረጅም ዕድሜና ሙሉ ጤና ከሕዝባቸውና ከመንግሥታቸው ጋራ ይስጥልን እያልን ፈጣሪያችንን በመለመን ደስታችንን እንገልጻለን ። ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

ታማኝዎ አዛጋር ወ.ቅነህ።

ከዚህ በኋላ የሻይ ግብዣ ሆነና በሽምፓኝ ተመራርቀው ልዕልት ተነሡ።

ያልታሰበ ጉዳት

በ፳፪ ግንቦት ይመር አዲሰ የሚባል ነጂ በቍጥር ፫፻፰ በአቶመቢልወደለጋርከሚወስደው መንገድ ላይ ገብረ ጊዮርጊስ የሚባለውን የከምቤታ ሰው ስላስዳጠ ።

በዚህም ቀን ተክለ ዮሐንስ የሚባል ነጂ ሁል ጊዜ ገነት የምትባለዋን የልጅ ግዛው በላይነህን አገልጋይ ወደጃን ሜዳ በሚወስደው መንገድ ላይ በአቶመቢል ስላስዳጠ እነዚህ ሁለቱ አቶመቢል ነጂዎች የደምቡን ፍርድ አስቲቀበሉ ድረስ በአቶመቢል አካሔድ መጠባበቂያ ቢሮ በኍል ተይዘው ከታሠሩ በኋላ ቍስለኞቹ በሆስፒታል ገብተው ሲታከሙ ቈይ-ተዋል ።

እንደዚህ የመሰለውን ድንገተኛ አደጋ ስለሚያደርጉ ነጅዎችና በግርም ሆነ ወይም በበቅሎ ስለሚተላለፉ ሰዎች መጠንቀቂያ እዲሆናቸው ተብለው ከዚህ ቀደም በየጊዜው የተነገሩትን የደንብና የማስታወቂያ ቃሎች ሁለቱም ወገኖች ሳይዘነጉ አስተዋይ ቢሆኑ ይህን ከመሰለው ካልታሰበው ጉዳት እንደማይደርሱ ሁነው ይጠበቁ ስንል እናሳስባለን ።

፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት ግንቦት ፳፬ ቀን እሑድ የበአተ ግብዕ በዓልና የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ምሳ ግብዣ ሁኖ ወዳጆቻቸው ክቡራን መምህራንና ሊቃውንት፥አለቆችም ነበሩ።ጥንተ ምእመናን መኳንንት ሐዲሳን አትክልት ንዋይ ኅሩይ የሆኑ የንዋየ ክርስቶስ ደቀ መዛሙ-ርት እዚያው ነበሩ ። የግብዣውን ነገር ጠንቅቆ ምስጋናውን ለመናገር ዓይነቱ ከመብዛቱ የተነሣ እንኳን ለሰሚው እኛም እዚያ የነበርነው ጣዕሙ በፍቅር እየሳበን ተመግበን ከመንፈ-ርዘገ በቀር ስልቱን ለመለየት አልቻንም ነበር ። ቸርነቱ የማያልቅ ጌታ የማቱሳላን ዕድሜ ለክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ዕድሜ በብዙው ሠጥቶልን ሁሉም በየተራው እየገባ ይቀመሰው እንጂ በግብዣም መክከል ያ ሁሉ መጠጥ ሲወርድ በጸጥታ አንዱ ከንዱ ምሥጢረ እግዚአብሔርን ከመጨዋወት በቀር ጫጫታ አልነበረም ።

እንዲህም መሆኑ የክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ አእምሮ ረቂቅ ስለ ሆነ የተጠሩትም አዋቂዎች ስለ ሆኑ በጥንቃቄ አንዱም አንዱም እየተራቀቀ ለብልህ አይነግሩ ላንበሳ አይ-መትሩ እያለ ከመጠጡ ኃይልና ከብላቴን ጌታ ዕውቀት የተነሣ በያጥቂቱ ነበር ። አለቆች በየሥራቸው መልካም ንግ-ግሮች ተናገሩ ። ከንዋየ ክርስቶስም ደቀ መዛሙርት አንዱ እኛ እንጠላው የነበረው የክርስቲያን ሃይማኖት ፍቅሩ እንደ ፋና በልባችን ሲበራ ዘመድ ዘመድ የሚለን ወገን በማጣት ልጆቻችን እስላም ይፋቀራል ምነው ክርስቲያን አይፈላለግ እያሉ ተስፋ እንዳይቈርጡ ስናዝን ከእልፍ አእላፋት የሚበ-ልጡ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ስለ ሰበሰቡን ፈጣሪያችንን አመሰገን ካለ በኋላ የሰው ሁሉ ከንፈር ጭብጨባውን አቀለጠ አንከረ ወተፋጸየ እንዲል ። እኔም ሥላሴ ቅኔ ።

ይቤሉክ አጋእዝት እግዚአ ኅሩይ ብላቴን ጌታ ።
በላዕሌነ ተነክረ አእምሮትከ እግዚአ
ጥበብከ ኀበ ፀንዐተነ ኢንክሃል አውሥአ
ለቀላየ ሜስ ጽሩይ ሰበ ቀላየ ወይን ጻውዖ
በቃለ አስረቢክ ተጋብአ
እስመ እግረ ትዕቢት ምዕረ ኢይመጽአ
ለልብክ ዘጻውሎስ ነሥአ

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስኤ ኃዘን ።

ሹም ሽር

በግንቦት ፳፬ ቀን ፊታውራሪ ዓምዴ ደጃዝማች ተብለው አን ጾኪያን ፥ ግድምን ፥ ኤፍራታን ፤ ለገሆራን ፥ ተሾሙ ።

ሊቀ መኳስ አምባቸው ደጃዝማች ተብለው ዋድላን ፥ ደላ-ንታን ። ተሾሙ።

ፊታውራሪ በየነ መርዕድ ደጃዝማች ተብለው ጐፋን በከ ን ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ክንፈ የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የነበሩት በመንግሥት ብላታ ተብለው የማረቆን ምስለኔነት ተሾሙ ።

ቢሾፍቱ በርሻ ምንስቴር ክፍል መልካም ሆቴል እህልና አትክልት በያይነቱ ለማብዛት መንግሥት አስበ የርሻ መኪ-

ናዎች ስለአሰናዳ ለዚሁ ሥራ ማከናወን የሚችሉ አቶ ተሰማ እሸቴ ዋና ሹም ልጅ ኃይሉ ማርያም ገዝሙ ምክትል ሹም፤ ሁነው ተሾሙ ። ይህም ሥራ አሁን ቀላል ቢመስል መንግሥት አስቦበታልና በሁለቱ ትጉሆች ሰዎች ብርታት ስመ ጥሩ ሥራ እንዲሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

የሁሉም ሹመት በሚገባ ስለሆነ የሰማ ሰው ሁሉ እጅጓ ደስ ብሎታል ሹመት ያዳብር ።

የሚያስደንቅ ነገር ።

ልጅ መልአኩ በያን የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእናታቸው ወገን የቅርብ ዘመድ ነው።እርሱም ከልጅነቱ ጀምሮ የእልፍኝ አሽከር ሁኖ እያገለገለ ይኖር ነበርና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብልህነቱንና የአእምሮውን መተከከል አይተው ለትምህርት ወደ አሜሪካ ዩናይትድ እስቴት ሰደውት ሲኖር አሁን በቅርብ በተደረገው በራስ ጉግሣ ወሌ መሸፈት ነገር የኢትዮጵያና የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጠላቶች የሆኑ ሰዎች ክፉ ክፉ የሐሰት ወሬ በጋዜጣ እየጻፉ ስለ አወጡ በነገሩ አዝኖ ለማናቸውም ቢሆን ወደ ኢትዮጵያ ሒጄ ነገሩን ሁሉ በዓይኔ ማየት ይሻለኛል ብሎ ለመምጣት ተነሣ።በሚነሣበትም ጊዜ።ሙሴ ጁልየን የሚባል የአሜሪካ ሰው ትውልዱ ከጥቍሮች ወገን የሆነ አይሮፕላን በመንዳት እጅግ የሠለጠነ ሰው ነበርና ንጉሠ ነገሥት ከፈረንሳዊ አገር ገዝተው ያመጡዋቸው አይሮፕላኖች መኖራቸውን ያውቅ ነበርና ምናልባት አይሮፕላን ነጂ ያነሰ እንደሆነ እንዲረዳ ብሎ ይዞት መጥቶ ነበር ።

ነገር ግን ልጅ መልአኩ በያን ይህን ሰው ይዞ አዲስ አበባ ሲደርስ የራስ ጉግሣ ወሌ ነገር ተጨርሶ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ተቀምጠው ስለደረሰ ኀዘኑ ወደ ደስታ ተለወጠለት።

ይህም ተአሜሪካ የመጣው ሰው የአይሮፕላን ነጂነት ልማድ እንዳለው ለማስረዳት ፈቃድ ከጃንሆይ ተቀብሎ በግንቦት ፳፯ ቀን በሥር ሰዓት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጃንሜዳ በአይሮፕላኑ ቤት ጳጳሳቱንና መኳንንቱን ግራና ቀኝ አድርገው ተቀምጠው ሲመለከቱ ይህ የአሜሪካ ሰው እንደጥላ የሚመስል በነፋስ የሚዘረጋ ጨርቅ በገመድ ከወገቡ ላይ አስሮ ትንሽ ነገር መስሎ ተአይሮፕላኑ ውሥጥ ብቅ አለ፤ ከዚህ በኋላ ጥቂት በጥቂት እያለ ወደ መሬት በወረደ ጊዜ ላየው ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አሰኝና ተጨበጨበለት ።

ከዚህ በኋላ ልጅ መልአኩ በያን የሚከተለውን ዲስኩር አንባበና ሦስት ጊዜ ተጨበጨበለት ።

ክቡራን መኳንንቶችና መሳፍንት ሆይ ።

ሙሴ ጁልየን የዛሬ ስድስት ዓመት ከሜሪካ ተነሥቶ ወደ አፍሪካ በአውሮፕላን በሮ ለመጣባት አውሮፕላን አሰናድቶ ቀዳማዊ ኢትዮጵያ ብሎ ሰይሟት ነበር ተብሎ ተጽፎአል ። በዚያውም አውሮፕላን መንገዱን ከጀመረ በኋላ ያምስት ሰዓት መንገድ ከአትላንቲክ ባሕር ከገባ በኋላ መኪናው ተበላሽቶበት ወድቆ አውሮፕላኑም ሰመጠ።እርሱ ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ ረዳቶች ደርሰው ነፍሱን አዳኑት ይባላል ።

ዛሬ በለፉት ወራቶች በኢትዮጵያ ውሥጥ ሁከት ተነሥቶአል ተብሎ በጋዜጣ እየበዛ ይወራ ነበር።አስፍተውም ይጽፉ ነበር። ይኸነንም እየሰማን ባሜሪካ የነበርን የግርማዊ ጃንሆይ ተማሪዎች ትልቅ ስጋት ገብቶን ነበር። ስለዚህም መቸም ዛሬ ለጊዜው የአውሮፕላን ነጂ ውድ መሆኑን እናውቃለንና አንድ ሰው ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ለመግስገስ ቍርጥ አደረግን፤ እኔውም ራሴ የዚህን ሰው ባገር መኖር እሰማ ነበረና አለበት አገር ድረስ ሒጄ ችግራችንን ባስረዳሁት ጊዜ ገኘት የመሰለች ቤቱንና ሚስቱንም ትቶ ለመሔድ ቅር ሳይለው ለጥቍሮች መከበሪያ ሁና የምትኖረውን መንግሥትንና ይህንኑም ብርሃን ሁኖ ኢትዮጵያን የሚመራውን ንጉሥ ለመርዳት ሒጄ ደሜን አፍስሼ ብሠዋላቸው ክብሬ ነውና ነገ ጧት ብትል አብሬህ ለመሔድ የተዘጋጀሁ ነኝ ብሎ ደስ በሚል ቃል አሰማኝ እነሆ እኔም ደስ ብሎኝ የወዳያን ሰዎች ፍቅር፤ ይልቁንም አሜሪካኖች ለኢትዮጵያ ያላቸውን ፍቅርና በዓለም ያሉ ጥቍሮችም የሚያስቡልንን ፍቅር የሚገልጽ መስሎ ስለታየኝ ይዤው መጣሁ ።

አሁን ግን አገር አማን ሁኖ ስላገኘን ደሙን ሊያፈስላቸው የነበሩትን ንጉሠ ነገሥትና መኳንንቶቻቸውን እንዲገናኝ ስለ ፈቀድን ግርማዊ ጃንሆይንና የአውሮፕላኑን ሹም ፈቃድ ለምነን ይኸነን የድፍረትና የዕውቀት ሥራውን እንዲያሳይ አስፈቀድን።ግርማዊም መጥተው እንዲያዩለት ፈቃድ ለመንን። ይኸውም ልመና ተሰጠን ።

ስለዚህም ይኸንን ሐሳብ አስበው በላኩት በግርማዊ ጃንሆይ ተማሪዎች ስም ሁኜ ለዚህ ለቸርነትዎ የሚገባ እንደበት ተናግሮ ሊቻል የማይበቃውን ምስጋና «ለግርማዊ ጃንሆይና ለመኳንንቶቻውም አቀርባለሁ ።

አሁን የዚህ ሰው ሚስት ባሏ ሥራውን ትቶ ወደዚህ በመምጣቱ ችግረኛ መሆንዋ የታወቀ ነውና ስለዚህ ግርማዊ ጃንሆይና ክቡራን መኳንንቶች የችሎታችሁን አድርጋችሁ ደስ እንድታሰኙት ይኸውም አድርጎት የማይረሳ ነውና ለብዙ ጊዜ መታሰቢያ ይሆናል ስል ላስታውሳችሁ እደፍራለሁ ።

መልአኩ በያን ።

ይህም ነገር ጃንሆይንና መኳንንቱን እጅግ ደስ ስላሰኘ ልሻንና ሺ ብር ከጃንሆይ ተሸለመ ።

የቀሩትም መኳንንት እንደተቻላቸው እርዳታቸውን ሰጡ። የገንዘቡን ልክና የሰዎቹን ስም በሚከተለው ቍጥር እናትማለን ።

ደግሞ ሙሴ ያዕቆብ የሚባል አንድ ጀግና ሰው እንደዚሁ በድፍረት ወረደ ።

ማስታወቂያ ።

ክቡር ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርት ያሳተሙት ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት የተባለ ብዙ ዕውቀት የሚሰጥ መጽሐፍ ዋጋው ሁለት ብር ተአላድ ነው ። በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታገኙታላችሁ ።



ዋጋው ፩ ብር

ማስታወቂያ ።

በጉምሩክ ቅጥር ውሥጥ ብዙ ጋዝና ቤንዚን ሌላም የእሳት አደጋ የሚአመጣ ብዙ ዕቃ ስለአለ እንደተቻለ ከእሳት አደጋ ለመጠንቀቅ በኋል በዚህ በቅጥር ውሥጥ ሲጋራ መጠጣት አጥብቆ ክልክል መሆኑን ለሰው ሁሉ እናስታውቃለን። በዚህ ቅጥር ውሥጥ ሲጋራ ሲጠጣ የተገኘ ሰው በመጀመሪያ አምስት ብር በሁለተኛ ኀሥር ብር በሦስተኛ ሐያ ብር ። በአራተኛ አርባ ብር መቀጮ ይከፍላል ።

፩ተኛ በሲጋራም መጠጣት ወይም በማናቸውም ምክንያት በጉምሩክ ውሥጥ የሳት አደጋ ያመጣ ሰው ሁሉ ስለ አለፊነቱ በሥርዓቱ መንገድ ጉምሩክ ይፈልገዋል።

ማስታወቂያ ።

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር የኒ ክልፉስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጕሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሣባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ፤

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባሩ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኸላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ከ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC SP.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
6me ANNÉE № 24

ሐሙስ ሰኔ ፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 12 JIUN 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዋጅ

በየጊዜው ነገር እየፈጠርህ ያልሆነ ወሬ ታወራለህ አሁንም በሐሰት ወሬ የተነሣ እርስ በርሳችን ደም ከመፋሰስ አገር ከመበደል ደረሰ ። ከእንግዲህ ወዲህ ግን እየሁ ብሎ የማይመሰክርበትን ሐሰት ነገር አውርቶ የተገኘ ፈጥሮ ያወራው የመንግሥት ነገር የሚነካ የሆነ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ መጠን ቅጣት ይፈረድበታል ። በሌላውም ነገር ሐሰት ወሬ ያወራው ባለቀሚስ የሆነ እንደሆነ ፴፫ ብር ። ያልተሾመ ሰው ቢሆን ፲፰ ብር መቀጫ እየከፈለ እኩሌታው ለከሳሹ ተሰጥቶ እኩሌታው ወደ መንግሥት ይግባ ።

ይህነንም መቀጫ መክፈል የሚያቅተው ሰው እንደ ገንዘቡ ግምት ታሥሮ ሥራ በመሥራት ይክፈል ።

ትከውን ሀገር እፍላገ ማይ ወሙሐዘ ማይ ወእለ ጸምዑ ይሑሩ ኀበ ማይ ወይስተዩ ዘእንበለ ወርቅ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሐሳብና ድካማቸው ሁሉ ሀገራችን ኢትዮጵያ በሥልጣኔና በመስማማት እንድትከናወንና እንድትከብር ስለሆነ በየጊዜው የትምህርት ቤት እያቆሙ ያድሳሉ።ይኸውም ሥልጣኔና መስማማት ጥቅምና ጉዳት የሚለየው በትምህርት ቤት ነውና አሁንም በቅርቡ በሐረር ከተማ ውሥጥ በልዑል ራስ መኰንን ስም መልክም የሆነ የሥልጣኔ ትምህርት ቤት ስላቆሙ የሀገሩ ሕዝብ ሁሉ የልዑል ራስ መኰንን ፍቅርና ውለታ አይረሰውም ና በደከሙበትና ባረፉበት ከተማ ለስማቸው መታሰቢያ የሚሆን የሥልጣኔ ተማሪቤት ስላቆሙልን ልጆቻችንም የልዑል ራስ መኰንንን ስም ለዘለዓለም አይረሱብንም በማለት በጣም ደስ ብሎታል የተማሪቤቱም ዋና ዲሬክተር ሙሴ ሞሬል የተማሪ ቤቱን ሕግ በፍጥነት አከናውነው አስተማሪዎችንም በየክፍሉ አድርገው እሳቸውም በ፫ኛው ክፍል ሁነው ሲያስተምሩ እጅግ ደስ ያሰኛሉ ትምርታቸውም መልክም ስለሆነ ብዙ ተማሪዎች ተሰብስበዋል ።

ጃንሆይም አስተማሪዎቹ በማነኛውም ነገር ችግር እንዳያገኛቸው የሐረር ጉምሩክ ዲሬክተር አቶ እሸቴን ረዳትና አስታዋሽ አድርገውላቸው በየጊዜው እየሔዱ የጐደለውን ነገር በፍጥነት ስለሚረድዋቸው አስተማሪዎቹ በጣም አመሰግነዋል ።

ተማሪዎቹም እናንት ዕድለኞች በኛ ጊዜ እንደነበረው ትምርት በችግርና በስደት ሳትጐለሉ በየተወለዳችሁበት አገር የተማሪቤት እያቆሙ ለሚያስቡላችሁ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ዕድሜ ይስጥልን እያላችሁ በጸሎታችሁና

ብትምህርታችሁ መጀመሪያና መጨረሻ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር አመልክቱ ።

ባለፉት ዘመናት የሀገራችንን ትምህርት የተማሩት ጥቂቶች ያልተማሩት ብዙዎች የሆንበት ምክንያት ስደትና ችግር ስለሚያሳቀቀን ነውና ይህቺን የዕድል ጊዜያችሁን በስንፍና ሳታሳልፉ በትጋት እየተማራችሁ ለፍሬ እንድትበቁ እበቃው። ሳትችሉሁ እያሉ ያነታቷቸዋል ።

ግንቦት ፲፪ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ ም ማክሰኞ በ፱ ሰዓት የሐረርን መኳንንቶች አስከተለው ክቡር ፊታውራሪ ገብረ ማርያምም ይህን ትምህርት ቤት ለመጐብኘት ሔዱ።

ገና የተማሪቤቱን ያጥር በር ገባ ሲሉ አይተው ዲሬክተሩ ሙሴ ገርዜፍ ሞሬል ከትምህርት ቤት ወጥተው እውጪ ቁመው ተቀብለዋቸው ወደ ራሳቸው ክፍል ወሰድዋቸው ።

ገናም እክፍሉ በር ሲደርሱ ተማሪወቹ ብድግ ብለው ቁመው እጅ ነሷቸው፤ ክቡር ፊታውራሪም ልጆቹ እንዲቀመጡ አድርገው እተሰናዳላቸው ወንበር ላይ ሔደው ተቀመጡ ።

በዚያን ጊዜ ሙሴ ገርዜፍ ሞሬል የተማሪወቹን ደብተር እያነሡ ያሳዩአቸው ጀመር አስተርጓሚውም አፊታውራሪ አጠገብ ቁመው እልጆቹ ደብተር ላይ የተጻፈውን እያነበቡ በአማርኛ ይፈቱላቸው ጀመሩ። ሁለት ሦስትም ደብተር እንዳዩ ከሙሴ ሞሬል ጋራ ሁነው እንደቆሙ የቀሩትን ሁለቱን ክፍሎች አይተው ተመልሰው አበታቸው ተቀመጡ። በዚያን ጊዜ ልጆቹ ሁሉ እሙሴ ሞሬል ክፍል ተሰብስበው ቀጥሎ ያለውን የምስጋና ቃል በሆሬ ጽዮን የሚባል ተማሪ አነበበላቸው

ክቡር ፊታውራሪ ሆይ

ከልዑል ራስ መኰንን ትምርት ቤት ያለነውን ወጣቶች ተማሪዎች ለማዬት ክቡድ ሥራዎን ትተው አክብረውና አፍቅረው በማዕርግና በሥርዓት እመሃከላችን በመገኘትዎ የድንቅና የብርቅ ደስታ ተመልተን ክቡር ሰውነትዎን ባንድ ልብና አሳብ በውሣጣዊም ፍቅር ተይዘ፥ ምስጋናችንን እናቀርባለን ።

ክቡር ፊታውራሪ ሆይ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ስለ ሐረር ወጣት ልጆች ጥቅም ብለው በልዑል ራስ መኰንን ስም ሰይመው ተማሪ ቤት ስላቆሙልን እኛ የበቃ ምስጋና ለማቅረብ አንችልምና ክቡር ፈቃድዎ ሁኖ ስለኛ የከበረ ምስጋና ለጃንሆይ እንዲያቀርቡልን እንለምንዎታለን ።

ደግሞ የሐረር ጉምርክ ዲሬክተር ክቡር አቶ እሹቴም በመልካም በልደረብነታቸው በየጊዜው ለሚጠይቁንና ለደከሙልን ሁሉ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደራሴ ፊት ቁመን ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን።እኛንም በትጋት የሚያስተምሩን የመምህራኖቻችንን ያገልግሎት ሥራቸውንና ድካማቸውን ክቡር ፊታውራሪ ስለ ጃንሆይ ሁነው እንዲሁ እልፍ እልፍ ያመቱንም ድካማቸውን መከር በደስታ እንዲያዩላቸው ተስፋ እናደርጋለን። ለኛም ለልዑል ራስ መኰንን ትምህርት ቤት ላለነው ወጣት ተማሪዎች ድጋፍ እንዲሆኑን ዕድሜና ሙሉ ጤንነት ስንመኝለዎት ባንድ ኅብር ሁነን ክቡር ፊታውራሪ ይኑሩ ክቡር ፊታውራሪ ረድኤታችን ይሁኑ እንላለን ብሎ እንባቢው ሲጨርስ ወስዶ ወረቀቱን ሰጣቸው ወረቀቱንም ተቀብለው ብድግ ብለው ቁመው ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ።

ክቡራን ልጆቼ ሆይ እንዲህ ያለች መልካም ዘመን ያደረሰችሁን አምላክ እያመሰገናችሁ ዕድሜና ጤና ሌት ቀን እናንተን ወደከፍተኛዋ ደረጃ ለማድረስ ለሚደክሙላችሁ ለንጉሠ ነገሥት ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መለመን አለባችሁ ።

እንደምታዩት ሁሉ እናንተ እንዳትጐዱባቸው ሲሉ አስተማሪዎች ከሩቅ አቅርበውላችኋልና ዛሬ ባባት በናታችሁ ሐሳብ ሳላችሁ ጠንክራችሁ እንድትማሩ አሳስባችኋለሁ ።

ዛሬ በትጋት የተማራችሁ እንደሆን ለኋላ እንጀራችሁ ክፍ ያለ አገራችሁንና መንግሥታችሁን አስከባሪዎች ትሆናላችሁ።

ወደፊትም በቶሎ በቶሎ እየመጣሁ አያችኋለሁ ብለው ሲቀመጡ ልጆቹ ሁሉ ባንድነት ኢትዮጵያ እናታችን ለዘለዓለም ትኑር ብለው አጨብጭበው ተደወለና ወጡ ።

ልጆቹም ሲወጡ ብዛታቸውን አይተው ክቡር ፊታውራሪ አድንቀው መምህራኖቹን ተሰነባብተው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

፩ኛ በኃይለ ሥላሴ የፈለቀ ውሀ ።
ሐረር ላይ ይፈሳል ለሀብታም ለድሀ ።
እንዳዲሀ ሞት የለም በወኃ ጥም ታሥሮ ።
በለጠጋው ነፍኑ ደሀው ተቸግሮ ።
፪ኛ በሐረር ከተማ ትልቅ ውኃ ፈልቆ ።
ምንኛ ሞኝ ነው የማይጠጣ ጠፋቆ ።
፫ኛ ዕድሜ ለንጉሡ ለልበ ብርሃን ።
እንዳንጐዳበት ለሚያስብልን ።
እርቀን ሳንሔድ መንገድ ሳይመታን ።
ሳይርበን ሳይጠማን ልብስ ሳያልቅብን ።
ደግሞም በሰው አገር ሞት ሳያስፈራን ።
አባት እናታችን ንብረት ተቀምጠን ።
እንማር እንግዲህ በጣም ጠንክረን ።
አምላክ ከነገሠው አሳቢያችነን ።
መንግሥቱን ያስፋለት ዕድሜ ይስጥልን ።
ከበት ከናት ይበልጥ ለሚደክምልን ።
ጨለማውን ሽሮ ላሳየን ብርሃን ።
እግዜር ፈጽምለት ጥልቅ ምኞቱን።
ብሎ ይፈጽማል አጭር ሐሳቡን ።

አበበ ገድል የ ት ጥ ሚ ሠ ሐረር ።

ስለ ጉምሩክ ጥቅም ።

ጉምሩክ ማለት የዓለም መጽሐፍ የመንግሥትና የሕዝብ ምሰሶ ማለት ነው፤ይኸውም ከብዙ በጥቂቱ ተከፍሎ የተለየ ዋና ዋና ስሙ ነው እንጂ የጥቅሙስ መንገድ ቢቈጠር በጣም ብዙነው

፩ኛ ጥቅሙ ማናቸውም የንግድ ዕቃ የሆነ ሁሉ ከቅጠል ጀምሮ እስከ ወርቅ፥ከዶሮ ጀምሮ እስከ ግመል ሲቀረጥ በትክክል ተቈጥሮ ተሰፍሮ ተመዝኖ ታሥር እንድ ከዚህም የሚቀል የዋጋ መለኪያ የሚሆን ሸረፍና ዕቃው እንዲ መወደዱና እንደመርከሱ ታስቦለት ሕዝቡም በግዛ ራሱ ፈርዶ

ይህ ለመንግሥት የሚገባ ነው ብሎ ያለ ጭቅጭቅ ዕንባና ግፍ ሳይቀላቀሉበት ወዶ የሚሰጠው ስለ ሆነ ይህ ለመንግሥት የፃማ ገንዘቡ በመሆኑ ነው

ሁለተኛ፥ ሕዝቡ በመንገዱም ባለመንገዱም ከቀረጥ በቀር ብመሬት ግብርና በዳኝነት በሌላም ምክንያት ሁሉ የወርና ያመት ግብር ሲል በመንግሥት ስም የሚያወጣው ገንዘብ በጣም ብዙ ነው።ነገር ግን በወርም ሁኖ በመት ገቢውን ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ ምኒስቴር ቤት ቢያመዛዝኑት ያውም ያዲስ አበባና የሐረር አውራጃ ብቻ ሁኖ የውነት ገንዘብ መሆኑን በኋላ ሲያስረዳን ከዓለም ገቢ ሁሉ የጉምሩክ ገቢ በልጦ ዕፅፍ ድርብ ሁኖ ይገኛል ። ካዲስ አበባና ከድሬ ዳዋ ጉምሩክ ብቻ፥ ይህን ያህል ጥቅም የተገኘበት በኢትዮጵያ መላው ያለውና የቀረጥ ነገር ሁሉ እንዳሁኑ እንደተጀመረውአያያዝ አዲስ አበባ ላይ በቆመው በንግድ ምኒስቴር እጅ ተጠቅልሎ ባንድ ፊት የሚሠራ ቢሆን ለደጉ አብነት መሪ ላገራቸው አክባሪ ለጃንሆይ ለቀዳማዊ ኃ ይ ለ ሥ ላ ሴ ሕዝባቸውን የሚያንፁበትና አገራቸውን የሚያሰፉበት እንዴት ዋና ዋናው ሐሳባቸውን የሚወስንላቸው የነበረ ይመስላችኋል።

ሦስተኛ ሕዝባቸውን ለማሠልጠንና ሥራቸውን ለማስፋት የነፃነትን መንገድ እየሰበኩ ደገኛውን በር ለከፈቱልን ለጃንሆይ ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ የተለየ ምስጋና ይገባቸዋል ። የሚመሰገኑበትም ምክንያት ባጭሩ ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ።ተዚህ ቀደም ከአውሮፓ ወደኢትዮጵያ የሚመጣ የነበረ የንግድ ዕቃ ሁሉ ምንም ዕቃው ከውጭ አገር ተሠርቶ የሚመጣ ቢሆን የተገዛበት ገንዘብና ቱጃሩና ነጋዴው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጭምር ስለሆነ ጉዳቱ ጉዳታችን ነበርና የዕቃው ባለቤትና ዕቃው የሚወርድበት አዲስ አበባ እያለ ባላገበቡ ድሬዳዋ ላይ እየተፈታ ሲቀረጥ ይልቅ ሕዝቡ ለመንግሥት ከሚሰጠው ገንዘብ በቀር ዕቃውን ከማውረድና ከማውጣት የተነሣ በየጉምሩክና በየለጋሩ ሲንገላታ በዚሁ ማኅል ግብዝ የሆነ የሚሰበርና የሚፈስ ዕቃ ብዙ ነበር ከዚህም በቀር ለየወኪሉና ለየሐማሉ ዋጋ ከማውጣት ጋራ ብርቱ ጉዳት ነበረበትና ይህንኑ የሕዝብ ጉዳት ተመልክተው ዕቃውን ያለስጋት አዲስ አበባ ድረስ በቀጥታ መጥቶለት ቱጃሩም ከቤቱ ሳይወጣ በአውሮፓ ደምብ ልክ ቀረጡን ሰጥቶ እንዲነግድ ስለ ፈጸሙለት ነው ። ከዚህም ሌላ በየዳር አገር ያለው ኬላና ገበያ ሁሉ የቀረጥ ደምብና ተመን አልተወሰነለትም ነበር በያንዳንዱ ኬላ ቀረጡ በጣም ከባድ ነው በንዳንዱም በኩል ዝቅተኛ ይሆናል ከዚህም የሚብሰው ነጋዴው አንድ ጊዜ አስቀርጫለሁ ብሎ ኃላፊ ወረቀቱን ይዞ ኬላ ለማለፍ አይችልም ። በየኬላው ቍጥር በግድ ማስቀረጥ ነበረበት። ከተነሣበት ኬላ ጀምሮ እስከ አዲስ አበባ ድረስ ትርፉን ለየበረኛው ሰጥቶ ከዋና ገንዘቤ ጕድሎብኝ ይሆን በማለት እየተጠራጠረና እየሰጋ አትርፋለሁ ባይ አጕዳይ ሁኖ ብዶ እጁን በመግባት ይህ ለሕዝብ ብርቱ ጉዳት መሆኑን ማንም አይስተውም ነበር ። ሥራው በቀጡ ስለ አልተተከለ ገንዘቡም እንደሚቀረጠው ልክ ለመንግሥት አይገባም ነበርና ለሕዝቡን ቀምበር አቅለውለታል።ይህም መሆኑ ልክ ስለ ወሰኑለት ነው ። ወደፊትም ደግነታቸውን የሚመሰክርላቸው ከሁኑ የሚበልጥ መንግሥትንና ሕዝብን አስተባብሮ የሚጠቅም ልዩ ልዩ የሆነ የሥልጣኔ ሐውልት ለማቆም ሐሰባቸው መሆኑን የሥራቸው ንድፍ ገልጦ ያስረዳል ። አራተኛ የገዛ ሕዝቡን መንግሥት ካላበለጠገው ማንም ሊያበለጥግለት አይችልምና በሀሳብና በጕልበት በምክርና በዕውቀት ምክንያት ከሚሰጡን ሀብታት ሁሉ በደረጃ ዝቅተኞች እንደንባል ሁለቱን እጅ ለመንግሥታችን ሚሰውን ለኀጃችን ብናደርግ እንኳን በመንግሥታችን። እጅ ያለውን ገንዘብ ዞረን አናጣውም። እስኪጋገርና እስኪሰናዳ እንጠብቃለን የማይባል የበሰለ እንጀራ ማለት ነው ለዚሁም ትንሽ ምሳሌ ያስረዳናል ከማዕድ በቀረብን ጊዜ በፋችን ጕርሰን ለመዋጥ እንደምናላምጠው በቤታችን ያሉ ገንዘባችን ነው ። ቀጥለን በእጃችን ቈርሰን ለመጕረስ የምናሰናዳው በመንግሥታችን እጅ ያለ ገንዘብ ነው። ይህ ከሆነ ሰው እንዴት ለገዛ ራሱ ሊለግም ይችላል አባቶች ሲተርቱ ምላጭ ከበጠ በምን ይበጡ ወህ ከነቀ በምን ይውጡ ይሉ ነበር ሕዝብ የተቸገረ እንደሆን ጉልበት ያለው ሠርቶ ጉልበት የሌለው ለምኖ ወትውቶ ከመንግሥቱ ይወስዳል። መንግሥትሳ የተቸገረ እንደሆን ከማን ይለምናል ለዚህ ማስረጃ ያለው አይመስለኝም።

አምስተኛ ማናቸውም ሕዝብ የሆነ ሁሉ በባሕርይ ረገድ ለሚሰጠው ሁሉ እደ እግዚአብሔርን በጸጋ ረገድ ለሚሰጠው ሁሉ እደ ንጉሥን ጠብቆ ሲኖር በጣም ያምርበታል። የእግዚአብሔርና የንጉሥን እጅ ጠብቆ መኖር ይገባል ። ማለት መቸውንም ሰው በትክክል ከሠራ የሥራውን ሚዛን ዋጋ(ደመወዙን) አያጣምና እግዚአብሔርና መንግሥት የማይፈቅድለትን ልዕልና በምኞትና በፈቲው ማደኑን ትቶ በዕድል ፈንታ ያገኛትሞያውን ሠርቶ እንዲበላበት የተወሰደች ሙያ ዋዕት አድርጎ አሰናድቶ ለመንግሥት ማቅረብ ነው ። እንደራሴ ሀሳብ ሁሉ አእምሮ ጠባይዕ ያለበትና የኢትዮጵያ ፍቅር ያደረበት ከሆነ ይህን ፈቃድ የማይወድ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም ። ነገር ግን አስጀምሮ ማስፈጸም የሚቻለው ላንዱ የባሕርይ አምላክ ብቻ ስለሆነ የተጀመረ ነፃነቷን ለፍጻሜ ያብቃው ብላችሁ ለምትወዱት ላዲሷ ሙሽራ አገራችሁ ለምትኑላት ስል በዝቅተኛው አቅሜ አሳስባችኋለሁ ።ጸጋየ ተክለ ሃይማኖት ዘብሔረ ትግሬ ። እስከሁን የቍጢ ገበያ ሠራተኛ

ስለ ሀገር ፍቅር ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ራሷን ችላ ለምታ ተስፋፍታ ሲትኖር የሚወዱ ብርሃንና ሰላምን ይከተላሉ ደግሞ ስለሀገራችን ፍቅር በየሐሳባችን እንድንጽፍ ጨለማን አስግደው ሌትና ቀኑን አስበው ለሀገራችን መልማያ ለሕዝባችን መጠቀሚያ ብርሃንና ሰላምን እንደ ኤሌትሪክ መቃሰቢያ ስላበሩልን እግዚአብሔር የማቱሳላን ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ይስጥልን ብለን እንለምናለን አሜን ።

መጀመሪያ የኢትዮጵያ መንግሥት ካለፈው ዘመን የበለጠ ወደፊት ሐገሩን ማዘጋጀትና ማሰናዳት እንደዓለም ደምብ ሁሉ ማስኬድ በብዙ ሐሳብ አለበት ።

ሁለተኛ፣ ኢትዮጵያ በላዋ ላይ ያለ ሕዝብ ተጐድቷልና የዱሮውን ሕግ ትቶ እቶ እንደጊዜው ብለው ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንደሰየሙት አዲስ ሕግ አውጥቶ በየአውራጃዋ ሁሉ በየዓመቱ እያሻሻሉ እንደ ዓለም ደምብ ማስኬድ ያስፈልጋታል ። ይህ የወትሮ ሕጋችን ግን እየዋዳን ይሄዳል እንጂ ሥልጣኔ እንዳይሰጠን የታወቀ ነው ። ነገር ግን ለሀገር ጥቅም የሚሆን ለሕዝብ የተስማማ እንዳይጐዳና እንዲሠለጥን አዲስ ሕግ አውጥተዋል ማለትን ከሰማን ቈይተናል። ይኸን የሰማነውን ሕግ በዙሪያ ያለ ሕዝብ ቢደርሰውና ቢገለጽለት ፀሐይ ለመ=ፊት ብርሃን እንደምትሰጥ እንዲሁ እንደዔት ደስ ባለው ነበር።

ሦስተኛ፣ ዘዙረው የውጭ አገር ያላዩና ያልተመለከቱ ከዚህ ላይ የተጻፈውን ቃል የሚቃወሙ አንድ አንድ ሰዎች ጦር ወርውረን ፈረስ ጋልበን እንኖራለን በማለት የራሳቸውን ጥቅም ያስባሉ እንጂ ሀገራችን ተስፋ ትበልጥግ ሕዝባችን ይሰልጥን መንግሥታችን ይክበር የሚሉ ጥቂቶች ናቸው ይመስሉኛል ። አሁንም የኢትዮጵያ መብራት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ሐሳባቸውን እንዲፈጽሙልን ተስፋ አድርገን እንጠብቃለን ።

፬ተኛ ፤ የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆይ ቀዳማዊ ጃንሆይ ባዲስ አበባ የተማሪ ቤት አቁመው ብርሃንና ሰላም ከደረጉ ቈይተዋል እንደዚህ ያለውን ጥቅም በኢትዮጵያ ዙሪ ያሉት ሀገረ ገዥ-ዎች በየክፍላቸው ዓሥር ዓሥር የተማሪ ቤት ቢያቆሙ እጅግ ቢያንስ አንድ ሽህ አይጠፋም ነበር ። ለዚሁም ለሚአቆሙት የተማሪ ቤት ችግር እንዳያገኛቸው የሚበቃ ገቢ አያጡም ። ይህም በሆነ ጊዜ ገቢውን እንገልጸዋለን እንኳንስ ለሕፃኖቻችን የተማሪ ቤት ለማቆሚያ ይቅርና መሠረቱ የጠና ትክል ሁነው የሚኖሩ ፋብሪኮች ለማቆም እንችላለን ። የኢትዮጵያ ልጆችም እንደ ፀሐይ ሙቀው እንደጨረቃ ደምቀው ጨለማውን አብ=ርተው የዕውቀቱን መንገድ ጠርገው ብርሃንና ሰላም ላቈዩን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለማገልገልና ለመርዳት ተዘጋጅተዋል ። ትንሹም ትልቁም የሀገር ፍቅር አድሮበት ለትምህርትና ለመልካሙ ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር በልቡናው ያሳድርበት ።

፭ተኛ፣ በየሀገሩ አውራጃ የትምህርት ቤት ከሚቆምበት ሁሉ እንደዛኒጋባ ቤት እየተሠሩ ከትምህርትም የተላለፉቸው ጐበዛዝት የጦር ሰልፍ እየተስተማሩ የጅ ሥራ ቢማሩ ለነሱም ጥቅም ነው ለመንግሥታችንም እርዳታ ነው በሰማይ ጠያር መብረሩ በባሕር መርከብ መንሳፈፉ በምድር ባቡር መሽከርከሩ ከዚህም የበለጠ ረቂቅ ሥራ ሁሉ መሠራቱ ከትምህርትና ከት-ዕግሥት የተነሣ ነው ። ትዕግሥት ያላቸው ሙሉ ሕይወት ያገኛሉ ትዕግሥት የሌላቸው ግን እንደዚሁ ሁነው ይቀራሉ።

፮ተኛ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ግን ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ዓለም ደምብ ሁሉ ካላገኘች እንደዚሁ በዋዛ በፈዛዛ በተጠየቅ ብተጠለቅ ባልብሺኝ ባተርሺኝ አትኖርም እንደምንሰማው ከለም በፊት የሠለጠነችው ከኋላ ቀርታ ቸል እያለች እየተጓደደች እስካሁን በመቈየቷ እናዝናለን ለዚሁ ሁሉ መድኃኒት እግዚ-አብሔር ቀብቶ ሠራዊት መርጦ የሰጠንን መንግሥታችንን ወደን እንደሌሎቹ ሁሉ አንድ ልብ ሁነን ብንረዳዳ ከብዙ ዕውቀትና ጥቅም እንደርሳለን።

፯ተኛ፣ አንድ አንዶች ሽለቆችና የሀገር ባላባቶች በኢ-ትዮጵያ ዙሪያ በየክፍላቸው ተሹመው ክብርና ሞገስ አግኝተው ሊሹን መልበሳቸው መንግሥታቸውን እየረዱ ሀገር እያሰፉ ደሀውን አለ ሁከት እንዲጠብቁ ነው እንጂ የሀገር ፍቅር ከማያውቁ ሰዎች ጋራ እየተስማሙ ሕዝቡን ለመጐዳት በየጊ-ዜው ሁከት (ሬቦሊሲዎ) እያደረጉ በሀገር ሌባና ወስላታ ማስነሣት ለኢትዮጵያ ጉዳት እንዲሆን አያውቁት ይሆንን ወይ ያለማሰብ።አሁንም ወደፊት ማሰብና መመልከት ያሳስባል ያለ-ሁከትና ያለድካም ያለሐሳብ የምትመጣበ ነን እናታችንን ማስ-ቀየማችን በጣም ይጐዳናል ። የኢትዮጵያ ወዳጆች ሆይ ሰው ሁኖ ተፈጥሮ የሀገር ፍቅር ካላደረበት የዲያብሎስ ጥገኛ መሆኑ አይጠረጠርም።የማይዘለቅ ምክር እየተመከረ ደሀው ፥ በየቤቱ እጅግ ተቸገረ ፥ አፍ ሲያርፍ ወዳጁን ያማል የሚሉት ነገር ቢያወጡት ቢያወርዱት ያለ አንተም አይሆን፥እስቲ ተመልከቱት ያለምን ትዳር ብዙ ዓመት አያልቅም አንድ ትንሽ ቃል ይኸ-ንን መርምሮ እንዳይጠብቀን ሐሰዊ መሢሖች አላርፍም አሉን እንደነሱ ሐሳብ እንደልቦናቸው ለሕዝብ ሕግ እንዳይቆም ነበር ፈቃዳቸው ሰነፍን ካልቀጡት ባለጌ ይሆናል ይኸን ሳና-ውቀው ምንያስጨንቀናል ጥንትም ቃል ነበረው መኰንን ቃኘው ያባቱን ጠባቂ ጠቅሎ ያዘው ።

ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ይህችን አጭር ቃል ለመጻፍ ያነሳሳኝ በኑሮዬ ዘወትር የውጭ አገር ጠረፍ ስላየሁ ነውና የሀገር ፍቅር ስላሳሰበኝ ነው እንጂ ይህ እንኳን ሥራዬ ሁኖ አይደለም የተሳተውን አርሙትሁ የጐደለውን ሞልታችሁ እንድታቃኑት ባማክበር እለምናለሁ ። ፊታውራሪ ፈንታ ወልደ ገብርኤል።

ስለ መኰንን ሥላሴ ሕንፃ

፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ጥር አንድቀን ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ሲሆን የእስክንድርያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ዮሐንስ ከጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ለመኰንን ሥላሴ ሕንፃ በተዘጋጀው በታ መሠረቱን ለመባረክ መጥተው ሳለ የመኰንን ሥላሴ ቀሳውስትና ዲያቆናት ከሊቃውንቱ ጋር የክብር ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ቆመው ፩፻እግዚኦታ ካደረሱ ብኋላ የእስክ=ንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ከጳጳሳቱ ጋር ሁነው ጸሎተ ቡራኬ አድርሰው መሠረቱን ባረኩ።ጊዜውም ፀሐይ ሳስ ለበ-ረከት ያህል ትንሽ ዝናም ዘነመ ይህም መደረጉ ፈቃደ እግዚ አብሔር ቢሆን ነው። ይህችም መኰንን ሥላሴ ወትከውን አሐ-ቲ ሀገር ምሥዋዖ ለእግዚአብሔር የተባለች ናት ። ይህም ሊታወቅ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የማያውቁ የእስክንድርያ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያ መጥተው መሠረቱን መ ባረካቸው እጅግ ያስደንቃል።ካህናቱም ለመኰንን ሥላሴ በተደረገ ው ክብር እጅግ ደስ አላቸው ቡራኬውንም ከጨረሱ በኋላ ከመሠረቱ ውሥጥ የሚደረገውን ወርቅ ባርከው ሐዲ-ስመሠረትኪ የሐትዎ ዕንቍ ክቡር አንቲ ውእቱ መንፈሳዊት ሀገር መኰንን ሥላሴ ንጽሕት ፀምር ዘኅረያ ፅባዖት ኀይለ ሥላሴ

ስለመኮንን ሥላሴ ሕንፃ (ዘይእዜ)

ለአዳም ሕንፃኪ ቀዳሚ ኵሉ።
መኮንን ሥላሴ ገነት ክልልት ሃይማኖት ድንጋሌ።
ፈጠሮ መቅደመ ኃይለ ሥላሴ ።
ካልዕ ዘኢይትማሰሎ ወዓዲ ቢረሌ ።
እመ ሕዝበ ሮሜ ፈትዉ ይርአይዎ እምሉዓሌ።
ወመሠረታ ዘዕንቍ ባሕርዩ ምሳሌ
እስመ ድኅረ ዓለም የኀልፍ እንዘ ቀድም ዓለም ሃሌ።
ወመሠረታ ዘዕንቍ ባሕርዩ ምሳሌ

መወድስ ።

ለጊዜ ሥጋዌ ሕንፃኪ መኮንን ሥላሴ ።
ዓይነ ፍጡራን አብርሃም ተመነየ ከመ ይርአያ።
ወለመሠረትኪ ጽዮን ዘእግዚአብሔር ኀረያ።
በአንጻረ ሮሜ ቤተ መቅደስ።
እምፈልፈለ ብዕሉ ጳውሎስ አርወያ።
ለወንጌለ ወንግሥት መሠረትኪ።
ኃይለ ሥላሴ ይሰብክ፡ እምጣነ ሐዲስ ሐዋርያ።
ንጹሓንሂ አእዳዊሁ ለኃይለ ሥላሴ ኬንያ ።
ካልዕተ ምሳሌ መሠረትኪ አሠነዩ እምኒቅያ
ወለሕንፃ ዚአኪ አሰቴር ዑዕፍተ ልብሰ ወርቅ ነያ
በኢዮሩሳሌም አዲስ አበባ አልቦ ዘይሜንያ ።

ብርሃን አልፍነህ ዘመኮንን ሥላሴ

ማስረጃ ።

በለፈው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ የአቃቂን ድልድይ ምረቃ ስንጽፍ የመጡትን ለመንገዱም እርዳታ የሰጡትን መኳንንት ስምና የገንዘቡን ቍጥር ጽፈን ነበር።ነገር ግን ከፍጥነት የተነሣ የተሳሳተውን እናስታውቃለን ።

የራስ ሥዩም መንገሻ	፳ሺ ብር
የፊታውራሪ ጣሰው	፪ሺ ብር
የቀኛዝማች ፍቅረሥላሴ	፩ሺ ብር

ነው እርዳታቸው

የከተማ ወሬ ።

በግንቦት ፳፱ ቀን ደጃዝማች ደስታ የከፋና ያውራጃዋ፡ የጉማ ገዢ ከባለቤታቸው ከልዕልት ወይዘሮ ተናኘወርቅ ጋራ በደኅና ወደ አዲስ አበባ ገቡ።በመጀመሪያ ከማንም ሰው ሳይገናኙ ወደመኻሰቢያ ቤት ገብተው ስለ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ሞት እጅግ አለቀሱ።ኀዘንተኞችም፤እያለቀሱ ተቀብ - ሏቸው ።

ቅን ፍርድ

ደግሞ በዚሁ ቀን ጃንሆይ የእሥር ችሎት አድርገው ነበር አባ ድንቁ (ባላታ ድንቁ) የሚባሉ ባሕታዊ በዑራኤል ቤተክርስቲያን የመቃብር ቤት ብዙ ጊዜ ይኖሩ ነበርና ብዙ ያትርሱኝ ገንዘብ እናገኝባቸዋልን መስሎአቸው ሌቦች ገድ- ለዋቸው በከንቲባ ነሲቡና በዘበኞች ብርታት ሌቦቹ ተይዘው ሲመረመሩ ከዘጌ ለአቤቱታ ወደ አዲስአበባ መጥተው የነበሩ የዘጌ ካህናት ከኒሁ ባሕታዊ ጐረቤት ሁነው ሰንብተው ነበሩና ከሌቦቹ አንዱ እነሱ ልከውን ገደልን ብሎ አሣሥርዋቸው ሰን ብተው እንደ ታሠሩ ከጃንሆይ ችሎት ቀረቡ ጃንሆይም በብርቱ ቢመረምርዋቸው እኛኒ ሁነን ነው እንጂ የመከርን እነሱ አልገቡ በትም ብለው መሰከሩ።ብዙዎች ምስክሮች ከመሰከሩላቸ ባንድ ምስክር አይያዙም ተገዝተው ይፈቱ ብለው ጃንሆይ ስለፈ ረዱላቸው ተገዝተው ተፈቱ።

ምሳሌ ።

አንድ ሰው በችግር ምክንያት ከጐጃም ወደ ጐንደር ስደት ሲሔዱ አፄ ቴዎድሮስን አገውና ሚጫ ከድተቸው በኃ- ይል አቸነፈው የተማረከውን ሁሉ በሰይፍ እንዲቀጣ አዝዘው በዘበኛ ሲአስነዱት ሰውዩው አልፌ እሔዳለሁ ሲሉ አሳስቶ ዘበኛው እውሥጥ አገባቸውና ከሬሳው ውሥጥ ገብተው የሞቱ መስለው ፫ ቀን ቈይተው ጠባቂዎች ሲሔዱ ከዚያ ወጥተው እንዲህ ብለው አለቀሱ ።

እንዲህን ክፉ ነው ሰው ከተቸገረ
ቤቱ ሲአባርረኝ ወድቄ ነበረ

አሁን እኒህ ሰዎች ዕድል አግኝተው የብርሃን ጊዜ ሁኖ በጥብቅ ባይመረመርላቸው እንደ ቀድሞ ዘመን ቢሆን በከንቱ ሊአልቁ ነበር።ነገር ግን በዘመናችን እንዲህ ያለ መርማሪ ዳኛ የሰጠን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ።

ም ስ ጋ ና

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ።
እስኪ አንድ ጊዜ ሰላምታ ላድርስ።
ለኃይለ ሥላሴ ለቀዳማዊው ንጉሥ ።
ብርሃን ፊቱን ወደኛ እንዲመልስ ።
ፀዳለ ምሕረቱ ደረስ እስከ አድማስ ።

ሥላሴ ።

ነፋሳተ ሶበ ነፍሑ ለመንግሥት ቤትከ ኢገፍዕዎ ፤ ዘተ- ውህበ ለከ ልቡና ኃይለ ሥላሴ ዳዊት ።
ለውእቱ እንዘ መሠረቱ ፍትሐ ጽድቅ ብርት ።
ኅፀንትከ ጥበብ እኮኑ ወእልሐቀተከ ትዕግሥት ።
ወመኑ ከማከ እምነገሥታት።
ኃይለ ሥላሴ ብርሃን ሰዳዴ ጽልመት ።
ከመ ትብራህ ለኵሉ ፍጥረት።

ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ

ሰቆቃወ ጐንደር ራሔል ምልእተ አእምሮ ።
ለለዕለቱ ሐዲስ ወለለዕለቱ እንግዳ ።
እምጣነ ደቂቃ ተቀትሉ ወኢኮንዋ ውሉዳ ።
ሶበ ነግሠ ብኪ የልማሎዴቅ ፍዳ ።
ወተከዕወ ከመ ማይ ደመ ሰማዕታት ኵሎሙ ዘኅበሬሁ ፀዓዳ ።
ድኅረ ኀልቀሂ መከራ ጐንደር ወአመ ተፈጸመ ዕዳ።
መጽአ ኃይለ ሥላሴ እምዘርአ ዳዊት ዘይሁዳ ።

ዘተኀጕለ ይርዳእ ወዘተገድፈ በዓውዳ ።
ወይሕንፅ ዘተመዝበረት ሀገረ ጐንደር ቤተ ሳይዳ ።
ይቤ አለቃ ገሠሠ ዘጐንደር

ለአስበ አሳሳቢ
ላስተውሎ አንባቢ

ሞዐ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ
ሥዩመ እግዚአብሔር
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ምሥጢሩ ሲረቀቀንቃኛው ያንተንሙያ
ወልደህ ጠቅል ስትል ያን ትልቅ ገበያ
በይኃለ ሥላሴ አወቅነው ማለፊያ
ጠቅል ጠቀለለ መከተ ብቻውን
ሊሠራ ተዘንቶ ማዕርግ ያለውን
እመኑት ይሠራል ጠቅል ያሰበውን
ሞኞች ብልህ ሁኑ ክፉዎች ደግ ሁኑ ተውት የቀረውን
ኑሮ መለያየት ክቶ አይቀርምና
ርቀቅ ያለው ጥበብ ትልቅ ድንቀኀርና
እያወቀ እምያውቅ የሰው ልጅ ነውና
ማሰብ ግን አይተውም ተፈጥሮው ነውና
እስቲ መለስብየ ላስብ ያለፈውን
ጊዜ ዋጋ እያጣ ባጕል የጠፋውን
መጸጸት ደካ ነው ማወቅ የሆነውን
እንዲአስጠነቅቀን ወደፊት መጭውን
ከንቱ ሰው በከንቱ ማዕርግ ይመኛል
ያለ መልካም ሥራ ክብረት የትገኛል
እኔ ይህን ስላልኩ ሰዎች ደወዱኛል
እኔ ይህን ስላልኩ ሰዎች ይጠሉኛል
ሳይቸግር መጨነቅ እጅግ ያሳዝናል
ሁሉን ተፈራማ ሰው እንዴት ይሆናል
ይሉኝታ የሚሉት መከን ስም አውቀናል
መዝነን ብናውቀው እጅግ ይጠቅመናል
ገና በልጅነት እርጅና መጥቶበት
ደግሞም አረጀሁ ሲል ልጅነት ደርሶበት
ሐሳብ ሲአበክነው ከተቀመጠበት
አዘንኩኝ ለሰው ልጅ ይህ ለደረሰበት
መጨነቅ መጠበብ እግዜር ባለው ሊሆን
አወይ ከንቱ ድካም ሥጋ ለበሽ መሆን
ሲመጣ የማያልፍ ሲአልፍ የማይመጣ ሲመስለን ዘላለም
ተመስገን ጠገብኩሽ ያላትኮ የለም እዩት ይችን ዓለም
አንድ ቀን አንድ ዓመት መቶ ዓመት ቢኖሩ
ያለ መልካም ሥራ የማን አገር ሰዎች በመፈጠር ከሩ?
መኖርም መሞት ነው መሞትም መኖር ነው
ለምናልፈው ዘመን ክብሩ ሥራችን ነው
የጊዜአችን ክብሩአ ከሆነ ሥራችን
በኃይለ ሥላሴ ተስፋ እርገን ሁላችን
ከንቱ ሞትም ይቅር መወላወላችን
ኢትዮጵያም ተፈሪ እናት አባታችን
ክብራችን ጌጣችን ልብሳችን ጕርሳችን
ጠቅል ባንድ ሐሳብ ለነፃነታችን
መስለህ የንቁ ሚዛን ለዚች ለርስታችን
እንድንኰራብህ ልጅ እስከ ልጃችን
ሰፊውን አጥብቤ ጠባቡን አስፍቼ የምናገራችሁ
ለጨዋታም አይደል ልብ እርጉ እባካችሁ
ለጊዜ ሥር የለው ሲሮጥ ታያላችሁ
ታለፈ ወዲያማ ምን ታደርጋላችሁ
አየጕድ ከንቱ ነው ጸጸት ዋጋ የለው
ተጣጥሮ መብለጥ ሳይበለጡ ነው ።
ተጣጥሮ መቅደም ሳይቀደሙ ነው
የሰው ድካም ፍሬው ለጊዜው ይኸው ነው። እጅግ አየሁ

ሹም ሽር ።

የዕቃ ቤትን የሽለቅነት በጅሮንድ ተብለው ቀኛዝማች ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ተሾሙ ።

የማፉድን የሽምበልነት ቀኛዝማች ነዋይ ተሾሙ ።

የአራድማን ሽምበልነት ግራዝማች አንድአርጌ ተሾሙ ።

ባሊንና አሽገዴን አዛዥ ደገፌ ተሾሙ ።

የባላምባራስ ገብረ መስቀልን የአጋፋሪዎች የሽምበልነት ግራዝማች ያረጋል ተሾሙ ።

የጭዋ ልጆችን የሽምበልነት ፊታውራሪ ደምሴ ያየሁ ይራድ ተሾሙ ።

ልጅ አስፋው ወልደ ጊዮርጊስ ቀድሞ በያዙት አገር ላይ ባላምባራስ ተባሉ ።

የባሽ ደስታን የሽምበልነት ዘበኛው ባሻ በላይነህ ተሹሙ ።

ቃለ በረከት ዘአለቃ ቀጸላ ።

ምሳሐ ደብረ ጽዮን ማለት በዚች ቀን በዕለተ እሑድ የሚደረግ የመንግሥተ ሰማያት መንፈሳዊ ምግብ ነው ። አሁንም ብላቴን ጌታ ከዕውቀታቸው ብዛት የተነሣ ይችን ምሳችንን በዕለተ እሑድ ስላደረጓት ቀን አስተባብረታልና ከምሳሐ ደብረ ጽዮን ጋራ አንድ ያድርጋት ። እኔም ከደስታዬ ብዛት የተነሣ ከዳዊት መዝሙር ፹፰ቍ ፰ ወአልዐልኩ ኅሩይየ እምሕዝብየ ብዬ ከሐዋርያት ሥራ ም ፱ ቍ ፲፰ እስመ ንዋየ ኅሩየ ረሰይክዎ ። ዳግም ም ፲ ቁ ፴፩ና ፴፰ አማነ ርኢኩ ከመ ኢያደሉ እግዚአብሔር ኃይለ ሥላሴ ለገጽ አላ ዘፈርሆ ወገብረ ጽድቀ ኅሩይ ውእቱ በቅድሚሁ ብዬ ሦስት የበረከት ቃል እናገራለሁ ። የዚህም ትርጓሜ ከወገኖቼ ይልቅ ኅሩይን ከፍ ከፍ አደረግሁት አበለጥሁት የተመረጠ ዕቃ አድርጌዋለሁና ። ኃይለ ሥላሴም ለሰው ፊት እንዳያደላ በውነት አወቅሁ እሱን የሚፈራው እውነት ሥራ የሚሠራ በሱ ዘንድ የተመረጠ ኅሩይ ነው እንጂ ማለት ነው ። በዚች ቀን የተሰበሰብን እኛም አንድ አንድ ሥራ እየያዝን መንግሥታችንን ለመርዳት እናስበለንና አባቶቻችን እስራኤል በግሬ ኅሩያን እንደተባሉ እኛም በኅሩይ ኅሩያን ለመባልና ለመመረጥ ያብቃን ስል ምርቃቴን አቀርባለሁ ።

የምክር ቃል ።

ሥልጥንናችን በሚጠቀመን በኩል ይሁን ።

የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት ኢትዮጵያ፥የሰውን ሥራ ለማየት አውሮፓ፥ክብር ማለት ጥበብ አገር ውሥጥ ስትጸድቅ ነው። እውቀትና ብረት ናቸው በዓለም ላይ ሰውን ጌታ ያደረጉ በሌላው አገር ያለ በኛም አገር አለ ።

በገራችን የድንጋይ ከሰል አለ ያንን ለማምጣት የብረት መንገድ ቢሠራ ከሣራውን ቶሎ ከፍሎ ብዙ ትርፍ ይገኝበት ነበር ። ሥራ ማለት ለመኪና ቀለብ የሚሆን ከገር ውሥጥ ሲገኝ ነው ።

በያመቱ በመላ ኢትዮጵያ የሚገኘው የንግድ ዕቃ ዳር ዳሩን ከሚሔደው በቀር አዲስ አበባ ድረስ የሚመጣው በከብት እየተጫነ ነው ። እነከሚዎን ምንም ቢበዙ እንደ ምድር ባብር አያገለግሉም ።

ስለ አዲስ አበባ ከተማ

ያዲስ አበባ በታ አፈሩ ቀላል ስለ ሆነ ዝናብ አይችል፥ ፀሐይ አይችል በበጋ አቧራ በክረምት ጭቃ ይሆናል ። አንድ አንድ በታ ድንጋያም ነው ። አንድ አንድ በታ ማለቂያ የሌለው አፈር ብቻ ነው ።

ከሁን ቀደም የተሠሩ የግንብ ቤቶች ተበላሽተዋል ። ከንግዲህ ወዲህ መሠረቱ ድንጋይ እየሆነ በጡብና በንጨት የሚሠሩ ቤቶች ደኅና ሳይሆኑ አይቀሩም፤ያዲስ አበባ ድንጋይ ክበድ ዓይነቱም ብዙ ነው ።

ያዲስ አበባ ከተማ እንደ ሰማይ ኮከብ ፍንጥቅጥቅ ያለ ስለሆነ ወኃና መብራት ስልክ ለመስጠት አይመችም ።

ከተማ ማለት እርስ በርሱ የተያያዘና የተቀራረበ ሲሆን ነው መሐንድሶች ስለ አዲስ አበባ ከተማ በብዙ ሊያስቡበት ይገባቸዋል ። ዓለሙ ሀብተ ሚከኤል።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር የኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ክጕሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ።የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፱ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሣባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ፤

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን ብሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የቍላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋታ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግፖና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኤይ።
አ በ ክ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር፤ ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
6me ANNÉE № 2

ሐሙስ ሰኔ ፲፪ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓም።
JEUDI 19 JIUN 1950

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir regner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Diréction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ፌዬብር ቴፎይድ ለሚባል በሽታ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ማመልከቻ ።

አዲስ አበባ ከገባሁ ካንድ ወር በኋላ አንድ በሽተኛ ከሌላም ቅልቅል በሽታ በብሮንሺት በሳምባ በኰላሊት በሽታ (ፌዬብር) ቴፎይድ) ተስቦ ታሞ ነበር ። ሁለተኛ ፤ እንደዚሁ በተስቦ በሽታ የታመመ ነበርና ይህን ሁሉ ስላየሁና ስለመረመርሁ ይህ በሽታ ሕዝብን እንዳያገኘው ስል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን አመለክታለሁ ።

ማናቸውም መንግሥት ሁሉ ይህ የተስቦ በሽታ ከሌሎች ሁሉ ጠንካራና የሚጋባ ስለሆነ ሕዝቡ ከዚህ አደገኛ በሽታ እንዲድን ሲል የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ሁሉ ያደርጋል ።

ይህ የተስቦ በሽታ ሁለት አይነት ነው ። አንደኛው ከውጪ መጥቶ የሚጋባ፤ሁለተኛው፤ከሀገር ውሥጥ የሚነሣ ነው ከውጪ ለሚጋባው በሽታ በሌላ ጊዜያት ቄይተን በረጂሙ ማስረጃ እንሰጣለን።ነገር ግን ከዚሁ አገር ለሚነሣው በሽታ ቀጥሎ እንደተጻፈው እናስረዳለን ።

ይህ የተስቦ በሽታ የሚነሣው ይልቁንም ከጕድጓድ ውኃ ከዝናብና ከያይነቱ አታክልት ምግብ ነው ።

መጀመርያ የጕድጓድ ውኃ ይህን በሽታ ያመጣል ማለታችን ተስቦ የታመመው ሰው አካላቱን የታጠበበትን ውኃ ሽንቱን ዓይነ ምድሩን ባንድ ጕድጓድ አከማችቶ ኖራ ሳያለብስ እንዲያው ሲለቀቅ ነው ። ከዚህ ባኋላ በዝናብ ጊዜያት ዝናቡ ይህነኙ ሁሉ ዕድፍ ጠርጎ ወደ ምድር ሲያገባው ከውኃ ጕድጓድ ጋራ ይቀላቀልና የተስቦው ኋላ እውኃው ውሥጥ ይክተትና ይበዛል ። ይህነንም ውኃ የጠጡት ሰዎች አካላታቸው ጠንካራ ካልሆነ ተስቦው ይይዛቸዋል ። ይኸውም በሽታ ከታክልት ይነሣል ያልነው በንደዚህ ያለ ውኃ ሲተከልና ሲጸድቅ አታክልቱ ወኃውን ሲስበው የበሽታው ትል እየተደባለቀ ስለሚጋባ ይህ አታክልት ሲበላ በሽታው በሰውነት ላይ ያድራል። አታክልቱን በወኃ እንኳ ብናጥበው በሽታው ከቶ አይለቅም።

ሁለተኛ፤ የዝናብ ወኃ የሚጠጡም ሰዎች ይኸው ተስቦ ይይዛቸዋል ፤ ለዚሁም ቀጥሎ ያለውን ማስረጃ እንሰጣለን ።

ተስቦ የታመመው አካላቱን የታጠበበትን ወኃ ሽንቱን ዓይነ ምድሩን ባንድ ጕድጓድ አከማችቶ ኖራ ሳያለብስ ቀርቶ ዝናብ ሲዘንብ ይህነን ጕድፍ በምድር ላይ ያሰራጨዋል።ካሰራጨውም በኋላ ይደርቃል፤ከደረቀ በኋላ ነፋስ ሲነፍስ በየግድግዳው በየቆርቆሮው ላይ እንደ አቧራ እየተነሣ ዓርፎ እንደገና ዝናብ ሲዘንብ የዝናብ ወኃ ተብሎ ከቆርቆሮ እየተደቀነ ይቀዳና ሲጠጣ ያን ጊዜ ወኃውን የጠጣ በዚህ በተስቦ በሽታ ይታመማል የተስቦም በሽታ የሚነሳው በእንደዚህ ያለ ምክንያት ነው።

ይህ በሽታ እንዳያገኝ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ።

፩ኛ ፤ በያመቱ የጕድጓዱን ወኃ ሁሉ በውሥጡ ያለውን ወኃ አውጥቶ ጠርጎ ጥቂት ኖራ ማድረግ ነው ። ወኃውን አፍልቶ መጠጣት ሰውነትን ይጐዳልና አፍልቶ ኦለ መጠጣት ነው ። ይህነንም ማለታችን ወኃው የተፈላ እንደሆነ በወኃው ውሥጥ ለሰውነት የሚስማማ ልዩ ልዩን ፍጥረታዊ ነገር ስለሚያጠፋው ነውና ሰውነት የሚጐዳው በዚህ ምክንያት ነው ። የዝናብ ወኃ የማይስማማው እንደ ተፈላ ወኃ አይነት ነውና ስንጠጣውም ከበድ ስለሆነ ለሰውነት አይስማማም ።

፪ኛ ፤ በያይነቱ ጐመን ጐመኑን አስቀድሞ ጥቂት ኖራ በወኃ ውሥጥ ነክሮ ማጠብ ነው ። ከዚህ በኋላ በተፈላ ቀዝቃዛ ወኃ መለቅለቅ ነው ።

ለዚህ በሽታ ዋና መጠንቀቂያ በአውሮፓ ሁሉ የተስቦ ክትባት ይደረጋል። ይህ ክትባት በሽታውን አያስነካም ማለት

አይደለም።ነገር ግን ኬትበት ከተደረገ በኋላ በሽታው ቢይዝ በቀላል ይቀራል አያስፈራም ማለት ነው። እንደ ቀላል (ግሪፕ) ይሆናል ።

ይህንን መጻፌ ሐኪምነት ያለው ሰው ከንደዚህ ያለ ፊደገኛ በሽተኛ ሕዝብ እንዲድን ለማስጠንቀቅ ነውና ወደፊትም ለልዩ ልዩ በሽታ ሁሉ እንደዚህ ያለ ምክር ባለ መሀልቸት በመልከሙ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እጽፋለሁ ።

ዶክተር ያኒ ከልፋስ ።

እናታችን ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዕሙቀትን እንብታ ብዙ ሕፃናት ወልዳ ትኖር ነበረ ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥት ዕውቀት ዓርበኛ በረሀ ደፋሪ ነበረና በንዳድ ምክንያት ሳል ተተክሎበት ልቡ ታማሚ ሽበተኛ ከቤት ዋይ ሁኖ ይኖር ነበር ። የወለደቻቸውም ልጆቹ ሁሉ እንደሱ ዓርበኞች በረሀ ደፋሪዎች ስለ ሆኑ ትምህርት የሚባል መሣሪያ ጋሻና ጦር አልነበራቸውምና የበረሀ አውሬ ሠልጥኖባቸው ይኖር ነበር ። እናታችን ኢትዮጵያ ግን ባሏ ንጉሠ ነገሥት ዕውቀት ሶስ ታመመበት እያዘነች ብዙ ጊዜ ስታስታምም ልጆችዋንም በጥንቃቄና በክብሬታ ስታሳድግ በፍጹም ትጋት ኖረች ። ከልጆችዋ አንዱ ቀዳማዊ ምኒልክ ከዕለታት አንድ ቀን እናቱን ንግሥተ ዓዜብን እያታችን ኢትዮጵያ ምን ሁናለች ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፡ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ፡ የሐዩ ወይሁብዎ እምወርቀ ዓረብ ተብሎ ትንቢት ተነግሮላታል እጆዋን ዘርግታ ከእግዚአብሔር ጋራ ትነጋገራለች ምን ያሳዝናታል ብሎ ጠየቃት። አባታችን ንጉሠ ነግሥት ዕውቀትን ያህል ሰው ታሞባት እሷ ያባዘነች ማን ይዘን ልጆችዋ ሁሉ ያባታቸውን በሽታ እያዩ የሷንም ኃዘን እየሰሙ ዝም ይሏታል ፤ ወደ ሐኪም ሒዶ መድኃኒት ፈልጎ ሕምዋቶ ባልዋን የሚያድንላት ብታጣ ነዋ ብላ ነገረችው። እሱም የማን አባት መድኃኒት አጥቶ ሊሞት ነው ብሎ እንደ ፍከራ እድርጎ ሲናገር ሰማችና አንተማ ከወደድህ ወዲያስ ወዲህስ ብለህ ብትፈልግለት መች መድኃኒት ታጣለት ነበር።ወዲያውስ የሐኪሙ የሰሎሞን ልጅ አልነበርከምን አለችውና ሌሊቱን ከዓይኑ እንቅልፍ ቢያጣ እኩለ ሌሊት ሳይሆን ተንሥቶ ስንቁን ደግሺልኝ ካሽከሮቼም መወደድና መራራት ልዕልናና ክብር እኒህ አራቱ ይከተሉኝና ሳይነጋብኝ እሔዳለሁ አላት ፤ እሷም የወደዳቸውን አሽከሮቹን አስነሥታ ለመድኃኒት የሚሆንና ከሐኪሙ ጋራ የሚነጋገርበት ብዙ ገንዘብ አሲዛ ሰደደችው ። እሱም የወደዳቸውን አሽከሮቹን አስከትሎ የሰጠችውን ገንዘብ እሲዞ ባሕሩን ምርምር ጥያቄ ክርክር መረዳት በሚባሉ መርከቦች ተሻግሮ በግስጋሴ ደረሰ፤ሐኪሙ በሮቅ ሲመላለስ መልኩን አይቶ ይህ ልጅ ከኔ ደም የተከፈለ ነው መልኩ እኔን ይመስላል ግባ ብሉት ብሎ አስገብቶ ምን አመጣህ ምን ሆንህ ብሎ ጠየቀው ። እሱም ዝቅ ብሎ ጫማውን ስሞ አዎን የወለድከኝ አባቴ አንተ ነህ የመጣሁበት ግን የናቴ አባት ንጉሠ ነገሥት ሰውቀት ይባላል የዓለም ሁሉ ገዢ ነው አንተም ሳታውቀው አትቀርም በረሀ ደፋሪ ነበረና በዚህ ምክንያት ሳል ተተክሎበት እቤት መዋል ከጀመረና ከታመመ ብዙ ቀን ሆነው። አሁን እኔ የመጣሁበት የዚህን የበሽታውን ነገር መድኃኒት ከእተ ቤት አይታጣምና ትሰጠኝ አለህ ብዬ ወዳንተ መጣሁ በሽታው በጣም የጠነከረ እንደ ሆነ ከሞት ያደርሰዋልና ድል ሳያደርገው መድኃኒቱን አሳይተህ ሕክምናውን አስተምረህ ትሰደኛለህ ብዬ ወዳንተ መጣሁ ብሎ ምርምርና ጥያቄ ክርክርና መረዳት በሚባሉ መርከቦች ጭኖ የወሰደውን ገንዘብ ከፊቱ አፈሰሰለት። ከዚህ በኋላ የምክር ገበታ ዘርግተው ጨዋታ ጀመሩ ።

ጨዋታው ካለቀ በኋላ እንግዲህ የመጣህበትን ላድርግልህ ልብህንና ዓይንህን አንድ አድርገህ የምነግርህን ሁሉ ጻፍ ብሎ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሚባል ብዕርና ምክር ሠናይት ለኵሉ ዘይገብራ የሚባል ቀለም ሰጠውና ይጽፍ ጀመረ።

መድኃኒቱን በታውቁት ነው እንጂ እንኳን ሞት ታሞ መዋል የለውም ነበረ። ንጽሐ ልብ የሚባል ቤት ሠርተህ ከዚያ አኑረህ ከበቶቹ ያገናኋቸው ከዓንት የቄዩ ዓሥር ዕፀዋት አሉ እነዚያን ምግብ አድርገህለት የኖረ እንደ ሆነ በነፍስም በሥጋም ሕያው ሁኖ ይኖራል ።በንዳድ ምክንያት ሳልተተክሎበት ልበ ታማሚ ሆነ ትላላለህ እንጂ በሽታው ዓይኑ ጭምር ነው አለውና ከዚህ በኋላ ስማቸውን እየለየ ያስጽፈው ጀመር

፩ኛ ኢታምልክ ባዕደ አምላከ ዘእንበሌየ ።
፪ኛ ኢትኩን ስማዐ በሐሰት ።
፫ኛ ኢትኅሥሥ ንዋየ ካልእከ ።
፬ኛ ኢትሑር ኀበ ብእሲተ ብእሲ ።
፭ኛ ኢትዘሙ ።
፮ኛ ኢትስርቅ ።
፯ኛ ኢትቅትል ነፍሰ ።
፰ኛ አፍቅር ቢጽከ ከመ ነፍስከ ።
፱ኛ አክብር አባከ ወእመከ ።
፲ኛ አክብር ሰንበቶ ለአምላክከ ።

መድኃኒቶቹ እኒህ ናቸው ሕክምናውን ግን ትጉህ ልቡናን ይዞ መኖር ነው ለዓይኑ ግን በኋለኛው ዘመን ደገኛው ብርሃን ይወጣል ከዚያ ቀጥለው ለሚነሡ ዓሩማን ነገሥታት ነው እንጂ ላንተም ለኔም አይሆንልንም ብሎ ነገረው። እሱም እነዚህን ዓሥር ዕፀዋት ከነስሌዳቸው ሰጠውና ይዞ መጥቶ ንጽሐ ልቡና ከሚባል ሕክምና ቤት አስቀምጦ በመልካም አድርጎ በፍጹም ትጋት ሲያክመው ኑሮ ሕይወት አግኝቶ ወዲያና ወዲህ መመላለስ ከጀመረ በኋላ ውስተ ገነተ ትፍሥሕት ብሔረ አግዓዚ ኀበ አልበ ደዌ ወአልበ ሕማም በምትባል ከተማ አኑሮት ወደ ሩቅ አገር ሔደ ። ዕውቀትም ከዚያው ከኖረው ከተማ ሁኖ ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ እማንቱ ይምርሐኒ ወይሰዳኒ ደብረ መቅደስከ እያለ ብዙ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኖረ ።

ደገኛው ብርሃን ከተገኘላቸው በኋላ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ በሺህ ፰፻ ፹፪ ዓመተ ምሕረት አባታቸውን ዕውቀትን ለመሸት መቻል በጎን መልካም ምግባርን። አስተዋይ ልቡናን ሰሚ ጆሮን ተመልካች ዓይንን እነዚህን አምስቱን አሽከሮቻቸውን ይዘው ተነሡ። አባታቸውን ዕውቀትን በሕይወት ከተማ

ተቀምጦ ቢያገኙት ክብረ ንግሥት አስበ ልዕልት። አዳር ቀና ከሚባል ጥጥ የተፈተለ የጥበብ ሸታ አሰርተው ነጭ ሀር ቀሚስና የተፈሪ ቅድ ሱሪ አሰፍተው አልብሰው አጽንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመዓዕ እግዚአብሔር የሚል ቃል የተጻፈበት የወርቅ ዘንግ አሲዘው ሲያመጡት አሽከሮቻቸው እነመቻል በጎ፥ እነመልከም ምግባር፥ እነ አስተዋይ ልቡና፥እነሰሚ ጆሮ፥እነተመልካች ዓይን ሽበዬ አረሰጋው ሽበ አሰምሱምና ይዘሁልኝና። አዲስ አበባ ያብባል ገና አዲስ አበባ የዕውቀት ከታማ እያሰኙ አምጥተው ከተማቸውን አዲስ አበባ ብለው ስም ሰይመውት ተመሀሩ ገቢረ ጽድቅ አለ ትንብሩ ውስተ ዓለም የሚባል አደራሽ ሠርተውለት አባታቸው ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ሔዱበት አገር ሔዱ ።

ከዚህ በኋላ እናታችን ኢትዮጵያ ማሚቴ መነን ምጥቀ እያለች ማግም ድርም ታሠራ ጀመረች ።

በሺ፱፻፱ ዓ ም የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑል አልጋ ወራሽና እንደራሴ ባለሙሉ ሥልጣን ዕውቀት ተፈሪ ተባለ ። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ልጆች በኛማ ዘመን በኛማ ዘመን ሱሪያችን ተፈሪ ሸታችን መነን፥ በኛማ ዘመን ይሉ ጀመር ።

በኛማ ዘመን በኛማ ዘመን ሱሪያችን ተፈሪ ሸታችን መነን እያሉ በከበሮና በበገና በሙዚቃ በመሰንቆ ይጫወቱ ጀመሩ።

ከዚህም በኋላ ተቀማጮቹ ሕዝብ ሁሉ ትልቁም ትንሹም አየነው አየነው። ዕውቀት ተፈሪ ነው እያሉ ይቀበሉ ጀመሩ ።

እኔ ይህነን መጻፌ የማጥም ሥራ ነው ብዬ አይደለም አስቀድመው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ አስበውት የነበረውን ሥራ በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እየተስተካከለ መቆሙንና የድካማቸው ብዛት ለዓለሙ ሁሉ ጥቅም ስለ ሆነ ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ ፈቃዱ ሁኖ የጀመሩትን ሥራቸውን እንዲያስፈጽማቸውና የሰጠን አበባችን እንዳይረግፍብን ብርሃንዋን ዘርግታ የቆመች የኢትዮጵያ ፀሐይ እንዳትጨልምብን በእርስዎ ጊዜ ከቆመው ሥራ በከፊል ተናገርሁኝ እንጂ ምሥጢር አውቄ አማርኛ ጠንቅቄ አይደለም ። ዳግመኛም ይህን የጀመሩትን ሥራ ለመፈጸም አብቃቸው እኛንም ፍጻሜውን ለማየት አብቃን እያልን በየሥራችን ሁነን እንድንለምነው ይህ ሥራቸው ለዘለዓለም የማይጠፋ ሐውልት ነውና ፀንቶ እንዲኖር የሁላችን ፈቃድ እንደ ሆነ ምኞቴን ለክቡራን አንባቢዎች እገልጻለሁ ለጠፋውም ጥፋቴ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። ከዚህ የሚከተል ቃል አለ ለሚመጣው ይጻፋል ። የኢትዮጵያ መንግሥት ማኅተም ቤት ሠራተኛ ኃይሉ ዘውገ።

ስለ ተማሪዎችና ስለ ትምህርት ።

ታላቁ የኢትዮጵያ ግርማና የዕውቀት መሪአችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኢትዮጵያ ሀገራቸው በመሥራትና ባሠራር በትምህርትና ባሠለጣጠን ልክ እንደ አውሮፓ ሀገራቸው እንድትሠለጥንና እንድትከብር እያሉ ሲያስቡ መጀመሪያ ሀገራቸውን ለማሠልጠኛ አሠራር የሚያመለክትና የሚያስተምር መጀመሪያው ነገር ትምህርት መሆኑን ተረድተውት ከ፲፱፻፲፪ ዓመተ ምሕረት በፊት ጥቂቶችን ልጆች ወደ አሜሪካንና ወደ ኢጣሊያን ወደ ፈረንሳይና ወደ ቤልጊክ ወደ ምድረግብፅ ለትምህርት ልከው ሲያስተምሩ በ፲፱፻፲፮ ዓመተ ምሕረትም ከመሳፍንቶቻቸው ጋር አውሮፓ ሔደው የሀገሩን ሥልጣኔና የተማረውን በትጋት መማር የፋብሪካዎችን አበዛዝ ወሬ ከመስማትና ከማድነቅ ይልቅ ባይናቸው አይተውና ተረድተው ከተመለሱ ወዲህ የኢትዮጵያን ተማሪዎች ማነቃቃትና ትምህርት ቤቶችን ማሠራትና ማስፋትን ተማሪዎችንም በየጊዜው ማበረታታትና ሙሉ ተስፋ መስጠትን ጭምር እያደረጉ በትምህርታቸውም ወደ ከፍተኛው ደረጃ የደረሱትን እያዩና እየተመለከቱ በግብፅ በእስያ በፈረንሳይ በኢጣሊያ በቤልጊክ ባሜሪካ አገር መላክ ጀመሩ።ደግሞ ከወይዛዝሮችም ወገን መሪ እንዲሆኑ ልጃቸውን ልዕልት ፀሐይን ወይዘሮ ምስራች እምሩን ወይዘሮ እምሳሉ ኅሩይን ላኩ።ልጃቸውን መላካቸው የትምህርትን ነገር መውደዳቸውንና ማፍቀራቸውን ያስረዳል።ደግሞ እንደዚሁ ጌቶች ሁሉ ሀብታችን ይበቃቸዋል ሳይሉ ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ ለማስረዳ ብለው መሆኑ እርግጥ ነው።በኢትዮጵያ ሀገራችን ከንዳንዶች የደሃ ልጆች በተቀር ከመኳንንቶች ልጆች ሴቶቹ ቀርተው ወንዶቹም ምንም ያህል የተማሩት ቍጥራቸው አይታወቅም ። ይኸውም አባቶቻቸው ለልጆቻችን የኛ ገንዘብ ይበቃቸዋል እያሉ ልጆቻቸውን እያሳነፉ ልጆቹም በበቶቻቸው ንግግር እየሰነፉ መሆኑ አይጠረጠርም።ግን ፈላስፎች ሲናገሩ ከብዙ ገንዘብ ትንሽ ጥበብ ታከራለች ይላሉ እንደምን ቢሏቸውም ብዙ ገንዘብ ሲበሉትና ሲቸሩትም ያልቃል በኋላም ወደድኅነት ያደርሳል ትምህርትና ጥበብ ግን እስከ ጊዜ ሞት ድረስ የምታኰራ ናት ቢቸሯትም ቢያበድሯትም ከም ስመስገን በቀር የማታልቅ ናት ይባላል ።

ክቡራን የሀገሬ ወይዛዝርና መኳንንቶች ሆይ ለልጆቻችሁ ብዙ ገንዘብ እያከማቻችሁ ከማቄየትና ልጆቻችሁም ይኸንን ያልደከሙበትን ገንዘብ ባገኙ ጊዜ በቶሎ በታትነው አበካክነው ርስታችሁንም ሸሽጠው ስማችሁንም እንደነኝህ አሁን በአዲስ አበባ ላይ እንደምናያቸው አንዳንዶች የመኳንንት ልጆች ርስታቸውን እየሸጡና እያስያዙ በከንቱ እንደሚአጠፉ ሁሉ እንዳይሆኑባችሁ ያንን ለኋላ እምትአቈዩአቸውን ገንዘብ አሁኑ በሕይወታችሁ ሳላችሁ ወደ መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርት ቤት እየላካችኋቸው በመልካም መምህሮች ምክርና ተግሣፅ ገንዘባችሁን እየከፈላችሁ በጥበብ ትምህርት ብታስተምሯቸው ይሻላል ምንም ቢሆን ከተማሩ ስማችሁን ባልሆነ ቦታ አያስጠሩትም ርስታችሁንና ገንዘባችሁንም ከንቱን ነገር በማደንና ማፍቀር አያስቀሩትም ስል የኔን የታናሻችሁን ሐሳብ ላሳሰባችሁና ላመለከታችሁ ምኞቴን ጽፌላችኋለሁና በተወዳጅ ብርሃናችሁና በተስማማ ሰላማችሁ ተመልከቱት ። በቀለ ዘለቀ ።

ስለ ኢትዮጵያ ጀግኖች ።

የኢትዮጵያ ጀግኖች ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምረው ለኢትዮጵያ ለናታቸው ሲሉ ነፃነቷን ሲጠብቁ ጠላቶቻቸውን ሲአስጠግዱ ደማቸውን እያፈሰሱ በትጋትና በእምነት ይኸንን ክብራዊ ሥራ ሲፈጽሙ ሁል ጊዜ በታሪክ ይህችን ያገር ፍቅር ፓትሪአቲዝም የምትባለዋን ታላቅ ሥራ እንዳፀኑ እናነባለን

ደህች ያንበሰው መንግሥት በሌላ አገር ታሪክ ውሥጥ ያልተጻፉ ጀግኖች ልጆች እንደምታወጣ ጥርጥር የለውም ። ይኸንኑም የውጭ አገር ሰዎች የጀግና አገር መሆንዋን ገልጸውልናል ። ይልቁንም አንድ የግሪክ አገር ሰው የመርከብ መኳንንት ኢትዮጵያን አሁን በቅርብ ቀን ጐብኝቶ እግሪክ አገር የተመለሰ አክሮፖሊስ በሚባለው ጋዜጣ የኢትዮጵያ የጐበኘውንና የኢትዮጵያን ልማድ ነገር ሲጽፍ እንዲህ ይቀጥላል። የሐበሻ ሰዎች ወታደር ለመሆንና ከኢትዮጵያ ከብዙው መኳንንቶቿ በንጉሡ ነገሥታቱ ከሚገዙት ለያንዳንዱ በእምነት ሊአድሩላቸው አሳባቸውና ምኞታቸው ይህ ነው። እንደምንም ብለው የሚያስፈልጋቸውን መሳሪያዎች ይዘው ለሌሎቻቸው በትጋትና በእምነት ይገዙላቸዋል ። በእንደዚህ ያለ ነገር ቀልድ የለም ፡ ማለት ይህ ሰው አንድ ቀን እንደሚዘምት በጣም ያውቀዋል ። በኢትዮጵያ ዘመቻ የተለመደ ነውና እንኳ ወታደሮች በጦር ሥራ የሠለጠኑ ስለሆኑ በእምነትና ሰውነታቸውን መሥዋዕት እስኪያደርጉ ድረስ በጀግንነት ይዘምታሉ ። እንደዚህ ያለውን ባውሮፓም አናገኝለን ለማለት ያስጠረጥረኛል ይላል ። ከብዙ በጥቂቱ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለማስረዳት ተርጕሜላቸዋለሁ ስለዚሁ ይህ ቃል በጣም እርግጥ መሆኑን የኢትዮጵያ ጀግኖች አይስቱትም ። በታሪክ ውሥጥ ስናነብ በዘመቻ ድል ሁነው ያልተገዙ ያልገበሩ ምኖልባት ጥቂቶች ናቸው። ነገር ግን ኢትዮጵያ በኀጋርነት እንጂ በተገዥነት ቀምበር ሳትገባ ሦስቱን ቀለማት በንዲራ ተክላ መንግሥቷንና አገሯን አፅንታ በነፃነቷ ትኖራለች ይኸንንም ታላቅ ሥራ የኢትዮጵያን የጀግንነቷንና ያገር ፍቅር የምትባለውን ቃል ማሰናታቸውን ደገልጾልናል ። በአጭር ቃል የኢትዮጵያ ትንንሾች ጀግኖች ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው የጀግና አገር ልጆች መሆናቸውንና አንድ ቀን ለአገራቸው የተገቡ ጀግኖች ወታደሮች መሆናቸውን ሲያስረዱን በትንሽነታቸው የሚሠሩት የጨዋታ አንቀጽ ይመሰክርልናል በጭር ቃል እንኳ የኢትዮጵያ ወጣት ልጆች የንጨት ጕራዴ የኮብ ጠመንጃ የወረቀት መለዮ እያደረጉ እየተሰለፉና እየፎከሩ የጨዋታ ዘመቻ ሲዘምቱ እናያለን። ምንም ለጊዜው የጨዋታ ቢሆን እኋባቸው ውሥጥ የሚፈላውን የጀግንነት ሥራ በዚህ በምሳሌዎቻቸው የጀግናዎች ጀግና ተወላጆችና እኛም ስናድግ እንደነሱ ነን ማለታቸው መሆኑን ምሳሌአቸውና ምኞታቸው ይመሰክራል።

ሚክኤል ማክራስ ።

የሚአሳዝን ሞት

በሐማሴን ክፍል አከለ ጕዛይ የተወለደ ልጅ አማረ ተሰማ የደጃዝማች ተሰማ ልጅ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ የፖስጣ ቤት ሠራተኛ ሁኖ ሲኖር ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የልብ በሽታ ነበረበትና ለመታከም ወደ ዶክቶር በራ ሔዶ ሐኪሙም በሽታህ ብርቱ ነውና ካልተቈደደህ አይሆንም ቢሉት በደዌው ብርታት ላይ ድንጋጤ ተጨምሮበት ተንቀጥቅጦ ከመቀደጃው ቤት ሳይወርድ በሰኔ ፫ ቀን ሞተ ። ዕድሜውም ገና የ፳፫ ዓመት ነበር ።

ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር አልቅሰውለት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ።

ከተቀበረም በኋላ በሕዝቡ መሰናበቻ ጊዜ አቶ አራዶም የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ክቡራን ጌቶች

በኢትዮጵያችን ልማድ በአውሮፓም ሳይቀር እንደ ልጅ አማረ የነዋሪው የደጃዝማች ተሰማ ልጅ ያለ ሰው ሲሞት ጌጥ እንዳለው ጌጡ እየታዬ ሙያ እንዳለው ሙያው እየተነገረ ሲለቀስለት የሚገባ መሆኑን ሁላችሁም ታውቂታላችሁ ።

ስለዚህ ልጅ አማረ ተሰማ ምንም እንኳ እዚህ አገር የመጣበት በቅርብ ጊዜ ስለሆነና ጀምሮት በነበረ የመንግሥታችን አገልግሎት የሚገባውና የማይቀረው የነበረ የመዓርግ ደረጃ ሳያገኝ ሞት ስላቀደመው እኛ የባሕሪው ደግነት የሐሳቡ ጠንካርነት የትውልዱም ጭውነት የምናውቅ ሰዎች እንደ ማንም ልናየውና የሚገባውን ምስጋና ልናስቀርበት አይገባንም።

ልጅ አማረ ተሰማ በተወለደበት አከለ ጕዛይ በሚባለው አገር አያሌ ሰዎች እንደምናውቀው ትዳሩ እንኳን ለራሱ ለሰው የሚተርፍ ግናና መሆኑን እርግጥ ነው ።

ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረው እንለ እመሕያውስ አኮ ዘይነብር በኅብስት ባሕቲቱ አላ በቃል ዘይወፅእ እምአፉሁ ለእግዚአብሔር ይነብር በፍሥሐ እንደተባለው በዚያ ምቾት ከመኖር መከራም ሆነ ደስታም ከሕዝቡ እየተካፈልኩ የሀገሬን መንግሥት ማገልገል ይበልጥብኛል ሚስቴንና ልጆቸንም ትዳር ከተቀበልኩ አስመጣቸዋለሁ ብሎ ክብር በመላውና ከፍ ባለ ሐሳብ የሚወዳቸው ልጆቹንና ሚስቱን የሚያኰራው ርስቱን የሞቀ ቤቱን ትቶ እዚህ አገር መጣ ። እውነትም የለመኑትን በማይነሳ የነገሩትን በማይረሳ በእግዚአብሔርረድኤትም እንደተመኘው የገዛ የሀገሩን መንግሥት ለማገልገል ጀምሮ ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴም ለሚስቱና ለልጆቹ የሚያስመጣበት እርዳታቸውን አላጐደሉበትም ነበር ። ነገር ግን ዘወትር የሰውን ሐሳብ የሚያስፈጽም እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ የእርሱ ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ይህ ደግ ሰው እንደሰሙ ሁለመናው ያማረ መንግሥቱን አክባሪ ለሕዝቡ ተቈርቋሪ ሐሳቡ ሳይፈጸምለት በአፍላ ልጅነቱ በሰኔ ፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ምዓርፎ በተመደበለት መቃብር በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበረ ።

እንግዲህ ክቡራን ጌቶች። በሰፈራችሁበት ይሰፈርባችኋል የተባለው ትርጕሙ ክፉ የሠራ ክፉ ይሠራበታል ደግ የሠራም ደግ ይሠራለታል መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ። እንደዚሁም ደግነት ቅንነት የነበረው ሰው ደግነቱ ይነገርለታልና ለደጉና ለአፍቃሬ ብሔሩ ለልጅ አማረ መንግሥተ ሰማያትን ያውርሰው ለኛም ለያንዳንዳችን በሞታችን ጊዜ ለመጭው ትውልድ የሚተላለፍና የማይሞት ስም ለመንግሥቱ አክባሪ ለሕዝቡ አፍቃሪና ተቈርቋሪ ተብለን ለመጠራት ያብቃን እናንተም ሬሳውን ለማክበርና ለመቅበር የመጣችሁ ጌቶችና እመ

ቤቶች ወሰን የሌለው ምስጋናችንን እናቀርብላችኋለን ። ደግሞ ለክብርት ባለቤቱና ለክቡር አባቱ ለደጃዝማች ተሰማ ከነቤተ ሰዎቻቸው ጋራ እግዚአብሔር ያኑራችሁ። አሬዶም ዕቅበ ።

ስለሕዝብ ቍጥር

የከተማም ሆነ የባላገር ሰው ሁሉ በየወገኑ ቢቈጠር እጅግ መልካም ይመስለኛል።ይኸውም የሕዝብ አቈጣጠር አስቀድሞ የከተማውን ሕዝብ መቍጠር ነው ማለት በከተማው ሊብ ማሬ (ወስላታ) ማንዘራሹ በቶሎ (እዲሊይ) ሊታወቅ ነው

ከሁን ቀደም በክርኒ ሁኖ የከተማው ሕዝብ ከነቤቱ ከነመሣሪው ከነከብቱ ቍጥር ተጀምሮ ነበር።ነገር ግን የዚህ የሕዝብ ቍጥር ተጀምሮ ያልተፈጸመበትን ምክንያትእንዳልጽፍ ስላልተረዳሁት ከኣንባቢዎች ዘንድ ይቅርታ አለምናለሁ ።

በኛዶ እንኳ እንደምንሰማው በሥልጣኔ ደረጃ ያሉ በውጭ አገር ሰዎች ዘንድ ስለሕዝብ ቍጥር የተነገ ያንድሰው ሥራው የሚውልበት ሳይቀር ይጻፋል ይባሉ ። ነገር ግን የሀገራችን ሕዝብ እንቍጠርህ ቢሉት ጥቅሙን ሳይመለከት ዛሬስ አሉ- አሉና ኑ እንደበግ ተቈጠሩ ሆኑ? የሚል ይመስለኛል ።

ጥቅሙን ሳይመለከት ማለቱ መጀመሪ የሕዝብ ቍጥር ለመንግሥትም ለድሐም ጥቅሙ ነው ለመንግሥት ጥቅሙ የሕ ዝቡን ብዛት ለማወቅ እንዲያው በማምት ይህን ያህል ሚሊዮን ይሆናሉ በመባል ፋንታ ይህን ያህል ሚሊዮን ሕዝብ ናቸው መ- ባል ጥቅሙ ነው ይህም ለጥቅሙ ነው እንጂ ለትዕቢት አይደለም

ሁለተኛ ። ለሕዝብ ጥቅም ነጋዴ ወጥቶ ወርዶ ነጋዶ አት- ርፎ ከሆነም ጾሮ ያንስ፡ገበሬም ቆፍሮ (አርሶ) የሚያገኘውን ገንዘቡን ሲበ ቀጣሪ ወንበዴ,ዘንግዶ ፣፣ፌው በቍጥር ቢሆን እጅግ መልክም ነው።፩ዱን ጥሎ ፩ዱን ይጫወታል እንዲሉ ይልቁንም ለሕዝብ ትልቅ ጥቅሙ ከሁን ቀደም አሁንም ክርስቶየን ሁሉ በየወሩና በየዓመቱ እንዲቱን እኖሬታ ሲላዶቱን እያገባ በዚህ ምክንያት ወጥቶ ወርዶ ያተረፈው ገንዘብ ዘወትር በጥሎሽ ያልቃል።እግዚአብሔርም ይቀየመዋል ቢወልድም ያሞትበታል አሁን ግን የሕዝብ ቍጥር ደምብ ከቆመ በኋላ ሰው ሁሉ ሚስ- ቱን ቶሎ ቶሎ ሊፈታ አይችልም ማለት ይህ ሰው ሁል ጊዜ የሚስቱን ስም ሲያጽፍና ሲያስፍቅ ይኖራል ይሉኛል ሲል አንድም ገንዘብ አምጣ ይሉኛል በማለት ይልቁንም ደጅ ጥና- ቱ እጅግ ያስመርራልና ስለዚህ ከንዲት ሚስቱ ጋራ ይኖራል እግዚአሐርም ይታረቀዋል ልጅም ቢወልድ ያድግለታል ገንዘ- ብም ይጠራቀምለታል

የሰውም መቈጠር ቢሆን ከጥንት የቈየነው እንጂ በኛ ብቻ አልተጀመረም ይህም ይታወቅ ዘንድ በሉቃስ ወንጌል በምዕራፍ ፩ቍጥር፩ ወበውእቱ መዋዕል ወጽአ ትእዛዝ እምኀበ አውግስጦስ ቄሣር ከመ ይጽሐፍ ኵሉ ዓለም ባለው ያስረዳል

ሕዝብም ባመቈጠሩ የሚያዝን ሰው ቢገኝ ሲያስቡለት የሚጠላ ሰው ይመስላል (ሲመትሩለት ይነጭ እንዲሉ ዳግም ያልተማረ ሰው በጎው ነገር ክፉ ክፉው ነገር በጎ መስሎ ይታ- የዋል ይህም ሁሉ ከትምህርት መጉደል የተነሣ መሆኑ ታውቋል

ስለሰውም ከለመቈጠር የተነሣ አንዳንድ ሰው በየቤቱ የሚሠራው ሥራ ሁሉ ሌባና ቀጣሪ (ቀማኛ) እያስቀመጡ እሱ በደኅና ስም እየተጠራ ሌባውን አንተ እየሰረቅህ አምጣ ይለዋል ቀጣሪ ቀማኛውንም እንዲሁ አንተ ቀን (ጊዜ)ሲመሽ- ልህ እየቀማህ አምጣ ይለዋል።ቤት አይቆጣራችሁ የኔ ቤት አለ ገንዘቡንም አብረን እንበላዋለን ተይዛችሁ ብትታሠሩ ወንድ ልጅና ሰንሰለት ተለያይቶ አያውቅም የሚሉ የቀድሞ አጥፊ ተረት አለ በዚህ ያታልላቸዋል።በዚሁም ላይ ታስራችሁ በተ- ፈታችሁ ጊዜ ዋስ እኔ አለኋችሁ ይላቸዋል ይህ ሰው በአፍአዊ ደኅና ሰው መስሎ የሌባ ዋሻ የቀማኛ መሸሻ ሁኖ የሰው ገንዘብ ሲያከስር ይኖራል

ሌባውም በተያዘ ጊዜ ሌላ ሰው ይመራል እንጂ ይህን ሰው ይመራው አይመስለኝም ማለት ስፈታ(መጠጊያዬ)መግ- ቢያዬ ነው ብሎ ።

ይህንም ሌባ በሐሰት በተሰጠው ደምብ በቍጥር የኔ አሽከር ነው ብሎ አጽፎትም ቢገኝ በሰረቀ ጊዜ የእገሌ አሽ- ከር ነው ተብሎ ባለቤቱ ይያዛል ሳያጽፈውም ቢገኝ ትርፍ አስቀምጠሀል ተብሎ በተሠራው ደምብ ይቀጣል ስለዚህ እን- ደኔ ሐሳብ የሕዝብ ቍጥር ይከፋ አይመስለኝም።

ከሁንም ቀደም እንዲሁ የብርሃንና ሰላም ወንድሞቼ ሳይጽፉት ቀርቶ አይደለም ለማስታወስ ስል ጽፌዋለሁ ።

ደህ የሕዝብ ቍጥር ደምብ ተሠርቶ ሳይፈጸም ይቀራል ብዬ አይደለም ።

በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ እንደሚ- ሰው ሁሉ በቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ዘመን ቀዳ- ማዊ የሚሆን የሕዝብ ቍጥር ደምብ እንዲሠራልን ስል ነው ደግሞም ስለመሣሪና ስለከብት ስለሌላም ብዙ ብዙ ለመንግ- ሥት ጥቅም የሚሆን መጻፌ አይቀርም ነገር ግን ለሰሚና ለአንባቢ እንዳይሰለች ስል በአጭር ወስኜዋለሁ ።

በፈቃዱ ወልደ መስቀል።

ከኤሮፕላን ለወረደው የአሜሪክ ሰው ደስ ብሏቸው ። ገንዘብ የሰጡ ሰዎች ስም ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

ጃንሆይ ።	፩ሺ ብር
ልዕልት መነን	፫፻ ብር
ልዑል ልጅ አስፋው ወሰን	፪፻ ብር
ልጅ መኰንን ኃ ሥ	፻ ብር
ራስ ሥዩም	፻ ብር
ደጃዝማች ብሩ	፻ ብር
አፈ ንጉሥ አረጋይ	፶ ብር
ብላቴን ጌታ ኅሩይ	፴ ብር
ቀኛ ዝማች ኃይሌ ሥላሴ	፶ ብር
ባላምባራስ ተክለ ማርቆስ	፶ ብር
ፊታውራሪ ዓሥራት ወ ገ አንድ ወቄት ወርቅ	
አቶ ታደሰ መሸሻ	፲፭ ብር

ልጅ ከበደ ተሰማ ፲ ብር

በቃላቸውም እንሰጣለን ብለው ያነጻፉትን በሚመጣው ብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ።

የውጭ አገር ወሬ ስለ ስዊድን ንግሥት ሞት ።

ከብዙ በጥቂቱ ከረጅሙ በጭሩ አመለክታለሁ።የስዊድን ንግሥት ከዚህ ዓለም ወደ ዘለዓለም ቤታቸው እንዳለፉና ደግሞ በሕይወታቸው ሳሉ እንዴት ያሉ ንግሥት እንደነበሩ በስዊድን ቋንቋ ጋዜጣ ወጥቶ በወንጌላዊት ማኅበር ስዊድሽ ምሽን ነጆ በተባለ አገር ወደ ክቡር ቄስ ማርቲን ኖርድፊልት መጣ ከመጣውም ጋዜጣ በስዊድን ቋንቋ የተጻፈውን ቃል ክብርት እሜት ሒልማ ኡልሰን በነጆ የመድኃኒት ቤት አገልጋይ ከስዊድን ቋንቋ በእንግሊዝ እየፈቱ ነገሩኝ።እኔ ደግሞ የችሎቴን ያህል ከእንግሊዝ ቋንቋ ይህችን አጭር ቃል በአማርኛ ተረጐምሁት ነገሩ እንኳ ብዙ ነበር፡ ግን ከሁሉ ደስ የሚያሰኘውን ቃል ብቻ ለቃቅሜ ጻፍሁት፤ ነገሩም እንደሚከተለው ነው የስዊድን ንግሥት ቢክቶርያ የተባሉ ምንም ንግሥት ቢባሉ ይኸ ዓለም አላፊ ዓላም እንደሆነ ያውቁ ነበርና ስለዚህ በሃይማኖታቸው ጠንክረው ሳይደክሙ ሳይሰለቹ ዕድሚያቸውን ምሉ ወደ ልዑል እግዚአብሔር ጥዋትና ማታ ይጸልዩ ነበር። በዚያውም ልባቸው የቀና ርኅሩኅ የተቸገረውን እያገዙ ድኃውን እየረዱ ይኖሩ ነበር ። ደግሞ በሕይወታቸው ሳሉ ዘወትር እንዲህ የሚል መዝሙር እርሳቸው በገዛጇቸው አውጥተው ከፋቸው አይለይም ነበር ። መዝሙሩም እንደዚህ ነው፤ እጄን ያዝና ምራኝ ካሁን ጀምረህ እስከ ዘላለም ሕይወት ድረስ ። ደግሞ በዮሐንስ ራእይ በምዕራፍ ፪ ፡ ቍ ፲ ፡ የመጨረሻው ክፍል የተጻፈው ቃል እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን፤ እኔም የሕይወት አክሊል እሰጥሃለሁ የሚለውንና ደግሞ በትዕግሥት ነፍስህን ታድናለህ የተባለው ጭምር ከወንጌል ቃል ይዘው በትዕግሥት ጥዋትና ማታም እያዘወተሩ በመጸለይ ዕድሚያቸውን ገፉ ፡ ተፈጥሮ ሰው ሁሉ ሥጋ ለብሶ ከሞት የሚቀር የለምና በኤውሮፓ ቍጥር ሚያዝያ (አፕሪል) ፬ ቀን ፡ ፲፱፻፴ ዓመተ ምሕረት ተወልደው በ፷፯ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ወደ ዘላለም ሕይወት አለፉ በዚህ በዓረፉ ቀንም ሬሳቸውን በሠረገላ ውሥጥ አድርገው ሠረገላውን በብዙ አይነት አበባ አስጊጠው ከመቶ ሺህ የሚበልጥ ሠራዊት ተከትለዋቸው ወደ መቃብሩ ስፍራ መንገዝ ጀመረ ።

ከመቃብሩ ስፍራም ሲደርሱ ሠራዊቱ ሁሉ ያውቁ ነበርና ንግሥቲቱ ሳያርፉ እንዲህ የሚለውን መዝሙር በጣም አድርገው እንዲወዱትና አዘውትረው እንዲዘምሩት እጄን ያዝና ምራኝ ካሁን ጀምረህ እስከ ዘላለም ሕይወት ድረስ ስለዚህ በመቃብሩ ስፍራ በደረሱ ጊዜ ሠራዊቱ ሁሉ እያለቀሱ እንባቸውን እያፈሰሱ ይህነን እጄን ያዝና ምራኝ ካሁን ጀምረህ እስከ ዘላለም ሕይወት ድረስ የሚለውን መዝሙር ዘመሩ። ይህነንም መጻፌ ነገሩ በልቤ ውሥጥ ስለ ገባና በጣም ደስ ስላለኝ ጻፍሁት አሁንም የስዊድን ንግሥት ቢክቶሪያ የተባሉት በኋላ ለቀሩት ክርስቲያኖች በእውነት በክርስትና መንገድ ለሚሔዱ ሰዎች መልካም ምሳሌና ተስፋ ሆኑ ። እንደዚሁ ኢትዮጵያ ሀገሬ ሆይ በሃይማኖትሽና በጸሎትሽ የበረታሽ ሁኚ ለእግዚአብሔርና ለመንግሥትሽም እስከ ሞት ድረስ የታመንሽ ሁኚ ። ደግሞ ክቡራንየ ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ከሰው ስሕተት አይጠፋምና በተሳሳትሁት እንዳት ስቁብኝ አለምናችኋለሁ ።

ገመቺስ አኤሲሞስ ነሲቡ ።

የከተማ ወሬ ።

፲፱፻፳፪ ዓ ም ግንቦት ፲፯ ቀን የቅዱስ ሩፋኤል ካህናት (አለቃ) የአለቃ ሠርጹ የባለቤታቸው ተዝካር ነበርና በዚሁ ቀን የአዲስ አበባ ቤተ ክርስቲያን አለቆችና መምህራን ደግሞ የጴጥሮስ ጳውሎስ ካህናትና አለቃ በሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ከሌሊቱ በ፩ ሰዓት ተደውሎ ማኅሌት ተቁሞ ብዙ ዳዊትም ተደግሞ አደረና ጡዋት እንደሚገባው ቅዳሴ ገቡና ወደዚያው ለዕጣን ሞገር ጊዜ አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ ።

ክብር ይእቲ ።

ሙሴ እምኰኵሐ ለለ ዓሙ፤ ለእመ አንቅአ ማየ
ኅዳጥ ውእቱ በዘእምኔሁ ረወየ
እመ ሐሬዊሰ ድኅረ፤ ዕብነ ዳንኤል ከረየ
ኢየሐልቅ ምንተ ለዓለም ወኢይትመተር እምዝየ

ዕጣን ሞገር ።

ለዘሕፍነ ማይ አቀረበ እንተ ኢመንንኪ በቱ
መዊዖ አእላፈ እስከ የአቱ
ወለተ ጻድቅ ዘአቅረበት መሳብክተ ወይን እስፍንቱ
ዘአግመረቶን በበስድስቱ
እምጣነ መፍትው ይትቀፈጽ መንጦላዕተ ብርሃን ዝንቱ
ወታዕርፍ ወለተ ጻዳቅ ለዓለም ውስቴቱ

እሡረ ንጉሥ

ሀሎኪ ዘልፈ ቅድመ ገጹ ለሠርፀ ድንግል ብእሲቱ
እንዘ ማርያም ዓይንኪ በከርሠ ከመ ዕንቈ ባሕርይ ተኀቱ
እስመ ሠርፀ ድንግል በየውሃቱ
በከመ በአቱ ዘከሞ ፀዓቱ ብፁዕ ውእቱ
ዘከሞ ልቡ ሠረገላ ለጸሎት ብፁዕ ውእቱ

ግብረ ድንግል ድባቤ ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪	ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲	ብር
የዳግማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱	ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯	ብር
ዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯	ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፫	ብር
ጎሀ ጽባሕ	፫	ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫	ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫	ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፰	መሐ
የርሻ ትምህርት	፪ ብር ከ፰	መሐ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪	ብር
ትምህርተ ኅቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪	ብር
ወዳጄ ልቤ	፩	ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩	ብር
የቁጥር ትምህርት	፩	ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩	ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩	ብር
የብድር ደንብ	፩	ብር
የነፃነት ደንብ	፩	ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩	ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩	ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩	ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰	መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፰	መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፰	መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፰	መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፰	መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፰	መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንደር)	፰	መሐ
አሳብና ምኞት	፭	መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፭	መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪	መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪	መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪	መሐ
የንቁጣጣሽ ግጥም	፪	መሐ

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ። ሌት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጉበት፤ የኩላሊት፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቋቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጕርጕርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱርውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፤ የርሻ፤ የፋብሪካ፤ የደን፤ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር፤ ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
6me ANNÉE № 26

ሐሙስ ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ·ም።
JEUDI 26 JUIN 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግዛታቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ደረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ስፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አከባበር ።

በሰኔ ፲፪ ቀን የታወቀውን የቅዱስ ሚካኤልን በዓል ለማክበር ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መኳንንቱንና ሠራዊቱን አስከትለው ወደ የካ ሚካኤል ሒደው ነበር ። ታቦቱ ወጣና ዑደት ተደርጎ ካህናቱ ያማረ መዝሙር እየዘመሩ ማኅሌታቸውን ከጨረሱ በኋላ ብፁዕ አባታችን አቡነ ጴጥሮስ ስለ ቅዱስ ሚካኤልና ስለ መላእክት ተፈጥሮ ነገር እሚያስደንቅ አነጋገር ተናግረው ሕዝቡንም ደስ በሚአሰኝ ቃል መክረው አሳርገው ታቦት ገባ ።

ሹም ሽር ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሲባሉ ጀምረው በአጋፋሪነትና በጦር እንደራሴነት ሲአገለግሉ ጃንሆይን ደስ አሰኝተው ስለ ኖሩ ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ደጃዝማች ተብለው የሐረርጌን እንደራሴነት ተሾሙ ።

ደጃዝማች ደበበ ማጅንና ጉልድያን ተሾሙ ።

በገሞ ክፍል የደጃዝማች ደበበ የነበረውን በልታን ፊታውራሪ ወልደ ማርያም ተሾሙ ።

ግራዝማች ባንት ይዋሉ ጋረ ገኑን ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ተገኝ የግራዝማች ባንት ይዋሉን ወምበርነት ተሾሙ ።

አቶ አበበ ናቄ ባለምበራስ ተብለው የግራዝማች ገብረ ወልድን ወምበርነት ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ዴሬሳ ብላታ ተብለው የርሻ ዲረክቴርነት ተሾሙ ።

አቶ ወልደ አማኑኤል ጠምቄ የይሉአባቦርን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

አቶ ታፈሰ ወርቅ በፊታውራሪ ሙሉ ጌታ ግዛት ነጋድራስነት ተሾሙ ።

አቶ ወርቄ የጐመይን የቡኖን የዱረኒን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

አቶ ደስአለኝ ያቶ ታፈሰ ወርቅ የነበረውን ሹመት ተሾሙ ።

እንኳን ደስ አላችሁ ሹመት ያዳብር ።

ሽልማት ።

ከጦር ሚኒስቴሩ ከፊታውራሪ ሙሉ ጌታ ጋር ተልከው በአርበኝነትና በመታመን የበለጡት ሹማምት የክብር ኒሻንና የወርቅ ሜዳይ ተሸለሙ ። የሽልማቱን መዓርግና የሰዎቹ ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ሻለቆች

አዛጋር ወሰኔ ፬ኛውን	የክብር ኮከብ ኒሻን
ግራዝማች ኃይሌ ፬ኛውን	የክብር ኮከብ ኒሻን
ፊታውራሪ ተሰማ ጋረደው ባለአምበል	የዳግማዊ ምኒልክ ኒሻን
ፊታውራሪ ተፈሪደኝ ፫ኛውን	የክብር ኮከብ ኒሻን
ፊታውራሪ ዘለቀ በላቸው ባለአምበል	የክብር ኮከብ ኒሻን
ፊታውራሪ ኃይሌ ደገፌ	የክብር ኮከብ ኒሻን
ፊታውራሪ ይገባዋል	የክብር ኮከብ ኒሻን
ቀኛዝማች ዳኜ	የክብር ኮከብ ኒሻን
ቀኛዝማች ዘለቀ አብቴ	የክብር ኮከብ ኒሻን
ቀኛዝማች ተክሌ	የክብር ኮከብ ኒሻን

እንደራሴዎች

ግራዝማች ደስታ ወልደ ኪሮስ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ንዋይ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ

ግራዝማች ኃይሌ ወልደ ጻድቅ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ፍሬው	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ኃይሌ አብተ ገብሬል	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ ወልደ ጻድቅ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ ወልደ ሐኔ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ባሻ አሸናፊ	ባለአምበል ወቅር ሜዳይ
ግራዝማች በዳኔ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ተክሌ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች አሰፋው ሰጊድ	ባለአበምል ወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ ፈንታዬ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ሰይፉ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ወልደ የስ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ ወንድምሁነኝ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች አበቅጣው	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ሺበሺ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ዓለሜ	ባለአምበል ወርቅ ሜዳይ

ወርቅ ሜዳይ እንደተሸለሙ

ቀኛዝማች ወልዴ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ተክሌ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች በቀለ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ሊንጂባ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች አበበ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ደስታ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች በድሉ	የወርቅ ሜዳይ
ልጅ መኰንን	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ በሳይነህ	የወርቅ ሜዳይ
ልጅ ጽጌ ይማሙ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ዘውዱ አበዬ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ገብረ ኪዳን	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ጥላሁን	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ገብረየስ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች መንገሻ አየለ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ኃይሌ አሰፋው	የወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች አውላቸው	የወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ዘውዱ አስጓዴ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች በቀለ ቢሻው	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች አይተንፍሱ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ሳሙኤል	የወርቅ ሜዳይ
ደጅአዝማች ታችበሌ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ደገፉው	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች ወልደ ጻድቅ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች መዙሬ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ተሚኔ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች አድነው	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ አረዶ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ አጠኑ	የወርቅ ሜዳይ
ልጅ ተፈራ አምበርብር	የወርቅ ሜዳይ
ልጅ ደምሴ አምበርብር	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ገብረ ክርስቶስ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ አማረ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ወንድማገኘሁ	የወርቅ ሜዳይ
ፊታውራሪ ታምራት	የወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ አስፋው	የወርቅ ሜዳይ
ባሻ ጣሹ	የወርቅ ሜዳይ
ቀኛዝማች መለሰ	የወርቅ ሜዳይ
ባሻ ደምሴ	የወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ አየለ	የወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች ኃይለ ማርያም	የወርቅ ሜዳይ
ባሻ ደሳለኝ	የወርቅ ሜዳይ
ባላምባራስ ይመር	የወርቅ ሜዳይ
ባሻ ደገፉ	የወርቅ ሜዳይ
ባሻ ቀጻሚ	የወርቅ ሜዳይ
ግራዝማች የሱፍ	የወርቅ ሜዳይ
ልጅ መንገሻ	የወርቅ ሜዳይ

ደግሞ ለያንዳንዱ የተሰጠው የምስክር ወረቀት ቀጥሎ እንደ ተጻፈው ነው በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፈቃድና ትእዛዝ እገሌ በመታመኑና በአርበኝነት ሥራው መንግሥቱን ስለ አገለገለ በዳግማዊ ምኒልክ መልክ የታተመ የወርቅ ሜዳይ መሸለሙን እንመሰክራለን ሰኔ ፲፪ቀን ፲፱፻፳፪ዓ

የጦር ሚኒስቴር	የጽሕፈት ሚኒስ
ፊርማ	ቴር ፊርማ

ደግሞ በደዌም በሌላም ምክንያት ያልተቀበሉ ሰዎች አሉና በተቀበሉ ጊዜ እናስታውቃለን የክብር ኮከብ ኒሻንም የተቀበሉት ሰዎች የተቀበሉትን የምስክር ወረቀት በሚመጣው እናስታውቃለን

ድኃ ያበድራል ባለጸጋ ይበደራል ።

እንዲህ ብዬ ስጀምር አንባቢዎች ሁሉ ምን ማለቱ ነው ድኃ ማለት ገንዘብ የሌለው ሰው ማለት ነው ። ባለጸጋ ማለት ገንዘብ የሞላው የተረፈው ማለት ነው ። ገንዘብ የሌለው ሰው ገንዘብ ለመላውና ለተረፈው እንዴት ያበድራል ባለጸጋስ ምን ቸገረኝ ብሎ ይበደራል? ይህን የጻፈ ሰው ራሱ የዞረና የጃጀ ነው እንዲለኝ አውቃለሁ። ነገር ግን አስቀድሞ ማማት ለማመስገን አስቀድሞ ማመስገን ለማማት ይቸግራል እንደሚሉት ሁሉ የኋላው አሳብ እንዳይደፈርስ ከመንታው ጐዳና መከከል ሁኖ መጠበቅ ይሻላል ።

ብድር መበደር ለሚአውቅበት ሰው መልካም ነው ያሸ-ራል ይጠቅማል ። ለማያውቅበት ሰው ግን ያዋርዳል ። ሥራ የማያውቅና የማይችል ሰው ማበደር ልማዱ ነው ። ስለምን ምንም ባረጣ ባይከብር በያዘው ገንዘብ ሥራ ክልሠራበት እያበ-ደረ እንዳይሞት እንዳይድን ሁኖ በረጣው ዕድሜውን ይሸኛል ባለጸጋ ደግሞ በተበደረው ገንዘብ ላይ የገዛ ወረቱን ጨምር እየነገደ ብዙ ማትረፍና ጥቂት አረጣ መክፈል ለመቻውም ል

ማድ ነው።አበዳሪውንም ተበዳሪውንም ጥቅም ያጋጥማቸዋል።የትርፍን አደራረግና የጥቅምን መንገድ የማያውቅ ሰው ግን መበደር ቀና ሳያውቅ ከጥልቅ ባሕርና ፏፏቴ ዘሎ እንደመደርገም ያለ ነው ። ብድር የሚፈራ ነጋዴ ባገኘት ለጥቂት ወረቱ ብቻ ሸቀጥ ገዝቶ ባንድ አጋሰሥ ጭኖ ተጅማ ዘይላ ወይም ጅቡቲ ተጕዳም ምጥዋ ሲሔድና ሲመጣ ዓመት ሙሉ ተጕዞ የደጋ ድደን የበረሃ ሐሩር መከራውን አሳይቶት ካንድ አጋሰሥ ሸቀጥ እስቲ አምሳ ብር ትርፍ ያገኝ ይሆናል ከዚያው ከምሳው ብር ለስንቅና ለሎሌ ደመወዝ ተነሥቶለት ሀያ አምስት ብር ይቀረው ይሆናል። እንዲህ ያለው ነጋዴ የኔ ቢጤ ሞኝ ነው። ትንሽ ዕውቀት ያለው ነጋዴ የሆነ እንደሆነ ግን በረሃውና ውርጩ ድካሙና ምስኑ ቃልቀረልኝ ተበድሬ ተቀድሜ ባንድ አጋሰስ ብቻ ከመነግድ ይልቅ ባሥር አጋሰስ ጭኜ ብሔድ አምስት መቶ ብር አትርፌ መቶው ለስንቅና ላሽከር ደመወዝ መቶው ለተበደርኩት ብር ወለድ ሁኖ ሦስት መቶ ብር ይተርፈኛል ይላል ። ያመት መንገድ ተጕዞ ፳፭ ብር ብቻ ከማትረፍ ፫፻ ብር ማትረፍ ይሻላል ። ከዚህ የተሻለ ብልህ ነጋዴ የሆነ እንደሆነ ገፋ አድርጎ ተበድሮ በሀያ አጋሠሥ ጭኖ ይሔዳል ። ከሀያው ጭነት ሸቀጥ ሺ ብር ያተርፋል ። አራቱ መቶ ብር ላራጣና ለስንቅ ላሽከር ደመወዝ ሁኖ ስድስት መቶ ነፃ ትርፍ ይሆነዋል ። ደግሞ ከብልህ ብልህ ክብልጥ ብልጥ አይጠፋምና የዚህ ዓይነት ነጋዴ የተገኘ እንደሆነ ያገኘውን ያህል ደፈር አድርጎ ተበድሮ በመቶ በሁለት መቶ በሦስት መቶ አጋሰስ ሲሔድ በጕን ሰሙን ቄርበቱን ሲመልስ ሀሩን ባምጃውን ሲራራውን ጭኖ ባንድ ጊዜ መንገዱ ሁለት ሺ ሦስት ሺ አምስት ሺ ብር ያተርፋል ። እንዲህ በዚህ ዓይነት የሚነግድን ነጋዴ ብድር ያከብረዋል እንጂ አያዋርደውም።

ስለዚህ አዋቂ ብልህ የሆነ ነጋዴ ሁሉ በገዛ ወረቱ ብቻ ነግዶ የሚጠቀምና የሚከብር የለም ። ብቻ እስከ ሆነለትና እስከ ቻለ ድርስ ተበድሮ ከወረቱ ላይ ጨምሮ ቢነግድ እንደ ብድሩ ብዛት ትርፉም ብዙ ይሆንለታል ። ለራሱም ብቻ አይደለ ጥቅሙ ተከበረ ዘንድ ላገሩም ለመንግሥቱም አጋዥና መዓርግ ለተራበም እራት ለታረዘም ልብስ ይሆናል ።

ብድር የሚፈራ ነጋዴ ግን ያመት መንገድ እየተጓዘ በትንሽ ወረቱ ብቻ እንደ ዘሀ ዘጊ እየተመላለሰና እየተውተረተረ ራሱን ሳይችል ለልጆቹ ሳይጠቅም ዕድሜውን ሙሉ እንዳዘነ እንደተከዘ ዓይኑ ነሁልሎ ላሀዩ ጓያ ቆሎ መስሎ በበረሃ ጆሮው ተጨማዶ ሕይወቱን ይጨርሳል። ብድር ለነጋዴ ብቻም አይደለ በዚህ ዓለም ለሚኖር ሰው ሁሉ ለመንግሥት ሳይቀር ታላቅ ጥቅም ይሰጣል። ቄፋሪ ባላገር ካንቻ የሚመታበት ምሳር፣ የሚቄፍርበት መቄፈሪአ በጣ ጊዜ ብድር ፈርቶ እጁን አጣምሮ በዝኖ ቢውል ጥቅሙ ምንድር ይሆን? ቀንጃ በሬ ያለው አራሽ ተበድሮ ሌላ በሬ ገዝቶ በጥንድ በሬ ቢአርስ ብዙ አምርቶ ራሱ ጠግቦ ካመረተው እህል እኩሉን አቅንቶ ብድሩን ነቅሎ ከመኖርና በቀንጃ በሬ ብቻ እያረሰ እንደልቡ ሳይበላ ከመኖር ሂትኛው ይሻለዋል? አራሽ ገበሬ መሬቱን ሁሉ አርሶ አለስልሶ ዘር ያጣ እንደሆነ ብድር ፈርቶ ያረሰውን መሬትን ጠሙን ቢያሳድረው ጥቅሙ ምን ይሆን? ደኅ እናት ተበድራ ተቀድማ ልጆቿን ተከፉ ዘመን ያወጣች እንደሆን እነዚያ ልጆች አድገው ጕልምሰው እናታቸውን ለመጦር ዕዳቸውን ለመንቀል ይደርሳሉ ። እናታቸውን ብርድ ፈርታ ዝም ብላ ቢሆን እሷም ልጆቿንም ተያይዘው አላቂናቸው በራብ አልቀው ቢሆን ምን ኑሯል ይሆን ጥቅማቸው?

ባንክ ሀብታም ነው ለቸገረው ሁሉ ያበድራል ይባላል። እውነት ነው ሀብታም ነው ያበድራል። ነገር ግን እሱም ራሱ ሲጀምርም ሲቆምም ሲሠራም በገዛ ገንዘቡ አይደለም በመዋጮ ገንዘብና በብድር ነው ። ብድር ለሁሉ ጥቅም መሆኑ በዚህ ይታወቃል ። ብድር መበደር ክብረት እንጂ ውርደት አለመሆኑ በዚህ ይታወቃል ። ብድር ያለበት ሰው ብዙ ሀብታም ነው ።

በኤውሮፓ መንግሥት ሲባል ብድር የሌለበት የለም ይልቁንም ትልቅ ሀብታም መንግሥት የሆነ እንደሆነ በትልቅነቱ መጠን ብድሩም ትልቅ ነው ። ስለምን ትልቅ መንግሥት ሥራውም ትልቅ ነውና ትልቅ ሥራ ለመሥራት ትልቅ ብዙ ገንዘብ ያስፈልገዋል ። ያትልቅ ገንዘብ የሚገኘው ከደኅው በመበደር ነው ። በዚያ ከደኅው በተበደረው ገንዘብ መንግሥት አገሩን ያለማል ለደኅው የሚጠቅም ትልልቅ ሥራ ይሠራበታል ። ለደኅው ሲል የሦስትና ያራት ቀን መንገድ የራቀውን ወንዝ እንደዋስ አጋች ገትቶ ባላሰበው ጕዳና መርቶ ያመጣበታል ድልድይ ሠርቶ መንገደኛው ውሃ እንዳይበላው ያደርጋል በያገሩና በያውራጃው የምድር ባቡር ይዘረጋል ተራራውን ቀዶ ገደሉን ንዶ ቍልቍለቱን ደልድሎ ለሕዝብ እንዲመች ያደርጋል ።

በምድር ባቡሩም ነጋዴ ሁሉ አጋሰስ ሳይገዛ መጫኛ ሳያለፋ ችሀል ሳይመታ ዘብ ሳያድር እግሩን ሳይጣምነው ዝናም ሳያበሰብሰው ባምሳ በስልሳ በመቶ አጋሰስ የሚጭነውን ሸቀጥ ወር ሁለት ወር የሚአስጕዘውን መንገድ ባንድ ቀን ባንድ ሌሊት ይደርስበታል ። እንዲህ ያለ ሥራ የሚሠራበት ብድር ነው ። ብድር የማያስጠቃ ጠንካራ መሳርያ መሆኑ በድፍን ዓለሙ ሁሉ የታወቀ ነው ። ገንዘብ ለመንግሥት የሚያበድር ደኅ ሁለት ጥቅም አለው ። በቀኝ እጁ የሰጠውን እንደገና በግራ እጁ መልሶ እንደመቀበሉ ነው ። ስለምን ባንድ ወገን አራጣውን ይቀበላል ባንድ ወገን ደግሞ እሱ ባበደረው ገንዘብ መንግሥት ቍጥር ስፍሩ የማይታወቅ ጥቅም ይሠራለታል ሀብታም ነጋዴና መንግሥት ለመበደር ደኅ ለማበደር ልማድ ነው ። ከመንግሥትም ብዙ ሀብታምና ደኅ ይገኛል ። ብዙ ሀብታም መንግሥት ለልማዱ ብዙ ብድር ይበደራል ። ስለምን ሥራውም እንደ ሀብቱ መጠን ብዙ ነው ። ለዚህ ምሳሌ አመጣለሁ ። ከትልቁ ከኤውሮፓ ጦርነት በፊት በዓለሙ የታወቀ ሀብታም የፈረንሳዊ መንግሥት ወደሰላሳ አምስት ሚሊ.አርድ ፍራንክ የሕዝቡ ብድር ነበረበት ። የኢጣልያ መንግሥት የዚያን ጊዜ እንደዛሬ አንድነቱ አልጠና እንደዛሬ አሳቡ ምኞቱ አንድ አልሆነ ብቻ መማክርቱ ሁሉ ወገን ወገን አብጅተው

ፖለቲካቸው ሁሉ ላልቶ ስለነበረ እንደዛሬ የኢጣልያ ገንዘብ አልበረከተም ነበረና ከሥራ አምስት ሚሊ. አርድ ሊ.ር በላይ የሕዝብ ዕዳ አልነበረበትም ። የዚያን ጊዜ ዛሬም ቢሆን የኢ-ጣልያ መንግሥት ዕዳ ከፈረንሳዊ መንግሥት ዕዳ በጣም ስላነሰ በገንዘብ ነገር ከፈረንሳይ ኢጣልያ ይከብራል አይባልም ። ዕዳው የበዛ መንግሥት በሀብትም የበለጠ መሆኑ የታወቀ ነው። ዛሬ ግን የፋሽሽት መንግሥት ባንድ አሳብ ባንድ ምኞት ባንድ ቃል ባንድ ፍቅር ሁኖ ስላሠራ ኢጣልያን የመልከም ፖሊቲካ ምንጭ አደረጋት። ከዚያች ምንጭ ዓለሙ ሁሉ ሊቀ-ዳና ሊወጣ ይመኝ ጀምሯል ። በዚሁ እምነት የተነሣ ዛሬ የኢጣልያ መንግሥት ብድር የሚፈልግ ቢሆን እንኳን ያገሩ ሕዝብ የሌላውም የውጭ አገር ሕዝብም ቢሆን በጠየቀው ዓሥር እጥፍ እያደረገ ለማበደር ባልተገበዘም ነበረ። ዛሬ የፋሽ-ሽት መንግሥት ያገር ሕይወት ያገር ፍቅር የፖሊቲክ አንድ መሆን ለዓለሙ ሁሉ ጣዕሙን አሳውቆታል ።

ይህን ሁሉ ምሳሌና የነገር ክብ ማምጣቱ ብድር መበደር ብዙ ጥቅም አለበት ። ታላቅ አገር ታላቅ መንግሥት ሁኖ አለብድር አገር ማልማት እርሻ ማብዛት ንግድ ማስፋት ባቡር መዘርጋት አይሆንለትም ስለማለት ነው ። ብድር የፈራች ድሃ እናትና ብድር የፈራ መንግሥት አንድ ናቸው ፡ ሁለቱም ልጆቻቸውን ከሞት ያደርሳሉ ። ብድር ካልተለመደበት አገር ግን መንግሥት ብድር ከተለመደበት አገር መበደር የተለመደ ነውር የሌለበት ነገር ነው ። አፈ ወርቅ ዘብሔረ ዘጌ።

ክብሩን በስካር የለወጠ ሰው

ከዕለታት አንድ ቀን ፖስታ ልቀበል ወደ ፖስታ ቤት ሔጄ አምሽቼ ፖስታዬንም ተቀብዬ ስመለስ ቀኑንም ዝናብ ሲዘንብ ውሎ ነበርና መንገዶቹም ጭቃ ነበሩ እኔም ከምሽቱ ጉስ ሰዓት ሲሆን መንገዴን ይገር ወደቤቴ ስሔድ አበቃችን ሰፈር ስደርስ እፊቱውራሪ ሙሉ ጌታ ቤት በላይ አንድ ሰው ብግምቱ ዕድሜያቸው ፫ ዓመት የሚሆን ሽማግሌ ሰክረው እጭ ቃው ውስጥ ወድቀው ሲጉላሉና ሲንገላቱ አየኋቸው ወደዚ-ያውም ቀረብ ብዬ ሁናቴ አቸውን ለማወቅና ለመረዳት ምን ሁነዋል ብዬ ብጠይቃቸው ንግግራቸውን እንደ ዲዳና እንደ መንፈቅ ልጅ አኳኋን እየዘበራረቁ አንዳንድ ጊዜም እረቂ እረቂ እያሉ ከስካራቸው የተነሣ ምንም መልስ ሊሰጡኝ አል-ቻሉም ነበረ ። አሳቸውን ተከትሏቸው የነበረውን ሕፃን አጠገ-ባቸው ቁሞ አግኝቼ ብጠይቀው ሰው አረቂ ጋብዟቸው ሲጠጡ ውለው ነበርና ሰክረው ነው እንዲህ የሚሆኑት ብሎ ነገረኝ እኔም በስካር ምክንያት መውደቃቸውን ከተረዳሁ በኋላ መን-ገዴን ቀጠልሁ ።

ክቡራን ተመልካቾች ሆይ ፥

የዚህ አልኮልና የኢስቢርቶ ያለበትን መጠጥ በብዙ ብኩል ሀገራችንና ሕዝባችንን እንደሚጐዳ እርግጥ ነው ። ፩ኛ ሽማግሌዎቻችንን በሥር ስለሚያጕላላብን፥ ፪ተኛም የጐበዛዝቶ ችንና የአርበኞቻችንን ጕልበትና ኃይል ስለሚያደክምብን ፫ተኛ የሕዝባችንን ገንዘብ በከንቱ ስለሚፈጅብን ፬ተኛም ብዙዎቹን ባለርስቶች ሱሰኛ አድርጎ ገንዘባቸውንና ርስታቸውን ስለ ሚአሸጥብን ከዚህም ይበልጥ አብዙ ልዩ ልዩ ውርደት ብዙ ዎችን ስለ ሚአደርሳቸው ዋናው ጕዳት ለመንግሥታችን ነው

በአሜሪካን አገር ዕውቀትና ብልሃት ሠልጥነውና ተከና-ውነው በሚኖሩበት ሀገር እንኳን ሕጋቸውን ስንሰማ ይህን አልኮልና የስቢርቶ ያለበት መጠጥ ለሕዝብ ጕዳት መሆኑን ስለ ተረዱት ጨርሶ በአሜሪካ እንዳይሸጥና እንዳይጠጣ መን ግሥት ከልክል አድርጎት ይኖራል ይባላል ።

አሁንም በሀገራችን የአረቂ ነገር ፈጽሞ ቢከለከል መልካም ነበር ። ምናልባት አንዳንዶቹ የመንግሥት ገቢ ለምን ደቀራል መንግሥት በቀረጡ የሚገባለት ብዙ ነው የሚሉና የሚያጕረመርሙ እንኳ ቢገኙ መንግሥት ምንም ገንዘብ ቢያበዛና ቢበለጥግአማካሪ ሽማግሌዎች ጠላት አጥፊ አርበኞችና ወታደሮች ከሌለው ከልኩ ያለፈም ቢበለጥግ ምንም ያህል ኃይልና ጕልበት ኑሮት ጠላቶቹን ለማጥፋትና ሰላምን ለማልማት አይችልምና ሽማግሌውም አእምሮውን አስተካክሎ ጐበዛዝትና ወታደሮቹም ኃይላቸውን አበራተውና ጕልበታቸውንም አሰፋ-ፍተው በመንግሥታቸው ላይ ለሚነሡ ፈያቶችም ጋሻቸውን መክተውና ጦራቸውንም አስማምተው እንዲረዱና በኃያሉ ጕልበታቸው እንዲአገለግሉ የዚህን ከውጭ አገር እየመጣ ለሚሸጥ የአልኮልና የስቢርቶ መጠጥ ሁሉ ቢያግዱትና ቢያ-ቆሙት ይሻል ነበር ስል ሕግና ደንብን እየአስተካከሉ የሕዝብንም ሰላምና ጤንነት እየጠበቁ ለሚኖሩ የመንግሥት አገልጋዮችና አማካሪዎች ለማሳሰብ ምኞቴን አቀርባለሁ ።

በቀለ ዘለቀ ።

፲፱፻፳፬ ዓ ም ሰኔ ፲፪ ቀን ለታተመው ።
የምክር ቃል ሁለተኛ ተከታይ ።

የእግዚአብሔር አብ ብርሃንነቱ የተገለጸ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። የጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ብርሃንነትም የተ-ገለጸ በተከታያቻው ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ነው ። ኢትዮጵያ የውጭ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን አትሻም ፀ-ሐይዋ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጨረቃዋ ልዕልት መነን ናቸው ። ከዋክብትዋም ድውያን ፈውሱ ሙታን አንሥኡ እለ ለምጽ አንጽሑ አጋንንተ አውጽኡ ተብለው በዘመናቸው የ-ተሾሙ ብሩሃን ከዋክብት ጳጳሳት እመኑ በብርሃን ከመ ትኩኑ ውሉደ ብርሃን እያሉ ሲያስተምሩ እየሰማች በፍጹም ደስታ ትኖራለች ። ይልቁንም የኢትዮጵያ መንፈሳዊት ጉባኤ በራሷ ቋንቋ በግዕዝ ተነቦ ባማርኛ ተተርጕሞ መጻሕፍትን የሚያስ ተምሩ የሀገሬ ሐዋርያትን ስላገኘች የማያልቅ ደስታ አላት ደግሞም የዕውቀትና የትምህርት ቤት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ቁሞላት የሐበሻ ትምህርት ንባብና ዜማ የውጭ ሀገርም ትምህርት የፈረንሳዊና የእንግሊዝ ቋንቋ እየተሰበከላት በደስታ እየጮኸች ብርሃንነቷን ትገልጸዋለች ።

ሁለተኛ በቃሁ ነቃሁ ብሎ ሥልጣኑ መንግሥትን ሥልጣኑ

ቅህነትን ገንዘብ ለማድረግ የሚቻለው ሰው የለም የእግዚአብሔር ኃይልና ሥልጣን ለተሰጠው ሰው ነው እንጂ ። ዮሐንስ ም ፬ ቍ ፳፯ ተመልከት የሺ ፍልጥ ማሰኘው ልጥ እንዲሉ ፍቅርን ለያዘ ሰው ሥራው ሁሉ ይጠቀለልለታል ፍቅር ካለ እንኳን ደም ሊፈስ ሰው ሊሞት አገር ሊበደል ይቀርና አባት ልጁን ታላቁ ታናሹን ጌታ ሎሌውን እመቤት ገረድዋን በቊጣ ቃል ሊናገርዋቸው አይችሉም ። የፍቅር ሥራው ምንድን ነው መተባበር መተዛዘን ትንሹ የትልቁን ትእዛዝ መፈጸም ነው ይህ ያልሆነ እንደ ሆነ ግን ቅያሜ መግባቱ ያለጥርጥር የታወቀ ነው ። ሙሴ ትእዛዝ ፈጻሚዎች ኢያሱን ካሌብን ሰሎሞንን ሹሞ በሰሰጽአደ የፈረደውን መመርመር ነው ጌታ ሎሌውን እመ ቤት ገረድዋን አባት ልጁን ሳይቀጡ ነውን ። ጳውሎስ ም ፲፫ ቍ፱ ወዘሰ አበየ ተኰንኖ ለመኰንን ትእዛዘ እግዚአብሔር አበየ ወእለሰ አበዩ ተኰንኖ ኵነኔ ያመጽኡ ለርእሶሙ ያለውን ተመልከት ። ሦስተኛ ሳይከፍቱለት ገብቶ ሳይጠሩት መጥቶ ሳያማክሩት አማካሪ ሁኖ ሳያይ ሳይሰማ መናገር ፍጹም ኃጢአት ነው። የማይገባውን ሐሰት ነገር ይቅርና የሚገባውንም ቢሆን ጊዜው ሳይደርስ ፈጥኖ መናገር የማይገባ መሆኑን ያዕቆብ ም ፩ ቍ ፲፱ ወይእዜኒ አኀዊነ ይኩን ኵሉ ብእሲ ፍጡነ ለሰሚዐ ወጐንዱየ ለነቢብ ወጐንዱየ ለመዓት ያለውን ተመልከት ። ሐሰት ነገር የማይገባ መሆኑን ክምዕራፍ ፫ ቍ ፲፰ ወዘሰ ኢይሰሕት በቃሉ ፍጹም ውእቱ ከለው ጀምሮ ወፍሬሃኒ ዘጽድቅ በሰላም ይዘራእ ለእለ ይገብርዋ ለሰላም ብሎ እስከ ፲፰ ቍጥር ድረስ የተናገርነውን ቃል ልብ አድርጎ መመልከት ነው ንባቡን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው አለመጻፌ ቃሉ ሲበዛ ለስፍራ አይመችም በማለት ነው ከዚህ ቀጥሎ የየሥራው መሻሻል ይከተላል የኢትዮጵያ መንግሥት ቤት ሠራተኛ ኃይሉ ዘወገ

አ ዋ ጅ

ስለ ድርና ማግ እሥራት ለየጣቃውም ጨርቅ አጥፋት ከጉምሩክ ከወጣ በኋላ የማታለያ ሥራ እንዳይሠራ ለማድረግ ከዚህ ቀደም የወጣው አዋጅ በፍጹም እንዲጸና ስንል ቀጥሎ የተጻፈውን እናስታውቃለን ።

አንደኛ ።

ማናቸውም ነጋዴዎች በማናቸውም ምክንያት ሆነ የድርና የማግን አከፋፈል የየጣቃውንም ጨርቅ አጥፋት የደንቡን አስቀርተው የሐሰት አጥፋትና ክፍል እንዳያደርጉ አጥብቆ ክልክል ነው ።

ሁለተኛ ።

የዚህን የአዋጅ ቃል አፍርሶ የተገኘ ሰው ሁሉ በመጀመርያ መቶ ብር መቀጮ ይከፍላል ። ጥፋቱ የተደገመ እንደሆነ ግን የማታለያ ሥራ የሠራበት ሸቀጥ ተወርሶ አምስት መቶ ብር መቀጮ ይከፍላል ።

ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን አንሥቶ ከስምንት ቀን በኋላ የጸና ይሆናል ። አዲስ አበባ ሰኔ ፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ገብረ እግዚአብሔር ።

AVIS

Afin d'assurer la mise en vigueur des decrets concernant la confection des filets de coton et des pièces de tissus et empêcher la contrefaçon sur place le Ministre du Commerce p. i

DECRETE:

I

Que tous les paquets de filets de coton et pièces de tissus ne devront sous aucun motif être manipulés par les Commerçants pour rendre irrégulières les sub-divisions des filets de coton et le pliage des pièces de tissus.

II

Que tous contrevenants sera passible d'une amende n'excédant pas les thalers 100 pour la première fois, et en cas de récidive il lui serait confisquées les marchandises falsifiées et il lui sera appliquée une amende n'excédant pas les thalers 500.

III

Que huit jours après sa publication le présent avis entrera en vigueur.

Addis-Abeba, le 16 Juin 1930

ስለ አዲስ አበባ ማዘጋጃቤት ሥልጣኔ ።

የአዲስ ኣበባ ማዘጋጃ ቤት በክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዘአማኑኤል ትጋት ሥልጣኔ ሥራውን እያሻሻለና እየቀጠለ ሲሔድ እናያለን ። ምንም የደግነትና የዕውቀት ሥራቸው በወረቀት ተጽፎ በቃል ተነግሮ ባያልቅ ትጉህነታቸውን የሚያስረዳ ምልክት ከብዙ በጥቂቱ ከዋናው በቲንሹ ከሠሩት አዳራሎት ልቤን የተሰማኝን ለመጻፍ ስለ ሞክርሁ ምናልባት በሐሳቤ ውስጥ ያልተከከለ ነገር ቢገኝ የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች የጠመመውን አቅንታችሁ የጐደለውን መልታችሁ በሰሌዳ ብርሃን እንድትገልጹት ፈቃዴ መሆኑን ለጥልቅ ዕውቀታችሁ በትሕትና አመለክታለሁ ። ከሠሩትም ሥራ የሚታሰበኝ ወደፊት ቀጥሎ የተጻፈው ነው።፩ኛ በአለፈው ጊዜ በየዓውዳ ዓመቱ በየበዓላቱ ጠበንጃ እየተተኰሰ አያሌ ሰው ይጐዳ የነበረውን ልማድ በአዋጅ

ስለ ከለከሉት ዛሬ በክብረ በዓል ጊዜ ሕዝቡ ሲበላ ሲጠጣ ከተማው ጸጥ ብሎ ይታያል እንጂ የተኵስ ድምፅ ተሰምቶ አያውቅም። ፪ኛ ሽጉጥ ለመታጠቅ ለሕዝቡ ነፃነት ስለ ነበረው በአምባጓሮ ብዙ ሰው ይቈስል ነበርና አሁን ከዋናዎች ከዘበኞች አለቆች በተቀር ጥራውን ወታደርና ዘመናዮችንም እንዳይታጠቁ መቀጮ ስላደረጉ በአምባጓሮ ምክንያት ለሞት የሚደርስ እምብዛም አይገኝም። ፫ኛ የሠራተኞቹን ሕይወት ለመጠበቅ በተለየ ለማዘጋጃ ቤት ሐኪም በደመወዝ ቀጥረው እንዲታከሙ የመድኃኒት ቤት ስለ አቆሙ በድንገትም አደጋ ያገኘው ሰው ሁሉ እንዲታከም ስለፈቀዱ ዋና የሕዝብ ጥበቃ ማድረጋቸውን ያስረዳናል ። ፬ኛ ደምብና ሕግ ተላልፎ አንዳች ጥፋት ያደረገ ሰው ከከተማ ውስጥ አምልጦ ወደ ውጭ እየሔደ በአገር ቤት ልዩ ልዩ የሆነ የክፋት ሥራ እየሠራ ስለ አስቸገረ በቶሎ እንዲያዝ ብለው ለትእዛዝ ማፋጠኛ በየከሚሣርያው የስልክ ቴሌፎን አስገብተዋል ። ስለዚህ ማንም ጥፋተኛ የሆነ ሊያመልጥና በጥፋቱ ፀንቶ ሊቈይ አልቻለም። ፭ኛ በየመንገዱ አቅራቢያ የሚወድቅ ጉድፍና ቈሻሻ የሚሞተውም የእንስሳ ሬሳ እየከረፋ እየተነፈገ በዚሁ ምክንያት የሚጋባ በሽታ ተላላፊ ሁኖ አያሌ ሰው ይታመም ነበርና በየቦታው ጉድጓድ እንዲቈፈር የሚሞተውም የእንስሳ ሬሳ እንዲቀበር የጥዳት ዘበኞች ስላደረጉ ዛሬ ተላላፊ በሽታ እየበረደ ሔዷል። ፮ኛ፤ የከተማው ሕዝብ ከብዛቱ የተነሣ በክረምት ጊዜ በጭቃና በድጥ መቸገሩን ስላሰቡ በየክፍሉ በየ ውሥጣ ውሥጡ መንገድ እንዲሠራ በማድረጋቸው ዛሬ ተመንጥሮ ቈጥቋጦው ተጠርጎ መንገደኛና ተላላፊ የሆነ ሁሉ ያለ ችግርና ያለ መሰናክል በቀጥታ እየሔደ ጉዳዩን ይፈጽማል ። ፯ኛውል የሚቀዋል ሰው በየቤቱ በየገርቢቱ እየተዋዋለ በኋላም ከቀን ብዛት እየተካካደ በሙግትና በጭቅጭቅ ሥራ እየፈታ ከንዱ ዳኛ ወደ አንዱ በተመላለሶ ጊዜውን በከንቱ ያሳልፍ ነበርና አሁን በማዘጋጃ ቤት እንዲዋዋል ደምብ ስለቆመ የተዋዋሉት ሰዎች ሁለቱም የምስክር ወረቀት ተቀብለው በዕረፍት ይኖራሉ ። ፰ኛ፤ የሰልፍ አረማመድና አከሔድ እንደ አውሮፓውያን ሥርዓት እንዲሆን አስበው ከውጭ አገር አዋቆች በብዙ ደመወዝና ቀለብ አስተማሪ ቀጥረው ዘበኞችን ስለ አሠለጠኑ በሰልፍ ጊዜ ለተመለከተ ስንኳን ተላላቆቹና ሕፃናቱ ለትንግርት ይታያሉ። ፱ኛ በአዲስ አበባ በየመንገዱ ዳር በየቦታው ሁኖ ቤት ለሚሠራ ሰው ከመንግሥት ገንዘብ እየተበደረ የተሻለ ቤት እንዲሠራ ብለው ፈቃድ አስደርገዋል። ፲ኛ ወስላታና አታላይ ሌባና ፈንጋይ በሌሊት አደጋ እየጣለ ብዙ ሁከት ስለአደረጉ መርማሪ ዘበኛ በማድረጋቸው ይልቁንም ከሥልጣኔ ሥራቸው ሁሉ የአእምሯቸው ስፋት የጥንቃቄያቸው ብዛት ልባችንን እየነካው ከዚህ የተነሣ ውዳሴ ከቱ ያልሆነ ምሥጋና እናቀርብላቸው ዘንድ ይገባቸዋል። አሁንም በቅርቡ ጊዜ ለምርመራ ሥራ አለቃ ሆነው ዘበኞችን ለማትጋት ስራውን ለማስኬድ ተመረጠው የተሾሙ በልዩ ለቆመ ለፍርድ ቤት አጋፋሪ የነበሩ ክቡር ልጅ ኃይሌ ሮባ ናቸው። በእግዚአብሔር ኃይል በክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዕድል መንግሥታቸውን በቅን ለማገልገልና የተሰጣቸው ሥራ እንዲከናወንላቸው ተስፋ እናደርጋለን። ለወደፊትም በከተማ ውሥጥ የሚኖረውን ከውጭ ከገር ቤት የመጣውን ሥራ ፈት ሁኖ የሚኖረውን ሰው በተሰጣቸው ሥልጣን መርምረው በጽሕፈት እንዲያኖሩት ለክቡር ልጅ ኃይሌ አስታውሳቸዋለሁ። ነገር ግን በአለቃ ሳይታዘዝ ሥራ ሳይዝ እንዲያው የተንኰል ፖለቲካ እያወራ ፀብእ እየዘራ በከተማው ውሥጥ እያውደለደለ የሚኖረውን አታላይ በምርመራ ዘበኞች እየያዙ ፀ ደ አገር ግዛት ምኒስቴር አስተላልፎ አገር ቤት እየሠራ እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋቸዋል።

እንደዚህም ሲሆን ፀብአ ክርክር ያንሳል ሰላምና ፍቅር ይበዛል ሰሎሞን በመጻሕፍቱ ውሥጥ እንዲህ ይላል ም ሳ ም ፅ ፳፪ ቍ ፲ ክርክር እንዲወጣ ፌዘኛን አውጣ ጠብና ስድብም ያልቃል ። አሁን በአዲስ አበባ ከተማችን ጥፋት ሲያደርጉ ወይም ሲሰርቁና የሐሰት ምስክር (መልቲ) እየሆኑ ተይዘው ወደ ወህኒ (ዘብጥያ)የሚገቡ በአንድ ወር ውሥጥ ቍጥራቸው ከአንድ መቶ አያንስም ይባላል።ከነዚህም እንደ ኃጢአቱ መጠን እኵሉ በእሥራት እኵሉም በግርፋት ይቀጣል ፤ አንዳንዱም እንደታሠረ በተስቦ በሽታ ይሞታል ፤ አንዳንዱም ታሥሮ ይለቀቃል በተለቀቀም ጊዜ የዕለት ምግብ እንኳ የለውምና በማጣትም ሆነ ወይም በልማድ ወደ ቀደመ ስርቆቱ ይመለሳል ። ስለዚህ ታሥሮ ሲለቀቅ ሥራ እስኪይዝ ድረስ መንግሥት የሚበቃውን ገምቶ ድርጎ ቢያወጣለት ይሻል ይመስለኛል። ወይም ቶሎ ብለው ሥራ ቢሰጡት ፈቃደኛ መሆኑ በሥራው ይታወቃል ፤ ለማናቸውም ጥንቃቄ ነገር ከላይ እንደ ተጻፈ በከተማ የሚኖረውን ወታደርና ነጋዴን ከራይ ሠራተኛና ሴትኛ አዳሪን በምን ዓይነት አስተዳደር እንደሚኖሩ ምንስ ዓይነት ሥራ እንደሚሠሩ የማግኘታቸውንም አመጣጥ በምን እንደሆነ መርማሪ ቹም በጥልቅ ሐሳብ መፈተሽና መመርመር ያስፈልገዋል ። እንግዴህ ነገሬን አሳጥራለሁ ልዑል እግዚአብሔር ለመንግሥቱ ሰፋት ለከተማው ጽዳት ለሚጥሩ ለክቡር ከንቲባ ነሲቡ የደገኛውን ንጉሠ ነገሥት ምርቃት ያድላቸው ስል ምኞቴን አቀርባለሁ ።

ክቡር ልጅ ኃይሌ ሮባንም ሹመት ያዳብር እላለሁ ። ጥቂት ተረፈ ኤርምያስ አስታውሳለሁ ዘዕሙር በብርሃን ዓዕይንቲከ አንሥር ብርሃንና ሰላም ለከ እብለከ ሖር በሰላም ወበሕይወት አብጽሕ ለነ ዜና ፤ ወለእመ ረከቡከ ዕድዋኒሃ ለሀገር (ኢትዮጵያ) ተባደር በቃለ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

በቀለ አበዬ ።

በአየርላይ ከኤሮፕላን ስለ ወረደው የአሜሪካ ሰው ደስ ብሏቸው ገንዘብ የሰጡትን ሰዎች ስም እንዳመለከትን እንቀጥላለን።

አቡነ ሳዊሮስ ።	፲ ብር
ደጃዝማች መኰንን ደምሰው ።	፴ ብር
ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ።	፴ ብር

ሊጋባ ወዳጆ ፩ ወቄት ወርቅ እንሰጣለን ብለው በቃላቸው ያስጻፉትን ደግሞ በሚመጣው ብርሃንና ሰላም እንቀጥላለን ።

ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው ለማገልገል የቀነሡ ታላልቆች ብቻ አይደሉም፡ነገር ግን ቲናንሾቱም ባለንአቅማችን መንግሥታችነንና ሀገራችነን ለመርዳት እንወዳለን ይልቁንም አሁን በውነተኛው ፀሐያችን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ከታናናሾቹ አገራቸውንም ለመርዳት ከሚወዱትም አንዱ እኔ ልሆን እችላለሁ። የልብ ሐሳብ በአፕሬሺን ሊታይ አይቻሌምና ነው እንጂ። እኔም በመቅኔ መንግሥታችነንና ሀገራችነን ለመርዳት የተነሣሁበት ምኞት ይህ ነው የኤሮፕላን ስራ ተምሬ ሕይወቴ ምንም እንደሆነች ሳልቈጥር ፍጹም አገልግሎቴን ለማሳየት የኤሮፕላን ሥራ እማራለሁ ብዬ ደጅ ጥናት ከጀመርሁ ሰባት ዓመት ሆነኝ። ፀት ታላላቆችን ብዙ ወረት ጃጅ ጠንቱ ነጻሬ ነበር ኤሮፕላን ሊመጣ አይቻልም መስሏቸው ነበርና ተስፋ አጥቼ እስከዚህ ቈየሁ እንጂ። እንዲሁም ለዚህ ሥራ እኔን የሚመስሉ ደግሞ ብዙ ይገኛሉ

የሚቻል ቢሆን ለዚህ አገልግሎት ሕይወቴን አሳልፌ መስጠቴን በብርሃንና ሰላም አገልጣለሁ። ጤፍ ከዘመዱ ጐታ ትሞለለችና። ኃይለ ጊዮርጊስ ሀብተማርያም

ማስታወቂያ ።

ማዘጋጃ ቤት ከዚህ በፊት ስለከተማው ሕዝብ ጕዳት እንዳያመጣ ሲል መጥፎ መጥፎውን ውሻ ሁሉ ለመግደል ጀምሮ እንደነበረ አሁንም ከስምንት ቀን በኋላ እንደ፡ቀድሞው መጥፎ መጥፎውን ውሻ ሁሉ ለመግደል አስቢልና ደኅና ውሻ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በየቤታቸው እንዲያሥሩ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ያስታውቃል።

ሰኔ ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርደና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ፀታች ክኅሀ ድባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ። ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

— —የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጆሮማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ማጋርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፎር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኸላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ-ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

COGNAC S.&E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
6ᵐᵉ ANNÉE № 27

ሐሙስ ሰኔ ፳፮ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም።
JEUDI 3 JUILLET 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ጸሐፊተኑ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሹ ም ሽ ር

ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ የርሻ ሚኒስቴርነት ተሾሙ። ሊቀመኳስ መንገሻ ወሰኔ ደጃዝማች ተብለው ቅምብቢትንና ትቢን ተሾሙ። ደጃዝማች መስፍን ቋሬን ተሾሙ ።

እንኳን ደስ አላችሁ ሹመት ያዳብር ።



እ ሚ አ ሳ ዝ ን ሞ ት ፦

አሁን ባለፈው በሚያዝያ ወር የደጃዝማች መታፈርያ ታና-ሽዋ ልጃቸው የቀኛዝማች ኃይሌ ሀብተሥላሴ (ዘለቃ) ባለቤት ሙተው ደጃዝማች መታፈሪ በኀዘን ቈይተው ነበር ደግሞ ታላቋ ልጃቸው ሞቱባቸው። ደግሞ የደጃዝማች ገርማሜ የልጅ ልጅ የወይዘሮ እምወድሽ ልጅ ቀኛዝማች ብርሃኔ አምና ሞተባቸው። ፪ኛ፤ ወይዘሮ አከሌ ያቆ ንዋይ ባለቤት፥ ፫ኛ ታላቁ ልጃቸው ፊታውራሪ ፍሬ ሕይወት ሞቱባቸውና የሚአውቃቸው ሰው ሁሉ እጅግ አዘነላቸው።ወይዘሮ እምወድሽ ገና በመጀመሪው ልጃቸው ሞትጊዜ ጀምረው ወደ ቤቴ አልመለስም ብለው ዝቋላ ተቀምጠው ነበር።ነገር ግን የሁለቱም ልጆቻቸው ሞት እዚያው ሔደላቸው የሞትና የኀዘን ማምለጫ የሌለውን ሰው በከንቱ ይደክማል ። እንደ ደጃዝማች መታፈሪና እንደ ወይዘሮ እምወድሽ በሽምግልና ጊዜ እንዲህ ያለ መከራ ሲደርስ እጅግ ያሳዝናል እግዚአብሔር ያጥናቸው ።

አዲስ መንፈስ በኢትዮጵያ ሰፈፈ ።

ልዑል እግዚአብሔር ኢትዮጵያ በሰላም እንድትኖርና ሕዝቧ ሁሉ በውቀት ደረጃ ከፍ ከፍ እንዲል ፈቃዱ ሲሆን በየመኳንንቱና በየመሳፍንቱ ልብ የቅንነት ሥራ እንዲሠሩና ክፉን ሥራ ጠልተው ደግ ሥራን እንዲወዱ ልባቸውን ባዲስ መንፈሱ ይጐበኝዋል።እንደዚሁም የኢትዮጵያ መኳንንቶችና መሳፍንቶች ሁሉ ወደቀናው መንገድ ሲያመሩ በማዮታችን ደስ እያለን ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። ይኸንንም ለመጻፍ ያነሳሳኝ እነሆ ብልሁና ትጉሁ ክቡር ደጃዝማች ብሩ በሲዳሞ ግዛታቸው የሠሩትን መልካሙን ሥራቸውን ዘወትር በጋዜጣ ስላነበብኩና የሌሎችንም የየመኳንንቶቹን መልካም መልካም ሥራቸውንና ሐሳባቸውን ስላየሁና ስለሰማሁ ነው ። ይኸውም ባጭሩ መጀመሪ የክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠውን አገዛዝና የግዛታቸውንም ልማትና ጸጥታ ታላቁን ቸርነታቸውንም ጥር ፳፱ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም በ፮ኛው ቊጥር በወጣው ብርሃ-ንና ሰላም በ፵፮ኛው ገጽ እንዳነበብነው ምንም መልካሙን ሥራቸውን ሁሉ በዝርዝር ቈጥሬ ለመጻፍ ባልችል መልካሙ ሐሳባቸውና የደግነት አገዛዛቸው ለመላ ኢትዮጵያ ደስ እንዲ-ያሰኝ አስረግጥላችኋለሁ ። ለዚሁም ምስክር የሚሆነውን ነገር ባጭሩ እጽፋለሁ ። ስለክቡር ራስ ናደው ሞት ለኀዘኑ ሲሉ ከልዕልት ባለቤታቸው ጋራ በእንግድነት ጊዜአቸው በጐሬከተማ ያለውን የሚካኤልንና የጊዮርጊስን ደግሞ መቱ ያለውን የሚ-ካኤልን እነዚህን ሦስቱን ቤተ ክርስቲያኖች በግምብና በቆርቆሮ ለመሥራት ኮንትራት ተዋውለው ለባለኮንትራቱ ገንዘባቸውን ሰጥተው ስለሄዱ ይኸውና ሦስቱም ቤተ ክርስቲያኖች ሥራቸው ተጀምሯል።ደግሞ በከፋ በጎ ጊዮርጊስ የሚባለውን ቤተ ክር-ስቲያንና ጐጀብ የሚባለውን ወንዝ ድልድይ ለመሥራት ከጐሬ

መሐንዲስ ቀጥርው ከብዙ ግምበኞችና አናጢዎች ጋራ ወስደዋል።ደግሞ በከፋ ተማሪ ቤት ማቆማቸውን ከሁን ቀደም ሰምተናል። በተረፈ በኢሉባቦር በእንግድነት በተቀመጡበት ጊዜያት ለችግረኞች የረዱትን ገንዘብ በዝርዝር ልቆጥረው አልችልም።ይልቁንም በጣም የሚገርመው ውጪዊ ስሙ መተያያ፡ ውስጣዊ ስሙ ማታለያ የተባለው ነገር በፊታቸው በጣም የተጠላና የተናቀ በመሆኑ የእንግድነት ጊዜአቸውን ጨርሰው እስኪሄዱ ድረስ ሰው የሚያመጣውን ሁሉ እየመለሱ ከንድ ሰው አንድ ነገር ሳይቀበሉ በመሄዳቸው የኢሉባቦር ሕዝብ ሁሉ እንደ እንግዳ ነገር ቈጥሮት የማያደንቅ የለም በዚሁም በእንግደነት ጊዜአቸው የኢሉባቦር ጸጥታና ሰላምነት እጅግ ያስደነቅ ነበር ። በዚህ በጥቂት ቀን ይኸን ያህል ቸርነት ያደረጉ በግዛታቸው ላይ ምን ያህል ቸርነት ያደርጉ ይሆን?ከቶ ሊገመት አይቻልም ።

ሁለተኛ።የቈለምና ያቢጋር አውራጃ ገገር ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ የገባሩን ግብር ማቃለላቸውንና በግዛታቸው በኩል የአቶመቢል መንገድ ለማሠረት ማሰባቸውን ባለፈው ዓመት በጋዜጣ አንብበናል። ፍጻሜው እንደምን እንደሆነ አላወቅንም እንጂ የአቶመቢሉንም መንገድ ማስጀመራቸውን ሰምተን ነበረና ስለዚህ ይህ የክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ሐሳብ እጅግ መልካም መሆኑ በየልባችን ይሰማናል። ሦስተኛ ክቡር ግራዝማች ካሣ ውቃው የላሎ ቅሌ ገገር። በግዛታቸው የሠሩትን መልካም ሥራቸውን እንደሰማሁትና እንዳየሁት ከዚህ ቀጥዬ እጽፋለሁ።የላሎ ቅሌ አገር ገገር የነበሩት ክቡር ደጃዝማች ክንፉ እንደሞቱ አገሩ መንገደኛ ባገሩ ለመተላለፍ እስኪከለክል ድረስ ባልጎ ነበር። ግራዝማች ካሣ ውቃው ይኸን አገር ተሹመው እንደመጡ ያገሩን መበለግ ስለሰሙ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደንብና ሕግ ባዋጅ አድርገው ለሕዝቡ አሰሙ ።

፩ኛ።በላሎ ቅሌ ክፍል ያለህ ገበሬም ነጋዴም ወታደርም ብትሆን መንግሥት የሠጠውን ደንብ እየጠበቅህ ያንኑ ሥራህን ሥራ እንጂ ክፉ ከሕግ የወጣ ሥራ ከመሥራት ተጠበቅ።እኔም ስለናንተ መጣሁላችሁ እንጂ አልመጣሁብችሁም ።ነጋዴም ብሰላም ነግድ ገበሬም እረስ ቡንና ጥጥ ይኸን የመሰለ አትክልት ሁሉ ትከል ። ፪ኛ በየትም ቢሆን ያለምክንያት ጠመንጃ እንዳይተኰስ ክልክል ነውና ጠመንጃ የሚተኵሰውን ሰው እየያዛችሁ ወደኔ እንድታመጡ ጠመንጃ የተኰሰውን ሰው ይዛችሁ ወደኔ ሳታመጡ የቀራችሁ እንደሆነ ጠመንጃ በተተኰሰበት ቦታ ያለው ባለመሬቱ ወይም ባላባቱ የሚገባውን መቀጫ ይከፍላል። ፫ኛ፥ ባላባቶች ሁሉ በያገራችሁ ያለውን ሌባና ቀጣፊ እየያዛችሁ አምጡ ሌላም ሰው ስደተኛ ነኝ ብሎ ወደናንተ ቢመጣ ወደኔ አቅርባችሁ የመጣበትን አገርና ወገኖቹን የመጣበትን ምክንያት አጽፎ ለመታመኛ ዋስ ጠርቶ ይቀመጣል እንጂ እንደዚሁ ዝም ብለህ እንዳታስቀምጥ።በተረፈ ማናቸውም ነገር ቢሆን ከገር ውሥጥ ቢሰርቅና ቢጠፋ ያው ባላባቱ የጠፋውን ገንዘብ ይከፍላል እንጂ አገር አውጪጭኝ መቀመጥና መቀጫ መክፈል የለበትም።ብለው ይኸን የተከከለ ሕግ ስለሰጡ መጥፎ ሥራ ይሠራ የነበረው ሁሉ ከግዛታቸው ተሰዶ ሄደ። ይልቁንም በጣም የሚገርመው ነገር በላሎ ቅሌ እስከዛሬ ድረስ ይህ ሁሉ ሻለቃ ሲተላለፍ ሌባና ቀጣፊ እየተያዘ የሚታሠርበት ወህኒ ቤት አልተሠራም ነበር። ሌባና ቀጣፊም የተያዘም እንደሆነ ለየባላባቱ እሥር እየተባለ ይሰጥ ነበር እንጂ በሻለቃው እጅ አይታሠርም ነበር።ይኸውም ወህኒ ቤት እስከዛሬ ያልታሠራበት ምክንያቱ አጭር ነው ማለት ሻለቃው ሁሉ ይህን አገር ተሹሞ እንደመጣ ወህኒ ቤቱን ለመሥራት ሲጀምር ባላባቶቹ ሁሉ እየተሰበሰቡ ወህኒ ቤት አይሠራብን እያሉ መተያያ ወይም ማታለያ በሚባለው መሣሪያ የየሻለቃውን ሐሳብ ሁሉ ሲሰብሩት ይኖሩ ነበር።ይኸውም የወህኒ ቤት እንዳይሠራ የላሎ ቅሌ ባላባቶች የሚጨነቁት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው ማለት ሲሰርቅና ሲቀማ የሚገኘው የነሱው ወገን ስለሆነ ወህኒ ቤት ካልተሠራ የሚታሠረው በኛው እጅ ነውና ከማናቸውም ጕዳት እናድነዋለን በማለት ነው።ይኸውም ሓሳባቸው እስከዛሬ ፀንቶላቸው ይኖር ነበር ማለት ድረስ የላሎ ቅሌ አገረ ገዥ ወህኒ ቤት ስለሌለው ሌባና ቀጣፊ ሲያዝ እሥር እየተባለ ለባላባት ይሠጥ ነበር።ያም ባላባት ያ ሌባና ቀጣፊ ወገኑ ስለሆነ ለማሠር ከቤቱ ወስዶ እሥራት በሚባለው ቅጣት ፈንታ ሙሽርነት በሚባለው ቦታ እያስቀመጠ ይለቀው ስለነበረ በላሎ ቅሌ ሌባና ቀጣፊ እምብዛም ርቆ አያውቅም ነበር።አሁን ግን ግራዝማች ካሣ ውቃው የሀገሩን ገዥነት ተቀብለው እንደመጡ የሥራቸውን መጀመሪያ ወህኒ ቤት መሥራትን አደረጉ።ባላባቶቹም ካሁን ቀደም እንደለመዱት መተያያ ወይም ማታለያ የሚባለውን መሣሪያ ይዘው ወህኒ ቤት አይሠራብን ብለው ቢለምኑዋቸው በብርታታቸው ይኸን (መተያያ) ወይም ማታለያ የሚባለውን ታላቅ መሣሪያ ሰባብረው ስለጣሉት ያሰቡትን ሓሳብ ለመፈጸም ተመችቷቸው ዛሬ በላሎ ቅሌ ያሠሩት ወህኒ ቤት እጅግ ያለመጠን ያስደንቃል ይባላል ። ሌባና ቀጣፊም ይህ ወህኒ ቤት መሠራቱን አይቶ እንግዲህ በጥፋት ሥራ ከተገኘ ብርቱ ቅጣት እንዲያገኘው ተረድቶ ከግዛታቸው በመሰደዱ ዛሬ አገሪቱ አማን ሆናለች ደግሞ ክቡር ግራዝማች ካሣ ውቃው ዋና ቅጣት ማለት ብርቱ ሥራ መሠራት መሆኑን አውቀው በወህኒ ቤት የታሠረውን እሥረኛ የድንጋይ መንገድ ለማሠራት ለዚሁ መሣሪያ መዶሻና ድጅኖ ይኸን የመሰለ መሣሪያ ሁሉ ከጐሬ አስገዝተው አሰስደዋል ይልቁንም በጣም የሚደነቀው ይኸን ወህኒ ቤት በማሠራታቸው ባላባቶቹ እንደኃጢአት ቈጥረውት ክሳቸውን ወደመንግሥት አቅርበው ነበር ስለሚባለው ወሬ ነው ። አሁንም ክቡር ግራዝማች ካሣ ውቃው እስከዛሬ በግዛታቸው ስልክ አልገባም ነበርና አሁን ለማግባትና ሌላውንም ቃላላቁን ነገር ሁሉ ለመሥራት ያስባሉ ይባላል።እንደዚህ መልካም ሥራ ለመሥራት መልካም ሐሳባቸውን ለሚያቀኑ ለኢትዮጵያ መኳንንቶችና መሳፍንቶች ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር በመልካሙ ሥራቸው ሁሉ እንዲረዳቸው የሁላችንም ምኞት ነውና ለቅን ሠሪዎች መኳንንቶችና መሳፍንቶች ሁሉ ጤና ሕይወታቸውን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን እንለምና ለን።ክቡራኞች ሆይ ለሰው ከሞተ በኋላ ዋናው መታሰቢያው መልካሙ ሥራው ነው እንጂ ታላቁ ጌትነቱ ሁሉ ከሞት

ከኋላ ምንም ላንድ ቀን እንኳን መታሰቢያ አይሆነውም ። እነሆ ብልሁና ትጉሁ ክቡር ራስ ናደው አሁን ከዕረፍታቸው በኋላ ወደኣቢያቸው ሐደን ስንመለከት ያ ሁሉ ጌትነታቸውና ማዕረጋቸው አሁኑ መረሳት ጀምሩዋል ። ግን በያለበት ያለው ለዘላለም የማይሞተው መልካሙ ሥራቸው በየመንገዱና በየወንዙ በየቤተ ክርስቲያኑ በታናሽ በታላቁ አፍ ሲነበብ ይውላል ። ይኸውም ክቡር ራስ ናደው የሠሩት መልካም ሥራቸው ሁሉ እስከ መጨረሻው ትውልድ ድረስ ለስማቸው መታሰቢያ ሁኖ እንደሚኖር አይጠረጠርም ። ክቡራኖች ሆይ እንግዲህ ሰው ከሞተ በኋላ ለሰው ዋና መታሰቢያ የሚሆ- ነው መልካሙ ሥራው መሆኑን ከተረዳነው ጊዜአችን ሳያልፍ መልካም ሥራ ለመሥራት መሽቀዳደም ይገባናል ።

ከዚህ ቀጥዬ (መተያያ) የሚባለው ቃል ማታለያ ማለት መሆኑን ስለጻፍሁ ብዙ ሰዎች ይደነቁ ይሆናልና ይኸነን በጭር ቃል ላንባቢዎች ለማስረዳት እወዳለሁ፤ መጀመሪ መተያያ የሚሉትን ነገር ወደሹሞችና ወደዳኞች የሚያመጡት ከሰው በተጣሉ ጊዜ ባላጋራዬን ለማጥቃት እንዲቻለኝ ዕርዳኝ ሲሉ ያልሆነውን ነገር ባላጋራቸው እሱለበት ተናግረው ዳኛውን ለማታለል ነው ።

፪ኛ መንግሥት ያቆመውን ደንብ ሰብረው የሚገባው መቀጫ በተቈረጠባቸው ጊዜ ይህ ነገር የሆነብን በስሕተት ነው እንጂ አውቀን አላደረግነውም በማለት ሕግ አስፈጻሚ- ውን ለማታለል ነው ።

፫ኛ ሰርቀውና ቀምተው ሲገኙ የሚገባውን ቅጣት እን- ዳይቀጡ ቀን ጥሎን ነው እንጂ እኛ እንደዚህ ያለው ልማድ አልነበረብንም በሚባለው ምክንያት ቀጭዎችን ለማታለል ነው።

፬ኛ በንግድም ሆነ ወይም በማናቸውም ሥራ ቢሆን ብዙውን በጥቂት ለመግዛት እኛ ሥራ ከመፍታት ይሻለናል ብለን ነው እንጂ ምንም ጥቅም የለበትምና እንደዚህ ያለው- ውል ይፈቀድልን ሲሉ የውል ሹሞችን ለማታለል ነው ።

ስለዚህ መተያያ የሚመጣው ይኸን በመሰለው ነገር ሁሉ ስለሆነ እርግጥ ማታለያ ማለት መሆኑን አምናለሁ ። ግን አን- ዳንድ ሰዎች ነገሩን በጣም ሳይመረምሩ ይህን መተያያ ወይም ማታለያ የሚባለውን ነገር ስሙን ለውጠው ኮሚሲዮን ይሉ- ታል እንጂ በሌላውም አገር ክፍል ይቀበሉታል የሚሉ ሰዎች ይኖራሉ ። ግን ይህን ሐሳብ የሚናገሩ ሰዎች ነገሩን ሳያስተ- ውሉ ይሆናል ኮሚሲዮን ማለት የድካም ዋጋ ነው እንጂ ወደ መተያያ ወይም ማታለያ ወደሚባለው ቋንቋ አይጠጋም። ማለት ኮሚሲዎን የሚሰጠው ሰው ገንዘብ ተበድሮ ስጠኝ ሲሉት አልሰጥም ያለ እንደሆነ (አበካነት) ጥብቅና የሚያውቅ ተፈልጎ እገሌ ይኸን ያህል ገንዘብ ተበድሮ ከለከለኝ ይህን ሰውዬ በዳኛ ይዘህ ገንዘቤን የተቀበልክልኝ እንደሆነ ከምት- ቀበልልኝ ገንዘብ ከ፻ ፭ ወይም ከ፻ ፲ ኮሚሲዮን እሰጥሃለሁ ብሎ ይዋዋለዋል ይህም ለዚያ (ላበካ) ለጠበቃ የደከመበት የድካሙ ዋጋ መሆኑ አይጠረጠርም ።

፪ኛ አንድ ነጋዴ ብዙ ሸቀጥ አምጥቶ በቶሎ አልነግለት ሲለው ደላላ ለሆነ ሰው ይኸን እቃዬን እያዞርክ የሸጥክልኝ እንደሆነ ከትርፉ ከ፻ ፳ ወይም ከ፻ ፴ እሰጥሃለሁ ብሎ ይዋዋ- ለዋል ይህም ለዚህ ለደላላ የደከመበት የድካሙ ዋጋ መሆኑ አይጠረጠርም።እንደዚሁ ሁሉ ኮሚሲዮን የሚባለው ነገር የሚ- ሰጠው ይኸን በመሰለ ነገር ስለሆነ ወደ መተያያ ወይም ማታለያ ወደሚባለው የተጠጋ አለመሆኑ እርግጥ ነው።ሁለተኛ አንዳንድ መምህራኖች መተያያ ወይም ማታለያ የሚባለው ከመጽሐፍ ያለ ነው እያሉ (ኢትቁም ራቀከ በቅድመ ነቢየ እግዚአብሔር ዘእንበለ አሐቲ ግርሽ) የእግዚአብሔር መንፈስ ባደረበት በነቢዩ ፊት ስትቀርብ ያላንድ ግርሽ ባዶ እጅ- ህን አትቁም የሚለውንና ጌታ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻም ሰጡት ወርቅ ዕጣን ከርቤም የሚለውን ጥቅስ ያስጠናሉ ። ግን እኔ ምንም የመጽሐፉን ትርጉም ጠንቅቄ የማላውቅ ብሆን እንደሚመስለኝ (ኢትቁም ራቀከ በቅድመ ነቢየ እግዚአብሔር ዘእንበለ አሐቲ ግርሽ) የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን መልካሙንና እውነተኛውን ነገር ሳትይዝ እግዚአብሔርን የሚያስከፋውን ክፋውን ሥራህን ይዘህ የእግዚአብሔር መንፈስ ባደረበት ነቢይ ፊት አትቁም ሲል የተናገረው ይመስለኛል እንጂ ስለ ገንዘብ የተናገረው አይመስለኝም፤ይኸስ ባይሆን ነቢዩ ገንዘብ አምጥተው በሰጡት ጊዜ ባልመለሰም ነበር ። ደግሞ ጌታ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ የሰብአ ሰገል ሰዎች ወርቅ ዕጣን ከርቤ አመጡ- የሚል እንጂ ተቀበሏቸው የሚል አላነበብንም ። መተያያ መቀበል በመጽሐፍስ ያለ ቢሆን በብሉዩና በሐዲስ በብዙ ሥፍራ በማናቸውም ምክንያት መተያያ እንዳንቀበል ባልከ- ለከለን ነበር ። ይኸንኑም ለመረዳት የሐዋርያት ሥራ ምዕ ፰ ከቁጥር ፲፰-፳፬ መዝሙረ ዳዊት ፳፮ ከቍጥር ፱ ፲፩። ትንቢተ ኢሳያስ ም ፴፫ ከቍጥር ፲፬-፲፯ አሞጽ ፭ ከቁጥር ፲፩ ፲፫ ኢዮብ ም ፲፭ ከቁጥር ፴፫-፴፭ በጣሙን እንብበህ ተመከት። ሰብአ ሰገል አመጡት ስለ ተባለውም ለሕይወቱና ለሞቱ ምሳሌ መሆኑን በየሊቃውንቱ አፍ ሲተርክ ስምተናልና ወደ መተያያ ወይም ወደ ማታለያ ልናስጠጋው አይገባንም ። ይኸ- ንኑም የመጻሕፍትን ትርጉም ጠንቅቀው የሚያውቁ ዘርዝረው- ሊያስረዱን ይችሉ ይሆናል።ቢሆንም የመንፈሳዊ ስጦታ ሕፃ- ናት ተምረው እውቀት ለሚያገኙበት ለተማሪ ቤትና የእግዚ- አብሔርን ወንጌል ለሚሰብኩ ሐዋርያቶች እርዳታ መስጠትና ይኸን በመሰለው ነገር ሁሉ የሚሰጠው እግዚአብሔርን በማ- ሰብ በበጎነት ሥራ የተሠራ ታላቅ ቸርነት ነው ይባላል እንጂ ወደ መተያያ ወይም ማታለያ ወደሚባለው ነገር በምንም አይ- ጠጋጋም።እንግዲህ መተያያ የሚባለው ነገር በርግጥ የክፋትና የጭካኔ ሥራ መሥሪና ማታለያ መሆኑን ከተረዳን በኋላ አውቆ መታለል እስከ ራቁትነት መሔድ ድረስ ያደርሳልና አውቆ ከመ- ታለል እንጠበቅ ስል ሐሳቤን እገልጻለሁ ። አውቆ መታለል እስከ ራቁትነት መሔድ የሚያደርስበትን ከመጽሐፍ ያገኘሁትን ታሪክ በሚከተለው ጋዜጣ ልጽፍላችሁ እመኛለሁ ።

ታናሽ ወንድማችሁ ጋ ጊ ወልደ አማኑኤል ።

የምክር ቃል ።

የአሮፓ ሕዝብ ክብረ በዓል እጅግ ይወዳል ። አገሩንም ያስከብራታል ማስከበሩም ክብሩ የርሱ ነው ፣ ክብረ በዓል መቼ በደረሰልኝናቤቱን በሰንደቅ ዓለማና በኤሌትሪክ አሳምሬ አጊጬ ለሚተላለፈው ሕዝብ ደስ እንዲለው ከጐሮቤቴም ይበልጥ አጊጫለሁ ብሎ እንዲመክ ይጥራል ፣ በፓሪስ ከተማ በክብረ በዓል ቀን ያያት ምን ያህል ደስ ታሰኛለች ከመንግሥትዋ ክምትጌጥ ከሕዝብዋ የታሰበላት ይበልጣል ።

የሀገራችን ሕዝብ ግን መንግሥት ሲያጌጥ እንዲያይ ይፈልጋል እንጂ ራሱ ላድርግ ልሥራ ላሰምር ልርዳና ክብሩ ለንጉሤ ቢሆን ላገሬ መክበሯ ነው ። ክብሩ ለኔም ይደርሰኛል አይልም ። ይህን አለማለቱ የገንዘብ ማጣት የዕውቀት ማነስ አይደለም እኔ ምን ቸገረኝ እንደ ማለት ይመስለኛል እንጂ ገንዘብና ዕውቀት አያሻም በመንገድ ዳር ያለውን ቤቱን ኖራ ቢቀባ ቆርቆሮ ቢያለብስ ይችላል።ሰፈ በታ ከመያዝ ትንሽዋን ማሳመርና ሥራ ማስያዝ ይበልጥ ነበር ይመስለኛል ፣ ለሌላ ቢሆን ተበድሮ ለከንቱ ያጠፉዋል እንጂ ከብዙው ጥቂቱ ነው በንደዚህ ያለ ገንዘቡን የሚያለማ። መንግሥት ግን ለሕዝቡ ቤት ማስጌጫ ቢያስላብት ጉዳት ነው ሕዝቡ ሲጥር መንግሥት ሲረዳው ይሻላል እንጂ ፈጽሞ በመንግሥት ላይ መጣል አይገባም። ሁለት ዓመት በወዝ ዓመት በደመወዝ እንደሚባለው መንግሥት ዘለዓለም ረድቶ አይዘለቅምና መንግሥትን ደስ ለማሰኘት ከተማውን እንደተቻለ ማሳመር ማስጌጥ ነው ። ንጉሥ ደስ ቢለው ደስታው ለሕዝቡ ነው ። አገር ቢከብር ክብሩ የሕዝቡ ነው ፣ መንግሥት ቢከስር ላገር ነው ፣ ሕዝብም ቢከስር ላገር ነው አብሮ መግደል ሸሽቶ ማምለጥ ሁለቱም ጥቅም ነው ፣ እንደሚሉት ነውና ሲሆን በራሳችሁ ጕልበት በመንገድ ዳር ያላችሁ ባለበታ ቤታችሁን ከዛሬው አድሳችሁ አሳምሩ እንጂ የመንግሥትን እርዳታ መጠበቅ አያሻችሁ ስል ሐሳቤን አቀርብላችኋሁ ።

ክ መ ያ አ

ከአዲስ አበባ በጅማ ገምቤላ የአቶመቢልና የሐዲድ መንገድ ማኅበር አክስዮን ለሕዝብ እንዲገዙ ማስታወቂያ

ያገሩ ንግድና ሀብት እንዲያድግ ለሕዝቡም እንዲመቸውና እንዲከናወንለት የተራራቁትንም ያገር ክፍሎች ሰዎች ስምምነታቸውና ወዳጅነታቸው መደጋገፋቸውም እንዲጨመር የመንግሥትም ያስተዳዳሪነት ሥራ ፍጹምነቱና አሰኪያጅነቱ እንዲሻሻል ባገር ውሥጥ በፍጥነት መንገድ የሚያመላልሱ ነገር እንደሚያስፈልግ በጣም የታወቀ ነገር ነው። መንግሥታችንም የዚህን ነገር ጥቅም ስላወቀው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ፈቃዳቸው ሁኖ በጅማ በኩል ከአዲስ አበባ ወደ ገምቤላ የሚሔድ የንግድ እቃና መንገዶች የሚያመላልስ የአቶመቢልና የባቡር መንገድ ለመሥራት ለጃንሆይ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኮንሲስዮን ፈቃድ ሰጥተው ነበር። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታታችንም የራሳቸውን ጥቅም ብቻ የማይፈልጉ ስለሆኑ ለራሳቸው ብቻ የተሰጠውን የመንገድ ሥራ ፈቃድ የሚሠዙቱ የኢትዮጵያ ሰዎች ከሆኑ ማኅበር ጋራ አብረው ለመሥራት ማኅበሩንም ለመርዳትና ለማበርታት የ፳ ሚልዮን ብር አክስዮን ይገዛሉ ። መንግሥታችንም በዚሁ ሐሳብ ለዚሁ ሥራ አንድ ሚልዮን ብር ሊያወጣ ቃል ሰጥቶዋል። ነገር ግን መንግሥት ከኩባንያው አክስዮን መግዛቱ አንዳንድ ተራ ማኅበረተኛ ሁኖ ነው እንጂ በኩባንያው የሥራ አስተዳደር የዋናነት ሥራ ሊሠራ ማለት እንዳልሆነ አገልጽላችኋለሁ የሥራውስ ሥልጣኔ ሁሉ ፈጽሞ ኩባንያው ራሱ በሾማቸው ዲሬክተሮችና ሹማምንቶች እጅ ይሆናል ። የኩባንያው ዋና ገንዘብ ለመጀመሪያ ሺሚልዮን ብር ይሆናል ይህም ገንዘብ የአቶመቢሉ መንገድና የጽፈት ቤት የባቡር ማረፊያዎች ይሠራበታል፤ መንገደኞችና ዕቃ የሚያመላልሱ አቶመቢልና ካሚዮን ይገዛበታል ብዙ ገንዘብ የሌላቸውም ሰዎች በዚሁ ሥራ ተካፋዮች ሊሆኑ እንዲችሉ ብለን ያንዱ አክስዮን ዋጋ ላሁኑ ሁለት መቶ ብር ሁኖ ተወስኖል ማለት አንድ ሰው ሁለት መቶ ብር ከፍሎ በማኅበሩ ሊገባ ይችላል። ከሚገኘው ገንዘብ በከፈለው ገንዘብ ሒሳብ ድርሻውን ባመት ባመት ይቀበላል። በግምት በታሰበው በታሰበው ሒሳብ ዓይነት ባመት ከመቶ ዓሥር ትርፍ እንደሚገኝ ተገምቷል ይኸም በግምት የታየ ትርፍ በዚሁ ሥራ በሚገኙ ጥቅሞች አንዱ ብቻ ነው በጣም አገራቸውን የሚወዱ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለሀገር ልማትና ለራሳቸውሀብት ሲሉ በዚሁ በዋና የሕዝብ ሥራ ተካፋዮች እንደሚሆኑ አያጠራጥርም። ደልቄንም በዋና ትልቅ ሥራ እምነትና ድፍረት በጣም እንደሚያስፈልግ ሁሉም ያውቀዋል፤ ግን ያገራችን ሰዎች ይህን የመሰለ ሥራ ስላልተጀመረ ለማመንና ለመድፈር የሚሰጉ ስለሆነ ብልሁ ንጉሣችን ያገራችንን ልማትና ሥልጣኔ እንዲበዛ ለሕዝቡም ወደፊት በመልካም መንገድ ንግድ እንዲሰፋ ብለው በልግስናና በመልካም ፈቃድ አንድ ሚልዮን ብር ሊያወጡ ዝግጁ ናቸው ደግሞ ሥራው እንዲከናወን ሊረዱ የሚገባውንና የሚቻላቸውንም ሁሉ ሊያደርጉ ፈቃዳቸው ነውና ይኸ ለሕዝቡ እምነት ሊሰጠው ይችላል ። ዋና ፈሪ ለሆነውም ሰው ላይሰጋና ሳይዘገይ በዚሁ ሥራ አክስዮን እንዲገዛ ያደፋፍረዋል ኋላ ግን የሥራው ትርፍ እያደገ ሲሔድ የአክስዮኑ ዋጋ ከፍ ይላልና ያን ጊዜ በውድ ከመግዛት አሁን መግዛት እንደሚሻል ማመልከት ይገባል አሁንም አክስዮን ልትገዙ የሚትፈልጉ ሰዎች ሁሉ ከኔጋራ ተነጋገሩ እርሱም አክስዮን የገዙትን ማኅበርተኞች ስም በደብተር እንዲገባ አቶ ወልደ ጻድቅ ጋሼ ታዚል ይኸ ጥቅም ለገዛ ራሱና ላገሩ የሚበጃት ሥራ መሥራት ማለት ነውና ከዚሁ ልዩ ከሆነ ዕድል አለመቅረት ነው ስንል እናስታውቃለን ። የዚህን የሥራ ደምብ ስታቴ የሚባለውን በሚከተለው ጋዜታ እንጽፋለንና ከማኅበሩ የሚገባ ሰው ሁሉ ይህን ተመልክቶ ቅር የሚለውንና የጐደለውንም መጥቶ እንዲጠይቅና እንድንማከር መፍቀዳችንን በማክበር አመለክታለሁ ።

አዛዥ ወርቅነህ ።

ዓይን ሲአይ ልብ ሲአውቅ ስለመዘረፍ ።

የሁለት ተማሪዎች ወቀሳና ተክንካኝ፡ መትከነከን የተዋያዩት የዋይታ ዋይታ ።

ተንከንካኝ ፥ ሰማህ ወይ ወንድሜ ወቀሳ እረ ስለምድነው በሀገራችን ውሥጥ ይህ ጊኒ የሚባለው ወርቅ ፡ ፈረሱን ጭኖ ሽምጥ በብራችን ላይ የሚጋልበው፥? ምሥጢሩን ታውቀው አለህን ፥ ? እሌላ አገር እንደማየው እንኳን ሽምጥ ሊጋልብና ደንገላሳ እንኳን ሊያደርግ ሥልጣን የለውም ።

ወቀሳ ። እንዴት ሽምጥ ሲጋልብ አየኸውን በሌላው አገር አምስት ብር ብቻ ሲመነዘር ፥ በሀገራችን ከምስት አስር ብር ካሥር አሥራ አንድ፥ ደጋሞም አሥራ ሦስት ፡ አሥራ አራት፥ አሥራ አምስት ብር ድረስ ስለመመንዘሩ ነው ፡ ? ዋ ጉድ ወንድሜ ሆይ ከሐያ ብር እንዳይደርስ ነው የምፈራው ።

ደግሞስ ሰማህ ወይ ፥ እረበል እረ እንዴት ያለህ ሰው ነህ፥እኔን ነው እንዴ የምትጠይቀው፥ እኔ ሥራዬ ነው እንዴ? በል ፥ ? ወዬው ጉድ ፥ ባልደረባዬ በትሆን ኖሮ አሳይህ ነበር። ሰማህ ወይ በል ፥ መከራህን መጨረስ እምሮህ የለምን ሞከረው ፥ የአገርህን የንግድ ሚኒስቴር ፥ የገንዘብ ሚኒስቴርና ዲሬክተሮቹን ጠይቃቸው መልክም አርገው የሚአስፈልገውን መልስ ይሰጡሀል ።

ተክነካኝ ፥ ሰማህ ወይ ወንድሜ እረ ስለምንድነው እንዲህ አርገህ የተቈጣኸው ፥ ይህን ስለጠየቅሁህ ክፉ ነገር ሆኖ ነውን።

ወቀሳ (ውቅሽ ፥) ቶሎኝ እባክህ ወንድሜ ፥ የበረደልኝን ንዴቴን አታስነሳብኝ፥ይልቁንም ይህን ጊኒ የሚባለውን ወርቅና ፥ ፍራንክ የሚባለውን ወረቀት ስሙን እፊቴ አታንሳብኝ።

ተንከንካኝ ፥ ምነው ፥ ምን አረገህ ፥ ምን ደባ ዋለብህ ፥ እንዲህ የምትንገፈገፈው ፥ ንገረኝ ምን ውሎብሀል ።

ወቀሳ ፥ አኸ ፥ ወይ እኔ ፥ ወይ ነዶ ? ተክንካኝ ልትሰማው ትፈልጋለህ የእንግሊዝ ጊኒ የዋለብኝን ደባ ? ልናዘዝልህ? ያውልህ በትክክል ስማኝ የእንግሊዝ ጊኒ ገድሎኛል እኮ በል፥ እንገቴን እኮ ነው እርዶ የጣለኝ ፥ መቀንፈሻዬን ፥ መፈናፈኛዬን ፥ እኮ ነው ዘግቶ አፍኖ የያዘኝ ፥ ልንገርህ ፥ ? ትሰማው፥ ትረዳው ፥ ? ምናልባት አንተን በጣም አይነካህ ይሆናል እኮ በል

ተክንካኝ ፥ ንገረኝ እባክህ ሰምቸው ልረፍ ምን አረገህ ምን ደባ ዋለብህ የእንግሊዝ ጊኒ ።

ውቅሽ ፥ ወይ ነዶ፥ ወይ እኔ ፥ ያደረገኝን ልትሰማው ትፈልጋለህን የእንግሊዝ ጊኒ ያደረገኝን ጉድ ፥ ስማኝ ያውልህ።

ከዛሬ ሦስት ዓመት በፊት እዚህ በምታየው ባለንበት አገር ሳለሁ ፥ የአንድ ሺ መቶ ብር ወረቀት በኪሴ ነበረኝ፥ ያለሱም ሌላ የለኝም ነበር፥ ደኸውልህ ወንድሜ ሆይ በኪሴ ቋጥሬ ብዙ ቀን ከቈየሁ በኋላ፥ ይጠፋብኛል ፥ ወይም የልጅነት ባሕርይ ያስተኝና አጠፋዋለሁ ብዬ ፈርቼ ላጐቴ አዲስ አበባ ላለው እንዲከትልኝ ላኩለት ፥ ታውቀዋለህ እንዴት አድርጌ የላኩለት ይመስልሀል፥ያን ጊዜ ታዲያ ወንድሜ ሆይ በሀገራችን አንድ የእንግሊዝ ጊኒ ወርቅ፥ አሥራ አንድ ብር ነበር የሚመነዘረው ፥ ይኸውልህ እዚህ ለለንበት አገር እባንክ ሒጄ ገንዘቤን ለመቶ ጊኒ ወርቅ ወረቀት ለውጬ ወደ አጐቴ ወደ አዲስ አበባ ላኩለት ፥ እንግሊዝ ባንክ ሒዶ ወረቀቱን ሰጥቶ ሺ መቶ ብሬን ተቀብሎ እንደከትልኝ ለምኘው ። ይኸውልህ እሱም ሺ መቶውን ብር ተቀብዬ ከትቼልህ አለሁ ብሎ ጻፈልኝ፥ እኔም ደስ ብሎኝ ስኖር ነበር ። አሁን ይኸውልህ ዓሥር ቀንይሆናል ትልቅ ችግር ስላገኘኝ ከችግሬ ለመውጣት በቶሎ ላክልኝ ብዬ ላጐቴ ወረቀት ጽፌለት እሱም በቶሎ እንደ ደንቡ አዲስ አበባ ባለው በእንግሊዝ ባንክ በኩል መንዝሮ ወረቀቱን ላከልኝ፥ ታዲያስ በል ስንት ጊኒ ወርቅ ይመስልሀል የተቀበልኩት ታውቀዋለህን ፥ የሰደድኩውን መቶ ጊኒ ትለኝ ይሆናል አይደለም አሰት ሰባ ሦስት ጊኒ ብቻ ነው የተቀበልኩት። ስለምን በሀገራችን ባብራችን ላይ የእንግሊዝ ጊኒ የሚሉት ወርቅና ፍራንክ የሚሉት ወረቀት በሀገራችን በብራችን ላይ ፈረሳቸውን ጭነው ሺምጥ ስለሚጋልቡበት መሆኑን ተረድቼ እንባዬን እያፈሰስሁ ጣረሞት እንዳያዘው ጥርሴን እያፋጨሁ ፥ ዓይኔ እያየ ገንዘቤን ጊኒ ዘርፎኝ ይኸውልህ ተቀምጬ አለሁ ።

ሰማህ ወይ ወንድሜ ከዚች ከትንሽ ገንዘቤ ላይ ስንት ያጐደለብኝ ይመስልሀል ፥ ታውቀዋለህ ፤ ያውልህ ሁለት መቶ አርባ ብር ነው የዘረፈኝ ወይኔ፥ ወይጉድ ፥ ወዬው እኔን።

ተክንካኝ። ዋዋ። አዬጉድ። ወንድሜሆይ የማን ጥፋት ይመስልሀል ፥ ከዚህ ለማምለጥ የምንችለው የገንዘቡ ጠባቂዎች እረኛዎቹ በጣም ብርቱ ተታጋዮች ደረተ ሰፊዎች፥ አጠላለፍ አዋቂዎች፥ሁነው ይህንን ዋለው ካላዳኑን በተቀር ተቀማን ተዘረፍን፥ ተወረስን፤ ማለት ነው።

የሆነው ሆኖ ሰማህ ወይ ወዳጄ አሁን እንዲህ ያለውን ትልቅ ጉዳታችንን ወየው ጉድ ጉዳታችን አላለሁ ጉዳታቸውን ብል ይሻላል ይሆን የንግድ ሚኒስቴር ፥ የገንዘብ ሚኒስቴር ዲሬክተሮቹ አያውቁት ይመስልሀልን አዬ ጉድ አትጠራጠር ደኅና አርገው ያውቁታል፥ ምን አልባት እኛ የማናውቀው ትልቅ ምሥጢር አጓጉቸው ይሆናል እንጂ በደኅና እንዲህ ዝም ያሉ አይመስለኝም።

ውቅሽ። ሰማህ ወይ ወንድሜ እረ ነገሩ የሚገርም ነው አርዝሞስ ሲመለከቱት እኔ ለዚች ለትንሽ ብር እንዲህ እንዲህ ስቃጠል እረ ብዙ የሚአጠፉት ምን ይውጣቸዋል፥ የሀገራችን መንግሥት እንዴት እንዴት አርጎ ችሎታል በል። ተመልከት እስቲ የኛ ገንዘብ በሀገራችን በገዛ አገራችንየረከሰ ሲሆን ጊዜ ፥ የሰው አገር ገንዘብ ይልቁንም በሀገራችን የተወደደ ሲሆን ጊዜ እኛ ኢትዮጵያኖች የሚአስፈልገንን ነገር ሁሉ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እቃ ሳይቀር ከውጭ እያስመጣን ሲሆን ጊዜ የምንኖረው ምን ይውጠን፥ ምን እንሆን ይመስልሀል፥–

እዬው እስቲ በምሳሌ እጐረቤታችን እግብፅ አገር፥ አንድ ጊኔ የእንግሊዝ ወርቅ አምስት ብር ብቻ ነው የሚመነዘረው የፈረንሳዊም ፍራንክ በአንድ በግብፅ ብር ሐያ አምስት ነው የሚመነዘረው፥ በልስቲ በኛ ሀገር ብቻ ምን መጣብን ፥ ምን

ሆነናል እንዲህ፡ የምንደረገው ዓይናችን ፈጦ እያየ ልባችን እያወቀ፣ እስከ መቼ ነው እየተጐዳን እምንቀመጠው፡

ተከንካኝ። ወይ ጒድ፥ ወንድሜ ሆዬ ምን ይሁን ትላለህ ነገሩ ግን በጣም የሚገርም ነው እኔ ግን የማስበውን ሌላ ቀን ነው የማጫውትህ፡ግን የሆነው ሆኖ ሥልጣን ያላቸው ጠባቂ እረኞች ያለጥርጥር መልክም የሆነ መድኀኒት እንዲያገኙለት ሙሉ ተስፋ አለኝ፡

ውቅሻ። እንዴት በል፡ ተስፋ አለን ትላለህ፡ ከንደዚህ ያለው ቀማኛ እያድኑንም ብልህ ትጠረጥራለህ እንዴ በል፡ እ-ንዴት ሲዘረፉ ሲቀሙ ዓይናቸው እያየ ልባቸው እያወቀ፡ ያለፈው ያነሰ ይመስል ዝም ብለው ያዘርፉን፡ ያስቀሙን ይመ-ስልሀል፣ ውሸት ውሸት አትጠራጠር፡ በቶሎ ነው ከዚህ ከቀማኛ የሚያድኑን።

ተከንካኝ። ሰማህ ወይ ውቅሻ፡ ወይ ጒድ ሲእስቡትስ በጣም ይገርማል፡ እራስ ይዞ ያስጮሃል፡ አየው በምሳሌ የግብፅ መንግሥትና የኛ አገር መንግሥት ጕረቤታሞቼ እቃ ለመግዛት፡ ከፈረንሳዊ ወይም ከእንግሊዝ አገር ቢፈልጉ በኵል ዋጋ ይገዙ ይመስልሀል፣ አሰት ውሸት፣ የኛ አገር መንግሥት የበለጠ ገንዘብ ካላፈሰሰ ሊገዛው አይችልም። ታዲያስ ስለምን ድነው፣ ይታወቃሀል በብራችን በሀገራችን ገንዘባችን ላይ ጊኒ የሚሉት ወርቅና ፍራንክ የሚሉት ወረቀት ፈረሳቸውን ጭ-ነው ሽምጥ ስለሚጋልቡበት ነዋ ገበሀ በምሳሌ የግብፅ መንግሥት ክፈረንሳዊ፣ በአምስት መቶ ሺ ብር መኪና ቢገዛ የኛ አገር መንግሥት እንደዚሁ የመሰለውን መኪና በስንት ብር ይገዛይመስልሀል ፤ ታውቀዋለህ፡ ባምስት መቶ ሐያ ሺ ብር ነው የሚገዛው፡ እየሀልኝ፡ ሐያ ሺ ብር ለሌባ፣ ለቀማኛ መል-ቀቃችን፣ ነው ፤ ስለምን በሀገራችን ላይ የሰው አገር ገንዘብ ስለተወደደ የኛ የራሳችን ገንዘብ ስለረከሰ ነው፣ አስበው እስቲ ወንድሜ፡ የኛ ብርና የግብፅ ብር በክብደትም ብትል በሥራም ብትል በሁሉም ነገር እኩል ነው ።

ታዲያስ ፤ ምን አለ ፤ የግብፅ አምስት ብር አንድ ጊኒ ያወጣል ፤ ግን የኛ አገር ብር አሥራ አምስቱ አንድ ጊኒ ያወጣል ፤ ሌላ ነገር ምንም ፤ የለም አየኸው ወንድሜ ።

ወቃሽ። ወየው ጒድ ምን ይሁን ትላለህ ወንድሜ ሆይ። ሥልጣን ያላቸው ጠባቂ እረኞች በጋቸውን ዓይናቸው እያየ ልባቸው እያወቀ ተኵላና ቀበሮ እየሰረቀ እየዘረፈ ወስዶ እንዳይጨርስብን ትጉህ እረኞች ሆነው ከዚህ ከቀማኛ ዘራፊ በጋቸውን ተከላክለው ተከራክረው እዲያድኑልን፣ የናታቸውን የኢትዮጵያ አምላክ መድኀኔ ዓለም ይርዳቸው ልቡና ይስጣቸ እያልን ልመናችንን እናረዝማለን። ሁላችን የኢትዮ-ጵያ ልጆች።

አንዱ የኢትዮጵያ፡ ተማሪ፥ መ ወ ይ።

ማስታወሻ።

የወታደር ሰልፍ ትምህርት ካግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ብዙ የጦርነት ሰልፍ የተማሩና የሠለጠኑ አሉ ነገርግን አስቀድሞ ለሰልፍ መምህራኖቹ ለወታደር ሰልፍ የሚሆኑ መጻሕፍት መንግሥት ሊሰጣቸው ይገባ ነበር አሰጣጡንና ሰልፉን አካሄድ የጦር ምንስቴሩ ለሰ ልፍ-የሚሆኑ ቃሎች ጽፎ አሰናድቶ ለወታደር አለቆች መስጠት ይገባዋል ይህ መጽሐፍ ግን አንድ ጊዜ ተጽፎ ለዘለዓለም ቀዋሚ የሚሆን አይደለም የጦር ምንስቴሩ በራትና በምስት ዓመት ለሰልፍ የሚስማሙ ቃሎች እያሻሻለ መጽሐፉን ለማደስ ይችላል አሁን ብዙ መምህራን ሰልፍ የሚያስተምሩ አሉ መምህራኖቹ የሚስተምሩት በየራሳቸው ሐሳብ ስለሆነ ልዩ ልዩ የሆኑ ቃሎች ያስተምራሉ ይህ መሆኑ መጽሐፍ ባለ መኖሩ ነው። ሰልፍ የተማረውም ወታደር አስተማሪው በተለወጠ ቍጥር እዲስ ተማሪ እየሆነ ይቸግራል ይህ የሰልፍ ትምህርት መጽሐፍ የሚያስፈልግ ነውና መንግሥት ለወታደር መማሪ የሚሆነውን መጽሐፍለሰልፍ መምህራኖች ቢሰጣቸው ትምህርቱም አንድ አይነት ይሆናል።መጽሐፉን ተቀብለው መምህራኖቹና የወታደር አለቆች የሰልፉን ትምህርትና የሰላምታ አሰጣጡን በንድ አይነት በቀዳማዊ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ልዑል መኰንን አካሔድ አዘጋጅተው ሰልፉን ለጃንሆይ ቢያሳዩ ድንቅ ሆኖ ይታይ ነበር ደንቡና ሥራውም በጣም የተሻሻለ ይሆናል ስል አስታውሳለሁ ።

ባሻ ክፍለ እግዚእ ።

ክቡራን ጌቶቼ አባቶቼ ሊታውንት ክህናት በዚህ ዘመን በግብዝነትና በሐሰት የተደረገ የሀገራችንን ሕዝብ መጕዳል በልቤ ሳወጣና ሳወርድ ያለፈ ጠጠት አለመጥቀሙን ተረ-ዳሁና ይህችን አንዲት ጠብታ የምታህል አሳቤን በብርሃንና ሰላም ልገልጸት ወደድሁ ።

አዕማደ ሰማይ ወምድር የተባላችሁ ሊቃውንት መም-ሕራን እንደዚህ ያለ ግብዝና የሐሰት ወሬ በተሰማ ጊዜ ከዚህ ቀድሞ የበጌምድር ሕዝብ በሃይማኖት ጥግ ሆኖ የተወራውን ወሬ ሐሰቱን ከውቀት ለይቶ ሳይመረምር በከንቱ ስለ አለቀ ከልብ የማይጠፋ እንደ እሳት የሚያቃጥል ኀዘን በል-ባችን እንደ ገባ ታውቃላችሁ አዕማደ ሰማይ ወምድር የተ-ባልነው እንደህ ጠላታችን ሰይጣን በሰው ልቡና ተጠግቶ ወንድም ወንድሙን እንዳያጠፋ ፈጣሪውን እንደ ያስከፋ ነው እንዲ ሰማይ እንዳይወድቅ ምድር እንዳይነቃነቅ ለመደገፍ ኖ-ራልን አሁንም የአበው ኃጢአት ለውሉድ ምልአት ሆኖ የነደደው የእሳት ትርኳስ እየፋገ እንዳያስቸግር በማየ ጸሎት በብዝኅ ትምህርት ብናጠፋው አዕማድ መባላችን በእውነት የተረገጠ ይሆናል ።

ዳግመኛ ይህችን ሐዋርያዊት ማዕርግ ላገራችን እግዚእ-ብሔር ካንድ እስከ ስድስት ቍጥር አብዝቶ የሰጠን እንዲህ በየሀገሩ ሁከት እንዳይነሳ። ባይሆንም አንድ ሊቀ ጳጳስ በየሀገሩ ደርሶ ሁከት ለማጥፋት ፍቅር ለማስፋት አይችልም በማለት ነው እንጂ ካንድ ቦታ ተቀምጦ የማያልቀውን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን ለማደል የሚሳነው የማይችል የለም ነበር። ወንበወንዙ ብቻ ሲፈስ ቢኖር ያለበትን ቦታ ከመጥቀም በስተቀር ለሀገር ምን ይጠቅማል ያውምቢሆን ቢበዛበት ይደርቃል ።

ከዚህ ቀድሞ በሰገሌ ዘመቻ ጊዜ የደብረ ሊባኖስና የጀር መንከሶት ያዲስ አበባ አድባራት ሊቃውንትና ካህናት ቀሳውስት ዲያቆናት መስቀል ይዘው ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ተልእኮአቸውን ፈጽመው እንደመጡ ዛሬም ከምስቱ አዕማድ አንዱ እርድእቱን አስከትሎ ሒዶ ይህን ሐሰት መሆኑን ገልጦት ቢሆን የቅንአት ጥገኛ መሆኑን አገሩ ስለ አወቀ ራስ ጉግሣን ያህሉ የባላባት ዘርና ቤገምድርን ያህል የክርስቲያን አገር ባልተጐዳም ነበር ።

አሁንም ሕግ ወደፊት እንጂ ላለፈው አይሠራምና ቅዱስ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች በ፫ም ፲፬ቁ እስመ ዘቅድሜየ እዴኅን ወዘድኅሬየ እረስዕ ብሎ እንደጻፈላቸው እኔም ኅፁፀ አእምሮ ወንድማችሁ ያለፈው ስሕተት እንዲጠፋ ፍቅር እንደ-ሰፋ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ወንድሞቼ በትሕትና እመ-ለክታችኋለሁ ።

አለቃ ዳኜ ።

ማስታወቂያ ።

የተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት በሰኔ ፳፰ ቀን መዘጋቱን እናስታውቃለን ። አዛዥ ወርቅነህ ።

ማስታወቂያ

በስድስተኛ ዓመት ፳፫ቍጥር በ፻፸፯ ገጽ የአቀቂኝ ድል ድይ ምሬቃ ስንጽፍ መኳንንቱ እኔ ይህን እሰጣለሁ እያሉ ሲአጽፉ ሰምተን እርዳታቸውን ሰጡ ብለን ጽፈን አትመን ነበር ። ነገር ግን መኳንንቱ የሰጡት ለማኅበርነት መሆኑን ከዋናው ሠራተኛ ስለሰማን መኳንንቱ የሰጡት ገንዘብ ለማኅበርነት መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመመ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ። ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የቍላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ፟አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቃችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
6me ANNÉE № 28

ሐሙስ ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም።
JEUDI 10 JUILLET 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በዓል አከባበር ።

በሰኔ ፳፰ ቀን ስለ ክረምቱ ዕረፍት ለማድረግና በትምህርታቸው ለበለጡ ተማሪዎች የመጻሕፍት ሽልማት እሚሸለሙበት ቀን ነበር ። በዚሁ ቀን በተማሪ ቤቱ ታላቅ በዓል ነበርና ይህነኑ በዓል ለማክበር ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብፁዓን ጳጳሳትና ፥ ሌሎችም ታላላቅ መኳንንት ከውጭ አገር ሰዎችም ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር ተጠርተው ነበር ። በተቈረጠውም ሰዓት ጃንሆይ መኳንንቱን አስከትለው ልክ፲ ሰዓት ሲሆን መጡ።ከበሩ ውጪም ባለው ሜዳ ተማሪዎች ጥሩ ሰልፍ አድርገው ልብ የሚሰርቅ ሙዚቃ እየነፉ ተቀበሉዋቸው ከዚህ በኋላ (ሲግናሊስት) በባንዲራ እየተነጋጋሩ ሲጽፉ እጅግ አስደነቁ።ቀጥለው የኢትዮጵያን መዝሙር በሚአምር ሙዚቃ ዘመሩ ። ቀጥለው ሬዱዊላንስ በሚባለው የሰልፍ አካሔድ ሲሔዱ እጅግ ያምሩ ነበር ። ለበዓሉ ከተዘጋጀው አዳራሽ ከገቡ በኋላም ጃንሆይ ከፍ ባለ በሚያምር ወንበር ተቀመጡና ጳጳሳቱና መኳንንቱም የውጪ አገር መኳንንት ወይዛዝርም በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። ቀጥሎ ከለሪዎቤላር የተጻፈው ትያትር ተደረገና ታናናሾች ልጆች እጅግ ያምሩ ነበር።

ቀጥለው የተማሪ ቤቱ ዋና ሹም የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበላቸው ።

ጃንሆይ

ልዑላንና ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር የተማሪቤታችንን በዓል በምናከብርበት ቀን በመምጣታችሁ ባስተማሪዎችና በተማሪዎች ስም ሁኜ ምስጋናዬን ለማቅረብ እለምናለሁ ።

ሌላ ነገር ሳልጀምር በሁላችን ስም ሆኜ ግርማዊት ንግሥት ነገሥታት ዘንድሮ ከኛ በመለየታቸው የጠለቀ ኀዘናችንን ለመግለጽ እንዲፈቀድልኝ እለምናለሁ ።

ዓምና ባሁኑ ጊዜ በትምህርት ለበለጡት ልጆች በእጃቸው ሽልማት ሰጥተው ነበር የግርማዊት ንግሥተነገሥታት እውነተኛ ሀሳባቸው ላስተማሪዎችና ለተማሪዎች፤በጠለቀ በማይረሳ ምስጋና ለዘላዓለም ሲታሰብ ይኖራል።ይጠባበቁትና ይለምኑት የነበረውን የማ ያልፈውን መንግሥተ ሰማያት ያውርሳቸውስል እመኛለሁ

ምንም እንኳን በንግሥተ ነገሥታት ሞት ብናዝን በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ ሕዝብ የተወደዱ የዚች ትምህርት ቤት መሥራች በኢትዮጵያ ላይ በታላቅ ክብር እንዲ ነግሡና ያገሪቱም ኀላፊነት በርሳቸው ብቻ እንዲሆን ስለተመረጡ በጣም ደስ ሊለንና ልንኰራባቸው የተገባን ነው። ጃንሆይ እኛ ታዛዥች ሕዝቦችዎ በሙሉ ልባችንና በፍጹም ትሕትናችን እንኳን ለዚህ አበቃዎ እያልን የተገባዎ ጌታችን ንጉሠ ነገሥታችን መሆንዎን እየመሰከርን ፤ እግዚአብሔርንም ሙሉ ጤናና ኃይልን ፤ ጥበብን ሰጥቶዎ በኛ ላይ በሰላምና በደስታ ብዙ ዓመታት እንዲነግሡልን እንለምነዋለን

በግርማዊነትዎ ትምህርትና ዕውቀት ብርሃን አገራችንም ወደፊት እንድትገፋ ዋና ሐሳብዎ ነውና የተካከለ ፍርድ ፤ ትምህርት ፥ የተሻሻለ የሥራ አካሔድ፤ ለታዛዦች ሕዝቦችዎ ብዙ ትልቅ ስጦታ መሆኑን አንጠራጠርም ።

በዚህና በሌላ ተማሪቤት በኮሌጅም ያሉ ዕውቀትን ለማግኘት በጣም የሚጣጣሩ የኢትዮጵያ ልጆች በሥልጣኔ አገራቸው ወደፊት በምትገፋበት በሥራ አካሔድ ሊረዱ የሚፈልጉ ፤ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ እንደ ዕድላቸው የተስማማ ሥራ ተቀብለው አገራቸውንና ንጉሣቸውን ለማገልገል ግርማዊነትዎን ይጠባበቃሉ ።

ተማሪዎቹም በሕዝባቸውና በንጉሣቸው ፊት ማዕርግና ክብር ቢፈልጉ የተገባ የሰውነት አካሔድና ጠባይ ማሰመር ነው እንጂ ከፍ ከፍ ያለ የቋንቋ ዕውቀት ብቻ አይበቃቸውም ።

ዘንድሮ በተማሪቤታችን ብዙዎቹ አስተማሪዎች የሚገባቸውን ሥራ ስለፈጸሙና ብዙዎቹም ተማሪዎች አመላቸውን ስላሳመሩ መናገር ደስ ይለኛል። ይህ ተማሪ ቤት ከተከፈተ ዘንድሮ ፭ኛ ዓመቱ ነው።ያምና ተማሪዎች ፪፻ ነበሩ፤ ዘንድሮ ፻፷፪ አዳሪዎችና ፻፭፩ ተመላላሾች በድምሩ ፪፻፷፯ ተማሪዎች ናቸው። ዓምና ፭የፈረንሳዊና ፭የእንግሊዝ ክፍል ነበር ዘንድሮ ፯ክፍል የፈረንሳዊ ፯ክፍል የእንግሊዝ ሁኑዋል በዚህ ዓመት በየቀኑ የሚገኙ ተማሪዎች ፪፻ ያህል ናቸው ፡

ብዙዎቹ አስተማሪዎች በሥራቸው እውነተኛ ትጋት አ- ለማሳየታቸው ኮንቲራታቸው አጭር ስለሆነና በየጊዜው ስለ- ተለዋወጡ ነው፡ ይኸውም ለተማሪዎች በጣም ትልቅ ጕዳት መሆኑ የታወቀ ነው። ነገር ግን ለወደፊት ለዚህ ነገር ጥቂት በጥቂት ሲል መድኃኒት እንዲገኝለት ተስፋ አለኝ። ባለፈው ዓመት ተማሪቤቱ ሲዘጋ ገቢና ወጭ ተመዛዝኖ ወደዚህኛው ዓመት የመጣ ገንዘብ ድምር ፬ሺ፻፵፬ ብር፲፰መ፩ቤሳ

የተማሪዎች ገቢ ፲ሺ፹፯ ብር

ከጃንሆይ የመጣ ፴፱ሺ፫፻፺፫ ብር፭መ

ካትክልት፡ ከሸማና ከሹራብ፡ ከሌላም ከልዩ ልዩ

ገቢ ፫ሺ፻፺፫ ብር

እርዳታ ፬ሺ፪፻፳፫ ብር፲፫መ፩ቤሳ

የገቢ ድምር ፷፪ሺ፬፻፵፪ ብር፲፬መ

ወጭ ላስተማሪዎችና ለሠራተኞች ደመወዝ

፴፫ሺ፱፻፴፫ ብር፲፪መ

ለሥራና ለማሠሪ ፲፪ሺ፱፻፸፫ ብር፲፪መ

ለተማሪዎች ምግብና ልብስ ለመጻሕፍት

፳፰ሺ፫፻፶፪ ብር ፬መ፩ቤሳ

ልዩ ወጭ ፯ሺ፪፻፳፫ ብር፲፫መ

የወጭ ድምር ፹፬ሺ፱፻፹፫ ብር፲፬መ፩ቤሳ

የተማሪዎች ገቢ ከተባለው ፲ሺ፹፯ ብር የሚበልጠው ለ፳፩ ያህል ዘመድ ለሌላቸው ተማሪዎች ጃንሆይ የከፈሉላቸው ነው አዳሪዎች ተማሪዎች በወር የሚከፍሉት ፲ ፲ ብር ሌላው ቀርቶ ለልብሳቸውና ለምግባቸው ፈጽሞ የማይበቃቸው ስለ- ሆነ ለተማሪዎች የተሻለ ምግብ ለመስጠት እንዲያስችለን ፩ አዳሪ ተማሪ በወር ፳ ፳ ብር ቢከፍል ደኅና ሐሳብ ሁኖ ይ- ታየኛል ። በዚህ ዓመት ወይዘሮ የሺመቤት ኃ ሥ አዲስ የመጻሕፍት ቤት ለመሥራት ፬ሺ፪፻፳፫ ብር ፲፫ መ ፩ ቤሳ ከሰጡን በቀር ለተማሪቤታችን እርዳታ የሰጠ ሰው የለም። ባ- ለፈው ዓመት ፩ሺ፩፻፲፯ ብር ፬ መ ባለፈው በ፪ተኛው ዓመት ፫ሺ፫፻፺ ብር እርዳታ ተቀብለን ነበር ፤ በዚህ ዓመት እርዳታ እያነሰ መሔዱ በጣም ያሳዝናል። ነገር ግን ለሚመጣው ዓመት ወዳጆቻችንና የሚያስቡልን ሰዎች እው- ነተኛ ሐሳባቸውን ሳያሳዩን አይቀሩም እያልኩ በሙሉ ልቤ ተስፋ አደርጋለሁ።

ለተማሪዎቹ ለጃንሆይና ለቤተ ሰዎቻቸው ረጅም ዕድሜና ደስታ እመኛለሁ ሰኔ ፳፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም

አዛዥ ወርቅነህ ።

ቀጥሎ የፈረንሣዊ ቋንቋ ተማሪዎች በየማዕርጋቸው ተሸ- ለሙና ተጨበጨበላቸው ።

ቀጥለው የፈረንሣዊ መንግሥት ዋና ጸሐፊ ሙሴ ሽምባር የኢትዮጵያን ታሪክ ያስተምሩ ነበርና በትምህርት ለበለጡ ተማሪዎች በገንዘባቸው የገዙአቸውን ብዙ መጻሕፍቶች በትምህርት ለበለጡ ተማሪዎች ሸለሙ።አባታችን አቡነ ቄርሎስ ሊቀ ጳጳሳት በትምህርት ለበለጡ ፪ ልጆች የሚአምር የቀለም መያዣ ሰጡ ።

ቀጥለው በፈረንሳዊ ቋንቋ በሦስት ክፍል ሁነው ዘመሩ ።

ቀጥሎ የእንግሊዝ ትያትር ተደረገና እጅግ አማረ ።

ቀጥለው የእንግሊዝ ቋንቋ ተማሪዎች በየማዕርጋቸው ተሸለሙ ።

ቀጥሎ ሙሉጌታ ደመራ የሚባል ተማሪ ስለ ሀገር ፍቅር በእንግሊዝ ቋንቋ ሲናገር እጅግ ያምር ነበር ።

ቀጥለው በ፫ ክፍል ሁነው የእንግሊዝ መዝሙር ዘመሩ።

ቀጥሎ የሻይ ግብዣ ተደረገና በዚያን ጊዜ በሙዚቃ እየተመሩ ታናናሽ ልጆች ጅምናስቲክ ሲአደርጉ እጅግ አማ- ረባቸው ።

ቀጥሎ ራስ ኃይሉ በገንዘባቸው ከሚአስተምሩአቸው ፩ ተማሪ በትረጽድቅ ካሣ የሚባለው በግዕዝና ባማርኛ ያዘጋጀውን መዝሙር ሲዘምሩ እጅግ ደስ አሰኙ ። ቃሉም ቀጥሎ የተጻ- ፈው ነው ።

የ ኢ ት ዮ ጵ ያ መ ዝ ሙ ር ።

፩ ፤ አምላክ እስራኤል ታማኝ ጌታችን ።
በውነት ይወዳታል ኢትዮጵያን ።
ልጅዋን ጠበቀላት ኃይለ ሥላሴን ።
የጥበቡን መንገድ የክብሩን ጐዳና ።
እንዳይከለክላት ክፉ ድንቁርና ።
ይመራ ጀመረ ጥበብን በቀና ።
ኢትዮጵያ ትጊ ትጊ በኃይለ ሥላሴ ጥበብን ፈልጊ ።
፪ ፤ ይህም የሚያመጣው ጥበብን ቢወድ ።
ኃይለ ሥላሴ ነው ጭኖ በላይ ዘውድ ።
በሰጠሽው ትእዛዝ በዚህ ባንቺው ፍርድ ።
ኃይለ ሥላሴ ነው ያንቺ መነጠርሽ ።
ጥበብን አቅርቦ ከሩቅ የሚያሳይሽ ።
ተጠንቀቂሽ ያጋሆው ክፉ እንዳይሰብርብሽ ።
ኢትዮጵያ ትጊ ትጊ በኃይለ ሥላሴ ጥበብን ፈልጊ ።
፫ ፤ ክፉስ አይሰብረውም እንዲሁ በቀላል ።
በትዕግሥት ማኅደር አምላክ ይዘልሻል ።
በማይደፈረው በማይቃጣው ኃይል ።
ኢትዮጵያ ታማ በትምህርት መአጣት ።
በጭንቅ ትኖር ነበር አጥታ የሚፈውሳት ።
ገንዘብ መልትዋት ሳለ መክፈል ሳያቅታት ።
ኢትዮጵያ ትጊ ትጊ በኃይለ ሥላሴ ጥበብን ፈልጊ ።
፬ ፤ ኃይለ ሥላሴ ግን አሁን ያድናታል ።
በጥበብ ጠበሉ ይዞ ያጠምቃታል ።
የተማሪ ቤትን ማጥመቂያውን ይዝዋል ።

ሁላችን ልጆችዋ እኛ ካልረዳነው ።
ወደ ኋላ ሳንል አብረን ባንለየው ።
በሽታዋ አይለቅም ተጠምቃ ባንድ ሰው ።
ኢትዮጵያ ትጊ ትጊ በኃይለ ሥላሴ ጥበብን ፈልጊ ።

መዝሙር ።

፩ ፤ ሕንፃ ቤተ ጥበብ መክነ ፍሥሓ ።
ሕንፃ ቤተ ጥበብ መክነ ፍሥሐ ።
በወርቅ ወበዕንቍ ዓረፋቲሃ ።
በወርቅ ወበዕንቍ ዓረፋቲሃ ።

፪ ፤ እንዳዘዝኸን አንተ እንዳልኸን ።
ጌታችን ኃይለ ሥላሴ ።
እንዳዘዝኸን አንተ እንዳልኸን ።
ጌታችን ኃይለ ሥላሴ ።
እኛ አየን እኛ አየን እኛ አየን ።
አመከርን ጥበብን መረጥን።

፫ ፤ ግርምት ባሕረ ዓረፍት ንብረ እግዚአብሔር ።
ወበ ውስቴታ ወበ ውስቴታ ።
ጽርሐ ፍኖተ ኢየሩሳሌም ።

፬ ፤ በእደ መልእኩ ማርቆስ።
ዐቀበሙ ወሴሰዮሙ ።
መና ኅብስተ ሴሰዮሙ ።
ለኃይለ ሥላሴ ወኃይለ ኢየሱስ ።
ደቂቀ ምኒልክ ወተክለ ሃይማኖት ።

በትረ ጽድቅ ካሣ ።

ቀጥለው በማርኛ ፪ተማሪዎች የተዋሕዶን ሃይማኖት ነገር ፩ ሲጠይቅ ፩ ሲመልስ ሰውን ሁሉ አስደነቁት ። ከዚህ በኋላ ያማርኛና የግዕዝ አስተማሪ መምሬ ራስ ወርቅ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ጃንሆይ ።

የእግዚአብሔር ሀብት ለየአንዳንዱ በልዩ ልዩ ስጦታ ትሰጣለች የሀብትም ስጦታ ለሰው እንደ ሃይማኖቱ ፅናት እንደ አእምሮው ስፋት ስለሆነ የሥራ ሁሉ መሠረቱ ትዕግሥት እግዚአብሔር ባወቀ መርጦ ባባትዎ በዳዊት ዙፋን ካስቀመጠዎ ጀምሮ ከሀብታት ሁሉ የተከፈለብዎ ሀብት የለም። ይኸውም ሊታወቅ ስለ ሀገርዎና ስለ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም የስምዎ መታሰቢያ የሚሆን ይህ የከበረ ተማሪ ቤትዎ ከተከፈተ ፳ት ዓመት ከሁለት ወር ሆነ ይኸውም የዳጉን የገናናውን የአፄ ምኒልክን ፍለጋ እየተከተሉ የኢትዮጵያን ልጆች ከታችኛው ደረጃ ወደላይኛው ደረጃ ለማድረስ ሐሳብዎ ሌሊትና ቀን አያቋርጥም ። ደልቁንም የውጭን አገር ቋንቋ ልጆች እየተማሩ ካገራቸው ትምህርት ወደኋላ እንዳይሉ ግርማዊነትዎ መርጠው ለተዋሕዶ ሃይማኖት መምርነት ካስቀመጡኝ ፳ዓመት ሆነ እኔ ለልጆች የማስተምራቸው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

በቅዱስ ማርቆስ ወንበር የተቀመጣችሁ አባቶቻችን ብፁዓን ጳጳሳት ልዑላን ጌቶች ክቡራን መኳንንት በሀገራችን ቋንቋ አማርኛና ግዕዝ እየተማሩ ደግሞ የሥላሴን አንድነት ሦስትነት የተዋሕዶን ሃይማኖት የቤተ ክርስቲያንን ሕግ ሥርዓት የአጽዋማትን የበዓላትን የእመቤታችን የንጽሕት የድንግል ማርያምን አማላጅነት የጻድቃን የሰማዕታትን አማላጅነት ተምረው አውቀው የተመሰገኑ ልጆች መሆናቸውን ያለ ሐሰት በውነት ምስክራቸው ነኝ ለኔም እግዚአብሔር ምስክሬ ነው። ቸርነቱ የማያልቅ እግዚአብሔር ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜዎን ረጅም መንግሥትዎን ሰላም ያድርግልን ኢትዮጵያንም በነፃነቷ ይጠብቅልን አሜን ።

ከዚህም በኋላ የፈረንሣዊ ማርሽ ሙዚቃ ተዘመረ ።

ቀጥሎ የተፈሪ ማርሽ በተዘመረ ጊዜ ጃንሆይና ጳጳሳቱ መኳንንቱና የውጪ አገር ሰዎች ሁሉ ተነሥተው ቆሙ።

ከዚህ በኋላ የውጪ አገር ሰዎች ተሰናብተው ሔዱ ። ከዚህም በኋላ ጃንሆይ መኳንንቶቻቸውን አስከትለው አናጢነትና ሽማኔነት ወደ ሚማሩበት ቤት ገቡ። በልጆቹ አሰላጣጠንና በሥራቸው ማማር ሰው ሁሉ ተደነቀ መኳንንቱም ስለ ተማሪ ቤቱ እርዳታ ጠረጴዛውን ወምበሩን ከአናጢ ቤት ፤ ፎጣውን ሹራቡን ከሽማኔ ቤት እየገዙ ሔዱ ። ስለ ተማሪ ቤቱ እርዳታ የገዙትን ዕቃና የመኳንንቱን ስም በሚከተለው ብርሃንና ሰላም እናስታውቃለን ።

ደስ የሚአሰኝ ፍርድ ።

የሰው ብድር አይቀር በምድር የተባለውተረት እውነተኛ ነው።ላቀውከተማና ደጄኑ ዐወቀ የሚባሉ የዳውንት ሰዎች ነበሩ። ላቀው የደጄኑን እኅት አግብቶ ሲኖሩ ደምሴ የሚባለውን ያገር ሹም የታሠረ ሰው ፍታልን እያሉ እያባበሉ ቀስ ብለው ቀርበው በገዛ ጐራዴው አርደውት ተሰደው ራስ ከበደ መንገሻ ከፋን ተሹመው የሔዱ ጊዜ ወደከፋ ሒደው ሲኖሩ ከዚያም ተመልሰው በልዑል ራስ ካሣ ግዛት ደራ ሲኖሩ እውነተኛው ዳኛ እግዚአብሔር ብድር ሊያከፋፍል የቈረጣት ቀን ስትደርስ ላቀውና ደጄኑ ተጣሉና ተካሰው በዳኛ ፊት ቀርበው የተጣሉበትን ነገር ትተው ደጄኑ ላቀውን ደምሴ የሚባለውን ሹም ገድለሃል ብሎ ከሰሰው ከዚህ በኋላ ዳኛው ምርምር ሲአበዛባቸው ጊዜ ጠጠት ገባውና እንዲአው አመሀኘሁበት እንጂ አልገደለም አለ ። ዳኛውም በተለ ለወንጀለኛ ዳኞች አድርጎ መንግሥት ወደሾማቸው ዳኞች ልኮአቸው በሰንሰለት ሁነው ሲነጋገሩ ከሳሹ ደጄኑ እንዲያው አመሀኘሁበት እንጂ አልገደለም ቢል ብልሁ ዳኛ አቶ ተሰማ በልሁ እውነቱን ነገር ለማግኘት ሲሉ እጃዲያስ ከሳሹን አሠሩና ገደላ ተብሎ የተከሰሰውን በዋስ ፍቱ ባሉ ጊዜ የገዶለው ሲፈታ እኔ እንዴት ልታሠር አለ ። ላቀውንም ተከሳሹን ቢጠይቁት ደጄኑ ነው እንጂ የገደለ እኔ አልገደሁልም አለ።ከዚህ በኋላ ሁለቱም ምስክር ቈጥረው በፍርድ ሚኒስቴር በኩል ምስክሮች በስልክ መስክረው ። በሰኔ ፳፯ ቀን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ችሎት ቀርበው የምስክሮቹ ቃልና ሁለቱ አማኞች

የተነጋገሩት ቃል ተነበ ለሙዋቹ ዘመድ ስለ ሌለው የመንግሥት ዘበኛ ተፋርዶአቸው ዳኞችና ባለ ፍትሐነገሥቱ አለቃ ገብረክርስቶስ አደባባይም ያለው ሕዝብ ሁሉ ፈርዶባቸው መግደላቸውንም አምነው ተደበደበ። በጾሮ የተንኰሻኰሻችሁት በሰገነት ይወራል። በጨለማ የተነጋገራችሁት በብርሃን ይወራል ያለው የወንጌል ቃል ተፈጸመ ። በግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት መጀመሪያ እንዲህ ያለ እውነተኛ ፍርድ መገኘቱ እስከ ፍጻሜ ድረስ የእውነት ዘመን እንዲሆን ተስፋ ይሰጣል ።

እ ሚ አ ሳ ዝ ን ሞ ት ።

ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ በልጅነቱ ጀምሮ በጽሕፈት ደንብ ሲአገለግል በቤተ መንግሥት ይኖር ነበር ። ኋላም ዳግማዊ ምኒልክ ሳሉ አፈንጉሥ ነሲቡም ሳሉ የከሳሽና የተከሳሽ ነገር እየተሳሳተ አስቸግሮአልና ነገራቸው ይጻፍ ተብሎ ለዚህ ለመጀመሪያ ነገር የሚሆን ብልህ ጸሐፊ ፈልጉ ቢባል ኃይሌ ሹምዬ ነው የሚችል ብልህ ጸሐፊ ተብሎ ተመርጦ የአፈንጉሥ ነሲቡን ግርማ ችሎ ሲኖር ሥራውን አስተካክሎ አስረክቦ ወደ ባንክ ተሹሞ ነበር።ቀጥሎም በልዩ ለቆመው የፍርድ ቤት ዳኛ ነበር ። ኋላም ግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የወሎን ነጋድራስነት ሹመውት ለነጋዴው መልካም ደምብ ሰጥቶ ለመንግሥቱ ታማኝ ሁኖ ሲኖር መቸም የሰው መጨረሻው ይህ ነውና ታሞ በጥቂት ቀን ሞተ ብለው ሊሸማግሌ አበቱ ለቀኛዝማች ሹምዬና ለልጁ ለትርፌ ኃይሌ ለሌሎችም ልጆቹ ስለ አረዱአቸው እጅግ አዝነናል እንዲዚህ ያለ የታመነ ሰው ሲሞት ጕዳቱ ምንም ለመንግሥት ቢሆን አባቱንና እናቱን ልጆቹንም እግዚአብሔር ያጥናችሁ ።

ጊዜን ከመመልከት የሚገኘው ሐሳብ ።

ክቡራን ሆይ ምነው ሰው ሁሉ ምድርን ይፈልጋታል? ለስም፥ ፪ኛም ለክብር ነው፤ ፩ኛ ለስም ማለትም ሰው ከምድር የሚገኘው ጥቅሙን ሳይፈልግ ይህን ያህል ጋሻ የሰሞን ፤ ይህን ያህል ጋሻ የማር ፤ ይህን ያህል ጋሻ የፈቃይ አለው ይበሉኝ በማለት ርስት እየገዛ ፤ ከመንግሥትም ቢሆን እየለመነ ፤ ባላባቱንም በሱቲ በጠጅ አባብሎ እየወረሰ ሳያርሰው ስሙን ሲጠብቅ ይኖራል ። ግን እነዚህ መሬቶች ውድማና ሜካ ሁነው ብዙ አውሬ እያፈሩ የጕበዝ ሲሳይ ሁነው ይኖራሉ ።

፪ኛ፥ ለክብር ማለትም ሰው ጥቅሙን ሲፈልግ መሬቱን ከማብዛት ባሳርሰውና አትክልት ባረገው ብዙ ገንዘብ ይሆነኛል ሲል በትጋት ሥራውን እየሠራ ክብሩን ይጠብቃል። ምድሩዋም መልካም ገበሬ ይዟታልና ለምልማ በአበባም አጊጣ ለሠራተኛውና ለተመልካቹም በጣም ደስ እሰኝታ ትኖራለች ። መንግሥትም እንዲሁ ሁለት ምሳሌዎች በሕዝቡ ላይ ይገልጻል ፤ መንግሥት መልካም ሠራተኞች አማካሪዎች ያሉት እንደሆነ መጀመሪያ የራሳቸውን ጥቅም ሳይፈልጉ የሀገር ወሰን የሚፀናበትን ፤ አገር የሚለማበትንና ሕዝቡም የሚበዛበትን፥ የሚበለጥግበትን፥ ንግድም የሚሰፋበትን፣ ድኃም የማይጕላላበትን ለሕዝቡም የሚስማማ ዕንዕ የሆነ የበጎ ሕግጋት እያቀረቡ ፤ መንግሥትም እነዚህ አማካሪዎች ያቀረቡለትን የበጎ ምክር እንዲፀና ሲል አዋጁን አናግሮ ድኃውም እንደልቡ መንፈሱ የመከረውን ሥራ ሲሠራ ይኖራል፥ ድኃውም እንዳይዘርፍ ዘበኛውን በየስፍራው አስቀምጦ ድኃው እንደልቡ ሲአርስ ፤ ሲቆፍር፤ ሲነግድ፤ ከብትን ሲአረባ ይኖራል አገሩዋም በከብትና በእርሻ በንግድና በወርቅ በሕዝብ በልጥጋ መንግሥቷንም አበልጥጋ ተከብራ ተፈርታ ትኖራለች ።

ክቡራን ሆይ የመንግሥት መከበሪያው ሕዝብ ነው ። የሕዝብ መከበሪያው ገንዘብ ነው ፤ ሕዝብ ደግሞ ገንዘብ ከሌለው ክንፏን እንደተመታች አሞራ ከመውደቅ በቀር ፈጽሞ ኃይል የለውም ። ክቡራን ሆይ ዛሬ በሀገራችን የብርን ክብር ተረድታችሁታልን ። ምናልባት እኮ አንድ ሩብ ሁናለች ። ከቶ የሽማግሌ ተረት ሐሰት አይደለም የሰው ወርቅ አያደምቅ ይላል ፤ እርግጥ ነው እርግጥ ነው ፤ እንግዲያማ የራሳችን ገንዘብ ብትሆን ባሏ እንደሞተባት ቆንጆ ሴት መቸ የሁሉ መዘባበቻ ትሆን ነበር ። እውነትም የሰው ወርቅ አያደምቅ ነው ። አሁን እንደምንመለከተው በየቀን በየቀኑ ዘወትር ክብሩዋ እየተጓደለ እንደ ሚሔድ የኛም ብዕል እንደዚሁ እየተጓደለ መሔዱ ጥርጥር የለውም ። መቶ ብር ያለው ሰው ሐያ አምስት ብር አለኝ ይበል እንጂ መቶ ብር አለኝ ለማለት ፈጽሞ የማይቻል ነው ። ምክንያቱስ ከምን የመጣ ይመስላችኋል ። ከውጭ አገር ወደኢትዮጵያ የሚገባው ዕቃ ስለበዛና ከኢትዮጵያም ወደውጪ አገር የሚሔደው ዕቃ ስለአነሰ ይመስላል ።

እነሆ እንደ ዛሬ አገር ሳይሠለጥን ኃይለኛው ንጉሥ ነገሥት ናፖሊዎን በመንግሥቱ ጊዜ እንዲህ አደረገ ይባላል ፥ በግዛቱ ውሥጥ እንደኛ እንደዛሬው ለሕዝቡ ኑሮ የሚአስፈልገውን ዕቃ ሁሉ ከውጪ አገር ነጋዴ እያመጣ ለሕዝቡ ይሸጥ ነበር ። በዚያን ጊዜ ኃይለኛው ስመ ጥሩ ንጉሥ ነገሥት ናፖሊዎን የውጪ አገር ዕቃ ሁሉ በግዛቱ ውሥጥ ፈጽሞ እንዳይገባ የጠነከረ አዋጅ አረገና ሕዝቡንም ለሕይወቱ የሚአስፈልገውን ነገር ሁሉ በዚያው በሀገሩ እንዲሠራ በኃይል ያለውዴታ አዘዘው፥ አበራታውም ። ሕዝቡም የእግዚአብሔርንና የንጉሡን ትእዛዝ ይፈራልና የንጉሡን ቃል ለማክበርና ለመፈጸም ሁሉም በየወገኑ መንፈሱ እንደመራው ለኑሮው የሚሆነውንና የሚስማማውን ሥራ መስራት ጀመረ ። በንጉሡም ኃይልና ብርታት ራሱን ቻለ የንጉሡም ሓሳብ በሕዝቡ ብርታት ተከናወነ ይባላል ።

ክቡራን ሆይ እኛስ ምን እስኪሆን ነው የምንጠብቀው ውኃና ገደል እያሳሳቀ ነው የሚወስደው እስከ ዛሬም በሰው አገር ጨርቅና ወርቅ አጌጥን ከእንግዲህስ ወዲህ በገናናው ንጉሥ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ሙሉ ተስፋችንን አርገን የሰውን ገንዘብ ከመመልከት የራሳችንን ገንዘብ ብንመለከተውና

ብናሰናዳው እጅግ መልካም ሁኖ ለሀገሩና ለሕዝቡ ታላቅ ጥቅም ነበረው ።

ውሂብ ወ ማ ።

የእግዚአብሔር ስጦታና ጸጋ።

እግዚአብሔር የሰጠውን ጸጋና ስጦታ መናቅ ማቃለል አይገባም፤ ጳውሎስ በጢሞቴዎስ መጀመሪያ ክታብ ም ፬ ቊ ፲፬ የእግዚአብሔርን ስጦታና ጸጋ አትናቅ አታቃል ይላል። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ከተባሉበት ዘመን ጀምሮ ንጉሠ ነገሥት እስከተባሉበት እስከ ዛሬ ድረስ ለሰው የተሰጠው ጸጋ እጅግ ብዙ ነው።የስጦታውም ቍጥር ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው፤፩ኛ በብዙ ዓይነት ያጌጠ ልብስ መልበስ፤ ሁለተኛ በጭቃ እስከአንገቱ ሲዘፈቅ የነበረ ሰው በሲምንቶና በጥርብ ደንጊያ በተሠራ መንገድ መሔድ ሶስተኛ ዶኅና ባለጸጋ ትንሹና ትልቅ ሳይበል ሰው ሁሉ በውቀቱና በሥራው መፈለግ። አራተኛ ነጠላ ጫማ ያልነበረው በሹፍ ጫማ መሞናሞን፤ አምስተኛ በመስታዋትና በቀለም በምንጣፍና በአበባ ባጌጠቤት መኖር ነው፤ የጕላ የጕላውን መናገር ነው እንጂ የቀረውማ ምን ተቈጥሮ እኔ እንኳ በቅሜ የተቀበልሁት ጸጋ ብዙ ነው፤የተወለድሁት አዳ ወረዳ ቃሊቲ ውሥጥ ነው ያባቴ ቤት ግድግዳው የዘንጋዳ አገዳና የጕሎ ዕንጨት ነበር እልፍም ቢል የግራርና የዋንዛ ዕንጨት ነበር ምን የኔብቻ የብዙውም ሰው እንደዚህ ነበር አሁን ግን ከዕድላሙ ንጉሥ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘመን ስለደረስሁ በጣንዲላና በመስተዋት ያጌጠ ቤት ጃንሜዳ አጠገብ ሠራሁ የጃንሆይን ስጦታ ታምኚ ። ወይ የእግዚአብሔር ስጦታ እጅግ ይገርማል እጅግ ይደንቃል አላዋቆች ሰዎች ባለፈው ዘመናችን ብዙ ማርና ቅቤ ሥጋ ብዙ ተድላ ደስታ ነበር እያሉ ያደንቃሉ የኛን ዘመን ለመንቀፍ ይመስላል ነገር ግን ብዙ ማርና ቅቤ ሥጋ ቢኖር የሚመገቡት ጥቂት ሰዎች ነበሩ እንጂ ብዙው ሰው የምግቡን አከናወን ስልቱን እያውቀውም ነበር፤ምግብ ከልበሉት እንዴት ያልቃል ቅቤውም እወጥ ሲገባ እንደ ሜሮን ተመጥኖ ሥጋው በሹሮና ወይም በተልባ ተለውሶ ነበር የሚቀርብ እንዲህ ያለው ተድላ አይበልም፤ጠጅማ ጥንቱን እደኃ ቤት ምንሊያደርግ ገብቶ በዚህ ዘመን ግን በማንም ቤት ቢሆን አልጫ መረቁ፤ ጥብሱና ድቁሱ፤አፍርንጁና ምንቸት አብሹ እንሬላውና ቋሊማው፤ ለምለም ዝግኒ ክትፎው በያይነቱ ከመጠጥም ወገን ወይን ጠጁ ሎሚናቱ፤ቢራውና ሰዳው፤ኮኛኩና ሽምባንያው በያይነቱ የማይቀርብበት የለም ሥጋና ቅቤ ማነሳቸው ዛሬ በላተኛ ስለበዛ ይመስላል ዘመንን ከመንቀፍና የእግዚአብሔርን ስጦታ ከማቃለልስ ኃጢአትን መተው እግዚአብሔርን መፍራት ሕጉን መጠበቅ ንጉሥን በቅን ማገልገል ሥራ መውደድ እውነት መፍረድ ለዕድላሙ ንጉሣችን ዕድሚና ጤና መለመን ፍቅርና ሃይማኖትን ማፅናት ንስሓ መግባት ነው ዘመኑን ደግ የሚደረገው።

የእስጢፋኖሱ አለቃ ቀጸላ።

መሰናበቻ ።

ክቡር ቅዱስ አባታችን የኢትዮጵያና የግብፅ ሊቀ ጳጳሳት ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ በሰፊው አሳባቸው የፀቱን አገር ሕዝብ ለማቃረብና እስካሁን የኖረውን ፍቅር ለማጽናት ፍጹም ምኞታቸው መሆኑን መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው አገራችንን ባርከው በመመለሳቸው የውነተኛ አባታ መሆናቸውን ገለጹልን። ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ በዚያው ወራት ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱና ግርማዊ ንጉሥ በቸርነታቸው በአቡነ ዮሐንስ ስም የሚቆም ለተማሪቤት የሚሆን ታላቅ በታና በጥብቅ እምሮ የተሠራ ቤት ስለመታሰቢያ ስጡአቸው አሁን ሁለተኛ የሥጋዊና የመንፈሳዊ ትምህርት የሚማሩ ፰ ሕፃናት ይላኩልኝ ብለው በብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በኩል ወደ ጃንሆይ ስላመለከቱ ይህ አሳባቸው በውነት ለፀቱ አገር ሕዝብ የፍቅር ሰንሰለት የሚሆን ለዘወትርም መታሰቢያ ሁኖ የሚኖር ስለሆነ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስን ጥያቄ ተቀብለው ልጆቹ ከተመረጡ በኋላ ከጃንሆይ ሲሰናበቱ ከሕፃናቱ አንድኛው ንጋቱ ሣህሌ የተባለው የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት የንግሊዝ የመጀመሪያ ክፍል ተማሪ ያነበበውን የመሰናበቻ ቃል ከዚህ በታች ጽፈነዋል ።

ጃንሆይ ።

የእስክንድርያና የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ከዚህ በፊት ኢትዮጵያን መጐብኘታቸውን በታሪክ አላነበብንም በወሬም አልሰማንም ነበር ነገር ግን በአሁኑ ዓመት አቡነ ዮሐንስ የእስክንድርያና የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታትና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ዘመን ጐብኝተው ኢትዮጵያ በሊቀ ጳጳሱ መባረኳና በዚሁ በጐበኙበት ከኢትዮጵያ ሕፃናቶች ወደ ግብፅ አገር ሔደው እንዲማሩ ሊቀ ጳጳሱ መፍቀዳቸው ለኛ ለወጣቶቹ መልካም ዕድልና ለኢትዮጵያ የማይረሳ መታሰቢያ ሁኖ እንዲኖር አይጠረጠርምና ለአቡነ ዮሐንስ ለሊቀ ጳጳሱ ምስጋናችን አያቋርጥም ።

ጃንሆይ ።

በኢትዮጵያ መጀመሪያዋ የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት የኢትዮጵያ ወጣቶች ማስተማር ከጀመረች ብዙ ዘመን ሁኖዋል፤ ነገር ግን የሥላሴ ኃይል የኢትዮጵያን ወጣችቶ እንደአሁኑ ጊዜ አበረታትቶ የአውሮፓን መንገድ መመላለሻ እስከ አደረገላቸው ቀን ድረስ ምንም የኢትዮጵያ ወጣቶች ለትምህርት ቢተጉ ዛሬ በተማሪ ቤት እንዳሉት ልጆች ለትምህርት መሽቀዳደም አልነበራቸውም ለማለት እንደፍራለን ይሁን እንጂ ተማሪ የመምህሩን ፍለጋ እንደሚከተል ሁሉ እኛም እንደዚሁ በመሰለ መልካም ሐሳብ መሪያችንን ተከትለን ያለመሰልቸት ትምህርታችንን ፈጽመን ስለ ኢትዮጵያ ያለማቋረጥ ሁለጊዜ ለሚያስቡልን ጌታችን አገልጋሎታችንን ለመግለጽ ሐሳባችን ከልብ መሆኑን በአለመጠራጠር ጃንሆይ ይመኑት ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

እውነተኛ የኢትዮጵያ ጥቅም ፈላጊ አገሩን አክባሪና አስከባሪ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታጩበት መንበረ ዳዊት ከተቀመጡ በኋላ ባለፈው ሳምንት በጥቂት ወራት ውሥጥ እኛ የኢትዮጵያ ወጣት ተማሪዎች ትምህርታችንን ለመጨረስ ወደ ምድረ ግብፅ እንድ ንሔድ በመመረጣችን ዛሬ በጃንሆይ ፊት ትልቅ ዕድልና ሞገስ ያገኘንበት ቀን ነው ።

ይህንንም ዛሬ ያገኘነውን ዕድልና ሞገስ ከልባችን ሳናጠፋ ትምህርታችንን ለመማር በምንቈይበት ዘመን ሁሉ በመልካም ባሕሪና አካሔድ ለትጋትም እንድንማር መታመናችንን ለጃንሆይ እየገለጽን ከዝፋኑም ፊት ወድቀን ስንብታችንን እንለምናለን።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት መነን ደግሞም ለጃንሆይ ቤተ ቤት ዘመዶች ሁሉ እንመኛለን ።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ።

የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት በእንግሊዝ ክፍል መጀመሪያ ተማሪ ንጋቱ ሣህሌ ።

ባለፈው ሳምንት በኢትዮጵያ ሐዲስ መንፈስ ሰፈፈ ያለውና አዕማድ መባላችን በገንዘን፡ በጸሎት፡በትምህርት ልንረዳ ነው እንጂ ምድርን ያለ ክስማ ሰማይን ያለ ባላ ያቆመ እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰማይ መደገፍ ምድርን ከመነቃነቅ። ለማትረፍ አይደለም ብለው የጻፉ ሊቃውንት ደስ አሉኝ ። ከዚህ ቀደም ትግሬ ላይ ላአስተርእዮ አንጓ ከምትባል ገዳም ላይ ሁለት መነኰሳት አንዱ የተክለ አልፋ አንዱ የማርያም እናቱ ናቸው።አዕማደ ምሥጢር ሲነግሩ እመቤታችን በቤተ ዮሴፍ ስለ ትሕትናዋ በቀዳችው ውኃ አንዱ በመንቀል ነው አንዱ በማድጋ ነው ብለው እስከ ብትር ድረስ ደርሰው ሊቃውንቱ አስቀድሰው ሲወጡ አከራክሩን ብለው ቢቆሙ ከሊቃውንቱ አንዱ ተገልጦለት ወደፊት የሚነሣ ነገር ይኖራል እንጂ መንቀልና እንስራ ማድጋ አያጣላም ብሎ ሸንጐውን ፈታን በመቱ አንድ መለኮት በአካል ሶስት የሚሉ ተነሥተው ቢሰበሰቡ አገረ ገዠ አከራክራለሁ ብሎ ጉባኤ ቢሠራ አንድ ስደተኛ አማራ ንጉሠ ነገሥት፤ሊቀ ጳጳሳት፤አፈ ጉባኤው እጨጌ አዲስአበባ ክር ክር እዚህ ብሎ ተናገረ አገረ ገዥው ተደፈርሁ ብሎ በመኰዳው ተገላብጦ ስደተኛውን ገላምጦ እልፍኙ ተከተተ ያን ጊዜ አንድ ጳጳስ ባገር ነበር ብቻውን ከመሆኑ የተነሣ እቃለው ፩ዓይነት አሳተሙት እንጂ ።

መወድስ

ሰማዕተ ትንቢት ጽዱቅ ነቢያተ ሕግ ።
ዘኀረየ ቅድመ እግዚአብሔር ልዑል ።
እለ ተነበዩ ሎቱ ትንቢተ ምሕረት ወሣህል ።
ነቢያተ ይባርክ ሰብ ይበጽሑ ዘነበቡ ቃል ።
ወዘሎንደዮ ትንቢተ ቃል ።
በቃለ ጕጕዓ ብዙኀ ነቢያተ ይዔፅል ።
ይርከብሚ ባቢሎናዊ ትርጓሜ ራእዩ ብጡል ።
ሜሞ በምድረ ፋርስ ሊቀ አጰይዶን ለዳንኤል ።
በስምዐ ፫ይንግሮ በዘራእዩ አምሳል ።
ዜና መዋዕል ዘኀለፈ ወዜና ዘይመጽእ መዋዕል ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን —

በአየር ላይ ከአኤሮፕላን ስለወረደው የአሜሪካ ሰው ደስ ብሏቸው ገንዘብ የሰጡትን ሰዎች እንዳመለከትን ከኑሜሮ ፳፮ ቍጥር ፳፯ ተከታይ

በጅሮንድ ዘለቀ አግደው	፶ ብር
ደጃዝማች ዓምዴ	፶ ብር
ባሻ በላይ	፳ ብር

ደግሞ እንሰጣለን ብለው በቃላቸው ያስጣፉት ሰዎች ጨርሰው ሰጥተው በሚመጣው ብርሃንና ሰላም ስማቸው እዲጻፍ ቢያደርጉ ደስ ይለናል።

ማስታወቂያ

በ፳ኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም ስለ ጅማ መንገድ አክስዮን ለሚገዙ ለአገራቸው ወዳጆች በተጻፈው ማስታወቂያ ከጃንሆይ የ፩ ሚሊዮን ብር፡ከሕዝቡ የ፳ ሚልዮን ብር ተብሎ የታተመው ከጽሕፈት ተሳስቶ ነውና የሚአስፈልገው አክስዮን ከሕዝቡ ፲፱፡ ከመንግሥት ፩ሚሊዮን በድምሩ ፳ሚሊዮን ነው፤፩ሚሊዮን ትርፍ ሁኖ በስሕተት የተጻፈ መሆኑን እናስታውቃለን ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጂዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፮ ብር
ጎህ ጽባሕ	፮ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መ
የርሻ ትምህርት	፪ ብር ከ፳ መ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ክርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪያ (ካሌንድር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጆማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ፤፤ላ፡

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጴጥሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ. ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፌ ፈርናዲ. ስኖልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከበሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
6me ANNÉE № 29

ሐሙስ ሐምሌ ፲ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 17 JUILLET 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መጣዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የከተማ ወሬ ።

በሐምሌ ፯ ቀን የሐምሌ ሥላሴ በዓል ነበርና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከብዙ መኳንንትና ሠራዊት ጋራ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ሔደው ነበር። ብፁዓን ጳጳሳትም ከዚያው ነበሩ ።

ካህናቱም ሲዘምሩ እጅግ አምረው ይታዩ ነበር። ከዑደቱም በኋላ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የአብርሃምን ታሪክ ተርከው በመጨረሻው እሚያስደንቅ ንግግር ተናገሩ ። ቃሉም ይህ ነው ። ለአብርሃም ከገረዶች የወለዳቸው ፯ልጆች ነበሩት። ነገር ግን ዘር በዲቃላ ልጅ አይቈጠርምና ሥላሴ ወደቤቱ በመጡ ጊዜ ሳራ ሚስትህ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች አሉት ተወልዶ ካደገም በኋላ ለፈተና አንዱን ልጅህን ይስሐቅን ሠዋልኝአለው። አንዱን ልጅህን ማለቱም ከሚስቱ የተወለደውን ብቻ ልጅ ማለቱ ። አንድ ወንድ በአንዲት ሴት ፀንቶ መኖር የተገባ መሆኑን ሲአዝዝ ነው ብለው ብዙ የሚአስደንቅ ስብከት ሰብከው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ ።

ከቤተ ክርስቲያንም ስንወጣ ያረፈዱት ሰዎች ወደ ቤተ-ክርስቲያን ሲገቡ የሚወጣውና የሚገባው ሲጋፉ አይቶ አንድ ብልህ ሰው እንዲህ ብሎ ተናገረ ።

ይህ ሕዝብ አሮጌውንና አዲሱን ሕግ ይመስላል ። አሮጌው ሕግ ሲወጣ አዲሱ ሕግ ሲገባ እንዲህ ተጋፍቶ ነው ።
ነገር ግን ማስጨነቁ ነው እንጂ ያም መውጣቱ ያም መግባቱ በጊዜው አይቀርም ። አሪት ተሽራ ወንጌል በተሾመች ጊዜ ብዙ ጭንቅ እንደነበረ ። በመጻሕፍት እንብበናልና በርቱ ተስፋ አትቍረጡ ብሎ እፅናና እውነት እኮ ነው ያለ መከራ ሀብት ሁሉ አይገኝም ።

ስለመልካም አርአያና ምሳሌ ።

መልካም ሹም በፍጹም ልብ መንግሥቱን ለማገልገልና ሕዝቡን ለመጠበቅ ሲል ለጊዜው የሚሠራው ሥራ ሁሉ ወደፊት ለሚነሡት ትውልድ መልካም አርአያና ምሳሌ ሁኖ በታሪክ ሲነገር ይኖራል ። ከዚህ በፊት ባለፉት ዘመናት የነገሡት ነገሥታትና ከሥልጣናቸውም በታች ሁነው በዓለም ላይ የሠለጠኑት መኳንንትና መሳፍንት እንደምንሰማው በተጻፈው ታሪክ ሕዝባቸውን በመበደል አገር በማጥፋት ፍርድን በማጒደል ቀናውን ነገር በማጣመም የሚኖሩ ሰዎች የከፉትና የጥፉት አርአያና ምሳሌ ሁነው ያኖራሉ ። ሕዝባቸውን በመጠበቅና ሀገር በማቅናት ፍርድን በማደላደል እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት ማቴ ም ፭ ቍ ፴፯ ብለው የሚኖሩ ሰዎች እንደመልካም ሽቱ የሚጣፍጠው ስማቸውና ታሪካቸው በየጊዜው ሲነበብ በመስኖ ዳር እንደበቀለች እትክልት የሰሚ ልብ ትለመልማለች ደገኛው ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደ መስቀል በእውቀትና በአርምሞ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ያለውንም በመከተል በቅን ልቡና በትሑት ሰብእና ሌት ተቀን ለመንግሥታቸው ሲያገለግሉ ግርማ ሌሊት ሊከለክላቸው አይችልም ። ምሳሌ ም ፲፱ ቍ ፵፩ አእምሮ ያለው አጋልጋይ በንጉሥ ዘንድ የተወደደ ነው ። ፪ኛም ም ፳፯ ቍ ፲፰ በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል ጌታውን የጠበቀ ይከብራል ይላል ። በትጋትና በእውቀት የሚሠሩትን ደግነትና ቸርነት ከፊታቸው የቀረበ ሁሉ የሚገባቸውን ምስጋና ሳይ-ናገር የሚሔድ የለም። ከዚህም ሌላ ምሥጢረ መንግሥት ሠናይ ለኅቢእ እንደተባለው በየጊዜው የሚሠራውን ምሥጢር ላኅ-ፊውና ላግዳሚዊ ሳይዘረዝሩ ወአርመምኩ ለሠናይ የሚለውን ቃል ጠብቀው ይኖራሉ ። ወረከብዎ ለዳዊት ገብርየ ብእሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ በተባለው ቃል መጀመሪያውን የመታ-መን ማዕርግ ልሻን በንጉሠ ነገሥት ልብ መሸለም ይገባቸዋል

ለማለት ያስስበል ። በ፯ኛው ዓመት ብርሃንና ሰላም በቍጥር ፳፯ለክቡር ክንቲባ ነሲቡ የሚገባቸውን ምስጋና አቶ በቀ አበየ ስለ ጻፉላቸው ምስጋናው በሚገባቸው ስለሆነ ብርሃንና ሰላም የሚያነብ ሰው ሁሉ ይደልዎ ይደልዎ ሳይል ይቀራል ብዬ አልጠረጥርም ። አቶ በቀለ አበየ ክቡር ክንቲባ ነሲቡ በእውነተኛው መንገድ እንደደንቡ የሠሩትን ሥራ ስለጻፉ ሁለተኛ ሆኜ ለመጻፍ ያሰሰበኝ እግዚአብሔር የቀባው ሹም በሚገባው ሲመሰገን ሀገርን ደስ ይላታል። ክንቱ ውዳሴ የሚባለው ሰውን ባልሠራውና በማይገባው ማመስገን ላመስጋኙም ኃፍረት ነው። እንደ ክቡር ክንቲባ ነሲቡ ዛማኔል በሚገባውና በሠራው ሥራ መመስገን ለኋላም ልጅ ምሳሌ ሁኖ ይነገራል ። እገሌ በእውነትና በቅን ቢሠራ በታሪክ አንባቢዎች አፍ ሲመሰገን ይኖራል እየተባለ ለመልካም ሥራ አርአያ ሁኖ ይኖራል ።ምሳሌም ም ፳፺ ቍ፪ ይወድስከ አፈ ነኪር ወአኮ አፈ ዚአከ ብሂል ። ቅዱሳንም በተወለዱበት ቀንና ወይም በዕለተ ዕረፍታቸው ለፃናናውእምላክ፤ሲያገለግሉና መንፈሳዊን ሕገ ትሩፋት ሲከተሉ በቅን ልቡና በእውነት የሠሩት ሥራቸው በገድላቸውና በተአምራቸው ሲነበብ የሰማዕያን ጆሮ ከመስማቱ የተነሣ ትጠሣግባለች ። ማቴ ምዕ፲ ቍ ፱ ዘቦ ዕዝን ሰሚዐ ለይስማዕ እንዲል የጻድቃንና የሰማዕታት ገድልና ተአምር ሲነበብ የሰሙ መናንያን እነሱን ለመምሰል መንገዳቸውን ይከታተላሉ ። ለክቡር ክንቲባ ነሲቡ የሚገባቸውን ምስጋና አቶ በቀለ አበየ ከጻፉ በኋላ ሁለተኛ ለመጻፍ ያሳሰበኝ በአእምሮና በእውቀት ስፋት ከሠሩት ሥራ ይልቅ አርበኝነታቸውና በታዘዙበት ሥራ ለመንግሥታቸው በፍጹም መታመን ፊታቸውን ሳይመልሱ ። ግርማዊውን የጃንሆይን ትእዛዝ ፈጽመው በሙሉ ደስታ ዘወትር ይመላለሳሉ ። ፈጻሚ ፈቃድነታቸውና ጀግንነታቸውም ለልጅ ልጅ የማይረሳ መታሰቢያ ሁኖ ይኖራል ። ስለማዘጋጃቤትም ሥልጣኔ ነገር በዝርዝር በወረቀት ጽፌን ለማስረዳት ይበዛል። ለጊዜው ያየሁትን ሳልጽፍ ብቀር ከስንፍና ይቈጠርብኛል ። ከዕለታት ባንድ ቀን ስለርስት ነገር ወደማዘጋጃ ቤት ሔጄ ሳለ ወደዚያው አማላጅነት ሰው ልኮኝ ነበርና ከግምጃ ቤቱ ክፍል ሹም ልጅ አበበ ወንድማገኘሁ ዘንድ ሔጄ የሚገባውን ሰላምታ ከተቀባበልን በኋላ።ለጊዜው የማዘጋጃ ቤትን የገቢና የወጭ ሒሳብ ስለያዙ አሁን የያዙት ሥራ የሚፈጸምበትንና ለመኳንንቶችን ሰዓት ቀጠሮ ይሰጡኝ ብዬ ክቡር ፈቃዳቸውን ብጠይቅ ሥራው ባ፲ደቂቃ ውሥጥ መፈጸሙን ካስረዱኝ በኋላ በጸጥታ ከመለከት የማዘጋጃ ቤት ገቢና ወጭ ለቀለብም ለመንገድም ለማናቸውም ይህን ለመሰለ ሥራ ሁሉ የወጣው ተደምሮ ከንዱ ሳምንት ወደ፪ኛው ከንዱ ወር ወዳንዱ ወር የሚተላለፈውንና ቀሪውን ገንዘብ ለማወቅ በኮፒ ከሒሳብ ቤቶች ጋራ ሲደማመሩ። ለሥራው መፋጠናቸውንና መከናወናቸውን አይቼ ከብዙ መደነቅ የተነሣ የሥራውን አካሄድ ብጠይቃቸው ። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ካስረዱኝ በኋላ ይኸውም ሥራ በትጉሁና በማእምሩ ክቡር አቶ አየለ ገብሬ ብርታት መፈጸሙን አስታውቁኝ። በየክፍሉ ያለው የኢትዮጵያ ሥራ ሁሉ ይህንን አርአያና አምሳል ይዞ ይከከናወናል በማለት ልቤ በሙሉ ደስታ ስለተነካ ለክቡር አቶ አየለ ገብሬና ። በሥራ ተከታይ ለሆኑት ለልጅ አበበ ወንድማገኘሁ በትጋትና በእውቀት ለሠሩት ሥራ ምስጋና ልናቀርብላቸው ይገባል ። ምሳሌ ምዕ፳ቍ፱ ፲ አምሮ ለጠቢብ ከመ ይወስክ ጥበበ፡ የጥበብም መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው እንዳለ ። ከዚህ ቀደም በማዘጋጃ ቤት ከወጭ ተርፎ የሚተላለፈውና የሚቀረው ገንዘብ ልኩና ቍጥሩ ስላልታወቀ ላዲስ አበባ ከተማ ጥበቃ የሌሊቱን ቍር የቀኑን ሐሩር ችለው የሚቆሙት ዘበኞች ቀለባቸውን በየወሩ ባለማግኘታቸው ምክንያት ስለቀባቸው ከጃንሆይ ለመጮህ ዘወትር ሲደክሙ ይኖሩ ነበር ። ብርሃናዊው ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቅን ልቡናና በትጋት ያለሀኬት ሀገራቸውን የሚወዱትንና ለመንግሥታቸው የሚያገለግሉትን እንደ እሸት እየመረጡ በየሥራው ላይ ያቆሙዋቸዋል ስለ በፍጹም ተስፋ እናገራለሁ ። ከዚህ በላይ የተጻፉትን ባለሥልጣኖችን እያመሰገን መጻፋችን። ከሥልጣናቸው በታች በየክፍሉ ያሉት ሹማምቶች ቀናውን ጐዳናቸውን እንዲከተሉና በሥራ እንዲመስሉዋቸው ብለን ነው ።

ከዚህ በፊት ሩቅና ቅርቡን መነሻውንና መድረሻውን ለዩተው የሚጽፉ ከተማሪ ቤት የኖሩና የቀለም ሠረገላ የሚያውቁ አንዳንድ ሰዎች ነበሩ ። ታላቁ መምር ብርሃንና ሰላም ዓለመ ኢትዮጵያን ለመስበክ ከወጣ በኋላ ብርሃንንና ሰላም የሚያነብና የሚቀበል ሁሉ በረቂቅ እውቀት መሠልጠኑን ማንም አይስተውም ታላቁን መምህር ብርሃንና ሰላምን ያቈይልን አሜን ። ጸጋ ሥላሴ ጌታሁን

ስለ ብድር ።

በብርሃንና ሰላም በ፯ኛው ዓመት በቍጥር ፳፯ ክቡር ነጋድራስ አፈወርቅ እንደጻፉት ብድር ጥቅም ይሰጣል ጉዳትም ያመጣል ፤ ጥቅም መሆኑ እንዴት ነው ቢሉ ቤት ቢሠሩበት ተክል ቢተክሉበት መንገድ ቢያስበጁበት ጥቅምነቱ ለሀገርም ለመንግሥትም በብዙ ረገድ እንደ፡ረዳ ያለጥርጥር እርግጥ ነው ። ግን በአራጣ ተበድሮ እንዲያው አበዝኖ ሥራ ሳይገዝ ለመብል ለመጠጥ ለፈንጠዝያ ለጌጥ ለአዝማሪ ለዘዋሪ ቢያደርጉት እንኳን ይጠቅምና ከውርደት ሥፍራ ያደርሳል ። ጥቅምነቱን ለማስረዳት ያህል ቀጥዬ እጽፋለሁ በ፲፰፻፹፰ ዓመት ምሕረት በአድዋ ጦርነት እንዲሆን እርግጡ በታወቀ ጊዜ ዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለጊዜው ከግምጃ ቤትና ከጓዳ ቤት የተገኘ ገንዘብ ለጦር መጓጓዣና ለወታደር ስንቅ ሁኖ እንደማይበቃ ስለገመቱት ባገር ቤት ወደሚኖሩ ሀብታሞችና አራጮች ገንዘብ ለመበደር ይልኩ ጀመር ፤ የኢትዮጵያም ሕዝብ አገሩን አፍቃሪ ንጉሡን አክባሪ ነውና በየማጀቱ በየበረቱ ያኖረውን (የቀበረውን) እያወጣ ለእምዬ ምኒልክ ያልሆነ ለማን ሊሆን ነው እያለ ፊቱን ሳይመልስ አንገቱን ሳይቀልስ በፍጹም እምነት ገንዘብ አበደራቸው ። በዚያን ዘመን ብር በጣም ውድ ነበርና ከገንዘብ ማነስ የተነሣ በአንድ ብር ፳ ዳውላ እህል ይሸመት (ይለወጥ) ነበር ። ሀብታሞቹ አራጮች በእንደዚህ ያለ

ትጋት እየጣሩ በብዙ ድካም ሠርተሙ እህል ሸምተሙ ያጠፍቀሩት ገንዘብ ሳያሳሳቸው እንደ አስቆሮታዊ ይሁዳ ፍቅረ ንዋይ ሳያታልላቸው ከአንድ እስከ ፻ሺ ድረስ አንዳንዱም እራሽ ገበሬ እስከ ፫ሺ ብር ድረስ ያለ አራጣ አበደሩቸው ይባላል። ጃንሆይ አፄ ምኒልክም በዚሁ ከሀገራቸው ልጆች በተበደሩት ገንዘብ የጦር መሣሪያ ገዝተው ለወታደር ስንቅ ሰጥተው ሰሰልፍ ተዘጋጅተው ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለው ባሕር ቀዶ ድምበር ንዶ የመጣውን ጠላት ድል ነሡበት። የኢትዮጵያ ሰንደቃ ዓላማ በአርበኞቿ ደም ተዋጅታ በነፃነቷ ፀንታ እንድትኖር አደረጓት። በኋላም በእግዚአብሔር ኃይል ከዘመቻው በድኅና በተመለሱ ጊዜ አበዳሪዎቹን ሰዎች ሐረርጌ ወርዳችሁ ከራስ መኰንን ዘንድ ያበደራችሁኝን ገንዘብ እንድትቀበሉ ይሁን አሏቸውና ሐረር ከተማ ወርደው ዋና ገንዘባቸውን ከተቀበሉ በኋላ ልዑል ራስ መኰንን እንደገና ጠበንጃውን ጥይቱን ጠቃውን ምንጣፉን እየሰጡ ደስ አሰኝተው ወደሀገራቸው በእልፍ መለሱዋቸው እየተባለ እስከ ዛሬ ድረስ ሲነገር ይኖራል። አሁንም ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሥልጣኔና የእውቀት ሥራ በሀገራቸው ለማስፋት እንዲጥሩ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ማንም ሰው ያውቃል፤ ነገር ግን አገራቸውን በቶሎ ለማሠልጠን ከሰበ ዘንድ አያሌ ገንዘብ ሳያሻቸው አይቀርምና ከሀገራችን ሕዝብ ጥቂት ለሥራ የሚያግዝ ገንዘብ ቢበደሩ ለቤተ መንግሥቱ እንዳች ጒዳት አያመጣም፤ ይቅርና ድኆች ሳይጨመሩ ስመ ጥሩዎች ሀብታሞች ብቻ በልዩ ሁነው በድፍን ኢትዮጵያ በሸዋ፤ በትግሬ፤ በጐንደር፤ በጐጃም፤ በወሎ፤ በየጁ፤ በሐረር፤ በዳር አገር፤ በአዳል፤ በሱማሌ፤ ያሉ አገረ ገዦዎችና የማረሻ ጌቶች በየግዳማቱ ገንዘብ ያኖሩ መነከሳትና የከበት ዘላኖች ለቤት ጒዳይና ለሠራተኛ ደመወዝ የሚበቃ ያህል አስቀርተው የተረፈውን ገንዘብ በቅን ለመንግሥት ቢያበድሩ በአጭር ግምት አርባ ሚሊዮን የሚሆን ብር በተገኘ ነበር። ይኸም ገንዘብ ምንም ለመንግሥታችን በጠቅላላው የሐሳቡን ፍጻሜ ባይጨርስለት በአንድ ወገን ያለውን ሥራ እንዲያከናወንለት አይጠረጠርም፤ መንግሥትም ከሕዝቡ ሲበደር በማኅተምና በጒርድ ሁኖ የምስክር ወረቀት መስጠት ይገባዋል። ሕዝብም ለመንግሥት ገንዘብ ሲያበድር ያለ አራጣ ማድረግ ይገባዋል። ይኸውም ከእርዳታ ይቈጠርለታል፤ ግን መንግሥት ከሕዝቡ፡ ከተበደረው ከመላው ገንዘብ በ፫በ፫ ዓመት ከብድሩ ገንዘብ ከራት አንድ ይከፍላል፤ እስከ ፲፪ ዓመት ድረስ ግን ጨርሶ እንዲከፍል ውል ይደረጋል። መንግሥትም ከብዙዎቹ ከሥራዎቹ ዓይነቶች ገቢ ገንዘብ በቶሎ እንዲያገኝ መጀመሪያ የመንገድና የድልድይን ሥራ ማስቀደምና ማፋጠን ያስፈልገዋል። በየአውራጃው በየሀገሩ፡በየኬላው፡በየበሩ መንገዱ በፍጥነት ከተሠራ ሠረገላ፡ አውቶሞቢል፡ ጋሪ፡ ካሚዮን፡ እየተመላለሱ የራቀውን እያቀረቡ የቀረበውን እያሰናዱ ሰፍር ቍጥር የሌለው ጥቅም ያስገኛሉ ስንል ተስፋ እናደርጋለ። የሆነ ሁኖ የሀገሬ መንግሥት ከውጭ ሰዎች ባንክ ገንዘብ ይበደር ለማለት እንደኔ ሐሳብ በጽንቀርናዬ ውሥጥ የተሻለ ነገር አይመስለኝም፤ ሊበደር ይገባዋል ባንክ ዓለም ያቆመው ደንብ ነው የሚል ቢኖር የዚህን ትርጓሜ በዝርዝር ለመጻፍ አልችልምና ነጋድራስ ገብረ ሕይወት የሕዝብ አስተዳደር ብለው ያወጡትን መጽሐፍ እንባቢ ተመልከት። የንጉሣችን ሐሳብና ምኞት ድብቅ አይደለም እንደ ፀሐይ የሞቀ እንደ ጨረቃ የደመቀ ግልጥ ነገር ነው። ፲፬ ዓመት በአባታቸው በዳዊት ዙፋን ከተቀመጡ ጀምሮ የሠሩት ሥራ ምልክት (ዓረቡን) ይሆነናል። ይኸውም ቤተ መንግሥቱንና ቤተ ክህነቱን በሚገባቸው ጥንቃቄ መጠበቅ፤ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ቅዱሳት መጻሕፍትን ማሳተም፤ ለካህናቱ ንዋየ ቅድሳት ሽልማት ለድኆቹ ምጽዋት መስጠት፤ ተማሪ ቤት መክፈት፤ ሆፒታል ማቆም፤ ድኆችን ያለ ዋጋ ማሳከም፤ ለባሮ የነፃ ደንብ ማውጣት፤ ድልድይ ማስደልደል መንገድ ማሠራት፤ ተበድሎ ከሩቅ አገር ለመጣ ድኃ ነገሩ እስኪያልቅ ስንቅ መስጠት፤ በየውጭ አገር እንደ ጨው ተዘርተው የነበሩትን የኢትዮጵያን ልጆች መሰብሰብ፤ ለሠራተኛ ደመወዙን መስጠት የድኃውን ልጅ ማሳደግ፤ ለነዳያኑ የዕለት ድርጎ ማስቀበል፤ ለባላገር የከበደውን ግብር ማቅለል ሌሊት በጸሎት ቀን በችሎት መገኘት ነው። የቀረውን የሠሩትን ትሩፋት ለአንባቢ እንዳይበዛ ፈጽሜ ትቸዋለሁ። ሕያው እግዚአብሔር በቸርነቱ ብዛት ዕድለኛ ሀብታም ብልህ ትጉህ እጁ ለመስጠት እንጂ ለመቀጣት የማይፈጥን፡ አንደበቱ ቁም ነገር እንጂ ቀሌት የማይናገር፡ በተዓቅቦ የሚኖር፡ ከዳዊት ከሰሎሞን ዘር ቸር ጠባቂ አስነሥቶልናልና እንደዚህ ያለውን ራትዕ ንጉሥ ተከባክበን ጥልቅ ሐሳቡን እየረዳን ምኞቱን ማስፈጸም ይገባናል፤ መንግሥትና ሕዝብ እርስ በርሱ ሲተጋገዝ ሀብት እየበዛ እውቀት እየሠፋ ምቀኝነት እየጠፋ ይሔዳል። ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ የሰሎሞን አርእያ፤ ወሀብከሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ፡ ለዘለዓለም ትንር አሜን ለይኩን።

በቶለ አበዩ።

የአዲስ አበባ ጅማ ገምቤላ የአቶሞቢልና የባቡር መንገድ ማኅበር።

፩፡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ከዚያም እስከ ገምቤላ የሚሔድ የባቡር መንገድ ሊሠሩ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፈቃድ ከንሲስዮን ሰጥተዋቸዋል። ባለ ከንሲስዮኑ (ባለፈቃዱ) ግን ለብቻቸው የተሰጠውን ፈቃድ ሥራውን ሊፈጽም ከአዲስ አበባ ጅማ ገምቤላ ማኅበር ጋራ ተረዳድተው ሊሠሩ ተባበሩ።

፪፡ ማኅበሩ ሲቆም ያዲስ አበባ ጅማ፡ ገምቤላ፡ መንገድ ማኅበር ተብሎ ይጠራል ዋና መቀመጫውም በአዲስ አበባ ይሆናል።

፫፡ የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ለመጀመሪያ ሐያ ሚልዮን ብር ሊሆን ነው።

፬፡ ያሁኑ የአንድ አክስዮን ዋጋ ሁለት መቶ ብር ቈይቶ ግን እንደጊዜው ዋጋ በውድ ይሸጣል።

፭፡ ከመቶው ሽሕ አክስዮን እስከ ፳፭ሺ ድረስ ቢፈቅዱ ባለከንሲስዮኑ ሊገዙ ይችላሉ። ከቀሩት አክስዮን ፭ሺ በልዩ

ለኢትዮጵያ መንግሥት ይጠባበቃል ። ከቀረውም ፺ሺህ አክስዮን ለኢትዮጵያ ዜጐች ይሸጣል ። ሌላው ግን ለመላ ሕዝብ ሊሸጥ ይችላል ። ነገር ግን ባለ አክሲዮኖች አክሲዮናቸውን ለመሸጥ ቢፈልጉ አስቀድሞ ከማኅበሩ ማስፈቀድ ያስፈልጋል። ቢፈቀድለትም የአክሲዮኖቹ ዕድል ከላይ እንደተመደበው በየክፍሉ አይነት ካልሆነ አዘዋውሮ ለሌላ ለውጭ ክፍልና ነገድ ለመሸጥ አይችልም ።

፯፡ መንግሥት ለባለአክስዮን እንደሚገባ ካልሆነ በቀር በማኅበሩ የሥራ አስተዳደር አክሔድ ወይም ማዘዝ የዋናነት ሥራ የለውም ።

፰ ፡ ማኅበሩ ሰባት ዲሬክተሮች ይሾማል ። እነዚህንም ሰባት ዲሬክተሮች አክስዮን የያዙ ሰዎች ናቸው የሚመርጥዋቸው ሌሎቹ ባለአክስዮኖች ሁሉ ናቸው ፕሬዚዳንቱና ቢስ ፕሬዚዳንቱ በዲሬክተሮች ነው የሚመርጡ ፡ የምርጫውም አኳኋን በጽሕፈት አድርጎ ለዚህ ሥራ በተዘጋጀው ዝግ ሣጥን ማግባት ነው ። ከነዚህም አምስቱ ኢትዮጵያውያን እንዲሆኑ ያስፈልጋል ። ዲሬክተሮቹ ስለማኅበሩ ሥራ ጉዳዮች ለምክር በማኅበሩ ዋና የጽፈት ቤት አንድ ጊዜ በወር ይገናኛሉ ከዚ- ህም ሌላ ለመማከር የሚያስፈልግ የተለየ ነገር የመጣ እንደሆነ ከፕሬዚዳንቱ ወይም ከቤስ ፕሬዚዳንቱ ጋራ ሁነው አራት ዲሬክተሮች የጊዜውን ጉዳይ ሊጨርሱት ይችላሉ ።

፱፡ ዲሬክተሮቹ አንድ ሥራውን የሚያስኬድ ባለደመወዝ ዲሬክተር ይሾማሉ ። እርሱም ለማኅበሩ ሥራ አክሔድ ሁሉ አላፊ ነው ።

፲፡ የሥራው አስኪያጅ ዲሬክተር ለመንገድና ለቤቶች መሥሪ ስለ ሌላም የሚያስፈልግ ነገር ስለደመወዝም በተ- ቀበለው ገንዘብ ላይ ሙሉ ሥልጣን አለው።የሥራው አስኪያጅ ደሬክተር የሚመራበትን ደንብ ዲሬክተሮቹ ይደነቡለታል ።

፲፩፡የሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር የማኅበር ሒሳብ በትክክልና በሥርዓት እንዲሆን ያደርጋል ። ዲሬክተሮቹም በየጊዜው ይፈትሹታል ።

፲፪፡የሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር በየዓመቱ ገቢና ወጭ ትርፍም የባለ አክስዮኖች ድርሻም የሚያሳይ የማኅበሩን ሒሳብ ያስደርጋል።ይህ ሒሳብ ዲሬክተሮቹ ፈትሸውት ሲያበቁ ታትሞ ለባለአክስዮኖች ይታደላል ። ማኅበሩ ሁሉ በየዓመቱ ታላቅ ጉባዔ እንዲያደርግ ይሰበሰባሉ

፲፫፡የሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር ከፕሬዚዳንቱ ወይም ከቤ- ስፕሬዚዳንቱ ጋራ ተማክሮ የማኅበሩን ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች ይቀጥራል።እርሱም እራሱ የማኅበሩ ሥራ በትክክል ስለመሔዱ አላፊ ይሆናል ።

፲፬፡ዲሬክተሩ አስኪያጅነት ለማኅበሩ ጥቅምና ትርፍ የሚ- ጐዳ እንደሆነ ፕሬዚዳንቱ ከዲሬክተሮቹ ጋር ተማክሮ ከሶስት ወር በፊት በጽሕፈት አስታውቆ ያሰናብተዋል እንደዚሁ ዲሬ- ክተሩም ደግሞ ለመሰናበት የፈቀደ እንደሆን ከሶስት ወር በፊት ለፕሬዚዳንቱ በጽፈት አስታውቆ ሊሰናበት ይችላል ።

፲፭፡የሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር የኩፓንያውን ሠራተኞች ለማስወጣት ቢፈልግ የሚያስወጣበት ምክንያትን ካንድ ወር በፊት ጽፎ ሰጥቶ ከሥራ ሊያስወጣቸው ይችላል።ከሥራ የወ- ጣው ሠራተኛ ግን ወደፕሬዚዳንቱና ወደ ዲሬክተሮቹ ሊጮህ ይችላል ።

፲፮፡የደረሰኝ ምስክር ለባለ አክስዮኖቹ ይሰጣል እርሱም ቀጥሎ እንደተጻፈው አይነት ነው።የጅማ ገምቤላ የአቶመቢልና የባቡር መንገድ ማኅበር

የአ ጅ ገ ማኅበር የገንዘብ ደረሰኝ

ከ

ስለ

የአንድ አክስዮን ዋጋ ሁለት መቶ ብር ሒሳብ

ለ አክስዮን ዋጋ ብር ተቀብለናል

ወር ቀን ዘመን

የጸሐፊ ፊርማ የሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር ፊርማ

የፕሬዚዳንት ፊርማና የማኅበሩ ማኅተም ማኅበሩ በማና- ቸውም ምክንያት ቢሆን እስከ ዓሥር ዓመት ሊፈርስ አይችልም ከዚያም በኋላ ቢሆን ከማኅበረተኞቹ የሚበልጡት መፍረሱን ካልፈቀዱ በቀር ሊፈርስ አይችልም ።

ስለ ንግድ ሥራ መሻሻል ።

የንግድን ሥራ ለመሻሻል ሲሉ ባለፈው ዓመት ነጋድረስ መኰንን ጀምረው ነበር። በመካከሉ የኢትዮጵያ መንግሥት የንግድ ሚኒስቴርና የሎንዶን ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ተብለው ወደ እንግሊዝ አገር ስለሄዱ ክቡር አቶ ገብረ እግ- ዚአብሔር እንደራሴ አድርገዋቸው ሔዱ ።

ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔርም አስቀድሞ በፍጹም ልባቸው ለንግድ ሥራ አክሔድ ሕግ ለማቆምና የሀገራችን ንግድ በትክክል እየሰፋ እንዲሄድ ሲሉ እውነተኛ ሐሳብ ስለነበራቸው ዛሬ በፍጹም ለነጋዴው ታላቅ ጥቅም ያለው ሕግና ደንብ አወጡለት። ማለት ይኸውም በጭሩ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው። መጀመሪያ የሀገራችን ነጋዴዎች ንባብና ጽሕፈት ባለማወቃቸው ባልተቀበሉት ገንዘብና ውል በጣታቸው እያስፈረሙ ብዙ ጉዳት ያገኛቸው ነበር ዛሬ ግን ለማናቸውም ውልና ገንዘብ መቀበበያ ጽሕፈት ቤት በየበሩ ቆመላቸው ደግሞ ለዚሁም ገንዘብ ሲቀ- በበሉና ሲዋዋሉ ምንም የሚከፍሉት ገንዘብ ሳይኖር ማድረ- ጋቸው እጅግ መልካም ነው ።

፪ተኛ፡ በኛ አገር ነጋዲዎችና በውጭ አገር ነጋዴዎች መካከል በንግድ ነገር ላይ በሚነሳው ጠብ ሁሉ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ የሀገራችን ነጋዲዎች በውጭ አገር ዜጐች እጅ አላአገባብ እየተመቱና እየተገፉ በከንቱ ይቀሩ ነበር ። ዛሬ ግን እንደዚህ ያለው ነገር ሁሉ እንዳይሆን ሲባል ለነጋዲዎች በልዩ የቆመ የንግድ ክፍል ሥራ ዳኝነት ቤት በማቆማቸው ለነጋዴው ታላቅ ጥቅም ያለው ነገር ሆነለት ። ደግሞ ነጋዴ የሆነ ሰው ሁሉ ለንግዱ ሥራ የሚመሰክር ወረቀት (ፓስፓርት) ካለው በማናቸውም ስፍራ ቢሆን በንግድ ነገር ቢከሰስ የክፍሉ ዳኛ ነጋዴ መሆኑን የሚመሰክር ወረቀት ካየና ነገሩም በንግድ ነገር መሆኑን ከመረመረ አፈጣጥሞ በልዩ ወደቆመው

የንግድ ክፍል ዳኝነት ቤት መላክ ግዴታ ስለሆነበት ስለዚህ ለነጋዴው መልካም ሆነ ።

ደልቁንም አሁን በየዳር አገሩ ያለው ገባያና ኬላ ሁሉ በንግድ ሚኒስቴር እጅ እንዲሠራ ስለተፈቀደ ስለዚህ ነጋዴዎቹ በየመንገዱ ችግር ሳያገኛቸው እንዲመላለሱ አይጠረጠርም።

ደግሞ ክቡር አቶ ገብረ እግዚአብሔርም እንደሐሳባቸውና እንደ አሁኑ ሥራ አያይዝ የንግድ ሥራ በሀገራችን ላይ ያለ እንድ ዕንቅፋት ይሔዳል በማለት ተስፋ አለን ።

ማለት የሥራ ቤቱንም ማማርና የሥራውን አካሔድ ላየው ሰው እጅግ የሚያስደቅ ነው ።

እጓለ ጽዮን ።

የሥልጣኔ መንገድ አሰፋፍ ።

እውነተኛ የውቀት መሪያችን አፄ ኃይለ ሥላሴ ልዑል አልጋ ወራሽ ተብለውና ግርማዊ ንጉሥ ባለሙሉ ሥልጣን ተብለው ይህች ለምለም የሆነች አገራችን በ፲፫ ዓመት ውሥጥ የሥጋ እንቅልፍ በማያሸንፈው ትጋታቸው በሰላም ሠርተው በብርሃን እየገለጹ በሥልጣኔ መንገድ እንደልቧ እንድትራመድ ከጥቂቱ በብዙ ከፍ አደረጉዋት። አሁንም ይህነን ደግ ሥራቸውን እየለማ እየሰፋ እንዲሔድ ብዙ ተስፋ አለኝና ከዚህ በታች ለሥራው አሰፋፍ የሚስማማ አጭር ቃል አጽፋለሁ ።

ዋና የሥልጣኔ መንገድ የሚያስፋፋ ዓይነተኛውን ሥራ በየወረዳው ባሉ ትልልቅ ከተሞች የተማሪ ቤት ማቆም ነበር፤ ስለሆነ ግን በየክፍሉ ብዙ ተማሪ ቤት ሲቆም ላስተማሪዎቹ ደሞዝ ለተማሪዎቹ ምግብና ልብስ ለመጻሕፍቱ መግዣ ለተማሪ ቤቱ ማሠሪ ለጊዜው ከመንግሥት ግምጃ ቤት ብዙ ገንዘብ የሚያስፈልግ ስለሆነ ሥራው ቶሎ ሊከናወን አይችልም ። እንዲህ ስላልሁም ብዙ ገንዘብ ይፈጃልና ተማሪ ቤት አይሠራ ይቅር ለማለት አይደለም ብቻ የተማሪ ቤት በየወረዳው ማቆም ሥራው ትልቅ ነውና የታሰበው እስኪፈጸም አሁን ለጊዜው ከመንግሥት ግምጃ ቤት የገንዘብ ኪሳራ ሳይፈልግ ካገር በሚገኘው ቀረጥ ራሱን ችሎ (ያውም ለመንግሥት ግምጃ ቤት ሲያተርፍ) ያገር ሥልጣኔ የሚያስፋፋ በመላ ኢትዮጵያ ያለ ኬላና ገበያ ያቀራረጡን ሥራ ለሻለቃ ሳይሰጡ ከንግድ ምንስቴር ሥልጣን በታች ሁኖ የሠለጠኑ ነጋድራሶችና የተመረጡ ጸሐፊዎች ቢሠሩት ነው ። እኒህ የተመረጡ ነጋድራሶችና የሠለጠኑ ጸሐፊዎች ያገር ሥልጣኔ ማስፊያ ሊሆን የሚሠሩት ሥራ ምን እንደሆነ እንድንረዳው ከብዙ በጥቂቱ ከረጂሙ ባጭሩ ከዚህ ቀጥለን እናመለክታለን ።

፩ ደኛ ፤ የመንግሥት ሠራተኞች የሚሠሩት ሥራ ከመንግሥት ግምጃ ቤት በየወሩ የሚገባቸውን ቀለብ እየተሰፈሩ ስለሚሠሩት በጥንቃቄ ይሠሩታል ። ሥራውን በደምብ የሚሠሩት ስለሆነ በማናቸውም ከተማ የውጭ አገር ነጋዴ ይበዛል። አንዲት ልጃገረድ ጓደኞቿዋ የሚሆኑ ነገር በጨዋታ አነሳሥተው መልክ መልካም ብትሆኝ ትወጃለሽን ወይንስ ባለሟያ? ብለው ቢጠይቋት መልኬ ይመርልኝእንጂ ሞያውንስ ከጐረቤት እበደረዋለሁ» ብላ መልስ ሰጠች ተብሎ በተረት እንደሚወራ ሁሉ በያንዳንዱ ከተማ የውጭ አገር (ማለት ከሠለጠኑ ወገኖች) ሰው ከበዛ ዘንድ ተመክሮ የማይሰማ ተምሮ የማያጠና ደለሞና የነሱን ሥራ እያዩ ሁሉም ሠርቶ አዳሪ ይሆናል ። ስለዚህ ንግድ ሰፋ አገር ሠለጠነ ማለት ነው ።

፪ ተኛ የሠለጠኑ የመንግሥት ሠራተኞች በሔዱበት ክፍል በማናቸውም ነገር ከትልቁ ከተማ (ንጉሠ ነገሥት የሚኖርበት) ሁልጊዜ በወረቀት መገናኘት ግድ የሚያስፈልግ ስለሆነ የወር ገቢ ወጭ ማስታወቂያ ጊዜ የለወጠው የመንግሥት ደንብ ጋዜጣ የዘመድ ሰላምታ ሌላም ይህን የመሳሰለ ሁሉ የሚያመላልስ በስጣ ይቆማልና ደግ ሆኑ ክፉ ያገር የፑለቲክ ወሬ የጥዋቱ ማታ የማታው ጥዋት ከመንግሥት ጆሮ ይገኛል መንግሥትም ከከተማው ወይንም ካገሩ የሚመጣለትን የፑለቲክ ምሥጢር እያዩ እየመረመረ የጠመመውን አቅንቶ የጐደለውን ሞልቶ ላገሩ ለከተማው ለሕዝቡ ለደኃው የሚሰማማው የሚያስፈልገውን ከማድረግ አይመለስም ስለዚህ ይህን በመሰለ ሥራ ሁሉ ያገር ሥልጣኔ ይሰፋል ለማለት እንችላለን ።

፫ ተኛ እውነተኞች የመንግሥት ሠራተኞች አገራቸውን የሚያፈቅሩ መንግሥታቸውን የሚያከብሩ ባሉበት አገር በሥራቸው ሁሉ ማለት ሕሊና በሚያስበው አንደበት በሚናገረው እጅ በሚጽፈው አፍ በሚያነበው አገርን ማፍቀር ንጉሥን ማክበር ባንድነት ፍቅር መተሳሠር እንዴት ያለ የጥቅም መሠረት እንደሆነ ጠብ ክርክር መለያየት ግን ያገር ነፃነት ተቃዋሚ መሆኑን ለህዝብ ገልጸው ያስረዳሉና በዚሁ በደግ ሥራቸው ለሔዱበት አገር መልካም አርአያ ይሆናሉ በዚህ ምክንያት ያገር ሥልጣኔ ከጥበት ወደስፋት ሲገሠግሥ ያድራል ።

፬ተኛ የታመኑ የመንግሥት ሠራተኞች በሔዱበት ክፍል የሚገዛ የሻለቃ በላይኛው መስመር በመለከትነው ደግ ሥራቸው ለሱ ለራሱ መልካም አርአያ ይሆኑለታልና በውነት ለመንግሥቱ የሚረዳ የሚያገለግል በንደበቱ ክፉ የማይናገር ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሚል ትክክለኛ ፍርድ የሚፈርድ የማያደላ ጉቦን የሚጠላ የሕዝቡን ጉዳት የማይወድ አገሩን የሚያፈቅር መንግሥቱን የሚያከብር እውተኛ ታማኝ ይሆናልና በውሥጡ የሚገዛ ሕዝብ ሀብታም ባለጸጋ የሚገዛው አገር ለምለም የጠዳ ይሆናል ስለዚህ ያገር ሥልጣኔ እየሰፋ ይሔዳል

፭ተኛ የንግድ ሥራ አርአስት አድርጌ ተናገርሁ እንጂ ንጉሥንና መንግሥትን (ንጉሥንና ሕዝብን) አስተቃቅሮ ሳያነቃቅፍ እንዲያስተዳድር አገር እንዲያሠለጥን ከሻለቃ ወደ መንግሥት ሊዞር የሚገባውስ ሥራ ይህ ብቻ አልነበረም እውነት ከሻለቃ ወደ መንግሥት ሊዞር የሚገባውስ ሥራ የሻለቃ ራሱ ሲሆን ጠቅላይ ወንበርና የፍርድ ጸሐፊዎች ከመንግሥት የሻለቃ ራሱ ሲሆን የከተማ ከንቲባ ከመንግሥት የሻለቃ ራሱ ሲሆን ያገር ዓሥራት ጠባቂ ከመንግሥት ሁኖ ቢሆን ሥራው በትክክል ይሠራ ነበር ማለት ጠቅላዩ ወንበርና የፍርድ ጸሐፊዎች ከመንግሥት ከሆኑ ባደባባይ ፍርድና በልፍኝ ምክር ከሻለቃ ጋር አይነጣጠሉምና ደኃ ይጠበቃል አይጐዳም ።

እንዲዚሁ ሁሉ ከንቲባ ከመንግሥት ከሆነ ዘንድ ዓይነተኛ ሥራው ሌባ ቀማኛ ፈንጋይ ቤት አቃጣይ ካገር ማጥፋት

ከተማን ማጥዳት ነውና ሌባ ካገር ከጠፋ ሕዝብ በለጠገ፡ከተማ ከጠዳ ሰው ከበሽታ ዳነ፡ አገር ሠለጠነ ማለት ነው ።

ያገር ዓሥራት ጠባቂም ከመንግሥት ሲሆን ትልቁ ዋነኛ ሥራው መሬቱን በትክክል አርሶ ባመት በመቱ ለመንግሥት ዓሥራት ከሌላው ገበሬ ይልቅ አብልጦ ያሰፈረ ሰው ስሙን ጠርቶ አገሩን ለይቶ ወደመንግሥት ማመልከት ነው፡ መንግሥትም በየወረዳው የሚመጣለትን የገበሬዎች ስም አይቶ የሥራቸውን ፍሬ አመዛዝኖ የሚገባቸውን መዓርግ ይልክላቸዋል (ይሸልማቸዋል) የቀረውም ገበሬ ከመንግሥት የሚላከውን ሽልማት አገኛለሁ ሲል ጠፍ መሬቱን አልምቶ ያርሳል፡ከሽልማቱም ሌላ ከእህሉ ምርት ከሥር አንድ ወደመንግሥት ይሔድበታል እንጂ ዘጠኙን እጅ ከጉታራው ስለሚከት የድካሙ ፍሬ ጌትነት ባለጸግነት መሆኑን ያረጋል ። በንዲህ ያለ የጥቅም ፖለቲክ ያገር ሥልጣኔ እየሰፋ ይሔዳል ለማለት እንችላለን ።

፯ተኛ፤ በላይኛው መስመር በዝርዝር ጽፌን ያመለከትነውን የሥራ ክፍል ከሻለቃ ወደመንግሥት ቢዘር ለሻለቃ የሚገባውን አበል መንግሥት አይወስድበትምና ድካሙ ቀለለት እንጂ መዓርጉ አልተቀነሰበትም ። ይልቁንም ደግሞ ከወሰን እንዳይተላለፍ (የማይገባውን ከማሰብ) እኒህ ከላይ ስማቸውን የጠራናቸው ሠራተኞች በምክር ሆነ በደንብ ይከለክሉታልና ሕይወቱ በክብር እንደተጠበቀ ይኖራል። ክቡር የሰው ደምም በከንቱ እስከመፍሰስ አይደርስም ።

፰ተኛ፤ በኔ ዓቅም ቃሉ እንዲህ ብዬ መጻፌ እርዳታ መስሎ ስለታየኝ ነው እንጂ የደንብ ማስተካከል ሥልጣን ተሰጥቶኝ አይደለም ። ከኔ ይልቅ አብልጠው ሥራቸውም ሁኖ የሚያስቡበት ብዙ የተማሩ እንዳሉ አውቃለሁና በደፈርሁ ይቅርታችሁን እለምናለሁ ። ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ተጻፈ ክምባታ ሆሣዕና ከተማ ።

ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ።

ስለ ደብተራ ክንፈ ዕረፍት ።

ሚያዝያ ፳፬ ቀን ዓርብ ከሌሊቱ በ፲ ሰዓት ተኩል አባታችን ደብተራ ክንፈ አዲሱ ዐረፉና ቅዳሜ ሚያዝያ ፳፭ ቀን በ፯ ሰዓት ተኩል በማረ ፍታት አዲስ አበባ ግብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ፤ዕድሚያቸውም ፷፯ ዓመት ነው።ካገራቸውም ከጐዣም ከዲማ ጊዮርጊስ ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ የመጡም በ፲፰፻፹፫ ዓመተ ምሕረት በዘመነ ማቴዎስ ነው።አዲስ አበባ በገቡ በ፴፯ ዓመታቸው መሞታቸው ነው ከዚህም ቀጥዬ የኃዘን ግጥም እጽፋለሁ ።

አልደርስበትም አልኩ ብሮጥ ብጣደፍ ፤ አሁን ለኔ ማነው የሚሰጠኝ ክንፍ ። ብዬ ብነግራቸው አባቴ ጠፉብኝ ፤ በቀበና አለፈ ብለው መለሱልኝ ። ካሰቡበት ሰፍረ ደርሶ መምጣት ቀረ ፤ ላይ ላይ የማይበት ክንፌ ተሰበረ ። አባቴ ሳለልኝ ብዙ አምር ነበረ ፤ ባለብስ ባላጌጥ ብዙ አምር ነበረ ፤ ባልበላ ባልጠጣ ብዙ አምር ነበረ ፤ ማዕረጌ አባቴ ብዙ ዓለሜ ቀረ ። ሁሉም ከባቴ ጋር አብሮ ተቀበረ።

ስንት ዓለም ይሆናል ቢገመት አንድ አባት ፤ ይሆን መርምራችሁ ገምታችሁ በውነት ፤ ወንድሞቼ አስረዱኝ ያንድ አባትን ዓምት ።

ልጆቼ ሳሉልኝ አገሌ ሳለልኝ የሚነክኝ ማነው ፤ እንዲህ ብሎ ማለት በብዙ ሐሰት ነው ። ሞት በመጣ ጊዜ ማነው የሚያድነው እንኳን ማዳንና ማነው የሚቀርበው ፤ እንደ ትንሽ ዕቃ ጥሎ ገለል ነው ፤ አታውቁትም ብሎ ሞት ቢጠይቃቸው ጥለውት ሸሹ አሉ አናውቀውም ብለው ።

እንግዲህ አላዝንም ብከሳ ብጠቍር፤ ገላ ጋይ ነውና ሰውነትም አፈር ። ቀድሞ ዘመድ ሙቶት ያለቅስ የነበረው ። ያደ ጀመር ተቀምጦ ደግሞ እሱ በፈንታው ። እሱን ሲያዝን ሲያለቅስ ከዳር ሁኖ ያየው ።

ሞት ከቤቱ ገብቶ ቢደርስበት ተራው።ይዘል ይፈርጥ ጀመር አዙሮ እስኪጥለው ። የሞተ ሰው የለም ያለሱ ሌላ ሰው ደህን መራር ኃዘን በል እንዲህ ቀመሰው ። እሱንም ያንጊዜ ያረገው እንዲህ ነው ። አላዝንም ብሎ የሚቀየም ማነው ። ለሁሉም ይኸ ሞት ይደርሳል በዙሯው ። በራሱ ይዞ ነው ሁሉም የሚሔደው ። ከሞት በዚህ ዓለም ተርፎ እሚቀር ማነው ። ተራውን ጠብቆ ዝም ብሎ ማለፍ ነው ። ልብ ላረገው ሰው ለተመለከተው ። ይኸው አሮጌው ሞት ዘወትር አዲስ ነው ሞት ያልገባበት ቤት ሞት የገባ እደሆን ። እንደምን ተጨንቀው ይቀበሉት ይሆን ። ሞት በሰው ላይ ሲያዩት እንደምን ይቀላል።በራስ የመጣ እንደሁ አዙሮ ይጥላል። ዳዊት ልጻፍ ብሎ ጀምሮ ካንድ መዝሙር ። የብረት ብዕር ጽፈት ብዕሩ እጅግ ባያምር። ሰብእሰ ከንቶ ይመስል ወመዋዕሊሁኒ ከመ ጽላሎት የሐልፍ የሚለውን መስመር ። ብረት ብዕሩን ትቶ ጻፈው በመቃብር ። ክንፌ አዲሱ ብልህ አዋቂ ሰው ነበር።

በብረት ብዕር መጻፍ አታውቅም ይላሉ፤ እንግዲህ ማደሻሁ መቃብር ነው አሉ ። ሁለተኛ የኛ ትንሽ ወንድም ኃይሉ ክንፌ ደግሞ የወንድማችን ያቶ መኰንን ክንፌ ልጆች ሐዲስና ኂሩት የሚባሉት በሕፃንነታቸው ወራት ስለሞቱ አባታችን በብዙ አዘኑ ለመፅናንትም አልቻሉም ወዳያው አባታችን ሞቱ።ምን ያለው አባት ነው መሔድ የለመደ።ልጆቹ ቢጠሩት ተከትሎ ሔደ ። አንድ ላይ ተቀምጦ ከልጅ ልጆቹ ጋር ። ትንሽ ልጅ ይመስል ይጫወታል ባፈር ። እናንት ወንድሞቼ ሰው ፈረደባችሁ ። አባት አስከትሎ መሔድ ይቅርባችሁ ።

ሦስተኛ ያልታሰበ አደጋ አባቴ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ያረፉ ሚያዝያ ፳፯ ቀን የትንሽ እኅታችን ሠርግ ነበረ ። አባታችንን ቅዳሜ ቀብረን እሑድ ሙሽራው መጥቶ ማታውን ሙሽራይቱን ይዞ ሔደ በዚያም ለልቅሶ የመጡት ሰዎችና ዘመዱም ጕረቤቱም ተዚህ ቀደም ያልተደረገ አዲስ ነገር ስለሆነ ቅር አላቸው፡የቅርብ ዘመድ የሆኑትም ሰዎች አትሔድም እስከ ማለት ደረሱ።እኛም ላባታችን ከኛ የሚቀርባቸው ሰው ባለመኖሩና ቀርቶም የሚጠቅመን ነገር ባለመኖሩ ያለ ይሉኝታ ሰደድናት ። አባታችንስ የሚነሡ ቢሆን እሽ ብለን ነገራቸውን እንቀበላቸው ነበር። ነገር ግን ከነገራቸው ውሥጥ ፍሬ አጣንበት እንጂ በዚህም በሥራችን የሥልጣኔን መንገድ የተከተልን ያስመስ-

ለናል ። ግን እንደዚህ ያለ አደጋ ከዚህ ቀደም የተደረገ አይመስለኝም ። እንዲህም ማለቴ የዋናው ሠርግለት ሠርገኛ ብልቶ ጠጥቶ ተሳክሮ ሲጣላ አበት ለማገልገል ወይም ይህንን ብመስለ በሌላ ምክንያት አምባ ጓሮ ውሥጥ ይሞታል ሲሉ እንሰማለን እንጂ ፥ እንደዚህ ሁኖ የሞተ ይገኝ አይመስለኝም። ስለዚህም ትንሽ የኀዘን ግጥም እጽፋለሁ ።

እንጀራው ተጋግሮ ወጡ ተሰናድቶ ጠላው ጠጁ ቀርቦ የተ-ቸገረ ሰው ደግ ሰው መሰለ ፤ ምነው አባታችን አፈር ቀምሶ ዋለ ፤ እንደ ቋሚ ሁኖ አንድ ቀን ሳይከራ ፤ ዐርፎ ያበላናል ልጆቹን እንጀራ ፤ ዐርፈው ከቤታቸው አንድ ቀን ሳይውሉ፤ ለኛ ትዳር ብለው ወዲያ ወዲህ ሲሉ ዛሬስ ደከሙና አባቴ ዐርፈው ዋሉ ። በውል ተጠንቅቀህ ድግሡን ደግሠህ ። ሠርግ አለብኝ ብለህ ዘመድ ወዳጅ ጠርተህ ። ሠርገኛ ሲገባ ለምን ነው መጥፋትህ። ልንገርህ አባቴ ይህ ነገር ነውር ነው። እንዳላሰናዳ እንዳልደገሥ ሰው ፥ ለምን ትታጣለህ አባቴ ከስፍ-ራው ። አንተን ከቤት ቢያጣ ዘመዱ ቅር አለው ። ይህንን የሰነበተውን ነገር አዲስ ነገር አድርጌ ስጽፍ ቅር የሚለው ሰው ይኖር ይሆናል ። ነገር የቈየበትን ምክንያት ከዚህ ቀጥየ እጽፋለሁ አባቴ ባረፉ በ፪ኛው ቀን ታምሜ ሕመሜ ቢፀናብኝ እዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ገብቼ በሐኪሞቹ ትጋትና በእግ-ዚአብሔር ቸርነት ስለ ዳንኩ ምንም ቢሆን ከዳንኩ ያባቴ መታሰቢያ እንዳይቀር ብዬ ጻፍኩ እንጂ የሰነበተ ነገር ከጊዜው ካለፈ ቅር ማሰኘቱ አይቀርም ፤ ደኅሞ በሩቅ ያሉት ዘመዶ-ቻቸውና ወዳጆቻቸ እንዳልሰሙ እውቃለሁና እንዲሰሙ-ያባቴን ዕረፍትና የኀዘኔን እንጉርጉሮ ለብርሃንና ሰላም አን-ባቢዎች ለኀዘኔ ተካፋዮች ጽፌላችኋለሁ ። እሸቴ ክንፎ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን ባታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው ።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ፥ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሽክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኩላ።

ፔር ዳኜይ።

አ በ ከ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው፡ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።

የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S. E. & A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴
6me ANNÉE № 30

ሐሙስ ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 24 JUILLET 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዋጅ

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ።
ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የኢትዮጵያ ዜጋ ሁኖ ለመቈጠር ለሚገባው ለውጭ አገር ዜጋ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሕግ አቁመናል ።

መጀመሪያ ።

በኢትዮጵያ ወይም በውጭ አገር ከአንድ ኢትዮጵያዊ ወይም ከአንዲት ኢትዮጵያዊት የተወለደ ሁሉ የኢትዮጵያ ዜጋ ነው ።

ሁለተኛ ።

አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጭ አገር ሴት ጋራ በሥርዓት የተጋባ እንደ ሆነ ሴትዮዋ የኢትዮጵያ ዜጋ ትሆናለች ።

ሦስተኛ ።

ይህን በመሰለ ጊዜ በሥርዓት የተደረገ ሁኖ የሚቈጠረው ጋብቻ ።

ሀ) አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ከአንዲት የውጭ አገር ሴት ጋራ እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ወይም እንደ ኢትዮጵያ ጋብቻ ልማድ በባለ እኩል ደንብ (ሲቢል) በኢትዮጵያ የሚደረገው ጋብቻ ነው ።

ለ) አንድ የኢትዮጵያ ሰው ከአንዲት የውጭ አገር ሴት ጋራ በተጋቡበት አገር እንደሚደረገው የጋብቻ ሥርዓት በውጭ አገር የሚደረገው ጋብቻ ነው ።

አራተኛ ።

አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነች ሴት ከአንድ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በሥርዓት የተጋባች እንደ ሆነ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በመጋባቷ ምክንያት የባሏን ዜግነት የምትይዝ የሆነች እንደ ሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆንዋ ይቀራል ። የጋብቻዋ ሥርዓት የባሏን ዜግነት የማይሰጣት የሆነ እንደሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜጋ እንደሆነች ትቀራለች። ነገር ግን በጋብቻ ምክንያት የውጭ አገር ዜጋ የሆነችው ሴት ባለርስት የሆነች እንደሆነ ፣ የርስቷ ነገር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በቆመው የርስት ደንብ ይጨረሳል ።

አምስተኛ ።

ይህን በመሰለ ጊዜ በሥርዓት የተደረገ ሁኖ የሚቈጠረው ጋብቻ።

ሀ) የኢትዮጵያ ሴት ከአንድ የውጭ አገር ሰው ጋራ በባሏ ቆንስል ፊት በኢትዮጵያ የምታደርገው ጋብቻ ነው ።

ለ) የኢትዮጵያ ሴት ከአንድ የውጭ አገር ሰው ጋራ እንደ ባሉዋ አገር ሕግ ፣ ጋብቻውም በሚፈጸምበት አገር እንደ ሚደረገው የሕግ ሥራዓት በውጭ አገር የምታደርገው ጋብቻ ነው ።

ስድስተኛ

ከዚህ በላይ በተጻፈው ክፍል እንደ ተነገረው የኢትዮጵያና የውጭ አገር ሰዎች በሥርዓት ተጋብተው ልጆች የወለዱ እንደ ሆነ የተወለዱት ልጆች ሁሉ የአባታቸውን ዜግነት ይይዛሉ ። ስለሆነ የጋብቻ ሥርዓት ፈጽመው ከተጋቡ ከአንድ ኢትዮጵያዊና ከአንዲት የውጭ አገር ሴት የተወለደ ልጅ የእናቱን የቀድሞ ዜግነት አለመያዙን ሥልጣን ባላቸው በኢትዮጵያ ሹማምንቶች ፊት ተጠይቆ ማስረዳት አለበት ።

ሰባተኛ ።

የጋብቻ ሥርዓት ፈጽመው ከተጋቡ ከአንዲት የኢትዮጵያ ሴትና ከአንድ የውጭ አገር ሰው የተወለደ ልጅ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ እንደ ሆነ ፤ ከአባቱ ዜግነት መውጣቱን አስመስክሮ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ወደ ኢትዮጵያ ዜግነት ሊመለስ ይችላል ።

ስምንተኛ ።

አንድ የውጭ አገር ሰውና አንዲት የኢትዮጵያ ሴት ልጅ ከወለዱ በኋላ እንደ አባትየው አገር ሕግ በሥራዓት የተጋቡ እንደሆነ ፤ ደግሞ የአባትየው አገር ሕግ ልጁን የውጭ አገር ዜጋ የሚያደርገውና የውጭ አገር ዜጋም በመሆኑ ምክንያት የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ የሚያሳጣው የሆነ እንደ ሆነ፤ ከጋብቻ በፊት የተወለደው ልጅ የአባቱን የውጭ አገር ዜግነት ይይዛል ። በዜግነቱ የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ ለማግኘት ያልቻለ እንደ ሆነ ግን የኢትዮጵያ ዜግነቱን ጠብቆ ይኖራል።

ዘጠነኛ ።

አንድ የውጭ አገር ሰውና አንዲት የኢትዮጵያ ሴት ሳይጋቡ ልጅ የወለዱ እንደ ሆነ ፤ የውጭው አገር ሰው ልጄ ነው ብሎ ቢቀበለውም ፤ ልጄ ነው ብሎ በተቀበለ ጊዜ የአባትየው አገር ሕግና ሥርዓት ለልጁ የአባቱን ዜግነትና ዜጋ በመሆኑ ምክንያት የሚቀበለውን ሥልጣን ሁሉ የሚያገኝ ካልሆነ በቀር የኢትዮጵያ ዜጋ መሆኑ ሊቀርበት አይችልም።

ዓሥረኛ ።

የውጭ አገር ሰዎች እንደ አገራቸው ሥርዓትና ሕግ አንድ የኢትዮጵያ ልጅ ዋጋሳ አድርገው ያሳደጉ እንደ ሆነ የልጁ የቀድሞ የኢትዮጵያ ዜግነቱ ምንም ቢሆን አይለወጥም ።

ዓሥራ አንደኛ ።

ሀ) አንዲት የኢትዮጵያ ዜጋ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በመጋባቷ ምክንያት የሌላ አገር ዜጋ ሁና ልትቈጠር የተገባት እንደ ሆነ ።

ለ) አንድ የኢትዮጵያ ዜጋ ዜግነቱን ለውጦ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ እንደሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ መሆናቸው ይቀራል።

ዓሥራ ሁለተኛ ።

ሀ) እንደ አገሩ ሕግ በፈቃዱ አዳሪ ለመሆን ወደሚችልበት ዕድሜ የደረሰ ።

ለ) ቢያንስ ቢያንስ አምስት ዓመት በኢትዮጵያ የኖረ ።

ሐ) ለሕይወቱና ለራሱ ለቤተ ዘመዱም የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት የሚችል ።

መ) የአማርኛ ቋንቋ የሚናገርና የሚጽፍ ።

ሠ) ከዚህ ቀድሞ በኃጢአት ወይም በወንጀል ያልተፈረደበት መሆኑን የሚያስመሰክር የውጭ አገር ሰው ሁሉ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይችላል ።

ዓሥራ ሦስተኛ ።

የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን የሚፈልገውም የውጭ አገር ሰው ጥያቄውን ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያቀርባል ። ከዚህም ጥያቄ ጋራ ማን እንደ ሆነ የሚመሰክርለትን ወረቀትና ከዚህ ቀድሞ ተከሶ እንደሆነ የተፈረደውን ነገር የሚያስረዳ የፍርድ ወረቀቱን ጨምሮ ያቀርባል ።

ዓሥራ አራተኛ ።

በተለየ የአገር ግዛት ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሌላም አንድ የመንግሥት ሹም በአንድነት ሁነው የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ከሚጠይቀው ሰው ጋራ በቀጥታ ከተነጋገሩ በኋላ ፤ ጥያቄውን ተመልክተው የሚያስፈልገውን ምርመራ አድርገው የኢትዮጵያ ዜጋ እንዲሆን ይፈቅዱለታል ወይም ይከለክላል ።

ዓሥራ አምስተኛ ።

ዜግነቱንም በመንግሥት ማስታወቂያ (በዲክሬ) ይቀበላል ። አዲሱም የኢትዮጵያ ዜጋ በነዚሁ ዳኞች ፊት ቀርቦ የኢትዮጵያን መንግሥት እንዳይከዳ ይምላል ።

ዓሥራ ስድስተኛ ።

የውጭ አገር ሰው በዚህ አደራረግ የተቀበለው የኢትዮጵያ ዜግነት ለራሱ ብቻ ይረጋል እንጂ ሚስቱ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ካልጠየቀች በቀር አስቀድሞ የያዘቿውን ዜግነት አይለውጠውም ።

ዓሥራ ሰባተኛ ።

አስቀድሞ የኢትዮጵያ ዜጋ የነበሩ የውጭ አገር ዜጋ የሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ለመኖር ተመልሰው መጥተው እንደ ገና ወደ ኢትዮጵያ ዜግነት ለመመለስ ከመንግሥት የጠየቁ እንደሆነ የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ይችላሉ ።

ዓሥራ ስምንተኛ ።

ከውጭ አገር ሰው ጋራ በመጋባትዋ ምክንያት የኢትዮጵያ ዜጋ መሆኑዋ የቀረ የኢትዮጵያ ሴት ከባሏ ተፋትታ ወይም ባሏ ሙቶባት ጋብቻዋ ፈርሶ ወይም ከርሱ በመለየቷ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ የተቀመጠች እንደ ሆነና እንደ ቀድሞ የኢትዮጵያ ዜጋ ልሁን ብላ ከኢትዮጵያ መንግሥት የጠየቀች እንደሆነ ፤ እንደ ገና የኢትዮጵያ ዜጋ ለመሆን ትችላለች ።

ይህ ሕግ ከዚህ ቀድሞ ስለ ዜግነት ነገር የወጡትን ሕጎች ሁሉ ያፈርሳል ።

ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመተ ምሕረት አዲስ አበባ ።

Lion Vainqueur de la Tribu de Juda
HAILE SELLASSIE Ier
Elu du Seigneur, Empereur d'Ethiopie

LOI SUR LA NATIONALITE ETHIOPIENNE

Nationalité des enfants nés de sujets éthiopiens en Ethiopie ou a l'etranger

Titre 1

Tout individu né d'un éthiopien ou d'une éthiopienne, en Ethiopie ou à l'étranger, est sujet éthiopien.

Nationalité en cas de mariage entre ethiopiens et non-ethiopiens

Titre 2

Le mariage régulier d'un sujet éthiopien avec une femme étrangère confère à celle-ci la nationalité éthopienne.

Titre 3

Est considéré en ce cas, comme mariage régulier

a) Le mariage d'un sujet éthiopien, contracté en Ethiopie, avec une femme étrangère, selon la forme religieuse éthiopienne, ou selon la forme du marige civil éthiopien créant entre les époux la communauté des biens.

b) Le mariage d'un sujet ethiopien contracté à l'étrangèr, avec une femme étrangère, selon la loi et les formes du lieu de la célébration du mariage

Titre 4.

Le mariage régulier d'une femme sujette éthiopienne, avec un étranger fait perdre à celle-ci sa nationalité ethiopienne, si son mariage avec l'étranger lui confère la nationalité de son mari; au cas contraire, elle conserve sa nationalité éthiopienne. Dans le cas ou la femme perdant sa nationalité èthiopienne serait propriétaire de biens immobiliers, le régime de ses propriétés sera règlé conformément à la loi instituée à cet effet par le Gouvernement Impérial Ethiopien.

Titre 5

Est considéré comme marige régulier:

a) Le mariage contracté en Ethiopie, par la femme éthiopienne avec une étranger, devant les autorités consulaire du mari.

b) Le mariage de la femme éthiopienne, contracté à l'étranger, avec un étranger, selon la loi nationale du mari et selon les formes légales du lieu de célébration du mariage.

Nationalité des enfants issus d'une union entre éthiopien et non-éthiopien

Titre 6

Tout enfant né d'une union mixte régulière, comme il est dit aux articles précédents, suivra la nationalité de son père.

L'enfant né d'un père éthiopien et d'une mère étrangère unis par les liens d'un mariage régulier, devra cependant justifier auprès des autorités éthiopiennes, sur demande de leur part, de sa non appartenance à la nationalité d'origine de sa mère

Titre 7

L'enfant né du mariage régulier de sa mère sujette ethiopienne avec un etranger, pourra en tout temps revendiquer le bénéfice de la nationalité ethiopienne, à condition d'être domicilié en Ethiopie et de justifier qu'il est dégagé complètement de la nationalité paternelle.

Nationalité des enfants Légitimés par un mariage régulier entre Ethiopien et non-Ethiopien

Titre 8

Si le mariage régulier, selon la loi nationale du père étranger, est postérieur à la naissance de l'enfant issu de ses relations avec une femme sujette ethiopienne, l'enfant reconnu par mariage subséquent ne suivra la nationalité de son père étranger, que dans le cas oú la loi nationale de ce dernier, lui confère la nationalité étrangère avec tous les droits qui y sont attachés. Au cas contraire, l'enfant conservera sa nationalité éthiopienne.

Nationalité des enfants reconnus sans mariage subsequent du père etrangèr avec la mere sujette éthiopienne

Titre 9

La reconnaissance, sans mariage régulier subséquent du père étranger avec la mère éthiopienne, de l'enfant issu de leurs relations hors mariage régulier, ne pourra priver l'enfant de sa nationalité éthiopienne que dans le cas oú la reconnaissance, faite selon les formes de la loi du père étranger, conférerait à l'enfant ainsi reconnu la nationalité de son père avec tous les droits qui y sont attachés.

Nationalité de l'enfant éthiopien adopté, par un étranger.

Titre 10

L'adoption, par un homme ou une femme de nationalité étrangère, d'un enfant éthiopien, adoption faite selon les formes de la loi personnelle de l'adoptant, n'entrainera pour l'adopté aucun changement de sa nationalité éthiopienne originaire.

Perte de la nationalité éthiopienné:

Titre 11

Perd la nationalité éthiopienne ;

a) Le sujet ethiopien qui acquiert une autre nationalité

b) La femme éthiopienne par l'effet de son mariagé avec un étranger. (art 4)

Naturalisation.

Titre 12

Tout étranger remplissant le conditions suivantes:

a) Majeur selon les dispositions de la loi nationale,

b) Domicilié en Ethiopie depuis cinq ans au moins,

c) Capable de gagner sa vie, de subvenir à ses besoins et à ceux de sa famille,

d) Connaissant parfaitement, parlant et écrivant couramment la langue amharique ;

e) Justifiant de l'absence de toute condamnation pènale antèrieure pour crime ou dèlit de droit commun

pourra obtenir la nationalité éthiopienne.

Titre 13

La demande de naturalisation sera adressée par l'inéressè au Ministére des Affaires Etrangéres.

A cette demande devront ètre jointes les piéces d'identitè de l'étranger ainsi qu'un exrait de son casier judiciaire.

Titre 14

Uue Commission spéciale du Gouvernement comprenant le Ministre de l'Intérieur, le Ministre des Affaires Etrangères, et un autre grand Dignitaire de l'Empire examinera la demande, fera procéder aux enquêtes nécessaires et aprés avoir entendu directemnt l'impétrant. accordera ou refusera la naturalisation.

Titre. 15

La naturalisation sera conférée par dècret et le nouveau sujet éthiopien prêtera serment de fidélitè à l'Empire devant la Commission.

Titre. 16

La naturalisation ainsi confèrée n'ètendra ses effets à la femme lègitime du naturalisè que dans le cas où celle-ci en demanderait personnellement le bènèfice

Reintégration dans la nationalité éthiopienne.

Titre. 17

Pourront toujours obtenir le bènéfice de la nationalitè èthiopienne les sujets èthiopiens d'origine, qui ,ayant acquis ùne nationalitè ètrangère reviéndront se fixer dans le pays et demanderont au Gouvernement Impérial leur rèintégration

Titre 18

La femme èthiopienne qui par son mariage avec un ètranger aura perdu sa nationalitè èthiopienne, pourra la recouvrer ensuite de la dissolution dé ce mariage, par le fait d'un divorce, d'un sèparation de corps ou par le fait de la mort de son mari, si elle revient prendre domicile en Ethiopie et demande au Gouvernement Ethipoien sa rèintégraion dans sa nationalitè èthiopienne originaire.

La présente loi abroge toutes les lois pècédemment promulguées sur la matiére.

Fait a Addis Abeba le 15 Hamlié 1922 an de grâce (22 juillet 1930)

አ ዋ ጅ ።

መኳንንትም የሽአለቃም በየሰጠንህ ግዛት ለነፍስ ደኅንነት ለሰላም ኑሮ ዕረፍት የሚለመንበት ቤተ ክርስቲያን ሳይሠራ መኖርያ ቤትህን በማደራጀት ባለአገሩም ተጐዳን ብሎ ይጮሃል እንጂ ቤተ ክርስቲያን በመፍረሱ የተሠራውም ከተበላሸ በኋላ ባለመታደሱ ተቈርቋሪ ስላላገኘ ለነፍስም ጕዳት ለሥጋም መቅሠፍት የሚአመጣ ሁኖአልና በየአውራጃህ የተተከሉትን አብያተ ክርስቲያን የፈረሱትን አሠራ ፤ ያረጁትን አሳድስ ። የክርስቲያን ምልክቱ የሃይማኖት መሠረቱ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው ። ነገር ግን በዚህ ምክንያት አለወገን ጭ ግዛህ ድሀ አትበድልብኝ። አጥቢያውም በገንዘቡና በጕልበቱ

ረድቶ ካወጣና ከአሠራ በኋላ ከጉልበቱና ከገንዘቡ የሚተርፈውን ሥራ እኔ እረዳለሁና ችግርህን በደጃዝማች ደስታ ዳምጠው በኩል አስታውቀኝ፡ከዚህ አዋጅ ወዲህ ግን እስከ አንድ ዓመት ድረስ ቤተ ክርስቲያኑ ሳይሠራ ቀርቶ መፍረሱን አለመታደሱንም የሰማን እንደሆነ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የሚፈጀው ታስቦ በወጠፌታ መቀጮ ይከፍላል ። ይህም ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራና ጉዳይ ይገባል ።

ስለ መንግሥትና ስለ ሕዝብ ጥቅም ።

በከተማ ውሥጥ ያሉ ወዳጆቻችን በከተማ ሲመላለሱ የሚያገኙትን የሥራ ጕድለትና ያዩትንና የሰሙትንም የድኃ በደል የምክር እርዳታ አድርገው ቢያስታውቁን እጅግ ደስ ይለናል ። ይኸንንም ማለታችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ትእዛዝ የከተማውን ሥራ ኃላፊነት የተቀበልነው እንደተቻለን ያህል የከተማውን ሕዝብ በጥንቃቄ ለመጠበቅና ለከተማ ሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆነውን ሥራችንንም በሚገባ ለመሥራት ስለ ሆነ ራሳችን አስበን በቅንነት በምንደክምበት ላይ ያልታሰበና የተዘነጋ ነገር ያገኘን እንደሆነ በከተማ ውሥጥ የሚኖሩ ወዳጆቻችን ጥቅም ያለው የሆነ ምክራቸውን ሲያከፍሉን ለሕዝብ ጥቅምና ለሕዝብ ጉዳት የሚሆነውን ጉዳይ ስንሰማ እጥርተን እየመረመርን የሚቻለውን ተግተን ለመፈጸም እንድንጥርበት ለጊዜው የማይቻለውን ግን ጊዜው እደረሰ ድረስ ለወደፊት እንድናስብበት ነውና ስለዚህ የታየውንና የሰማውን ነገር ለሚያከፍለን ሰው ከእሑድ ቀንና ከትልቅ በዓል ቀን በቀር ከእኩል ቀን በኋላ ከ፱ሰዓት እንሥቶ እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ እማዘጋጃ ቤት ቢመጣ ወይም የሰማውንና ያየውን የተረዳውንና የመሰለውንም ነገር በጽሕፈት ቢያስታውቅ ዋና ዋና ጉዳይ ለሆነው የማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር በማዘጋጃ ቤት ይገኛል ። ቀላል ጉዳይ ለሆነው ነገር ግን ከዚያ ለማይለዩ ለዋና ጉዳይ ጸሐፊዎች የቃሉን በቃል ሊናገር የወረቀቱንም በወረቀት አድርጎ ሊያስረክብ ይችላል። የነዚህም ጸሐፊዎች የጽሕፈት ቤታቸው በማዘጋጃ ቤት እመግመኛው ፎቅ ላይ ነውና የሚገኘው ምልክቱ እበሩ ላይ ፤ (ክፉን አሳብ መጣል ደግን ነገር ማስተዋል ፤) የሚል ጽሕፈት ተጽፎበታል ። የሰውንም ምክርና እርዳታ የግልጹን በግልጽ፤ የሥውሩንም በሥውር፤ ለመቀበልና ምሥጢር ለመቻል ጸሐፊዎቻችን በአምንት ያሉ ናቸው ።

ሐምሌ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት ።

የአዲስ አበባ ከንቲባ።

ስለ ሀገር ፍቅር ።

ስለ ንጉሠ ነገሥት ክብር ትንሽ በረከት ።

መወድስ ።

እልበ ወሰን ለስፍሐ መንግሥቱ፡ ለቀዳማዊ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ አኩኑ ።
ኵሉ እኍዝ ውስተ የማኑ።
ወላሕም ወንጌላዊ ዘበበጊዜሁ ይትኄየል በቀርኑ።
እለ ወትረ ያማስኑ ።
ምልእተ ተድላ ወክብር ኢትዮጵያ ዓፀደ ወይኑ ።
ይቤሎሙ ሂ በጉባኤ ለዘእምርኁቅ ትንትኑ ።
ሐዋርያተ ጣፍዕ ሰብአ ጐንደር በእሳት ዘተፈትኑ ።
ኢየጎድግክሙ እንከ አጓለ ማውታ ትኩኑ ።
ሕይወተ ዓለም ሰላምየ በልሳኑ እሳት እስመ እፌኑ ።

መምሬ ይገዙ ዘደብረ ዝቋላ እንተ ይእቲ ።

ደብረ ከዋክብት ።

ሹም ሽር

ደጃዝማች አደፍርሰው ኖኖን እነሞርን እነቆርን ግዛት ጨምረው የዘበኛ አለቅነት ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደ ሩፌ የባሶን ግዛት ጨምረው የፖስታና የስልክ ሚኒስቴርነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ በግርማዊት መንን ቤት አዛዠነትና የቡልጋን የሙሎን የየከን የአዳ በርጋን ምስለኔዎች በላይነት ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ጣሰው ሊበንና ከረዩን ደግሞ በውሥጡ ብዙ አገሮችና ምስለኔነት አሉ፡ ይህን ጨምረው የእልፍኝ አስከልካይነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ወልደ ዮሐንስ ጥይት ቤትን በሙሉ በላይኛው ግቢም በታችኛው ግቢም በኮረግሽም ባለው በመድፉ በማናቸውም የጦር መሣሪያ ሁሉ በቡልጋ ውሥጥ መስኖን ግዛት ጨምረው ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ለቃ ይበሉ ጥቍር ምድርን ግዛት ጨምረው የዘበኛ ዲሬክተርነት ተሾሙ።

ቀኛዝማች ፀጋዬ በጦር ሚኒስቴሩ በፊታውራሪ ሙሉ ጌታ ውሥጥ በቀለብና በደመወዝ ዋና ኃላፊ ሹም ሁነው ተሾሙ ።

በላምባራስ ተክለ ማርቆስ ግራዝማች ተብለው የጽሕፈት ዲሬክተርነት ተሾሙ ።

ቀኛዝማች አበበ አስፋው ፊታውራሪ ተብለው ጭፍራም ተጨምሮላቸው ቀድሞ በያዙት ማደሪያቸው ላይ ምድረ ከብድን ተሾሙ ።

ግራዝማች ኃይሌ እንደብልሃቱ የሰደፍ ጃግሬነት ተሾሙ ።

ግራዝማች ግርማ ማሞ በሲዳሞ ውሥጥ የፊታውራሪ ወልደ ጊዮርጊስ የነበረውን አገር ተሾሙ ።

ቀኛዝማች ደስታ የሐረርን ባምጃቤትነት ተሾሙ ።

አቶ አሽኔ የብር ቤቱን ዲሬክተርነት ተሾሙ ።

ልጅ መንገሻ ባልቻ ባላምባራስ ተብለው የጥይት ቤትን ዲሬክተርነት ተሾሙ ።

በሻ ወልደ ዮሐንስ የገንት የአዛዥ ምክትልነት ተሾሙ ።

ሹመት ያዳብር

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

የመወለድ በዓል ።

በሐምሌ ፲፮ ቀን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተወለዱበት ቀን ስለ ሆነ በዓሉ ለማክበር በማለዳ ፳፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ወዲያውም በታላቁ ቤተመንግሥት ውሥጥ ዙፋን ቤቶች አሳምረው አንጥፈው አዘጋጅተው ሲጠባበቁ ከ፩ሰዓት ጀምረው ጥሩ ጥሩ የበዓል ልብሳቸውን እየለበሱ ኒሻናቸውን እያደረጉ የኢትዮጵያ መኳንንት ወደታላቁ ግቢ ደገቡ ጀመር ወታደሩና ዘበኛውም በግቢው ዙሯ ተሰልፎ ሲአዩት እጅግ ያምር ነበር ። ይልቁንም ሰልፍ የተማሩ ወታደሮች ባሥርዓት ተሰልፈው ሰላምታ ሲሰጡ እጅግ ያምሩ ነበር ። ፪ሰዓት ያህል ሲሆን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በታላቁ ዙፋን ተቀመጡና መኳንንቱ ገብተው እጅ እየነሡ በየማዓርጋቸው ተቀመጡ፡ መኳንንቱና ሚኒስቴሮችም ጥሩ ጥሩ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው በተራ በወምበር በወምበር ተቀምጠው ላያቸው እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር። ፬ሰዓት ሲሆን ጳጳሳቱና የውጭ አገር ሚኒስቴሮች ቈንስሎች ያማረ ያማረ የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ገብተው እንኳን ወደ ሀብታሚቱና ዕድለኛይቱ ቀን አደረስዎ ። ደግሞ ብዙ ዓመት ለመድረስ ያብቃዎ እያሉ እየተሰናበቱ ወጡ። ቀጥሎ‐ ውም በከተማ የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች በንግድም በሌላም ሥራ ኑዋሪዎች እንዲሁ እያሉ እየተሰናበቱ ወጡ ። እንዲሁ እስከ ፮ሰዓት ድረስ በታላቁ ዙፋን ተቀምጠው እንግዶችን ሁሉ ሲቀበሉ ዋሉና ወደ ኪዳነምሕረት ቤተክርስቲያን ገቡና ቅዳሴ ተደረገ ። ከቅዳሴም በኋላ ወደ ግብር ገቡ ።

ይህች ዕድለኛይቱ ቀን እንዲሁ በደስታ ተፈጸመች ። ይህች የተወለዱበት ቀን የኢትዮጵያ ዕድል ናትና ዕድሜዎን አብዝቶ ብዙ ዓመታት እንድናከብራት ያድርግልን እያልን ልዑል እግዚአብሔርን እንለምናለን ።

ማስታወቂያ ።

በሐምሌ ፲፪ቀን የተደረገውን የጊዮርጊስ ትምህርት ቤት በዓል እጅግ ያማረ ነበር ። ነገር ግን ስፍራ ስለ ጠበበን እየከ‐ ፍልን እናዳናገባውም ነገሩ በስፍራ በስፍራው ካልገባ ለአን‐ ባቢው ደስ አያሰኝምና በሚመጣው ጋዜጣ ባንድ ላይ ለማድረግ አቈይተነዋል ። ወሬውን የሰማችሁ ሰዎች ለማንበብ ሳትቸኵሉ ባሁኑ ብርሃንና ሰላም አለመታተሙን አይታችሁ የቀረ እንዳ‐ ይመስላችሁ ለሚመጣው ጊዜ ያቈየንበትን ምክንያት ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እናስታውቃለን ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ‐ በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያከማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገ‐ ራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሀ ጸባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መ
የርሻ ትምህርት	፪ ብር ከ፳ መ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡኣትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
መዳጇ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቁጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳላም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፳ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፳ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፳ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፳ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፳ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፳ መሐ
የቀን መቁጠሪ (ካሌንደር)	፳ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቍጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኔክላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

COGNAC S.A.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፩
6me ANNÉE № 31

ሐሙስ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 51 JUILLET 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣቱ ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ስለ ቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት በዓል ።

በሐምሌ ፲፪ቀን የቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ስለ ክረምቱ ዕረፍት ለማድረግ የሚዘጋበት ቀን ነበርና ይህኑ በዓል ለማየት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብፁዓን ጳጳሳትና ብዙ መኳንንትም ተጠርተው ነበር። የተቀጠረው በ፰ ሰዓት ነበርና በዚያው ሰዓት ጃንሆይና ጳጳሳቱ መኳንንቱም ወደ ትምህርት ቤቱ በደረሱ ጊዜ ልብ የሚነካ ሙዚቃ እየተነፋ ደጃፉ አጊጠ ሕፃናቱ ለምለም ሰሌን ይዘው ሆሣዕና በአርያም እያሉ ተቀበሏቸው ። ከዚህም በኋላ ወደ ተሰናዳው አዳራሽ ገብተው በየቦታቸው በተቀመጡ ጊዜ የተመረጡ ድምፃቸው ያማረ ተማሪዎች የሚከተለውን መዝሙር ዘመሩ ።

መ ዝ ሙ ር ።

ልጆች ሆይ ደስ ይበለን ።
ሞግዚታችን መጡልን ።
ብርሃናችን መሪያችን ሰላማችን ።

፩ኛ መዝሙር ።

አንደኛ ።

ይኑሩልን ንጉሣችን ።
ሁነውልናል ብርሃናችን ።
በጣም እናቅርብ ምሥጋናችን ።
ዕድሜዎን ያርዝምልን ።
ለዘለዓለም ያኑርልን ።
የሰሎሞንን ጥበብ ይስጥልን አምላካችን።

ሁለተኛ ።

ልጆች ሆይ ደስ ይበለን ።
በጣሙንም ደስ ይበለን ።
አደገኝም የዛሬ ቀን ።
እናጨብጭብ እጥብቀን ።
እንዝለልም ደስ ብሎን ።
እንድንቀበል ጸጋ ቡራኬውን ።

ሦስተኛ ።

ልጆች ይወዳል እንደ ኢየሱስ ።
ሰበሰበን በአንድነት ።
ሊመራንም ወደ ሕይወት ።
ደስታ ነህ ለልባችን ።
ፍጹም ብርሃን ለዕውቀታችን ።
ከንተ ወዲያ አሳዳጊያችን ።
ተከተተ ምኞታችን ።

አራተኛ ።

ልጆች ሆይ ደስ ይበለን ።
ደስታችንንም እንግለጥ ።
በንጉሣችን ፊት ቁመን ።
ከጨለማ አወጡን ።
ለብርሃን አደረሱን ።
ምንም አይከፉን ኃይለ ሥላሴ ሳለልን ።

አምስተኛ ።

ሳንለያይ ልጆች ሁሉ ።
ምስጋና እናቀርብ ለሁሉ ።
ለአሳቢያችንም ለሣህሌ ፀዳሉ ።
በጃንሆይ ትጋት የረዳን ።
ጥዋትም ማታ ኀበኘን ።
እሱን የመሰለ አባት አይገኝም ይኑርልን ።

፱ ተኛ መዝሙር ።

አንደኛ ።

ልጆች እናዚም ለጌታችን ።
በመሆን ስምም በድምፃችን ።
ጋሻ ነውና ለሚጠጉት ።
ይሆናል ፋና ለሚያፈቅሩት ።

ሁለተኛ ።

ምስጋናህን ስማ የደሆችህን ።
አንተን አግኝተው የሚያዜሙትን ።
እየን ተመልከተን እና ያንተ ነን ።
ላንተ ለጃንሆይ በጅጉ ጤና ይስጥልን ።

ሦስተኛ ።

ዛሬ ፬ ኛ ቃችን ተፈጸመልን ።
በመኻከላችን በመገኘትህ ።
እኛ ተማሪዎችህ የምናሰማህ ።
ዕድሜ አለንና በኃይለ ሥላሴ።

አራተኛ ።

ኃይለ ሥላሴ አንተ ከመጣህ ።
ክብር ንጓሥና ላንተ ይግባህ ።
ገጋር ነህና ላገራችን ።
መርጦሃልና ኃይለ ሥላሴን ።

አምስተኛ ።

ላንተ ይገባል ጥሩ ምስጋና ።
ጠላት ይፈራል አንተን ያይና ።
ይክበር ይመስገን አምላካችን ።
በደጓና ዘመን አንተን የሰጠን ።

ቀጥለው የፈረንሳዊ መዝሙር ዘመሩ ።

ቀጥለው የተመረጡ አኒጋገራቸው ያማረ ተማሪዎች ጠያቂና መላሽ ሁነው ፫ቱን አዕማደ ምሥጢር (የሃይማኖት ምሥጢር ዋና መሠረቶች) ተናገሩ ።

ቀጥለው ወይዘሮ ፈቃዴ ጳውሎስ ያስተማርዋቸው ሴቶች ልጆች እንደዚሁ ጠያቂና መላሽ ሁነው አዕማደ ምስጢር ሲናገሩ እጅግ አማሩ። ከወንጌሉም እንዳንዱ ገጽ የሚሆን በቃላቸው አጥንተው ባተራ ባተራ ሲአነቡ ሰውን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙ ።

ቀጥለው ዜማ የሚማሩ ልጆች የሚከተለውን ዝማሬ ዘመሩ።

፩ ጽዋዕ ። ወይቤልዎ ደቂቀ ዘብዴዎስ እንብርኒ በየማንከ ወይቤሎሙ ኢየሱስ ጽዋዕየሰ ትሰትዩ ዘአነ እሰቲ ትሰትዩ ጽዋዕየሰ ትሰትዩ ወንቢረ በየማንየ ወበፀጋምየ ኢትክሉ ጽዋዕየሰ ትሰትዩ ጽዋዓ መድኃኒት ጽዋዐ ፍሥሓ ፤ ወሐሤት ጽዋዕየሰ ትስትዩ ጽዋዕየሰ ትሰትዩ ።

፪ ጽዋዕ ። ሶበሰ አእመረ ሰይጣን በመስቀሉ ለወልድ ከመ ይሰደድ እምኢያምክሮሙ ለአይሁድ፥ ዕፀ መስቀል ከመ ይትክሉ፥ ናዝሬዌ ከመ ይስቅሉ ማኅየዌ ከመ ይቅትሉ፥ በዘመከረ ተኀፍረ፥ ወበዘአትክለ ተሰደ ወእምዝ ሐለየ ክመ ይሠውር ፀሐየ ኅበ ዕሙቀ ለደፊነ መስቀል አክረየ፥ መስቀል ብርሃን ከመ ይሠውርዎ አበየ፡ ዝንቱ መስቀል ኀብስተ ሕይወት አፍረየ አውኃዘ ለነ ደመ ወማየ ጽውዓ መድኃኒት ጽሩየ ዘኢይነጽፍ ቀላየ ከመ ጌራ ወርቅ ጽሩይ ሥርግው በበሕርይ መስቀል ነቢሮ ላዕለ ርእስየ ያስተርኢ ጊዜ ትወጽእ ነፍስየ ።

ዝማሬ ዘእግዝእትነ ማርያም ።

፫ አንቲ ይእቲ ማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ እምነ ሥርወ ለአዳም አንተ ሠረፀት ነለ ነፍሳ ቀደስከ ወሥጋሃ አንጻሕከ እንተ በላዕሌሃ አኅደርከ ወልደከ ወበደመ ወልደ ዚአሃ ቀደስከሙ ለቅዱሳኒከ ሥጋከ ወደመከ ዘወሀብከሙ ለአርዳኢከ ከመ ይብልዑ ወይጽገቡ እምኔሁ በውእቱ ሥጋ ቅዱስ ወበውእቱ ደም ክቡር ተሳተፍነ ምስለ ወልድከ ወከነ አሐደ ሥጋ ።

ቀጥለው እስመ ለዓለም መርተው ወረቡን ሲዘምሩ እጅጓ ደስ አሰኙ ።

እስመ ለዓለም።

ፀሐይ ሠረቀ ቀርን ጸርሐ ዓዋዲ በጽሐ ትጉሃን ይረውጹ መንበር ረትዐ ለኵንኖ እለ ፃመው ይትፌሥሑ ወእለ ተሃከዩ ይደነግፁ እለ በየማኑ ይትፌሥሑ ሶበ ይሬእዩ ገጸ እለ ሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ ።

ወረብ ።

እግዚእ አእምሮ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ወዜናዌ ጥበብ ዘከሠተ ለነ ዘከነ ሥውረ ዘከነ ሥውረ ።

ቀጥለውም የሠለጠኑ ልጆች ስለ መንፈሳውያን ጋብቻ ትያትር ሲአደርጉ እጅግ አማሩ። የማማሩንም ነገር በጽሕፈት ለመግለጽ እጅግ ያስቸግራል።

ቀጥለው የትምህርትና የጥበብ ዋና ድረክቴር አቶ ማህሉ ፀዳሉ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበ ።

ጃንሆይ ብፁዓን ጳጳሳት ክቡራን ጌቶች ።
ክቡራን ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ።

በዚች ዕለት የቅዱስ ጊዮርጊስን ተማሪቤት ለመጐብኘት ስለመጣችሁልን በታላቅ ደስታ ምስጋናችነን እናቀርባለን ።

ቫርማዊ ሆይ ለቸርነቱ ወሰን የሌለው አምላክ ሁለጊዜ ተአምራቱን ከሰው ልጅ አያርቅምና ለኢትዮጵያ አስተዳዳሪ ሊሆኑ ከተመረጡበት ቀን ጀምረው እንዲቱ ሰዓት እንኳን በከንቱ ሳታልፍብዎ ሕዝብዎን በትጋትና በትዕግሥት እየጠበቁ በመልካም መንገድ ለማስኬድ የደከሙትን የዓለም ታሪክ ይመሰክርለዎታል ። አሁንም ለጊዜው በትዕግሥት የደከሙት ሁሉ መልካም ፍሬ እያፈራ ለኢትዮጵያ ሕፃናት ሕይወት ሲሆናቸው እነሆ በብዙ መንገድ እናያለን። ገሮች የተባረኩ ናቸው ምድርን ይወርሳሉና እንዳለ ጌታ። እነሆ በትዕግሥትዎ የኢትዮጵያን ዙፋን ለመውረስ አበቃዎ ። የኢትዮጵያ ዕድል ዘወትር ሲያብብ ሲያፈራ እንደኖረ ዛሬም በዚህ ባሁኑ ሰዓት መልካም እረኛ ትጉህ እረኛ ቫርማዎን የሰጣት አምላክ የተ-

ባረከና የተቀደሰ ይሁን፡፡መንግሥቱም ለዘለዓለም ይኑር የድካምዎን ዋጋ ከፍሎዎታልና ።

ጃንሆይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት ከተከፈተ ፲ወር ሁኖታል በዚህ በ፲፩ ወር ውስጥ የተሰበሰቡት ሕፃናት ፫፻፹ ያህላሉ።ከነዚሁ ፵የሚያህሉት ተማሪዎች በትምህርት ከፍ ስላሉ መርጠን ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት አዛርናቸው፡ አሁን ፫፻፵ የሚያህሉ ልጆች በዚህ ተማሪ ቤት ተግተው ይማራሉ። የትጋታቸውም ነገር እጅግ ያስደንቃል ከነዚሁም አርባ የሚያህሉት ሴቶች ልጆች ናቸው ዘመዶቻቸው በተወሰነው ሰዓት ልጆቻቸውን እየያዙ ወደ ተማሪቤት ሲመጡ ያያቸው ሰው ሁሉ ይገረማል ። ቦታችን ከመጥበቡ በቀር ሌላ ችግር የለብንም ከቦታ መጥበብ የተነሣ የመለስናቸው ልጆች ከ፻ አይንሱም። የተማሪቤቱ ዲሬክተር አቶ መኰንን የተማሪቤቱን ግቢ አጽድቶ አስተማሪዎቹን በፍቅር እየመከረ ሕፃናቱን እንደ ሞግዚት ተጠንቅቆ እየጠበቀ ሥራውን ተግቶ ስለሠራ የሥራውን አካሄድ አያዩት የልጆቹ ዘመዶች ሁሉ በፍጹም እምነት ልጆቻቸውን እያመጡ ያስረክቡታል ። በውጭ አገር ሳይሄድ አዲስ አበባ አድጎ አዳግማዊ ምኒልክ ተማሪቤት ተምሮ አሁን ይህነን ያህል ሕፃናት በተሰበሰበበት ቦታ ለአንድ ተማሪቤት መሪ ለመሆን በመቻሉ በግርማዎ ፊት ላመሰግነው አደፍራለሁ ። የትምህርቱን አካሄድ የሥራውን መከናወን የሕፃናቱን መሽቀዳደም የመምህራኑን ትጋት በዘወትሩ ቀን ብዙ ሰው እየመጣ እየጐበኘ ይደነቃል። የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት ወደፊት ለሚከፈቱት ተማሪቤቶች ሁሉ መልካም ምሳሌ መዝገብ እንዲሆን ጥርጥር የለበትም ።

ግርማዊ ሆይ ይህ አሁን በኋላ የመሠረቱት የትምህትና የጥበብ ሚኒስቴር ለኢትዮጵያ ነፍሷ ነው።ነፍስ ከሌለ በድን መበል አይቀርምና አንድ ቤት ለማቆም ፫ነገር ያስፈልጋታል የቀረው ትርፍ ጌጥ ነው ። መጀመሪ ግምቡ ሁለተኛ ማሬው ፫ተኛ ክዳኑ ነው ።

የተከበራችሁ ጌቶቼ ሆይ እስቲ ተመለከቱት ግምቡ ከል ቆመ ከምን ላይ ይዋቀራል ፡ ካልተዋቀረስ ክዳኑ ከምን ላይ ይወድቃል።ካልተከደነስ ግምቡ እንዴት ይፀናል እንግዴህ አንዳቸው ተለይተው ቤት ለመበል አይችሉም ። እንደዚህ ሁሉ ለአንድ አገር ፫ ነገር ያስፈልጋልታ።መጀመሪ ሀብት፡ ፪ ተኛ ጉልበት ፫ተኛ ዕውቀት ናቸው ከነዚህም አንደኛው ከጐደለ መንግሥት ለመባል አያስደፍርም ። ክቡራን ጌቶቼ ሆይ እስኪ ይህነንም አስቡት ሀብት ከሌለ ጉልበት ከምን ይመጣል ካልሠሩትስ ሀብት ከምን ይወጣል ። ሥራስ ለመሥራት ካልተማሩና የሥራውን አቅድ ካላወቁት ሥራው እንዴት ይዘጋጃል።እንግዴህ ትምርት የሥራን ፍቅር ትወልዳለች ሥራም ሀብትን ታፈልቃለች ሀብትም ጉልበትን እያጐላመሰች እያጋነነች አገሯን ታሰድጋለች ታሰፍራለች ። ሰው የሚከበር በመንግሥቱ እድገት ነው ይባላልና ። አስቀድሞ መንግሥቱ የሚያድግበትን መንገድ እንጥረግ እንደልድል ታዳጊ ያላት በግ ላቷን በውጭ ታሳድራለች እንዲሉ፡ እንዲሁ መንግሥቱ ያደገለት ሕዝብ ይመስላል ። ክቡራን ጌቶቼ ሆይ እስኪ ተመልከቱት አሁን እኔ ባለብዙ ሚልዮን ብሆንና መንግሥቴ ያልተዘጋጀ ያልፀና ቢሆን ክብረቴ ከምን ያድነኛል ። ምንስ ታዳጊ አለኝ ወይስ መንግሥቴ የተዘጋጀ የተከናወነ ሆኖ እኔ ብደኸይ ምን እጐዳለሁ

መንግሥቱ ካላደገ መከበር አይገኝም። መንግሥትንም የሚያሳድገው አንድነት ነው።ይበላው ካጣ ይበላበት ያጣ እንደሚሉት ነው ። እንግዴህ የኢትዮጵያ ሕፃናት የነገ ወራሾች ናቸውና ያሁኑን ዘመን ሥልጣኔ እንዲከተሉ ክቡራን መኳንንቶች በየወገናችሁ ለተማሪቤት እንድትጥሩ አተጋችሁኋለሁ ጥበብ ትኄይስ እምኵሉ መዛግብት እንዳለ ደራሲ፡ ዕውቀት ያገኜ ነፍስ ናት ከብዙም ከምዝምዝ ወርቅ ዋጋዋ ይበልጣል ተብሏል ። የማትከሰስ የማትወረስ ሀብት እሷ ናትና ።

እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ በማስተዋልም ሰማይን አፀና ብሎ መጽሐፍ ይነግረናል ። ሁሉ በጥበብ ይመሠረታል ሁሉ በጥበብ ይፈጸማል ። ጥበብ ፍቅርን አንድነትን ትዕግሥትን ትወልዳለች።ፍቅር በወገኑዋ ትታመናለች አንድነት ያገር ጋሻ ናት፡ትዕግሥት ዘውድ ናት ከደፋር ታጋሽ ይሻላል እንዳለ ደራሲ ። ጥበብ አይነተኛይቱ ነገር ናትና ጥበብን ግዛ በከብትህም ሁሉ ማስተዋልን አትርፍ ከፍ ከፍ አድርጋት፡እሷም ከፍ ከፍ ታደርግሃለች። ብታቀፋትም ታከብርሃለች ። ለራስህ የጸጋ ዘውድ ትሰጥሃለች በተዋበም አክሊል ትከልልሃለች ብሎ ሰሎሞን በምሳሌው ያስተምረናል።ክቡራን መኳንንቶች ሆይ ስለ ሰማሁት አይደለም በዓይኔ ስለ አየሁት በትንሹ ዕውቀቴ ልመክራችሁ እደፍራለሁ ። አንድ መኰንን ለተወላጆቹ አያሌ ገንዘብ ርስቱን ጉልቱን ሊያወርሳቸው ሲያከማች ቢኖር ለልጆቹ መርዝ ያቈያቸዋል እንጂ አይጠቅማቸውም በዘመናችን ብዙ የታላላቅ ልጆች እንደተጐዱ አይተናልና ። የገጋ ልጆች ባባታቸው ማዕርግ ለመተከት የማይችሉ ሲሆኑ ይህም ታላቅ ያገር ጉዳት ነው ።

አሁንም የከበራችሁ ጌቶቼን አለምናችኋለሁ ። ለልጆቻችሁ ለሕይወታቸው መሪ የሚሆናቸውን ዕውቀት እንድታስተምሯቸው አሳስባችኋለሁ ። ባሁኑ ሰዓት ኃይለ ሥላሴን መምህር የሰጠን አምላክ ይክበር ይመስገን ለዘለዓለምም ሕያው ይሁን።

ጃንሆይ ይህች ሰዓት የተባረከች ትሁን ።

የግርማዎን ምስጋና በጉባዔ ለመናገር ምክንያተ አግኝቻለሁና ለኢትዮጵያ ዙፋን ታጭተው ለመንግሥት አስተዳዳሪ ሲሆኑ ከሁሉ አስቀድመው የተፈሬ መኰንን ተማሬ ቤት መሠረቱ፡ ይህም ታላቅ ምሳሌ ነው። እነሆ ዛሬ በተፈሬ መኰንን ተማሬ ቤት የሕይወት ውሀ ይመነጭበታል ። ዝናውም በዓለም ሁሉ ተሰምቷል ። ልጅ ከመውለድ ስም መውለድ ይሻላል ። ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል እንዳለ ደራሲ። ከቀዳማዊ ዘመን ጀምሬ ፀንታ የኖረች አገራችን በመካከለኛው ዘመን በአረማውያን ተከባ ታፍና ብዙ ዘመን ታውካ የነበረችውን ታላቁ ንጉሥ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ተነስተው ደኑን መንጥረው ግራ ቀኙን ገላልጠው መንገዱን ጠርገው ደልድለው መንግሥታቸውን በሲምንቶ አጥብቀው ስለመሠረቱት ኢትዮጵያ እንደገና ተወለደች።ዳሩ ግን የሥራው ጊዜአልደረሰም ነበርና

ጌታችን ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ ገና በሚጕላ ቤቷ ሳለች ተለይተውን ወደ ማይመለሱበት አገር ሔዱ። ከዚያም ወዲህ ኢትዮጵያዋ ቂት ጊዜ ተደናግሯት ቈየች። ዳሩ ግን ዕድሏ ብርቱ ነውና በመካከሉ ሁሉን የሚችል ለቸርነቱ ወሰን የሌለው አምላክ ዘውዲቱን ተፈሪ ብሎ በቀኝ አቆማት።ሚዛኑም ረጋ ተተካከለ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ወዴት መሄዷ ይሆን እያሉ የተዘበበቱበት ሁሉ በጣም አፈሩ። እንዲሁም የዕድሏ ብርታት እጮኛዋ ተፈሪ ሁኖ እስከብሮ እስከዚሁ አቈያት ።

የግርማዎ ታሪክ በሰው ልብ ሁሉ የተጻፈ ነውና እኔ በዝርዝር መጻፍ አያስፈልገኝም ። አሁን ግን በኀይለ ሥላሴ የጋብቻው ጊዜ ደረሰ። ምኞታችንም ተፈጸመልን እንግዴህ ኢትዮጵያ እናታችን መልክም አሳዳሪ ትጉህ ጠባቂ ከገኘች ያለ ሥጋት ልጆቿዋን እየፈለፈለች ቀኍጥራቸውን ቃብዛ አብበ አፍርታ ፍሬዋን ለመቅመስ ያብቃን።የኢትዮጵያ ልጆች ደስ ይበላችሁ እልል በሉ በዘመናችሁ መልክም ጠባቂ አግኝታችኋልና ዕድሜ ለኀይለ ሥላሴ ።

ኀይለ ሥላሴን ሺህ ዓመት ያንግሥልን ዘሩም ይስፋ ይግነን ስሙም በዓለም ታሪክ ተጽፎ ለዘለዓለም ይኑር ፡ ኢትዮጵያ ትለምልም አሜን ።

የትምህርትና የጥበብ ዋና ዲሬክተር ማህሌ ፀዳሉ ።

ቀጥለው በትምህርት የበለጡ ተማሪዎች የመጻሕፍት ሽልማት ከተሸለሙ በኋላ ደግሞ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት እጅ የወርቅ ሜዳይ ተሸለሙ።የተሸለሙትም ብዙዎች ናቸው ።

ቀጥሎ የቻይ ግብዣ ተደረገ ፡ ቀጥሎ የሚከተለውን የአማርኛ መዝሙር ድምፃቸው ያማረ ልጆች ዘመሩ ።

ቀጥሎ በሙዚቃ እየተመሩ ትንንሾች ሕፃናት ጅምናስቲክ ሲአደርጉ እጅግ አማሩ ።

ቀጥለው አስተማሪዎች በጃንሆይ እጅ የወርቅ ሜዳይ ተሸለሙ ደግሞ ከዚህ የበለጠ ትምህርት ያስተማራችሁ እንደ ሆነ ከዚህ የበለጠ ሽልማት ትሸለማላችሁ ብለው ጃንሆይ ተስፋ ሰጧቸው።

የተማሪ ቤቱ ዲሬክተር አቶ መኰንን ክንፌ ከአስተማሪዎች ሳይለዩ ያስተምሩ ነበርና እንደ አስተማሪዎች የወርቅ ሜዳይ ከተሸለሙ በኋላ ጃንሆይ ጠርተው አለቃህ አቶ ማህሌ ፀዳሉ እጅግ ስለ አመሰገነህ እኔንም እጅግ ደስ ብሎኛልና ለዲሬክተርነትህ የሚገባህ ዋጋህ ነው ብለው ባንድ ወገን የጃንሆ ባንድ ወገን የአይሮፕላን ሥዕል ያለበት ትልቅ የወርቅ ሜዳይ ተቀበሉ ።

ቀጥለው ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ ከኢትዮጵያ ወደ እስ ክንድርያ ለማስተማር ፫ልጆች ላኩልኝ ብለው ለመንግሥት አስታውቀው ለመሔድ ከተመረጡት ተማሪዎች ፲፭ቱ ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ነበሩና ለማሰነባበት የትምህርት ዋና ዲረክተር አቶ ማህሌ ፀዳሉ ወደ ጃንሆይ አቅርበዋቸው ሲሰነባበቱ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ከልክሌ መዠሯ አነበበና እጅ እየነሡ ከጃንሆይ ተሰነባበቱ ።

ጃንሆይ

ወደ እስክንድርያ ለመሄድ የተመረጥን ተማሪዎችዎ በች ኰላና በጠበበች አእምሮዋችን የጻፍነውን ያልታረመ ቃላችንን ለመናገር እንዲፈቀድልን ከዙፋንዎ ሥር ወድቀን እንለምናለን።

ጃንሆይ

ከአልጋ ወራሽነትዎ ጀምረው በምሉ ሐሳብዎ ለኢትዮጵያ እንደሚጥሩና ልጆችዎንም በውቀት ለማጕልመስ ገንዘብዎን እንደ ጕርፍ እንደሚአፈሱ ማንም አይስተውም ግን ሕዝቡ የጃንሆይን መንገድና ደግ ሐሳብ የጥበብንም ጥቅሚንና ጣዕሚን ራስ ማስቻሏን ከልቡ መርምሮ በፍጹም ቢከተል ኢትዮጵያ ከሠለጠኑት ሀገሮች እንደአንዱ ሁና ነበር አሁንም ቢሆን ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ገንዘብዎን እንደሚአፈሱና ሌት ተቀን ለኢትዮጵያ እንደሚጥሩላት አይቶ ከአልጋ ወራሽነት ወደ ንጉሥነት ከንጉሥነት ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ካበቃዎ ኢትዮጵያን ከሠለጠኑት ሀገሮች እንደ አንዱ ሳያደርጓት ይቀራሉ ብሎ ማንም አይጠረጥርም።

ደግሞ የእስክንድርያ ወኖብያ ወኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስም የጃንሆይን አነሳስ አይተው የኢትዮጵያን ፍቅር በጃንሆይ ለመግለጽ በ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት መጥተው ለኢትዮጵያ የሚጥሩላትና የጃንሆይን ደግ ሐሳብ የሚከተሉት ጥቂቶች መሆናቸውን ስለተረዱት በማንም ጊዜ ያልተደረገ የፍቅርና የርዳታ ሥራ ፈልገው የኢትዮጵያን ልጆች እደተቻላቸው ለማስተማር ልጆች ይላኩልኝ ብለው ስለጠየቁዎ እኛም ይምጡልኝ ከተባሉት ከስድሳ ተማሪዎች አሥራ አምስቱ ከተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ስለተመረጥን ለደስታችን ወሰን የለውም።አሁንም የጃንሆይን ዕድሜ አርዝሞ የኢትዮጵያና የእስክንድርያን ፍቅር እንዲፀና እኛም ተምረን ሀገራችንን በፍጹም ልቡናችን እድናገለግል የብፁዕ አቡነ ዮሐንስን ዕድሜ ያርዝምልን ስንል እግዚአብሔርን እንለምናለን።

ከዚህ በኋላ ጃንሆይ ተነሡ ጳጳሳቱና መኳንንቱ እየተሰናበቱ ሔዱ ። የውጪ አገር ቋንቋና ቤተክርስቲያናችን ባለ መስማማታቸው እጅግ ስናዝን ዛሬ በሰላማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ጊዜ በመቀረባቸው እጅግ ደስ ብሎናል።

ተጥርተው ከመጡት መኳንንት ለተማሪዎቹ እርዳታ የሰጡት ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው።

ራስ ኀይሉ	፫፻ ብር
ራስ ሥዩም	፪፻ ብር

የቀሩትን መኳንንት እርዳታ የሰጡትን በሚመጣው እናስታውቃለን።

ደግሞ በሐምሌ ፲፫ ቀን ግርማዊት መንበዓሉን ለማክበር ወይዘዝሩን አስከትለው መጥተው ነበር። የበዓሉ አኳኋን እንደ ፊተኛው ቀን ከተደረገ በኋላ የትምህርትና የጥበብ ዲረክቴር አቶማህሌ ፀዳሉ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ግርማዊት ሆይ ።

የተከበራችሁ እመቤቶችና ወይዛዝሮች።

በዚች ዕለት የቅዱስ ጊዮርጊስን ተማሪ ቤት ልንጎበኙልን ስለ መጣችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናችንን እናቀርባለን።

ግርማዊት ሆይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪ ቤት ከተከፈተ ፲ወር ሁኖታል። በዚህ በ፲ወር ውሥጥ የተሰበሰቡት ሕፃናት ቍጥራቸው ፫፻፹ይሆናሉ ። ከነዚሁም ውሥጥ በትምህርት ከፍ ከፍ ያሉትን ፵ልጆች መርጠን ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት አዛውረናቸዋል። አሁን ፫፻፵የሚሆኑ ልጆች በዚሁ ተማሪ ቤት ተግተው ይማራሉ ። የትጋታቸው ነገር እጅግ ያስደንቃል ። ከነዚሁም አርባ የሚሆኑት ሴቶች ልጆች ናቸው ። ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በቸርነታቸው ያቆሙልን የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት እንደምታዩት ብዙ ሕፃናት አብበውበታል። እንዲሁ ደግሞ ፍሬያቸውን ለማየት እንዲያበቃን እንመኛለን።

ግርማዊት ሆይ አሁን እነዚህ ሕፃናት አበባ መስለው ይታያሉ። ነገር ግን ከኛ የሚወርሱ ወጣቶች ናቸውና እናታቸው ኢትዮጵያ ነገ ለችግሬ ይደርሱልኛል እያለች ተስፋ አድርጋ ትጠብቃቸዋለች ። ግርማዊት ሆይ እነዚህ ሕፃናት በውነት የተባረኩ ናቸው በዘመናቸው ትጉህ እረኛ ኃይለ ሥላሴን አግኝተዋልና ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ አስተዳዳሪ ሁነው መንግሥት ሲይዙ ከሁሉ አስቀድመው የተፈሪ መኰንን ተማሪቤት አቆሙ ።

ይህም መሆኑ ከእንግዲህ ወዲፊት ለኢትዮጵያ መድኃኒት ተማሪቤት መሆኑን ሊገልጹልን ፈቅደው ነው ። በአውሮፓም ከፍ ከፍ ያለ ዕውቀት እንዲማሩ ገንዘባቸውን እንደ አሸዋ እያፈሰሱ በየጊዜው የላኩዋቸው ሕፃናት ከ፱እያንሱም፡ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለኢትዮጵያ ዙፋን ከታጩ ጀምረው የጨለማን ሥልጣን በውቀት ብርሃን ሽረውልናል ። እነሆ የደከሙበት ሁሉ ፍሬ እያፈራ ለኢትዮጵያ ልጆች ሕይወት ሲሆናቸው በብዙ መንገድ እናያለን ። ኢትዮጵያ ዕድሏ ዘወትር ሲያብብ ይኖራልና ። እርሻዋ ተፈሪ ሁኖ እስካሁን አስከብሮ አቈያት። ከንግዲህም ወደፊት መልካም አሳዳሪ ኃይለ ሥላሴን ካገኘች ያለ ሥጋት ያለ መወላወል ፍሬዋን እያፈራች የሕይወት ምግብ ትመግበናለች እያልን ፍጹም ተስፋ እናድርግ ።

ግርማዊት ሆይ ልጅ አበባ ነው እንላለን እስኪ ማነው መልካሚቱን አበባ ከፊቱ የሚያርቃት እነሆ ግርማዊት እመቤታችን አበባ ልጅዋን እንኳን ለወለዳት ላወቃት የምታሳዝን እመቤት ጨክነው ወደ ሮፓ ሰደዷት ። ይህንንም ማድረግዎ ለኢትዮጵያ እመቤቶች ምሳሌ ለመሆን ነው ።

የከበራችሁ ወይዛዝሮች ሆይ ልጅ ለመውለድ አትቦዝኑ በምድር ላይ ከዚህ የሚሻል ሞገስ የለምና ዓለም ሲፈጠር መጀመሪ የተሰጠችን ሥልጣን ይህች ናትና ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሏት ብሎ የሰማያዊ አባታችን አዞናል ። መልካም ምድር ጥሩ እህል እንዲያበቅል እንዲሁም የኢትዮጵያ ወይዛዝሮች ልጆቻችሁን ብታበዙ አገራችሁን ታስከብራላችሁ ኢትዮጵያ ዘሯን ከእናንት ትፈልጋለችና እናንተ ግን የሚገባችሁን ባታደርጉ አገራችሁን መጥላታችሁ ነው። በእናንተም የሚገኙት ሕፃናት አድገው ሠልጥነው እንደስጦታቸው መጠን አገራቸውን ያገለግላሉ። እኩሉ ጋሻ ጦር አንሥተው አውሬ ይከላከላሉ ። እኩሉም ያገር አስተዳደር አውቀው የሕዝብ መሪ ይሆናሉ ። ሌሎቹም እንደዚሁ እንደስጦታቸው በክህነትም በርሻም በንግድም አገራቸውን ያገለግላሉ። ሁሉም ላገር ልማት ነውና አንዱም ከሌላው በፍቅር ካልተረዳዳ አንድነትም ካልተገኘ አገራችን አታድግምና የከበራችሁ ወይዛዝሮች ሆይ ከኢትዮጵያም በቀር ሌላ ታላላቅ ሰፊ አገር ብዙም የገነነ የሠለጠነ መንግሥት ሕዝቡም ከባሕር አሸዋ ይልቅ የበዛ አገር እንዳለ አስቡ ። ከእናንተም ውሥጥ ጥቂቶቹ እመቤቶች ሮፓን አይተው የተመለሱት ሳያስረዱዋችሁ አልቀሩም ። በዓለም ላይ ያለችው ኢትዮጵያ ብቻ አይደለችም ። ይልቁስ አገራችን ኢትዮጵያ ምንም ከቀዳማዊ ዘመን ጀምራ በሃማኖቷ ፀንታ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች መንግሥት ብትሆን ከሁሉ ዘመን ሥልጣኔ ብዙ የጐደላት ነገር አለና ይህንን በኃይለ ሥላሴ እንድታገኝ በፍጹም እምነት ለሥራ እንዘጋጅ ።

ግርማዊት ሆይ በቀድሞ ዘመን በፈረንጅ አገር እንዲህ ተደረገ በዘራቸውም በሀብታቸውም በውቀታቸውም የተከበሩ ታላላቅ እመቤቶች ከዕለታት አንድ ቀን ተድላ ደስታ በሚያደርጉበት ቦታ እንዲገናኙ ሲቃጠሩ ከሀብታቸውና ከውበታቸው የተነሣ በተቃጠሩበት ቀን የበለጠ የበለጠ ጌጣቸውን ከወርቅ ከፈርጥ ከአልማዝ ከሌላም ከልዩ ልዩ ደንጊያ የተሠራ የውበት ጌጣቸውን እየለበሱ እንዲመጡ ደምብ ያለው ቀጠሮ አደረጉ በቀጠሮውም ቀን እንዳዚያው እንደተወሰነው ሁሉም አምረው ደምቀው ጎብሩ በማይታወቅ ጌጥ ብርሃን መስለው ሲመጡ አንዲቱ ወይዘሮ ፪ ልጆቹዋን አስከትላ እሷ የዘወትር ልብሷን ለብሳ መጣች በዚያን ጊዜ እነዚያ ለመታየት የጒመጁ ወይዛዝሮች ውበታቸው ሁሉ እንደጢስ እንደ ጥላ ፈጥኖ የሚጠፋ መሆኑን ሳይገነዘቡት ቀርተው ይህች ትጉህ ወይዘሮ የበደለቻቸው መስሏቸው ስለምን ደምብ አፈረሰሽብን ብለው ምክንያቱን ቢጠይቋት የኔ ጌጥ የኔ ውበት የኔ አበባ እነዚህ ናቸው ይኸስ እናንተ ጌጥ የምትሉት ከንቱ ሸክም የነጋዴ ጓዝ ነው ብላ ልጆቹዋን አቅርባ አሳየቻቸው እነሱም አፍረው ተመለሱ ይባላል፡ ይህም ታሪክ ከ፩፻ ዘመን በፊት የተነገረ ነው ። ስለዚህ ልጅ ለመውለድ የሚጥር ሁሉ አገሩን ይወዳል ። ልጁንም ያስተማረ እራሱ ይከብራል ። የተከበራችሁ ወይዛዝሮች ሆይ እነሆ አዲሱ ልማድ የቀድሞውን የማይጠቅም ከንቱ ልማድ እሽራለሁ እያለ በሀገራችን ደንብ ተጋጥመው ይከራከራሉ አሮጌው ልማድ ላዲሱ ቦታ ለመልቀቅ በንፍና መስሎት ሲግደረደር ጊዜው ሊያልፍበት ሆነ ። እመቤቶቼ ሆይ እስኪ ይምሰላችሁ አንድ ሽማግሌ እንዴት አድርጎ ጉበዙን ሊቋቋመው ይችላል ። ፈጥኖስ አይሰብረውምን እንግዴህ አዲሱ ልማድ በውዱም በግዱም ታግሎ እንዲጥለን አስቡ። ሰው ሁሉ መከበሪው በወገኑ ነውና ልጆቻችሁን ወገኖቻችሁን ብታስተምሯቸው ስማችሁን በደግ ታስጠራላችሁ እስኪ እነዚህን ሕፃናት ተመልከቷቸው ከመስከረም ወዲህ ፊደል እየቈጠሩ ይህንን የመሰለ ሥልጣኔ በማትረፋቸው ያያቸው ሁሉ ይደነቃል ።

ግርማዊት ሆይ ይህም የቅዱስ ጊዮርጊስ ተማሪቤት ወደ ፊት ለሚከፈቱት ተማሪቤቶች ሁሉ ምሳሌና መዝገብ እንዲሆናቸው ጥርጥር የለበትም። በሁኑ ሰዓት ኃይለ ሥላሴን የመሰለ መምህር የሰጠን እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። ለዘለዓለምም ሕያው ሁኖ ይኑር። ኃይለ ሥላሴን ሺህ ዓመት ያንግሥልን ዘሩን ያስፋው ያለምልመው፤ ዛፉቱም የደመቀ የገነነ ይሁን ። ረጅም ዕድሜ ለንግሥታችን ይስጥዎ ፤ ክርስዎ የበቀለ ዘር ለኢትዮጵያ ጥላ ከለላ ይሁናት ። እመቤታችንን በቀኝ አቁሞ የኢትዮጵያ እናት ለመባል ያብቃዎ፤ ኢትዮጵያ ተፈሪ ሁና ትኑር ። የትምህርትና የጥበብዋና ዲሬክተር ማህሌ ፀዳሉ ።

ከዚህም በኋላ የሥራውን መክናወንና የልጆቹን መቀልጠፍ አይተው ደስ ብሏቸው እርዳታ የሰጡ ወይዛዝርና መኳንንት ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው ።

ግርማዊት መንን ።	፪ሺ ብር
ልዑል አስፋ ወሰን ኃ ሥ	፩ሺ ብር
ልጅ መኰንን ኃ ሥ	፫፻
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው	፫፻
ልዕልት ተናኘ ወርቅ	፫፻
ወይዘሮ የሻሽ ወርቅ	፪፻
ወይዘሮ ሮማን ወርቅ	፪፻
ወይዘሮ ዘርፈሽዋል	፻
ወይዘሮ አሰለፈች	፻
ወይዘሮ ትሰሜ አባ ደርጋ	፶
ወይዘሮ ደስታ የሊጋባ ባለቤት	፻
ወይዘሮ ጣይቱ የደጃ ይገዙ ባለቤት	፻
ወይዘሮ አዛለች የብላቴንጌታ ዘለቀ ባለቤት	፻
ወይዘሮ ዓፀደ ገነሜ	፷
ወይዘሮ ወለተ ኪዳን ማሞ	፳
ወይዘሮ አሰለፈች ኃይለ ሥ	፲፭

ደስ የሚያሰኝ በዓል ።

በሐምሌ ፲፯ቀን የአዛጋር ወርቅነህ ባለቤት ወይዘሮ ቀጸላወርቅ የግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የልደት በዓል ለማክበር በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የሻይ ግብዣ አሰናድተው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንና ግርማዊት መነንን ታላላቆችን መኳንንት በየ ማዕርጋቸው ወይዛዝርም ጠርተው ነበር ። ልክ በተቀጠረው ሰዓት ግርማዊት መነን መጡ።ተማሪዎች ደስ በሚያሰኝ ሙዚቃ ተቀብልዋቸው ቀጥለው ጃንሆይ መጡ። ተማሪዎችም እንዲሁ ባማረ ሙዚቃ ተቀበልዋቸው።የአዛጋር ወርቅነህ ልጅ ርብቃ ወርቅነህ በጥሩ የተሠራ አበባ ይዛ እንኳን ከዚህ ዓመት አደረስዎ ብላለጃንሆይ ባቀረበች ጊዜ የነበረውን ሰው ሁሉ እጅግ ደስ አሰኘች።አበባውም በኢትዮጵያ ባንዲራ ያጌጠ ነበር። ልጅቱም መልከ ቀና የረጋች ናት፤ አነጋገርዋና አካሔድዋም እንደ አዋቂ ነው ። ዕድሜዋም ፫ ዓመት ያህል ይሆናል ።

የትምህርት ቤቱም አዳራሽ በጥሩ አበባና በጥሩ ምንጣፍ አጊጦ ጥሩ ጥሩ ወምበር ተደርድሮ የተጠሩት ሰዎችም ስም በወረቀት እየተጻፈ በየወምበሩ ላይ ሁኖ ሰዎችም ለአጋፋሪ ሳያስቸግሩ ስማቸውን እያነበቡ ተቀመጡ ።

— —በጃንሆይና በግርማዊት መነን ፊት ለፊት በንጉሠ ነገሥቱና በእቴጌይቱ ዘውድ አምሳል የተሠራ ብስኩት ከፍ ባለ ጠረጴዛ ላይ ሁኖ ሲታይ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር።ይህም መልካም ምሳሌ ነው ። ከፍ ባለ ቦታ ላይ መሆኑ በደግነትና በዕውቀት ለበለጡ ለጃንሆይና ለግርማዊት መነን የተዘጋጀ ለመሆኑ ምሳሌ ነው ። በብስኩትም መሠራቱ ለገበሬ ለነጋዴ ለሠራተኛ ለወታደር መልክም ሕግን፤ ለሕፃናት ጣፋጭ ትምህርትን ለመስጠታቸው ምሳሌ ነው።እንግዴህ ወደ መጀመሪያው ነገር እንመለስ ከዚህ በኋላ ድምፀ መልካሞች ተማሪዎች መዝሙር ዘመሩና ከልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የተጻፈውን ቁምነገር ያለውን ጨዋታ (ትያትር) አደረጉና ጃንሆይንና ግርማዊት መነንን የነበሩትንም መኳንንት እጅግ ደስ አሰኙ።ቀጥሎ የሻይ ግብዣ ተደረገና ሻምፓኝ በቀረበ ጊዜ ወይዘሮ ቀጸላወርቅ ዲስኩር አለ ፍርሀት እንብበው እጅግ ደስ ስለ አሰኙ ፫ ጊዜ ተጨበጨበላቸው ።

ቃሉንም ስፍራ ስለ ጠበበን በሚከተለው እንጽፋለን ።

ወይዘሮ ቀጸላወርቅ ለወዛይዝር መሪ መሆናቸው እጅግ ደስ ያሰኛል።

የኢትዮጵያ ብርሃን ጃንሆይ በተወለዱበት ቀንም እንደህ ያለ የተመሰገነ በዓል ማድረጋቸው ለመንግሥት አሳቢ መሆናቸውን ያስረዳል፡ነገር ግን የሺ ፍልጥ ማሠርያው ልጥ እንዲሉ ባለቤታቸው ባያስተምሩአቸውና ባይፈቅዱላቸው እንዲህ ለወይዛዝር መሪ ባልሆኑም ነበርና ደጉን አስተማሪአቸውንና መሪአቸውን አዛጋር ወርቅነህን እጅግ ልናመሰግናቸው ይገባናል። ይህም ቁምነገር ያለበት ጨዋታ (ትያትር) እጅግ ደስ የሚአሰኝ ስለሆነ ሁለተኛ ይደገም ተብሏልና አነጋገሩን በሚመጣው ጊዜ እናስታውቃችኋለን ።

ሹም ሽር ።

በሐምሌ ፳ቀን ልጅ ተፈራ ገብረ ማርያም የደጃዝማች ገብረማርያም ልጅ የጅቡቲን ቆንስልነት ተሾሙ ።

ሹመት ያዳብር

የነፋስ አደጋ ።

በሐምሌ ፳ቀን በእንጦጦ ከተማ ታላቅ ነፋስ ነፍሶ ታላላቆችን ቤቶች አፈረሰ።ታላላቆች ብዙ ዘመን የኖሩትን ዛፎች እየነቃቀለ ጣላቸው ሰው ግን አላጠፋም ።

እሚአሳዝን አደጋ ።

የባለፍትሐ ነገሥቱ የአለቃ ገብረ ክርስቶስ ባለቤት ወይዘሮ የውብዳር በአባታቸው የዳጃዝማች መኰንን የልጅ ልጅ እናታቸው የወይዘሮ ባፈና የጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የመጀመሪያ ባለቤት የነበሩት የልጅ ልጅ እጅግ የተዋቡ መልከ መልካምና

ጠባየ መልካም የመንፈሳዊ ሥራ የሚወዱ እጅግ መልካም ሴት ከባላቸው ጋራ በቁርባን የፀኑ ነበሩ ። ነገር ግን የሰው መጠሯው ልዩ ልዩ ነውና እንጦጦ ወደ መላእክ ገነት ወልደሐና ቤት እኅታቸውን ለመጠየቅ ሲሔዱ ከሚሔዱበት ቤት አጠገብ ትንሽ ጕርንዳ ቦታ አለችና በጕርፍ ብዛት ሞልታ ቈይታቸው መቸም ደግ ናቸውና ሰው አላደክምም ብለው ሁለት አነስ አነስ ያሉ ልጆች ነበሩና ያስከተልዋቸው በቅሎው አንቅፎት ሲወድቁ ልጆቹ ኃይል ስለ አነሳቸው ማንሣት አቅቷቸው በሐሌም ፳፭ቀን በ፲ሰዓትውሀ ወሰዳቸው። የጃንሆይም ርኅራኄ እጅግ ይበዛልና በነጋው ሠራዊቱን ሁሉ በየሰፍራው አዝዘው ጃንሆ-ይም በግርም በበቅሎም ወንዝ ወንዙን ሲለፉ ውስው ሬሳቸው ሳይገኝ ቀረ። ልብሳቸውና ማተባቸው የባሬቸው ሹሩብ ሳይቀር ተገኘ ሬሳቸው ግን እስከ ዛሬ አልተገኘም ። ጃንሆይም እጅግ አስበውበታልና ባላገሩንና ሠራዊቱን እስከ አዋሽ ድረስ ፈልጉ ብለው አዝዘዋልና ሬሳቸው ይገኛል የማለት ተስፋ አለን ። የአ-ሊቃ ገብረ ክርስቶስን ኃዘን ያየ ሰው መሆኑን ይጠላል ነገር ግን ያለፈ ነገር ቢመኙት አይሆን ። ዝም ብሎ ተራ ተራውን መጠበቅ ነው ፤ እንጂ መቸስ ምን ይደረጋል ለአለቃ ገብረ ክርስቶስም እግዚአብሔር ጥናቱን ይስጣቸው ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የሴብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ባንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ አሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቶችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። ሀጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረን ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፊርና ዲስና ልጆቹ ።

የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE

BORSALINO

ALESSANDRIA

(ITALIA)

MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S&E&A METAXA

LE PIRÉE-GRÈCE

KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፪
6me ANNÉE № 32

ሐሙስ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 7 AOUT 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers — Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሐሰት ወሬ ስለሚያወሩ ሰዎች ሐሳታቸውን የሚገልጽ እውነተኛ ቃል ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በመጋቢት ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት በንጉሠ ነገሥት ዙፋን ስለ ተቀመጡ የንጉሠ ነገሥቱን ዘውድ የሚጭኑበትና የዘውዱ በዓል የሚከበርበት በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት እንዲሆን ግርማዊነታቸው ወስኖ ፡ በዚሁ በዘውድ በዓል ቀን ታላላቆች መንግሥቶች እንደራሴዎቻቸውን እየላኩ የደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ለልዩ ልዩ መንግሥቶች የጥሪ ደብዳቤ ተልኳል።

ነገር ግን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ የሚጭኑበት ቀን በጥቅምት ፳፫ መሆኑ ቀርቶ በጥር ወር ሁንዋል የሚል ሐሰት ወሬ በአውሮፓ ልዩ ልዩ ጋዜጦች ታትሞ እናያለን ። ይህን የመሰለ ቃል በጋዜጣ በመታተሙ የተነሣ ጋዜጣውን ያነበቡ ብዙ ሰዎች ነገሩ እውነት እንደ ሆነ እያሉ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አንዳንዶቹ የጥያቃ ወረቀት ይጽፋሉ ። አንዳንዶቹም በቃል ይጠይቃሉ ።

እነዚህ ይህን ወሬ እያተሙ ያወጡ ጋዜጦች ከሐሰት ተናጋሪዎችና ፤ ይህንም የኢትዮጵያ ጠላት መሆናቸውን ከሚገልጽባቸው ሰዎች የተገኘውን ሐሰት ወሬ መሠረት ከማድረግ በፊት አስቀድሞ የታመነና እውነተኛ ነገር ለሕዝብ ለመግለጽ በየስፍራው ያሉትን የኢትዮጵያ ሌጋሲዮኖችና ቆንስላቶች፤ ወይም ከሌሎች ከሚታመኑ ከእርግጠኛ ሰዎች ቢጠይቁ ይህን ከእውነት የተራራቀ ነገር በማተም አይሳሳቱም ነበር ። ይህን ሐሰት ወሬ በማቀበል ጋዜጠኞችን በተንኰል ያሳሳቱና በዚሁም ሥራቸው የጠላትነታቸውን አሳብ የገለጹ ሰዎች ሳይታወቁ ይቀራሉ ብለን አንጠረጥርም ።

የዘውዱ በዓል ግን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከዚህ ቀድሞ በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት እንዲሆን የወሰኑት የፀና መሆኑን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሁሉ እንገልጻለን።

MISE AU POINT

Sa Majesté l'Empereur HAILe SELLASIE Ier étant montée sur le Trône Impérial le 25 Megabit 1922 (3 Avril 1930) fixa la date des Cérémonies de Son Couronnement au 23 Tekemt 1923 (2 Novembre 1930).

Des invitations furent, à cette occasion, adressées à diverses Nations, pour les prier de se faire représenter á ces cérémonies et de prendre part à la joie de Sa Majesté

Cependant, nous lisons dans différents journaux d'Europe une fausse nouvelle d'aprés laquelle la date du Couronnement aurait été reportée du 23 Tekemt (2 Novembre) au mois de Janvier .

Comme suite de la publication de cette nonvelle tendancieuse, des lecteurs de ces journaux, s'imaginant qn'elle était fondée, se sont adressés, soit par écrit soit verbalement, au Ministère des Affaires Etrangères.

Si les journaux qui ont publié cette information en se basant sur des affirmations erronées et de faux bruits émanant de personnes qui manifestent ainsi leurs sentiments d'hostilité envers l'Ethiopie, avaient eu le souci de faire connaître au Public des choses

vraies et bien fondées, ils auraient dù demander des renseignements aux Légations et Consulats institués dans diverses contrées ou bien à des informateurs de bonne foi. Ils auraient ainsi évité de répandre un tel bruit et de commettre des erreurs grossières en publiant ces nouvelles qui ne correspondent pas à la vérité.

Nous ne doutons par que les correspondants qui ont abusé de la bonne foi des journalistes en leur communiquant cette nouvelle qu'ils savaient fausse et qui ont en cette circonstance, dévoilé leurs sentiments d'hostilité ne soient démasqués.

Nous faisons connaitre à tous les lecturs de "BRHANNA SALAM" que la décision prise antérieurement par Sa Majesté l'Empereur HAILe SELLASIE Ier fixant la date de Son Couronnement au 25 Tekmt 1923 (2 Novembre 1930) demeure irrévocable.

ስለ ዕርቅ ድርድር

አቶ በቀለ ዘለቀ ስለኢትዮጵያውያን ወይዛዝር ስለጻፉት የምክርና የወቀሳ ቃል መልሱን በግንቦት ፯ ቀን በቍጥር ፳ ብርሃንና ሰላም ጽፌ ነበርና ። አሁን አቶ ተስፋዬ ካሣ በግንቦት ፳፩ ቀን በቍጥር ፳፱ ብርሃንና ሰላም የጻፉትን የዕርቅ ድርድር አይቼ መልሱን በጭሩ ከዚህ ቀጥዬ ጽፌአለሁና እንደ አቶ ተስፋዬ ካሣ ትንሽ ያድልዎ ነገር ሳታገቡ በተካከለ አእምሮ እስተውላችሁ እንድታነቡልኝ አንባቢዎችን እለምናሁ። አቶ ተስፋዬ ካሣ ያገራችን ወንዶች እንደ ውአሮፓውያኖች ለኛ ለሴቶች እምነትን ለምን አይሰጡንም ብዬ በጻፍኩት ነገር በጣም ተደንቀዋል ። እውነት ነው የማያደርጉት ነገር በጣም ያስደንቃል ። እኔም ይኸንን የጻፍኩት አቶ በቀለ ዘለቀ የኢትዮጵያን ወይዛዝር ፈጽማችሁ እንደ አውሮፓውያን ወይዛዝር ሁኑ እንጂ እንደጐደኛ እንደ ቍስላም አትሁኑ እያሉ ዘወትር የሚጽፉትን የስድብ ቃል አይቼ ፈጽማችሁ እንደ አውሮፓ ወይዛዝር ሁኑ ካላችሁን እናንተም እንደ አውሮፓውያን እምነትን ስጥታችሁን በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ መሪያችን ሁኑ በማለት ነበር ። አቶ ተስፋዬ ካሣ አቶ በቀለ ዘለቀ ዘወትር የሚጽፉትን አስረግጠው የተመለከቱት አይመስለኝም እንጂ ደኅና አድርገው ተመለክተውስ ቢሆን አቶ በቀለ ዘለቀ እንደዚህ ያለውን አልጻፈላችሁም ብለው አይከዱም ነበር የሆነ ሆኖ አሁን አቶ ተስፋዬ ካሣ ያውሮፓ ወይዛዝርት ቀሚሳቸው በማጠሩና ሳይከናነቡ በግልጽ በመሔዳቸው ደግሞም ባሎቻቸው እምነትን ለሚስቶቻቸው በመስጠታቸው ስሑቶች ናቸው ብለው ወደ ድንቍርና ቄጥረውባቸው ለኛም ለኢትዮጵያውያን ወይዛዝር እንደ ቀድሞው ልማዳችን ቀሚስ ማስረዘምና መከናነብን ፈቅደውልናልና አሁን እኔ በዚህ መከራከር አያሻኝም ግን አቶ ተስፋዬ ካሣ ከጻፉት ውሥጥ ያልተረዳሁት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በገነት በስቀመጣቸው ጊዜ አዳምን ከሔዋን ፈቃድ አትውጣ ብሎት ነበር ይባላል ያሉትን ቃል ከቶ በመጽሐፍ አላነበብኩምና ከመጽሐፍ ጠቅሰው ቢያስረዱኝ እወዳለሁ ግን በኔ ሐሳብ እግዚአብሔር ያደረገው ሔዋን ከአዳም ፈቃድ እንዳትወጣ ይመስለኛል ። ይህስ ባይሆን በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ፪ ከቍጥር ፳ ፳፭ ። ለአዳም ግን በጠገቡ የምትሆን ረዳት አላገኘለትም ነበርና ከጐድኑ አጥንት ሔዋንን ፈጥሮ አመጣለት ባላለም ነበር ። ረዳት ማለት ታዛዥ እንጂ አዛዥ ማለት ነው ብሎ ለመተርጐም በጣም ያስቸግራል ። ግን ወንዶች ዘወትር እኛ ስሑቶች አይደለንም ለማለት ይኸን ያስት ነገር ይተርካሉ ። ደግሞ ከዚህም ሌላ ወንዶች እኛ ስሑቶች አይደለንም ሲሉ ዕፀ በለሱን ሔዋን ስለዋጠችው ሴት ማንቍርት የላትም አዳም ግን ሔዋን አታላ ሌላ ነው ብላ ነበርና ዕፀ በለሱን የሰጠችው ከሰጠችው በኋላ ሊውጥ ሲል ዕፀ በለስ ነው ብላ ብትነግረው አክ ሲል እጕሮሮው ላይ ማንቁርት ሁኖ ወንድ ሁሉ ማንቍርት አለው እያሉ ራሳቸውን ንጹሕ ለማድረግ ይጥራሉና አቶ ተስፋዬ ካሣም እግዚአብሔር አዳምን ከሔዋን ፈቃድ አትውጣ ብሎት ነበር ያሉት ይኸን የሐሰት የአፍ ታሪክ ይዘው ይመስለኛል ። ይኸንን ሁሉ ግን እኛ በመጽሐፍ አላገኘነውም ሔዋን አዳምን አሳተችው የሚባለውም በኦሪት ዘፍጥረት በምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፩ ፲፬ በተጻፈው ነው ያን ንግግር ሲያነቡት ሔዋን እባቢቱ እንደነገረቻት ዕፀ በለሱን በልታ ለአዳም ወስዳ ብትሰጠው እሱም እንደሔዋን የማይገባውን ክብር ለማግኘት ሲል ፈቃዱ ሆኖ ዕፀ በለስን ስለበላ ወደጥፋት ደረሰ እንጂ ሔዋን በግድ አሥራ ገርፋ ዕፀ በለሱን አብልታ ወደ ጥፋት እንዳላደረሰችው ያሳያል ። መቼም ጥፋተኛ ምክንያት መስጠቱ ልማድ ስለሆነአዳም ሔዋን አሳተችኝ ቢል ሔዋንም እባቢቱ አሳተችኝ ብላለችና በምክንያት እኩል ናቸው እንደዚህ ከሆነ ጥፋተኛዋ እባቢቱ ብቻ ናት ማለት ነው ። የሆነ ሆኖ እኔ ይኸን ለመከራከር የሚበቃ ትምህርት የለኝምና በጭሩ እተወዋለሁ ።

ሁለተኛ አቶ ተስፋዬ ካሣ ቀሚስ ማስረዘማችን መከናነባችን ሴቶች ልጆቻችንንም ወደ ትምህርት ቤት አለመላካችን ምክንያቱ በወንዶች መሆኑን ተረድተው ዝቅ ብለው ለምን በበቅሎ ራሳቸው ወጥተው ወርደው ያለ ደጋፊ ለመሔድ አለመቻላቸው ብለው ወቅሰውናል። ግን ለዚህ እሳቸው መቼም የተጠየቀ ሰው ሐሳቡና መልሱ እንዲከናወንለት ይጥራል እንጂ የሚጐድልበትን አያስተውለውም ያሉት ንግግር ፈጽሞ ለራሳቸው ሆነ ። ማለት ቅልጥፍና እንጂ የሚገኘው ከትምህርት ነው ። ደግሞ አቶ ተስፋዬ ካሣ ባይክዱ የአውሮፓ ሰዎች ሴቶች ልጆቻቸውን ገና በልጅነታቸው ቅልጥፍናን እንደሚያስተምሯቸው ሁላችንም ሰምተናል ለዚሁም በዚሁ በ፳፱ ኛ ቍጥር ብርሃንና ሰላም በ፩፻ኛው ገጽ በፈረሶች መቀዳደም የተነሣ ስለሙሴ ዶሮቢያር ልጅ የተጻፈውን ብናነብ ለመረጃ ይበቃል። የአውሮፓ ሰዎች ሴቶች ልጆቻቸውን ገና በሕፃንነት ቅልጥፍናን ያስተምሯቸዋል ማለት ሴት ልጆቻቸውን ወደ ቀማሪ ቤት ሒደው ሲማሩ ለሴት ልጅ የሚገባውን ጅምናስቲክ

የሚባለውን ጨዋታ ይጫወታሉና በዚያው ቅልጥፍናን ይማ-ራሉ ወዲያውም ወላጅ አባቶቻቸው በልጅነታቸው ጀምረው ወደ ተማሪ ቤት ሲሔዱ ብቻቸውን በበቅሎና በፈረስ እያስኬዱ ያስለምዷቸዋል ። ትምህርት ማለት መልመድ ነውና ይኸው ትምህርት ሆኖአቸው ቅልጥፍናን ይዘው ይኖራሉ ። አቶ ተስ-ፋዬ ከማም ተከተማ ወጥተው በያውቁ ይሆናል እንጂ በኢት ዮጵያም ውሥጥ ራሳቸው ርከብ ረግጠው ዘብ ጨብጠው እኩብት ላይ ለመውጣትና ለመውረድ ከወጡም በኋላ ለበቅሎዋ መሪ ሳያሻቸው ብቻቸውን ለመሔድና ፈረስ እስከመጋለብ ድረስ የሚችሉ ። ከማራም ወገን ከጋላም ወገን ብዙ ሴቶች ይገኛሉ ። ይኸውም በልማድ ነውና ያገራችን ወንዶች ሁሉ እኛን ከመውቀስ ሴቶች ልጆቻችሁን በሕፃንነት እንደዚህ ያለ-ውን ልማድ ብታስለምዱ ይሻላል ።

፫ተኛ አቶ ተስፋዬ ከማ በዛሬው ጊዜ ቀሚስ ማሳጠር ክንብንብ መተው አብድ ያሰኛል ካሉ በኋላ ደግሞ ቅልጥፍና መልከም ነው ይላሉ ። ይኸውም ቀሚስ ከረዘመ ክንብንብ ካለ ቅልጥፍና እንዴት አድርጎ እንደሚያውክ ልብ አድርገው ባያውስተሉት ነውና የአውሮፓ ወይዛዝር ቀሚሳቸውን በማ-ሳጠራቸው ሳይከናነቡ በግልጽ በመሔዳቸው ባሉቻቸውም እምነትን በመስጠታቸው በነውር ከተቈጠረባቸው እኛ የኢ-ትዮጵያውያን ወይዛዝር የሚሻለውን መንገድ ይዘናልና በቀሚሳችን ርዝማኔና በክንብንባችን የተነሣ ለመቀልጠፍ ባንችል ልንወቀስበት አይቻልም ። ግን አቶ ተስፋዬ ከማ የተ-ናገሩት በግልግል ጀምረው ስለሆነ በግልግሉ ውሥጥ ለወገ ኖቻቸው አድልተው ቢናገሩ አይፈረድባቸውምና የአውሮፓ መኳንንትና ወይዛዝር ከልተቀየሟቸው ለኛ ያንኑ የቀድሞ ልማዳችንን ስለፈቀዱልን ረዳታችን ሆነዋልና በጣም እናመሰግ-ናቸዋለን ። እኔ ግን በሁሉም በፊተኛውም በሐሳቤ የተንቀሳ-ቀሰውን ነገር ጻፍኩ እንጂ ለክርክር ብዬ አይደለምና ከሁሉ ቀደም ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ በብርሃንና ሰላም ዘጸሐፍኩ ጸሐፍኩ ብለው እንዳመለክቱት እኔም የጻፍ ኩትን ጽፌአለሁና ሁላችሁም ይቅርታ እንድትሰጡኝ እለም ናለሁ ።

ምዕራብ ወሰጋ ።

ወ እምሳለ ጥበብ ወልደ አብ ።

ሠርግ።

በሐምሌ ፳፮ቀን ነጋድራስ አፈወርቅ ልጃቸውን ወይዘር ፅሌናን ለሙሴ ኤርኒስቶ ሳከኒ ሲድሩ ብዙ ከኢትዮጵያና ከሮጳ ሰዎች ጠርተው ነበር። በመጥሪውም ደብዳቤ መጨረሻ ከምርቃት በቀር ሌላ ነገር ክልክል ነው አንቀበልም የሚል ቃል ተጽፎበት ነበር ። ወደ ቤተክርስቲያን ሒደው የተክሊሉን ሥርዓት ጨርሰው በዚያው በቀጠሮው በ፲ሰዓት ሮቢንስን በሚ-ባለው በልዑል ራስጎይሉ ሆቴል ነጋድራስ አፈወርቅ ከባለቤ-ታቸው ጋራ ሙሽሮችና የተጠሩትም ሁሉ ባንድ ጊዜ ደረሱ የማዘጋጃ ቤት ሙዚቃ ነፊዎችም ደስ በሚአሰኝ ሙዚቃ ተቀበሏቸው ። ሆቴሉም ባበባና ደስ በሚአሰኝ ጌጥ አምሮ ተሸናድቶ ነበር ። ለሙሽሮችም ለብቻ አንድ ክፍል ተዘጋጅ-ቶላቸው ነበርና ገብተው ተቀመጡ።እንግዶችም በየማዕረጋቸው ተቀመጡ ። የተጠሩትም ሰዎች ከኢትዮጵያና ከሮጳ ሰዎች ብዙ ነበሩ።ከኢትዮጵያ ሰዎችም ከተጠሩት የመጡ ታላላቅ መኳንንት ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ።

ልዑል ራስ ጎይሉ
ልዑል ራስ ሥዩም
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው
ከንቲባ ነሲቡ
ብላቴን ጌታ ኅሩይ
አቶ ብርሃነ ማርቆስ
አቶ አየለ ገብሬ
አቶ ተስፋዬ ተገኝ
አቶ ገብረ ክርስቶስ
አቶ በቀለ ኪሮስ
አቶ ተስፋ ግዮርጊስ

የቀሩትም እንግዶች ነበሩ ፤ የሮጳ ሰዎችም ብዙዎች ነበሩ ነገር ግን ስማቸውን እንዳንጽፍ ስፍራ ስለ ጠበበን ነው እንግዲህ ወደ መጀመሪያው ነገር እንመለስ ሽምፓኝና ብስ ኩት በቀረበ ጊዜ እጅግ ደስ የሚአሰኝ ሙዚቃ እተየመታ ታላላቆች የሮጳ ሰዎች ሁለት ሁለት ሴትና ወንድ እየሆኑ ዳንስ ጀመሩ።ሙሽራውና ሙሽራይቱም ተያይዘው እመሀል ገብተው ዳንስ ሲአደርጉ ደስ ያላቸው ሙሽሮችን ሽፋፍሞ አስቀምጦ ባልና ሚስት ሊተዋወቁ የሠርገኛ ልቡ ያብጥ እንደተባለው ተረት ሌሊትና ቀን በሰው ደስታ ልባቸው በዘፈን የሚወልቀውን የሀገሬን ሰዎች አሰቤ እጅግ አዘንሁ። እውነት ነውና በገዛ ደስታቸው ማን ያድምቀላቸው? ወዲያ ውም በሚአምር በታናናሽ የወረቀት ማጥንስኣር ተምልቶ ሙሽራይቱ ለተጠሩት ሰዎች ሁሉ ታድል ጀመረች፤በዚህ ሁሉ ጊዜ ሼምፓኙ አያቋርጥም ነበር ።

ከዚህ በኋላ ብዙ ጣፋጭ ምግብ ወደ አለበት ክፍል የተጠሩት ሁሉ ገቡና የሚወዱትን ተጋብዘው ቢራና ሼምፓኝ ጠጥተው እየመረቁ ሔዱ ። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የቈየነው ሁለት ሰዓት ያህል ይሆናል ። አሁን ነጋድራስ አፈወርቅ በዚህ ድግስ ያጠፉት ገንዘብ በግምት ሁለት ሺህብር ያህል ይሆናል። ምንም ገንዘቡ ብዙ ቢሆን ነጋድራስ አፈወርቅን ያህል ሰው እንደ ሀገራችን ልማድ ቢደግሱ ሁለቱ ሺህ ብር ለጌጥ መግዣ ብቻ አይበቃቸውም ነበር ። አላንድ ቀን በማይ-ለበስ ጌጥና ማንም ተጫውቶበት በሚሔድ ድግስ ዓሥር ሺ ብር ቢአጠፉ ምድነው ጥቅሙ?ይልቁንስ የድግሱን ግማሽ ለአ-ዲሶች ቤት ሠሪዎች ሙሽሮች ቢሰጧቸው መልካም ጥቅም ነው ። ሰውም ሥራ ሳይፈታ ደጋሹም ገንዘቡን ሳይጨርስ እንዲህ በቀላል ቢደረግ የሠርግ ነገር እጅግ መልካም ይሆን ነበር ። ድግሱ በሁለት ሺህ ብር ተተገመተ መቼ ቀላል ነው-ትለኝ እንደ ሆነ ?ዓሥር ሺህ የሚፈጅባቸውን ድግስ በሁለት ሺህ ብር ብቻ ቢገላገሉ ከስምንቱ ሺህ አራቱን ሽህ ለድሀ ልጆች እርዳታ ቢሰጧቸው ምን ያህል ጥቅም ይመስልሃል

ይልቁንስ ስምንት ቀን ዘፍኖ ስምንት ዓመት ከማልቀስ። ስምንት ቀን አለልክ ጠግቦ ስምንት ዓመት ከመራብ የሥርግን ድካም ቀላል ማድረግ ይሻል ይመስለኛል ።

የፍርክኔ ሥራ ።

የተፈሪ መኰንን ትማሪቤት ሠራተኛ አቶ አስፋው ያሳደጉት አንድ አገልጋይ ነበራቸው ። ያሳደጉት ስለሆነ ጥፋቱን ሁሉ ታግሠውት ሲኖሩ ፩ቀን መስከት ሰብሮ የተማሪዎችን ልብስ ሰርቆ ሣጥኑንም ሰብሮ ከነመጻሕፍቱ ከቤታቸው ጓሮ በቅጠል ውሥጥ ሸሽጎት ተገኘ ከዚህ በኋላ በጥርጣሬ ተይዞ ቢመረመር መውሰዱን አምኖ ልብሱንም ከሸሸገበት አምጥቶ ሰዓቱ ብቻ ሲቀር ጊዜ እንደታሠረ ቈይቶ ነበርና ሰዓቱን አቅጠሉ ውሥጥ አድርጌዋለሁና ሒዱ አምጡ ብሎ የሚጠብቁት ሰዎች ሲወጡለት በትልቅ ካራ አንገቱንና ሆዱን ቀዶት ቢመለሱ ወድቆ ተገኘ። ወደ ሆስፒታልም ቢወስዱት ዶክቶር ሐነር መድኃኒቱን አይተው ወደዚያ አቈዩት አሉና አንድ ሰዓት ያህል ቈይቶ ሞተ።

ለአዲስ አበባ ከተማ ኑዋሪዎችና ነጋዴዎች ማስታወቂያ ።

የከተማ ዘበኛ ከተማውን በሙሉ ለመጠበቅ የተዘጋጀ ሆኖ መኖሩን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ለኑዋሪዎቹና ለነጋዴዎች ያስታውቃል ።

በተለየ ግን ቊልፍ ተረክቦ ቤትና ሱቅ አይጠብቅም ፤ ከእንግዴህ ወዲያ ሌሊት ቤታቸውና ሱቃቸውን ለመጠበቅ የሚገባቸው ነዋሪዎችና ነጋዴዎች ናቸው ። ከቤትም ወይም ከሱቅ አንድ ነገር ቢጠፋ በማናቸውም ነገር ማዘጋጃ ቤት ኀላፊ አይሆንም። ዘበኛ በከተማ መንገድ እየቆመ ሌሊት ሰውም ቢጣላ ሌላም ክፉ አድራጊ ቢገኝ ይይዛል ። ሱቃቸውን ወይም ቤታቸውን ሳይጠብቁ ቀርተው ዕቃቸው ቢጠፋ ግን የዘበኞቹ ጥበቃ ማዘጋጃ ቤትን ኀላፊ አያደርገውም። ይኸው የተደረገው በቀድሞው ጊዜ ባዲስ አበባ ገበያ ውሥጥ የነበሩት የጥንት ሱቆች ቊጥራቸው እጅግ ያልበዛ ጥቂቶች ስለነበሩ የከተማው ዘበኝነት ሥራ ያንድ አንዱን ሱቅ ደጃፍ ባንድ አንድ ዘበኛ ለማስጠበቅ ተችሎት ነበረ ። አሁን ግን የሱቆቹ ሁሉ ቊጥራቸው ስለበዛ ወደፊትም እየበዙ የሚሔዱ ስለሆኑ በያንዳንዱ ሱቅ በር አንዳንድ ዘበኛ ለማድረግ ቢያስፈልግ እንኳ የማዘጋጃ ቤት ዘበኛ ቊጥር ሊበቃው አይችልም ። ይልቁንም ደግሞ የነጋዴዎችን ሱቅ ማታ ማታ በሩን አስቆልፎ እየተረከበ ለማስጠበቅ ያዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት እስካሁን ያደረገው ለነጋዴዎች እርዳታ ሲል የፈቃዱ ሥራ ነበር እንጂ በየትም አገር ቢሆን የሌላውን የጥበቃ አደራረግ በተለየ የሱቁን ቊልፍ ተረክቦ ማስጠበቅ ለአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ብቻ የተገባው ሆኖ አልነበረም ። ከእንግዴህ ወዲያ ግን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ዘበኛ ያንዳንዱን ሰው ሱቅ ቊልፍ እንዳይረከብ ደምብ መቀበሉን እናስታውቃለን ።

የከተማውን ሕዝብና ማናቸውንም ነጋዴ ቢሆን ዘበኛ ለመጠበቅ የሚገባው ግን የከተማው ሕዝብ ገንዘቡን እንዳይሰረቅና ሕይወቱም እንዲጠበቅ እያደረገ በማስተዋል እየተጠነቀቀ በጠቅላላው ለመሥራት እርግጠኛ እንዲሆን ማዘጋጀት ነው ። በዚህ ዓይነት አደራረግ የማዘጋጃ ቤት ዘበኛ የማንም ሰው ቢሆን ቤትና ሱቅ እንዳይሰረቅ የሚቻለውን እርዳታ እየረዳ የከተማውንም ሕዝብ በፀጥታ እንዲኖር ያደርጋልና ስለዚህ ከእንግዴህ ወዲያ የያንዳንዱን ነጋዴ ሱቅ በተለየ የሱቁን ቊልፍ መረከቡ ቀርቶ ማናቸውም ቤትም ሱቅም እንዳይሰረቅ የሚቻለውን እርዳታ ያደርጋል ። ነገር ግን ሌባ በከተማ ውሥጥ ቤትም ሱቅም ሰብሮ የሠረቀ እንደሆነ የከተማ ዘበኞች ተከታትለው እንደተቻላቸው በትጋት ይፈልጋሉ ። የተሰረቀባቸው ባለ ገንዘቦችም የስርቆት ነገር ባገኟቸው ጊዜ ሌባው እንዲፈለግላቸው ለከተማ ዘበኛ ፈጥነው ያስታውቃሉ ።

ይኸውም ደምብ የሚፀናው ማስታወቂያው ከወጣበት ከሐምሌ ፯ ቀን በኋላ እጅግ ቢበዛ ከሐምሌ ፴ ቀን አንሥቶ ወደፊት ነውና ስለዚህ በገበያ ውሥጥ ሱቅ ያላቸው ነጋዴዎች በገበያ ሱቃቸው ውሥጥ የሌሊት ንቁዎች እያደረጉ እንዲያስጠብቁ ቊልፋቸውንም እነሱው እራሳቸው እየያዙ በታዘዘው ሰዓት እንዲዘጉና እንዲከፍቱ የተገባቸው መሆኑን እናስታውቃለን ። ሐምሌ ፯ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም ።

የአዲስ አበባ ክንቲባ ።

የጸጋ የመከበርና በመላው የሥልጣኔ መሠረት ሁሉ ጤንነት ነው። ሐመምተኛ ሰው ለራሱ ለቤተ ሰቦቹና ለመንግሥት የከበደ ነው። ታሪክ እንደሚነግረን ብዘዎች ሕዝቦች ጤንነታቸውን ከጡ በኋላ አደጋ ወደቀባቸው ይላል በአሜሪካ አገር የተጻፈ የዶክቶር ፓፓዶፑሎስ ስለጤንነት ጥቅም የጻፈው መጽሐፍ ቀጥሎ እዲህ ይላል ታላቁ ናፓሌዎን በመስኮብ አገር አደጋ የወደቀበት ባንድ ትልቅ እራስ ምታት የተነሣ ነው ሌሊቱን ከሰስት ሰዓት የበለጠ መተኛት አልቻለም ነበር በጥቅምት ፲፱ ሺ፲፱፻፲፪ ዓ ም ጠዋት አንጐሉ እያዞረው ተነሣ በከንቱ አንድ አሳብ ወይም አንድ ፍቺ ለወታደሮቹ ሊሰጥ አሰበ ነገር ግን አልቻለም ጌዜው ተላልፎ ነበር ያትልቅ የራስ ምታት ምክንያት መስኮብን አዳናት »ጤንነት ብዙ የከበረች ስትሆን በጣም ጥቂት እንጠነቀቅላታለን ለአውቶመቢላቿን ወይም ለምንሠራባቸው መሣሪዎች እንደምንጠነቀቅላቸውና እደምንጠብቃቸው እንደዚሁም ጤንነታችንን ብንጠብቃትና ብንጠነቀቅላት ዕጥፍ ዕድሜ እንኖር ነበረ ዕጥፍ ባለጸግነትም እናገኝ ነበር ከዚህ ቀደም ብዙ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች በተክሊል ስለመጋባት ነገር እንደጸፉት ይኸንኑ ላሳስባችሁ ይኸንን ጽፌአለሁ እው-

ንትም ሰው ሁሉ ሚስት በተክሊል እያገባ የኢትዮጵያን ሕግ ቢፈጽም እንዴት ትልቅ ጥቅም ይሆን ነበር ሰው በተክሊል ሚስት ሳላገባ ልቡ ሊአርፍ አይችልም።በዚሁም ልቡ ባለማረፉ ስንት በሽታ ያመጣል ይልቁንም በዛሬ ጊዜ ቂጥኝና ጨብጥ የሚባሉት ጅራፎች ሕዝብን በጣም ይገርፋሉ።ዶክቶር ሚሊን እንዲህ ይላል ቂጥኝ ወይም ጨብጥ በመጀመሪ ብቻ ለሚይዛቸው ሰዎች አባት እናት ልጅ በዕድሜአቸው ሁሉ(አደገኛ በሽተኛ) ሊአደርጋቸው ይችላል ይላል በሚገባችሁ ጥንቃቄ ተጠንቀቁ ይላል፤ይህ በሽታ አይቀልድምና ያልተማሩ ሰዎችና ቂሎች ብቻ ቀልድ ይመስላቸዋል ስሙ ብቻ በጣም የሚአንቀጠቅጥ ነው ይላል የቂጥኝ የጨብጥ መጨረሻ ይህ ነው የራስ ጠጉር የሸፋል ጠጉር ያረግፋል ራስ ይለውጣል ለምጻም ያደርጋል መላስ ይቈራርጣል አንጎል ያናውጻል ሆድ እቃ ውስጥ ያለውን ሕዋሳት ሁሉ ያበሰብሳል ስለዚሁ ምክንያት በኢትዮጵያ ሕዝብ መኻከል ይህ በሽታ በጣም በትልቅድፍረት ስለተሳለፈ አደጋው ሳይበዛ መከላከል ያስፈልጋል መጀመሪሰው ሁሉ በተክሊል ሚስት እንዲያገባ ከጥንት ያለውን ሕግ መፈጸም ያስፈልጋል።ሁለተኛ በተለየ ሚስት በተክሊል ለማግባት የፈለገው ሰው ሆስፒታል ሔዶ ጤነኛ መሆኑን ተመርምሮ ሴርቲፊኬት ከሐኪሙ ተቀብሎ ያጫትን ሴት እንዲአገባ ደንብ ማድረግ ነው በአውሮፓም እንደሚደረገው ሚስት የሚያጭ ሰው ሁሉ ሆስፒታል ሂዶ ተመርምሮ ጤነኛ የሆነ እንደሆነ ሴርቲፊኬቱን ተቀብሎ ያጫትን ሴት ያገባል ደኅሞም ሲመረመር ውርዴ የሆነ ሰው እንደሆነና በሽታውን በፍጻሜ ያልታከመው እንደሆነ ያጫትን ሴት ተፈጣጥሞ በሽታውን እየሄደ እስከ ፍጻሜ መዳን ድረስ ይታከማል ከዚህ በኋላ ሐኪሞቹ በሽታው ለሴትዮ የማያስፈራት መሆኑና በፍጹም መዳኑን ከመረመሩ ወዲያ ሴርቲፊኬቱን ሰጥተውት ሂዶ የተፈጣጠማትን ሴት በተክሊል ያገባታል። ሶስተኛ ከተማ ውሥጥ ያሉትን ሴት አዳሪዎች ከከተማው ዳር በተለየ ቤቶች አሠርተው እዚያ እንዲቀመጡ ማድረግ ነው እንባጓሮና ጥል ሰው እዳያደርግባቸው በዘበኛ ማስጠበቅ ነው በየሳምንቱ ጤንነት እንዳላቸው ሐኪም ዘንድ እተመረመሩ መንግሥት በሚሰጣቸው የሴት አዳሪ መዝገብ ጤንነታቸውን ከተመረመሩ በኋላ ሐኪሙ በመዝገብ ላይ ይመሰክርላቸዋል ይህ ከሆነ በኋላ በከተማው ውሥጥ የሴት አዳሪዎች እየተደበቁ እንዳይኖሩ በዘበኛ አያስያዙ መቀጮ ወይም እሥራት መወሰን ነው

በንደዚህ ምክንያት ይህ ትልቁ የሰው ጠላት መርዘኛው ጅራፍ ብሎ እንደሰየመው ፕሮፌሰር ፉርኒዶ ክንፎቹን በጣም ሳይዘረጋ ልንከላከለው እንችላለን ክቡራን ወንድሞቼ ሆይ ብዙ የትልልቆች ሐኪሞች መጻሕፍቶች እንደሚነግሩን ስለ ቂጥኝና ጨብጥ በሰውነት ላይ ስለሚአመጣው አደጋ እንኳንስ ተክሊል የመሰለችዋን ነገር ልንንቅና ይልቁንም ምናኔነትን እንደሚአሳስበን ጥርጥር የለውም (ያለ ጤንነት ኑሮ ከንቱ ነው) ይላል ኤስኪሎስ) በንት የዋሆች ልጆች በአዲሱ በፍጥረት ብርሃን ብቅ ሲሉ ከአባታቸውና ከእናታቸው የተላለፈውን ውርስ ቂጥኝ ወይም ጨብጥ ይዘው ይወጣሉ ስንት ልጆች በቂጥኝና በጨብጥ ምክንያት ዓይነ ስውሮች ሁነው ይወለዳሉ ይኸውም ያባትና የናት ጥፋት ነው ከትንሽ ጊዜ በኋላ ለሚወልዱት ሕፃናት አስበው በሽታውን በመድኃኒት ሳይነቅሉት ይቀሩና እነኛን ብቃያ ቢራቢሮ ሕፃናቶች በስንፍና ብዛት ባለመታከማቸው የዘለዓለም አደጋ ይሰጧቸዋል።እነኚህ አባትና እናት በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ምሕረት የሌላቸው ኃጢአተኞች ናቸው ስንት ልጆች በመሳም ብቻ ከዚህ ከሚአስፈራው በሽታ ይካፈላሉ ምሳሌ ባይኔ ያየሁት እፊት በር አቶ ገብረ ሚካኤል የሚባል ሰው ሶስት ዓመት ዕድሜ የሚሆነው በጣም ውብ የሆነ ልጅ አለው ይኸኑም ልጅ አንድ ሴት ከንፈሩን ስማው ቂጥኛም ነበረቺና ልጁን ቂጥኝ አጋባችበት ስለዚህ የዚያን የውብ ልጅ ከንፈር ቂጥኙ ቆረጠበት ያን የመሰለ ልጅ ያየ ሰው በጣም የሚያሳዝን ነው ለዚሁም ሕፃናቶችን በጭራሽ አለመሳም ነው ምን አለበት በመሳም አንድ አንድ ሰዎች የወደዱአቸው የሚመስላቸው እንደሆን አሳባቸው በጣም ተሳስቷቸዋል ማለት ብዙ ሰዎች ሕማም ያለባቸው እነኛን ሕፃናቶች ከንፈራቸውን በሳሙ ጊዜ በሽታ ያገቡባቸዋል ስለዚህ ይህ ኃጢአት ይባላልእንጂ መውደድ አይባልም ደግሞም ሕፃናቶችን መሳም ግዴታ የሚመስላቸው ሰዎች እንዳሉ እጆቻቸውን ይሳሙእንጂ ከንፈራቸውን መሳም አይገባም በውሮፓ ልጆቻቸውን በሽታ እንዳይናኝባቸው ቤተ ሰዎቻቸው አባትናእናትይህን ብልሃት አድርገዋል (አትሳሙኝ) የሚል ክርታስ እየጻፉ እልጆቻቸው አንገት ላይ በክር ያንጠለጥሉላቸዋል እንግዴህ ልጆች የምትወልዱና ልጆች ያሏችሁ አባቶችና እናቶች ይኸን ሕግ መፈጸም ነው ምንም አለመፍራት ነው ። ወዳጅ ይቀየመናል ከማለት የሕፃናቶችን ጤንነት መጠበቅ ይበልጣል ። ማለት ያየሚወዳችሁ ወዳጅ ልጆቻችሁን በመሳም ውዴታውን የሚገልጥበት አንድም ምክንያት የለውም ስለዚሁም የጤንነትን መሠረት ለመጠበቅ ሚስት በተክሊል የማግባትን ሕግ መፈጸም ነው።በዚሁም ነገር አዋቂነት ያላቸው ጃንሆይ በጣም በመመልከት ያስቡበታል ስል ሙሉ ተስፋ አለኝ

ስለ ደዌ ሥጋ የታመሙት ሰዎች በከተማው ውሥጥ ብዙ ደዌ ሥጋ የታመሙት ሰዎች በዝናብና ከዚህ በታች በጻፍኩት ዓይነት ምክንያት ይኸንን የሚያስፈራውን በሽታ ይነዛሉ እልመና ሂደው አረቄ ጠጅ ወይም ጠላ ይመጸውቷቸዋል በዚያ በጠጡበት ዋንጫ ብርሌ ብርጭቆ ወይም መለኪያ ጤነኛ የሆነ ሰው ይጠጣበታል በዚሁ ያ በሽታ ተናኝቶት ያጤናማ ሰው ደዌ ሥጋ ሕመምተኛ ይሆናል ሁለተኛ በልመና በሚአገኙት ገንዘብ ከጤናማ ሴት ጋር ተገናኝተው ልጅ ትወልድለታለች በተወለደው ልጅና በናቱ በሽታው ተጋብቶ ደዌ ሥጋ ሕመምተኞች ይሆናሉ ሶስተኛ ጤናማ ድኆች ከደዌ ሥጋ ሕመምተኞች ጋር ባንድ ቤት ይቀመጣሉ ባንድ ገበታ ይበላሉ ያሚክሮብ) ይነዛና ጤናማዎቹም ድኆዎች ደዌ ሥጋ ሕመምተኛዎች ሁነው ይቀራሉ ። አራተኛ ደዌ ሥጋ ሕመምተኞች መጠጥ ጠጥተው እመንገድ ላይ ይወድቃሉ ለነፍሱ ያለ መንገደኛ ይልቁንም ዘበኞች ለአገራቸውና ለመንግሥታቸው ሲሉ ግዴታ ሁኖባቸው ከመንገድ ላይ ሲአነሷቸው ያየሚአስፈራው ሚክሮብ ይናኝባቸዋል አምስተኛ በየ-

ድግሱ በየተሰከሩ በየማኅበሩ ሂደው ሲመጻወቱ በሚጠጡበት እቃና በሚአድሏቸው ሰዎች ላይ ያን የሚአንቀጠቀጠውን ሚክሮብ) ያናኙባቸዋል ስለዚህ ከዚህ ቀድሞ ጃንሆይ ምኒልክ እደብረሊባኖስ ላይ አስበው በተለየ ስፍራ ቤት አቁመው እንዳለው እንደዚሁም አሁንም ቢሆን ደዌ ሥጋ የታመሙትን ሰዎችን ለመለየትና የጤናማዎቹን ሰዎች ጤንነት ለመጠበቅ ምንም አንድ ጊዜ ለመፈጸም ባይቻል ጥቂት በጥቂት በተለየ ስፍራ ወስኖ ማስቀመጥ ነው እንደዚህ ሲሆን አደጋው በጣም ሳይዘልቅ ሚክርቡ ሳይናኝ የሚአከላከል ታላቅ ሥራ ይህ ነው ስል አሳስባለሁ ።

ሚካኤል ማክራስ

ስለ ከተማ ዘበኞች ትጋት ።

አሁንባለፈው በሐምሌ ወር ውሥጥ ፊታውራሪ ማንደፍሮ የሚባሉትን ሰው ሌቦች በሚያበግርም ጭከና እገዛ ቤታቸው ድረስ በሌሊት ሒደው በገዛ መሣሪያቸው ደብድበው ገንዘባቸ–ውን ዘርፈው መውሰዳቸው በከተማ ዘበኞች በኩል ተሰምቶ ነበረና የከተማ ዘበኞች በትጋት ሲፈላለጉ ቈይተው ሳለ ይል፡ቁንም የዋና ምርመራ ዘበኞች አለቃ አቶ ኃይሌ ሮባ በዚህ ነገር በጣም አስበ ሌት ተቀን ብሎ በመፈላለግና ጥልቅ በሆነው አመራመሩ በፊታውራሪ ማንደፍሮ ላይ የጭከና ሥራ የሠሩ–ትን ሌቦች ፈለቀ ገዛኸኝ ወልደ ሥላሴ ወልደ ሰንበት ከፋ። አበጋዝ ወልደ የስ ብዩ የሚባሉትን ደግሞ እነዚህኑ ሌቦች በምግብና በመጠጥ የሚትረዳቸውን እኅተ የምትበለዋን ሴትዮ አንድነት አስተባብሮ ይዞ አቅርቦ ጥፋታቸውን አሳምኖ ወደ ቅጣት ፍርድ መለያ ቤት ካሳለፋቸው በኋላ ሌላ የተለየ ከዚህ ልዩ ልዩ ጥፋት መሥራታቸውን ተናግረው በ፳፫ ሐምሌ አጃ ንሆይ ችሎት ቀርበው ፈለቀና ገዛኸኝ ወልደ ሥላሴ የሞት ፍርድ ስለተፈረደባቸው የጥፋት ሥራ በሠሩበት ቦታ ላይ ተሰቅለዋል። የቀሩትም ሌቦች እንደሚገባቸው ቅጣታቸውን ተቀብለው በእ ¨ር ቤት ሆነው እንዲኖሩ ለየ አገረ ገገው ተሰጥተዋል ።

ደግሞ ተሰማ ደነቀ የሚባል ጥፋተኛ እዘብጥያ ታሥሮ ይኖር ነበረና ቅጣቱን ተቀብሎ በውጭ አገር እንዲኖር ከተ–ፈጠመ በኋላ ያ የለመደው ጥፋቱ የማይለቀው ስለሆነየተቀበለውን ቅጣት ሁሉ ዘንግቶት እንደገና ደግሞ ከሰላሌ ደምሴ የሚባለውን ሰው በቅሎ ሰርቆ ወደ አዲስ ዓለም ሲሄድ የዋና ምርመራ ዘበኞች አለቃ አቶ ኃይሌ ሮባ በከተማው የጥፋት ሥራ ሠርተው ወደ አዲስ ዓለም የወረዱ አሉ ማለትን ሰምቶ ለመመርመር ወርዶ በድንገት ተሰማ ደነቀን ከሰረቀው በቅሎ ጋራ ይዞ አምጥቶ መስረቁን ካመነ በኋላ ቅጣቱን እስቲቀበል ድረስ በዘኞች እጅ ታሥሮ እንዲቈይ ወደዘብጥያ አልፏል ።

እነዚህ የዋና ምርመራ ዘበኞች የምርመራውን ሥራ ከጀመሩ አንስቶ ብዙ ልዩ ልዩ ደስ የሚያሰኝ ሥራ መሥራ–ታቸውን አስታዋይ የሆኑት የከተማ ሕዝቦች አዘውትረው እንደታናገሩ ከዚህም ቀደም ሰምተናል አሁንም ፊታውራሪ ማንደፍሮ የጉዳታቸውን ካሣ ባቶ ኃሌ ሮባ ብርታትና ትጋት ስላገኙ ወገኖቻቸው ሁሉ ደም መላሾችን ነህ እያሉ ደስታቸውን በግልጽ ተናግረዋል

ሹ ም ሽ ር

ፊታውራሪ ሽህ አምጥ ዠሎ የግራዝማች ዕንቈ ሥላሴ የነበረውን ሹመት ተሾሙ ። ግራዝማች ያረጋል የግራዝማች ኃይሌ እንደብልህቱ የነበረውን ዘጊነትን ተሾሙ ። አቶ ሐረ ሰማይ የሻምበልነት ጨምረው የዠሎንና የኰንታን ነጋድራስነት ተሾሙ ።

ልጅ ለማ ደገፌ ዠሎ የፊታውራሪ ደምሴ ያየህ ይራድ የነበረውን የሽ አምበልነት ተሾሙ ።ባሻ ተገን በያዙት ማደ–ሪያ ላይ ሌላ ማደሪያ ተጨምሮላቸው ባላምባራስ ተባሉ ። ባሻ ተክለማርያም በያዙት ማደሪያ ላይ ባላምባራስ ተባሉ ልጅ ታደሰ አምመው ያባታቸውን የሽአምበልነት ተሾሙ።

ሹመት ያዳብር ።

ማስታወቂያ

ታደሰ ተሰማ የሚባል ዕድሜው ዓሥራ አራት ዓመት ያህል የሚሆን አገሩ ሰቈጣ ዋኳ ውሥጥ ዳግብጊ ይባላል።ልጁም የዳጃዝማች ደስታ ጌንጉል የወንድማቸው ልጅ ነው በሐምሌ ፳፫ቀን ጠፍቷልና ያገኘው ሰው የድካሙን ዋጋ ይቀበላል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኑ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንኑም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ከከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ–ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ድርሳነ ሚካኤል የምትገዙ ሰዎች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በጥንቃቄ ታርሞ ታትሟልና እየመጣችሁ ግዙ ።

ዋጋውም
- ፩ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፲ብር ነው
- ፪ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፯ብር ነው
- ፫ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፮ብር ነው

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ክንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሳላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አሳድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ቶመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጒበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቋቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፤ የርሻ የፋብሪክ፤ የደን፤ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዦና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም ባቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልየን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናዲ ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፫
6me ANNÉE № 33

ሐሙስ ነሐሴ ፰ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም ።
JEUDI 14 AOUT 1930

ብርሃንና ሰላም

LUMIÈRE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የፍርድ ቀን።

በነሐሴ ፪ ቀን ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስለ ዝናሙ በእልፍኝ አዳራሹ ውሥጥ አስችለው ነበር። ችሎቱም ለነፍስ ገዳዮች ብቻ ነበርና የተፈረደባቸውን ሁሉ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ የሚያስፈልግ ስለሆነ እጅግ ክፉ ያደረጉትን ፪ሰዎች ጽፈንላቸዋል።

አንዱ ከወለጋ ከደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ግዛት የመጣ ስሙ ወሬሳ የሚባል ጨካኝ ሰው አቶ በኪ ለሚባል ሰው አሽከር ሁኖ ሲኖር ፩ቀን ወደ ዘመድ ቤት ተጠርቶ ሲሔድ ይኸው ወሬሳ የሚባለው አሽከር ጌታውን አቶ በኪን ተከትሎ ሒዶ ነበርና ከምግብና ከመጠጥ በኋላ ሒድና በቅሎ አምጣልኝ ቢለው አላመጣም ሲለው ጊዜ የት አባትህ ሒድና አምጣ እክ ቢለው አሽከርህ ነኝ እንጂ ባርያህ አይደለሁም ለምን አባቴን ትሰድበዋለህ ? ብሎ ጌታውን ሊገድል በጩቤ ልብሱን ቀዶት ገላጋዮች አዳኑት። በዚያም አሽከር የስካርና የቊጣ መንፈስ አድሮበት ነበርና ከገላጋዮች አንዱን በጩቤ ወግቶ ገድሎት ተይዞ መጥቶ በጃንሆይ ችሎት ቀርቦ መግደሉንም አምኖ በፍትሐነገሥት ይሙት በቃ ተፈርዶበት ሔደ።የሆዱን ልክ ለማያውቅ ሰው መጠጥ ዋና መቅሠፍቱ ነው።

ሁለተኛይቱ ማሚቴ የምትባል ሴት ባሌ ጊኒር የምትኖር ሴት ነበረች አገልጋይዋን አሥራ ደብድባ ነበረችና የማሚቴ እማትና አይቷ የአገልጋይቱን መጐዳት ስለ አወቁ እማኝ ሰብስበው ዳኛ ጨምረው ቢአሳይዋት ሌላ ሕመም የለብኝም ማሚቴ ናት የገደለችኝ ብላ ተናዛ ነበረች ማሚቴም መግደልዋን ክዳ ነበረችና ስትናዘዝ የነበሩት ሰዎች መስክረውባት ሕፃን ልጅ እዝላ ስለነበረች ልጅዋን እስከ ሦስት ዓመት አጥብታ ትሙት ተብሎ በፍትሐነገሥት ተፈረደባት።ዘመድ የለውም ብሎ በደ-ኻው የሚጨክን ሰው ብድሩን ሳይቀበል አይቀርም።ለዚች ደኻ ምንም ዘመድ አልነበራትም ነገርግን ሁሉን የሚችል አምላክ ደምዋን ሊመልስላት ባሰበ ጊዜ እማትዋንና አይቷን የባልዋን እኅት አስነሥቶ የተሸሸገው ነገር እንዲገለጽ አደረገ።ይህ ነገር አሳብ የሌላቸውን ሁሉ ያስጠነቅቃል። ልጅዋም የሁለት ዓመት ከመንፈቅ ሁኖታልና በሥር ቤት የምትቈየው የመንፈቅ ዕድሜ ብቻ ነው።

ማሳያ ።

ከሚያዝያ ጀምሮ ብዙ ጊዜ እምናትመውን ጋዜጣ ይህ የባለቤቱን ስም እማያናገር ጋዜጣ የማነው እያሉ የሚጠይቁን ብዙ ሰዎች አሉ ። አእምሮም ሁለት ሰዎች ማለፊያ ቁ ምነገር ያለበት ነገር በጥሩ አማርኛ ጽፈዋል።አንዱ አስፋው አንዳርጌ ነው። የአንዱስም አላወቅነውም ብሎጽፎ ነበር።ስም ያልተጻፈበት ጋዜጣ የጋዜጣው ዲሬክቴር ነው።ስሙ በመጀመሪያው ስለ ተጻፈ ሁለተኛ አንጽፍምና ከመጀመሪያው ተጽፎ ታገኙታላችሁ ተመልከቱ

ማኅበር ።

፩ ብልህ ሰው ያየውንና የሰማውን በርሳስ ጫጭሮ ጽፎ ሲአኑብ ሰንብቶ አሳየኝ። ብመለከተው ደስ እሚአሰኝ ነገር ስላየሁበት የንጉሥንና የመኳንንቱን ፍቅርም የሚገልጽ ስለሆነ ምንም ነገሩ የቈየ ቢሆን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ልገልጽላችሁ ወደድሁ።የሐምሌ ሥላሴ ማኅበር ከበጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ቤት ነበርና በዚሁ ቀን የሆነውን የበዓሉን አከባበር ቀድሞ እንዳስታወቅነው ነው።የቤተ ክርስ-ያን ሥርዓት ከተፈጸመ በኋላ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ወደ ጃንሆይ ቀርበው ለመሔድ ሲሰናበቱ ጃንሆይ የዘሬው ቀን ሥላሴ ወደ ባርያቸው ወደ አብርሃም ቤት የገቡበት ቀን ነውና

ከማኅበራችን እንዲገቡልን ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴን ይስጡን አሉ።በዚሁም አነጋገራቸው ጃንሆይ እጅግ ተደነቁና ትሕትና ልማድዎ ስለሆነ እሺ ብለው ልዑል አስፋ ወሰንን ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ይዘዋቸው እንዲሔዱ አዝዘውላቸው በተቀጠረው ሰዓት ወደ በጅሮንድ ፍቅሬ ሥላሴ ቤት ገብተው ከማኅበሩም በአንድነት ከተመረቁ በኋላ በሽምፓኝ ጊዜ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡ ።

ልዑል ሆይ እናንተም ወንድሞቼ ሆይ በመሀከላችሁ ቁሜ ስለ ተበረከችቱ የዛሬ ቀን የተቻለኝን ያህል እንድናገር የከበረ ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። ሊቃውንት እንደነገሩን በዛሬ ቀን ሥላሴ ወደ አብርሃም ቤት ገብተው ከባርያቸው ከአብርሃም ጋራ ተጋብዘው ተአምራት ሠርተው አብርሃምን ደስ ስለአሰኙት በመጽሐፍ ተጽፎ እስከ ዛሬ እንዲኖር ይህችም ቀን ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ወደኔ ወደ ባርያቸው ቤት ገብተው ከእናንተም ከንደኔ ከላችሁ ባሮቻቸው ጋራ በአንድነት ማኅበር ገብተው የተጋበዙባት ቀን በሰው ልብ ሁሉ ተጽፋ እማትረቅ ስለሆነች ለደስታዬ ፍጻሜ የለውም።ልዑል ሆይ በታሪክ ነገሥት እንደምናነበው የዳዊት ዙፋን ወደ ሰሎሞን የሰሎሞን ወደ ቀዳማዊ ምኒልክና ወደ ልጆቹ አልፎ ሲኖር በመካከሉ ወደ ዛጔ ዘር አልፎ ሲኖር በታደለው በይኩኖ አምላክ ጊዜ ተመልሶላችሁ ከዘራችሁ ሳይወጣ ይኖራል ። ይኸውም መደረጉ ባባቶቻችሁ ደግነት እንደሆነ አይጠረጠርም ። አሁንም ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘር የኢትዮጵያን መንግሥት አይወጣው እያልን እማይቸግረውን አምላክ እንለምናለን።ይህንም ያሰበኝ የደጉ አባትዎ የጃንሆይ ቸርነትና ትሕትና ነው ። ከዚሁም ጥቂቱን እናገራለሁ።በየስፍራው ሆፒታል (የበሽተኞች መታመሚያ) ሠርተዋል ከነዚህ ሆስፒታሎችም አንዱ ዋናው ቤተ ሣይዳ ነው ። በታመምንም ጊዜ መልክም መኝታና በዋቂዎች ሐኪሞች ያስታምሙናል ። ይልቁንም ያነን ሁሉ የሥራ ብዛት ቀምበር ተሸክመው እኛን በሽተኞችን ለመጐብኘት ወደ ሆስፒታል ይመላለሳሉ። ዛሬም ልዑል ያደረጉልን የፈቃድ ትሕትናዎ ለዘላለም የማይረሳ ነው ። ይልቁንም ከኔ ከድሀው ጐጆ በመኀብትዎ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ስለሆነ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን ለልዕልናዎ አቀርባለሁ ። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት መነን ለወንድምዎና ለእኅቶችዎ ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ኢትዮጵያን ለዘላለም ያኑርልን እያልሁ የሥላሴን ጽዋ እጠጣለሁ ብለው ሲጨርሱ ሶስት ጊዜ ተጨበጨበ ።

በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ ።

ሐውልተ ስም ዘነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ።

ስለክቡር ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ከዚህ ዓለም በሞት መለየትና የመታመን አገልግሎታቸውን ብርሃንና ሰላም በ፳፫ ቍጥር በ፪፻፳፮ ገጽ ጥቂት ብቻ ስለገለጸልን አስቀድመን የሰማነውንና ደግሞም ባይናችን ያየነውን ከብዙ በጥቂቱ ከምሉ በክፍሉ ጽፈን ለቀደመው ተከታይ ሁኖ በብርሃንና ሰላም ተገልጾ እንዲነበብ እስመ እምነ ብዙኅ ሕማም ወኀዘነ ልብ ጸሐፍኩ ዘንተ ይህንንም መጻፌ ከእንግዴህ ወዲህ ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ተመርጠው ታዘው ስለነበር የንግድ አገልግሎታቸውናን እውነተኛነታቸውን በሥራቸው ገልጸው ለሥጋ ጥቅም የሚሆን በረከት ዋጋ ያገኙበታል ። ሰዎች ይስሙት በማለት አይደለም ። ነገር ግን ሰው ሁሉ በተሰጠው ዕውቀት ለመንግሥቱ በመታመን የራሱን ለራሱ ብቻ ጥቅሙን ሳይፈልግ ቅንኡ ለእንተ ተዐቢ ጸጋ ተብሎ በተነገረው ቃል ፀንቶ ቢያገለግል መንግሥትም የእምሮውን ስፋት የሃይማኖቱን ፅናት አይቶ ቸርነቱን እያገለበትም።ይሁን እንጂ ወጥቼ ወርጄ ደጅ ጠንቼ እንደጓደኞቼ ከፍ ያለ ማዕርግ ስንኳን ባላገኝ የለት ራት አገኛለሁ፥ ወይም መታመንን ብቻ ዋና ገንዘብ አደርጋለሁ ሰዎችንም ደጅ ሳልጠና መንግሥት ድካሜን አውቆ የሚያሸኝን ይሰጠኛል ብሎ ተስፋውን በመንግሥት ላይ ቢጥል መንግሥትም አንብር ወምእመን ዘበውኁድ ምእመነ ኮንከ ዲበ ብዙኅ እሠየመከ ባእ ውስተ ፍሥሐሁ ለእግዚእከ የሚል መልክም ተስፋውን ሰጥቶ ከሚአውቀው ዓለም ወደማያውቀው ዓለም ቢሔድ ዘክርስቶስ ዘንድ የበጎ ሥራ ዋጋውን እንዳያጣ በፍጹም የታመነ ስለሆነ እውነተኛነት ላደለው በሥጋ ደግሞም ላልከፈለው በነፍስ እንዲጠቅም ካወቅን ዘንድ እውነተኛ መሆን ትልቅ ዕድል ነውና እውነተኛ በመሆን እንፅና። ከመልክም ሽቶ መልካም ስም ይሻላል የተባለው በክቡር ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ላይ ደምቆ ይኖር ነበር ። ስማቸውን የማያውቅ ሰው በኢትዮጵያ የለም ብል አያሳፍረኝም ። ሀብት ያስመሰግን ቢሆን ስንት ሰዎች በመሰገን ። ፩ኛ ቀድሞ በአፈ ንጉሥ ነሲቡ ፊት ሁነው የፍርድ ጽሕፈት ሲሠሩ ቀደም ብለው የፈረዱትን መልክም ፍርድ ጽፈው ኑሮ ቈይተው ያንኑ በመሰለ ነገር ሰዎች ተያይዘው መጥተው ላፈ ንጉሥ አመለከቱ በፍርድ ጊዜ በመዘንጋትም እንደሆነ ከፊተኛው ፍርድ ስለተለየየ ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ተነሥተው ይህ ያሁን ፍርድና ካሁን በፊት የተጻፈው ፍርድ አንድ መንገድ ነው ። አሁን ተለየየ ብለው ቢያመለክቷቸው ለጊዜው ተቈጥተው በኋላ ከቤታቸው አስጠርተው በስሕተት የሆነበትን ምክንያት አስረዳኝ ብለው ነገሩን ዘርዝረው ባስረዷቸው ጊዜ ለጊዜውም መኳንንቶች ነበሩና ገና በሕፃንነት ሳሉ ዕውቀታቸውን ገልጸው ለማክበር ሲሉ በነሱ መካከል ይህ ልጅ ሕፃን ሲሆን በነቢዩ በዳንኤል ያደረው መንፈስ ቅዱስ አድሮበት ነፍሴን ከወቀሳ እንዳዳናት ታያላችሁን? ብለው መርቀው ሙሉ ሽልማት ሸልመው በቤትም የሚረዷቸው ሰጥተው ደስ እንዳሰኝዋቸው ብዙዎች ያውቃሉ ። ፪ተኛ በ፲፱፻፳ ዓ ም በሐረር አውራጃ የመንግሥት ብረት ይቈጠር ስለተባለ በመንግሥት ትእዛዝ መጥተው የታዘዙትን ሥራ ፈጽመው በመካከል አገር በየክፍሉ ዞረው ተመልሰዋል ። ፫ተኛ፥ በኢትዮጵያ መንግሥትና በእንግሊዝ መንግሥት ጠረፍ በበረና ከመኳንንቶች ጋራ ተልከው ሒደው የተላኩበትን ጉዳይ ፈጽመው በደኅና ተመልሰዋል ። ፬ተኛ በ፲፱፻፳፱ ዓ ም በሆነው ጦርነት ምክንያት በሐረርና ባውራጃዋ ሁሉ የሚነግዱ የውጭ አገር ሰዎች ገንዘባችን ተዘርፎብናል ብለው ክሣራቸውን ከመንግሥት ስለጠየቁ ከየመንግሥታቱ ሹማምት ጋራ ሁነው ነገሩን እየመረመሩ እንዲሠሩ ክቡር ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ተመርጠው ታዘው ስለነበር የንግድ

ዕቃዎችን ማለት ገንዘባችን ጠፍቶብናል እያሉ ከመለከቱ በት ፋክቱር በውነት የጠፋውንና በሐሰት የሆነውን እየመረመሩ ሁለት ሦስት ጊዜ እያስፈረሙ ነገሩን አጣርተው ካገኙት በኋላ ዳግመኛም ከሀገር ሰዎች ነገሩን ለመረዳት ስንት ድካም እንዳገኛቸው እውነተኛ የሆነ ሰው ሁሉ ይመሰክርላቸዋል ። ነጋዴዎችም ጠፋብን ብለው ከመለከቱት ገንዘብ በብዙ ትጋትና በምርመራ ብዛት ሁለቱ እጅ ያህል ቀርቶ አንዱ እጅ ይሆናል የተገኘውና የታወቀው። በዚሁም ነገር ከውጭ አገር ሹማምቶች ጋራ ከንጉሡ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፊት ቀርበው ክርክር አድርገው ሥራቸው ስለተመሰገነ ከጃንሆይ ሰአለኒ ዘትፈቅድ የሚል ቃለ ብዕዓን አግኝተው ደስ ብሏቸው ሀገራቸውን እስሙስግነው ነበር ። ስለሀገራቸውም መድከማቸውን የሚያውቂ ሁሉ ብፁዕ ዘይሜጡ ነፍሶ ቤዛ ሀገሩ እያሉ እንዲያመሰግኗቸው ሁላችንም ተረድተነዋል። ፫ተኛ፡ በልዩ ለቆመው የፍርድ ቤት ዳኛ ሁነው ሳሉም የውጭ አገር ሰዎች ለዜጋቸው ዋስና ጠበቃ ሁነው እንደሚከራከሩ እሳቸውም ለሀገራቸው ሲከራከሩ ለኃይለ ቃላቸው ምላሴ አል ነበረውምና አንበብያን ሆይ አንከሩ ሞገስ ቃሉ ወጣዕመ ነገሩ ወሣዕማዐ አፉሁ ያለውን ንበቡን ከነምሥጢሩ ዓይን ከልብ አድርጋችሁ እንድታስቡት አስገነዝባችኋለሁ ። ፬ተኛ፡ በወሎ አውራጃ በጦር ምክንያት አገሩን ጉዳት ተሰምቶት ስለነበረ በ፲፱፻፲፰ ዓ ም ነጋድራስነት ተሾመው ሒደው ሥራውን አሻሽለው ለነጋዴዎችም የሥልጣናቸውን የማሻሻል ደምብ ሰጥተው ለቀረው ነገር ወደጃንሆይ እንዲመጡ ፈቃድ ለምነ እንዲመጡም አገር የሚጎዳበትንና ሰው የሚያዝንበትን በየክፍሉ ጽፈው ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቅርበው ላገሩና ለሕዝቡ በጣም የተስማማ ደምብ ተቀብለው በደስታ ወደተሾሙበት አገር ተመለሱ ። አመጣጣቸውም ስለ አገሩና ስለሕዝቡ ችግር ለማመልከት ነበረ እንጂ ስለራሳቸው ጥቅም አስበውት አያውቁም ። ሌሎች ሥጋውያን ደቅናና መንፈሳውያን ስንኳን ቢሆን የራሳቸውን ጥቅም ሳያስከትሉ ለሌላው ራሳቸውን አሳልፈው እንዳይሰጡ አትዘነጉትም ። ፭ተኛ፡ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ያሳሰበኝ ከቡር ነጋድራስ ኃይሉ ሹምዩ ብዙ ዕውቀት ሳላቸው ዕውቀቱን ሰው ይወቅልኝ ብለው ራሳቸውን ከፍ ከፍ በማድረግ ከሆን ጀምሮ ውዳሴ ከንቱ አልተቃወማቸውም።ነገር ግን ዘነገርኩክሙ በጽልመት ንግሮዎ በብርሃን ወዘሂ እልኖሰስኩ ውስተ እዝኒክሙ ስብክዎ በዲበ አንሕስት ይላልና በዠሮዬ ሰምቼ ባይኔ አይቼ የተረዳሁትን ሳልገልጸው ብቀር ሕሊናዬ ይወቅሰኛል ብዬ ነው እንጂ እሳቸውስ እውነተኛውን የክርስቶስን መንገድ ተከትለው ለመንግሥትም ላገራቸውም እምነታቸውን አስመስክረው በድረየኒ ፈጸምኩ ወሃይማኖትየኒ ዐቀብኩ እንከሰ ጽኑሕ ሊተ አክሊል ዘየአስየኒ መኰንን ጽድቅ ብለው ከሚያልፈው ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ሒደዋል ። ሕይወትም ሞትም በክርስቶስ እጅ ነውና እንግዲህ ምን እንላለን። የሰውም ዕውቀቱና አገልግሎቱ ከመቃብር በአፍአ ሁኖ ሽማግሌዎች አባትና እናታውቸን አደዚችሁ እኔ አለኋችሁ ብሎ የሚያፅናናቸው በሆነ ያፅቀብ በብዙ ዘመን የልጁ የሴፍን ሕያውነት ሰምቶ ልጁን ለማየት በናፍቆት ተይዞ ነበርና እንደተበረታታ ሽማግሌዎቹም በተበረታቱና በተፅናኑ ነበር ። ነገር ግን ሰው ከዕውቀቱ፡ ዕውቀቱም ከሰው በሞት ጊዜ ይለያል የሚለውን ፅኑ ቃል በምን ይተላለፉዋል ። ይሁን እንጂ መልከም ልጅ አባት እናቱን በሕይወትም ሳለ ከሞተም በኋላ አገልግሎቱን አይተውም ። እንዲህም ማለት እምነቱ፣ አገልግሎቱ ለመንግሥትና ለሀገር የሆነ ሁሉ በሕይወቱ ካለ ዘንድ ላባት ለናቱ ለልጆቹም አይዙዋችሁ ይላቸው እንደነበረ በሞተም ጊዜ እናት አባቱን ልጆቹን ለመንግሥት አደራ አስጠብቋልና መንግሥትም አደራውን ተቀብሎ የሚያፅናና ተስፋውን እንደሰጣቸው በፍጹም እናምናለን።

አክሊለ ደጀን ሐረር ።

ስለ መንግሥት ገቢ ገንዘብ

የመንግሥት ገቢ ገንዘብ ማለት ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው።የመንግሥት ገንዘብ ሲወጣም ሲገባም በመዝገብ ካል ተጻፈና ሠራተኛ ካልቆመበት እንዲጠፋ ሌባም እንዲሰርቀው የታወቀ ነው።ስለዚህ በመንፈሳዊ ትምርትም ቢሆን በሥጋዊ ትምርትም ቢሆን ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ተምረው ሲመጡ የሚቀበሏቸው ሁለት ሰዎች መርጦ ማቆም ያስፈልጋል።ለሥጋዊው ሥጋዊ ትህምርት የተማረ፡ለመንፈሳዊው መንፈሳዊ ትምህርት የተመረ ፡ ዕውቀታችንን ለመንግሥት ንገሩልን ሲሉ የሚነግርላቸው በማጣት እንዱን በለሜል ተከትለው በባቡር መንገድ አግራቸው እስቲነቃ ድረስ የሚሮጡ፥ሩጠውም የማይጠቀመሙ ስንት ሰዎች ይመስሏችኋል? ። ደግሞም ይህን የሚያስረዳ ምሳሌ እጽፋለሁ።ልጃ ገረድ ሴት ምንም ሙልከ መልክምና ባለሚያ ብትሆን በጕረቤት ያለ ሰው ሞያዋን አይቶ ለደገና ባል ካላሜትና ካላስማማት ራሷ ባለሞያ ነኝና አግቡኝ ለማለት ኃፍረቷ ነው ክብር አይሆናትም።እንደዚሁም ዕውቀት ያለው ሰው በመሮጥና ጉብ በመስጠት ሥራ ቢያገኝ ክብሩ አይደለምና ሰብሳቢና ተቀባይ ቢያገኝ ዕውቀት ያለው ሰው ሁሉ እየበዛ እንዲሔድ እርግጥ ነው። እንዲህማ ቢሆን ስንቱ ሰው አዋቂ በሆነ ነበር ። እኒያም ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች ለመቀበል የተሾሙ የሚበቃ ያህል ገንዘብ ተመንግሥት ተቀብለው ዕውቀት ያለውን ሰው ለመንግሥት እስኪአገናኙት ድረስ ተበሳጭቶ እንዳይሔድ በጥቂት ቀለብ ማቈየት ያስፈልጋቸዋል ። መንግሥት የዚያን ሰው ዕውቀት ካየ በኋላ እንደ ዕውቀቱ መጠን የሚበቃ ቀለብ ሰጥቶ በሥራ ላይ ያቆመዋል። እንዲህ የሆነ እንደሆነ በየሥራው ላይ የተሾሙ ሚኒስቴሮች ከኒያ ከሁለት ሰዎች ዘንድ እየላኩ ለየሥራቸው የሚአስፈልጋቸውን ዕውቀት ያለውን ሠራተኛ ይቀበላሉ ይህም ሊታወቅ በአውሮፓ ለሥራ የሚመረጥ ሰው ሁሉ ከተ ማሪ ቤት ነው ሲሉ እንሰማለን። እንዳለፈው ዘመናችን ሰው ሁሉ በወገኑና በወዳጁ መመረጡ ቀርቶ በሥራውና በዕውቀቱ እንዲመረጥ ከዛሬ ጀምሮ ተስፋ አለን ፡ ይህ ሁሉ ተስፋ በላያቸው ላለ ለንጉሣችን ዘመን አብዝቶ ወራት አስፍቶ ይሰጥልን

የእስጢፋኖሱ አለቃ ቀጸላ ።

ባሕርይን መርምሮ የማይገባ ልማድን ለመተው እንዲገባ ።

ማቴዎስ ም ፲፭ ቍ ፲፩ ሰውን የሚጐዳው ከወደ አፉ የሚወጣ ነው እንጂ ወደ አፉ የሚገባ አይደለም ብሏል።ያዕቅብም ምዕራፍ ፫ ቍጥር ፯ ወልሳንኒ እሳት ይእቲ ለዓለም ዘዓመፃ ወናሁ ልሳንኒ ንስቲት ፍጥረት ዘውስተ ነፍስትነ ወቃረምያ ለሥጋነ ወትለሉ ክበተ ፍጥረትነ ወቃውዲ እምገሃነም እስ ። ሐዋርያው ጳውሎስም በኤፌሶን መልእክቱ ም ፬ ቍ ፳፱ ወኵሉ ነገር ሕሱም ኢይፃእ እምአፉክሙ ዘእንበለ ሠናይ በዘይትሐነፅ ቢጽክሙ ወከመ ይርከቡ ሞገሰ እለ ይሰምዑክሙ ወኵሎ መሪረ ወቍጥዓ ወዕርፍተ አእትቱ እምላዕሌክሙ ብሏል። እነዚህ የታመኑትን ሦስት ምስክሮች ከስመሰክርሁ በኋላ የገዛ ሕዋሳቶቼን ለመውቀስ ሐሳቤ ሆነ።የመብልን ምረት የምናውቀው በምላሳችን ነው የነገርን ምረት የምናውቀው በጆሯችን ነው ምላስ ደህ የማይረባ መሬር ነገሩን ለአፍአዊት ጆሮ ባትሰጣት አፍአዊት ጆሮም ለውሣጣዊት ጆሮ ባትሰጣት ውሣጣዊት ጆሮም ይህ ከአፍአዊት ጆሮ የተባለችው መሬር ነገር የማይረባና የማይጠቅም ገንዘብ መሆኑን ስታውቀው ቢሻው በስብሰም ቢቀር ባይሆን ባደራ ምክንያት ከብረት ሣጥን ልቡናዋ ውሥጥ ከታማናቸውም ዓይነት ቍልፍ ቢመጣ በማይፈታው ሰምቶ መቻል በሚባል ቍልፏ ቈልፋ ማስቀመጧን ትታ ላልሰማ ጆሮና ለሕዋሳት ሁሉ አዛምታ በዚህ በማይረባ ገንዘብ ዘመዶችዋ የሚሆኑ ሕዋሳትን ሁሉ በቃፋጃቸው ሰውመላው ዕድሜውን በጤና ይኖር ነበር።አብሰ ምላስማ ዘትጸልእ ለርእስከ ኢትግበር ዲበ ቢጽከ የሚለውን ቃል ሠርክ ስታላምጠው ስትኖር አንድ ቀን ስንኳ ጣዕሙን ሳታውቀው ትኖራለች ያለማወቋም የሚያስረዳ ሌላውስ ደቅርና ለገዛ ራሷ ሕይወት የሚሆናትን እንደ መራር መድኃኒት ያቀመስዋት እንደሆን ከእሳት ውሥጥ እንደገባ ፲ማት ተኰማትራ ልሙት ትላለች ። ከሷ የሚመጣው ምሬት ግን መላው ሕዋሳትን አስከሮ ወንድምና ወንድምን እያጋደለ ዓለሙን ሁሉ ለማጥፋት እንደገሰገሰ አለ ። ይኸውም የማይገባ ልማድ መተው እንዲገባ ለመጻፍ ያነሣሣኝ የኢትዮጵያ መዲና በምትሆን በአዲስ አበባ ላይ አንድ መሪር ነገር ስለሰማሁ ነው፣ ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈ ነው ከጉምሩክ ሥራ ጀምሮ የዓለምን ሥራ ሁሉ በየዓይነቱ ለማቀላጠፍና ሠርቶ ለመብላት ስለሚሽከሙ ሕዝቦች ለሰው የግብር ስም እንዳለው እያወቁ በሚሠሩበት ተሸካሚ)ሐማል)ወይም ሥራ ፈላጊ ብለው መጥራታቸውን ትተው ልጁም አዋቂውም ከባቡር መንገድ ዳር እየሆኑ ጕራጌጕራጌእያሉ በስመ ውላጤ ሲጠሯቸው እየሰማሁ በጣም ሲገርመኝ ደኖራል። ከጕራጌ አገር የተወለዱ ምርጥ ምርጥ ሰዎች መንግሥት አምኖ የሾማቸው በመንፈሳዊና በሥጋዊ ሥራ በኩል ከፍ ከፍ ካለው ደረጃ ላይ የተቀመጡ እነዚህን ሁሉ በድፍረት አጋገርነት ኑተሸከሙ ማለት መሆኑን ለጠሪዎች ማን ባስረዳልን ይሆን?ያውስ ቢሆን ከህገሬ ሠርቼ እበላለሁ ያለ ሕዝብ ሲሸከምና ሠርቶ ሲበላ እናያለን እንጂ ጕራጌ አገሩ መጥቶ ሲሸከም አላየንም አሁን ሸዋ ተሸካሚ ትግሬ ተሸካሚ ጐንደሬ ተሸካሚ ጐጃም ተሸካሚ ብሎ መጥራት አገባብ ይሆናልን ሲጠሯቸውም ሠርቶ እንደሚበላ ሕዝብና በአርአያ ሥላሴ እንደተፈጠረ ሰው አጠራር ልክ አይጠሯቸውም እንደ ውሻ አጠራር ዓይነት በቃለ አግሥሮ ጕራጌ ጕራጌ እያሉ ነው የሚጠሯቸው - ምንም መርገምና ኪዳን የተቀላቀለበት ቃል ቢሆን ባለቤቱ ለአዳም ብላዕ በአፈ ገጽከ ብሎ የሰጠውን ውል ለጊዜው ይዘው የተገኙ እነዚህ የመንግሥታቸውን ሥራ ለማቀላጠፍና ሠርቶ ለመብላት የሚሸከሙና በማናቸውም ዓይነት ሥራ ክፍል በሞያና በደሞዝ የሚሠሩ ሕዝቦች ብቻ ናቸውየሚመስለኝ ፡ በጣሙ የሚገርመኝ አንዳንዱ ሥራ ፈት ሕዝብም ምንም ሥራ ሳይኖረው በዚሁ በተለመደው ስም ሲጠራው ሥራ ፈላጊው ሕዝብ እውነት መስሎት አምጣ ሥራ እንከ ሥራ ሊለው)ስጣዊ)ሥራ ፈቱ ሕዝብ ሞኝ ነህ መሰለኝ ማን ነው የጠራህ ብሎ በዚሁ በመሪር ቃሉ ሲሸኘው ስለሰማሁ ነው ፤ ይህም ክፉ ልማድ በልጁም በአዋቂውም አፍ ከመዘውተሩ የተነሣ ያዲስ አበባ ሕፃናት አበ እመ እደማለት ሁሉ ጕራጌ ጕራጌ በማለት ነው አፋቸውን የሚፈቱ፤እንደ ዘንድሮ ሥራ አበዛዝ እነዚህን የመሰሉ ሥራ ፈላጊዎችና ሁለት ገባያ የሚገበዩ ሕዝቦች ባይኖሩ ሥራውን ሁሉ እንዲያው ለይኩን ቢሉት በቀጥታ የሚኪያሔድ ኑሮ ይመስላችኋልን፤ ያለፈውስ አለፈ ዛሬ በዕድለኛይቱ ዘመን ሰላማዊ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አገራቸውን ለማስፋትና ሕዝባቸውን ከግብርናት ነፃ ለማውጣት ታጥቀው በተነሡበት ጊዜ ነፃነትንና ሥራ ፈላጊዎች ሕዝቦቻቸው የዕድል መሣሪያቸውን ይዘው ሲከተሏቸው በስንፍናም ሁኖ በሌላ ወደኋላ ተለይተው የሚቀሩ ሕዝቦች ወዮላቸው ማቴዎስ ። ምዕራፍ ፳፭ ከ፴ እስከ ፲፫ቍ በኃምስ አብዳት ላይ የወደቀ ጨለማ እንዳያገኛቸው በጣም ያስፈራቸዋል ። ደህነን ሠርቶ የሚበላውን ሕዝብ በቃለ አግሥሮ ከሚጠሩት ሕዝቦች አንዳንድ ሰዎች እርም ነው የሰው ሥጋ የምትለውን የመሐላ ቃል ሁለጊዜ ከፋቸው አይለይዋትም።አንዱ ወዙን እንጠፍጥፎ ጕልበቱን አፍሶ ደክሞ ያመጣውን ገንዘብ አንዱ ጕልበት እያለው ሳይሠራ ቍጭብሎ መብላት ደህ ያለጥርጥር እርም ያለውን የሰውን ሥጋ መብላት መሆኑን አሁንም ያልተረዱት ይሆን? ምናልባት ይህን ነገር መላልሼ ስለጻፍሁ የነገሩን ስልት ያልመረመሩ ፩፱ሰዎች ወይም ሥራ ፈትዎች ለኢትዮጵያ ተቈርቋሪ መስሎ ይህን ጊዜ ያንዱ ጕራጌ ልጅ ይሆናል በማለት በደነዝ ቢላዋ ሐሜት ይገዘግዙኝ ይሆናል ። መቸውንም ባንዲራሙ ፩የሆነ ሕዝብ ከንዲት እናት ስለተወለዱ ቍጥር ነውና በጠበቡ እውቀቴና ባጭሩ ዓቅሜ ስለ ባዲንራዩ ወተወትሁ እንጂ ከኢትዮጵያስ ውሥጥ የኔ አገርና ጕርጌ አገር በስንት ክፍል እንደሚራራቅ ከስሜ ቀጥሎ ደገኛል። ይህም ክፉ ልማድ በበጎ ልማድ እንዲቃደስ ማስገደድ ለሚቻላቸውና መንግሥት አምኖ ልዩ ሥልጣን ለሰጣቸው ክቡራን ሹሞች በማክበር አስታውሳቸዋለሁ።ጸጋየ ተክለ ሃይማኖት ዘእምብሔረ ትግሬ መቀሌ።

የምኞትን ነገር አንድ ጊዜ ልናገር ።

(ምሳሌ) መልእክት ወደጌትነት ።

ይድረስ ከክቡር አቶ ጌትነት ያቶ ሹመት እንደራሴ እጫማዎ ወድቄ ለማዕርግዎ የቀገባ ሰላምታ አቀርባለሁ ።

እንደምን ሰንብተዋል እኔ ግን ወደርስዎ ለመምጣት ሳስብ ምኞት የሚባል በሽታ በሆዴ አድሮ በልቤ እየወጣ እየወረደ ሆዴንም እየጐረበጠ አሞኝ ስለሰነበተ ቀረሁ ። እኔም ምናልባት ማጣት የሚባለው የኮሶ ቀኔ ደርሶ እንደሆነ ብዬ ሐሳብ የሚባለውን ኮሶ ብጠጣው እጅግ አንገፈገፈኝ። ከምረቱም የተነሣ እንጀቴን ቄርጦ ጥሎኝ ሌሊቱን ሁሉ እሀ፡ሲአሰኘኝ ሰነበተ፡ በዚያውም ላይ የተሻለኝ መስሎኝ ማግኘት ወደሚባለው ሽንን ብቅ አላለሁ ስል ድኽነት የሚባለው ምች እንደገና አጨናፍሮ ጥሎኝ ግርሻው ፀንቶብኝ ሰነበተ ። ዶክተር ረኃብ የሚባሉትም ሐኪም መጥተው ሆዴንና የቀረውንም ሰውነቴን ሁሉ መርምረው አይተው ሥጋህ ገዝፏል ደምህ አድፏል ብለው ክሳት በሚባለው መርፌ ወግተው እንጀራና ሥጋ ጠጅና ጠላ እንዳልቀምስ ከልክለውኝ ሔዱ ። እኔም ንዴት የሚባለው በሽታ ሣል ተክሎብኝ ስለሔደ ብስጭት የሚባለውን መራራ ቅቤ በባዶ ሆዴ ብጠጣበት አንገቴ ተገሰፈሰፈ። አሁንም ጌታዬ ሆይ ይኸው የያዘኝ በሽታ ለሞት ሳያደርሰኝ አንድ ጊዜ ጽጋብ የሚባለውን ሐኪም ይዘው በክብት እግር ጋልበው መጥተው ጐብኝተውኝ እንዲሔዱ የማያልቅ ቸርነትዎን እለምናለሁ ። ይኸንም ማለቴ ቢጨንቀኝ ነው እንጂ ይህ ጽጋብ የሚባለው ሐኪም በዚህ በደከመ ሰውነቴ ላይ ኵራት የሚባለውን መድኃኒት ያቀመሰኝ እንደሆነ እንደገና ትዕቢት የሚባለውን ውጋት ያስነሣብኝና ሰውነቴን ወጥሮ ነፍሴን ከሥጋዬ (ማለት ከፈጣሪዬ) አለያይቶ እንዲገድለኝ አጥቼው አይደለም።ነገር ግን ይኸው ድኽነት የሚባለው በሽታ ሀብት የሚባለውን እግሬን አስነክሶ ከሰሙ በታች አርጎኝ ከምኖር ይኸው ጽጋብ የሚባለው ሐኪም ኵራት የሚባለውን መድኃኒት አቅምሶኝ አንድ ሰሞን እንደሰው ሁኜ እንደልቤ ረግጬ ከዚያ በኋላ የፈቀደው ይሁን ብዬ ነው ። ትዕቢት የሚባለውንም ውጋት ቢአስነሣብኝ ትሕትና የሚባለው ወጌሻ ወዳጄ ነውና ፍቅር በሚባለው ዋገምቱ እያገመ ነቅሎ ይጥልልኛል አሁንም ክቡር ሆይ የልቤን ሁሉ እንዳልጽፍልዎ ይበዛና ከመሰልቸት የተነሣ ሳይመለከቱልኝ እንዳይቀሩ ይህችኑ አጭር ቃል ከሥር እስከ ሚፍ ልብ አርገው ተመልክተው የሚሻለውን ነገር እንዲያደርጉልኝ በማክበር አመለክታለሁ ። በደኅና ያገናኘን አይርሱኝ ። ትስብእተ ወልድ አግዴ ፍ ጸ ።

ስለ አፈርሳታ ።

በዚሁ ባለፈው ወራት የድንገተኛውን ዘመቻ ወሬና የሌላውንም ወሬ ብርሃንና ሰላም ብለው ደጉ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ በሰየሙት ጋዜጣ የሚመነጨውን የምክር ቃል በከምባታ ክፍል በሆሣዕና ከተማ የሚኖር ብዙ የተማረ ሰው በያመቱ የሚከፍለውን የጋዜጣውን ዋጋ አምስቱን ብር እንደከፈለ ልክ ሁኖ ጋዜጣውን ከቶ ፍሥሐ ወደሚካኤል እጅ እየወሰደ የምክሩን ቃል ሲሰማ ሲረዳ ከረመ ።

እኔም እንደዚሁ ጋዜጣ መጣላቸው የሚል ወሬ በሰማሁ ልክ ራሴ ሐጄ ወይንም ልጅ ልኬ ጋዜጣውን እያስመጣሁ ከማንበብና ከመረዳት አልቦልዘንሁም። ጋዜጣውንም አንብቤ ምክሩን በተረዳሁኝ ልክ እንደቀደሙት አባቶቼ ይህን የመሳሰለውን የብርሃን ልጆች ቃል ሳያዩ ሳይሰሙ እንደሞቱት ያላደረግኸኝ የጕልምስናዬ ዘመንም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንግሥ ዘመን ያደረግህልኝ አምላክ ክብርና ምስጋና ዘወትር ሳላቋርጥ አቀርብልህ ዘንድ ይገባኛል ብዬ ፈጣሪዬን ከማመስገን ቸል አላልሁም።

አሁንም ከዚሁ ሰዓት ላደረሰኝ አምላክና ይህኑ ብርሃን ለገለጹልን ላገራችንም ኢትዮጵያ የውቀት መሪ እንዲሆኑ ከሠራዊት ጌታ ለተመረጡ ለንጉሣችን የሚገባ ምስጋና ከማቅረብ አላቋርጥም ።

ደህነንም ብርሃን በየጊዜው የሚገባውን ገንዘብ ከፍለው እያስመጡ ራሱ አንብቦ ለማይረዳ ራሳቸው አንብበው አንብቦ ለሚረዳም በጄ ሰጥተው ስብከቱን ለሚያሰሙ ለኔም በተለየ እቤቴ ድረስ እየላኩ እውነተኛውን ምክር ለመረዳት ምክንያት ለሆኑኝ ላቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል የሚገባቸውን ምስጋና አቀርብላቸዋለሁ።አሁንም ከዚህ በታች ምንም እጅግ የተማርሁ ባልሆን የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም የሚሉትን ተረት ይዤ አጭር ቃል እጽፋለሁ ።

እንደዚሁ ሁሉ ይህነን ጋዜጣ ባስፈለገኝ ጊዜ ከቤቴ ድረስ እየወሰድሁ ስመለከት ሚያዝያ ፳፫ ቀን በቍጥር ፲፰ አቶ ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ስላፈርሳታ ነገር የጻፉትን አይቼ እጅግ ደስ አለኝ ማለት በዚህ ባለነው አገር ያፍርሳታ ሥራ ዓሥራ አምስት የሚሆኑ ሰዎች ብቻ ሲጠቀሙበት ከ፲፱፻፳ የሚበልጥ ገባር ሲጐዳበት የሚኖር ነውና እንዲህ በብርሃን ከተጻፈ ወደመንግሥት ጆሮ ደርሶልን ተንግዲህ ወዲህ ሥራውን እንደንግድ መሆኑ ቀርቶ በውነት ይሠራልናል በማለት ነው።ያፈርሳታ ሥራ ጥፋት በውነቱ ሞልቼ አስፍቼ እንዳልጽፈው ሆዴን ፍራት ፍራት ብሎኛልና እንዲያው ጀምሬ ደስታዬን ገልጨ አተወዋለሁ ማለት አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል ሦስት ዓመት ሙሉ ከምባታ ሆሣዕና ከተማ ሲቀመጡ ትልቁን ጌታዬ አባቴ ብለው እጅ ነሥተው ትንሹንም ወንድሚ ብለው ሰላምታ ሰጥተው ከማለፍ በፍቅር ቃል ከመነጋገር በቀር ካንድ ሰው ተጣልተው አዳኛ ፊት ተቋቍመው አይተናቸው አናውቅም ነበር።ይህነንም ውሸት እንዳይባል ሌላው ሰው ቀርቶ ትልልቆቹ ማለት ዳኞቹ ይመስክሩላቸዋል ።

ስለሆነ ግን ለደኻ ኀዘኔታ ሲሉ በዳር አገር በኵል በከምባታ ክፍል የሚሠራውን ያፈርሳታ ሥራ ሳይሰፋ በጠባቡ ውሸት ያይደለ በውነቱ ጥፋቱን ገልጠው በጋዜጣ ጽፈው ነበርና ጋዜጣው ታትሞ በተነበበ ወር ሳይሞላው ላረቂ ሥራ የጽሬሕት ቤት ለራሳቸውም መኖርያ ያሠሩትን ቤት በውሥጡ ተኝተው ሳለ ከሌሊቱ በሰባት ሰዓት ተኵል እሳት ተቃጠለባቸው ከቃጠሎውም ሰውና ከብት ወጣላቸው እንጂ ገንዘብና ዕቃ አልቀረላቸውም።ስለዚህ እኔም ፍራት ፍራት ይለኛል ያሰኘኝ ይህ ነው ስል ጀምሬን አተዋለሁ፡ተሰማ ይማም።ብሔረ ጐጃም።

የፍከራ ትርጓሜ ።

ብርሃንና ሰላም ፮ኛ ዓመት ቍጥር ፳፱ ስለ ፍከራና ስለ መቀዳደም የመሰለኝን ጽፌን እንድንገልጽ አመለከትን ስለዚሁም እኔ የመሰለኝንና ከረብኛም መጽሐፍ እንደ ተመለከትሁት የሚከተለውን ስለ ፍከራ ላንባቢዎች እገልጻለሁ ።

ብርሃንና ሰላም በመጀመሪያው ቃሉ አማርኛ ከግዕዝ የተገኘ ነው ብሏልና ፍከራ ባነጋገር ፈክርን መስሎ ቢያገኘው ከዚያው የወጣ ነው አለ። ይህ ም መልክም ምርመራ ነው የሚከፋ አይደለም ። ስለ ሆነ ግን ፍከራ ከረብኛ የሐዶ ራሱን የቻለ ቋንቋ ነው እንጂ ፈከረ ካለው ከግዕዝ ቋንቋ የወጣ አይደለም። በረብኛ ፈከረ ማለት ከን በትናግ አናግር (እንደ ትግርኛ ኸ ተመከ ታበየ ማለት ነው።ጥሬ ሲሆን ፋክር ይላል ። በረቡ ትምክሕት ሲል ሊአናሁ ኢን ከነ ኢብራሂም ቃድ ተበረረ ቢልአዕማል ፋክር ይላል ። ይህም አብርሃምንስ በምግባሩ ቢጸድቅ ትምክሕት አለው ማለት ነው።ሮሜ ፬ ፪ ። ታበየ ሲል ፋላ ትፈኪር ዐለ እሌ አቋጿን ይላል። ይህም በሚሬች ላይ አትኵራ (አትታበይ) ማለት ነው።ሮሜ ፲፩ ፲፰ የከን ድምፅ ግን ከላይኛው መስመር እንደ ተናገርሁት ያረብ ፊደሎች ድምፃቸው የሚያስቸግር ስለ ሆነ በዚህ ምክንያት ከፈከረ ተረጕመ ጋራ ተመሳሰሉ በገራችንም ቸጋራው ያረቡ ፊደል ይቅርና ቀናውን ያገራችንን ፊደል እያለዋወጡ ኃይሉ በማለት ፈንታ ከይሉ ሀብታም በማለት ፈንታ ከብታም እያሉ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች አሉ።ይህ ግን ደግ አይደለም ሲለምድ በቀን ብዛት እንደዚሁ ሁኖ ይቀርና የጥንቱን ቋንቋ ያጠፈዋል ። በዚሁ አካሔድ የፍከራ ትርጓሜ ለኔ እንደ መሰለኝና እንደ ተረዳሁት እንደ ዓረብኛው ይመስለኛል፤ ማለት ፍከራ ምንም ባገራችን የቈየ ልማድና የጀግኖች ሥራ ቢሆን ሰው የራሱን ሚያና ዕውቀት የገዛ ራሱ ሲናገረው ትምሕቱኛ ትዕቢተኛ መባሉ ርግጥ ነው ። እስከዚህ ድረስ ስለ ፍከራ የመሰለኝን ተናገርሁ ስለ መቀዳደም ግን ከጥንት የቈየ ጒግስ የተባለ መልካም ስም አለው ስለዚህ በጒግስ ጨዋታ ጊዜ የአገሉ ፈረስ ቀደመ ቢሉት አይከፋም ይመስለኛል።አባ ተወልደ መድኅን።

ስለ ሀገር ፍቅርና ስለ ርዳታ

በብርሃንና ሰላም በቍጥር ፳፱ ሐምሌ ፲ቀን አቶ በቀለ አበዩ ስለ ብድር የጻፉት ቃል ለሀገራቸውና ለመንግሥታችን ፍቅር ሲሉ እንደሆነ ነገሩን ከተረዳሁት በኋላ በልብዬ የሚወጣ የሚወርደውን ለመጻፍ መነሣሳት አነሣሣኝ ። አረግ ቢሳብ ዱር ይሰበሰብ እንዲሉ በኢትዮጵያ ውሥጥ ያለ ሕዝብ ቍጥሩ ምን ያህል ሚልዮን ነው ።መንግሥት ለሀገሩና ለሕዝቡ ሲዕር ሕዝቡ ለመንግሥቱና ለሀገሩ አለመፃሩ ስለ ምን ይሆን በጥቂቱ ግምት አምስት አምስት ብር ቢያወጣ በሀገራችን ላይ ምንም ችግር ነገር እንዳይመጣ ያለጥርጥር ርግጥ የታወቀ ነው ። ይህንንስ መንግሥት እስቦ ለሚያቆመው ሥራ ሁሉ ፈጽሞ በይደራጅለት ለመንግሥታቸውና ለሀገራቸው ሲሉ ዕለት ዕለት ደማቸውን የሚያፈሱላት መኳንንቱ ዓርበኞች ሠራዊት ካህናትም ምን አገር አለን ይላሉ ።

በትግሬ፥በበጌ ምድር፥በጐጃም፥በጐንደር፥በሸዋ፥በሐረር በደጋውም፥በቈላውም ስንት ዓይንትከብት አለ፥ከብት እያረባ መሬት እያረሰ ባለጸጋ ሁኖ የሚኖር ስንት መኳንንት ስንት ከሀናት ስንት ሠራዊት አለ ። የፈረስ የባዝራ ወላድ፥የግመል ወላድ፥የአህያ ወላድ፥የላም ወላድ፥የበግ የፍየል ወላድ፥ይህን ሁሉ ከብት አርብቶ የሚኖር አማራና ጋላ(ቆ ፑ)ከረዩ፥አዳል፥ሱማሌ፥ውጋዴ፥ሲዳሞ፥ወላሞ፥ ውራጌ፥ በቦረና በበረዳ በየሀገሩ አውራጃ ሁሉ የሚኖር ሕዝብ ሁሉ ከከብቱም ከወርቁም ከብሩም ደክሞ ከሚያገኘው ገንዘብ ሁሉ ይህ ለመንግሥት ርዳታ ይሁን እያለ ዓሥራት ቢያወጣ መንግሥት በሚሠራው ሥራ ሁሉ ሕዝቡን ፈጽሞ ደስ ለማሰኘት በተቻላቸው ነበር ።

በውጭ ሀገር ያለ የብርሴ ብርጭቆ፥ የብር የወርቅ፥የመዳብ የነሐስ ያማረ ያማረ ልብስ፥ወርቅ ዘቦ፥ዓብደላ ከኒ፥ቍፍጣን ይህን የመሰለ ያመረ ልብስና መጫሪያ ጌጥ ሁሉ በየዓይነቱ የሚሠሩልን መኪና ለማምጣት ትንሽ ቀን ቢያስፈልገው በሀገራችን ላይ በምሥራቅ፥በምዕራብ፥ በሰሜን፥በደቡብ፥ ባራት ማእዝን መንገድ እየሠራ ለጥዋት ለማታ መመላለስ ከተመቸ በኋላ ሥጋ ማር መብላት፥ቅቤ መጠጣት፥ እህል ዳውል ዳውላ በሩብ በአላድ መሸመት ፥ በበቶቻችን ጊዜ ነበር እንጂ ዛሬማ እህል በሰው ሊለወጥ ጥቂት ቀርቶታል እያሉ ከማማትና የሰውን ጊዜ ከመንቀፍ ለአውቶሞቢልና ለካሚዮን ለጋሪና ለበቅር ። መንገድ ከተሠራ በኋላ ይህ ሁሉ ቀርቶ ሰው ሁሉ በደስታ እንዲኖር በርግጥ የታወቀ ነው ። እኔ ይህንን ቃል መጻፌ ነገሩን አቶ በቀለ ከነቃቁት ብዬ ነው እንጂ ዕውቀት አለኝ ከሰው አማርኛ የኔ ይበልጣል ብዬ አይደለም። አሁንም እኔ ደኻ ነኝ ብሰጥስ ማን ያውቅልኛል እኔ ብዙ ገንዘብ ቢኖረኝ ከሞትኩ በኋላ ልጆቼ እንደምን ይሆናሉ አባት ያበጀው ለልጅ ይቈየው እንዲሉ እያለ ሰው ሁሉ ስንፍና እንዳይገባው መንግሥት የእግዚአብሔር ወኪል ነው እንደናት እንዳባት እንደ ፈጣሪ ሁኖ ልጅ ማሳደጉን እንደልጅ ሁኖ ሽማግሌን መጦሩን ማመልከቴነው።ያውም በሀገሩ ጥቃት ሳይነካው ውርደት ሳያገኘው እንደኵራ እንደ ተከበረ መኖሩን በትንሽዋ ዕውቀቴ አሳስባችኋለሁ ። ክቡር አቶ በቀለ እንዲህ ያለውን ምክር ስለ አበደሩን ምስጋና አቀርባለሁ ። ለኢትዮጵያ መምህር ብርሃንና ሰላም ሰላምታ አቀርባለሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ማተሚያ ቤት ሠራተኛ ።

ኃይሉ ዘሙገ ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ድርሳነ ሚከኤል የምትገዙ ሰዎች በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት በጥንቃቄ ታርሞ ታትሚልና እየመጣችሁ ግዙ ።

ዋጋውም
- ፩ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፲ብር ነው
- ፪ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፯ብር ነው
- ፫ኛ ጥራዝ ፩መጽሐፍ ፮ብር ነው

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፊልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ፤ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

ቡበላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በቃመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኑኩሉ።





Borsalino

አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ መጭ በኢትዮጵያና በፈረን ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።

የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

S. F. FERNANDES&SONS,

ፕር ዳኔዶ።
አ በ ከ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ጴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC SdEaA METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
6me ANNÉE № 34

ሐሙስ ነሐሴ ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓም።
JEUDI 21 AOUT 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግዛታቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ደረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመጨከን ሥራ ።

በአዲስ አበባ ብዙ ጊዜ የሚነሣው ጠብ በመሸታ ምክንያት ነው ። አሁንም በቅርቡ ጊዜ በዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አንድ ሰው ሚስቱን ገድሎ ተያዘ አሉ። በዚህ በመሸታ ነገር የጨዋነት አሳብ ያላቸው ሁሉ እጅግ ያዝናሉ ። ማዘናቸውም ከሎሌ፡ከገረድ፡ ከልጅ፡ ከሚስት የለየውን ሰው እያዩ ነው ። አንዳንድ ሰው ማዕርጉን፡ ሚስቱን ፡ ሎሌውን፡ ገረዱን ትቶ ርስቱን እየሸጠ በመሸቻ ገንዘቡን ጨርሶ እንደ ዕብድ እሚንቀዋለል አለ። በአገር ቤት የሚኖር ሰው ሁሉ ሠርቶ ነውና የሚበላው አሁን ትንሽ ማር በብዙ ውኃ በጥብጦ አዲስ አበባ ብዙ ገንዘብ ይገኛል ሲባል ጊዜ ሴት ሁሉ ባል አገርዋን ትታ ወደ ከተማ መጣች።ትውልድም ሊአንስ ነው። ጠጁም በየመኳንንቱ ቤት አምሮ ይጠጣ የነበረው ቀርቶ በየመሸታው ቤት ሳያምርበት በከንቱ አለቀ ። ወዳጆቼ ይህን ጊዜ ከሩቅ አገር የመጣ ሰው ምን ይጠጣ እንዳዳስ ቢመጣብን በምን እንሸኘው፡ ልጅስ በከተማ መሸታ ሽጣ ቃልበላች በምን ትደር ደሉ ይሆናል ። ነገር ግን ይህ ሁሉ የሚበቃ ምክንያት አይደለም ። ከሩቅ አገር የመጣውንም ሰው ከጥንቱም የሚመጣበት ምክንያት ወይ በነገር፥ ወይም ሹመት ፍለጋ ለደጅ ጥናት ነው።ሹመቱን ገና ሳያገኘው የመሸታ ጠጅ ለምዶ ቢሔድ ጉዳቱ ነው፡ቢሾምም ገንዘብ አጥፊ ይሆናል ። ባይሾምም ክፉ ልማድ ለምድዋልና ርስቱን እየሸጠ በከተማ ኑዋሪ ሁኖ ገንዘቡን ሁሉ ያጠፋና እንደ ዕብድ ይሆናል ። ለሴቲቱም ከላይ እንዳልነው ባልአገርን በመሰለ መልካም ኑሮ ከመኖር ከልጅ እሸት ከንብረት ምርት ተለይታ ብትኖር ጥቅም አይመስለንምና ተዚህ ወዲያ ያለውን ለአማካሪዎች ትተናል ። ብርሃንና ሰላም አንባቢዎችም የመሰላችሁን ብታስታውቁን እንወዳለን ።

ክረምት ።

የዘንድሮ ክረምት ገና በበጋው ጀምሮ ሲዘንም ባጅቶ ነበር። ከሰኔ ጀምሮ እስከ ነሐሴ እጅግ በርትቶ ነበር አሁን ከነሐሴ ፭ ጀምሮ እስከ ፲፫ ቀን ድረስ ብራ ነበር ። አንዳንድ ቀን እንኳን ትንሽ ትንሽ ያካፋ ነበር ምንም ቢሆን ለጤፍ አልጠቀመም ደሉናል እንጂ ለሥንዴና ለገብስ ለሌላም ጥራ ጥሬ እህል አልከፋም ይላሉ።ዛሬ በ፲፬ኛው ሌሊት አዲስ አበባ መልካም ዝናም ዘንሞአል ። ነፋስ አልጀመረምና ገና ይዘንማል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።ቀድሞ በፍልሰታ እንደዚህ ያለ ብራ ሁኖ ያውቃል አያውቅም እየተባባሉ ሲከራከሩ ስለ ሰማን ለሌላ ምው ጊዜ መታሰቢያ እንዲሆን ጽፈነዋል ።

ስለ ባሮ ነፃነት ።

በቀድሞ ዘመን በዓለም ሁሉ ባሮች መሸጥና መግዛት የተለመደ በመሆኑ በኢትዮጵያም እንደ ሌሎቹ አገሮች በቀድሞ ዘመን ባሮች መኖራቸው የታወቀ ነበር ።

ነገር ግን ቀድሞ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ በኢትዮጵያ ባሮ እንዳይሸጥና እንዳይለወጥ በአዋጅ ከከለከሉ ብዙ ዘመን ነው ። ከዚያም ወዲህ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለ ሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሁነው ሳሉ ፤ ኢትዮጵያ ወደ መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ ካደረጉ በኋላ በየጊዜው የባሮን ነፃነት ደምብ እያሻሻሉ ከአዋጅ በፊት በየሰው እጅ የሚኖሩት ብዙ ባሮች ነፃነት እንዲያገኙ አድርገዋል ።

ነገር ግን የኢትዮጵያ ጠላቶች የሆኑ ይልቁንም በኢትዮጵያ ከንሴሲዮን እየለመኑ ልመናቸው ሰይፈጸምላቸው እየተመለሱ የሔዱ አንድ አንድ የውጭ አገር ሰዎች በኢትዮጵያ የባርነት ነገር እንደ ጥንቱ ነው እንጂ አልተለወጠም

እያሉ በጋዜጣ በማውጣታቸው በኢትዮጵያ የባርነት ነገር እየተሻሻለ መሔዱን የሚያውቁ ብዙ የአውሮፓ ሰዎች በጋዜጣቸው ይስቁባቸዋል ።

አሁን እንኳ ባለፈው በ፲፱፻፳፪ ዓመት በኢትዮጵያ አውራጆች ሁሉ የባርችን ነገር እንዲመረምሩ የታዘዙ ሹሞች በአገር ግዛት ሚኒስቴር በኩል ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በቀረቡት ራፖራቸው ፱፻፸፮ ባሮች ነፃ መውጣታቸውን አስታውቀዋል ።

ደግሞ በማንም አገር ቢሆን አንዳንድ ክፉ ሰዎች አይታጡምና የባሮችን ነፃነት ሲያሰናክሉ እየተገኙ ተይዘው ለቅጣት የታሠሩ ሰዎች ከ፬፻ ይበልጣሉ ።

በአንድ ዓመት ውስጥ እነዚህን የሚያህሉ ባሮች ነፃነት ካገኙ ወደ ፊት በጥቂት ዘመን ብዙ ባሮች ነፃነት እንዲያገኙና በየጊዜው እንደዚህ እየተደረገ በኢትዮጵያ የባርነት ነገር እንዲጠፋ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አጥብቆ መሥራቱን ያስረዳል ።

L'AFFRANCHISSEMENT DES ESCLAVES

Nul n'ignore que jadis l'esclavage existait en Ethiopie, comme d'ailleurs dans les autres contrées de la terre où la coutume de vendre et d'acheter des esclaves subsistait anciennement.

Mais, Sa Majesté l'Empereur Ménélick II, édicta il y a fort longtemps une loi interdisant la vente et l'échange des esclaves en Ethiopie. Par la suite, à l'époque où Sa Majesté l'Empereur Hailé Sellasié était Héritier du Trône et Régent Suprême de l'Empire, lorsqu'elle fit admettre l'Ethiopie au sein de la Société des Nations, les lois et reglements concernant la libération des esclaves qui existaient, furent renforcés par Sa Majesté, ce qui eut pour résultat que beaucoup d'esclaves qui appartenaient à des maîtres, bien avant ces édits obtinrent leur liberté.

Cependant les adversaires de l'Ethiopie, principalement certains solliciteurs étrangers qui n'avaient pu obtenir les diverses concessions qu'ils convoitaient, prétendirent, par voie d'articles de presse, à leur retour dans leur pays, que la situation des esclaves n'avait pas été modifiée. De nombreux européens au courant de la situation, et qui savaient combien elle avait été améliorée s'étonnèrent grandement de leurs articles.

Tout récemment, dans le courant de l'année 1922 (1930) les fonctionnaires chargés d'enquêter dans toutes les Provinces de l'Empire d'Ethiopie sur la situation des esclaves, signalèrent, dans les rapports qu'ils adressèrent à Sa Majesté l'Empereur, par l'entremise du Ministère de l'Intérieur, qu'au cours de la présente année 976 esclaves avaient été libérés.

De même que dans tous les pays il se trouve des contrevenants, plus de 400 individus qui avaient enfreint les lois règlementant la libération des esclaves furent arrêtés et emprisonnés en attendant le jugement devant décider de leur sort.

Si donc, dans le courant d'une année, un si grand nombre d'esclaves ont pu obtenir leur liberté, ce fait démontre une fois de plus que le Gouvernement Impérial s'occupe avec activité de la question de l'esclavage en Ethiopie et que de nombreux esclaves ne manqueront pas d'être libérés en peu d'années, ce qui permet de prévoir l'abolition progressive de l'esclavage.

ስለ ዕርቅ እምቢታ መልስ ።

በአቶ በቀለ ዘለቀና በወይዘሮ አምሳለ ጥበብ መካከል ስላለው ስለ ባሕርይ ልማድ መነቃቀፍ ነገር ሁለቱም ወገኖች መነቃቀፋቸውን ትተው ተስማምተው እንዲኖሩ በማለት ለኔ እንደመሰለኝ የሚከፋውን ትተው የሚሻለውን ይዘው እንዲታረቁ ስል እንደመሰለኝ ጽፌ ነበር ።

ነገር ግን ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ጥንቱንም እነሣሣቸው ለከ ለጠብ ኑረዋልና የዕርቁ ነገር ስላልመሰላቸው እኔን አድላዊ አድርገው የዘለፉ ቃል ስለ ጻፉልኝና ይልቁንም ከመጻሕፍት ጥቅስ ስለ ጠየቁኝ ከዚህ በሚከተለው ቃል አስረዳቸዋለሁ ።

አንደኛ፥ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በገነት ባስቀመጣቸው ጊዜ አዳምን ከሔዋን ፈቃድ አትውጣ ብሎት ነበር ይባላል ያሉትን ቃል ከመጽሐፍ አላነበብኩምና ከመጽሐፍ ጠቅሰው አስረዳኝ ስላሉኝ እውነት ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ እሳቸው እንዳሉት ከማንበቡ ገፋ ባያደርጉ ይሆናል እንጂ ለኔ ጠቅሰው በጻፉት ምዕራፍ ውስጥ በኦሪት ዘፍጥረት በምዕ ፫ በቍ ፲፮ ስናነብ ሔዋን በፈቃዷ ዕፀ በለስን በልታ ባሏን ስላበላችው እግዚአብሔር ሲፈርድባት ፃርሽን እጅግ አበዛዋለሁ ፅንስሽንም በፃር ልጆች ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ትሆናለች እርሱም ይገዛሻል ብሎ የፈረደባት ፍርድ አስተዋይ ለሆነ ሰው ሔዋን አስቀድማ ባለፈቃድ መሆኗን በትክክል ያስረዳል ።

ሁለተኛም ፥ በምክንያት አዳምና ሔዋን እኩል ናቸው ስላሉት ፍርዱ ሲፈረድ ሔዋን አዛዥነቷን ተሽራ ፈቃድዋ ለባሏ መሰጠቱ አዳም ካጠፋው ጥፋት ሔዋን በአዛዥነቷ ያጠፋችው ጥፋት የበለጠ መሆኑን ያስረዳናልና አስቀድሞ ሔዋን ባለፈቃድ መሆንዋ ጥርጥር የለበትምና አፈ ታሪክ ብቻ አለመሆኑን በዚህ እገልጽላቸዋለሁ ። ደግሞስ ሔዋን ባለ ፈቃድ ካልሆነች የተከለከለውን ዕፀ በለስ አስቀድማ እሷ በልታ ለባሏ ያበላችው በአዳም ፈቃድ አይደለም በራሷ ፈቃድ ነው እንጂ ።

ምስተኛም ሔዋን አስቀድሞ ባለ ፈቃድ መሆንዋን የሚያስረዳ በወንድ ላይም እንዳታገዘ ሥልጣንዋ እንደቀረባት ከሐዲስ አው ዋቹ ምስክር እጨምር ላቸዋለሁ። አዳም አልተታለለም ሴቲቱ ተታላ ወደ መተላለፍ ገባች እንጂ፤ ጢ.ሞ ፩ ምዕቍ፲፬ መመልከት ነው።እንግዲህ ከመጽሐፍ ጠቅሰህ አስረዳኝ ላሉት ክብሯ በዋቂቱ ደህ ይበቃቸዋል ። እንዲያውም ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ የሚበቃ ትምህርት የለኝም ብለው ራሳቸው መስከረዋልና በዚህ ቢሳሳቱ አይፈረድባቸውም ።

አራተኛ አቶ በቀለ ዘለቀ የጻፈው የምክር ቃል እንደ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ላሉት ለወይዛዝሮች ነው እንጂ ለተራዎች ሴቶች አልጻፈም ነበር።ተራዎቹማ ሴቶች እንኳን በባላገር ያሉትና በከተማስ የሚኖሩት ቀሚሳቸውንም አላስረዘሙም ፊታቸውንም አልሸፈኑም በገዛ እጃቸውም እርከብ ረግጠው ዛብ ጨብጠው አክብት ላይ የሚወጡት ሴቶች ከተራዎች ወገን ናቸው እንጂ ከወይዛዝሮች ወገን አይደሉም። እነዚሁም ቢሆኑ እንደ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ቀሚሴ አወላከፈኝ ክንብንቤ ሸፈነኝ ሳይሉ በገዛ እጃቸው ለመዱት እንጂ ተማሬ ቤት ተከፍቶላቸው ተምረው አላገኙትም ። አስቀድሞ እንደጻፍኩት ከማንም ጋር መዋል ብቻ ቀርቶ የትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ይህን የመሰለውን በገዛ እጅ የሚለመደውን የሥልጣኔን የቀልጥፍናን ሥራ ወይዛዝሮቹም እንልመድ ብትሉ የከለከላችሁ ይገኝ አይመስለኝም ። ያቦን ስለት ለጊዮርጊስ ሶጡት እንደሚሉ ሁሉ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ለወይዛዝሮች የተጻፈውን የምክር ቃል አዛውረው በገዛ እጃቸው አውቀው ስለሠጡት ለተራዎቹ ሴቶች ወቀሳ የጻፍን ቢያስመስሉት እነዚያ ነገሩን ያውቁታልና አይቀየሙብንም ።

አምስተኛ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ለኔ በጻፉት ወቀሳ ላይ አንድ ጊዜ ለወገኑ አድልቷል ይሉኛል ፤ አንድ ጊዜ ደግሞ ለኛ ረድቷል ይሉኛል ጥንቱንስ ቢሆን ነገሩ ባይገባቸው ይሆናል እንጂ ገላጋይ የሆነ ሰው እንዲህ ከቍልቍለት መልሰ አንተም ይህንን ተው አንተም ይህ ይቅርብህ ብሎ መገላገሉ በኔ አልተገመረም ነበር ። የሁለቱን ነገር መርምሮ በንደ.ጥፋተኛ ላይ የሚፈርድ ባለ ሥልጣን የሆነ ዳኛ ነው እንጂ የገላጋይ ሥራ አይደለም ። ነገር ግን ወይዘሮ አምሳለ ጥበብ አድልተህብኛልና አልገላገልም ብለው የተደላደለ ቍርጥ ቃል ቢጽፉልኝ ኑሮ እንደገና ይህን ለመጻፍ ባላስፈለገኝ ነበር ። ግን ቃላቸው ሁለት ስለሆነብኝና ከመጽሐፍ እሳቸው ያላነበቡትን ቃል አስረዳኝ ስላሉኝ ይህን ጽፌ ላቸዋለሁና ዕርቁ የማይሆንላቸው ከሆነ ወደዳኛ ይሒዱ ስል ይቅርታቸውን እለምናለሁ።ሽማግሌ ሲተርት ገላጋይ በመከከል ይሞታል የሚለውንና ሰሎሞን በምሳሌው በም ፱ ቁ ፯ ፳ ም ፳፮ ቁ ፲፯ የተናገረውን ቃል አስቤ ተገላገሉ ማለቱን እንግዲህ ትቸዋለሁ።ተሰፋዬ ከማ።

መልስ ።

በስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፳፩ ብርሃንና ሰላም አቶ ቀጣው ይታጠቁ በላፈርሳታ መልስ » ብለው የጻፉት መንግሥት ለደኻው የተሻለ ደንብ ቢያወጣለት አይከፋም ነበር ብዬ ላስታወስሁት ቃል የሚመሳሰለው ቢሆን « ስሕተት ነው » ተብሎ ለተጻፈው መልሱን ጽፌ ማስረዳት የሚያስፈልገኝ ስለሆነ ከዚህ በታች አጭር ቃል እጽፋለሁ ።

— —፩ደኛ ያቶ ቅጣው ይታጠቁ የመጀመርያው ክፍል ቃል በዳር አገር በኩል ለሚሠራው ያፈርሳታ ሥራ ጥፋት የሌባሻይን ሥራ ምሳሌ አድርጌ የጻፍሑትን ሌባሻይ ማለፊያ ነበር ጥፋት አልነበረበትም ብዬ ያሞገስሁት ያስመስለዋል።ሰው ሁሉ ማንኛውም የከበደ ነገር ያገኘ እንደሆን ከሱ የሚብስ ወይም እሱን የሚመስል ተምሳሌት አድርጎ መናገር የቈየ ልማድ ስለሆነ እኔም በዚህ ልማድ ላፈርሳታ ሌባሻይ ምስሌ አድርጌ ተናገርሁንጂ ሌባሻይ ደኅና ነበር ብዬ እንዳላመስገንሁት በዚያው በጻፍሁት ጋዜጣ በ፻፴፰ ገጽ የሰረቀ ወይም ያቃጠለ ደኅና ሲኖር ደኅንኛውን ሰው ይይዛል ማለቴን ያስረዳጥልኛል ።

፪ተኛ » አፈርሳታ ጒዳቱ በጣም ትንሽ ነው ጥቅሙግን ብዙ ነው » ለተባለው እውነትም በሠለጠነው ከተማ ሁኖ የወጣውን ትክክለኛ ደንብ እያዩ ያሠራሩን ነገር ዙረው ሳይመለከቱ (ሳይፈትሹ) ከኖሩ በዚያው ልክ የሚሠራ ይመስላልንጂ ላንድ ጊዜ አፈርሳታ ከዘጠኝ መቶ የሚበልጥ ሕዝብ ተሰብስቦ ስድስት ወር ያህል ሳይነሣ መቀመጡን በጀሮ መስማት ያደደለ ባይኑ ያዬ ሰውስ ጥቅሙን አብዝቶ ጒዳቱን አሳንሶ ለመጻፍ ባልቻለም ነበር።ስለሆነ ግን በላይኛው መስመር እንዳመለከትሁት ቃል በሠለጠነው ክፍል ተቀምጦ ጥቅሙንና ጒዳቱን ለመረዳት ዙሮ ያላዬ ሰው እሱ የሚኖርበት ወረዳ እንደሚሠራው ልክ የሚሠራ ይመስለዋልና ጥቅሙቱንጂ ጒዳቱን አይሰማውም ።

፫ተኛ » ሕዝብ ላፈርሳታ እንዲሰበሰብ የሚታዘዝበት ጊዜ ብዙ ሥራ የማይሠራበት ወራት እንዲሆን ያስፈልጋል » ተብሎ ለተጻፈው ቃል ባሁኑ ጊዜያችን እንደምናየው አሠራር ባፈርሳታ ምክንያት ከስድስት ወር በላይ በጥር ውሥጥ ለሚታጐረው ሕዝብ ከመስከረም ጀምሮ እስከ የካቲት ድረስ ያለውን ወራት ሊመረጥለት ይሆን ? ወይንስ ከመጋቢት እስከ ነሐሴ። እንደኔስ ሐሳብ ከሥራሁለቱ ወር ውሥጥ ይህ የሥራ ወራት ነው ይህ የዐዘንተኝነት ነው ብዬ የምመርጥበት (ማገኝ) ይመስለኝም ።

፬ተኛ ስላፈርሳታ መሰብሰብያ ጊዜ ማመልከቻ » በሁለተኛው ክፍል ካንድ እስከሥራምስት የተነገረው ቃል እውነትም በጥንቃቄ ቢፈጸም ለሕዝብ ጥቅም የሚሆን ነውንጂ የሚጎዳ አይደለም ።

፭ተኛ እውነተኛ ላገር ጥቅም የሚሆን ሥራ አስቀድሞ የወጣውን ደንብ የንጉሥ ቃል ማለት ነውና በማንኛውም አገር ሁሉ (ማለት በኢትዮጵያ በብዙኅ ፍርሀት እንዲፈጸም ማድረግ ነው ። አስቀድሞ የወጣው ደንብ በጥንቃቄ ሳይፈጸም ሌላ ሌላውን መጨመር ግን ፊት የወጣውን ደንብ ባለመፈጸሙ ተከታዩን ያሳንቀዋልንጂ ሕዝብ ሊጠቅም አገር ሊያሠለጥን አይችልም ብዬ ለመጻፍ እደፍራለሁ ።

እንዲህ ማለቴ ግን ደንብ አይውጣ የወጣው ይበቃል ለማለት አይደለም ዓይነተኛውን የሕዝብ ጥቅም ደንብ አብዝቶ

ከማውጣት ይልቅ አስቀድሞ የወጣውን ኃይል ማልበስ ማለት በግድ እንዲፈጸም ማድረግ እንደሆነ ላንባቢዎች ማሳሰቤ ነው

፯ተኛ፤ አስቀድሞ የወጣውን ደንብ ተፈጽሞ ቢሆን ከሁን ቀደም አፈርሳታ እንዲሠራበት ተብሎ የተሰጠውን ሰነድ በየሻለቃው ግምጃ ቤት ተቀምጦ እያለ አሽከሮቼን ሰራ የማስታጥቅበት ገንዘብ አገኝበታለሁና የእገሌን አገር ወረዳ ያፈርሳታ ሥራ ጌታዬ እባክዎ ይፍቀዱልኝ » ብሎ በደጅ ጥናት (በመተያያ) ባልተሾመበትም ነበር ። በንደዚህ ያለ ምክንያት በዶ የሚሠራ ሠራተኛ ሁሉ አስቀድሞ ደጅ ከጠናበት (ጎዋይ) የሚበልጥ ለማግኘት የሚጥር ነው እንጂ የሕዝብ ጥቅም ፈላጊ የደኃ እንባ ጠባቂ አለመሆኑን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች አይስቱትም ።

፰ተኛ፤ በሁኑ ጊዜአችን በፈርሳታ ምክንያት የሚገኘውን ጉዳት በዝርዝር ብጽፈው አሠሪዎቼን ማሰጣት ያስመስልብኛልና እንዲያው ነገሩን በጅምር አቄየዋለሁ። ስለሆነም በብዙ አዋቂዎች ተመርምሮ የሚወጣውን የመንግሥት ደንብ ከመውጣቱ ይልቅ መፈጸሙ ነውና የሚጠቅመው በዛሬው ጊዜያችን በጥንቃቄ እንዲፈጸምልን ብዙ ተስፋ አለን ።

ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አኵሱም ።

ልጅን ወደ ብርሃን በመምራት ፈንታ ወደ ጨለማ በለመመለስ ።

እናቴ ዘመዶቼ እኔን ከተማሪ ቤት ስለ አስቀሩኝ አልቤ ውሥጥ ዐዐት ሆኖብኝ እስከ ዕለተ ጊዜዬ ድረስ የማይረሳኝ ስለ ሆነ ከዚህ በታች የጻፍሁትን ልጆቻችሁን አተማሪ ቤት ያገባችሁ ሰዎች ሁሉ በደስታ እንድታነቡልኝ በማክበር እለምናችኋለሁ።እኔን ዘመዶቼ ከተማሪ ቤት ከስቀሩኝ ቀን ጀምሮ አንድ ባልንጀራዬ ወይም አንድ ያገሬ ልጅ የሆነ ከውጭ አገር ሰው ጋራ በፈረንሣይ ወይም በእንግሊዝ ቋንቋ እንደ አማሩ አማርኛ አድርጎ ሳይሳሳት ንግግሩን ሲየሳምር በየሁና ብሰማሁ ጊዜ እንደ ተራጋሚና ተሰዳቢ አብድ ይመስል ዘመዶቼን እግዚአብሔር ይይላችሁ እያልሁ በቀን ሁለት ሦስት ጊዜ በእንደዚህ ያለ መታሰቢያ ሳላነሣቸው አልውልም ። እናንተም እኒህ አተማሪ ቤት የገቡት ልጆቻችሁ ጠንክረው ትምህርታቸውን ከተማሩ ዘንድ ቸሩና ብልሁ ንጉሣችን ወደ ከፍተኛ ተማሪ ቤት ለራሳቸው ልጆቻቸው ጥበብ እንዲማሩ መፍቀዳቸው የታወቀ ነውና ለልጆቻችሁ በፈቀዱላቸው ጊዜ ሲሆን ላገራችን መንግሥት እርዳታ አድርጋችሁ የማትችሉም እንደሆን ንጉሣችንን እያመሰገናችሁ ልጆቻችሁን በቅንልበናችሁ መርቃችሁ ልጆቹ እንዲሄዱ ኗንሆይ ወደ ፈቀዱላቸው አገር እግዚአብሔር በሰላም እንዲያደርሳቸው መርቃችሁ ስደዷቸው እንጂ በከንቱ ዕድሜያቸውን እንዲያሳልፉ አታድርጓቸው ። እኔ በዘመዶቼ በየጊዜው እንደማዝንባቸው ልጆቻችሁም በናንተ ማዘናቸው አይቀርምና። ግን እኔን አነቃቅቶኝ ይህንን ለመጻፍ የደረስሁበት ምክንያት በዕድሜው ከኔ ያነሰ ያክስቴ ልጅ የሆነ ዓለማየሁ ክንፌ የሚባል ልጅ አሁን በሐምሌው ውሥጥ ከሔዱት ልጆች ጋራ ወደ ግብፅ አገር ሊሔድ ቢነግዘመዶቹ ማስታጐል ልማዳቸው ነውና ይህን ለትምህርት የኼንውን ተማሪ እንዳይሄድ አስታጐሉት ግን ይህ ልጅ ባልንጀሮቹ በጥበብ በልጠውት መጥተው ባያቸው ጊዜ በባትና እናቱ ማዘኑ አይቀርም ። ግን እኔን የሚገርመኝ ካንድ ቤተ ዘመድ እኛው ሁለታችን አንዳችን እንግሊዝ አንዳችን ፈረንሣይ ብንጀምር እኛኑ በዛችሁ ብለው ማስተጓጐላቸው ነው የሚሰዝነኝ ይልቁንም አገራችን በሠለጠነችበት ሰዓት አተማሪ ቤት ላሉት ተማሪዎች ሁሉ እንደኛ እንዳያስታጉሏቸው ሙሉ ተስፋ አለኝ ዘመዶቻችን እንዳንማር ከፉ በጎን እንዳንለይ አስረው ያስቀሩን ልጆች ሁሉ በትምህርታችን ተስፋ አንቁረጥ ከቀን ብዛት የተሰጠንን ፈቃድ ሳናየው አንቀርምና ከቡራን የተማሪዎች አባትና እናት ሆይ ይህን የጻፍሁበት ምክንያት ለልባችሁ ለማሳሰብ ብዬ ነው እንጂ ዕውቀቴን አስፍቻለሁና በዕውቀቴ እመክራችኋለሁ ብዬ አይደለም ።

ከጻፍኳቸውም ቃላቶች ውሥጥ ለምታገኙት ስሕተት ይቅርታችሁን እለምናሁ ።

በትምህርቱ ተስፋውን ያልቈረጠ ተማሪ ክንፋ ይመር

ስለሀገር ጥቅም

ሀገርን የሚያበለጥግና መንግሥትን የሚያስከብር ነገር በተሰማና በተወራ ጊዜ ሌሊት እንቅልፋን አስወግዶ ቀኑንም ተበራቶ በርሳስና በወረቀት አሰናድቶ ለብርሃንና ሰላም ማቅረብ የሚገባ ስለሆነ ከውጭ ሀገር ካሉ ወዳጆቼ ዘንድ ያገኘሁትን ለሀገር ጥቅም የመላበት ወሬ ላሳስብ እወዳለሁኝ በአውሮፓ አገር ያሉ ነጋዴዎች እቃ ሲሸጡና ሲገዙም ፋክቱር ሽጩ ለገዢው ሲሰጥ እንደ ገንዘቡ ማነስና መብዛት የሚለጠፍበት ቴንብር ስላለ ፋክቱሩን ለገዢው ሲሰጥ በፋክቱሩ ላይ እንደነቡ የመንግሥት ቴንብር ይለጠፍበትና ለገዢው ይሰጣል።ገዢው ም የተለጠፈበትን ቴንብር ለይቶ ይቀበላል ግን ሻጭውም የመንግሥቱን ደንብ አንድሎ ቴንብር ሳይለጠፍበት ለገዢው ቢሰጥ ገዢውም ቴንብር ሳይለጠፍበት ቢቀበል ሁለቱም ሕግ አፍራሾች ናቸው ፋክቱሩም የበቃ ምስክር ሊሆን አይችልም ብለው አወሩኝ

፪ተኛም፤ ማስታወቂያና የሲኒማ ወረቀትም ሁሉ ቴንብር ሳይለጠፍበት ለመለጠፍና ለመሸጥም የተሰጠ ደንብ የለውም የመንግሥቱን ቴንብር ከለጠፈበት ለመሸጥና ለመለጠፍም ይችላል ብለው አወሩኝ።በዚሁም በቴንብር ሽያጭ ዋጋም መንግሥት ብዙ ጥቅም ያገኛል። ስለዚህ ይህን የሰማሁትን ወሬ በዚህ ሥራ ነገር ለመሥራት ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ነገሩን መርምረው የውነትም እንዲሁ እደሰማሁት በቶሎ ብሎ ሕጉን ማቆም ያስፈልጋል ስል በሥራው ሥልጣን ለተሰጣቸው ሹማምንቶች አሳስባለሁኝ

በቀለ ዘለቀ ።

ስለ ሁለት ሕፃናት ንግግር ።

፲፱፻፳፱ ዓ ም ሐምሌ ፳ ቀን ከድሬደዋ ወደ ሐረር ግንብ አዲስ ወደሚሠራው የአውቶ ሞቢል መንገድ ለማየት ከድሬደዋ ከተማ እራቅ ብዬ የአወቶሞቢሉን መንገንድ አይቼ ይልቁንም ነፋስ ተቀብዬ ስመለስ ሁለት ልጆች ከከተማው ውጪ

ወጥተው በተለየ ስፍራ ተቀምጠው አንደኛው እንዲህ ሲል ተናገረ ። ወንድሜ ሆይ ይህ የኛ ጊዜ በጣም የተባረከ ጊዜ ሆነልን፤ትምህርት፣ ሰፋ ድንቍርናም ተገፋ ፣ እኛ ሕፃናቶችም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትጋት እንማራለን፤ በተሰፋ ልዑል እግዚአብሔር መንግሥታቸውን ያጥና ዕድሜአቸውን ያብዛ እያልን እምላክን እንለምነው አለን። ብሰቱን ስባልጀራው ነገረው። ባልጀራውም መለሰለት አለውም፤ ወንድሜ ሆይ ይህስ ያልኸው ሁሉም ይፈጸም ደግምም ተናገርኸኝ ላን የትምህርት መስፋት የድንቍርና መገፋት የታየውና የተገኘው ባጊታችን በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ነውና አንተው እንዳልኸው በጤና ያኑርልን አለና ነገሩን ጨረሰ።

እኔም እንዲህ ሲነጋገሩ ከነሱ በላይ እኮረብታ ስፍራ ተቀምጬ እሰማ ነበር ፤እስኪ ሰምንት ፰ ዓመት ማይሆናቸው ሕፃናት በተለየ ስፍራ ሒደው መንግሥታችንን ማመስገናቸው ዳግም የትምህርትን መስፋት መጫወታቸውና መውደዳቸው በጣም ያስደንቃል ስለዚህ እግዚአብሔር ወደፊት ለሚወለዱ ሕፃናትና ትምህርት ለሚማሩም ልጆች እንደዚሁ እንደሁለቱ ሕፃናት ልቡና ይሰጣቸው እያልሁ እመኛለሁ ። በተረፈ ክቡራን አንባቢዎች ሆይ ከጊዜ በኋላ ተምሬ ከዚህ በላይ፤ለጻፍሁት የሆነ ነገር የኋላውን እፊት የፊቱን እኋላ አድርጌው እንደሆነ ድፍረቴን በይቅርታ እንድትወስኑልኝ እለምናችኋለሁ ።

ወዳጅነህ ገብረ ኢየሱስ።

ስለ፳፭ ሕፃናት የከንቱ ሐሳብ ምኞት ።

አንዳንድ ሕፃናት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ዕድሜአቸው ከ ፯ እስከ ፲፪ ዓመት የሚሆናቸው ሕፃናት ንግድ እንነግዳለን እያሉ ምላጭና ክብሪት መርፌ እየያዙ ክብሪት ገዢ፤ምላጭ ገዢ፤ መርፌ ገዢ እያሉ በአራዳ ውስጥ ሲያዞሩና ገዢ እየፈለጉ ሲንከራተቱ እናያለን። እነኝህም ልጆች የያዙት የንግድ እቃቸው የሩብ ወይም ያላድ የሚያህል ነው ።

ይኸነኑም እነሱ ያተርፈናል እያሉ የሚያዞሩትን እቃ በየከተማው ዳር ዳር እንኳ እየሔዱ ቢያዞሩ ለለት ምግባቸው እንኳን ትርፍ አያጡበትም ገዢዎቹ ምንም አራዳ የሚገዛበትን ዋጋ ቢያውቁት ስለመንገዱ ድካም ሲሉ አትርፈው ይገዙአቸው ነበር ። እነኝህም ጉልበታቸው ያልጠና አእምሮአቸው ያልቀና ሕፃናት ካራዳ ውስጥ ፪ትና ሦስትኪሎ ሜትር መሬት የሚያህሉ መንገዶች ለመሔድ ሐሳባቸው ስለማይፈቅድ ከራዳ ጉምሩክ እስተፖስታ ቤት ድረስ በመንገዱ ላይ እየተመላለሱ ክብሪት ፈላጊ፤ምላጭ ፈላጊ፤ መርፌ ፈላጊ፤ እያሉ ጉሮሯቸው እስኪደርቅ እየጮሁ እንነግድበታለን ብለው የያዙትን ነገር ይዘው በመንገድ ላይ ሲመላለሱ ይውላሉ ።

ምናልባት አንዳንዶቹ ባላገሮች የገባያውን ሁናቴ ያልተረዱት ቢገዙአቸው እንኳን ከዋናው በተቀር ትርፍ አንድ ቤሳ ወይም ሁለት ቤሳ በቀን ቢያገኙ ነው።የሚገዛቸውም ያላገኙ እንደሆነ በከንቱ ሲዞሩ ውለው ለለት ምግባቸው የሚበቃ ትርፍ እንኳ ሳያገኙ እየዋሉ ከሳዳጊዎቻቸው ዘንድ ይመገባሉ።

ዳግም በማር ገበያም እንደዚሁ ከድሜአቸው ከ ፯ እስከ ፲፪ የሚያል ሕፃናት ማር ባላገሩ ከባላገር አምጥቶ ከሚሸጥበት ቦታ ማር የቀጫኑት ከበቶች እርስ በርሳቸው ሲተላለፉና ሲጋፉ ተሰባብሮ የወደቀወን ሲለቃቅሙና ባላገሮቹ አራግፈው ለገዢው ሲሹጡ የረገፈውን ርጋፊና ጥርግራጊ ሲሰበስቡ ጊዜአቸውን ለለት ምግባቸው በማይበቃና ለኋላም ማደሪ ሆኖ በማያኖራቸው ነገር የትምህርት ጊዜአቸውን በከንቱ ሐሳብ ለውጠው ሲኖሩና ሲውሉ ሶለምናይ በጣም ያሳዝናሉ።

ይልቁንም እነኝህ ሕፃናት በበቃ ተግሣፅና ትምህርት ስላላደጉ በውስልትናና የከተማውን ባህልና ሁናቴ በማወቅ ስላደጉ ውስጥ አወቅ ሳይታወቅ እንደሚባለው ለከተማዎች ዘበኞችና ከንቲባውም ቢሆን ባደጉ ጊዜ ብዙን ጥንቃቄና ድካም ሳያመጡባቸው አይቀሩም ይመስላሉ ማለት አስተዳደጋቸው በተግሣፅና በትምህርተ ስላልሆነ ።

ስለነኝህ ልጆችና እነኝህን ለመሳሰሉ ሕፃናት ሁሉ የትምህርት ምንስቴር ዕድሜአቸው ከ ፯ እስከ ፲፪ የሚሆኑትን በንግድ በታና እንዲሁም በሥራ ፈትነት በከተማ ውስጥ ትምህርትን ሳይመለከቱና ሳይማሩ ወዲህና ወዲያ የሚሉት ሕፃናት ሁሉ በቃማኝ ዘበኞች በከንቲባው አስጊነት እያስያዙ አባትና እናት ያላቸውንም አባትና እናታቸውን እየጠየቁ በልጆቹ መሪነት ወላጆቻቸውን እየያዙ ካሁን ቀደም ልጆቻቸውን አስተምሩ ብሎ መንግሥት ያደረገውን አዋጅ ሳይጠብቁ ስላፈረሱትም የሚገባ ቅጣታቸውን እየተቀጡ ለወደፊቱም የጠነከረ ደንብና አዋጅ ተደርጎ እንዲያስተምሩ ቢታዘዙ ።

፪ተኛም አባትና እናት ረዳት ዘመድ የሌላቸውን የድኻ ልጆች በአርፍ ማለት ወገን በሌላቸው በሙታን ተማሪ ቤት በክቡር ከንቲባ ብርታት እየሰበሰቡ ለትምህርት ምንስቴር እያስረከቡ ያዲሱን የሥልጣኔ ትምህርት ቢማሩ ይሻላል እንጂ እንዲያው በከንቱ ያንድ ሩብ ክብሪትና ምላጭ እየያዙ በገበያ ውስጥ እየዞሩ ሌብነትና ወስላትነትን ቀጥፈትን አታላይነትን ይህንንም የመሰለውን ነገር ሁሉ የሠለጠኑበት እንደሆነ ለከተባውም (ጸ፡ የ) ለዳኞችም ጭንቅ ለንጉሥም እሩቅ እየሆነ ከመታወክ በስተቀር የእነዚህ ሕፃናት አጀማመርና አያያዝ እውነስ እራሳቸውን የሚአስችላቸው አይመስለኝምና ክቡር ከንቲባና ክቡር የትምህርት ምንስቴርም በዚህ ነገር እንዲአስቡበት አስተዋሽነቴን ለጌቶቼ በማክበር አቀርባለሁ ።

በቀለ ዘለቀ።

ስለ መንግሥትና ስለ ሕዝብ ጥቅም ።

በከተማ ውስጥ ያሉ ወዳጆቻችን በከተማ ሲመላለሱ የሚያገኙትን የሥራ ጕድለትና ያዩትንና የሰሙትንም የድኃ በደል የምክር እርዳታ አድርገው ቢያስታውቁን እጅግ ደስ ይለናል ። ይህንንም ማለታችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ትእዛዝ የከተማውን ሥራ ኃላፊነት የተቀበልነው እንደተቻለን ያህል የከተማውን ሕዝብ በጥንቃቄ ለመጠበቅና ለከተማ ሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ የሆነውን ሥራችንንም በሚገባ ለመሥራት ስለሆነ ራሳችን አስበን በቅንነት በምንደክምበት ላይ ያልታሰበና የተዘነጋ ነገር ያገኘን እንደሆን

በከተማ ውሥጥ የሚኖሩ ወዳጆቻችን ጥቅም ያለው የሆነ ምክራቸውን ሲያከፍሉን ለሕዝብ ጥቅምና ለሕዝብ ጉዳት የሚሆነውን ጉዳይ ስንሰማ አኅጢተን እየመረመርን የሚቻለውን ተግተን ለመፈጸም እንድንጥርበት ለጊዜው የማይቻለውን ግን ጊዜው እደረሰ ድረስ ለወደፊት እንድናስብበት ነውና ስለዚህ የታየውንና የሰማውን ነገር ለሚየከፍለን ሰው ከእሑድ ቀንና ከትልቅ በዓል ቀን በተቀር ከእኩል ቀን በኋላ ከ፱ሰዓት እንሥቶ እስከ ፲፩ ሰዓት ድረስ እማዘጋጃ ቤት ቢመጣ ወይም የሰማውንና ያየውን የተረዳውንና የመሰለውንም ነገር በጽሕፈት ቢያስታውቅ ዋና ዋና ጉዳይ ለሆነው የማዘጋጃ ቤትን ዲሬክተር በማዘጋጃ ቤት ይገኛል ። ቀላል ጉዳይ ለሆነው ነገር ግን ከዚያ ለማይለዩ ለዋና ጉዳይ ጸሐፊዎች የቃሉን በቃል ሊናገር፤ የወረቀቱንም በወረቀት አድርጎ ሊያስረክብ ይችላል ።

የነዚህም ጸሐፊዎች የጽሕፈት ቤታቸው በመዘጋጃ ቤት እመገምመርው ሮቅ ላይ ነውና የሚገኘው ምልክቱ እበሩ ላይ ክፉን አሳብ መተው ደኅን ነገር ማስተዋል የሚል ጽሕፈት ተጽፎበታል።የሰውንም ምክርና እርዳታ የግልጹን በግልጽ የሥውሩንም በሥውር ለመቀበልና ምሥጢር ለመቻል ጸሐፊዎቻችን በእምነት ያሉ ናቸው ። የዲስ አበበ ከንቲባ ።

የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በከተማ ውስጥ ላለው ለማዘጋጃ ቤት የሥራ ጉዳይና ወይም የርስትና ያቤቱታ ጉዳይ ለሆነው ነገር ለክርታ ማስነሣትም ሆነ ለሌላ ነገርም ቢሆን ወደ ከንቲባውና ወይም ወደማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር ወረቀት የሚጽፉ ሰዎች እንደዚሁም ከየምንስቴር ቤት ሹማምቶችና ከየጽሕፈት ቤቶቻቸው ለየሥራ የሚጽፉልን ሹማምንቶች በኛ ስም አመልክተውና ወይም በማዘጋጃ ስም አድርገው የሚልኳቸውን ማናቸውንም የየሥራ ጉዳይ ወረቀቶች በቀጥታው ወደ ማዘጋጃ ዋናጽሕፈት ቤት እንዲልኩልን እናስታውቃለን።ይኸውም የጽሕፈት ቤት ምልክቱ እማዘጋጃ ቤት እመገምመሯው ሮቅ ላይ መዳረሻ ያለው ክፍል ቤት ነውና እበሩ መግቢያ ላይ የከተማ ጉዳይ የመልክተ ሰጭና ተቀባይ ዋና ጽሕፈት ቤት የሚል ቃል ተጽፎበታል።

ይህን ማስታወቂያ ካወጣንበኋላ ግን ምናልባት የድንገተኛ ነገር ተገኝቶ በጣም የሚያስቸግል የመንግሥትና የሌላም ሰው ጉዳይ የጥድፊያ ደብዳቤ ካልሆነ በቀር በየቤታችን የሥራ ወረቀት ቢመጣ አንቀበልም። ወደ ማዘጋጃ ቤት በቀጥታው ለሄደውም የሥራ ወረቀት ምላሽ ያለውንም እያስናዳንለት የሚፈጸመውንም እንደችሎታችን እያደረግንለት ማንም ሰው ቢሆን በቶሎ ምላሹን ሊያገኝ ይችላል፤ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ዓም

የአዲስ አበበ ከንቲበ።

የምስክር ወረቀት።

ይህነን የምስክር ወረቀት የያዘ ሙሴ ሚናስ ኬርቤጊያን በአዲስ አበባ ከተማ ያለውን በታና ቤት ሁሉ እየመረመረ የግብሩን ልክ ለመወሰን ከፀናውም ደንብ ጋራ እያስማማ እንዲወስን አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት አዞታልና ስለዚህ ባለ በታዎችና ተከራዮችም ቢሆኑ ሙሴ ሚናስ ይህነን የታዘዘውን ሥራ ለማስኬድ ስለሚፈጽመው ጉዳይ የሚጠይቃቸውን ነገር ገልጦ ማስረዳት አለባቸው።

ነገር ግን ይህነን ሥራ ለመፈጸም ሙሴ ሚናስ በጠየቀ ጊዜ የተጠየቀውን ነገር ለማስረዳት እምቢ ያለና ሥራውንም የከለከለና ያሰናከለውን ሰው፤ ወይም ለተጠየቀው ጉዳይ ሐሰተኛ ነገርና ማስረጃ አቅርቦ የተገኘ ሰው ብርቱ ቅጣት አለበት።

ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፪ የአዲስ አበባ ከንቲባ

ማስታወቂያ ።

በኢትዮጵያ መጀመሪያው ትክክለኛው የሴት ልጆች ሕክምና ትምህርት በቤተ ማይዳ ሆስፒታል ባለፈው ሰኞ በነሐሴ ፭ቀን ተከፈተ

በዚሁም አስተማሪነት ሥራ የሕዝብን ቋንቋ ደኅና አድርገው የሚአውቁትንና ለአስተማሪነት ሥራ ባጣም የሚችሉ ዶክቶር ኔስተርምን መቅጠር በመቻሉ ሆስፒታሉን ደስ ብሎታል እንዚሁትም ተማሮቹን ለሆስፒታሉ ሥራ የሚአሠለጥኑ ሁለት ዋናች የስዊድሽ አስታማሚዎች ወይስ ረዳቶች ናቸው። ሚስ ሐገና ሚስ በስተሮም ናቸው አሁን ለጊዜው አዲስ ትምህርት ቤት ያሉ ዘጠኝ ሴት ልጆችና ሁለት ወንዶች ናቸው ወደፊት በመልካም አስተዳደግ ያደጉ ወጣት ሴት ልጆች እየገቡ ራሳቸው ተምረው እነሱን ለመሰሉና ለታመሙ ወገኖታቸው ለመርዳት እንዲችሉ ደክቶር ሐነር ተስፋ ያደርጋሉ ለትምህርቱም የሚመጡት ሁሉ አስቀድመው የአማሪኛን ንባብና ጽፈት ማወቅ ያስፈልጋል ከዚህ በኋላ ወደ ተማሪ ቤት ይምጡ።

፲፱፻፳፪ ዓ ም ነሐሴ ፲፪ ቀን።

እርዳታ ።

በፍርድ ቤት በታው ስለ ጠበበ በዙሪያው የነበረውን በታ ሁሉ ወደ ግቢው ለማግባት አስበ በዙሪያው የነበሩትን ሰዎች የበታቸውንና የቤታቸውን ግምት እየሰጠ ሲአስለቅቅ የጃንሆይ ጋሽ ጃግሬ የበሽ ብላይም ደኅና ደኅና ቤቶች የሰሩበት በታ ከዚህ ከፍርድ ቤት አቅራብያ ነበራቸውና የቤታቸውንና የበታቸውን ግምት ተቀብለው ከዚሁ ከተቀበሉት ገንዘብ ፩ሺህ ፱፻፳ ውን ብር ለተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት እርዳታ ሰጡ ይህንም ወሬ ብሰማ አላምንም ብዬ የአቶ ታደሰ መሸሻን የደረሰኝ ፊርማ አይቼ ተደነቅሁ።በልጸጋም አለወዳጁ አይተርፍ ድሀም ለወዳጁ አይሰንፍ የተባለው ተረት ዛሬ ተፈጸመ። መንግሥታቸውንና አገራቸውን ስለ ወደዱ ነው እንጂ ሰፊ አገር አይገዙ በታቸውን ሸጠው ያላቸቸውን ሁሉ ስለማግባታቸው ይእቲስ አብአት እምተዕናሳ እንደተባለችቱ ሴት መደነቂያ ሁኖ እንዲኖር ብለን ጽፈንላቸዋል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኑ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ክምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከክምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የክምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሺቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፌኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ፤፤ ላ፣

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።
በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

COGNAC S.&E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፭
6me ANNÉE № 35

ሐሙስ ነሐሴ ፳፪ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓም።
JEUDI 28 AOUT 1950

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ግርማዊት መነን ።

የክብር ክብር ።

በነሐሴ ፲፱ ቀን ግርማዊት መነን ከላይኛው ግቢ ወደ ታላቁ ግቢ ሲገቡ በማረ ኦቶሞቢል ሁነው ባለ ወርቅ ጉብጉብ ግምጃ ጥላ አሲዘው ታላላቅ መኳንንትና ወይዛዝር በልዩ ልዩ ኦቶሞቢል ሁነው ተከትለዋቸው ነበር። የሥርዓት ሰልፍ የተማረ ብዙ እግረኛና ፈረሰኛ ወታደርም ተከትሏቸው ነበር ። በፈረስና በበቅሎ ሁነውም የተከተሉ ብዙ መኳንንት ነበሩ። የሰውም ደስታ ከልክ ያለፈ ነበር። ጊኪሎ ከሚባለው ሲደርሱ አንዲት ሴት ዕልልታ ብትጀምር በየመንገዱ ዳር ያሉ ሴቶች ሁሉ እልል አሉ ። ይህም እልልታ ላስተዋለው ሰው ታላቅ ምሥጢር አለበት። ይህም ታላቁ ግቢ ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የሠሩት ነው ። ሳይታደስ ብዙ ጊዜ የቈየ ስለሆነ ይህኑ ግቢ ለማደስ ብልህትና ትጋት ያላቸው ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ታዝዘው ሌሊትና ቀን በትጋት ሲአሳድሱ ሥራው እስቲአልቅ ድረስ ግርማዊት መነን አላይኛው ግቢ የቈዩበት ምክንያት ይህ ነበር። እልፍኝም እጅግ አምሮ ታድሶ ከገቡ በኋላ ታላቅ ደስታ ተደረገ። ለመኳንንቱና ለወይዛዝሩም ሽምፓኝ ቀርቦ እየተመረቀ ሲጠጣ ነበር ። የመኳንንቱና የወይዛዝሩን አቀማመጥና የግብዣውን ነገር ላየው ሰው እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር።

ሹም ሽር ።

ግራዝማች ወልደ መድኅን የአዳን ምስለኔነት ተሾሙ።

ግራዝማች አበበ ረዴ የበለሙዋል ን አለቅነት ተሾሙ ።

ግራዝማች አስፋው ሰይድ የግራዝማች ወልደ መድኅን የነበረውን የዘበኛ የሽ አምበልነት ተሾሙ ።

ልጅ ታፈሰ አደፍርስ አዲስ በሚሠራው ያቡጂዲ ፋብሪካ ተሾሙ። ልጅ ተረፈ ወልደ ገብርኤል ከልጅ ተሰማ ዓሊ በታች የልፍኝ አስከልካይነት ተሾሙ ።

ልጅ ጌታሁን ዋለሉ በግቢው ሥራ የግራዝማች አበበ ረዴ ምክትል ሁነው ተሾሙ ።

ላገር ጥቅምና ማስፋት መጣጣር በሁሉ ልብ ነው

አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ በሰኔ ወር ውስጥ ከድሬ ዳዋ አዲስ አበባ መጥተው ነበረና ከቶ የሺጥላማሬ ጋራ ከግቢ እየተጫወቱ ሲወጡ በኋላ በኋላቸው ስሔድ ንግግራቸው ታላቅ ፍሬ ያለበት ስለሆነ ለመጻፍ ሳይታ በልቤ ስለ መላ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ልገልጸው ወደድሁ። አቶ በሻህ ውረድ ሀብተ ወልድ አቶ የሺጥላማሬን ሥራህን ከለቀቅህ ወዲህ ሌላ ሥራ አልያዝህምን ጊዜ እኮ አትቆምም ትሮጣለች አሏቸው።አቶ የሺጥላም አዎን አልያዝሁም ምን ላድርግ አገኝሁበት በፈቃዴ ለመፈላለግ እንደ ማልችል የምታውቀው ነው።ይልቁንስ አሁን እሳ ብንተ እንዲሠራና እንዲቀና ታዘሃል ማለት ሰምቻለሁና ከጃንሆይ ፈቃድህ ልሥራ አሏቸው ። አቶ በሻህ ውረድም አይመስለኝም የኔም ሥራ ብዙ ነው ይበዛብኛል ነገር ግን ቢሆንስ ላሠራሩ ያልከውን እኳኋን ግለጽልኝ ቢሏቸው አቶ የሺጥላ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አስረዷቸው።መጀመሪያ ውጋዙንና ደሚኖቹን (ባላባቶች ሎኩና አበሳንጋ) የእህልና የብር ቀለብ እየሰጡ ድሬዳዋ እንዲቀመጡ ማድረግ፥ ፪ኛ ፤ የውኃ ጉድጓድ ባለበት ሁሉ ላይ (ስፍራ) ያሠራና የሱማሌ ወታደር ጠያርና ፈረስ እየሰጡ ሳስቀምጥ ያም ወታደር በየሳምንቱ ሁሉ ፪ ጊዜ እርስ በርሱ እንዲገናኝ፥ ፫ተኛ በሥራ አምስት ባ፲፭ ቀን ወደ ሹሞች የሆነውን እንዲያስታውቁ፥፬ተኛ ግብራቸውን በየደሚናው ብዙና ጥቂቱን ጉዛ አይቶ መቍረጥ ዳግም ኢሳና ጉርጉራ የአላና ኖሌ ቶላ ስላሚዘረፍና ስለሚጋደል ምስለኔዎቹ ለየግዛታቸው እየረዱ ቍርጠኛ ቅጣትና ጎክክለኛ ደንብ በለመቆሙ በየዓመቱ ደንቡ ንይገርድምና ስለዚህ እነዚህን ወረዳዎች ባንድ ሹም መጠቅለል ነው ። ለሥራውም መጠንኛው ይሆናልና የድንቍርና ሐሳቤ ይህ ነው ብለው ከጨረሱላቸው በኋላ እስከህ አስታውቀን ሳይባሉ ሳጊዜው ይህን በመመለሳቸው አቶ በሻህ ውረድ ቆም ብለው ተገረመው መልካም ሐሳብ ነውና ቢሆንም ቢቀርም እስኪ መውረዴ ነውና ጻፍልኝ ግን አንድ ታላቅ ነገር የሚያስፈልግና ያንተን ሐሳብ የሚያፀና አለ።የምድር ባቡር ሐዲድ የተዘረጋ በኢሳ ማሀል ስለሆነ በየጣቢያው የተማሩ ቤቶች ቢቆሙ ብዙ መልካም ይሆናል ብለው ቀኑም መሽቶ ነበርና ተለያዩ ።

ምስኪኑ ሲራክ አፈ ወርቅ ዘብሔረ፳ላስታ ።

የዘመን ዕድል ።

፲፱፻፳፬ ዓ ም ነሐሴ ፩ ቀን በቍጥር ፴፱ የወጣው ብርሃንና ሰላም ስለከተማ ዘበኞች ትጋት በ፪፻፶፬ ተኛው ገጽ የተጻፈውን አንብቤ በጣሙን ደስ አለኝ ። አቶ ኃይሌ ሮባ በዚህ በትጋቱና በውቀቱ በሥራው መቀልጠፍና ማሳመር የምንሰጠው ምስጋና ለሱ የሚገባው ስለሆነ ይልቁንም ብልሁን ረቂቁን ክቡር ከንቲባ ነሲቡን ዕጥፍ አድርገን ልናመሰግናቸው ይገባል ። በውቀታቸው መፈራትና ጉልበት ለመንግሥት የታመነ አገልጋይ መሆኑን መርምረው አቶ ኃይሌ ሮባን በመሾማቸው የምርመራውን ሥራ ገና ከመጀመሩ በሥልጣኔ አካሔድ ስላራመደው አገሩን የሚወድ ሰው ሁሉ ደስ ብሎታል። ይህም የዘመን ዕድል ይባላል ። ሕዝብ ኃጢአት ሠርቶ እግዚአብሔርን ያስቈጣ እንደሆነ የዘመን ዕድል ለሕዝብ መቅጫ ክፉ ንጉሥ ያነግሥበታል ከነሠራዊቱ ይከፋና ሕዝቡንም ያለ መራራት ይቀጣዋል ። የዚያን ጊዜ ምሕረት ወደ እግዚአብሔር መለመን ነው እንጂ ንጉሡን ማማት አይገባም ። ደግም ሕዝብ አካሔዱን አሳምሮ እግዚአብሔር የታረቀው እንደሆነ የዘመን ዕድል ደግ ንጉሥ ያነግሥለታል ። በዚያን ጊዜ ምስጋናውን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ የንጉሡ ዕድሜ እንዲረዝም መለመን ነው። እኛንም እግዚአብሔር ስለታረቀን ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሲባሉ አዲስ ከገባላቸው ሠራዊት በተቀር አሽከሮቻቸው ሁሉ የልዑል ራስ መኰንን አሽከሮች ናቸው ። ሁሉም ሕጋውያን ፡ጸሎተኞች፥ ትሕትናሞች ናቸው ። ስለትሕትናቸውም ያልጋ ወራሽ አሽከሮች ነንና በኍራት ሰውን እንበድል የማለት ሐሳብ ሊያድርባቸውና እንዲያውም አንዳንድ ሻለቃ አሽከር እንኳ ያሀል አይኰሩም ነበር። ስለዚህም ዘመኑን ሁሉ የልዑል አልጋ ወራሽ አሽከር ከዚህ በታ ላይ በኍራት የኃይል ሥራ ወይም የግፍ ነገር ሠራ ሲባል አልተሰማም ። ይህም የዘመን ዕድል ነው ። በከተማችን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ፍለጋ ተከትለው ለሥልጣኔ ጐዳና መሪ የሆኑን ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይና ክቡር ከንቲባ ነሲቡ፥ ክቡር አዛዥ ወርቅነህና ክቡር ነጋድራስ አፈ ወርቅ ናቸው ። ለይቼ ስም በመጥራቴ ግን ክቡራን አንባቢዎችን ይቅርታ ስለምን ላውራኝ አገረ ገዥማ ለግብረ መልከሙ ለክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው በብርሃንና ሰላም ተጽፎ የለምን ? መጀመሪው የሥልጣኔ ደረጃ ማማለኛ የፈራጁን ዓይን ያሳውራል ያለውን ንብብ ማዘውተር ነው ። ይህንንም ንብብ እነዚህ በጣም ያውቁታል ። ይህም የዘመን ዕድል በብርሃኑ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የሆነው ነው ። ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዳዊትን ዕድል ይስጣቸው ። ይህስ እንዴምን ነው ቢሉ ዳዊት አካሔዱንና ሥራውን ስላሰመረ እግዚአብሔርም ደስ ቢለው መንግሥትህን ከልጆችህ አልቈርጥብህም ኃጢአት እንኳ ሠርተው ቢያስቈጡኝም እንዳባት በተግሣፅ እመክራቸዋለሁ እንጂ መንግሥትን አልነሣቸውም አለው ። እኔም ይህንን መጽሐፍ ከተመለከትሁ በኋላ ታሪክ አዋቂዎቹንና ሊቃውንትን እስከ ዛሬ ድረስ በመንበረ መንግሥቱ የዳዊት ዘር በየሩሳሌም ይኖራልን ብዬ ብጠይቃቸው፡ዛሬ በኢየሩሳሌም የዳዊት ዘር የለም።ግን ዳዊት ሰሎሞንን፥ ሰሎሞንም ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደ ። የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ግልሆን በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት የተቀመጠ ብዙ የለም ። በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት የሚቀመጡት ሁሉ የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ናቸው ። እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠውን ቃል ኪዳን ያለማፍረሱን በዚህ ያስረዳል አሉኝ ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የትውልዳቸው ዜና ከቀዳማዊ ምኒልክ ሲያያዝ የመጣ መሆኑን ምንም ቤተ መንግሥት ቢያርቀውም እኛ አሁን ብነግሥታቱ

ታሪክ በትውልዳቸው ዲብዳቤ ስለተረዳነው የማይወሰን ደስታ ይዘናል ። ተጨፍኖ የነበረ ዓይናችንን ለገለጡልን ለደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን መንበረ መንግሥት ለልጆቻቸው እንዳያልፍ መሠረት አድርጎ እግዚአብሔር ይስጥልን ። ይህም መንበረ መንግሥት የሚገኝ በመልካም አስተዳደግ ነው ። ከአስተዳደግ መጕደል የተነሣ መንበረ መንግሥት የሚገባቸው ሁሉ ይቀርባቸዋል ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ብልሁ አባታቸው የንጉሥታቱ ዘር ልዑል ራስ መኰንን በትምህርትና በትሕትና አሳደጓቸው ፃርማዊ ንጉሠ ነገሥት በዚያን ዘመን የልጅነታቸው ወራት ሳያልፍ ልዑል ራስ መኰንን ቢሞቱባቸው ከጨካኝ ሰው በተቀር ያባት ኃዘን እንደሳት ይፈጃልና ያርታቸው ኃርን ሰቀቀን ስለሆነባቸው ልባቸው ወደመንፈሳዊ ተሰበረ ። በጾምና በጸሎት የተጸመዱ ሆኑ ። ልዑል እግዚአብሔር ልቡናቸውን ተመልክቶ ለክ ቀበቶ መንግሥቱን ሰጥቷቸው ነሯል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አላወቀም ከግዛት ወደግዛት እየተረማመዱ ሲሔዱ ያውራጃ ገጋር ይመስሉት ነበረ ። የእግዚአብሔር ጥበብ አይመረመርምና በልጋ ወራሹ በልጅ ኢያሱ መንፈሱን አሳድሮ ያለሐሳብ ከግዛታቸው ከሐረርጌ ተጠርተው መጥተው አዲስ አበባ እንዲቀመጡ አደረጋቸው ። ከዚያ በኋላ ሮሚገርም ነገር መንበረ መንግሥቱን አወረሳቸው ። ከዚየን ዕለት ጀምሮ እስከ ዛሬ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ኃይል እንደለበሱ ናቸው ። ዕድሜያቸውን ያርዝምልን እንጂ በየሥራው ላይ ያለው ሁሉ ሹማምንት ፍለጋቸውን እየተከለ ስሙን ለማስጠራት ይጣጣር ጀመረ ። ኢትዮጵያም ቄንጆይቱ ዕድሏ ተገለጠ አሁንም ክቡራን የከተማ ዘበኞች ሆይ አይዟችሁ በርቱ ገንዘብ አይመራችሁ ። ይህ ዕለት ዕለት እየታተመ የሚወጣው የምትጋናችሁ ፍሬ ከገንዘብ እንዲበልጥ ዕወቁት ። ገንዘብ ቶሎ ያልቃል መልካም ሞገስና ምስጋና አያልቅም ። ደግ ስም አይሞት አይቀበር ። ለዘላለም ይኖራል። እውነት ነው ዘበኞች የሕዝብ ረኞች ጠባቂዎች መንግሥት አደላድሎ የሚበቃ ማደሪ እንዲሰጣችሁ እንጠራጠርም የዘመን ዕድል የታመናችሁ መሆንን ሰጣችሁ አይዟችሁ ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለምኑ እንጂ የሚበቃችሁን ማደሪ እያንዳንዳችሁ እንድታገኙና ደስ እንዲላችሁ ተስፋችሁን አትቍረጡ ደግሞ የኢትዮጵያ ድርቦች ሆይ ኃያላኑ ፍቅራችሁና ኃይላችሁ ሥልጣኔያችሁም እየገሰመሰ እንዲሔድ የንጉሠ ነገሥታችንን ፍለጋ እንድትከተሉ እለምናችኋለሁ።መክብብ ደስታ ።

ትንቢትና ነገር በየጊዜው ይፈጸማል ።

ለዚኸው ነገር ያነሳኝ ምክንያት እንደሚከተለው ነው። በ፲፱፻፳፱ ዓ ም ሐምሌ ፲፯ ቀን የጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ልደት ለማክበር ሲሉ ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ብዙ መኳንንትና ወይዛዝሮችን ወደ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ለሻይ ግብዣ ጠርተው ነበር።ስለዚህም ተማሮቹ ፥ የትያትር ጨዋታ አዘጋጅተው ነበርና፥ በዚያው ተሰብስቦ ለነበረው ሰው ከተማሮቹ በየተራቸው እየተነሡ ጫዋታቸውን ያሳዩ ጀመር። እኔም እንደዚህ ያለ ጨዋታ በሩቅ ሁኜ በወሬ ስሰማው የነበረ በዓይኔ ለማየት ብዙ ናፍቆት ነበረብኝና ፥ ምንም ባልጠራ ቀን አጋጥሞኝ ሳለ ክቤቴ ከመቀመጥ ከዚያው ሒጄ በስተ ውጭ ሁኜ ያኳኋኑን ልክ መጠየቅ ይሻለኛል ስል ከዚያው ሒጄ ነበር ። በማቴ ም ፯ ፡ ቍ፯ ፡ ለምኑ ይሰጣችኋል ሹ ተገኙም አላችሁ ፥ ደጅ ምቱ ይከፈትላችኋል እንደሚለው ቃል ሁኖልኝ ወዲያው በውሥጥ ግብቶ ለማየት ተፈቀደልኝና ፥ ልቤ የተመኘውን በዓይኔ ለማየት ያበቃኝን አምላክ በጣም አመሰገንሁ።ይህንም ተማሪ ቤት አስበው ላቆሙ ለጃንሆይ በየጊዜው ሐሳባቸው እንዲከናወንላቸው ምሉ ምኞቴን ተመኘሁ ።

የጫዋታው አኳኋንም ከልደቱ ክብረ በዓል ጋር ስምምነት ያለው ግሥ ይመስል ነበረ መቸም ነገሥታት ሁሉ የተወለዱበትን ቀን አክብረው ለመዋል ከጥንት ከባቶች ተያይዞ የመጣ ማዕርግ ነው።ምክንያቱም ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣ ከለ መኖርም ወደ መኖር ያመጣ አምላክን ታላቅ ክብር ምስጋና ይገባሃል ለማለት እንደሆነ መላችን እንስተውም እንደሁ ደግሞ የተማሮቹ የትያትር ጨዋታቸው እርሱን ይመስላል ። የጨዋታው አጀማመርም ሦስት ልጆች ወንድማሞች ባንድ ቦታ ሲጨዋወቱ ከብዙ ጊዜ ይዞ ሐሳባቸውን የሚያውቅ አንድ ልበ ብሩህ ወዳጅ ባሉበት ቦታ መጥቶ የሚሠሩትን እንደጠየቃቸውና እሱም ከመጫወት ባተቀር የሚረባ ሌላ ቁም ነገር እንደሌላቸው መልስ ይሰጡታል ። እርሱም እንደገና በማይረባ ነገር አጕል ከመኖር ገና በሕፃንነት ዕድሜያቸውን ድንቍርናና ጨለማ የሚባሉ ከብዙ ዘመን ተለምደው ሥር ይዘው ለቈየ የሰው ሁሉ ምቀኞች አዲስ ትምርት በሚባለው መብራትና እጀ ጥበብ በሚባለው መሣርያ እንዲያሸንፍዋቸውና ከገራቸውም ተጣጥረው በቶሎ እንዲያባርርዋቸው አዲስ አሳብ ያነሣሣቸዋል ። እነርሱም ደግሞ ለራሳቸው ሠልጥነው ላገራቸው ልጆችም ለወደፊቱ መልካም አርአያና አብነት እንዲሆኑ ያነቃቅዋቸዋል።እነርሱም ምክሩን በጣም እንደሚያስፈልግ ተረድተውት የመከሯቸውን ላመፈጸምና በንድነት ወንድማሞችም ሁነው ዕውቀት ወደሚገኝበት ቦታ በቶሎ እንዲገሰግሱ ተስፋ ይሰጡታል ይልቅ ያ አሮጌ ልማድ የሚባለውን እሰናካይ በፊታቸው አልፎ የሚሔዱበትን መንገድ እንዳይጋርዳቸው ያማክሩታል። እርሱም በአወላዋይ አሳብ የሚኖር ሰው ያሰበውን ጕዳይ እንዳይፈጸምለት ቈርጦ የሠራ ግን ያሰበውን ሥራ እንዲፈጽም ይልቁን ወንድ ልጅ ሁኖ ያሰበውን በቶሎ መፈጸም እንዲገባው በግምበሩ የሚቈይበት ፈተናና እሰናካይ ነገርም እንደሥጋው ያ ወዳጃቸው በእምነት እንዲሠሩ ያደፋፍራቸዋል። እነርሱም የርሱን ምክር አጥንተው ሦስቱ ወንድማማች ባንድ ምክር ሁነው ወደ አመለከታቸው አገር አብረው ይጓዛሉ ። ወድያው ያ የፈሩት ያረጀ ልማድ ካሰቡበት ቦታ ገና ሳይደርሱ በቶሎ ገስግሶ እነርሱን ይዞ በጨነቀ አየያዝ ተያይዘው ወደእሥር ቤት እንዲገቡ ያደርጋል። በከፋ አጨካከኑም እንዳስጨነቃቸውና እንዳይፀናባቸውም አይተው እነርሱም ከጭንቀታቸው ፈጥኖ የሚያድናቸውና ከእሥራታቸው የሚያስፈታቸውን ምክር አስበው ያገኛሉ። ፍትሕና ርትዕ ወደሚያውቅ ዳኛም ጭሆታቸውን ያቀርባሉ።ዳኛውም የጭንቀታቸውን ጩኸት ሰምቶ በፍጥነት

ከሰሠራቸው ጋራ በፊት እንዲቀርቡ ያደርጋል ። እነርሱም በፅኑ ሐያያዝ ተይዘው ከሳሠራቸው ጋራ በዳኛው ፊት ቀርበው ይጠየቃሉ ። እነርሱም ቀድሞ ባባቶቻችን በሊቀውንት ሲተረት የሰማነውን ምክር ተቀብለን ብ'ሠራ ነው ። ልጆቼሆይ ዘመን ለወለደውና ንጉሥ ለወደደው ነገር መቀበሉን አይቀድሙብትም ይሉናል። እኛም ጥበብን ለመማርና ማስተዋልና አእምሮን ለማገኘት ብንፈልግ ነው።በዚኸው ምክንያትም አገራችን በሥልጣኔእንዲቱ በናቀጥሎም ብርሃንና ልማት እንዲሆንላት ብለን ስንመኝ ነው ይላሉ። የከሳሻቸው መልስም ያረጀው ያ የቀድሞ ልማድ እንዳይጠፋና ምቀኝነት የተባለ መዛሪያም እንዳይበላሽ ሡርቶ መብላትና ሰዓትን ጠብቆ መኖር እንዳይመጣ በመሆኑ በዳኛው ፊት ምሥጢሩ ተገለጠበት ። ዳኛው ጊዜና ሰዓት ያጋጠመው ነውና ክሱ ፍሬ እንደሌለው መርምሮ የታሠሩትን እንዲፈቱና በሰቡት ነገርም ዳኛው ራሱ የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ወደ እንዲፈጸምላቸው ምሉ ተስፋ ያለው ቃል ይሰጣቸዋል ። እነርሱም ከሥራታቸው ተፈትተው በተደረገላቸው ታላቅ ምሕረትና ደግነትም ዳኛውን አሞግሰው ወዳሰቡት አገርም ስንቅ ወረቀት ተቀብለው በታላቅ ክብርና ተስፋም ከዳኛው ፊት ተሰናብተው መንገዳቸውን ይጓዛሉ ።

ከዚያ ወዲያም ባሰቡት አገር በደኅና ደርሰው ከዳኛ የተቀበሉትን ወረቀት ለታዘዙት ሰው ይሰጣሉ።ወረቀቱ የደረሰበትም ሰው በጣም ብልህ ነውና እነርሱን የክብር አቀባበል ተቀብሎ ፤ እንደ ወረቀቱ ቃልና እነርሱ እንዳሰቡት አሳብም ምሉ ምኞታቸውን ይፈጽምላቸዋል ። ፍጹም ደስታ በሞላ ሐሳብና በታላቅ መዓርግም ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ። በፊት አክብሮ ወደ ሰደዳቸው ዳኛና፡ ወደ ተወለዱበት አገርም እንደገና በደኅና ይደርሳሉ ። ወዲየው እንደደረሱም ታላቅ ትዳርና ሹመት ከዳኛው ዘንድ ይቀበላሉ። ከዚያ በፊት ያገኛቸው ብዙ መከራም ወደ ታላቅ ደስታና መዓርግ ይለወጥላቸዋል። ከከሳሻቸውም ጋራ በምሉ ይቅርታ ይታረቃሉ ።

በዚኸው ጨዋታ ግን ጃንሆይንና ግርማዊትን ተከትለው ለክብረ በዓሉ የተጠሩ በላይ እንደተመለከተው ብዙ ናቸው። ከተጠሩት ሳይመጡ የቀሩግንጥቂቶች አይደሉም፡ይህንም ማለቴ በዚያው ውሥጥ ሁኔ ብመለከት ስም ስማቸው የተጻፈበት ወረቀት በየወንበሩ ላይ ተቀማጭ ያልነበረበት ለተጠሩት ማረፊያ የተዘጋጀ ብዙ ባዶ ወንበር ስላየሁ ነው። እኔም በዚያች ሰዓት እስመ ብዙኃን እሙንቱ ጽዉዓን ወኅዳጣን ኅሩያን ማቴ ምዕቍ ፳፪ የሚለውን የወንጌል ቃል አሰብሁ። በከበሬታ ተጠርተው ሲያበቁ እንደዚህ ያለውን ጥሪ ችላ ማለታቸው የሰው ሐሳብ እጅግ ያስገርማል።እንኳን ብዙ አዲስ ነገርና የሕፃናት በትምርት አሠለጣጠን የሚታይበት ከዚህ ባላይም ደግሞ ነገሥታት ባሉበትና ዝናምም ባበራበት ቀን በትንሽ ነገር እንኳ ተጠርቶ ወደ ወዳጅ ቤት ስለ ፍቅር ተብሎ ይኬዳል ደኅና ሰው ተብሎ ስሙ ከተጠራ እጁ ካልታሠረና ወይምትንሽ ካልታመመ በተቀር ከተቈረጠው ሰዓት፤ጊዜያት ሊያሳልፍ አይገባውም። ሰዓት ፤ጠብቆ ማክበር አንድ ታላቅ መዓርግ ነው ስል ነገሬን አሳጥራለሁ።

አለቃ ገብረ ሥላሴ ፰ ዘሩፋኤል ተግሬ ፩ ዙፋን።

ስለአፈርሳታ ።

ስለአፈርሳታ ነገር አቶ ፍሥሓ ወልደ ሚካኤል በብርሃንና ሰላም ይጽፋሉ ። እኔም እንደዚሁ የመሰለኝን እጽፋለሁ ። ሁላችንን በየሐሳባችን እንደመሰለን ስለጻፍን ለአገር የሚጠቅም ፍሬ ቢያፈራ ብለን ነው እንጂ ክርክር የመውደድ አይደለም ።

በነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓመት በቍጥር ፴፩ ብርሃንና ሰላም አቶ ፍሥሓ ለጻፉት ስለአፈርሳታ ነገር ።

በ፩ደኛው ቍጥር ስለተጻፈው ስለሌባሻይ ነገር በቍጥር ፲፫ ብርሃንና ሰላም አቶ ፍሥሓ ከጻፉት ቃል ውሥጥ»የአፈርሳታ ሥራ ከሌባሻይ ጥሬት ይልቅ ፲እጅ የሚከፋ ሁኖ ስለተገኘ »የሚል ቃል ስላለበት ለዚሁ በቍጥር ፳፩ ምላሹን ብጽፍ ለአፈርሳታ ምሳሌ ጻፍሁት እንጂ የሌባሻይን ነገር ማሞገሴ አይደለም ብልዋልና ከዚህ በኋላ መጻፍ አያስፈልግም ብዬ ትቼዋለሁ ።

በ፪ተኛውና በ፫ተኛው ቍጥር ስለአፈርሳታ ጕዳትና ስለአፈርሳታ መሰብሰቢያ ጊዜ ለተጻፈው ቃል ።

በዓይን ማየት የሚያስገድድ ምስክርነት ብቻ ነው እንጂ ለተጻፈና ለተነገረ ምላሽ ምክር ማመልከቻ መስጠት የዓይን ማየት አያሻም ። አቶ ፍሥሓ እንደጻፉት ሕዝቡ በአፈርሳታ የሚጐዳበት ነገር እንዲቀር የሕዝቡ መሰብሰብና የምርምሩ ነገር ከርቀን እንዳያልፍ ሕዝቡ ለአፈርሳታ እንዲሰበሰብ የሚታዘዝበት ጊዜ ብዙ ሥራ የማይሠራበት ወራት እንዲሆን ያስፈልጋል የሚል ቃል አለበትና እኔ የጻፍሁት ሐሳብ ሕዝቡ ለአፍርሳታ ፯ወር ይታጐር፤አፈርሳታ መሰብሰብያውም ጊዜ ብዙ ሥራ የሌለበት ፯ወር ይመረጥ ለማለት ነው ብሎ ለመተርጐም የማይስማማ ነው ።

አፈርሳታ በዓመት ፪ ወይም ፫ጊዜ ቢደርግ ለአንዱ አፈርሳታ ፫ ቀን ሒሳብ ፯ወይም ፱ ቀን የሚመረጠው እህል ተዘርቶ ካለቀ በኋላ ለአረም እስኪ ደርስ፤ የአረም ጊዜ አልቆ ለዓጨዳ እስኪደርስ ብዙ ሥራ የሌለበት ወራት ማለት ይህ ነው፤ ደግሞ ከገና፤ከጥምቀት፤ ከፋሲካ ከሌላውም በዓል ውሥጥ የዕረፍት ጊዜ ፫ቀን እንዲገኝ የታወቀ ነውና ለአፈርሳታ የሚሆነውን ፫ቀን ለማግኘት የማያስቸግር ነው ።

ስለ ፬ተኛው፤ስለ ፮ተኛው፤ስለ ፯ተኛው ቍጥር።

እውነተኛ ላገር ጥቅም የሚሆን ሥራ አስቀድሞ የወጣውን ደንብ በኢትዮጵያ ግዛት ሁሉ በብዙ ፍርሀት እንዲፈጸም ማድረግ የደንብ ጥቅሙ ከማውጣቱ ይልቅ መፈጸሙ ነው ስለተባለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትልቅ እስተትንሹ ደንብ አክባሪ ትእዛዝ ፈጻሚ ቢሆንም እንኳ ከዳኞችና ከሹማምቶች በኩል በማወቅም በለማወቅ ቢሆን የታወጀው ደንብ እንዳይፋለስ አቶ ፍሥሓ እንዳሉት በትክክል እንዲፈጸም ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑ እውነት ነው ።

በሮፓ አገር ሕግና ደንብ ተጽፎ ከታወጀ በኋላ የተጻፈ ደንብ ሳይኖር በፊት ዳኛው ሁሉ በመሰለው ይፈርድበት ከነበረው ጊዜ በጣም የተሻለ ሆነ ። ስለሆነ ግን ባለማወቅም ወይም እያወቁ በማድላት ዳኞችና ሹማምንቶች አንዳንድ ጊዜ ደንቡን በትክክል ሳይከቱሉ ስለቀሩ ምንም የተጻፈ ደንብ ስለወጣ ከፊተኛው ይሻል እንጂ ፍጹም ትክክል ሳይሆን ቀረ ።

ስለዚህ ዳኞች ደንብን ሳይተላለፉ በደንብ በትክክል መፍረዳቸውን ሹማምንቶችም በደንብ እንዲታዘዘው መሥራታቸውን ባጭሩ የመንግሥቱን ደንብ የሚያስከብርና የሚጠብቅ ዓይነ ንጉሥ የተባለ ሹም ተሾመ ። በኋላም ስለንጉሥ ሁኖ ደንብ እንዳይጐድል፡ ድሀ እንዳይበደል የሚጠብቅ ሹም ተባለ። (በፈረንሣዊ procureur de l'empereur ይላል ።)

እሱም በትልቁ ይግባኝ ፍርድ ቤት ከሉ ዳኞች ጋራ ይቀመጣል።ምክትሎቹም በየፍርድ ቤቱ ከሉ ዳኞች ጋራ ተቀምጠው ደንቡን ይጠብቃሉ ።

ስለንጉሥ ሁኖ ደንብ እንዳይጐድል፡ ድሀ እንዳይበደል የሚጠብቀው ሹም ማናቸውንም ዓይነት ልዩ ልዩ የወንጀልን ነገር ሁሉ እየመረመረ ለወንጀለኛው ባላጋራ ሁኖ የሚከስና የሚነጋገር እሱ ሆነ። ስለዚህ አገር የሚያውክ ወንጀለኛ ከእውነተኛው ፍርድ ለማምለጥ አልቻለም። የግፍንና የወንጀልን ሥራ በተለየ ጥንቃቄ ይጠብቅ ጀመር ።

ስለንጉሥ ሁኖ ደንብ እንዳይጓደል፡ ድሀ እንዳይበደል የሚጠብቀው ሹም ከሳሽና ተከሳሽ በገንዘብ ነገር ከፍርድ ቤት ተቃርበው ሁለቱም ወገኖች ሕግንና ደንቡን እየጠቀሱ በይግባል ከተከራከሩ በኋላ ዳኞች ከደንብ የማይስማማ ፍርድ የፈረዱ እንደሆነ እሱ ራሱ ይግባኝ ብሎ ተከራክሮም ሁኖ ፍርዱን ያስገለብጣል ። ስለዚህ በፍርድ የግፍ ሥራ ለመሥራት የማይቻል ሆነ ።

ስለንጉሥ ሁኖ ደንብ እንዳይጐድል፡ ድሀ እንዳይበደል የሚጠባበቅ ሹም ከተሾመ በኋላ ግን ደንብ ተከበረ በትክክልም ይፈጸም ጀመር።

ይኸውም የደንብ ተጠባባቂ ሹም ዛሬ በብዙ መንግሥት አለ ።

በኢትዮጵያ እስከዛሬ እንባ ጠባቂ የሚባሉ ባለሟሎች እሱን ይመስላሉ። ስለሆነ ሥራ እየበዛ ንግድ እየበፋ ሒዷልና የደንብ መጠባበቂያ፡የድሀ መጠበቂያ የተባለ ሥራ በተለየ ማቆም የሚያስፈልግ ይመስላል።

ቅጣው ይታጠቁ

አዋጅ

መጀመሪያ ክፍል

ከውጭ አገር እንዳይወጣ ለተከለከለ ለሚያደነዝዝና ለሚያሰክር መድኃኒት ንግድና ሽያጭ የተሰጠ ደንብ ።

የሚያደነዝዙና የሚያሰክሩ መድኃኒቶች ሁነው የተለዩ እነዚህ ከዚህ በታች የተጻፉት መድኃኒቶች በዚሁ ደንብ በተወሰነው ቅጣት ያገኛቸዋል ።

፭፡ የኦፕዩም ዱቄት ያልተበጠበጠና እነዚህን የመሳሰሉ መድኃኒቶች ሁሉ ።

፮፡ የኮካ ቅጠሎች ።

፯፡ የኮካይን ዱቄት ከነጨው የተሰናዳ ኖቦካይን ኢሶካይን እንዲሁም እያይነቱ መድኃኒቶች ።

፰፡ ኤክጎኒን ።

፱፡ ሞርፊን ዲያሲቲልሞርፊን ዲያሞርፊናን ኤሮይን ከነጨዎቻቸው እንደተዘጋጁ ።

፲፡ ከህንድ ሻንቬር ተሰናድቶ የወጣ የሚቀብ ቴንቸር

፲፩፡ ከኦፕዩም የወጣ መድኃኒት።

፲፪፡ የኦፕዩም የሆነ አልካላይድ ሁሉ ።

ሁለተኛ ክፍል ።

ከውጭ አገር ስለ ሚመጣ መድኃኒት

ለመሸጥ ከተፈቀደላቸው ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች በቀር እነዚህን መድኃኒቶች ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ለማስመጣት ፈጽሞ ክልክል ነው እነዚህም ሐኪሞች መድኃኒቶች ባስመጡ ቍጥር ከአገር ግዛት ሚኒስቴር ፈቃድ መጠየቅ አለባቸው።

በፈቃዱም ጥያቄ ወረቀት ላይ ከዚህ በሚከተለው ይጻፍበታል።

፩ ፡ ለማስመጣት የተጠየቀው መድኃኒት መጠኑንና ስሙ።

፪፡ የሚልከው የፋብሪከው ቤት ስምና መኖርያው ።

፫፡ የሚመጣው መድኃኒት የሚላከው በፖስታ ወይም በምድር ባቡር በኩል እንደሆነ የሚመጣበትም መንገድ ።

መድኃኒት ሁሉ ከጥሩ አልካሎይድ ሳይሆን የተቀመመ ወይም የተለየ መድኃኒት እንደሆነ ከመድኃኒቱ ጋር የተቀላቀለውን የአልካላይድን ዓይነት ከመቶ ይህን ያህል ነው ተብሎ በጥያቄ ወረቀት ላይ እንዲወሰን ያስፈልጋል

የአገር ግዛት ሚኒስቴር በፈቃድ መጠየቂያው ወረቀት ላይ ለማስመጣት የተጻፈውን መድኃኒት ለመፍቀድ ወይም መጠኑን ለማሳነስ ወይም ጨርሶ ለመከልከል ይችላል ።

የማስመጫውም ፈቃድ ወረቀት ለባለ ፈቃድ ሲሰጥ አንድ ብር ይከፍላል

ስለ ንግድ

በመጀመሪያው ክፍል ላይ የተወሰኑትን መድኃኒቶች ለመሸጥ፥ ለማሰናዳት፥ ለማስቀመጥ፥ ወይም ያለዋጋ ለመስጠት የሚችሉ በኢትዮጵያ ለመሥራት የተፈቀደላቸው ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች ብቻ ናቸው ።

በኢትዮጵያ ለመሥራት የተፈቀደለት ሐኪምና መድኃኒት ቀማሚ ለራሱ ሥራ መድኃኒት በስፈለገው ጊዜ መድኃኒት ለማስመጣት የተፈቀደለት ሐኪምና መድኃኒት ቀማሚ እየመጠነ ሊሸጥለት ይችላል።

የነዚህም የመድኃኒቶች አሸሻጥና አደራረግ ከዚህ በሚከተለው በሶስተኛው ክፍል ላይ እንደተጻፈው ቃል ይመረመራል።

ወደ ውጭ አገር ስለ መስደድ ።

በመጀመሪያው ክፍል የተጻፉት መድኃኒቶች ወደ ውጭ አገር እንዳይላኩ ፈጽመው በጥንካሬ ተከልክለዋል ።

E D I T

concernant le Commerce, l'importation et le trafic illicite des stupéfiants.

Art.1

Sont qualifiés stupéfiants et tombent sous le coup des dispositions de la présente loi, les produits suivant.

1. Opium brut et médicinal sous toutes ses formes.

2.-Feuilles de coca

3.-Cocaine, brute, préparée et ses sels. (Novocaine, Isocaine etc)

4.-Ecgonine.

5.- Morphine, diacéthylmorphine (diamorphine et héroine) leurs sels et préparations.

6.- Les préparations galéniques (extraits et teinture) de chanvre indien.

7.- Extrait d'Opium.

8.- Tous les Alcaloides de l'opium

Art. 2

Importation, commerce et exportation

A. Importation.

L'importation de ces drogues est int rdite sur tout le territoire de l'Empire, sauf par les médecins, pharmaciens autorisés à pratiquer.

Ceux-ci devront préalablement à toute importation, demander une licence au Ministère de l'Intérieur.

La demande de licence indiquera:

1.- Le nom et la quantité de drogue dont l'importation, est demandée

2.- Le nom et le domicile du fabricant ou du fournisseur.

5.- Le mode d'envoi de la commande (poste, chemin de fer, etc.) et la voie d'importation.

Toutes les fois que les drogues ne seront pas des alcaloides purs qu'il s'agira de médicaments composés ou de spécialités. la demande devra indiquer le pourcentage et la nature des alcaloides composant la drogue.

Le Ministère de l'Intérieur statuera définitivement sur l'octroi, le refus ou la réduction d'importation des quantités indiquées dans la demande de licence.

La délivrance de l'autorisation d'importation donne lieu à perception d'un droit d'un thaler. Lorsque le pays d'origine l'exigera, le Ministère de l'Intérieur délivrera gratuitement un certificat attestant que les produits dont il autorise l'importation sont destinés à des fins légitimes.

B. Commerce.

Les médecins pharmaciens autorisés à exercer leur profession en Ethiopie ont seuls le droit de vendre, détenir, préparer, délivrer d'une façon quelconque, même gratuitement, les produits spécifiés à l'art premier.

Le médecin, pharmacien, importateur autorisé pourra remettre ou vendre les quantités de ces drogues qui lui seraient demandées par un médecin, pharmacien, autorisé à pratiquer en Ethiopie, et ce pour les besoins de sa profession.

L'emploi et la vente de ces produits sont soumis au mesures de contrôle de l'article 3 ci-dessous.

C. Exportation.

L'exportation des produits visés à l'article premier est formellement prohib e

---

ማስታወቂያ ።

ከ፲፱፻፳፫ ዓ ም ከመስከረም ፩ ቀን ጀምሮ የጉምሩክ ታሪፍ በፋክቱር ለሚገመት እቃ አንድ ጊኒ በሀያ ብር ታስቦ ቀረጡን ይከፍላል ።

የጉምሩክ ዋና ዲሬክተር ።

ማመልከቻ።

አስቀድመን እንዳስታወቅነው በሐምሌ ፲፰ቀን ስለ ጃንሆይ ልደት በዓል የአዛዥ ወርቅነህ ባለቤት ወይዘሮ ቀጸላወርቅ ጃንሆይንና ግርማዊት መነንን፡ታላላቆችንም መኳንንት ጋብዘው ነበር። የትያትሩም አኳኋን እጅግ ስላ አማረ ሁለተኛ ይደገም ተብሎ ነበርና ደግሞ በነሐሴ ፲፰ቀን ቀደሞ እጅግ አምሮ ነበር። ለጊዜው ስፍራ ጠቦ ስለ አቄየነው በሚከተለው ብርሃንና ሰላም እናትመዋለንና የቀረመስሎአችሁ እንዳታዝኑ እናስታውቃለን ።

ማስታወቂያ።

አሁን አቶ ብርሃነ ማርቆስ ባሉበት ቤት አጠገብ ባለውበሙሴ ሊዎን ኬቦርኮፍ ቤት ውሥጥ ለመኝታ ቤት፡ለመብል ቤት፡ ለማረፊያ ቤት፡ ለሌላም ቤት የሚሆን ሙሉ ልዩ ልዩ የቤት እቃና ፒያኖ አሙስ ፳፱ ቀን ነሐሴ ፲፱፻፳፪ ከጧቱ በሶስት ሰዓት በሐራጅ መሸጡን ለሕዝብ እናስታውቃለን። ገዢዎቹም ከሚገዙት እቃ ዋጋ በላይ ከመቶ አምስት የጽሕፈት ግብርና ኪሣራ ይከፍላሉ። ገንዘቡ እጅ በእጅ ይከፈላል።

የሐራጁ ዳኛ ፔሽዲማልጂ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኳ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ከምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከከምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መስክረ የከምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመ- ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግጋርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ እንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቴክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥቃችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፈርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC SaE&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAXA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኪዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
6me ANNÉE № 36

ሐሙስ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓም።
JEUDI 4 SEPTEMBRE 1950

ብርሃንና ሰላም
LUMIÈRE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ሰሌት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ጸሐፊና አቶ ማተሚያ ወረቀት እሽጉ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በዓመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር በዓመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የቤተ ክርስቲያን በዓል ።

በነሐሴ ፳፬ ቀን የአቡነ ተክለሃይማኖትን በዓል ለማክበር ጃንሆይና ግርማዊት መነን ፥ብፁዓን ጳጳሳትና ልዑላን መኳንንት ከአቡነ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን መጥተው ነበር።ብዙ ሕዝብና ሠራዊትም ተሰብስበው ነበር።እንደቤተክርስቲያን ሕግ ካህናቱ እየዘመሩ ዑደቱ ከተደረገ በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ የአቡነ ተክለሃይማትን ሥራ ጨምረው ለነዳያን እርዳታ እንደሚያስፈልግ መልካም ስብከት ሰብከው ሕዝቡን እጅግ ደስ አሰኙ። በአባትና በእናት ቋንቋ ስብከት መስማት እንዴት ደስ ያሰኛል?።

በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ስለተደረገው ትያትር።

በሐምሌ ፲፫ ቀን ስለ ጃንሆይ ልደት በዓል የአዛጋር ወርቅነህ ባለቤት ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ በዓል አድርገው የአደራረጉንም ነገር ከዚህ ቀድሞ ጽፈንላችኋል ። ለዚሁ በዓል ቀን የተደረገው ትያትር (ቁም ነገር ያለበት ጨዋታ) ከልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የተሰናዳው እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበርና ሁለተኛ ይደገም ስለተባለ የፍልሰታ ጾም በመግባቱ ቈይቶ ነበርና የጾሙ ቀን ከተፈጸመ በኋላ ጃንሆይና ግርማዊት መነን ፥ ታላላቆች መኳንንትና ወይዛዝር መጥተው በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ባለው በታላቁ አዳራሽ ውስጥ በነሐሴ ፲፰ ቀን ዳግመኛ ታየ።መጀመሪያ ፍሥሐ አበራ የሚባል ተማሪ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዞ ቀጥሎ የሚመጣውን ልብ የሚነካ ንግግር ተናገረና የሰሙትን ሁሉ እጅግ ደስ አሰኘ ።

ጃንሆይ ።

እንደ ቀድሞው ሕግና ሥርዓት ቢሆን እንደኔ ያለ በዕውቀትና በዕድሜ ሕፃን የሆነ ልጅ በግርማዊነትዎ ፊት ቁሞ ለመናገር አይችልም ነበር ። ዛሬ ግን በኃይለ ሥላሴ የነፃነት መንገድ ስለሰፋ ነፃነትን ተማምኜ እናገራለሁ ብዬ ለማሰብ ደፈርሁ ።

አሁንም በጠበበ አእምሮዬና ባልታረመ አማርኛዬ ስለዚች ሰንደቅ ዓላማ ለመናገር እንዲፈቀድልኝ ከዙፋንዎ በታች ወድቄ በትሕትና ግርማዊነትዎን እለምናለሁ ።

ይህች ሰንደቅ ዓላማችን ምን እንደሆነች ምሥጢሯን ሁሉ መርምረን ለማወቅ ግድ አለብን ። በመጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራትና ማክበር ይገባናል ። ቀጥሎም ይህች ሰንደቅ ዓላማችንን መውደድና ማክበር ነው ። ይህችንም ባለ ሦስት ቀለም ጨርቅ ከፈጣሪያችን በታች ልንወዳትና ልናከብራት ነፍሳችንንም ልናሳልፍላት ይገባናል ። ይህችም ሰንደቅ ዓላማችን እንዳትወድቅብን ትልቅ ትጋት ፥ ሴትና ወንድም ሳንል ሁላችን ደማችንን ለማፍሰስ የተዘጋጀን ልንሆን ይገባናል ። ሰንደቅ ዓላማችን ወድቃ ወደባዕድ አገር ያለፈች እንደሆነ ግን ፍጹም ባሮች መሆናችን ነው ።

ይህች ሰንደቅ ዓላማችን ያገራችን ምልክት ናት። ወይም አገራችን ናትና ስለዚህ የወደቀች እንደሆነ ኢትዮጵያ ቅድስት አገራችን ወደባዕድ እጅ ማለፏዋ ነው ። እኛም ለዘላለም አያልፍልንም።ኀዘንና ለቅሶም በልባችን እንደማይነቀሉ ሁነው ይተከላሉ፥ እቶ ሥቃይም ሁለጊዜ እንደማያሳርፉን ጥርጥር የለውም። አሁንም ይህች ሰንደቅ ዓላማችን እንዳትወድቅብንና ይህም ሁሉ መከራ እንዳይደርስብን መተባበር የሚባለውን ጋሻና ጦር አንግበን ፍቅር የሚባለውን ሸማ ተላብሰን ሁላችን በአንድነት ተደጋግፈን ልንጠብቃትና በሚያስፈልግ ጊዜም ልንሞትላት ይገባናል ። ደግሞ በጭንቅ ቀን እረ ወንድሞቻችን አለቁ፥ ጠላቶቻችንም በረቱ እኛስ ለምን እንጨረሳለን ሳንል ሳንሰጋም ከሰንደቅ ዓላማችን በፊት እያለፍን ጋሻና ዕርድ ልንሆንላት ይገባናል ።

በዚህ ዓለም ስለ ሰንደቅ ዓላማቸው ወይም ስለሀገራቸው የሚሞቱ ጀግኖች ምንም ሽልማት ለጊዜው ቢኖራቸው ዋና የበለጠ ሽልማታቸው እዩ የዚህች አገር ጀግኖች እዩ ጀግኖች እየተባሉ ያገራቸውንና የራሳቸውን ስም ለዘላለም እያስጠሩ ሲኖሩ ነው ። አሁንም እስከ ዘመናችን ድረስ ሰንደቅ ዓላማችንን አቁመው ላቄዩልን ለኢትዮጵያ ጀግኖች የማያልቅ ምስጋና ልንቀርብላቸው ይገባናል።ለነዚሁም ጀግኖች የሚረዳና የኢትዮጵያን ነፃነት ለሚጠብቅ አምላክም ክብርና ምስጋና ይግባው ።

ዛሬም ደኸሙና በኃይለ ሥላሴ ሰንደቅ ዓላማችን ቀጥ ብላ ቆማ ለምናይ ለኢትዮጵያ ልጆች መዓርጋችንና ክብራችን እንደሆነ ማንም አይስተውም።ስለዚህ ከክብረት ወደ ውርደት ከነፃነት ወደባርነት እንዳንመለስ ምሕረታዊ እጁን በኢትዮጵያ ላይ ዘርግቶ ለሚጠብቀን አምላክ ያለማቋረጥ ቀንና ሌሊት ልናመሰግነው ይገባናል ። ግን ቅድም እንደተባለው ያገር ፍቅር የሚፈጸመው ያምን በማፍሰስ ብቻ አይደለም በጉልበት ማገልገል በገንዘብ መርዳት በሌላም ይህን በመሰለ ሁሉ ነው እንጂ ስለዚህ በየስጦታችን ኢትዮጵያ እናታችንን ለመርዳትና ለማገልገል በጣም እንጣጣር በኋላም ለምለሚን አገራችን ወደ ላይኛው ደረጃ ከፍ የሚያደርግ ሥራ ሁሉ ለመሥራት እንደምንችል ጥርጥር የለውም ።

ደግሞ በሥላሴ ቸርነት በመላ ኢትዮጵያ ሰላም ሥር ሰዳ ለችና ይህንም ሥር እንዳማይነቀል ለማድረግ ፍቅር ማፅናትና መስማማት ያስፈልገናል ። የሆነ ሆኖ ዕንወቅ፥ዕንወቅ፥ እጥብቀንም እንመርምር ይህች ሰንደቅ ዓላማችን ምን እንደሆነች ። አቤቱ የእሥራኤል አምላክ የኢትዮጵያን ነፃነት ለዘላዓለም ጠብቅልን፤ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር አሜን ።

ዕድሜ ለደጉ ንጉሣችንና ለደጊቱ ግርማዊት መንግ ይስጥልን አሜን ።

ቀጥሎ ትያትር (ቁም ነገር ያለበት ጨዋታ) ተጀመረ ። ነገሩም አንዳንድ አታላዮች ሰዎች እናውቃለን ። ሀብትም እናቀናለን እያሉ በሞኞች ሰዎች የሚያላግጡትን አኳኋን ነው ከነገሩም ጥቂት እንጽፋለን ።

፩ ሚስቱና ልጁ ታመውበት የተቸገረ ሰው አቶ የጽድቅ ጠላት ወደሚባል ወዳጁ ቤት ሒዶ ሚስቴና ልጄ ታመውብኛልና እባክዎ መድኃኒት የሚአውቅ ሰው ይፈልጉልኝ እርስዎም ያውቁ እንደሆነ ያድርጉላቸው ብሎ ከጫማው ቢወድቅ እሱም እሺ ወዳጄ እረ ዋና የአየር ጋኔን ሳቢ ወዳጅ አለ እሱን አመጣልሃለሁ ብሎት ወዲያው ለዚያ ለጠንቋዩ ወዳጁ ሒዶ ነግሮት ለጊዜው አምስት ብር ይቀበሉና ፩ን ለኔ ይስጡኝ ብሎት ተቀውሎ ባለቤቱን ጠርቶ አጋጥሞት አምስት ብሩን ተቀብሎ ሒዶ በቄደታ በሽተኛይቱን ከባልሽ ከልተፋታሽ አትድኝም ይላታል ። እሷም አድነኝ አልሁህ እንጂ ከባሌ ልታፋታኝ ትፈልጋለህን ብላ ስትጣላው ባልዋ በውጪ ሰምቶ ሲደበድበው ዘበኞች የጠንቋዩን ጩኸት ሰምተው ባለቤቱን ከጠንቋዩ ጋራ አቴራኝተው ወደ ክንቲባው ወሰድዋቸው ክንቲባውም ነገሩን መርምረው ጠንቋዩንና አጋጣሚውን ንስሐ በሚባል ጂራፍ ገርፈው አሥረው በሽተኞቹን ወደ ሐኪም ልከዋቸው ከዳኑ በኋላ ከንቲባው ወደ እቴጌ አቅርበው ከንቲባውንና ሴቲቱን ሸልመው እቴጌ የተናገሩት ቃል የሚከተለው ነው።

እቴጌ ። ወይ ግሩም አንቺ መልካም ሴት የሰይጣን ፈተና ሳያሸንፍሽና ተፈትሆ ሳያገኝሽ የሰይጣንን ፈተና ድል በመንሳትሽ ሰሎሞን በምሳሌው መልካሚቱን ሴት ማን ያገኛታል ከክቡር ድንጋይ ይልቅ ዋጋዋ ይበልጣል የባሏ ልብ ይታመንባታል ምርኮም አይጐድልበትም ያለው ቃል በዘመኔ በንቺ ስለ ተፈጸመና ለሚመጡት ልጆች መልካም አርአያ በመሆንሽ በጣም ደስ ስላሰኘኝ ይህን እምነት የሚባል ልሽን ሸልሜሻለሁ ። አንተም ከንቲባው ሥራህን ተግተህ በመሥራትህና አምልኮ ባዕድ በመጥላትህ በጣም የተመሰገንህና የታመንህ ሹም ነህና ስለዚህ ቅንነት ሰይፈከ ኃያል ውስተ ሐቌከ እንዳለ ክቡር ዳዊት ለኃያልነት መታነቢያ ይህን ሰይፍ ሸልሜሃለሁ። ይህንም ምስጋናህን ለንጉሡ ነገሥት አቀርብልሃለሁ እርስዎም አባቴ ይህችን እውነተኛ ክርስቲያን ሴትና የታመነውንም ሹማችንን እንዲባርኩልን እለምንዎታለሁ ። ብለው በጨረሱ ጊዜ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ቄሱ መረቁ።

አባ። ግርማዊት እቴጌ ሆይ የዚች የሴት ታማኝነት ደስ ያሰኛዎ የውነተኛ አሳብዎ ሕግ ማፅናት መሆኑን ይገልጽልናል።እንደዚሁም ደናግሉ ሁሉ አሳብዎን እንዲከተሉ እጸልያለሁ ይህችም ሴት ያደረገችውን ተጋድሎ በመጽሐፍ የሰማነውን ታሪክ ያሳስበናል ይህም ከንቲባው ያደረገውን ድንቅ ሥራ ትጉህነቱና መልካም ክርስቲያንነቱን ስላሳየን እባርከዋለሁ እመሰግነዋለሁም አንች ሴት እግዚአብሔር ይባርክሽ ዘር ያውጣልሽ፥ዕድሜሽን ያርዝምልሽ፥ ጃንሆይና እቴጌ ሕያዋን ይሁኑ ፤ ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ። አቡነ ዘበሰማያት እንበል። ከዚህም በኋላ የሚከተለውን መዝሙር ዘመሩ ።

መዝሙር ለግርማዊት መነን ።

፩ የኢትዮጵያ ልጆች እልል እንበል ።
መነን ዘውድ ጫነች በሥላሴ ኃይል ።
የመልካም አርአያ ለመሆን አምሳል ።
ድሀ ጠባቂናት እንዳይበደል ።
በላገር መውደዷን ማንም ያውቀዋል ።
ዕድሜዋን ያርዝመው እግዚአብሔር ልዑል ።

ላገር ለሕዝባቸው ጥቅም እንዲሠሩ ።
ጃንሆይና እቴጌ ዘላለም ይኑሩ ።

፪ እዲሲቱ እቴጌ ግርማዊት መነን ።
በውነት ትወዳለች ኢትዮጵያን ።
ገልጻ ለማሳየት የሀገር ፍቅሯን ።
ተማሪ ቤት ሠራች ለልጆቻችን ።
ዕድሜዋን ያርግላት የማቱ ሳላን ።
የሰማችሁ ሁሉ በሉ አሜን አሜን ።

ላገር ለሕዝባቸው ጥቅም እንዲሠሩ ።
ጃንሆይና እቴጌ ዘላለም ይኑሩ ።

መስፍን ቀለመወርቅ ።

ከዚህ በኋላ ሁለተኛው ትያትር(ቀምንገር ያለበት ጨዋታ) ተጀመረ ። ነገሩም ቀጥሎ የሚመጣው ነው ።

አዲሴ ፤ ብርሃኑ ፤ ለማ የሚባሉ ወንድማማቾች የአበ ልማድ ልጆች የነበሩ ፩ ቀን በአንድነት ሲጫወቱ አቶ አወቀ የሚባል ሰው መጥቶ እዚህ በማዶአችን አቶ ሰሎሞን የሚባሉ ከበርቴ ሽማግሌ አሉ ። ለርሳቸውም ጥበብ፡ማስተዋል፡አእምሮ የሚባሉ ሦስት ሴቶች ልጆች አሉዋቸውና አንተ ታላቁ ልጅ አዲሴ ጥበብን ፤ ብርሃኑ ማስተዋልን ፤ ለማ አእምሮን ብታገቡ መልካም ነው ቢላቸው እነሱም ከአባታችን ከአቶ ልማድ እናስፈቅድና ቢወዱ መልካም ነው ባይወዱ ግን እንደምንም ብለን እኒህን ልጆች ሳናገባ አንቀርም አሉና ሲማከሩ ቈይተው አበ ልማድ ታላቁን ልጃቸውን አዲሴን ጠርተው ልጄ እጨዋ ቤት ገብቼ የአለቃ ዘገየን ልጅ አማከለችን አጭቼልሃለሁና አግባ ቢሉት አባቴ ስለ ሐሳብዎ አመሰግንዎታለሁ ። ነገር ግን እኔ የማገባት የአቶ ሰሎሞንን ልጅ ጥበብን ነው እንጂ አማከለችን የአለቃ ዘገየን ልጅ አላገባም አላቸው ። እሳቸውም ወይ የዛሬ ዘመን ልጆች ሁሉን እናውቃለን ትላላችሁ እኔ ያልሁህን ታገባለህ እንጂ ቢሉት ምንም ቢሆን እርሷን አላገባም አላቸው ። አበ ልማድም እኔ ይህን ያህል ስለምንህ እምቢ ካልኸኝ ምን አደርጋለሁ ከወንድሞችህ ለአንዱ አመጣለታለሁና ባይሆንም አደራህን ደግሞ ሶርሱ እንዳታስተምርብኝ አሉት።እሱም እኔስ አላስተምራቸውም እነሱ ግን እሺ ይሉዎ አይመስለኝም አላቸው። ከዚህ በኋላ አዲሴ የፈቀዳትን ልጅ ለማግባት እንዲፈቅዱለት ወደ አባቱ አማለጆች ይልካል። አማላጆቹም ቢነግሯቸው እየተቈጡ የአለቃ ዘገየን ልጅ አማከለችን አግባ ብለው እምቢ ብሎ እኒያን የማልወዳቸውን ሰዎች ልጆች በሰቡብ በሰባብ ብሎ ወደ ሀገሬ ሊያገባብኝ ነውና ምንም ቢሆን አይሆንም አሉ ። ከሽማግሌዎች አንዱ ብላታ ምሕረቱ የሚባሉት አባ ሆይ እንዲህ ያለው አሳብና ወገን ማብዛት ደስ ያሰኛል እንጂ ይህን ያህል ያስቀይማልን ። እባክዎ ይዳሩለት ብለው ቢለምኑ እማይሆንላቸው ሆነ ። ከዚህ በኋላ አዲሴ ለአባቷ ሎሌ ሆኜ ጥበብን ሳላገባ አልቀርም ብሎ ከወንድሞቹ ሲሰነባበት ወንድሞቹ ብርሃኑና ለማ አብረንህ ሔደን እኛም ሎሌዎች ሁነን እንኖራለን ብለው ከአባታቸው ከአቶ ልማድ ተለይተው ሲሔዱ ባሻ ጋረዶ የሚባል ሰው ሔዶ ከመንገድ መልሶአቸው ደጅ ጥናት በሚባለው ሰፈ አዳራሽ አግብተው ጉብ በሚባለው መንቄር አሥረህ ጠብቅልኝ ብለው አበ ልማድ ለአቶ ከልክሉ ሰጥተውት እኒህም ሰዎች እንደታሠሩ ለሊቀ ጠበብት ኃይለ ሥላሴ ጮኸው ከአባታቸው ከአበ ልማድ ጋራ አደባበይ ተቋቊመው ዳኛው ሊቀ ጠበብት ኃይለ ሥላሴ መኳንንቱን ፍረዱ ብሉ ጊዜ መኳንንቱ ተነሥተው የሚከተለውን መዝሙር እየዘመሩ ፈረዱ።

ኢትዮጵያ ተናገሪ የሚለውን መዝሙር ።

አረት ልጆች በየተራ መዘመር ።

የኢትዮጵያ መዝሙር ።

፩ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ ።
በንት ብዬ ልንገራቸው አያጡትም በልባቸው
ኢትዮጵያ እናታችን ታለቅሳለች በፊታችን
፪ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
የናታችን ልቅሶ ያሳዝናል ልማድ እያጠቃት ምን ይሆናል
አደዞሽ አይዞሽ እማማዬ ልማድ ቢቀር ምንተዳዬ
፫ ኢትዮጵያ እናታችን ታለቅሳለች በፊታችን
ሰላምታዬን አቀርባለሁ ጕዳቴንም እነግራለሁ
አንድ ነገር እሱ ይብቃኝ አቶ ልማድ እያጠቃኝ
፬ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
ስምቻለሁ እንዳጠቃሽ ወደ ፊቱ እሱ አይንካሽ
በል ተፈጠም እንዳትነካኝ አገር አጥፊ አንተ ጨካኝ
፭ ነፃነቱ ከታወቀኝ አቶ ልማድ ተው ልቀቀኝ
የጃፓን ሥራ እያማረኝ አቶ ልማድ ይዞ አስቸገረኝ
ከሥራ ላይ ምን አቆመህ ልማድ ልቀቅ ተፈጥመህ
፮ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትችን ለተፈሪ
ልማድ እየፈሩ ከማግደምደም ገፋ ገፋ ብሎ ሥራ መቅደም
በሉ በሉ ተጋገዙ ጠሐይ ወጣ ሥራ ያዙ
፯ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
በሥራ ላይ አግኝተውኝ አበ ልማድ ገዝተውኝ
አበ ልማድ ተዉ ፍቱ በሥራ ላይ አትገዝቱ
፰ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
በአላት ሁሉ ከተሻረ ኑፋቄ መጣ ተጀመረ
ስድስት ቀን ሥራ ሥሩ ሰባተኛው ባል አክብሩ
፱ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
ዓመት ከዓመት ባል ከሆነ ፍጹም ደስታ ለበዘነ
ሥራ ቢቀር ተጐዳነ ሠራተኞች በለጡነ
፲ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
መክበር አይገኝም ያለ ድካም ምንም ቢታክቱ ሥራ መልካም
በርኖስ ለብሶ ከመጓደድ አጭር ታጥቆ ሥራ መውደድ
፲፩ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
የእጅ ሥራ ትቼ ሰማር ተረት ደሞዜ ሆነ ኋላ መቅረት
የእጅ ሥራ የተማሩ በሕሩን በክንፍ ተሻገሩ
፲፪ ኢትዮጵያ ተናገሪ ጕዳትሽን ለተፈሪ
ሁሉም ኃላፊ ነው ጥበብ ቀረ ዕድሜ ይስጠው ለተፈሪ
የሰማችሁ አሜን በሉ ጥበብንም አስተውሉ
፲፫ ዕድሜ ይስጥልን እየለቱ ለተፈሪ ለባለቤቱ
እኔ የሰማሁት የምስራች ጥበብ ሸዋ ገብታ ጐጆ ሠራች
አይዞሽ ጥበብ ጎጆ ሥሪ ልጆችሽን አስተምሪ

የማነ ብርሃን አበራ ዓድዋ ።

ከዚህም በኋላ ዳኛው ሊቀ ጠበብት ኃይለ ሥላሴ እሥረኞቹም ይፈቱ ይህም ደጅ ጥናት የሚባለው አዳራሽ ይፍረስና ሠርቶ መብላት የሚባለውን አዳራሽ እንሠራለን ። ይህንም ጕብ የሚባለውን መንቄር አምጡና በፊቴ አቃጥሉት ብለው አዘዙና በተቃጠለ ጊዜ ሰው ሁሉ ከደስታው ብዛት የተነሣ እልልክ ላቀ ። ምን ይሆናል ማንበብ እንደማየት አይሆን እን- ዴት አድርጌ ላስረዳችሁ ። መቸስ ምን አደርጋለሁ ጥቂት ጽፌ- ላችኋለሁ ቢበዛም ትሰለቹላችሁ። እንግዴህ ወደፊተኛው ነገራ- ችን እንመለስ ። ከዚህም በኋላ ዳኛው ወረቀት ሰጥተዋቸው

ባሕር ተሻግረው ቃላቅ አደሴ ጥበብን ፤ ብርሃኑ ማስተዋልን ፤ ለማ አእምሮን አግብተው በመጡ ጊዜ የሆነው ደስታ እንዲህ አልነበረም ። እኛም ያየናቸው መስሎን እጅግ ደስ አለን ። ከዚህ በኋላ እኒያ ሽማግሌ አባታቸው በዶ ልማድ በሠሩት ሥራ ተጠጥተው ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገሩ ።

ልጆቼ ደጎቼ ማሩኝ ተለመኑኝ
በሠራሁት ጥፋት በጣም ተጸጸትሁኝ
የለት የለት ጥቅሜን እየተመኘሁኝ
ሌሎች ሲበሩ ሲሰፉ እኔ ታች ቀረሁኝ
አሁን ግን ነገሩን እየመረመርሁኝ
ርግማኑን ትቼ መልሼ መረቅሁኝ

ልጆችም ቀጥሎ ያለውን መዝሙር ዘመሩ ።

፲፩ የልጆች መዝሙር ለሊቀ ጠበብት
ኃይለ ሥላሴ ዕድሜህ ይርዘም
እንድትጠቅመን ዘለዓለም
ይጠብቅህ መድኃኔ ዓለም
ሀገርህን አርጋት ለምለም
አንተ ሐኪም አጥፋ ሕመም
ከኢትዮጵያ ለዘላለም

ቀጥለውም እኒያ ያገቢቸው ሙሽሮች ሴቶች የሚከተለውን መዝሙር ዘመሩ ።

፲፪ የሴቶች መዝሙር ላገሩና ለሕዝቡ
ኢትዮጵያ ተቀበይን መጣንልሽ
ታዛጋ ሎሌ ልንሆንሽ
አገልጋይም ለልጆችሽ
እንደ ኮከብ ይብዛ ሕዝብሽ
እንዲፈሩ ጠላቶችሽ
ይጠንክሩ ምሽጎችሽ
አሜን አሜን አሜን
(ጭብጨባ ፩ ጊዜ)

ከዚህ በኋላ የሻይ ግብዣ ተደረገና በሽምፓኝ ጊዜ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ተጨበጨበ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፣ ግርማዊት እመቤታችን

ልዑላን መሳፍንት፣ ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ ።

ይህችን ጨዋታ ለማየት ስለ መጣችሁ በጣም እያመሰገን ከዚህ በታች የተጻፉትን ቃላት እንድናገር ፈቃድ እለምናለሁ። ፩ኛ፣ ቴአትሮ በዓለም ሁሉ የተወደደና የተመሰገነ የተለመደም ነገር ነው።በሀገራችን በኢትዮጵያ ግን የቴአትሮ ጨዋታ እስከሁን አልተለደም ነበር። ደግሞ አንዳንድ በዘፈን በቀረርቶ በንጉርጉሮ በዜማና በግጥም በሌላም በልዩ ልዩ ነገር እያደረጉ የሰውን አሳብና ነገርን ሁሉ የሚገልጹ ሰዎች ቢገኙም አዝማሪ፣ አርሆ፣ ምንኛ እየተባሉ እየተናቁ ነገራቸውም ወደ ቁም ነገር እጅግም አይቈጠር ነበር።አሁን ግን ግርማዊነትዎ የዓለም አኳኋን ያወቁና የመረመሩ ስለሆነ የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ዕውቀት ደረጃ ስለተቃረብንና ታሪክም ስላነበብን ደግሞ አንዳንዶችንም በቸርነትዎ ኤውሮፓን ስላየን ቴአትሮ መጫወትና የግጥም ቃል መጻፍ ጥበብ እንጂ ነውር አለመሆኑን ስለተረዳነው ቴአትሮ መጫወትና ግጥም (ቅኔ) መጻፍ ጀመርን ይኸውም በግርማዊነትዎ እርዳታ ነው እንጂ መጀመሩ እስ-ዚያማ ቢሆን ማን ሊሰማኝ ብሎ ጸሐፊው አይጽፍም።ባለ ቴአትሮውም አይጫወትም ነበር ።ነገር ግን ጃንሆይ የዕውቀት መሪ የጥበብ ጀማሪ ስለሆኑና ማንም ሰው የደግነት አሳብ ሲጀምር ስለሚረዱትና ስለሚፈቅዱለት የሰው ሁሉ ተስፋ እየተዐናና ሔደ ይህም ይታወቅ ዘንድ በመጀመሪ ጊዜ በልዑል አባትዎ ቸርነት የተማሩ ፊ ተክለ ሐዋርያትና ጥቂቶች የኢትዮጵያልጆች በፈረንሳይ ሆቴል ቴአትሮ ቢአደርጉ ግርማዊነትዎ ሔዶ ጉብኙላቸው ሁለተኛ እምነትና ቅንነት የመላባቸው የሀገር ፍቅር እንደሰንሰለት ይዞ የሚጐትታቸው ብልሁ አገልጋይዎ አዛጋ ወርቅነህ ከሽምግልናቸው በኋላ ከኛ ከልጆቻቸው ጋራ ተባብረው አባት ሆነው ፍቅርና አገልግሎት የሚባል ማኅበር አቁመን ማኅበሩ ነፃ ለወጡ ባሮችና እናት አባት ለሌላቸው ልጆች የጅ ሥራ ተማሪ ቤት ለመሥራት በልዑል ራስ ኃይሉ ሆቴል ሦስት ጊዜ ቴአትሮ ብናደርግ ጃንሆይና ግርማዊት እየመጣችሁ ብዙ ቸርነት አደረጋችሁ። ይልቁንም ጃንሆይ ቅድም እንዳልሁት የዕውቀት መሪ በመሆንዎ ከልብስ መንግሥትዎ ላይ ሰባት ቃላት የተጻፉበትን የፍቅርና አገልግሎትን መለዮ መስቀል ማድረግዎ እናቴን ኢትዮጵያን አገለግላለሁ ሕዜቤን በፍቅር እገዛዋለሁ ማለትዎ መሆኑን ገልጸልናል ።

ሦስተኛ በዳግማዊ ምኒልክና በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት በየመቱ በሚዘጋበት ጊዜ መኳንንቱንና ወይዛዝሩን እያመጡ የቲያትሮ ጨዋታ ማሳየትዎ መኳንንቱና ወይዛዝሩ ሕዝቡም የቲያትሮ ጥቅምና አሳብ እንዲገባቸው መሆኑን ያስረዳናል ።

አራተኛ፣ይልቁንም አሁን ባለፈው በሐምሌ ወር በቅዱስ ጊዮርጊስ ትምህርት ቤት ጃንሆይ መኳንንቱን፣ ግርማዊትም ወይዛዝሩን ይዛችሁ በየተራ ቲያትሮውን ማያታችሁ ተማሪ ቤቱን መጐብኘታችሁ ሁለታችሁም እየተረዳዳችሁ የሥልጣኔ መሪ ሐዋርያት መሆናችሁን ይገልጽልናል ።

አምስተኛ፣ አሁን ባለፈው በሐምሌ ፲፰ቀን ስለ ጃንሆይ ልደት ክብር ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት አዘጋጅተው ጃንሆይና ግርማዊት መጥታችሁ በተደረገው ቲያትሮና ይልቁንም እንደናቶቻቸው እንደ ወይዛዝሩ ልማድ ሳያፍሩ ሳይፈሩ በጉባዔው ፊት ያንን ልብ የሚነካ ቃል በመናገራቸው ጃንሆይና ግርማዊት በጣም ደስ እንዲላችሁ የጃንሆይን በተናገሯቸው ቃላት፣የግርማዊትንም በተዋበው ገጽዎ ብሩህነትና ፈገግታ ተረድተነዋል ። ይህም ጃንሆይንና ግርማዊትን ደስ ያሰኘ ነገር ስንኳን ያየውንና የሰማውንም ደስ ያሰኛል። ማለት የታላቅ ወገን የሆኑት ወይዘሮ ቀድሞ ለሴት ወይዛዝር ነውር ይባል የነበረውን ነገር ዕውቀት ነው ብለው መጀመርዎና ለወይዛዝር ምሳሌ መሆንዎ ነው ።ይኸንኑም አርአያቸውን ብዙ ወይዛዝር በቶሎ እንዲይዙላቸው ተስፋ አለን ይልቁንም አሁን ወደፊት በጃንሆይ ዘውድ በዓል ጊዜ ከወይዛዝሩ ውሥጥ አገር የሚያሸሙስግንና ሰውን ደስ የሚያሰኝ የጥ-

ብብና የዕውቀት፣ የክብር ሥራ ለሚመጡት እንግዶች ሳያሳዩ ይቀራሉ ብዬ አልጠረጥርም ።

ስድስተኛ፣ ከላይ እንዳመለከትሁት የጃንሆይን የልደት በዓል ወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ሲያዘጋጁ ሰው ወዳጅ ዘመዱን በሚቻለው መርዳት ስለሚገባው እኔም ክብርት እናቴንበውቀቱ መርዳት ፈቀድሁና ይህችን ጨዋታ አበጅቼ ፡ ዚያችው ክብር በተሰጣት ቀን በጃንሆይና በግርማዊት፣ በመኳንንቱና በወይዘሩም ፊት ጨወታው ታዬ።ጃንሆይ ሳን ሕዝብዎን ማበርታትና ማመስገን ልማድዎ ስለሆነ ይህች ትንሽ ጨዋታ ግርማዊነትዎን ደስ አሰኝታ እንድትደገም በመፍቀድዎ ለምስጋናዬ ወሰን የለውም። ደግሞ እንደዚህ የታናናሽ አገልጋዮችዎ ሥራ ሁሉ ደስ እያሰኘዎ የንጉሡ ነገሥትነትዎን ምስጋና በጉባዔ ፊት ማግኘት ከሁሉ የበለጠ ክብር ስለሆነ እንደዚሁ ይህችን ምስጋና ያዩና የሰሙ የኢትዮጵያ ልጆች ከዚህ የበለጠ እየሠሩ ግርማዊነትዎን ደስ እንዲያሰኙ አይጠረጠርም ።

የመንግሥትዎንም ሥራ ትተው ከዚህ ከላይ በመለከትናቸው ስፍራዎች ሁሉ በመሔድዎ ይደንቀናል ይህም አድራጎትዎ ፍቅር ሰሐበ ለወልድ ኃያል አመንበሩ እንዳለ ደራሲ ለሀገርዎና ለሕዝብዎ ፍቅር ሲሉ መሆኑን ያረዳናል ። ቴያትሮ ስሙ ጨዋታ ቢሆን በውሥጡ ለሀገርና ለመግሥት ጥቅም የሚሆን ቁም ነገር እንዳለው አውቀው ይህንኑ ገልጸው ለሕዝብዎ ለማስታወቅ ሲሉ ማድረግዎን ያሳስበናልና በልዩ ልዩ ቦታ በመምጣትዎ በዚህ ምክንያት ባለፈው የሥራ ጊዜዎ ደስ ያሰኙናል እንጂ አያሳዝነንም ።

ግርማዊት ሆይ ከላይ እንዳመለከትነው ከቤተ መንግሥት እልፍኝዎ ወጥተው በዚህ ሁሉ ስፍራ ከሕዝብ ጋራ ባንድነት መቀመጠዎ ለሀገራችን እመቤቶች አዲስ ልማድ ነው።ግርማዊትም ይህን ማድረግዎ አሮጌውን ልማድ አስወጥተው አዲሱን ሥልጣኔ መያዝዎን ያስረዳናል ። ስለዚህ በጣም እናመሰግናለን ።

ክቡራን መኳንንቶችና ወዛዝር ሆይ?እንደቀደመው ልማድ ቢሆን ሹኳን በንገሥታት ፊትና በሠርግ በተስካር በልቅሶም በሌላም ይህን በመሰለ በጉባዔስፍራ ሁሉ ባልከሚስቱ፣ሚስት ከባልዋ ጋራ ባንድ ቤት ውሥጥ በግልጽ አይቀመጡም ነበር።አሁን ግን በኃይለ ሥላሴ ጊዜ ይኸው ባንድነት የመሰብሰባችሁ መጀመር በጣም ደስ ያሰኝ ደመስለናል ።

ጌቶቼና እመቤቶቼ ሆይ ደግሞም አንድ ነገር አስታውሳችሁ አለሁ አሁን ባየናቸው ጨዋታዎች ውሥጥ ደስ የሚያሰኝና የሚያሳዝን ተስፋም የሚሰጥ ነገር ይታያል፡ ደስ የሚያሰኘው የሁላችንም ደስታ ነው።የሚያሳዝነውም የሁላችን ኃዘን ነው ተስፋውም የሁላችን ተስፋ ነው እንጂ ለማንም የመለዮ ነገርና አንዱንም አንዱን የመዝለፍ የመውቀስ ወይም አንዱን አመስግኖ አንዱን የመንቀፍ ነገር የለበትም።ብቻ ጨዋታው የሚያሳየው የሰውን ጠባይና ኑሮውን ነውና ደጉ የኔ ነው ክፉ የገሌ ነው ተስፋውም አይደረግም እያልን ሳንጠራጠር እርስበርሳችንም ሳንቀያየም በፍቅር ተባብረን የሰማያዊና የምድራዊ ንጉሥን ትእዛዝና ሕግ እየጠበቅን እንኑር ስል አመለክታለሁ።

ዕድሜ ለጃንሆይና ለግርማዊት ለቤት ዘመዶቻቸውም ኢትዮጵያ ለዘላለም ሕያው ትሁን ። መንፍን ቀለመወርቅ ።

ቀጥለው ክቡር አዛዥ ወርቅነህ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ፫ጊዜ ተጨበጨበ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት፣ ግርማዊት እመቤታችን።
ልዑላን መሳፍንት፣ ክቡራን መኳንንትና ወይዛዝር ሆይ።

ጥሪዬን ተቀብላችሁ በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ስለመጣችሁልኝ አመሰግናለሁ። ከዚህም ቀጥዬ የትያትሮን ጥቅምና ትርፍ በጥቂቱ እንድናገር ፈቃድ እለምናለሁ።

ቴያትሮ የሚደረገው ለሶስት ነገር ነው። ፩ኛ ለደስታ ፪ኛ ለጥቅም፣፫ኛ ለትምህርት ነው፣ እንደዚሁ በሠለጠኑት አገሮች በቴአትሮ ሕይወታቸውን ደስ ያሰኛሉ በቴአትሮ ብዙ ጥቅም እያገኙ ትዳር ሁኖዋቸው ይኖራሉ። በዚሁ በቴአትሮ ብዙ ብልሀትና ትምህርት ያገኙበታል እንዲሁ እኛም ይህን ስላወቅነው ለሀገራችን ደስታና ጥቅም ለልጆችም ትምህርት እንዲሆን ብለን ቴአትሮ ጨዋታ ጀምረን፣ በዚህም በጨዋታ ከላይ ያመለከትናቸውን ፫ ነገሮች ጥቂት ጥቂት ያሳየን ይመስለኛል ማለት ስለ ደስታው በሥራ ተጠምዶ የነበረ ሰውነታችን በዚህ ምክንያት አርፈን የምታስቅ ነገር ስናይ ደስ ይለናል።ትምህርትም ለተባለው በቴአትሮ ውሥጥ የጥበብና የዕውቀት ነገር ስላየን ልባችን ብዙ ነገር ተምሯል ጥቅም ለተባለው ምንም እንኳ ራሳችን ባንጠቀምበት በፊት ልጅ መስፍን ቀለመወርቅ እንዳለው ተማሪ ቤት ሠርተን እናት አባት የሌላቸውን ልጆች ጠቅመንበታልና ስለዚህ ቴአትሮ ጥቅም ያለውን ነገር መሆኑን እንወቅ ጥቅም ያለው ነገር መሆኑንም ካወቅን በቴአትሮ ውሥጥ መልካምና ክፉ ጠባይን የሚያሳይ ጨዋታ ስናይ መልካሙን ጠባይ ይዘን ክፉውን ጠባይ ከልባችንለማስወገድ ነው እንጂ ማንንም ለመስደብና ለማስከፋት እንዳልሆነ አስታውቃለሁ አሁን ከዚህ ጨዋታ ምንአልባት ቅር የሚል ነገር ኑሮበት እንደሆነ ይቅርታ እለምናለሁ ።

ይህነን ጨዋታ ለአበጀው ለልጄ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅና ቴአትሮንም ለተጫወቱት ልጆች ከልብ የሆነ ምስጋናዬን በግርማዊነትዎ ፊት አቀርብላቸዋለሁ

ጃንሆይና ግርማዊት ሕያው ይሁኑ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር።አዛዥ ወርቅነህ።

ጨዋታው ተፈጸመ፣ እንግዶችም ከጃንሆይና ከግርማዊት መነን እየተሰነባበቱ ሔዱ ።

፪ኛ መልእክት)የነፍሳዊን ነገር አንድ ጌዜ ልናገር ባለፈው ሳምንት በ፴፫ቍጥር የሥጋዊን ነገርጽፌ ነበርና አሁን ደግሜ የመንፈስዊን ነገር እጽፋለሁ።

(ምሳሌ) መልእክት ወደደግ ሐሳብ ።

ይድረስ ከክቡር እቶ ደግ ሐሳብ የሥራ ሚኒስቴር እንደምን ሰንብተዋል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ በዚህ ዓለም ያማረቤት እሠራለሁ ብዬ ስላሰብሁ ሰውነት የሚባለውን የበሕር ዛፍ እንጨትና ዕድሜ የሚባለውን ቱቦ ገመድ ገዝቼ ነበር።ነገር ግን ይህ ሰውነት የሚባለው የበሕር ዛፍ እን

ጨት ምስጥ የሚባላው በቍሎፈራሽና በስባሽ ስለሆነና ዕድሜ የሚባለውም ቱቻ ገመድ ሲማግሩበት ብጥስ እያለ ሰውን ሁሉ ወደኋላው እየፈነቸረ የሚጥል ስለሆነ ምንም የምድሩቤት ባያ ምር የላይኛው ቤት ሳያምር አይቀርም ብዬ ፎቅ ቤት (ማለት መንግሥተ ሰማያት)ልሠራ አስቤአለሁና ምጽዋት የሚባለውን መሐንዲስ ልከውልኝ በኮንቲራት እንድንዋዋል አመለክትዎታለሁ የሥራውንም ዓይነት እንዲህ ሳደርገው ከጅያለሁ፤ንጹሕ ልብ እሚባለው በታዬ ላይ የዋህነትየሚባለውን መሠረት መሥርቼ ጾም የሚባለውን ሕንፃ ድንጋይ ከጨት እስከ ማታ ሰብስቤ ጸሎት የሚባለውንያ ኖራ ሌሊትና ቀኑን አጠራቅሜ እምነት በሚባለው ሲሚንቶ አስገነባዋለሁ ብያለሁ።ኖምቡም ከለቀ በኋላ ሃይማኖት የሚባለውን ምሰሶ አቁሜ ተዋሕዶ በሚባለው ምስማር መትቼ በላይ ማዘኑን ጩምሬ ትሕትና የሚባለውን ባርግጻ ፍቅር በሚባለው ገመድ አስማግሬ ከዚያ በኋላ ንስሓ የሚባለውን ቆርቆሮ አስከድነዋለሁ ብያለሁ።እንዲሁም የተኰልሁበት ምክንያት ሞት የሚባሉ ታላቅ የንጉሥ መላክተኛ ቀን እመጣ ሌሊት እመጣ እታውቀውምና ተሰናድተህ ቈየኝ ብለው ስለላኩብኝ በዚህ ቶሎ በሚፈርስ በጠማማ ጐዶ ያለምንጣፍ አፈርላይ ተቀምጬ ሳልሰናዳ በድንገት የመጡ እንደሆነ እንዳላፍር ብዬ ነው።ከሳተውም ይልቅ የምፈራው ሕማም የሚባለው ሰው የጠር እንደሴራእቸውና ፃዕር የሚባለው አጋፋሪእቸው በጣም የሚአስጨንቁ ስለሆኑና መቃብር የሚባለውም ሥጋ ቤታቸው ያለሥጋ የማይቀምስ ስለሆነ እንዲያው እባዶቤት ጦም አሳደረን ብለው እጅና እጄን ይዘው እያደፉ ወስደው እክቡር አቶ ሞት ፊት ያቀረቡኝ እንደሆነ ከግርማቸው የተነሣ እደነግጥና መላሴ ደርቆ እንደበቴ ተዩዞ የምመልሰው አጣለሁ ብዬ ነው።አቶ ሞትም በዚህ ነገር ተቈጥተው ግናዝ በሚባለው ሰንሰለት አሥረው መቃብር እሚባለው ዘብጥያ አቈየተው በኋላ ለታላቁ ለግርማዊ ንጉሥ በደሌን ነግረው ሲአል ወደሚባለው ወህኒ አሳልፈው ይሰጡኛል ብዬ ነው የንጉሡም ችሎት በሆነ ጊዜ እስከድሜ ልክህ ድረስ ዘለዓለም ታሥረህ ትኖራለህ ተብሎ ተፈርዶብኝ ገሃነም እሚባለው ታላቅ ወህኒ የገባሁእንደሆነ መውጫ አላገኝምና መሐንዲሱን በቶሎ እንዲልኩልኝ ይሁን። ይኸውም ምጽዋት የሚባለው መሐንዲስ ወደኔ ሲመጣ ንፍገትና ስስት የሚባሉ ጃውሶች እመንገድ ደብድበው እንዳያስቀሩት መስጠትና ቸርነት የሚባሉትን ዘበኞች አስጠብቀዋለሁ ብያለሁ።ሥራውንም አስተካክሎ ተሠራልኝ በደመወዙ ነገር እንዳይቸገር የቀገኘውን ያሀል በየቀኑ ወጭ አደርጋለታለሁ። ነገር ግን ቤቱ ተሠርቶ ከለቀ በኋላ የላይኛው ፎቁ ቤት የዘለዓለም መቀመጫዬ ስለሆነ አሁን ኃጢአት በሚባለው ጕድፍ ተጕደፍድፎ እንዳይበላሽብኝ እላይኛው እፎቁ ቤት (ማለት እሰማይ)መውጣቴ ቈይቶ እምድሩ ቤት ሆኜ (ቁርባን የሚባለውን)ልኳንዳ አድ-ርጌ ከሚስቴ ጋራ በሥጋ ብነግድ ብዙ ትርፍ እንዳገኝ አውቃለሁና አሁን ለጊዜው እላይኛው ቤት ለመውጣት አልቸኰልም።ይኸውም ለመነጌጃ የታረደው በሬ ምንም የተገፈፈ ቢሆንና ደም ቢሰርበው በሬው ከላይ ከደጋ የወረደ ስለሆነ ቍርጡ በረከት አለው።ሥጋውም በንጨት ላይ ተሰቅሎ የዋለ ስለሆነ ከንደሙ ቢበሉት ሕይወት ይሆናል።ሰንበርና መላሱም ባሞት ታሽቶ ሲበላ ለሰውነት የሚስማማና ጤንነት የሚሰጥ ነው።ሙሁም እንዳይቸግር እዚያው እጐኑ ጕድጓድ ተምሶ ጥሩ ውሀ ስለመነጨ ለዓለም ሁሉ ይበቃል ። አሁንም ጌታዬ ሆይ እንደዚህ እንዳሰብሁት በሥጋ እየነገድሁ ጽድቅ የሚ ባለውን ገንዘብ አትርፌ በዚያው በትርፉ (መንግሥተ ሰማያት የሚባለውን)ርስት ገዝቼ ከዚያ በኋላ እላይኛው እፎቁ ቤቴ ወጥቼ በጌትነት ለመቀመጥ አስባለሁና ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ቃል እንዲያደርጉልኝ በማክበር እለምንዎታለሁ። ነገር ግን የልቤን ሁሉ እንዳልጽፍልዎ ይሰለችዎና ሳይመለከቱልኝ ይቀራሉ ብዬ ነው እንጂ ሐሳቤ ይኸው ብቻ ሆኖ አይደለም ወደፊት ቢሆን እንደዚሁ ሐሳቤን ሁሉ ፍጭር ቃል እያደረግሁ እንድጽፍልዎ ተስፋ አለኝ አሁንም ይኸነኑ ያሰብሁትን ሥራ ለመፈጸም ያብቃው ብለው አደርሱኝ አሜን ።

ትስብእተ ወልድ አግዴ ፍርድ ጸሐፊው ።

እ ሚ አ ሳ ዝ ን ሞ ት

የአቶ ወርቁ ደስታ ከድሬዳዋ እስከ አዋሽ የጉምሩክ ሹም ባለቤት ወይዘሮ አየለች በተወለዱ ፳፯ ዓመታቸው በነሐሴ ፲ቀን በወሊድ ምክንያት ሙተው ሥሬሣቸ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። በዕድሜ ሕፃን ስለ ነበሩ ሰው ሁሉ እጅግ አዘኑላቸው።ይልቁንም አምስት ዓመት የሆነው ሕፃን ልጃቸው እየተንሰቀሰቀ ሲያለቅስ እጅግ ያሳዝናል።

የብርሃንና ሰላም ተላላኪ።

የከተማ ወሬ ።

አፍና ቅብቅብ ዘወትር አያበላም። ወንድሞቼ ሆይ።

መልክም መላስ ከመልክዎ ታደርሳለች ። በሰውነት ወሥጥም ገብታ አጥንት ታለመልማለች ። ክፉ መላስ ግን በሰውነት ውሥጥ ገብታ አጥንት ትሰብራለች ።

አቶ ወልደ ኪሮስ ሀብተ ገብርኤል በጃንሆይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቤት በላይኛው ግቢ የታመነ ሠራተኛ ነው ።

በዚሁ ባአቶ ወልደ ኪሮስ ሥራ ውሥጥ አቶ መርድ ጃንሆይ ፈቅደውልኛል ብሎ በማዘዣ ሁለት መቶ ፴፬ ቆርቆሮ፤ ፳ ማዕዘን ሆኖ የተሠራበት ቤት አፍርሼ ልውሰድ አለው ። አሁን ለጊዜው ከብቶች አሉበት ፍጻሜውን ግን ጃንሆይን እጠይቃለሁ ብሎ ቢመልስለት።መቼም ዕለት እኪትናትና አቶ መርድ አቶ ወልደ ኪሮስን ተሳዳቢ ሊሳደበው፤ ተሰዳቢ ሊቀበለው የማይገባ ፤ የባለጌ ንግግር ፤ እንኳን ለተሰዳቢውና ለተሳዳቢውም የማያምሩ ለዛ የሌላቸውንም ስድቦች መራርጦ ጨማመረና ስለ ሰደበው ፤ ነሐሴ ፳፫ ቀን በጃንሆይ ችሎት ተፈርደው አቶ መርድ በሰላሣ ጅራፍ ተቀጣ ። ለትዕግሥተኛና ለደካማ ግርማውና ጕልበቱ መንግሥት ነው ።

ወንድሞቼ ሆይ አፋችሁን ጠብቁ አሁን ከዚህ በስድብ ከቈሰለውና በጅራፍ ከቈሰለው አካል የትኛው ጐን ይታመም ይመስላችሁኋል ? አሁንም ባለፈው ወራት የአላየኸውንና የአልሰማኸውን አታውራ ብሎ ብርሃንና ሰላም በአዋጅ ቃል መክሮ ነበር ። ይህን የአየህ ተቀጣ።የአየህ ይራድ ወንዴ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኩ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኤዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛውለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፤ የልብ፤ የደረት፤ የጕበት፤ የኵላሊት ፤ የጅማት፤ የጨብጥ፤ የቂጥኝና፤ የቋቋቻ፤የሚያዋልድ፤ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፤ የርሻ የፋብሪካ፤ የደን፤ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቴክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ያገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ደ.ር አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል። ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው። ይኸ በዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነ ባርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል በ ፈ ፈርናዲ ስናልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
6me ANNÉE № 37

ሐሙስ መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 11 SEPTEMBRE 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix".

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ከአዲስ አበባ ወደ አዋሽ ።

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የቄላውን አዝመራና የጣቢአውን አኳኋን ለማየት በነሐሴ ፳፰ቀን ከማታው በ፩ሰዓት ከታላላቆች መኳንንት ራስ ሥዩምን ጨምረው ከጥቂት ሰዎች ጋራ በባቡር ተሳፍረው ገናኅህ ሲቀድ በ፲፩ ሰዓት አዋሽ ጣቢያ ደረሱ ጥቂት ዕረፍት አድርገው ቈዩና ወደ በርሃ ገብተው ሲአድኑ ውለው መልከቻው የሚአማምር ፺የዱር እንስሶች ገድለው እዚያው አድረው በነጋው ከአዋሽ ጣቢያ በባቡር ተሳፍረው በ፫መንገዱ ዳር ያለውን የእህል ቡቃያና ቢሾፍቱ ያለውን አዝመራና በአቶ ተሰማ እሼቴ ሹምነት የሚሠራውን ሆቴል ዓይተው ከማታው በ፪ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ ።

ከአዲስ አበባ ወደ ቢሾፍቱ

በጳጕሜ ፪ቀን አቶ ተሰማ እሼቴ የደከሙበትን ጅምር ሊአሳዩን ከወዳጆቻቸው ፫ ሰዎች ጠርተውን እሑድ በ፺ሰዓት በባቡር ተሳፍረን ወደ ቢሾፍቱ ወረድን ፱ ሰዓት ሲሆን ቢሾፍቱ ገባንና የእህሉን ቡቃያና የአትክልቱን ቡቃያ ሁሉ የበርበሬውንና የሽንኩርቱን አበቃቀል በመልካም ሁኖ የተሠራውን የክብት ቤት አይተን ለሰው እንደ ማያስቸግር ሁኖ በተሠራው መንገድ ወደ ባሕሩ ወርደን በባሕሩ ዳር ዳር የተተከለውን ወይንና ቡን ሌላውንም የሚበላ አትክልት ሁሉ ስናይ አምሽተን ተመልሰን በመልካም ተጋብዘን አድረን በጧት ወደ ባሕሩ ወርደን ዋናም እምናቅ ዋኝተን እማያውቁም ገላቸውን ታጥበው ወደ ቤት ተመልሰን ምሳችንን ተጋብዘን ፺ሰዓት ተሩብ ሲሆን በባቡር ተሳፍረን ፱ሰዓት ሲሆን አዲስ አበባ ገባን ። ዝናም የጨማመረለት እንደሆነ እንደቡቃያው ማማሬ ብዙ እህል እናገኛለን። አቶ ተሰማ እሼቴም የሚአሠሩት አዲሱ ሆቴል እጅግ ደስ የሚአሰኝ ትንኝ የሌለበት ነፋሻ ነው ተጨርሶ ለአየው እጅግ ደስ ይለዋል ። ወይ ጉድ ለቦታም ዕድል አለውን። ዝቋላ ያን የመሰለ ዓለም የሚአውቀው ተራራ መንገድ ሳይወጣለት ይህ ያልታወቀ ቦታ እንደዚህ ያለ ዕድል ማግኘቱ ያስደንቃል ። ምንም ለዝቋላ ሳይታሰብለት ባይቀር በሩቅ ከሚታየው የማይታየው መቅደሙ አስደነቀን እንጂ ዝቋላም የማይረሳ መሆኑ አይጠረጠርም።

የጃንሆይ መልካም ሥራ።

ነሐሴ ፳፱ ቀን የስልክና የፖስታ ቤት ውስጥ ሹም አቶ ወልደ ማርያም ከማታው ሩብ ሰዓት ሲሆን ጕረቤቶቻቸውን ሁሉ ሲጠሩ ፤ እኔም ተጠሪ ቼ ነበር ። መሽቶ ነበርና ለምን ጠርተውኝ ይሆን እያልኩ እየተከዝሁ ስሔድ እውጭው በራቻው አጠገብ ስደርስ፡እንደኔው የተጠሩ አቶ ወልዳረጋይ የሚባሉ ጠበቃ ተጠርተው ኖሮ ተገናኝተን ሰላምታችንን ከተነጋገርን በኋላ ዛሬ አቶ ወልደ ማርያም ለምን ጠርተውን ይሆን ብዬ ብጠይቃቸው፤እኔም ጨንቆኛል ። አቶ ወልደ ማርያም እየጠሩ የሚጋብዙን ለድሆች ዝክር በደጋጉ ቀን ነበር ቀኖቹንም እኛው በልማድ እናውቃቸዋለን።ዝክራቸውም መድኃኔ ዓለም፣ ሥላሴ፣ መስቀለ ክርስቶስ፣ ማርያም፣ ኪዳነ ምሕረት፣ቅዱስ ሚካኤል የቀሩትንም በዓሎች በምንጋበዝበት ቀን እናውቃቸዋለን እየተባባልን ስንጫወት እቤት ደረስን ። በገባን ጊዜ ከኛ በፊት ለገቡ ጕረቤቶች መጠጥ ሰጥተዋቸው ታላቅ ደስታ አድርገው ደኅስን እኛም ፩ ፩ ድ ብርጭቆ እንደያዝን አቶ ወልዳረጋይ የተጠሩት ለጥብቅና መወያየት መስኳቸው የተጠራሁበት ነገር ምንድነው ምንስ ነገር አገኝዎ ብለው አቶ ወልደ ማርያምን ቢጠይቋቸው አሽከሬን በውቀቱን እቃ ግዛ ብዬ አቡዋራ ገበያ ልኬዋለሁ። እሱ ሲመለስ እነግራችኋለሁ ብለዊቸው የሰጡንን ስንጠጣ

ጥቂት ቆይቶ በውቀቱ የሚባለው አሽከራቸው በኩታው ታቅሮ ጥሩ ጥሩ የኤሮፓ መጠጥ ይዞ መጣ። ከዚህ በላኋ ከተገዘው መጠጥ ለተሰበሰብነው ጕረቤቶች ሁሉ ከታደለ በኋላ ፡ ክቡር አቶ ወልደ ማርያም ቆሙና ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ተናገሩ። እናንተ ወንድሞቼ ጕረቤቶቼ አሁን ከመሸ የጠራኋችሁ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያደረጉልኝን ውለታ ሁሉ ባጭሩ እነግራችኋለሁ ብዬ ነው። ከዚህ ቀደም በ፲፱፻፲፰ ዓ ም በስልክ ቤት ሥራዬ ባውሥጤ ሆኖ የሚሠራ ገብረ እግዚአብሔር የሚባል ሰው ያልሠራሁትን የሐሰት ቃል ጽፎ ፈርማዬን አስመስሎ ፈርሞ አቶ ወልደ ማርያም ታማኝ አሽከርዎ አይደለም መንግሥትዎን የሚበድል ወረቀት በቍጥር ቃል እየጻፈ ይላላክል እውነቱንም እንዲረዱት ይኸው ፈርማው ብሎ ቢሰጣቸው ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥበብ የሞላባቸው ናቸውና በረቂቅ አእምሮአቸው ነገሩን መርምረው ወረቀቱን የሰጣቸው ገብረ እግዚአብሔር ራሱ የሐሰት ቃል ጽፎ የኔንም ፈርማ አስመስሎ መፈረሙን አሳምነው እችሎት አቅርበው በብርቱ ቅጣት ቀጥተው ። እኔን የቀኛዝማች ማዕርግ ሽልማት ሸልመው ደስ አሰኙኝ። ይህንን ታላቅ አእምሮዋቸውን ። ያየ ሕዝብ ሁሉ ሺህ ዓመት ያንግሥልን ብሎ መረቀ ። እኔም ይህንን የሠሩልኝን ቸርነት ሳልረሳ ዘለዓለም በሆዴ ይዤ ስኖር በየጊዜው ከሚያደርጉልኝ እርዳታቸውና ቸርነታቸው በቀር ዛሬ አልፍኝ አደራሽ ግብር አድርገው ፡ ነበርና እኔም ወደ ግብሩ ለመብላት ሔድሁ ። ነገር ግን ቀድሞ አብረን በመሶብ የምንቀ በው ባልንጀሮቼ ቀድም ብለው ገብተው ኖሮ አጋፋሪዎቹም ሥራ በዝቶባቸው ፡ እኔም አልጋፋም በማለት ዘግይቼ እግብሩ ገባሁ ። ቀድሞ እቀመጥበት የነበረውን ስፍራ በፊት የገቡት ተቀምጠውበታልና ዝም ብዬ አጠገቤ ከገኘሁት ገበታ ተቀምጬ ስበላ ርኅሩኁና አስተዋዩ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥለሴ በክበረ ዙፋናቸው ላይ ሆነው ከሩቅ ተመልክተው አስጠርተው አጠገባቸው በመሶብ በላሁ ጠገብሁ። ወንድሞቼ ሆይ የሠሩልኝን ችሮታ ሁሉ አያችሁን። እግዚአብሔር እንደ ዚሁ ያለ ቸርና ርኅሩኅ ተመልካች ንጉሠ ነገሥት አነገሠልን። እስቲ ተመልከቱት ፡ ከዚያ ሁሉ ሕዝባቸው መካከል እኔን እንደ ድኃ መመልከታቸውን እሉና እየመላለሱ እኔን እንደ ድኃ ። እኔን እንደ ደኃ ሲሉ ከደስታ ጋራ እንባቸው በጕንጫቸው ላይ ሲወርድ ይታይ ነበር ።ከዚህ ቀጥሎ አቶ ወልደ ረጋይ እኔም ሥራዬ እችሎት መዋል ነውና የጃንሆይን የተከ ከለ ፍርዳችውን ሁል ጊዜ በመስማት ዘወትር ደስ ይለኛል ። ምን ለኔ ብቻ መላው ኢትዮጵያ ዐሕይ ወጣለት እንጂ እያሉ እዚያ ያለው ሰው ሁሉ ጃንሆይን በመመረቅና በማመስገን ሲሻማ ቈየና አቶ ወልደ ማርያም ቆመው ሲናገሩ ፡ ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ ማርያም እንዳልካቸው አብረው ቆመው ነበርና ቀጥሎ የተጻፈውን አጭር ቃል ተናገሩ።እናንተ ባሎቻችን ስትሾሙ ስትሸለሙ ደስ ሲያሰኛዋችሁ ሁሉ አብዝቶ ደስ የሚለን እኛን ሴቶቻችሁንና አሽከሮቻችሁን ነው ። አሁንም ይህ የተናገራችሁት የጃንሆይ ቸርነት ሁሉ ለኛም ለሴቶቹ ታላቅ ደስታችን ነው።ስለዚህ ለንጉሠ ነገሥታችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለግርማዊት መንን ረጅም ዕድሜ ይስጥልን መንግሥታቸው ለልጅ ልጅ ይሁን ሲሉ እዚያው የነበሩ ቄስ ጃንሆይን በጣም መርቀው በነገራቸው መጨረሻ አሳርገው ተሰብስበው የነበሩ ጕረቤቶች የቀረበላቸውን ተጋበዘው ደስ ብልዋቸው እግዚአብሔር የጃንሆይን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥታቸውን ጽንዕ፡ግዛታቸውን ሰላም ያድርግልን እያሉ እየመረቁ ሔዱ ።

ክቡሩን የብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ ይህን የጃንሆይን መልካም ሥራና ያቶ ወልደ ማርያምን ደስታ ስጽፍ የነገሩ ፍሬ መልካምነቱን እንጂ ያልታረመ የኋተት ቃል ቢኖርበት ይቅርታችሁን እለምናለሁ ።

ገቶ ወልደ ማርያም ጋሼ ደስታ ከተከራሉት ። (አንዱ ።)

ማመልከቻ ለኢትዮጵያ ልጆች ።

የኢትዮጵያ ልጆች በውጭ ሀገር ቋንቋ እንደ ሠለጠኑ። ደግሞም በዓረቢ ቋንቋ ቢሠለጥኑ እጅግ መልከም ነው።ይልቁንም በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ኢትዮጵያ ከታላላቆች ነገሥታት ማኅበር አንድ ስለሆነች ።

ምስርና ኢትዮጵያም በሃይማኖትና በፍቅር ስለተባበሩ ዓረቢ ትምህርት ያስፈልጋል ። ደግሞም የኢትዮጵያ የሃይማኖት መጻሕፍት ብዙዎቹ ወደግዕዝ የተመለሱት ከዓረብኛ ነውና ለዚሁም ማስረጃ በጥቂቱ ማቴዎስ ም ፲ቍ፴፪ ወዘአስተየ ለሐዱ እምእሉ ንዑሳን ጽዋዓ ማይ ቆሪር በስመ ረድእ አማን እብለክሙ ኢየኃጕል ዓስበ የሚለውን የጥንቱ በጅ የተጻፈው ግዕዝ በስመ ረድአየ ይላል የን ጨምሮ ። ዓረቢውግን በስመ ረድእ ይላል እንደዚሁ ያለ ለመጻሕፍታችን የሚረዳና የሚስማማ ብዙ አለ ።

በዙሪያችንም ያሉ ሕዝብ ጕረቤቶቻችን የሚበዙት ቋንቋቸው ዓረብኛ ስለሆነ ትምህርቱ መልካም ነበር ። ይህነንም ለክቡሩን ጌቶቼ ለኢትዮጵያ ልጆች ለማመልከት ያነሳሳኝ ብርሃንና ሰላም ፮ኛ ዓመት ቍጥር ፴፫ ፪፻ ፴፮ ገጽ ስለፍከሬ የተጻፈውን መልስ ስላየሁ ነው ። ነገሩ ደግ ነበር ።ስንኳን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥልጣን የያዙ መጻሕፍት መርማሪዎችና ወታደሮችም ቢሆኑ ዓረቢ ቋንቋ ለማወቅ ቢተጉ የሚያስፈልጋ መሆኑን ማንም አይስተውም ። ግን መልስ ለመስጠትና ወይም ምስክር ለመሆን የሁለቱን ቋንቋ ግሡንና ነባሩን ቅኔውንና ንግግሩን በጣሙን ለይቶ ማወቅ ይገባል ። ዓሊምተ ሸይአን ወነሲተ አሺየአ ። አንዱን ነገር አውቀህ ብዙ ነገር ረሳህ እንደተባለው ምሳሌ እንዳይሆን ። በዓረብኛው ፈከረ ማለት አሰበ ዩፋኪሩ ያስባል ማለት ነው ። በጕሮሮ ፈኸረ ማለት ግን ለፋከሬ አገባቡ አይደለም ። ፈከረሲል ግሱ ኢፍተኸሩ የፍተኺሩ ነው።ይህም ከሆነ ፈከረ ማለት ከዓረብኛና ከግዕዝ ተያይዞ የመጣ አለመሆኑን ያስረዳል።ራሱን የቻለ ጥልቅ አማሪኛ ቋንቋ ነው።ይኸውም ሊታወቅ የኢትዮጵያ ጀግኖችና አርበኞች።የሀገራቸውን ክብር ስለ መጠበቅ አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው የሃይማኖታቸውን ጽናት የኃይላቸውን ብርታት ። በዘመኑ ለተቀባው ንጉሠ ነገሥት በግልጽ የሠሩትን ኃይል አስታውቀው የድካማቸውን ዋጋ ከእግዚአብሔርና ከን–

ጉሥ የሚቀበሉበት ነው በጦርነትም ጊዜ በእውነት የሠሩትን ኃይል በግልጥ መናገር እንደሚገባ መጻሕፍት ነግረውናል። መዝሙር ፲፯ቍ ፴፱ ለሰልፍ ኃይል ታስታጥቀኛለህ፥ በላዬም የቆሙትን ሁሉ በበታቼ ትጥላቸዋለህ እንዳለ ። ግን ፈከረ አሰበ ነው ብለን በለጻፍን ፈከረ ተረጐመም ቢባል ምሥጢሩ ያስኬዳል እንዳረቢው ቅኔ ።

ኢነልከላመ ለፈፋልፉአዲ ወኢነማ ። ጀኢለለ ሳኑ ዓኒልፉአዲ ደሊላ ። የዚህም ትርጉሙ ንግግር በልብ ነው እንደበት ግን ለልብ ትርጁማንና መሪ ነው ማለት ነው ።

በእውነትም ሰው በልቡ ያሰበውን በአንደበቱ ይናገራል ስለዚህ ፈከረ አሰበ ያልነው ተረጐመ ቢባል መልከም ነው። ለሁሉም ነገር በሥራቅና በምዕራብ በሰሜንና በደቡብ ላለው ባዓረቢ ቋንቋ ለሚናገር ሁሉ ለቋንቋቸው መሠረት የሆነ በየነቃቀፉም ጊዜ የሚመሰከሩበት ቃሙስ አልሙሒጥ የሚባል ቋንቋ መፍቻ፥ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለዚሁ ሥራ ለተማሪ ቤት አርዳታ ሲሉ ያስገዙት አሁን ለጊዜው እኔ ዘንድ ይገኛልና እንደዚሁ ለአስቸገረ ነገር ሁሉ ብንመለከተው ይመችናል እኛም ሐሳባችን እኔ አበልጣለሁ ። ሰውን እነቅፋለሁ ለማለት አይደለም ። በየዓይነቱ ትምህርት ስንፍ እንዳይገባንና ልጆች እንዲነቁ ሀገራችንን ለማሠልጠንና ለማስከበር ነው።

ቃዛጛ አሽከራችሁ ዓረቢ አስተማሪ ወልደ ሥላሴ።

ምክር ።

በ፳ኛው ዓመት በቍጥር ፴፬ ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ አለቃ ቀጸላ የጻፉት የምክር ቃል ቢደረግ መልክም ነው ።

እኔም ብዙ ቀን ሳስበው እኖር የነበረውንከዚሁ አያይገር ልጽፍ ጀመርሁ ።

፩ኛ ክፍል ።

ልዩ በሆነ ስፍራ ፩ ዋና ሰው አድርጎ ከሀናትን እየተቀበለ ማረፊያ ቦታ ሰጥቶ የትምህርቱን ነገር ጠይቆ በቶሎ በቅርብም በሩቅም አገር ማደሪያው ለአገረ ገዢው እየተጻፈ ለማስተማር መንኩ በየጋሳው አገርም ሁሉ መምህራን እንዲበዙ ማድረግ ።

፪ኛ ክፍል ።

በአገራችን ለመድኃኒት የሚሆኑ ብዙ ዕፀዋት አሉና እንድ አለቃ አድርጎ ቦታ ለይቶ የሀገራችንን ሐኪም ማድረግ ። የጥንቈላ ሥራ እናውቃለን እያሉ ለማታለል የሰውን ገንዘብ የሚበሉትን የመርዝንና የክፉውን ሥራ የሚሠሩትን በየአገሩ እየፈተሸ የሚያጠፋቸው ብልሁን የፈውስን ነገር የሚያውቀውን እየመረጠ የሚያደርግ ያስፈልጋል ።ደግናውና መጥፎው ሳይለይ ሁሉም በጠንቋይ ስም መጠራቱ ደግ አይደለምና ከመንግሥታችን ፈቃድ ባገኙ ሐኪሞቹን ለይቼ ለማቆም እችል ነበር ። ለፈውስም የሚሆነው መዝገብ በመንግሥት እጅ እንዲሆን ።

፫ኛ ።

የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንደ መጽሐፉ እየታየ እንዲደረግ፥ ሥጋ ወደሙ የሚቀበሉትና የማይቀበሉ ሁሉም ተጋፍተው መቆም ነውና ተቀብዩና ደጅ ጠኚው በየቦታቸው እንዲቆሙ ማድረግ ያስፈልጋል ። ቤተ መንግሥት በከልካይ ብዛት ያልተጠራ እንዳይገባ ተጠብቆ በሥርዓት ፀንቶ ይኖራል። የቤተ ክርስቲያንም አጋፋሪው ሊቀ ዲያቆኑ ወደቅድስት እየጠራቸው እስኪያቀርባቸው ወደቅድስት ማንም እንዳይገባ ሰክርያን ወዘማውያን ኢይበውእዋ ለመንግሥተ እግዚአብሔር ተብሎ እንደ ተጻፈው ሁሉ እየተደፋፈረ ማንም እንዳይገባ ጳጳሳትና መምህራንም በማስተማር በንጉሥም አዋጅ በከልክይም ፅናት ቤተ ክርስቲያን እንድትከበር ማድረግ ። የጋብቻም ነገር በየአገሩና በየ አጥቢያው የሚኖሩትን እየተመራመረ የሚጠባበቅ የመንፈሳዊ ዳኛ የተማረ ማድረግ ። መሸታም ይቅር እንዳይባል መንገደኛና ችግረኛ ገዝቶ እንዲበላና እንዲጠጣ ደግ ነውና በወንድ እጅ ወይም በባልና ሚስት እጅ አድርጎ አመንዝሮችን ማስወጣት፥ ለሕዝብ ጉዳት ሆነዋልና፤ እግዚአብሔርም የኃጢአትን ብዛት ብየ ጊዜ ጦርነት ፥ረኃብ፥ መቅሠፍት ፫ን ነገር እያፈራረቀ ለዓለም መቅጫ አድርጓልና ከማየ አይኅ ወዲህ ፥ በዚሁ እንዳይቀጣን እግዚአብሔርን ፈርተን የንጉሥን ትእዛዝና አዋጅ ጠብቀን እርስ በራሳችን ተፋቅረንእንድንኖር መምህራን ይብዙ ። ባገር ቤት የሚኖሩ ሴቶች ባላቸውን እየፈቱ አዲስ አበባ እየመጡ ጠጅ እየሸጡ መቀመጥን ወደዱና ሁለት የቄሰኝ ሚስቶች ቤታቸውን ዘግተው ቢሸፍቱ በባቡር ተሳፍረው ሊመጡ ሲጠባበቁ ባሎቻቸው ደርሰውባቸው በዕርቅ ይዘው መለሷቸው ። የትልትሔዱ ኑሩዋል ቢሏቸው አዲስ አበባ ጠጥተን መሸታ እየሸጥን ልንቀመጥ ነበር አሉ ። የሴቶች መሸታ መሸጥ ቢቀር ደግ ነበር የምንለው ለከተማም ወታደር ለባላገርም አራሽ ደግ አልሆነም ብለን ነው ።

ቄም ጸሐፊ ገብረ ጻድቅ ።

ከንግድ ሥራ ክፍል የመጣልን ማስረጃ ።

ስለጨው ዋጋ መወደድ ።

ከውጭ አገር ወደ አገራችን የሚገባው የንግድ ዕቃ ሁሉ በየዕለቱ እየተወደደ ሲሔድ እናያለን።እንደዚሁም የጨው ዋጋ በኢትዮጵያ ስለተወደደ ብዙ ሰዎች ምክንያቱን ባለማወቅ ተደናግጠው ይህ የሆነበት ምክንያት ከውጭ አገር የሚመጣውን የጨው ንግድ ሥራ በተለየ« ፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ሥራ ማኅበር » ለሚባለው ማኅበር ብቻ ስለተሰጠ ነው እያሉ ያወራሉ ማለትን ስለሰማን በስሕተት መንገድ ያሉትን ሰዎች ለመመለስ ከውጭ አገር እንደሚመጣው የንግድ ዕቃ ሁሉ ጨውም የተወደደበትን እውነተኛ ምክንያት ለማስረዳት ፈቀድን። ይህነንም በቃል ብቻ አይደለም ቀጥሎ በተጻፉት በግልጽ በሚታዩ ቍጥሮች እናስረዳለን።

በዓለም ሁሉ ውስጥ ባለው ገበያ የብር ዋጋ እጅግ ተዋርዶ ስለረከሰ በአገራችንም በደምብ የቆመ የራሳችን ገንዘብ የሆነ የመገበያያ ብር ስለሌለን፥ እስከ ዛሬም ድረስ የምንገበያይበት ገንዘብ የማሪ ቴሬዝ መልክ የተሳለበት የውጭ አገር ብር ስለሆነ ገንዘባችን ሁሉ የብርን ዋጋ መርከስ መከተል ግድ ሆኖበት በአገራችን ውስጥም ያለው የብር ገንዘብ ሁሉ በመቶው መቶ ዋጋውን አጣ፤ እነሆ የዛሬ ዓመት ሽረፍ ባንድ

ብር ከ፲፩ ፍራንክ እስከ ፲፪ ፍራንክ ድረስ ይመነዘር ነበር አሁን ግን ባንድ ብር ከ፯ ፍራንክ እስከ ፮ፍራንክ ብቻ ይመነዘር ጀመር። ስለዚህ የዛሬ ዓመት መቶ ኪሎ የሚመዘን ፩ጆንያ ጨው እንዱ አዲስ አበባ ላይ ዋጋው ዓሥር ብር ያህል ነበር በፍራንክም እንደምንዛሬው ፻፲ ወይም ፻፳ ፍራንክ ይሆን ነበር ዛሬ ግን መቶ ኪሎ የሚመዘን ፩ጆንያ ጨው አዲስ አበባ ላይ ፲፯ ብር ተኩል ይሸጣል በፍራንክ ምንዛሬውን እንዱን ብር በ፮ፍራንክ ሒሳብ ብናስበው የ፻፭ፍራንክ መሆኑነው። «በፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ማኅበር »ጨውን የሚያመጣው ከጅቡቲ ስለሆነ መሠረት አድርጎ የቆመበትና የንግዱን ሥራ የሚሠራበት ዋና ገንዘቡ ፍራንክ ነው ስለዚህ የጨውንም ዋጋ እንደውኑ ቃል ሲወስን የብርንና የፍራንክ ምንዛሬ መውጣትና መውረድ እየተከተለ መሆኑ በግድ የሚያስፈልገው ነው። ስለዚህ በፍራንክ ሒሳብ የዛሬ ዓመት መቶ ኪሎ የሚመዘን ፩ጆንያ ጨው ተሸጠበት ዋጋና ዛሬ መቶ ኪሎ የሚመዘን ፩ጆንያ ጨው የሚሸጥበትን ዋጋ ብናመዛዝነው ማኅበሩ ከቆመ ዠምሮ ከዋጋው በመቶ ፭ አጕድሎ መሸጡን በግልጽ እናያለን ፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ማኅበር እሱ ብቻ ጨው ከውጭ አገር እንዲያመጣ የውሉን ፈቃድ ሲቀበልና የብር ዋጋ ሲረክስ ሁለቱ ነገር በመጋጠሙ ነገሩን መርምሮ ላላወቀው ሰው የጨውን መወደድ ምክንያት በዚህ ውል መሰጠት ለማድረግ አሳሰበው እንጂ በእርግጥ በብር ሒሳብ ዛሬ የጨው ዋጋ የተወደደበት እውነተኛ ምክንያት በአገራችን ስንገበያይ-በት የኖርንበት ብር በመርከሱ ብቻ መሆኑ ከቶ አይጠረጠርም።

ይልቁንም ይህ የጨው ውል ለዚህ ማኅበር በመሰጠቱ ምክንያት ከውጭ አገር የሚመጣው ጨው ሁሉ የሚሸጥበት ዋጋና የሚያገኘውም ትርፍ ልክ በቍርጥ ተወስኖ በውል የታሠረ ባይሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ ጕዳት ያገኝን ነበር ። በእንደ ዚህ ያለ የንግድ ዕቃ የሚነግዱ አትራፊዎች ሁሉ የብርን ምንዛሬ መርከስ ምክንያት አድርገው ከዚህ ቀደም እንዳደረጉት ሁሉ ከውጭ የሚመጣው ጨው በሙሉ በጅምላ ገዝተው ከገበያው ጨው እንዳይገኝ አድርገው ዋጋውንም የተቻላቸውን ያህል ወደላይ አውጥተው አስወድደው የፈቀዱትን ትርፍ ለማግኘት ሳይጥሩ አይቀሩም ነበረ ። ነገር ግን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ማኅበር የኢትዮጵያን ጨው ሳይነካ እርሱ ብቻ ጨው ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ እንዲያገባ ልዩ ፈቃድ ሲፈቅዱለት በውሉ ከተጻፉት ግዴታዎች ሁሉ ይልቁንም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፉትን ሁለቱን ግዴታዎች በውሉ አስቀብለውታል።

፩ኛ ፤ ፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ማኅበር ለምግብና ለሥራ የሚሆነውን ጨው ለአሁንና ለወደፊትም ለአገሩ የሚያስፈልገውን ጨው ሁሉ ሊያመጣ ግዴታ አለበት ።

፪ኛ ፤ ፍራንኮ ኢትዮጵያ የጨው ንግድ ማኅበር ጨው የሚሸጥበትን ዋጋና የሚያተርፈውም ልክ በቍርጥ ተወስኖአል ከዚህ በቍርጥ ከተወሰነው ዋጋ በላይ ለመሸጥ በፍጹም ክልክል ነው ። ስለዚህ አትራፊዎች የሆኑት ነጋዴዎች ጨውን በጅምላ ገዝተው በገበያ እንዳይገኝ አድርገው ዋጋውን አስወድደው ጨውም ለሕይወት በግድ የሚያስፈልግ ስለሆነ ሕዝባችንም በሆነው ዋጋ መግዛቱ አይቀረም ነበር ፤ ነገር ግን እንደዚህ ያለውን ጊዜያት እየጠበቁ በአገሩ ሕዝብ ላይ ብዙ ትርፍ ለማትረፍ ለሚያስቡት የአንዳንድ ነጋዴዎች ሐሳብ እንዳይፈጸም ማኅበሩ በውሉ በተቀበላቸው ከዚህ በላይ በተጻፉት በሁለቱ ግዴታዎች ተጠብቆ ይኖራል ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሕዝባቸው ጥቅም እንዳይነካ ተጠብቆ እንዲኖር ያደረጉት ውል ምክንያት አንዳንድ የውጭ አገር ነጋዴዎች ከዚህ በላይ በመለከትነው ዓይነት ሠርተው ለማግኘት ያሰቡትን ትርፍ ባለማግኘታቸው ተቈጭተው ጨው የተወደደበት ምክንያት ውሉ ለማኅበር በመሰጠቱ ነው እያሉ ያስወራሉ ነገር ግን ይህ ያለመሆኑ ከዚህ በላይ ባስረዳነው ቃል በእርግጥ የታወቀ ነው ። ምክንያቱ እጅግ የሚያሳዝን ገንዘባችን አድርገን የኖርንበት ብር በመርከሱ ምክንያት መሆኑ አይጠረጠርም ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም ብራችን በመርከሱ ምክንያት ለመጣብን ጕዳት ሁሉ እንደተቻለ በቶሎ የሚያስፈልገውን ሊያደርጉልን ቍርጥ ሐሳብ ማድረጋቸውን እናውቃለን ይኸውም ለመላው ኢትዮጵያ መድኀኒት የሚሆን የቍርጥ ሐሳባቸውና የድካማቸው ፍሬ በጥቂት ጊዜያት ተፈጽሞ እናየዋለን ስንል በሙሉ ተስፋ እንጠብቃለን ።

መርሐ ዕውር ።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ቢቈጠር ፯ሺሕ ፬፻ ፳፫ ሆነ በዘመን ሉቃስ ። ጌታችን ግን ከመቤታችን ከተወለደ ሺሕ ፱፻ ፳፫ ዘመን ሆነ ። ከጌታችን ልደት ወዲህ ያለው ዓመተ ምሕረት ዓመተ ሥጋዌ ይባላል ። መላው ዓመተ ዓለም ይባላል። ለዚህም መስፈሪያ መቍጠሪያ የሚሆኑ ፯ አዕዋዳት አሉ ።

፩ዱ፤ ዓውደ ዕለት ይባላል ፯ ቀን ነው ።

፪ኛው፤ ዓውደ ወርኅ ይባላል ፴ ቀን ነው ።

፫ኛው፤ ዓውደ ጨረቃ ይባላል ፫፻፶፬ ቀን ነው ።

፬ኛው፤ ዓውደ ዓመት ይባላል ፫፻፷፭ ቀን ነው ።

እሊህ ፬ቱ በቀን የቀሩት በዘመን ይቈጠራሉ ።

፭ኛው፤ ዓውደ አበቅቴ ይባላል ፲፱ ዘመን ነው በዚህ ፀሐይና ጨረቃ መንገዳቸውን እየፈጸሙ በተፈጠሩበት ኖኅት ይገናኙበታል ።

፮ኛው፤ ዓውደ ማኅተም ይባላል ፸፮ ዘመን በዚህ አበቅቴና ወንጌላዊ ይገናኙበታል ።

፯ኛው፤ ዓውደ ቀመር ይባላል ፭፻፴፪ ዘመን ነው በዚህ ዕለት አበቅቴ ወንጌላዊ ይገናኙበታል ዓውደ አበቅቴ ንዑስ ቀመር ። ዓውደ ማኅተም ማእከላዊ ቀመር ። ዓውደ ቀመር ዐቢይ ቀመር ይባላል ። ዓውደ ፀሐይ ፳፰ ዘመን ነው በዚህ ዕለትና ወንጌላዊ ይገናኙበታል ። እስከ ዚህ አርእስት ነው። አበቅቴና መጥቅዕን ለማግኘት ፯ቱን ሺሕ ዘመን በዓቢይ ቀመር ቢሰፍሩት ፲፫ መደብ ሆኖ ፹፬ ተረፈ ፤ ተረፈ ቀመር ይባላል። ተረፈ ዘመን ፬፻፳፫ አለ ከ፹፬ ቢያገናኙት ፭፻፯ ይሆናል ። ፲፬ኛው ዓቢይ ቀመር ከተጀመረ ፭፻፯ ሆነ በዘመን ሉቃስ ።

ዴ ፩ን በማዕከላዊ ቀመር ቢሰፍሩት ፫ማዕከላዊ ቀመር ሁኖ ፺፩ ይተርፋል ። ፺፩ዱን በንዑስ ቀመር ቢሰፍሩት ፪ ንዑስ ቀመር ሁኖ ፲፫ ይተርፋል።፩ን ዘመን ትቶ ፲፪ቱ ዘመን አምራ-ሁለት ወምበር ይባላል። ከ፲፪ ዘመን ፲፩ ፲፩ ቀን ነሥቶ ቢያገናኙት ፻፴፪ ፻፳ውን በ፬፴ገድፎ ፲፪አበቅቴ ይሆናል ። ደግሞ ከ፲፪ ዘመን ፲፱ ፲፱ ነሥቶ ቢያገናኙት ፪፻፳፰ ይሆናል።፪፻፲ሩን በ፯፴ገድፎ ፲፰ቱ መጥቅዕ ይሆናል ። ፲፰ መጥቅዕና ፲፪ አበቅቴ ፴ይሆናል።አበቅቴ ከሕፀፅና ከሥርቀ ዕለት ጋራ የሌሊት ማውጫ ነው ። መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋራ የአጽዋማት የበዓላት ማውጫ ነው። ከ፲፭ በላይ ያለ መጥቅዕ በመስከረም፡ ከ፲፬ በታች ያለ መጥቅዕ በጥቅምት ይውላል ። በመስከረም ሳኒታ ጥር፡ በጥቅምት ሳኒታ የካቲት ይብታል።ከዚህ ላይ አጽዋማትን በዓላትን ያወጧል ።መስከረም ሐሙስ ይብታል፣ ሐሙስ እስከ ሐሙስ ፲፭፡ ዓርብ ፲፮፡ ቅዳሜ ፲፯፡ እሑድ ፲፰፡ የእሑድ ተውሳክ ፯፡ ፯፣ ፲፰ ፳፭ ይሆናል ። መበጃ ሐመሩ ይህ ነው ። ለነነዌ ተውሳክ የለውም ። ጥር ዓርብ ይብታል። ዓርብ እስከ ዓርብ ፳፱፡ቅዳሜ ፴፡እሑድ ፴፩፡ ሰኞ ፳፭ በጥር በ፳፭ ነነዌ ። የበዓት ጾም ተውሳክ ፲፬ ቀን ከ፳፭ ቢያገናኙት ፴፱ ፴ውን ገድፎ ፱ይተርፋል የካቲት እሑድ ይብታል እሑድ እስከ እሑድ ፯ ሰኞ ፱ የካቲት ፱ዓት ጾም ይሆናል ። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፴፯ ፴ውን ሲገድፉት ፯ይተርፋል ። መጋቢት ማክሰኞ ይብታል ማክሰኞ ፩ ረቡዕ ፪ ሐሙስ ፫ ዓርብ ፬ ቅዳሜ ፭ እሑድ ፯ መጋቢት ፯ ቀን ደብረ ዘይት ይሆናል ። የሆሣዕና ተውሳክ ፪ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፳፯ ማክሰኞ እስከ ማክሰኞ ፳፱፡ ማክሰኞንና ሰኞን ትቶ እሑድ መጋቢት ፳፯ ሆሣዕና ይሆናል ። የስቅለት ተውሳክ ፯ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፴፪ ፴ውን ሲገድፉት ፪ ይተርፋል ። ሚያዝያ ሐሙስ ይብታል። ሐሙስ ፩ ዓርብ ሚያዝያ ፪ ቀን ስቅለት። የትንሣኤ ተውሳክ ፱፡ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፴፬ ፴ውን ሲገድፉት ፬ ይተርፋል ። ሚያዝያ ፬ ቀን ትንሣኤ ይሆናል ። የረክበ ተውሳክ ፫ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፳፰፡ ሐሙስ እስከ ሐሙስ ፳፱ ሐሙስን ትቶ ረቡዕ ሚያዝያ ፳፰ ቀን ረክበ ካህናት ይሆናል ። የዕርገት ተውሳክ ፲፰ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፵፫ ፴ውን ሲገድፉት ፲፫ ይተርፋል ። ግንቦት ቅዳሜ ይብታል። ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ ፰፡ እሑድ ፱ ፡ ሰኞ ፲፡ ማክሰኞ ፲፩፡ ረቡዕ ፲፪፡ ሐሙስ ግንቦት ፲፫ ቀን ዕርገት ይሆናል ።የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፶፫ ፴ውን ሲገድፉት ፳፫ ይተርፋል። ቅዳሜ እስከ ቅዳሜ ፳፪ እሑድ ፳፫ ግንቦት ፳፫ ጰራቅሊጦስ። ግንቦት ፳፬ ጾመ ሐዋርያት ። የጾመ ድኅነት ተውሳክ ፩ ከ፳፭ ቢያገናኙት ፳፮ ግንቦት ፳፮ ጾመ ድኅነት ይሆናል ።

የዘመናትን የአጽዋማትና የበዓላትን ማውጫ ሰው ሁሉ እንዲያውቀው ያሚያስፈልግ ስለሆነ እስከ ፍጻሜ ዘመን እንዲያገለግላቸው ለኢትዮጵያ ልጆች ወንድሞቼ መክፈቻውን ብጭር ቃል አውጥቼ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች እንቀጣጣለሁ አበረክታለሁ ።

ዘእምቤተ ማርቆስ ሥረቀ ብርሃን ፀዳሉ ።

ስለ ክቡር ባራዝማች ከብትህ ይመር ዕረፍት ።

— ሊመንግሥታቸው ተገዥ ለሀገራቸው ክብር ፈላጊ እሆናለሁ ብለው ከባሌ አዲስ አበባ ስለመጡ ከትንሽ ቀን በኋላ ታመው ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆፒታል ገብተው ምንጊዜም የማይቀር ሞት በተራቸው ነሐሴ ፲፰ ቀን ዐርፈዋልና ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ለወንድሞቻቸው አስታውቁልን።

የፍቅር ወንድማቸው ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ።

የርሻና የመሥሪያ ሚኒስቴር ላጋር በያይነቱ ያለውን እህል ለመሸመት ጳጉሜ ፬ ቀን እንደወጣው ማስታወቂያ ቃል ከዚያው ቀን ጀምሮ ላጋር ለመሸመት የሚሔድ ሰው ከጧቱ ከ፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ፲ ሰዓት ድረስ እንደመጣ ሸምቶ ለመሔድ ይችላል።

የሸመታውም ልክ ላጋር ከለው ከርሻ ሚኒስቴር ማጋዘን በበሩ ላይ ተወስኖ ይገኛል ።

ብ ዴሬ ።

ማስታወቂያ።

ከሼህ ሳሊም በዝርዓ ቤት በያይነቱ ጥሩ በጣም ያማረ ምንጣፍ ይገኛል።ቤቱም ወደ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ቤት መሔጃ ወዳለው ድልድይ ሳይደርሱ ከሼህ ሆጃሊ ቤት ከፎቁ ነው ምንጣፍ ለመግዛት የሚፈልግ ሰው ሁሉ እዚያ ድረስ እየመጣ ለመግዛት ይችላል። ስለ ሼህ ሳሊም ሐጂ አብደላ

ማመልከቻ ።

«መዓዛ የተባለው ጣዕም» ደግሞ «የሰሜን ተራራ በትግሬ ውሥጥ» የተባለው በበጌምድር ውሥጥ ተብሎ እንዲነበብ ።

እነዚህ ሁለት ዋና ስሕተቶች ላንባቢዎች ጉዳት እንዳይሆኑ ነው

ፊታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ።

ማስታወቂያ ።

ስለ የኢትዮጵያ ዓመት መለወጫ ክብር መስከረም ፫ ቀን ቅዳሜ ዕለት ከማታው ፱ ሰዓት ልዑል ራስ ኃይሉ ባሉበት በሮቢንሶን ሆቴል የደስታ ጨዋታ ይደረጋል ። ተጠርተው የመጡ ሰዎችም ሲገቡ ቍጥር ቍጥራቸውን ይቀበሉና ይህን ቍጥር ማርቲኒ ሮሲ የተባለ የንግድ ቤት ያሰናዳው የዕጣ ክፍል ግብዣ ለመቀበል ዕድል ይሰጣቸዋል ።

ሬኔ ጉዮን ።

የ፪፻፸፯ ገጽ ተከታይ።

ሦስተኛ ክፍል ።

ስለ ምርመራ ።

ለሥራ የተፈቀዳላቸው ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች ለራሳቸው ሥራ ያስመጡትን መድኃኒት የአከሙበትና የሸጡትን የመድኃኒት መጠን የሚተሳሰቡበት ገጽ በቍጥር የሆነ በመስመሩም መካከል አዝል ያልተጻፈበት በትክክል የሚያመለክት አንድ ልዩ የሆነ መዝገብ ይይዛሉ ።

ይኸውም የሒሳብ ደብተር በ፮ ፮ ወር መጨረሻ ማለት በሰኔ ፴ቀንና በታኅሣሥ ፴ቀን እንዲመረመርና በመስከረም እንዲዘጋ ላገር ግዛት ሚኒስቴር ይቀርባል ።

ከውጭ አገር መድኃኒት ለማስመጣት ፈቃድ በተጠየቀ ቍጥር ይህ የሒሳብ መዝገብ ላገር ግዛት ሚኒስቴር ይቀርባል።

እነዚህም ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች ከሥራ ጉዋደኞቻቸው ዘንድ አንደኛቸውን ከነዚሁ መድኃኒቶች ሲገዙ ይህንኑ ዓይነት የመተሳሰብያ መዝገብ እንዲኖራቸውና ይኸውም መዝገብ ባገር ግዛት ሚኒስቴር መቈጣጠሪያ ቤት እንዲያቀርቡ ግዴታ አለባቸው ።

አራተኛ ክፍል

ልዩ ልዩ ለሆነ አደራረግ

መኃድኒት ቀማሚዎች የሕክምና ሥራ ከተፈቀደለት ሐኪም በጽሕፈት የተሰጠ ትእዛዝ ካልተቀበሉ በቀር በመጀመሪያው ክፍል ላይ የተጻፉት መድኃኒቶች ለማናቸውም ሰው ለመሸጥ አይችሉም ።

በትእዛዙም ወረቀት ላይ ከሐኪሙ ፊርማ በቀር የራሱንና የበሽተኛውም ስም በሙሉ ፊደል ተነባቢ ሆኖ ይጻፍበታል

የዚሁም የማዘዣው ቃል መድኃኒት ቀማሚው በሚይዘው በተለየ መዝገብ ላይ እየተጻፈ ለምስክርነት እንዲሆነው በእጁ ይቀመጣል ።

ከንደኛው ሐኪም በጽሕፈት የተሰጠ ሌላ ትእዛዝ ካልሆነ በቀር በዚሁ በመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሁለተኛ ሥራ እንዳይፈጸምበት ተከልክልዋል ።

አምስተኛ ክፍል ።

ስለ ሚያፋጥን ምክንያት ።

መድኃኒት ቀማሚዎች ለሚያስቸኩል ጊዜ በራሳቸው ኃላፊነት ባዋቂ የተቀመሙትን እኒህ የሚከተሉት መድኃኒቶች ለመስጠት ይችላሉ ።

ኤሌክሲር ፓሬጎሪክና የሺዴናም ላውዳኑምና የዶቨር ዱቄት ደሞ የአፕዮም መድኃኒት አፎግ ቢበዛ ልኩ ከሀያ ሳንቲግራም በላይ ለሆነ አይችልም ።

መድኃኒት ቀማሚ በሚያደነዝዝና በሚያሰክር መድኃኒት መዝገብ ውስጥ የሚሰጠው መድኃኒት ልክ ይጽፋል ።

Art. 3

Contrôle.

Les médecins, pharmaciens, autorisés à pratiquer tiendront une comtabilité régulière de ces drogues dans un registre spécial dont les pages seront numérotées, écrites sans interligne, indiquant exactement les quantités entrées en leur possession ainsi que les quantités vendues ou employées.

Cette comptabilité sera présentée à la fin de chaque semestre (30 juin et 30 décembre) au ministère de l'Intérieur qui la contrôlera et la paraphera (Service compétant).

Elle devra également être présentée au Ministère de l'Intérieur pour chaque demande nouvelle d'importation Les médecins, pharmaciens qui achèteront l'une ou l'autre de ces drogues de leurs confères sont tenus d'avoir laméme comptabilité et de la présenter au contrôle du Ministère de l'Intérieur.

Art. 4

Dispositions spéciales

Les pharmaciens ne pourront vendre à des particuliers les produits spécifiés sous chiffre 1 que sur présentation d'une ordonnance d'un médecin autorisé à pratiquer.

L'ordonnance devra porter, outre la signature du médecin, son nom en entier et celui du malade les deux en caractères parfaitement lisibles.

Ces ordonnances seront transcrites dans un registre spécial tenu par le pharmacien et elles seront conservées par lui à titre de justificatif.

Il est interdit d'exécuter à nouveau la même ordonnances sans une autoriastion écrite d'un médecin.

Art. 5

Cas d'urgence.

Les pharmaciens peuvent délivrer sous leur responsabilité, comme médicaments d'usage immédiat en cas d'urgence, les préparations galéniques suivantes

L'elexir parégorique, laudanum de Sydenham et poudre de Dover pourvu que la quantité maximum délivrée ne contienne pas plus de 0.20 grs d'opium médicinal.

Le pharmacien inscrira sur le registre des stupéfiants les quantités ainsi fournies.

ከዚህ የቀረው በሚመጣው ቍጥር ይታተማል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ፤ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደ መሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር ብጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ ባሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሲንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኒዮ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአብጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ደ.ሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino



Borsalino

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን በርኔጣ መጥታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ እስ

(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፉ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፰ 6me ANNEE № 38		ሐሙስ መስከረም ፰ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም። JEUDI 18 SEPTEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie — Un an 5 Thalers Etranger — Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

የሕዝብ ዳኞች ለሆኑ ሁሉ ለዳኝነት ሥራቸው መሪ የሚሆን አጥፊ የሚቀጣበት ኃጢአት የሚሆነውንም በደል እንዳይሠራ አስቀድሞ ተመራምሮ ከመበደል የሚጠነቀቅበት ደምብ ተጽፎ ወጥቷል። ይኸውም ለተማሩት ማሳሰቢያ ላልተማሩት መመከሪያ የሚሆን ነው ።

ዋጋውም ፲፪ ብር ነውና ይኸንን በውሥጡ ብዙ ጥቅም ያለበትን መጽሐፍ የምትፈልጉ ሰዎች ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ማተሚያ ቤት ልትገዙ ትችላላችሁ ።

ቢያስፈልግም ከዚሁ ደምብ ጋራ የባሮ ነፃነት ደንብ የጦር መሣሪያ ደምብ ፥ የብድር ደምብ፥ ይህ አራቱ ዓይነት በአንድነት ተጠርዞ ይገኛልና እንደዚህም ሲሆን ዋጋው አስራ አምስት ብር መሆኑን እናስታውቃለን ።

ለተመልካቾች ማመልከቻ ።

ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር በዓለም የአለውን ፍጥረት ሁሉ በአንድ ጊዜ አልፈጠረም ። ነገር ግን በ፮ቀን ሥራውን ሁሉ ጨረሰ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ። ይህንም ማድረጉ በአንድ ጊዜ ሥራችሁን መጨረስ አትችሉምና ጥቂት በጥቂት ሥራችሁን አሳድጉ ብሎ ለኛ ለማመልከት ይመስለኛል እንጂ እንዲህ ይሁን ብሎ በቃሉ ለማዘዝ በአንድ ቀን ቢናገር ቸግሮት እንዳልሆነ የታወቀ ነገር ነው ። አሁንም በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ለኢ-

ዜው የሚስማማውን አዲስ ደምብ ለማቆም አሮጌውንም ደምብ ለማደስ ስለተጀመረ በአዲሱ ዓመተ ምሕረት የብርሃንና ሰላምን ምልክት ለውጠነዋል ። መልካም ምስሌ ታገኙበታላችሁና ተመልከቱት በዘውዲ ግራና ቀኝ የጃንሆይ ስም አለበት። በላዩም አበበና ፍሬ አለበት። ትርጓሜ ። ፍሬው አሁን የተጀመረው ሕግ ነው ። አበባውም ለሀገራችንና ለጊዜው የሚስማማ እየቈየ የሚሠራው ሕግ ነው ። ብርሃኑንም ገልጦ በጕልህ ያሳያል ፤ ይኸውም በሰላም እንዲሆን ሲአስረዳ የተያያዙ እጆች ያሳያል፤ ይህንም በክልሼ አድርገው ለሠሩልን ለሙሴ ሀይግ ሰርኪስ ብዙ ምስጋና እናቀርብላቸዋለን ። የሀገራችንን መታደስ በዚህ እንድታውቁት እነሆ ዕንቍጣጣሽ ።

ሹም ሽር ።

ልጅ ትርፌ ኃይሌ አባቱ ነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬ ተሹመውት የነበረውን የወሎን ነጋድራስነት ተሾመ ።

አቶ አወቀ ወልደ መድኅን የግራዝማች ዕንቍ ሥላሴ የነበረውን የዘበኛ የሻአምበልነት ተሾመ።

ምንም ሁለቱ የአገልጋዮች ልጆች ቢሆኑ ልጅ ትርፌ ኃይሌ የሙት ልጅ ነውና የአባቱን ስፍራ በማግኘቱ ሰውን ሁሉ እጅግ ደስ ብሎታል። ብዙ ርስት ተገዝሰው ለመንግሥቱ በቅን አገልግሎ መልካም ስም ያቈየ ሰው ልጁን ይጠቅማል። የነጋድራስ ኃይሌ ሹምዬን ለመንግሥቱ ታማኝ አገልጋይ መሆን ከአንድ ጊዜ ሁለት ጊዜ በብርሃንና ሰላም አስታውቀናልና ። የአባቱን ውለታ ለልጁ ስለከፈሉ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን እጅግ እናመሰግናለን ። ከእንግዴህ ወዲህ ከመልካም ሽቱ መልካም ስም ይሻላል ያለውን የሰሎሞንን ቃል እያሰብን ብዙ ገንዘብ ከመሰብሰብ ለመንግሥታችን በቅን ብናገለግል ለልጆቻችን ርስት ሁኖ እንዲቈዩቸው እንወቅ ።

ዕንቍጣጣሽ።

በ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ሐሙስ አራት ሰዓት ሲሆን ሰው ሁሉ አበባውን እየያዘ እንኳን ከዘመነ ማርቆስ ወደ ዘመነ ሉቃስ አሸጋገረዎ እያለ ወደ ጃንሆይ እየቀረበ እጅ ይነሳ ነበርና በዚያ ጊዜ ፩ ሮፓዊ ሰው ያነበበው ዲስኩር ቀጥሎ ያለው ነው።

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ምስጋና ።

ከቀድሞ ዓለም እስከ ዛሬ ስምዋ ከዘመን እስከ ዘመን ስትሸጋገርና እንደ ሴት ወይዘሮች ስትቀማጠል የኖረችው ኢትዮጵያ ዛሬም ባንተ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተባረከው ንጉሠ ነገሥት እንደ ገና አበበች፤ እንደ ጥዋት ጀንበር ከርቀት ተራራንያ ነግተህላቸው እንደ ቀስት በሚወረወረው ጮራህ ለመቀማጠል የታደለችውን ኢትዮጵያ ከጠፈር እስከ ጠፈር በብርሃንና ሰላም ወለውልህ በጽልመት ደመና ተሸፍና ለኖረው ጥብብና ከፀሐይ እጦት ለጠወለገው ዕውቀት እንደ ገና ሕይወት ሰጠሃቸው።

የሥላሶችን ኃይል ስለ በትር ይዘህ ምቀኞችህን አዘቀጥሃቸው፤ ጠላቶችህም ምስለ ነበልባል ገጽህን ባዩ ጊዜ እሳት ከውሀ እደሚፈራ ፈርተው፤ጽልመት ከብርሃን እንደ ሚሸሽ፤የሸሹ ከኔፋስ ኃይል መሐጃውን እንደ አጣ ገለባ ይበናሉ።

ዝናህ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ ያስተጋባል። መውጅና ሞገድ ውቅያኖሶችን እንደ ሚያናወጠው እንዲሁም ስምህ ኢትዮጵያን ዳር እስከ ዳር ያናውጠዋል።በምስለ ንሥር አስተያየትህና በነጐድጓድ ድምጽህ ወሰን የሌላቸው ምድረበዳዎች የተንቀጠቀጡ ዳርቻቸው እስከ ኅልፈት የሚዘረጋ ሕንፃ ገደሎች ይናዳሉ።

አንቺ እንደ ሴት ወይዘሮች ለመቀማጠል የታደልሽ ኢትዮጵያ ሆይ ሕዝብሽ ይረፍ ላንቺም ደስ ይበልሽ እንደንሥር ከአየር አክናፉን ለነገዱ ዘርግተውለት ከሐሩር ጥላ ከዝናብ ከለላ የሆነ ንጉሥ ነግሦልሻልና።

አንቺ እንደ ሴት ወይዘሮች በመቀማጠል የታደልሽ ኢትዮጵያ ሆይ ሕዝብሽ ይረፍ ላንቺም ደስ ይበልሽ ገበሬን ከእርፉ፤በሬን ከቀምበሩ፤ ሕዝቡን ከመንግሥቱ አስማምቶ የሚያኖርና ለደካማ ድጋፍ፤ለድኃ ሲሳይ፤ለተበዳለ ፍሥሓ፤ላጣ ጸጋ፤ ለዕውር ብርሃን የሆነ ንጉሥ ነግሦልሻልና ።

አንት ዘረ ቡሩክ መኰንን ሆይ ስማኽ ስለአገርህ ልማትና ስለ መንግሥትህ ፅናት ደክሞ የረገፈ አፅምህ አይንቀሳቀስ አይስጋም ለንጓዲሁ ይረፍ ባማንና በሰላም ከጉልበትህ የወጣው ፍሬ ተከታይህ የነበረ ቀዳማዊ ሁና ድምርህን በቀጥታ ፈጽሞ ልሃልና ።

በፅና ኃይልህ በማይፈዝ ጉልበትህና በማይታጠፍ ክንድህ የተከልኸው ወርካ አሁን ለምልሞ ጠቅልሎ ለነገዱ ከለላ ሁኖዋል ቤተ መቅደስህን ከቀስተ ደመና በላይ እየተከልህ ዙፋንህንም ከሰባቱ ሰማያት ላይ ዘርግተህ የፍሬህን ሲሳይ እየተመለከትህ ኵራ ለኵራት የተገባህ ለምስጋናም የታደልህ ነህና።

አንት በተቀደሰች ሜሮን የተቀባህ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ኑር ለዘለዓለም ዕውቀትን ለክንድህ ጋሻ፤ ቸርነትን ለእጅህ ማርዳ፤ጸሎትን ለወገብህ ሰይፍ፤ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ላንገትህ ድሪ፤ ምሕረትን ላይኖችህ መነጽር፤ፍቅርን ለራስህ ዘውድ፤ቀጥታን፤ለእግርህ ጫማ፤ ፍርድን ለፊትህ መሪ እያደረግህ ሕዝብህን በብርሃንና ሰላም ጐዳና አድርገህ ወደ ዕውቀትና ሥልጣኔ ምድረ በዳ ምራቸው ።

ዕድሜህ የማይቀነስ፤ ዙፋንህ የማይንቀሳቀስ ይሁን፤ የብርሃን አሸንዳ፤የጥበብ ምንጭ፤ የዕውቀት ፈለግ በንድ ቃል ለታደለች ኢትዮጵያ አልፋና ኦሜጋ አንተ ነህ።ኑር ለዘለዓለም ።

ስለ ዕንቍጣጣሽ መታሰቢያ ተጻፈ ከዮሐንስ ጴጥሮስያን

ስለ ሐሰት ወሬ ።

ማንም ሰው ቢሆን አየሁ ብሎ የማይመሰክርበትን፤ ሰማሁ ብሎ ዋቢ የማያሰልፍበትን ያልሆነ ወሬ ፈጥሮ እንዳያወራ። የሐሰት ወሬም አውርቶ የተገኘ ሰው የቅጣት ኀላፊነት እንዲያገኘውና እንዲቀጣ ይወቅ ተብሎ በግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመተ ምሕረት አዋጅ ተደርጎ ነበረ ። አለማረፍ ከቅጣት

ያደርሳል እንደሚባለው እናርፍም ብለው ቅጣት የተፈረደባ-ቸው ሰዎች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።

መጀመሪያ አቶ ወልደ ጻድቅ አስረስ ያልሰማውንና ያላ-የውን ነገር ሰምቻለሁ ብሎ ተናግሮ እሱም ራሱ ቀርቦ ይህነን ነገር ሰምተሃልወይ ተብሎ በቃሉ ቢጠየቅ አዎን እገሌ እገሌ ነግረውኝ ከነርሱ ቃል ሰምቻለሁ ብሎ ቢናገር ። ይህነኑ ነገር ለማጣራት መርማሪዎች ታዘው እሱንም አቅርበው ነግ-ረውኛል ያላቸውንም ሰዎች ጠርተው ቢጠይቋቸው ይህነኑ ቃል አስቀድሞ እሱ ነግሮን ከርሱ ቃል ሰማን እንጂ እኛ አል-ተናገርንም ብለው መስክረውበት አቶ ወልደ ጻድቅ አስረስ ያወራው ነገር ሐሰት ሆኖ ሁለቱን የመንግሥት ሹሞች የሚ-አጣላና የመንግሥትም አዋጅና ደምብ የሚቃወም ሆኖ ስለ ተገኘ ከሹመቱ ተሽሮ ወደ አገር ቤት ሒዶ እንዲታሠር ተፈ-ረደበት ።

ፊታውራሪ እሥራትም እንኳን አዋጅ አስጠንቅቆትና በቤተ መንግሥት በለማዕርግ ሁኖ ያደገ ስለሆነ ከክፉ ነገር እንደመሸሽና የሐሰት ወሬ እንዲጠፋ እንደ ማሰብና ወደጃን-ሆይ እንደማስታወቅ ሁሉ ሰውና ሰው የሚአጣላ የሐሰት ወሬ እያወራ ያንዱን ነገር ላንዱ ወስዶ ለማጋጨት ስለተናገረና አዋጅ ስለአፈረሰ አራት መቶ ብር መቀጫ እንዲከፍል ተፈ-ረደበት ። አቶ ግዝሙና ወርቄ ደስታም እንደዚሁ አላፊ የማ-ያገኙበትን ያልተረገጠ የሐሰት ወሬና አንዱን ከንዱ የሚአጣላ የሐሰት ነገር ተናግረው ስለተገኙ ሁለት ሁለት መቶ ብር መቀጫ እንዲከፍሉ ተፈረደባቸው ። ደግሞ ያረገዘች ቃስታ-ውቅ በደረቷ ትታጠቅ እንደሚባለው ይህ ከዚህ በላይ የተጻ-ፈው ፍርድ ገናሳይነበብላቸው ጥፋታቸውን ራሳቸው ስለተረዱት ከአደባባይ እየሸሹ ጠፍተው ስለተገኙ ባቶ ግዝሙ የሁለት ወር እሥራት ፍርድ ተጨመረበት ። ቅዱስ ዳዊት ግበ ከረየ ወደሐየ፤ ወይወድቅ ውስተ ግብ ዘገብረ ያለው በነሱ ደረሰ የተደላደለውን የመንግሥትን አዋጅ የሚአፈርስ እውነት ያልሆነ ነገር የሐሰት ወሬ እያወሩ ከሹመት እመሻር ከማዕርግ እመዋረድ፤ በመልካሙና በለምለሙ መንግሥታችን የተገኘውን ትዳር እማጣት ከመድረስ ብንጠነቀቅና ዕድሚ ላዒ ኃይለ ሥላሴ እያልን አርፈን ሥራ ሥራችንን ብቻ ብንሠራ እጅግ መልካም መሆኑን ለወድሞቻችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ እና-ስታውቃለን ።

የመሬት ጩኸት ወይም አቤቱታ ።

ከዕለታት ፩ቀን በጽሕፈት በታዬ ሁኜ መጽሐፍ ስመለ-ከት የሥጋ ዘመዳችን የምትሆን መሬት በሰብአናዬ ሕሊና ውሥጥ በስተቀኝ በኩል ሁና«አቤት አቤት»እያለች ጩኸትዋን ታሰማኝ ጀመር እኔም የመላ አእምሮዬን ወዳቤቱታዋ መልሼ ም ፥ ሆንሽ? ተናገሪ ብላት ከዚህ በታች የሚከተለውን ቃል ፊትዋን በንባዋ እያጠበች አቀረበችልኝ (ነገረችኝ)»እግዚአ-ብሔር ያሰይህ ላንተም በሥጋ የቅርብ ዘመድህነኝና አደራህን ጉዳቴን ልብ ብለህ ስማኝ እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ የሚ-ባል አባታችን እኔንና እኅቴ ወይዘሮ ሰማይን መንትያ አድርጎ በመጀመርያ ቀን ወለደን፤በተወለድን በሦስተኛው ቀን እኔ ወይ ዘሮ መሬት ዛሬ በያንዳንዱ ክፍል ገላዬን እደምታየው መልኬ በመልካም ሐመልማል(ቡቃያ)ዘርና ፍሬ በየደነቱ እንደዘመደ በሚሰጥ ሽልማት ከራሴ ጠጉር እስከ እግሬ ጥፍር ድረስ እንቄጥቍጦ አስጌጠኝ፤በተወለድሁ በስድስተኛው ቀን ሁሉን የሚችል አምላክ አባቴ ብዙ ጉልቄ መጣፍርት የሌላቸው ተሐዋስያን ፍጥረቶች ከኔው ሽልማት ውሥጥ የሚገኘውን ፍሬ የሚመገቡ ብዙ ጭፍሮች ሰጠኝ ። ቀጥሎ የዘመዶችህንና ያንተን የቀድም አያቶች አዳምና ሔዋን የሚባሉ ሰዎች ከሥ-ጋዬ ቈርጦ በተለየ ከራሱ ሕይወት አካፍሎ አእምሮ ያላቸው ፍጥረቶች አድርጎ ሥራቸውና እኔ ከሽልማቱ እንዳልራቄት የኔን ሽልማት አዘጋጆች እንዲሆኑ የነሱም ሀብት ብልጥግና ከኔ ላይ በሚገኘው ሽልማት እንዲሆን አስተካክሎ ደንብቶ ላንቺም ያውልሽ ያንችን ጌጥ አሳማሪዎች አዳምና ሔዋንን ሰጥቸሻለሁ ለላንተም ክበረትና ብልጥግና ምግብ ልብስ እን-ድትሆናችሁ መሬትን ሰጥቻችኋለሁ አደራ አዳም ሆይ ተጠን-ቅቀህ ያዛት ከሰጠኋት ሽልማት እንዳትራቄት ሽልማትዋን የም-ታዘጋጅበትን ሰዓት ከሰባቱ ዕለታት ስድስቱን ዕለት ፈቅጆ-ልሃለሁ፥ ሰባተኛው ቀን ግን ከሥራህ የምታርፍበት የደስታ ቀን ይሁንህ፥ ስድስተ ዕለተ ተገበር ግብረከ ወሳብዕተ ሰ ዕለት ዕረፍተ ለትኩንከ ብሎ አዘዘው ።

ዛሬ በየትኛው ገላዬ ሽልማት ሳይጐድልብኝ በትክክል ሳድር ኢትዮጵያ »በምትባል አውራ ጣቴ ላይ የማር ቀላድ፥ የሙክት፥ ጋሻ፥ የሰሞን መሬት፥የፈታይ፥ የመጠርያ፥ የደስ ደስ የባለሟል ርስተ ጕልት፥የግምት መሬት ሌላም ይህን የመሳሰለ ስም ሰጥተው ላውራ ጣቴ አለቃ(ንጉሥ)እንዳልሆንቈራርጠው ለሕዝብ ስላካፈሉኝ በግምት መሬት ብቻ ትንሽ በትንሽ ሳጌጥ ካዚህ በላይ ስሙን በቈጠርሁልህ ሁሉ ከሽልማቴ ተራቍቼ የመላው ገላዬ ዓለም መዘባበቻ ሁኜልሃለሁ፥አሁን እነኛ ከኔው ሽልማት ክብረትና ብልጥግና ፈላጊዎች በግምት መሬት በኩል ሁኖ ከሽልማቴ እንዳልራቄት የሚጥርልኝን ገበር(ገበሬ)ጥዋት ማታ ክፉ እየፈለቀቁ ቢወስዱበት እየዘለለ ወታደር ሆነሁ እያለ አንዳንዱም በወታደርነት ስም ሥራወን ሳይዝ ስሙን ብቻ ይዞ ፈንጋይ፥ቤት አቃጣይ፥ ሌባ፥ወሮበላ ደሆንልህ ጀመር፥ዛሬ በዚሁ አኳኋን ጥቂት ዘመናት የጨምርሁ እንደሆን ከሽልማቴ በፊት በተወለድሁበት በመጀርያው ቀን እንደነበርሁት መሆኔ ነውና ዘፍ ምዕ ፩ ቍጥ ፪ ጭራሽ በጣሙ ሳልራቄት የዓለም መዘባበቻ ሳልሆን ላውራ ጣቴ ኢትዮጵያ አለቃ(ንጉሥ)ጩኸ-ቴንና ልቅሶዬን ንገርልኝ ስል በብርቱ እለምንሀለሁ »ብላ አቤቱታዋን ጨረሰች ።

እኔም ለጊዜው ነገሩ ስለከበደኝ ያውራ ጣትሽ አለቃ ልኔ ሰማየ ለማየት የማይደረስ ማለት ነው፤እናቴ የሥጋ ዘመዴ በዚህ አትቀየሚብኝ እኔ የማውቃቸው ጩኸትሽን በፍጥ ነት የሚያደርሱልሽ ብዙ ቅልልቅ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁና ልጠቍምሽ አንቺ እኔ እንዳልነገርሁሽ ሁሉ ሒደሽ አቤቱታሽን አቅርቢላቸው ብላት ከፊተኛው ይልቅ ልቅሰዋን አበርትታ አይሆንም አይሆንም »እንደችሎትህ ሥራ በማለት አጥብቃ

ትንሀዓዘኝጀመር አሁን ጨኸኘ ዋና ልቅሶዋ ቢበዛብኝ ንግግርዋን ብጀሮዬ እየዳመጥሁ በንደቡ እያጣራሁ በእጄ ጽፌ እንደኔ እንድትቸገሩበትና ምክር እንድታክፍሉኝ ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች የመሬትን ጩኸት አቀርብላችኋለሁ ።

ፍሥሐ ወልደ ሚካኤል ዘብሔረ አክሱም

ምክር ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያን ነፃነትና የሀገራቸውን ልማት የሕዝቧን ብልጥግና ሲፈልጉ ድር ቢያብር፤አንበሳ ያስር እንደሚባል ሁሉ እኛም ሕዝባቻቸው በሚቻለን መርዳት በደ ስታ ይገባናል ። እኔም ባለኝ አቅምና በታሰበኝ ዕውቀት ለደሀ ጠባቂዎች ከተመረጡት በቀር በያውራጃው ከዚያው ከባላገሩ ማንኛውንም ነገር የሚጠብቅና ሀገሩን የሚመረምር ረዳት ስለ ሌላቸው ማናቸውም ነገር ያለድካም በቶሎ ሊገለጽላቸውና ሊፈጸምም ደሀውም ከጥቃት ሊድን የተቻለ ስላልመሰለኝ ብጭሩ ላስታውቅ ቀጥዬ ጽፌአለሁ ።

ማለት በየሀገሩ ሁሉ ባላገሩ የመረጠውን ወይንም መንግሥት ቀንደኛ ቀንደኛ የሆነውን ሁለትም ቢሆን ሦስት ሽማግሌ የሀገሩን ባህልና ለመንግሥትም ለሕዝብም ጥቅም የሚሆንን ነገር ውሥጥ አዋቂ የሌብንም እያለ በማታለል የሚ- ኖርንም ሌባና ወስላታ ሁሉ ተወልደው በረጁበት አገር ስንኳ ንስ የሰው የንጨቱ ጠማማ ስለማይሳታቸው ሀገር የሚለማ በትን እየ ማከሩ ለዚሁም አማካሪዎች የተለየ ቦታና የሚመጡ በት ጊዜ በመጡም ሰዓት ነገሩን ተቀብሎ የሚያቀርብ ሹም ተደ ርጎላቸው ያገሩን ሰርዶ ያገሩ በሬ ያወጣዋል እንደ ሚባለው የሽማግሌ ተረት እንመጡ ቢያመለክቱ ነገሩም በቂራጮች ፊት ብጭር ይቀርባል ። ለጥፋተኛውም ቅጣት የማያሳዝን ይሆናል ሕዝቱም ከጉዳት ይድናል ፡ ሌባና ወንላታም በአፍ ብልጠት እወጣለሁ ሳይል ያለቅርታ ይቀጣል ። መንግሥትም የሀገሩን ባህል ከተረዳው ሕዝቡ የሚበለጥግበትን ሀገሩ የሚለማበትን ያስብ ይሆናል በማለት ልጽፍ አሳሰበኝ ።

ነገር ግን አምሳ ሎሚ ላንድ ሰው ሸክሙ ለብዙ ጌጡ ነው እንደሚባለው ለሀገራችን ጥቅም መስሎ የሚታየንን ሁሉ እኛ ምናገባን ይኸን ማድረግ የሚችል መንግሥት ነው ብለን እንደዚሁ ሁላችንም የታሰበንን ገልጸን ባንናገር ከምንም የማ- ይቈጠር ይሆናል ። ይልቁንም ሁላችንም ለሀገራችን ጥቅም የታሰበንን ሁሉ እኛው አስበን የማይጠቅም ይሆን ብለን አስበን ከምናፈርሰው የተቻለንን ብንሠራ ከ፻ አንዱ።ወይም ከ፳ አንዱ የሚጠቅም ይሆናል በማለት ያለፍርሃት ልናስታውቅ ይገባናል በይሉኝታና ወይንም ይኸንን በመሚስል ነገር ስለሀገራችንና ስለመንግሥታችን ትዝ የሚለንን ሁሉ ባናመለክትም በፍቅሮች መሃከል እነኝህ ነገሮች የተወገዱ እንደሆኑ መንግሥቱንና ሀገሩን ያለመውደዱን ይገልጽ ይሆናል ።

ክቡራን ብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ሆይ የበላገር ጤና የዓለም ሕይወት ነው በማለት አነቃቃኝ እንጂ የሚያደፋፍር ዕውቀትና ይህንም የተዘነጋችሁ ነው ብዬ አይደለም ። ስለዚህ ከዚህ በላይ በጻፍኋቸው ቃሎች ስሕተትም ቢኖር ይቅርታ- ችሁን እየለመንኩ የብርሃንና ሰላም ሕፃንነቱን አረጋግጣለሁ።

አድማሱ ተሰማ ቀ ኃ ማ ቢሮ ።

ሰኔ ፩ ቀን ፲፱፻፳፪ ዓ ም የተደረገ ጋብቻ ።

አቶ ኃይሉ ለውጤ የሚባል ወንድማችን የመጽሐፍ ቅዱስ ወዳጆች በሚባሉ የስዌድን ሚሲዮኖች ። በሁለት ወዳ- ጆቹ እርዳታ ለትምህርት በ፲፱፻፳፩ በፈረንጅ ቍጥር ኅዳር ፩ ቀን ገብቶ በስዊዲሽ ሚሲዮን ሲማር ቈየ ከዚያ በኋላ በፈረ- ንጅ ቍጥር ፲፱፻፳፬ ታኅሣሥ ስምንት ቀን በተወለደ በሐያ አመቱ መምህራኖቹ መርቀው ባርከው ለእንግሊዝ መንግሥት ቆንሲል ለደቡብ ኢትዮጵያ ማጆር ማየልስ ለሚባሉ በአነጋ ጋሪነትና በጸሐፊነት ተቀጥሮ ወደ ቦረና ሜጋ ከሚባል ከተማ ሲሠራ ቈየ ጌታውም በታማኝነት ስለ ሚሠራላቸው በሰጡት የምስክርነት ወረቀት እንዳየሁት በሚሔዱበት ስፍራ ሁሉ አይ- ለዩትም ነበረ ስለዚህ በሞላ ኬንያ ኮሎኒን አዙረው አሳይተውታል

ከኬንያ በ፲፱፻፳፯ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ ወይዘሮ ጽጌረዳ አዳሙን አዚያው አቦረና ሳለ አጭቷት ነበርና በተወ- ለደች ፲፭ አመቷ የወር መንገድ አጉዞ ይዟት ወደ አዲስ አበባ መጣ፡፡ና ሳትማር ሊያገባት አልፈቀደምና ጥንት እሱ እውነተኛ መንፈሳዊ ምግብን ካገኘበት ተማሪ ቤት እሷም ይህንን እውነተኛ መንፈሳዊ አእምሮ እንድታገኝ ሲል አተማሪ ቤት አገባት ስትማር ቈይታ አሁን አቶ ኃይሉ ከሔደበት አገር ሲመለስ መምህሯ ወይዘሮ አናሊና የሚባሉ የስዌድን ማኅ- በር የልጃገረዶች ተማሪ ቤት ዋና በሥራዋና በትምህርቷ አስደስታኛለች ብለው ስለ መሰከሩላት በአውሮፓውን ሕግ በስዌድሽ ሚሲዮን ቤተ ክርስቲያን ሰኔ ፩ ቀን በሚያስደንቅ አኳኋን ጋብቻውን ስላደረገ በጣም ደስ አለን በተለየ ከዛሬ ከአዲሱ ዘመን ወጣቶች በጋብቻና ሚስቱን ይህን ያህል ዓመት ታግሦ በማስተማሩ አንደኛ በመሆኑ ለሀገሩ ለኢትዮጵያ በድ- ኅነት አቅሙ አሰቢና ተቆርቋሪ መሆኑ አይጠረጠርም፣ ግን ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋብቻቸው እንዲህ ሳይሆን የቀረ ነው ብዬ አይደለም የአቶ ኃይሉ ለውጤ የጋብቻ ሐሳቡ ከሌሎች የተለየና የሚያስመሰግን ሆኖ ስለታየኝና እሑድ አጣብቶ ሮብ ወደ ሥራ መሥርያ ቦታው ረጅም ጉዞውን ከነባለቤቱ ስለ ተጓዘ ነው እንጂ፤አሁንም ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር በበለ ወገንነት የማይጠረጠር የአብርሃምንና የሳራን ጋብቻ ያድርግ- ላቸው ሲል ለተወደዱ ሙሽሮች ምኞቴን እገልጻለሁ ።

ደግሞ ወይዘሮ አናሊና ተማሪያቸውን ወይዘሮ ጽጌረዳን እንደናት ሆነው በተቻላቸው ደግሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጣውን ሁሉ ምሳ በመጋበዛቸው በጣም የሚመሰገኑ ናቸው ይልቁንም የሚያስመሰግናቸው ለኢትዮጵያ ልጆች ሥልጣኔ በመጣራቸውና የሠርጉ ለት በውነት እንደወለዱ ሰውና በጎ ሥራቸው በለዩሉት የተለዩ ልብስ ነው ።

ማ ጉሹ ።

ማስማማት።

ከብዙ በጥቂቱ ከረጅሙ በጭሩ።

በወይዘሮ አምሳለ ጥበብና በአቶ ተስፋዬ ካሣ መካከል ቆላለው የነገር ድርድርና አቶ ተስፋዬ ካሣም በግልግል ስም ለጻፉት መልስ መሠረት አድርገን መስሎ የታየንን ሐሳብ ከዚህ በሚከተለው ለወዳጆቻችን እንገልጻለን።

ወይዘሮ እምሳለ ጥበብ በሴቶች ወገን ያለውን ችግር ዘር ዝረው ሲያመለክቱ ርእስ ነገሩ ነፃነት ስለነበር አቶ ተስፋዬ የሚያስፈልገውን መልስ እንደመስጠት ፋንታ ነፃነትን በሥራ ፈት ጥያ (ሸርሸር ተረጕሙት፡ የዚህ ትርጕም አካሔድ እንደኔ ሐሳብ እንደሆነ ልብ ያለማድረግ እንደሆነ ነው እንጂ እውንስ ነፃነት በዚህ ዓይነት አተረጓጐም መወጠን አይቻልም ምን ጊዜም ቢሆን በጠያቂና በተጠያቂ መካከል ዋናው ግልግሉ ስርነገሩ ነው እንደ አቶ ተስፋዬ አያይዝ እንደሆነ ግን ግልግሉ ክጫፉ ላይ ስለሆነ ነገሩ ወደ ግጭት አጋደለ፡ስለዚህ ወይዘሮ አምሳለ ጥበብና አቶ በቀለ ለተሰጣጡት መልስ እግልግል አያስኬድም ነበር፥ ቢያስፈልግም ቅሉ በሚያስገድድ ጊዜ የሁለቱ ወገን ጥያቄ በሚስማማ ግልግል ማድረግ ነበር።

ሁለተኛ።

ወይዘሮ አምሳለ አላይ ከተጻፈው ቃል አስተባብረው በሚስት ላይ የባል ሥልጣን ብልጫነት ለማስረዳት ሲፈልጉ ስለ አዳምና ሔዋን ለጻፉት ማስረጃ አቶ ተስፋዬ የሚስማማውን መልስ እንደመስጠት አዳምና ሔዋን ቀዳሚ ተቀዳሚ ሆነው ለተላለፉት ትእዛዝ (ሥልጣን) ብለው ተረጕሙት በመዘንጋት ነው እኮ?

አቶ ተስፋዬ ስለዚህ ነገር ያመለከቱት ጥቅስና በዘፍጥረት ፬ ከ፰ ፳፩ተኛ ቍጥር ከተጻፈው ቃል ጋራ ቢያመዛዝኑት የወይዘሮ አምሳለ ጥቅስ በአቶ ተስፋዬ ካሣ በኩል ዋጋ ሳያገኝ አይቀርም።

ቢሆንም በቀና ልቦና ነገሩን ለማቃናት የደከሙበት ይመስላልና የሚገባቸውን ምስጋና ለማስቀረት አንፈቅድም ።

ይህን ቃል ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምክንያቱ የሴቶች ዓይን ወንዶች ናቸውና የወይዘሮ አምሳለ ጥበብ ጅምር እንዳያቋርጥ ለማደፋፈር ጻፍኩ እንጂ በተቀረማ የኔን የተለየ ጥቅም የሚነካ ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው።

የነፃነት ዋጋ ዲካ የለውም። ሀብተ ሥላሴ ሀብተ እንድርያስ ።

ስለ አውቶሞቢል መንገድ ።

፲፱፻፳፪ ዓ ም ሐምሌ ፩ ቀን ከዲሬደዋ እስከ ሐረር ጫምብ ድረስ አውቶሞቢል እንደሔድ የዲሬደዋ ማዘጋጃ ቤት ዲሬክተር አቶ በሻህ ውረድ ከሳላህ ጀማል ጋራ በፍጥነት እንዲሠራ በኰንትራት ጨርሰው ሥራውም ተጀምሯል ነገር ግን ከዚህ በፊት እንደዚሁ ይሠራል ከተባለ እኔ እንኳን ስሰማ ከ፲፪ ዓመት ይበዛ ይሆናል ። አሁን ግን አቶ በሻህ ውረድ ዲሬደዋ ማዘጋጃ ቤት ከተሾሙ ፩ ዓመት ሳይሆናቸው እስታውሰውዋ ተግተው ይህን የአውቶ ሞቢል መንገድ አፋጥነው በማስጀመራቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል ። ደግሞ ለዚህ ሥራ የተዋዋሉት ዓረብ ሳላህ ጀማል የሚባለው በሚቋረጠው ኰንትራት ሁሉ ያለሐሰት በውነት በተነጋገረበት ቀን ሥራውን እንዲፈጽም የዚህ ቀድሞ ሥራዎቹ ይመሰክሩለታል ። የሥራውም አጀማመር አሁን እንደምናየው ከ፩ ዓመት ያልፍ አይመስለኝም ግን የሚሠራውና የሚቋረጠው ምንም በኰንትራትና በገንዘብ ቢሆን ስለ ትጋቱና ስለ እሙነቱ ለሳላህ ምስጋና አይቀርበትም፥ ይኸውም ከጥቅሙ ይልቅ ስሙን ብቻ መፈለጉን ሥራዎቹ ይገልጹልናል።ይህ የተጀመረም ሥራ በፍጥነት እንዲአልቅ ተስፋ እናደርጋለን ።

ተሰማ ስንቄ ።

ዕንቍጣጣሽ እላለሁ ለእናቴ ለኢትዮጵያ ።

እንኳን ቸሩ አምላክሽ በሰላምና በደስታ አዲሱ ዘመን ያደረሰሽ ። ደግሞም ጥንት እነበርሺበት ደረጃሽ የሚመልስሽና ከጓደኞችሽ ጋራም በጥበብ አስተካክሎ የሚያኰራሽ፡ቡሩክና ብልህ ንጉሥ የሰጠሽ፥ የዳዊት ሥር ዘሩም ነው የሚያበራ የንጋት ኮከብ፥ የዮሐ ራእይ ምዕ ፳፱ ቍ ፲፮ ይኸውም ቀዳማዊ የሆነውና የተባለው ንጉሥሽ ከዓለም ሁሉ ልዩ የሆነ ዕድልና ታሪክ ያለው ነው ። እነሆ አልጋ ወራሽና እንደራሴነት ሁለተኛም ሙሉ ሥልጣንና ንጉሥነት ካልጋ ወራሽነት ጋራ በንድነት የተሰጠው በታሪክም አላየን ባላየነውም አልሰማን ይኸው አሁንም ለንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓተ ንግሥ በዓል ኢትዮጵያ ሆይ ግርማሺንና ልምላሜሽን በመ ጥሩዎቹን አርበኞች ልጆችሽን ለማየት በፈቃዳቸው ሊመጡ የሚመኙ ብዙዎች ናቸው ይርባል ። ደግሞ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጓደኞችሽ ጋራ ባሰሩት ፍቅር በጥበብ የሠለጠኑት መንግሥቶች ሁሉ እንደራሴዎቻቸውን ሊሰዱ በደስታ በሙሉ ፈቃዳቸው ቍርጥ መሆኑን ብርሃንና ሰላም ገልጾ አረጋግጦልናል። ይልቁንም ታላቁ የብሪታንያን ንጉሥ ፯ኛው ኢድዋርድን ሥርዓተ ንግሥ ለማክበር በ፲፰፻፺፬ ዓ ም ከታላቁ ዳግማዊ ምኒልክ በሙሉ መታመን ተልከው ሒደው ያነገሡትን የዕድለኛውንና የስመ ጥሩውን የልዑል ራስ መኰንንን ውለታ ለመመለስ ጊዜው ስላ አጋጠመ የእንግሊዝ መንግሥት መላክተኞች በጣም ደስ እንዲላቸው አይጠረጠርም። ደግሞ በ፲፱፻፳ ዓም ሐምሌ ፳፭ ቀን በእግዚአብሔር ቸርነት ያገኘነውን ጌታችንን ለዚህ ሁሉ ክብር እንዲያደርስልሽ እንደልማድሽ ወደ አምላክሽ እጅሽን ዘርግተሽ እንድትለምኚ በሙሉ ተስፋ እናስታውሳለን ደጊቱ እናታችን በትሕትና በሰላም ዘለዓለም ኑሪልን። የሺጥላ ማሬ።

እሰዩታና እልልታ

ነሐሴ ፲፱ ቀን ግራማዊት መንን ከንጉሡ ቤት ተነሥተው በኢቶጌኖትዎ ግርማ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቤት ሲሔዱ የተከተለዎ የሠራዊታቸው እጅብ እምሮ ሲገዝ እምቢልታው መለከቱ እየተነፋ በማረ ዜማ ሙዚቀኞቹ እየዘመሩ አጅበው ሲሔዱ የመንገዱ ግራና ቀኝ ወንዶች በሰይታ፥ ሴቶች በዕልልታ ደስታቸውን ሲገልጹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ

ፍቅር ያልተመሰጠ የለምና ይህን ታላቅ የክብር ቀን ለማየት ሲፈሯጥ ለሚያየው ሁሉ እጅግ ያስደንቅ ነበር ። እልልታው ከስተጋባ በኋላ ምንም ለደስታዬ መጠን ለመጻፍ የሚበቃ ዕውቀት ባይኖረኝ እርሳስ ተኪሴ አውጥቼ የጻፍኩትን ማስታወሻ አላስቀርም ስል ላንባቢዎች አከፍላለሁ ።

ማህሉ ጽጌ ።

ስለ ክቡር ራስ በጎ ስምና ።

ስለ ባላምባራስ ክፉ ስም።

ገቢና ወጭ ገንዘብ ።

ክቡር ራስ በጎ ስም ድሀ ሳይበድሉ ፡ ማማለጃ ሳይበሉ በሚገባ ዳኝተው፡ ቃኝተው ባገኙት ገንዘብ ለበጎ ስማቸው መኖርያ መንግሥተ ሰማይ የምትባል ጥሩ ቤት ባባታቸው በክርስቶስ ርስት ሠርተው ይኖራሉ ። ባላምባራስ ክፉ ስምም ሰው ሸንግለው፡በሐሰት ምለው፡ የሰው ርስት ነቅለው፡የማይሞቱትውን ገድለው፡ የሚሞተውን አድነው ባገኙት የግፍ ገንዘብ ለክፉ ስማቸው መኖርያ ቤት ገሃነም የምትባል ጥቅጥቅ ያለች ጠንካራ ቤት ባባታቸው በዲያብሎስ ርስት ሠርተው ይኖራሉ።

ነገር ግን ብርሃንና ሰላም ሳይጻፍ የሁሉም ነገራቸው ተሠውሮ ይቀር ነበር ። ስንኳን ለሌላ ሰውን ከብዙ መከራ ለማዳን የሚፋጠኑ መላእክት ከተሳለ ሰለት፡ ከነደደ እሳት፡ ከተተከለ ግንድ፡ ከተፈተለ ገመድ ደርሰው ላለቁ ሰማዕታት ዳዋ ጥሰው፡ ጤዛ ልሰው፡ ድምፀ አራዊትን ፀብዐ አጋንንትን ታግሠው ላለቁ ጻድቃን ሥራቸው የተጻፈው በግዕዝ ስለ ሆነና ከንባቢውም ከሰሚውም ትርጓሜውን የሚሰማው ከሺ አንድ ስለ ሆነ ተሠውሮ ይኖራል ። ያውም የሚገኘው በፊክ ነው ብርሃንና ሰላም ግን የሊቃውንቱን ዕውቀት፡የጀግኖችን ብርታት፡ የዳኞችን እውነት ገልጦ ሲጽፍ ደስ ይለኛል ። ከለዕታት በንዳቸው ቀን የብርሃንና ሰላም ዋጋ ተቀባይ ያምስተኛውን ዓመት ዋጋ አምስት ብር ላክ ፤ሎሃል ብሎ የብርሃንና ሰላምን ማፋተም ቢያሳየኝ ለኔ አምስት መቶ ብር ይዞልኝ የመጣ መሰለኝ ብርሃንና ሰላምን ከመውደዴ የተነሣ የሦስቱን ዓመት አንድ ላይ ባስጠርዘው ታላቅ መጽሐፍ ሆነ ከጠረጴዛዬ ላይ መጕናጸፊያውን ለብሶ ሲታይ ይገርማል።ያንንም አይቶ ብልህ ያደንቃል ሞኝ ይስቃል ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን

ማመልከቻ ።

ትንሽ መፈተኛ ስለ እርሻ ትምህርት በተባለ መጽሐፍ «መዓዛ የተባለው ጣዕም» ደግሞ «የሰሚን ተራራ በትግሬ ውሥጥ»የተባለው በበጌምድር ውሥጥ ተቀሎ እንዲነበቡ ።

እነዚህ ሁለት ዋና ስሕተቶች ላንባቢዎች ጕዳት እንዳይሆኑ ነው

ሬታውራሪ ተክለ ሐዋርያት ።



የ፩፱፻፺፩ገጽ ተከታይ።

ስድስተኛ ክፍል ።

ስለ ደምብ አኩዋሆን ።

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ከውጭ አገር የመድኃኒት ማስመጫ ጥያቄ ወረቀቶች የሚመረምሩ አንድ ወይም ሁለት ሐኪሞች ያቆማል ።

የአገር ግዛት ሚኒስቴር ወይም ዲሬክተሩ በተቀመጡበት ሁለት የተለዩ ሐኪሞች ተጨምረው የሐኪሞችና የመድኃኒቶች ቀማሚዎች መዝገብ ይመረምራሉ ።

ይኸውም የምስክር ቤት ክፍል ሥራ በዚሁ ሕግ መተላለፍ፡ በሆነው ነገር ሁሉ በሰማውና እሱም ራሱ በገኘው ነገር ሁሉ እንደዚሁ እንዲጠይቅና እንዲመረምርም ግዴታ አለበት ነገር ግን ተከሳሹ የውጭ አገር ሰው የሆነ እንደሆነ ይሁ የምክርቤት ክፍል ሥራ የተወላጅነቱ ወይም የጥገኝነቱን ቆንስል ጨምሮ አንድ ላይ ሊመክር ግድ ያስፈልገዋል ።

Art. 6

Dispositions d'application.

Le Ministère de l'Intérieur chargera un ou deux médecins qui statuera sur toute demande d'importation.

Une commission spéciale composée de deux médecins sous la présidence du Ministre de l'Intérieur ou du directeur contrôlera les registres des médecins et phaarmaciens.

Cette commission est également chargée d'instruire et d'enquêter au sujet des infractions à la présente loi qui lui seront signalées ou qu'elle découvrira elle même. Si l'accusé est un étranger cette commission s'adjoindra obligatoirement le consul dont il est ressortissant ou protégé.

ከዚህ የቀረው በሚመጣው ቍጥር ይቀጠላል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠደቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር ብጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-ብላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ ባያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያከማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያከማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቴክ ኬዎርኪፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM



የወርቅ ሰዓት ።



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ- ነት የተሰማ አሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኜይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



አዲስ ዓይነ ቦርሳሊ ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው ። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ። በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲ- ስናልጆቹ -የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፴፱
6me ANNEE № 39

ሐሙስ መስከረም ፲፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 25 SEPTEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የአፄ መስቀል።

በመስከረም ፲ ቀን የአፄ መስቀል ነበርና በዓሉን ለማክበር በታላቁ ቤተ መንግሥት ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ነበር ። ብመንገዱ ግራና ቀኝ የሮፓን ሰልፍ የተማሩ ወታደሮች ተሰልፈው እጅግ ያምሩ ነበር ። ፬ ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ ወደ ሰገነቱ መጡና ከፍ ባለው ዙፋን ተቀመጡ ። ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በቀኝ፥ የኢትዮጵያ ጳጳሳት በግራ ተቀመጡ ። ቀጥለው ልዑል ራስ ሥዩም፥ ልዑል ራስ ጉግሣ ፥ ፊታውራሪ ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴር፥ ልዑል አስፋ ወሰን ተቀመጡ። የቀሩትም መኳንንት በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ፡ ቀጥለው የውጪ አገር መኳንንትና ወይዛዝር ከውጪ ጉዳይ ዋና ዲሬክቴር ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ጋራ መጡና ከሰላምታ በኋላ በተዘጋጀላቸው በቀኝ ወገን በየማዕርጋቸው ተቀመጡ ። ቀጥለው ካህናቱ እንደ ቀድሞው ልማድ ቀሳውስቱ መስቀላቸውን ይዘው፥ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፥ ዲያቆናትም ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው አክሊላቸውን ደፍተው ታላላቅ መስቀላቸውን ይዘው ከሊቀ ካህናቱ ከመልአከ ገነት ወልደ ሐና ጋራ መጥተው እጅ ነስተው ቆሙ።ከዚህ በኋላ ሽማግሎች ተቀመጡና መዘምራኑ በአማረ ሰልፍ ቆሙ፥ ተራው የመናገሻ ማርቆስ ካህናት ነበርና ቄሱና ዲያቆኑ ለብቻ ተለይተው ቆመው ዲያቆኑ ቅንት ሰይፈከ ኃያል ውስተ ሐቌከ በሥንከ ወበላህይከ አርትዕ ተሠራህ ወንገሥ የሚለውን ፵፬ተኛውን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አቈጣጠር ፵ን ፵፭ ኛውን መዝሙር ሰበከ። ቄሱ ከማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፬ ቍጥር ፩ አነበቡ ። ከዚህ በኋላ ደብተራ ወልደ ማርያም የሚባሉ ድምፀ መልካም ሽማግሌ ከተመረአቸው ከመምሬ ወልደ ሚካኤል ጋራ እስመለዓለሙን ቃኝተው አንገርጋሪውን ርእዩ ዘገብረ እግዚአብሔር ብለው ዜማውን ሲአንቈረቍሩት

የደብተራ ወልደ ማርያም ድምፅ እጅግ ያምር ነበር ። ከማማሩም የተነሣ ልብ ያዘነጋ ነበር። ምሥጢሩም ዘንድሮ እግዚአብሔር ለአደረገው ነገር ታስቦ የተነገረ ይመስል ነበር እንጂ ቀድሞ የተባለ አይመስልም ነበር ። ከዚህ በኋላ ካህናቱ የወርቅና የብር ከበሮአቸውን ይዘው ሲአሸበሽቡና ሲወዛወዙ ነፋስ የሚአወዛውዘው በበረሃ የበቀለ ሸምበቆ መስለው እጅግ ያምሩ ነበር ። ከዚህም በኋላ የእስመ ለዓለሙን መጨረሻ ኢይሔሱ ቃሎ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት እያሉ ይወዛወዙ ነበር ። ከዚህም በኋላ በከመ ይቤ ሰሎሞን የሚለውን ዕዝል ደብተራ ወልደ ማርያም መሩና ምልጣኑን ተቀጸል ጽጌ ኃይለ ሥላሴ ጎዜጌ ተቀጸል ጽጌ ብለው ሲመሩ የማማራቸው ነገር በላይ እንደጻፍነው ነው ። የመጀመሪው እንሺ የአቃቂ መድኃኔ ዓለም ደብተራ ገብረ አምላክ፥ ፪ኛው እንሺ የእስጢፋኖስ ደብተራ ተክሉ ነበሩ። ሁለቱም ድምፀ መልካሞች ናቸው።

እንግዲህ የከርሞ መሪዎች በመጀመሪ ያነሣው ወገኖች የአቃቂ መድኃኔ ዓለም ካህናት ይሆናሉ ። የሁለተኛው ዓመት መሪዎች ሁለተኛ ያነሣው ወገኖች የእስጢፋኖስ ካህናት ይሆናሉ ። ምራቱ የኛ ነው ፤ የኛ ነው እየተባባሉ ሲከራከሩ ሰምቼ ነበርና ለሚመጣው ጊዜ መታሰቢያ እንዲሆን ጽፌዋለሁ ። ምን አገባውና የመሪዎችን ተራ ይጽፋል ትሉኝ እንደሆነ ፤ ሰው ተራውን ቃወቀው አይጣላምና ሰላምን ማሳሰብ ሥራዬ ስለሆነ ነው ።

እንግዲህ ወደ ጀመርነው ነገር እንመለስ። ወረቡ ከለቀ በኋላ ካህናቱ አበባ ይዘው ለጃንሆይና ለጳጳሳቱ ፥ ለመኳንንቱ ሰጥተው መስቀል አሳልመው ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ በበጅሮንድ ዮሴፍ አስተርጓሚነት ስለ መስቀል በዓል አከባበር መልክም ስብከት ሰብከው መርቀው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ።

የውጪ አገር መኳንንትና ወይዛዝርም ከጃንሆይ እየተሰናበቱ ወጡ ። ከ፯ ሰዓት በኋላ ለካህናቱ ታላቅ ግብር ተደርጎላቸው ዋለ ። ያች ስመ ጥሩይቱ ቀን እንዲህ ሁና በመልካም ዋለች ።

የአፄ መስቀል ማለት እኔ እንዳነበብሁት ታሪክ ዕሌኒ ንግሥት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል አይሁድ ተቀብረውበት አስወጥታ ለክርስቲያን መንግሥት ሁሉ ስታካፍል የኢትዮጵያ ንጉሥ መልእክተኛ ድርሻውን ይዞ ሲመጣ የኢትዮጵያ ንጉሥ አፄ ዳዊት ሰናር ድረስ ወርደው ተቀብለው በዓል ያደረጉበት ቀን ነው ይላል ። ስለዚህም ለዚያ ቀን መታሰቢያ በዓመት በዓመቱ በመስከረም ፲ ቀን ወደ ንጉሡ አደባባይ ሒደው በዓል የሚአደርጉ ስለሆኑ የአፄ መስቀል ብለው ካህናቱ ሰየሙት ይባላል ። እኔ ያነበብሁት ታሪክ ይህ ነው ። ደግሞ ሌላ ታሪክ የምታውቁ ሰዎች ብትጽፉልኝ በብርሃንና ሰላም ታትሞ ይታይላችኋል ።

አረቄ ስለ መጠጣት የሀገር ጕዳት ።

በትንሽዋ በድሬዳዋ ከተማ አርባ ሁለት ስፍራ አረቄ የሚጠጣባቸው ቤታዎች ተዘጋጅተዋል። በድሬዳዋ ከተማችን ከክርስቲያኖቹ ይልቅ የእስላሞቹ ቍጥር ይበዛል መንደራቸውም ጥቂት ጥቂት የመለየት ምልክት አለባቸው። በነዚህም በዋና በዋናው መንደር የአረቄ መደብሮች ተከፍተው ሰውን ሁሉ በጤናውና በገንዘቡ ያለመጠን ይጐዱታል ። በዚሁ ምክንያት የድሬዳዋ ሕዝብ ሀብቱና ጤናው እያነሰ ሒዷል።አንድ አንድ አደሬዎችና ዓረቦች በየመንገዱ ሰክረው ሲንገደገዱ ማነው የገፋን እያሉ እየተሳደቡ ወደማታ ያልጠጣውን ሰው ሁሉ ሲያስቁት ያመሻሉ ። ይህም አረቄ በድሬዳዋ ከተማ ያለውን ሕዝብ ብቻ ለመጕዳት አልበቃውም ። አስቀድሞ አረቄው ከምድር በቡር እንደወረደ መጀመርያ የድሬዳዋን ሕዝብ ድል አድርጎን አለፈ ለማለት ነው እንጂ ከጨርጨር ጀምሮ በጫ በሚተከልባቸው አገሮች ሁሉ እስከ ጅጅጋ ነጋዴዎች አረቄ አቸውን እየጫኑ ይሸቀጻደማሉ ። እንደዚህም መቀዳደማቸው ጥቅሙ በሁለት በኩል ስለሆነ በጣም ይተጉበታል ። በመጀመርያ አረቄውን ሲሸጡ ብዙ ትርፍ ያገኛሉ፤ ሁለተኛ በዚያው ትርፍ ቡና ገዝተው ሸጠው የበለጠ ትርፍ ያገኛሉ፤ የቡናው ትርፍ መልካም ነበር ዳሩ ግን ቡናን ለመፈለግ የአረቄ ረዳትነት ሰውን ጐዳው ብለን ነው እንጂ የቡናስ ትርፍ ለመንግሥትም ለሕዝብም አይጐዳውም ። ስለምን አረቄውን እቡና ተካዩ ደጅ ስለ አቀረቡት ቡናህን ለአረቄ ለውጠን ለማለት ነውና ቡናውን የሚሸጥላቸው ገበሬ አረቄው እዚያው አጠገቡ ስለሆነ አረቄ ከመጠጣት አደጋ አለመዳኑ የታወቀ የተረገጠ ነው ። ይህ አራሽ ገበሬ ካጠገቡ አረቄው በሩቅ ካልሆነለት ለመጣዛት ግዴታ አለበትና ሊታገሥ አይችልም።ፈተና አሳቡን ያስፈጽመዋል ገበሬዎችም እንደከተማ ሰዎች አረቄ የሚጠጡ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጕዳት መሆኑን የሚስተው የለምና ለማስረዳት አልደፍርም ። ገበሬው በዚሁ በመጠጣቱ ምክንያት ዓቅሙ አነሰ፥ የርሻም ሥራ ተቀነሰ ለማለት ይቻላል ። ጕበዙ፥ ትጉሁ ፤ ባለጤናው፥ የሁሉ ፥ ምሳ ፤ የሁሉ ራት ፥ የሁሉ የሀብት መሠረት ፤ ዋደጉ ሰው የገበሬው ደረት ልቡ ተነካ የርሻ ሥራ ቀረ ወደቀ ሕዝብም አለቀ የሀብትም መሠረቱ ተነቃነቀ ማለት ነው ። እንግዲህ የሐረርን አውራጃ ምሳሌ አድርገን በሙሉ ኢትዮጵያ አርቀን ብንመለከተው ከዚህ ይዘልጣል እንጂ እያንስም ይህም አረቄ ብልሀት ሳይደረግበት እንደዚሁ ከቈየ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጤናውና ሀብቱ እየአነሰ፥ እየደከመ እየበረደ፥ ዘሩም እያነሰ መሔዱ አይጠረጠርም ። በኢትዮጵያ አእምሮና ብርሃንና ሰላም የሚባሉት ጋዜጦች ከቆሙ ጀምሮ እስካሁን የዚህን የአረቄ ነገር በዝርዝር እያደረጉ ሕዝቡን እንደሚጐዳው አስረድተዋል ደክመዋል ። እንግዲህ ለሀገራቸው ለሕዝባቸው ለወገናቸው ለወንዛቸው አስበው ደክመው እየጻፉ ያስታወቁት የኢትዮጵያ ልጆች አንድ አንደ እንኳን የዚህ የአረቄ ነገር ካልተፈጸመ ጋዜጣ የሚአትሙትም፥ ጋዜጣ ገዝተው የሚአነቡትም በከንቱ እንዳይደክሙ ያሰበባል ። ሰው የሆነ ፍጥረት መልካም አሳቡና ምኞቱ ካልተፈጸመለት አሳቡ እየደከመ እውቀቱ እየነቀሰ ይሔዳልና ማነቃቃት ማስፋፋት ማፅናናት ያስፈልገዋል።በጋዜጣም የሚጻፈው ቢፈጸም ጋዜጣ የሚያነቡትም የሚጽፉትም የሚአዳምጡትም እየበዙ ለመሔድ ይችላሉ እንደዚህም ሲሆኑ አንድነታቸው እየፀና ሐሳባቸው እየቀና

ኃይላቸው እየገነነ፥ ሀብታቸው እየበረከተ ፥ ደስታቸው እየሞቀ ከፍ ብሎ ይልቅ ጠላቶቻቸውን ያሳፍራሉ ወዳጆቻቸውንም ያኰራሉ አረቄ መጠጣትና ከወጭ አገር የመጣ ሐር መልበስ ቢቀርብን ይሻላል እንጂ አንጐዳም።በአረቄም ፈንታ ከሀገራችን ጋራዎች የሚፈልቁት ምንጭዎች የላሞቻችን ወተት በየጫካችን ያለው ማርና ጌሾአችን ይበቃናል ። ሐርና ከችም በብዙ ቀለማት አጊጠው ከውጭ አገር የሚመጡትም ሸማዎች የኛን ገንዘብ ለመከፋፈል ነው እንጂ የሚጠቅሙን ነገር የለም።ሐር መልበስ ስንኳን ቢአምረን እኛ ሥርተን እለበስን ድረስ ይቈየን ሌላ ሸማ እንለብሳለን፥ አሁን ሥራ አለብን የሥራ ጊዜ ሐር አይለበስም ይኸንን ትተነው ወደ ቀደሞአችን እንመለስ ። እንግዲህ ዕውቀትና ጤና ገንዘብ ለሰው የሚያስፈልጉ የኑሮው መሠረት ናቸውና ሦስቱን ሰው ካላገኘ የዚህ ዓለም አሸናፊ አይደለምና ገንዘቡ ያነሰ፥ ኃይሉና ጤናው የተቀነሰ ሕዝብ እንኳን ጠላቱ ሊፈራው መኖሩም አይታወቅ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ አረቄ መጠጣት ዘቶሎ ካላመለጠ ለነፃነቱ እንኳን ያስፈሪዋል ። በገንዘብና በጤና በኩል የመጣ ጠላት ከጦርነት ይበልጣልና በቶሎ ሰው ሳያልቅ መቃወም ነው ። የሰውም ሕለ የሚባልበት ዋና መሠረቱ ኑሮው ገንዘቡና ጤናው ነውና ከቀረው የሚበልጥበት የብርሃንና ሰላም ማኅበረተኞች የሀገራቸውን ጕዳት እያዩ በዝምታ ጊዜአቸውን ለማሳለፍ የማይፈቅዱ ስለሆኑ አይሰለቹም ።

በዓሰቦትና በበተሐራ ሚዳ የሚኖሩ ሕዝቦች ጤናቸው በከተማ ከሚኖሩ ሕዝቦች ይበልጣል ። ፋጠው አይደክሙ፥ ተናግረው አይፈሩ፥ምን ቢራቡ ቢጠሙ አይከሱ፥የወለዱአቸው ልጆች ከማደጓ በተቀር አይሞቱ ፥ ሴቶቻቸው አይመክኑ እንደዚህም የሆኑት ባይጠጡ ነው እንጂ የሚቀመጡበትማ አገር ወበና አረሞጫው ያለመጠን ብርቱ ነው ።

የዚህም የበረሐው ሕዝቦች የቀረባቸው ነጭ መልበስ በፍራሽ መተኛት፥አረቄ ጠጥቶ መታመም፥ገንዘባቸውን ለማይ ረባው አረቄ መለወጥ ነው እንጂ ከሌላው ሕዝብ ምንም አላነሱም ።

ይህንንም አረቄ መጠጣት ብንተው የሚቀየምብን ሰው የለም ምናልባት የአረቄ ፋብሪካ ያላቸውና ከዚያም የሚአመጡ ነጋዴዎች የሚቀየሙ ቢሆን እንኳን አይገባቸውም ስለምን በኢትዮጵያ አረቄ መሸጥ ከጀመሩ ወደ ፴፫ ዓመት ሁኑዋልና በግድ ራሳቸውን ሳይችሉ አልቀሩም እንግዲህ ይበቃቸዋል እኛም ሰውነታችን ተጐዳ፥ ዘመዶቻችንም አለቁ እንግፈገፈን በቃን ። ዘለቀ ታችበሌ ።

ምክር ።

ጥበብን መግዛት ምንኛ ከወርቅ ትሻላለች፥ በጥበብ የሚሠራ መልካም ነገር ይገኛል፥የትምህርት ቤት የሥልጣኔ ምንጭ መሠረትና የከፍት አሳብ አስወጋጅ መሆንዋን አውቀው ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰሎሞንን መንበር ወራሽ ከሆኑ ጀምረው ንጉሠ ነገሥት እስከተባሉ ድረስ ሁል ጊዜ ፍጻሜነት ያላቸው ባለ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ፣ ትምህርት ቤት ማቆማቸው ከጨለማ መንገድ ወደ ሥልጣኔ ብርሃን የወጡ የኢትዮጵያ ልጆች ትምህርት ያስረዳናል። ያለ ትምህርት ቤት ጥቅምና ሥልጣኔ እንደማይገኝ አንድ ምሳሌ እንዲህ ይላል፥ ያልተማረ ሰውና ያልታነፀ እንጨት አንድ ነው ይላል፥ሁለተኛ ከመጽሐፍ የተረጐሙ ሁት የ ሁዳዎች ምሳሌ ደግሞ እንዲህ ይላል፥ መጽሐፈ ሳምበት ልጆቹን የማታስተምረውን አገር ይረግማታል የትምህርት ቤት ጸላት ከመቅደስ ጸላት ትበልጣለች ይላል፥ ትምህርት ቤትም አይፈርስም የየሩሳሌም መቅደስ እንኳን ሊሠራበት ቢአስፈልግ ይላል ይህ የይሁዳዎች ምሳሌ በማናቸው በኢትዮጵያ መንግሥት ክፍል በመኳንንቶቹ ቤት በወርቅ ጽሕፈት ሊጻፍ የተገባ ነው።ስለዚህ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ ክፍል ብዙ የትምህርት ቤት ማቆማቸውን ማናቸውም የኢትዮጵያ ሰው አይስተውም።ነገር ግን መንግሥት ያለ ሕዝብ፥ሕዝብ ያለመንግሥት ሊቆም የሚያስቸግር ነገር ነውና በኢትዮጵያ ክፍል ውሥጥ ያሉ መኳንንቶች መሳፍንቶችና አገረ ገዢዎች አንዳንድ የትምህርት ቤትና አንዳንድ መታከሚያ ቤት ሊአቆሙ በጥቂት ዓመታት ውሥጥ በመላው የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ የሠለጠኑ ተማሪዎች እንደሚሆኑ አይጠረጠርም። እነሆ ክቡር ደጃዝማች ብሩ በግዛታቸው ሲዳሞ እንደገቡ በተመልካች አሳባቸው የመታከሚያ ቤትና ትምህርት ቤት እንዳቆሙ በብርሃንና ሰላ ም ስለምረቃው የተጻፉት ቃሎች ያስረዱናል፥ክቡር ደጃዝማች ብሩ ያገር ፍቅር የምትባለውን ቃል የትምህርት ቤትና የመታከሚያ ቤት በማቆማቸው ፈጽመዋል። ስማቸው ም ስለታላቁ ሥራቸው በወርቅ ቀለም በታሪክ ጸሐፊዎቹ መጻሕፍት ሊጻፍ የተገባ ነው። ሁለተኛ በሰላም ያረፉት ክቡር ራስ ናደው በኢሉባቦር ትምህርት ቤት ማቆማቸው ለመንግሥታቸው እርዳታና ለሀገራቸው ጥቅም በማሰባቸው ነው ። ደግሞም የሰው አሳብና የእግዚአብሔር አሳብ ባልተለያየና ዕድሜአቸው በቆመ ብዙ የሚጠቅም ሥራ ለመንግሥታቸው እርዳታ አሳብ እንደነበረባቸው ከስማቸው ጋራ ሐውልት ሁና የቀረው የተማሪ ቤታቸው ያስረዳናል ። ስለዚህ ባውሮፓ እንኳን በየነገሥታቱ መንግሥቱ ከሚአቆማቸው የትምህርት ቤትና የመታከሚያ ቤቶች በስተቀር ሕዝቦችም በየክፍላቸው እየሆኑ የትምህርት ቤቶችና የመታከሚያ ቤቶች እንደሚአቆሙ በኢትዮጵያ መንግሥት እንኳ የሚኖሩ ጥቂቶች አውሮፓውያኖች ያለመንግሥታቸው እርዳታ ትምህርት ቤት ማቆማቸው ያስረዳናል ። የግሪክ መንግሥት የነፃነት ስለነበረ በኢትዮጵያ ያለው የግሪክ ማኅበር በሆቴል በዓል አድርገው ነበረና በዚያው በበዓል ቀን የግሪክ መንግሥት ቆንሲል ዶክተር ዘርቦስ ለሕፃናቶች ፍጻሜነት ያለው አዲስ የትምህርት ቤት በልዩ ዓይነት ቋንቋዎች ለማቆም እንደሚአስፈልግ በማኅበሩ ስም ሁነው ለበዓሉ ለተጠሩት ግሪኮች ዲስኩር አድርገው ወዲያው ሁለት ሺህ ብር ከራሳቸው በሰጡ ወዲያው ሙሴ ቴማሊዎን አርማንዛስ ዓሥራ ስድስት ሺህ ብር ስለሰጠ በአንድ ሌሊት ወደ አምሳ ሺህ ብር ያህል ገንዘብ ለማኅበሩ እርዳታ ለተማሪ ቤት ማቆሚያ ተሰጠ።ደግሞም የግሪክ ቤተ ክርስቲያን በማኅበሩ እርዳታ እንደተሠራ ብዙ ሰዎች አይስቱም።ስለዚህ ይህ ለተማሪ ቤቱ የተሰጠ እርዳታ በጣም የሚአስመሰግን ነው ። ደህንን

መልካም አሳብና ለተማሪ ቤቱ የሆነውን እርዳታ ካየሁ በኋላ አንድ የሚያስገርም ጥያቄ በአሳቤ ተወለደብኝ፤ እኒህ ጥቂቶች ግሪኮች ለጠቃሚ ሥራ ለትምህርት ቤት ደክመው ለፍተው ከሚጥሩበት ገንዘባቸው ይህን ያህል ገንዘብ ሲሰጡ የኢትዮጵያ መሳፍንቶች መኳንንቶችና አገረ ገዦዎች ገንዘባቸው እንኳን ለትምህርት ቤቶችና ለብዙ ታላላቅ ሥራ የሚበቃ ትምህርት ቤት ሆርቃሎች በየግዛታቸው አለማቆማቸው ምክንያቱ ምን እንደሆነ የጥያቄዬን መልስ መወሰኛ አጣሁ ። እነሆ አርመኖችም ጥቂቶች በኢትዮጵያ ያሉ ትምህርት ቤትም ቤተ ክርስቲያንም አላቸው። ደግሞም በማኅበራቸው እርዳታ በጥኑ ሕንፃ እየሆነ አዲስ ቤተ መቅደስ መሥራት ከተጀመረ ብዙ ጊዜው ነው ። ስለዚሁ ለክቡራን መኳንንቶች ማስረጃ በጭር ቃል ይህን ጽፌአለሁ ። ሁለተኛም የትምህርትን ቤትና የመታከሚያ ቤትን ጥቅም በዝርዝር ለመጻፍ ስለማይቻለኝ ጥቅም እንዳለው የሚያስረዳን በጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በራሳቸው ገንዘብ የተሠሩትን ትምህርት ቤቶችንና የመታከሚያ ቤቶችን ብንመለከት ጥቅሙ ከዕንቍ የከበረ መሆኑን እንደፋና ሆኖ ያስረዳናል ፤ ክቡራን መኳንንቶች መሳፍንቶችና አገረ ገዦዎች ለሀገራችሁ ጥቅም ፤ ለመንግሥታችሁ እርዳታ ለስማችሁ መከበሪያ እንዲሆናችሁ በየግዛታችሁ የትምህርት ቤቶችና የመታከሚያ ቤቶች ታቆማላችሁ ስል ሙሉ ተስፋ አድርጌ አሳስባለሁ ።

ሚካኤል ማክራስ

ትምህርትን በማቆም ስለሚገኝ ጥቅም ።

ሽፈራ ወልደየስ የቢሮ ሳንትራል ጸሐፊና ማናለ ይግለጡ የቢሮ ቴሌፎኒስት(ስልከኛ)ስለጨርጨር አውራጃ ብርሃንና ሰላም ሲጽፉ ሌላውን ሁሉ ያገር ጉዳትና መልማት ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በብርሃንና ሰላም ሲአስታውቁ የትምህርት ቤት ያለመኖሩን ጉዳትነቱን አስበው ባለመጻፋቸው ቅር ስለሚአሰኝ ከነርሱ ሶስተኛ ሆኜ ባልቃረመች ዕውቀቴ ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ትልቅ ጉዳት መሆኑን በግልጽ አስታውቅ ዘንድ ጃንሆይ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ሲሉ በያለበት ያዘጋጁትን የሥልጣኔ ትምህርት ቤት በማየቴና የሀገሬ ፍቅር ስለሚአስገድደኝ ባልተቃናች ሐሳቤና በደከማው ጉልበቴ ይህንን እጽፍ ዘንድ ይፈቅዱልኝና ይታተምልኛል በማለት ጥልቅ የሆነ ሐሳብና ምኞት ወደፊት ይታየኛል።መቼም ሰው ያሰበው ነገር ይሆንልኛል ይላል እንጂ ይከፋብኛል አይልምና ክቡራን የብርሃንና ሰላም ወዳጆችና አንባቢዎች ሆይ የነቀፌታ ቃል ቢገኝብኝ እናንት አርሙልኝ እንጂ ከፍ ፋት እንዳትቄጥሩብኝ ክቡርነታችሁን እለምናለሁ ።

ከዚህ በኋላ ቀጥሎ ያለውን እስከትላለሁ፡ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ሐሳባቸውና ድካማቸው መልካሟ ሀገራችን ወደመጀመርያ ሥልጣኔ ደረጃ እንድትደርስና ከሌላው አገር ሁሉ እንድትተጋ በዕውቀትም አጥር እንድትከበብ ስለሆነ የሚጥሩት በሐረር አውራጃ ላሉ ወጣቶች የትምህርት ቤት በማቆማቸው ሕዝቡ ሁሉ ደስ ብሎታል ማለትን እንሰማለን።እኛም የጨርጨር አውራጃ ወጣቶች ጃንሆይ ለሐረር ልጆች ያደረጉላቸውን የዕውቀት መክፈቻ ለኛም እን ደዚያው ሳያደርጉልን አይቀሩም ሐሳባቸው ሁሉ ለሀገራቸው ልጆች ነውና በማለት በተስፋ ተሞልተናል ባልችንም ዕውቀታችን ሀገራችን ከመንግሥታችን ጋራ ለዘለዓለም ትኑር እንላለን።

ደግም ከዚህ በታች የጨርጨርን ወጣቶች በከንቱ መቅረት እጽፋለሁ ። ጨርጨር በሚ ትንሽ ነው እንጂ ሕዝቧ ብዙ ነው ነገር ግን እንደ ሌላው ሀገር በቶሎ አለመቅናቷና አለመሠልጠንዋ መልካም የሆነ የመንግሥት ተማሪ ቤት ደኅውም ጌታውም እኩል ያለችግር የሚማርበት ስላጣች ነው እንጂ የሕዝቧ ማነስ አላሳነሳትም ነበር ።እንኳን ትልልቁ ሰዎች በውራጃዋ ያሉትን የባላገር ልጆች ለመቍጠር በጣም ይቸግራል።ይሁን እንጂ እንደዚህም በመብዛታቸው ለሀገራቸው ውና ለመንግሥታቸው አያስቡም ማለት ሀገራቸውን ጠልተዋት አይደለም።ነገር ግን ትምህርት ባለመማራቸው ጥቅሙን ሳያውቁት ቀርተው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዕውቀት የሚያከናውንላቸው ሰው በማጣታቸው በከንቱ በጭለማ ውሥጥ ይኖራሉ አባቶቻቸውም ልጆቻቸውን አስተምረው ከጭለማ ወደ ብርሃን ቢወጡላቸው አይጠሉም ነበር። ነገር ግን ገንዘብ እየከፈሉ ወደ ሌላ አገር ልከው ሊአስተምሯቸው የማይቻላቸው ስለሆነ ነው እንጂ ልጆቻቸው ዕውቀት ቢአገኙላቸው አይጠሉም ። ይኸንን ሁሉ ያሰሰበኝ ብዙ መልካም የሆኑ ልጆች በያለበት ስመለከት ለዕለት እንጀራቸውና ጥቅማቸው ሲጥሩ አያቸዋለሁ።እንጂ ባለን ዕውቀታችን ተምረን ለሀገሬችን ጋሻ እንሁንላት ሲሉ አልሰማሁም። ሐሳባቸው ሁሉ የተሰጣቸውን በልተው ጠጥተው ከንዱ ቤት አንዱ ቤት እየተመላለሱ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ማውራት ነው በተቻላቸው ጉልበታቸው ስንኳን አባት እናታቸውን በሙሉ ልባቸው ለመርዳት ትልቅ ለመውጣት የማይቻል ኩረብታ መስሎ ሥራው ሁሉ ይታያቸዋል ይልቁንም አባትና እናታቸው በተቄጠ.ቸው ጊዜ አራት አምስት ሁነው ለመክዳት ይዶልታሉ እንጂ አባት እናታችን ለፍተው አሳድገውን እስቲ ቢጣሉን እንኳን አሳልፈን በተቻለን አቅማችን እንርዳቸው እንጡራቸው እንደማለት ከነርሳቸው ርቀን ጌታ ብናገኝ ለጌታ አድረን ብናጣም በበረሃ እንኖራለን ለቁራሽ እንጀራ ብለን እንጨቀጨቅም ተባብለው መልካሞች የሆኑ ዘመዶቻቸውን ትተው ይልቁንም መልካሚቱን የተወለዱባትን ሀገር ተለይተዋት በሰው አገር ይሔዱና የሚአውቀን ሰው የለም ብለው ሌባ ወይም ሽፍታ ሆነው ይኖራሉ። ጊዜ ባጋለጣቸው ቀን በሌባ ወይም በሽፍታ ስም ተይዘው በዘብጥያ ይታሰሩና እዚያ በበሽታ ሰበብ ይሞታሉ እግዚአብሔር በሰጣቸው ዕውቀትና ጉልበት አንድም ፍሬ ያለው ነገር ለሀገራቸው ሳይሠሩ ለዘመዶቻቸውም ሳይጠቅሙ በከንቱ ራሳቸውን በድለው ጊዜአቸውን ያሳልፋሉ ለዚህ ሁሉ መድኃኒቱ ጃንሆይ በከንቱ የሚጠፉ በጎቻቸው አሳዝነዋቸው እንደ ሌላው አገር ሁሉ ትልቅ የሆነ ተማሪ ቤት ቢአቆሙላቸው ከንደዚህ ያለ ድንቍርና ወጥተው መልካም ዕውቀት አግኝተው ለመንግሥታቸው ረዳትና ለሀገራቸው ሚች ይሆናሉ እንጂ ወደ ሌላ ምኞት አይመለሱም ነበር በማለት ነገሬን እፈጽማለሁ። ለዚሁም ጃንሆይ የሚአሳያቸው ነገር ሆኖ ለጨርጨር አው-

ራጁ ተማሪ ቤት ያቆሙልን እንደሆን በተቻለኝ አቅሜ ከባቴና ከናቴ ገንዘብ ጀብር እርዳታ ዓስበ ኃይለ ሥላሴ ግምጃ ቤት ብመጀ ሪያ አገባለሁ። ስለሽ ወልደየስ ዘብሔረ ግሼ ።

ምክር ።

በአደስ አበባና በሌላውም ልዩ ልዩ ከተማ ሁሉ የሚኖሩ ሴትኛ አዳሪዎች ከባላገር በትንሽ ምክንያት ወደከተማ ይመጣሉ ከመጡም በኋላ እንደቀኖች (ደግ)ሴቶች ንብረት ይዞ ለርል አገልግሎ (ረድቶ) መኖር ነውር መስሏቸው ደመቅ ባለ ባቡር መንገድ ዳር ላሉ ቀደም ብለው በከተማ ለሠለጠኑ ሴትኛ አዳሪ ዎች ግርድና ተቀጥረው የቀድሞዎቹን ክፉ ግብር(ትምህርት) ይማራሉ እነዚሁም እንግዳ ባላገር ሴቶች የኑሮ መግፊያ የሴትኛ አዳሪ ትምህርት ከሠለጠኑ በኋላ የሥራ ማሰናከያ ቆጥሎዳቸውን በመንገድ ላይ አጥምደው ብዙ ሕፃናት ተማሪዎችና ሌሎችም በሥራ የተወሰኑትን ሠራተኞች በምግብና በመጠጥ (በጠጅ) እያስመሰሉ ከትምህርታቸውና ከሥራቸው ሰንክለው ያስቀሯቸዋል። አሁንም ይህ ከንቱ ትምህርታቸው በየጊዜው እየበዛ ስለሄደ ይኸንንም ከመሰለ ሥራ ለማዳንና ለማሻሻል ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ለብርሃንና ሰላም አንባቢዎች ትንሽ አሳቤን እንድታስቡበት አስታውሳችኋለሁ ።

(መጀመሪያ) በከተማ ለሚኖሩት በከንቲባው ውሥጥ፡በባላገር ለሚኖሩት በእርሻ ግዛት ሚኒስቴር ውስጥ በተለየ ሹም ሹሞ በመንግሥት ስም ልዩ ልዩ ቤቶች አሠርቶ መጀመሪያ ከባላገር ወደከተማ ሲቶቹ ሲመጡ ከከተማ የሚገቡበትን ምክንያት የሚያስታውቅ ምስክር ወረቀት ከእገር ግዛት ሚኒስቴር ጸኛ ወደአገር ግዛት ሚኒስቴር ዋና ቢሮ ይዘው መምጣት።

፪ተኛ፡ የአገር ግዛት ሚኒስቴርም ወደ ከንቲባው በከተማ የሚኖሩበትን ገልጾ የሚያስታውቅ ምስክርወረቀት(ካስፓርት) ተቀብለው ከንቲባው ወደአሰናዳው መኖሪያ ቤት ገቢ ተጽፈው ከንቲባው እንደሥራቸው መጠን ምግብና ልብሳቸውን (ወይንም ደሞዛቸውን) ከመንግሥት እድርጎ የሚችሉትን ሥራ ቢያሲዛቸውና በሥራቸውም ገቢ ገንዘባቸው ለመንግሥት እንዲሆን

፫ተኛ ፡ ከከተማ ወደ ባላገር የሚገቡትንም እንደዚሁ ከከንቲባው ወደአገር ግዛት ሚኒስቴሩ ካስፓርት ተቀብለው ባገር ግዛት ሚኒስቴሩ ጠባቂነት በሚኖሩበት አገር ቢሄዱና ያገር ግዛት ሚኒስቴሩም ዳኛ ለከንቲባው እላይ እንደተጻፈ አድርጎ በየሀገሩ መሥራት ።

፬ተኛ፡ በከተማም በባላገርም ያገር ግዛት ሚኒስቴርና ከንቲባው እንደሥራውቸው አገባብ እነዚህን የመሰሉትን ሴቶች ሁሉ ባገር ቤት የሚኖሩትን ያገር ግዛት ሚኒስቴሩ በከተማ የሚኖሩትን ከንቲባው አስቀድመው ቈጥረው በመዝገብ እንዲገኙ ማድረግ ።

፭ተኛ፡ሥራውም ከቆመ በኋላ መንግሥት በየቦታው መርማሪ አድርጎ ትእዛዝ አስተላልፈው የተገኙትን ብርቱ ቅጣት ወስኖ እነዚህን ሥራ አሰናካይ ሴቶች ካላስጠበቃቸው ወጥመዳቸው አይፈታም። ነገር ግን ለዚሁ ሥራ የሚስማማ መላ ሐሳቤን እንዳልጽፈው የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ከማንበብ እንዳትሰለቹኝ በዚሁ ወሰኜ አለሁ። ደምሴ ወልደ ሐዋርያት።

የንግድ ሚኒስቴር ለሕዝብ ጤንነት ጥበቃ ሲል ያቆመው ሥራ ቤት።

የሕዝብን ጤንነት የሚለዋውጡና የሚአጠፉ ብዙ ዓይነት መብልና መጠጥ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ በንግድ ዕቃ ምክንያት እየሆኑ ሳይመረመሩ መግባታቸውን የንግድ ሚኒስቴር ስለተረዳው ለዚሁም ሥራ ብቻ በተለይ አንድ መርማሪ (ሺሚስት)የሚባል ሥራ ቤት አቁሞአል።

ማለት ከዚህ ቀደም ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ያልተመረመረ መብልና መጠጥ ሁሉ በቀስታ ሳይታወቅ የሌላ በሽታ ምክንያት እየመሰለ አያሌ ሰዎች ጐድቷል። ይልቁንም በኮሶና በአረቄ ምክንያት የሞቱ ሰዎች ልክ የላቸውም ። ግን ይህ ሁሉ ባልተመረመረ መብልና መጠጥ ሳይሆን ይቀር አይመስለኝም። እንግዲህ የውጭውን አገር መብልና መጠጥ እንተውና በሀገራችን ላይ ያለው መብልና መጠጥም ቢሆን እንደዚሁ የግድ መመርመር ያስፈልገዋል። ደግሞ እንደዚሁ ካልጠተነቀቅንበትና ወሰን ከሌለው በሽታ መሆኑ አይጠረጠርም።መጠጥ የሚባለውን ነገር ፈጽመን ብንተወው አያገዳንም ግን የዚህን ሥራ ለመተው የማይችሉ አጥብቆ ልማድ ያላቸው ሰዎች ቢገኙ ይህ (ሽሚስት) የሚባለው ሥራ ቤት ከሚአገኛቸው አደጋ ሕይወታቸውን በትክክል መጠበቁ አይጠረጠርም። ይልቁንም በዚሁ በከተማችን ውሥጥ መሸታ በሚባለው ጠጅ ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት የሕዝብን ጤንነት የሚያደፈርሱና የሚለዋውጡ መድኃኒቶችና ቲምብርሱክር የሚባለው ነገር ሁሉ እየገባ እየተሠራ ሕዝብም ከመጠጥ የማያቋርጥ ስለሆነ እየሄደ እየጠጣ በዚህ ምክንያት እንኳን ደማቸው እስከመበላሸትና የሳንባ የልብ በሽታ ያደረባቸው ብዙ ሰዎች አሉ።መቼም መጠጥ የሚባለው አደጋ የሚሠራውን ሥራ ጨርሰን ለመጻፍ ጊዜ አናገኝምና እንዲያው እንተወዋለን። ግን ይኸንን መጠጥ በሀገራችን ላይ በጭራሽ ለማስቀረት መንግሥት መንገድ ቢፈልግለት መልካም ይመስለኛል። እስከዚያውም ድረስ ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ በሚገባው መብልና መጠጥ የንግድ ሚኒስቴር በከተማው ላለው መብልና መጠጥ ማዘጋጃ ቤት ሁሉ ባለ አቅምና ሥልጣን በትክክል መመርመር ተጀምሯልና የኛም የሕዝቦች ጤንነታችን በትክክል መጠበቁ ስለማይጠረጠር አግ ብቃን ልናመሰግናቸው ይገባናል።

እንደዚሁ ደግሞ መድኃኒትን ከውጭ አገር ለማስመጣት በተለይ ፈቃድ የተሰጠው የአገር ግዛት ሚኒስቴርና ፪ተኛም የእርሻ ሚኒስቴር እንደዚህ ያለ አንዳንድ ሥራ ቤት ማቆም ሳያስፈልጋቸው ይቀር አይመስለኝም ።

ማለት ይህ ሺሚስት የሚባለውም ሥራ ቤት በዚህ ብቻ ተወስኖ አይቀርም።ሌላም ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት ሥራና ደግሞ የጣት ፊርማ፡የጽሕፈት ፊርማ፡ ማኅተም ይኸንን የመሰለ ነገር ሁሉ በትክክል ለመመርመር ይችላል። እጓለ ጽዮን ንጋቱ።

ሹም ሽር ።

ባሻ ኃይለ ማርያም የዶባንና የወረይሉን ነጋድራስነት አቶ በቀለ ጉሹ አቶ ወልደ ጻድቅ አበረበ ይዞት የነበረውን

ሹመት ። አቶ ተበጀ አቶ ገዝሙ ይዞት የነበረውን ሹመት ተሾሙ።

ስለክብርት ወይዘሮ የተመኙ ዕረፍት

ክብርት ወይዘሮ የተመኙ ማዕርጋቸውና ክብራቸው እንዲህ ነበር።ባለቤታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ነጋድራስ የነበሩ ክቡር ነጋድራስ አግደው ቀድሞ የክቡር ራስ ወሌ ነጋድራስ ነበሩ በኋላ ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ አስተዋይነታቸውንና መታመናቸውን ስለተመለከቱ ከየጁ አስመጥተው ነጋድራስ አደረጓቸው።ክብርት ወይዘሮ የተመኙን ደግሞ ራስ ወሌ እቴ እንደ ሴት አትቈጠርም ብርታትና ቁም ነገር የመላባት ናትና የባሏን ሹመት ሰጥቻታለሁ ብለው በማዕርግ ተሹመው ያላንድ መነቀፍ ብይናቸውም ትክክል በመሆኑ ሰውን ሁሉ ሲያስደንቁና ሲመረቁ ይኖሩ ነበር።በኋላ ግን ባለቤታቸው ክቡር ነጋድራስ አግደው ቢሞቱባቸው ልጄ ዘለቀ ብቻውን ነውና ያባቱን ኀዘን ከናቱ ጋራ ነው የሚችለው ሲሉ ለራስ ወሌ ነግረው ተሰናብተው አዲስ አበባ መጡ።ራስ ወሌም ሹመትሽን በንደራሴ አድርገሽ ሂጂ እንጂ አንችን አልሽርሽም አሏቸው።እስከ ብዙ ዘመን በንደራሴ ይገዙ ነበር ይባላል ፤ ከዚህም ከመጡ እቴጌ ጣይቱ ባለሟል አደረጓቸው ክብርት ወይዘሮ የተመኙ ከቤተ ክርስቲያን የማይለዩ ጸሎተኛ ነበሩ።ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱም የምግባራቸውንና የሃይማኖታቸውን ዕናት ተመልክተው ማዕርጋቸውንም ከፍ አድርገው ይወዷቸው ነበር፡ክብርት ወይዘሮ የተመኙ ቤተ ክርስቲያ በማፍቀራቸውና ካህናትን በመውደዳቸው እጅግ ባማረ ፍታት ካህናቱ እያለቀሱ በይባቤ ቃለ እግዚአብሔርን አደረሱላቸው፤እንደ ሐውልት ሲነገርላቸው የኖረውን የወይዘሮ የተመኙን ታሪክ ዘር ዝርዞ ለመጻፍ እቦቤ ነበር ሳንባቢ እንዳይሰለች በወሬ ሳይሆን እመቤቴ ጉረቤቴ ነበሩና የማውቀውን የታመነውን ነገር ባጭሩ ጻፍሁት ክብርት ወይዘሮ የተመኙ ልጃቸውንም ክቡር በጅሮንድ ዘለቀን በምክርና በተግሣፅ ስላሳደጓቸው ከባታቸው ለበለጠ ማዕርግ ደረሱ የክብርት ወይዘሮ የተመኙ ዕድሜያቸው ፸፯ ዓመት ሲሆናቸው መስከረም ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመተ ምሕረት ዓርፈው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በማዕርግ ተቀበሩ።ምንስቴሮችና መኳንንቶች እጅግም ወይዛዝሮች መጥተው ነበር እንዳባትም እንደናትም ሆነው መክረው ያሳደጓቸው ጠንካራይቱ እናታቸው ወይዘሮ የተመኙ ስለሞቱባቸው መሪር ኀዘን ነውና ክቡር በጅሮንድ ዘለቀ አግደውን ከኄቶቹና ከወንድሞቹ ክብርነትና ሰላም እንባቢዎች ጋራ ሆኜ እግዚአብሔር ያጥናዎ እላለሁ ።

መክብብ ደስታ ።

የ፲፱፻፱ ግጽ ተከታይ ።

ሰባተኛ ክፍል ።

ስለ ቅጣት ደምብ ።

የኢትዮጵያ ዜጋ ወይም በማናቸውም ቆንስል ቤት መዝገብ ስሙን ያላስጻፈ የውጭ አገር ሰው በአንደኛው ክፍል ላይ ክልክል ሆኖ የተጻፈውን መድኃኒት በድብቅ ሲያመጣ ሲሸጥ ሲለቅ ሲያሰናዳ ወይም ያለ ዋጋ እንኳ ቢሆን ሲያሳልፍ የተገኘ እንደሆነ እንደ ጥፋቱ መጠን እየታየ ከ፳ እስከ ሺ ብር ድረስ መቀጮ ይከፍላል ።

በቆንስላቸው መዝገብ የተጻፉ የውጭ አገር ዜጎች ሕጓ አፍራሾች ሆነው የተገኙ እንደሆነ በጥብቅናታቸው አገር ሕግ ቅጣት ያገኛቸዋል ።

አንድ ወይም ብዙ የውጭ አገር ዜጎች ይህን ደምብ ተላልፈው ባገራቸው ወይም በጥብቅናታቸው አገር ሕግ ሳይቀጡ የቀሩ እንደሆነ ለዚሁ ሕግ ክብር ማረጋገጫ ሲል የኢትዮጵያ መንግሥት ሕግ ካፈረሰው ዜጋ ቆንስል ጋር ተስማምቶ ያስቀጣል ።

Art. 7

Dispositions pénales.

Toute importation clandestine, toute vente, détention sans ordinnance médicale, préparation ou délivrance, même gratuite, toute exportation de l'une ou l'autre ou de plusieurs des drogues visées à l'article en contravention des dispositions précédentes, par un sujet éthiopien ou par un étranger non immatricué auprès d'un consulat, sera passible d'une amende de 20 à 1000 thalers, selon la gravité de l'infraction.

Les étrangers immatriculés auprès d'un consulat seront passibles, en cas de contravention aux dispositions de cette loi, des peines prévues par la loi de leur protection sur la matière.

Toute contravention commise par un ou plusieurs étrangers aux dispositions de cette loi, nom punie par la loi nationale ou de protection, entrainera l'application de mesures admistratives qui seront prises par le Gouvernement Impérial, d'acord avec le Consulat dont relève le contrevenant étranger, de façon à assurer le respect de la présente loi déclarée d'ordre public.

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ቍጥር ይታተማል ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛ፤ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኤ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ክልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፱ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመመ-ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ቤት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የሆላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቍቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዲቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ጓካላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደተበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ፀ ፊ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልከ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵ 6me ANNEE № 40		ሐሙስ መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም። JEUDI 2 OCTOBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የመስቀል በዓል አከባበር ።

በመስከረም ፲፯ ቀን የደመራ በዓል ነበር ። በታላቁም ግቢ አጠገብ በአለው ሜዳ ታላላቆች ድንኳኖች ተቀጣጥለው ተተክለው ውሥጡም ከፍ ብሎ ተደልድሎ መሐሉም ከፍታ ተጨምሮለት የጃንሆይ ወምበር ተቀምጦበት ነበር ። ግራና ቀኝም ጥሩ ወምበር ተደርድሮበት ነበር ። ደመራውም በድንኳኑ ፊት ለፊት ተደምሮ በአበባ አጊጦ እጅግ ያምር ነበር ። ከ፱ሰዓት በኋላ ጃንሆይ መጡና በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ ። ብፁዓን ጳጳሳትና የውጪ አገር ሚኒስቴሮችና ቆንስሎች፣ ወይዛዝሮች፣ ሌሎችም የዲፕሎማቲክ ሰዎች በቀኝ፣ የኢትዮጵያ መኳንንትም በግራ ተቀመጡ ። ካህናቱም ልብሰ ተክህኖ ለብሰው የሚገባውን ጸሎትና እግዚአታ አድርሰው ብፁዓን ጳጳሳትና ካህናቱም ደመራውን ዞሩ። ጃንሆይም ታላላቆችን መኳንንት አስከትለው ደመራውን ዞረው ወደ ድንኳኑ ተመልሰው ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ የባልደራሶች አለቃ ቀኛዝማች ገብረ ጊዮርጊስ ብዙ ጭፍራቸውን አሰልፈው ኢዮሐ አበባዬ እያሉ ደመራውን ዞረው አለፉ ።

ቀጥለው የሰይፍ ጃግሬዎች ተሰልፈው ደመራውን ዞረው አለፉ ።

ቀጥለው የግቢው ሚኒስቴር ቢትወደድ ወልደ ገብርኤል የግቢውን ሠራዊት አሰልፈው አዛጋር በየነን ወደፊት አስቀድመው ደመራውን ዞረው አለፉ ።

ቀጥለው የክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው የቤት አሽከሮች ባለቃ በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው የሮፓን ሰልፍ የተማሩ የልፍኝ ዘበኞች በአማረ ሰልፍ ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ሙሉጌታ አሽከሮች በእንደራሴአቸው ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው ግራዝማች ባንቲዋሉ የወረገኑ ሹም ጭፍሮቻቸውን አሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ በመልከም ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው የስልክና የፖስጣ ሚኒስቴር ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደሩፌ በመልከም ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው ኀዶች በዲረክተሩ በአቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው የእቴጌ መነን ሰዎች በአለቃቸው በአዛጋር ኃይለ ሥላሴ፡ ቀጥለው የግቢ ጸሐፊዎች በዲሬክተሩ በግራዝማች ተክለ ማርቆስ ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው የአገር ግዛት ሚኒስቴር የደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ጭፍሮች በአለቃ በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ።ከነዚህ ውሥጥ የዳኅማዊ ምኒልክ ሆፒታል ሠራተኞች ነጭ ነጭ ኰት ለብሰው መልከም መለዮአቸውን አድርገው በአለቃቸው በአቶ በላቸው መሪነት በሥርዓት ተሰልፈው በአንድ ጊዜ ሰላምታ ሰጥተው ሲአልፉ እጅግ አማሩ ።

ቀጥለው ሊጋባ ወዳጆ አጋፋሪ መሸሻን በፊት አድርገው ፀኋላ እሳቸው ሁነው ወታደሩን አሰልፈው አለፉ ። ቀጥለው የጨዋ ልጆች በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ ። ቀጥለው የአፈንጉሥ አረጋይ አሽከሮች በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ።

ቀጥለው ጋሻ ጃግሮች በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ ። ቀጥለው በወላሞ ትክለኞች ሁነው ከሚኖሩ ወታደሮች የሆኑቱ በአለቃቸው ተሰልፈው አለፉ ።

ቀጥለው አረርጌዎች በደጆ አጋፋሪው በቀኛዝማች ክልክሌ በልፍኝ አስከልካዩ በግራዝማች ዘውዴ አረጋይ ጓዶችም በበጅሮንድ ተሰማ ባንቲ የግቢ ሠራተኞች በአዛጋር ይርዳው እነሆ ሁሉ በአንድነት ተሰልፈው እጅግ አምረው አለፉ።

ቀጥለው የሥራ ሚኒስቴር አቶ ፋሲካ ጭፍሮቻቸውን አሰልፈው አለፉ ።

ደግሞ በሰተማችን ሥራ ስለበዛ ለወታደሩ የሚመች ሰፍራ ለማዘጋጀት አልተቻለምና ደመራው በየክፍሉ ስለሆነ ክንቲባ ነሲቡ ዛማኤል በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ አስደምረው ነበርና የከተማው ነጋዴና የከተማው ዘበኛ በየአለቃው ተሰልፎ ኢዮሐ አበበዬ እያለ ደመራውን ሲዞር እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር። በሩቅ ያሉ ሰዎች የሀገራቸውን ወሬ ይናፍቃሉና አንብበው የሀገራቸውን ታሪክ እንዲአውቁ ጽፈነዋል እንጂ የከተማው ሰውማ ታሪኩን ጠግቦታልና ብርቅ እንዳያደርገው እናውቃለን"።

ተማሪ ቤት ስለ መጐብኘት ።

ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የስዊድን ማኅበር ተማሪ ቤት በእንጦጦ ያለውን ለመጐብኘት ፲፱፻፳፫ ዓም መስከረም ፲፯ ቀን መጥተው ነበርና ከተማሪ ቤቱ ገብተው በተዘጋጀላቸው ቦታ በተቀመጡ ጊዜ ጣዛው፡ እሸቴ የተባለ ተማሪ ተነሥቶ አርእስቱን ከግዕዝ ጠቅሶ እጅግ ደስ የሚያሰኝ የምስጋና ቃል ተናገረ ።

ቀጥለው ተማሮቹ ስለ ኢትዮጵያ መኳንንቶችና ስለ ጃንሆይ ምስጋና የሚናገር ከቴስ ባድማ የተገጠመ መዝሙር ዘመሩና በጣም ደስ አሰኙን ። ከዚህ ቀጥሎ በየክፍላቸው እንግሊዝና ፈረንሳዊ ቍጥር፡ ግዕዝና አማርኛ እየቀረበ ተጠየቁ ልጆች ሁሉ ከተጠየቁ በኋላ ክቡር ቄስ ባድማ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ ።

ጥበብ ሐፀነተከ ከመ ጥብ ልቡና ፈሰየተከ መከና ።

፩ኛ ፤ ጥበብ በጡትዋ ያሳደገችዎ አገርዎንና ሕዝበዎን ለመርዳት የወዳጅነትንም መሠረት ለማፅናት ልባዌ ቤትዋን የሠራችብዎ ክቡር ጌታችን ሆይ ። ዛሬ በዚህ ቀን የስዊድን ማኅበር የኢትዮጵያን ልጆች ድኖችንና ሀብታሞችን በደስታ እየተቀበለች ማስተማር ዋና ድካምዋ ሁሉ የተሻለ ዕውቀትና ጥበብ እንዲያገኙ በየጊዜው የሚያስቡላት አሳብ ጥቅሙ ለኢትዮጵያና ለወጣቶች ልጆችዋ መሆኑን ተረድተው በዛሬ ቀን ተማሪ ቤታችንን ለመጐብኘት ስለመጡልን በክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅና በስዊድን ማኅበር መሀከል ታላቅ የደስታ ምልክትና መሠረት ያለው ነዋሪ ፍቅር እንዳለ የሚያስረዳ ነገር ነው ።

፪ኛ፤ ዳግም በዓለም ሁሉ መንግሥትንና ሕዝብን የሚረዱ ሁለት ታላላቅ ሥራዎች አሉ ። እነዚህም ትምህርት ቤትና ሆስፒታል ናቸው።በተማሪ ቤቶች ብዙ ሕፃናት ልዩ ልዩ ዕውቀትና ጥበብ ተምረው የምድር ባቡርና የባሕር መርከብ አውቶሞቢልና በሰማይ የሚበር አይሮፕላን እንዲሁም ብዙ ይህን የመሰለ ሥራና በመሬት የሚገኘው ማዕድን ሁሉ ማወቅ ተምረው መንግሥታቸውንና አገራቸውን ይጠቅሙበታል ።

፫ኛ በሆስፒታሉም በዓለም ያሉ ሰዎች በልዩ ልዩ ደዌና ለማየት በሚያሰቅቅ ሕማም ተይዘው የሚጨነቁትን በሽተኞች ሐኪሙ አምላክ በሰጠው ዕውቀት ሳይፈራና ሳይሰቀቅ በትጋት ሌትና ቀን ብሎ ለሕይወታቸው የሚያስፈልገውን ሁሉ ሲረዳቸው እያዩ ከበቷቱ ያሉ ሠራተኞች ሁሉ ይህነን መልከም ሥራ አውቀው ለሕዝባቸው ጥቅም የሚሆን ትልቅ ትምህርት ያገኙበታል ።

፬ኛ ደግሞ ክቡር ሆይ እነዚህ በፊትዎ ቁመው ያሉ የኢትዮጵያ ልጆች አስተማሮችና ተማሪዎችም ደስታ የመላበት ፊትዎን ባዩ ጊዜ በሥራቸው ለመፋጠንና ወደ ፊት ለመግፋት ኃይል እንደሚያገኙ የታወቀ መሆኑን ማንም አይስተውም ። ክቡር ሆይ የርስዎ ተከታዮች የሆኑት መኳንንቶችም ለራሳቸው ረብና ጥቅም ሳይፈልጉ ሁሉም በየተቻላቸው ለአገራቸው ቢያስቡላትና ቢረዷዋት ቶሎ ብላ ወደ ሥልጣኔ እንድትደርስና ለጥቅምዋ የሚሆነውን ሁሉ እንድታውቅ ጥርጥር የለበትም ።

፭ኛ በኤውሮጳ ያሉ አንዳንድ ሀብታሞች እግዚአብሔር በሰጣቸው ገንዘብ ከማንም እርዳታ ሳይፈልጉ በገንዘባቸው ተማሪ ቤትና ሆስፒታል እየሠሩ በተማሪ ቤቱም ብዙ የድኆች ልጆች እየተማሩበት በሆስፒታሉም ብዙ በሽተኞች እየተፈ-

[illegible]

ወሑበት ለሕዝብ ጥቅምና ለመንግሥት ታላቅ እርዳታ ሁኖ ይኖራል ።

፮ኛ በኢትዮጵያም ከዚህ በፊት ባለፉት ዘመናት ሁሉ ያልተደረገ እግዚአብሔር በታላቅ ምሕረቱ በስነግልን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ በምሥራቅና በምዕራብ ፡ በሰሜንና በደቡብ የተማሪ ቤቶችና ሆስፒታሎች ቁመዋል ። ይህነንም መልካም አሳብና ታላቅ ሥራ በዘመናችን አድርሶ በዓይናችን ያሳየነን አምላክ እያመሰገን ያስጀመረውን ሥራ እንዲያስፈጽመው ልንለምነው ይገባናል ።

፯ኛ በፈቃዳቸው ይህን የመሰለ መልካም መታሰቢያ የሆነ ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ ስማቸው እንደፀና ዓምድ ቁሞ ይኖራልና ክብራቸውም እንደማይነቀነቅ ሐውልት ሁኖ በዓለም ባሉ ወንድሞቻቸው ከዘመን ወደ ዘመን እያለፈ ከትውልድ እስከ ትውልድ ሲታሰብ ይኖራል

ለክቡር ጌታዬ ደጃዝማች ወልዴ ጻድቅና ይህችን ትንሽ የምስጋና ቃል እንድናገር ለፈቀዱልኝ ለተማሪ ቤቱ ዲሬክተር ለክቡር ሙሴ ሸርኔ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ብለው ከጨረሱ በኋላ ተጨበጨበላቸው ።

በመጨረሻ ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ከዚህ በታች የተጻፈውን ቃል ተናገሩና ሦስት ጊዜ ተጨበጨበላቸው ።

ክቡር ዲሬክተር አስተማሪዎችና ተማሪዎች ነገር ሁሉ ከላዩትና ከልመረመሩት እዩታወቅምና ከዚህ በፊት እንዲህ በየዓይነቱ ትምህርት የሚገኝበት ትልቅ የተማሪ ቤት አልመሰለኝም ነበር ። አሁን ግን በመሀከላችሁ ሁኜ የትምህርቱን ልክ በየሁ ጊዜ በጣም ደስ አለኝና ለወደፊቱም ብዙ ዕውቀትና ትምህርት እየጨመራችሁ ላገራችሁ ለኢትዮጵያ አጋዥና ለመንግሥታችሁ የታመናችሁ አገልጋዮች እንድትሆኑ ብዬ እየተመኘሁ ተስፋዬ ወደ ፊት እየገፋ መሔዱን እገልጽላችኋለሁ በሉ ጊዜ የሁላችን ልብ በደስታ ተነካ ።

ከዚህ በኋላ ለመጻሕፍት መግዣ ብለው መቶ ብር ሰጡ ክቡራን እንበቢዎች ሆይ ይህ የተማሪ ቤትና የትምህርት ሥራ ለኢትዮጵያ ታላቅ የሚያስፈልግ ጉዳይ መሆኑን ተረድተው ተማሪ ቤታችነን ለመጐብኘት ስለመጡ ለክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል ። እንዲሁም ታላላቅ መኳንንቶች ያገራቸው ፍቅር ያለባቸው ሁሉ አንዳንድ ጊዜ በከተማ ያሉትን ተማሪ ቤቶችን ቢጐበኙዋቸው ለአስተማሪዎችና ለተማሪዎች ማነቃቃትና ትጋት እንደሚሆናቸው ጥርጥር የለበትም። አማኑኤል ገ ሥላሴ ።

የሠራተኞች ጥፋት ።

ብረት ሠራተኞች ብልሆች አዋቂዎች ነን እያሉ ሥራውን ለመሥራት የማይገባቸው ሥርተው ስላየሁና ለመንግሥትም ጉዳት እንደሆነ ስለተረዳሁት ከዚህ በታች አሳስባለሁ ።

አስቀድሞ ብረት ሲሠራ ረጅም ጠመንጃ ወይም ነፍጥ በተለየ ለእግረኛ ወታደር እንዲሰጥ የተዘጋጀው ለጦርነት ሲታዘዙ ጊዜ ረጅሙን ጠመንጃ ተቀብሎ ባላጋራ ሲመጣበት በሩቅ በሦስትና በራት ሺ ክንድ ርቀት ባላጋራውን የሚነድፍበት የጠመንጃ ባለቤት ለብረት ሠራተኛው ሲሶ እንጨት አድርገህ ብረቱን አሳጥረህ ሥራልኝ ብሎ ቢያሳየው ልቡ እያወቀ አለቅሬታ ደስ ደስ እያለው ረጅሙን ጠመንጃ ከመማሯ ሁሉ አንደኛ ቀጥር የጠላት መግፊያ እንደሆነ እያወቀ ማጕደሉ ሳያሳዝነው ለራሱ ጥቅም ብቻ ለመፈለግ ተለክቶ አምሮ የተሠራውን ረጅሙን ጠመንጃ ብረቱን ነርዶ አጥሶሮ ሲሶ እንጨት አድርጎ በማበላሸቱ እጅግ ያሳዝናል ። በጣምም ያስጐዳል ። ባለጠመንጃው አሳጥረህ ሲሶ እንጨት አድርገህ ሥራልኝ ብሎ ለሠራተኛው መስጠቱ ለመልክ ቁንጅ እንዲሆንለት ይመስለኛል ። ይህ ግን ባለማወቅና ባለማስተዋል ነው እንጂ የጠመንጃው ቍንጅናው ጠላት በሩቅ ማጥቃቱና ማሸነፉ ነው ። ትልቅ እርዳታው ይልቁን እንደ ኢትዮጵያ ያለ ወታደር ፈጣን እንደንብ የሚናደፈው በረጅም ጠመንጃ በራትና በምስት ሺህ ክንድ ርቀት ሰላማና እርባ ሊነድፍ ይችላል ። ብረት ሠራተኞች በልክ የተሠራውን ጠመንጃ ቈርጠው እንዳያሳጥሩ መንግሥት በፀና ትእዛዝ አዋጁን ነግሮ ቢከለክላቸው ለመንግሥት ታላቅ ጥቅም ነው ። ድንገት አጭር ጠመንጃ እንደረጅሙ ጥቅም ከሌለው አስቀድሞ ለምን ተሠራ ብሎ የሚጠራጠር ሰው ቢኖር ለዓላማ መፈተኛ ብሎ መንግሥት በሰናዳው በታ ሔዶ የረጅሙና ያጭሩን ጠመንጃ አኳኋን መርምሮ ሊያገኘው ይችላል ። የረጅሙ ጠመንጃ ደምብ ለብቻ ነው፤ያጭሩም ደምብ ለብቻ ነው ። ረጅም ጠመንጃ ለእግረኛ ወታደር የሚሰጥ ነው አጭር ጠመንጃ የሚገባቸው መድፈኞች፣ መትረየስ ዘበኞች፣ ፈረሰኞች እንደነዚህ ባለሥራ ለሆኑ ወታደሮች እንዲሰጥ የተዘጋጀ መሆኑን የሚስተው ያለ አይመስለኝም ። ነፍጥ ሠራተኞች ለምን እንደዚህ ብሎ ጻፈብን ብላችሁ እንዳትቀየሙኝ አደራችሁ የብረትን ሥራ ከኔ እናንተ ታውቁታላችሁ ። ባሻ ክፍለ እግዚእ።

በከተማ ውሥጥ ስለሚያስቸግሩ ሰዎች ።

በአራዳ ገበያ ውሥጥ ብዙ ቀጣፊዎችና አታላዮች ሕዝቡን ለማታለል ዕብዶች ነን እያሉ ገበኞችን በመንገድ እናስኬድም በማለት ያውከሉ ። ይልቁንም ለዕለት እራቱ አተርፋለሁ እያለች ማናቸውንም ልዩ ልዩ ነገር ሁሉ ለመሸጥ በገበያ የተቀመጠችውን በድንገት መጥተው የያዘችውን ይደፉብታል ። ገበኛውም ዕብዶች ናቸው ሲሉ በሰሙ ጊዜ መቸም አንድ ጊዜ ዕብዶች ብለውናል ብለው በድፍረት እንደ ዚሁ ያውካሉ ።ይህን የሚያደርጉት ግን ሴት ሁና የምትነግደውን ከውጭም ለገበያቸው የሚመጡትን ጋሎችን ነው ። ይልቁንም በከተማ ተቀማጭ የሆነች ሴት ባል ያላትም ሆነ ወይንም ሴትኛ አዳሪ የሆነች ለገባያ በወጣች ጊዜ ዕቃ ለመግዛት ክንዱ በታ ወዳንዱ ስትተላለፍ እየተከተሉ መሳደብና ሽማቸውንም እየጐተቱ መቅደድ የያዙትንም ዕቃ ከጃቸው ላይ መንጠቅና መጣል ሆነ ሥራቸው ። ይህነኑም ምና ልባት የደረሰበት ወይንም ባይኑ ያየ ሰው ይታጣ አይመስለኝም ። እንግዲያውማ ምነዋ እውነት ልባቸውን የሚሠውራቸው ዕብዶች ከሆኑ በከተማ የሚኖረውንወንዱን አይነኩትም።

ስለዚህ ዕብዶች ነን እያሉ በመንገድና በገባያ ውስጥ ሕዝብ የሚያስቸግሩትን ሰዎች ሕዝቡንና ከተማውን የሚጠብቁ ዘበኞች እየፈለጉና እየያዙ እሥራትና የበረታ ቅጣት ቢወስኑላቸው እነዚህም ሕዝብ ክፋታቸውን ይተዋሉ፤ ድኃውም ሁሉ እግዚአብሔርንና ንጉሣችንን እያመሰገነ ያለችግር ገባያውን ግብይቶ ይገባል ።

ከበደ ገሠሠ

የሠላሳ ስድስተኛ ቍጥር ተከታይ የዳኝነት ምሳሌ

ይድረስ ከክቡር ጌታዬ ከቶ ዳኝነት
ለክበሬታዎ የተገባ ሰላምታ አቀርባለሁ
እግዚአብሔር ያሰዩዎ

ነገርና ሙግት ያለበት አንድ አንድ ሞኝ ሰው ለነገር ወደርስዎ በመጣ ጊዜ ሰውነት የሚባለውን ቤቱን ትዕግሥት በሚባል አጥር ሳያጥርና ደጃፉንም አርምሞ በሚባለው መዝጊያ ሳይዘጋ ልብ የሚባለውንም ሣጥኑን ንጽሕና በሚባለው ቍልፍ ሳይቈልፍ ወይም ፍቅረ እግዚአብሔር የሚባለውን ታማኝ ወዳጁን ጠባቂ ሳያደርግ እንዲያው በድፍረት ክፍቱን እየተወ እየመጣ ሠሬና ስብቀት የሚባሉት አታላዮች ጆሮ በሚባለው መስኮቱ እየገቡና እብለትና ሐሰት የሚባሉትም ሌቦች በደጃፉ እየገቡ ልብ የሚባለውን ሣጥኑን እየሰበሩ ሆድ የሚባለውንም ማጀቱን እየቀሰቀሱ እምነት የሚባለውን ልብሱንና ደግነት የሚባለውን የቤት እቃውን ሁሉ በዝብዘው ወሰዱበት ። ይልቁንም እምነት የሚባለውን ከመንግሥት በደንብ የተቀበለውን ብረት ስለወሰዱበት አለቃዬ ባሻ የውነቱ ይይዙኛል ብሎ እንደ ዕብድ ሁኖ ሲቅበዘበዝ አይቼ ስለቤቱና ስለ ሣጥኑ መበላሸት ተጸጽቼ አይ ልቡና ወአይ ነቢብ ወአይ ሰሚዕ ብዬ በጣም አዝኜ ሔድሁ። እሱ ግን ለዳኛ አቤት አላለሁ ብሎ ሔዶ ለመንደሩ ዳኛ ነገር ይቅረቡልህ የሚል ቃል ይዞ ቢመጣ እስከ ዳኛውም እንግድላለን ብለው ጕቦ የሚባለውን በቀለህ ሽጕጥ ስለክልክልነቱ ደብቀው ታጥቀው ሌሊቱን ሁሉ ሲገሰግሱ ሔደው እዚያ ሲደርሱ ፲ ፲ አጕርሰው በዳኛው ተኵሰውበት ሲሸሹ የዘበኛው አለቃ ክንቲባውና (ነ) ብላቴን (ጌ) (ጎ) መተያያ እሚባለው በር ላይ አሲዘው ይኸን ጕቦ የሚባለውን ሽጕጥ ማንኛውም ሰው እንዳይታጠቅ ጃንሆይ ቀ ኃ ባዋጅ ተከለከሉ በኋላ እናንተ ታጥቃችሁ ከተገኛችሁ ታሥራችሁ ቈዩ ብለው መተው በሚባለው ዘብጥያ አሥረው ተጣማዕ የሚባለውን ድንጋይ ሲያስፈልጧቸው አገኘኋቸው።እነሱም እኔን ሠርቶ መብላት በሚባለው በቡር መንገድ ስሔድ አይተው ስለ ማርያም እራታችንን የምንገዛበትን ገንዘብ መጽውተን ብለው የግድ ለመኑኝ፡ እኔም በምን ምክንያት ታሥራችኋል ብዬ ብጠይቃቸው ይኸን ጕቦ የሚባለውን ሽጕጥ ብዙ ሰው ሲታጠቅ አይተን እኛም ብንታጠቅ ዳኛ ለመግደል አሰባችኋል ብለው በግፍ አሥረውናል ብለው ቢነግሩኝ እኔም ይኸው ጕቦ የሚባለው ሽጕጥ መጠበቂያ የሌለው ስለሆነ ፍርድ የሚባል ቃታው ወደአንድ ፊት አድልቶ ባርቆ ሰው የገደለ ወይም ያቈሰለ እንደሆነ እናንተም ተይዛችሁ ሳይፈረድባችሁ አይቀርምና ብትተውት ይሻላል። አሁንም እግዚአብሔር ያውጣችሁ ብዬ እንዳቅሜ ምክር የምትባለዋን ዕቢሳ ተኪሴ አውጥቼ በዚህ ምግባር የሚባለውን መልካም ቂጣ ገዝታችሁ ብሉ ብዬ መጽውቻቸው ሔድሁ።እነሱም እንደገና ከታሠሩበት ሰብረው ሔደው ሽፍጥ እሚባል ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ገብተው ሌብነትና ስርቆት የሚባሉትን የሥጋ አውሬዎች እያደኑ ሲበሉ ሰንብተው በኋላ ውሸት የሚባለውን ዘሆን ገድለናል ብለው ስብቀት የሚባለውን ሎቲ በገሮአቸው አንጠልጥለው መጥተው ሲደነፉ እንደበጎ ና መላስ የሚባሉት ያቶ ጥብቅና ልጆች እውነት እውነት ለከ ለከ እያሉ ጥያቄ የሚባለውን ቀረርቶ እያቀረሩ ሲያፏክሯቸው አይቼ አይ ልሳን ወአይ ነቢብ ብዬ ተደነቅሁ። ከነዚሁም ግማሾቹ ጽሕፈት ያውቁ ኑሮ በሌብ ጣታቸው ብዕሩን እንሥተው ሒሳብ ጀምረው ሲዘረዝሩና ሲደምሩ፥ ሲአበዙና ሲቀንሱ፥ሲአካፍሉና ሲአሳንሱ አይቼ በሰሙ ጸሐፊ እነዚህም እኩል ጸሐፊ ይባሉ ይሆናል አዬ ብር አጨባበጥ ብዬ በጣም ተገረምሁ ። ማታ ማታም ከሥራ በወጡ ጊዜ እንዳይወርስባቸው በዕራቸውን በየኪሳቸው እየከተቱ መሔዳቸው እጅግ ያስደንቃል አሁንም ጌታዬ ሆይ ነገር ደበዛብዎታል ብዬ ሐሳቤን ሁሉ አልጻፍሁልዎትምና እንደነዚህ ያሉትን የሠለጠኑ ሠራተኞች እያስፈለጉ ቅጣትና እሥራት የሚባለውን ዋና ዋና ሥራ እንደአሲዟቸው በማክበር አመለክትዎታለሁ ።

ትስብእተ ወልደ አግዴ ፍ ጸ፡

ምክር ።

መስከረም ፳ ቀን ለጕዳዬ ወደ ልጅ አስፋው ዘርጋባቸው ቤት ሔድሁ። እቤቱም ስደርስ የብዙ ቁሶች ድምጥ ሰማሁ ምን ይሆን ብዬ ሳመነታ ልጅ አስፋው በደጅ ላሉ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን ምግብና መጠጥ ለመስጠት ብቅ አለ፥ እኔንም እዝያ ቆሜ ባየኝ ጊዜ ለምን እዶጅ ቆምህ ግባ እንጂ አለኝ ወንድሜ የመጣሁት ለጕዳዬ ነበር የድግስ ቤት ይመስለኛልና በሌላ ቀን እመጣለሁ አልሁት ፤ እሱም እንዲህ አለኝ እንኳን እግዚአብሔር ያመጣህ እንጂ አሁንስ እትሔድም ግባ ነገሩንም ሁኋላ እነግርሃለሁ አንድ ጊዜ ቁሱ ያሳርጉልኝ አለኝ እኔም ቁሱ እስቲአሳርጉ ድረስ እዝያው በታ ቈየሁ ።

ከዚህ በኋላ ወደቤት ገባን ለኔም መጠጥ አቀረቡልኝ እኔም የድግሱን ምክንያት ሳላውቅ አልጠጣም ብለው ድግሱስ ዛሬ ልጄን ክርስትና ስለ አስነሣሁ ነው አለኝ ። እኔም በቍጣ ቃል እንዲህ አልሁት ለክርስትና እንኳን ወዳጅና ጠላት ሲጠሩት ያሳስባል ብዬ ተቈጣሁ እሱም ወንድሜ አትቈጣ ነገሩ እንዲህ ቢሆንብኝ ነው ልንገርህ አለኝ። እኔም ምክንያቱን ለማወቅ በል እስቲ ንገረኝ አልሁት፥ስማኝ እንግዲህ አንድ ሰው ልጁን ክርስትና ለማስነሣት ባሰበ ጊዜ ወዳጆቹን ለመጥራት ወረቀት ጻፈ ለወዳጆቹ የጻፈው የወረቀት ቃል ሲነበብ ለጊዜው እኔ እዝያ ነበርሁ እንደዚሁ እያሉ ይበሰጩ፥ ጀመር አንድ ጊዜ በሠርግ፥ አንድ ጊዜ በክርስትና፥አንድ ጊዜ በቤት ምረቃ ገንዘባችንን ልንከስር ነው ሲሉ ሰማሁ እነዝያ ሰዎች ቢበዛ ፩ብር ወይም ፪ ብር ነው የሚሰጡት እሱ ግን አንድ ሰው የመጣ

እንደሆነ የወዳጄ መጣቢሉ ምን ባቋርብለት ደስ ይለው ይሆን ብሎ ይጨነቃል። መደክሳውን፣ ሻምፓኙን፣ ጠጁን ያለውን ሁሉ ያቀርባል ፤ ከምጣብም ወገን ይቀጥላል ደባሞ ከሥጋ ወገን እነቶናሽ ፣ እነ ሽንጥ ሌላም ደኅንን የመሰለ ያቀርባል ያም የተጠራ ሰው መጀመሪያ ወረቀቱ የደረሰለት ጊዜ የተናገረውን ይረሳውና ወይም አምስት አሽከሮች በተቀርም እንደ ማዕርጉ ያሉትን አሽከሮች አስከትሎ ያችን ፪ ብር ይይዝና ይሔዳል እኔስ ወንድሜ ንጉሤን ኃይለ ሥላሴን ፺ ዓመት ያንግሥልኝ እንጂ የሱ አንድ ብር ወይም ሁለት ብር ያመጣል ብዬ እግዚአብሔር በቸርነቱ ያለ አንድ ሌሳ የሰጠኝን ልጄን አላስገምትም አለኝ። እንግዲያውማ ንጉሣችን ቸር፣ ሰጭ ናቸው ክርስትና አለብኝ ብዬ አንድ ባለሟል ብልክ ሰንጋውን ፤ ቅቤውን ማሩን ፤ እህሉን፣ ጌሾውን ፣ በርበሬውንም ይሰጡኛል ። ከኔ ምን ገንዘብ ይወጣ ይመስለሃል አለኝ ፤ እኔም እንዲህ አልሁት ከቂጠሽው ድግስ ሁሉ አንዱ አልገዳለም ለኔስ የሚመስለኝ ዘመድ ወዳጅህን ብትጠራ መልካም ይመስለኛል አልሁት ። ወንድሜ የግዴማ ወዳጆቼ የሚሰቱን እርግዝናዋን በሰሙ ጊዜ ከሲ ይልቅ በዚህ ቀን ትወልዳለች ፤ በዚህ ወራት ትወልድ ይሆን እያሉ ይጨነቃሉ ። እንኳን የክርስትና ቀንና ሌላም ቀን ቢሆን አውቀው ይመጣሉ ወንድሜ የንጉሣችንን ዕድሜ እየለመንን ጠላችንን እንጠጣ አለኝ ።

እኔም ልጅ አስፋው ዘርጋባቸው እንዴት ያለ ወቀሳ ቢሰማ ይሆን ብዬ ዕውቀትና ጥበብ ለዘለታቸው ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ላስታውቃቸው ወደድሁ ። ባሻ ገብሬ።

የበዓል አከባበር ።

በመስከረም ፳፩ቀን የብዙኃን ማርያምን በዓል ለማክበር ጃንሆይና እቴጌ ወደ እንጦጦ ማርያም ወጥተው ነበር ። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ብዙ መኳንንት ሠራዊትም በዚያው ነበሩ ። ፫ሰዓት ሲሆን ጃንሆይና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ማኅሌቱን ለማየት በወምበር ፣ በወምበር በዓምደ ወርቁ ሥር ተቀምጠው ነበር ። ካህናቱም ሰላም ለእማውትኪ ነበልባለ ኀዘንዘእው ፀዮ እያሉ ሲአሸበሽቡ እጅግ ያምሩ ነበር ። ከዚህ በኋላ ፀሎት ተደረገና ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ መልካም ስብከት ሰብከው አሳርገው ባርከው ሕዝቡን አሰናበቱ ።

ስለ ኃይሌ ሀብተሥላሴ ዕረፍት ።

አባቱ አቶ ሀብተሥላሴ የልዑል ራስ መኰንን አሽከር በአረርጌ ውሥጥ ወበራ በሚባለው አገር ታማኝና በአለ ብዙ ሥራ ነበሩ ። በዚሁም ሥራቸው ብዙ ማደርያ ተቀብለው ቃላቁ ሀብተሥላሴ ሲባሉ ይኖሩ ነበር ። ምንም ታማኝ ቢሆኑ ሰው ሁኖ ከሞት የሚቀር የለምና ሲሞቱ ለኛ ለልጆቻቸው ያለ ገንዘባቸውን ርስታቸውን ሰጥተውን ልጆቼ ተገዳደፉ እንጂ አትነቃቀፉ ብለውን ዓረፉ።እኔ ከወንድሜ ጋራ አባትና ልጅ መስልን ፳፩ ዓመት ስንኖር ታናሽ ወንድሜ ኃይሌ ሀብተ ሥላሴ በተወለደ ፴፫ ዓመቱ በ፲፱፻፳፪ ዓ ም በዘመነ ማርቆስ በነሐሴ ፳፰ ዓርብ ደሩ ማርያም በአማረ ፍትሐት ተቀበረ አሉኝ ። እኔም ለመንግሥት ጉዳይ ከቤቴ ተወጣሁ ጌወር ሁኜኝ ነበርና ታሞ ሳላስታምመው ቢሞትም ሳልቀብረው በሐረር ከተማ ሳለሁ መርዶው ስለመጣልኝ የኃዘኔ ተካፋዮች እንድትሆኑ ለብርሃንና ሰላም ተካፋዮቼ አስታውቃለሁ ።

መንገሽ ሀብተ ሥላሴ ።

ማስታወቂያ ።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ የሚጭኑት በጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ስለ ሆነ በዚሁ ቀን ዘውድ ጭነው ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ መንግሥት ሲመለሱ በየመንገዱ ዳር በተዘጋጀው ስፍራ ተቀምጦ ለማየት የሚፈልግ ሰው ከጥቅምት ፩ቀን ጀምሮ የፈቃድ ወረቀት ከማዘጋጃ ቤት ለማግኘት ይችላል ።

ለማየትም የተዘጋጀው ስፍራ ሦስት ማዕርግ ነው ።
መጀመሪያው ማዕርግ ዓሥር ብር ይከፈልበታል ።
ሁለተኛው ማዕርግ ፤ አምስት ብር ይከፈልበታል ።
ሦስተኛው ማዕርግ ሁለት ብር ተኩል ይከፈልበታል ።

መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።
ያዲስ አበባ ከንቲባ ።

ማስታወቂያ ።

በዓለም ላይ ምቀኛ የሌለው የለም ፤ ሐሰተኞች ሰዎች ፍልውኃ በሽታ ገብቷል እያሉ ሰውን እንዳይታጠብ ሲከለክሉ የሰማ ሰው ነግሮናል ። ይህም የሐሰት ወሬ በሁሉ ስፍራ የደረሰ ይመስላል። እስተዋይ ግን ይህን የሐሰት ወሬ ያውቀዋል ሰው ገብቶ ሲወጣ የፍልውኃው መግቢያ ይታጠባል፤ያ በሽታ ወዴት ይሆን የሚቈየው? በሽታ የሚያስነሣ እድፍ ነው ይባላል እንጂ መታጠብ በሽታ ይሆናል ሲባል አልሰማንም። አሁንም ማንም ወሬ ቢአወራላችሁ አትመኑ ለመረዳትም ብትፈልጉ መጥታችሁ እዚያው የሚኖሩትን የፍልውኃ ሠራተኞችን ጤና ማየት ትችላላችሁና ይህ ወሬ ሐሰት መሆኑን እንድታውቁት እናስታውቃለን ።

የፍልውኃ ዋና ጸሐፊ ።

የ፫፻፲ ገጽ ተከታይ ።

ስምንተኛ ክፍል ።

ስለ ሚለዋወጥ ደምብ ።

ይህ አዋጅ ሳይነገር አስቀድሞ በመድኃኒትነት ስም ያል ተጻፉ ካንድ እስከ ብዙ ያሉዋቸው በመጀመሪያ ክፍል የተ- ጠሩትን መድኃኒቶች የያዙሰዎች በፍጥነት ላገር ግዛት ሚኒ- ስቴር ማስታወቅ ይገባቸዋል ።

ሐኪሞችና መድኃኒት ቀማሚዎች በዚሁ ደምብ ለተጻፉት መድኃኒቶች ማመልከቻ የሚሆን አንድ ደብተር ይቀበላሉ በዚሁም ደብተር ላይ በኛቸው ያለውን የመድኃኒቱ መጠን በፍጥነት ይጻፍበታል ።

ነገር ግን እነዚህ መድኃኒቶች ለመያዝ ፈቃድ ያልተ- ሰጣቸው ካንድ እስከ ብዙ ቍጥር ያሉዋቸው ሰዎች የደረሰኝ ወረቀት እየተቀበሉ መድኃኒቱንና ያስመጡበትንም የፋብሪካው ቤት ሠነድ (ፋክቱር)ጨምረው ላገር ግዛት ሚኒስቴር ማስ- ረከብ አለባቸው ።

እነዚህም መድኃኒቶች በመንግሥት ሐኪሞች ከተመ- ረመሩ በሁዋላ ባስረከቡት መድኃኒቶች ልክ ዋጋ እየተከፈለ- ባቸው ለመንግሥት ሆፒታሎች ይሰጣሉ ።

ከዚሁም ከመጨረሻው ቀን ጀምሮ በመጀመሪያው ክፍል የተለየውን መድኃኒት በትክክል ደምብ ሳይዝ ቀርቶ የተገኘ ሰው ሁሉ በተወሰነው ቅጣት ይቀጣል በከተማ ውሥጥ ያሉ እስከ ፩ወር ድረስ ያስታውቃሉ ይህ አዋጅ ከሰኔ ፲፮–፲፰ ቀን ጀምሮ ወደፊት የፀና ሁኖዋል

Art. 8

Dispositions transitoires.

Toutes les personnes qui lors de la promulgation de la présente auront en leur possession, sans prescription médicale, une quantité quelconque de l'un ou de plusieurs des produits visés à l'article 1 doivent l'annoncer immédiatement au Ministère de l'Intérieur.

Les médecins, pharmaciens, reçevront un registre pour tenir la comptabilité des drogues visées par cette loi et la quantité qu'ils annonceront en leur possession sera portée immédiatement dans ce registre.

Les personnes n'ayant aucun titre pour avoir en leur possession l'un ou l'autre ou plusieurs de ces produits les consigneront contre reçu au Ministère de l'Intérieur si possible avec la facture du fournisseur.

Après examen de ces produits par les médecins du Gouvernement, les quantités ainsi remises seront payées et mises à la disposition des hopitaux de l'Etat.

La présente loi entrera en vigueur le

A partir de cette dernière date, tout détenteur des produits visés à l'article 1, sans titre régulier, sera passible des peines prévues.

Adis-Abeda le

ከዚህ የቀረ በሚመጣው ቍጥር ይታተማል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለሀገ- ራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሲራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጆዖግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ድርሳነ ሚካኤል	፮ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ጎሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መ
የርሻ ትምህርት	፪ ብር ከ፳ መ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኅቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ከርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የልዕልት ወይዘሮ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፸ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፸ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፸ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፸ መሐ
የማርኛ ምሳሌ	፸ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፸ መሐ
የቀን መቍጠሪ (ካሌንደር)	፸ መሐ
አሳብና ምኞት	፶ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፶ መሐ

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሚል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኒ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከንህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዲሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዛና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሺቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዴስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀደድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኮኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኮኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፩
6me ANNÉE № 41

ሐሙስ መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም ።
JEUDI 9 OCTOBRE 1950

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በግዛታቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።
Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የመስቀል ግብር ።

ከቀድሞ ጀምሮ ለመስቀልና ለፋሲክ፥ ሹማምት ለጭፍሮቻቸው ግብር ያበላሉ ። ዛሬም ቢሆን ከአንዳንድ ሰው በቀር ለመስቀል ወይም ለፋሲካ ለጭፍራው ግብር የማያገባ ሹም የለም ። ዛሬም በዚሁ ልማድ የጽሕፈት ዲሬክተር ግራዝማች ተክለማርቆስ በመስከረም ፳፬ ቀን ቅዳሜ እንዲመጡላቸው ወደ ጽሕፈት ሚኒስቴሩ ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጻፉላቸው ትሕትና የመላበት የመጥሪያ ደብዳቤ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ክቡር ሆይ ።

ትሕትና ገንዘብዎ መሆኑን አውቃለሁና ምሳሌና ሐተታ በማብዛት ላደክምዎ አይገባኝም ። ምንም እርስዎ ልምዴ ቢሆኑና እኔም ታዛዥዎ ብሆን የቀሩትን ወንድሞቼን ለመልመጃ ምክንያት እንዲሆነኝ በመስከረም ፳፬ ቀን ቅዳሜት ከጧቱ በ፩ሰዓት ከኔ ከልጅዎ ቤት ድረስ መጥተው በኔ ፊንታ ተቀምጠው ባልደረቦችዎንና ልጆችዎን ቍርስ እንዲጋብዙልኝ ስል ቁሜ እለምናለሁ ።

በዚህም ቀንና ሰዓት ሥራ መፍታትዎ እንዲፈቀድልኝ ጃንሆይን ለምኜ ፈቃድ ተቀብያለሁ ።

ታዛዥዎ ግ ተክለ ማርቆስ ።

የተጠሩትም ከወዳጆቻቸው ብዙ መኳንንት ነበሩ ። የቀሩትም የግቢና በሌላ ቦታ ሁሉ ጸሐፊዎችና ከጉምሩክና ከማዘጋጃቤት ጸሐፊዎች በቀር ሁሉ ተጠርተው ነበር። የአእምሮና የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ሁሉ ተጠርተው ነበር። በግራዝማች ተክሌ ውሥጥ ያሉት ወታደሮች

ሁሉ ተጠርተው ነበር ። ፬ ሰዓት ተኩል ሲሆን የጽሕፈት ሚኒስቴር ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል በአቶሞቢል ሁነው በደረሱ ጊዜ ሰውን ሁሉ እጅግ ደስ አለው።የተጠራውም ሰው ሁሉ ይጠብቅ ነበርና ልክ ፭ሰዓት ሲሆን የጽሕፈት ሚኒስቴር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ወደ ድንኳኑ ገብተው ከፍ ብሎ በተደለደለው መካከለኛው ቦታ ተቀመጡ። ቀጥለ ውም መኳንንቱና ሹማምንቱ ተቀመጡና የመጀመሪያው ግብር ገባ ።

ቀጥሎ መጋረጃው ተገለጠና ሁለተኛው ግብር ገባ ። ቀጥሎ ሦስተኛ ግብር ገባ። ሕዝቡ እጅግ ብዙ ነበር ። ድንኳኑም እጅግ ሰፊ ነበር ። ምግቡና መጠጡ እጅግ ብዙ ፣ በጣዕሙም እጅግ የበለጠ ነበር ። ይልቁንም ከፍትፍቱ ፊቱ እንደሚባለው ፣ ረት በአላቤቱ ለሚግድገው ቁመው እንደአንድ ሠራተኛ ወዲህና ወዲያ እየሉ ሲጋብዙ እጅግ ደስ አሰኙ። ከ፫ተኛ ግብር በኋላ ሸምቢጥን ተረባና ግራዝማች ተክለማርቆስ የሚከተለውን ዲስኩር (የምረቃ አነጋገር) ተናገሩና ፫ጊዜ ተጨበጨበ።

ግራዝማች ተክለ ማርቆስ የጽሕፈት ዲሬክተር ።

ክቡር ጌታዬ የጽሕፈት ሚኒስቴር ሆይ ።

ምንም ሰው ሁሉ ከፈጣሪው የሚያገኘው ዕድል በብዙ ልዩነት የተከፋፈለ ቢሆን የተሰጠው ደኅነትና ትዕግሥት፤ወሰን የሌለው መሆኑን ማንም ሁሉ ተረድቶታል ።

ዛሬም የክቡርነትዎ ወደኔ ቤት መምጣት ፍጻሜ የሌለው የጋለ ደስታ ስለሰጠኝ ለዚህ አድራጎትዎ የምመልሰው ወረታ የለኝምና ይህን ከታደለና ከተመረጠ ሰው በቀር ማንም ሊያገኘው የማይቻል ስመ ጥሩነትንና ትሕትና የሚባል ልማድዎን አይቶ የቅንነትን ዋጋ የማያስቀር ቸሩ ፈጣሪያችን ለልጆችዎ ቀሪ ገንዘብ አድርጎላቸው የስምዎ መታሰቢያ ሁኖ ለዘለዓለም እንዲኖር እመኛለሁ ።

በዚሁም ቀን አባት ለልጁ የሚያሳየውን ትሕትና ለመመልከት የልጃችሁን ጥሪ አክብራችሁ ለመጣችሁ መኳንንት ሁሉ ፍጻሜ የሌለው ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ ።

ደግሞ ደግነትና ቸርነት የመላባቸው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በደረጉልኝ ክብር ያገኘኋችሁ የሥራ ጓደኞቼና ወንድሞቼ በዛሬ ቀን በመምጣታችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ። በመጨረሻውም ለትሕትና መምህር ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለእቴጌ መነን ለልጆቻቸውም ረጅም ዕድሜ ከጤና ጋራ እንዲሰጥልኝ ኢትዮጵያንም በቸርነቱ ብዛት ለዘለዓለሙ እንዲጠብቃት እግዚአብሔርን እለምናለሁ።

ቀጥለው የጽሕፈት ሚኒስቴር ጸሓፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የሚከተለውን ዲስኩር ተናገሩና ፫ጊዜ ተጨበጨበ።

ንጉሥ ዳዊት ፤

የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ያለውን መሠረት አድርገን ምንም ክብርና ምስጋናው ገናንነቱና ጌትነቱ የፈጣሪያችን ገንዘቡ ቢሆን ለኛ ለፍጡራኑ ያደረገው የለጋሥነቱ ምላት ስፋት የማይሰፈርና የማይቈጠር ወሰን የሌለው በመሆኑ ለቤዛ ዓለም የሚሆን ልጁን በዚህ ዓለም ልኮ በልጁ ደም ኃጢአታችንን ደምስሶ ልጅነቱን ሰጥቶ አንድ ወገን አድርጎ እንዳቀረበንና እንዳስታረቀን አሁንም እነሆ የክርስቶስ ፈቃዱ ሁኖ ተለያይተን የነበርነውን ሰብስቦ፤ ተራርቀን የነበርነውን አቃርቦ እምንፈራራ የነበርነውን ልብ ለልብ አገናኝቶ ባንድ ጠረጴዛ ለመሥራት፤ባ፩ ገበታ ለመብላት፤ባ፩ ጽዋ ለመጠጣት ላበቃን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ዕድሜውን አስረዝሞ ያቈይልን፤ ዘሩም የተባረከ ሁኖ በመንግሥቱ እንዲተከና ለልጅ ልጁ እንዲያልፍ ያድርልግን አገራችን ኢትዮጵያም አብባ፤ ለምልማ፤ አፍርታ፣ ከክፉ ዓይን ተጠብቃ ፍሬዋን እየበላን እንድንኖር ።

እስከ ምጽአተ ክርስቶስ የበዕድ ዓይን ከመልካም ምኞትና ከሥልጣኔ መሪ በቀር የክፉ አሳብ ዓይን እንዳያሳያት ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የተባለው ልመናዋ እስከ ፍጻሜ ዘመን አጥር ከለላ ሁኖ እንዲጠብቃልን የሁላችን ምኞት ነው ።

አሁንም ወንድሞቼ እኔም እስካሁን እድግስ ቤት መሔድ ምንኛ እንደሚከብደኝና እንደሚጨንቀኝ ሁላችሁም ታውቁታላችሁ።

ነገር ግን ዛሬ ወንድማችሁ ከናንተ ለመላመድና ፍቅርን ለመጨመር ሲል ስለጋበዛችሁ ፤ እኔንም እንድመጣለት ስለለመነኝ ሐሳቡን ለመፈጸም በመምጣቴ እጅግ ደስ አለኝ ።

እሱንም እግዚአብሔር የልቡን አይቶ የደገሠውን አዋሕዶለት ወንድሞቹን ደስ ለማሰኘት አበቃው ።

አሁንም ፍቅርን፤ አንድነትን መተባበርን፤እንዳሰበ ቸርነቱ የማይወሰን አምላክ ሐሳቡን ይቀበለው ።

ፍቅርን ለማፅናት አንድነት እንደሰበሰባችሁ እናንተም ወንድሞቼ መተባበር ኃይል መስጠቱን አስባችሁ ከዚህ በፊት የነበረውን ፍቅር እያፀናችሁ መተባበርን ፈላጊ ያድርጋችሁ ።

በዚህም ላይ ባላችሁ ዕውቀት አገራችሁን ሳትለያዩ ባንድነት እንድትረዱዋት የፍቅር ኃይሉን ይስጣችሁ ። የሀገርና የመንግሥት መውደድ ልቡናችሁ አይለይባችሁ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።በላይዋም የወጣው ፀሐይ ብርሃኑ የማይጠፋ ኃይሉ የማይደክም ይሁን።

አቴጌ መነንንም እንደዚሁ ከልዑላን ልጆቻቸው ጋራ ይጠብቅልን። አሁንም በቅርብ ቀን የተለዩንን የኢዮጵያን አበባና ጌጥ፣ የሃይማኖት መሠረት፣የድኃ ሽላ፣ የሕዝብ መድኃኒት፣ የሁላችን እናት፣ አዛኝና ርኅርኅት የነበሩትን የንግሥት ዘወዲቱን ነፍሳቸውን ይማር፣ ዛሬም የመንፈቃቸው መታሰቢያ ሁኖ ቀኑ ስላጋጠመን የሁላችን አሳብ መሆኑን ስለተረዳሁት በሁላችሁ ቃል ተገብቼ እናገራለሁ ።

ቀጥሎ አቶ ካሣ ተሰማኔ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገረና ተጨበጨበ ።

ከሁሉ መጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፡ ሕዝብና ሠራዊትን፣ ባሕርና ቀላያትን ሕዝቡን በምሕረቱ የጐበኘ የሠራዊት አምላክ ይክበር ይመስገን ።

ሁለተኛም አንበሳው ያሸነፈ መመረጥን ከእሴዘ እተ ሐር ዘንድ የተቀበለ የይሁዳ ወገን የሰሎሞን ተወላጅ የሆኑ ንጉሠ ነገሥታችንን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ረጅም ዕድሜ ሰጥቶ መንግሥታቸውንና ግዛታቸውን አስፍቶ ጠላታቸውን አጥፍቶ የዚችን ያአዲሱዋን የኢትዮጵያን ትውልድ የሥልጣኔና የማሻሻል ጽዋ ያሲያዙበትን እውነተኛውን ሐሳባቸውን አስፈጽሞልን በዕንቀና በአልማዝ በሰፔርና በፕላቲን በወርቅና በብር በዝሆን ጥርስና በዘጸ ቅጥር የተቀጠረችውንና የተጐናጸፈችዋን ቅድስት አገራችንን መጀመሪያውን የሥልጣኔ ደረጃ አሲይዘውልን እንዳንዳቸው እንደሠለጠኑት የዓለም ነገሥታት ትክክል ለማድረግ ቸርነትና ምሕረት ደግነትና ትዕግሥት ዘለዓለማዊት ክብርና ምስጋና የመለኮትነት ሥልጣኑ የማትለየው አምላክ አገራችንን ለማሠልጠን ያብቃልን ።

ሦስተኛም ጌታችን ክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ የከበረ ማዕድዎን በደስታ ለመክፈል ፍጹም ደስታዎ ሁኖ በማዕርግ ጠርተውን ስለ ተጋበዝን እጅግ ደስ ስላለን የማተሚያ ቤት ሠራተኞች ሁላችንም በፍጹም ልባችን እናመሰግንዎታለን ።

እንዲሁ ክቡር ጌታችን ግራዝማች ተክለ ማርቆስ የደግነትና እንደተናገሩት የቅንነት የትሑትነት ሥራ ልማድ ለማይለያቸው ለክቡሩ ለተመሰገኑ ክቡር ጌታችን ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ረጅም ዕድሜ ይስጥልን ።

ለብልሁ ለገናናው ንጉሥ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ረጅም ሕይወትና ጳዛት፣ለክቡር ጌታችን ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል ጤንነት፣ለክቡር ጌታችን ግራዝማች ተክለ ማርቆስ ሀብትና በረከት ለባለቤታቸው ዕድልና ክብረት ለልጃቸውና ለቤተ ሰባቸው ልማት እግዚአብሔር እንዲሰጥልን እየተመኘን ደስታችንን እንገልጻለን።

ቀጥሎ አንድ ሰው የቃል ንግግር ተናግሮ እጅግ ደስአሰኘ።

ቀጥሎ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ የሚከተለውን ዲስኩር ተናገረና ተጨበጨበ ።

ክቡራን የጽሕፈት ሚኒስቴርና ዲሬክተር ሆይ ።

ከፊታችሁ ቁሜ በኔ በራሴና በማተሚያ ቤት ስም ከዚህ በታች የሚከተለውን ምሳሌና ምስጋና ለክቡርነታችሁ ባቀርብ ድፍረት አይሆንብኝም ። ወእመ ሳብዕት ዕለት አዕረፈ እምኵሉ ግብሩ እግዲል እግዚኣብሔር ስድስት ቀን ሥራውን ሠርቶ ፍጥረቱን በብዙ ኅብረ መልክዕና በብዙ ኅብረ አምሳል አከናውኖ ከፈጠረ በኋላ ይህችን ዕድለኛይቱን የዛሬን ቀን(ቀዳሜ) ዕረፍት ትሁን ብሎ እርሱ ራሱ ድካም የሌለበት ሲሆን በዛሬ ቀን ዓርፎ እንደዋለ እኛም ከዚች መዓዛ ዕረፍት ፤ ጣዕመ መባልዕት ከመላበት ቤትዎ ገብተን በሥራ የደከመ ሰውነታችን ዕረፍት አግኝቶ ፤ ጠል ነሥቶ ስለዋለ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የምናቀርበው ምስጋና በኢትዮጵያ አጕርፎ ፤ በዓለም ላይ ሰፎ ከልክ ያለፈ፤ ከመጠን የተረፈ መሆኑን የሚጠራጠር የለም ።

ሁለተኛም፤ ከአብራክህ የተከፈለ ልጅህን በዙፋንህ አስቀምጥልሀለሁ ብሎ ለዳዊት የነገረውን የተስፋ ቃል ለልጆቻቸው እንዲፈጽምልን በሙሉ ተስፋ ሁነን ልዑል እግዚአብሔርን በየጊዜው እንለምናለን ።

ሦስተኛም፤ በማዕርግ ተከታያቸው ከሚሆኑ ከክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ ቤት ገብተው የትሕትናቸውንና የፍቅራቸውን ብዛት ለመግለጽ በዓል ስላደረጉ ለክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የምናቀርብላቸው ምስጋና አያቋርጥም።

አራተኛም፤ ለክቡርነትዎ የተከከለ ምሳሌና ጥልቅ የሆነ ምስጋና እናቀርባለን ። ኢዮስያስን አልቦ ዘገብረ በዓለ ዘከመ ገብረ ኢዮስያስ እንዳለው እንዲሁም ይህ የዛሬው በዓላችን እግዚአብሔር በሠራው ዕረፍት ላይ ስለዋለ ርእሰ ዓውደ ዓመት ወይም ርእሰ በዓላት ብለን ብንሰይመው ነውር አይሆንብንም ።

አብርሃም ጠላቶቹን ድል ነሥቶ በተመለሰ ጊዜ በመዋዕልየኑ ትሬኑ ወልደከ እንዲል ልጅህ ሥጋ የሚለብሰው ተስፋ የሚደርሰው በኔ ዘመን ይሆን? ወይስ ያችን ተድላ ደስታ የሚገኝባትን ቀን ታሳየኛለህ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ምሳሌውን ታያለህና ወደዮርዳኖስ ማዶ ሒድ ብሎት ቢሔድ የደገኛይቱ ሕግ የወንጌል ምሳሌ የሚሆን ኅብስተ አኰቴት፣ ጽዋዐ በረከት ይዞ መልከ ጼዴቅ ቢቀበለው ጽዋዐ በረከቱን አይቶ ምሳሌውን ተረድቶ እጅግ ደስ እንዳለው እኛም በጥቅምት ፳፫ ቀን አብበ፡ አፍርታ ለምናያት ለደገኛይቱ በዓላችን ምሳሌ በምትሆን በዛሬይቱ በዓል ደስታችን ዕፅፍ ድርብ ሁኖ እንደዋለ ከስረዳሁ በኋላ ጽዋዐ ሕይወቱን እቀበላለሁ ።

ቀጥሎ አባተ ብሩ የሚባል ጸሐፊ የሚከተለውን ቅኔ ተቀኘ ።

ሥላሴ

ቅሩብ ለየውሃን እግዚአ አእምሮ ወልደ መስቀል
በከመይቤ ዳዊት ዕረፍተ ብዙኃን ዘከነ ።
መርሐ ጽድቅ ወተስፋ እስመ ከነ ለነ ።
ወረዳኢሁ ማርቆስ አሥረ ፍኖቱ ዴገነ ።
በተክለ ሃይማኖት ለዘአምነ ።
አምጣነ በሰንበት ገብረ ትንሣኤ ዚአነ ።
እምእግዚኡ ነሢአ ሥልጣነ ።

ቀጥሎ አቶ ተክለ ጊዮርጊስ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ የተቀኘው ቅኔ ቀጥሎ የሚመጣው ነው።

ሥላሴ ።

ማርቆስ ይበቊዐኒ ይቤለከ ሊቅ ወልደ መስቀል
ለውሉደ ሰላም ወፍቅር ከመ ታስተራትዕ ቤተ ።
እስመ ኄር በኅበ እግእዚ ወሥሉጥ አንተ ።
አመኒ ተዐርዳ ይእዜ ደብረ አብርሃም ኂሩተ ።
እንዘ ትትገለበብ ብርሃናተ ።
ለሙሴ ሀብትነ በከንቱ ዘሞተ ።
ትንሣኤሁ ንግረነ ክሡተ ።

በዚሁም ቀን ሰውን ሁሉ እጅግ ደስ ብሎት ዋለ ። ምክንያቱም የሚኒስቴሩና የዲሬክተሩ ፍቅር እንደ አባትና ልጅ ሁነው ስለታዩ ነው ። እውነት ነው የሁለቱ መስማማት ለሠራተኛ ሁሉ ታላቅ ጥቅም ሁኖ የእኅሌ ወገን ነው ። የእኅሌ ወገን ነው ክመበል ያድናልና ። እውነት ነውና መሰቡ ከላይና ከታች ከአልገጠመ በውሥጡ ያለው እንጀራ ይደርቃል ለመብላትም ያቅታል።

የኢጣልያ መንግሥት ሚኒስቴር ወደ አዲስ አበባ መግባት ።

በመስከረም ፲፰ ቀን እንግዳው የኢጣልያ መንግሥት መልእክተኛ ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር በሙሴ ኰራ ምትክ ለመሆን መጡ።ጃንሆይም መድፍ አስተኵሰው፡ወታደር አሰልፈው በክብር ተቀበልዋቸውና ከሰላምታ በኋላ ከኢጣልያ መንግሥት ያመጡትን ወረቀት ከሰጡ በኋላ የተናገሩት ዲስኩር ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

ክፍ ያሉ ገዦዬ ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ በግርማዊነትዎ ዘንድ ልዩ መላክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር አድርገው የሾሙበትን ደብዳቤ ለግርማዊነትዎ በማክበር አቀርባለሁ ። ብዙ ዘመን በምሥራቃዊ አገር ሳለሁ የኢትዮጵያ ታላቅ አሳብ ከሺ ዘመናት አስቀድሞ የኖረውን የዚህን አገር ስፋትና ልማት የሚያደርግለት መሆኑን በቅርብ ሁኜ በሙሉ አሳብ ለመመልከትና ለመከተል ችያለሁ ። ይህንኑም አሳብ የአውሮፓ መንግሥታት የመተካከልና የሰላም ዋና መሪ አድርገው ተመልክተውታል ።

ኢትዮጵያ ለመፈጸም የሚገባትን ሁለቱን ሥራዎች በጥልቅ የተረዳው ግርማዊነትዎ ብርሃን በመላበት ጥበቡ እጅግ ደስ የሚያሰኝ እርዳታ ይገኝባቸዋል ተብሎ ለማሰብ ከሚቻል ከታላላቅ መንግሥቶች ጋራ የሚያገናኝ ሥራ በመሥራቱ ደስ የሚያሰኝ አጀማመር አደረገላት ። ይህንም የመሰለው መገናኛ ለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የገንዘብን ጥቅምና የዕውቀትን ስፋት ፤ ደግሞ ግርማዊነትዎ በብዙ ጥንቃቄ የሚያስቡበትን የኢትዮጵያን ሕዝብ መልካም አነዋወር በእርግጥ ያፈራል ።

ይህንም ከመሰለው እጅግ ታላቅ ከሆነው አሳብ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል በመታደል ከዚህ ቀድሞ ያሉትን ማስተሳሠሮች የሚያጠብቅ ነገር የሚገኝበት ብቻ አይደለም ደግሞ ለሁለቱ አገሮች የጋራ ጥቅማቸውን ለማስፋትና ለማረጋገጥ ይቻላል ። ይኸውም ሁለቱን አገሮች የሚያስተሳሥራቸው ወዳጅነት እንዲፀና የሚያደርግ አኳኋንና ማረጋገጫ ነው።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

ይህን ክፍ ያለ ሥራ ለመፈጸም የፋሺስት መንግሥት በግርማዊነትዎ ዘንድ ስለ ሾመኝ ብዙ ዘመን በማየትና በመስማት በአገኘሁት ዕውቀቴ ላይ የተመሠረተውን እምነቴን ሁሉ የኢትዮጵያንና የኢጣልያንን የጋራ አሳብ እየመረመርሁ ይህንኑ ለመፈጸም እንዲያገለግለኝ አደርገዋለሁ ።

ይህንም ሥልጣን የተቀበልሁበትን ሥራ የግርማዊነትዎን በጎ አድራጊነትና የመንግሥቱን እጅግ የተወደደ እርዳታ መሠረት አድርጌ በደስታ ለመፈጸም ክብር ባገኝ ተስፋዬ የተረጋገጠ ይሆናል።

SIRE ,

Ho l'onore di presentare alla Maestà Vostra le lettere con le quale Sua Maestà il Re d'Italia mio Augusto Souvrano, ha voluto accreditarmi presso la Maestà Vostra inqualità di Inviato Straordinario e Ministro plenipotenziario .

Da molti anni in Oriente ho potuto seguire da vicino con tutta l'attenzione e con tutto l'interesse che il grandioso problema etiopico suscitá , lo sviluppo di questo millennario Paese al quale l'Europa guarda come ad un essenziale fattore di equilibrio e di pace .

Vostra Maestà che ha appieno sentito questa duplice missione dell' Etiopia ha voluto nella Sua illuminata saggezza darvi un felice inizio con l'instaurare rapporti con le potenze dai quali è lecito trarré i più lieti auspici Da tali rapporti risulteranno concretamente l'incremento economico e culturale dell'Impero ed il benessere del popolo abissino cui la Maestà Vostra dedica le Sue più amorevoli cure

Da tale grandioso compito sortiranno non soltanto maggiormente rafforzati i legami già feliceme-

nte creati fra l'Abissinia e l'Italia, ma sará pure possibile curare lo sviluppo degli interessi comuni ai due Paesi che é condizione e garanzia della cordiale amicizia che li lega .

SIRE .

Mandato dal Governo Fascista presso la Maestà Vostra per collaborare a tali altissimi scopi io porró al servizio di essi la mia Fedóe formato dalla lunga esperienza dallo studio dei problemi comuni all'Abissinia e all'Italia .

Nello espletamento del mio mandato la speranza diverrà certezza se avró la gioia e l'onore di poter fare assegnamento sul benevolo appoggio di Vostra Maestà e sul prezioso concorso del Suo Governo .

ቀዋሉ የተነበበውም የጃንሆይ ዲስኩር የሚከተለው ነው ።

ክቡር ሚኒስቴር ሆይ ።

ግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ በእኛ ዘንድ እርስዎን ልዩ መልክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አድርገው መሾማቸውን የሚያስታውቁ ደብዳቤዎች ስንቀበል ደስ ይለናል ።

ኢትዮጵያ ከመንግሥታት ሁሉ ጋራ የወዳጅነት መገናኛ ይዛ እንድትኖር ምኞታችን ነው ። በኢጣልያና በኢትዮጵያ መከከል የነበሩት የወዳጅነት መገናኛዎች ባለፉት ዓመቶች በመታደል እየሰፉና እየጠነከሩ ሔዱ ። እርስዎም በእኛ ዘንድ የኢጣልያ ልዩ መልክተኛና ባለ ሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ሁነው በሚቀመጡበት ጊዜ ሁሉ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መከከል ያለውን እጅግ መልካም የሆነውን የወዳጅነት መገናኛ ለሁለቱ አገሮች ታላቅ ጥቅም እየሰፋ እንዲሔድ ሳያደርጉ ይቀራሉ ብለን አንጠረጥርም ። ስለዚህም ከፋሺስት መንግሥት የተላኩበትን ይህን ከፍ ያለ ሥራ ለመፈጸም ብርቱ ምኞት እንዳለዎ ስለ ገለጹልን እኛም በበኩላችን ይህ የወዳጅነት አሳብ የተመራ ሥራዎ እንዲከናወንልዎ እርዳታችንን አናጎድልብዎትም ። ወደ አገራችን እንኳን በደኅና ገቡ እያልን ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ጤና ከፍ ላለው ለግርማዊነታቸው ቤተ ዘመድ ደስታ ፤ ለንጉሣዊው መንግሥት ልማት እንዲሆን የምንመኘውን ምኞት እንዲገልጹልን እንለምናለን ።

Monsieur le MINISTRE.

C'est avec la plus vive satisfaction que Nous recevons les lettres per lesquelles Sa Majesté le Roi d'Italie a bien voulu vous accréditer auprès de Nous en qualité d'Envoyé Extraordinaire et de Ministre plénipotentiaire.

Nous avons toujours été animé du désir que l'Ethiopie entretienne avec tous les pays des rapports cordiaux. Les liens de constante amitié qui existaient entre l'Italie et l'Ethiopie se sont heureusement développés et affirmés au cours de ces dernières années. Nous ne doutons pas un seul instant que pendant la durée de votre séjour auprès de Nous, vous ne contribuiez puissamment et pour le plus grand bien de Nos deux Pays à développer les relations excellentes qui les unissent.

Vous avez bien voulu Nous exprimer le désir, fervent qui vous anime d'accomplir cette Haute Mission dont vous êtes chargé par le Gouvernement, Fasciste. De Notre côté, Nous ne manquerons pas de vous apporter Notre concours dans l'accomplissement de votre tâche inspirée d'un esprit amical.

En vous exprimant Nos souhaits de cordiale bienvenue, Nous vous prions de bien vouloir être Notre Interprète auprès de Sa Majesté le Roi d'Italie pour Lui exprimer les vœux que Nous formons pour Sa santé, pour la prospérité de Son Illustre Famille et de Son Royaume.

የምስራች ለክቡራን ኢትዮጵያ ልጆች ።

ኢትዮጵያ ከግራኝ በፊት ወደ ነበረችበት ወደ ጥንት ማዕርጓ እንድትመለስ ተከፋ አድርጌ በደስታና በደባቤ ከዚህ ቀጥሎ የሚጻፈውን ቃል አቀርባለሁ ።

ሕያው እግዚአብሔር የብዙ ሠራዊት ጌታ በየጊዜው ሁሉ ፍጥረቱን የሚጠብቅ ሠራዊቱን የሚያሠለጥን እውነተኛ ገገር አላሳጣትም ።

ኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን በዚህ ዓለም ሥልጣን ካላቸው ከተከበሩት ነገሥታት ቍጥር ነበረች ። ይልቁንም ከወሰንዋ አልፋ ተርፋ በምዕራብ ኖባንና ሱዳንን ላዕላይ ግብፅ ድረስ፥ በምሥራቅም የዓረብን ሀገር የመንን ትገዛ ነበር ። የዚህም ምስክሩ አብርሃና አጽብሐ በየመን ሀገር ስንዓ በሚባለው ዋና ከተማ ሕንፃው በብርና በወርቅ የሆነ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ነበር።አሁንም ጀበሉል ሐበሽ የሚባል አለ ። ይኸውም የኢትዮጵያ ተራራ ማለት ነው ። በየወገኑ ታሪክ እንደምናነበው ኢትዮጵያ መላ አፍሪካን ትገዛ ነበር ለማለት ያስደፍራል ።

የእስራኤል አምላክ በሙሴ ዘመን ሕዝበ ፳ ኤልን አሻግሮ ፈርዖንን ከነሠራዊቱ በባሕረ ኤርትራ በሰጠመ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፈርዖንን ሠራዊት ሲሳይ ገንዘብ አድርገዋል ይላል ታሪክ ። መዝሙርም ፸፫ ቍ ፲፬ አንተ ቀጥቀጥከ አርእስቲሁ ለከይሲ ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ ይላል ። በእውቀትም ወገን የፋርሶና የቄሳር የሮም ነገሥታቶች በመጽሐፍ ትርጉም ሲነቃቀፉ የኢትዮጵያን ንጉሥ ያስመሰክሩ ነበር ። ኢትዮጵያ በቀድሞ ዘመን የውጭ አገር ትገዛ ነበር ማለቴ አሁን ያሉትን የውጭ አገር ገዝዎችን የኢትዮጵያን ወዳጆች የፍቅር ወንድሞች ለማስተሐቀር ብዬ አይደለም ከጥንት ጀምሮ ዓለም የሚያውቀውን ታሪክ የመሰከረውን የኢትዮጵያን መንግሥት የገናንነቱዋን ስፋት የዕውቀቱዋን ብዛት ልኩን ለመናገር ብዬ ነው ።

ታላቁም ንጉሥ እስክንድር ዘ፪ኤ አቅርቲሁም የምሥራቅንና የምዕራብን ነገሥታት የፋርስንም ነገሥታት ድል ነሥቶ የህንድንም ንጉሥ ፉዝን ገድሎ ወደምሥራቅ ዘምቶ ከተመለሰ በኋላ ታሪኩ በዓለም ላይ የታወቀው የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ እስክንድር ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት ህንደኬ ስምንት ቀን ያህል ከጡዋት ጀምሮ እስተማታ ሰልፍ ካሳየችው በኋላ የመጣውም ራሱን ሠውሮ መላክተኛ ነኝ ብሎ ነበርና ከእወቀቱዋ ርቀት ከብልህትዋ ብዛት የተነሣ ዓለምን ሁሉ በዕውቀቱ የበለጠውን እስክንድርን አንት የዓለም ንጉሥ አሁን በኔ እጅ ገብተሀል ብላ ዕውቀቱንና ርቀቱን ያገኘች የኢትዮጵያ ንግሥት ህንደኬ ናት ።

ግን ሁለቱም ዓለምን ለማቅናት ሕዝብን ለማሠልጠን ሠራዊትን የሚጠቅም ነገር ለመሥራት በፍቅር ተሰማምተው ተለያዩ ። እግዚአብሔር በየጊዜው ፍጥረቱን የሚጠብቅለት እውነተኛ ዳኛ አያሳጣትም ።

የዕውቀት መሪውን የሥልጣኔውን መሠረት ናፖልዮንን ለፈረንሣዮች የዓለሙዋን ብርሃን የባሕሮችን አለቃ ፀሐይ የማትጠልቀውን አገር የምትገዛ ቢክቶርያን ለእንግሊዞች።

ለዓለም ዳኞች ለዕውቀት መሪዎች ላሜሪካኖች ዌልስን በቀድሞ ዘመን በጀርመኖች ሀገር በንዴራቸው በየአውራጃው የነበረውን አንድ ያደረገ በዕውቀቱ የታወቀ ቢስመርግን ለጀርመኖች ። ደግሞም የጥበቡን መሪ የዕውቀቱን አሽጋጋሪ የብልሆችን አለቃ ሲኞር ሙሴሊኒን ለኢጣልያኖች ። ደግሞም ለጥበብ ጀማሪዎች ለጻድቃን ለእንጠንስና ለመቃርስ አገር ለምስር ሡልጣን ፉዓድን ።

የጥበቡን መሠረት የጊዜውን መስታዋት የዕውቀቱን መሪ የዓለሙን ማእዘን የአፍሪካን ብርሃን የነገሥታትን አበበ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለኢትዮጵያ ሰጥቷል ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ታማኞች አሽከሮች ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ሰውነታቸውን የማያሳልፉ ወታደሮች እያሉዋቸው ከጕልበት ዕውቀት ይበልጣል ጕልበትም ያለ ዕውቀት ዕውቀትም ያለ ጕልበት ሁለቱ በንድነት ካልተገኙ አይሆንም እንደተባለው ምሳሌ ኢትዮጵያን ለማስፋትና ሕዝባቸውን ለማሠልጠን ሲሉ ከኢትዮጵያ ነገሥታት አንድ ንጉሥ እንኳ ወደ አውሮፓ ሒዶ የማይውቀውን ግርማዊነታቸው በ፲፱፻፲፮ ዓመት አውሮፓ ሒደው በዓለም ላይ ካሉት ነገሥታት ማኅበር ገብተው የሀገራቸውን ነፃነት አፅንተው በደስታና በይባቤ መጡ ። ደግሞ አሁን በእግዚአብሔር ቸርነት ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ በአብርሃና በአጽብሐ በእጼ ካሌብ በላሊበላና በነአኵቶ ለአብ የዓባይን ውኃ የመለሱ በነአጼ ዳዊት ላዕላይ ዓብዕ ድረስ ዘምተው የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ግማደ መስቀል ተቀብለው የመጡ በአጼ ሰይፈ አርዕድም ጊዜ የምስርን ፀትረ ያርክ ማርቆስ ቺኛውን በግብር ምክንያት ቢታሠር አስፈትተው መጡ ስለ ሃይማኖታቸው ፅናት እንደ ፀሐይ ወገግታ የሚያንጸበርቅ መስቀል ከምስር ሊቀ ጳጳሳት በረከት መጣላቸው ። በነዘርአ ያዕቆብና በአጼ ልብነ ድንግል የነበረ የኢትዮጵያ የጥንት ማዕርጓ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ተመልሶላት ይህንም የደስታ ዘመን ለማየት ያበቃንን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ብርሃናዊውንም ንጉሠ ነገሥት እንዲጠብቅልን ሕያው እግዚአብሔርን እንለምናለን።

የዓረቢ አስተማሪ ወልደ ሥላሴ ።

ሹምሽር ።

ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ አሩሲን ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ወልደ አማኑኤል ደጃዝማች ተብለው መርሐቤትንና ጃማን ተሾሙ ።

አቶ ተሰማ ደባልቄ የነጋድራስ ደስታ የነበረውን በልዩ የቆመውን የፍርድ ቤት ዳኝነት ተሾሙ ።

ፊታውራሪ ደቻሳ የመታሰቢያ ቤትን ዘበኝነት ተሾሙ ።

ልጅ ግርማ ያየህ ይርዳድ የዕንጨት ጉምሩክን ተሾሙ።

ልጅ መኰንን ቀለመወርቅ የጨርጨርን ዲሬክተርነት ተሾሙ።

ሹመት ያዳብር እንኳን ደስ አላችሁ ።

ስለ አቶ ወልደማርያም ገርሜ ዕረፍት ።

የጉምሩክ ጸሐፊ አቶ ወልደ ማርያም ገርሜ የተማረ ምግባረ መልካም፡ ሰው የተስማማ እጅግ ደግ ሰው ነበር። የታመነ በመሆኑም የነቆርንና የነሞርን ገባያና ኬላ ዲሬክተርነት ተሹሞ ሒዶ ነበርና የሥራውን ነገር ካለቃው ለመማከር አዲስ አበባ መጥቶ ሰንብቶ አባቱ አቶ ገርሜ ቤት በድንገት ታሞ በተወለደ በ፴፫ዓመቱ በመስከረም ፳፮ቀን ዓርብ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ያማረ ፍታት ተደርጎለት ብዙ መኳንንትና ሠራዊት ተሰብስበው በማዕርግ ተቀበረ ። እንደዚህ ያለው ወጣት ልጅ ሲሞት እጅግ ያሳዝናልና አባቱን አቶ ገርሜንና ወንድሙን አቶ መልከን እግዚአብሔር ያጽናቸው ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ አሸቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ነክላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሕ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ደሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት ብርሳሊን ባርኔጣ መጥቶላችሁ አዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፊርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅስ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርከፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም
LUMIERE ET PAIX

፮ኛ ዓመት ቍጥር ፵፪ 6me ANNÉE № 42		ሐሙስ ጥቅምት ፯ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም። JEUDI 17 OCTOBRE 1950

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ደስ የሚያሰኝ ሥራ ።

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በዓል በከተማው ውሥጥ እጅግ የሚያስደንቅ ሥራ ይሠራል ።ሲጀመር የማያልቅ የመሰለው ሥራ ሁሉ ሕዝቡ ስለደስታው ክትእዛዙ በቀር በፈቃዱ ተግቶ ስለ ሚሠራ የጀመረውንም ከመጨረስ ወደፊትም ለመጀመር ዓላረፈም ። ከላጋር አንሥቶ እስከ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ድረስ ። ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አንሥቶ እስከ ታላቁ ቤተ መንግሥት፡ ከታላቁ ቤተ መንግሥትም እስከ አልጋ ወራሹ ቤት ድረስ በጥሩ ድንጋይ እየተደለደለ በቀዝቃዛ አስፋልትና በሙቅ አስፋልት ሊሠራ የተጀመረው መድረሱ የማያጠራጥር ሊሆን ነው ።

በከተማውም መካከል ሊበራ የታሰበው ኤሌክትሪክ የሲሚንቶው ምሰሶና የሽቦው አዘረጋግ እጅግ ደስ የሚያሰኝ እየሆነ ኤሌክትሪኩም በመካከሉ ጐዳና ላይ ብርሃኑ እንዲወድቅ እየሆነ የተተከለው ፋኖስ የሚያስገርም ሆንዋል ።

በየመንገዱም ዳር ያለው ቤት በካልቢቶስ እንጨት እንደ ሚያምር እየተገጠመ ተሠርቶ ደምቆ ይታያል። በዚሁም ሥራ አኳኋን የሊጋባውና የከንቲባው የሥራ ሚኒስቴሩ ትጋት እጅግ ደስ ያሰኛል፥ የቀሩትንም ለዚህ ሥራ ረዳት የሆኑትን ፀሚከተለው እናስታውቃለን ። ከዳር አገር የዘውዱን በዓል ለማክበር እንዲመጡ የተፈቀደላቸው መኳንንት ክቡር ዋና ሹም ከበደ፥ክቡር ደጃዝማች ብሩ፥ክቡር ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ፥ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል፥ክቡር ደጃዝማች እምሩ።ክቡር ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፥ክቡር ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር ። ሊቀ መኳስ መኰንን ዋልቴ ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም። ደጃዝማች ከበደ ጓንጉል። ደጃዝማች አምባቸው። የክቡር ጅማ አባጅፋር ዋና ልጃቸው አባ ጆሎ ። እነዚህ ናቸው ።

የኢትዮጵያ መንግሥት የሥልጣኔ ደረጃና ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሣዊ ማዕርግ ከፍታ።

ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ኢትዮጵያን ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ በማገናኘታቸውና በማቀራረባቸው የሥልጣኔ መንገድ አዘጋጅተው ስለ ቆዩ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይህን አፄ ምኒልክ ያዘጋጁትን መንገድ ተከትለው በ፲፱፻፲፭ ዓመት ኢትዮጵያ ወደ መንግሥታት ማኅበር እንድትገባ አደረጉ ። አሁንም የንጉሠ ነገሥት ዘውድ በሚጭኑበት በዓል ከአውሮፓ መንግሥቶች የደስታቸው ተካፋይ እንዲሆኑ ከዚህ በታች የተጻፉትን መንግሥቶች ጠርተው ነበርና ጥሪያቸውን አክብረውና ተቀብለው ለዘውዱ በዓል የሚልኳቸውን መላክተኞች በየስማቸው አድርገው አስታውቀዋል ። የመላክተኞቹም ስም ከዚህ በታች እንዳለው ነው ።

፩)፡ የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መላክተኞች ።
ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተር የግርማዊ ንጉሥ ልጅ ።
ክቡር ኤርል ኦፍ አርሊ ።
ማዦር እስታኒፎርት ።
መስተር ብሩክ ።
መስተር ኖብል።
ማጆር ማይልስ ።
መስተር ቲሲጀር ።

፪) ፡ የክቡር የአስቴትስ ኦፍ አሜሪካ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን መላክተኞች ።
ክቡር ሀ መሬ ጃኮቤ የክቡር ፕሬዚዳን ልዩ አምባሳደር
ጄኔራል ዊልያም ሀርድ ።
መስተር ቻርልስ ሌ ኩክ ።

፫) ፡ የግርማዊ የጃፓን ንጉሠ ነገሥት መላክተኞች ።
ክቡር ሙሴ ኢዛቡሮ ዮሺዳ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ልዩ አምባሳደር ።
ሙሴ ሳዴዮሺ ታክሰዋ

፬) ፡ የግርማዊት የሆላንድ ንግሥት መላክተኞች ።
ክቡር ዮንሔር ሀ መ ባን ሔርስማይ የግርማዊት ንግሥት ልዩ አምባሳደር ።
ባሮን ባን ሐሬንክስ ማቶዊ አሉተን ።
ሙሴ ሕሩመር ።

፭) የግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ መላክተኞች ።
ልዑል ፌርዲናንዶ የሳቦያና ጄኖባ የኡዲኒ ፕሪንስ። ከአሬሲዮ ዶርዶናንሰቸው ከከፒታኖ ዲ ባሺሎ ማርኬዜ ፍራንክ ስፒኖሎ ጋራ ።
ክቡር ሲናተር ያኮፖ ጋስፓሪኒ ።
ኮማንዳቶር ማሪዮ እንዲሌ ።
ኮንት አርቦሪዮ ሚላ ዲሳንቲሊያ ።
~~ቲኔንቲ ክሎኔሎ ሞኔሬ ዲቤላር ።~~
ኮማንዳቶር ጂ ቦቺ ።
ቲኔንቲ ዲባሺሎ ማዙኬቲ ።
ካባሊዬሬ ሚሺሌ እስከማካ ።

፮) የክቡር የፈረንሣዊ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን መላክተኞች ።
ማሬሻል ፍራንሼ ዲስፔሬ ከኤድ ደካ ጋራ ።
ክቡር ሙሴ ሽፖ ቤማክ ።
ሙሴ ጋዜል ።

፯) የክቡር የግሪክ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን መላክተኞች ።
ክቡር ኮንት ፔ መተክሳስ የክቡር ፕሬዚዳን ልዩ አምባሳደር ።
ሙሴ እስፒሮ ካፔታኒዴስ ።

፰)የግርማዊ የስዊደን ንጉሥ መላክተኞች ።
ክቡር ሆክ አሮልድ ደቤልት የግርማዊ ንጉሥ ልዩ አምባሳደር ።
ኮንት ኤሪክ ፎን ሮዘን ።
ኮንት እስቴን ፎን ሮዘን ።

፱) ፤ የክቡር የጀርመን ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን መላክተኞች
ክቡር ባሮ ቦን ባልትሐውዘን የክቡር ፕሬዚዳን ልዩ አምባሶድር ።
ባሮ ፎን ፕሌሰን ።

፲) ፡ የግርማዊ የቤልጂክ ንጉሥ መላክተኞች ።
ክቡር ሙሴ ማክሲሞጀራር የግርማዊ ንጉሥ ልዩ አምባሳደር ።
ጀኔራል ባን ላንዠንደንክ ።
ሙሴ ሙስኒ ።

፲፩)፡ የግርማዊ የግብፅ ንጉሥ መላክተኞች ።
ክቡር ሞሐመድ ቶፊክ ነሲምፓሻ የግርማዊ ንጉሥ ልዩ አምባሳደር ።
ክቡር ሸሪፍ ሳብሪ ቤይ ።
ሰሊብ ሳሚ ቤይ ።
ማጆር ዑመር ፋዚ ።
ሙሴ አዚዝ ሚርዛ ።

፲፪)፡ ክቡር የቱርክ ሬፑብሊክ መንግሥት ፕሬዚዳን የመልክተኞቻቸውን ስም ገና አላስታወቁም ።

ሹም ሽር ።

አቶ ሙሉጌታ የሐረርጌው፥ ቀኛዝማች ተብለው የቡልጋን ምስለኔነት ተሾሙ ።

ልጅ በልሁና ልጅ ከበደ በያዙት ሥራ ላይ በቤተመንግሥት ባለው ሠረገላና አቶመቢል ዲሬክቴርነት ተሾሙ ።

አዣዥ ሥነጊዮርጊስ በእቴጌ መነን ቤት ሁለተኛ አዛዥ ሁነው ተሾሙ ።

አቶ ድጋፌ በእቴጌ መነን ቤት ጸሐፌ ትእዛዝነት ተሾሙ ።

ሹመት ያዳብር ።

የአይሮፕላን ትምህርት ።

ሚሽካ ባብቸፍና አስፋው አሊ አይሮፕላን መንዳት እን-ዲማሩ ጃንሆይ ፈቀደውላቸው ከመምህራቸው ከሙሴ ቢደል ጋራ ወደ ጅጅጋ ወርደው ፫ወ ሳይሆናቸው አይሮፕላን መንዳት ደኅና አድርገው ተምረው ወደ አዲስ አበባ መጡ ። መምህራቸውም የተማሪዎቻቸውን ዕውቀት ለማሳየት ጃንሆይን ለምነው ፈቃድ ተቀብለው ጃንሆይም በተቀጠረው ሰዓት ወደ ጃን ሜዳ መጥተው በትክክል ማወቃቸውን ተረድተው ለመ-ምህራቸው የሚነገት ኒሻን፣ ለሚሽካና ለአስፋው የክብር ኮከብ ኒሻን ሸለሟቸው ።



ስለ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ዕረፍት

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ እጅግ ብልህና ጀግና ነበሩ፡ ለጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክም እጅግ ባለሟልና ረቃደኛ ነበሩ። በኋላ ግን በልጅ ኢያሱ ጊዜ ከመንግሥት ተጣልተው ወደበረሃ ሲኖሩ ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ በነገሡ ጊዜ፣ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም አልጋ ወራሽ በተባሉ ጊዜ ምሕረት አድርገውላቸው ወደአዲስ አበባ ገብተው በማዕርግ ሲኖ ሩ እንደ ቍርጥማት ያለ ሕማም አምዋቸው ሐኪም ወደሙ-ቀት አገር እንዲሔዱ አዝዘአቸው ሔደው ሕማማቸው የማይ-ሻላቸው ቢሆን ወደ ሚጣቅ ጠበል ለመጠመቅ ሔደው እዚያው ሙተው ሬሳቸው አዲስ አበባ ቤታቸው ገብቶ ሲፈቱ አድረው ጃንሆይና ጳጳሳቱ፣ መኳንንትና ወይዛዝር ከብዙ ሕዝብ ጋራ አልቅሰውላቸው በጥቅምት ፮ ቀን በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በክብር ተቀበሩ ። የዕድሜአቸውንና የታሪካቸውን ነገር በሚ ከተለው እናስታውቃለን ።

ስለ ወይዘሮ ዘነበች ዕረፍት ።

ወይዘሮ ዘነበች የቀኛዝማች ዘውዱ አባኰራን ባለቤት አባታቸው ቀኛዝማች ሶርሱ ነበሩ ።

በእናታቸው ወገን የቆቅ ማሪ አበዬ የልጅ ልጅ የወይ-ዘሮ መንጣልያ ልጅ ናቸው ። እጅግ የተዋቡ ጠባየ መልካም ነበሩ ። በፅኑ ታመው ሐኪሞችም ቢደክሙ ቢደክሙ ቀኑ የደረሰውን ሰው የሚአድነው የለምና በተወለዱ በ፳፰ ዓመ-ታቸው በመስከረም ፳፰ ቀን ዓርፈው ብዙ መኳንንትና ወይ ዛዝር ተሰብስበው እጅግ አልቅሰውላቸው አዲስ አበባ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በአማረ ፍትሐት ተቀበሩ ።

ያገርን ድኆች ስለ መርዳት ።

ልዑል ራስ ኃይሉ በ፲፱፻፲፮ ዓ መ ከጃንሆይ ጋራ ወደ አውሮፓ ሲሔዱ አምስት አሽከሮቻቸውንና አንድ የወንድማ ቸውን ልጅ በስዊድሽ ሚስዮን ተማሪ ቤት አግብተዋቸው ሔዱ ልጆቹ ግን የተማሪ ቤቱን ሕግ መጠበቅ ስላ አልሆነላቸው አን ዳንድ እያሉ ወጡ። ከአውሮፓ ከተመለሱም የሥራ ሁሉ መሠ-ረት ትምህርት መሆኑን ስላወቁ ከጐጃም ዓሥር ልጆች ወደ ጃንሆይ ተማሪ ቤት እንዲማሩ ልከው ነበር ። ነገር ግን ልጆቹ የትምህርትን ጥቅም ስላላወቁ ቶሎ ከተማሪ ቤት ወጡና ተበታተኑ ። ከዚያ በኋላ ግን ለጌታቸው ታማኝ የሆኑና ሥራ ቸውን በጥንቃቄ ለመሥራት የተዘጋጁ ክቡር ቀኛዝማች ደመር በግዕዝ ተማሪ ቤት የተማሩትን ስድስት የድኆች ልጆች በተ-ማሪ ቤት አገቡና ለልዑል ራስ ኃይሉ ቢያመለክቱላቸው እርሳቸ ውም በእውነት ትምህርት የሚወዱ ልጆች ከተገኙ ደግ ነው እንደ ደንቡ ክፈልላቸውና ይማሩ ብለው ስለ ፈቀዱላቸው ሶስት ዓመት ያህል በተፈሪ መኰንን ተማሪ ቤት ሲማሩ ቈይ-ተው ከፍ ያለ ትምህርት እንዲያገኙ በመስከረም ፳፰ ቀን ወደ ቤይሩት ሰደዱዋቸው ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች የሚባሉ መኳንንት ሁሉ የልዑል ራስ ኃይሉን መልካም አሳብ ተከትለው ያገራቸውን ድኆች ትምህርት እንዲያገኙ ቢረዱዋ ቸው የመንግሥት ረዳቶችና የሀገራቸው ወዳጆች ተብለው ከሚጠሩት ጋራ ስማቸው ተጽፎ እንዲኖር ጥርጥር የለበትም ትምህርት ፈልገው በምን በኩል ተማሪ ቤት እንደሚያገኙ የሚጨነቁ ድኆች ብዙ ናቸው ።

ቄስ ባድማ ያለው ።

የሚያነቃቃ ምክር ።

የለምለሚቱ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ። ፀሐይ ወጣ። ብርሃን መጣ ። ተነሡ ጥበብ ኩታችሁን ልበሱ ። ጐረ-ቤቶቻችሁን ተመልከቱ ። የውቀት ጋሻችሁን መክቱ ። የሥራ መሪአችሁን ተከተሉ ። እቤት አትዋሉ ። ዕውቀትን ለማግኘት ተጋደሉ ። ቁ ንቁ ከሥራ ጋራ ተናነቁ ። ያንድ አሳቢ ልብ ብቻ አታስጨንቁ። ያባታችሁን አገር ሳትንቁ። ያገ ራችሁን ቋንቋ ዘይቤን ሳትለቁ ። የሌሎችን ቋንቋ እወቁ ። ለቋንቋም ብቻ አትራቀቁ ። የጅ ሥራም ደባልቁ ። በቀድሞ ዘመን ተማሮች ልብሳቸው ደበሎ ። ምግባቸው ቆሎ ። ያውም ጦም ውሎ።አገር ላገር ለልመና ተንቀዋሎ ነበር ። በዕድላሙ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ግን ተማሪ ነጭ ለብሶ፣ነጭ ጐርሶ፣ አልጋ ዘርግቶ ፍራሽ አን-ጥፎ መከዳ ተንተርሶ ሆነ፣በቀድሞ ዘመን ባላባቶች ቤተ ክር ስቲያን ቢፈርስባቸው ፍሪዳ ነድተው፣ማር ጭነው፣ ከተማ ገብ ተው፣ የሚነግርላቸው አጥተው ተንገላተው ንጉሡን ባገኙ ጊዜ ግብር ያቅሉልን የቤተ ክርስቲያን ሥራ ይፍቀዱልን ብለው ጨኸው በተፈቀደላቸው ጊዜ ጨዋው እልል እያለ ካህኑ ንሴብሖ እያለ ይሠራ ነበር ። አሁን ግን በዕድላሙ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አፄ ኃ ጊዜ ግርማዊነትዎ አውቆ ቤተ ክርስ-ቲያን ሥሩ ያልሠራችሁ በመቀጫችሁ ቤተ ክርስቲያን ትሠራ

ላችሁ፥ እንዲሁም ስባልኋችሁ አይዝዋችሁ እኔ አለሁላችሁ የጕደለ የምመላላችሁ፥ የዘበ የማቀናላችሁ፤ ለዚህም ደጃዝማች ደስታ ባልደረባችሁ ማለት ሆነ ። በቀድሞ ዘመን የሙንግሥት ተወላጅ ሲነግሥ ባላቤቶች ተሰብስበው ገጸ በረከት ይዘው የጥንት ደብቃ ደበሉን ሽህ ዓመት ያንግሥዎ ይሉ ነበር ። ይህንም ማለቷ ቸው የበሰ ነገር እንዳይመጣ ነው እንጂ ፥ የተሻሻለ ተሠርቶላቸው እንዳይቀርባቸው አልነበረም። ይህንም ማለቴ ጊዜው የኃይልና የጦር ብቻ ስለ ሆነ ነው እንጂ ክፉዎች ነበሩ አላልሁም። ክፎዎችማ ቢሆኑ መቼ እንዲህ ያለ ዘር ኃይለ ሥላሴ ይወጣላቸው ነበር? ለወጣቶች ማሳሰቢያ፥ ማትጊያ ለዚህም ምስጋና በግዕዝ መወድስ ቅኔ ።

ለዘያፈቅሮ ሰናክሬም እስከ፣ ጊዜሁ፥
ንዋመ አዕይንት ክቡደ እግዚአብሔር ወሀበ ።
ወእግዚአብሔር ፈጠረ ንዋመ አዕይንት ዘአልቦ ።
ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ።
ዘየዓቢ እምአዕይንቲሁ ዓይነ ልብ ዘቦ።
በሕሊና ጥበብ ወተናብቦ ።
እምነ አርምሞ ንዋም ዕረፍት ዘባን ወገቦ ።
ለሐክይሰ ዘያከብር ዓራት ሕማም ምስከቦ ።
እንዘ ኢይከውን መመግበ እምእመጋቢሁ ዘአመገቦ ።
እንበለ ለሊሁ ይሠራዕ ወዘእንበለ ይሥራዕ ሕዝቦ ።
ንዋመ አዕይንት መግኑዕ ዕረፍተ ፍልስጥኤም ተራከቦ ።

አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ስለ አዲስ አበባ መንገዶች ማስታወሻ ።

በአዲስ አበባ ያሉት መንገዶች ሊአምሩና ሊመሠረቱ ተጀምረዋል። ለጸጉ ሳቢልሁ ለቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ መልካም ታሪካቸው በዚሁ ክፍል ሥራ ግሩም ድንቅ የሆኑ መልካካም ቃሎች ተጽፈውላቸው ለስማቸው መታሰቢያ ሆነው ይኖሩላቸዋል።

በዚሁ ታሪክ ውሥጥም የክቡር ከንቲባ ነሲቡ ዛማኑኤልና የክቡር አቶ አየለ ገበሬ ስምም በውነተኛ ምስጋና ሳይጻፍላቸው አይቀርም ።

ከዚህ ቀጥሎ ግን ያዲስ አበባዋና ዋና መንገዶች ስም እንዲወጣላቸው እናስታውሳለን ። የመንገዶችም ስም ሥያሜ ከዚህ ቀድሞ እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያን ነፃነት ደማቸውን እንደጕርፍ አፍስሰው ያቆዩን ነገሥታትና አርበኞች መንገዱ ሁሉ በነሱ ስም በጽሕፈት ተጠርቶ እንዲታይና በዚሁ የተነሣ ስማቸው ለዘለዓለም እንዲኖር አሁንም ወደፊት ያሉት ነገሥታትና አርበኞች ይኸንን የዘለዓለም ስም ተመልክተው ጕብዝናቸው እየጠናላቸው እንዲሔድ አይጠረጠርም ። ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ አደባባይ ባራዳ መካከል ወደ ጊዮርጊስ ሲወጡ ወደ ግራ ያለው ሞላላ ሱቅ የከተማውን መልክ አበላሽቶ መንገዱንም አጥቦ ይልቁንም አሁን የተሠራው የዳግማዊ ምኒልክን ሐውልትና በጥሩ የተሠራውን የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን እስልክ ቤት ሁኖ በቀጥታ እንዳይታይ አድርጎ ሳይን ግራ ማግባቱ እጅግ ያሳዝናል ።

ይህም ሞላላ ሱቅ በተሠራበት ቦታ ላይ የኢትዮጵያ ነገሥታትና አርበኞች ሐውልት እየተሠራላቸው በዚሁ ስፍራ እያየን እንዳናስታውሳቸው እመከከል ተጋርዶ መኖሩ በጣም ቁር የሚያሰኝ ሳይሆን አይቀርም ።

ዘለቀ ታችበሌ ።

መልካም መተጫጨት ።

የኢጣልያ ንጉሥ ሦስተኛይቱ ልጃቸው ልዕልት የሳቦያ ዦቫንሴስ ጂዮባና ። ከቡልጋር ንጉሥ ግርማዊ ቦሪስ የኮቡርግ ጎትሃ ጋራ መታጨትዋን የውጭ አገር ጋዜጦች ያስታውቃሉ ይኸውም በቅርብ ጊዜ የሚደረገው ሠርግ ለሁለቱ ለኢጣልያና ለቡልጋር ሕዝብ ደስታ ይሆናቸዋል ። ስለምን እነዚህ ሁለቱ ሕዝቦች የንጉሦቻቸውን ዘር ጥልቅ የሆነ መውደድ አላቸው ይኸውም መውደዳቸው የሁለቱ ነገሥታት የዕውቀትና የደግነት አኳኋናቸው ነው በሰፊው ገልጾ የሚያስረዳ። እንደዚህ የሁለቱ መሳፍንት ፍቅር ደስ የሚያሰኘውን መፈጸሚያ ያገኛል። ቦፖለቲካም ሥራ መንገድ ቢሆን ይኸው አኳኋን በጣም ትልቅ አኳኋን ሁኖ ይመለከታል፥ የኢጣልያም መሪ (ዱቼ) ስለ ትልቁ አገሩ የፍቅርንና የሰላምን ፖሊቲካ በብሩህ ልቡናና በጠነከረ መጠንቀቅ እንደሚያስኬደው ያሳያል ።

ለሁለቱ ንጉሣዊ ቤተዘመድና ለወዳጆቻችን መንግሥታት እውነተኛው ምኞታችን ይድረሳቸው ።

ስለ አረቂ ጕዳት ።

አረቂ መጠጣት የሀገር ጕዳት ነው ብሎ በብርሃና ሰላም ቍጥር ፫፻፷ገጽ ፫፻፯ ክቡር አቶ ዘለቀ ታችበሌ ስለ ጻፉው ለአንባቢዎችና ለሰሚዎች በተቻለኝ ዕውቀቴ ልናገር እደፍራለሁ እውነት ነው ለሀገራችን ጉዳት ለሰውነታችን ጥፋት መሆኑን ማንም ሰው ይስተዋል ብዬ አልጠራጠርም። ነገር ግን ሰው ሁኖ አጥፊውን ነው የሚያስወድደው እንደሚባል ሁሉ እኛም ለገንዘባችን ጠላት ለሰውነታችን ጥፋት እንደሆነን ከወቅነው በኋላ ያንኑ የሰውነታችን አጥፊ ጠላታችን አረቂ የሚባለውን መጠጥ እሱን ወደን በመቅረታችን በጣም እናሳዝናለን ጠጥተን ቢታመምን ጊዜም እንደመተው በማግሥቱም ያንኑ እሳት ነዳዲ የሆነውን አረቂ እንጠጣዋለን። ልብ የሚአቀዘቅዘውን እርጎ በመጠጣት ፈንታ ወዲያውም መጠጥ የገደለውን መጠጥ ያድነዋል እያልን እናወራለን ወደፊትም ለሚወለዱት ልጆች ትምህርት ማስተማራችንን አልተረዳነውም አሁን ግን ጉዳታችንን ሰው ሳይነግረን ራሳችን አውቀን ከተረዳነው መልካም የልብ መከሬ ዘመድ ብርሃንና ሰላም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ተገኝቶልናልና ምክሩን ወደ ክፉ ሳንተረጕም በቅን ልቡና ተርጕመን አረቂ መጠጣትን ወተት ብለን መተው ይሻላል። ክቡር ሆይ በቲንሸዋ በድሬደዋ ከተማ አርባ ሁለት ስፍራ አረቂ የሚጠጣባቸው ቦታዎች ተዘጋጅተዋል ስለ አልከውም አሳንሰኸዋል እንጂ መኖሩ እርግጥ ነው።ስለዚሁ ስለ መጠጥ ነገር ከዚህ ቀደም ሁላችንም

ጅፈን ነበር።መጀመሪ ነገር እኛም የጻፍነው ሰዎች ይህንኑ እሳት ነዳጅ የሆነውን አረቂ ከመጠጣት አልተወሰንም አጥብቀን እንጠጣለን እንጂ ሕዋሳታችንን እየቀሰቀሰ ወደ የሁም ደማችንን እያበላሸ ሲጫዋትብን ልንተወው አልቻልንም። አሁን ግን በቶሎ ፈጠን ብለን ከተውነው በአረቄ ፈንታ የምንጠጣቸው አንደኛ መጠጥ ከሀገራችን ተራሮች ሥር የሚፈልቁት አፍላገ ማያት፥ ሁለተኛ ክላሞቻችን የሚገኙት እነወተት እነአርጎ ልብ የሚአቀዘቅዙትና ሆድ የሚአርሱት ሶስተኛ ከንህብ እነማር፥ ከገጨት እነ ጌሾ፥ ጥሩ ጥሩ መጠጥ አሉን እንዳልኸውም ሁሉ እናደርገውም እንጂ ብናደርገው መልካም ነው ይበቁናል እንኳን ለእኛና ለውጭ ሀገር ሰው መትረፋቸውን ማንም አይሰተው።ደልቁንም አንድ ሊትሮ ወተት በሶስት መሐለቅ ስንሸጥ ብዙ ዋጋ ያገኘን ይመስለናል።ይኸውም በድሬደዋ ከተማ ነው እንጂ በሌላው ሀገር ከአንድ መሐለቅ በላይ ይሸጥ አይመስለኝም። እኛ ግን እንደ መለኪያ ውስኪ ከነሶዳው በአሥራአራት መሐለቅ ስንገዛ ጊዜ ምን ይባላል እንግዲያውስ በውነት ተመልካች ለሆነ ሰውምን መስሎ ይታየው ይሆን እንደኔ ሀሳብ አደዚህ መስሎ ይታየዋል ብዬ እመልሰለታለሁ። እኛም እንግዲህ ጉዳታችንን ካወቅነው መተው ከዚህ ቀደም ስለጠጣነውም አይቀጨን የሀገራችን ሽማግሌ እንኳን ሲተርት እንዲህ ይላል የአለፈ ነገር አይቀጭህ፥ የሚያድግ ልጅ አይጥላህ፥ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ የሚያልፍ ውሃ አይውሰድህ ብሎ እንደሚተርት ሁሉ።ስለ ሐርና ቁለ ከች ይቅርብን ስለ አልከውም መልካም አንተ እንዳልኸው ጭራሽ ባይቀርብን እንኳን ሠርተን እስትንለብስ ድረስ ብንቆይግድ የለም።አሁን ግን ለጊዜው ጥጡ በጣም ተወደ ልና እስቲረክስልን ድረስ ሐርና ከች ባንለብስ እንኳን እነ ሰነፊ ሴቱን እነ አረፈጣቴን እነ አትንኩኝን ብንለብስ ክፉ አይመስለኝም።የሀገራችን ጥጥ ከልሆነ ትለኝ እንደሆን መልሱን እኔም በተሰጠኝ አእምሮዬ ማቅ ይሞቃል ሻሽ ይደምቃል ገቢውን ባለቤቱ ያውቃል ብዬ በማክበር እመልስልሃለሁ ።

ገብረ. እግዚአብሔር ጉሣ የድሬደዋ ጉምሩክ ጸሐፊ

እናስብ እንመልከት

የ፷ኛ ዓመት ቀ. ፴፬ ብርሃንና ሰላም ለጥቅማችን መንገድ የሚመስለንን ስለጠየቀ ምሳሌ ፲፰ ቀ. ፴ መልካም ወሬ መስማት ልብ ያለመልማል እንዳለው በጣም ደስ እሚያሰኝ ነው ።ላንባቢ እንዳይሰለች የመሰለኝንና ያየሁትን በጥቂቱ እጦለክታለሁ ። ብዙ አረቂና የመሸታ ጠጅ ሻጭዎች እናያለን። ምክንያቱም ፈላጊዎች ቢበዙ ይሆናል እሚያሰኝ ነው። መሸታ ሻጭ ሴቶች እስከ፳ና ፺ እየሆኑ ሱቅ እየተከራዩ ፩፩ ጭነት ማር እስከ፹ና፸ ብር ድረስ እየገዙ መሸታ መሸጥ ትልቅ ሰውና ጨዋ የሆነ እያፈረ እንዳይቀርብን በማለት በሠዋራ ቦታና በየመንደርም ውስጥ የሚሸጡ አሉ ። በመሸጫቸውም አቅራቢያ ያሉ ጐረቤቶች በመሸተኞች አምባጓሮና ጩኸት እንደሚታወኩ የታወቀ ነው።እነዚህ ሥራ ፈቶች ሴቶች እንደልባቸው ለመሆንና ገንዘብ ለመፈለግ ስለሆነ ሌላውን መናገር አያስፈልግም ብዙ ገንዘብና ጌጥ ያገኛሉ።ስለዚህ እነዚህኑ ሴቶች ያዩ ፩፩ የዋሃን የሆኑ የጨዋ ሚስቶች ከባሎቻቸው ባለመስማማት የተነሣ ከብዙ ጉዳት ይደርሳሉ ። ከንዱ ወዳንዱ ከሚተላለፈውም ደዌ ለመዳን አይቻላቸውምና ለሚወልዷቸውም ሕፃናት ደግ አይሆንም ። ተላላፊውም በሺታ ብዙ ሰው መጉዳቱ ለማንም አይሰተውም ሥራ ከመፍታት የተነሣ ነውና ሴቶች የመሸታ ጠጅ ለመሸጥ የሚደርሱት ። አቶ በቀለ ዘለቀ በ፷ተኛ ዓ ቀ. ፴፰ ፫፻፲፪ ገጽ ብርሃንና ሰላም ወንዱ ልፍታሽ ወይም ሴቷ ፍታኝ ባለች ጊዜ አልፈልግም ያለውን አንደኛቸውን ዳኛ መርምሮ እምቢ ያለውን ሰማንያ ቢያሰክፍል ይሻላል ብለው እንዳመለከቱት መስማት ብቻ ሳይሆን መደረግ እንዲከተለው እየደጋገምን ሕበለ ክፍል ሹሞች ብናስታውስ ክፉ አይመስለኝም አለ ወንድና ሴት ስለሚቀመጡ በ፩ወንድና ሴት ተወስኖ መኖርን በመጥላት ነውና ሀብታምና ድሐ ሳይለይ ከፍ ያለ የወር ግብር ቢደረግላቸው አይከፋቸውም።

ወተት መድኃኒት ነው ፥ ለሰውነት የሚስማማ ጤና የሚሰጥ ። አረቂ ሻጮች ከ፲- ፺ና ፪፻ ብር ድረስ ሱቅ እየተከራዩ ፩ ጠርሙስ አረቂ ካላድ እስከ ፫ ብር እየሸጡ ባለ ብዙ ገንዘብ መሆን ። ጠጅ ሻጮች ከ፲ እስከ ፳ና ፴ ብር ድረስ ሱቅ እየተከራዩ ፩ ጠርሙስ ጠጅ እስከ ሩብ እየሸጡ ። ባለ ብዙ ገንዘብ ለመሆን መድረስ ወተት ሻጮች እፀሐይና እዝናም ላይ እየሆኑ ፩ጠርሙስ ወተት በ፩ና ፪ መሐለቅ ይሸጣሉ እስከ ዚሁም የሚገዛ እያጡ እየዞሩ ገዥ የሚፈልጉበት ጊዜ አለ ። በጣም የሚገርም ነው ከቶ ማናቸው ለሕይወት ይስማሙ ይሆን?ቅቤስ የሚገኘው ከምን ይሆን? ሐኪሞችም ከሚከለክሉት ምግብ ሁሉ ለበሽተኞች ወተት እጅግም አይከለክሉ።

አረቄንና የመሸታን ጠጅ ባመጠጣት አለደዌ ጥቅም አገኘሁበት የሚል አይገኝም። ምሳ ምሽ ቀ.፩ ጠጅ ዋዛ ነው ስካርም መጃጃት ነው። ም ፳፫ ቀ. ፳፱ ወይታ ለማን ነው ሐዘን ለማን ነው ፀብ ለማን ነው ጩኸት ለማን ነው ያለምክንያት መቍሰል ለማን ነው፥ የዓይን ቅላት ለማን ነው ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን።

በንድአንድ አረቂ መሸጫ ስፍራ በጠረጴዛ ላይ ብርጭቆውን እየሞሉ ያንን እንደ እሳት የሚያቃጥል አረቂ እንደ ውሐ ይጠጡታል ። ከጥቂት ዓመት በፊት በ፩ የላምበ የጋዝ ታኒካ ነጭ አረቂ ከ፫ እስከ ፭ ብር ይሸጥ ነበረ ።ዛሬ እስከ ፲፯ ብር ደርሷል ። ፩ ፩ ከከተማ ውጭ የሚመጡ ሰዎች እነዚህን ፪ መጠጦች ከልክ በማሳለፍ ላታላዮች እየተመቹ እብዙ ጉዳት ያደርሳቸዋል ። በረቂና በመሸታ ጠጅ ምክንያት ስንቱ ወንድማችን በሳል ተጐድቷል ። ስንቱ ደም እየተፋ ከሞት ይደርሳል?። ስንቱ እየመነመነ በልዩ ልዩ ደዌ የተጐዳ ይገኝ ይሆን ስንቱን የጨዋ ልጅ ገና በሕፃንነት ወራቱ በየመንገድ ዳር እንደ ወጽመድ እየሆኑ ያበቱን ርስት ለመሸጥና እስከ ሞት አፋፍ ያደርሳሉ ። እንደኔ ከዚህ የበለጠ ጉዳት ያለ አይመስለኝም።

ወጭው ቲንሽ ጥቅሙ ትልቅ

እንደ አረቂና ደመሸታ ጠጅ ሻጭ ብዙ ያልሆኑ አልፎ አልፎ ባንዳንድ ስፍራ በቲናንሽ ሱቅ የሚነግዱ ዓረቦች ቢኖሩ

ንግዳቸው በኑ፡ቻይ።ሱክር፣ ክብሪት ማሙና ይህን የመሰለ ነው ከጥቂት ዓመት በፊት ይህን የመሰለ ለመግዛት እዋናው ገቢያ ድረስ ከኑስ ሰዓት እስከ ፩ሰዓት እየተሔደ ነበር፡፡ዛሬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ጊዜ ባቅራቢያችን እያገኘን ከብዙ ድካም ካረፍን ብዙ ቀን ሆነን ወጭው ቲንሽ ጥቅሙ ትልቅ ይህንን የመሰለ እያለ ጥቅም ለማይገኝበት አረቂና የመሸታ ጠጅ ገንዘባችን እያወጣን እብዙ ጉዳት መድረስ፣ ወተት መጠጣት ይመስል አረቂ መጠጣት በጣም ይገርማል ። ያረቂንና የመሸታን ጉዳት እናስብ እንመልከት ።

ኢሳ ምዕቀኗ፬ ወዮላቸው ጠጅ ለመጠጣት የሚበረቱ የሚያሰክረውንም ለመደባለቅ የሚጨክኑ ይላል ። ሰባኪው ከሰማይ በታች ላለው ነገር ሁሉ ጊዜ አለው እንዳለው ማለት ነው እንጂ የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ያረቂንና የመሸታ ጠጅን ጉዳት ተመልክተው ብዙ ጊዜ አስታውቀዋል። ይኸም መስማት ብቻ ሳይሆን ማድረግ እንዲከተለው ለአማካሪዎች ብናስታውስ አይነውርብንም ።

አረቂ ከውጭ እንዳይመጣና እዚህም እንዳይሠራ የመሸታም ጠጅ እንዳይሸጥ ቢከለከል ጉዳት ነው የሚል አይገኝም። በነዚህ ምክንያት የሚገኘው ገንዘብ ቢቀር መንግሥታችን አይጐዳም ፡ ጥቅሙ ሕዝቡ በጤና ቢኖር ነው።
የመሸታ ጠጅና አረቂ ቢቀር ወስላታ ይታገሣል እንጂ አይጐዳም።ስለዚሁም ነገር የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ዘወትር አስበውቡታልና ፍሬና ገለባውን ሳይለዩት ይቀራሉ ብዬ አሳስብምና ደስ ይለኛል።ለሐሳባችን መገናኛ ብርሃንና ሰላምን ላቆሙልን ለብርሃናዊው ንጉሣችን ረጅሙን ዕድሜ ከልዑል እግዚአብሔር እየተመኘን ለሕይወታችንና ለመልካሙ አናንዋራችንም ሌት ከቀን ለሚጥሩልን አስተዋዩ ቸር ርኅሩኅ ንጉሣችን በመሰለንና በተቻለን ዕውቀታችን ብናስታውስ ክፉ አይመስለኝምና ምናልባት ስሕተት ቢገኝ ከአንባቢዎች ይቅርታ እለምናለሁ።

ጌታቸው ቀንድቤ ።

የቤተ ክርስቲያን በዓል አከባበር ።

በጥቅምት ፭ ቀን የአቡነ ገብረ ሕይወት በዓል ነበር።ጃንሆይና እቴጌ፥ ጳጳሳትና መኳንንት ወይዛዝር ወደ አቡነ ገብረ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ነበር።በ፬ሰዓት ተኩል ዑደት ተጀመረና ካህናቱ እየዘመሩ ዑደቱ ከተፈጸመ በኋላ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ መርቀው አሳርገው ሕዝቡን አሰናበቱ ።

የኦፊሲዬል ማስታወቂያ።

ማዳም ኤርቲል ወደ ግርማዊት እቴጌ መነን ለመግባት ለሚፈቀድላቸው የውጭ አገር ወይዛዝሮች ባልደረባ ሆነው ተሾመዋልና ወደ ግርማዊት እቴጌ መነን ለመግባት የሚፈልጉ የውጭ አገር ወይዛዝሮች በቀጥታ ለማዳም ኤርቲል እያስታወቁ ሲፈቀድላቸው የቀጠሮውን ቀንና ሰዓት ለመቀበል ይችላሉ ።

የሌጋሲዮን ወይዛዝሮች ግን በቀጥታ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሺፍፕሮቶኮል እያስታወቁ የሺፍፕሮቶኮሉ የቀጠሮውን ቀንና ሰዓት እየተቀበለ ያስታውቃቸዋል ።

A V I S O F F I C I E L

Madame HAERTE3 ayant été nommée Dame d'Honneur de Sa Majesté l'Impératrice MANEN, toutes les dames étrangéres qui d'sireraient solliciter l'autorisation d'étre admises à l'audience de Sa Majesté l'impératrice, devront s'adresser directement à Madame Haertel pour faire fixer le jour et l'heure de l'audience.

En ce qui concerne les Légations, les dames desireuses d'être reçues par Sa Majesté l'impératrice devront s'adresser directement au Chef du Protocole, au Ministère des Affaires Etrangères, qui se chargera de leur indiquer le jour et l'heure de l'audience.

መልእክት ።

ይድረስ ለክብርት የሀገር ፍቅርን ተመልካቿ ለታላቁ ማዕርግሽ የተገባ ሰላም ላንች ይሁን። አቅራቢሽንም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን እግዚአብሔር ያሰንብትልሽ ።

ከዚህ ቀጥዬ አንድ የሚሳዝነኝን ነገር አይቼ ስለጻፍሁ ልሽ እንዳልነቀፍ እለምናለሁ ። ብዙዎች በጽሕፈት በቋንቋም በገር ፍቅርም በንግግርም በማናቸውም ነገር ቢሆን የብዙውን ሰዎች ሐሳብ በየገጾርናሉ ስንመለከተው እጅግ መልካም ነበር ዳሩ ግን እነዚህንም እውቀት ያላቸውን ያገር ፍቅር ያደረባቸውን ጀግኖች ስንመለከታቸው ብዙ ጊዜ ሐሳባቸውን በገዞርናል የገለጡ ሁሉ ሐሳባቸው ስላልተፈጸመላቸው ልባቸው ሁሉን ሲአውቀው ለማድረግ አልቻሉምና ብስጭታቸው በከተማ ውስጥ ይታያል። እነዚሁም ሰዎች ሐሳበ ትጉሆች፣ ነገረ ጣፋጮች መሆናቸውን ብርሃንና ሰላም በእስታስቲክ ሊያወጣቸው ይችል ይመስለኛል ።

ለማስረጃ ሳይበዛ ባጭሩ ከቅርብ ቀን ስንኳን ወዲህ ብዙዎች ጕበዛዝት ሥልጣኔ እንዲሰፋ፡ወታደር እንዲያሰፋ፡ወይዛዝሩ ሥልጣኔን እንዲገፉ፡ሕፃናቱ እንዲፋፉ እያሉ ስንቱን የሥልጣኔ አነጋገር እንደጻፉ ብርሃንና ሰላም ነግሮናል ። እንግዲህ ብዙ እውቀተኞች ብልሆች ሁሉ በብርሃንና ሰላም የተናገሩትን ሁሉ ከመጀመሪያው ዓመት ጀምሮ እስከሁን ድረስ ያሉትን ብልሆችን ስማቸውን የብርሃንና ሰላም ዲሬክተር ከብርሃን ማተሚያ አውጥተው ለሕዝብ ቢገልጡለት ለንጉሡ ደስታ፣ ለሕዝቡ የውቀት ብልጭታ፣ ለሕፃናቱ ተግታ እየሆነ ሀለም በብርታት ይኖሩ ነበር። ስንፍና የሚባለውም ሸክም እየቀለለ ሚሔዱን ለክብርት እመቤቴ ለሀገር ፍቅር በማክበር አመለክትሻለሁ ይላል ታዛዥ አክባሪሽ ።

በቀለ ዘለቀ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማየትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በተመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። ብሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፣ የደረት፣ የጕበት፣ የኵላሊት ፤ የጅማት፣ የጨብጥ፣ የቂጥኝና፣ የቋቋ፣የሚያዋልድ፣ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፣ የርሻ የፋብሪካ፣ የደን፣ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዠና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም

ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗኳላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከታማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK-METAΞA

ከሚሠራው ኩኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኩኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፫ 6me ANNÉE № 43		ሐሙስ ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም። JEUDI 23 OCTOBRE 1930

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጻዚት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

አይሮፕላን

ክቡር ዳጃዝማች እምሩ የወሎ እንደራሴ የዘውዱን በዓል ለማክበር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡ ስለተፈቀደላቸው ሁለተኛውም ሹም ቀኛዝማች ፍቅረማርያም ለሥራ ተጠርተው አዲስ አበባ ነበሩና በደጃዝማች ምትክ ሁነው አገሩን እንዲጠብቁ ታዘዙ ። በበቅሎና በፈረስ ለመሔድ ፯ ፰ ቀን የሚያቈይ ስለ ሆነ በአይሮፕላን እንዲሔዱ ታዝዘው በጥቅምት ፰ ቀን ከጧቱ በ፲፪ሰዓት ከአዲስ አበባ ተነሥተው ፫ሰዓት ያህል ሲሆን ደሴ ገብተው ሠራዊቱ በክብር ተቀበልዋቸው ። በችኰላ ቀን ምነው ክንፍ በነበረኝ ይባል የነበረው ምኞት ዛሬ ደረሰ።

የከተማ ወሬ ።

ልዕልት ፀሐይ (የሺመቤት) ኀይለ ሥላሴ ።
ቢትወደድ ጌታቸው አባተ።
የብላቴን ጌታ ኅሩይ ልጅ።
የደጃዝማች እምሩ ልጅ።

ልጅ መልአኩ በያን በልዩ ብቡር በጥቅምት ፲ቀን ማታ ከሮም አዲስ አበባ ገቡ፡በደኅና በመግባታቸው እጅግ ደስ ብሎናል።

በፊተኛው ብርሃንና ሰላም እንደአስታወቅነው የዘውዱን በዓል ለማክበር እንዲመጡ ተፈቅዶላቸው ክቡር ደጃዝማች ብሩ በጥቅምት ፲፪ ቀን አዲስ አበባ ገቡ።

ሁለተኛ የከተማ ወሬ ።

ቀድሞ እንዳስታወቅነው የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን የዘውድ በዓል ለማክበር ይመጣሉ ከልናቸው የመንግሥታት መልእክተኞች።

የአሜሪካና የጀርመን፡የዮናኒ (የግሪክ) መልእክተኞች በጥቅምት ፲፩ ቀን በ፤ ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ። እንግዶቹንም ለመቀበል ታዝዘው በባቡር መቋሚያ ይጠባበቁ የነበሩት መኳንን ት ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ።

፩ኛ፡ ልዑል አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ።

፪ኛ፡ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ ።

፫ና፡ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ያግር ግዛት ሚኒስቴር ።

፬ኛ፡ ደጃዝማች መኰንን ደምሰው ።

፭ኛ፡ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ።

፮ኛ፡ ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ ነበሩ ።

ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤልም እንግዶቹን ከድሬ ደዋ ተቀብለው አብረው መጥተው ነበር ። ሌሎችም ስማቸው ያልተጻፈ ብዙ መኳንንት ነበሩ።ደግሞ ከቤልጅግ የመጡ ሰልፍ አስተማሪዎች ማጆር ፖሊ፡ ካፒቴን ፋኑኤል ፡ ካፒቴን ሲስተ ርማን፡ሌትና ዣንዳርም ፡ የትና ዋክኤር መልክም አድርገው ሰልፍ የተማሩ ጥሩ ጥሩ የወታደር ልብስ የለበሱ ብዙ የኢ ትዮጵያ ወታደሮች ግራና ቀኝ አሰልፈው አለቆቻቸው የአን በሳ ጋማ ያለበት መለዮ በራሳቸው አድርገው ሰይፋቸውን መዝዘው መዝዘው ቆመው በሥዕል ያየናቸውን መላእክት ይመስሉ ነበር ። ይልቁንም የሺ አለቃቸው ባላምባራስ መኰሸ ጥንቱንም ከተፈጥሮው ባለግርማ ነውና ባለ አንበሳ መለዮውን በራሱ አድርጎ ሰይፉን መዝዞ ሲታይ ያንቀጠቅጥ ነበር ። ገና ባቡሩ ሲቆም ከስዊስ የመጡ ሙዚቃ አስተማሪው ሙሴ ኒኮ እየመሩዋቸው የሾገሌ ጉብዛዝት ደስ የሚያሰኝ ሙዚቃ ይነፉ ነበር። ልዑል አስፋ ወሰንና መኳንንቱም በመጀመሪ የአሜሪካን መንግሥት መልእክተኛ ተቀብለው ከማክበር ሰላምታ በኋላ የአሜሪካን ማርሽ ሲነፉ ጸጥ ብለው ቆመው ቈይተው ለማረ ፊያ ወደተሰናዳው ቦታ ይዘዋቸው ገቡ። ቀጥለው የጀርመንን መንግሥት መልእክተኛ ተቀብለው ከማክበር ሰላምታ በኋላ እንዲሁ የጀርመን ማርሽ ከተነፋ በኋላ ለማረፊያ ወደ ተሰና ዳው ቦታ ይዘዋቸው ገቡ።ቀጥለው የዮናኒን(የግሪክን)መንግሥት መልእክተኛ እንዲሁ እንዳለፈው የግሪክ ማርሽ ከተነፋ በኋላ ተቀብለው ለማረፊያ ወደ ተሰናዳው ቦታ ይዘዋቸው ሲገቡ ጳጳሱና ብዙ የሀገራቸው ሕዝብ ነበሩና ጭብጨባውን አደመ ቁላቸው ። ከዚህ በኋላ የአሜሪካ መንግሥት መልእክተኛና ባልደረባቸው የሀገር ግዛት ሚኒስቴር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ አስተርጓሚውን አቶ ተስፋዬ ተገኝን ጨምረው በአንድ አቶ ሞቢል ተሳፍረው ሔዱ ።

ቀጥለው የጀርመን መንግሥት መልእክተኛና ባልደረባቸው ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ አስተርጓሚውን አቶ ወልደ ጊዮርጊስን ጨምረው በአንድ አቶሞቢል ተሳፍረው ሔዱ ። ቀጥለው የዮናኒ (የግሪክ) መንግሥት መልእክተኛና ባልደረባቸው ደጃዝማች መኰንን ደምሰው ከቆንስሉ ከዶክተር ዘርቦስ ጋራ በአንድ አቶሞቢል ተሳፍረው ሔዱ ። ልዑል አስፋ ወሰንም ቆመው እንግዶቹን ከአሳፈሩ በኋላ በአቶሞቢላቸው ተሳፍረው ሔዱ ። የቀሩትም መኳንንት እንዲሁ በየአቶሞ ቢላቸው እየተሳፈሩ ተከተሉ ። ሰልፍ የተማረው እግረኛና ፈረሰኛው ወታደር በመንገዱ ግራና ቀኝ ተሰልፎ ሲያዩት እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ። የአቶሞቢሉም ብዛት መንገድ አል በቃው ብሎ እጅግ ተቸግረን ነበር ። የንጉሣችንን የዘውድ በዓል ለማክበር ስለመጡ ሕዝቡ ደስ ብሎት በየመንገዱ ዳር ቁሞ እንግዶቹን ይመለከት ነበር ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹን ባልደረቦቻቸው እየመሩዋቸው በየተሰናዳላቸው ቦታ ገቡ ። የቀሩትም እንግዶቻችን በደኅና ገብተው ልን ከደገኛዪቱም ቀን ደኅና አድርሰን እጅግ ደስ የሚአሰኛችሁን ወሬ እንድንጽፍ ላችሁ ተስፋ እናደርጋለን ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ዕረፍት ።

ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ የደጃዝማች ባርያ ጋብር ልጅ የትግሬ ባላባት ናቸው።ደጃዝማች ባርያ ጋብርም ያፄ ቴዎድሮስ ባለሟል ነበሩ።ደጃዝማች ገብረ ሥላሴም በሺ ፰፻፵፯ ዓ ም ጥቅምት ፲፬ ቀን ተወለዱ።በሺ ፰፻፶፩ ዓ ም ታላቅ ወንድማ ቸው ፊታውራሪ ደባልቀው ወደ ምጥዋ ሰደዋቸው ከዚያው የኢጣልያ ቋንቋ ተምረው ወደ አገራቸው ተመለሱ፡ጃንሆይ አፄ ምኒልክም ባፄ ቴዎድሮስ ቤት ካባታቸው ከደጃዝማች ባርያ ጋብር ጋር ወዳጅ ነበሩና አስፈልገው አስጠሩዋቸው።እሳቸውም ከሉበት ሁነው ወዳጃንሆይ ይላላኩ ነበር ። ልዑል ራስ መንገሻ ወደሸዋ በመጡ ጊዜ ልዑል ራስ መኰንን ትግሬን ሲሾሙ ዕውቀት ያላቸው ብልሀና አገራቸውን አፍቃሪ መሆናቸውን አይተው ከመረብና ወር፡ ተከዜ ምላሽ አገር ጠብቅ ብለው ስጥተዋቸው ሔዱ።በኋላም ለጃንሆይ አስታውቀው ሾሙዋቸው በሺ ፰፻፺፪ ዓ ም ጃንሆይ አፄ ምኒልክ አዲስ ዓለምን ሲቈረቍሩ መጥተው ተገናኝተው በክብሬታ ተቀበሏቸው ። ኋላም ብልሀነታቸውንና ቁም ነገራምነታቸውን አይተው በዓድዋላይ ሺሬን ጨምረው ባዋጅ ሹመው ሰደዱዋቸው ። ከዚህም በኋላ ድጎ በመጠበቅና ሽፍታ በማጥፋት ደስ ስላሰኙዋቸው ባድዋና በሺሬ ላይ ንቡረ እድ ዘአክሱም ብለው ሾሙዋቸው ። ቀጥ ለው ዓድዋና አክሱምን፡ሺሬን፡ሁለት በለሳን፡አጋሜን፡እምበራና መጠቃን ተሾሙ ። ኋላ ግን በልጅ ኢያሱ ጊዜ በአምባጓሮ ተጣልተው ጦርነት ስላደረጉ ራጋይሌ ከሚባል በረሃ ተቀም-

ጠው ነበረ ። ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በነገሡ ጊዜ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ሲባሉ ምሕረት አድርገውላቸው ወደ አዲስ አበባ ገብተው ከቀድሞው የበለጠ ባለሟልና አማካሪ ሁነው ነበር ። ጥንት የሚገዙት የነበረውን አገራቸውን ዓድዋና አክሱምን ተሹመው ነበር። በኋላም በጥቂት ነገር ተጣዘው ሚጫ ከጣዘታቸው አንድ ዓመት ከመንፈቅ ተቀምጠው ተምረው ገብተው በድንገተኛ በሽታ ታመው ጥቅምት ፪ ቀን በ፲ ፱፻፳፫ ዓ በተወለዱ በ፶፯ ዓመታቸው ዓርፈው በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ። ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ አባ ክበድ ይጣናው አገራቸውን አፍቃሪ፥ መንግሥታቸውን አክባሪ፥ ሕዝባቸውን ጠባቂ፥ ወገናቸውን ወዳጅ የዱሮ ታሪክ መርማሪ ነበሩ ። በሕይወታቸውም ሳሉ የሠሩዋቸውን ሥራዎች ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን ።

መጀመሪያ ከአክሱም በየደንጊያ ሐወልት ላይ የተጻፉትን የዱሮን ታሪኮች ከጀርመን አገር የኢትዮጵያን ታሪክ የጥንቱን ሁሉ የሚያውቁ ፕሮፌሶር ሊትማን የሚባሉትን በጃንሆይ ፈቃድ አስመጥተው በደንጊያ ሐውልት የተጻፉትን ሁሉ እያስመረመሩ ፬ሺ ፰፻፺፰ ዓመት የቀዳማዊ ምኒልክን ዓፅም አውጥተው ወደ ዳግማዊ ምኒልክ የምስራች ያ...ተዎን የቀዳማዊ ምኒልክን ዓፅም አግኝቼ አወጣሁ ብለው ቢልኩባቸው ልጄ እግዚአብሔር ይባርክህ ይህስ በኛ ጊዜ ሊገለጽ የማይቻለውን አንተ አገኘህ ይህ ለበቁ ለደጋግ ሰዎች ይገለጽላቸው ነበር እንጂ ዛሬ መገኘቱ በጣም ያስደንቃል ብለው ደስ ብሎዋቸው ሽልማትና ኒሻን ላኩላቸው ።

፪ኛም ያፄ ካሌብና ያፄ ገብረ መስቀልን መቃብር አፈር ውጦት፥ ማር ፀቅሎበት የነበረውን ሕንፃ አስጠርገው አስቈፍረው ብዙ ምልክትና ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆን ነገርአወጡ።

የጀርመኑም ሊቅ ፕሮፌሶር ሊትማንም ወደ አገራቸው ተመልሰው ለመንግሥታቸው ነግረው ለሳቸው የሚገባቸውን ኒሻን ሽልማት በጃንሆይ በኩል አድርገው ሰደዱላቸው ።

፫ኛም ተሰባብረው ከቀሩት ከጥንት ሐውልቶች አንዱን በኖራና በስሚንቶ አድርገው እግርጌውን አሳደለደሉት ።

፬ኛም ፡ ያክሱም ቤተ ክርስቲያን አርጅቶ የነበረውን አፍርሰው ከቀድሞ የበለጠ አድርገው አድሰው አሠሩት ።

፭ኛም በጃንሆይ አፄ ምኒልክ ስም ትልቅ ቤተ መንግሥት አሠሩ ።

፮ኛ ከአክሱም ወራጅ ውኃና ምንጭ ስለሌለው የከተማው ሕዝብ የኵሬ ውኃ ነበር የሚጠጣው፥ ያውም ዓመት እስከ ዓመት አያጠጣውም ነበር ። የሕዝቡን መቸገር አይተው በአሽከሮቻቸውና በገንዘባቸው በሕዝቡ ሳይሆን ፊት የነበረውን ኵሬ አፍርሰው ከፊተኛው ኵሬ ሁለት እጅ ጨምረው አስቈፍረው በኖራና በስሚንቶ አሠሩት ።

ደግሞም ደግነታቸውና ቁም ነገረኛነታቸው ሊታወቅ በነበሩበት ዘመን ባሉት ነገሥታት ሁሉ ለትልቁም ለትንሹም፥ለሀብታሙም ለድኻውም አማላጅ ሁነው ያሾሙና ያሸለሙ ነበረ ። ቅጣትና እሥራት ያገኘውንም እያማለዱ ያስፈቱትና ያስማሩት እጅግ ብዙ ነው።

በተቀበሩም ጊዜ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እቴጌ መነን፥ የኢትዮጵያ ጳጳሳትና መኳንንት ብዙ የውጭ አገር ሰዎችም ተሰብስበው እየተለቀሰ ብዙ ፍታት እየተፈታ ነጋሪት እየተመታ መለከትና ጥሩምባ እምቢልታ እየተነፋ በማዕርግ ተቀበሩ ። ግብአተ መሬቱም ሲሆን ጳጳሳቱ ገብተው ባርከው ወጡ ። ስለልቅሶውም ጃንሆይና እቴጌ፥መኳንንቱም ሁሉ እጅግ አድርገው ሲያለቅሱላቸው ዋሉ ። ክብርት ባለቤታቸውም ወይዘሮ ወለተ እስራኤል ሥዩም አባቴ አባቴ አሳዳጊዬ እያሉ ሲያለቅሱ ሕዝቡ በንባ ሲራጭ ዋለ ። አሽከሮቻቸውም መሣሪያቸውንና የኢትዮጵያ የክብር ኒሻናቸውን የውጭ አገርም ነገሥታት የሰጧቸውን ኒሻን ይዘው ሲላቀሱ ያዩ ዓለምን አያስመኝም ። ግ አ የ ።

ስለ ክቡር ደጃዝማች ገብረ ሥላሴ ዕረፍት የልቅሶ ዜማ።

ማለፊያውን መውዜር ከቤትህ ትተህ ፥
ማለፊያውን ጐፈር ከቤት ትተህ፥
ማለፊያውን ኒሻን ከቤትህ ትተህ
ምን ይረባኝ ብለህ መርገፉን ወደድህ
እኛስ የምንወደው የኒሻኑን ጌጥ ነው
እኛስ የምንወደው የጐፈሩን ጌጥ ነው
ይቅርብህ መርገፉ ያባትህ ጠላት ነው
ሰማይ አዘነልህ ጭጋጉን ደርቦ ።
የቀስቱን ባንዴራ ፀሐይ ተከናንቦ
ኮከቡም ቢጨንቀው የምድሩ ጭኸት
ያለጊዜው ታዬ በ፷ ሰዓት
ለጎጃም መኳንንት ሲያማልድ ተንገሡ
ለጐንደር መኳንንት ሲያማልድ ተንገሡ
ለሸዋ ደጅ ጠኒ ሲነግር ለንጉሡ
የትግሬ ጠበቃው ተቀበረ ዋሱ
አፌ አትናገሪ አርምሚ መላሴ
አሙስ በማለዳ ተቀበረ ዋሴ
ጌታዬን ከልፍኙ እፈልገዋለሁ
ከተማሰው ገብቶ የት አገኜዋለሁ
አባ ክበድ ገብሩ ኵሩ ነው ሲሉኝ
የገዛ ዘመዱን አንጀቴን በላኝ
እስቲ ሥጋ ስጡኝ በቅመም ተጠብሶ
የጌታማ ሞቱ ይመራል ተኮሶ ።
ቢጠይቁኝ ወሬ ምን ብዬ ልናገር
መንግሥቱን ያጠናል ያባ ክበድ ምክር
ተጽፎ አገኘሁት ስሙ በመቃብር
ልጽፈው አልችልም ያንተንስ ምስጋና
አጥፌ አስቀመጥሁት እንዲያው በደፈና
የይርጋ ወይዘሮ የክበድ ሙሽራ
ወለተ እስራኤል ልብሽ እንዳይፈራ
መጽደቁን አይተናል በፀሐይ ባንዴራ
ፈረንጅ ተደነቀ አረብ አስታማራ

ንግሥት ዘውዲቱ ዓፀቡ ቢያንሳቸው
ጌታዬን አስጠሩት በጀወራቸው
ምን ይረባኝ ብለው በሰማይ አሽከር
መገናኘት የለ አይረዳ በምክር
ሺ ብረት ከፊቱ የሚደባለቀው
የዳሞትን መንገድ ብቻውን ዘለቀው
እኔን የጨነቀኝ ማነን ልጠይቀው
በዚያ በሚያስፈራው በዳሞት በረሀ ።
ብቻውን ተጓዘ ስንቁን ይዞ ውሀ
ምሥጢሩን ሳናውቀው ዘመቻ ተጠርቶ
በጎነኝ እያለ ሽንጡ ላይ ተውጣቶ
ጃንሆይና እቴጌ ምነው አሉ ዝም
ምሥጢርዎን ይዞ ሲገባ ገዳም
የጌታዬ አሽከሮች ከሜዳ ፈሰሱ
ዕንባ ቢያልቅባቸው ደም እያለቀሱ
ጌታዬ አሽከሮችህ እንዳዲህ ደረፉ
ወርከው ከወደቀ ተበተነ ዖፉ

ሰቆቃው ወበከይ ዘሊበን ዋልታው ዓጋሜ ።

ያንድ ኢትዮጵያዊና ኤሮፓዊ ጭውውት

(ኢ.ት)እንዴት ሰነበቱ ጌታው ከተያዬን ብዙ ቀን ሆነን ወደ እገርዎ ሒደው ኑሯልን ?

(ኢ.ሮ)የተወደዱ ወዳጄ እንዴት ነዎት ወደሮፓ ሒጄ ተመ-ለስሁ እርስዎ ሰውነትዎ እጅግ አምሮ አገኘሁዎት ለጤንነትዎ ሐኪም አገኙን ?

(ኢ.ት)በሐኪም አይደለም ሰውነቴ ያማረው ቸርነቱ የማ-ያልቅበት አምላክ አገሬ ኢትዮጵያ በፈለቀው ጠበል ታክሜ እንደበልንጀሮቼ ለመሆን በቃሁ ።

(ኤሮ) ይህስ እውነት ነው ያገር ነፋስና ያገር ጠበል ተሐኪም ይበልጣል።እኔም ወደ ኤሮፓ የሔድኩት ያገሬን ነፋስ ተቀብዬ ለመመለስ ነው ።

(ኢ.ት)ጌታው አገራችን ከመጡ ስንት ዘመንዎ ነው ስንትስ ጊዜ አገርዎ ሒደው ተመለሱ ?

(ኤሮ)፳፰ ዓመት ይሆነኛል ወደ አገሬም ሦስት ጊዜ ሒጄ ተመለስሁ መጀመሪያ የመጣሁ ጊዜ የምድር ባቡር ጣቢያ አዲጋላ ላይ ነበር ። ከዚያ ወደ አዲስ አበባ የመድረሴን ነገር ባሰብኩት ጊዜ ተጨንቄ ምነው ታገሬ ምን አቅብጦ አመጣኝ እያልሁ ሳስብ ለዕቃዬ መጫኛ ብዙ ግመሎች፣ ለኔም መቀመጫ በቅሎ ኪራይ አግኝቼ ስጓዝ አዲስ አበባ ደረስሁ የዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ከአምስት የሚበልጥ የቈርቆሮ ክዳን ቤት አልነበረም።መንገድም ምንም አልተሠራም የኪራይ ቤት አን-ድም እንኳ አይገኝም ነበር። በክረምት ወራት ያዲስ አበባ መንገድ ከ፴ሳንቲ ሜትር የሚበልጥ የጭቃ ማጥ ያጠልቅ ነበር ። በዳግማዊ ምኒልክ ብርታት መንገድ መሠራት ተጀመረ ፩ የተማሪ ቤት ተከፈተ የሥልጣኔ ሥራ እንደጀመሩ አፄ ምኒልክ ከቤት ቢውሉ የሥራቸው ውጥን ተቋርጦ ቈዩ ፲፱፻፰ ዓ ም የምድር ባቡር አቃቂ ደርሶ ነበርና ከዚያ ተሳፍሬ አገሬ ሔድሁ፤ ያፄ ምኒልክን ዕረፍት ከዚያው ሰማን ካፄ ምኒልክ ወዲህ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ሁና ትኖራለች አይመስለንም ነበር አልጋ ከተዛወረ ወዲህ በ፲፱፻፲፬ ዓም ተመልሼ ብመጣ አዲስ አበባ አዲስ አዲስ የሥልጣኔ ሥራ ተሠርቶ የከተማው መንገድ በያለበት ተሠርቶ በየሁ ጊዜ ኧእንዳዲህ ወዲህ ተስፋ የላትም ያልናት ኢትዮጵያ ዕድሏ ብልህ ትጉ አልጋ ወራሻ ሰጥቷት በሥልጣኔ መራመድ ጀመረች እያልሁ እያመሰገንሁ እከተማ መሐል ደረስኩ የሆቴል ቤት አማርጬ ገብቼ ካረ-ፍሁ በኋላ መጀመሪያ በመጣሁ ጊዜ እንኳንስ ሆቴል የቤት ኪራይ አጥቼ በእንግድነት ያደርሁት ቀን ትዝ ስላለኝ ምስ-ጋናዬ የበለጠ ሆነ። ማጣሥቱም ቤት መርጬ ተከራዬሁ ወደ ቆንስሌ ቤት ስሔድ ማጡ እቅልጥም ይደርስ የነበረው ጕዳና ያማረ መንገድ ተሠርቶበት ግራ ቀኙም ዳኅና ዳኅና የቆርቆሮ ክዳን ቤት ፍንትው ፍንትው ብሎ አየሁ፤ያገሩንም የቢሮ ሥራ አካሔድ ብመለከተው የሥልጣኔ ሥራ ተስፋፍቶ ምኒስቴሮች ቀድሞ ባንድ ቤት ተሰብስበው ይሠሩ የነበሩት ለየራሳቸው የምኒስቴር ቢሮ ከፍተው በሠለጠኑ በብዙ ጸሐፊዎች ሥራ ጀምረው ሲሠራ አየሁ። ይህም እንደተጀመረ ጃንሆይ ባልጋ ወራሽነታቸው ዘመን መሳፍንቶቻቸውንና መኳንንቶቻቸውን አስከትለው ወደኤሮፓ ነገሥታት ከተሞች ሲሔዱ የተከተሏቸው መሳፍንቶቻቸውና መኳንንቶቻቸው በጥቂት ወራት እንደ ብዙ ዓመታት ትምህርት የሥልጣኔን ጥቅም እንዲረዱት አድርጓ-ቸዋል፤ ስለምን ከመስማት ማዬት ይበልጣልና ነው ኤሮፓ-ዎች የኢትዮጵያን አልጋ ወራሽ ባይናቸው ካይዋቸው ወዲህ ጃንሆይ ተመልሰው የሠሩትን የሥልጣኔ ሥራ በጋዜታ የሚ-ጻፈውን ለማንበብ እንደሚቻኰሉ የሚአውቁኝ ሁሉ ወሬ ጻፍልን እያሉ ይጽፉልኝ ነበር።አሁን በቅርቡ ጊዜ ወደ ሀገሬ ሒጄ ነበርና ያየሁትንም የሰማሁትንም የኢትዮጵያን የሥልጣኔ እርምጃ ሳወጋቸው በመደነቅ እየመላለሱ ይጠይቁኝ ነበር እኔም አሁን እንደተጫወትነው ቃል እየመላለስሁ አወጋኋቸው ።

(ኢ.ት) ጌታው ሆይ የዛሬ ዕለት የውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ ያሰማችኝ ቀን በመሆንዎ የተቀደሰች ትሁን ላስተኞች እውነተኞችን ምስክሮች የሚሰጥ አምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰው እርስዎን የሚአህል የተማረ ሰው ታሪክ ለመጻፍ የማይቦዝን ስለ ሆነ የኢትዮጵያን የውነተኛውን ታሪክ ሳይ-ጽፉት አይቀሩምና አሁን እኔ ተቃልዎ ሰምቼ ደስ እንዳለኝ የዚያን ታሪክ መጻፍ ገዝተው የሚአነቡ ደስታቸው እንዴት የተስፋፋ ይሆን ይህን ማለቴ የኢትዮጵያን ታሪክ የጻፉ ብዙ ሰዎች ናቸው እንዲህ አሁን እርስዎ በየዘመኑ የሆነውን ነገር አስተካክለው ስለነገሩኝ የማውቀውን ነገር ስለ አወጉኝ ሕፃን ሁኜ የማላውቀውም ነገር ልክ የሆነ ነው ብዬ በማመን ነው። የኢትዮጵያን የሥልጣኔ ሥራ በጣም የመሻሻሏን የሚያውቁት

እንደርስም እስተማችን ብዙ ዓመት የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች ምንም ቢአውቁት ለጊዜው መጥተው በቶሎ የሚሔዱ ሁሉ በሮፓ ዓይን ኢትዮጵያ የሥልጣኔዋ ደረጃ ባገር ሥርዓትና በወታደር ሥልጣኔ ሥራ (ሲቪልና ሚሊቴር) ከዚያ እስከዚህ መድረሷን ተረድተው በጣም ምስጋና ለመስጠት ይቀርታ ይገባቸው ይሆንን ?

(ኤሮ)ቅር ለሚላቸው ሰዎች እኛ ነባሮቹ የጻፍነው እንዳነበቡት በቃላችን የምናወጋቸው ያስረዳቸዋል ኢትዮጵያ እጁዋን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታለች የተባላውን ቃል ዘበት አድርገው ነበር፤እጁዋን ወደአምላኳ በመዘርጋቷ ትጉህ አሠልጣኝ ቸር መሐሪ ኃያል ንጉሠ ነገሥት ተቀበለች ዕድሏ ከፍ ከፍ የሚል ኢትዮጵያ ጃንሆይ በንጉሥነታቸው የተሠራው ብዙ ሲበልጥ በንጉሠ ነገሥትነታቸው ዙፋኑን ከተቀመጡ እስከሁን እንደሚሠራው ባልጋ ወራሽነታቸው ቀን ጀምሮ ተሠርቶ ቢሆን ጃፖን የሥልጣኔ ሥራ ጀምራ ትራመድ በነበረው ፴ ዓመት ኢትዮጵያ ትደርስ ነበረች።እግዚአብሔር አገሪቱንም ሕዝቡንም ሲባርክ ይህን የመሰለ እንደራሴውን ልኳልና እናንት ኢትዮጵያውያን ደስ ይበላችሁ ።

(ኢ.ት)ጌታዬ ሆይ በባዕድ አንደበት መመስገን ከባት ምርቃን ይበልጣልና የርስዎን ለመስማት ነው እንጂ እስካሁን የቈዩሁት የሥራ ጊዜያቴ ነውና ሳይረፍድብኝ ሔድኩ ብሏቸው የሥልጣኔ አምላክ ይጠብቅህ ብለውት ወደሥራው ሲሔድ አየሁ ።

ማህሉ ጽጌ ።

የሚያስገርም የእግዚአብሔር ስነ ፍጥረት።

አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ታላቁን እስክንድርን ቀንድ ነበረው እያሉ የጻፉ ሰዎች አሉ፤ ነገር ግን ያሞገሱትና ያከበሩት እየመሰላቸው ነው እንጂ እስክንድር ምንም ቀንድ እንዳልነበረው አስረድተው ዳግሞ የጻፉ ብዙ ሰዎች አሉ፤አሁን ግን እውነት ያይደለውን የእስክድርን ማዕርግ የሚቃወም ስለ እርግጠኛው ሺህ ፎሻንጂ የሚባል ሁለት ቀንዶች ያሉት የሺን ሰው ከሀያ ዓመት ጀምሮ የዚህን ሰው ወሬ የሚሰሙ ሰዎች ሁሉ አያምኑም ነበር፤ አሁን በቅርብ ጊዜ አንድ የተማረ የመስኮብ (የሩሲያ) ሰው ደህና ሰው ባይኑ አይቶ እርግጡን ለመረዳት ወደ ሺን አገር ሔደ፥ ይኸውም ፎሻንጂ የሚኖርበት አገር ዓለምን ከማያውቁ እነሱንም ሰው ከማያውቃቸው በብዙ ትልልቅ ተራሮች ከተከበበ ባላገሮች ጋራ ነው፤ ጥቂት የከተማና የውጭ አገር ባህል ካለባቸው ከተሞች (መንደሮች) ሰላሳ ኪሎ ሜትር ይርቃል፤ ይህም የመስኮብ ሰው፥ ፎሻንጂ ያለበትን እየፈለገ ካለበት ደርሶ በጭቃ ብቻ ከተሠራው ቤት ፎሻንጂ እንግድነት ተቀብሎት ሻይም ጠጡና ከዚያ በኋላ ፎሻንጂ ጨዋታ ጀመረ፤ አንዳንድ ጊዜ ከቤቱ ወጥቶ በቅርብ ካሉት መንደሮች ለመናፈስ ሲሔድ በዚያ መንደር ያሉ ሰዎች ሁሉ እየሸሹ በቤታቸው ውስጥ ይደበቃሉ፤ የሚሸሽጉበትን ምሥጢር አያውቅም ብሎ ነገረው ፤ መስኮቡም መለሰ ከኔ ጋራ ወደ ኢሮፓና ወደ አሜሪካ ብትሔድ ሰውነትህን በማሳየት ብዙ ለቍጥር የሚያስቸግር ገንዘብ ሰብስበህ ወደ ሀገርህ ትመለስ ነበር ቢለው። ፎሻንጂም በነገሩ አስባለሁ አለ። ከዚህም በኋላ ቀንዶቹን መለከት ጀመረ እያንዳንዱ ርዝመታቸው ሰላሳ አምስት ሴንቲ ሜትር ያህል ነበር፤ አበቃቀላቸውም ከጆሮቹ ከፍ ብለው ነው።

ሺህ ፎሻንጂ ሲወለድ ከነቀንዶቹ ተወለደ።ነገር ግን ለይተው አልወጡም ነበር ጉም ጉም ያሉ ነበሩ እንጂ፡ከዚያም በኋላ እያደጉና እየወፈሩ ሔዱ የሀያ ዓመት ጐበዝ በሆነ ጊዜ ከሥር ሴንቲሜትር አይበልጡም ነበር።ዓሥር ዓመት ጨምሮ ሀያ ሴንቲሜትር ሆኑ እንዲያ እየሆኑ ሲያድጉና ሲወፍሩ እስከ ዓርባ ዓመት ድረስ አሁን እንዳለው ቁመታቸው ሆኑ፡ ከርባ ዓመት በኋላ ግን ማደጋቸው ቀርቶ ወደኋላ መቀለፍ ጀመሩ።መልክቸውም ከጥቁረት ወደ ብጫ ተመለሰ ብሎ ተነገረው ወዲያ ዕድሜውን ጠየቀው ፎሻንጂም የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነኝ አለው።

በሺህ ፲፱፻፶፤ ዓመተ ምሕረት በፈረንጆች ቁጥር እንዲሁ ሻረል የሚባል የፈረንሳዊ ሰው ሚስቱ ቀንድ አበቀለችና በተጣሉ ጊዜ በቀንድዋ እየተዋጋች መከራውን ስታበላው ወደ ፓሪስ ፍርድ ቤት ሒዶ አቤቱታውን አቀረበ።ዳኛውም በደረቱ የፈሰሰውን ደምና የተወጋውን ሰውነቱን አየና ነገሩን ጠየቀው ባሥራ ስድስት ዓመትዋ ያገባኋት ሚስቴ ቀንድ አብቅላ በማናቸውም ነገር በተከራረፍን ጊዜ እየተዋጋች አላኖረኝ ብላለችና አፈታለሁ።ነገር ግን መጀመርያ ዘበኞች ይታዘዙና ትቅረብልኝ አለ፤ ዳኛውም ለማኛነት የተቀመጡትም ሽማግሎች ነገሩን በሰሙ ጊዜ በጣም ተገረሙ፤ በኋላም የታዘዙት ዘበኞች ይዘዋት መጡ ስምዋም ቴይሬዝ ትባል ነበር፤ ሻረልና ቴይሬዝ በዳኛው ፊት ቆሙ ሻረል ሲል አሁን ነገሩን ለማየት አትችሉም እነዚህ የቆሙ ዘበኞች የተጠመጠመውን ጠጕርዋን ቢፈቱት እውነትና ሐሰቱን ታገኙታላችሁ እኔ ግን ቀርቤ እንዳልፈታው ደግሞ እንደ ልማድዋ ትወጋኛለች አለ ፤ ዳኛው ቴሬዝን ጠጕርሽን ፍቺ አላት ፤ አልፈታም ብላ መለሰች ፤ ከዚህ በኋላ ዳኛው የቆሙትን ዘበኞች ጠጕርዋን እንዲፈቱ አዘዘ ፤ አላስፈታም በማለትዋ የተነሣ ብዙ ጩኸትና ትግል ሆነ ፤ ዘበኞቹ እየሉና በፈቱት ጊዜ ሁለቱ ትንንሾች ቀንዶችዋ ተገለጡ።ከዚያ የነበሩት አማኞችና ዳኛው በብዙ ተደነቁ ። እያንዳንዱ ርዝመታቸው ፯ ሴንቲሜትር ነበር ፤ የዚያን ጊዜ የፈረንሳዊ የሕግ ሥርዓታቸው መለያየታቸውን ለጊዜው የማይፈቅድ ስለሆነ ዳኛው ማፋታታቸውን ተወና ጥል በሚያነሱበት ሰዓት ባልየው ሚስቱን እንገትዋን በሰንሰለት ይሰር ብሎ ወደ ቤታቸው መለሳቸው ። አዲስ ወሬና ያላዩትን ነገር ማየት ለጊዜው ደስ ማሰኘቱ አይቀርምና በማለት ይህን ቃል ሮዝ አልዮሴፍ ከሚባል ከምስር ዓረብኛ ጋዜጣ ተጽፎ አግኝቼው ስላነበብሁት የብርሃንና ሰላም ወዳጆች ቢሰሙት ደስ ይላቸው ይሆናል ብዬ በጥቂቱ ተረጐምሁት ።

ፀሐዩ ደስታ ዘጐንደር ።

የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

በንግድ ሚኒስቴር አጠገብ በድሮው የፈረስ ገበያ ላይ ያለ የእንጨትና የማር፥የማዕዘንና የማንቃ፥የጠርብና የጭድ፥ያልጋና የኩበት ገበያ ጉለሌ በእስላሞች መቃብር አጠገብ እንዲቆም ማዘጋጃ ቤት የገበያውን ልክ ወስኖ ስፍራውን አሰናድቷል። ለዚሁም ምልክት እንዲሆን ተብሎ ይህ ገበያ በሚቆምበት ስፍራ ላይ ባንዲራ ተተክሏልና ከ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጥቅምት ፲ቀን ጀምሮ የእንጨትና የማር፥የማዕዘንና የማንቃ፥የጠርብና የጭድ፥ ያልጋና የኩበት ገቢያ በዚያ ቦታ እንዲቆምና ነጋዶዎችም ከዚያ እየሔዱ እንዲገዙ ሻጮችም በዚያው ላይ እየተቀመጡ እንዲሸጡ ማዘጋጃ ቤት ለሕዝቡና ለነጋዴዎች ያስታውቃል ።

መስከረም ፴ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

የአዲስ አበባ ከንቲባ ።

ማስታወቂያ

ማናቸውም ሰው በሚሰበሰብበት ስፍራ ላይና ሰው በሚተላለፍበት በየመንገዱ ላይ ወይም በማናቸውም ስፍራ ላይ በከተማውስጥ የሕዝብ ጸጥታ የሚነሳ የማይገባ ጩኸትና አምባጓሮ ፤ ግርግርታ የሚያነሡ ከተሰጠው ደምብ ተላልፈው ማናቸውንም መሣሪያ ይዘው በጠብና በአምባጓሮ ላይ የሚገኙ ሰዎች በፍጥነት ተይዘው ወደ ኰሚሣሪያ ይሔዳሉ ።

፪ተኛ ።

እነዚህም ሰዎች በኰሚሣሪያ ላይ ከተመረመሩ በኋላ የጥፋታቸው መጠን ታይቶ ጥፋት ያልተገኘባቸው እንደሆነ ይለቀቃሉ፥ ጥፋት የተገኘባቸው ግን ይታሠራሉ ።

፫ተኛ ።

ባ፩ኛው ክፍል ላይ በተባለው ጥፋት ተገኝቶ የሚያዘው ሰው የውጭ አገር ዜጋ የሆነ እንደሆነ በኰሚሣሪያ ሔዶ ከተመረመረ በኋላ ተይዞ ለቆንስሉ ይሰጣል።ጥፋተኛ ሁኖ ተገኝቶ ለቆንስሉ ከተሰጠም በኋላ በቆንስሉ እጅ ቈይቶ መጀመሪ በሚሆነው በልዩ ፍርድ ቤት ችሎት ላይ ቀርቦ ነገሩ ይታያል።

፬ተኛ ።

በእንደዚህ ያለ ጥፋት ላይ የተገኙትን ሰዎች በፍርድ ቤት ላይ ስለ መንግሥት ሆኖ የሚነጋገርና ወይም የሚፋረዳቸው የከተማው ሹም የሚወክለው ሰው ነው ።

፭ተኛ ።

በመጀመሪያው ክፍል ላይ የተባለውን ጥፋት ማናቸውም ሰው ቢሆን አድርጎ የተገኘ እንደሆነ ከ፲፩ ቀን እስከ ፮ ወር በእሥራትና ከ፺ብር እስከ ፭፻ብር መቀጮም እንዲከፍል ይፈረድበታል ።

፮ተኛ

ከዚህ በላይ እንደተባለው ማናቸውም ሰው አምባጓሮ አንሥቶና አሥነስቶ በምባጓሮው ላይም መሣሪያ ይዞ ፤ ወይም ሰው መትቶ ወይም ሰክሮ ፤ ጠብ አሥነስቶ የተገኘ እንደሆነ ባምስተኛው ክፍል ላይ የተባለውን መቀጮ በእጥፍ አድርጎ ይከፍላል ።

፯ተኛ

ነገር ግን በንደዚሁ ያለው አምባጓሮ ምክንያት ተመትቶ የሚገኘው ሰው በትሩ የሚጐዳውና አቅም አጥቶ አያል ጊዜ ሥራ የሚያስፈታው ፤ ወይም ከበትሩ የተነሣ አሳልፎ ለሞት የሚሰጠው ሁኖ የተገኘ እንደሆነ ዳኛው በሚገባ ሊፈርድበት የሚቻለው ስለሆነ ይህ ያምስተኛውና የስድተስተኛው ክፍል ቅጣት ውሳኔ ሁኖ ዳኛውን እንደ ደምቡ በሌላ ዓይነት አገባብ ከመፍረድ አይከለክለውም ።

፰ተኛ

ግርግርታና ጠብ የሚያነሡት ወይም የሚያስነሡት ሰዎች አባምጓሮ ያነሡበት ምክንያቱ ታላቅ ነገር ሁኖ የተገኘ እንደሆኑ ባ፭ተኛውና በ፮ተኛውም ክፍል ላይ ከተባለው መቀጮ በተቀር ጥፋተኛ የሆነውን ሰው ዳኛው ከከተማ ለማስወጣትና ወይም ከኢትዮጵያ ግዛት ለማስወጣት ይችላል ። ደግሞ ከዚህ ቀደም በመጀመሪያው ክፍል ላይ የተባለውን ጥፋት አጥፍተው ተይዘው ወደዳኛው ቀርበው የነበሩ ሰዎች ለወደፊትም በንደዚሁ ያለው ጥፋት ላይ ደግመው የተገኙ እንደሆነ በከተማ እንዳይኖሩም ለመከልከል ፤ ከኢትዮጵያም ግዛት እንዲወጡ ለማስገደድ ይችላል ።

ጥቅምት ፲፪ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም

የዲስ አበባ ከንቲባ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፊልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ክካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ። ’

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ክቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ክጎሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ካ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በየይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያ ስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎ ርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤቷ አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና ብግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግጋርና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።



አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አሸ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፌ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
- አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

COGNAC S.E.&A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METÀΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፬ 6me ANNÉE № 44		ሐሙስ ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም። JEUDI 30 OCTOBRE 1950

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ባገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie — Un an 5 Thalers Etranger — Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የዘውድ ክብር ።

የጃንሆይን ዘውድ ክህናት በመታሰቢያ ቤት ብዙ ቀን ሲጸልዩበት ሰንብተው ደግሞ ጃንሆይ በሚነግሡበት በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውሥጥ ፯ቀን ክህናቱ እንዲጸልዩበት ስለ ተፈቀደ ክህናቱ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ወደ መታሰቢያ ቤት እንዲመጡ በሊቀ ክህናቱ በመልአከ ገነት ወልደ ሐና ታዝዘው ነበርና በዚያው በተቀጠረው በጥቅምት ፲፰ ቀን በ፲ሰዓት ጳጳሳቱና ሊቃውንቱ፥ ክህናቱና መዘምራኑ ወደ መታሰቢያ ቤት ተሰበሰቡና ጳጳሳቱና ሊቃውንቱ በየ-ማዕርጋቸው ተቀምጠው መዘምራኑ መልካም ምሥጢር ያለው ወረብ ወርበው በጸናጽልና በከበሮ ይወዘወዙ ነበር ። ቃሉንም ቀጥዬ ጽፌዋለሁ ።

እመሰ ጸምከ ወጸለይከ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ። ትፀውር ባዝግና ወርቅ ውስተ ክሳድከ አክሊለ ክብር ዲበ ርእ-ስከ ። በጽርሐ ቅድሳቱ ለምኒልክ ይኤምኁከ ጳጳሳት። ይህን ሲጨርሱ ጸጥ ብለው ቈይተው ሁለት ድምፀ መልካሞች ደብ-ተሮች ቀጥሎ የሚመጣውን ወረብ ሁለተኛ ወረቡ ።

ዝኒ ኃይለ ሥላሴ ከነ በፈቃደ እግዚአብሔር ፡ ወአንቲኒ ወለተ ጊዮርጊስ መድኃኒተ ኩኒ ለኢትዮጵያ ባሉ ጊዜ የድምጻቸውና የምሥጢሩ ማማር ሊቃውንቱንና ሕዝቡን አስደ-ነቀ። ከዚህ በኋላ በጅሮንድ ዘለቀ አግደው በውስጣቸው ያሉትን መኳንንትና ሠራዊት አሰልፈው ጠበንጃቸውን ይዘው መጡ ቀጥለው ቀኛዝማች ለጥይበሉ የግቢ ዘበኛ ዲሬክተር እን-ዲሁ ተሰልፈው መጡ ። ፲ሰዓት ተኩል ሲሆን ዘውዱ ከመታ-ሰቢያ ቤተ መቅደስ ወጣና ሠታደር በፊት፥በፊት ቀጥለው

ክህናትና አለቆች፥ቀጥሎ ለንጉሥ ጊዜ የሚያስፈልገውን የቀረው መሣሪ የያዙ ክህናት ፥ በኋላ የጃንሆይን ዘውድ በመሐል አድርገው የያዙ ክህናት ። ቀጥለው የእቴጌን ዘውድ የያዙ ክህናት በኋላ ጳጳሳትና መኳንንት አጅበው እምቢልታውና መለከቱ ጥሩምበው እየተነፋ፥አይሮፕላን በሰማይ እየዞረ በዝግታ እንደ ጥምቀት ቀን በከብካብ ሁኖ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ደረስንና የጃንሆይና የእቴጌ ዘውድ ወደ መቅደስ ገባ ። ወደ ደገኛይቱ ቀን ለመድረስ ሁላችንንም ያብቃን ብለን ተመለስን ።

የእንግዶች መገናኘት ።

በፊተኛው ብርሃንና ሰላም እንዳስታወቅነው ከመጡት እንግዶች በጥቅምት ፲፫ ቀን የአሜሪካ መንግሥት መልእክተኞችና የጀርመን መንግሥት መልእክተኞች ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመገናኘት ተፈቅዶላቸው ነበር፥ ፬ ሰዓት ሲሆን ማጆር ፖሊና የቀሩት ከፒቴኖች የሰልፍ አስተማሪዎች መልክም አድርገው ሰልፍ የተማሩትን ወታደሮች ከበሩ እስከ እንግዳ መቀበያው እልፍኝ ድረስ አሰልፈው ሲጠባበቁ ልክ ፭ ሰዓት ሲሆን ልዑል ራስ ጉግሣና ብላቴን ጌታ ኅሩይ እንግዶችን ይዘው ገቡ ። ጃንሆይም የሚአንጸበርቅ ልብስ ለብሰው በዙፋንም ተቀምጠው ነበር ። ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ነበር ። እንግዶችም ሲገቡ ክቡር ሊጋባ ወዳጄ የሚአንጸበርቅ ለምድና ድርብ ለብሰው የወርቅ ጐራዴአቸውን ታጥቀው የወርቅ ጋሻና ጠመንጃቸውን ይዘው እንግዶችን እየመሩ ይዘዋቸው ሲገቡ ሙሴ ኒኮ የሙዚቃ አስተማሪው እየመርዋቸው የሾገሌ ጉበዛዝት ደስ የሚአሰኝ ሙዚቃ እየነፉ ወታደሩ ሁሉ ሰላምታ ሰጥዋቸው።ጃንሆይ ወደ ተቀመጡበት ገብተው ከተገናኙ በኋላ ደስ የሚያሰኝ ዲስኩር አነበቡ ። ከዚህ በኋላ ስለ እንግዶች ክብር ፲፫ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ። እንግዶችም በማዕርግ ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

የወታደሮችም አሰላለፍና መስማማት እጅግ የተመሰገነ ስለ ሆነ ሹማምቱ በየማዕርጋቸው በጃንሆይ እጅ ሜዳይ ተሸለሙ ።

፪ኛ የእንግዶች መገናኘት ።

ደግሞ በጥቅምት ፲፬ ቀን የግሪክ (የዮናኒ) መልእክተኞች ከጃንሆይ የሚገናኙበት ቀን ነበር ። ልክ ፬ ሰዓት ሲሆን ማጆር ፖሊና የቀሩትም የሰልፍ አስተማሪዎች ወታደሮችን ይዘው ወደ ግቢ ገብተው በግራና በቀኝ አሰልፈው ሲጠባበቁ ልክ ፭ ሰዓት ሲሆን የጃዝማች መኰንን ደምሰውና የውጭ ጉዳይ ዲሬክቴር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ከእንግዶቹ ጋራ በአንድ ኦቶ ሞቢል ሁነው የግሪክ ቆንስል ዶክቶር ዘርቦስ በአንድ ኦቶሞቢል ሁነው በደረሱ ጊዜ ሊጋባ ወዳጄ እንዲሁ እንደላይኛው ተሰናድተው ተቀበልዋቸው፥ወታደሮች ደስ የሚአሰኝ ሰላምታ ሰጡ። ሙዚቃውም ተነፋ፥ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም እንደፊተኛው አድርገው ከተገናኙ በኋላ ያነበቡትን ዲስኩር ስፍራ ስለጠበበ ትተ ነዋል ።

ስለ እንግዶችም ክብር ፲፫ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ከዚህ በኋላ በፈረሰኞች ታጅበው በክብር ወደ ቤታቸው ተመለሱ፥ በዚሁ ቀን ጃንሆይንተከትለው እንዲመጡ ተፈቅዶላቸው የነበሩ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮች ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው

ልዑል ራስ ካሣ።
ልዑል ራስ ኃይሉ።
ልዑል ራስ ሥዩም።
ልዑል ራስ ጉግሣ።
ልዑል አስፋ ወሰን ።
ፊታውራሪ ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴር።
ደጃዝማች ብሩ ።
ቢትወደድ ጌታቸው አባተ።
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ።
አፈ ንጉሥ አረጋይ የፍርድ ሚኒስቴር።
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ።
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው።
ደጃዝማች መኰንን ደምሰው።
ደጃዝማች አደፍርሰው የግቢ ዘበኞች ጠቅላይ አለቃ።
ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ከድሬዳዋ እንግዶችን ተቀብለው አብረው እንዲመጡ ታዝዘው መጥተው ነበር ።
ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ።
ፊታውራሪ ጣሰው የልፍኝ አስከልካዩ።
የቀሩትም ስማቸው ያልተጻፈ ብዙ መኳንንት ነበሩ።

ለኢትዮጵያ ብርሃን የዘውድ ባዓል ለማክበር ወዳጆቻችን ስለመጡልን እጅግ ደስ ብሎናል እንኳን ደኅና ገቡልን።

የእንግዶች መግባት ።

በጥቅምት ፲፮ቀን ከጧቱ በ፬ሰዓት በልዩ ባቡር ሲገቡ ለመቀበል የታዘዙት ልዑል አስፋ ወሰንና ክቡራን መኳንንት ነበሩ። በዚሁ ቀን የገቡት እንግዶች ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

የጃፓን መንግሥት እምባሳደር ።
የግብፅ መንግሥት አምባሳደር ።
የሆላንድ መንግሥት ልዩ መልእክተኛ ሚኒስቴር ።
የፖሎኝ መንግሥት አምባሳደር ናቸው ። የአቀባበላቸው ክብር እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነበር ።በዝርዝር እንዳንጽፈው ስፍራ ጠበን ትተነዋል ። ይልቁንም የአቀባበሉን ደምብ አስቀድመን ጽፈን ነበረና ታውቁታላችሁ ብለን ነው ። የወዳጆቻችን በደኅና መምጣት እጅግ ደስ ብሎናል ።

የእንግዶች መምጣት ።

በጥቅምት ፲፯ቀን የፈረንሳዊ መንግሥት መልእክተኞች ማሬሻል ፍራንሼ ደ እስፔሬ የሚመጡበት ቀን ነው ተብሎ ታውቆ ነበርና ።እንግዶችን ለመቀበል ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ባቡር ማረፊያ ወርደው ይጠባበቁ ነበር ። ተከትለውም የወረዱ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮች ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ።

ልዑል ራስ ካሣ
ልዑል ራስ ኃይሉ
ልዑል ራስ ሥዩም
ልዑል አስፋወሰን
ፊታውራሪ ሙሉጌታ የጦር ሚኒስቴር
ደጃዝማች ብሩ ወልደ ገብርኤል
ቢትወደድ ጌታቸው አባተ
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የአገር ግዛት ሚኒስቴር
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ
ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው
ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ መስቀል የጽሕፈት ሚኒስቴር
ጸሐፊ ትእዛዝ አፈወርቅ የርሻ ሚኒስቴር
አፈንጉሥ አረጋይ የፍርድ ሚኒስቴር
ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ

ደጃዝማች አደፍርሰው የግቢ ዘበኛ አለቃ። ደጃዝማች ጐበና እንግዶችን ለመቀበል ታዝዘው ከድሬዳዋ አብረው መጥተው ነበር።ከንቲባ ነሲቡ ዛማኔል።ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የውጪ ጉዳይ ዲረክተር ። ፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ፊታውራሪ ጣሰው የልፍኝ አስከልካዩ

ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ የምድር ባቡር ተቆጣጣሪ ሹም የቀሩትም ስማቸው ያልተጻፈ ብዙ መኳንንት ነበሩ ። የባቡር መቋሚያ ግቢ በጥሩ ወታደር ታጥሮ ነበር ። ፬ሰዓት ተሩብ ሲሆን ባቡሩ በደረሰ ጊዜ ሙሴ ኒኮ የሙዚቃ አስተማሪው እየመርዋቸው የሾገሌ ጐበዛዝት ደስ የሚአሰኝ ሙዚቃ ይነፉ ነበር። ጃንሆይም ከልዑላን መኳንንት ጋራ ወደ ባቡር ቀርበው ተቀበልዋቸው። ከማክበር ሰላምታ በኋላ የፈረንሳዊ ማርሽ ሙዚቃ ተነፋና ጻጥ ብለው ሰምተው የሰለጠኑ ወታደሮች ሰላምታ ሰጡ ። ከዚህ በኋላ በአንድ ወገን ያሉትን ወታደሮች ዙረው አይተው ወደ ማረፊያ ቤት ገብተው ከማርሻል ፍራንሼ ደስፔሬ ጋራ ልዑላን መኳንንቱና ሚኒስቴሮችን በየስማቸው አስተዋወቁ ። ከዚህ በኋላ ማርሻል ከልዑል ራስ ሥዩም ጋራ በአቶመቢል ሁነው ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሔዱ ። ወታደሮችም ደስ የሚአሰኝ የሙዚቃ ድምጽ አሰምተው ያማረ ሰላምታ ሰጥተው ተሰናበቷቸው ። የክብር ዘበኞች የሚባሉት ፈረሰኞች ግን ተከተለዋቸው።ጃንሆይም ጥቂት ቈይተው ተነሡ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም ተከትለዋቸው ሔዱ ።

የወዳጆቻችን አቀባበል መልካም በመሆኑ እጅግ ደስ ብሎናል።

የእንግዶች አቀባበል ።

በጥቅምት ፲፰ ቀን የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መልእክተኞች ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎስተርና የቀሩትም መኳንንት የሚመጡበት ቀን ነበር ። ቀደም ብለው ማዝር ፖሊና የቀሩት ካፒቴኖች ሰልፍ አስተማሪዎች ወታደሩን በሥርዓት አሰልፈው የሙዚቃ አስተማሪው ሙሴ ኒኮም ሙዚቃ ነፊዎችን በሥርዓት አሰልፈው ሲጠባበቁ ፬ሰዓት ተኩል ሲሆን ጃንሆይ ልዑላን መኳንንቱንና ሚኒስቴሮችን አስከትለው ወደ ባቡር ማረፊያ በደረሱ ጊዜ ወታደሩ በአንድ ቃል ተባብሮ ሰላምታ ሲሰጥ እጅግ አማረ።፭ሰዓት ሲሆን ባቡሩ መጣና ሲቆም በአስተማሪአቸው በሙሴ ኒኮ እየተመሩ የሾገሌ ጐበዛዝት ደስ የሚአሰኝ ሙዚቃ ነፉ።በአዲስ አበባ የሚኖሩት የእንግሊዝ ሚኒስቴርና ቆንስል የቀሩትም የእንግሊዝ መኳንንት ጥሩ ጥሩ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ይጠባበቁ ነበርና ወደ ባቡሩ ገብተው ተገናኙ።ቀጥለው ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጪ ጉዳይ ዲሬክተር ገብተው ተገናኙና ይዘዋቸው ወጡ ። ጃንሆይም ከማረፊያው ቤት ወጥተው ተገናኙ ። ከዚህ በኋላ የእንግሊዝ ማርሽ ሲነፋ ጻጥ ብለው ቁመው የሰላምታ እጃቸውን ሳያወርዱ ቆይተው ሙዚቃ ሲአልቅ ፊት ለፊት ያሉትን ወታደሮች ዙረው አይተው ወደ ማረፊያው ቦታ ገብተው ከኢትዮጵያ መኳንንት ጋራ በየስማቸው አስተዋወቁአቸው። ልዑልም የእንግሊዝን መኳንንት ከጃንሆይ ጋራ አስተዋወቁአቸው።ስለ ደኅንነትም ስለ መንገዱም በደኅና መምጣታቸውን ከተጠያየቁ በኋላ ልዑል ዱክ ግሎስተርና አብረዋቸው የመጡ መኳንንት ተሰናብተው ወጡና ልዑል ዱክ ከልዑል ራስ ካሣ ጋራ በአንድ አቶመቢል ሁነው አነጋጋሪ ጆርጅ ኅሩይን ጨምረው ፤ ክቡር ደጃዝማች ብሩና ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው ፤ክቡር ደጃዝማች ደስታ ዳምጠው ከሌሎች ከእንግሊዝ መኳንንት ጋራ ሁነው ብዙ ፈረሰኞች ተከትለዋቸው በክብርለማረፊያ ወደ ተሰናዳላቸው ቦታ ገቡ።

የንግዶች አቀባበል

በጥቅምት ፲፰ቀን ከጃንሆይ የተገናኙት እንግዶች ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው የፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ መልእክተኞች አቡነ ዮሴብና ረዳታቸው ቆሞስ አቡነ ጊዮርጊስ
ቀጥለው የጀርመን መንግሥት አምበሳደር
ቀጥለው የጃፓን መንግሥት አምባ ሳደር
ቀጥለው የግብፅ መንግሥት አምባ ሳደር
ቀጥለው የሆላንድ መንግሥት ልዩ መልእክተኛ ሚኒስቴር

ተገናኙ።በተገናኙም ጊዜ የአቀባበሉን ክብርና ማዕርግ በመጀመሪያው አቀባበል ጽፈነዋልና በዝርዝር እየጻፍን በፊተኛው ያነበባችሁትን እንደግመው ትሰለቻላችሁ ብለን ትተነዋል ። በዚሁም በአቀባበል ተራ ለየ እንዳንዳቸው ፲፫ ፲፫ ጊዜ መድፍ ተተኵሶላቸዋል።እኒህ መንግሥታት ጥሪአችንን አክብረው በመምጣታቸው እጅግ ደስ ብሎናል ።

ዋዜማ ።

ዘበዓለ ዘውዱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ዋዜማ የክብረ በዓል ወይም ወደፊት ለሚመጣ የደስታ ነገር መጀመሪያ ስለሆነ እንደክብረ በዓሉ ቀን ይቆጠራል ። የክብረ በዓሉም ደስታ ይጀመርበታል ።

እንደዚሁ ሁሉ መስከረም ለጥቅምት ዋዜማ ሲሆን የመስከረም ፳፯ተኛው ቀን የጃንሆይ የንጉሥነት ዘውድ በዓል ለጥቅምት ፳፫ኛ ቀን የጃንሆይ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ በዓል

ዋዜማ ነውና የግርማዊ ዋነኛ ደስታ የተጀመረበትን ቀን የመስከረም መድኅኔ ዓለምን ክብር በማሰብ ለብርሃንና ሰላም ልጆች ጥቂት የግጥም ቃሎች ለመጻፍ እደፍራለሁ ።

ደግሞ መስከረም ምንም በኢትዮጵያ አገራችን የደስታና የዘመን መጀመሪያ ቢሆን በተለየ ለጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለልዕልናቸውና ለግርማዊነታቸው የደስታ በዓል መጀመሪያ ነው ። እነሆ ጃንሆይ በመስከረም ወር በአልጋ ወራሽነት ልዕልናን ተቀበሉ ። በመስከረም ወር በንጉሥነትና በባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴነት በግርማዊነት ከፍ ከፍ አሉ ።

ስለዚህ ጃንሆይን ለምንወድ ለኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ይህን ወርኃ መስከረምን ይልቁንም ፳፯ኛውን ቀን ለዘላለም የደስታ ወርና ቀን እንድናደርገው በታናሽ እውቀቴ አሳስባለሁ ።

ሰላምታ ለናት አገር ኢትዮጵያ።

፩፤ ይድረስ ሰምላታችን ከምንወድሽ
ልዕልት ዘአፍሪካ ሀገር እንዴት ነሽ
ሁላችን ደኅና ነን እኛ ልጆችሽ
ቸሩ አምላክ ይመስገን የሚጠብቅሽ
እጅግ ደስ ብሎናል እንኳን ደስ ያለሽ
ወዳዲሱ ዘመን ስላሻገረሽ
፪፤ ታየ አዲስ አበባ ጠባ መስከርም
ብርሃኑን ገልጾ ንጉሠ ሰላም

ከቀኑ አደረሰን መድኅኔ ዓለም
፫፤ ክረምቱም አለፈ ችግርም አናይ
ደመናውም ሸሸ ወጣልን ፀሐይ
በወርኃ መስከረም ዘመነ ሠናይ
ታየ አዲስ አበባ ከፍ ብሎ ከላይ

ኢሳ ፲፩ ከማህለ ሥላሴ ከስርወ ዕሴይ ።
በትር ኃይለ ሥላሴ ፈራጅ ለነዳይ ።
ወጣ ለሁላችን ታየ አደባባይ ።
፬፤ከተወለዱቱ ከእሴይ መንግሥት ።
ከአምላክ የተሰጡት ብዙዎች ሀብታት ።
ተቀባ በፍጥነት ተፈሪ ዳዊት ።
፭፤የሰላሙ ንጉሥ ከወጣህልን ።

ዘሌ፡፳፭ ፳፤ ከጭንቅ መከራ የምታድነን ።
የችግር ዓመታት ወዲያ አልፈውልን ።
የደስታው ዓመት እንዲገባልን ።
መለከት ተነፍቶ አዋጅ ወጥቶልን ።
ይቅርታም ተደርጎ ለጥፋታችን ።
እንግባ ወዳገር በየርስታችን ።

ኢሳ ፷፩፤ ተቀባልን አንተን ቸሩ አምላካችን ።
ለትሑታን ንገር የምስራችን ።
ጠማን ልባቸውን ተሰብሮ ያለን ።
የይቅርታን ዓመት ያምላካችንን ።
ነፃ የሚያወጣ የተጋዙትን ።
የሚፈታም ደግሞ የታሰሩትን
በምሕረተኛ ቃል ፈጥነህ አሰማን ።
ታጸናናቸው ዘንድ የሚያለቅሱትን ።
፮፤የሐኪም መድኃኒት ለማይፈውሰው ።
የደኅ መድኃኒት እንደምናውቀው ።
ላገራችን ንጉሥ አምላክ ለቀበው ።
ሁሉም በየቤቱ እንደሚያስበው ።
እኛም የምንለው በጥቅምት ማር ነው ።
፯፤ አገራችን በጥቅምት አበባው ሲያምር ።
የንበቹም አውራ ሲገለጽ በክብር ።
ማሩን ስንል መጣን ከገደል ከዱር ።

አሐዱ ኢትዮጵያዊ ።

ምሳሌ ነገር ።

ይድረስ ለክቡር ወዳጄ ቀኛዝማች ክብረት ጤናህን እንደምን ሰንብተሃል እኔ ሥላሴ ይመስገኑ ደህና ነኝ ምንም አንተ ዘመድ ባትለኝ እኔ ዝምድናህን አልጠላምና ከውለታ ትቆጥርልኛለህ ብዬ ያባትህ የፈታውራሪ ቦሩ ቸርነት የሚባል አገልጋይ እኔ ዘንድ መጥቶ አድሮ የማነህ ብየ ብጠይቀው ማሻኔት የሚባል ፈንጋይ ለፈታውራሪ ቦሩ ሺጦኝ የምሠራው ስራ የለ እንዲአው ለስሙ አገልጋይ አላቸው እየተባልሁ እኖራለሁ አለኝ ። እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ ነገሩ ሐሰት መሰለኝ ይኸ አገልጋይ በጣም ያረጀ ነው፤ፊታውራሪ ቦሩ ገና ጎበዝ በጣም የሚአድጉ ምንም ሲበዛ ቢውል የፊታውራሪ ቦሩ ገንዘብ ያለ ብርቱ ነገር ወጣ ሲሉኝ ሰምቼ አላውቅ ብየ ከስር ደገፎ ለመመርመር ጥንት የማን ኑረሃል ብየ ብጠይቀው የጥንት ጌታየማ አብርሃም ይባል ነበር ገና በልጅነቴ ርኅራኄ በሚባል በሬ ለውጦ አሳደገኝ እኔም ስራ ያለኝን ሁሉ እየሠራሁ እጅግ አክብሬው ነበረ ። የሀብታምነቱ ምስክር ከዕለታቱ ባንድ ቀን ሦስት ነገሥታት ሀገረ ሰዶም ወደምትባል ከተማ ሲሄዱ መሸባቸውና ከቤቱ በታች ቢሰፍሩ ጌታዬ እኔን ብቻ አስከትሎ ወርዶ ጋብዞ አቤቱ አግብቶ በመልካም አሳደራቸው ። ለንጉሥ ከሚገባም መሳሪያ አንድ አልጐደለበትም፤እነሱም እጅግ አደነቁና ለስሙ መጠሪያ ሐውልት የሚሆን ብርሃኑ ዓለምን የሚመላ አልማዝ ሰጡትና ወደ ሀገረ ሰዶም ሄዱ ። ወደ ሰዶምስ ምን ጉዳይ ኑሮዋቸዋል ብየ ብጠይቀው ይህን እስከ ዛሬ አታውቅምን ብሎ የሰዶምንማ ነገር ስንቱን ነግሬህ እንደ ያው በጭሩ መቸም ዓለምና ተድላ ሥጋ እዚያ ነው የተፈጸመ ስለዚህ ነገሥታቱ ሄደው አዩና እጅግ አደነቁ ።

ዳግም እንደዚህ ያለ ከተማ እንዳይሠራ ይህች ማብቂያ ትሁን መክበሷ ገነት ዳርቻዋ እሳት ይሁን ብለው ደብረዋት ነበልባል የሚባል በንዲራ አቁመውበት ሄዱ ። ዛሬም ቢሆን በዚያ ከተማ ይሠራ እንደነበር ያለ ጌጥ ከልክል ነው ያስቀጣል አለኝ ። እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ ይኸ ሰው ሲያዩት ቀላል መስሎ ትልቅ ሰው ነው ብየ ትንሽ እህልና ውሃ ሰጠሁት ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ቆመና እባክህ እንቅልፍ ካየሁ ብዙ ጊዜየ

ኅው ትንሽ ልተኛ ዕቃዩን ጠብቅልኝ አለኝ። እኔም መቸም ያለሁት በዱር ነው እንጂ ቤት አልሠራሁምና አሁንስ ቤት ቢኖረኝ እንደልቡ ተኝቶ ያድር ነበር ብዬ አዘንሁ። ምነው እንቅልፍ ማጣትህ ትልቅ ዕቃ ይዘሃልን ወይስ ጠላት አለህ ብዬ ብጠይቀው አዎን አፍቅሮ ንዋይም የሚባል ጠላት ይፈልገኛል የያዝሁትም ዕቃ ብዙ ነው ደግሞ ከሁሉ ገንት በምትባል ሀገር ለሚነግዱ ሰዎች መበደሪያ ባንክ ቤት ጸሐፊነኝና መዝገቡ እንዳይጠፋብኝ እፈራለሁ አለኝ። እኔም ብቻህን ነው የምትሠራ ብዬ ብጠይቀው መኖርስ ፍቅርየሚባል ዳና ነበረኝ ግን እደኔ ዕድሜው ገፋ አለና ዓቅም አጣ ያመውማል ይኸውም ጭራሽ ነፍሱ አለመውጣቷ በቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ብርታት ነው እግዚአብሔር ሀብታችውን ሰፋ ዕድሜአቸውን ገፋ ያድርገውና እስከ መንፈቅና እስከመት ጉዳና ድረስ ሄደው ከድካም ወደብርታት ካለማወቅ ወደ እውቀት የሚመልስ ትዕግሥት የሚባል መጽሐፍ የተደገመበት ፀበል አምጥተውለት ያንን ከቀመሰ በኋላ እያደረ ይሻለው ጀምሮአል። ዛሬ ግን አለመምጣቱ በጣም ሰውነቱ እስቲበረታ ነው እኔም ቤት ስለሌለኝ ትክዜዬን አልረሳሁምና ምከረኝ ብለው ልብህ ይህነን ካሰበ ማዘንፈልግ አለኝእኔም ማዘንስ በደል በደል እህል የገዛሁት አለኝብየ ባሳየው መልካም ጀምረሃል አሁንም በማዘኑ ጨምርበት ከንጉሡም የፈቃድ ወረቀት ተቀበል ብሎኝ ተኛ ።

አስረሴ የኔሰው

ኤስፒርቶ የሚባል የማይደክም ጉረምሳ።

በ፴፱ነኛው ቁጥር የተጻፈውን ቃል ከመጀመርያው እንስቼ እያነበብኩ ከመካከለኛው ስደርስ የአቶ ዘለቀ ቻችበሌ ስለ አረቂ አጠጣጥ ፈጽሞ ካልጠፋና ለሀገራቸውና ለወንዛቸው ለወገናቸው አስበው ደክመው እየጻፉ ያስታወቁት ከለተፈጸመላቸው በከንቱ ያሳስባል። ሰው አሳብና ምኞቱ ካልተፈጸመለት አሳቡ እየደከመ እውቀቱ እያነሰ ይሄዳል ብሎ ከጻፈው ስደርስ ከልቤ ቄስሎ የነበረውን ነካኩቶኝ ይህንን ለመጻፍ አሳሰበኝ።

ይገርማል ያስገርማል ለተመለከተው አንጀት ይበጥሳል ምንኛ ግሩም ነው ሰው ለፍቶና ደክሞ በስንት ፈተና ያከናወነውን ምቀኛ ለሀገሩ ጉጂ የሆነ ሲጠናወትበት በዚያን ጊዜ ግን ምን ሊሆን ይገባዋል (ችግር ነው) እንዲሁም አቶ ዘለቀ ታችበሌ እንዳለው በሥራው ደክሞና ለፍቶ ለሀገሩ መክበርያ ለመንግሥቱ ማኩርያ በሥራም በእርዳታም በምክርም ለስራው በላይ ለሹሙ ወይም ላለቃው ያቀረበላትን ሳያከናውንለት የቀረ እንደሆን ተስፋ እየቈረጠ እኔ ምንተዳዬ ምንስ ያደክመኛል የሚባል ተስፋ እየገባው እርዳታውና ሥራው ትጋቱ ሁሉ እንደተሰበረ ባቡር ይቆማል። እንደዚሁ ሁለተኛ ገንዘቡ ያነሰ ኃይሉና ጤናው የተቀነሰ ሕዝብ እንኳን ጠላቱ ሊፈራው መኖሩም አይታወቅም ሕዝባችን አረቂ መጠጣት ካልተወ ለነጻነቱ ያስፈራዋል በገንዘብና ባጤና በኩል የመጣ ጠላት ክጦርነት ይበልጣልና በቶሎ ሰው ሳያልቅ መቃወም ነው ስላለው እንደዚሁ ሁላችንም በየጊዜው እየጻፍን ማመልከታችን አላቋረጠም ብር ነገር ሳይፈጸምልን ዘመቶየቱ እናዝናለን ከዚህ በላይ የጻፍኩትና ከዚህም በፊት በሀገራቸው ፍቅር እየተናዳዱ ሲጽፉት የነበሩ አሁን በማቆማቸው ከዚህ በላይ እንደተናገርነው በዚህ ይመሰክራል ይህስ ጊዜውን ይጠብቅና ወደፊታችን ንግግር እንመለስ እንዴት ግሩም ነው የመጠጥ ጥቅም ምን ትርፍ እንደተገኘበት ለማወቅ ታላቅ ችግር ነው ታላላቆቹን መንግሥት ያጠፋ ስንት ወላድ ያመከነ ስንትስ ጐበዛዝቶች በጉልበታቸው የሚታመኑትን ያሸነፈ መሆኑን ማወቅ ነው በብልጽግና የበለጡ በእውቀት የራቁ በሕዝብ የበዙ አሜሪካኖች እንኳን ይህ የእስፒርቶ መጠጥ ይቅርና የደከመም መጠጥ በአገራቸው እንዳይጠጣ ከውጭም እንዳይገባ ክልክል ነው።ሕዝቦቹም የመጠጥ ነገር አያውቁም አንዳ አንዶች እንኳን ቀበጦች ሀብታሞች ለመጠጥ ሲሉ ብዙ ገንዘብ አጥፍተው መጠጥ ወደአለበት አገር ሄደው ጠጥተው ይመለሳሉ ማለትን እንሰማለን ዳግመኛም በእንግሊዝ አገር የሚደረገውን መጠየቅ ነው መጠጥ አገር ማደህየቱን ከተማን በዶ ማድረጉን ማምከኑን ማሳወሩን ማድከሙን አለጊዜ መግደሉን ከፈጣሪ ማጣላቱን ዝሙት ማጋነንን ከሁሉ የበለጠ ታላቅ መከራ ነፃነትን አሳጥቶ ለባዕድ አሳልፎ መስጠቱን ማንም የሚስተው የለም። ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ ያረቂን ገቢ ገንዘብ ሳይመለከቱ እንደሌሎች ማኅበርተኞቻችን የአረቂን ሽያጭ እንደሚከለክሉትና ሕዝባቸውን እንደ ሕፃን እንደሚጠብቁት እኛም ይህ መጠጥ የሚጠቅም ሽታው ማለፍያ ነው ይህ የሚጐዳ ነው ብለን ሁለት አሳብ ሳንመለከት ሁሉንም በግድ መከልከል ነው። ማለፍያ መጠጥ ተብሎ የሚመረጠው ለአፍና ለሽታ ነው እንጂ ከጕረሮ ከወረደ በኋላ የሚጐዳው እንደ ድማሚት ነው እንግዲህ ይብቃን ሰው የያዘውን ከወረወረ ፈሪ አይባልምና በተቻለን መክረናል።

(እሮይ ደከመኝ) መጠጥ እንኳን ከሆድ ሊያገቡትና አሁንም ለመጻፍ አሸነፈኝ አደከመኝ እርሳሴ ሰከረች ወረቀቴም ለፈለፈች ፥ ናልፋት ከዚህ በላይ እንደተጻፈው ክልክል የሚባለውን ጥቅም አግኝታ ደስታ ይወርሳታል ብርታት ያጠግባታል በማለት ነገሬን አተዋለሁ።

ጥሩነህ ክ።

የአባትና የልጅ ፍቅር ።

ፓትረያርክ አቡነ ዮሐንስ የግብፅና የኖብያ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ልጃቸውን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ቀብተው ለማንገሥ ፈቃዳቸው ነበር ፥ ነገር ግን በዕድሜ ስለ ሸመገሉ መምጣት ባይቻላቸው ምንም እኔ የሾምኋቸው ልጆቼ ከዚያው ቢኖሩ መልእክተኞቼን ብልክ ደስ ሳያሰኛቸው አይቀርም ብለው ከቡራኬ ደብዳቤአቸው ጋራ የጊርጋውን ጳጳስ አቡነ ዮሳብንና ረዳት የሚሆኑአቸውን ቆሞሱን የቁለሉን መጅሊስ ወኪል አቡነ ጊዮርጊስን ልከውልናል አባት ለልጁ ማሰቡ ምንም የቀድሞ ልማድ ቢሆን አባታችን ለልጃቸው መልካም አሳብ በማሰባቸው እጅግ ደስ ብሎናል ።

የልጅ ታፈሰ ሺመልስ ዕረፍት ።

ልጅ ታፈሰ ሺመልስ የቀኛዝማች ሺመልስ ልጅ ፈረስና ተዝናስ ንባብና ጽሕፈት ያወቀ መልካም ወጣት ሲአዩት ደስ የሚያሰኝ ነበር ። መቸም የበረታ ደጀ ጠኝ ነበርና ወደ ግቢ ሒዶ አርፍዶ ተመልሶ አዲስ አበባ ያለውን የአባቱን ቤት ሲአሠራ ውሎ በጥቅምት ፲፩ ቀን በድንገት ሞተ ። በዕድሜውም ገና የ፳፫ ዓመት ልጅ ነበር ቀድሞ በሽታ አለበት ይሆን? ብለን ብንጠይቅ የሳል በሽታ ነበረበት አሉን ። ሞት ምንም የማይቀር ቢሆን አላጊዜ ሲመጣ እጅግ ያሳዝናል ።

ስለ ወይዘሮ ደብሬቱ ዕረፍት ።

ወይዘሮ ደብሬቱ ቀድሞ በንጉሥ ሚካኤል ቤት ያደጉ እጅግ የተመሰገኑ ባለሙያ ነበሩ አሁንም በላይኛው ግቢ የግንዘብ ሹም አቶ ደስታን አግብተው ባላቸውን ደስ አሰኝተው ሲኖሩ ባልታወቀ ደዌ ታመው ፫ ወር ተኝተው በጥቅምት ፲፩ ቀን በ፵፫ ዓመታቸው ሞቱ ። ብዙ መኳንንትና ወይዛዝር አልቅሰውላቸው በማዕርግ በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ ።

የአገር ውስጥ ወሬ

ከዚህ ቀደም የሹም ሽር ነገር ስንጽፍ አቶ ተሰማ እሸቴ በቢሾፍቱ መሾማቸውን ጽፈን ይህ ሥራ ለጊዜው ትንሽ ቢመስል የኋላ ኋላ ታላቅ ሥራ ይሆናል ያልነው ቃል ደረሰ አሁን ሥራው ሁሉ አለቀና እጅግ ደስ አሰኘ ጁልባም ገብቷል ለመናፈስ የሚፈልጉ ሰዎችም ሒደው ያዩት እጅግ አመስግነዋል እንግዶቻችንም የፈረንሳዊ መንግሥት መልእክተኞች ማርሻልና የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሠ ነግሥት ልጅ ዱክ ኦፍ ግሎስተርና ቆቀሩትም አብረዋቸው የመጡት እንግዶች ከአዋሽ ተነስተው ሌሊቱን ሲሔዱ አድረው ጧት እዚያው ቢሾፍቱ ማረፊያ ከተባለው በአቶ ተሰማ እሼቴ ትጋት በተሠራው ሆቴል ዓርፈው ቁርስ ተጋብዘው በጀልባው ገብተው ተናፍሰው ስለመጡ እጅግ ደስ ብሎናል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ለህዝ ራቸው ሕዝብ ጥቅም ሲሉ በማተሚያ ቤታቸው ያሳተሟቸው መጻሕፍት ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ።

የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣፅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
ማር ይስሐቅ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲፪ ብር
፬ቱ ወንጌል ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
፲፬ቱ ቅዳሴ ንባቡ ከነትርጓሜው	፲ ብር
የግርማዊ ንጉሥ የኢየሩሳሌምና ያውሮጳ መንገድ ታሪክ	፱ ብር
መጻሕፍተ ሰሎሞንና ሢራክ ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ሕዝቅኤል ንባቡ ከነትርጓሜው	፯ ብር
ዓለም ጅዮግራፊ በአማርኛ ቋንቋ	፯ ብር
ድርሰነ ሚካኤል	፯ ብር
ደግሞ ፲፬ ቅዳሴ ንባቡና ነጠላ ትርጓሜ	፭ ብር
ኀሀ ጽባሕ	፭ ብር
ውዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፫ ብር
የቀድሞና የዛሬ ዘመን መጽሐፈ ቅኔ	፫ ብር
የሕይወት ታሪክ	፪ ብር ከ፳ መ
የርሻ ትምህርት	፪ ብር ከ፳ መ
መዝሙረ ዳዊት ትንሽ በኪስ የሚያዝ	፪ ብር
ትምህርተ ኀቡአትና ኪዳን ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ቅዳሴ ማርያም ንባቡ ከነትርጓሜው	፪ ብር
ወዳጄ ልቤ	፩ ብር
መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የአማርኛ ሰዋስው	፩ ብር
የኢትዮጵያ መጻሕፍት ካታሎግ	፩ ብር
የብድር ደንብ	፩ ብር
የነፃነት ደንብ	፩ ብር
የጦር መሣሪያ ደንብ	፩ ብር
የኢየሩሳሌም ገዳም ደንብ	፩ ብር
የኢትዮጵያ መኳንንት ካርት ፖስታል ፳፬ቱ	፩ ብር
የቍጥር ትምህርት	፩ ብር
የእቴጌ መነን የኢየሩሳሌም መንገዳቸው ታሪክ	፰ መሐ
የግርማዊ ንጉሥ የአደን መንገዳቸው አኳኋን	፰ መሐ
አጭር የዓለም ታሪክ	፰ መሐ
የሣልና የነቀርሳ የምክር ቃል	፰ መሐ
ያማርኛ ምሳሌ	፰ መሐ
ከጥንት ጀምሮ የመጣ የበገና ሰላምታ	፰ መሐ
የቀን መቍጠሪያ (ካሌንድር)	፰ መሐ
አሳብና ምኞት	፬ መሐ
ትምህርተ ሕፃናት	፬ መሐ
ፊደልና ፊደለ ሐዋርያ	፪ መሐ
ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ	፪ መሐ
የንቀጣጣሽ ግጥም	፪ መሐ
የልብ አሳብ ግጥም	፪ መሐ

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛኹ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪክ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከነህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሽመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቁቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪክ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዳቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኒዮ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዴድ ፋብሪካ አጠገብ ዴሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት በርሳሊን ባርኔጣ መጥቃችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

GOGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኪፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፭		ሐሙስ ጥቅምት ፳፯ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
6me ANNÉE № 45		JEUDI 6 NOVEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ በመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ደክፈላል ።
በየሳምንቱ መዛዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ደሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie: Un an 5 Thalers
Etranger: Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ሥርዓተ ንግሥ ።

የንጉሠ ነገሥቱና የእቴጌይቱ ዘውዳቸውና ሌላውም የንጉሥ መሣሪያና ዕቃ ሁሉ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ወደ አለው ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ከያውራጃው የመጡት መነኰሳትና ቆሞሳት ጳጳሳቱም የሚገባውን ጸሎት ፀሎት ፯ቱ ባዔ ሙሉ ከጸለዩበት በኋላ ሲዘውዱ በዓል ሰባት ቀን ሲቀረው በጅሮንዱ ለንጉሠ ነገሥቱና ለእቴጌይቱ የሚገባውን የሥርዓተ ንግሥ መሣርያ ሁሉ ለትልልቆች ሹሞች አስይዞ የክብር ዘበኞች በፊትና በኋላ በቀኝና በግራ ዐጅበውት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሔደ። የቤተ ክርስቲያኑ ሊቃ ካህናቱን ሰብስቦ ከቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ ሁኖ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ተቀበሉት ። ለንጉሠ ነገሥቱ የሚገባው የሥርዓተ ንግሥ መሣሪያ ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው።

፩ኛ ሰገባው በወርቅና በአልማዝ ያጌጠ ሰይፍ ።
፪ኛ በትረ መንግሥት።
፫ኛ ሉል።
፬ኛ ባለ አልማዝ ቀለበት።
፭ኛ ሁለት ባለወርቅ ጦሮች።
፮ኛ ልብሰ መንግሥት።
፯ኛ ዘውድ ነው።
፰ኛ በወርቅ ያጌጠ መጽሐፍ ቅዱስ።

ለእቴጌይቱ የሚገባ የሥርዓተ ንግሥ መሣሪያ

፩ኛ ባለ አልማዝ ቀለበት።
፪ኛ ልብሰ መንግሥት።
፫ኛ ዘውድ ነው።

በዚሁም ቀን ፯ቱን አፈዋተ መንግሥት ቅብዐ ቅዱስ ተጨምሮና ተዋሕዶ በቀርነ ቅብዑ ሁኖ ክንጉሡ መሣሪያ ጋራ

ወደ ቤተ ክርስቲያን ደሖ። ለዚህም ሥራ የተመረጡ ቀሳውስት የሥዓርተ ንግሡን መሣሪያ ሁሉ ከበጅሮንዱ ተቀብለው በመቅደስ ውሥጥ ለዚሁ በተሰናዳው ጠረጴዛ ላይ እየደረደሩ አስቀመጡ ።

ከቀሳውስትና ከመነኰሳት ወገን አርባ ዘጠኝ የሚሆኑ ካህናት ተመርጠው ሰባት ቀን ሙሉ ፯ ፯ እየሆኑ ከ፯ ቦታ ላይ በየቀኑ ዓ፻ኍን ዳዊት ደገሙ ።

ጧትና ማታ ዳዊትና ውዳሴ ማርያም ከነአንቀጸ ብርሃኑ፥ መልክዐ ማርያም፥መልክዐ ኢየሱስ ፡ ከመልክዐ ተክለሃይማኖት ጋራ እየደገሙ በእግዚአታ ምህላ እያደረሱ ሲቀድሱበት ሰነበቱ ።

የዘውዱ በዓል ቀን ።

የዘውዱ በዓል በዕለተ እሑድ እንዲሆን ይገባል፥ በዚሁም ቀን ካህናቱ ከማታው በ፬ ሰዓት ጀምረው ማኅሌት ቁመው መወድስና አርያም አደረሱ

ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ በዋዜማው ቅዳሚት ማታ ከቤተ መንግሥት ተነሥተው በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅበው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሒደው ከዚህ ጊዜ ላደረሳቸው ለዚህ ማዕርግ ላበቃቸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ሲያቀርቡ አደሩ። እሑድ ከጧቱ ባ፩ ሰዓት ንጉሠ ነገሥቱ ለሥርዓተ ንግሡ በተሰናዳው ስፍራ ቀርበው ከተሳለሙ በኋላ ጸሎተ ሐሊና ጸልየው ሲጨርሱ ከዳዊት መዝሙር ፻፳፩ኛውን ተፈሣሕኩ እስመ ይቤሉኒ ቤተ እግዚአብሔር ነሐውር የሚለውን እስከ መጨረሻው በታላቅ ድምፅ ደገሙ ።

ከዚህም በኋላ በተሰናዳው ወርቅ ወምበር ላይ ተቀመጡ ። ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ የሥርዓተ ንግሡ መሣሪያ ሁሉ ከመቅደስ እየወጣ ተደርድሮ ወደተቀመጠበት ጠረጴዛ ቀርበው ፊታቸውን ወደ መሳፍንቱና ወደ መኳንንቱ አዙረው ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ቃል ተናገሩ ።

እናንተ የኢትዮጵያ መሳፍንትና ሚኒስቲሮች፥ መኳንንትና የጦር አለቆች፥ ወታደሮችና ሠራዊቶች፥ በቤተ ክህነትም ወገን ያላችሁ ሊቃውንትና አለቆች፥ መምህራንና ቀሳውስት ሁሉ ይህ ንጉሠ ነገሥታችን ግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ሳያቋርጥ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር መሆኑን ሁላችሁም ታውቁታላችሁ ።

አሁንም በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ጭኖ እንዲነግሥ ልቀበው ነውና በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሥራው ሁሉ አገርም በማሠልጠን ሃይማኖትም በማፅናት በዘመኑም ኢትዮጵያ በዕውቀትና በትምህርት በጥበብም ከፍ ከፍ እንድትል በመትጋቱ ከወሰንም እስከ ወሰን የኢትዮጵያን ባንዲራ እንዲዘረጋ በማድረጉ ይኸነንም በመሰለው በመልካሙ ሥራው ሁሉ እንድትገዙለትና እንድትረዱት አደራ እንላችኋለን ብለው ጨረሱ ። ሕዝቡም ለንጉሠ ነገሥታችን እግዚአብሔር እንደቃልዎ ያድርግላቸው አሜን አሉ ። ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱ እጃቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጭነው ፊታቸውን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አዙረው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ጠየቁ ።

ሊቀ ጳጳሱ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ እንደ ነገሥታት ያምብ ሲነግሡ የሚገባውን መሐላ ለመማል ይፈቅዳሉን፤

ንጉሠ ነገሥቱ። አዎን እፈቅዳለሁ ።

ሊቀ ጳጳሱ ፥ ከቅዱሳን ነገሥታት ከአብርሃና ከአጽብሐ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፀንቶ የኖረውን የእስክንድርያ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት አፅንተው ለመኖርና የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የወሰነችውን ሕግና ሥርዓት ባለማፍረስ ለመጠበቅ ይምሉ ዘንድ ይፈቅዳሉን ።

ንጉሠ ነገሥቱ። የእስክንድርያን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እስካሁንም አምኜበት የምኖር ነውና ወደ ፊትም በእግዚአብሔር እርዳታ ጠብቄ እንድኖር ለመማል ፈቃዴ ነው ።

ሊቀ ጳጳሱ። በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በኢትዮጵያ ያለውን ሕዝብ በሥልጣንዎና በኃይልዎ በሚሠሩት ሥራ ሁሉ በርኅራኄና በትዕግሥት እንደ ሕጉ ለጥቅሙ እያሰቡ ይጠብቁታልን።

ንጉሠ ነገሥቱ። እነዚህ ቃሎች የበጎ ሥራ መሪ መሆናቸውን አውቃለሁና በሚቻለኝ ሁሉ ለመጠበቅ ፈቃዴ ነው ።

ሊቀ ጳጳሱ። ግርማዊነትዎ ፈቅዶ በምክር ቤት አስመክሮ የሚያቆመውን ሕግ ጠብቆ ለመኖር ይፈቅዳሉን የኢትዮጵያን ግዛቱንም ፤ ሕዝቡንም ሁሉ እንደሚቆመው ሕግና እንደ ምክር ቤቱ ሥርዓት አድርገው ይጠብቃሉን።

ንጉሠ ነገሥቱ። ሕግ ለሰው አነዋወር መሠረት መሆኑን አውቃለሁና የምክር ቤቱንም ሕግ አክብሬ እጠብቃለሁ በሚቻለኝም ሁሉ ሕጉ እንዲፈጸም አደርጋለሁ ።

ሊቀ ጳጳሱ። በኢትዮጵያ ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰፋበትን ወንጌል የሚሰበክበት የትምህርት ቤት እንዲቆም በቸርነትዎና በሥልጣንዎ ይረዳሉን ።

ንጉሠ ነገሥቱ፥ ትምህርት ለቤተ መንግሥትና ለቤተ ክህነት ትልቅ ጥቅም መሆኑን አውቃለሁና በሚቻለኝ ሁሉ ለመርዳት ፈቃዴ ነው ።

የመሐላው ቃል ከተነገረ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ እጃቸውን በወንጌል ላይ ጭነው አሁን የተናገርሁትን ሁሉ በእግዚአብሔር ረዳትነት ለመፈጸም ምያለሁ ብለው ወንጌሉን ተሳለሙ ።

ወዲያውም ከዚህ በላይ የተነገረው ቃል በተጻፈበት ደብተር ላይ ፊርማቸውን ፈርመው በወምበራቸው ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሳቱ ከዳዊት መዝሙር ፳ ኛውን እግዚኦ ሠነኤከ ሀበ ለንጉሥ የሚለውን ወይሰዓዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር እስከሚለው ጸልየው ተቀመጡ ።

ከዚህ ቀጥሎ የሥርዓተ ንግሥ መሣሪያ ሁሉ ተደርድሮ ወደ ተቀመጠበት ጠረጴዛ አጠገብ ለዚሁ ሥራ የተመረጡት ሁለት ቀሳውስት ሁለት ዲያቆናት ፩ዱ ቄስ ጥና ይዞ እያጠነ ፩ዱ ዲያቆን መስቀል ይዞ በጳጳሱ ቀኝ ደግሞ ፩ዱ ቄስ ጥና ይዞ እያጠነ ፩ዱ ዲያቆን መስቀል ይዞ በጳጳሳቱ ፊት ቀኝና ግራ ቆመ ።

ከዚህም በኋላ ዲያቆኑ ተንሥኡ ለጸሎት ሲል አንደኛው ቄስ ሰላም ብሎ ነአኵቶ ለገባሬ ሠናያት እያለ ጸሎተ ወንጌል ተጀመረ ። ከቀሳውስቱም ሁለተኛው በእንተ እለ ያበውኡ የሚለውን መስተብቍዕ ሲጀምር በጅሮንዱ በንጉሠ ነገሥቱ ስም ዓሥር ወቄት ወርቅ አምጥቶ ለቤተ ክርስቲያኑ መባ በጠረጴዛው ላይ አስቀመጠ ። በእንተ ቅድሳትና ንስሐድ ከተባለ በኋላ ፩ኛው ዲያቆን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የጳውሎስን መልእክት አነበበ። መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ሮሜ በረከተ አምላኩ የሀሉ ምስለ ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ወምስለ ንግሥትነ ወለተ ጊዮርጊስ ።

ለኵሉ ነፍስ መኰንን ተኰነኑ እስመ ኢይሠየም መኰንን ዘእንበለ እምኀበ እግዚአብሔር ወእምከመሰ እምኀበ እግዚአብሔር ውእቱ ኵሉ ብውሕ ሎቱ ። ወዘሰ ዐበየ ተኰንኖ ለመኰንን ትእዛዘ እግዚአብሔር ዐበየ ። ወእለሰ ዐበዩ ተኰንኖ ኵነኔ ያመጽኡ ለርእሶሙ ። ወመኳንንትኒ ኢኮኑ ግሩማነ ለዘይገብር ሠናየ ዘእንበለ ለዘእኩይ ምግባሩ ። ወእመሰ ትፈቅድ ኢትፍርሆሙ ለመኳንንት ግበር ሠናየ ። ወዓዲ እሙንቱ የአኵቱከ እስመ ላእካነ እግዚአብሔር እሙንቱ ከመ አንተ ትሠኒ ምግባሪከ። ወእመሰ ፈቀድከ ኢትፍራህ ግበር ሠናየ ወዘአከ ለከንቱ አኰነንዎሙ መጥባሕተ እስመ ላእካነ እግዚአብሔር እሙንቱ ከመ ይትበቀልዎ ለገባሬ እኪት ። ወይእዜኒ በግብር ተኰነኑ ሎሙ ወአኮ ዳዕሙ ለዘእኩይ ዓዲ ለዘሠናይኒ ምግባሩ።ወበእንተዝ ታገብኡ ሎሙ ጸባሕተ እስመ ላእካነ እግዚአብሔር እሙንቱ ። ወለዝ ግብር ተሠይሙ ወለኵሉ በዘይረትዕ ግበሩ። ወለዘሂ ጸባሕተ ጸብሑ። ወለዘሂ ብነተ በንቱ ። ወለዘሂ አሥራተ አሥሩ፤ወለዘሂ ፍርሃተ ፍርሁ፤ ወለዘሂ ክብረ አክብሩ። ሮሜ ፲፫ ፩ ፰ ።

ከዚህ በኋላ ሁለተኛው ዲያቆን ቀጥሎ ያለውን አነበበ።

መልእክተ ጴጥሮስ ቀዳማዊ በረከተ እምላኩ የሀሉ ምስለ ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ወምስለ ንግሥትነ ወለተ ጊዮርጊስ ።

አትሕቱ እንከ ርእሰክሙ ለኵሉ ፍጥረተ እጓለ እመሕያው በእንተ እግዚአብሔር ወለንጉሥኒ እስመ ኵሉ ሎቱ ወለመኳንንትኒ እስመ ውእቱ ይፌንዎሙ ከመ ይኰንንዎሙ ለእለ ይገብርዎ ለእኪት ወያአኵትዎሙ ለእለ ይገብርዎ ለሠናይት። እስመ ከመዝ ውእቱ ፈቃዱ ለእግዚአብሔር ከመ በሠናይ ምግባሪክሙ ትእሥሩ አፉሆሙ ለዓብዳን ሰብእ እለ ኢየአምርዎ ለእግዚአብሔር ፤ ወኩኑ ከመ አግአዝያን ወአኮ ከመ እለ በሙ ጌጋይ ዘእኩይ ወአንትሙሰ ከመ አግብርተ እግዚአብሔር ኵሎ አክብሩ፤ ወቢጸክሙኒ አፍቅሩ ፤ ለእግዚአብሔርኒ ፍርህዎ ወለንጉሥኒ አክብርዎ።፩ ጴጥሮስ ፪ ፲፫ ፲፯ ።

ከዚህም በኋላ አንደኛው ቄስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አነበበ። ነቅዐ ንጹሕ ዘእምአንቀዕተ ሕግንጹሐን በረከተ አምላከሙ የሀሉ ምስለ ንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ወምስለ ንግሥትነ ወለተ ጊዮርጊስ።

ወተንሥአ ጳውሎስ ወአዘዘ ያርምሙ ወይቤሎሙ ስምዑ ሰብአ እስራኤል ወእለኒ ትፈርህዎ ለእግዚአብሔር አምላከሙ ለሕዝበ እስራኤል ኀረዮሙ ለአበዊነ ወአዕበዮሙ ለሕዝቡ በኀበ አፍለሶሙ በምድረ ግብፅ ወበመዝራዕቱ ልዑል አውጽኦሙ እምህየ። ወሴሰዮሙ በገዳም ፵ ዓመተ ወአትተተ ሰብዓተ ሕዝበ ከነዓን ወአውረሶሙ ምድሮሙ።ወእምድኅረዝ ሤመ ሎሙ መሳፍንተ አርባዕተ ምእተ ወ፶ ዓመተ እስከ አመ ሳሙኤል ነቢይ። ወእምህየ ሰአሉ እንከ ያንግሥ ሎሙ ንጉሠ ወአንገሠ ሎሙ እግዚአብሔር ሳኦልሃ ወልደ ቂስ ብእሴ ዘእምነገደ ብንያም ፵ ዓመተ ወሰአሮ ኪያሁኒ፣ወእምድኅሬሁ አንገሠ ሎሙ ዳዊትሃ ወሰማዕተ ኮኖ ወይቤ ረከብክዎ ለዳዊት ወልደ ዕሤይ ብእሴ ዘከመ ልብየ ዘይገብር ኵሎ ፈቃድየ ወእምዘርአ ዚአሁ አምጽአ ሎሙ እግዚአብሔር መድኃኒተ ለእስራኤል ኢየሱስሃ በከመ አሰፈዎሙ።የሐዋ ፲፫ ፲፯ ፳፬ ።

ከዚህም በኋላ ጸሎተ ኪዳን ተደረሰ ።

ጸሎተ ኪዳን ከተጨረሰ በኋላ የላስታው መምህር ልብሰ መንግሥቱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ለሊቀ ጳጳሱ ሰጠ ። ሊቀ ጳጳሱም ከባረከው በኋላ መምህሩ ተቀብሎ ለኢትዮጵያ ሰሜን ጳጳስ ሰጠ ። ጳጳሱም ከጸለየበትና ከባረከው በኋላ መልሶ ለላስታው መምህር ሰጠ። መምህሩም እንደገና ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ መልሶ ሰጠ። ጳጳሱም ለንጉሠ ነገሥቱ አለበሰ ።

ከዚህ ቀጥሎ ከመዘምራኑ መካከል ዓሥር የሚሆኑ ድምጸ መልካሞች ተመርጠው ወደ መካከል ትንሽ ገባ ብለው ፊታቸውን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ አድርገው እንደ አርባዕት ዜማ ጕሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ እያሉ እየተቀባበሉ አዜሙ ።

ቅንት ሰይፈከ ኃያል ውስተ ሐቌከ በሥንከ ወበላሕይከ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ። በዚያ ጊዜ የተድባበ ማርያም መምህር ሰይፉን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለኢትዮጵያው የደቡብ ጳጳስ ሰጠ ።

ጳጳሱም አቤቱ አምላክ ሆይ ጸሎታችንን ትሰማ ዘንድ እንለምንሃለን አገልጋይህን ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴን በሥራው ሁሉ ምራው፤ ደግፈው በዚህም አሁን በሚታጠቀው ሰይፍ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሆኖ ክፉ አድራጎችን እንዲበቀልበትና እንዲቀጣበት ለመልካም አድራጎችም እንዲመክትበትና እንዲያጽናናበት አድርገው ። በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን ብሎ ከጸለየበትና ከባረከው በኋላ መልሶ ለተድባበ ማርያም መምህር ሰጠ። መምህሩም እንደገና ወስዶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ ሰጠ ።

ጳጳሱም የመከዳውን ጫፍ ለንጉሠ ነገሥቱ አሲዞ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ተናገረ ።

በዚህ ሰይፍ እውነተኛ ፍርድ ፍረድበት ።

የእግዚአብሔርን ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ጠብቅበት ። ልጆቻቸውና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ባልቴቶች አባትና እናታቸው የሞቱባቸውን ሕፃናቶች እርዳበት ። የተበላሸውን አድስበት፤ የታደሰውንም አፅናበት ።

ዓመፀኞችን ቅጣበት፤ ፈቃደኞችን ሹምበት፤ በዘመንህም ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አገልግልበት ፤ እንደዚህም ብታደርግ በሚመጣው በዘለዓለም ሕይወት መንግሥት ከርሱ ጋራ ትነግሣለህ አሏቸው ።

ንጉሠ ነገሥቱም ይህን የተናገሩትን ለመፈጸም ያብቃኝ እያሉ ተቀብለው በቀኝ ወገብ በኩል ታጠቁት ።

ከዚህም ቀጥለው መዘምራኑ አርትዕ ተሠራሕ ወንግሥ ብለው በትረ ጽድቅ ወበትረ መንግሥትከ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ። በዚያን ጊዜ የሐይቁ መምህር በትረ መንግሥቱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ ሰጠ ። ጳጳሱም በእጃቸው ይዘው ከዳዊት መዝሙር ፻፱ነኛውን ይቤሎ እግዚእ ለእግዚእየ ንበር በየማንየ የሚለውን በትረ ኃይል ይፌኑ ለከ እግዚአብሔር እምጽዮን ወትኴንን በማእከለ ጸላእትከ እስከሚለው ደግመው ከጸለዩበትና ከባረኩት በኋላ መልሰው ለሐይቁ መምህር ሰጡት ። መምህሩም እንደገና ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ ሰጠ ። ጳጳሱም በትረ መንግሥቱን ለንጉሠ ነገሥቱ በቀኝ እጃቸው አሲያዟቸው ።

ከዚያም ቀጥሎ የመርጡለ ማርያም መምህር ሉሉን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለኢትዮጵያ ምዕራብ ጳጳስ ሰጠ ። ጳጳሱም ጸሎተ ምናሴን መሐሪ ርኁቀ መዓት ወብዙኀ ሣህል እስከሚለው ድረስ ደግሞ ከጸለዩበትና ከባረከው በኋላ ለመርጡለ ማርያም መምህር ሰጠ ። መምህሩም ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለምዕራብ ጳጳስ ሰጠ ። የምዕራብ ጳጳስም ወስዶ ለንጉሠ ነገሥቱ ሰማይና ምድርን በእጁ የያዘ አምላክ ዲኸንን ሉል ይባርክልዎ ብሎ ሰጣቸው ። ንጉሠ ነገሥቱም ሉሉን በግራ እጃቸው ተቀብለው ያዙ ።

ከዚህም ቀጥሎ የጣና ቂርቆስ መምህር ሕልቀተ ወርቁን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለኢትዮጵያ ሐዜብ ጳጳስ ሰጠ ። ጳጳሱም ከጸለዩበትና ከባረከው በኋላ መልሶ ለጣና ቂርቆስ መምህር ሰጠ ። መምህሩም እንደገና ወስዶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ ሰጠ ። ጳጳሱም ለንጉሥነት ክብር የሚሆን ይህን ቀለበት ይቀበሉ ብሎ በቀኝ እጃቸው ባራተኛው ጣታቸው አደረገላቸው ።

ከዚህም ቀጥለው መዘምራኑ አርትዕ ተሠራሕ ወንግሥ ብለው አኅዝ ስሑል ኃያል ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚህም ጊዜ የደብረ ወገግ (አሰቦት) መምህር ጦሮቹን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለኢትዮጵያ ምሥራቅ ጳጳስ ሰጠ ። ጳጳሱም ንሣእ ወልታ ወኩናተ ወተንሥአ ለረዲኤትየ፥ በላ ለነፍሱ ረዳኢኪ አነ በበአቱ ወበፀአቱ ከመ ብንተ ዓይን ዕቀቦ ለንጉሥነ ኃይለ ሥላሴ ብሎ ከጸለየበትና ከባረከው በኋላ መልሶ ለደብረ ወገግ መምህር ሰጠ ። መምህሩ እንደገና ወስዶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለጳጳሱ ሰጠ ። ጳጳሱም ጦሮቹን ሲሰጠው ንጉሠ ነገሥቱ ከዳዊት መዝሙር ፵፬ኛውን እግዚኦ ሰማዕነ በእዘኒነ የሚለውን ወኩናትየኒ ኢያድኅነኒ ዘእንበለ የማንከ ወመዝራዕትከ ወብርሃነ ገጽከ እስከሚለው ደግሞ ጦሮቹን ተቀበለ ።

የንጉሠ ነገሥቱም ጋሻ ጃግሬ ሁለቱን ጦሮች ከንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሎ ያዘ ።

ከዚህም ቀጥለው መዘምራኑ አፍቀርከ ጽድቀ ወዓመፃ ጸላእከ ብለው ከርቤ ወቀንዓት ወሰሊሖት እምነ አልባሲከ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚያም ጊዜ የደብረ ሊባኖስ ፀባቴ ቀርን ቅብዑን ከጠረጴዛው ላይ አንሥቶ ከሊቀ ጳጳሱ አስባርኮ ለኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ሰጠ ። ጳጳሱም ቀርን ቅብዑን በእጁ እንደያዘ ለሊቀ ጳጳሱ አቅርቦ ሊቀ ጳጳሱም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለየ ።

ቅዱስ አምላክ ሆይ ከተቀደሰው መንበረ መንግሥትህ ከማይወሰነውም ሥልጣንህ ከዘላለሙ ጌትነትህ የሚያፅናናውን መንፈስ ቅዱስን(ጰራቅሊጦስን)በዚህ ቅብህ መንግሥት ላይ ላክ ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በዚህ በተቀደሰው ቅብዐ መንግሥት ተቀብቶ የከበረና የተቀደሰ ይሆን ዘንድ በጽድቅህም ብርሃን መጐናጸፊያ ተጐናጽፎ የሚቃወሙትን የመንግሥቱን ጠላቶች ያሸንፍ ዘንድ ኃይሉን አበርታው ።

አንተንም ደስ በሚያሰኙህ በቅዱሳን ነገሥታት መካከል እንደሰማይ ከከብ ያበራ ዘንድ ጸጋህን ስጠው ።

ቅዱስ አማላክ ሆይ የብሉይ ነገሥታት፥ካህናት፡ ነቢያትም፥ ሕዝብህን እስራኤልን እንዲገዙና እንዲያስተምሩ በተቀደሰ ቅብዕ እንደቀባሃቸው አሁንም በዚያው ልማድ አንተ የመረጥ-ከውን አገልጋይህን ኃይለ ሥላሴን ባርከው ቀድሰው ።

ለኛም በሰጠኸን ሥልጣን ቅብዐ መንግሥቱን ተቀብቶ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይሆን ዘንድ ኃይልን ስጠው በመንፈስህም አበርታው ፤ የጥበብና የማስተዋል ፤ የምክርና የኃይል፥ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ አሳድርበት፥ ከሁን ጀምሮ ለዘለዓለም አሜን ብሎ ሲጨርስ ለሊቀ ጳጳሱ አቀረበለት ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱ ከቅብዐ መንግሥቱ በአውራ ጣቱ እየጠቀሰ ሳሙኤል ዳዊትን ፤ ሳዶቅና ናታን ሰሎሞንን እንደቀቡ እኔም በዚህ በተቀደሰውና በተባረከው ቅብዐ መንግሥት እቀባዎታለሁ ብሎ የንጉሡን ራስ ይቀባል ። ቀጥሎም በእንተ ንጉሥ የሚለውን መስተብቍዕ ደግሞ ወተናገር ጽድቀ በውስተ ልቡ ከሚለው ሲደርስ ደረታቸውንና ልባቸውን ቀባ ።

ከዚህም ቀጥለው መዘምራኑ እምከቡዳነ አቅርንት ዘእምኔሆሙ አስተፌሥሐከ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚህም ጊዜ ከአክሱም መምህር ቁምስና ያለው ዘውዱን ከጠረጴዛ ላይ አንሥቶ ለሊቀ ጳጳሱ አቀረበ ።

ሊቀጳጳሱም ከዳዊት መዝሙር ፳ኛውን እግዚኦ በኃይልከ ይትፌሣሕ ንጉሥ የሚለውን እስከ መጨረሻው አንብቦ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለየ ።

አቤቱ የታመንህ አምላካችን ሆይ ይህን ዘውድ ትባርክ ዘንድ እንለምንሃለን ። ይህንንም አገልጋይህን ንጉሣችንን ኃይለ ሥላሴን ዘውዱን ለመቀበል የበቃና የተዘጋጀ እንዲሆን ቀድሰው ። ይህንንም ከጥሩ ወርቅ የተሠራውን ዘውድ እንደ ጫንህለት በቸርነትህ ብዛት የበጎነትን ዘውድ በልቡ ጫንለት በዘለዓለሙ ንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አሜን ።

ከዚህም በኋላ ወደ ንጉሡ ቀርቦ እግዚአብሔር ይህን ዘውድ የጽድቅና የምስጋና ዘውድ ያድርግልዎ።በዚህም በእኛ ቡራኬ የቅና ሃይማኖትና መልካም ምግባር ይዘው የዘለዓለም መንግሥቱን ዘውድ ለማግኘት ያብቃዎ አሜን እያሉ ዘውዱን ጫኑላቸው ።

ንጉሡም ቅብዐ መንግሥቱ ተቀብተው ዘውድ ከጫኑ በኋላ እንደቆሙ ከባቢት መዘሙር ንዑስ አነ እምኃውየ የሚለውን ወቀብዐኒ ቅብዐ ቅዱስ እስከሚለው በታላቅ ድምጽ እንባበው ተቀመጡ ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱና ጳጳሳቱ ወደንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ሊቀ ጳጳሱ እንዲህ ብለው ተናገሩ ። ግርማዊ ኃይለሥላሴ ሆይ።

ዛሬ በፊትዎ የታመንሁና እውነተኛ እሆናለሁ ሃይማኖትና እውነትም ፤ይመሰክሩልኛል ። ከኔም ጋራ ያሉት ጳጳሳትና ሥልጣንም የሰጧቸው ቀሳውስትና ዲያቆናት እንደ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ለመንግሥትዎ እንዲታዘዙና ቤተ ክርስቲያንንም እንዲጠብቁ አደርጋለሁ ።

ለዚህም ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል በክንድዎ ላይ ሆኖ ይርዳዎ ብለው የንጉሠ ነገሥቱን ቀኝ ትከሻቸውን ሳሙ ።

የቀሩትም ጳጳሳት መስቀል አሳልመው እግዝእትነ ማርያም ብረድኤት አትለይዎ እያሉ እጅ ነሥተው ተቀመጡ ።

ከዚህም ቀጥሎ ሕልጋ ወራሹ የራስ ወርቁን (አክሊሉን) አውልቆ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ በጉልበቱ ተንበረከከ ። ወዲያው ሊቀ ጳጳሱ ቀርበ አልጋ ወራሹን ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጥያቄ ጠየቀ ።

ሊቀ ጳጳሱ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ለአባትህ በሕይወትህ ሁሉ አገል ጋይ ለመሆን ትፈቅዳለህን ።

አልጋ ወራሹ።አክብር አባከ ወእመከ የተባለውን ትእዛዝ ሰምቻ ለሁና በፍጹም ልቤ እገዛለሁ ።

ሊቀ ጳጳሱ። እንደ አቤሴሎም ደፍረህ፤እንደ አዶንያስ ቸኩለህ ከአ ባትህ ፈቃድ ለመውጣት ያልሰጠህን ለመሻት ከሚመክሩህ ጋር እንዳት ተባበርና እንዳትከተል አጥብቀህ ትጠነ ቀቃለህን ።

አልጋ ወራሹ።ከአባቱ ፈቃድ የሚወጣ የተረገመና ሞት የሚ ገባው መሆኑን ሰምቻለሁና ይኸንን በመሰለው መንገድ አባቴን እንዳላስቀይም እጠነቀቃለሁ።

ሊቀ ጳጳሱ። አባትህ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቅዶ በምክር ቤት አስመ ክሮ ያቆመውን ሕግ ከክፉ ሰዎች ጋራ ተቀላቅለህ እን ቅፋት ሳትሆን ለሕግ ፈቃደኛ ለመሆን ትወዳለህን።

አልጋ ወራሹ። ንጉሠ ነገሥቱ አባቴ ተቀብሎ ያቆመውን ሕግ አክብሬ ለመጠበቅ እውነተኛ ፈቃዴ ነው ብሎ ቃሉን ሰጠ። ወዲያውም ቃሉ በተጻፈበት ደብተር ላይ ፊርማውን ፈርሞ ያባቱን የንጉሠ ነገሥቱን ጉልበት ሳመ ።

ከዚህም ቀጥሎ ንጉሠ ነገሥቱ ፡ እግዚአብሔር የኃይሌና የሥልጣኔ የዙፋኔና የዘውዴ ተቀባይ ያድርግህ ብሎ በትረ መንግሥቱን የያዘበትን ቀኝ እጁን ዘረጋበት ።

አልጋ ወራሹም ። አሜን እግዚአብሔር እንደቃልዎ ያድርግልኝ ብሎ ቀኝ እጃቸውን ተሳልሞ አክሊሉን አድርጎ ወደ መቀመጫው ተመለሰ ።

ከዚህም ቀጥሎ መሳፍንቱ ሁሉ የራስ ወርቃቸውን እያ ወለቁ በየራሳቸው እየሆኑ እጅ ነሡ ።ሚኒስትሮችና መኳ ንንቶችም ሌላውም በንጉሡ ሰፍራ የተቀመጠው ሁሉ እየ ተነሣና እየቆመ ሺህ ዓመት ያንግሥዎ እያለ እጅ ነሣ ። ሕዝ ቡም ሁሉ አጨበጨበ ።

ወዲያው የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ሂም ናሲዮናል ተነፋ ቀጥሎም መድፍ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

የእቴጌ እነጋገሥ ።

የንጉሠ ነገሥቱ ሥርዓተ ንግሥ ከተፈጸመ በኋላ መዘ ምራኑ አዋልደ ንግሥት ለክብርከ ወትቀውም ንግሥት በየ ማንከ ብለው በአልባሰ ወርቅ ዑጽፍት ወኅብርት ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚያም ጊዜ እቴጌይቱ ከቆዩበት ስፍራ ልብሰ መን ግሥታቸውን እንደለበሱ ተነሥተው በስተኋላና በስተፊት በብዙ ወይዛዝርት ታጅበው በንጉሡ ቀኝ በተዘረጋላቸው የወርቅ ወምበር ተቀመጡ ።

ከነዚህም የመንግሥት ዘር የሆኑት ወይዛዝሮች አክሊላቸ ውን ሳያደርጉ የማዕርግ ልብሳቸውን ብቻ እንደለበሱ በእቴጌ ኋላ ቆመው ቆዩ ።

ከዚህም በኋላ መዘምራኑ ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ብለው አፅምዒ ዕዝነኪ ... እስመ ፈተወ ንጉሥ ሥነኪ እስመ ውእቱ እግዚእኪ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚያም ጊዜ የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ባለአልማዝ ቀለበት ከጠረጴዛው ላይ አንሥተው የሃይማኖት ምልክት የሚሆን ይህን ቀለበት ይቀበሉ በዚህም ቀለበት ምልክትነት ሥልጣን ሁሉ ገንዘቡ የሚሆን እግዚአብሔር ክብርዎን ያብዛልዎ፥ ሁል ጊዜም ፍጹም እንዲሆኑ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በልብዎ ያሳድርብዎ፥ ሁልጊዜም እሱን ደስ የሚያሰኝ ሥራ ለመሥራት ያብቃዎ እያሉ በቀኝ እጃቸው ባራተኛዋ ጣታቸው አደረጉላ ቸው ።

ከዚህም ቀጥሎ ሁለት ቆሞሳት የእቴጌይቱን ዘውድ ከነ ጠረጴዛው አንሥተው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት አቀረቡ ። በዚህም ጊዜ ሊቀ ጳጳሱ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀርበው ቆሙ ። ንጉሠ ነገሥቱም ዘውዱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥተው እኔ ከእግዚአብሔር የተፈቀደልኝን ዘውድ ከርስዎ እጅ እንደ ተቀበልሁ፤እቴጌይቱም ይህን ዘውድ ከኔ ተቀብላ የክብሬ ተካፋይ እንድትሆን እውነተኛ ፈቃዴ ነውና ዘውዱን እርስዎ እንዲ ጭኑላት ብፁዕነትዎን እለምናለሁ አሏቸው ። ሊቀ ጳጳሱም ዘውዱን ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተቀብለው ይዘው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ጸሎት ጸለዩ ።

አቤቱ አምላካችን ሆይ በአገልጋይህ በእቴጌ መነን ላይ ይህን የደስታና የክብር ዘውድ አኑር፥ ይኸውም የቸርነትና የርኅራኄ የእውቀትና የጥበብ ዘውድ ይሁንላቸው ።

አቤቱ ቅዱስ አብ ሆይ የክብር የምስጋናም ዘውድ አድ ርግላቸው አሜን ።

ጸሎቱንም ሲጨርሱ ይህን የደስታና የክብር ዘውድ ይቀ በሉ ። ይህን የወርቅ ዘውድ እንደጫኑ እግዚአብሔር በል ብዎ እርሱን የሚፈሩበት ንጉሠ ነሥቱን የሚያከብሩበት ዘውድ ይጫንልዎ ብለው ዘውዱን ጫኑላቸው ።

እቴጌይቱም ዘውዱን ከጫኑ በኋላ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ቀር በው በንገት እጅ ነሥተው በወርቅ ወምበራቸው ላይ ተቀመጡ።

ከዚህ በኋላ በዚያው ስፍራ የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ይበጅ ያድርግ እያሉ በየቆሙበት ሆነው እጅ ነሡ ።

ሴቶች፤ወይዛዝሮችም ዕልል እሉ ካህናቱም አክሊለ ተቀጸላ ታንሶሱ የሚለውን ወርበው በክብሮና በጸናጽል ደስታቸውን ገለጹ ።

ከዚህ ቀጥለው መዘምራኑ ወይሰግዱ ሎቱ አዋልደ ጢሮስ በአምኃ ብለው ወያበውእዎን ውስተ ጽርሐ ንጉሥ ከሚለው ሲደርሱ ዝም አሉ ።

በዚያም ጊዜ የመንግሥት ዘር የሚሆኑት አራት ወይዛዝር ለእቴጌይቱም በአንገት እጅ ከነሱ በኋላ አክሊላቸውን እያደረጉ በእቴጌይቱ ኋላ በተዘጋጀላቸው ወምበር ተቀመጡ ።

ከዚህ በኋላ አሥሉስ ቅዱስ መሐረነ ተብሎ ዲያቆኑ እስመ በጸሕኮ በበረከት ሠናይ።ወአንበርከ አክሊለ ዲበ ርእሱ ዘምዕንቍ ክቡር ። ሐዩ-ወ ሰአለከ ወሀብኮ ብሎ ሰበከ ።

ቀጥሎም የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ወንጌል አነበቡ ።

ወንጌል ዘማቴዎስ ። ወእምዝ ሖሩ ፈሪሳውያን ወተማከሩ ከመ ያስሕትዎ በቃሉ ወፈነዉ ኀቤሁ አርዳኢሆሙ ምስለ ሰብአ ሄሮድስ ወይቤልዎ ሊቅ ነአምር ከመ ራትዕ አንተ ወበጽድቅ ትሜህር ፍኖተ እግዚአብሔር ወኢተሐስብ መነሂ ወኢታደሉ ለገጸ ሰብእ ንግረነኬ እንከ ዘይረትዕ ይከውንሁ ውሂበ ጸበሕተ ዲናር ለንጉሥ ወሚመ ኢይከውንኑ ወአእመሮሙ እግዚእ ኢየሱስ እከዮሙ ወይቤሎሙ ምንተ ታሜክሩኒ መደልዋን አርእዩኒ እላደ ዲናሩ ወአምጽኡ ሎቱ ዲናረ ወይቤሎሙ እግዚእ ኢየሱስ ዘመኑ ዝንቱ መልክዑ ወጽሕፈቱ ወይቤልዎ ዘንጉሢ ወይቤሎሙ ሀቡ ዘንጉሢ ለንጉሢ ወዘእግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ወሰሚዖሙ አንከሩ ወኅደግዎ ወሖሩ ። ማቴዎስ ፳፪ ፲፭ ፳፪።

የወንጌሉንም ቃል የኢትዮጵያ ምዕራብ ጳጳስ ባጭሩ አድርገው ባማርኛ ተረጐሙ ።

ከዚህም በኋላ ሊቀ ጳጳሱ የፓትርያርኩን የአቡነ ዮሐንስን የቡራኬ ቃል በዐረብኛ ከተናገሩ በኋላ አስተርጓሚው ቀጥሎ እንደተጻፈው በአማርኛ አነበቡ ።

በስም ፲፱ነኛ በቅዱስ ማርቆስ መንበር ለተቀመጡት ፻፲፫ተኛ ፓፓና ፓትሪያርክ ዮሐንስ ።

እምቅድመ ዓለም በጌትነቱ በአምላክነቱ ብቻሙን የሆነ በአካል ሶስት የሆነ የውነተኛ አምላክ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ የሥሉስ ቅዱስ በረከት ምሉእነትና የእግዚአብሔር ጸጋ በላይኛይቱ ጽዮን ላንጹሐን ሐዋርያት የተሰጠ ሰላሙ ይህ ሁሉ በፍጹም እግዚአብሔርን በሚፈሩ ልዕልናና ክብራቸው ከፍ ከፍ ባለ በእግዚአብሔር ወዳጅ በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ ይደሩ ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኢትዮጵያን መንግሥት ዘውድ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ የጫኑ የውነተኛይቱን እምነት አደራ ጠባቂ የኦርቶዶክሳውያንን ቤተ ክርስቲያን ክብር በመጠበቅ የቆሙ ልዑል እግዚአብሔር የግርማዊነታቸውን ሰውነት በእምላክነቱ አጥር ውስጥ ይጠብቃቸው። የሰማይም መላእክት መልካም ሰውነታቸውን ዙሯቸውን ከበው ይጠብቋቸው፤ በኀኑትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ፍርድ ማስተካከል እምነት በመንግሥታቸውና በሃገራቸው የተዘረጋ ይሁን።ልዑል እግዚአብሔር የተባረኩትን ግርማዊት መነንን በቀኝ እጁ ይጠብቅ፤የተከበሩትን ሀብታሞቹን ልጆቻቸውን ይጠብቅ።በአባታቸው ጥላ ውስጥ ክብርን ሀብትን ይጨምርላቸው፤ሁለተኛውንም ደስ የሚያሰኘውን ረጅሙን የጤና ዕድሜ ይስጣቸው። ራሶችና ሚኒስቴሮችን የመንግሥቱን ሹማምቶች በታመነው ግርማዊነታቸው ጥላ ስር ዕድሜያቸውን አቆይቶት ደስታና ጤና ሰላምና ክብር ይስጣቸው ። የመንፈስ ቅዱስ በረከት የኢትዮጵያን መንግሥት በመላ ያደርሱ ይሁን ። በግርማዊ ሰውነታቸው ዕድሜ ከመርዘም ጋራ ኢትዮጵያንም ስጦታዋንና ክብሩዋን ለዘለዓለም ያቆያት ።በቅድስት ንጽሕት እመቤታችን በድንግል ማርያም አማላጅነት በእስክንድርያ ሐዋርያ በቅዱስ ማርቆስ በብፁዓን ሐዋርያት በንጹሐን ቅዱሳን በባለ አክሊሎች ሰማዕታት በእውነተኞች ጻድቃን አማላጅነት አሜን ።

ንጉሠ ነገሥት ሆይ የእግዚአብሔር ጸጋ ለርስዎ ይሁን። የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ የአባታችን የእግዚአብሔር አብ ሰላም ለርስዎ ይሁን ። እኔም በየጊዜው ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ ። በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋን ላይ የመውጣትን ጸጋ እግዚአብሔር ስለ ሰጠዎ ልባችንንም ደስታ የመላው ይባቤ የከበረው ነገር ይህ ነው ።

እኛንም ወንድሞቻችንንም ጳጳሳትን ኤጲስቆጶሳትን የቤተ ክርስቲያናትንም ሰዎች ማኅበሩን የሚገኘውንንም ኦርቶዶክሳውያን ሕዝብ በምድረ ግብፅ እጅግ ደስ አለን ።

ስለዚህም እኛም ደግሞ ይኸንን ዋና ታላቅ ከፍ ማለትን ከሰማን ቀን ጀምሮ ስለ እናንተ እንጸልያለን እንለምናለንም ።

ከመንፈስ ቅዱስ እውቀትን ጥበብን አእምሮን ሁሉ በፈቃዱ እንዲመላችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባው በሚወደው ሁሉ አካሔድ እንድትሔዱ በነ ሥራችሁ ሁሉ ያፈራ ሆኖ የእግዚአብሔር ዕውቀት አድሮባችሁ ሁሉን የሚችል አምላክ ጸጋውን ከሱ ዘንድ እንዲሰጣችሁ የተቀደሰውን ስሙን ታመሰግኑ ዘንድ እኔም በሥጋ ከናንተ የራቅሁ ብሆን እንኳ በመንፈስ ከናንተ ጋራ ነኝ ደስ እያለኝ የአካሔዳችሁን መልካምነት በኢየሱስ ክርስቶስ የእምነታችሁን ጽናት እመለከታለሁ። በዳዊት በነቢዩ የተናገረው የእግዚአብሔር እጁ በንጉሥ ልቡ ላይ ነው እንዳለው ልባችሁን የገዛት ይሁን ። ዋና የሆነች መንግሥታችሁን የምታዘጋጁበትን ጥበቡንና በረከቱን እግዚአብሔር ሰላሙን ያሳድርባችሁ ።

እኔም ደግሞ ለግብፃውያን ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያን ፍቅራችሁ ለዘለዓለሙ እየጨመረና እየበረታ መሔዱን በእውነት አውቃለሁ።ደግሞም ወደ ፊት በመጨረሻው በግብፃውያን ኦርቶዶክሳውያን ቤተ ክርስቲያንና በልጅዋ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ዋና የበረታ የጸና ፍቅር ይሆናል ። ደግሞም ለዘለዓለሙ የኢትዮጵያ መንግሥት በናንተ እጅ እንደሆነች ለዘወትር መልካም ዝናችሁን ደስ በሚያሰኝ ነገር እንድንሰማ እወዳለሁ ። ሁሉንም የሚችል እግዚአብሔር

ብጸጋው ክብሩን ከፍ አድርጎ በጣሙን እስኪያሰድጋት ድረስ ኃይሉን እውቀቱን እ^ዚአብሔር ይስጣችሁ ። ኢትዮጵያ እን ድታድግ ከፍ እንድትል ለዘለዓለሙ ትሁሩ ዘንድ ክብርና ም ስጋና ለተቀደሰው ስሙ ይሁን ።

ይህችም የበረከት ቃል ከኔ ከታናሹ በስም ከ፲፱ ነኛው ዮሐንስ በእግዚአብሔር ጸጋ የሐዋርያው የእ^ክንድርያ መን- በር ፓፓና ፓትረያርክ የተጻፈች ነች ።

የሥሉስ ቅዱስ በረከት በግርማዊነትዎ ላይ ትደር ።

እንደዚሁም ሁሉ የሥሉስ ቅዱስ በረከት በባለቤትዎ ብግርማዊት መነን ላይ ይደር ። በልዑላን ልጆችዎም ላይ ይደር ብመንግሥታችሁም ላይ እግዚአብሔር የነቢዩን የዳዊትን መን ግሥት መንበር እንዳፀና ሁሉ አልጋችሁን ያፅናው ። በጌትነቱ ይጠብቃችሁ ።

በኛም በታናናሾቹ አፍ ከተሠራ ኃጢአታችሁ የተፈታችሁ የተባረካችሁ ሁኑ ክብርና ምስጋና ለዘለዓለሙ ለርሱ ይሁን ።

ከዚህ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ደቡብ ጳጳስ ተነሥተው ጸጋ ዘአብ ጊሩት ዘወልድ ሱታፌ ዘመንፈስ ቅዱስ የሚለውን የቡ- ራኬ ቃል እስከ መጨረሻው ተናግረው አሳርገውና ባርከው ተቀመጡ ።

በዚህም ጊዜ ሊጋባውና ጸሐፌ ትእዛዙ ወደ አዋጅ መንገሪያው ሒደው የንጉሠ ነገሥቱን ያዋጅ ቃል ተናገሩ ።

ከዚህም በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴ ተጀመረ ። ንጉሡና ንግ- ሥቲቱም ከወምበራቸው ላይ እየተነሡ ዘውዳቸውን እያወለቁ ብጠረጴዛ ላይ አስቀመጡ ። የላይኛውንም ልብሰ መንግሥታቸ- ውን አውልቀው ሌላ የሥጋ ወደሙ መቀበያ ልብስ ለበሱ ።

ሥጋ ወደሙ ከተቀበሉና ጸሎተ ቅዳሴው ከተጨረሰ በኋላ እንደገና ልብሰ መንግሥታቸውን ለብሰው ዘውዳቸውን ጭነው ብትረ መንግሥታቸውን ይዘው ሉሉን ጨብጠው ወጡ ። ጳጳሳቱና ቀሳውስቱ ታቦቱን አውጥተው ሕዝቡ ሁሉ የሰሌን ቅጠል በእጁ እየያዘ መዘምራኑም ቡሩክ አንተ ንጉሠ እስራ- ኤል እያሉ እየወረቡ በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅበው በ- ቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያ ዑደት ተደረገ ።

ከዑደትም በኋላ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ከፍ ብሎ በተሠራው ስፍራ ላይ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ብቻ ቆመው ለሕዝብ ታዩ ። በዚያ ጊዜ ወንድ ወንዱ በማጨብጨብ ሴት ሴቱ በዕልልታ ደስታቸውን ገለጹ ።

ከዚህም በኋላ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ በወርቅ ሠረ- ገላ ተቀምጠው በፊት በኋላ በመሳፍንትና በመኳንንት ታጅ- በው በወታደሩ ሰልፍ መካከል አለፉ ።

በየመንገዱም ዳር ለማየት ለተሰበሰበው ሕዝብ በእንገት ሰላምታ እየሰጡ ሲያልፉ ሕዝቡ ሺህ ዓመት ያንግሥዎ እያለ አጨበጨበ ።

ወደቤተ መንግሥቱም በደረሱ ጊዜ ለማሰናበቻ በተዘጋ- ጀው ስፍራ ላይ ቁመው በእንገት ሰላምታ ሰጥተው አሰና- በቱ ።

መሳፍንቱና መኳንንቱም ሕዝቡም ሁሉ እንደገና አጨ ብጭበ ሺ ዓመት ያንግሥዎ እያለ ተሰናበተ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት ።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መስክረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ ያመሰለ ነው ።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል ። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል ። ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ባታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- በላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው ። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው ። ሐኪም አምባር

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

. አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፊ ፊርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቲ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኗ፥ ሳ፥

ሜር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበኋል ።(ቤታቸውም ብአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፭ 6 ne ANNÉE № 45		ሐሙስ ኅዳር ፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ። JEUDI 15 Novembre 1930

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለደረክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መፃዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የሐውልት ምረቃ ።

በጥቅምት ፳፱ ቀን የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት የሚገለጥበት ቀን ነበር ። ከጧቱ ፩ሰዓት ሲሆን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና እቴጌ መነን ፥ ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስና ጳጳሳት ፥ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮች፤የውጪ አገር መንግሥታት መልእክተኞችና ሚኒስቴሮች፥ ቆንስሎችና ሌሎችም የዲፕሎማቲክ ሰዎች ሁሉ ነበሩ ። ወታደሩም በየመንገዱ ዳር ግራና ቀኝ ሁኖ ተሰልፎ ነበር ። ሊቀ ጳጳሳቱና ጳጳሳቱ ጸሎት አድርገው ባርከው ጃንሆይም የተናገሩትን ዲስኩር በሚከተለው እናስታውቃለን ። ሐውልቱ በኢትዮጵያ ባንዲራ ተሸፍኖ በ፩ቱ ማዕዘን ፩ቱ መሐንዲሶች ይዘውት ነበርና በመጀመሪያ ጃንሆይ ገለጡትና ተጨበጨበ። ሐውልቱም ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒክ በፈረስ ሁነው ዘውዳቸውን ደፍተው፥ላንቃ እንደለበሱ ሁነው ወርቅ በመሰለ ነሐስ የተሠራ ነው ። በዚሁ ቦታ ላይ ፩ሻላ ነበረበት ይኸውም ሾላ አሾላው ድረስ እንገናኝ እያለ ሕዝብ ተቃጥሮ የሚገናኝበት ከድካሙ የሚአርፍበት ነበር። ዛሬም ኢትዮጵያንና አይሮፓን ያገናኙ ሕዝቡንም ከብዙ ድካም ያሳረፉ የኢትዮጵያ ሾላ የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ስለቆመበት ዕድለኛ ቦታ መሆኑ እጅግ ያስደንቃል ።

የንጉሠ ነገሥት የዘውድ በዓል ።

አስቀድመን እንዳስታወቅነው በጥቅምት ፳፫ ቀን ጃንሆይ የንጉሠ ነገሥቱን ማዕርግ ተቀብለው የሚነግሡበት ፥ እቴጌ መነንም የእቴጌነትን ማዕርግ ተቀብለው የሚነግሡበት፥ልዑል አስፋ ወሰንም የአልጋወራሹን ማዕርግ የሚቀበሉበት ቀን ነበርና ቅዳሜ ማታ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሒደው አደሩ ። በዚያውም ሌሊት ጳጳሳቱና መምህራኑ መነኰሳቱ በጸሎት ፡ መዘምራኑ በማኅሌት አድረው አንድ ሰዓት ሲሆን ሊቀ ጳጳሱና ጳጳሳቱ ፥ ካህናቱ፥ መምህራኑ ዘውዱን ይዘው በግብዕ ቋንቋ ሊቀ ጳጳሱና የቀሩት ግብፃውያን እየዘመሩ ከመቅደስ በልዩ አምሮ ወደ ተሰናዳው የመናገሻ ቦታ ይዘውት ገቡ። ጃንሆይና እቴጌ በወርቅ አጕበር ውሥጥ ከወርቅ በተሠራው

መንበረ ዳዊት አስቀድመው ተቀምጠው ነበር ። የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ሁነው የሚቀበሉት ልዑል አስፋወሰንም ከጃንሆይ ዙፋን በግራ ወገን ተቀምጠው ነበር ። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮች ፥ የውጪ አገር መንግሥታት ታላላቆች መልእክተኞችና ሚኒስቴሮች ፥ ቆንስሎች ሁሉ በወርቅ የተንቈጠቈጠ የማዕርግ ልብሳቸውን እየለበሱ ገብተው አምሮ በተሰናዳላቸው ቦታ ግራና ቀኝ ሁነው ተቀመጡ ። ታላላቆች የኢትዮጵያ ወይዛዝርም ከእቴጌ መንበረ ዳዊት በቀኝ ወገን ተቀምጠው ነበር ። ከዚህ በኋላ በጃንሆይና በእቴጌ መንን መልክ የታተመ የወርቅና የብር ሜዳይ በየ ዕድሉ ታደለ ። ከ፩ሰዓት እስከ ፫ሰዓት ለዘውድ ጊዜ የሚገባውን ጸሎት ጨርሰው መጀመሪያ ሰገባው በወርቅና በአልማዝ ያጌጠ ወርቅ የተሠራ ሰይፍ አስታጥቀው ። ፪ኛ፡ ከወርቅ የተሠራ ዘንግ (ኅለተ ወርቅ) ፫ኛ ሉል አሲዘው ፬ኛ፡ ባለ አልማዝ ቀለበት ፥ ፭ኛ ሁለት ከወርቅ የተሠሩ ጦሮች ፮ኛ፡ ልብሰ መንግሥት አልብሰው ቅብዐ መንግሥት ቀብተው በወርቅና በአልማዝ የተሠራውን ዘውድ ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ከአቡነ ሳዊሮስ ተቀብለው በጃንሆይ ራስ ላይ ጫኑላቸው በዚያጊዜ በውሥጥ ያሉት መኳንንትና ሠራዊት በጨበጨቡ ጊዜ በውጪ ካለው ወታደርና ሕዝብ ሰምቶ በከተማው መንገድ ዳር ዳር የነበረው ሁሉ አጨበጨበ ከዚህ በኋላ ከእንግሊዝ መኳንንት ጋራ የመጡ በመርከብ ሙዚቃ የሚነፉ የእንግሊዝ ጉበዛዝት የኢትዮጵያን ሙዚቃ ነፉ። የኒህ ጉበዛዝት አለባበስና መተባበር እጅግ የሚአምርና ደስ የሚአሰኝ ነበር ። ልዑላን መኳንንትም አክሊላቸውን እያወረዱ የውጪ መንግሥታት መልእክተኞችም እንዲሁ እያደረጉ ሺህ ዓመት ያንግሥዎ እያሉ ሰገዱ ። ጃንሆይም ከመንበረ ዳዊቱ ተነሥተው ቁመው ንዑስ አንእምአኃውየን ከዳዊት መዝሙር በቃላቸው አንብበው በመንበረ ዳዊቱ ላይ ተቀመጡ። ከዚህ በኋላ ልዑል አስፋወሰን ከአባታቸው ፈቃድ ላይወጡ ቃል ኪዳን ገብተው የአልጋ ወራሽነትን ማዕርግ ተቀበሉ ።

ከዚህ በኋላ የእቴጌ ሥርዓተ ንግሥ ተጀመረ ። መዘምራኑ አዋልደ ንግሥት ለክብርከ ወትቀውም ንግሥት በየማንከ እያሉ ዘመሩ ። ቀጥለውም ስምዒ ወለትየ ወርእዪ ወአፅምዒ እዝነኪ እስመ ፈተወ ንጉሥ ስነኪ እስመ ውእቱ እግዚእኪ ካሉ በኋላ ቆሞሳቱ የእቴጌን ዘውድ ከነጠረጴዛው ወደ ጃንሆይ ይዘውት ቀረቡ። ጃንሆይም ዘውዱን ከጠረጴዛው ላይ አንሥተው እኔ ከእግዚአብሔር የተፈቀደልኝን ዘውድ ከርስዎ እጅ እንደተቀበልሁ እቴጌይቱም ከእኔ ተቀብላ የክብሬ ተካፋይ እንድትሆን እውነተኛ ፈቃዴ ነውና እርስዎ እንዲጭኑላት ብፁዕነትዎን እለምናለሁ ብለው ለሊቀ ጳጳሱ ሰጥተዋቸው የተዘጋጀላቸውን ቅብዐ መንግሥት ቀብተው በወርቅና በአልማዝ የተሠራውን ዘውድ ሊቀ ጳጳሱ ለእቴጌ መንን ጫኑላቸው ለጃንሆይ ዘውድ ከጫኑላቸው ጀምሮ እስከ እቴጌ ዘውድ መጫን ድረስ መቶ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ጭብጨባውም ከመናገሻው ግቢ ጀምሮ እስከ ውጪ ፥ ከውጪ ጀምሮ በየመንገዱ ዳር እስከ አለው ሕዝብ ሁሉ ደመቀ ። ልዑላን መኳንንትም አክሊላቸውን እያወረዱ ሺሕ ዓመት ያንግሥዎ እያሉ ሰገዱ። የሮፓ መኳንንትም መለዮአቸውን እያወረዱ ሺሕ ዓመት ያንግሥዎ አሉ ። ከውጪ አገር የመጡ እንግዶች አይሮፕላኖችና የእኛ አይሮፕላኖች በሰማይ ሲዘምሩ ሺሕ ዓመት ያንግሥዎ መንግሥዎትን ሰላም አገርዎን ለምለም ያድርግልዎ የሚሉ ይመስል ነበር ። የራሶችና የደጃዝማቾች፥ የሚኒስቴሮች ልብስ ልዩ ልዩ ነበር ። ራሶች ልዑል ራስ ካሣ ፥ ልዑል ራስ ኃይሉ ልዑል ራስ ሥዩም ልዑል ራስ ጉግሣ እጅግ የሚያምር አዲስ ዓይነት ልብስ ለብሰው ጥሩ ጥሩ የወርቅ አክሊል ደፍተው እጅግ ያምሩ ነበር። ከወይዛዝሩም ወ አሰለፈች ል ተናኝ ወር ወ ዓፀደ ፥ የወ አክሊል ደፍተው ሚኒስቴሮችም በወርቅ የጠለቀ ከላይ እንደ ካባ ያለ መደረቢያ ያለው ኮት ለብሰው የማዕርግ ልሻናቸውን አድርገው እጅግ ያምሩ ነበር ። ደጃዝማቾችም እንደሁ በወርቅ የጠለቀ ለምድና ልዩ ልዩ ሁኖ የተሠራ የአንበሳ ጋማ አሥረው ነበር ። የነጋሪቱም ድምፅ ገብር ገብር ሲልመሬት ያነቃንቅ ነበር ። የመኳንንቱ የወታደሩ አለባበስ እጅግ ያስደንቅ ነበር ። ሊጋባና ጸሓፌ ትእዛዝም ከፍ ባለው ማማ ላይ ሁነው የተናገሩትን አዋጅ በሚከተለው እናትማለን ።

ቅዳሴው ከ፫ሰዓት ጀምሮ እስከ ፮ሰዓት ነበር ። የተቀደሰውም በግብፅ ቋንቋ ነበር፤ ቀዳሾቹም ሊቀጳጳሳቱ አቡነ ቄርሎስና ከፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ የተላኩት አቡነ ዮሳብና ቆሞሱ አቡነ ጊዮርጊስ ሌሎችም ግብፃዊያን ነበሩ። በሊቀጳጳሱ በአቡነ ቄርሎስ እጅ ጃንሆይና እቴጌ ቅዱስ ቍርባን ተቀብለው በወጡ ጊዜ ካህናቱ ታቦት ይዘው እየዘመሩ ዑደት አድርገው ጃንሆይና እቴጌ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰንም ለማረፊያ በተሰናዳው ቦታ ተቀመጡ ። ልዑላን መኳንንትና ሚኒስትሮች ። የውጭ አገር መኳንንትም በየማዕርጋቸው ተቀምጠው ቈይተው ጃንሆይና እቴጌ ፬ፈረሶች በሚስቡት በመስታዋትና በወርቅ በተሠራ ሠረገላ ተቀምጠው መንገድ ጀመሩ ። ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮችም በአቶ መቢል እየሆኑ ተከተሉ። ቀስ ብለው በዕልልታና በደስታ ወደ ግቢ ገቡ ። የውጪ አገር መኳንንትም እየተሰናበቱ በየቦታቸው ተመለሱ። ለመኳንንቱና ለመሳፍቱ ግብር አድርገው ዋሉ። ዳግም ማታ በ፪ሰዓት ለታላላቆች ለሮፓና ለኢትዮጵያ መኳንንት ግብር አደረጉ። ዳግም ፬ሰዓት ሲሆን በዲስ አበባ የሚኖሩ የመንግሥታት ሚኒስቴሮችና ቆንስሎች ገብተው ሼፓኝ እየተጠጣ በደስታ አምሽተው ለዓይን ደስ የሚያሰኝ የወረቀት ተኵስ ሲተኰስ ቈይቶ ፯ሰዓት ያህል ሲሆን ሰው ሁሉ እየተሰናበተ ወጣ። ሰውን ሁሉ እደዚያ ቀን ደስ ብሎት አያውቅም። በነጋውም በጥቅምት ፳፬ ቀን ለመኳንንቱና ለወታደሩ ግብር አድርገው ዋሉ ። የመጠጡና የምግቡ ነገር ላየው ሰው እጅግ ያስደንቃል። የተደረገውን ሁሉ ለመጻፍ ጌዜ አላገኘንምና በፕሮግራሙ ታገኙታላችሁ ።

በጥቅምት ፳፱ቀን ከማታው ፪ሰዓት ተሩብ ሲሆን ስለ ጃንሆይና እቴጌ ዘውድ በዓል የኢጣልያ ሌጋሲዮን ጃንሆይንና እቴጌን ፥ ልዕልት ተናኘ ወርቅን ፥ ልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰንን ፤ ልዑል ራስ ካሣን፥ ልዑል ራስ ኃይሉን፥ ልዑል

ራስ ሥዩም፣ ልዑል ራስ ጉግሣን ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይን ለእራት ጠርተው ነበር ። ግቢውም መብራት ብቻ ነበር ፣ የተጠሩቱም በተቀጠረው ሰዓት ደረሱ ። ጃንሆይንና እቴጌንም ብዙ መብራት አስበርተው ተቀበልዋቸው ። በአትክልቱና በየዛፉ ላይም ጌጥ ባለው ወረቀት ውስጥ የሻማው መብራት ሲበራ ከአበባው ውስጥ ብርሃን የወጣ ይመስል ነበር ። እራት ከተጋበዙ በኋላ ፬ሰዓት ሲሆን ደግሞ ዳንስና ጨዋታ ለማየት የተጠሩት መኳንንት መጡ፣ከውጪ አገር የዲፕሎማቲክ ሰዎችም እጅግ ብዙ ዎች ነበሩ ። ወዲያው በደረጃው ላይ ወምበር ተደረደረና ጃንሆይና እቴጌ ልዕልት ተናኘ ወርቅ የቀሩትም ስማቸውን በላይ የጻፍናቸው ልዑላን መኳንንት ተቀምጠው ሲመለከቱ ስለ በዓሉ ቀን የተሰናዳው የወረቀት ተኵስ ይንጣጣ ጀመረ። አንዳንዱ ጁራታም ከከብ መስሎ ይወረወር ነበር ። አንዳን-ዱም ዘንዶ እየመሰለ ይወረወር ነበር ። ጌጥ መስሎ ተራውን የተደረደረውንም የሚፈነዳ ወረቀት አንዱን ሲአያይዘው ተያ-ይዞ ተራውን ሲንጣጣ ፈረ ቢአገኝ ገደል ያገባ ነበር ። እንዲሁ በደስታ ቈይተው ፭ሰዓት ሲሆን ጃንሆይና እቴጌ የቀሩትም ከላይ የጻፍናቸው ልዑላን መኳንንት ሔዱ። እኛም ወደ ውስጥ ገብተን ተቀመጥን ። ከዚህ በኋላ ደስ የሚአሰኝ ፒያኖ እየተመታ ዳንስ ተጀመረ ። ስንመለከትም ቈይተን ብዙ ጣፋጭ ምግብና በያይነቱ ብዙ መጠጥ ወደ ተሰናዳበት ቦታ ገብ-ተን የተጠራን ሰዎች ሁሉ የወደድነውን እንብላ የወደድነውንም እንጠጣ ነበር ፤ እንዲህ ደስ ብሎን አምሽተን ፯ሰዓት ሲሆን ወደ ቤታችን መጣን። ብዙ ሰዎችም እዚያው ቀሩ እስከ፲ሰዓትም የቈዩ አሉ ሲሉ ሰማን ፤ እንዲህም ያች ሌሊት የፋሲካ ቀን ሁና አደረች ።

በጥቅምት ፳፫ቀን ደግሞ እንደ ፕሮግራሙ ቃል ጃንሆይና እቴጌ በየቤተክርስቲያኑ እየሔዱ ለዚህ ክብር ማዕርግ ያበ-ቃቸውን አምላክ ሲአመሰግኑ አርፍደው መኳንንቱና ወታደሩ በሥርዓት ተሰልፎ አጅበአቸው ፯ሰዓት ያህል ሲሆን ወደጓቢ ተመልሰው ለመኳንንቱና ለካህናቱ ታላቅ ግብር አድረገው ዋሉ።

የዘውድ በዓል ።

በጥቅምት ፳፭ቀን እንደ ፕሮግራሙ ቃል ከማታው በ፱ሰዓት ጃንሆይና እቴጌ ልዑላን የኢትዮጵያ መኳንንትና የውጪ አገር መኳንንት ወደ ልዑል አልጋ ወራሹ አስፋ ወሰን ቤት ለራት ተጠርተው ነበር። በዚሁ በተቀጠረው ሰዓት ሁሉም ተሰብስበው አምሮ በተሰናዳው የእንግዳ መቀበያ ቦታ(ሳሎን) ቆይተው ከሩብ ሰዓት በኋላለእራት ወደ ተሰናዳው ቦታ ገቡ። ከእራትም በኋላ የኢትዮጵያ ሴቶችና ወንዶች ልጆች በሙዚቃ አስተማሪው በሙሴ አልባንድያን እየተመሩ የኢትዮጵያን መዝሙር ዘምረው ደስ አሰኙ ። እጅግ ደስ የሚአሰኝ ስኒማም ነበረ ።

የፈረሶች መቀዳደም ።

በጥቅምት ፳፮ቀን ፈረሶች የሚቀዳደሙበት ቀን ነበረ ። በዚሁም ቀን ፹ሰዓት ሲሆን ጃንሆይ ወደ ጃን ሜዳ መጡ። የኢትዮጵያና የውጪ አገር መኳንንትም መጡና በየ ማዕርጋቸው ተቀመጡ ።

፩ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ፰፻ ሜትር ነው ። መጀመሪያ ጊሂላን የሚባለው የክምት ዘር ፈረስ ሆነና ኖቢስ የሚባለውን ዋን-ጫና ፺ብር አገኘ ።

ሁለተኛ ሰገሌ የሚባለው የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ-ወሰን ፈረስ ሆነና ፳፭ብር አገኘ ።

፫ኛ ዳጡድ የሚባለው የከንት ዘር ፈረስ ሆነና ፲፭ብር አገኘ ።

፪ኛ መቀዳደም።

የሚዳው ርዝመት ፩ሺ፰፻ ሜትርነው። መጀመሪያና ሁለተኛ የማዳም ሻምባር ፈረሶች ሆኑና መጀመሪያው የኢጣልያ ሚኒ ስቴር ሞንስኘር ያሲንቲኒ የሰጡትን ዋንጫና ሙሴ ደረፎ የፈረንሣዊ ሚኒስቴር የሰጡትን ዋንጫና ፪ኛው አንዲት ትንሽ ዋንጫ አገኙ ።

፫ኛው የሰር ሲዲኒየ ባርተን ፈረስ ሆነና አንዲት ትንሽ ዋንጫ አገኘ ።

፫ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ፩ሺ፪፻ሜትር ነው ። ይኸውም እሽቅድ ምድም በተለየ የኢትዮጵያ ወታደር አለቆች ብቻ ሆነና መጀ መሪያ ባራ የሚባለው አቶ በቀለ ጅምሬ የተቀመጠው ፈረስሆነና ፴ብርና ተማረሻል ፍራንሼ ዲስፔሬ አንድ የረሽጠመንጃ አገኘ።

፪ኛ ይላቅ የሚባለው አቶ ተስፋዬ ዳወሌ የተቀመጠው ፈረስ ሆነና ፲፭ብር አገኘ ።

፫ኛ ፍጨው የሚባለው ልጅ ተሰማ አያኔ የተቀመጠበት ፈረስ ሆነና ፲ብር አገኘ ።

፬ኛ መቀዳደም ።

የሚዳው ርዝመት ሺ፪፻ ሜትር ነው ። መጀመሪያ ሐረር የሚባለው የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ፈረስ ሆነና ደፕሬንስ ኡዳን የሰጡትን ዋንጫና ፺ብር አገኘ ።

፪ኛ ጊን የሚባለው የማርኩዊስ ፖተርኖ ፈረስ ሆነና ፴ ብር አገኘ ።

፫ኛ ቱምቱ የሚባለው የእቴጌ ፈረስ ሆነና ፳ብር አገኘ

፭መቀዳደም ።

መጀመሪያ ነብሬ የሚባለው የማዳም ሻምባር ፈረስ ሆነና ሙሴ ኅሰ'ን የሰጡትን ዋንጫና ፺ብር አገኘ ።

፪ኛ ሲሞስየሚባለው የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ፈረስ ሆነና ፴ብር አገኘ ።

፯ኛ መቀዳደም ።

የሜዳው ርዝመት ፪ሺ ሜትርነው። መጀመሪያ ቲሮ የሚ-ባለው የማዳም ሽምብር ፈረስ ሆኖና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሰጡትን ዋንጫና ፶ ብር አገኘ ።

፪ኛ ጉራ የሚባለው የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ፈረስ ሆኖና ፴ ብር አገኘ ።

፫ኛ ሽሬፉ የሚባለው የባሮን ሙዚ ፋልኮኒ ፈረስ ሆኖና ፳ ብር አገኘ ።

፰ኛ መቀዳደም ።

የሜዳው ርዝምት ፩ ሺ ፫፻ ሜትርነው።መጀመሪያ ጋማ የሚባለው የሙሴ አድሬ ፈረስ ሆኖና ልዑል ዱክ ኦፍ ግሎ ስተር የሰጡትን ዋንጫና ፳ ብር አገኘ ።

፪ኛ ሉክስ የሚባለው የካፕቲያን ዳንክሌ ፈረስ ሆኖና ፵ ብር አገኘ ።

፫ኛ ሃሊል የሚባለው የባሮ መዚ ፋልኮኒ ፈረስ ሆኖና ፴ ብር አገኘ ።

ሙሴ ክስሮፍ ጎርጎርዮስ ብዙ ጊዜ በጃንሆይ ፈረስ ውር ርድ እየገባ ሲቀድም ደስ ሲአሰኝ ይኖር ነበር ፤ በዚህ ቀንም ፩ ጊዜ መጀመሪያ ሁኖ ፩ የወርቅ ዋንጫ አገኘ በመጨረሻው ጊዜ ግን አንድ ፈረሰኛ ፈረሱን አጋጭቶበት ፈረሱ ወደቀና እሱም ወድቆ ብዙ ጉዳት ሳያገኘው ዳነ ያም ያጋጨው ፈረሰኛ አብ ሮት ወደቀ። ጉዳት ግን አላገኘውም በሕይወታቸው መዳን እጅግ ደስ ብሎናል ።

የዘውድ በዓል

በጥቅምት ፳፫ ቀን ጃንሆይ የመንግሥታት መልእክተ ኞችንና መኳንቱን ጨምረው ወደ አዲስ ዓለም ወርደው ጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የሠሩትን ቤተ ክርስቲያን አይተው የጥሩ ሜዳ ነፋስ ተቀብለው ወደ ገነት ከተማ ተመልሰው ግብር አድርገው ውለው ወደ ማታ ተመልሰው አዲስ አበባ ገቡ።

በጥቅምት ፳፫ ቀን በፍልውሀሜዳ ሰልፍ ተደርጎ ነበር። ፬ሰዓት ሲሆን የመንግሥታት መልእክተኞች የማዕርግ ልብ-ሳቸውን እየለበሱ መጥተው ሦስት ድንኳን ተቀጣጥሎ ተተክሎ ሥጋጃው ተነጥፎ ጥሩ ጥሩ ወምበርተደርድሮበት ወደ ነበረው ቦታ ገብተው ተቀመጡ አስቀድመውም ከታላላቆች የኢትዮጵያ መኳንንት ብዙዎች መጥተው ጃንሆይን ይጠባበቁ ነበር ። እንጋቾች የሚባሉት የመትረየስ ዘበኞችም በድንኳኑ ዙሪ ተሰልፈው የማይገባው ሰው ወደ ድንኳኑ እንዳይገባ እየከለከሉ በትክክል ቁመው ያምሩ ነበረ ። ወታደሩ የፍልውሀን ሜዳ ጣጥም አድርጎ መልቶት ነበረ።ከ፬ሰዓት በኋላ ጃንሆይ በፈረሰኞች ታጅበው መጡ በድንኳኑ አጠገብ ሲደርሱ ከአቶመቢል ሲወርዱ ልዩ የሆነ በወርቅ የተሠራ አምፋሮአቸውን በራሳቸው ደፍተው ይቃጠል የመሰለ ላንቃቸውን ለብሰው በወርቅ የጠ-ለቀ ግምጃ ሱሪአቸውን ታጥቀው በየናቸው ጊዜ ሞፀ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ተብሎ ለአባቶቻቸው ሁሉ ሲነገር የመጣው አሁን የተነገረ መሰለን። ታላላቆች መኳንንትም በየማዕርጋቸው እንዲሁ በወርቅ የጠለቀ ጉፈሩና አምፋሮ፥የወርቅ ለምድ እየ-ለበሱ በየማዕርጋቸው ተቀመጡ።ከዚህ በኋላ ጃንሆይ እንግዶ-ችንና ታላላቆችን መኳንንት ጨምረው በአቶመቢል ሁነው ሰልፉን እየዞሩ አዩ በዚያ ጊዜ የጦር ሚኒስቴሩ ፊታውራሪ ሙሉጌታና ሊጋባ ወዳጆ ጥሩ ጥሩ መሣሪ በተጫኑ ታላላቅ በቅሎዎች ተቀምጠው ሰልፉን ያሳዩአቸው ነበር ። የጦር ሚኒ-ስቴሩ ጌጥ እጅግ ልዩ ነበር በወርቅ የጠለቀ የጃንሆይን ዓይነት ግምጃ ሱሪ ታጥቀው መረሻቱና ኰርቻው ሳይቀር በወርቅ የጠለቀ መሣሪ በቅሎአቸው ተሸልማ ነበር ። ሰልፉን ዙረው ካዩ በኋላ ወደ ድንኳኑ ገብተው በመንበረ ዳዊቱ ላይ ተቀ-መጡ ። ከዚህ በኋላ ፈረሰኛ በፊት፥ ቀጥሎ እግረኛ፥ በኋላ በአ-ለበቅሎ እየሆነ በተራ በተራ እየተሰለፈ እየፈከረ ያልፍ ጀመር በመጀመሪያ የቤት ልጆች ተሰልፈው አምረው አለፉ። ቀጥለው የፈረስ ዘበኞች በፈረስ እየፈከሩ አልፈው ጉግሥ ሲጫወቱ ቈይተው አለፉ ። ቀጥሎ የፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ የነበረው ወታደር(ሠራዊት)ተሰልፎ ፈክሮ አለፈ ።ቀጥሎ የደጃዝማች ብሩ ሠራዊት ተሰልፎ አለፈ። ቀጥሎ ነጭ ከት የለበሰ ባንዲራ የያዘ ብዙ ጥሩ ወታደር የማዘጋጃ ቤት በትክክል ተሰልፎ ጸሓፊዎች ነጭ ከት ለብሰው ማዕርግ ያላቸው በፈረስ በፈረስ ሁነው በሙዚቃና በክብሮ እየተመሩ ዘበኛው ከት ከቱን ለብሰ ጣሩና ቀኝ አስተካክሎ እየረገጠ ደስ አሰኝቶ አለፈ። የማዘጋ-ጃቤት ዘበኞች ጠቅላይ አለቃ ግራዝማች አማረና ባሻ ደነቀ የቀሩትም አለቆች ሰይፋቸውን መዘው በፈረስ በፈረስ ሁነው ሲሔዱ እጅግ ያምሩ ነበር ።

ቀጥለው ጅጅጋ በፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተሚካኤል ውሥጥ ከአሉት ተከፍለው የመጡት ወታደሮች በልጅ ተስፋዬ ያየህ ይራድ እግር ተሰልፈው ግራና ቀኝ በሥራት እየረገጡ ተሰ-ልፈው ደስ አሰኝተው አለፉ ። ቀጥለው ማዡር ፖሊ የአሳተ-ማርዋቸው ወታደሮች በካፒቴኖችና በአለቆቻቸው ተሰልፈው በረጃጅም በቅ ሎዎች መትረየሶችን ጭነው በመሀል አድርገው በ ጥሩምባና በክብሮ ድምፅ ልክ እየረገጡ አምረው ደስ አሰኝተው አለፉ ። ቀጥለው የጦር ሚኒስተሩ የፊታውራሪ ሙሉጌታ ጥሩ ጥሩ የሰልፍ ልብስ የለበሰ ብዙ ወታደር ተሰልፎ እየፈከረ አለፈ በመሀል በመሀሉ ልዩ ልዩ ዓይነት ከት የለበሰ እምቢልታና መለ ከት ጥሩምባ ነፊ ነበረ ሊጋባ ወዳጆ ከላይ እንዳልነው ጥሩ መሣሪ በተጫነች ከፍ ባለች በቅሎ ተቀምጠው በፊት ነበሩ፥ የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ሙሉጌታ ግባ ገብር ገብር የሚል ነጋሪታቸውን ከፊታቸው አድርገው የሸልማትን (የአለባበሳቸ-ውን)ነገርስ በመጀመሪያ ተናግረነዋልና ከፍ ያለ ሰገነት በምታህል በቅሎ ተቀምጠው ብቅ ባሉ ጊዜ እጅግ አማሩ ሠራዊቱም ብዙ ነበርና ሲተላለፍ ብዙ ቈዩ።የዳግማዊ ምኒልክ ሆፒታል ሠራተኞች ነጭ ነጭ ከት ለብሰው በአላቃቸው በአቶ በላቸው ተሰልፈው አምረው አለፉ ። ከዚህ በኋላ ፯ሰዓት ሆነና ጃንሆይ ተነሡ ሰልፉን ግን እስከ መጨረሻው ለማየት ሁለት ቀንም አይበቃም ነበረ ።

ደዘውድ በዓል ።

በጥቅምት ፳፫ ቀን ስለ ጃንሆይ ዘውድ በዓል ቢትወደድ ጌታቸው አባተና ክብርት ወይዘሮ አስቴር ብዙ ሰዎች ለእራት ጠርተው ነበር ። ከተጠሩትም ሰዎች ጥቂቶችን በሚከተለው መስመር ጽፈናቸዋል ።

ልዑል ራስ ሥዩም ባለቤታቸው ወይዘሮ ዓፀደ አስፋው ወይዘሮ አልማዝ መንገሻ ።

ከንቲባ ገብሩ ፡ የአሜሪካ አምባሳደር ሚስተር ያቆቢን ከባለቤታቸው ጋራ

ጄኔራል ኸትርስ ከነባለቤታቸው ሚስተር ኩክ ሴክረቴሩ ሚኒስቴር ሳውተርድ ከነባለቤታቸው ፕሮፌሶር ምርክ የጃፓን አምባሳደር ሚስተር ኢዛቡሮ ዮሺዳ ከነተከታያቸው ነበሩ ልጅ መስፍን ቀለመ ወርቅ አፈተርጓሚዎች ልጅ መላኩ በያንና አቶ ዳባ ብሩ ነበሩ ። እጅግ ደስ የሚያሰኝ ምግብና መጠጥ ቀርቦ ከተጋበዝን በኋላ የኢትዮጵያ ዘፋኞች ወንዶች በመሰንቆ በክራር ሴቶች በእንገታቸውና በቃላቸው ሲዘፍኑ እንግዶችን እጅግ ደስ አሰኙአቸው ። ፯ሰዓት ሲሆን እንግዶች የኢትዮጵያን ጉዳይ ፈጻሚ ሚኒስቴር በፓሪ ቢትወደድ ጌታቸውን እጅግ አመ-ስግነው እንግዶቹ ተነሡ ሁላችንም እያመሰገን ወጣን ።

የዘውድ በዓል ።

እንደ ፕሮግራሙ ቃል በጥቅምት ፳፫ ቀን ክቡር ደጃዝ ማች ደስታ ዳምጠውና ባለቤታቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ጃንሆይንና እቴጌን መሳፍቱንና መኳንንቱን ሚኒስቴሮችን ታላላቆችንም ወይዛዝር የመንግሥታቱን መልክተ ኞችንና ሚኒስቴሮችን ቆንስሎችንና ብዙዎችን የዲፕሎማቲክ ሰዎችን ሁሉ ለእራት ጠርተው ነበር ። በአጥር ግቢው ከጨረቃ የደመቀ ኤሌትሪክ በርቶበት የሠለጠነ ወታደር ከበሩ እስከ እልፍኙ በር ድረስ ተሰልፎበት ነበር። ሁለት ሰዓት ሲሆን እቴጌ ቀጥለው ጃንሆይ ገቡ ። ወታደሩ ሰላምታ ሰጠ የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችም ደስ የሚያሰኝ ሙዚቃ ነፉ ። መኳንንትና ወይዛዝር ሚኒስቴሮችም የውጭ አገር መኳንንትም ሚኒስቴሮችና ቆንሲሎችም ገቡ የእንግዳው መቀበያ ቤትም እጅግ አምሮ ነበር ያማረ ምንጣፍም ተነጥፎበት ጥሩ ጥሩ ወምበር ተዘርግቶበት ነበር ። ጃንሆይና እቴጌ በልዩ ወምበር ተቀመጡ ። የተጠሩትም መኳንንትና ወይዛዝር ገብተው በየማ ዕርጋቸው ተቀምጠው ቈይተው እራት ወደ ሚጋበዙበት ቦታ ሲሔዱ እጅግ የሚያምር አዲስ መንገድ ከታችኛው ቤት እስከ ላይኛው ቤት ድረስ ቤት ተሠርቶበት ስጋጃ ተነጥፎበት ኤሌ ትሪኩ በቅርብ በቅርብ ሁኖ በርቶ ሲያዩት እንደሰማነው የሰማይ መንገድ ይመስል ነበር ። ወይም ራእይ ይመስል ነበር እንጂ በእውነት በሰው እጅ የተሠራ መንገድ አይመስልም ነበር። ከዚህ በኋላ ጃንሆይና እቴጌ ልዩ በሆነ የወርቅ ወምበር ተቀመጡ የቀ ሩትም መኳንንትና ወይዛዝር በየማዕርጋቸው ተቀምጠው እራት ተጋበዙ የምግቡና የመጠጡ ዓይነት እጅግ ብዙ ነበር ። የወጡ ዓይነት ብዙ ስለሆነ ወጡን በያይነቱ ሳይቀምሱት በመሀል ጠግ በው የተውት እጅግ ብዙ ናቸው።የእራቱ ግብዣ ከተፈጸመ በኋላ በ፬ሰዓት የተጠሩት ሰዎች ዳግም ገቡ ፡ መጀመሪያ ወደነበሩበት ቦታ ተመልሰው ገብተው በየቦታቸው ተቀመጡና ዳንስ ተጀ-መረ ። ስለ ዘውዱ በዓል ደስታ ታላላቆች የሮፓ ሰዎች ከሮፓ ወይዛዝር ጋራ እየተያያዙ ዳንስ ያደርጉ ነበር ፡ መጠጡም በየዓ ይነቱ እንደ ዝናብ ይወርድ ነበር ፡ ጣፋጩንም ምግብ ከለበት ሁሉ እንደፈቀዱ ገብተው ከሚወዱት ዓይነት ይጋበዙ ነበር ከዚህ በኋላ ወደ ታላቁ አዳራሽ ተመልሰን ገብተን የሀገራችን ዘፋኞች ወንዶች በመሰንቆና በዋሽንት ሴቶች በቃላቸውና በአንገታቸው ሲዘፍኑ ቈይተው በ፮ ሰዓት ተኩል እንግዶችን ድካም ስለተሰማቸው ተሰናብተው ወጡ ፡ የሀገራችን መኳንንትና ወይዛዝርም እየተሰናበቱ ወጡ ፡ ሰውን ካሰናበቱ በኋላ ጃንሆይና እቴጌ ወጡ በእውነት የደስታ ቀን መባል የሚገባት ያች ሌሊት ነበረች ።

የእንግዶች አቀባበል ።

የቤልጅግ የስዌድን የቱርክ መልእክተኞች ሙሴ ለጋርድም በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ የኖሩ የፈረንሳዊ መ አምባሳደር ሁነው የኖሩት በጥቅምት ፳ ቀን በ፬ ሰዓት ተኩል በልዩ ባቡር ገቡ። ለመበቀል ታዝዘው የወረዱ መኳንንት ።

ልዑል እልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን
ፊታውራሪ ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴር
ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የአገር ግዛት ሚኒስቴር
ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ
ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ
ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ
ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ
ማዦር ፖሊና የቀሩት ካፒቴኖች የሰልፍ አስተማሪዎች የሙ-ዚቃ አስተማሪው ሙሴ ኒኮ
የፈረንሳዊና የቤልጅግ የስዌድን የቱርክ ቆንሲሎችና ሚኒስ-ቴሮች ጥሩጥሩ የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ሌሎችም የየክ ፍላቸው ዜጎች ከዚያው ነበሩ ።

የኢትዮጵያ መኳንንትም ከነሠራዊታቸው ከባቡር መቋ-ሚያ ጀምረው እንግዶች እስከሚገቡበት ቦታ ድረስ እስከ ታላቁ ግቢና እስከ አልጋወራሹ ግቢ ድረስ በየመንገዱ ግራና ቀኝ አምረው ተሰልፈው ነበር ።

የኢጣልያ መንግሥት መላክተኞች ልዑል ዱክና የቀሩ-ትም የኢጣልያ መኳንንት በጥቅምት ፳፩ ቀን ከአዋሽ ተነሥ ተው በሌሊት ባቡር ከነጋ በኋላ ረፈድ ሲል ቢሾፍቱ በባቡር ማረፊያ ደረሱ ። ከዚህ በኋላ አቶ ተሰማ እሼቴ ከአሠሩት ማረፊያ ወደ እሚባለው ሆቴል ገብተው የጧት ቊርስ ተጋብ ዘው ወደ ቢሾፍቱ ባሕር ገብተው ሲናፈሱ ቆይተው ፫ ሰዓት ተኩል ሲሆን አዲስ አበባ እባቡር ማቋሚያ ደረሱ ። ጃንሆ-ይም አስቀድመው ደርሰው ነበር ። አብረዋቸውም የነበሩ ልዑላን መኳንንትና ሚኒስቴሮች ስም ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

ልዑል ራስ ካሣ ።
ልዑል ራስ ኃይሉ ።

ልዑል ራስ ሥዩም ።
ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ።
ክቡር ፊተውራሪ ሙሉ ጌታ የጦር ሚኒስቴር ።
ክቡር ደጃዝማች ብሩ ።
ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር በፓሪ ።
ክቡር ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ የአገር ግዛት ሚኒስቴር
ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ።
ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አፈ ወርቅ የእርሻ ሚኒስቴር ።
ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያም የሐረርጌና የአውራጃዋ እንደራሴም ከድሬ ደዋ እንግዶችን እየተቀበሉ ሲሸኙሰንኖቸው ከልዑል ዱክ ጋራ አብረው መጥተው ነበር ።

ክቡር ደጃዝማች አደፍርሰው የግቢ ዘበኛ አለቃ ።
ክቡር ደጃዝማች መኰንን ደምሰው ።
ክቡር ብላቴን ጌታ ኅሩይ የውጭ ጉዳይ ዋና ዲሬክተር
ክቡር ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገሠሠ ።
ክቡር ግራዝማች ተክለ ማርቆስ የጽሕፈት ዲሬክተር ።
ክቡር ሙሉ ማዥር ፖሊና የቀሩትም ካፒቴኖች የሠለጠኑትን ወታደሮች የሙዚቃ አስተማሪው ሙሴኒኮም ሙዚቃ ነፊዎችን አሰልፈው በአማረ ሙዚቃ ነፉ ። ባቡር በደረሰ ጊዜ ልዑል ራስ ኃይሉና ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወደ ባቡር ገብተው ተቀበልዋቸው ። ከባቡሩም ከወጡ በኋላ ጃንሆይ ሒደው ተገናኙአቸው ። በዚያን ጊዜ የኢጣልያ ማርሽ ሲነፋ የሰላምታ እጃቸውን ከፍ እንዳደረጉ ቆዩና በባቡሩ ፊት ለፊት ያሉትን ወታደሮች ዞረው አይተው ወደ ማረፊያው ቤት ገብተው ልዑል ፈርድናንዶ የሳቡያና ጄኖባ የኡዲኒ ፕሪንስ ከኢትዮጵያ መኳንንት ጋራ አስተዋወቁአቸው ። የኢጣልያንንም መኳንንት ከጃንሆይ አስተዋወቁዋቸው ። ተሰነባብተው ልዑል ፈርድናንዶ የሳቡያና ጄኖባ የኡዲኒ ፕሪንስ ከልዑል ራስ ኃይሉና ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ጋራ በአንድ አቶ ሞቢል ሁነው ደጃዝማች ብሩና ቢትወደድ ጌታቸውም ከሌሎች የኢጣልያ መኳንንት ጋራ በአቶ ሞቢል እየሆኑ የሰላምታ ሙዚቃ እየተነፋላቸው ወታደሩም በየመንገዱ ተሰልፎ ሰላምታ እየሰጣቸው የክብር ዘበኞች በፈረስ ተከትለዋቸው ነበር ።

የእንግዶች መገናኘት።

በጥቅምት ፳፭ ቀን ከ፮ ሰዓት በኋላ ወደ ግቢ ገብተው ከጃንሆይ የተገናኙት የመንግሥታት መልእክተኞች ቀጥለው የተጻፉት ናቸው ።

የቤልጅግ መንግሥት መልእክተኞች ።
የስዌድን መንግሥት መልእክተኞች ።
የቱርክ መንግሥት መልእክተኞች ።
የኢጣልያ መንግሥት መልእክተኞች ።
የፖሎኝ መንግሥት መልእክተኞች ነበሩ ።
የአቀባበሉ ነገር ከላይ እንደጻፍነው ነው ። ለሁሉም በየማዕርጋቸው መድፍ ተተኰሰላቸዋል ።

አይሮፕላኖች በአዲስ አበባ ።

ጃይሆይ ደጃዝማች አምባቸው ገሠሠን ዋድላንና ደላንታን ሹመው እንግዴህ አገሩ ተጕድቷልና ሒድ ቢልዋቸው ጃንሆይ የሚነግሡበትን ቀን ለማክበር ከውጭ አገር መኳንንቱ ሲመጡ ያነን የተባረከ ቀን ሳላይ እንዴምን እሔዳለሁ ከርሜ እንድሔድ ይፍቀዱልኝ ብለው ቢለምኑ ። ጃንሆይም አገሩ ተጕድቷልና አሁን ሒድ፤ ኋላ ግን በዚያው ቀን በአይሮፕላን አስመጣሃለሁ ብለው ተስፋ ሰጥተዋቸው ነበርና በዚያው ለሰጧቸው ተስፋ አይሮፕላን ልከውላቸው ቅዳሜ በጥቅምት ፳፱ ቀን ጧት ሒዶ ማታ ይዞአቸው መጣ ። ደጃዝማች አምባቸውም ሰው ሁሉ በአይሮፕላን አይውጡ ብሎ ሲገላግላቸው በድፍረት በአይሮፕላን በመምጣታቸው እጅግ ተመስግነዋል ።

ደግሞ የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥን ልጅ ተከትለው ፫ አይሮፕላኖች መጥተዋል ። ደግሞ ጋዜጣ ጸሐፊዎች በ፪ አይሮፕላን መጥተው ፩ ቀን አድረው የመናገሻውን ቀን አይተው በፎቶግራፍም የአዩትን አንሥተው ዕለቱን ተመልሰው ወደ አገራቸው ተመለሱ ።

ደግሞ ኮማንዳ ዌስ የሚባሉ ፩ ሀብታም የፈረንሣዊ ሰውሴትና ቤርነሽ የሚባሉትን ጨምረው ሴርዣ ተራፎና የሚባለውን ነጂ ድርገስ የሚባለውን ማኪኒሲያ (መኪናውን) ተመልካች) አድርገው የመናገሻውን ቀን ለማየት አስፈቅደው ሲመጡ እሑድ እንኳን አልደረሱም ሰኞ በጥቅምት ፳፱ ቀን በ፫ ሰዓት አዲስ አበባ ደርሰው የአይሮፕላኑን ማረፊያ አሳስቶ ከጃን ሜዳ ውጪ በኃይል ወድቆ አይሮፕላኑ ተሰበረ ። ሰዎቹ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ዳኑ ። የእኛን ደስታ ለመካፈል ሲመጡ ጥፋት ቢአገኛቸው ለኛ ታላቅ ኀዘን ይሆንብን ነበር ነገር ግን የሰዎቹ መዳን እጅግ ደስ ብሎናል ። አይሮፕላኑቤ መቹም ገንዘብ ነውና ይሠራል ከፈረሰ መልሶ የማይሠራ ሰው ነው ።

በጥቅምት ፴ ቀን ባቡር የተሳፈሩ የፈረንሳዊ መንግሥት መልእክተኞችማርሻል ፍራንሼዲስፒሬና የቀሩት ተከታዮቻቸው
የጀርመን ዋና አምባ ሳደር
የአሜሪካ መንግሥት መልእክተኞች ።
የግብፅ መንግሥት መልእክተኞች ።
የሆላንድ መንግሥት መልእክተኞች ።
የስዊድን መንግሥት መልእክተኞች ።
የቱርክ መንግሥት መልእክተኞች ።
የፖሎኝ መንግሥት መልእክተኞች ።
ከእንግሊዞችም መኳንንት በጥቅምት ፴ ቀን በባቡር ተሳፈሩ የኢትዮጵያም መኳንንት ከወዳጆቻቸው በመለየታቸው እጅግ እያዘኑ ሸኙአቸው እነሱም እያዘኑ ሔዱ ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ከልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያከማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ-በላቸውን በቅን ልበናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኩላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፋፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቈሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ዝኒት የተባለ ባለ ፈረስ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፺ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሄለኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።





አዲስ ዓይነት በርሳሊን በርኔጣ መቆታችሁ እዩ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወይችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፯ 6me ANNÉE № 47		ሐሙስ ኅዳር ፲፩ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ። JEUDI 20 NOVEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé "Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ወደ ዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie: Un an 5 Thalers Etranger: Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የዳግማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሐውልት የተመረቀ ዕለት ጃንሆይ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተናገሩትን ዲስኩር በፊተኛው ጊዜ ስፍራ ስለጠበበን በሚከተለው እናትማለን ብለን ነበር።አሁንም እነሆ በአማርኛና በፈረንሣዊ አትመነዋልና ተመልክቱት ብዙ ጥቅም ታገኙበ ታላችሁና ።

ልዑላን የኢትዮጵያና የውጭ አገር መሳፍንቶችና መኳንንቶች ሆይ ።

የታላቁ ንጉሥ የዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት የቆመበት ይህ ቀን ለሙሉ ኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ የደስታ ቀን መሆኑን ማንም አይዘነጋውም። ሰው በዚህ ዓለም ሲኖር ድካሙ እጅግ ብዙ ነው ። ነገር ግን ደግሞ በሠራው ሥራ ለስሙ መልካም መታሰቢያ ትቶ ከመሔዱ በቀር ሌላ የሚበልጥ ነገር የለምና ዛሬ ይህ ሐውልት መቆሙ አፄ ምኒልክ የድካማቸውን ዋጋ ለማግኘት የሚገባቸው እጅግ የታደሉ መሆናቸውን ያስረዳናል።

አፄ ምኒልክ ከቀድሞ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በነጋሢ ተወላጅነታቸው ምንም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቢሆኑ በዚህም ላይ ዕድለኛ ነበሩና በአባታቸው በአፄ ልብነ ድንግል ዘመን በግራኝ መሐመድ ጦርነት የተለያዩትንና የተከፋፈሉትን የኢትዮጵያን አውራጆች አፄ ቴዎድሮስና አፄ ዮሐንስ የጀመሩትን የመሠረቱትን ተከትለው አንድ ለማድረግ በየጊዜው ጦርነት ያደርጉ እንደ ነበረ የኢትዮጵያ አርበኞችና ጀግኖች ሁላችሁም የምታውቁት ነው ።

በዚሁም ሁሉ ድካማቸው እግዚአብሔር ስለ ረዳቸውና ኢትዮጵያን አንድ ስላደረጉ ስማቸው በዓለም ላይ የታወቀ ሆነ።

የኢትዮጵያንም አንድነት ከደላደሉና ከፀኑ በኋላ ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ የሚያገናኝ የወዳጅነት ሥራ ለመሥራት ጀመሩ ። ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥት ጋራ ተዛመደች ። ሕዝባቸውም ወደ ሥልጣኔ ደረጃ እንዲራመድ አደረጉ ።

ዕድለኛም ከመሆናቸው የተነሣ ዘመናቸው ዘመነ ሰላም ስለ ሆነ ገበሬ በማረሱ፥ ነጋዴ በመነገዱ ወደ ትልቅ ብልጥግና ደረሰ ።

አፄ ምኒልክ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሠሩትን መልካም ሥራ ታሪካቸው ይቍጠረው እንጂ አሁን ጨርሰን ለመናገር ጊዜ አናገኝም። ነገር ግን በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው ምንም አዋቂና ትጉህ ቢሆን ከሞት ለማምለጥ የሚችል የለምና ለኢትዮጵያ ሰፋት ፥ ለሕዝባቸው ልማት የሚሆነውን ሥራ እስከሚቻላቸው ከሠሩ በኋላ በታኅሣሥ ፫ቀን ፲፱፻፮ ዓመተ ምሕረት ከዚህ ከምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዓለም አለፉ ።

ሰው ፍጡር ስለ ሆነ ከዚህ የበለጠ ለማድረግ አይችልምና ነው እንጂ ፥ አፄ ምኒልክ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው የሠሩትን መልካም ሥራ ሁሉ ስናመዛዝነው ይህ ሐውልት ዋጋቸው ለመሆን አይበቃም ።

በኢዮጵያ በቀድሞ ዘመን ለመንግሥታቸው መልካም ሥራ የሠሩ ብዙ ነገሥታት ነበሩ ። ነገር ግን ሐውልት የቆመለት አንድ ንጉሥ እንኳ መኖሩን አልሰማንም። አሁን ግን አፄ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥቶች የሚያገናኝ ሥራ ጀምረው ስለ አቆዩን መልካም ሥራ ለሠሩ ነገሥታት ሐውልት ማቆም የሚገባ መሆኑን ስላወቅን በዚህ ሐውልት ሥራቸው ተመሰክረላቸው ለማለት እንችላለን ።

ከሁሉም ይልቅ አፄ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግሥቶች ጋራ የወዳጅነት መገናኛ ከማድረጋቸው የተነሣ የወዳጅነት ውል የተዋዋሏቸውና የሌሎችም የልዩ ልዩ መንግሥቶች መሳፍንቶችና እንደራሴዎች ለዘውድ በዓላችን መጥተው ሳሉ አጋጣሚቸው የአፄ ምኒልክ ሐውልት ሲመረቅ ከእኛ ጋራ ቆመው የደስታችን ተካፋይ መሆናቸው የአፄ ምኒልክን ዕድለኛ መሆን ያስረዳናል ።

ወደ ፊትም ለነገሥታት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ትልልቅ ሥራ የሚሠሩና የሠሩ አርበኞች ለሥራቸውና ለስማቸው መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት እያከታተልን እናቆማለን ።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር

የእንግዶች መሰናበት ።

ሙዚቃ እየተነፋ ወታደሩ በሥርዓት ተሰልፎ እንደ አመጣጣቸው ጊዜ በክብር ከጃንሆይ እየተሰነባበቱ እንግዶቻችን በሥርዓት ተሸኝተው ሔዱ ። የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ ዱክ ኦፍ ግሎስተር አብረዋቸው ካሉት መኳንንት ጋራ በኅዳር ፫ ቀን በ፮ ሰዓት በባቡር ተሳፈሩ ። የሚሔዱትም ሞጆ አድረው ወደ አሩሲ ሒደው ልዩ ልዩ መልካቸው የሚ ሕምር የዱር እንስሶች ቢአገኙ አድነው በክብት ወደ አዋሽ ወርደው በባቡር ተሳፍረው ወደ ውድ ሀገራቸው ሊሔዱ ነው ይባላል ። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ዱክ ኦፍ ግሎስተርን እጅግ ይወዷቸዋልና በማያውቁት አገር እንዳይቸገሩ ትጋትና ቁም ነገር ያላቸው በጅሮንድ ተሰማ ባንቴን ብዙ ወታደሮች ጨምረው ልከውላቸዋል ። በረሀ ደፋሩን ብዙ ጊዜ የኢትዮጵያን በረሀ የዞረውን አቶ ደባ ብሩንም ለአስተርጓሚነት ጨምረውላቸዋል ። ከሐሩሩና ከበረሀው በሽታ ተጠብቀው በደኅና ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ እንገምኛለን። ደግሞ የጀርመን መንግሥት ሁለተኛው መልእክተኛ ከጃንሆይ ፈቃድ ተቀብለው ሜጫ አምቦ ወደ እሚባለው አገር ሒደው ከዚያ ተመልሰው ወደአሩሲ ዚይን ለማየት ሒደዋል ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው መጥተው ወደ ሀገራቸው ይሔዳሉ ይባላል። የእስክንድርያና የጳብዕ፥የኖብያ የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ፓትርያርክ አቡነ ዮሐንስ መልእክተኞች አቡነ ዮሳብና ቆሞስ አቡነ ጊዮርጊስ በኅዳር ፮ ቀን በ፬ ሰዓት በባቡር ተሳፈሩ ።

የስዊድን መንግሥትም መልእክተኞች ከዚህ ቀደም የሔዱት ሁለተኛው ነበሩ ። ዋናው መልእክተኛ ግን ቈይተው በዚሁ ቀን ተሳፈሩ ቀኑና ሰዓቱን ከላይ ጽፈናልና ተመልከቱት። ደግሞ በዚሁ ቀን በማታው ባቡር የቤልጅግ መልእክተኞች ሔዱ ። የጃፓን መልእክተኞች ብቻ ቀርተዋል ። ወዳጆቻችን ሁሉ በደኅና ወደ ሀገራቸው እንዲገቡ እንመኛለን ።

ማመልከቻ ።

ለክቡራን ለኢትዮጵያ ልጆች ባለፈው ብርሃንና ሰላም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ኃያልነት ከግራኝ በፊት የነበረችበትን ማዕርጓንና ሰፋቷን (ዕውቀቷን)ተናግሬ ነበር ። ደግሞም አሁን በቤተ ክህነቱ ወገን ከግራኝ በፊት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት የነበረውን ታሪክ ባጭር ቃል አመለክታለሁ ። የጠላት ምስክር እንዴት ደስ ያሰኛል እንዴት ያምር። አሕመድ ግራኝ የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ዮናን ሰገድን አፄ ልብነ ድንግልን ለመውጋት አስቦ በገጠመ ጊዜ እሱ ራሱ የኢትዮጵያን አብያተ ክርስቲያን አመስግኑአል ያመሰገነበትም እሱ ራሱ ያጻፈው ፈትሐ አል ሐበሻ ይባላል ትርጓሜውም ኢትዮጵያን የከፈትንበትን ታሪክ ማለት ነው። እሱም ለማጥፋት ከተነሣ እሳከሁን ፬፻፳፫ዘመን ያህል ይሆናል ። እሱም የጻፈው መጽሐፍ ፈትሐ አል ሐበሻ በዓረቢኛ የተጻፈው በጃንሆይ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መጻሕፍት ቤት ይገኛል አሕመድ ግራኝም የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትን ክብር ተናግሮአል እንዲህ ሲል አንኮበርን፥አንጾኪያን፥ደዋሮን፥ካጠፋን በኋላ ወረኢሉ መካነ ሥላሴ የሚባል ገዳም ግራና ቀኝ ውኃ በሚፈስበት ቦታ የተተከለ ቤተ ክርስቲያን አገኘን ያም ቤተ ክርስቲያን ጉልላቱ የሰባት ቀን ጉዳና ድረስ ያንጸበርቅ ነበር በሩም ሰባት ነበር አንዱ ወደግሼ፥ አንዱ ወደ አህያ ፈጅ፥ አንዱ ወደ ግሸን፥ አንዱ ወደ አማራ ሳይንት ነበር።በዚሁም ቤተ ክርስቲያን ባገባን ጊዜ አንዱ ዓምድ የብር፥ አንዱ ዓምድ የወርቅ ሁኖ አገኘነው ደግሞም ጥጃ የሚያህል የወርቅ ቡችላ አገኘን እዚያ ቤተ ክርስቲያን ውሥጥ ያለውን ወርቅ ዘርፈን የድሀነታችንን እከክ በዚያ ታጥበን እያለ የግሼን ማርያምን የሐይቅን፥ የጐንደርን፥ የአክሱም ጽዮንን አብያተ ክርስቲያናት ያመሰግናል።ደግሞም የካህናትን የሃይማኖታቸውን ፅናት ይናገ

ራል እንዳለውም አልቀረም የኢትዮጵያ ካህናት ስለሃይማኖታቸው ፅናት ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው ከሚፈርስ ሞትን ወደው ሞቂቶች ካህናቶች በበረሃ አቋርጠው ወደ ብርቱጋል መንግሥት ሄደው ነግረው ያነን ኃይለኛ ሰው ግራኝን ለሞት አደረሱት ደግሞም ባለፈው ብርሃንና ሰላም ኢትዮጵያ ከግራኝ በፊት ወደነበረችበት ማዕርግ ተመለሰች ብዬ ጽፌ ነበር። አሁን ግን ሐሳቤን እስረዝሜ ብመለከት ከቀድሞ ማዕርጓ በልጣ አየኋት ቅዱስ ወብፁዕ የቅዱስ ማርቆ፣ ስብከት ፓፓና ፓትሪያርክ ፻፲፫ኛው አቡነ ዮሐንስ ኢትዮጵያን ስለማፍቀር ብለው ምስርና ኢትዮጵያ ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሃይማኖትና በወንድምነት አንድነትና ከሁሉም ወገን ጳጳስ እሾማለሁ ብለው ከኢትዮጵያ አምስት ጳጳስ አቡነ ሳዊሮስን፥ አቡነ አብርሃምን፥ አቡነ ጴጥሮስን፥ አቡነ ሚካኤልን፥ አቡነ ይስሐቅን ሾሙ።ደግሞም የዓለምን ነገሥታት መላክተኞች ተሰብስበው የምስርና የኢትዮጵያ ጳጳሳት በንድነት ሆነው ቀብተው በኤሌትሪክ ሌሊቱን እንዴ ቀን ያደረጉ ሰሎሞንን በሰማይ ንስሮች በክንፋቸው እያነጋበቡ ያጠሉት ነበር እደሚባል ሁሉ በአሮፕላን ጥላ ታጅበ በቀድሞ ዘመን የነገሡ ማነው ከቀድሞው ዘመን ይልቅ አሁን የኢትዮጵያ ልጆች እውቀታቸው የሰፋ ጥበባቸው የበዛ በአሮፓውያን እውቀት አንጻር ሁኑአል ልጅ መልአኩ በያንን ደህነን ሕፃን አታዩትምን ለኢትዮጵያ ለሀገሩ እርዳታ በፍጥነት እንደመጣ ሁሉ ።

ክቡራን የኢትዮጵያ ልጆች ስንኳን ደስ አላችሁ ይህነን ብርሃን ለማየት ያበቃንን አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን እንመሰግናለን ። ብርሃናችንን ንጉሣችን ጃንሆይን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ለዘለዓለም ያኑርልን አሜን ።

ታዛዢ አሽከራችሁ አረቢ አስተማሪ ወልደ ሥላሴ

ስለ ዘውድ በዓል የተደረገ ግብዣ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ስላደረጉና ደስታው ስለበዛ ፩ኛ የደስታ ተካፋይ የሆኑት ክቡር ደጃዝማች ብሩ በኅዳር ፬ ቀን ሐሙስ ደስታዬን ቤተ ዘመድን ጠርቼ እንድገልጽ ሲሉ ለግብዣ ከቤታቸው ድረስ ብዙ መኳንንትና የሴት ወይዛዝር ጠርተው ነበር።የተጠሩትም ሰዎች ስማቸው ከዚህ ቀጥሎ እንደተጻፈው ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል አስፋ ወሰን ። ክቡር ልጅ መኰንን።ክቡር ደጃዝማች ደስታ።ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ፤ ክቡር ቢትወደድ ጌታቸው።ክቡር ደጃዝማች አበበ።ክቡር ደጃዝማች አምባቸው። ክቡር ደጃዝማች አበራ።ክቡር ደጃዝማች አቻሜለህ።ክቡር ደጃዝማች በላይ። ክቡር ደጃዝማች አምዴ። ክቡር ራስ ገብረ ሕይወት።ክብርት ወይዘሮ ተናኘ ወርቅ።ክብርት ወይዘሮ ሮማነ ወርቅ።ክብርት ወይዘሮ ፀሐይ። ክብርት ወይዘሮ ዘነበ ወርቅ። ክብርት ወይዘሮ ወሰን የለሽ።የምስራች እምሩ። እምሳለ ኅሩይ።ክብርት ወይዘሮ አስቴር። እነዚህ ነበሩ።ልክ በ፮ ሰዓት መጥተው ብዙ ግብዣ ተደርጎላቸው ነበርና እንደማዕርጉ እስከ፱ ሰዓት ተጋበዙ።የተሰናዳውንም የግብዣውን ዓይነት ቍጥሩን ለማወቅ አልችልም።በጣም ያማረ ግብዣ ተደርጎ ነበር። ግብዣውም አልቆ ሽምፓኝ መከፈት በተጀመረ ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ተነሥተው ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር ተናገሩና ሰውን በጣም ደስ አሰኙት ።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ክቡርልጅ መኰንን፡ክቡራን መኳንንቶችና ወይዛዝሮች ሆይ።

የበዓላችንን ደስታ ለመካፈል ጥሪዬን አክብራችሁ እቤቴ ድረስ በመምጣታችሁ እጅግ ደስ ይለኛል ። ከደስታዬም ብዛት የተነሣ በፊታችሁ ቆሜ አመሰግናችሁ ዘንድ ይገባኛል። ይኸውም የዛሬው አንድነት መሰብሰባችን የደጉን ንጉሠ ነገሥታችንን በዓል ለማክበርና ለዘለዓለሙ መታሰቢያ አድርገን ልንተሰሰብበት እንደሆነ ይገልጽልኛል ። ሀገራችን ኢትዮጵያ እኛም ልጆቿ ታላቅ ዕድለኞች ነን። ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በዚሁ ዕድሜአችን ስንት ደጋግ ሥራ አየን።ይልቁንም አሁን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አልጋ ወራሽ ተብለው ተያዙ ጀምሮ እስከ ዛሬ የኢትዮጵያን አካኋንና የኛን የልጆቿን አሠለጣጠን የከተማውን ጽዳት ልብ አድርጎ ለተመለከተው በጣም ያስደንቃል። ይህ ሁሉ እግዚአብሔር መንፈሱን በኛ ላይ ስላበረከተ ነው።

ልዑል የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና

ክቡር ልጅ መኰንን ሆይ፡እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ የደጉ አባታችሁን በረከት ይከፍላችሁ ዘንድ፥አባታችሁንም በውቀትና በገልግሎት ትረዱ ዘንድ የደጉ የአባታችሁ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቅብዐ መንፈስ ቅዱስ አይለያችሁ፥ አባታችሁ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በድካማቸውና ለሀገራቸው በማሰባቸው በርኅራኄ አቸውም ዋጋቸውን አላሳጣቸውምና እናንተም በደግነትና በቅንነት የአባታችሁን ሐሳብ በመከተል አጸናንቶ ያባታችሁን ዕድል ፈንታ ጽዋ ተርታውን እንድታገኙ ያድርጋችሁ።እግዚአብሔር ያባታችሁን ድካም ደግሞ በናንተ ላይ ይግለጽ ። እናንተንም በዕደሜአችሁ አቆይቶ ደጉ አባታችሁ እኛን ሰብስበው በዓልና ደስታ እንዳደረጉ ልጆቻችሁን ሰብስባችሁ በዓልና ደስታ እንድ ትካፈሉ ያድርጋችሁ።እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ብርሃናችንን ከመሀከላችን እያጥፋብን፥ ዕድለኛዪቱ ለእቴጌ መነን፥ ለሐሳብዎ ተካፋይ ለሆነው ለልዑል አስፋ ወሰን ሰላምና ጤና ይሁንልን ብዬ ምርቃቴን ጨርሼ ጽዋዬን አነሣለሁ ።

ከዚህ በኋላ ብዙ አውቶሞቢል እንደማዕርጉ ተሰናድቶ ነበርና ከአውቶሞቢሉ ክብርት ወይዘሮ አማከለችም ያማረ ልብሳቸውን ለብሰው ልጆቻቸውንም ጨምረው ለግብዣ የተጠሩት ሁሉ ፩ ሳይቀሩ ነፋስ ለመቀበል የጊፈርሳን ድልድይ አልፎ ካለው ወንዝ ላይ ያማረ ድንኳን ተተክሎ ብዙ ሽምፓኝና ሌላም በያይነቱ መጠጥ ተሰናድቶ ቆይቶ ነበርና ከዚያ እንደደረሱ የሴት ወይዛዝሩን ከድንኳን አሳርፈው መኳንንቱ ይላማ

ወረቀት ተተክሎ ብዙ ተኵስ አደረጉ። በዚየም መሀከል ሽምፓኝ ግብዣ ተደረገ።ከዚያውም ላይ ተሰማ አቡላሽ የሚባል አጫዋች ነበርና እየሸለለና እየተጫወተ የጃንሆይን ልጆች እጅግ ደስ አሰኛቸው። እንዲህም ሆኖ ነፋስ ከተቀበሉ በኋላ በ፲፩ሰዓት ከዚያ ተነሥተው ሮቤንስ ሆቴል ቻይ ግብዣ ተደረገና ብዙ አመሹ። በዚያም ጊዜ ሮፓውያን ደስ የሚያሰኝ ዳንስ አደረጉ። የኢትዮጵያም አጫዋቾች በአንገታቸውና በቃላቸው እየዘፈኑ ደስ ሲአሰኙ አምሽተው ከዚያ በኋላ ከሌሊቱ ፩ሰዓት ሲሆን ተነሥተው ግሌዝ ሆቴል ሒደው ሲኒማ ሲያዩ አምሽተው እየተ ሰነባበቱ ሔዱ። ክቡር ደጃዝማች ብሩ ግን የንጉሥን ልጆች እቤታቸው አግብተው ልክ ፫ ሰዓት ሲሆን ከቤታቸው ገቡ ክቡር ደጃዝማች ብሩ ይህን ሁሉ ፈንጠዝያና ጨዋታ የጃንሆይን ልጆች ያዘው ማድረጋቸው በውነት የፍቅር አገልጋይና መን ግሥታቸውን አጥብቀው የሚወዱ መሆናቸውን ይገልጽልናል። ግብዣቸውም የኢትዮጵያን ሰው ብቻ እንኳ አይደለም። አስቀድመውም ከኤሮፓ እንግዶችና እዚህም ካሉት ከሮፓውያን ወዳጆቻቸውን ጠርተው ጋብዘዋል ።

የሚአስደንቅ ግብር ።

ለዘውዱ በዓል ከተመረጡት ከ፯ቀን በኋላ ከረቡዕና ከዓርብ በቀር ደግሞ በሁለተኛው ሳምንት ግብር ሁኖ ሰንበተ፡በኅዳር ፯ቀን እሑድ የተደረገው ግብር እጅግ የሚያስደንቅ ነበር።አደራረጉንም ቀጥለን ጽፈነዋል ። ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና እቴጌ ለመኳንንቱና ለወይዛዝሩ ግብር አድርገው ውለው ከ፯ሰዓት በኋላ ወደታላቁ አዳራሽ ገብተው በወርቅ ከተሠራው አጐበር አጠገብ ልዩ ሁኖ በተሠራው የወርቅ ወምበር ተቀመጡ፤በከተማ ኑዋሪዎች የጦሬ አገር ሰዎች ሁሉ ተጠርተው ነበርና በልዩ ልዩ ሥራ ላይ ያሉትም ዲሬክተሮች ሁሉ ተጠርተው ከታላላቆች የኢትዮጵያ መኳንንትም እንግዶችን ለማስተናገድ በየገበታው መጀመሪያ ተቀምጠው ቀጥለው እንግዶች ተቀምጠው ነበር ። ዲሬክተሮችም እንዲሁም በመጀመሪያው ገበታ ተቀምጠው ቀጥለው እንግዶች ተቀምጠው ነበር። የእንግዶችም አቀማመጥ በየነገዳቸው በካርታ ተለይቶ ነበር ። የመጠጡ ዓይነት በየፊቱ ተደርድሮ ለዓይን እጅግ ያምር ነበር። የሰውንም ብዛት ስናየው መቀመጫ የሚአጣ መስሎን ነበር። ነገር ግን አሰናጂዎች እጅግ ጥንቁቆች ስለሆኑ ቦታው ተርፎ ቀረ እንጂ አልጐደለባቸውም።የግብዣው ነገር እጅግ የሚአስደንቅ ነበር አሳላፊዎችም እጅግ የጠዳ የጠዳ ልብስ ለብሰው እጃቸውን በነጭ ሹራብ ሸፍነው ሲፋጠኑ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ። የመጠጡም ዓይነት እጅግ ብዙ ነበርና የተቀመጠው ሰው የፈቀደውን ዓይነት ቀድቶ ይጠጣ ነበር ። ከዚያ ሁሉ ከተሰበሰበው ከሮፓ መጠጥ ሁሉ የኢትዮጵያን የማር ጠጅና የማር አረቄ እንግዶች በጣም አደነቁ፣ብርቱ ስለሆነ አረቄውን እጅግ አል ደፈሩትም፣ጠጁን ግን ብዙዎቹ ደስ ብልዋቸው ሌላውን ትተው ጠጁን ብቻ ጠጡ ። በልተን ጠጥተን ከጠገብን በኋላ በሼፓኝም ጊዜ ክቡር ደጃዝማች ብሩ የሲዳሞ ገዥ የሚከተለውን ዲስኩር አነበቡና ሰውን ሁሉ ደስ አሰኝተው አስጨበጨቡት።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጃንሆይ፥ እቴጌ ሆይ ።

ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ፈጣሪዎን እየፈሩና እያመሰገኑ በንጹሕ ልቦናዎም ትእዛዙን እየፈጸሙ ለታላቅ አገርዎ ለለምለሚቷ ኢትዮጵያ የደከሙላት ድካምና የሠሩላት ሥራ በዓለሙ ሁሉ ተሰምቶ ይኖራል ።

ልዑል እግዚአብሔርም ጥቂት ጥቂት እያለ የድካምዎን ዋጋ በየጊዜው አላሳጣዎትም። ነገር ግን ምንም እንኳ በየጊዜው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኙት ዋጋ ሁላችንን ቢየልቁ ደስ የሚአሰኝ ቢሆን ልዑል አልጋ ወራሽ ከተባሉ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ታላቁ አሳብና ደስታችን የሚገለጽበት ቀን መፈጸሚያና መጨረሻው አልደረሰም ነበርና እነሆ ዛሬ በተሰበሰቡት በታላላቅ በኢትዮጵያ መኳንንትና ደግሞም ጥበብና እውቀት ተስፋፍቶ በተሰጣቸው በኤሮፓውያን ወዳጆቻችንና ክቡራኖች ጉባኤ መሐከል የሚገለጽበትና በተለየ ግርማዊነትዎ ላይ ሉል የሚጨብጡበት ቀን ስለሆነ ለቸሩ እግዚአብሔር የሚገባውን ጥልቅ ምስጋናዬንና የርዕዎንም የክብርዎን ገናንነት ከዚህ ቀጥዬ የጻፍኩትን ትንሽ ቃል እናገር ዘንድ ፈቃድ እለምናለሁ።

የመወደድና የመፈራት የውቀትና የትዕግሥት ሀብትና ቅባት የተሰጠዎ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በድካምዎና በትጋትዎ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኙትን ክብርዎንና ገናናነትዎን ፈጽሞ በጭራሽ የሚናገር አንደበትና ልሳን አገኝ አይመስለኝም ።

ጃንሆይ ።

ይኸውም የክብርዎ ገናናነት በመንግሥት ተወላጅነትዎ ብቻ ሳይሆን በደግነትዎና በጥበብዎ በፍቅር አገልግሎትዎና በትሕትናዎ ኢትዮጵያ ለወጠነችው መንገድ መሪዋና ፈጻሚዋ መሆንዎን አውቃ መርጣዎታለች።እግዚአብሔርም ሐሳብዋን ፈጽሞ ያባትዎን የቅዱስ ዳዊትን ቅብዐ መንግሥት ስለከፈለዎ የተለየ ምስጋናዬን ለዘለዓለሙ አላቋርጽም ።

ጃንሆይ ።

አልጋ ወራሽ ተብለው እስከ ዛሬ ለተገባዎ ዘውድ እስቲበቁ መንግሥትዎ ኢትዮጵያን እንደረዷትና እንዳስከበሩዋት እኛንም ሕዝቢቿን ካለ ማወቅ ወደ ማወቅ እንዳረማመዱን አእምሮአችን ይመለከተዋል ። የሥልጣኔአችንና የእርምጃችንም አፈጣጠን ለጐረቤቶቻችን ሁሉ ይገርማቸዋል ። ሥራዎ በመላ ኢትዮጵያውያን ልብ እንደሐውልት ሆኖ ተቀርጾ ይኖራል ። ይልቁንም ኤሮፓ አገር ሒደው ተራርቃ የነበረች ኢትዮጵያን ተዓለም ነገሥታት አቃርበው ያንድነት ማኅበር እንድታገኝ አድርገው ብዙ ነፃነታችንን ጠንቅቀው በፍቅር ያስተሳሰሩንን አንረሳውም ።

ደግሞ እንደዚሁም ለኢትዮጵያ ለሀገርዎና ለሕዝብዎ ቀን ድካም፥ሌት ንዋም ሳይወስንዎ ሕይወትዎን መሥዋዕት አድርገው የተለየ ፍቅርዎንና እርዳታዎን የገለጡባቸው ሥራዎች ብዙ ናቸው ። አሁንም በየክፍሉ በዝርዝር ለመናገር ጊዜ አላገኝም ። እንደ ማዕበል የሚፈስ ብርሃን ሥራዎንና

ሐሳብዎን ስንቱን እናገረዋለሁ ዓለሙ ሁሉ በሀገር ውዴታዎና ለሥራ በመፋጠንዎ እንዳመሰገነዎ እናውቃለን ።

እንዲያውም እኛ ከመንግሥትዎ በታች ሥልጣን ሰጥ-ተው በሀገር ግዛት ላይ ያቆሙን መኳንንትና መሳፍንቶችዎ ፈጽመን በሥራዎና በሐሳብዎ በንረዳዎ ነው እንጂ እንደ ጃንሆይስ ሐሳብና ትጋት ኢትዮጵያ እንዳየናቸውና እንደምን ሰማቸው ሀገሮች ፈጽማ ትሆን ነበር።ለደግ ሥራ አለመፋጠ-ናችን ነው እንጂ የፀሐዩን ንጉሠ ነገሥታችንን ፍለጋ ተከት ለን ጥበብ ትጌይስ እምኵሉ መዛግብት ያለውን ይዘን በየሥ ራችን ለርዳታዎ ብንፋጠን እኛም አሽከሮችዎ ተከባሪዎችዎ እንደ ከነብ መብላለጥ ከመንበረ ዳዊትዎ በታች ተጽፈን የልጅ ልጆቻችን ያደንቁን ያመሰግኑን ነበር ። ይኸንኑም የጀመሩ ክቡራን አሉ በነሱ መቅናት ይገባናል ።

ጃንሆይ

እኛ የኢትዮጵያ ልጆች በምንሠራው ሥራ ሁሉ ከሌላው አገር ልዩ በመሆናችንና ወደ ኋላ በመቅረታችን እያዘንና እየ-ተሰቀቅን ስንኖር የነበርነው ቸር ርኅሩኅ የሆነ እምላክ እርስዎን ያህል ብርሃንና መሪ ከሰጠን በኋዘን ተሰብሮ የነበረ አንገታችንን በኃይለ ሥላሴ አቅንተን ሳንሰቀቅና ሳናስብ ግርማዊነትዎን ጋሻ አድርገን በተቻለን ትምህርት ለሀገራችን እያሰብንና እየ-ተፉ ብን ባመንግሥትዎም ላይ የሚነሣውን ዓመፀኛ ለመቅጣት የተዘጋጀን ነን ስንኳንስ ኤሮፕላኖችንና ታንክን ያህል አጋዥ አምጥተው እየረዱን ወደሁም የተሳሉ መድፎችንና መትረየሶ-ችም ተጨምረውልንና እንዲሁም በወትሮው መሣሪያችን ቢሆን ለሀገራችንና ለመንግሥታችን ደማችንን እንደ ውኃ እንድናፈስ ጥርጥር የለውም ።

መንግሥቶቻችንን ዓይናችን እስኪታክተን ያየናቸው በቀኝና በግራዎ ተቀምጠው የነበሩ ልዑላን ክቡራን መኳንንቶችዎና ደግሞም በኋላዎ ቆመው ይታዩ የነበሩ ታማኞች አርበኞችዎ በፊትዎም እንደ ጐርፍ ውኃ ይፈስ የነበረው ሠራዊትዎ ኢዮ-አብና አቢሣ ላባትዎ ለዳዊት ሕይወታቸውን ይሠዉለት እንደነበሩ እንደነዚያ ሁነው ለመንግሥትዎ ለሞታቸው የማ-ይገበዙ ቄራጦች መሆናቸውን ማንም አይስተውም ።

ከዚሁም ንግግራችን ላይ የኢትዮጵያን ስም አድሰው ላስጠሩ ለኃያሉ ለድል አድራጊው ለብርቱው ፎገና ለገናናው ንጉሥ ለዳግማዊ ምኒልክ ምንኛ ስጋና ይብቃቸው?ልንዘነጋቸው አይገባንም ።

፪ኛ ም፥ያቧታቸውን አልጋ ተቀብለው በትሕትናና በኀዘን ገዝተው የሚገባዎን እርስዎን የተኩልን ግርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ ምን ያውቁ ምን ይረቁ እያልን ልናመሰግናቸው ይገባናል ።

ደግሞም በሥራዎ ሁሉ የተመረጡና የተወደዱ ግርማዊ ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የትልቁ አባትዎ ያርበኛውን የስሙ ጥሩውን የልዑል ራስ መኰንንን ስምና ግርማ እንዳሉ አድርገው የሚያስነሡ ደጉ ፍሬ ምን ያደንቁ ለተለየ ክብርዎ ወሰን የሌለው ምስጋና ይገባዎታል። ።

ጃን ሆይ

ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ቅድስት ብፅዕት የነበሩት የኢትዮጵያውያን እናታችንን በ፲፱፻፳፪ ዓመት እግዚ-አብሔር ከሚያልፈው ወደማያልፈው ዓለም ወሰደብን እግዚ-አብሔር ቸርነቱ አያልቅበትምና በደከሙበት መንግሥትዎ ለሕዝቡ እረኛ ላልጋውም ዳኛ እርስዎን ተኳቶ በመንግሥትዎ ጊዜ ኢትዮጵያ ጐረቤቶችዋን ጠርታ ያንድነትዋን ምልክትና ክብሯን ስለገለጠች ታላቅ ደስታ በልቦናዬ ይፈላል።ይኸውም ታላቁ ደስታዬ ሁል ጊዜ በልቦናዬ አዲስ ሁኖ የሚኖር ነው ይህችን የዛሬን ቀን ለዘለዓለሙ አልረሳትም ። መንግሥትዎ ይፅናልን ሀብትና ዕድሜዎን ያስፋልንለዕድለኛዪቱ ለእቴጌ መነን ለሐሳብዎ ተካፋይ ለሆነው ለልዑል አስፋ ወሰን ሰላምና ጤና ይሁንልን አርበኞችዎ ጀግኖችዎ ኃይላቸው እየፀና ይኑሩ አገራ-ችን መኩሪያችን ኢትዮጵያ ነፃነቷን ይዛ ለዘለዓለሙ ሕያውትሁን ብዬ ከዙፋንዎ በታች ወድቄ ደስታዬን በመግለጥ በግርማዊ ፊትዎ ቁሜ ጽዋዬን አንሥቼ እጠጣለሁ ።

እኔ ታማኝ ገባርዎ ወታደርዎ ደጃዝማች ብሩ።

ከታላላቆች መኳንንት እንዲህ ያለ ቃል ሲወጣ እጅግ ደስ ያሰኛል። ከዚህ ነኚህ ብዙ የሮፓ ሰዎች እየተነሡ ዲስኩር ሲኣደርጉ ጭብጨባው ይደምቅ ነበር ።

ከዚህም አንዱ አርመናዊው ሙሴ ዋህራም የአነበቡት ዲስኩር የሚከተለው ነው ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ።

ግርማዊት እቴጌ ሆይ።

ልዑላን መኳንንትና ክቡራት ወይዛዝሮች ሆይ።
ይህ የዛሬው ዕለት ፍጹም ተድላ ደስታን የተሸከመ ቡሩክ ቀን ስለሆነ ፩ት ነገር ለመናገር ያሳስበኛል። ማለት አንዱ የሚደ-ረገው በዓል ፤ ፩ተኛው ይህ የዘውድ በዓል ከተፈጸመ በኋላ የሚከተለው የተሻሻለ መልካሙ ሐሳብና ሥራ ነው ። ይኸን-ኑም ፈቃድዎ ሁኖ ሐሳቤን በጭሩ ከግርማዊነትዎ ፊት ቁሜ እገልጽልዎ ዘንድ እንዲፈቅዱልኝ እለምናለሁ።

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እዴዊሃ ኀበ እግዚአብሔር።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ጠበቃት ወደፊትም የልጅ ልጆችሽን እንዲህ አድርጌ እጠብቅልሻለሁ ሲል ሁለቱን እጆ-ቹን በራሷ ላይ ዘርግቶ ያሳያትንና የነገራትን ቃል በውነተኛው ግርማዊ ን ነ ቀዳ ኃ ሥ መንግሥትና በግርማዊት ንግሥት እቴጌ መነን ጊዜ ተገለጸልን።

ከዚህም በፊት ታላቁ ግርማዊ ን ነ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከእግዚአብሔር በታች ከሕዝብ በላይ ሁነው የትምህርትንና ጥበብን ዕውቀትን በጣም ወዳጅ ስለነበሩ በሀገራቸው እንዲለማና እንዲሰፋ የሥልጣኔን መንገድ ተቀብለው ብዙ ሥራ ሠርተው አጸደቁ።

ከዚያም ወዲህ ልጃቸው ግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ(ነፍሳቸውን ይማርና)ግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንንን የኢ. መ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ አድርገው

ታላቁ አባታቸው የጀመሩትን መልካም ሥራ ለመፈጸም አጥብቀው ሲጥሩ ነበር።

ቀዳማዊ አፄ ኀይለ ሥላሴም ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሀገር ሥልጣኔ ለማብዛት፣የሕዝብን ፍቅር ለማስፋት የዛሬ ፯ ዓመት ኢትዮጵያ ከሥልጣኔ ደረጃ ተለይታ እንዳትቀር ብለው ከዓለም ነገሥታት ማኅበር እንድትገባ አደረጓት።

ይኸንንም ማድረጋቸው የአፄ ምኒልክን አልጋ በመውረሳቸው ብቻ አይደለም። ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣቸው መልካም ሰውነታቸውና ሀብታቸው ያገር ፍቅራቸው ፈጽመው ያባታቸውን ጐዳና ተከትለው ይበልጥ የአገራቸውን ትምህርት አብዝተው በአእምሮ ብርሃንና ሰላም ለማረግ ነው እንጂ።

ስለዘውዱ በዓል የተሠራውና የተዘጋጀው ሥራ ሁሉ የበዛና የተረፈ ለዘላለም የሚኖር መታሰቢያ ነው።

ሀገርዎ ኢትዮጵያ ትምህርትና ልማት እንድታገኝ ከታላላቅ በላባቶች የሆኑ መኳንንቶች ጋር በጣም ያማረና የተመሰገነ ጉዞ አድርገው አውሮጳ ተሻግረው ከየመንግሥቱና ከየንጉሡ በዓይነ ሥጋ ከሀገርዎ መኳንንቶች ጋራ አስተዋውቀው ከሀገራቸው ነገሥታት በኩል በክብር ሆነው አገራችችንን ኢትዮጵያን አስወድደው ፍቅር አፅንተው ስለተመለሱ አሁን በምናየው ስለክብረ ዘውዱ ምርቃንና ጸጋ የዋና ዋና ንጉሥ ልጆችና ታማኝ ከሆኑ መላክተኞቻቸው ጋር በመጡ ጊዜ የተደረገው ጌጥና አቀባበል መስተንግዶ እጅግ ያማረና የተመሰገነ ሁኑአል።

እነርሱም ማኅበርን ለማስፋት ፍቅርን ለማፅናት ብለው ከሩቅ ሀገራቸው ይኸንን ፅኑ ውድዎንና ፍቅርዎን አስበው በሰላም መጥተው የከበረ ዘውድዎን በዓል አክብረው መዋላቸው ይህ ተድላ ደስታ የሞገስ ቀን ሁኖልን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አዲስ ዘመን ተብሎ በወርቅ ቀለም ይጻፋል ።

ይህ አጀማመርዎ ወደፊት በትጋት ሳያቆምና ሳያቋርጥ በውነተኛው አካሔድ ያገርዎ ሥልጣኔ እንዲፀናና እንዲበረታ እውነተኛ ምኞቴን እገልጻለሁ ።

ከሁን በፊት የሠራሁትና ያገለገልሁት ድካሜም ሳይሰማኝ በአለኝ ዓቅሜና እግዚአብሔር በሰጠኝ እውቀት ለኢትዮጵያ መንግሥትዎ በትጋት ፈጽሜ ለማገልገል የተዘጋጀሁ ነኝ ።

እንደኔ ያሉ ከኔም የሚበልጡ የኢትዮጵያ ወጣቶችና ጐበዛዝቶች ሁሉ ትምህርትንና ሥራን ተጠምተዋል ሥልጣኔና ጥበብ በብዙ ለመጠጣት ተዘጋጅተዋል ይመስለኛልና ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ሳይሰለቸንና ሳይታክተን የውቀትና የሥራ ጥበብን ሳንለቅ የኢትዮጵያ የናታችንን ፍቅር ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልብ እንደማይለይ አድርገን ያገር ፍቅር ለጃንሆይ ክብር ነውና ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እያልን በተድላና በደስታ እንኖራለን ።

ጃንሆይ ።

ለዙፋንዎ ፅናት፣ ለመንግሥትዎ ስፋት፣ ለድሜዎ ብዛት ለእቴጌ መነንም ሕይወት ለልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን እድገት ኢትዮጵያን በቅንለሚያገለግሉና ለሚረዱ መኳንንትና ሕዝብ ኃይልና ስምምነት ይስጣቸው እያልሁ ስለገሬ ስለ ኢትዮጵያ ጽዋዬን እነሣለሁ ።

ኢትዮጵያ ከልጆቿና ከወዳጆቿ ጋራ በፍቅርና በሰላም ለዘለዓለም ትኑርልን ።

አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን ስል እጠጣለሁ ።

ዋሀራም

ሙዚቃ ነፊዎችም በአስተማሪአቸው በሙሴ ኒኮላ እየተመሩ በልዩ ልዩ ድምፅ ሲነፉ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር።

የአቀማመጥ ተራ ።

በጃንሆይ ቀኝ እቴጌ፣ ቀጥለው የፈረንሳዊ መንግሥት መልእክተኛ ሙሴ ለጋርድ፣ ልዑል ራስ ሥዩም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል አስፋ ወሰን፣ከቡር ራስ ከበደ መንገሻ ። በጃንሆይ ግራ ወገን ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ፣ ልዑል ራስ ጉግሣ አርአያ፣ የባንኩ ዋና ሹም ሙሴ ኰሌር ነበሩ ።

የተጠሩት እንግዶች ሁሉ እጅግ ደስ ብሏቸው በአንድነት እየተነሡ ለንጉሥና ለእቴጌይቱ ጤና እያሉ ይመርቁ ነበር ። ከየነገዳቸውም አንዳንዳቸው እየተነሡ ዲስኩር ያደርጉ ነበር። ምን ይሆናል መስማት እንደማይቻል እየሆን ላልነገርኋችሁ ሰዎች እንዴት አድርጌ ብጽፍላችሁ እንደሚቻል ይሆንላችሁ ይሆን? እስከ ፲ሰዓት ድረስ ደስ ብሎን ውለን ሰው ሁሉ በፈቃዱ እያመሰገነ ወጣ ጃንሆይና እቴጌም ተነሡ ። ሚለፍ እያቀርም ያችም ቀን አለፈች።

ታላቅ ብርሃን

ደጉን ንጉሥ አፄ ኃይለ ሥላሴን አምላክ ከሰጣችሁ ። የኢትዮጵያ ልጆች በጣም ደስ ይበላችሁ።በዙፋንዎ ላይ ሕይወትዎን ጠብቆልን ከርበኞቿ ጋራ ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑርልን አሜን።የኢትዮጵያ ወዳጅ ቴዎፋኒ ዳቢስ ወሰጋ ሰዩ።

ማመልከቻ

ኅዳር ፬ ቀን የወጣው ብርሃንና ሰላም ፵፩ ቍጥር የተባለው ፵፯ ቍጥር ነው።ይህ የዛሬው ጋዜጣ ፵፯ ቍጥር መሆኑ ነው ገጹም እንደዚሁ ተዛውሯል

የምሕረት ብዛት።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመባል የበቁ በትዕግሥትና በምሕረት ብዛት መሆኑን ማንም አይስተውም እነሆ አሁንም ደጃዝማች አባውቃውን መጀመሪያ የሞት ፍርድ ቢፈረድባቸው እንኳ በር ቃሥረው እንዲቀመጡ አድርገው ማርዋቸው።ቀጥለው የቁም እሥር ሁነው እንዲቈዩ አዝዘው ምሕረት አደረጉላቸው።አሁን ደግሞ ሙሉ ምሕረት አድርገውላቸው በኅዳር ፱ቀን አዲስ አበባ ገቡ።እንኳን የደጃዝማች አባውቃው ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ይህን ምሕረት የሰማ ሰው ሁሉ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ትዕግሥትና ምሕረት እጅግ ያመሰግናል።ላይችል አይሰጠውም የተባለውን ተረት እውነተኛ ቃል እንጂ ተረት አለመሆኑን ዛሬ ተረዳን ነው። ትዕግሥትና መንግሥት ሲገናኙ እንደምን ደስ ያሰኛሉ።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ከርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኩት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሰን ማክዳም የሚባል በኤ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ሰላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በቃመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሰምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኩላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ-ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዳሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ-ርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሠ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንምየንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX.)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

ኣዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልክ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፰
6me ANNEE № 48

ሐሙስ ኅዳር ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ።
JEUDI 26 NOVEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie Un an 5 Thalers
Etranger Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

የዘውድ በዓል መታሰቢያ ።

እስቀድመን እንዳስታወቅነው የዘውዱ በዓል እስከዛሬ ድረስ ገና እንደተዘጋጀ ነው ። በኅዳር ፲፩ቀን እስላሞችና ባንያኖች በታላቁ በጃንሆይ አዳራሽ በየጠባያቸው ተጋበዙ። የግርማዊ ንጉሥ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አሳባቸው ቅን ስለሆነ ለባንያኖች እንደጠባያቸው ለእስላሞችም እንደጠባያቸው የሚያሰናዱላቸው ቀጥረው ስለ ጋበዙአቸው እንኳን የተጋበዙትንና ዕውቀት የአላቸውን በከተማ ኑአሪዎችን ሰዎች ሁሉ እጅግ ደስ ብሎአቸዋል።እስላሞች በሃይማኖት አንድ ሲሆኑ በብዙ ነገድ ይለያያሉ የኢትዮጵያ እስላሞች፥ ቡሀሬዎች የተባሉ የህንድ እስላሞች፥ የዓረብ አገር እስላሞች ከልዩ ልዩ ነገድም የሆኑ ብዙ እስላሞች ነበሩ። ታላቁን አዳራሽ ከታች እስከላይ ሞልተውት ነበር እጅግ ደስ ብሎአቸው ተጋብዘው በየቋንቋቸው ሲአመሰግኑ ከኢትዮጵያ እስላሞች አንዱ የሚከተለውን ዲስኩር በግጥም አድርጎ ተናገረ ።

እግዚአብሔር ይመስገን ዓለሙ ደመቀ
የነፃነቱ ምንጭ ኢትዮጵያ ፈለቀ
የነገሥታት ፀሐይ ገናአሁን ዘለቀ
ዱሮ በሰሎሞን በርቶ የጠለቀ
እንደምን አማረ እንደምን ደመቀ
ሀገር ብርሃን ሆነ ጨለማው አለቀ
ሕዝቡም በአንድ አደረ እየተደነቀ
እስላም ክርስቲያኑም ደስ እያለው ሳቀ
የእግዚአብሔር ስጦታ መቸም አላለቀ
ኢትዮጵያ ዋሎ በሽፍን ሲቈላ
ዕውቀት እየጠፋው ደጋ እያለ ቈላ

ድንግርግር እያለው እየጠፋው መላ
በኃይለሥላሴ በትልቁ ጥላ
ክርስቲያን አረፈ እስላምና ጋላ
የዕውቀትን ፍሬ ለቃቅሞ እየበላ
እንዲህ ያለ ንጉሥ ሐሳብ የሚሞላ
ዕድሜውን ያርዝመው እንደ ማቱ ሳላ
ዛሬነው ያገኘች ኢትዮጵያ ፈንታ
ጃንሆይና እቴጌ ያገኙት ደስታ
ሕዝቡን ደስ አሰኙ በያለበት ቦታ
በጥቅምት ብቅ አለች ቀዳሚለት ማታ
እቴጌ መንንም በዙፋን ላይ ወጥታ
በጣም ይገባታል ኢትዮጵያ እልልታ
እስላም ክርስቲያኑ በጣም እንበርታ
አግኝተናልና የፀሐይ ወገግታ
ሁልህም አደራ ጸሎትህን አበርታ
ካለህ፣ት ቦታ በጧትም በማታ
ጠላታቸው እንዲያልቅ ጅግና እንዲበረታ
የእስክንድር ሹመት የሔደበት ጠፍቶ
ስንት ሺ ዓመታት እንዲያው ተጕላልቶ
ዛሬ ብቅ አለልን ብርሃኑን አብርቶ
ዕድሜአቸው ይሰንብት ጠላታቸው ጠፍቶ
ለልጅ ልጅ ይሻገር ዳር እስተ ዳር ሰፍቶ

የቀጥበሬው ሼህ

እናት ልጆቿን እንደጠባይ እንደ ጠበያቸው እንድታሳድግ መንግሥትም የሕዝብ እናት ነውና ሕዝቡን በየጠበያቸው ሲጠብቃቸው እጅግደስያሰኛል መንግሥቱም ሀብታም ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያን በዓል ።

በኅዳር ፲፪ ቀን የቅዱስ ሚካኤል በዓል ነበር። ጃንሆይና እቴጌ ጳጳሳቱና መኳንንቱ ወይዛዝሩ ተሰብስበው በየካ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ታላቅ በዓል ተደርጎ ነበር። ካህናቱም እስተምህር ለነ ሰዓልናከ በዓሥርቱ ወአርባዕቱ ትንብልናከ ዓይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ እያሉ ሲዘምሩ እጅግ ደስ ያሰኙ ነበር ዑደቱም ከተፈጸመ በኋላ አቡነ ሳዊሮስ ስብከት ሰብከው ሕዝቡንና መንግሥቱን ባርከው አሰናበቱ ።

የእንግዳው መሳፈር

የጀርመን መንግሥት ሁለተኛው መልእክተኛ በፊተኛው እንዳልነው አገር ለማየት ወደ አምቦና ወደ ሂይ ሒደው ሰንብተው ነበርና ከዚያ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው በኅዳር ፲፪ ቀን ከማታው በአንድ ሰዓት በባቡር ተሳፈሩ አካሔዳቸውም በጂቡቲ ባሕር ገብተው ወደ እንግሊዝ ቅኝ ወደ ናይሮቢ ሒደው ወደ ቻደና ሒደው ከዚያ በኋላ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ይባላል ባደህና ወደ አገራቸው እንዲገቡ እንመኝላቸዋለን ።

የከተማ ወሬ ።

በኅዳር ፲፱ቀን የከንቲባ ነሲቡ የልጃቸው ክርስትና በ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ነበር። የክርስትና አባቱም ል ጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ ነበሩ ። የክርስትና ስሙም ፍቁረ አምላክ ተባለ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል አስፋ ወሰንም ለማቋቋም መጥተው ነበር። ሌሎችም ለማቋቋም የተጠሩ መኳንንት ነበሩ። ከቅዳሴም በኋላ ልዑል አስፋ ወሰንና ልጅ መኰንን ኃይለ ሥላሴ ከንቲባ ነሲቡ ከልጆቻቸውና ከባለቤታቸው ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋራ ክቡር ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ክቡር ደጃዝማች አምዴን ጨምረው በቤተ ክርስቲያኑ ደረጃ ላይ ቁመው ለመታሰቢያ ፎቶግራፍ ተነሡ ። ከዚህ በኋላ በኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽ ልዑል አስፋወሰን ቤት ቀርስ ተጋብዘው ወደ ቤታቸው ሔዱና በዚያ በሚኣምረው በከንቲባ ነሲቡ አዳራሽ ታላቅ ግብዣ ተደረገ። ሰውም እጅግ ብዙ ነበረ የአቀማመጡ ሥርዓትና የምግቡና የመጠጡ ዓይነት እጅግ የሚያስደንቅ ነበር። ፲ ሰዓት እስኪሆን ድረስ ከተጠሩት ሰዎች ብዙዎች ቆዩ።ከዚህም በኋላ እየመረቁ ሔዱ።

መቼም ሲቀናም ሲጠምም ፩ቀን ነውና ደግሞ ፪ዚሁ ቀን ለእሩት ወደ ክቡር ደጃዝማች ዓምዴ ቤት ተጠርቼ ሒጄ ነበር የተጠሩትም ብዙ ሰዎች ነበሩ ። ከተጠሩትም የሚበዙት ሰዎች ቤተ ዘመዶቻችው ነበሩ። ከወዳጆቻቸውም ጥቂቶች ነበሩ። የአቀማመጡና የግብዣው ነገር እንደ ሮፓ ሥርዓት በ ሹካና በሣህን ነበረ። የድግሱም ምክንያት ስለ ዘውዱ በዓል መታሰብያ ነበረ የምግቡና የመጠጡ ዓይነት እጅግ ብዙ ነበረ በጣዕሙም እጅግ የተደነቀ ነበረ ስንጫወትና ስንበላ ስንጠጣ አምሽተን ሳናውቀው ፫ ሰዓት አለፈ ከዚህ በኋላ በሽምፓኝ ተመራርቀን ተለያየን። በፍቅር ጊዜውን የሚያሳልፍ ሰው እንዴት የታደለ ነው? የዘውድ በዓል መታሰቢያ እስከ ዛሬ አለማቋረጡን ለብርሃንና ሰላም ወዳጆች ለማስታወቅ ጽፌላችኋለሁ።

ትርፌ ወዳጄ።

መንግሥተ ኢትዮጵያ ቀዳማዊ ወደኃራዊ

የኢትዮጵያ መሳፍንት ሊቃውንትና መኳንንት ወይዛዝርና ሠራዊት። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጥበብና ከዕውቀት ከሥልጣኔም ሥራ ሁሉ ወደ ኋላ መቄየቷ ብዙ ደስ የሚአሰኝ ተስፋ ያለበት ምሥጢር ነው እንጂ የሚያሳዝንና የሚያስቆረቍር እንዳይደለ የልቡናዬን ሐሳብ አስታውቃችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችሁን እለምናለሁ ። አሳቡም እንደሚከተለው ቃል ነው ደስ የሚያሰኘውን ደግ ሥራ ሁሉ ወደ ኋላ ማድረግ ለእግዚአብሔር ልማዱ ነው ። ይኸውም በብዙ ወገን ይመረመራል ። መጀመሪ በጨለማና በብርሃን፥ በሌሊትና በመዓልት ይታያል ። ሁለተኛም በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን ይታወቃል ። ሦስተኛም በምድራዊት ኢየሩሳሌምና በኢየሩሳሌም ሰማያዊት መወረስ ይረዳል ። ምንም ወደፊት ለሚመጣው ዘመን ጥንት ቢሆን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ ዛሬ ሲያያዝ ለመጣው ዘመን ወደኋላ የሚሆን መጨረሻ ጌታችን ሰው የሆነበት ዘመን ነው ። ከጌታችን ሰው መሆን አስቀድሞ በነበረው ዘመን ሁሉ ከተገለጠው ዕውቀትና ጥበብ በጌታችን ሰው መሆን የተገለጠው ዕውቀትና ጥበብ የበለጠ እንደ ሆነ ሲያስረዳ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው በመጀመሪያ መልእክቱ ነግሮናል። ምዕራፍ ፪ቍ፯ ። አሁንም ዛሬ በዓለም ሁሉ ከተገለጠው ዕውቀትና

ጥበብ ከተደረገውም ሥልጣኔ በኢትዮጵያ ከዛሬ ጀምሮ እን-ጓዲህ ወዲህ የሚገኘው ዕውቀትና ጥበብ የሚደረገውም ሥልጣኔእ ጅግ የበለጠ ደስ የሚያሰኝ እየሆነ እንዲሔድ ብዙ ተስፋ እናደርጋለን።በዮሐንስ ወንጌል እንደተነገረ ። ምዕ ፪ ቍ ፲ ሰው ሁሉ ጣዕሙ ደስ የሚያሰኘውን መልካም ወይን አስቀ-ድሞ ያጠጣል ። ኋላ መናኛውን ተርታውን ያቀርባል አንተ ግን ጣዕሙ ደስ የሚያሰኘውን መልካም ወይን ወደኋላ አቈየህ ብሎ የሠርግ ቤት አለቃ ለሙሽራው የነገረው ነገር ኢትዮጵያ እስከ አሁን ከሥልጣኔ ወደኋላ መቈየቷ በውቀትና በጥበብ በሥልጣኔም አረማመድ ከሁሉ የበለጠችደስ የምታሰኝ እንድ ትሆን ያስረዳናል ። ወደኋላም የቈየ ነገር ሁሉ ደገኛ እንደሆነ ወጕንድዮታ ያጤይቅ ጽድቀ ዚአሃ ብሎ ዮሐንስ አፈ ወርቅ የተናገረው ቃል ይገልጥልናል ። ወደኋላም የመቈየቷ ምክ-ንያት ለልጆቷ የዕውቀት መሪ የሥልጣኔ ፊታውራሪ የሚሆን ደገኛው ልጅዋ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴንጉሠ ነገሥት የሚነግሥበት ዘመን ወደኋላ ስለ ሆነ ይመስለናል።ለዚህም የታመነ ምስክር አለው ። ደገኛይቱ የብርሃን ሕግ ወንጌል ወደኋላ መሆንዋ መሬ ሠሪዋ ዓቢይ ሊቀ ካህናቷ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግሥበት ዘመን ወደኋላ ስለሆነ መሆኑንማንም ክርስቲያን አይስተውም ። የኢትዮጵያም መንግሥት ለእግዚአብሔር መንግሥተ ለወንጌል የታመነች የተረዳች ምሳሌዋ እንደ ሆነች ከዚህ በሚከተለው ቃል እናሳያለን ። ደገኛይቱ የብርሃን ሕግ ወንጌል ቀዳማዊ ደኃራዊ ናት።ቀዳማዊነቷ ከዖሪት ሊቀ ካህናት ከአሮን በሚቀ-ድም በመልከ ጼዴቅ ለአብርሃም ተገልጻለች፤ነገርግን በዚያ ጊዜ ሀብትና ልጅነት ጥበብና ዕውቀት ብርሃንና ሥልጣን አልተገ-ኘባትም ። ደኃራዊነቷም ውሥጥ ለውሥጥ በተስፋ ስትነገር ከኖረች በኋላ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼ-ዴቅ ንጉሠ ጽድቅንጉሠ ሰላም በተባለ በአማናዊ መልከጼዴቅ በክርስቶስ ሀብትና ልጅነት ጥበብና ዕውቀት ብርሃንና ሥልጣን ተገኝቶባታል ። የኢትዮጵያም መንግሥት ቀዳማዊነቷ ከዓለም ነገሥታት ሁሉ በሚቀድም በቀዳማዊ ዳዊት ልጅ በዕብነ ሐኪም ተጀምራለች ። ነገር ግን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ጥበብና የሥልጣኔ ሥራ አልተገለጸባትም።ደኃራዊነቷም ከዕብነ ሐኪም ጀምሮ እስከ ዛሬ በተስፋ ስታያያዝ ከኖረች በኋላ ዛሬ ንጉሠ ጽድቅ ንጉሠ ሰላም ለተባለው ለክርስቶስ ምስለኔ በሆነ ማልሳዊ መልከ ጼዴቅ ልንለው በሚገባ በንጉሠ ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጥበብና ዕውቀት ሥልጣኔና ሰላም ተገልጾባት ይኸውና እንደ ፀሐይ አሸብርቃ ስታበራ እናያታለን።እስከ አሁን በጥ-በብና በዕውቀት ከሁሉ በታች የነበረች ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲህ የዕውቀትደረጃ እየተራመደች የሥልጣኔ ሥራ እየሠራች ከከፍታ ወደከፍታ መሄድዋ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ለሚያትም ዓይን ሁሉ እጅግ ድንቅ እንደሆነች ክቡር ዳዊት የተናገረውን ቃል ምስክር እናደርጋለን። ዕብን እንተ መነንዋ ነደቅት ወይእቲ ኮነት ውስተ ርእሰ ማእዘንት።እምኀበ እግዚ-አብሔር ኮነት ዛቲ ወነካር ይእቲ ለአዕይንቲነ፡ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፌሣሕ ወንትኃሠይ ባቲ ። አእግዚኦ እድኅነነ አእግዚኦ ሰርኅ ፍኖተነ ። ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ባረክናክሙ እምቤተ እግዚአብሔር።እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ ። ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት በኀበ እለ ያስተሐምምዎ እስከአቅርንቲሁ ለምሥዋዕ።ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነ ግርማዊ ንጉሣችንን በማን እንመስለዋለን በሙሴን በኢ-ያሱ፤ በዳዊትን በሰሎሞን፤በሕዝቅያስን በኢዮስያስ፤ ወይስ በዘ-ሩባቤል፤በቈስጠንጢኖስ በአኖሬዎስ፤ በዘይኑን በአርቃዲዎስ ። እነዚህ አሁን የጠራናቸው ሁሉ የውቀትና የደግነት ሥራ ቢሠሩ ዘመንና ሰው እያገዛቸው አብነት የሚሆን መሪ ፊታውራሪ እየኖራቸው ነው ግርማዊ ንጉሣችን ግን አጋዥና መሪ ሳይኖረው አበባ ከቅጠሉ ጫፍ እንዲፈነዳ ጥበብንና የሀገርን ሥልጣኔ ከራሱ አንቅቶ መሪ አብነት ስለ ሆነልን ምሳሌ ለመሻት ብንዞር ብንባክን አናገኝለትምና እንዲያው በጠቅላላው ሺሕ ዓመት ያንግሠው፣ ዕድሜውን ያርዝመው ፤ ዘሩን የተባረከ ያድርገው ብለን ነገራችንን በአንክሮ በተዘክሮ በተደሞ እንወስናለን ።

የሊቃውንትና የሐዲሳት መምህር አለቃ ኅሩይ ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ።

እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ አስመስሎ እንደ ፈጠረው ለማስረዳት ከአካሉ አንዳንዱን በየጊዜው በዚህ ዓለም በሚ-ነግሡ ነገሥታት ላይይገልጣል።እግዚአብሔር ዓይኑን በነገሠ ጊዜ ተቀብቶ የነገሠ ንጉሥ ከክፉውም ከበጎውም የሚሠወረው አንድ ነገር የለም ። የዱር አንበሳ በባሕር ያለ ዓሣ ሳይቀር ተገልጦ ይታየዋል። ነገር ግን ዘመኑ የፍቅር የስምም ዘመን ካልሆነ ክፉውን ሳያጠፋ በጎውን ሳያሰፋ ይቀራል ። እግዚ-አብሔር ጆሮውን በነገሠ ጊዜ ተቀብቶ የነገሠ ንጉሥ በዓለም ሁሉ የተሠራ ነገር በጆሮው ሳይገባ አያድርም። ነገር ግን ዘመኑ የሥልጣኔ ስላልሆነና ፍቅር ስላልሰፋ ክፉውን ሳያጠፋ በጎ-ውን ነገር ሳያሰፋ ይቀራል።ግርማዊ ጃንሆይ ተቀብተው የነገ-ሡበት ዘመን እግዚአብሔር ዓለምን ጠቅልሎ የያዘበት ገናና ቀኝ ክንዱንና ፍጹም ልቡናውን በነገሠበት ጊዜ መሆኑ አይጠረጠርም።ወረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ ብእሴ ምእመን ዘከመ ልብየ እንዲል ። ይህም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር በ፮ቀን ሥራውን ሁሉ ጨርሶ በሰባተኛው ቀን እንዳረፈ ። ግርማዊነ-ትዎም ዓለምን ጠቅልሎ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ በነገሠ በ፯ ትያው ወር ጀምሮ ብዙዎች የዓለም ነገሥታት ዘሮች ከሕዝብና ከአሕዛብ ጋራ በብዙ ሠረገላ የሚሔዱበት መንገድ የሚገቡበት ጥሩ ጥሩ ቤት በፊታቸው ለመቅረብ የሚገባ ሁሉ ማሰናዳቱና በሰባተኛው ወር የልብ ዕረፍት የሚሆን የዘውድ በዓል ማድ-ረጉ የተካከለ ምሳሌ ነው። ይልቁንም እንደ ጳንጠሌዎን ዕለቱን ዘፍ አለምልሞ ለሥራ ማድረስ።ሐወ አቈረ በምርዋይ እንዲል። እንደ ሮሙ ንጉሥ ልጅ እንደ ገሪማ ዕለቱን ዘርቶ አለምልሞ ላበባ ለፍሬ ማድረሱ ደገርማል ፤ ገረምከኒ ያሰኛል ። ከዚህም ቀጥሎ እግዚአብሔር ሲመሰገን የሠራዊት ጌታ እንደ መሆኑ ከበውት የቆሙት በክብር የሚያመሰግኑት መላእክት በትጋታቸ ው አብረው እንዲመሰገኑ ካገራችን ተወልደው በሚገባ፤ተመ-ርጠው ኢትዮጵያ ካመነች ከተጠመቀች ጀምሮ እስካሁን ሁኖ የማያውቀውን ዕድላቸው ከድልም ጋራ ገጥሞ ጳጳሳት ለሆኑ ለኢትዮጵያ ልጆች ምስጋና እናቀርባለን ።

ከዚህም ቀጥለን ለልዑላን ክቡራን የመንግሥት ዘሮች እንዲሁም እንደ ልብ መክሬ እንዳንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው ለመንግሥትዎ ረዳቶች ስለ ሆኑ እናመሰግናቸዋለን። አገርንና አገርንም ላማስታረቅና በፍቅር ለማስተሳሰር ባሕሩን በመርከብ የብሱን በባቡር ገሥግሰው የመጡትን እንግዶች እናመሰግናቸዋለን በጎውም ነገር ተፈጽሞላቸው ብፁዓን ገብርያነ ሰላም መባሏን እንመኝላቸዋለን ።

ስለ ጳጳሳት ምስጋና ፡፡

እሬ ገና እሬ ጕዱ ። ንጉሠ ነገሥት ባለ ዘውዱ ።
ስድስት ጳጳሳት ወለዱ ።
ጳጳሶቻችን ተወሐዱ ። በማዕርግም ተጓደዱ ።
መልካምን ልማድ አለመዱ። ድንግልናን አስወደዱ ፡፡

ስለ ልዑላን ምስጋና ።

የንጉሣችን ሰቀላው ። ልዑል ካሣ ነው ባላው ።
ነፋስ አይጥለው አይገፋው። ከሥሩ ጥኑ ነው ።
ራስ ኃይሉ ባለድሉ ። የንጉሣችን ባለሚሉ ።
እየ ጠባዩ ወይ አመሉ ።
እልፍኝ ተከተው እንዳልዋሉ ።
ለንጉሥ ሥራ ሲታገሉ ።
ይገርመዋል ሰው ሁሉ ።
ራስ ሥዩም ፊተ መልካም ለጠላቱ አይነካም ።
ጥልቅነቱ አይለካም ።
ራስ ጉግሣ አንበሳ። በትክክል በሬሳ ።

ጃንሆይ ሽሕ ዓመት ያንግሥዎ

ኢትዮጵያ ትቅና አርቶዶክሳዊት ሃይማኖት ትፅና። አሜን
አለቃ መርሻ ዘውእቱ መርስዔ ኀዘን ።

ዲስኩር ።

ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳሳት አቡነ ቄርሎስ ነቢዩ ሳሙኤል ለበቃው ማዕርግ መድረስዎ ደግነትዎን ያሳስበናል ትእዛዘ አበዊነ ሐዋርያት ኢያንብር ብእሲ ውስተ ልቡቂመ ወበቀለ ወቅንአተ ወጽልአ ላዕለ ቢጹ ወኢ ላዕለ መኑሂ አባቶቻችን ሐዋርያት ያዘዙትን ትእዛዝ ሰው በልቡናው ቂም በቀል እንዳያሳድር አንዱ በአንዱ እንዳይቀና ከወንድሙ ከማንም ጋራ እንዳይጣላ ሰላምና ፍቅር በሆነ ስብከትዎ አረጋግተው ንጉሣችንን ጠብቀው በመኖርዎ ኢትዮጵያ ምኞቷን ታቀርባለች

ቀዳማውያን የተባሉ ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት አፅማደ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ እንተ ሐዋርያት የሐዋርያት ክፍል በምትሆን በጸለዩት ጸሎት በአቀረቡት መሥዋዕት ልመናቸውን ተቀብሎ መዝገበ ጥበብ ንጉሣቸውን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ጠብቆ ዓባይ ከመፍሰስ ፀሐይ ከመመላለስ እንዳያቋርጥ ደገኛውምስጋናቸውን ሳያቋርጡ ይትቀፈጽ ኖኅተ ብርሃን የብርሃን ደጅ ይከፈት ብለው በክብር ዘውዳቸውን ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማቅረባቸው በልበ ሥላሴ መታወቁን ዕለቷ ትመሰክራለች እንድም ሊቀ ጳጳሳቸውን አቡነ ቄርሎስን ተከትለው መምህረ ትምህርት አጥተው ተረፈ መሥዋዕት ሁነው የሚኖሩ በኃጢአት ቍራኝነት ተይዘው በአረማውያን ስም የተቀመጡትን እንዘ ቀዲሙ ኢኮንክሙ ሕዝበ ይእዜሰ ሕዝበ እግዚአብሔር አንትሙ እያላችሁ ከይብሰተ ኃጢአት ወደልምላሜ ንስሐ ከልምላሜ ንስሐ ወደጽጌ ትሩፋት ከጽጌ ትሩፋት ወደፍሬ ክብር አድርሳችሁ ወአንበሮሙ ውስተ ገነተ ዔዶም ጽባሓዊ በአላው ቦታ መኖራቸውን ተስፋ እናደርጋለን ።

እስመ በዲበ ሠናይቱ ለሰብእተአዛዚ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘሠረፀ እምይሁዳ ወእምሥርወ ዕሤይ ።

ተውህበ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሰሎሞን ያለው ምንም ለጊዜውለነሱ ቢሆንፍጻሜው ለንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መሆኑ እጅግ ደስ ያሰኛል ብሩህ አእምሮ ጨለማውን ወደ ብርሃን የመለሰው የጥበብዎ ምላት ስፋት ምን ይረቅ ምን ይደንቅ ይኸነን ለቻለ ጳርማዊነትዎ አንክሮ ይገባል ከኤሮጳ ነገሥታት ጋራ በመተያየት መ፡ዋወቅን ገንዘብ በማድረግ ያዘጋጁ በውቀት የገነነ በዓለም የታወቀ መንግሥትዎ ፀሐይ በደረሰበት ደርሶ መመስገኑ ክብሩ ምን ይበዛ በዓለም ያሉ ነገሥታትም ንዑ ናዕብዮ ንዑ ናብዕሎ ንዑ ናክብሮ ለበዓለ በዓላት ቅድስት ኢትዮጵያ እያሉ በትሕትና በትኅዕግሥት የሠሩት ዘውድዎን ርእሰ በዓላት ማድረጋቸው ፍጹም ታምራት ነው ። የኤፍራታ ዕፃ የምትሆኝ ክብርት ኢትዮጵያ ጽዋዐ መዓዛሺን በጥበቡ እየሰፈረ ለዓለም አድሎታልና ነገሥታተ ይሁዳ ከነገሡበት ብትበልጭ እንጂ አታንሺም ካህናትምኃያላነ ኢትዮጵያ መኳንንት አርኅዉ ኖኀተ መኳንንት ወይትረኃዋ ኖኀት እለ አምፍጥረት ይባእንጉሠ ስብሓትእያሉ በማንገሣቸው ብምንእንመስላቸዋለን ክዘንቱ ብርሃን ከኖሙ ጥበበ ወአእምሮበአለው መኖራቸውን እናስባለን ሙሴና ጴጥሮስ ኢትነውምኑ ብለው ቢጠይቁት ለጴጥሮስ በዕንቍ ጽዋዕ ውኃ መልቶ በአርአያ እንዳሳየው ሁሉ በዕውቀት ቀዳማዊ የሆኑ ተዐቀብ ኵሎ እንዘ ኢትነውም ያለውን ቃል ተመልክተው ንዋም ሳይኖርብዎ እንሰ ተሠየምኩ ንጉሠ በላዕሌሆሙ እያሰቡ ኢትዮጵያን ሲጠብቁ መኖርዎ ለኛ ዕድል ፈንታችን ጽዋዕ ተርታችን መሆኑን ተረዳነው ። መዓተ ንጉሥ ከመ ጣሕረ አንበሳ ያለውን አውቀን ከልቡናችን ክፉ ነገርን ማፍራትን ትተን በመረዳድ በመፍራት በመንቀጥቀጥ መኖር ለኛ ይገባናል መርከብን እምነት የተዋሐደው አሳብ መኪናን ጥበብ ባቡርን ፍቅር አድርገው በቆሙት ሐውልት አሳላፊ አስተናባሪ የሆነ የኢትዮጵያ ፍቅር መልከኛዋ ጽውዐ ብርሃን ይዞ ቁሞ ከመጠበቁ የተነሣ ፍሥሓ ወሰላም መሆኑን ያስረዳል ። ቦጋለ ደርሰህ ።

ዲስኩር ።

የነገሥታት ንጉሥ የጀግናዎች ጀግና የኢትዮጵያ ታላቁ ኮከብ በራሱ ጥበብ በእግዚአብሔር ኃይል ያሠለጠነን መንበርና ዕውቀት ወራሽ የክብር ዘውዳቸውን ጫኑ በዚች በተከበረቺዋ ቀን የክብሩ ፀዳል በዓለሙ ሁሉ ለዘለዓለም ክብራዊ ሞገሱን ያበራል(ኢትዮጵያ)በኅዘንና በትካዜ ለሕዝቧ ፅናትና ጠባቂ የለመነችበትን ተስፋዋን አስፈጸማት የኢትዮጵያን ዕውቀትና ሥልጣኔ መሠረት አዳሽ የተዋበችዋ የወይኑዋ ሙሽራ የኢትዮጵያ

ፀዳል የሕዝቧ ጠባቂ በሙሉ ልባቸው በታላቅ እውቀታቸው ብአስተዋይ ዓይናቸው ሌት ተቀን ለክብረቷና ለትልቅነቷ ብትጋት በታላቅ እርምጃ የደከሙላትን የድካማቸውን ዋጋ ብታላቁ እግዚአብሔር ቸርነት አገኙ የክብር ዘውዳቸውን ጫኑ፣ ይህቺውም ታላቂቱ የክብር ቀን በኢትዮጵያ ሕዝብና በመላው ዓለም ለዘለዓለም የማይረሳ ነው ። ኢትዮጵያ በታላላቅ ተራሮችዋ ላይ የተሰማትን የክብራዊ ደስታ በዓለሙ ሁሉ እያስተጋባች ክብራዊ ዜማዋን ትዘምራለች የኢትዮጵያ ታላቁ ኮከብ በ፲፱፻፱ ዓ ም ከሐረርጌ እንደመጡ ሀገራቸውንና ሕዝብቸውን አደጋ በሚአደርስ በታላቅ ጉዳት ላይ በማግኘታቸው አዘናቸውና ትካዜአቸው ወሰን የሌለው ነበር ነገር ግን የልብን ደኅና አሳብ አስተዋይ እግዚአብሔር እንደ ሕፃኑ ሳሙኤል ብኑሮአቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቁን ሥራ ፈጻሚነትና አንበሳውን መንግሥት ጠባቂነት አሰናድቶ አኑሮ ነበርና ኢትዮጵያን ከጉዳት የሚያድናትን ታላቁን አዋቂ ሰጣት ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤ በኋላ በተሰበሰቡት ሐዋርያት መሐከል ሳያስቡት ገብቶ ሰላም ለናንት ይሁን እንዳለ እንደዚሁም ጃንሆይ ኃይለሥላሴ ሰላም ለናንት ይሁን ብለው በትረመንግሥታቸውን ይዘው በዙፋኑ ላይ የእርዳታ ክንፋቸውን ዘረጉ ጃንሆይም የተረከቡትን ታላቅ ሥራ መፈጸም ጀመሩ ከዚአችም ከታሪከኛዋ ቀን ጀምሮ ኢትዮጵያ በሥልጣኔ እርምጃ ታበራ ጀመር ከዚህ ቀደም በብርሃንና ሰላም እንደጻፍኩት ሆፒታሎች መንገዶች የንግድ ማኅበር የርሻ ሚኒስቴርና እንደዚሁ የመሰሉትን ለኢትዮጵያ መንግሥት ጥቅምና ሥልጣኔ ከመ ቅጽበተ ዓይን በጥቂት ጊዜ ተቋቋመ ጃንሆይም በትጋትና በድካም ኢትዮጵያን እከፍተኛው እሥልጣኔው ደረጃ አደረሷት የጀመሩትም ሥራ ጥቂት አልነበረም በጥቂት ቀንም የሚፈጸም አልበረም ነገር ግን ብዙ ብርታትና ድካም ያስፈልግ ነበርእንጂ በመንገዳቸውም የተዘራውን እሾህና ምሣር ታላቁ አዋቂ ታግለውና ተራምደው በትዕግሥትና በርኅራኄነት ኢትዮጵያ (ኤውሮፓዊት) ኢትዮጵያ አደረጓት ከታላላቆቹም ከዓለም ክፍል ካሉት መንግሥታቶች በአደረሷት ጊዜ ጭለማዎች ተአምረኛውን ብርሃን ሊቃወሙ የጽልመት ጉማቸውን አጠሉባቸው ነገር ግን በብርሃናዊ ይቅርታቸው በአስተዋይ ዓይናቸው የሥልጣኔን ብርሃን ዘርተው ያጠሉትን ጉሞች ብታተኑ ለተመለከተውም ኢትዮጵያዊ ጃንሆይ ኃይለ ሥላሴ አሳባቸውና ምኞታቸው በሙሉ ልባቸው ኢትዮጵያን ለማሳደግና ደገኛውን የሥልጣኔ መንገድ ለመስጠት ቁርጥ አሳባቸውን በክብራዊ እውቀታቸው ፈጸሙ እንደዚሁም የንግሥት ሳባ ያውሮጳ ጉዞዋን ተከታይ መጀመሪያው ንጉሥ በተቀደሰው በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ከጉልላቱ በታች በጕረቤቶቻቸውና በማኅበረተኞቻቸው መሐከል የተገባቸው የክብር ዘውዳቸውን በዓል አከበሩ ኢትዮጵያም በዙፋኑ ላይ ክንፏን ዘርግታ እየባረከች የደስታ እልልታዋን ትዘምራለች ኪሩቤልና ሱራፌል ለክርስቲያናዊቱ መንግሥት ጽናትና ለገዢዋ ክብረት ለእግዚአብሔር ምስጋናቸውን ይዘምራሉ አእዋፎችም በሰማይ እያንዣበቡ ለተባረከችዋ ቀን ለጃንሆይ ክብር ይቀኛሉ እኛም ለደገኛው ንጉሥ ለመልካሙ መሪ ለትልቁ ኮከብ ክብረ በዓል ልባችን በደስታ እየሞላ ዕድሜ ለኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ለእቴጌ መነን ዕድሜ ለጃንሆይ ቤተሰቦች ዕድሜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ተኑር እያልን ለኢትዮጵያ ስፋትና ጽናት ለእግዚአብሔር ምስጋናችንን እናቀርባለን ።ሚካኤል ማክራስ

ስለ ዘውድ በዓል ግጥም ።

የዓለም እንግዶች ቢመጡ መልካም ነው ።
የሚበላው ሞልቷል አገሩ ለምለም ነው ።
የሚጠጣው ሞልቷል ጠጃችን ብዙ ነው ።
የማኅበሩ ሙሴ ኃይለ ሥላሴ ነው ።
በጃንሆይ ደግነት በእቴጌ ጸሎት ።
ዘውዱን በራሳቸው አቀማጠሉት ።
የጃንሆይን ዋና ሰዎችም አዩት ።
ከበሕር ጠልቀው ነው ዘውዱን ያወጡት ፡
ሲናገር ለስላሳ ሲፈርድ ሚዛን ።
አንድ ቀን አይሰለች አይንቅ ድኃውን ።
ያቄየው በዓለም ኃይለ ሥላሴን ።
መጀመሪያ ማዕርግ አንደኛ ቍጥር ፡
ኃይለ ሥላሴ ነው ያገሩ መምሕር ።
አስተካክሎ ገዛው ከዳር እስከ ዳር ።
እኔን ደስ ብሎኛል አምላክ ይመስከር ፡
ችግር አይነከንም እንግዲህ እኛን ።
እንኳን አጤ እያሉ ደግሞ አሸፉ ወሰን ።
ለኃይለ ሥላሴ እድሜ ይስጥልን ።
እቴጌ ዕንቍጣጣሽ መነን አበባዬ ።
እንደተመኘሁት ነገሠ ጌታዬ ።
ግብራቸው ሰፊ ነው እቴጌ መነን ።
አበሉት አጠጡት ያን ሁሉ ካህን ።
አልጋ ወራሽ ሆነ ልጅ አስፋ ወሰን ።
ተሱ ያስከትሉት ጃንሆይ አባክዎ ።
ያያቱን ስም ይዟል መኰንን ልጅዎ ።
ዕድሜውን ይስጥልኝ ከነደስታዎ ።
ተውት አትከልክሉት እንደልቡ ይብላ።
በመስቀል ተባርኮ የወጣውን አውራ።
ጥንቱን ሀረማያ ዋና የተማሩ ።
ጃንሆይ እንደሙሴ ባሕር ተሻገሩ ።
ከበሕር እንደ ዓሣ የወጣው ንጉሥ ።
ያስበርከን ጀመር በኗጻጻስ ።
እንዲህ ያለ ንጉሥ ታሪክ የሚሠራ ።
መትረየሱን በታንክ ፖስታውን በአሞራ ።
ግርግዳው ጠቅል ነው ጣራው መኰንን
እንደራ አሳላፊ እቴጌ መነን
ፍጥረቱ ለዚህ ነው የሚያመሰግን ።
መልካም ተናኘ ወርቅ ልዑል አስፋ ወሰን ።
ብዙ ዓለም አሳይዋት አገራችንን
ለኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ይስጥልን
ፍርዱ ትክክል ነው እግዚአብሔርን ፈሪ ።
ኃይለ ሥላሴ ነው የዕውቀታችን መሪ ፡ ጥሩ ብርሄ

መወድስ ቅኔ

ሆሣዕና ኵሉ ዓለም ኃይለ ሥላሴ
ላዕለ ነገሥታት ኵሎሙ እንዘ ነጋሢ ለሊሁ
እርአየ ቅድመ ትሕትናሁ
ለነገሥት ዘያፈትዎሙ ይርአዩ ኪያሁ
ወበክብረ ዓለም ትንሣኤሁ
ኃይለ ሥላሴ አዳም ለአዳም ፋሲካሁ
ይሰግድሂ ዘአንበሳ ታሕተ እገሪሁ
ወዘንሥር ምሥራቃዊ ይርዕድ እም ግርማሁ
አከኑ አቅርንት ውስተ እደዊሁ
ወፍትሐ ግፉዓን ነጐድጓድ ይወጽእ እምአፉሁ

መምሬ ይገዙ ።

መወደስ ቅኔ።

እፎኑ ይኤድም መከነ ሐረር
ኃይለ ሥላሴ ሰሎሞን አመ ነግሠ ላዕለ ሕዝብ
እምጣነ በቱ ኀደረ መንፈሰ ምኒልክ ዕፁብ
ወያበርህ ሎሙ ማህቶተ ፍቅር ለሰማዕት ክህናተ ሌዊ በንጹህ ልብ
አለቃ ደስታ ነቅዐ ጥበብ።
እስመ መልዐ ምድረ በረከተ ቄርሎስ ያዕቆብ
ወረደሂ መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ
መልዕልተ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ አክሊለ መንግሥት ዘይዘጋብ
ወይፌውሰሙ ከዐበ ለሕሙማነ ዓይን ወልብ
ፈለገ ሃይማኖት ዘይውኅዝ እምኢትዮጵያ በሕረ ጥበብ

ገብረ እግዚአብሔር ጐሣዬ ድሬ ዳዋ ጉምሩክ ጸሐፊ።

ስለ ዘውድ በዓል ደስታ አራራድያን በሚባለው
የአርመን ተማሪቤት የሚማሩ ልጆች ወደጃንሆይ ግቢ ሒደው
ደስታቸውን በገለጹ ጊዜ የተነበበ ዲስኩር ።

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቡሩክ ነገድ ስለ ጸባልን በሕይ-ወታችን የተሰማ ወሰን የሌለውን ደስታችንን ዳግም ይህ ነገድ ለመላው ኢትዮጵያ ፍሥሓ ይሆን ዘንድ ከርቀት ልብ የፈ-ለቀውን ንጹሕ ምኞታችነን በትሕትና እናቀርባለን።

ጃንሆይ ።

እስከ ዛሬ በጸጋዎ የተከለልንና በፍቅርዎ ስንጠግብ የኖ-ርነው ያርመን ርኁብ ንሕፃናት ይኸውና በፍጹም ደስታ ወደ ግር ማዊነትዎ እንገሰግሳለን።የጸጋና የእራሮት እክናፋዎን ዘርግተው ተቀብለውን ሕሊናችነን የሸፈነውን የድንቊርናን ጽልመት በብርሃን ሐሳብዎ አስወግደው የውቀትና የሥልጣኔን ተራራ በሰላም አዘለቁኝ ።

የቀን ጀምበር። የሌት ጨረቃ፡ የንጋት ከከባችን ነዎትና
ለዘላለም ያኑርዎ።

አራራድያን ከሚባል ያርመን ሕዝብ ተማሪ ቤት
በኵልለእቴጌ የተነበበላቸው መዝሙር ።

ያባት ምስጋና የናት ምርቃን።
ዕድሜ ጨምሮልዎ በቁ ለዚህ ቀን።
በሕይወት ካሉልን የለን ሰቀቀን።
እኛም ሌላውን አንሻም በቃን።
ለተሳተ መሪ ለዕውር ብርሃን።
ያጣን ጠይቀው ጠቀሙ ድሀን
እኛን ለመሰሉ ደግሞ ለብዙኃን።
ይሁን ፍሥሓ ተስፋ ለነዳያን።

ተጻፈ ከዮሐንስ ጴጥሮስያን ተነበበ ከዋርቱሂ ጉለስርያን።

ዲስኩር

በፅዌድኖች ሁሉ ስም ሁነው ክቡር ሙሴ ሻርኒ ቀጥሎ ያለውን ዲስኩር ተናገሩ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትና ግርማዊት እቴጌ ሆይ በራሴና ከዚህ አብረውኝ ባሉት በስዌድኖች ስም ሁኜ የልባችነን ደስታ ሁሉ ገልጨ ለግርማዊነታችሁ ጥልቅ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እኛ ከሩቅ አገር የመጣነ ሰዎች በዚህ አገር በኖርንበት ዘመን ሁሉ እንደ እንግድነት ሁኖ አይሰማንም ይኸውም የኢትዮጵያ ሰዎች ባሳዩን ፍቅር ነው ።

ግርማዊ ሆይ፡ ግርማዊት ሆይ ግርማዊነታችሁ ሥራችነን እንዴት እንዳበረታንና እንደደገፉን አሁን ልናገረው አልችልም ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ በነፃነት ራሲዋን ችላ መኖርዋ በዓ-ለም ሁሉ የታወቀ ነው። እንዲሁም ለወደፊቱ እግዚአብሔር እንዲጠብቃትና ለሁሉም የምታበራ የእውነተኛ ብርሃን እንዲያደርጋት በሰላምና በደኅንነትም እንድትለመልም የብዙ ሰዎች ልመናቸው ነው ።ሕያው አምላክ ጸሎትን ሰሚ ነውና አሁንም ኢትዮጵያን በመጐብኘት ግርማዊነትዎን ስላስነሣላት የንግሡ-ንም በዓል ለማየት ስላበቃን እርሱን እጅግ እናመሰግናለን ።

ዕድሜ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዕድሜ ለእቴጌ መነንና ለልዑላን ልጆቻቸው ይስጥልን ።

ኢትዮጵያን በነፃነት ለዘለዓለም ይጠብቅልን የስዊድን ማኅበር አለቃ ሙሴ ሻርኒ ።

መወደስ ።

በሐፀረ ጥበብ ሕጽራ ለኢትዮጵያ
በስመ ምኒልክ ቡሩክ ከመ ኢይምጻእ ሐሳዊ
ዜና መንግሥትከ ወይን ለእመ ኵሎ ያረዊ
ወንጌለ መንግሥትከ ውስተ ኵሉ
ለሰቢክ አምጣነ ተንሥአ ቄርሎስ ዜናዊ
ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ
ዘመጽሐፈ ዕዳ ሠጠጠ ኂሩትከ መለኮታዊ
ኢይትርፍሂ ከመ ተነግረ በእፈ ሲራክ ለባዊ
ብከ ተሐደሰ መንግሥተ ምኒልክ አረጋዊ
እም አይቴ ዘመጽአ ከመ ኢይበል ዓላዊ
እስመ አንተ ቀዳማዊ ወአንተ ደኃራዊ

ደብተራ መርዓዊ

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ከኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዢና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፈኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ፤፤ ላ፤

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS.

ፔር ዳኔይ።

አ በ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቀሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬምርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት ብወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚስቅ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ ከሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፵፱ 6me ANNÉE № 49		ሐሙስ ኅዳር ፳፭ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም ። JEUDI 4 DECEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።	የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣዘት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።	Abonnements Ethiopie Un an 5 Thalers Etranger Un an 7 Thalers le numero 2 piastres

የቤተ ክርስቲያን በዓል።

በኅዳር ፳፩ ቀን የኅዳር ጽዮን የሚባለው የእመቤታችን በዓል ነበረ። ጃንሆይና እቴጌ ብፁዓን ጳጳሳት መኳንንቱና ሠራዊቱ በከተማ ከሚኖረውም ብዙ ሕዝብ በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ተሰብስበው ታላቅ በዓል አደረጉ ካህናቱም ሲዘምሩ እጅግ አማሩ። ከዑደቱም በኋላ ብፁዕ አቡነ ሳዊሮስ ደስ የሚያሰኝ ስብከት ሰብከው አሳርገው ባርከው ሕዝቡን አሰናበቱ

የከተማ ወሬ

የጀርመን መንግሥት ዋና ጕዳይ ፈጻሚ ሚኒስቴር ሙሴ ሆስን ፌልደር በኅዳር ሐያ ሁለት ቀን አዲስ አበባ ገቡ፣ የውጪ ጕዳይ ዋና ዲሬክቴር ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወደ ብቡር መቋሚያ ወርደው ተቀበሉዋቸው። የከተማው ዘበኞች አለቃ ቫራዝማች አማረም ዘበኞችን በሥርዓት አሰልፈው ተቀበልዋቸው ከዚህ በኋላ ጃንሆይ በላኩላቸው በጥሩ አቶሞቢል ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ጋራ ተቀምጠው ወደ ጀርመን ሌጋስዮን ሔዱ ሰውዩውም እጅግ ባለግርማ ትልቅ ሰው ናቸው በሁለቱ መግሥታት መሀከል ያለውን ወዳጅነት እንዲአበረቱ ተስፋ እናደርጋለን።

የተማሪዎች መመለስ

ፓትሪያርክ አቡነ ዮሐንስ ሊአስተምሩ ሰልሳ ተማሪዎች ከኢትዮጵያ ወደካይሮ ወስደው ነበር።ከነዚህ ከሰልሳው ተማሪዎች ሐያው ለመንፈሳዊ ትምህርት አርባው ለሥጋዊ ትምህርት ነበር የሔዱት አሁን ለሥጋዊ ትምህርት የሔዱት አርባው ተማሪዎች ተመልሰው በኅዳር ፳ቀን ገቡ።ለመንፈሳዊ ትምህርት የሔዱት ሐያው ተማሪዎች ግን እዚያው ቈይተዋል ም-

ክንያቱን ግን መርምረን እውነተኛውን ነገር ስናገኘው እንጽፋለን።

የዘውድ በዓል ከወላሞ ክፍል አማረ ሶዶ ከተማ በክቡር ደጃዝማች ይገዙ ግዛት ።

ክቡር ደጃዝማች ይገዙ ለእንደራሴአቸው ለፈታውራሪ ንጋቱ የንግሥ በዓል በጥቅምት ፳፫ቀን ነው ለንግሥ ቀን የሚገባውን ሁሉ በጣም ማሰብና ማሰናዳት ያስፈልጋል ብለው አስቀድመው ትእዛዛቸውን አሳልፈው ነበርና ። ፊታውራሪ ንጋቱ ይህን የታዘዙትን ለመሥራት ተግተው ለኢትዮጵያ ብርሃን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ስለ ዘውድ በዓል ያደረጉት ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ላይ ይገኛል ። እጅግ ባማረና በተወደደ አክብሮ ፤ በቅን ልቡና በንጹሕ ሕሊና ሆነን ስለ ንግሥ በዓል የኢትዮጵያን ደስታ ተካፋይ እንሁን ብለው እንደልመና ያለ ቃል አስቀድመው ለየመኳንንቱ አመልክተው የሚወደድ ሐሳባቸውን ለመፈጸም ቍርጥ አደረጉ።በከተማም ባገር ቤትም ያለው ሕዝብ ሲሰበሰብ በመጥፎ ሽታ ምክንያት ሕመም እንዳያገኘው አማረ ሶዶ በከተማ ውሥጥ ላፍንጫ የሚሸት፤ ላይን የሚያስቀይም ጕድፍ ሁሉ እየተነሣ እሣሬት ይቀበር ። በከተማውም ውሥጥ ያለ ዛፍ ደን ሆኖ ከተማውን ስለሸፈነ ለሥራ የማይሆነው ፈጽሞ ይመንጠር ሥራ የሚይዘው ቅጠሉ ይመልመል መንገዱም በሰፊው ይሥራ ባገር ቤትም ያለ መኳንንት ወታደርና ባላገር ከባላገር ውሥጥ የጥንት ሽማግሌ እንዳለ ሳይቀር የሰልፍ ልብሱን የጦር መሣሪያውን ይዞ ጥቅምት ፳፪ ቀን አማረ ሶዶ ከተማ ይሰብሰብ ። በከተማም ያለ ካገር ቤትም የሚመጣ ሰው ሁሉ ጌታው ነጭ ልብስ ሲለብስ አሽከሩ እድፍ ልብስ ለብሶ እንዳይታይ አሽከርና ጌታ ሴትና ወንድ ትንሽና ትልቅ ማለት የለምና ሁሉም ልብሱን እያጠበ ንጹሕ ልብስ እንዲለብስ ብለው ለሁሉም አስታወቁት ። ወላሞ ውሥጥ በየድባራቱ ያሉትም ካህናት እንዲመጡ ብለው ፊታውራሪ ንጋቱ ለገዳሙ ሹም ማስታወቂያ የጻፉላቸው ቃል ይህ ነው። ይድረስ ከመምህር ገብረ ሕይወት ። የኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ስለ ክብረ መንግሥትዎ የዘውድዎን በዓል ለማክበር የምንሰበሰበው ጥቅምት ፳፫ ቀን ነው።ወላሞ አውራጃ በየድብራቱ ያሉት ካህናት ሁሉ ልብሰ ተክህኖዋቸውንና የቤተ ክርስቲያን ማገልገያ መሣሪያቸውን እየያዙ ፲፱፻፳፫ ዓ ም ጥቅምት ፳፪ ቀን ቅዳሜ ባራት ሰዓት አማረ ሶዶ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን እንዲሰበሰቡ ይሁን የሚል ትእዛዝ ጥቅምት ፲፮ ቀን አስቀድሞ አለፈላቸው ። በከተማውም ውሥጥ ስለ ፅዳት የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ሰውም የታዘዘውን ቃል ተቀብሎ በየይነቱ አስተካክሎ ሠርቶ ጨረሰ። በሥራው ይሥራ የተባለውም መንገድ ከግቢው ፊት በር ጀምሮ ፤ ገዳም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ድረስ ቢለካ ግራና ቀኝ ፩ሺ፯፻፳፭ ሜትር ቁመት ። ፳፭ ሜትር ወርድ ሆነ ። ስለመንገዱም ትይዩነትና ስፋት ሲመለከቱት በጣም ደስ ያሰኛል ። በዚሁም በ፩ሺ፯፻፳፭ ሜትር መንገድ ከግቢው ጀምሮ እቤተ ክርስቲያኑ ድረስ ግራና ቀኝ በንዲራ ቆመበት ። ደግመሞ ከፊት በር ጀምሮ ከ፫ት ቦታ ላይ ልዩ ልዩ አበባ የሚመስል ባለጌጥ ወረቀት በየይነቱ ተሠርቶ ግራና ቀኝ ባንዲራውን በያዘው እንጨት ላይ በ፳፭ ሜትር ወርድ በሲባን ሆኖ ባ፩ረድፍ ተደርጎ በመሀከሉ ክብረ ስማቸውን ሠራዊቱ ሁሉ እንዲያነበው የሚያስደንቅ በሠለጠነ ገበታ ላይ ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የሚል ቃል በጉልህ ተጽፎ ። ጌታ ሙሴን በታቦቱ ማስተሥርያ ላይ ፪ቱን ኪሩቤል አድርግና ማስተሥርያውን ይሸፍኑ ። ፊታቸው የተያዩ ይሁኑ ዘፀ ፳፭ ፳ ብሎ እንዳዘዘው ዓይነቱ ልዩ በሆነ በኢትዮጵያ ባንዲራ በጽሕፈቱ ግራና ቀኝ ባራት ገጽ ሆኖ የኢትዮጵያ ብርሃን ክብረ ስማቸው የተጻፈበትን ገበታ የባንዲራው ጥላ ፀሐይ አያስነካውም ነበር ። ከግቢውም ውሥጥ ከመጀመሪያው አጥር ከመግቢያው በር ጀምሮ ግብር ማግቢያው አዳራሽ በር ድረስ እንደዚሁ ግራና ቀኝ ባንዲራ ተተክሎ በባንዲራው ተርታውን በየይነቱ ጌጠኛ አበባ ሁሉ ታስሮበታል ። ይኸንንም ጌጠኛ ነገር ሁሉ ለማየት የተሰበሰበውን ሲመለከቱት ገበያ መስሎ ይታይ ነበር ። ጥቅምት ፳፪ ቀን ቅዳሜ በስምንት ሰዓት ለገዳሙ መምህር የጻፉላቸው ቃል ይድረስ ከመምህር ገብረ ሕይወት ጥቅምት ፲፮ ቀን እንደጻፍኩልዎ ስለ ዘውዱ በዓል አገልግሎት ከሩቅ ለሚመጡት ካህናት ራታቸውን የሚያስፈልግ ነውና በየደብሩ ቁጥራቸውን በማኅተምዎ አሁን እንዲያስታውቁኝ ። ላገልግሎቱም ከማታው በ፲፪ ሰዓት ተደውሎ ካህናቱን ከሶስት ቦታ ከፍለው ለኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፣ ከባታቸው ጀምሮ በቃለ እግዚአብሔር እየተነገረ የቆየውን ክብረ መንግሥት አንድ ነጥብ ሳይጐድል በማገልገል እንዲሠራና እንዲፈጸም በጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይሁን የሚል ቃል ጥቅምት ፳፪ ቀን ጻፉላቸው።መምህር ገብረ ሕይወትም ከያድባራቱ የተጠራውም ካህናት መጥቷል።ስለ ክብረ መንግሥቱም የሚሠራውን ሁሉ አሠራለሁ ብኋው መልሱን ቢልኩ ለካህናቱ እንደሚገባ አድርገው እራታቸውን ላኩላቸው።ካህናቱም ከማታው በ፲፪ ሰዓት ደውለው ከሶስት ቦታ ተከፍለው አንዱ ክፍል በሳታት ፪ቱ ክፍል በማኅሌት ሆነው ለነገሥታት የሚገባውን ሁሉ ምስጋናቸውን በቃለ እግዚአብሔር አቀረቡ በማኅሌትም ክፍል ያሉ ካህናት ስቡሕ ብለው ጀምረው ከመልክዐ ሥላሴ ሰላም ለርእስክሙ ዘአስተዋደደ ርእሰ።አጋእዝተ ሥጋ ሥላሴ እንዘ ኢትሌልዩ ነፍሰ።በርኦሰ ኃይለ ሥላሴ አንበሩ አክሊለክሙ ሞገሰብለው።ዚቅ ባረከ ለኃይለ ሥላሴ እን በረ አክሊለ ዲበ እርእሱ ባረከ ለኃይለ ሥላሴ። ለአክሊለ ስም ዘክርስቶስ ባረ ለኃ ሥ ወይቤሎ ዲበ ሠረገላ ዳዊት አንብረከ በረ ለኃ ሥ ብለው አመርግደው ወይቤሎ ዲበ ሠረገላ ዳዊት አነበረከ ባረ ለኃ ሥ እያሉ ወረብ በመልካም ዜማ እያዜሙ እንደ ትንሣኤ ሥርዓት ሁሉም በየጃቸው መብራት ይዘው ቤተ ክርስቲያኑን ውስጡንም ውጭውንም እየዞሩ ዝማሜያቸውን ሲያሳዩ የሥራውን አኳኋን ለመጐብኘት ፊታውራሪ ንጋቱ በለዘቡ ሰዓት ከጥቂት ሰዎች ጋር ሳይታሰቡ በድንገት

ደረሱ።ከማታው በሁለት ሰዓት የመጡ እስከ ሰባትሰዓት ድረስ በካህናቱ መካከል ቁመው ። ካህናቱን ይህች ዕለት ቀድሞም የተባረከች ዕለት ነበረች ። ዘፍጥ ምዕ፪ አሁንም የደስታችንና የብርሃናችን መጀመሪ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክብረ ስማቸውን የምናይበት ቀን ነውና ትጉ እያሉ ካህናቱን ያነቃቁቸዋል ። የሚናገሩትንም ቃለ እግዚአብሔር እየሰሙ የካህናቱን ብዛትና ለቃለ እግዚአብሔር መትጋታቸውን እየተ- መለከቱ ተደስተው ስለ ደስታቸውም የገዳሙን አለቃ መምህር ገብረ ሕይወትን ግምጃ ቀሚስና ወርቅ ጥብጣብ ካባ ሙሉ ልብስ ሸልመው ከመ ፍሕሶ ቀይሕ ከናፍርኪ ጽጌን መረጻድ ሲጀምሩ ፊታውራሪ ንጋቱ ከወደኛ ለሚሠራው ሥራ ሰውን እንደሚገባው በሰልፍ ሥራ አሰናደቼ ከጧቱ ባ፩ ሰዓት እናንተን ለመቀበል እመጣለሁና ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ልብሰ ተክህኖአቸውን ለብሰው መስቀል እየያዙ ተሰናድተው እንዲቆዩኝ ብለው ካህናቱን ለማስጠንቀቅ ላለቃው ነግረው በሰባት ሰዓት ወደግቢ ተመልሰው ሐዱ ዚቅ ሠርፀ መንግሥት ዘእምሥርወ ኃይለ ሥላሴ እንዘ ተሐቅፊዮን መርዓ- ደው ዚቅ አዳም አጥባትኪ እምወይን ይቤለኪ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ። ክበበ ጌራ ወርቅን አመርግደው ዚቅ እዌድሶ እነ ለኃይለ ሥላሴ እስመ አክሊለ ጸጋ አንበረ ዲበ ርእሱ እሉ ። መወድስ መዝሙር ኪነ ጥበቡ ። አርባዕት ፀርሐኃይለ ሥላሴ ። ፍታሕ ሊተ አባዚኦ ወተበቀል በቀልየ ።

ያለቃ ገብረ ኪዳን ቅኔ ።

ለመንግሥተ ዳዊት ጽዮን እመ የሐንፃ ።
ኃይለ ሥላሴ ሰሎሞን እንተ ርቱዓት ፍናዊሁ ።
ፀቃውዐ ጥበበ ይውኅዝ እምከናፍሪሁ ።
አኮኑ ለክብር ወለስብሓት ፤
አክሊል ደመና ሱራፌ ወረደላዕሌሁ ።
፯ቱ አናቅጺሁ ፣ ለወንጌላዊ ዮሐንስ ይትረኃዉ በእዴሁ።
መንግሥትሰ ባሕረ ምሕረት ለዘይጸምእ ተሰፋሁ ።
ኢትኅልፍ እምወሰና ወኢትርኃቅ እምኔሁ
ካህናትኒ ደቂቅ እንዘ ይፀርሑ ።
ይወፅኡ በጽባሕ ወሠርከ ይትፌሥሑ ።

ዓራራት ፤ ለክርስቶስ ይደሉ ስብሓት ።አቡን አልቦ ዘየዐቢ እምዝንቱ ስም ሰላም ናሁ አስተርአየ ጽጌ ካህናቱም ይኸንን ቅኔ ተቀብለው ሌላውንም ለክብረ መንግሥት የሚገባውን ሁሉ አድርገው ቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ልብሰ ተክህኖውን ለብ ሰው መስቀላቸውን ይዘው ደብተሮቹም ለአገልግሎት የሚገባ መሣሪያቸውን ይዘው ከቤተ ክርስቲያኑ ውሥጥ ሥርዓተ ንግሥ ምስባክ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወንጌል ወቀርበ በዓለ መጸለት ሉቃስ ም ፳፪ ፩ ፳፬ ፴ ብለው ምልጣን ርእዩ ዘገብረ እግዚአብሔር ትስመ ለዓለም እግዚኦ ኰነኔከ ሀበ ለንጉሥ ብለው አመልጥነው ሥራቸውን ጨርሰው ተሰናድተው ጠበቁ ። ከሌሊቱም ባሥር ሰዓት ስለሰዉ መሰብሰብ እግቢ ነጋሪት ይጎሰም ነበርና ፊታውራሪ ንጋቱ የሰልፍ ልብሳቸውን ለብሰው ግሬማ ያለው የጦር መሣሪያቸውን ይዘው ለሰልፍ ማስተካከያ ከግቢው ፊት በር ከሰልፍ መጀመሪያ ላይ ድንኳን አስተክለው መድፉን ከነተኳሹ ከሚተኰስበት ቦታ አስጠምደው ለመድፉ ጠባቂ ዘበኛ አድርገው ከባንዲራው መካከል ሙኳንንቱን ወታደሩንና ባላገሩን እንደ ማዕርጉ በመልካም አቋቋም ባለቃ ባለቃው ከግቢው ፊት በር ጀምሮ እስከ ተክለ ሃይማኖት ድረስ በመንገዱ ግራና ቀኝ በጦር መሣሪያው አሰልፈው በመቶ ሠላሳ አንድ ሜትር በሰልፉ መካከል የወላሞን መለከት አምስት ፭ ከበሮውን አራት ፬ አድርገው ለማየትና ለዘፈን የመጣውን ሴትና ሕፃን ሁሉ በሰልፉ ጀርባ ፳ ሜትር በሚ ሆን ርኅቀት እንዳይቀላቀል አስከልክለው፣ፈረሰኛውን በ፪ በ፪ ክፍል በሰልፉ መካከል አሰልፈው ነጋሪቱ ተጭኖ መለከትና እምቢልታ ተይዞ ለነጋሪቱና ለካህናቱ መከብከቢያ የከተማና ጤና ጠባቂ ዘበኛ ከነጋሪቱ ጋር አስቀድመው የውጭ አገር ነጋዶች ፈረንጆችንና ዓረቦችን ጥቂት መኳንንት ጭምር ይዘው ካህናቱን ለመቀበል ከጧቱ ባንድ ሰዓት እቤተ ክርስቲ ያን ደረሱ ።

ካህናቱም ተሰናድተው ይጠብቁ ነበርና ነገሠ በጽድቅ ወለብሰ ድርዐ ጽድቅ ንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ ወተቀጸለ ጌራ መድኃኒት እያሉ ዝማሚያቸውን እያሳዩ ወርበው ሩብ ሰዓት ያህል ቈይተው ፈጸሙ ሴቶችም ግባ በፋኖስ ግባ በፋኖስ በኃይለ ሥላሴ በደጉ ንጉሥ ። ዓመፀኞች ሁሉ የማይ ታዘዙ ። በኃይለ ሥላሴ በጠቅል ይገዙ ። እንቅልፌን አጥቼ ስጨነቅ ሌሊት ። ሽልብ አደረገኝ አሁን በንጋት ። አባ ይላቅ ጠብቅ ይህን ያልጋ ብረት ። ጠቅልን ያኑረው ሰው እንዳይገባበት እያሉ ዘፈኑ ። መስቀል የያዙትንም ዲያቆናት ፳፫ቱን በስድስት በ፮ ተራ ። ቀሳውስቱንም እንደ- ዚሁ በ፮ በ፮ ረድፍ በሰልፉ መካከል ከነጋሪቱና ከመለከቱ ከምቢልታውና ከጥሩምባው ኋላ።ከሊቃውንቱ ፊቱ እንዲሔዱ ተነግሮ እንደዚሁ ሁነው ደጀሰላሙን ሲወጡ ነጋሪቱ እየተጐሰመ እምቢልታና መለከቱ እየተነፋ ሊቃውንቱም ለመንገድ የሚ- ሆናቸውን ለዘብ ኢተዘኪሮ አበሳዚአነ ኢኅደገነ ኃይለ ሥላሴ እያሉ መንገድ ሲጀምሩ ፊታውራሪ ንጋቱ በግምባርና በጀርባ ያለውን ሰልፈኛ ለመጐብኘት በመካከሉ ወዲያና ወዲህ እለ ዕረፍት እየተመላለሱ ሲያነቃቁ አስቀድሞ ተነግሮ ነበርና ፈረ ሰኛው የነጋሪት ድምጥ ሰምቶ እንደዚያው እንደተደራጀ ሁኖ ሳይለያይ ነጋሪቱንና መስቀሉን ለመቀበል በፍጥነት አመጣጥ ደርሶ ከነጋሪት ፊት ካለው ዘበኛ ቀጥሎ ወደፊት ተሰልፎ ነጋሪቱና ካህናቱን እየከበከበ ሲሔድ ነጋሪት ሲመታ መለከት ሲነፋ አዝማሪው መሰንቆውን ሲደረድር የወላሞው መለከትና ከበሮ ሲመታ ደስታው ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ከጨኸታቸው የተነሣ ምድር እስትትንበደበድ ድረስ ሁኖ ስንሔድ ነገሥ ቀ ፩ ፴፱ ፵ ። አንድ የውጭ አገር ሰው በማየት ምክንያት ሰውነቱ ዘንግቶ ኑሮ ምንም ዕንቅፋት ሳያገኘው ከፈረሱ ላይ ወደቀ። በሰልፉም መካከል ፊትና ኋላ ሁነው የሚሄዱ መጀመሪ ፈረሰኛ ። ፪ተኛ ዘበኛ፣፫ ነጋሪት እምቢልታናመለከት ጥሩምባ ፬ተኛዲያቆናት።፭ተኛ ቀሳውስት ፮ተኛ ደብተሮች።ከደብተሮች ቀጥሎ ፊታውራሪ ንጋቱ የውጭ አገር ሰዎችን መኳንንቱንና

ይዘው ወደፊት ሲሔዱ በስተኋላ የሚቀረው ሰልፈኛ ነጋሪቱ ካህናቱ ራቅ ሲሉ ተቅሎ እየተከተለ ካህናቱ በሰልፉ መካከል በሚያስደንቅ አገልግሎታቸው በክብሮና በጸናጽል መንግሥታችንን ሲያመሰግኑ ሠራዊቱም እስከፊት በር ድረስ በቦታ ጠበት በመላ ከተማው ሁሉ ሰው ብቻ ሆኖ እያሸበሸበ በልብሱ ጽዳት ምክንያት ስለሕዝቡ ብዛት ሲመለከቱት ፀሐይ መስሎ ሲታይ እንኳንስ ለማየት ለመስማት የሚያስጐመጅ ሁኖ መድፉ እተጠመደበት ፊት በር እድንኳኑ ስንደርስ ካህናቱ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሐ እያሉ ሸ፫ ደቂቃ ቆይቶው አመስግነው ሲጨርሱ በአራት ሰዓት ዕሥራ አንድ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ሠራዊቱም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሺህ ዓመት ይንገሥ እያለ ፫ ጊዜ ቢያጨበጭብ ከሰው ብዛት የተነሣ መድፍ ሲተኰስ ያልደነገጠ በጭብጨባው ምክንያት ፈረስና በቅሎው ሁሉ እየደነገጠ አሥራ አምስት ያህል ፈረሰኛ ወደቀ በመጡደቃቸውም ምክንያት ጉዳት አላገኛቸውም በሰልፉ መካከል የነበረውም ፈረሰኛ ስድስት መቶ ሺ፭ ነበር

ስለግብር አገባብ ። መጀመሪያ ያጥሩን በር ሲገቡ እንዳይጋፉ ካህናቱን ፈረሶችንና ዓረቦችን ። መኳንንትን አስገብተው ዳብሩ እተሰናዳበት አዳራሽ ገቡ ። ያዳራሹም ስፋት ቀጥታው ሰባ አንድ ወርዱ ሃምሳ ሁለት ነበር ከዳራሹ ውስጥ እመንበረ ዳዊቱ ላይ የተደረገውም በንዳሩ ዕድሜ ለንጉሣችን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚል ቃል በጉልህ ተጽፎበታል ። ሠራዊቱም በየማዕርጉ እስቲከለከሉ መኳንንቱና ካህናቱ ከተዘጋጀላት ማረፊያ ሆኖ ልክ በሰባት ሰዓት የውጭ አገር ሰዎችን አስቀድመው መኳንንቱንና ካህናቱን ወታደሩንና ባላገሩን እንደማዕርጉ አስቀመጡት ከዳራሹም ውስጥ የነበረው አውራጃ ከመሶብና ከጠረጴዛ በቀር በ፪ቱም ክፍል ያለው አርባ ስድስት ነው ከዚህም ከ፵፪ቱ አውራጃ በሙሉ ሰው ተቀምጦበታል ።ከዳራሹም የነበረ ጌጠኛ ነገር ሁሉ እጅግ ያማረና የተዋበ ስለሆነ የሚያየው ሰው ሁሉ እዚህ እንዲህ ያማረ አዲስ አበባ እንደምን ያለ ብርሃን ይታይ ይሆን እያለ ናፍቆ ይኸን የመሰለ ነገር ከዚህ ቀደም በሀገራችን ተሰርቶ አያውቅም የመንግሥታችንን ክብር ሄደን ለማየት ስንፈቅድ አገሩ ስለራቀ በስንፍናችን ቀረን አሁን ደግሞ ሄደን የምናየውን ሁሉ እዚሁ ሆነን እግዚአብሔር አሳይቶናልና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን የሰጠንን አምላክ ማመስገን ይገባናል እያሉ ከሰባት እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ሲበሉ ሲጠጡ ቆይተው ከመሀከላቸው አንድ ሰው ሰሞ ገዳይ ማክሰኞ ገዳይ ብሎ ሲፎክር ቢነሣ መጠጥ ጐድቶታልና ጉልበቱ ስብር ስብር እያለ መቆም ከልክሎት ቢቀመጥ ግራ ቀኝ ያለው ሁሉ አንድ ጊዜ ፉከራ ጀመረ። በዚህ ምክንያት ሥራ የሚበላሽ ቢሆን ፊታውራሪ ንጋቱ አባቶቹና ወንድሞቹ ሆይ ይኸን ያሰባችሁትን ሐሳብ ወደፊት ታደርጉታላችሁ ለዛሬ ግን ይቅርታችሁን አድርጉልኝ ብለው ለምነው ከፉከራቸው የሚታገሡላቸው ሆነ ግብሩም ከሰባት እስከ ፲፪ ሰዓት ደጓሞ ከሌሊቱ አራት ሰዓት ድረስ ተበልቶ ሽምፓኝ ሲጠጣ የውጭ አገር ሰዎችም መኳንንትና ካህናቱ ከመረቁ በኋላፊታውራሪንጋቱየተናገሩት ቃል ይህ ነው እኔ ፊታውራሪ ንጋቱ ምንም እንደክብራቸው መጠን የሚገባቸውን ምስጋና በብዙ ሐሳብ ብፈልግ የማይገኝልኝ ስለሆነ ባጭሩ በተወሰነች ሐሳቤ ምስጋናዬን ለመንግሥታችን ከዚህ ቀጥሎ በተጻፈው ቃል እናገራለሁ ። መጀመሪያ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ያለውን ፍጥረት ሁሉ ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከነገሥታት ሁሉ አገር የከበረች መሆኑዋን ስሟ አስቀድሞ በመጠራቱ ሁላችንም እናውቀዋለን ። ዘፍ ፪ ፲፫ ፪ተኛ ለእውቀታችንም ተከታይ ዳዊትን ካባቱ ከዕሤይ ቤት በሕፃንነት ለቅብዐ መንግሥት መርጦት ሳ ቀ ፲፮ ፲፪ ኢትዮጵያን መሠረት አድርጎ የዓለም ገዥ ሲሆን አፈቅረከ እግዚአ በኃይልየ ብሎ ቢያመሰግን ፈጣሪውም ረከብክዎ ለዳዊት ገብርየ ብኡሴ ምእመነ ዘከመ ልብየ ብሎ ሶስቱን ዓበይተ ሀብታት ሰጥቶት ነበረ ዓበይተ ሀብታት የተባሉም ነቢይነት መምህርነት ንጉሥነት ናቸው ።፫ተኛ ንጉሠ ነገሥት ዳዊት በሕይወቱ ሳለ ልጁን ሰሎሞንን አንግሦ ዛሬ ዓይኔ ሲያይ በዙፋኔ የሚቀመጥ ልጅ የሰጠኝ እግዚአብሔር ምስጋናው ለዘለዓለም ይሁን ብሎ በምንጻፉ ላይ ቢሰግድ ሕዝቡም ሁሉ የልጅህን የሰሎሞንን ስም ከስምህ ዙፋኑን ከዙፋንህ ያብልጠው ሺህ ዓመት ይንገሥ ቀ ነገ ምዕ ፴፱ ፵፯ ብለው ሕዝቡ ሁሉ አመስግነው እንደተቀበሉ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ስለሰጠን እንደዚሁ እግዚአብሔርን ማመስገን ይገባናል። ፬ተኛ ንጉሡ ሰሎሞንም ሥጋዊን ሐሳብ ሳያስብ በመንፈሳዊ ዕውቀቱ ይኸንን ሁሉ ሕዝብ ለመጠበቅ ሕፃን ነኝ ነገርግን ጌታዬ ሆይ ለሕዝብህ ዳኝነት የማይበት ሕሊና ስጠኝ ብሎ ቢለምን ነገ ቀም ፫ ፯ ፯ ፰ ፱ የዚህን ዓለም ክብር አልፈልግህምና ብልሀተኝነትንና አስተዋይነትን ክብርንና ባለጠግነትን ከነገሥታት ሁሉ አንተን የሚመስል እንዳይኖር ማንም ካንተ በፊት እንዳልነበረ ካንተም በኋላ የሚመሳሰልህ እንዳይነሣ አድርጌ ሰጠሁህ ቀ ነገ ምሮ ፲፩ ፲፪ ፲፫ ብሎ እንደሰጠው ቀድሞም ለክብር ዕድለኛ የሆነች ሀገራችን ብርሃኑዋን ለመግለጽ እርግጠኛ ምስክር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ያዘ ስለተገኘች ከጨለማ ወደብርሃን ወጥተን ነፃነትን አገኘተናል ። አሁንም ብርሃናችን እንዳይጠፋ ነፃነታችንም እንዳይበላሽ ለኢትዮጵያ ብርሃን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለዳዊትና ለሰሎሞን የሰጠውን ክብርና አእምሮ ሳያጐድል እንዲሰጥልን ሁላችንም እግዚአብሔር በሚያውቀው በንጹሕ ልቡና በትሑት ሕሊና መጸለይ ያስፈልገናል ብለው ደስ የሚያሰኝ ምርቃታቸውን ቢያቀርቡ አዳራሹ ውሥጥ ያለ ሰው ሁሉ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሺህ ዓመት ይንገሥ እያሉ ተጨበጨበ ከዚህ በኋላ ከሌሊቱ ባራት ሰዓት ግብር ተመለሰ።

ሠራዊቱም ደጃዝማች ይገዙ ከሌሉበት ይኸን ያህል ክብር የተሠራ ጌታችን ቢኖሩ እንደምን ያለ ዓይነተኛ ደስታ እናይ ነበር እያለ አመሰገነ። ከግብሩም በኋላ ወደየቤቱ ለመሰብሰብ ሲሄድ በመጠጥ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች ለመራመድ የማይችሉ ለመሄድ የትሸነፉ ሆነው በየመንገዱዳር ስለወደቁ አስቀድሞ በከተማው ውስጥ ጤና ጠባቂ ዘበኛ ተደርጎ ነበርና ክፉ ነገር እንዳያገኛቸው ባለክፍሉ ዘበኛ ሲጠብቅ አድሮ በማግስቱ ከወደቁበት እየተነሡ ያደሩበትን ቦታ አይተው እያ-

ፈሩ ወደየቤታቸው ሔደዋል፡፡ይህንንም ከዚህ በላይ የተጻፈውን ቃል ሕዝቡ በሚወደድ ምስጋና መንግሥታችንን እያመሰገነ ሲለተደሰተ የተደረገውን ሥራ ለክቡራን ብርሃንና ሰላም ሠራተኞች ለማስታወቅ ልቦናዬ አሳስቦኝ ጽፌያለሁና ምንም ቃሉ ባይዘጋጅልኝ ይህን የጻፍኩትን ማስታወቂያ መልክም ብላችሁ እንድትቀበሉኝ ትሑት ወንድማችሁ ልመናዬን አስቀድሜአለሁ፡፡

ወልደ ሐና ገብ ኪ

መልክም ግብር

ከጥንት ከባቶቻችን የቈየ አለቃ ለጭፍራው እንደሚያበላ ልምድ ስለሆነ ኅዳር ፯ ቀን የ ፖ ቴ ቴ ሚኒስቴር ክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደሩፌ ለ ፖ ቴ ቴ ቤት ሠራተኞች በዚሁ ቀን መልክም ግብር አድርገውላቸው ነበር በዚሁም ቀን ሠራተኞቹም ከጧት በሀገራችን ቍጥር ፩ሰዓት ሲሆን ከክቡር ፊታውራሪ ኃይሌ ወልደ ሩፌ ቤት ተሰብስበው በስድስት ሰዓት ግብሩ ተጀመረና ሰው በእጋፋሪ እየገባ በየማዕርጉ ተቀመጠ መብሉም በያይነት በያነይቱ እየቀረበሕዝቡ ሲበላናሲጠጣ ውሎ ከጠገበ በኋላ ሽምፓኝ ቀርቦእየተመረቀ ተጠጣ ከዚህም በኋላ ከብርሌው ውሥጥ ሲያዩት ውስኪ የመሰለ ጠጅ ቀረበ በዚህ ጊዜ ከፖስታ ቤት ሠራተኞች አንደኛው ምሕረተ አብ የሚባል ቄ ሞ ከዚህ በታች የሚከተለውን ዲስኩር ተናገረ

ክቡር ሚኒስቴራችንና በዚህም ያላችሁ መኳንንቶች ሆይ በኔም በባልደረቦቼም ስም ሁኜ ይህችን ቃል ለመናገር ከፊታችሁ ቁሜ እዳፈራለሁ ክፍ ያሉ መንግሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታላቅ አገልጋይ እምነት የመላባቸውን ለኛ አለቃ እን ዲሆኑን በተለየ ባልደረባ መስጠታቸው እኛም እርሳቸውንየመ ሰለ ባልደረባ በማግኘታችን እንዴት ያለ እንፋሎት የሆነ ደስታ እንደተሰጠን ከዚህ ወዲህ ብለን ለመናገር አንችለውምክቡር ሆይ ዛሬ እኛን ጭፍሮችዎን በዕለተ እሑድ ሰብስበው ይህን ሁሉ ለቍጥር የማንችላቸውን ጣፋጮች ምግቦች ለኛ ማቅረብዎ ጭፍራ ወዳጅ መሆንዎን ይመሰክርለዎታል ፡፡

ደግሞ አንድ ለኛም ለሰሚም የሚሆን የማይረሳ ነገር ማድረግዎ ከሽምፓኝበኋላ በምርቃት ጊዜ ምንም ሽምፓኝ ዋጋው ክፍ ያለ ቢሆን ጣዕሙ ከሀገሬ መጠጥ አይበልጥ ክብሩ ክሀገሩ ነውና እኔም የሀገሬን በቃልል እኔ ያላከበርኩት ማን ይቀበልልኛል ብለው በሚሰጥበት ጊዜ ለምርቃቱ የሀገራችንን ጠጅ ማቅረብዎ ሀገርዎን ጠባቂ መንግሥተዎን አክባሪየሀገርዎን ሥራ ወዳጅ መሆነዎ ሁላችን ስለተሰማን ይህቺን ቃል ለመናገር ተዳፈርኩኝ ምንም በተለየ ልኛ ለፖ ቴ ቴ ሚኒስቴር ክሆኑ ወዲህ ብዙዎች ሥራ ለመጀመርና ለማስፋት እንዲሁም ለማሻሻ ልና መልካም ደንብ ለማቋቋም መቸኮልዎን ማንም የሚስተው የለም ኢትዮጵያ ሀገራቸን እንደኮራች ከገናናው መንግሥታችን ክቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጋር ትኑርል በማለት ጽዋየን እጠጣለሁ ብሎ ከፈጸመ በኋላ ሰውን ደስ አሰኝቶት ተጨበጨበ ከዚህም በኋላ ብዙ ሰዎች ዲስኩር አደረጉ የሰማነውን ሁሉ ስማቸውንና ዲስኩሩን በዝርዝር ለመጻፍ ላንባቢ ያሰለቻል በማለትትተነዋል ቁጥሎም መጋረጃ ተገለጠና ምሉ ግብር ሁኖእየተበላ እየተጠጣ ዋለ ከፍትፍቱ ፊቱ እንደሚባለው ይልቁንም የሠለጠኑ አሳ- ላፊዎች በዝግታ እየቀረቡ ለየአንድ አንዱ ሰው ምን ዓይነት መጠጥ ትፈልጋለህ እያሉ ያስፈለገውን የኤሮፓም የሀገሩንም መጠጥ እንደ መረጠው በፍጥነት ሲያቀርቡ ደስ ያሰኙ ነበር ከዚህም በኋላ በሀገራችን ቁጥር ፲፪ሰዓት ሲሆን ሰው እያመሰገነና እየተሰናበተ ወደ ቤቱ ጕዞ ጀመረ የቀረበውን የመብልና የመጠጡን ዓይነት እያንዳንዱ በዝርዝር ቈጥረን ለመጻፍ ጊዜ ፈጂ ስለሆነብን ባጭሩ ይህንን እንድታዩት ጽፈንላችኋል እንጂ ብዙ የሚያደክመን ነበር ፡፡ ከዚያ የነበረ ጥሩነህ ካ

የክብረ በዓል ዕንቍጣጣሽ ፡፡

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ፡፡

ካሁን ፊት ከ፲፱፻፱ ዓ ም ጀምረን የተሾሙነው ምኞት ንጉሠ ነገሥት ተብለው ኢትዮጵያን ቢቃኙዋት ምነው እያልን መቸም ስለ ነፃነታችን ስንል ነውና በሐሳባችን ውሥጥ እንደ- ዚህ ያለውን ምኞት ስናሰናዳ ነበረ ያለው አይቀርም፡፡ መቸም ከናትዎ ማኅፀን ሲፈጠሩ ጥንቱንም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነውና የተፈጠሩ እኛ በማናውቀው እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው ከክፉ ሰዎች ምክር በምሕረት ጋሻ እየከለለ የነፃነት አባትና የኢትዮጵያ መሪ እንዲሆኑ ከጥንት እግ- ዚአብሔር እርስዎን መረጠ፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰጠውን ሰው ሊያስቀርበት አይቻለውምና ከእግዚአብሔር አምላክ የተቀበሉት ጸጋ ከዕለት ወደ ዕለት እርምጃ እየጨመረ ከሰዓት ወደ ሰዓት ደረጃውን ሲወጣ እነሆ በመጨረሻው የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መኰንን ተባሉ ፡፡ ይኸውም የኢትዮጵያ ዕድል ነውና ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና ይገባዋል ፡፡ ሁለተኛም የንጉሠ ነገሥት- ነትዎ ክብረ በዓል በ፲፱፻፳፫ ዓ ም በሁለተኛው ወር ከወሩም ፳፫ ቀን እንዲሆን እምቅድመ ዓለም እግዚአብሔር ወስኖ- ታልና ለሸ፫ኛዪቱ እሑድም ምስጋና ይገባታል፡በሕዝብና በአ- ሕዛብ መካከልም የተብረከች ትሁን ፡፡ ንጉሠ ነገሥትነትዎም ለዘለዓለም የፀና ይሁን ስል ከዓመት ወደ ዓመት እንኳን በደ- ኅና አሸጋገረን በማለት ለግርማዊነትዎም የማክበር ደስታዬን ስገልጽ ለተከበረ ሥልጣንዎ ዕንቍጣጣሼን አበረክታለሁ ፡፡

ተማኑ ረምሃ

ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የንጉሠ ነገሥት ዘውድ የጫኑበት ቀን በሙሉ ኢትዮጵያ መከበሩ አዲስ ነገር ሁኖብን ስናደንቅ ነበር ፡፡

አሁን ደግሞ ይኸው ዘውድ የጫኑበት ቀን በአሜሪካ ዩናይትድ እስቴት ዋና ከተማ በዋሽንግቶን ባለው ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ተከብሮ ስለ ዋለ በዚያው ቀን ስለ ጃንሆይ የተ- ጸለየው ጸሎት አዲስ አበባ ባሉት በአሜሪካ ሚኒስቴር በክ- ቡር በምሰተር ሳውታርድ በኩል ወደውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ወደ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ተልኮ ስለ መጣልኝ ለኢትጵያ ወዳጆች ደስ እንዲላቸው ብለን አትመነዋል ፡፡

ቃሉም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ፡፡

(ግልባጭ)

በዋሽንግቶን ካቴድራል ።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ በጫኑበት ቀን — የተጸለየላቸው ጸሎት እሑድ ጥቅምት ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፫ ።

ሁሉን የምትችል አባት የዓለም ሁሉ ጌታ የመንግሥታት ሁሉ አምላክ የአገልጋይህን የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥት ልብ አሁንና ለዘላለም በሁሉ ነገር ያንተን ክብርና የሕዝቡን ደኅንነት እንዲፈልግ ፤ ሕዝቡንም ከእምነት ወደ እምነት ከኃይል ወደኃይል እየመራቸው ምሕረተኛና ኃያል ለሆነ ለመድኃኒታችን በመታዘዝና በፍቅር እንዲያሰድራቸው እንድታደርግለትና ንጉሠ ነገሥቱንና ሕዝቡን በጽድቅህና በሰላምህ በደስታህም በረከት በምላት ለዘላለም እንድትባርከው በትሕትና እንለምንሀለን ። ይህንንም ሁሉ ለዘላለም ነግሦ በሚኖር ስለ ልጅህ ስለ ጌታችን ስለ የሱስ ክርስቶስ ፍቅር ብለን እንለምንሀለን ። አሜን ።

Copy .

WAShINGTON CATHEDRAL .

A Prayer for the Emperor of Ethiopia on the Day of his Coronation ·

Sunday, Nvember 2, A. D. 1950

Almighty Father, Lord of the world and God of the Nations ; we humbly beseech thee, on this the day of his coronation, so to dispose and govern now and ever, the heart of they servant the Emperor of Ethiapia, that in all things he may seek thy honour, and the good of his people, leading them on from faith to faith and Strength to strength, in the obedience and love of their Sovereign Lord, our Merciful and Mighty saviour, and abundantly bless the Emperor and his people with thy gifts of righteousness, and peace, and joy for all the years to come. We ask these things for the love of their Master and ours, thine own Eternal and reigning Son, Jesus Christ, Amen

የእርዳታ ምስጋና ማስታወቂያ

አስቀድሞ የሙሴ ሽፍኔ ቤት የነበረው ከዚያ በኋላ ኪሙሴ ጴቤልፎን ከነበታው የገዛነው በተከራዮቹ በሚነድና በሚበራ ነገር ምክንያት ስላልተጠነቀቁ ቤቱም ስለ ተቃጠለብን በጣም እናዝናለን ። ነገር ግን እኛም በኋላ ስለ ሰማን ቤቱ እጅግ ትልቅና የማር ክዳን ቤት ስለ መሆኑ አይድንልንም በማለት ሙሉ ተስፋ ቈርጠን ነበር ።

ዕድሜ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነሲቡ በድንገት ሰምተው አቶ እየለ ገብሬም ፣ግራዝማች አማረም፣በሻ ደምሴም፣በሻ ይመኑም የቀሩትም ሹማምቶች እንዳሉ ከነወታደሩ በፍጥነት ደርሰው ግማሹ ከቤቱ ውሥጥ የወጣውን ዕቃ ሲጠብቁ የቀሩት ወታደሮች ቤቱ በሞላ እንዳይቃጠል ግሩን ሲገፉ የቀሩት ውኃ እያመላለሱ የተቃጠለውን ሲረጩ ከሌሊቱ ፫ ሰዓት ተኩል እስኪሆን ድረስ ቈይተው እሳቱን አጥፍተው ለዕቃው ዘበኞች ሰጥተው ዕቃ ሳይጠፋ ስለ አሳደሩልን በጣም እናመሰግናለን ። ግን ትልቁ ውኃ የሚያመላልስ የእሳት ማጥፊያ መኪና በፍጥነት ባይመላለስ የሚተርፍ ነገር አልነበረም እንደዚህ ያለ የእሳት ማጥፊያ መኪና ባያሌው ቢኖር እጅግ መልካም ነበር ብዙ ፈረንጆችም ሳይበዝኑ ከልብ ስለ ረዱን በጣም እናመሰግናለን ይልቁንም ምንም ለነፍሳቸው ሳይፈሩ ከቤት ላይ ሁነው እሳቱን ሲያጠፉ የአመሹትን ሰዎች በጣም እናመሰግናለን ። ሙሴ መዳም ኤባሌ ከነልጆቻቸው ።

ሹም ሽር ።

አዛጋር ወርቅነህ የፊታውራሪ መዝለቂያ የነበረውን የጨርጨርን አበጋዝነት ተሾሙ። መንግሥታቸውን በቅን ስለ አገለገሉ በየጊዜው በማዕርግ ላይ ማዕርግ ስለ ተጨመረላቸው ለሌሎች መንግሥታቸውን በቅን ለሚያገለግሉ ሁሉ ተስፋ ይሆናል ።

ስለ ከንቲባ ተሰፋዬ ጐበዜ ዕረፍት።

ከንቲባ ተሰፋዬ እጅግ ሀብትና ደግነት የሚጠቅምም ዕውቀት ያላቸው ሰው ነበሩ።ገና በጐብዝናቸው ከጐንደር ወደ ሺዋ መጥተው በዓሰብና በአውሳ በኩል ወደ በሕር እየወረዱ በንግድ ምክንያት ታላቅሀብታም ሁነው ኋላም ለደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ አሽከር ሁነው እጅግ ታማኝና ባለሟል ሁነው ሲኖሩ ደጃዝማች ተሰማ ዳርጌ ከሞቱ በኋላ ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ በጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ከንቲባ ተብለው የአርሻ ሚኒስቴርነት የተሾሙ ጊዜ የሚኒስቴሩ እንደራሴ ሁነው ተሹመው ጐንደርን ሊአቀኑ ጀምረው ነበር።ወዲውያም ሹም ሽር ተደረገና ዓሥር ሺህ ዳውላ የሚሆን እህል ለንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ አስረከቡ ። ከሰገሌ ጦርነትም ወደ አዲስ አበባ መጥተው መንግሥት በላከቸው እየተላኩ መንግሥትን ደስ አሰኝተው ሲኖሩ ልዑል ራስ ካሣ በጌምድርን ሲሾሙ እሳቸውም በጐንደር ከንቲባ ተብለው ተሸልመው ተሹመው ሒደው ነበር። መቸም የሰው መጨረሻው ይህ ነውና ገና ልጆቻቸውንና ቤታቸውን አይተው ሳይጠግቡ በኅዳር ፲፩ ቀን ሙተው በክብር ተቀበሩ የሚል የመርዶ ቃል መጥቶ የልብ ወዳጃቸው አብሮ አደጋቸው ደጃዝማች ወልደ ጻድቅ ተረድተው እጅግ አዘኑ ፍቅራቸውንም የሚያውቅ ዘመድ ወዳጃቸው ደጃዝማች ወልደ ጻድቅን እየሄደ አስተዛዘናቸው የመንግሥት ረዳት የደኆች አባት በድንገት በመሞታቸው ለመንግሥትና ለአዋቂው ሕዝብ ሁሉ ታላቅ ኀዘን ነው ለሰው የተሰጠው የመጨረሻ ዕድሉ ይህ ነውና ሙቸስ ምን ይደረጋል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህንንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ በጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም አሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤት ክርስቲያን በታች ከጎህ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አሳድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምበሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮው ማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር

የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሽያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።

ODEON



ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቱ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።

አ ቦ ካ ት ።

የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሄስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።ብጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ስ ፈ ፈርናንዲ-ስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም እንዳንድ ጠርሙሱ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ብርሃንና፡ሰላም

LUMIERE ET PAIX

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፶ 6me ANNÉE № 50		ሐሙስ ታኅሣሥ ፪ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም። JEUDI 11 DECEMBRE 1930

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በአገራቸው ብርሃንና ሰላም እንዲሆን የሚፈልጉ ስለሆነ ይህንን ጋዜጣ ብርሃንና ሰላም ብለው ሰየሙት ።

Hayle Sellassé I Roi des Rois profondément désireux de voir régner dans son pays la lumière et la paix, a voulu que ce journal soit intitulé" Lumière et Paix"

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲረክተሩ አቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ፡ መጣጥት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

በሐረር ከተማ

ስለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት የዘውድ በዓል

በሐረር ከተማ የተደረገው ክብርና ደስታ በሸዋ በርሚዳ ላይ ክህናቱና ሠራዊቱ በየተራው እየተሰለፈ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፎቶግራፍ ያለበትን ድንኳን እየዞረ ክህኑ ሲያስረግጥ ወታደሩም በያለቃው እየተሰለፈ እፎተግራፉ ፊት ሲፎክር እጅግ ደስ አሰኘ።ሰልፉም ሲያልፍ መድፉ እየተተኰሰ፥ነጋሪቱ እየተጐሸመ ከሸላዩ ጋር ሲገናኝ የቃኘው አሽከሮች ፉከራውን ደቀደቁት። ይህም ከተደረገ በኋላ ክቡር አለቃ ደስታ ቀጥሎ የተጻፈውን ዲስኩር አንብበው ሲጨርሱ ከዳር እስከዳር ፫ጊዜ ተጨበጨበ ።

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሐረር መኳንንትና በኔም በራሴ ስም ሆኜ ይህችን ቲንሽ

ምስጋና እናገራለሁ። ኃያል እግዚአብሔር ፍጹመ ህላዌ ዘልማዱ ኀሩት አብርሃምን ከመስጴጦምያ ካገርህ ውጣ ከዘመዶችህም ከባትህም ቤት እኔ ወደማሳይህ ምድር ለታላቅ ሕዝብ አደርግሀለሁ እባርክህም አለሁ።ስምህንም አከብረዋለሁ።ለበረከትም ትሆናለህ ብሎ ወደ ከነዓን አመጣውና ከዚያም እጅግ ሀብታም ሁኖ ሲኖር ልጅ አልነበረውምና ያዝን ነበር። ከዚያ የተስፋ ልጅ ይስሐቅ ተወለደለት፡ይስሐቅ ያዕቆብንና ኤሳውን ወለደ፥ ይስሐቅም ኤሳውን ለመባረክ ሲል በናቱ በርብቃ ምክንያት ያችን የተመረጠች በረከት እግዚአብሔር በያዕቆብ እንድታድር አደረጋት።እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ ኤሳውን ጠላሁ፥ ያዕቆብን ወደድሁ ይላል። ኤሳውን የጠላበትን ያዕቆብን የወደደበትን ምሥጢር የሚያውቅ የለም።ቅዱስ አምላክ የፈቀደውን ይሠራል የወደደውን ይመርጣል እንጂ ። ያዕቆብም ፲፪ት ልጆች ወለደና በሚሞትበት ቀን ሲመርቃቸው ለ፬ተኛው ልጁ ለይሁዳ

ለኛ ነገሥታት አያት መልካም በረከት ደረሰው።ከነዚህም ከ፲፪ቱ ያንድ አባት ልጆች እግዚአብሔር ይሁዳን የመረጠበትን ወረታ የሚያውቀው የለም።እርሱ የፈቀደውን ይመርጣል።ያችንይስሐቅ ለያዕቆብ የሰጣትን በረከት ያዕቆብ ለይሁዳ አሳለፋት እንዲህ ሲል ይሁዳ ወንድሞችህ ሁሉ አንተን ያመሰግናሉ ። እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው። ያባትህ ልጆች ይሰግዱልሀል ። የአንበሳ ግልገል ይሁዳ። በትር ከይሁዳ አይጠፋም። የገዠም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል የሰላም ንጉሥ እስኪመጣ ድረስ ለርሱም የአሕዛብ መታዛዝ ይሆናል ። እግዚአብሔር ሳሙኤልን አለው።ወደቤተ ልሔም ወደ ዕሤይ ሒድ በልጆቹ መካከል ንጉሥ የሚሆን አይቻለሁና። ሳሙኤልም ሔደ፥ ዕሤይም መልካሞቹን ልጆቹን አቀረበ። ሳሙኤልም ወደ ኤልያብ ተመለከተ። እጅግ የተዋበ ነበረና እግዚአብሔር አለ ፊቱን አትይ የቁመቱንም ዘለልታ ንቄዋለሁና። ሰው እንደሚያይ እኔ የማይ አይደለሁም ሰው ፊትን ያያል፤ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል፤ አሁንም ከሁሉ የተዋበውን ኤልያብን ንቆ ዳዊትን የመረጠበትን የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚያውቅ የለም ። ያች ለይሁዳ የተሰጠች በረከት ስትተላለፍ እንደ ቃሉ ለዳዊት ደረሰች። ከዚያ ለሰሎሞን ፥ በቅዱሳት መጻሕፍትና በታሪክ ስሟ የታወቀው የሴት አርዐያ ታላቂቱ የኢትዮጵያ ነገሥታት አያት ንግሥተ ዓዜብ ከሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደች ። ያች ለይሁዳ የተሰጠች በረከት በቀዳማዊ ምኒልክ አድራ ወደ ኢትዮጵያ መጣችና።ከዚያ ስትወርድ ስትተላለፍ በይኩኖ አምላክ አድራ ሸዋመጣች ። መንግሥት በሸዋ ፪፻፸፯ ዓመት እንደቆየ በግራኝና በጋሎች ዕንቅፋትነት ካፄ ሚናስ ሞት በኋላ የሸዋ ነጋሥታት ጐንደር ሒደው ከተማ ቈረቈሩ። ያፄ ልብነ ድንግል ልጅ ያዕቆብ የያዕቆብ ልጆች መንዝ ቀሩና መሳፍንት ሆነው ሸዋን ይገዙ ጀመር።የያዕቆብ የልጅ ልጅ ነጋሢ ሸዋን በጋሎች ጠፍቶ የነበረውን ማቅናት ጀመረ። እንዲህ ሲል እስከ ሣህለ ሥላሴ ደረሰ።አሁንም ያች የይሁዳ በረከት ተከታትላ ወረደች እንጂ አልቀረችም’ና ለኢትዮጵያ የእውቀት በር ከፋች ለዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ሆነች። ከዚህ በኋላ ይህች በረከት በዚያም በዚያም በየሐረጉ ላይ ክንፏን ስትዘረጋ ከሀሊው አምላክ በፈቀደ ጊዜ እንደ ዮናስ በተአምራት ከባሕር ወጥተው ከግርማዊት እናታቸው ጋራ ለኢትዮጵያ አልጋ ወራሽነት በተመረጡ ጊዜ ያች ለይሁዳ የተሰጠች በረከት ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በምሉ ደረሰች። ይህን ፲፬ ዘመን ባልጋ ወራሽነት ሳሉ ምንም ለሥራዎ ዕንቅፋት ባይታጣ ጥበብዎ እንደማለዳ ብርሃን እየገፋ ለኢትዮጵያ ጥቅም ብዙ አዲስ ሥራ ሠሩላት። ከዚሁም ውስጥ በ፲፱፻፳ና በ፲፱፻፳፪ ዓ ም፥የተሠራው የእግዚአብሔር ኃይል ነው እንጂ በሰው እውቀት የተሠራ አይመስልም። ዕኛ በዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ከወገናቸው ጳጳስ ሲሾሙ እኛ የኢትዮጵያ ሰዎች ብቻ ከወንድሞቻችን ጳጳሳት እንዳንሾም በመከልከላችን አጥብቀን ስናዝን እንኖር ነበር ዛሬ ግን በጆሮቂው ንጉሣችን ጊዜ የእስክንድርያውን አቡነ ቄርሎስን ሊቀ ጳጳሳት አድርገው ከወንድሞቻችን ፭ን ጳጳሳት ስለ አሾሙልን የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ምስጋናዋን ታቀርባለች ዕድላሙ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስም በዓለም ታሪክ ተጽፎ እስከ ኅልፈት ድረስ ሲመሰገን ይኖራል ። ፪ኛ ታላቅ ጥቅም ያለበት ጀግናው የአየር ወታደር አይሮፕላን ካሁን ቀደም ለንግሥትና ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንደበረከት አድርጎ ሊሰጥ ሙሴ ባያር ቢያመጣ የኢትዮጵያ ምቀኞች እንደ መልካም ሽቱ በሚጣፍጥ ስማቸው ላይ ከንቱ ወሬ አስወርተው ሳይታይ ተመልሶ ሔደ ። ጥበብ ጫማው ፥ ትዕግሥት መጐናጸፊያው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሳይበሳጩ ከእምነት ሳያጓድሉ በትዕግሥት ቆይተው በጊዜው ቢያመጡት ስንት ጉዳይ አቀላጠፈ ወደፊትም ብዙ ጥቅም ይሠራል ለማለት አያስፈራንም ። በዚሁም ጃንሆይን ልናመሰግን ይገባናል ። ያች ለይሁዳ የተሰጠች በረከት ይሁዳ የአንበሳ ግልገል ያባትህ ልጆች ይሰግዱልሀል እጅህ በጠላቶችህ ደንደስ ላይ ነው።በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም።የገዠም ዘንግ ከእግሮቹ መሀል የተባለችው ስትያያዝ መጥታ እነሆ አሁን ደረሰች። ተደረገም ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዘእምውስተ ሥርወ ለዳዊት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በዓቂቱ ጊዜ ኢትዮጵያን በሥልጣኔ ጐዳና እንዲህ ያራመዷት ቸር አምላክ ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልን እንጂ ከሠለጠኑት ዓለማት ጋራ እንዲያስተካክሏት ጥርጥር የለውም።እንደዚህ እያሉ ትጉህ መሪና ጠባቂ የሰጠን አምላክ ምስጋና ይድረሰው።ወንድሞቼ ሆይ እኛም ዕድላሞች ነን።የዚችን ዕለት ክብር ለማየት ያብቃን እያሉ እንደ እሳት በሆነ ምኞት ሲናፍቁ በሞት የተለዩን ስንት ነበሩ ። ይሁን እንጂ ምንም በሥጋ ሙታን ቢሆኑ በነፍስ ሕያዋን ናቸውና ልዑል ራስ መኰንን ከነወገኖቻቸው በሰማይ ሆነው ከእኛ ጋራ ደስታችንን ይካፈሉ ይሆናል ። እንግዲህ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ደግነትና ትዕግሥት የሠሩትም መልካም ሥራ በኔ አንደበት ተነግሮ ተመስግኖ አያልቅምና በዕፁብ ወስኖ መተው ይሻላል።

ቸር አምላክ ረጅም ዕድሜና ጤና ሰፊ እውቀት ሁል ጊዜ ድል መንሳትና ታላቅ ግርማ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ለልዑል አልጋ ወራሻቸው ይስጥልን ። ኢትዮጵያ ዘለዓለም ለልጅ ልጃቸው ትሁን። አሁንም እረጅም ዕድሜና ጤና ከመወደድ ጋራ ለደጊቱ ባለ ዕድል ለግርማዊት እቴጌ መነን ይስጥልን ። ዘራቸው የተባረከ ይሁን፤ እኛንም ለመንግሥታችንና ለልጅ ልጆቻቸው በቅንነት እንድናገለግል ያድርገን ይህችም ወረታዋ የማይረሳ የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕለት ዘለዓለም የተባረከች ትሁን።ኢትዮጵያ በ፬ ሺ ፫፻ዓ መት በገዦዎቿ እጅ ጠብቆ እስከዚህ ድረስ ያቆየ አምላክ ይክበር ይመስገን።ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር።ኢትዮ ዘለዓለም ትኑር።ኢትዮ ዘለዓለም ትኑር።

ቀጥሎ በየጓምቡ ላይ ያለው እስላም እልልታውን በየበሩ አደረሰ።ክቡር አለቃ ደስታም የጃንሆይን ፎቶግራፍ እፊት አሲዘው ከኋላም ዋና ዋና መኳንንቶችን ከፎተግራፉ ፊት ክቡር አቶ እሸቴን አድርገው ከፈረስ መጋላ የቆመውን ሰልፍ እየዞሩ ለሰልፈኛው ምስጋና አቀረቡና ፎቶግራፉ በመንበረ ዳዊቱ ላይ ሲቀመጥ ግብር መግባት ተጀመረና ስለሠ-

ራዊቱ ብዛት ፯ጊዜ ግብር ገባ በዚሁ ሁሉ ክቡር አዛጋር ክብርት አሉ ሞልቷል እያሉ አጋፋሪዎችንና ሰውን ደስ ያሰኙ ነበር እንጂ የለም እያሉ ሰውን ቅር አላሰኙም። በማግሥቱም የካህናትና የሠራተኛ ግብር ሆነና ደግሞ በ፫ተኛው ቀን ሙሉ ግብር ሆኖ ሠራዊቱ በሙሉ ሲጋበዝ ዋለና ባ፲ሰዓት ለውጭ አገር መኳንንቶች የሻይ ግብዣ ተደረገና ብዙ ዲስኩር ተነ-ገረ። ባ፲፩ሰዓት ተኩል ለውጭ አገር ነጋዴዎች የሻይ ግብዣ ተደረገና ሽምፓኝ ሲጮህ ዲስኩሩ ሲወርድ እጅግ ደስ አሰኘ። ሐሙስ የሥራ ቤት ክፍል ግብር ተደረገና ዓርብ በሐረር ከተማ ውሥጥ ያሉ እስላሞች የሐጂዎች ግብር ሆኖ ሐጂ አሕመድ አበኝና ሐጂ ሙሚ በሽር በከፍተኛው ማዕርግ ተቀምጠው ነበር ። ክቡር አቶ እሼቴና ክቡር አዛጋር ክብረትም በወምበር ተቀምጠው ይጋብዙ ነበር ።

ቅዳሜ በ፫ሰዓት መኳንንቶችንና የጉምሩክን የጣምጃቤት ሠራተኞችን ሌላውንም በየሥራው ክፍል ያለውን ሠራተኛ ሁሉ ክቡር ብላታ ሀብተ ማርያም የሐረር አውራጃ የጕተራ ሁሉ ሹም በዋናው መሥሪያ አውዚን በሚባለው ቦታ ላይ ጠርተው ስለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘውድ በዓል ትልቅ ግብዣ አድርገው ነበርና በ፫ሰዓት የገባ እስከ ማታ ድረስ ፈንጠዝያ ሆኖ ሽምፓኝና ውስኪ እየተቀዳ መኳንንቱ በየተራ እየተነሣ ዲስኩር ሲደረግና በየጊዜው ሲጨበጨብ እጅግ ደስ ያሰኝ ነበር ።

ጃርሶ የሚባል ከሐረር ከተማ ቅርብ የሆነ ለጤና የተ-ስማማ ደጋ አገር አለና ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተ-ወለዱ በዚሁ ከተማ ነበር።በዚሁ ቦታ ላይ ክቡር ደጃዝማች እምሩ የኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ብዙ ካህን ተክለውበታል ።

ክቡር ደጃዝማች ገብረ ማርያምም በዘውዱ በዓል ቀን በዚሁ ጃንሆይ በተወለዱበት አልፍኝ ላይ ማኅሌት ተቆሞ ቅዳ-ሴም ተቀድሶ ላቅራቢያው ያለም ካህናትና ሠራዊት በዚሁ ቦታ ላይ ሰልፍ እንዲያደርግ የከንቦልሻውም አዛጋር በጋሻው ዘለሌ እዚያው ሔዶ እንዲደግስ አዘው ነበርና በዚሁ ቦታ ላይ እዚያው ያሉት የኪዳነ ምሕረት ካህናትና የከንቦልሻ ካህናት የደሌ ሚካኤሎች የኒኒ ጊዮርጊሶች ሌሎችም በጃ-ርሶ ወረዳ ያሉ ካህናት ተሰብስበው ትልቅ በዓል አድርገው አደሩ ወረቡንና ቅኔውን ወደፊት እንጽፋለን ። ከቅዳሴ ውጭ አበጋዙ ግራዝማች መዥሪያ ዋሩንባ እያስነፉ ሠራዊቱን አሰ-ልፈው በተራ ከቆመ በኋላ በጃንሆይ ዕድሜ ልክ ፴፱ጊዜ መድፍ ተተኰሰና ከዳር እስከዳር ተጨበጨበ ። የሰልፉ ሥራ ሲፈጸም ግብር ሆነና እጅግ ትልቅ ያማረ ግብር ተደረገ ። ከግብሩ በኋላ ሽምፓኝ ተከፈተና አለቃ ፍቅረ ዮሐንስ የሚባሉ የጃርሶ ሚካ-ኤል አለቃ ጃንሆይ ሲወለዱ ከዚሁ ቦታ ነበሩና የዚያንለቱን ጭንቅና የዛሬውን ደስታ እየጠቀሱ ዲስኩር ስላደረጉ እጅግ ደስ አሰኙ ።

ማመልከቻ

ሙሴ ኪወርክ የተባሉ የአርመን ሰው በሌሊት ዘበኛ ሰፈር አጠገብ ባለው ወንዝ ዳር ቤት ሠርተው ብዙ ዘመን በሠራተኛ ጕልበት ብቻ የባሕር ዓረብ ያሥሩ ነበር።
መኪና ስላልኖራቸው የቈዳው ቍጥር አነሥተኛ በመሆኑ ግማ-ቱና የመርዙ ሽታ ባጠገቡ ያሉ የመንደሩን ሰዎችና የሳቸውን ጤና ለመጕዳት እጅግም ኃይል አልተሰጠውም ነበር።አሁን ግን በዚሁ ሥራ ላይ ብዙ ዘመን ስለ ቆዩና ሀብታቸው ስለበዛ የቆዳ መኪናና ሞተር አስመጥተው ሥራቸውን ከቀድሞ የበለጠ ስላደረጉ የቈዳው ግማትና የቀለሙ መርዝ ሽታ ብዙ ጕዳት እንዲያመጣ ለራሳቸው ስለፈሩ ለሰውነቴ ልጠንቀቅ፣ ከጕዳት ልራቅ ብለው ክርፋቱና ግማቱ የማይደርስበት ቤት ተከራይ-ተው ራቅ ካላ ስፍራ ተቀምጠው ሥራቸውን በወኪል ያሠራሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሙሴ ኪወርክ የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ፈልገው የመንደሩ ሰው ጕዳት ሳያሳዝናቸው ሐሳባቸው ፈጽሞ የራሳቸውን ሕይወት ለመጠበቅና ትርፋቸውን ለመሰብሰብ ብቻ ነው እንጂ ለሰው የሚያስቡ ቢሆኑ ይህን ክፉ የሆነ የ ሽታ መርዝ ከወንዝ እየበጠበጡ ክብት እንዲያልቅ፣ ከመንደር መካከል እያሸተቱ ሰው እንዲጐዳ ባላደረጉም ነበር ።

ይልቁንም ይህንኑ የቈዳውን መንከርያ የሚጠጡ እንስሳትና በዚሁ ውሀ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ሰዎች ባለማወቅ ብዙ ጕ-ዳት እንደሚያገኛቸው ጥርጥር የለበትም ። ይህም የቈዳውና የመርዙ ሽታ ከዘበኛ ሰፈር ተርፎ ወደመድኃኔ ዓለምና ወደ-ጕለሌ በሚያስኬደው ትልቅ ጐዳና መንገድ የሚመላለሰውን መንገደኛ ሁሉ አያሳልፍም።

ሙሴ ኪወርክ ዘትጸልእ ለርእስከ ኢትግበር ዲበ ቢጽከ ያለውን የሐዋርያውን ቃል ሳይመለከቱ ለሰው ባለመራራት ለራሳቸው በመፍራት ሁነው ይህ የሚሠሩት ሥራ በዚህ መ-ንደር የሚኖሩትን ሰዎች ሁሉ ጤንነት የሚጐዳና የሚቃወም ስለሆነ ጌታችን በወንጌል ጤነኞች ባለመድኃኒትን አይሹም-ሕመምተኞች እንጂ ብሎ እንደተናገረ እኛም የከተማውን ጥዳት የሚጠነቀቅ፣ የሕዝቡን ጤንነት የሚጠብቅ ማዘጋጃ ቤት መን-ግሥት በሰጠው ሥልጣን እንደዚህ ያለውን የሕዝብን ጤንነት የሚቃወም፣ የሰውን ሕይወት የሚያደክም መጥፎ ሥራ ከሕ-ዝብ ጕዳት አስቀድሞ ከብዙ መንደር መካከል አስነሥቶ ሰው ከማይኖርበት ቦታ እንዲመራልን ስለጤንነታችን እናስታውሳለን

የሕዝብን ጤንነት አስቦ የሚያሳስብ። አንዳርጌ ዳምጤ

የዘውድ በዓል ዲስኩር ።

ጃንሆይ ።

ለዘውድ በዓል የተሰበሰብን እኛ የሐረርጌ ልጆች ደስ-ታችንን ለመግለጽ በግርማዊነትዎ ፊት ቆመናል። እኔም በወን-ድሞቼና በራሴ ስም ሁኜ ቀጥዬ የምናገረውን ቃል የሚአደፋ-ፍረኝ በክርስቲያንና በእስላም መሐከል ሁና የኢትዮጵያ ጠላት የነበረ ሬናቲክነትን አጥፍቶ ሕዝብና አሕዛብን ፩አድርጎ

የሚገዛን ንጉሥ ስለአገኘን የፋጡማና የወለቴ ልጆች በሀገራቸው ፍቅር ተቈራኝተው እጅ ለጅ ተያይዘው የሚሞቱላት ጊዜ በርግጥ ዛሬ መሆኑ ስለተረዳኝ ነው ። የመላው አፍሪቃ ምሥራቅ በምትሆን በኢትዮጵያ የወጣው እውነተኛው ፀሐየ ጽድቅ ኃይለ ሥላሴ የተወለደበትና ያደገበት ሐረር ምሥራቅነቱ በቦታ ብቻ ሳይሆን በግብርም እውነተኛ ምሥራቅ ሁኖ ስለ ተገኘች የኛ የሐረር ልጆች ደስታ ግን ከዓለም ሁሉ ደስታ የተለየና የበለጠ ሁኖ ይሰማናል።ይህም ለኛ ኵራታችንና ትምክህታችን ነው ።

ሁለተኛም ፤ ልዑል ራስ መኰንን የሐረርን አውራጃ ብዙ ዘመን ሲገዙ በብዙ ቸርነትና ርኅራኄ እንደነበረ ዓለም ሁሉ ያውቃል። ነገር ግን የኛም አባቶች ምንም ያባትዎን ውረታ ለመመለስ ባይቻላቸው ከአፍ ሳይሆን ከአንጀት ዘር ይውጣልዎ ብለው በእውነተኛ በረከት እንደመረቋቸው እነሆ ዛሬ በዓለም ጉባዔ መሐከል ተገለጠ ።

ይኸውም በግዛትዎና በተገዥነታችን መሐከል ላለው ፍቅር ምስክር ሆኖ ለልጅ ልጅ ሲነገር ይኖራል ።

ጃንሆይ ።

ይህም የመንግሥትዎ ክብርና ደስታ በኛ በኢትዮጵያ በሐረር አውራጃ ባለነው እስላሞች ብቻ ተወስኖ የሚቀር አለመሆኑን ግርማዊነትዎ እንዳያስለችብኝ ከመፍራቴ በተቀር ከብዙ በጥቂቱ ለመናገር ያገሬ ፍቅር ያስገድደኛል ።

ከአምላክ የተሰጠው ጸጋና ክብር ይብዛለትና መሪያችን ነቢ መሐመድ በዓረቢ አገር የእስላምነትን ሃይማኖት መዘርጋት በጀመረ ጊዜ ብዙ መምለክያን ጣዖት ጠላቶች ነበሩበት ዘመዶቹንና ወገኖቹን እየፈራ ቢያስቸግሩት ፲፪ ሰዎች ለኢትዮጵያ ንጉሥ አደራ ብሎ ላከለት ይባላል ። የኢትዮጵያም ንጉሥ ደኅና በታ ሰጥቶ እንዳይፈሩ አጽናንቶ አኖራቸው ኋላም ጠላቶቻቸው ሲፈልጓቸው ቢመጡ ተከላክሎ መለሳቸው ስለዚህ ነቢያችን ኢትዮጵያን መንግሥቷ እንዲጸናላት በዕድ እንዳይገዛት ጸልዩላት ሲል በዓለም ላሉ እስላሞች ሁሉ አደራ መስጠቱን ያለ ጥርጥር እናውቃለንና ስለዚህ ኢትዮጵያ እስከሁን በነፃነት መኖርዋ በኛም ጸሎት ጭምር ነው ለማለት እንደፍራለን።እነሆ ዛሬ የተወደደችና የከበረች ሀገራችን ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እውቀትና ተጋት እንደገና ስትወለድና ስትታደስ የመታወቋም ጮራ በዓለም ሁሉ ሲፈነጠቅ በዓለም ላይ ላሉት ለ፬፻፶ሚልዮን እስላሞች እንዲሰማቸውና የደስታቀም ተካፋይ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም ይኸውም የተወደደች ሀገርዎና ጃንሆይ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ አደራ መሆንዎን እኛም ለገናናው መንግሥትዎና ለጃንሆይ አደራ መሆናችንን እያረጋገጠ መታሰቢያችን ሁኖ እንዲኖር ያለጥርጥር እናምናለን ።

ኢትዮጵያ ዘለዓለም ትኑር

ንጉሡ ሕያው ይሁን ።

ሐጂ አብዱላ ሸሪፍና የሐረር እስላሞች ወንድሞች ።

ዲስኩር ።

በእስክንድርያ ትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች በታናሽቱ የትምህርት ቤት ክፍላቸው ለዘውድ በዓል በተሰበሰቡ ጊዜ አንዱ ልጅ የተናገረውን ዲስኩር እውቀቱ ወደ ኋላ እንዳይል አትመነዋልና ተመልከቱ ።

ኢትዮጵያ አገራችን በአበባ ተጐናጽፋለች ። ወሰውለምለም ርኅሩኅ እናታችን ፤ እልልታዋን ካጽናፍ እስከ አጽናፍ አሰማች ። አምላክዋ ጸሎት ልመናዋን ፈጽሞላታልና ። ዛሬ በዚች ቀን በዚች ሰዓት የኢትዮጵያ ሾግኖች ቆነጃጅት ጐበዛዝቶች የደስታ ቀሚስ የብርሃን ኩታ፥ አጣፍተው በእልልታ ፤ እያደመቁ በከበሮ በእንቢልታ፥ በመሰንቆና በበገና እየተመሩ ሲያንዣብቡ ይታያሉ ። እናንት ወጣት ጉልማሶች ወንድሞቼ ልባችን በደስታ ይሞላ ዛሬ የኢትዮጵያ ሙሽራ መሪያችን እረኛችን ንጉሥ ብርሃን ኃይለ ሥላሴ ተመርቆልናልና ሰላም በኢትዮጵያ ደመቀ ሃሌሉያ። የኃይለ ሥላሴን የመሪያችንን ሐሳብ አምላክ ያስጨርስልን ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር ።

ይልማ መንገሻ

ዲስኩር

የኢትዮጵያን መንግሥት ማፍቀሬን ለመመስከር ይህ የምስጋና ዲስኩር እንዲታተምልኝ በማክበር እለምናለሁ ።

የባለ ዝናው ወገን የግርማዊ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ቀን ዛሬ የክብራችንና የደስታችን ዕለት ናትና ይህች ዕለት ያሸናፊው ንጉሥ ነገሥታችን የዘውድ በዓል የደስታችን መጀመሪያ ለዘለዓለም መታሰቢያ ልትሆን የተገባት ነው ። የኢትዮጵያን መንግሥት በልማትና በሥልጣኔ ማንም እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመራት የለምና በዓለም ሁሉ የመታሰቢያ ቀን ልትሆን ነው ። ታላቁ ባለግርማ ንጉሥ ነገሥታችን ኢትዮጵያን በሥልጣኔ እንደሌሎቹ አገር ለማስመሰል በታላቅ እርምጃ ሲያሠለጥኑ ተቃዋሚያቸውን በኃይል ይመልሱት እንደ ነበረ። ወዳጃቸውንም በጥቅም ያስቀምጡት እንደነበረ ማንም አይስተውም።በተወላጅነታቸውና በተገባው ሥራቸው በዕድላቸውም ንጉሠ ነገሥት ሆነው ለሚገዙ ለዘውዳቸው በዓል ደስታችንን ለመግለጽ ሁላችን እጅ እንንሳ።እጅ መንሳትም ብቻ ሳይሆን በጥልቅ በልቡናችን እጅ እንንሳ። እኔም ለንጉሠ ነገሥታችን ዘውድ በዓል እጅ እየነሳሁ ደስታዬን ስገልጽ እረጅም ዕድሜ፥ብዙ ጤነኝነት መልካም ዕድል እግዚአብሔር ሰጥቶልን ተወላጃቸውም እንዲገዛ ያድርግልን ስል እመኛለሁ።

ታላቁ ንጉሠ ነገሥታችን ለዘላዓለም ይኑሩ፥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቤተ ዘመዶች ለዘላዓለም ይኑሩ፥ የከበረች የኢትዮጵያ መንግሥት ለዘለዓለም ትኑር።

መጀመሪያ የግሪክ በኢትዮጵያ ለቆመው የኦርቶዶክሳዊት ተማሪ ቤት መሥራችና ዲሬክተር ኤለፍቴሪያ ኮስማስ ።

ብለ ጃንሆይ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ንግሥ የዘውድ በዓል ።

የመዳብ ኤለዶተሪያ ከስማስ ተማሪዎች መዝሙር።

ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
ኀይለ ሥላሴ ልጅሽ ክብሩን አሳዬ ለዓለም የሚያስደንቅ ሥራ
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
ኀይለ ሥላሴ ፀዳሉ ታዬ ለዓለም ሲያበራ ፡
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
ልጆችሽ ደስለን ያበቀልሽልን ኀይለ ሥላሴ የሚባል አውራ።
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ
መድኃኒቶችን በዘውድ ተከቧል እንደ ጧት ፀሐይ እያበራ ።
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
እናታችን ኢትዮጵያ ያለም ዘውድ ሰብስባ ልጇዋን ስታክራ
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
ይመስገን ፈጣሪ ያሳየን ይህንን አዝመራ ።
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።
ዘላለም ኑሪ ከግርማሽ ኀይለ ሥላሴ ትልቁ ተራራ ።
ኢትዮጵያ የወይን ዘለላሽ አፈራ የወይን ዘለላሽ አፈራ ።

ሹም ሽር ።

ልጅ እማኙ ይመር ባላምባራስ ተብሎ ዋና የሥራ ዲሬክተር ሁኖ ተሾመ ።

የተሾመበትም ምክንያት መጀመሪያ ልጅነት ሳያገኘው ሁልጊዜ በቁም ነገር የበረታ በመሆኑ ቤቱንና ኑሮውን በማክወናወኑ ነው ኋላም የጃንሆይ የዘውድ በዓል በደረሰ ጊዜ ሥራ እንዲረዳ ቢታዘዝ የታዘዘውን ሥራ ሁሉ በፍጥነት አከወናውኖ በጥቂት ጊዜ ለቁም ነገር አደረሰው ። ስለ ዚህም ጃንሆይ ይህን ሥራውን አይተው መርጠው ሾሙት በዚህ ነገር እንኳን ደስ አለህ ሊል የተሰበሰበው ወዳጅ ዘመድ ሁሉ ጃንሆይን ሲአመሰግን አመሸ ደጅ ሳይጠና እገሌ ለዚህ ሥራ ይሆናል ተብሎ ተመርጦ ሲሾም እጅግ ደስ ያሰኛል ።

የእንግዶች መሔድ ።

አስቀድመን እንደአመለከትነው የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ ልጅ ዱክ አፍ ግሎስተር የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴን የዘውድ በዓል ለማክበርና እኛን ደስ ለማሰኘት መጥተው የዘውዱ በዓል ቀን ከተፈጸመ በኋላ የዱር እንስሶች ለማደን ወደ አሩሲ ሒደው ነበርና የሚፈልጓቸውን እንስሶች አድነው በየአገሩ ያሉ ሹማምቶች ሁሉ ደስ አሰኝተው ተቀብለዋቸው እጅግ ደስ ብሏቸው ነበር።በኅዳር ፳፫ ቀን የተለየ ባቡር በተሐራ ድረስ ወርዶላቸው ከዚያ ተሳፍረው በ፮ሰዓት አዋሽ ደርሰው ዋናው የኩባንያው ዲሬክቴር ምሳ ጋብዘዋቸው ነበር።እሳቸውም ደግነትና ትሕትና ያላቸው ናቸውና በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ እንዲረዱዋቸው ከጃንሆይ ታዝዘው የሔዱትን በጅሮንድ ተሰማ ባንቴንና አስተርጓሚ እንዲሆን ከጃንሆይ ታዝዞ የሔደውን አቶ ዳባ ብሩን ዱክ (ልዑል) አፍ ግሎስተር ከተቀመጡበት ቦታ አቅርበው ጋበዝዋቸው ብንጋውም ተሳፍረው ወደ ሀገራቸው ሔዱ። በጅሮንድ ተሰማ ባንቴና አቶ ዳባም የቀሩትም ወታደሮች በባቡር ተሳፍረው ወደ አዲስ አበባ ገቡ፡፡ የእንግሊዝ ሌጋስዮን አንድ አሽከር አብሮአቸው የሔደው መንገድ ተሳስቶት ጠፍቶ በጅሮንድ ተሰማ እጅግ አዝነው በያገሩ ሁሉ ልከው ሲአስፈልጉ ሰንብተው በደህና ተገኘ፡የምስራች የሚል ቴሌግራም አልፎላቸው እጅግ ደስ አላቸው በዚያ በሚያስፈራው በአዳል በረሀ ከዚያ ሁሉ አውሬ ድኖ በደህና መገኘቱ እጅግ ደስ ያሰኛል ።

እሚአሳዝን ወሬ ።

ሐኪሞች እንደፈሩት በከተማችን አልፎ አልፎ (ግሪፕ) የጉንፋን በሽታ ገብቷል።በዚህ ሰሞን ደጋግ ሰዎች ሞቱ።በኅዳር ፲፰ቀን ወይዘሮ አየለች የቀኛዝማች ደፍሩ ባንት ይዳኝ ባለቤት ሞቱ። በኅዳር ፲፱ቀን የትልቁ መሐመድ ዓሊ ታላቅ ወንድም ለዘውዱ በዓል ጊዜ እንደመጡ እዚሁ ሰንብተው ነበርና በድንገት ታመው እዚሁ ሞቱ ። ደግሞ የእስጢፋኖስ ርእሰ ደብር አባ ዓሥራት እጅግ የተዋበ የተማሩ ንጹሕ መነኵሴ ነበሩ ። አገራቸውም ሼዋ ነበር በኅዳር ፴ቀን ሞቱ። ደግሞ ባልንጀራቸው አለቃ ገብረ ጻድቅ የሚባሉ ደሴ የሚኖሩ የተማሩ የሸዋ ሰው ነበሩ ። በዚሁ ቀን ሞቱና ሕዝቡ ሁሉ አዘነላቸው።በአንድ ጊዜ እነዚህን የመሰሰሉ ሊቃውንት በመሞታቸው ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ጉዳት ነው ።

ብፁዕ አባታችን የደብረ ቢዘኑ መምሕር ዓምደ ማርያም በታኅሣሥ ፩ቀን ዓረፉ።ታሪካቸውን በሚመጣው እናትማለን ።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ

በሐራጅ የሚሸጥ ብዙ የቤት ውሥጥ ዕቃ ።

ወደ ለጋር በሚወስደው መንገድ ወትሮ እሙሴ ሽፍኔርስት ግቢ የሙሴ ዶቤለፎን ከነበረው ቤት ውሥጥ ታኅሣሥ ፰ቀን (፲፩ ዴሳን ብር ፲፱፻፴ በፈረንጅ) እሑድ በራት ሰዓት ተኩል (፲ ሰዓት ተኩል በፈረንጅ) ሙሴ ሽንዋቀዋሎ የተጻፉትን የቤት ዕቃዎች ሁሉ በሐራጅ ይሸጣሉ ።

፩ኛ የመኝታ ቤት ዕቃዎች።

ወርዱ ፩ሜትር ታርባ ሳንቲሜትር የሚሆን ፩አልጋ እንደ ሞላ ። ፩ባለ መስተዋት ቁምሳጥን ባለ ሶስት ግጣም ። ፩ራስጌ የሚሆን የሌት ጠረጴዛ በለውዝ እንጨት የተሠራ ላዩ ባለ ዕብነ በረድ ። ዳግም ሌላ ፫አልጋዎች ተነላስቲካቸውና ተነፍራሽቻቸው ።፫ቁም ሳጥን ባለ ሙሉ ግጣም ። ፩ራስጌ የሚሆን የሌት ጠረጴዛ ። መስተዋት ወምበሮች ። የቀረውም ብዙ ነው ።

፪ኛ የመመገቢያ ቤት ዕቃዎች ።

፩አራት ማዕዘን ጠረጴዛ፤፩ድርብ የምግብና የዕቃ ማኖሪያ። ፩የፍራ ፍሬ ማኖሪያ ። መቀመጫው በቁርበት የተሠራ ፲፩በ- ፩የይነቱ ወምበር ። ፩ረዛሚ ጠረጴዛ ። ፩ተሰቃይ የቤት ሰዓት ። ብዙ የገበታ መሣሪያ ። የሻይና የቡና ማቅረቢያ ሙሉ መሣሪያዎች ። ብርጭቆዎች ። የቀረውም ብዙ ነው ።

፫ኛ የልፍኝ(የሳሎን) ዕቃዎች

፩ ምንም እንከን የሌለበት ደህና ፒአኖ ማርከው ክሌን። ፩ የልፍኝ መማሸ በአዜ እንጨት የተሠራ። ፬ ባለ ድጋፍ ወንበር(ፎተይ)፩ ድንክ አልጋ ዓይነት።(ከናፔ)።፩ጠረጴዛ። ፩ እማዕዘን ጥግ የሚሆን ማረፊያ (ዴባን) ተነቢብሊአቴኩና ተነመጋረጃው ። ፪ ዴባን ተነፍራሻቸው። ፪ የሚታጠፉ የመጫወቻ ጠረጴዛ ። ፪በጨርቅ ሥራ ያማሩ ባለ ድጋፍ ወንበሮች፡፫ ሰሌት የሚባሉ ያበባ ጽዋ ማስቀመጫ። ፫መስተዋት ብዙ ክብ ጠረጴዛዎች። ፩ ፎኖግራፍ(ሙዚካ) የኮሎ ምቢያማርክ የቀረውም ብዙ ነው ።

፬ኛ የቢሮ ዕቃዎች ።

፩ ባለ ዘጠኝ ጓዳ የጽሕፈት ጠረጴዛ ፩ ሙሉ የስልክ መሣሪያ ። ፪ ቢብሊአቴክ ዓይነት ሮብራብ ። ኤታዤር ። ፫ ባለ ድጋፍ የሸምበቆ ወንበር ። ፩ የመዳብ ቀለም መድ ፩ የወረቀት መጣያ እንቅብ። የቀረ-ውም ብዙ ነው ።

፭ኛ የጥዳት ጓዳ ዕቃዎች።

፩ በእንጨት ተሠርቶ ነጭ ላክ የተቀባ የፊት መታጠቢያ። ፩ ባላይነት መስተዋት። ፩ የብረት ወንበር። መስቀያዎች። ልብስ መስቀያ የቀረ-ውም ብዙ ነው ።

፮ኛ ምንጣፍና ግርጃድ ድማቂ።

፲ የምሥራቅ ስጋጃ ። ፩ጥቅል የተገዳ የምሥራቅ ስጋጃ።፩የጠረጴዛ ልብስ። የበር መጋረጃዎች።፲፪ ድርብ መጋረጃ የዲባን ልብስ። ብዙ መከዳዎች ። የቀረውም ብዙ ነው

፯ኛ መብራቶች ።

፩ተሰቃይ መብራት በላምባ የሚነድ። ፮ በበንዚን የሚነዱ መብራቶች። ግርግዳ ተለጣፊ መብራቶች ። በንፋስ ኃይል የሚነዱ መብራቶች ። በጋዝ የሚነድ መጣጃ ምድጃ የቀረውም ብዙ ነው።

፰ኛ ኮርቻዎች ።

፫ አዲስ ዓይነት የእንግሊዝ ኮርቻዎች ተመላ ልጓማቸው ጋር።፪አሮጌ ኮርቻ ተነልጓሙ ። ዳግም ፩ የበቅሎ ልጓም ።

፱ኛ የወጥቤት መሣሪያና ዕቃ በየይነቱ ።

ጨረታ በ፬ሰዓት ተኩል(፲ሰዓት ተኩል በፈረንጅ)ዕቃ መሸጥ ይጀመራል ። ዳግም ወደ ማታ ከ፱ሰዓት ጀምሮ የሚተርፈው ዕቃ ሲሸጥ ያመሽል ።

የሚሸጡት ዕቃዎች ሁሉ ከዚያው ከመሸጫቸው ስፍራ ቦታኅሣሥ ፫ትና ዓራት ቀን ዓርብና ቅዳሜ ለትተምሷ በኋላ ተር-ታውን ተደርድረው ይታያሉ።

የዕቃዎቹ አሻሻጥ፣ እጅ በጅ ነው ። ደግሞም በታረጀው ዋጋ ላይ ስለ ሸያጮች ከመቶ አምስት ጨምሮ ዕቃ ገዥው መክፈል አለበት ።

ለማናቸውም ነገር ከሙሴ ሽንዋ ጋር መነጋገር ነው ። ዘወትር ከ፫ ሰዓት ተኩል እስከስራ አንድ ሰዓት ድረስ እቤታቸው ይገኛሉ።

ጉለሌ ባሜሪካን ሚሲዮን ግቢ ምስተር ረሰል ከዚህ ስማቸው የተጠራውን ዕቃ ይሸጣሉና ለመግዛት ፈቃድ ያላቸው መጥተው እንዲነጋገሩ እናስታውቃለን ።

፩ማለፊያ ያሜሪካን ፒያኖ። ፮ የጠረጴዛ ወንበሮች። ፩ ቢፌ ወይም የሳጎን ቁም ሳጥን ባለ ኪሶች። ፪ ባለ መከዳ ወንበሮች። ፩ የስፌት መኪና ። ፩ የጽሕፈት መኪና።

ዊ ስ ኪ ።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግም ባለትልቁ ምልክት ኤኮስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያ ለሙሴ ኤ እ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሰን ማክዳም የሚባል በኢዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ በጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የፌብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በታች ከኀሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈትው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቁረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሰል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቆሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።

ODEON

ዓለም ሱቅ ፲፯ ዓይ-ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንጀር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ ላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

ODEON

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ በ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ደወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ሔልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።



Borsalino



አዲስ ዓይነቱ ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ እስ

QUALITÀ SUPERIORE
BORSALINO
ALESSANDRIA
(ITALIA)
MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፊ ፈርና ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.&A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኵኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልሱ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሱ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፶፩
6me ANNÉE № 51

ሐሙስ ታኅሣሥ ፱ ቀን ፲፱፻፳፫ ዓም።
JEUDI 18 DECEMBRE 1930

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአቶ ማኅተመ ወርቅ እሸቴ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውሥጥ ባመት ፭ ብር ።
በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ።
በየሳምንቱ መግዛት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

ታላቅ በዓል ስለ ዳግማዊ ምኒልክ ዕረፍት መታሰቢያ ።

በታኅሣሥ ፫ ቀን የጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ የ፲፯ኛ ዓመት መታሰቢያ ነበር። በዚሁ ቀን ለጃንሆይ ዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ በተሠራው ቤተ ክርስቲያን ክህናቱ ማኅሌት አድርገው ዋሉ። ጃንሆይና እቴጌ ብፁዓን ጳጳሳትና መኳንንት ተሰብስበው ታላቅ በዓል ተደርጎ ነበር ። ከፁደቱም በኋላ ፯ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ። ቅዳሜና እሑድም ታላቅ ግብር ተደርጎ ነበር ።

የእንግዳ መቀበል ።

የጀርመን መንግሥት ሚኒስቴር ሙሴ ሆስን ፈልደር ከዚህ አስቀድመን እንዳስታወቅነው ወደ አዲስ አበባ ገብተው ከጃንሆይ ሳይገናኙ ሰንብተው ነበርና በተቀጠረው በታኅሣሥ ፯ ቀን በ፫ ሰዓት ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በክብር ተገናኙ። ስለ ሚኒስቴሩ ክብርም ፲፩ ጊዜ መድፍ ተተኰሰ ።

የአቶ ሞቢል አደጋ ።

የጦር ሚኒስቴር ፊታውራሪ ሙሉ ጌታ በታኅሣሥ ፬ ቀን በአቶ ሞቢል ሁነው በአራዳ መካከል ባለው በዋናው መንገድ ሲሔዱ ኃይለ ማርያም የሚባለው አቶሞቢል ነጂአቸው ከመ ጠንቀቅ ቀርቶት አቶሞቢሉን ከግንብና ለኤሌትክትሪክ ማብሪ በተሠራው ሲሚንቶ መካከል አጣብቶ አጋጭቶት አቶሞቢሉ ተጐዳ። ፊታውራሪን ግን መስተዋት ተሠብሮ ጥቂት እጃቸውን አደማቸው እንጂ ምንም ጕዳት አላገኛቸውም ። ምክንያቱም ከልባቸው ድፍረት የተነሣ ባይደነግጡ ነው እንጂ ፈርተው ቢሆን ሰውነታቸው ሲላላ ወደ ላይ አዘልሎ ራሳቸውን አቶሞቢሉ ይመታቸውና ይጐዱ ነበር ። ከዚህ ቀድሞ ከአደረጉት ድፍረት (ጉብዝና) አያንስም ። ነገር ግን ለኃያላን ኃይልን ለጠቢባን ጥበብን የሰጣቸውን እግዚአብሔርን ከክፉ አደጋ ስለ አዳናቸው እጅግ ልናመሰግነው ይገባናል ።

ደፋር ሌባ ።

በታኅሣሥ ፯ ቀን ከጃንሆይ ጓዳ መግቢያው ሳይታወቅ ወደ ገንዘብ ማስቀመጫው ምድር ቤት ገብቶ አንድ ሣጥን መሐለቅ ተሸክሞ የወረደበትን ፎቅ ብናየው ያስደንቃል ። የመታሰቢያ ቤት ሲሠራ ለደንጊያ ማመላለሻ ተዘርግቶ የነበረው እንደ መሰላል ያለው ብረት ሥራው ከአለቀ በኋላ ከንዳው ሁሉ ተጋድሞ ነበርና ያነን ወደ ላይ ዘርግቶ ከግቢው ታላቅ ገመድ አሥሮ የወረደበት ተገኘ ። ዘበኞች አልነበሩም ይሆን ? ብለን ብንጠይቅ ዘበኞች ነበሩ አሉን ። የዚህን ነገር ጊዜ ይፍታው ብለን ተመለስን ።

ስለ ወይዘሮ ጥበብና ስለ ባሻ ልማድ ።

ወይዘሮ ጥበብ የምትባል እመቤት ትጋት የሚባል ዛፏ ዕውቀት የሚባል ፍሬ የሚያፈራ ፍሬውም የማያቋርጥ ክረምትና በጋ የማያደርቀው ወደ፲፫ የሚሔዱትን ሁሉ ከአደባባይ እጅዋን ዘርግታ እየተቀበለች የምትመግብበት ነበራት ።

ደግሞ ባሻ ልማድ የሚባል ከሚስቱ ከስንፍናና ከልጁ ከድንነት ጋራ ድንቊርና ከሚባል ዱር ውሥጥ ችግር በሚባል ቤት ሲኖሩ ከዕለታት አንድ ቀን ባሻ ልማድ ይሉኝታ የሚባል አሽከሩን አስከትሎ አገር ለማየት ወዲያና ወዲህ ሲል ተስፋ የሚባል መነጽሩን አውጥቶ አሻግሮ ቢመለከት ከተማ አየና ያንኑ ከተማ ለማየት ቢሔድ ድንገት በወይዘሮ ጥበብ ደጃፍ ሲያልፍ ወይዘሮ ጥበብ ዕውቀት ከሚባል አንድ ፍሬ እጕዳናው ላይ ብትጥልለት ያን ፍሬ አይቶ ደነገጠና እንዳያነሣው ፈራው። እንዳይተወው ያምራልና ጐመጀለት ። ትንሽ ቆም ብሎ የፍሬውን ማማር እያየ እየተደነቀ ልተወው ልውሰደው እያለ ሲያመዛዝን ቆይቶ ወደፍሬው ቀርቦ ሲፈራሲቸር አንሥቶ ቢያሸተው የሽታው መዓዛ ሰውነቱን እናወጸው ሽታው ሰውነቴን ያናወጸኝ ብቀምሰው እንዴት ያደርገኝ ይሆን? ብሎ ቢቀምሰው ለባሕርዩ የሚስማማ ስለሆነው ድገሙኝ ለማለት ፈርቶ ትኩር እያለ ወይዘሮ ጥበብን ቢመለከታት

ሐሳቡን አውቃ ከዕውቀት ፍሬ እየደጋገመች እየጣለችለት ይመገብ ጀመር፣ ከምግቡ ጣዕም የተነሣ ወደ ቤቱ ሳይመለስ እዚያው ሰንብቶ ከወይዘሮ ጥበብ ጋራ ወዳጅነት ጀመረ፣ ከቤቱ ከወጣ ውሎ አድሮ ነበርና ተመልሶ ወደቤቱ ሲሔድ ደሉኝታ የሚባል አሽከሩ ወይዘሮ ጥበብን ውበቷንና ደግነቷን የቤቷን ጥዳት አይቶ ጌታዬ ቢተፉ ነገር ቢሔድ አገር ይገኛል የሚባለው በኛ ደረሰ። እንግዲህ ከወይዘሮ ጥበብ ጋራ ወዳጅነት ከጀመሩ ይህች ስንፍና የምትባል ሚስትዎ ለዛሬ ዘመን ኑሮ አትስማማዎምና ይፍቷት። እሷን በዛሬ ዘመን ሚስት አድርጎ መቀመጥ በልቅሶ ቤት እንደ መዝፈን፣ ወይም በሠርግ ቤት እንደማልቀስ ያለ ነው እያለ እያጨዋወተው እቤታቸው ደረሱ። ከዚህ በኋላ ባሻ ልማድ እንዴት ሰነበታችሁ ብሎ እቤቱ ሲገባ ሚስቱ ስንፍና ምነው ጌታዬ በደኅና እስከሁን ሰነበቱ እስከሁን ቢዘገዩ እመንገድ አንድ ድንገተኛ ነገር አገኝዎ ብዬ ደንግጬ ነበር እያለች ስትናገር ወዲያው ልጁ ድኅነት ሲሮጥ መጥቶ እግርና እጁ ላይ ተጠምጥሞ ምነው አባባ እስከሁን ሰነበተህ እያለ ሲስመው ልጁን እጭኑ ላይ አድርጎ የሰነበተበትን ነገር ለሚስቱ ያጫውታት ጀመረ። አንዲት ወይዘሮ ጥበብ የምትባል እመቤት ድንገት በጐዳና ሳልፍ አግኝታ ወስዳ የቤቷን ጥዳት ፥ የመልኳን ውበት የርስዋን ደግነት ስታሳይ አሰነበተችኝ እያለ የሰነበተበትን ምክንያት ከሥር እስከ ጫፉ ቢያጫውታት ንዴት አድሮባት እንደ ወትሮው አላሳስቅና አላጫውት አለችው። እሱም የወይዘሮ ጥበብ፣ ወዳጅነት ከመልመዱ የተነሣ በልቡ አድሮበት ነበረና ወደ ወይዘሮ ጥበብ ቤት እየተመላለሰ እቤቱ የሚገባበት ከዓሥር አንድ ቀን ሆነ። ሚስቱም ስንፍና በዚህ ነገር እጅግ ተናደደችና ለአሮጊት እክስቷ ለመት ቅንአትና ለእክስቷ ባል ላቶ ምቀኝነት ሒዳ እንዲህ አለቻቸው ባሌ ባሻ ልማድ ወይዘሮ ጥበብ የምትባል ከኛ ዘር ጋራ በአለ ደም የሆነች አዲስ ወዳጅ አብጅቶ እኔን እንኳን ሊአነጋግረኝና ዘወር ብሎ ማየቱን ሊተወኝ ምንም ያህል አልቀረው ። እቤቱም ብቅ የሚለው ከሥር አንድ ቀን ይሆናል። ለዚህ ምን ይሻለኛል ብላ ብታማክራቸው ምቀኝነትና ቅንአት ባልና ሚስቱ እንዲህ በዪው አሏት። ያባልሽ ባሻ ልማድ እዚያው እለመደበት ሰንብቶ ሲመጣ ካንተ ከተለየሁ ወዲህ በጠና ታምሜ ስለ ሕመሜ ጥናት ዶብተራ አላምነህ የሚባለውን ወዳጃችንን አስጠርቼ ብጠይቀው መጣፉን አውጥቶ አየና ባልሽ ሁለተኛ ወደ ወይዘሮ ጥበብ ቤት የሔደ እንደ ሆነ ዕድሜሽ እንዲጠረ ዕወቂው አሁንም ያመመሽ በሱው አለማረፍ እዚያው እወይዘሮ ጥበብ ቤት ሲመላለስ ያመጣው ዕውቀት የሚባል የልብ በሽታ ነው ብሎ ነገረኝ ። አንተም እንደምታውቀው ዶብተራ አላምነህ የተናገረው እምድር ጠብ አይልምና የኔን ሞት ካልወደድኸው በተቀር ሁለተኛ አትሒድ ብለሽ አስፈራሪው እንጂ እርስዋን እየተመላለሰ ለምዶ የፈታሽ እንደሆነ ከሱ በቀር አንችን በዛሬ ዘመን የሚአገባሽ የለምና ተንቀዋለሽ እንደቀረሽ ዕወቂው ብለው መከረው ሰደዷት። እሷም እንደተመከረችው ባሏ ቢመጣ ታማ ተኝታ አገኛት። ምን ሆንሽ ብሎ ደንግጦ ቢጠይቃት እርስዋም ዘመዶቿ የመከርዋትን እየቃተተች ነገረችውና በመጨረሻው እዚሁ በራስጌዬ በግርጌዬ እያልህ አስታመኝ እንጂ እንግዲህ ሁለተኛ ታጠገቤ ትሔድና መሞቴን ዕወቀው አለችው ። እሱም ለጊዜው እሺ ብሎ ተቀምጦ ሲያስታምማት በመካከሉ ወይዘሮ ጥበብ ትዝ አለችውና ቁና ቁና ይተነፍስ ጀመር። እርስዋም የልቡን ዐውቃ ምነው ምንሁነሀል እኔኮ ጥቂት ሻል ብሎኛል አለችው። እሱም እኅቴ ሆይ ክፉም ልማድ ነው ደጋም ልማድ ነው ቢላት ምን ሆነ ምን ሆነ እኔ የምናገረው ሌላ እሱ የሚመልሰው ሌላ እኔ የታመምሁት እያለሁ እሱ በቁሙ ይቃጋር ጀመር ብላ ጥቂት ቈይታ ምንሁነሀል ብትለው እሱም እንደፊተኛው ክፉም ልማድ ነው፣ደግም ልማድ ነው አላት፥ ከዚህ በኋላ ልቡ እንዳልተመለሰላት ዐውቃ በሽታዋም በውነት እየጠና ስለሔደ አስባ ይህ ሰው ሊፈታኝ ነው እንዲያውም በዚህ ዘመንተማሪ ቤት የሚባል የሥልጣኔ ከረዳና የብልሃት ጐረምሳ መሰብሰቢያ አበጅተው ዘመዶቼን ሁሉ ከየባሎቻቸው ሲያፋቱ ባላይ በኔ ባልደረሰብኝ የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል የተባለው ተረት በኔ ተፈጸመብኝ እያለች ስታጣጥር ነፍስዋ ሳይወጣ ዘመዶቿ እነ ትዕቢት፥ እነ ቅንአት፥እነ ሌብነት፥ እነ ቅጥፈት ፥ እነ ማስመሰል ተሰብስበው አንች ከሞትሽ እኛም ዘራችን ጠፋ፣ ሥራችን ተነቀለ እያሉ ደግሞ በግጥም እንደዚህ እያሉ ለእኅታቸውና ለራሳቸው ያለቅሱ ነበር ።

ቅተርፋለች ብለን እኛ ስንፅናና ፤
ሞተች ተቀበረች ወይዘሮ ስንፍና ፤
ሲቀማጠል ኑሮ እስከሁን ካንች ጋራ
ልጅሺ፣ ድኅነትን ለማልሺው አደራ
እንዳላሳድገው እኔም አቶ ኵራት
ትሕትና የሚሉ ይዘኛል ቀኀርጥማት
እንግዲህ የት ልግባ እኔ ምቀኝነት
ፊቱን እያበራ መጣ ስምምነት
የት መግቢያ አገኛለሁ እኔ አቶ ቅጥፈት
ያክፉ ገትጋታ መጣብኝ አቶ እውነት
ወይኔ ማስመሰል ከንቱ ቀረሁኝ
ምርምር የሚባል መርዝ አቀመሱኝ
እኔማ ሌብነት ሰጫቼ ልሞት ነው
ሠርቶ መብላት መጣ ዓይኔን ሊያጠፋው ነው
ክፉ መርዝ አምጥተው ትምህርት የሚባል
ዘመዳችን ሁሉ ማለቅ ጀምሯል
የአባ ጠቅል ጃንሆይ መድኃኒት እያለ
እንግዲህ ዘራችን ሥሩ ተነቀለ

እያሉ ሲላቀሱና ሲተራመሱ አይቼ ወይ መሰንበት ደኅ እያሳየው የለ በናንተም መከራ መጣባችሁ ብዬ ጥያቸው ሔድሁ። እነሱ ሲላቀሱ በመካከሉ ባሻ ልማድ ወደ ወይዘሮ ጥበብ ቤት ለመሔድ ብድግ ቢል አንተ የኛን እኅት አናደህ ገድለህ ወዴት ትሔዳለህ ብለው ሸማውን ይዘው ሲተናነቁ ባሻ ልማድ ልብሱን ጥሎ(አሪት ዘ-ፍ ም ፴፱ ፲፪) ወደ ወይዘሮ ጥበብ ሲሮጥ እመንገድ አግኝቼ ምንሁነሀል ብዬ ብጠይቀው ተው ወንድሜ ዝም በለኝ ክፉም ልማድ ነው፥ ደግም

ልማድ ነው አለኝ አካሉንም ባየው የቀድሞ ልብሱን ሁሉ ለሚስቱ ዘመዶች ጥሎ ዕራቁቱን እየሮጠ እወይዘሮ ጥበብ ቤት ሲገባ አይቼ መክብብ ም ፫ ቍጥር ፩ ፳ ትዝ ብሎኝ እስካሁን ይገርመኛል ነገር ግን አቶ ማማለጃ የሚባለው የነሱ ዘመድ ከነሱ ተለይቶ ቀድሞ የከተማው ኤሌትሪክ በቅጡ እስኪበራ እንደሆን አላወቅሁም እንጂ አንድ አንድ ቀን ማታ ማታ በጨለማ ድምፁን አጥፍቶ ሲሔድ እመንገድ ዘበኛ አግኝቶ ማነህ አንተ ቁም ሲለው በአማርኛ የተናገረ እንደሆን እያዛለሁ ብሎ በውጪ አገር ቋንቋ ድምፁን ጕርነን አድርጎ ቢናገረው እኔህስ የውጭ አገር ሰው ናቸው ብሎ ያሳልፈውና ከተማውን እየዞረ መጐብኘቱን አልተወውም ። ዳሩ ግን እንደ ለመደው አንድ ቀን ካንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት ሲሹለከለክ የከተማው ጠባቂ አንቆ መከራውን ሳያሳየው አይቀርም ብለን ተስፋ አለን።

ኃይለ ጊዮርጊስ ብሩ ።

ስለትምህርት መስፋት ተስፋ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አስቀድሞ ያገራቸው ቀጥሎም የውጭ አገር ጥበብ እንዲሠለጥንና ኢትዮጵያ አገራችንም ከጥንት ጀምሮ በሀገርዋ ላይ የቈየውን ትምርትና ዕውቀት ዝኁ፤የውጭውን አገር ትምርት ማግ በማድረግ ሥልጣኔና ዕውቀትልብስን አሠርታ በልዩ ልዩ ዕውቀት ሽልማት እንድታጌጥ ፈቃዳቸው ስለ ሆነ ለጊዜው ይህን ሐሳብ ለመከተል ከጥቂቶች መኳንንት በቀር ይልቁንም ከካህናት ወገን ምንም ያህል ስለ አልተገኙ የብልህ ልብ ማዘኑ አልቀረም ነበር። ነገር ግን ኢየኀድጋ ለሀገር ዘእንበለ፩ዱ ኄር እንዲል ። ብዕድሜም በማዕረግም የሚቀድሟቸው ብዙ መምህራንና ሊቃውንት እያሉ ዘይንዕሶ የዐብዮ እንደተባለው በዕድሜም በማዕርግም ኋለኛ የሆኑት ክቡር አለቃ ገብረ አጋእዝት ገብረ ሚካኤል የጃንሆይን ደግ ሐሳብ በመከተል ከካህናት ወገን መጀመሪያ ሁነው አሳቀድሞ በደብረ ብርሃን ከተማ የመጻሕፍተ ትርጓሜና የቅኔም፥ የዜማም፥ የንባብም መምህራን ከያሉበት አስመጥተው ለጃንሆይ ነግረው ለመምህራኑም ለተማሪዎቹም እንደሚገባ እንደሚገባቸው ልብስና ቀለብ አስወጥተው ከራሳቸውም በየጊዜው እርዳታቸውን ሳያጓድሉ ካህናቱንም በየጊዜው ከጃንሆይ እያገናኙ ልብስም ቀለብም ሽልማትም እያሰጡ ቤተ ክርስቲያኑ በመልካም አገልግሎት እየተገለገለና ካህናቱም በፍቅር አንድነት ተጸምደው፥ ተማሪቤቱም በመልካም አረማመድ እየተሻሻለ መሔዱን ያሳያል። በዚሁም ላይ አለቃ ገብረ አጋእዝት ተማሪቤቱ በሰፊ ተሠርቶ ልዩ ልዩ ጥበብ የሚያስተምሩ መምህራን እንዲቀጠሩላቸው በየጊዜው ለጃንሆይ ከማስታወስ አልቦዘኑም።ጃንሆይም ይህ ሐሳባቸው እንዲፈጸምላቸው ሙሉ ተስፋ ሰጥተዋቸው ሳሉ አለቃ ገብረ አጋእዝትም የደብረ ብርሃንን ከተማ ለማሳደስና መንገዱን ለማስጠረግ፥ ተማሪቤቱን ለማስፋት ተዘጋጅተው ሳሉ ደጓን ሥራ ከጀመሩት ፈጻሚው እግዚአብሔር ነውና ከቤት በግ ቢታረድ ከዱር ድኩላ ይጠመድ እንዲሉ፥ አገራቸው እንዲሠለጥንና ሕዝባቸው እንዲከብር ፥ መንግሥታቸው እንዲበረታ ሙሉ ፈቃድ ያላቸው ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ በደብረ ብርሃን የሚቆመው ተማሪቤት የራሳቸው ና ያባታቸው የክቡር ደጃዝማች ገድሌ ስም የሚጠራበት እንዲሆን ሲሉ እርዳታቸውን በማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ለክቡር አለቃ ገብረ አጋእዝት ጻፉላቸው።

ይድረስ ለክቡር አለቃ ገብረ አጋእዝት

ሰላምታዬ ላንተ ይሁን

ከአዲስ አበባ ወደ ደብረ ብርሃን መንገድ ሥራ መጀመሩን ሰምቼ በጣም ደስ አለኝ። ነገር ግን አገር የሚለማውና የሚሠለጥነው በመንገድና በተማሪቤት መሆኑን ስለተረዳሁት እኔም ደስታዬን የምገልጽበትና ያባቴን ስም የማስጠራበት እርዳታዬ ለተማሪቤት እንዲሆንልኝ ደብረ ብርሃን እከተማው ውሥጥ አባቴ ደጃዝማች ገድሌ ለቤተ መቅደሱ በእንጣፌነት ይዘጢት የነበረውን ቦታ ለተማሪቤት እንዲሆንልኝ ርስት አድርጌ ሰጥቻለሁ። ሁለተኛም ለተማሪቤቱ መሥሪያ አንድ ሺ ብር ሰጥቻለሁ። ይህኑም ገንዘብ ከጂቡቲ በተመለስሁ ጊዜ አስረክባለሁ ። ይህንንም ቦታ ለተማሪቤት ርስት አድርጌ መስጠቴ ላባቴም ለኔም መታሰቢያ እንዲሆን ነው ። ይልቁንም አገሬን እወዳለሁ መንግሥቴን እረዳለሁ ብሎ በአፍ መናገር አይበቃምና ለሀገር ፍቅርና ለመንግሥት ጥቅም በተቻለ መርዳት የሚገባ ስለሆነ እኔም በተቻለኝ ይህኑ ቦታ ለተማሪቤት ማቆሚያ ሰጥቻለሁ ይህንንም ነገር አደራውን ወዳንተ መጣሌ ትጋትህንና የሀገር ፍቅር እንዳለብህ አይቼ ነውና ይህንንም ለመንግሥት አስታውቀህ፤ በተቻለህ ሁሉ እንድትደ ክምበት አደራ እልሀለሁ። ኅዳር ፳፲፫ቀን ፲፱፻፳፫ ዓ ም ።

ክቡር አለቃ ገብረ አጋእዝትም በደስታ ተቀብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ጨምረው ደብዳቤውን ለጃንሆይ አሳዩ።

ጃንሆይ ።

ስለ ተማሪቤት እርዳታ ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ስለ አባታቸው መታሰቢያ የልዩ ልዩ ጥበብ ተማሪቤት ደብረ ብርሃን ላይ እንዲቆም ያባታቸውን ቦታና ለተማሪቤቱ መሥሪያ ፩ሺ ብር ሰጥተዋል ። እኔም አሽከርዎ በሐሳቤ የደብረ ብርሃን ከተማ እንዲታደስና ተማሪቤቱም እንዲቆም እያሰብሁ በየዘመኑ ለማስታወስ አልቦዘንሁም ነበር ።

ጃንሆይም በቸርነትዎ የኢትዮጵያን የሊቃውንት ተማሪቤት አቁመው ለመምህራኑም ለተማሪውም የሠሩት ሥራ ብዙ ነው ።

በተማሪቤቱም ሁለት መቶ ሰባ የሚያህሉ ወጣቶች ተሰብስበው ልዩ ልዩ ትምህርት ይማራሉ ። አሁንም ወደፊት ልዩ ልዩ ጥበብ ተምረው ለመሠልጠን ደጅ ይጠናሉ ። ይህንኑ ለጃንሆይ እመለከታለሁ ብዬ ሳስብ እግዚአብሔር ያለ ምክንያት ሥራውን አይሠራውምና ክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ ስለ አባታቸው መታሰቢያ ይህነኑ ነገር ስለጀመሩት ጃንሆይ በቸርነትዎ የሚያስፈልገውን ነገር አስበው እንዲፈጽሙት ከዙፋንዎ ፊት በትሕትና አቀርባለሁ ።

አሽከርዎ

ገብረ አጋእዝት ገብረ ሚካኤል ።

ጃንሆይም ቃሉን አይተው ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌን እጅግ አመሰገንዋቸው ። ተከታል አለቃህን ተመልከት ዓላማህን እንዲሉ ወይዘሮ ሸዋረገድና አለቃ ገብረ አጋእዝት ፍለጋቸ-ውን ስለ ተከተሉ በሁለቱም ሐሣብ ጃንሆይ እጅግ ደስ ብሏቸው የድብረ ብርሃኑ ተማሪቤት በፍጥነት እንዲቆም ወደ ትምህርትና ዕውቀት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉ ትእዛዝ አሳልፈዋል ።

በሥራቸውና በትጋታቸው የተመሰገኑ ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉም በሥራቸው ትጋትና በዕውቀታቸው ብዛት ሐሳባቸው ምንም መላ ኢትዮጵያን ለመርዳት ቢሆን አስቀድሞ የደብረ ብርሃን ከተማ እንዲታደስና ሰዉም እንዲሠለጥን ፈቃዳቸው መሆኑ ሊታወቅ የደብረ ብርሃንን መንገድና ድልድይ ለማ-ሠራት ማኅበር ከሆኑት መኳንንት አንዱ እርሳቸው ሁነው የመንገዱ ሥራ እንዲከናወን ማፋጠናቸው ከዚህ ቀደም የታ-ወቀ ነውና አሁንም ተማሪቤቱ በፍጥነት እንዲቆም የተዘጋጁ መሆናቸውን እናረጋግጣለን። ለተማሪ ቤቱም እርዳታ እንሰጣለን ያሉትን ሰዎች ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን።

ክቡር አቶ ማህሌ ፀዳሉ	፪፻ ብር
ክቡር ደጃዝማች ይገዙ	፩፻ ብር
ክቡር መልአከ ገነት ወልደሐና	፩፻ ብር

ክ አለቃ ገብረ አጋእዝት መጀመሪ ፩፻ ብር፡ በየጊዜውም ባለኝ ዓቅሚ ሁሉ እርዳታዬን አላጓድልም ብለዋል። የሰው ነገር እጅግ ያስገርማል ብዙ ሰዎች ሴት ልጅ የወለደ እንደሆነ ምነው ወንድ በሆነችልን እያሉ ያዝናሉ ይህም ከንቱ አሳብ ነው ብዙ ወንዶች ወስላቶችና ቀጣፊዎች፤ዘራቸውን፤አሰዳቢዎች እየሆኑ ከመረገምና ከመካድ፡ ከአባት ርስትና ጉልት ከመነቀል ይደርሳሉ ሴትም የተባረከች ከሆነች እንደወይዘሮ ሸዋረገድ ከወንድ ሁለት እጅ አብልጣ የአባቷን ስም የምታስጠራ ትሆናለች።አሁንም ይህ ታላቁ ስመ ጥሩው የደብረ ብርሃን ከተማ በብርሃናችን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት አምሮ፤ ደምቆ እንዲታደስና ተማሪቤቱም እንዲሰፋ የክብርት ወይዘሮ ሸዋረገድን ሐሳብ እየተከተሉ ስማቸውን ለማስጠራት መኳ-ንንትና ወይዛዝሮች በጣም ሳይተጉበት አይቀሩም በማለት በብዙ ተስፋ እንጠብቃለን ።

ሁሉን ማድረግ የቻለ እግዚአብሔር በሁሉ ይመስገን ።

የኢትዮጵያን መንግሥት ገናና ስላደረገ ያባት የናቴ ልጆች ኢትዮጵያውያን እንኳን በጣሙ ደስአላችሁ። በዚህ ዓለም ካሉ መንግሥታት በፊት ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች መንግሥት እን-ደነበረች ያለ ክርክር የታወቀ ነው ።

ነገር ግን ለሁሉም ጊዜ አለውና ዛሬ በዙፋንዋ ጥሩ ብ ርሃን አኖረችና መጋረጃዋን ብትገልጥ ውበቷ፤አዋቂነቷ፤ ገና-ንነቷ በዓለም መንግሥታት ዓይን ሁሉ ታየ ። በኢትዮጵያ ከነገሡ ሁሉ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ክብሮ የነገሠ አል-ሰማሁም ። የደጉ ወልደ አምላክ ደግነት መሰከረ ። ዛሬም ከምድረ እስራኤል ምድረ ኢትዮጵያ እንደሚሰፋ ከመንግ-ሥተ ሰሎሞንም መንግሥተ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በለጠ ። የሰሎሞንን መንግሥት ልታይ፤ጥበቡን ልትሰማ የሔደች የኢ-ትዮጵያ ንግሥት ብቻ ናት ። አሁን ግን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን መንግሥት ለማየትና ጥበቡን ለመስማት የዓለም ነገ-ሥታት ሁሉ መጡ ። ሰሎሞን ንጉሥ ነበረ ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ግን ንጉሠ ነገሥት ሆኑ ። በለጠ ያልሁት ስለዚህ ነው። ለአሁኖች ሕዝበ ኢትዮጵያ ምስጋና ይገባችኋል። በአንድነት፤ በፍቅር፤በምክር ሁናችሁ መንግሥታችሁን ገናና ስላደረጋችሁ ይልቁንም አራት ፍሬዎች የሚጠቅሙ ስላፈራችሁ ። አንደኛ የመጻሕፍት መኪና፤ ሁለተኛ ካገር ውሥጥ ጳጳሳት መምረጥ፤ ሦስተኛ በትውልዱ፤ በዕውቀቱ የተመረጠ ንጉሥ ማንገሥ፤ አራተኛ ከዓለም መንግሥታት አንድነት መሆን ፤ ይህ አራት ፍሬ ኢትዮጵያን በጣም አከብሯልና ይህን መሰል ቢጨመር-በት ከሁሉ ይከብራል ። በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ ፍቅር ፤ ምክር፤ አንድነት ቢኖር በእጃቸው አይጠፉም ነበር ። በአፄ ተክለ ጊዮ-ርጊስም ቢኖር በክረምት ዘምተው አይዋጉም ነበር ። ባፄ ዮሐንስም ቢኖር ብቻቸውን መተማ ድረስ ዘምተው አይሞ-ቱም ነበር ። ስለዚህ ለዛሬ መኳንንትና ሕዝብ መንግሥታችሁን በፍቅር፤ በምክር አክብራችሁ ገናና ስላደረጋችሁ ምስጋና ይገ-ባችኋል ። ወደፊትም ኢትዮጵያ ትለምልም፤ ፍቅር ታፍራ፤ መን ግሥቷ ይባረክ፤ ምስጋና ለእግዚአብሔር አቡነ ዘበሰማያት ።

አባ ገብርኤል ።

ስለ ጃንሆይ የዘውድ በዓል መታሰቢያ ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን ሸሐ ዓመት ያንግሥልን ስል እሊ-ህን ቅኔዎች አቀርባለሁ ።

ይስግድ ለቃለ አብ ሄሮድስ ስእነ መካነ ወልድ ።
ሰበ ማርያም አግኅሠት ሕፃና ፤ እምነ ገሊላ ዓፀዳ ።
ኀበ ምስማከ ርእስ አልቦቱ ለወልዳ ።
ለኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ባሕቱ ፤ በአምኃ ወርቅ ጋዳ ።
አዋልደ ጢሮስ ይሰግዳ ።
እምጣነ መንበሩ ሜላተ እንተ ይሁዳ ።
ወምስማኩ ይእቲ መከዳ ።

መወድስ ።

ያገብእ ወልድ ፍዳ ወላዲሁ፤ ለአጽድቆ ዝኒ ነገር እንተ ኢከነ እንግዳ። እግዚአብሔር አብ ፍዳ ዘከደኖ እነዳ ።
ለአካለ አዳም ዘተዐርቀ ፤ እምልብስ ጸጋሁ ዘኅብሩ ፀዓዳ ።
ውሉደ አዳም መገብተ ፍዳ ።
ሰዕርቃነ ወልዱ ክርስቶስ አልበስዎ ከለሜዳ ።
ለጥበብሂ ዘሰሎሞን ንግሥተ ዓዜብ ማክዳ ።
ፍዳ ዘነገደት ወሖረት ኢየሩሳሌም ምድረ ይሁዳ ።
ለንግሥተ ዓዜብ እጓዝእት ፤ ፍቀረ ጥበቡ ለወልዳ ።
ሰሐቦሙ ለነገሥታት እምኢየሩሳሌም ኀበ ዓፀዳ ።

መወድስ

ሐወጺታ ዮም ለኢትዮጵያ ፤ መቃብረ ጥበብ ወልድ እንዘ ዓዲሁ ጽልመት ።
ወረከበቶ ለእብን ፤ ድንቃዌ ብዙኀ ፍጥረት ።

እቱ ኮ እምአፈ ሕፃናት መቃብር ክሡት ፡፡
ሀገረ ኤሮጳ እን ፦ ሰፍረት ፡፡
እንተ ቀብዓቶ ዕፍረተ ለኃይለ ሥላሴ ወልደ ዳዊት ፡፡
በእትሂ ለተማኅፅኖ ቤተ ጊዮርጊስ ሰማዕት ፡፡ ለንጉሠ ነገሥት ኃይለ ሥላሴ አክሊለ ንጻሡ ቢሩታዊት ፡፡ ከመ ኅቤሃ ኢይብጻሕ በእግረ ትዕቢት፡፡ፀራዊ አርዌ ዓመፃ ዘተረግዘ በኩናት

አለቃ ዳንኤል እ ደስታ

ስለ ብፁዕ መምህር ዓምደ ማርያም ዕረፍት

ባለፈው ብርሃንና ሰላም እንዳመለከትን የታላቁ ገዳም የደብረ ቢዘን አበምኔት ብፁዕ መምህር ዓምደ ማርያም አክለ ጉዛይ ውሥጥ በራቂት በሚባል አገር ተወልደው በተወለዱ በዓሥራ ሦስት ዓመታቸው ደብረ ቢዘን ገቡ፡፡ከዚያውም መጀመርያ መጻሕፍተ ምንባብን፡ ኋላም መጻሕፍተ ትርጓሜን ተምረው ሥርዓተ ምንኵስናን፡ አፅንተው ዕንጨት በመስበር፡ ውኃ በመቅዳት፡እሳር በማጠብ፡ ከዚህም ሌላ የትሩፋት ሥራን እየሠሩ ከዚያው የሚኖሩትን አበው ሲረዱና ከውጭ የሚገቡትን እንግዶች ሲቀበሉ አደጉ ፡፡ በተወለዱም በዓርባ ዓመታቸው ማኅበሩ በትሩፋቱ ያጸድቀናል፡በጸሎቱ ይጠብቀናል፡ማኅበራችንን ያሰፋልናል፡ አስተዳደር ያውቅልናል ብለው ተሾምልን አሉዋቸው፡፡እሳቸው ግን ትሕትና ኀዘባቸው ነውና እኔ ለዚህ ማዕርግ አልበቃምና አይሆንልኝም ተዉኝ ብለው ቢለምኑዋቸው ማኅበሩም የሚሻለንን እኛ እናውቃለን ብለው ያለውድ በግድ ይዘው ሾሙዋቸው፡፡ከተሾሙም ወዲህ ጌታ በወንጌል ዘይፈቅድ እምኔክሙ ዐቢየ ይኩን ሊቀ ይኩንክሙ ገብረ፡ወዘይፈቅድ እምኔክሙ ይኩን ዐቢየ ይኩንክሙ ላእከ ያለውን ተመልክተው (ማር ፲ ቁ ፵፫) ማዕርጋቸው ምጡቅ፡ አእምሮአቸው ረቂቅ ሲሆን በትሕትና ሁሉን ያገለግሉ ነበር ፡፡ መጠኑ ለረድእ እምከመ ኮነ ከመ ሊቁ እንዲል ያበታቸውን የአቡነ ፊልጶስን ሥርዓት ራሳቸው ፈጽመው፡ለሌላውም እያስተማሩ ገዳሙን አቅንተው፡ ማኅበሩን አስፍተው፡ በፍቅር ሰንሰለት አቈራኝተው በማናቸውም ነገር ካንድ ሕፃን ሳይበልጡ በዙርያቸው ላለው ሕዝብ ሁሉ ወንጌልን እየሰበኩና ፍቅርን ለሁሉ እያስተማሩ ይኖሩ ነበር፡፡በውሥጣቸውና በዙርያቸውም ያለው ሕዝብ ሁሉ ከደግነታቸው የተነሣ ለፍቅራቸው እጅግ ይሳሳ ነበር፡፡ ለገዳማቸውም የሠሩለት ሥራ በሙሉ ለመጻፍ ብዙ ጊዜ የሚወስድብን ስለ ሆነ ከሙሉ በከፍሉ፡ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን፡፡ መጀመርያ ገበታው በወርቅ ያጌጠ አንድ ወንጌል ፤ ሁለተኛ መጻሕፍተ ብሉያትንና መጻሕፍተ ሐዲሳትን አጽፈው አንድነት አስጠርዘዋል ፤ ሦስተኛ ከመንግሥት አስፈቀደው አንድ ዘውድ አሠርተዋል፡፡ከዚህም ሌላ ብዙ መጻሕፍትን አጽፈዋል፡፡ የጌታችንንም መቃብር እጅ ለመንሳት ሁለት ጊዜ ኢየሩሳሌም ተመላልሰዋል፡፡ ግብፅም ወርደው እስክንድርያን ሌሎችንም ገዳማት ሁሉ አይተዋል ፡፡

ደግሞ ግርማዊ የኢጣሊያ ንጉሥ አልጋወራሹን ልጃቸውን ሲድሩ በ፲፱፻፳፪ ዓም ጠርተዋቸው ወደ ሮማ ሔደው የደስታቸው ተካፋይ ስለ ሆኑ እጅግ የሚያስደንቅ ሽልማት ሸልመው ኒሻን ጨምረው አስጊጠው ወደ ሀገራቸው በብዙ ደስታ መለሱዋቸው ፡፡ ደግሞ በ፲፱፻፳፫ ዓም ጥቅምት ፳፫ ቀን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የዘውድን በዓል ሲያከብሩ ስለ ገዳሙ ክብርና ስለሳቸው ፍቅር ጠርተዋቸው መጥተው የዘውዱን በዓል በደስታ አክብረው ለማዕርጋቸው የተገባ ሽልማት ኒሻን ጭምር ተሸልመው እጅግ ደስ ብለዋቸው ነበርና ደብረ ሊባኖስንና አዲስ ዓለም ማርያምን ለማየት በአውቶሞቢል ሔደው ነበር ፡፡ ነገር ግን ከገድል ፅናትና ከሥራ ብዛት የተነሣ ሳል ያማቸው ነበርና ያው ተነሥቶባቸው ስለ ታመሙ ከዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገብተው ሲታከሙ ከሰነበቱ በኋላ ዕድሜው ለደረሰ መድኃኒት የለውምና ቀን ቢደርስ እምባ ይፈርስ እንዲሉ ፅኑ የሃይማኖት አምባ መምህር ዓምደ ማርያም ታኅሣሥ ፩ ቀን በ፩ ሰዓት ተኩል ዐረፉ ፡፡ በዓሉም ኤልያስ ነበር፡፡ ጌታ ኤልያስን ከዚህ ዓለም በሚለይበት ጊዜ ሠረገላ እሳት አፍራሰ እሳት መጥተው አሳረጉት እንዲለው ጃንሆይም ብፁዕ አባታችንን የሠረገላ እሳት ምሳሌ በሚሆን በአውሮፕላን ደብረ ቢዘን ወደ አባቶቻቸው መቃብር ስለ ሰደዱዋቸው እጅግ ያስደንቃል ፡፡ይኸውም በድኅነታቸው መለያየት የሌለባቸው የደብረ ቢዘን ማኅበር ሁሉ ጊዜ ከጾም ከጸሎት አለመለየታቸውን ያስረዳል፡፡ዕድሜያቸው ፷፩ ዓመት ነው፡ ከናት ከአባታቸው ቤት ፲፫፡ በደብረ ቢዘን ፵፩ ዓመት ነው፡፡ጃንሆይ የአባታችንን አስከሬን በአውሮፕላን ብሰደዱት ጊዜ ሠርግ መሰለን እንጂ ሞት አልመሰለንም፡፡ነገር ግን የቆምንበት መደብኀዘን ነውና ተድላ ደስታ ለማድረግ አልተቻለንም ፡፡

የጃንሆይንና የእቴጌን ዕድሜ ያርዝምልን፡ መንግሥቱም ለልጅ ልጃቸው እንዲያልፍ ፈጣሪያችንን እንለምናለን፡፡የሃይማኖታቸው ፅናትና የፍቅራቸው ብዛት ወሰን የለውምና ፍቅራቸውን በልቡናችን መሠረትነት ይንፅልን፡ በደብረ ቢዘን ማኅበርና በየሀገሩ ያሉትንም የመምህር ዓምደ ማርያም የሃይማኖት ልጆቻቸውንና ወዳጆቻቸውን ሁሉ እግዚአብሔር ያጥናቸው ፡፡

መወድስ

እሰፍንቱ አብያት እለ ተመዝበሩ ፤
ለአበ ብዙኃን አብርሃም ዓምደ ማርያም በተኃቅኦቱ ፡፡
ወእምነ እበል አሐዱ ለእመ ሐመ በሕቲቱ ፡፡
ኵሉ አበል — እምከመ ሐመ
ይትበሀል ማኅበረ ቢዘን ብዙኃን ሞቱ ፡፡
በሞተ ዋህድ አ ቡሆሙ
እንዘ ብዙኃን ርኁፉቁ እምጣነ ትለዱ እሙንቱ ፡፡
ተበሀሉሂ በትእይንት እለ ነጸርዎ ሎቱ
አማን በአማን መንክር በዕርገቱ
እንዘ በሥጋ የዐርግ ውስተ ሰማያዊት ቤቱ
ዓምደ ማርያም በኵረ ትንሣኤ ለኃይለ ሥላሴ በክሂሎቱ፡፡

ገብረ መስቀል ፡፡

የ መ ን ግ ሥ ት ማ ስ ታ ወ ቂ ያ።

ማንም ቢሆን በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ፈቃድ ሳይቀበል ማናቸውንም አውሬና እንስሳ ወፍም እንዳያድን ወይም ከነነፍሱ እንዳይዝ ከዚህ ቀድሞ በጥቅምት ፲ቀን ፲፱፻፳፪ ዓመት ፵፫ ቍጥር ብርሃናን ሰላም ጋዜጣ በወጣው የአዋጅ ቃል መከልከሉ አሁንም እንደ ጸና ነው ።

ደግሞ ከአዲስ አበባ እስከ ወሰን በፍራንኮ ኢትዮጵያ የምድር ባቡር መንገድ ቀኝና ግራ ባሉት አውራጆች ልዩ ፈቃድ ያልተቀበለ ሰው ማናቸውንም አውሬ እንዳያድን ክልክል ነው ተብሎ አዋጁ በሚያዝያ ፴ቀን ፲፱፻፳፩ ዓመት በ፲፱ ቁጥር ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ወጥቶ ነበር አሁን ግን በነዚሁ አውራጆች ያሉት አውሬዎችና እንስሶች በብዙ ከመታደናቸው የተነሣ ቁጥራቸው እያነሰ ስለ መሔዱ ወደ ፊት አዲስ አዋጅ እስኪወጣ ድረስ ከታኅሣሥ ፩ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ጀምሮ በነዚሁ አውራጆች አውሬና እንስሳ ለማደን ለማንም ቢሆን ልዩ ፈቃድ አለመሰጠቱን እናስታውቃለን።

ኅዳር ፴ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት አዲስ አበባ የእርሻ ሚኒስቴር።

ማስታወቂያ።

ሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ስለሞተ። ምናልባት የተወው ዕዳ እንዳለ ማስታወቂያ፥

ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው የሚባለው ነጋዴ የኢጣልያ ዜጋ ስለ ሞተ የሚቼን ገንዘብ አኳኋን ማደላደል መጀመሩን በአዲስ አበባ ያለ የኢጣልያ ሌጋስዮን ያስታውቃል፥

ስለዚህ ከሟቹ ከሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒኮላው ላይ ገንዘብ አለን የሚሉ ሰዎች ማስረጃ ወረቀታቸውንጨምረው ጥያቄያቸውን ለዚሁ ሌጋስዮን የቆንስላ መጻፍያ ቤት እንዲያስታውቁ ብለን እናመለክታለን ።

ጥያቄያቸውንም ለማቅረብ የወሰነው ጊዜ እስከ ጥር ፩ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ድረስ ነው። ከዚህ ክተወሰነውም ቀን በኋላ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል አይቻልም።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ክሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውስጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፡ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ዊ ስ ኪ ።

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግም ባለትልቁ ምልክት ኤክስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል ። በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ካርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፈንሶን ማክዳም የሚባል በኢ-ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። በዚሁም መታከሚያ ቤት ማናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ከቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከንሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀበላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሰል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጕበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፈያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግርማዊት ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በግርማዊ ንጉሥ ተፈሪ መኰንን ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና በታ አዲስ አበባ። የማኅበሩ ሥራ ማንኛውንም የንግድ፥ የርሻ የፋብሪካ፥ የደን፥ የማዕድን ሥራ ማንኛውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት አሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM

የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም በየዓይነቱ እንደ ሴንፓር ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻላል። ፊኒክስ (PHENIX.) የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ደቀበላል ። (ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪካ አጠገብ ዱሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ደኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ። መጥታችሁ እዩ።በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስመጭ።

በኢትዮጵያና በፈረንሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርናንዲስና ልጆቹ የወንዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ ።

S. F. FERNANDES&SONS,

COGNAC S.E.A. METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE.
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሳ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ስድስተኛ ዓመት ቍጥር ፶፪
6me ANNÉE № 52

ሐሙስ ታኅሣሥ ፲፮ ቀን ፲፱፻፵፫ ዓም።
JEUDI 24 DECEMBRE 1950

ብርሃንና ሰላም
LUMIERE et PAIX

በአዲስ አበባ ሐሙስ ዕለት በየሳምንቱ ይታተማል ።
Hébdomadaire paraissant tous les Jeudis

Direction et Rédaction
Addis-Abeba (Ethiopie)

ጋዜጣውንም የሚፈልጉ ለዲሬክተሩ ለአዶ ማሳተሚያ ወርቅ እሸቱ ያስታውቁ ።

የጋዜጣው ዋጋ በኢትዮጵያ ውስጥ ባመት ፭ ብር ። በውጭ አገር ባመት ፯ ብር አስቀድሞ ይከፈላል ። በየሳምንቱ መጣኝት ለፈለገ በ፪ መሐለቅ ይሸጣል ።

Abonnements
Ethiopie — Un an 5 Thalers
Etranger — Un an 7 Thalers
le numero 2 piastres

አዲስ ዘመን በኢትዮጵያ ታሪክ ።

በዚህ ወር ውስጥ መላው ዓለም ዓይኑን ወደ ኢትዮጵያና ወደ ንጉሠ ነገሥቱዋ መልሶ ነበርና በንግሥ በዓል በተደረገው ክብር አለመጠን ተደነቀበት ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግን አፄ ኃይለ ሥላሴ በአባቶቻቸው ዙፋን ላይ መውጣት አብዝቶ እልል ይል ዘንድ ወደ ኋላ ዘወር ብሎ ያለፈውን ታሪክ ካየ በኋላ የዛሬውን ዓለም አኳኋን ይመርምር ።

የዓለም ታሪክ ከታወቀበት ጊዜ አንሥቶ እስከ ዘመናችን ድረስ በየጊዜው የብዙዎችን አኳኋን ሲመለከቱት ያስደንቃል። አዲስ መለወጥ ወይም አኑዋንዋር በዓለም ሲጀመር የሥልጣኔውንና የመንግሥቱን ሥርዓት ከጊዜው አካሔድ ጋር ሳያስማማ የቀሩት ሕዝብ ሁሉ ከማዕርጋቸው ስፍራ ወርደው እንደተዋረዱ ታሪክ ያስተምረናል ። ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአለፉት ሰባት ሺህ ዓመታት ውስጥ ሥልጣኔያቸውንና ወጋቸውን ለሚከተሉዋቸው ትውልድ ለማስቀረት የቻሉበት ምክንያት አኳኋናቸውን ከዘመኑ ሥርዓት ጋር ማስማማት ስለተቻላቸው ይመስላል ። ስለዚህ ነገሥታት ሲነሡና ሲወድቁ ኢትዮጵያ በዘመን ብዛት ሳትነዳ እንደተራሮችዋ ፀንታ ቆመች ። ነገር ግን ያለፈውን ዘመን ታሪኩን ብንመረምር ለኢትዮጵያ ነፃነትና ኑሮ እንደአሁኑ ጊዜ የሚያሰጋ ሁኖ አልታወቀም ። በጥንት ጊዜ በአፍሪቃ በእስያ ወይም በአውሮፓ በብርታት የሚበልጡዋት አገሮች አልነበሩም ። የግሪክና የሮማ መንግሥቶች በየጊዜያቸው የታወቀውን ዓለም ግማሽ የገዙ የኢትዮጵያን ኃይል መሞከር የሚጠቅም ሁኖ አልታያቸውም ነበር ። በአለፈው ሺህ ዓመት ግን ዓለም በሃይማኖት ምክንያት ስለተከፈለ ከአውሮፓና ከእስያ ጋር ሳንገናኝ ቈየን ። ኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ የመርከቡን መስኮት ከፍቶ የመሬትን አኳኋን እንደተመለከተ እኛም የዛሬ መቶ ዓመት የሚሆን ከተራሮቻችን አሻግረን የዓለምን ጸጥታነት ብንሰልል ዱሮ ያወቅነው ሁሉ ተለውጦ ታየን ። በጠረፋች ያለውን የባሕር ሞገድ ብርታት የተነሣ ከባሕር ዘልቆ የዓለምን ሁኔታ የሚመለከት ርግብ ለመላክ ብዙ ዘመን አስፈለገ ።

በአለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ የገዙ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ ቅድስት አገራቸው ለዘላለም ትኖር ዘንድ የአውሮፓን የሙያ ሥልጣኔ በመቅዳት መሆኑን ለሕዝባቸው ገልጸዋል ። ታላቁ ንጉሠ ነገሥት አፄ ምኒልክ በዚሁ አሳብ ተይዘው ብዙ ነገር አደረጉ ። እርሳቸውም ከሞቱ በኋላ ሐሳባቸውንና ምኞታቸውን ለመፈጸም ኃይልንና ብልሃትን አዋሕዶ የያዘና ለወደፊቱ አስቦ የሚሆነውን ለማየት የሚችል ራስና አእምሮ አስፈለገ ።

ይህም ስጦታ ያላቸው አፄ ኃይለ ሥላሴ መሆናቸውን ኢትዮጵያ ስለተረዳች ልጄ እንደአባቶችህ ሕዝቤን ጠብቅልኝ ብላ አደራ ሰጠቻቸው በአለፈውም አስራአምስት ዓመት ያደረጉትን ብንመረምር ምኞቱዋን እንደ ፈጸሙላት እንረዳለን የዛሬ ፲፫ ዓመት አፄ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋወራሽና እንደራሴ በሆኑ ጊዜ የዓለም አኳኋን ለኛ በጣም የሚያሳስብ ነበር ። የአገራችን ብልጽግናና ሀብት ለሌሎቹ ፈተና ሁኖ የታየ ስለመሰለ ብዙዎቹም ሰዎች አንድ ጊዜ እንደዚህ ለማለት ያሰቡ ይመስላል።የአገራችሁ ስፋት ከአንድ ሚሊዮን ስኰር ማይልስ ይበልጣል (የጀርመን የፈረንሳዊና የእንግሊዝ አገር አንድነት ተጨምረው ኢትዮጵያን ያህላሉ ከዚህም በላይ ባልምላሜ በብልጽግናና በአየሩ ጥሩነት ለብዙ መቶ ሚሊዮን ሕዝብ ኑሮ የሚበቃ ነገር ይዘዋል ።እኛ ያለንን ሥርተን እንደምንሸጥላችሁ እናንተ ካለማወቅ የተነሣ ያላችሁን ሥርታችሁ ለጥቅም ታላገባችሁ እንዴት ሳትበሉ ወይም ሳታስበሉ ዝም ብላችሁ ለመቀመጥ ይቻላችኋል። እንደዚህ ያለውን ሐሳብ የያሁዳ አንበሳ እንዴት እንደተቃወመ አይተናል ።ኢትዮጵያ ከቀረው ዓለም ጋራ በወዳጅነትና በንግድ ብትቀራረብ የቀረበቻቸው መንግሥቶች ጥቅም እንደአላት አይተው ነፃነትዋ እንዲከበር ሳያደርጉ አይቀርም ተብሎ በጥንቃቄ ስለታሰበ የዛሬ ሰባት ዓመት አፄ ኃይለ ሥላሴ የአውሮፓን ዋና ከተሞች ከጎበኙ በኋላ በትልቅ ትግል መንግሥታቸውን ወደ ሕዝብ ማኅበር አስገቡ ።

የሕዝብ ማኅበር ጓደኛ ለመሆናችን ለአገራችን ነፃነት የሚያስፈራ ነገር ቢኖግ ለሕዝብ ማኅበር ጓደኛ የሆኑት መንግሥቶች እንዲቆሙልን ተስፋ ተቀበልን ይህ ለሞፀ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ትልቅ ድል መንሣት ሆነ ።

ለአገራቸው የባሕር መግቢያና መውጫ በጣም ማስፈለጉን በለተረዱ አፄ ኃይለ ሥላሴ በአውሮፓ ሳሉ ከፈረንሳዊ መንግሥትና ከኢጣሊያን መንግሥት የባሕር ጠረፍ ጠየቁ። (እነዚህ ሁለቱ መንግሥቶች ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸውን ወዳጅነት አስበው የጠየቅናቸውን ሳይሰጡን አይቀሩም የማለት ተስፋ አለን) ደግሞ ምናልባት የሕዝብ ማኅበር ከማኅበርተኞቹ አለመስማማት የተነሣ የደከመ እንደሆን ብለው በተለየ መንገድ ለኢትዮጵያ ብዙ ወዳጆች አበጁ። ስለዚህ ዛሬ ብዙ መንግሥቶች ይላሉ» የኢትዮጵያ ነፃነት ለዓለም የሚያስፈልግ ነው። » ብዙ መንግሥቶች ይህነን ተረድተዉት የኢትዮጵያን የንግሥ በዓል ለማክበር የከበሩ ምስለኔዎቻቸውን መላክ በኢዮትጵያ ታሪክ አዲስ ዘመን እንደተጀመረ ይመሰክራል።በዚህ ዓመት በአዲስ አበባ የተደረገው ክብር በማናቸውም ሽፍራ አልተደረገም። ሰሎሞን እንኳ እንደዚህ ያለ ክብር አላገኘም ። አፄ ኃይለ ሥላሴ በኢትዮጵያ ዙፍን ላይ በክብር የተቀመጡ ዕለት ለኢትዮጵያ የጥንት ውበቱዋ ተመለሰላት። የዳዊት ልጅ ከሦስት ሺሕ ዓመት እንቅልፍ ቀስቅሰዋት በፍቅር ክንፋቸው ዱሮ በመንገድና በአሳብ ከራቁዋት ቄነጃጂት ጋራ አለማመዷት ።

የንግሥ በዓል ዕለት ብዙዎች ጋዜጣዎች ይላሉ ። የአፍሪቃና ሥሌዎን ሕዝቡን ወደ ክብር ለመምራት የሚያስብ ተነሣ። አንድ የእንግሊዝ ጋዜጣ እንደዚህ ይላል ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ለንጉሦች ሁሉ ምሳሌ ናቸው።የንግሡ በዓል ቀን ብዙዎች ጋዜጣዎች የእንግሊዝ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ደስታቸውን ይካፈላሉ ብለው በመግለጻቸው ና ለንጉሠ ነገሥታችን ረጅም ዕድሜ መመኘታቸው በጣም ደስ የሚያሰኝ ነበር። ይህም የወዳጅነት አካሔድ ለአፍሪቃና ለዓለም ዕርቅና መስማማት መሠረት ዋና ተጨማሪ መሆኑን አንጠራጠርም።ንጉሠ ነገሥታችን ባለፈው ዓሥራ አምስት ዓመት በብርታትና በትጋት ለሌላ ሰው ከቶ የማይቻለውን ሥራ ሠርተው ለአገራቸው ነፃነትና ደስታ ዋና ብርቱ መሠረት እንደአቆሙ አየን።የጀመሩትንና ያሰቡትን ሥራ ለመፈጸም ረጅም ዕድሜ እንዲታደሉ መላው ኢትዮጵያ ይመኝላቸዋል።በሎንዶን ዩንበርስቲ ተማሪ አያና ብሩ።

ዲስኩር ።

አይቴ ብሔራ ለጥበብ ወአይቴ ማኅደራ አይቴ ደወላ ወበአይቴ ተረክበ አሥረ ፍኖታ ብለው ግርማዊ ሰውነታቸውን ያዘጋጁ ያስረከቡ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የእግዚአብሔር አገልጋይ በመሆናቸው ጥበብን ገንዘብ ካደረጉ በኋላ ከጥንት ጀምሮ የተሠወረውን ዕውቀት በጥበብዎ ብዛት ቸርነቱ የማያልቅበት ሰማያዊ ንጉሥ እስከ ሰጠዎ ዘመን ልክ ሰብአ ዓይን ረሰይኩከ ለቤተ እስራኤል ብላ ሀገሩ ለንጉሥ ዓቢይ ቅድስት ኢትዮጵያ ልጆቿን አደራ ብትጥልብዎ ተንሥኡ በጥበበ እግዚአብሔር ለፍጡሩ በገለጸው ከደረ የማይለይ ከተሰጠ የማይነሣ በአለው ዕውቀት ተነሡ ደቂቅኪኒ ይክውኑ ምሁራነ በኅበ እግዚአብሔር ብሎ ነቢዩ አዋጅዎ በሰበከ ጊዜ በንጽሕና ሁነው ሀገራቸውን የሚጠብቁ የኢትዮጵያ ልጆችም ንትንሣእ እንከ በመንፈስ ቅዱስ ከመ ለቢወነ ንልሖቅ በጺጋሁ ወንትመከሕ በስመ ዚአሁ ወንትሐነፅ ዲበ መሠረተ ነቢያት ወሐዋርያት ብለው ለሚመጣው ዘመን ምን ይዘን እንቈያቸዋለን የሰው አምሮ አራቆ አስበ ከፈረሰኛ ይቀድም ዘንድ ውሥጥ ለውሥጥ ገብቶ እየዋኘ ያዘ የሚወጣው ዕውቀት ስንኳንስ ፈጽሞ ለማጠየቅ በብዙ ምርምር የማይገኝ ይመስለኛል።ጥበብ ጥበብ የሚል አዋጅዎ እንደምን ያለች ናት ተሎ የሚጠይቅ ሰው ቢኖር ይእቲ ትኄይስ እምዕንቍ ክቡር ከከበረ ዕንቍ እስዋ ትበልጣለች ክብር ሁሉ አይመጣጠናትም ምክር ዕውቀት አላት ፅንዐ አእምሮ ትሰጣለች ነገሥታቱም በሷ ነግሠው ያነግሣሉ።መኳንንቱም በስዋ እውነትን ፈርደው አገራቸውን ይጠብቃሉ።ሕጓን የሚጠብቁ በለሟሎቿን ጕስቍልና የሌለው ምድረ ርስትን ከማውረሷ የተነሣ አምልኮተ እግዚአብሔርን ታስተምራለች ሀገር ጠባቂ አስተዋይ የሆነ አዋጅዎ በጣዕም ላይ ጣዕም በጸጋላይ ጸጋ ጨምሮ ጥበብ ተብላ ጠቢብ ብልህ ማሰኘቷን ለስብከተ ሀገር ይገልጻል። በሕርን በፈጠራት ጊዜ በአድማስ በናጌብ እንዳፀናት ሁሉ የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ የማነ እግዚአብሔር አልዐለተኒ ያለውን ቃል ዕኑዕ ኀኅፈድ ያደረጉ ንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም በሕገ ጥበባት ኢትዮጵያ ሀገራቸውን በበላይዋ ላይ ያጥቢያኮከብ የመሰለ ብርሃን ጥበብን ወሰን ድንበር አደረጉላት ይልቁንም ዓለምን የሚጕበኝ የዘውድዎ ምሳሌ ነቢይነት ያለው ምሳሌ ነው።ይህችውም የከበረች ዕለተ እሑድ የፍጥረት መጀመሪያ እንደመሆኑዋ ያለሙ ሁሉ ጌጽ የሚሆን አባትነት ያለው ደስታ ዘውድዎ ለኢትዮጵያ የክብር ክብር መሆኑ የጥንት ታሪኮች ይመሰክራሉ ውስተ ጽርሕከ ዘኢየሩሳሌም ቅድስት ኢትዮጵያ ለከ ያመጽኡ ነገሥት አምኃ ያለውን ብንመለከት ወናልዕል ስሞ ኅቡረ ብለን ለግርማዊነትዎ በሚገባ የታወቁ ታሪኮችን እንጽፋለን እንዲህ ያለ ትሕትና እንደምን ያለ ትሕትና ነው።እንዲህስ ያለ ትዓግሥት እንደምን ያለ ትዕግሥት ነው ይኸነን ያህል ዝምታ በመቻል ሰውን መውደድ እንደምን ያለ ፍቅር ነው። የሰው ፍቅር የአብ የባሕርይ ልጁን ከዙፋኑ አውርዶ ለዓለሙ ድኅነት የሚያድል እንደመሆኑ በፍቅርዎ ብዛት እሊህ ግሩማን የሚሆኑ ቃላትን እነሆ ከግርማዊነተዎ የሚቀበሉ ክቡራን ነገሥታት ምንኛ ድንቅ ነገር ነው። ወተከሥቱ መሠረታተ ዓለም ሀገረዎን ከመውደድዎ የተነሣ መሠረተ ዓለም በማሰኘትዎ ለመንግሥትዎ ሰፊ ወራት ረጅም ዘመናት ያድልለዎ ለሀገርዎም ሰላምና በረከት ለሕዝበዎም ጤና በማግኘት ላይ መስማማትንና ጥበቡን ያኑርልዎ ። ቦጋለ ደርሰህ ።

ስለሕመምተኞች ሆስፒታል መጻባት ።

በኢትዮጵያ ሀገራችን ውሥጥ ባለጠጎች ባለብዙ ርስትና ግዛት ያላቸው ሰዎችና ደሃዎች ሠርተው አዳሪዎች ለለት ምግባቸው ብቻ በየቀኑ የሚያገኙና ባለጸጎችም በልዩ ልዩ በሽታ እየታመሙ ብዙዎቹም እየተመላለሱ ለመታከም ብዙ

ዎቹም እንደበሽታቸው ኃያልነት እሆስፒታል እየገቡ ተኝተው ሕመማቸውን በእግዚአብሔር ቸርነትና በሐኪሞቹ በጥንቃቄ ማስታመም የሚፀኑ ሞልተዋል ።

ነገር ግን በዚሁም እሆስፒታል በመታመማቸውና ሕይወታቸውን አግኝተው ድነው የሚወጡበትን ጊዜ የባለደጎችንና የድኆችን ወገን ስንመለከት በጣም የሚአስገርሙና የሚያሳዝኑ ሁለት ነገሮች ይታዩበታል። ፩ኛው ገንዘብ የሌላቸው ድኆዎች የሆስፒታሉን መድኃኒት ዋጋና የቤቱን ኪራይ ድነው ሲወጡ ተዉንና ማሩን ሳይሉ ከሕመማቸው በጥንቁቆች ሐኪሞችና በትጉሆች አስታማሚዎች እጅ ታመውና ታክመው በመዳናቸው ያላቸው ገንዘብ ያላንድ ጭቅጭቅና መሰናክል እንደፋክቱሩ እየከፈሉ በደስታ በመሔዳቸው ፪ተኛም ባለብዙ ገንዘብ ገቢ ያላቸውን ባለጸጎች ከዚህ በላይ እንደጻፍኩት ሁሉ ታመው ከሕመማቸው በእግዚአብሔር ቸርነትና በሶታማሚዎቹ ጥንቃቄና ትጋት በመታመማቸውና ድነው ከሆስፒታል በመውጫቸው ጊዜ የሆስፒታሉን የመድኃኒት ዋጋና የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ በፋክቱር በተጠየቁ ጊዜ መንግሥትን ክፈሉልን ወይንም በነፃ እንድንታከም ፍቀዱልን እያሉ አንዳንዶቹ ባለጸጎች ስለሚጠይቁና መክፈል የሚችሉትን ጥቂት ነገሮች ክፈሉልን እያሉ ግማሾቹም ከመንግሥት ጓዳ እየተከፈለላቸው ግማሾቹም በፈቃድ ወረቀት ነፃ እየሆኑ የሆስፒታሉን ገቢ በማሳነሳቸው ያላቸው ሁነው እንደሌላቸው ሁነው ሲለምኑና ሲናገሩ ስለሚታዩ በጣም ያስገርማሉ ።

እነሆ በኤውሮፓ ያሉትን የሐኪም ቤቶች ዝናና ወሬ ስንሰማ ሳለን በጣም ይገርመናል። በኤውሮፓ ከበርቴዎች እሆስፒታል ገብተው ታመው በዳኑ ጊዜ ለሆስፒታሉ ከሚከፈለው ዋጋ አብልጠው ፭ና ፮ እጅ ይከፍላሉ ። ደግሞም ለሆስፒታሉም እርዳታ እንደመጠናቸው ይሰጣሉ። ለሆስፒታሉ ሐኪሞችና ረዳት አስታማሚዎችም ሳይቀር ሲሉ እንሰማለን። ይልቁንም ፩ ፩ ከበርቴዎች ለሆስፒታል መርጃ እያሉ ለሆስፒታል ምሊዮን ምሊዮን ፍራንክ እየሰጡ ስማቸው በሆስፒታሉ ግቢ ውሥጥ እርዳታቸውና ደግ አድራጎታቸው በእብነበረድ ላይ የተጻፈላቸው ያ በእብነበረድና በወርቅ ቀለም የተጻፈው ስማቸው እስከልጅ ልጅ ድረስ እየታየ ሲነበብና ዝናቸው ሲነገርና ስማቸው ሲጠራ ይኖራሉ ይባላል። ደኃዎች ግን የበቃ ገንዘብ ስለሌላቸው እሆስፒታልም ሒደው ቢታከሙ በነፃ ይሔዳሉ እንጂ ለመክፈል የሚያስገድዳቸው ነገር የለም ይላሉ ።

እንደዚሁም ሁሉ በጥበብና በትምህርት አከናውነው ያወቁት ሐኪሞች ከኤውሮፓ ከመጡልን ደንባቸውንና በኤውሮፓ የሚደረገውን የሆስፒታል ሕግና ሁናቴ እየጠየቅን መፈጸም ነው እንጂ ሐኪምን ወዶ ገንዘብ መክፈልን ጠልቶ ሕይወትን ለማዳንና ጤንነትን ለማሰፋፋት የሚሳነ ነገር አይመስልምና በዚህ ነገር ከበርቴዎችና ባለገንዘቦች የሆናችሁ ሁሉ እርዳታችሁንና ለየሆስፒታሎች በጎ ሥራ ማድረጋችሁን እንድታስቡበትና በታመማችሁም ጊዜ ዋጋ በዛብን ብላችሁ እራሳችሁ ለመክፈል የምትችሉትን እንዳጣ ሁሉ መንግሥትን መለመንና ክፈሉልን ማለትን ብትተዉት ደግ ነበር ስል በደከማው ዕውቀቴ አሳስባችኋለሁ። በቀለ ዘለቀ ።

ሥላሴ

ሠናያን ወኅሩያን፣ ዓሠርቱ ቃላት ነገሥተ ምድር።
ወእፃምን እሉ ነዮሙ ሠለስቱ፤ ዘየዐብዩ በክፍል።
ወየዐቢ እምነ እሎንቱ ማልሳይ ቃል።
ኃይለ ሥላሴነ ፍቅር አሐዱ፤ አምጣነ ማእሠር ሐብል።
ለሕገ ኦሪት ወወንጌል።
ወብዙኃ ማይ ለፍቅር፤ አበ ጠቅልል።
አጥፍአቶ በዓለም ኢይክል።

መወድስ

ረኃብ ወጽምእ ኢይረክብዎ፤ ለኃይለ ሥላሴ ኤልያስ፤
እንተ የዐይል አድባረ።
ከመ ይሴስዮ እግዚእ፣ አምጣነ ፈነወ ንስሥረ።
ጽባሐ ወምሴተ፤ ዘያመጽእ ሶቱ ሥጋ ሳሁም ጠማረ።
ወእምድኅረ መስሐ ወተደረ።
ለአስትዮ ዝንቱ አወ ኅዘ ፈለገ ሰላም ፍቅረ ።
አመ ዐርገኒ በሠረገላ፣ እንተ ይትሌዓል መንበረ።
ላዕለ ኤልሳዕ አስፋ ወሰን መንፈስ ጸጋሁ እንተ ኃደረ።
ለለ በዓሉ ያሐዩ ዘበደዌ ጌጋይ ተአሥረ።
ወያ ነሥአ በሥልጣኑ ዘሞተ ወተቀብረ።

ዘአለቃ ዳንኤል እ ደስታ።

ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የዘውድ በዓል ።

ኢትዮጵያ አዕረፈት እምፃማ ብሂል፣
ዘጳውሎስ አነ ወአነ ዘጴጥሮስ።
እስመ እምላዕሉ ወረደ አክሊለ ሰማዕት መንፈስ ።
ወነበረ ዲበ ርእሱ፣ ለኃይለ ሥላሴ ማሕየዊ ክርስቶስ ።
እስመ ተቀደሰት በጥምቀቱ ፤
እመ ምእመናን ውሉድ ወለተ ጊዮርጊስ ዮርዳኖስ ።
ከነሂ መዋዕሊሁ መዋዕለ ህዳሴት ወመርስ ።
እስመ እምውስተ ባሕር ኢተንሥአ ዘየሐውከ ኃያለ ነፋስ።
ወዝ ውእቱ፣ ኃይለ ሥላሴ ንጉሥ ።
አምላክ ወልደ አምላክ እንተ ይቤለነ ኤርምያስ ።

ሊቀ ጠበብት ድንቄ ዘራጉኤል ።

መወድስ ።

መኰንነ ጽድቅ አብርሃም ሥርወ ሃይማኖት ።
ለዕለተ ወልዱ ዋሕድ ከመ ይርአይ ተመነየ ።
እስመ ለዛቲ ዕለት በዓለ ኃሤት ሰመየ ።
ወለነ ደቂቀ ድማኅ በዓልነ ነየ ።
ወኢክህለ ነጽሮታ፣ ዳዕሙ አምሳለ በተነብዮቱ ረሰየ ።
ለክሙሰ ሰብአ ግብፅ ወእስክንድርያ ።
ብፁዓት እንበለ ነውር አዕይንቲክሙ እለ ርእያ ።
እስመ ክብረ ንግሡ ትግብር ኢትዮጵያ ።
እንዘ አርማንያ እንተ ቅድሜሁ ወእንተ ድኅሬሁ ቊስጥንጥንያ ።

አለቃ ንጉሤ ዘዲማ።

አይሮፕላን በአዲስ አበባ

ከፈረንሳዊ መንግሥት የመጣውን አዲስ አይሮፕላን ለማየት በታኅሣሥ ፲ቀን ጃንሆይ ወደጃንሜዳ ወጥተው ነበርና በዚያ ጊዜ ደጃዝማች መንገሻ ይልማና ደጃዝማች አያና ፍርሰው በአይሮፕላን እንዲበሩ ከጃንሆይ ፈቃድ ተቀብለው ወጥተው ነበር። እስከ ማታ ድረስ በአይሮፕላን ሲበሩ አምሽተው በደኅና ወረዱ። እነሱ በእልለመዱት ልማድ በመድፈራቸው እጅግ ስንደነቅ አንድ ሰው ደግሞ የሚያስደንቅ ጨዋታ አጫወተን ። ቅኑ ሙሴ ቢደል አይሮፕላን መንዳት ለልጆች ሊያስተምሩ ወደ ጅጅጋ በወረዱ ጊዜ የፊታውራሪ ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል ባለቤት ወይዘሮ ሙላትዋ በአይሮፕላን ወጥተው ብዙ ጊዜ ቈይተው ያለ ፍርሃት ደስ እያላቸው ወረዱ። ደግሞ ሚሽከ ባብቼፍና አስፋው አሊ ተምረው አይሮፕላን መንዳት በጀመሩ ጊዜ ልጅ ተስፋ ያየህ ይራድ ቢሰናከልም ከወንድሞቼ ጋራ እሞታለሁ ። ባይሰናከልም የወንድሞቼን እውቀት እመሰክራለሁ ብሎ በየተራ ከሁለቱም አይሮፕላን ላይ ወጥቶ ሁለት ሰዓት ተኩል ያህል ቆይቶ ወረደ። በዚያ ቀን የተደረገው በዓል እንዲህ አልነበረም ብሎ አጫወተንና እጅግ ተደነቅን ። ግን የሀገራችን ሰዎች ሞትን አለመፍራታቸው ከጥንት የታወቀነው ።

የሌቦች መያዝ ።

ባለፈው ጊዜ እንዳስታወቅነው ከ፫ዳ ፺ ሺ ህ መሐለቅ ተሰርቆ ነበር ። እኒህ ሌቦች አራት ሁነው ተካፍለው ገብሩ የሚባለውን ሌባ የምሥጢር ዘበኞች መሐልቅ ሲሸርፍ ይዘውት ወደ ግራዝማች እማሪ ወስደውት አብረውት የሰረቁት ባልንጀሮቹን ወርቁ፥ ታደሰ፥ ገብረ ሕይወት የሚባሉትን አሲዞ ቢመረመሩ መስረቃቸውን አምነው ለምርምር ቆይተዋል። እነዚህም ሁሉም የጓዳ ሠራተኞች ናቸው ። ሁለቱማ ጥንቱንም ጠላፊዎች ነን ብለዋል ። ባለፈውም ብዙ ጥፋት የተደረገውን ሁሉ ሳያወጡ አይቀሩም ። መሐለቁንም ሰርቀው ያስቀመጡት ከ፩ ሮፓዊ ነጋዴ ቤት ነው ። እሱም እንደ ተለመደው በቆንስሌ ብሎ ቆይቷል። የሰውዬውን ስምና የነገሩን አኳኋን በሚመጣው እንጽፍላችኋለን ።

ለኢትዮጵያ ልጆች ማመልከቻ ።

የመሥፖ ቤቶች ሁሉ ነጭ ቀለም ተቀብተዋል ። የማዘጋጃ ቤትም ተቀብታለች ። ደልቁንም ማዘጋጃ አቀባበ ከማዘኑ እነስ ካርመኑ በዛ ብሎበታል ።

ግብረ ድንግል ድቡቤ ።

ከውጭ አገር ጋዜጣ የተተረጐመ ።

በኢጣልያ መንግሥት ዘንድ የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር የሆኑት ሊቀ መኳስ መንገሻ ውቤ ከማታው በ፬ ሰዓት የክረምት ሳሎን በሚባለው በግራንድ (ትልቅ) ሆቴል አዳራሽ ውሥጥ ለዲፕሎማቲክ ሰዎች ግብዣ አደረጉ ። ሴክረተሩ ልጅ ይልማና አማካሪው አባጂሮም ሁለቱም የማዕርግ ልብሳቸውን ለብሰው ከሚኒስቴሩ ጋር ይጋበዙ ነበር ። ሚኒስቴር አቸርቦ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ አድርገው ከባለቤታቸው ጋር በግብዣው ነበሩ ። እንዲሁም የፈረንሳዊ አምባሳደርና የመስኮብ የአሜሪክ የነምሳ አምባሳደሮች የቺና ጕዳይ ፈጻሚ የምስር ሚኒስቴር የብልጋሪና የቸኮስሎባኪ የቤልጅግ የኤፂቶኒ የሌቶኒያ የሊቱዋኒያ የአልባንያ የደቡብ አፍሪካ የእሲያም መልእክተኞች ነበሩ ። የጦር ምኒስቴርና የቅኝ አገር ሚኒስቴርም ነበሩ ። በፍራስክቲ ያለው የኢትዮጵያ ሙዜዮ ዲሬክተር ኮሜንዳተር ፉሪና ሼባልያ ኦፊሲዳ ጓርኒስኬሊ ፥ ድሮ ለዘንዳና በሐረር ቆንስል የነበረው ሼባሴየ አጀኖረ ፍራንጃፖኒ ፥ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስቴር ኮሜንዳተር ታልያኒ ፥ ኮንት ዲዮባኒ ፌውሚ ፥ ለውሬንስ ላውሬንሲ ፥ ጂሎኩቲሊ ነበሩ ። ከዚህ በላይ ደግሞ በጣም ያጌጡ ብዙ ሴቶችና ልጃገረዶች ነበሩ ። አዲሱ ኤርትራዊ ካቶሊክ አቡን ሞንሴኞር ኪዳነ ማርያም ሁለት ካህናትና የኢትዮጵያ ኮሌዢ አለቃ አባ ተክለ ማርያምን አስከትለው በ፬ ሰዓት ተኩል ወደ አዳራሹ በገቡ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በብዙ ናፍቆት ተቀብሎ ከበባቸውና ሚኒስቴር አቸርቦም ከነሱ ብዙ ተነጋገሩ ። በማሪኒስቲ ኮሌዢ የሚማረው የልዑል ራስ ኃይሉ ዘመድ ልጅ ከበደም ነበረ ። ጕድ የሆነ ጠረጴዛ ተዘጋጅቶ ነበረ ። ሙዚቃውም ግብዣውን በደስታ መልቶ አድምቆት ነበር ። ስለ ንጉሡ ባዲስ አበባ ስለተደረገው በዓል የኢትዮጵያ ሚኒስቴር ብዙ ምርቃ ተቀበሉ ።

ማስጠንቀቂያ ።

አንዳንድ ሰዎች ጠይቆ መረዳትን ነውር ያደርጉና እንደ ተረት ሁኖ በፍ ሲነገር የሚኖረውን ከቁም ነገር አግብተው ይጽፋሉ። ስለዚህም ታሪክ ጸሐፊዎችና መጻሕፍት መርማሪዎች መምህራንም ታሪክ ሲጽፉና ሲያስተምሩም ብዙ ጥቃቄና ረዳትንም መሻት ያስገድዳቸዋል ። ይልቁንም በማኅተም የሚታተም ነገር ትንሽም ቢሆን እስከ ብዙ ዘመን የሚኖር ያገር ልጆችም ያገራቸውን ታሪክ የሚያጠኑበት ነውና ስሕተት እንዳይገኝበት የታረመ ሊሆን ይገባል ።

ይህንንም ያሳሰበኝ በብርሃንና ሰላም ፯ኛ ዓመት ቍጥር ፴፯ በተጻፈው ጋዜጣ ላይ ቅዱስ ወንጌልን ከሌሎች መጻሕፍት ጋራ ጨምሮ ካረበኛ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ ብሎ ያለውንና የታረመውን ስሕተት ስለ አየሁ ነው ። ማረሙስ ይሁን አይከፋም ወንጌል ካረብኛ ወደ ግዕዝ ተተረጐመ ማለት ግን ትልቅ ስሕተት ነው ። የጸሐፊው ሐሳብ ኢትዮጵያ ሐዲሱን እምነት የወሰደችው ከምስራውዋን እንደ ሆነ ተረድትዋልና የዛሬውም የምስራውያን ቋንቋ ዓረብኛ ከሆነ ያሰኛል በማለት ይመስለኛል ይህ ግን እንዲህ አይደለም ወንጌል ወደ ግዕዝ የተተረጐመው ከግብፅ ቋንቋ ነው ይህንንም የሚያስረዳ የኢትጵያ ሕዝብ በክርስቶስ ያመኑበትና ዋና ዋናዎችም የሃይማኖት መጻሕፍት ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ የተተረጐሙበት ጊዜ ዘመኑ ፫፻፴ ዓ ም ነበረ። ያን ጊዜም የምስራውያን ቋንቋ ቅብፅኛ ነበረ እንጂ ዓረብኛ አልነበረም ። ከፅርፅም ተገለበጠ ለማለት እንችላለን ማለት ያን ጊዜ ምስርን የሚገዙ ፅርዓውያን ስለ ነበ–

ሩና የሐዲስ ኪዳንም መሠረቱና ምስክሩ የዕርዕ ቋንቋ ስለ ሆነ ኢትዮጵያውያንም ሰነፎች እይደሉምና ከዋናው መዝገቡ (ከዕ-ርዕ) ገለበጡት ይባላል። ከግብፅም ከዕርዕም ተተረጐመ ብንል የግብፅና የዕርዕ ቋንቋ አይራራቅምና አንድ ነው። ይህ አያ-ከራክርም። ምስራውያን ግን በዓረብኛ ቋንቋ መናገር የጀመ-ሩት ከ፮፻፲፮ ዓ ም ወዲህ ነው ። እንዲህ ከሆነ በ፫፻፴ና በ፮፻፲፮ ዓም መካከል ፪፻፹፮ ዘመን አለ። እንግዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ በክርስቶስ ካመኑ ይህን ያህል ዘመን ወንጌልን ሳያስተ-ረጕሙ ተቀምጠው ነውን ፤ ወይስ ያን ጊዜ የምስራውያን ቋንቋ ዓረብኛ ሳይሆን ካረብኛ ተተረጐመ ለማለት መንገዱ እንደ ምን ያስኬደናል ። ይልቁንም ዋና ዋናዎቹ መጻሕፍ-ታችን ከዕርዕቋንቋ መተርጐማቸውን የሚያስረዳ በውሥጣቸው ያልተገለበጡ የዕርዕ ንግግሮች አሉባቸው። እነሱም ከብዙ በጥ-ቂቱ ቀጥሎ ያሉት ናቸው ። ክርስቶስ (ቅቡዕ) ጳራቅሊጦስ (መፅንዒ) (ኤጲስ ቆጶስ) መጥሮጶሊስ፤ አልፋ ዖሜጋ (ቀዳማዊ ደኃራዊ) አግዮስ ኪርዮስ (ቅዱስ እግዚአብሔር) ኪርያላይሶን (እግዚኦ መሐረነ) እንዲዚህም ያሉ ብዙ አሉ ።

አንባቢ ሆይ ካረብኛ ከተገለበጠ የዕርዑን ቋንቋ ወደዚህ ምን አመጣው ? ወይስ ፈረስ በሔደበት መንገድ የግመል ኮቴ ይገኛልን ። እኛስ ከመምህራንም የሰማነውና በታሪክም ያነበብነው መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ በዕብራይስጢ ቋንቋ ተጻፈ፤ ከዕብራይስጢም ወደ ዕርዕ ፤ ከዕርዕ ወደ ላቲን ፤ ከላቲን ወደ ግዕዝ ከዚያ በኋላ በዓለም ሁሉ ላይ ተዘረጋ ማለትን ው ። ወደ ዓረብኛ ቋንቋ ግን የተተረጐመው ከብዙ ዘመን በኋላ ነው ።

አንባቢም ምናልባት ምነው ከረብኛውስ አምጥቶ መሢሕ ዱል የለም ወይ ዩል ይሆናል ። የዚህም መልስ እንደዚህ ነው፤ ዓረብና ኢትዮጵያ በቦታ የሚቃረቡ ስለ ሆነ በንግግርም በብዙ በኩል ይገናኛሉና ነው እንጂ መሢሕ ላረብኛ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በግዕዝም መሢሕ ማለት ቅቡዕ ማለት ነው ። ለዚ-ህም ምስክር መዝሙር ፪ ፡ ፪ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ መ-ሢሑ ይላል ። ደግሞም ዮሐ ፩ ፡ ፵፩ ኢትግሥሥ መሢሐንየ ይላል ይህንንም የመሰለ በብሉያት መጻሕፍት መልቷል ። እንግዴህ መሢሕ ማለት ዓረብኛ ብቻ ከሆነ የብሉይ ኪዳንም መጻሕፍት ከረብኛ ወደ ግዕዝ ተተረጐሙ ማለት ነዋ ? እንዲህም ብንል ዓረቦች በብሉይ ዘመን እንኳን ለኛ ይተርፉ ብሉይ ኪዳንን እነሱ ራሳቸው አልተቀበሉትም ነበርና መንገዱ አያስኬደንም ። ከሐዲስ ኪዳን ጋራ ከረብኛ ተተረጐመ ለሚል ሰው ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት ብሉይ ኪዳንን አል ተቀበሉም ነበር ማለት ይሆንበታል ። ከክርስቶስ ልደት በፊት ብሉይ ኪዳን ወደ ግዕዝ መተርጐሙንም ለመረዳት (የሐዋ ፰ ፡ ፳፯ - ፴፰) ተመልከት ። ከረብኛ የተተረጐሙ ግን ከሐዲስና ከብሉይ ያልሆኑ ሌሎች መጻሕፍት አሉ። እነዚያውም ስሕተት ብለ አለባቸው በዕድለ መልካሙ በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ ይ ታረሙልናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

ይህንንም የጻፍሁበት ምክንያት የሊቁን ሐሳብ ለመንቀፍና ለማዋረድ አይደለም ነገር ግን በማስተዋል እንደ ሆነ የተጻፈው ለመረዳት በዝንጋታም እንደ ሆነ የቀለም ሠረገላ አያሳናክለው የለም የሚባል ተረት አለና ለማስጠንቀቅ ስል ነው የማስተ-ዋል አምላክ የምንጠነቀቅበት አእምሮ ይስጠን ።

አባ ተወልደ መድኅን ።

ደሴ ከተማ የስኒን ተማሪቤት ሲከፈት የተነገረ ቃል ።

በ፲፱፻፲፰ ዓመት የካቲት ፲፯ ቀን የወሎ ግዛት ወደ ጃን-ሆይ እንዲሆን አዋጅ ወጥቶ አገሩን ለመረከብ በግርማዊ አብረን ከመጣናቸው ብዙዎቹ ስለሔዱ የቀረነው ሰዎች ያንጊዜ የነበረውንና ከዚያ ወዲህ የተጨመረውን ሥልጣኔ የተሠራውን ቤት ላይተን እናውቀዋለን ። ብዙ የጣምብና ባለቆርቆሮ ክዳን ቤቶች ተሠርተዋል። ምንም ለሥራ የሚሆን የዕውቀት ተማሪ ቤት ስለሌለ በሩም ሐይቅ ገዳምም በየተማሪ ቤቱ ያገራችንን ትምህርት ይማሩ የነበሩ ትንሽ ትንሽ ጽሕፈት የሚአውቁ ልጆች ደሴ ቤተ መንግሥት ጽሕፈት ቤት እየመጡ አራቱን የቁጥር ደረጃ እየተማሩ ሙሉ ለሆነ ቁጥር ለመዝገብ ሥራ እየደረሱ ባገር ቤት ካሉት ወንድሞቻቸው በልጠው ደመወዝና ቀለብ ስለተቆረጠላቸው ሰው ትምህርት ተምሮ ዕውቀት ቢኖረው ስለኑሮው ሀብቱ ከፍ ያለ መሆኑን በከተማም ባገር ቤትም ያሉ ወጣት ልጆችና በዚች ሀገር ቀድሞ ጸሐፊዎች የነበሩ ሽማግሌዎች ባጭሩ ተረድተውታል ። ዕውቀት የሚገኝ በት-ምህርት ነው ዕውቀት ጌጥ ናት ዕውቀት የማትለይ የማታልቅ ሀብትና ገንዘብ ናት።የሚያሻውን ሁሉ ይገዛባታል ዕውቀት ክብር ናት ከብዙ ሰው መካከል አስመርጣ ከፍተኛውን ማዕርግ ታስ ጣለች። ይህን ሁሉ አስበው የወሎ ገዢ ባላባት የንጉሥ ሚካ ኤል ታላቋ ልጃቸው ወይዘሮ ስኒን ሚካኤል አገሬ ላይ ተማሪ ቤት አሠራለሁ የማለት ሐሳብ ነበራቸውና ሐሳባቸውን ሳይፈ ጽሙ ጊዜ ሞታቸው ስለደረሰ በኑዛዜ አስታውቀው ይኸው የእውቀት ትምህርት ቤት ተሠራ ። ያገሩ ሕዝብ የዕውቀት ትምህርት የተጠማ ስለሆነ ከትልቅ እስከ ሕፃናት ለመማር አስፍስፎዋል። እንደ ሰው ተፈጥሮ አእምሮ እያለው የሚሠራ-በት ዕውቀት ፣ሌለው ሰው ተምሮ የሚሠራበት ዕውቀት ሲአ-ገኝ እንግዲህ ወይዘሮ ስኒን ሚካኤል በወዲያኛው ዓለም መን-ግሥተ ሰማያትን በዚህኛው ዓለም ስማቸው እንደተጠራ እንደ ተመሰገነ ይኖራል። ይህ ትልቅ ዕድል ነው። አባትና እናት የሌላ ቸው ወገናቸው በከተማ ተቀማጭ ያልሆነ ረዳት የሌላቸው ብዙ ልጆች ትምህርት የሚፈልጉ አይቻለሁ ትምህርት እያ-ማራቸው በዚህ ምክንያት ተለይተው እንዳይቀሩ ድኆችን ማ ሳደግ እውነትን መውደድ ሐሳባቸው የሆነው ግርማዊት እቴጌ መነን አስፋው ሚካኤል ብርሃን ዘኢትዮጵያ እንዲአስቡላቸው ተስፋ አለኝ ከዚህ ቀደም የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ክር-ቱምና ከሰላን የመንና ምስርን መግዛታቸውን መላዋ ኤውሮፓ ታውቃላች። ኢትዮጵያ ባንዲራዋን እቦታዋ ድረስ እንዲዘረጋ በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እጅ ለዘለዓለም ትኑር፥ በዚች ተ ማሪ ቤት የተማሩ ልጆች ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው በው-ነት የሚያገለግሉ ያድርጋቸው አሜን ። ተፈራ ለወጠኝ ።

መልእክት።

ይድረስ ለክቡራን ወንድሞቼ ብርሃንና ሰላም ወዳጆች ከዕውቀት ወንድሜ ናፍቆት በቀር እግዚአብሔር ይመስገን እኔ ደኅና ነኝ። በትንሹ ጠጠር መመራመር ትልቁ ጋን ዕውቀታችሁን አስደግፌ ጥሩ መጠጥ ምሳሌን እቀዳለሁ። በተወለድሁ በ፳፱ ዘመን እቴን ለመዳር ወደሥርግ ቤት ሔድኩኝ፤ ምንም እርሷ የሥጋ ዘመዴ ስለሆነች ከወንዱ ሙሽራ ጋራ የፍቅር ማኅበር ስለኖረኝ ቤቱስ ድግሱስ ተዘጋጀልህን ለማለት ብደርስ የወንዱ ሙሽራ ታላቅ እኅት ወይዘሮ ጊዜ ለሙሽራይቱ እንደሚገባ እያይነቱ ሽቱዎች ታጣፍጥ ነበር። የሽቱ ዎችም ስም እንደሚከተለው ነው ። ጥቅም ለራስ ወገን መለየት።መነቃቀፍ ይባላሉ። እነዚህን አንድነት ማስመሰል በሚባል ብርሌ ቀላቅላ ሙሽራይቱን እንዲቀባት ባለሟል ለሚባለው ለሥርሚዜው ሰጠችው። ይልቁንም ጥቅም ልራስና ወገን መለየት የሚባሉት ሽቱዎች በዛ ብለው ኑሮ በኀዳና ስናልፍ አፍንጫችንን እየሰረነቀ ራስ ፍልጠት ሆነን። መነቃቀፍ የሚባለው ሽቱ ለክን ሲቀላቀል አዘቅጦ ወደ ሥር ቀርቶ ኑሮ ሙሽራይቱ ውላ አድራ ብትቀባው ባሏ ሽታውን ከመጥላቱ የተነሣ አላስጠጋት አለ።ምንም ወንዱን ሙሽራ ስለወደድሁ ከሴቲቱ ሙሽራ የሥጋ ዝምድና አለኝና መፋታታቸው ሐሳቤ ስለሆነ እንዲታረቁ እኒህን አራቱን ሽማግሌዎች አቶ መስማማትን፥ አቶ አንድነትን፥ አቶ አንተትብስን፥ አቶ አብሮ መብላትን አምስተኛ የዘመድ ዳኛ እግዚአብሐር ለሰጠው መገዛትን አማላጅ ልኬአለሁ። ሁለተኛ በተረት ምሳሌ የሀገሬን ጕዳት አስታውቃለሁ የግፍ ገበያ በሬው በሥር ቆዳው ብሀያ እንዲሉ ባንድ ብር ፲፩ ጠርሙስ ወተት ሲገዛ የሚአቃጥለውን አረቂ በብዙ መግዛት እጅግ የሚያሳዝን ነው ወርቅ በጠጠር፥ እህል በፈር እንደመለወጥ ያለ ነው ስልበትንሹ ዕውቀቴ እርዳታየን ለኢትዮጵያ ልጆች አቀርባለሁ።በቀለ ጕበና

ማስታወቂያ።

ሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒከላው ስለሞተ። ምናልባት የተወው ዕዳ እንዳለ ማስታወቂያ፡

ሞዴስቶ ፓፓኒከላው የሚባለው ነጋዴ የኢጣልያ ዜጋ ስለ ሞተ የሚቹን ገንዘብ አኳኋን ማደላደል መጀመሩን ባአዲስ አበባ ያለ የኢጣልያ ሌጋስዮን ያስታውቃል፡

ስለዚህ ከሟቹ ከሲኞር ሞዴስቶ ፓፓኒከላው ላይ ገንዘብ አለን የሚሉ ሰዎች ማስረጃ ወረቀታቸውንጨምሬው ጥያቄያቸውን ለዚሁ ሌጋስዮን የቆንስላ መጻፍያ ቤት እንዲያስታውቁ ብለን እናመለክታለን ።

ጥያቄያቸውንም ለማቅረብ የወሰነው ጊዜ እስከ ጥር ፪ቀን ፲፱፻፳፫ ዓመት ድረስ ነው። ከዚህ ከተወሰነውም ቀን በኋላ የሚቀርበውን ጥያቄ ለመቀበል አይቻልም ።

ማስታወቂያ ።

ዶክቶር ሚ ስ ሚካኤልያን በፈረንሳዊ አገር ከሞንፔሊዬ የሊቃውንት ትምህርት ቤት ስለ ሆድ ውሥጥና ስለ ሴት በሽታ ደግሞ ስለ ሴት አዋላጅነት ተመስክሮለታል። ቤቱ ከራስ መኰንን ድልድይ ወደ ጊዮርጊስ መውጫ መንገድ ነው።

ከጥዋቱ ከ፫ሰዓት፥ ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት፥ ማታ ከስምንት እስከ ፲፩ሰዓት ድረስ ይገኛል።

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

ስለ ዘውድ በዓል የተነገረ የምሕረት አዋጅ በትንሽ ደብተር እንደመጽሐፍ ሁኖ ታትሞ ወጥቷልና ለሚገዛ ሰው ዋጋው አንድ ሩብ መሆኑን እናስታውቃለን።

ዊስኪ

ባ ለ ነ ጭ ፈ ረ ስ ዊ ስ ኪ ።

ጤና እንድታገኝና አንድ ዊስኪ እንድትጠጣ ትፈልጋለህን? ልትጠጣ ብትፈልግም ባለትልቁ ምልክት ኤከስ ባለ ነጭ ፈረስ ዊስኪ ከሁሉ ሌላ ዓይነት ዊስኪ የበለጠ ነውና እርሱን ጠጣ ።

ይህ ግሩም የሆነ መጠጥ በእንግሊዝ አገር የግርማዊ ንጉሥ አሰናጂ በኢትዮጵያና ጂቡቲ ለሙሴ ኤ አ ጋኖታኪስ ወክሎታል።በትልልቁ ሆቴል ሁሉ በካዚኖ በቡና ቤትና በሱቆች ይገኛል።

ማስታወቂያ

ወይን ጠጅ

በሁሉ ስፍራ ፈልጉ ወይን ጠጅና ዘቢብ ማርኩ ክርሜል ኢየሩሳሌም እውነተኛ ወይን ጠጅና ዘቢብ ኮኛክ የተመሰከረለት ከወይን ብቻ የወጣ ። ወኪል ሙሴ ሳላንት።

በብላሽ መቅመስ ይቻላል ።

ይህነንም ሐኪሞች ሁሉ መርምረው አይተው ለበሽተኛ ብጣም ይፈልጉታል ።

የወይራ ዘይት

በሁሉ ስፍራ ጠይቁ ጥሩ የወይራ ዘይት ማርኩ ባለ ኮከብ ከዚህ ቀደም አዲስ አበባ የሌለ ለማያትም ለፈለገ በብላሽ የሚሰጥ ወኪል ሳላንት

ዊስኪ

ውስኪ ካምቤል ማለፍያ ዓይነት ዊስኪ ከሁሉ የሚበልጥ ከዚህ ቀጥሎ ዶክተር እንደመሰከረለት ተመልከት ። ወኪል ሳላንት ።

ከካምቤል ፋብሪካ የተሠራ በእንግሊዝ አገር በጣም እሮጌ ሆኖ የሚጣፍጥ ብስኮት ላንድ።

ታላቁ ሐኪም ሙሴ ስቴፌንሶን ማክዳም የሚባል በኢ- ዲምቡርግ አገር ቀጥሎ ያለውን መሰከረ የካምቤልን ዊስኪ ብጥንቃቄ መርምሬ ንጹሕ ሆኖ አገኘሁት ሲያረጅም መዓዛው ለሰውነት የሚስማማ ሆኖ ሽታውም አደይ አበባ የመሰለ ነው።

ለኢትዮጵያ ሀገር ወኪል ።

ማስታወቂያ

አዲስ መታከሚያ ቤት ዶክተር ያኒ ካልፋስ ከፍተዋል። ብዚሁም መታከሚያ ቤት ግናቸውንም ሕመምና የውርዴና የማዋለድ የጨብጥም ሕክምና በአዲስ ሥልጣኔ ለመታከም ይቻላል።ቤታቸውም ክቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ብታች ከነሀ ጽባሕ ማተሚያ ቤት አጠገብ ነው ። የሐኪሙም ቤት የሚከፈተው ከጧቱ ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ድረስ ነው ከ፰ እስከ ፲ ሰዓት ከ፲፪ እስከ ፪ ያክማሉ ።

ሐኪሙም ሥራቸውን የሚሠሩትና ሐሳባቸው ገንዘብ ለማግኘት ብቻ ስላልሆነ የኢትዮጵያውን ችግረኞችን በታመሙ ጊዜ ሕመማቸውን ለመመርመርያ ላንድ ጊዜ አላድ ብቻ መቀ- ብላቸውን በቅን ልቦናቸው ያስታውቃሉ።

ሰው በዘመኑ ሳይታመም የሚኖር የለም ።

በፈረንሳይ አገር አክሞ የተመሰከረለት ዋና ሐኪም ነው። በሽታን ሁሉ በያይነቱ እየመረመረ በጥንቃቄ ያክማል ።

ሴት በማዋለድም የተመሰገነ ነው ። ወደርሱ የሚመጡትን በሽተኞች ሁሉ በደስታ ሊመረምራቸው ይችላል ።

የሚያክምበትም ስፍራ በሸመታ ተራ ትይዩ ተመሐመድ ዓሊ ሱቆች አንዱ የመጀመሪያው ነው። ሐኪም አምባር

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

በዶክቶር ቤኪያር መድኃኒት ቤት በያይነቱ መድኃኒት ይገኛል የመቅደድም የመቍረጥም የፓሪስ መድኃኒት ቤት ሐኪም በሥራው ተመርምሮ የመጣ ለበሽተኞች ሁሉ የሚያስፈልግ የሳምባሳል ፥ የልብ፥ የደረት፥ የጉበት፥ የኵላሊት ፥ የጅማት፥ የጨብጥ፥ የቂጥኝና፥ የቋቋቻ፥የሚያዋልድ፥ በኤሌክ- ትሪክ የሚታከም በሽታ ሁሉ ያክማል ። ከሙሴ ጎርጎርዮስ ሱቅ ፊት ለፊት ከዱሮውማዘጋጃ ቤት አጠገብ ነው።

የርሻና የንግድ ማስፊያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማኅበር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ አንድ ሚሊዮን ብር ። በግ- ርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጠባቂነት ቁሟል ። የማኅበሩ ዋና ቦታ አዲስ አበባ ። የማኅበሩ ሥራ ማናቸውንም የንግድ ፥ የርሻ የፋብሪካ ፥ የደን ፥ የማዕድን ሥራ ማናቸውንም የሕዝብ ጥቅም የሚሆን ታላላቅ ሥራ የቤትና የመሬት ግዥና ሺያጭ ቤት ወይም መሬት ይዞ ገንዘብ ማበደር ።

OMEGA



በአውሮጳ አገር ከሚሠራው ሰዓት ሁሉ መብለጡ የተመሰከረለት ኦሜጋ የተባለ ባለ አንበሳ ሰዓት ከሙሴ ማቲክ ኬምርከፍ ቤት ይገኛል ።

ዓለም
ALEM



የወርቅ ሰዓት ።





ዓለም ሱቅ ፲፪ ዓይ-
ነት የተሰማ እሼቴ ሙዚቃ
ሸክላ ይገኛል። ሙዚቃም
በየዓይነቱ እንደ ሴንጆር
ቤት በዱቤ ለመሸጥ ይቻ
ላል። ፊኒክስ (PHENIX,)
የእጅ ወርቅ ሰዓትና የኪስ
ወርቅ ሰዓት ይገኛል

የምትፈልጉት ሁሉ ወደ ዓለም ቤት ይገኛል ኒኮላ።

ፔር ዳኔይ።
አ ቦ ካ ት ።
የፍትሐ ነገሥት ዶክቶር ።

ሁሉ ቀን ከስምንት ሰዓት እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ይቀበላል ።(ቤታቸውም በአቡጀዲድ ፋብሪክ አጠገብ ድሮ አቶ ብርሃን ማርቆስ ይኖሩበት የነበረ ነው።)

ማ ስ ታ ወ ቂ ያ ።

እስቶፕ የሚባል ኮኛክ በፈረንሳይ አገር ኮኛክ ከሚባል ከተማ ይወጣል።ሌላ ነገር ሳይቀላቀልበት በወይን ብቻ የተሠራ ለሰውነት ጤና የሚሰጥ መጠጥ ነው።ይኸ ባዲስ አበባ በሙሴ ኤልያስ በሂስኒልያን ቤት ብቻ ይገኛል ።

አዲስ ዓይነት ቦርሳሊን ባርኔጣ መጥታችሁ እዩ ። በጣም ያማረ ነው። በጣም ውድ አይደለም ። በተለየ አስ

MARCA DEPOSITATA

መጭ በኢትዮጵያና በፈረን-
ሳዊ ሱማሌ ወኪል ሰ ፈ ፈርና
ዲስና ልጆቹ ።
የወዶችና የሴቶች ልብስ ሰፊ።

COGNAC S.E.A.METAXA
LE PIRÉE-GRÈCE
KONIAK - METAΞA

ከሚሠራው ኰኛክ ሁሉ የሚበልጥ ክልስ የሌለበት ከባሕር አገር የመጣ ጥሩ መደቅሰ ኰኛክ በጅምላ ወይም አንዳንድ ጠርሙስ የሚፈልግ ሰው ከሙሴ ማቲክ ኬዎርኮፍ ሱቅ ይገኛል ።

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

21 36
B JUL M